ቅጽ ፩




# ትግላችን፡

## የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ

ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም



Brought to you by:
Ethiopian Bookstore
https://t.me/etbookstore

# ት ግ ላ ች ን

## የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ

ቅፅ አንድ

ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም

ፀሐይ
አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት

ትግላችን፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ [ቅፅ ፩]

በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም © ታኅሣሥ ወር 2004 ዓ.ም
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያው እትም በፀሐይ አሳታሚ ድርጅት በታኅሣሥ ወር 2004 ዓ.ም ታተመ።
የአሳታሚው ሙሉ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ይህንን ወይም ሌሎች የፀሐይ አሳታሚ ድርጅት መጽሐፍትን ለመግዛት፣ ለማከፋፈል ወይም ድርሰትዎን ለማሳተም ሲፈልጉ መልዕክትዎን ይላኩልን።

ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት
TSEHAI Publishers
Loyola Marymount University
1 LMU Drive, Suite 3012
Los Angeles, CA 90045

www.tsehaipublishers.com : info@tsehaipublishers.com

የመጽሐፉ መለያ ቁጥር ፡ ፱፯፰-፩-፭፱፱0፯-፰0፩-፬

ISBN:- 978-1-59907-801-4

አሳታሚና አርታኢ ኤልያስ ወንድሙ

ካለአሳታሚው ሕጋዊ ፍቃድ በስተቀር፣ ይህንን መጽሐፍ ማባዛት፣ መቅዳት፣ መተርጎምም ሆነ በማንኛውም አይነት ዘዴ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

የዚህ መጽሐፍ የሕትመት ምዝገባ መረጃ በወመዘክር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተመጻሕፍት እና በአሜሪካ የኮንግረስ ቤተመጻሕፍት ተመዝግቦ ይገኛል።

ይህ መጽሐፍ ከአሲድ ነፃ በሆነ ወረቀት በአሜሪካን ሀገር ታተመ።

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲

# ማውጫ


ምስጋና ........................................ ፩

የአሳታሚው ማስታወሻ ........................................ ፺

መቅድም ........................................ 1

መግቢያ ........................................ 9

ጥንታዊት ኢትዮጵያ ........................ 10
የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ አነሳስ ........................ 13
ኢትዮጵያ በመካከለኛው ዘመን ፡ የአክሱም መንግሥት ፍፃሜና የዛጉዌ መንግሥት አነሳስ . 16
ከዛጉዌ በኋላ የመጡ ሥርወ መንግሥታት የጠበቃቸው ሥራና የገጠሚቸው ፈተናዎች . . 19
ኢማም አህመድ ግራኝ የመራው አመፅ፣ የእስላም አገሮችና የፖርቱጋሎች
በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት ........................ 21
የኦሮሞ ማህበረሰብ ፈለሳና ወረራ ........................ 25
የሥርዓተ አልበኞች መስፋፋት ዘመን ........................ 29
ዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ........................ 33
የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና የአካባቢው ባዕዳን ተስፋፊዎች በኢትዮጵያ ላይ
ያደረጓቸው ከበባዎችና ብሎም ወረራዎች ........................ 34
የቱርኮች ከበባና ወረራ ........................ 35
የግብፅ መንግሥት ያደረገው ከበባና የሰነዘረው ወረራ ........................ 35
የአውሮፓ መንግሥታት ግብፆችን ተከተው በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ከበባና ወረራ . . . . 40
የኢጣሊያ መንግሥት ወረራ ........................ 41
ድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ........................ 55
የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና አይበገሬ አርበኝነት ........................ 70


## ክፍል አንድ


ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መቃረቢያ፣ ዋዜማና አጥቢያ ........................ 75
1. የአብዮቱ መቃረቢያ ........................ 77
2. የአብዮቱ ዋዜማ ........................ 99
3. የአብዮቱ አጥቢያ ........................ 115

# ማውጫ

## ክፍል ሁለት


አብዮታዊት ኢትዮጵያ፡ ከትግል ወደ ድል፣ ከድል ወደ ትግል የኢትዮጵያ አብዮተኞች ጉዞ .. 147

4. የአብዮቱ ማግሥት ........................ 149
5. ደርግና የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት ............. 159
6. ደርግ ከልጅ ሚካኤል እምሩ መንግሥት ጋር ............ 177
7. ዘውዱን ለመገርሰስ የተደረጉ የመጨረሻ ዝግጅቶች ........... 185
8. ደርግና ሌ/ጄነራል አማን ሚካኤል አንዶም ............ 191
9. ደርግና ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ................. 221
10. ደርግና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ................ 237
11. ደርግና አጼ ኃይለሥላሴ .................... 259
12. የጉልታዊውን ሥርዓት ማህበር ላዕላይና ታህታይ መዋቅር ስለማፈራረስ ....... 273


## ክፍል ሦስት


መሬት ለአራሹ ........................................275

13. የገጠሩን የእርሻ መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ የሚያደርገው አዋጅ ጥናትና መሰናዶ . 277
14. እድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ .................. 281
15. የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ገበሬዎች የቀበሌ ማህበር ወደ ከፍተኛ ንቃት፣ ድርጅት፣ ምርትና ማህበራዊ ይዞታ የማሸጋገር እምርታ ............. 285


## ክፍል አራት


የሠራተኛው መደብና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት ..........................289

16. የኢትዮጵያ ሠራተኞች መተዳደሪያ ሕግ ..................... 291
17. የሠራተኛው ማህበርና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት ........, 295
18. በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ................ 299


## ክፍል አምስት


በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ለሰላም የተደረጉ ጥረቶች ...............................305

19. አብዮታዊት ኢትዮጵያን ለማዳን አማራጭ የሌለው መድኃኒት ........... 307
20. ድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የሰላም ጥረት በኢትዮጵያዊያን መካከል ........ 311
21. ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ችግር ሰላማዊ መፍትሄ ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች ..... 317
22. ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለማምራት በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የተደረጉ የሰላም ጥረቶች ................ 323

# ማውጫ

## ክፍል ስድስት


**የውጭ ጥቃቶች** ........................................................ 361

23. ከውጭ የተሠነዘሩብን ጥቃቶች አብዛኛዎቹ በጠላቶቻችን ብርታት ሳይሆን በኛ ድክመትና የዋህነት ነው ........................ 363

24. በዳግማዊ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ........................ 365

25. በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ........................ 367

26. በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ........................ 371


## ክፍል ሰባት


**ሃገርንና አብዮትን የማዳን ጦርነት ዝግጅት** ........................................ 381

27. የታጠቅ ጦር ሰፈር ምስረታ ........................ 383

28. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሠራዊት አመሰራረት ........................ 389

29. ሕዝባዊ ሠራዊታችንን ለማስታጠቅ የተደረጉ ጥረቶች ........................ 395

30. የአብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አስተዳደር ........................ 399

31. የአብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት ........................ 403

32. ዓለም ያደነቀው የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ሰልፍ ......... 419


## ክፍል ስምንት


**ሃገርንና አብዮትን የማዳን ፍልሚያ** ........................................ 425

33. የሶማሊያን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጥቃት ለመከላከል በምሥራቅና በደቡብ ግምባር አብዮታዊ ሠራዊታችን ያደረገው ትግል ............. 427

34. በሐረርጌ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍላተሃገር ደጋማ አውራጃዎች ለሰባት ወራት የተደረገ የመከላከል ትግል ........................ 451

35. ከሞስኮ ስንመለስ በአገራችን የጠበቁን ሁኔታዎች ........................ 461

36. የኢሕአፓ አደገኛ ሴራ በቀሬ የጦር ግምባር ........................ 463


## ክፍል ዘጠኝ


**ከመከላከል ወደ ማጥቃት** ........................................................ 465

37. ለመልሶ ማጥቃት ውጊያ የተደረጉ መሰናዶዎች ........................ 467

38. ወራሪው የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል ሐረርጌን ለመያዝ ያደረገው የመጨረሻ ጥረት ........................ 471

39. የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ከመከላከል ወደ ማጥቃት መሸጋገር ....... 477

# ማውጫ

## ክፍል አስር


ማጠቃለያ ........ 483

40. ያሸነፈው አብዮት ነው! ........ 485

መዘርዝር ........ 489

ከየካቲት 1966 ዓ.ም እስከ መስከረም 1967 ዓ.ም ........ 489

ከመስከረም 1967 ዓ.ም እስከ መስከረም 1968 ዓ.ም ........ 492

ከመስከረም 1968 ዓ.ም እስከ መስከረም 1969 ዓ.ም ........ 493

ከመስከረም 1969 ዓ.ም እስከ መስከረም 1970 ዓ.ም ........ 493

የቃላቶች ትርጉም ........ 495

ዋቢ መጻሕፍት ........ 497

መጠቆም ........ 499

# ምስጋና

አብዮታችን ከተቀለበሰና መንግሥታችን ከፈረሰበት ማግሥት ጀምሮ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ ይዘኸው እንዳትሞት በማለት ከማንም ቀድሞ የቀሰቀሰኝ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጓድ ካሳ ከበደ፣

በተመሳሳይ ከመቀስቀስና ከማበረታታት ባሻገር ለታሪኩ በግብዓትነት የምፈልጋቸውን የተለያዩ ሰነዶች፣ መረጃዎችና መጻሕፍት እያፈላለገና እያሰባሰበ ከሰሜን አሜሪካ እስከ ደቡባዊ አፍሪካ ድረስ በመላክ ርዳታ ያደረገልኝ፣ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጓድ ፍስሀ ገዳ፣

በጓድ ፍስሀ አማካኝነት ተመሳሳይ ርዳታ ያደረጉልኝና ነገር ግን በዚህ ቅፅ ለደህንነታቸው ስል ስማቸውን ያልገለፅኩት ሁለት ጓዶች፣

በእጅ ጽሑፍ የተዘጋጀውን የታሪኩን ረቂቅ በኮምፒውተር የተየቡልኝን እህትማማች እህቶቼ ትዕግሥት እና ማህደር አየለ፣

ለመጽሐፉ ዝግጅት የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች በማቅረብ ብቻ ሳይሆን የእኔንም ጤንነት በመንከባከብ፣ በመላላክ እንደነሱ ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ከወሰደብኝ ጊዜ ባጠረ ጽፌ እንድጨርስ ከእኔ ባለመለየትና በመትጋት የረዱኝ ውድ ባለቤቴ ጓድ ውብአንች ቢሻው፣ልጆቼ ዶክተር ትምህርት፣ ዶክተር ትዕግሥትና ዶክተር አንድነት፣ እንዲሁም የልጅልጄ ወጣቷ ህሊና ለእኔ ብቻ ሳይሆን የታሪኩ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለ ውለታ ስለሆኑ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ።

ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም

መስከረም ወር 2004 ዓ.ም
ሐራሬ፣ ዝምቧብዌ

# የአሳታሚው ማስታወሻ

ዛሬ የእውቀት ፀሐይ ጠልቃብን ለሺህ ዓመታት በጋራ የተጓዘው ሕዝባችን አብሮ መራመድ እንኳ እንዳይችል እንምራህ በሚሉት ልጆቹ ወደሚያርፍበት ሳይሆን ወደሚፈጋበት፤ ወደ ሚድንበት ሳይሆን ወደሚጠፋበት ቁልቁለት እየመሩት ጭንቅ ላይ ይገኛል። ፀሐይ ሳታዳላ ለሁሉም ፍጡራን የቃልኪዳን ብርሃኗንና ሙቀቷን እንደምትለግስ ሁሉ፤ እውቀትም ሕዝባችንን ሳጠቃው ደዌ ፍቱን መድኃኒት ይሆነው ዘንድ መጽሐፍ እያሳተምን ማቅረቡን ከተያያዝነው እነሆ አስር ዓመታት አሳለፍን።

በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ከታሪካችን የተጓደለውን ለሟሟላት፣ የተጣመመውን ለማቃናት፣ የጠፋውን ለማግኘት ሙሉ በሙሉ ባንችልም የዛሬ አስር ዓመት ከነበረው በሃምሳ መጻሕፍት ያህል ለማሳደግ ችለናል። ከእነዚህ መካከል እነሆ በእጃችሁ ያለው መጽሐፍ አንዱ ነው።

አለመታደል ሆኖ የኢትዮጵያ የቀድሞ መሪዎች ካለፉ በኋላ የሚቀጥለው መንግሥት አልያም የታሪክ ጸሐፊዎች እንደ ገድል ያሰፈሩትን እንጅ ከግለሰቦቹ አንደበት እስካሁን ለመስማት አልቻልንም። እነዚህ ገድሎች ደግሞ መልካም ሆነው ሳለ ጸሐፊዎቹ የወደዱትን መልዓክ፣ የጠሉትን ደግሞ ጭራቅ ሲያደርጉ፤ የግለሰቡ ስብዕና በመሃከል ቤት ጠፍቶ መልካምም ሆነ እኩይ ሥራው የፖለቲካ መጠቀሚያ እንጅ ለታዳጊውና ለሚቀጥለው ትውልድ መማሪያ ሳይሆን እዚህ ደርሰናል።

በዚህ መጽሐፍ ግን እነሆ የቀድሞው ፕሬዝዳንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሥልጣን ላይ ሳሉ የመሩት አብዮት ስላካሄደው ትግል እራሳቸው እንደሚያስታውሱት ሲያካፍሉን የመጀመሪያው ርዕሰ ብሄር ይሆናሉ። ይሄ ደግሞ መልካም ጅምር ሲሆን የመጀመሪያው እንጅ የመጨረሻው እንደማይሆን ምኞታችንና ተስፋችንም ነው።

የአንድ ሃገር ርዕሰ ብሔር ሙሉ የሥራ ዘመን የግለሰቡና የሚመሩት መንግሥት ቢሆንም፤ ሥልጣን ላይ ሳሉ የሰሩት መልካምም ሆነ አሉታዊ ሥራ መስዋዕትነቱና ቅሪትነቱ ግን የዚያው ሃገር ሕዝብ ነው። ስለሆነም መሪዎቹ ይህን ሀገራዊ ትዝታ በረጋ አእምሮ ጽፈው የማስተላለፍ፣ ሕዝቡም አንብቦ፣ አገናዝቦ፣ መርምሮና አመሳክሮ ጥሩው ላይ ለመገንባት፣ መጥፎውን ደግሞ እንዳይደገም አድርጎ ማለፉ የሚጠበቅበት የዜግነት ድርሻው ይመስለናል።

እኛም እንደ አሳታሚ ድርጅት ዓላማችን በፖለቲካ፣ በዘር፣ በሐይማኖትና በግላዊ ማንነት ላይ ልዩነት ሳናደርግ ለሕዝብና ለታሪክ ጠቀሜታ አላቸው የምንላቸውን የተለያዩ ጥናታዊ ሥራዎች፣ ግላዊ ትውስታዎችን፣ አመለካከቶችንና የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶችን ያለተጽዕኖ ለማቅረብ ቃል እንገባለን።

ይህ መጽሐፍ እንደሌሎች ታሪካዊ መጽሐፍት ሁሉ በአንባብያን መካከል ብዙ ውይይቶችን እንደሚያስነሳ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ውይይት በወላጆቹና በታላላቆቹ መካሰስ ግራ ለተጋባና ለተደናቀረ ትውልድ መፍትሄ እንጅ ይባሱን ጆሮውን የሚያስይዘው፣ ዓይኑን የሚያስጨፍነውና አፉን የሚያስዘጋው እንደማይሆን እምነታችን ጽኑ ነው።

የዚህን ትውልድ የታሪክ ድርሻ በተለይም በጅምር የቀረውን የተማሪውን እንቅስቃሴና ሕዝባዊ ትግል አነሳስና ፍጻሜውን በቅጡ ሳናውቅና ሳንቋጭ ወደፊት መራመድ አዳጋች ነውና፣ በሚቀጥሉት ተከታታይ ዓመታት ፀሐይ አሳታሚ በአብዮቱ ዋዜማና ድህረ አብዮት የነበሩ የተለያዩ የትግል ታሪኮችን ከፖለቲካ እንቅስቃሴ መሪ ተዋንያን እይታ ይዘንላችሁ እንቀርባለን። ለሚቀጥለውም ትውልድ ሆነ አሁን ላሉ አንባብያን፣ በተለይ ለታሪክ ተመራማሪዎች ይህ መጽሐፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተስፋ እያደረግን፤ በመጽሐፉ ለተነሱ ነጥቦች አንባቢያን ገንቢ ውይይት እንድያደርጉ እንጋብዛለን።

ፀሐይ ውስጧ ባሉ የብርሃን ሕዋሳት እንደምትፈካና ሙቀቷን እንደምትለግስ ሁሉ፣ ለፀሐይ አሳታሚ ድርጅትም ጸሐፍት፣ አንባብያን፣ በአጠቃላይ አጋርና ተባባሪ ባልደረቦቻችን ዋልታና ማገራችን ናቸው።

ስለዚህም የሃያ ዓመታት ስራቸውን ላካፈሉን የመጽሐፉ ደራሲ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ በዚሁ ሥራ ላይ ቀና ትብብራቸውን ለለገሱን ለወ/ሮ ውብአንቺ ቢሻው እና ልጆቻቸው፤ ከውጥኑ አንስቶ ላልተለዩን ለአቶ ተሾመ ተስፋዬና ለአቶ ካሳ ከበደ፤ የመጀመሪያዎቹን ሰነዶች ላናበበን ለአቶ ወንድሙ ገዛኸኝ፣ እንዲሁም እነዚህን ሰነዶች ተራ በተራ በከፊል ለተየቡት ለሳራ ወንድሙ፣ ለኤልሳ ወንድሙ፣ ለሰብለ ወንድሙና ለፈትለወርቅ አራጋው ምስጋናችን እጅግ ከፍ ያለ ነው።

የመጨረሻውን ሰነድ አንብበው የቃላት እርማት ለሰጡን ለአቶ ክፍሌ ሙላት፣ ለራሔል ፋሲልና ለያሬድ መንግሥቱ፤ መጠቁሙን ላቀናበረው ለዳንኤል ያዕቆብ፤ ቃላቶቹን ለመረጡት ለሰሎሞን አባተና ለዮሴፍ ወንድሙ፤ ለሽፋኑ የሚሆን የትግላችንን ሐውልት ፎቶግራፍ ላነሱልን ለወንድወሰን ኃይሉና ለአዲስ ምንዳዬ፤ የሽፋኑን ምስል ላቀናበረችው ለኬሪ ብላክስቶን፤ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀምናቸውን ፎቶግራፎች እንድናገኝ ለረዱን ለአቶ ፈንታሁን ጥሩነህና ለአሜሪካ ኮንግረስ ቤተመጻሕፍት ባልደረባዎቹ፣ እንዲሁም በሎዮላ ሜሪማውንት ዩኒቨርሲቲ ለሚገኙ ባልደረቦቻችን በተለይም ለመምህር ቴረዝያ ዲ ቭሮም በዚህ ቀና ተግባራችሁ የፀሐይን የእውቀት ጮራ ከዳር እስከ ዳር እንዲዳረስ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጋችኋልና የአንባቢያን ባለውለታ ናችሁ፤ ለዚህም የጋራ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

በዚህ አጋጣሚ ድህረ ገጻችን [www.tsehaipublishers.com] ላይ በመሄድ በተለያዩ የኢትዮጵያ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያሳተምናቸውን መጽሐፍት እንድትጎበኙ፣ ብሎም ገዝታችሁ እንድታነቡ በአክብሮት እንጋብዛለን። መልካም ንባብ።

ኤልያስ ወንድሙ
አሳታሚና አርታኢ

ጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም

ሎስ አንጀለስ፣ አሜሪካ

# መቅድም

አገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ጥንታዊ ከሚባሉት አገሮች አንዷና ጥንታዊውን የሰው ልጅ ሥልጣኔ ተጋሪና አጋሪ፣ ሰፊ የየብስ ግዛት፣ የባሕር እመቤትና አኩሪ የትግል ታሪክ የነበራት ሆና ሳለ ታሪኳ በዝርዝር ተዘግቦ ለዓለም ሊቀርብ ይቅርና ለራሱ ለኢትዮጵያ ሕዝብም በውል አይታወቅም።

ይህንን ሰፊና ረጅም ታሪክ ከተቀበረበት ምሶ በማውጣት የሥነ ጽሑፍ ሕይወት ሰጥቶ ለንባብ ለማብቃት የሁለትና የሦስት ትውልድ ያላቋረጠ ጥረትና ራሱን የቻለ አንድ ታላቅ የባህል አብዮት የሚጠይቅ ይመስለኛል።

ጥንታዊና የበለጸጉ የራሳችን ቋንቋዎችና ፊደላት እያሉን ከሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ግኝትና ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ስለማንተዋወቅ ከዓለም ሕዝብ ወደ ኋላ እንደመቅረታችን መጠን በዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ እንዲሁ በመሆናችን የእኛ ቀደምት ወይም አንጋፋ ከሆኑ ተከታታይ ትውልዶች በጽሑፍ የወረስነው የታሪክ ቅርስ የለንም ለማለት ይቻላል።

አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን፣ ከያኒያንና የታሪክ ምሁራን ስለአገራችን ለመጻፍ ሲሞክሩ መረጃዎችንና የታሪክ ዋቢዎች ፍለጋ በአውሮፓና በአረብ አገሮች መዟዟርን ማዘውተራቸው ከሚያሳዝነን በላይ የራሳችንን ታሪክ ከባዕዳን መስማትና መማር ለመሸከም የሚያዳግት የሃፍረት ጫና ሆኖ ኖሯል። እስካሁንም አልተቃለለም።

ከታላቁ አብዮታችን ፍንዳት ማግስት ጀምሮ ይህ የሃፍረት ሸክም በጥቂቱም ቢሆን ደረጃ በደረጃ እየተቃለለ በአገራችን ሥነ ጽሑፍ የሚያድግበትን ቀና አቅጣጫ ለማስያዝና ፈጠን ባለ እርምጃ ለማራመድ ይቻል ዘንድ ከወዲሁ ከጥዋቱ ትኩረት ቢሰጠው ይበጃል የሚል አቋም ነበረን።

ስለሆነም ቀዳሚ ትኩረት ከተሰጣቸው አብዮታዊ ተግባሮች አንዱ ለመሆን በመቻሉ መሬት ለአራሹ የተሰኘውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የአያሌ ምዕት ዓመታት የዲሞክራሲ ጥያቄ መልስ ከመስጠት አኳያ በአፈፃፀም ረገድ ታላቅ ሚና ከነበረው ከእድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ጋር ሁለተኛውን የአጀንዳ ተራ ይዞ በደርጉ የእቅድ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንዲመከርበት ለውይይት ቀርቦ ነበር።

ቀናቶች ያስቆጠረ ጊዜ ወስደን በስፋትና በጥልቀት ስንወያይ ሥነ ጽሑፍን አስመልክቶ የምናነሳቸው ነገሮች አንዱ ከሌላው ጋር የተዛመደ ወይም በጥብቅ የተሳሰሩ ጉዳዮች በመሆናቸው ተጠላልፈውብን አንዱን ስናነሳ ሌላውን እየጎተተ ለማቆም ወዳዳገተ ሁኔታ ውስጥ ከተተን።

እነኚህ የተጠላለፉብን የምላቸው የውይይቶቻችን ጭብጦች፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ጥበብ፣ ሥነ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ከእነዚህ ጋር የሚዛመዱና በሕብረተሰብ የእድገት ሂደት ወሳኝነት ያላቸው ቁልፍ ጉዳዮች ነበሩ። እነኝህን በተናጠል እየመዘዝን በመወያየት

መመላለሱ ውይይቱን የትም እንደማያደርሰው በሁላችንም ዘንድ የጋራ ግንዛቤ በመገኘቱ ሁሉንም የሚያካትተው ቀፎ ባህል ወደ ተባለው ጉዳይ አመራን።

እንደሚታወቀው ባህል ለቁጥር የሚያታክቱ ረቂቅና ውስብስብ ጉዳዮችን ያቀፈ የሰውን ውስጥ ገንቢ ነገር ነው። ሥር ነቀል ማህበራዊ ለውጥ ለማካሄድ የሕዝብ ሕሊናዊ ሁኔታ ለአብዮት መዘጋጀት ወሳኝነት ስላለውና የኛም ወቅታዊ ፍላጎት ይሄው ስለነበረ ስለባህል ምንነት በጥልቀት ለመወያየትና ለመረዳት ሞከርን።

ባህል አዲስ የሞራል መሠረተ ሀሳብንና እንዲሁም አዲስ የአኗኗር ሥርዓትን ለማዳበር፣ ለሥነ ጽሑፍ፣ ለሥነ ጥበብ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝትና ርምጃ መንገድ ከፋች የሆነ የዕውቀት ቀፎ ነው። የሰው ልጅ ራሱን ለማወቅና ለማሻሻል ብሎም ለመለወጥ የሚያስፈልጉት ብዙ ኃይሎች ቢኖሩም የባህሉ ዓይነትና ደረጃ ግን ለግንዛቤው ወሳኝነት አለው ወደሚል መደምደሚያም ደረስን።

በመጨረሻም ባህል የዕውቀቶች ሁሉ ቀፎ፣ የዕውቀቶች ጎዳና ከፋች፣ ለሕብረተሰብ እድገት ወሳኝና የ ሕብረተሰብ ያለበት የእድገት ደረጃ መመዘኛ ከሆነ አገራችን ኢትዮጵያ የበለፀገ ባህል አላት እየተባለ የዓለም ኋላቀር ሰልፈኛ ጭራ የሆነችበት ምክንያት ምንድን ነው? ይህ ብዙ የሚነገርለት ጉልታዊ ወይም ፊውዳላዊ ባህል ባለንበት በ20ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ በምን ዓይነት የእድገት እርከን ላይ እንዳለ ያሳያል ብለን ራሳችንን ጠየቅን።

ስለባህል ምንነት ብዙ ቢባልም በሰው ልጅ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ብቻውን የቆመ ሳይሆን፣ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚው ጋር በፅኑ የተሳሰረ አንዱ የሌላው ነፀብራቅ ነው። ስለሆነም ላነሳነው ጥያቄ ያገኘነው መልስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኋላቀርነትና አሳፋሪ ድህነት የፖለቲካው ሥርዓት ከባህላችን ጋር ያለው ቁርኝት ግልፅ ከመሆኑ ባሻገር የባህሉን እድገት ያፈነውና ያዳፈነው መሰረታዊ ችግር፣ ሕዝቡን በማታለልና በመደለል፣ በመከፋፈልና በማደንቆር ለማኖር የጉልታዊው ሥርዓት የሚጠቀምበት መሣሪያው ማይምነት ነው።

በታሪክ አብዛኛው የሰው ልጅ አሳዛኝ ሁኔታዎች የሚመነጩት ከማይምነት ነው። ማይምነት የሰውን ልጅ ዓይን እንዳያስተውል ጋርዶ፣ እንዳያስብና እንዳይመራመር አፍኖ፣ ዘግቶና እግሩን አስሮ ርምጃውን ገቶታል። እንደ ኢትዮጵያ እጅግ ባረጀና ባፈጀ ኋላቀር ሥርዓት ማህበር የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሕዝቦች ውስጥ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ማይምነት ስር ሰዶ መኖር፣ ከማደግና ከመሻሻል ፈንታ እያደር የሚቆረቁዙበት የጊዜ ሂደት እየተራዘመ በሄደ መጠን የሞራል ዝቅጠትና የመንፈስ መራቆት በማስከተል ቀስ በቀስ የሰውን ልጅ ሰብዓዊ ባህሪያት በመለወጥ ከእንስሳት የማይሻል ›ከንቱና ባዶ ተንቀሳቃሽ ነገር ሊያደርገው ይችላል።

ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤ አንፃር ከጠቅላላው ሕዝቧ ከመቶ ዘጠና ሰባት በላይ በማይምነት መጋረጃ ዓይኑ የተጋረደ ሕዝብ ያላት አገራችን የወደፊት እድል ግልፅ በሆኑ በባህሉ ዘርፍ የሚካሄደው አብዮት በቅድሚያ በማይምነት ላይ እንዲያተኩር በመወሰኑ ብሔራዊ ፀረ-ማይምነት ዘመቻ በሃገር አቀፍ ደረጃ ታወጀ።

ማይምነትን ለመዋጋት በሚደረገው ትግል ሥነ ጽሑፍ በግምባር ቀደምትነት ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ በተጓዳኝ እሱም ራሱም ለእድገቱ ዳዴ ሊል የሚችልበት ርምጃዎች እንዲወሰዱ ተወሰነ። ይህንን ውሳኔ በተግባር ከመተርጎም አንፃር ሙያና ስጦታው እንዲሁም ፍላጎት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የብዕር ሰዎችና ደራሲዎችን በሃገር አቀፍ ደረጃ በማሰባሰብ በሙያ ማህበር እንዲደራጁ ተደረገ።

መጻሕፍት ጥራታቸው ተጠብቆ ከሕዝቡ የመክፈል አቅም ጋር በተመጣጠነ አነስተኛ ዋጋ የሚታተሙበትንና በገፍ የሚሰራጩበትን የማቀድና የመተግበር፣ የሥራውን ሂደት የመከታተልና አፈፃፀሙን የመቆጣጠር ኃላፊነትን ተግባሩ ያደረገ የኩራዝ አሳታሚ በመባል የሚጠራ፣ ዓላማው ትርፍ ሳይሆን ግን የንግድ ባህሪ የለበሰና ሕጋዊ ዕውቅና ያለው ድርጅት ተቋቁሞ ተልዕኮውን በብቃት ይወጣ ዘንድ በፓርቲያችን እየተመራ በመንግሥት እንዲደገፍ ተደረገ።

የሥነ ጽሑፍ ፍቅርና በሙያው የጠለቀ ዕውቀት ያላቸውን በሳልና ዕውቅ ምሁራንን ያሰባሰበ፣ በአገራችን ሥነ ጽሑፍ በተፋጠነ ሁኔታ የሚያድግበትን ዘዴ ለመንግሥት ከማማከር ሌላ በሥነ ጽሑፍ ጣዕምና ውበት እንዲሁም ለሕዝብ በሚሰጠው ጥቅምና አገልግሎቱ ረገድ ደራሲያንን የሚያበረታታ፣ ያለክፍያ ነፃ ምክርና የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት የሚረዳ የሥነ ጽሑፍ ቦርድ እንዲቋቋም ተደረገ።

ለሥነ ጽሑፍ እድገትና መሻሻል ይበጃሉ፣ ማይምነትን ለመዋጋት ይረዳሉ የተባሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ለማመቻቸት የተደረጉ ጥረቶች ነባርና በሳል ደራሲያንን በእጅጉ ሲያበረታቱት ወጣት ደራሲያንን ስላነሳሱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርትና የእውቀት ጥማት፣ ከጅምላ ማይምነትና እጅግ አሳፋሪ ድህነት አንፃር ሲታይ የትየለሌ ቢሆንም ፍፁም የማይናቅ የሥነ ጽሑፍ ምርት ማምረት ተጀመረ።

የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ከሞላ ጎደል፣ የኢማም አህመድ ግራኝን የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ ጨምሮ በ19ኛው ምዕት ዓመትና ከዚያ ወዲህ ባለው ጊዜ ኢትዮጵያን የመሩ ሦስት ነገሥታቶች ዘመነ መንግሥት ታሪክ ተፃፈ። የጥቂት ፀረ-ፋሽስት ሕዝባዊ ጀግኖች ገድሎችና ልብወለድ ድርሰቶችም በታሪካችን አይተነው በማናውቀው መጠን ብቅ ብቅ አሉ።

በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘመናዊ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ቋንቋ ጠበብት የጋራ ጥረት ከመዘጋጀቱ ሌላ በውጭ ሃገር ባዕዳን ፀሐፊዎች የተጻፉ ጠቃሚ መጻሕፍት በትርጉም ወደ አማርኛ ቋንቋ እየተመለሱ ለሕዝብ ቀረቡ። በዚህ ጊዜ ነበር በአፍሪካ አኅጉርና በአፍሪካዊ ቋንቋ የካርል ማርክስ የእድሜ ልክ ሥራ ውጤት የሆነው ካፒታል በመባል የሚታወቀው ታላቅ መጽሐፍ ቅፅ አንድ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ በትርጉም ተመልሶ ለሕዝብ ንባብ እንዲቀርብ የተደረገው።

ካፒታል የሰው ልጅ አዕምሮ ከደረሰባቸው ታላላቅ ሥራዎች አንዱ ነው። እነዚህና ሌሎችም ተዛማጅ ጥረቶች ከፀረ-ማይምነት ዘመቻ ጋር ተጣምረው በሕዝቡ ህሊና ውስጥ የሥነልቦና ለውጥ ፈጠሩ። አዲስ አስተሳሰብና አመለካከት፣ አዲስ የአነጋገር ዘይቤዎች ከመታየታቸውና ከመደመጣቸው ሌላ ማይምነትን ለሚታገለው ሰፊ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ተምሬያለሁ ለሚለው የሕብረተሰብ ክፍል ጆሮ ባዕድና እንግዳ የሆኑ አዳዲስ ቃላቶች መፍለቅ ጀመሩ።

ሆኖም እነዚህ አበረታች በጎ ክስተቶች ተስፋ የሚፈነጥቁ በጎ ጅምሮች እንጂ አዲሱን ተራማጅ ባህል ለመፍጠርና ለማዳበር ቀርቶ መሠረተ ትምህርቱንም ለሕዝቡ ከማዳረስ አኳያ ብዙ ሩቅ ነበርን። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማይምነት ጨለማ ማውጣት ማለት ፊደላትን ቅርፅና ድምፅ ማስተማር ብቻ አልነበረም።

ከኢትዮጵያ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ በማይምነት ላይ ዘመቻ አውጀው በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ ውጤት ካገኙ በጣም ጥቂት ወይም በአንድ እጅ ጣት ከሚቆጠሩ አገሮች መካከል ግምባር ቀደሞቹ ሶቭየት ሕብረትና ሕዝባዊት ቻይና ነበሩ። ከታላቁ የሩሲያ

የጥቅምቱ ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ በፊት ከሕዝቡ ከመቶ ሰባ አምስት የሚሆነው ማይም የነበረ ሲሆን የቻይና ማይማን መጠን ከኢትዮጵያ ጋር የሚቀራረብ ነበር።

ከእነዚህ ሁለት አብዮታዊ አገሮች ተመክሮ እንደተረዳነው በዘመቻ ከማይምነት ነፃ የወጣው ሕዝብ ከማንበብና ከመጻፍ ባሻገር በተጨማሪ አዳባሪ የሆኑ ድህረ መሠረት ትምህርቶችን ካላገኘ በጊዜ ሂደት ማንበብና መጻፍ እየተረሳ ማይምነት ተመልሶ ሲያገረሽ ታይቷል።

በኢትዮጵያም ይህ ሁኔታ እንዳይደገም ከመሠረተ ትምህርቱ ጋር በተጓዳኝ ሁኔታ ሕዝብ ማንበብና መጻፍን ሳያስልስ እንዲያዘወትርና ብሎም ባህሉ እንዲያደርገው ማድረግ ማይምነትን ከሃገር ለማጥፋት ወሳኝ ተግባር ነበር። በማይምነት ላይ የማያዳግም ዘላቂ ድል የመቀዳጀት ስኬታማነት አፈፃፀሙ ማንበብና መፃፍን ለመማር ያህል በቀለም ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን አፈር ገፊው ገበሬና ሠራተኛው መደብ የዕለትተለት ችግሮቻቸውን የፈቱባቸው፣ ኋላቀር የሆኑ ባህሎቻቸውንና ልማዶቻቸውን ለመለወጥ የሚረዱ፣ ኑሯቸውን ለማሻሻል የሚያስችሉ ሙያ ነክና ቴክኒካዊ እውቀት የሚሰጡ፣ ጠቅላላ ማህበራዊ ንቃትና የዕውቀት አድማስን የሚያሰፉ፣ የማምረትና የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያዳብሩ መሆን ነበረባቸው።

ለእነዚህ ዓላማዎቻችን ተፈፃሚነት በመስክ ካሰለፍናቸው የሁለተኛና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ኋላ የተለያየ ሙያ ያላቸው ምሁራንና የፈጠራ ሰዎችን፣ በተለይም የብዕር ሰዎችን ለማንቀሳቀስ ጥረት በምናደርግበት ጊዜ ነበር በርካታ ደራሲያንና የታሪክ ምሁራን በግልም በወልም እየቀረቡ የአብዮቱ ታሪክ ሳይዘገይ ከስር ከስሩ ይፃፍ በማለት ያሳሰቡን።

በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በታሪክ መምህርነት የተሰማሩ ምሁራን፣ ወጣቱን ስለ አገሩ ታሪክ ለማስተማር በማንችልበት ሁኔታ ላይ ስለምንገኝ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ እስከ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምስረታው ድረስ ያለውን የአስር ዓመት ታሪክ ለመፃፍ ቅድሚያውን በመስጠት አጣዳፊ ተግባር አድርጎ መሥራት አስፈላጊ ነው ሲሉ የደራሲያን ማህበር አመራር አካላትም ሀሳቡን ከመደገፍ ባሻገር በሥራውም ለመሳተፍ ያላቸውን ፍላጎት በመግለፅ ግፊት አደረጉ።

'ለወጣቱ ትውልድ የአገሩን ታሪክ ለማስተማር በማንችልበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን' ተብሎ የተነገረው ስሞታ ብዙዎቻችንን ስላሳሰበን በጉዳዩ ላይ ጊዜ ወስደን በጥልቀት ሳንወያይበት ታሪኩ እንዲጻፍ ከአሳሰቡት ምሁራን መካከል ፈቃደኛ የነበሩትን በሳል የሥነ-ጽሑፍና የታሪክ ባለሙያዎች ያሰባሰበ አንድ የታሪክ አርቃቂ ኮሚቴ በማቋቋም ትግላችን በተሰኘ ስያሜ በአስረኛው አብዮት በዓል ለሕዝቡ የሚቀርብ፣ እንደተባለውም ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ እስከ ሪፐብሊኩ ምስረታ ድረስ ያለውን የአስር ዓመት ታሪክ ረቂቅ የማስረቀቁ ሥራ እንዲጀመር ተወሰነ።

የታሪክ አርቃቂ ምሁራን ኮሚቴውም የሚከተሉትን ግለሰቦች ያካተተ ነበር፦

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ጓድ ሻለቃ ዳዊት ዘካሪያስ | የኮሚቴው ሰብሳቢና አስተባባሪ |
| 2ኛ/ ጓድ ፍሰሀ ዘውዴ | የኮሚቴው ፀሃፊ |
| 3ኛ/ ዶክተር መርዕድወ/አረጋይ | የኮሚቴው አባል |
| 4ኛ/ ዶክተር ባህሩ ዘውዴ | የኮሚቴው አባል |
| 5ኛ/ ዶክተር ብርሃኑ አበበ | የኮሚቴው አባል |
| 6ኛ/ አቶ ሽፈራው በቀለ | የኮሚቴው አባል |

የኮሚቴው አባላት ለሥራው በነበራቸው ፈቃደኝነትና ትጋት የመጀመሪያው ረቂቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ ቀረበልን። ረቂቁን ተመልክተን አስተያየታችንን መስጠት የነበረብን ጥቂት የአመራር አካላት በተሰበሰብንበት ጊዜ ስለ ረቂቁ ይዘት ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰነዘር "የፖለቲካዊ ሥርዓት አመራር አካላት በሥልጣን ላይ እያለን የታሪኩ ፀሐፊዎች ያላንዳች ስጋት ፍርጥርጥ አድርገው ለመጻፍ ድፍረቱ ይኖራቸዋል ወይ?" "ምናልባት ፀሐፊዎች ለዚህ ብቃት አላቸው ብለን ራሳችን ብናሳምንም እንኳን አንባቢው ሕዝብ ፀሐፊዎቹ በተሟላ ህሊና የፃፉት ታሪክ ነው ብሎ ይቀበለዋል ወይ?" በተሰኙ ጥያቄዎች ላይ ጊዜ ወስደን በስፋትና በግልፅነት ተወያየን። ባነሳናቸው ጥያቄዎች ህሊናችን የሚቀበለው አጥጋቢ መልስና ምክንያት ልናገኝ ስላልቻልን አብዛኛዎቻችን ረቂቁ ወደፊት ጊዜና ሁኔታዎች በፈቀዱና በጠየቁ ጊዜ ለሚፃፈው ታሪክ በግብዓትነት እንዲያገለግል ተስማማን።

ታሪክን የመፃፍ ጉዳይ ለራሱ ለታሪኩና ለሕዝቡ መተው ይኖርብናል ከማለት ባሻገር፤ አንድ ሀቀኛ ሕዝባዊ አብዮት ተግባሩ መሆን ያለበት ታሪክን መሥራት እንጂ የራሱን ታሪክ መፃፍ አይደለም በማለት የተዘጋጀውን ረቂቅ በቤተ-መዘክር እንዲቆይ ባንወስን ኖሮ ይህ ትግላችን የተሰኘ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ የመጀመሪያው ክፍል ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ተከታታዮቹ ጭምር ባለፉት ሀያ ዓመታቶች ውስጥ ተጽፈው ለሕዝብ በቀረቡ ነበር። ታሪኩን የማርቀቅ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከተለያዩ የፓርቲያችን ተዋረድ አመራሮችና የአስተዳደር ጠገኖች፣ ከሕዝባዊና ከሙያ ድርጅቶች ለታሪኩ ግብዓት የሚሆኑ ዘገባዎችንና መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሲባል ወሬው በሰፋት ተዛምቶ ስለነበር የተዘጋጀው ረቂቅ በበላይ አካል ይሁንታን ባለማግኘቱ ከሕትመት ታገደ መባሉ በሕዝብና በአብዮታዊ ሠራዊታችን ዘንድ አስደሳች ዜና ስላልነበረ የስሜት ማካካሻ ይሆን ዘንድ ከጦርነቱ ድል በኋላ እናደርገዋለን ብለን ያቀድነውን እቅድ በመለወጥ ለአገራቸው ክብርና ዳር ድንበር፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ሲፋለሙ ጥለው ለወደቁና ለሚወድቁ ጀግኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ትግላችን የተሰኘ ሐውልት በአገሪቱ ዕርሰ ከተማ እንዲቆምላቸው አደረግን።

ታሪክ የመፃፉን ተግባር ለራሱ ለታሪክና ለሕዝቡ እንተወው በሚለው አቋማችን ጸንተን ለአገራችን አንድነት፣ ለአብዮቱ ደህንነትና ለሕዝቡ የተፋጠነ ማህበራዊ እድገት ስንታገል በሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም፣ በከሃዲዎቹና አብዮት ቀልባሾቹ ሩሲያዊያን በተጎነጎነ ታላቅ ሴራ የተደገፉትና የተመሩት የውስጥ አድህሮት ኃይላት፣ በመምሰልና በማስመሰል አብረውን የተሰለፉ ከሀዲዎች ከያሉበት ተጠራርተውና ተረባርበው የኢትዮጵያ ሕዝብ እምጦ የወለደውን አብዮት ቀለበሱት። የወጠነውንና የገነባውን ሁሉ አፈረሱት።

ለአገሩ ታማኝና አለኝታ፣ ለሕዝቡ መከታና የሰላሙ ዋስትና የሆነውን ሕዝባዊና አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት በመበተን ከአንድ አናሳ ብሔረሰብ መካከል በወጡ ጎጠኞችና የባዕድ ምንደኞች፣ ሃገርን በመገንጠል የእናት ጡት ነካሽና አባት አሰለቃሽ በሆኑ ሕዝብ አሸባሪ ቀማኛ ፋኖዎች ተኩት።

ኤርትራን ገንጥለው በሕብረት አዲስ አበባ የገቡት ምንደኞች ኢትዮጵያ ቅኝ ሆና፣ በቋንቋና በጎጥ ተሸንሽና ዳግም የባሕር በር አልባ ሆነች። የአገራችን ታሪካዊ ጠላቶችን ክለው አገራቸውን የወጉ ምንደኞች ራሳቸውን ታጋይና የነፃነት አርበኛ፣ የፍትህ ዳኛ፣ እነሱ ከሳሽም ፈራጅም ሲሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር አጥፊና የጦር ወንጀለኛ ተብሎ ፈረጁን በመስማቴ ለታሪክና ለሕዝቡ የተውነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ እኔ እራሴ ለመፃፍ ተገደድኩ።

አስፈላጊው ነገር ሁሉ ባለበትና በተመቻቸበት፣ ለታሪኩ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ሁሉ በተገኙበት በበርካታ የታሪክ ምሁራን ከሀያ ዓመት በፊት ሊፃፍ የነበረውን ትግላችንን ለመፃፍ እያሌ ችግሮች ገጥመውኛል። ስለአንድ ታላቅ ሕዝባዊ አብዮት ለመተረክ የሚያስችል መሰናዶ ቀርቶ ጥቂት ሰነድ ወይም የጽሑፍ መረጃዎች እንኳን በእጄ ባለመኖራቸው ትግላችንን ለመፃፍ የሞከርኩት አእምሮዬ በዘገባቸው ትዝታዎቼ ብቻ ነው ለማለት እደፍራለሁ።

በፀረ-ማይምነት ዘመቻ ዓይኑን የገለጠው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግላችንን ማንበብ እንዳይጠጥርበት በሚያዘወትረው አማርኛና በለመዳቸው ቃላቶች ለመጠቀም ሞክሬያለሁ። በፀረ-ማይምነት ዘመቻው መሠረት ትምህርቱን ሲማር አሀዞችን ያወቀውና በእነሱም እየተጠቀመ የሂሳብ ስሌት የተማረው በአውሮፓዊ አሀዞች ስለነበረ በዚህም ረገድ ችግሩን አቃልል ይሆናል በማለት ትግላችንን ለመፃፍ የተጠቀምኩት በአውሮፓዊያን አሀዝ ነው። አብዮታችን ለሰው ልጅ ሁሉ ነፃነትንና እኩልነት የቆመው የዓለም አብዮት አካል በመሆኑና አንዳንድ ቃላቶች በአብዮታዊያን ሰፈር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ስለተወደዱና በሌሎችም አስፈላጊ ምክንያቶች አልፎ አልፎ ባዕዳን ቃላቶችን ተጠቅሚአለሁ።

የቀን አቆጣጠርን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ተብሎ ካልተገለጠ በስተቀር የተጠቀምኩት በኢትዮጵያዊያን የቀን አቆጣጠር ነው።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከተቀጣጠለበት እስከ ተቀለበሰበት ድረስ ያለውን የጊዜ መጠን ከሌሎች መሰል ታላላቅ ሕዝባዊ አብዮቶች ጋር ስናነፃፅረው በጣም ለጋና በአጭር የተቀጨ አብዮት ቢሆንም በአሥራ ሰባት ዓመታት ውስጥ ያደረገውን ፈጣን ጉዞ፣ ያስተናገዳቸውን ሕዝባዊ ተግባሮች፣ የገጠሙትን ፈተናዎችና የጠየቁትን መስዋዕትነት በሦስት ተከታታይ ቅፆች ለማቅረብ ተገድጃለሁ።


የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ መሪ ግለሰቦች የሚመጡና የሚሄዱ አላፊዎች ሲሆኑ ሃገርና ሕዝብ ግን ዘላለማዊ ናቸው። ይህም ቢሆን በአንድ ታሪካዊ ወቅት መንግሥታት፣ የፖለቲካ ደርጅቶች ወይም ግለሰቦች ያከናወኗቸው ገንቢም ሆነ አፍራሽ ተግባሮች ማንም ወደደ ጠላ የዚያ ሃገርና ሕዝብ ታሪክ ናቸው።

በአብዮት የትግል ጎራ ወይም አሰላለፍ ላይ ብቻ በማተኮር፣ በብቀላ፣ የአጥቂነት ወይም የተከላካይነት ስሜት አጥቅቶኝ በማጋነን ወይም በማቃለል ታሪኩን ላለማዛባት በተቻለኝ መጠን ከራሴ ጋር ታግያለሁ፣ ከህሊናዬም ጋር ተሟግቻለሁ።

በአንባብያን ዘንድ ታሪክ ፀሐፊዎችና ልብወለድ ደራሲዎች የሚመዘኑት በሥነ ጽሁፋቸው ጣዕምና ውበት ብቻ ሳይሆን ለአንባብያንም በሚሰጡት ትምህርት ነው የሚለውን ሕዝባዊ አስተያየት እኔም እጋራለሁ።

ይኸ ትግላችን የተሰኘ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ ትምህርት በመስጠቱ ረገድ ስለሚኖረው ፋይዳ ፍርዱን ለአንባቢው እተዋለሁ። ትግላችንን ለመፃፍ የሞከርኩት የመተረኩና የመድረሱ ሞያውም ሆነ ልምዱ ስለሌለኝ በአንባቢ ዘንድ እወደሳለሁ ብዬ ሳይሆን፣ የእኔ ትውልድ በቅርቡ ያከናወነው አብዮታዊ ታሪክ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በተነሱ ምንደኞች ተራክሶና አረም ለብሶ እንዳይቀር ለማድረግ ነው።

ይኸ ትግላችን ብዬና መልሼ የትግሉ ተዋናይ ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የማበረክተው ታሪክ በዓለማችን ከተከናወኑት በጣም ታላላቅ አብዮቶች አንዱ ነው ተብሎ




ለኢትዮጵያ አንድነት፣
ለሕዝቡና ለአብዮቱ ደህንነት፣
ከውጭ ወራሪዎች፣
ከውስጥ ገንጣዮችና አስገንጣዮች ጋር
ሲታገሉ ሞተው ለወደቁ
የሕዝብ ልጆች የቆመው ትግላችን
የመታሰቢያ ሐውልት
ለሕዝብ ተመርቆ ሲከፈት

በዓለም አብዮታዊያን የተመሰከረለትና በአመዛኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከማለት ይልቅ የአፍሪካ አብዮት እየተባለ በሰፊው የተነገረለት ታላቅ አብዮት ነው።

ትግላችን ስሙ እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ አንድ ትውልድ በሙሉ ቀፎው እንደተነካበት የንብ ሠራዊት ተቆጥቶ በመነሳት ገበሬው ከገባርነት፣ የሠራተኛውን መደብ ከምንዳ ባርነት፣ ጠቅላላውን ባተሌ ሠርቶአደር ሕዝብ ከድንቁርናና አረንቋና እጅግ አሳፋሪ ከሆነ የዘላለም ድህነት መንጥቆ በማውጣት ራሱንና አገሩን ለመለወጥ በጀመረው ትግል መሪር መስዋዕትነትን ከፍሎ የትግሉን ጣፋጭ ፍሬ ሳይቀምስ፣ አንድነቱንና ሰላሙን ሳያገኝ እንደገና የጨለመበት አሳዛኝ ሰፊ ሕዝብ ልሳን እንጂ አንባቢን በደስታ ለመመስጥ የተዘጋጀ የሥነፅሁፍ ድግስ አይደለም።

የየካቲት አብዮት ግምባር ቀደም ታጋዮች በዚያ እጅግ አስፈሪ በነበረ ጨለማ፡ ሕዝብ የጣለባቸውን አደራ የተቀበሉትና ያንን ከባድ ኃላፊነት የተሸከሙት በቅድሚያ እርስ በራሳቸው ተዋውቀውና ተጠራርተው፣ ለሥልጣን በመቋመጥ ዶልተው፣ በጎሳ ወይም በፖለቲካ ማህበር ተደራጅተው ከቤታቸው የወጡ አልነበሩም፤ ፈቃደኝነታቸውን እንኳ ሳይጠየቁ ሃገርና አብዮት አድኑ ብሎ ሕዝብ ባደረገው ጥሪ በነፍስ ወከፍ እየተመረጡ ለመስዋዕትነት የቀረቡ እንጂ። ሁሉም ከደሃው ሕብረተሰብ አብራክ የወጡ፣ በፅኑ የሃገር ፍቅራቸውና ብሔራዊ ስሜታቸው፣ ለሕዝብ የነበራቸውን ወገናዊነትና የለውጥ አቀንቃኝነት በመመልከት የተመረጡ የሕዝቡ የቀውጢ ቀን ልጆች ነበሩ።



የትግላችን ሐውልት

እነዚህ ግምባር ቀደም ታጋዮች አዲስ አበባ በሚገኘው የአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ ሰፈር በመባል በሚታወቀው ግቢ በመገናኘት መክረውና ዘክረው የቀየሱት ዓላማ የመነጨው፤ እጅግ ካረጀውና ካፈጀው፤ ራሱን መለኮታዊ ኃይል አድርጎ ከሚቆጥረው ጉልተኛ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ መደብ መዳፍ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ፈልቅቆ ለማውጣት በነበራቸው ፍላጎት ነው።

የእነዚህ ግምባር ቀደም ታጋዮች ዓላማ የመነጨው ከክህደት ሳይሆን ኢትዮጵያ የዓለም ኋላቀር ሰልፈኞች ጭራ ከመሆኗ ባሻገር ሕዝቡ ከድህነት ወለል በታች ቆሞ፤ ራሱን መመገብ ተስኖት ከባዕዳን እህል ተመፅዋች በመሆኑ፤ ራሱን ማልበስ አቅቶት የሰው ውራጅ አልባሳት ተቀባይ በመሆኑ የተነሳ ለሃገርና ለወገን ከመቆጨትና ከመቆርቆር ስሜት ነው። ሃገርና አብዮትን በማዳን፤ ኢትዮጵያን ጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆምና ብሎም ሕዝቡን የፖለቲካ ሥልጣን ሙሉ ባለቤት ለማድረግ ነው። አኩሪ ታሪካችንን ለማርከስ ሳይሆን በስር ነቀል ማህበራዊ ለውጥ ኢትዮጵያን ለማስቀደምም ነው።

አንድ ሀቀኛ አብዮት የመደብ ሹም ሽር ማለት ነውና፤ ገዥና ተገዥዎችን፤ በዝባዥና ተዝባዦችን እኩል በአንድነት በተለይም በመጀመሪያው አፍላ የአብዮት ዘመኑ ማስተናገድ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከርም ነው።

አብዮታችን ብቻውን ሳይሆን ከመላው ዓለም አብዮት ጋር የገጠመው የመጨረሻ እጣው ምንም ይሁን ምን አድህሮት ኃይላት እንደዚያ የፈሩትና ከያሉበት ተጠራርተው የተረባረቡበት ጥራቱንና ጥንካሬውን በመገንዘባቸው ነው። አንድ ሀቀኛ ሕዝባዊ አብዮት ታላቅነቱ መመዘን ያለበት የሕዝቡ ፀሮች ደህውን እየዘረፉና እየገፈፉ እነሱ የተበደሉ መስለው በሚያቀርቡት ክስና፤ እነሱ እየገደሉና እየገረፉ ግን እንደ ጅራፍ በሚያሰሙት ጩኸት ሳይሆን ለብዙሃኑ ሰፊ ሕዝብ በሚያስገኘው ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅም አንፃር ነው።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በአሥራ ሰባት ዓመታት ውስጥ ያከናወናቸውን አያሌ ዲሞክራሲያዊ ተግባሮችና የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀዳጃቸውን ድሎች ሁሉ ለጊዜው ወደጎን በመተው፤ ከብዙ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ ጎታችና ጨቋኝ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር የተላቀቀበትና የሪፐብሊክ መንግሥት ምስረታውን ብቻ ብንመለከት፤ ጠላቱንና ወገኑን በውል ለይቶ የሚያውቅ፤ የሚጎዳውንና የሚጠቅመውን የሚገነዘብ፤ የነቃና ውለታ የሚገባው ሕዝብ በአገራችን በሚፈጠርበት ጊዜ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በኢትዮጵያ ታሪክ ያለወደር ተንፈራጦ በተከታታይ ትውልዶች ህሊና ለዘላለም የአብዮት እንቁ ሆኖ ሲያበራ ይኖራል።

# መግቢያ

በኢትዮጵያችን የቡርዧው አብዮት ተካሂዶ፣ ምርትና የምርት ኃይሎች አድገው፣ አገሪቱ በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ተደራጅታ፣ የሠራተኛው መደብ ሰፊ ማህበራዊ መሠረት አግኝቶ፣ የፖለቲካ ባህል የዳበረባት ሃገር አልነበረችም።

የሕዝቡ ማህበራዊ ንቃተ ህሊና ጎልብቶ፣ መሪና አዝማች የሆነ የፖለቲካ ድርጅት አግኝቶ ስር ነቀል ማህበራዊ ለውጥ የሚያስፈልጉ ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ጊዜ የገነፈለ በመሆኑ በባዕዳንም፣ በኢትዮጵያውያንም ዘንድ ግብታዊ የተሰኘ ስም ቢሰጠውም መንስኤና ምክንያት አልባ የሆነ አየር ወለድ ክስተት ወይም ዱብ እዳ አልነበረም።

ለብዙ ዘመናት የተካበተ ችግር፣ ብሶትና ሰቆቃ እንደ ብል የበላውና በእጅጉ የተማረረ ሕዝብ ለአያሌ ዘመናት አምጦ የወለደው አመፅ ነው።

በእነዚህ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ከኢትዮጵያ ብዙ ቀደም ብለው በአውሮፓ የተካሄዱትን የሶሻሊስት አብዮቶች ፈለግ ለመከተል ካለመቻሉም በላይ ለጊዜው አስፈላጊም ስላልነበረ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገሮች የማህበራዊ ለውጥ ሂደት ይበጃል ተብሎ የታመነበትን የአዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርህ በመከተል የሶሻሊስት አብዮት ለማካሄድ በእድገት ኋላ ቀርነት ምክንያት የተጓደሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሂደት ለሟሟላት እንዲቻል የተመራ ትግል ነው።

የትግሉን ዝርዝር ባህሪ ወደ መተረኩ ከማምራቴ በፊት የረጅም ጊዜ ነፃነትና ህልውና ብቻ ሳይሆን አኩሪ የትግል ታሪክ ያላትና ቀደም ባለው ጊዜ ጥንታዊው የሰው ልጅ ሥልጣኔ የተንፀባረቀባትና ከዚያ ጊዜ አንፃር አመርቂ ዕድገትም የታዬባት አገራችን እያደረች በመቆርቆዝ የልጆችዋ መኩሪያ ከመሆን ይልቅ ማፈሪያ እየሆነች በመሄዷ፣ ሥርነቀል ማህበራዊ ለውጥ ወይም አብዮት ግድና ብቸኛ መፍትሄ የሆነበትን ምክንያት ለማስገንዘብ ይሞከራል።

ይህን ለማድረግ ደግሞ፣ ጥንታዊውን፣ የመካከለኛውን ጊዜና ኋለኛውን የዘመነ ኢምፔርያሊዝም ታሪካችንን ከውጭውም ዓለም አንፃራዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ፣ በጣም አጠርና ጠቅለል ባለ ሆኔታ አበይት ክስተቶችንና የታሪክ አንኳሮችን ወደኋላ መለስ ብለን መቃኘቱ አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህ ታሪክ መቅድም ላይ እንደገለጽኩት በኢኮኖሚው፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደኋላ እንደመቅረታችን ሁሉ በሥነ ጽሑፍም ካለብን ድህነት የተነሳ ከቀደምት ኢትዮጵያውያን በጽሑፍ የወረስነው የታሪክ ቅርስ አመርቂ አልነበረም።

እዚህ ላይ ይበልጥ የሚያሳዝነው ይህ ችግር የእኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካ ሕዝብ ችግር መሆኑ ነው። አፍሪካዊያን አፈታሪክ እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተፃፈ ታሪክ የለንም። ይህንን ማለት ግን፣ ታሪክ የለንም ወይም ለጥንታዊውና ለአኩሪው ታሪካችን ማስረጃ የለንም ማለት አይደለም።

ከሁሉ በፊት ልንገነዘበው ወይም ልናስታውሰው የሚገባ ነገር፣ አፍሪካ የሰው ዘርና የሰው ልጅ ሥልጣኔ ምንጭ መሆኗን ነው። በማስረጃም ረገድ ከጽሑፍ የጎሉ ምናልባትም የተሻሉ የድንጋይ ጽሑፎች፣ ሥዕሎች፣ ቅርፃቅርፆችና ሐውልቶች፣ ከወርቅ፣ ከብርና ከነሀስ ወዘተ የተቀረፁ ንዋየ ቅድሳትም ሆኑ ንዝቦችና ሌሎችም አያሌ ማስረጃዎች ይገኛሉ።

አፍሪካዊያን ታሪካችንን በጽሑፍ ለማስፈርና ለተከታታይ ትውልድ ለማቆየት ያላስቻለንን ድክመት በመጠቀም የቅኝ ግዛት ኃይሎችና በተለይም ዘረኞች ባህልና ታሪካችንን በተቻላቸው ሁሉ ለማጉደፍ እንደሞከሩት በእኛም ሃገር በኢትዮጵያ የበቀሉ የሰው እንክርዳዶች ከዓለም ዓቀፍ ኢምፔርያሊዝምና አድህሮት ኃይሎች ጋር ወግነው አብዮት መቀልበሳቸው ሃገር መገንጠልና ማስገንጠላቸው ያነሰ ይመስል ታሪክን ከማጣመምና ከማርከስ ባሻገር ክህደት የወለዳቸው አዳዲስ ታሪኮችን እየፃፉልን ነው።

ሻዕቢያ፡ ወያኔን መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ሱሪም በማስታጠቅ ኮትኩቶ ያሳደገው አባቱ በመሆኑ፣ ወያኔ ውለታ ለመክፈል ሲል "የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት?" በማለት በ1979 ዓ.ም በፃፈው መጣጥፍ ላይ ያላንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ "ዛሬ ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው ሃገር ምኒልክ የዛሬ መቶ ዓመት የፈጠራት ነች።" ከማለት ሌላ፣ ከኢትዮጵያም ምድር ወጥቶ "የዛሬዎቹ ነፃ አፍሪካዊ ሕዝቦች ታሪክና አገራዊ ወይም መንግሥታዊ ህልውና የጀመረው ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ወረራ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት አገራዊ ህልውናና ታሪክ አልነበራቸውም" እስከ ማለት ደርሷል።

የወያኔ ክህደት፣ ቅሌት፣ ውሸት፣ የጎጥ ፖለቲካ ታክቲትና አንገፍግፎት፣ የሚያደርገው ጠፍቶት ድንግዝግዝ ባለ ወቅት ውስጥ የወደቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ "ለመሆኑ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምንድናቸው? ኢትዮጵያዊያንስ እነማን ናቸው?" ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ላይ ይገኛል።

ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ በዚህ መጽሀፍ አማካኝነት መልስ ለመስጠት አዳጋች ቢሆንም፣ ቢያንስ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆኑ፣ ኢትዮጵያዊያንስ እነማን እንደሆኑና ወያኔ በአንድ መቶ ዓመት እድሜ ከወሰነው ባሻገር ታሪካችን የሦስት ሺህ ዓመታት ብቻም እንዳልሆነ ለመጠቆም ይሞከራል።

# ጥንታዊት ኢትዮጵያ

አለቃ ታዬ ገብረ-ማርያም ከተለያዩ ጥንታዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት ማለትም፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከቀደሞ ፍትሐ-ነገሥትና እንዲሁም ከክብረ ነገሥት፣ የግብጽ፣ የግሪክ፣ የአረብ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የጀርመንና የኢጣሊያን ወዘተ ዜጎች የሆኑ ጥንታዊ የታሪክ ሊቃውንትን በስም በመዘርዘር በተለያዩ ጊዜያቶች ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ከፃፏቸው የታሪክ መጽሐፍት በጥንቃቄ ቃርሚ ያዘጋጀሁት ነው በማለት *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ* ብለው የፃፉት ታሪክ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የታሪክ መረጃ ነው።

አጠርና ምጥን ባለ ቋምንገር አዘል መጽሃፋቸው ዓመተ ዓለም እየተባለ በሚጠራው ጊዜ ከአንድ ሺህ ዘጠኝ እስከ አራት ሺህ አምስት መቶ ድረስ ባለው የጊዜ ክልል ውስጥ ከእስያ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከግብጽ በተለያዩ ምክንያቶችና እንዲሁም ጊዜያቶች በነፍስ ወከፍ፣ በቤተሰብ፣ በቡድንና በተደራጀ መልክ ማለትም በነገድ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተለይም በቀይ ባሕር ጠረፋችን አካባቢና ዳርቻ ይኖር ከነበረው ነባር የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጋር በአመዛኙ በመጋባባት፣ በመፈላለግና በመተሳሰብ በሌላ ጊዜ ደግሞ

በመጋፋት ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገብተው በመሥፈር ተሰባስበው በመደራጀትና በመስፋፋት ነባሩን የኩሽ መንግሥት በመጣል የፖለቲካ ሥልጣን ይዘው ነባሩን የኩሽ ሕብረተሰብ በመበረዝ ሁሉን ያካተተ አዲስ ባሕርታዊ መንግሥት መሰረቱ ይላሉ። ባሕርታዊ የሚለው ቃል የሳቸው ሳይሆን የሳቸውን አባባል በተሻለ ይገልጣል ብዬ እኔ የተጠቀምኩበት ማብራሪያ ወይም ማዳበሪያ ቃል ነው።

አገራችን ዛሬ የምትጠራበትን ኢትዮጵያ የተባለውን ስም ያገኘችው የነገደ ዮቅጣን አባል ወይም እሳቸው እንደሚሉት ዝርያ የሆነውና ከሦስት ሺህ ስድስት መቶ እርባ አራት እስከ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ዓመተ-ዓለም ድረስ የአገሪቱ መሪ የነበረው ኢትዮጲስ የተባለው ንጉሥ በዘመነ መንግሥቱ አገሪቱን ኢትዮጵያ የተሰኘ ስም አሰጣት ይላሉ።

አለቃ ታዬ በዚሁ ጽሁፋቸው (ገፅ 56) ጥንታዊት ኢትዮጵያ በሚለው ርዕስ ስር ስለ አገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት፣ ስለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የዕድገት ደረጃዋና ሥልጣኔዋ በመጠቋቆም፣ በአራት መቶ ሃያ አራት ዓመተ-ዓለም የነበረና የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ግሪካዊ ታላቁ የታሪክ ምሁር ሄሮዶትስ፣ እሱ ከኖረበት ዘመን በፊት አሥራ ስምንት የኢትዮጵያ ነገሥታቶች ምስርን ጨምረው ይገዙ እንደነበረ መፃፉን ይገልፁና ጥንት ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ ሃገር ነበረች ይላሉ።

ስለቆዳዋ ስፋትም ሲገልፁ ድንበሮቿ በምሥራቅ የሕንድ ውቂያኖስ፣ በደቡብ ሲናር (ሱዳን ማለታቸው ነው)፣ በምዕራብ ነጭ አባይ፣ እና በሰሜን ቀይ ባህር ይሉና፣ ከቀይ ባህር ባሻገር ያለው የደቡብ አረቢያ ደቡባዊ ክልል የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያን ግዛት ከተቀሩት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር የሚያዋስናት መሆኑን ይገልፃሉ።

ጽሑፋቸውን በመቀጠል፣ ዛሬም ኢትዮጵያ ሰፊ ሃገር ናት ግን እንደ ጥንቱ አትሆንም። በጠረፍ ላይ የነበሩ አገሮች ዛሬ በብዙ ክልሎች ተከፋፍለው ከኢትዮጵያ የተነጠሉ ልዩ ልዩ መንግሥታት ሆነዋል ይላሉ። እንደተለመደው ባዕዳንም ይሁኑ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ጸሃፊዎች በተለያዩ ጊዜያቶች ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በቁንጽልም ቢሆን ስለ አንዱ የሰሜኑ ክፍል ብቻ ሲጽፉ ትልቁንና ሰፊውን የደቡቡን ክፍል እንደሌለ አድርገው ሲያልፉት ቆይተዋል።

ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ከስር ከመሰረቱ የሚያዛባና እንደ ወያኔ ላሉት አሳዛኝና ከሀዲ ፍጡሮች ቅጥፈት ያመቻል፣ አመችቷልም። የወያኔው አንበል "የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ሕዝብ ምኑ ነው?" ብሎ መናገሩን ያስታውሷል። እኔ እስከማውቀው ስለ ደቡብ ኢትዮጵያ የፃፉልን አለቃ ታዬና ዶክተር ላጲሶ ናቸው። አለቃ ታዬ ግን የሰሜኑን ያህል ሰፋና ዘርዘር አድርገው ባያብራሩትም በጥቅል ስሙ እናሪያ ተብሎ የሚጠራውን ሰፊ ባሕርታዊ ሕዝብ በሙሉ የካም ዘር ነው ይላሉ።

ነገደ ዮቅጣኖች ከሌሎች እድምተኞቻቸው ጋር ተባብረው ጥንት-ጥንታዊውን የኩሽ መንግሥት ታግለው በመጣል የፖለቲካ ሥልጣን በያዙ ጊዜ ከሕዝቡ ወገን የተቃወሟቸውንና የተቋቋሟቸውን በጦር ኃይል ባላደቆበት ጊዜ ከሰሜን ክልል እያፈገፈገ በአገሪቱ ደቡባዊ ክልል፣ በወላሞ፣ በሲዳሞ፣ በኩሎ፣ በኮንታ፣ በአማሮ፣ በጃንጀሮ ወዘተ የሚኖር ሕዝብ ነው ካሉ በኋላ ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ወድያው በሰሜኑና በደቡቡ ሕዝብ መካከል መረጋጋት ተፈጥሮ እርቅም ስለ ወረደ፣ ደቡቦች ማለትም እናሪያዎች በክልላቸው የራሳቸውን እራስ አገዝ አስተዳደር በመፍጠርና ከመካከላቸው ነገሥታትን እያነገሱ ባሕርታዊ አመራር በመመስረት ባሕርታዊ ከሆነው ማዕከላዊ መንግሥት ጋር በመተባበር ሥርዓት ማህበሩ በሚያዘው መሠረት እየገበሩ በአንዲት ኢትዮጵያና ባንድ ሰንደቅ ዓላማ ጥላ ስር መተዳደራቸውን ተርከውልናል።

እዚህ ላይ አንባቢ ሊያጤነውና በዚህ ታሪክ ደራሲ አስተያየትም ሊሰመርበት የሚገባ አንድ ቁምነገር፣ ይህ የሚሆነውና የሚደረገው የአክሱም ሐውልት ሊቆም ቀርቶ የአክሱም መንግሥት ራሱ ሳይመሠረትና አክሱማውያን ከመፈጠራቸው በፊት መሆኑን ነው።

በአፍሪካ የታሪክ ጥናትና ምርምር ዕውቅ ባለሙያ የሆኑት ኢትዮጵያዊ ምሁር ዶክተር ላጺሶ ጌ. ዴሌቦ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* ብለው በፃፉት ጽሁፋቸው መቅድም፣ "በድህረ አብዮትና በዘመነ ሪፐብሊኩ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በፖለቲካ፣ በድርጅት በትምህርት፣ በባህል፣ በኢኮኖሚና በአስተዳደር ፈጣን የሆነ የሃገር ግንባታ ፖሊሲና ተግባር በማካሄድ ላይ ይገኛል።

...በዚህ ታላቅ ፖሊሲና ፕሮግራም የአገሪቱ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ የአንድነትና የተግባር መሠረት መሣሪያ፣ መመሪያና ሚዛን እንደሆነ በከፍተኛ ደረጃና በትክክል ታምኖበታል። በሌላ በኩል ረጅም የሥልጣኔ ልምድና ታሪክ እንደሚያስተምረን የአንድ ሕዝብ የታሪክ ዕውቀት ለሕብረተሰቡ፣ ለአንድነት ለድርጅት፣ የተግባር፣ የፖሊሲና የሕይወት መሣሪያ፣ መመሪያና ሚዛን ሆኖ የሚያገለግለው ከሁሉ በፊት በእውነተኛ የታሪክ መረጃ የተገኘ የሰዎች የሥራ፣ የልምድ፣ የሕይወት፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የእምነትና የምርት መግለጫ ተግባራዊ ዕውቀትና እውነት ሲሆን ብቻ ነው።

...በመሆኑም በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የተገኘ የአንድ ሕዝብ እውነተኛ ታሪካዊ ዕውቀት እውነታና ትምህርት ምን እንደሆነ መሰረታዊ ባህሪውን ተስማሚና ተግባራዊ በሆነ የጥናት ስልትና ሚዛን ማወቅና ለሌሎችም ማሳወቅ የአንድ የታሪክ ባለሙያ ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታ ነው" ካሉ በኋላ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና መንግሥት ታሪክ* ብለው ያቀረቡትን የታሪክ መነሻ ሲያብራሩ፣ "የኢትዮጵያ ታሪክ ፈጣሪዎች፣ ባለቤቶች፣ ምክንያቶችና ተዋናዮች በአገሪቱ ማዕከላዊ መንግሥት ጥላ ስር ታሪካቸውን የመሰረቱና በአንድ ባሕርታዊ መንግሥትና ሕዝብነት የሚኖሩት ናያሎቲካዊ፣ ኦሞአዊ፣ ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦች ናቸው" በማለት አለቃ ታዬ በነገድ የዘረዘሯቸውን ዶክተር ላጺሶ በቋንቋ ቤተሰብነት ይገልጿቸዋል።

ይህን ገለፃቸውን ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲያብራሩ፡ "የኢትዮጵያ መንግሥት ሲባል የሦስት ተዛማጅና የማይነጣጠሉ ነባራዊና ነዋሪ ሁኔታዎች ማለትም የኢትዮጵያ ምድር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ታሪካዊ አንድነት ነው" ይላሉ።

ዛሬ የእኛ ሃገር የምትጠራበት ኢትዮጵያ የተባለው ስም ጥንት የእኛ ብቻ ሳይሆን ጥንታዊ ግሪኮች ለመላው ጥቁር ሕዝብ የሰጡት ስም ነበር የሚሉት ዶክተር ላጺሶ፣ ኢትዮጵያና ዓለም በተሰኘ ርዕስ ስር፣ የኢትዮጵያ ታላቁ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የሦስቱ ጥንታዊ የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ሕዝቦች የመገናኛ ጎዳናና ድልድይ በሆነው በቀይ ባሕር ስትራቴጂያዊ ክልል በዘመነ ክርስትና የመጀመሪያ አንድ ሺህ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከዘመኑ ታላላቅ የአረቢያ፣ የኑቢያ፣ የግብጽ፣ የሮማውያንና የፋርስ ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር እንደ ዘመኑ ዓለማቀፋዊ ሁኔታና አሰራር፣ በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በዲፕሎማሲና ወታደራዊ ጉዳዮች የተቀራረበ ጂኦፖለቲካዊ መስተጋብር የነበረው አንድ የአፍሪካ ኃያል መንግሥትና ሥልጣኔ ነበር ይላሉ።

የአክሱምን ሥልጣኔና ኃያልነት በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የትምህርትና የባህላዊ ጉዳዮች መምሪያ ቋሚ ጽሕፈት ቤት (ዩኔስኮ) አሳሳቢነት፣ አስተባባሪነትና የገንዘብ ድጋፍ፣ የዓለም እውቅ የታሪክ ምሁራን፣ ለታሪክ ምርምርና ጥናት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ሳይንቲስቶች በነቂስ ተመርጠው

በጻፉት ስምንት ቅጽ የአፍሪካ ታሪክ የአክሱም መንግሥት በጊዜው በዓለም ልዕለ-ኃያላን ከነበሩት ከሮማውያን፣ ከቻይናና ከፋርስ መንግሥታት መካከል አንዱ ነበር በማለት የአለቃ ታዬንና የዶክተር ላጵሶን ትረካ በበለጠ ያጠናክረዋል።

ዶክተር ላጵሶ ስለ አክሱም መንግሥት መጠነኛ መግለጫ ከሰጡ በኋላ ወደኋላ እራቅ ብለው በመሄድ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደራጀ ሕዝብነት ወይም ሉዓላዊነት ከጥንታዊዎቹ ፈርኦናዊ ግብፃውያን ጋር የነበረውን መልካም ጉርብትና እንዲሁም የንግድ ግንኙነት በማብራራት እስከ ዛሬ በተገኘው የታሪክ መረጃ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገርና ኢትዮጵያዊ የሚባለው አፍሪካዊ ሕዝብና መንግሥት ፑንት በሚባል ስም ይጠሩ እንደነበር ያስረዳሉ።

ከፑንት በኋላ በአፍሪካ ቀንድ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የሚታወቀው ሌላው መንግሥት ዳማት በመባል የሚጠራው ወይም የዳማታዊያን መንግሥት ነው። የህልውናውም ጊዜ ከአምስት መቶ ዓመተ ዓለም እስከ አንድ መቶ ዓመተ ምህረት ነው። ቅድመ አክሱም ጥንተ ጥንታዊው የኩሻይት ኢትዮጵያ መንግሥት፣ የፑንትና የዳማት መንግሥት በብዙ የታሪክ ማስረጃዎች አማካኝነት የነበሩበት የዕድገት ደረጃ ሲገመገም በተለይ በዳማት ዘመነ መንግሥት ከምድረ ግብጽ ወደ ዳማታዊያን ሃገር፣ እንዲሁም ከዳማት ወደ ግብጽ በአባይ ሸለቆና በቀይ ባሕር በንግዱ ሲለዋወጡ የነበረውን የሸቀጥ ዝርዝር፣ ሸቀጦቹ በባሕር የሚጓጓዙበትን ጥልቅ ባሕር የሚቀዝፉ ጀልባዎች፣ የግብርናና የእደ-ጥበብ ውጤት ምርቶች፣ ዳማት ብዙ ማህበረሰቦችን ያቀፈ ባሕርታዊ መንግሥት ሆኖ ሳለና በዚያን ጊዜ ሁሉም የሚግባቡበት አንድ የጋራ ቋንቋና ለሥነ-ጽሑፍ የበቁ ፊደላት ለመፍጠር መብቃቱን ስንመለከት ያለጥርጥር የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ከጥንተ-ጥንታዊው የኩሻይት መንግሥት ጀምሮ በፑንትና በዳማታዊያን እንደዳበረና ለአክሱማዊያን እንደተሸጋገረ እንረዳለን።

## የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ አነሳስ

ጥንታዊት ኢትዮጵያ ስንል የጥንታዊው ዓለም ማለትም የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ጥንታዊ አህጉራት አገሮችና ሕዝቦች ጥንታዊ አካልና አባል ማለታችን ነው።

ጥንታዊ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ ስንልም ኢትዮጵያ ለጥንታዊ ሥልጣኔዋ መንስኤ ወይም ምክንያት የሆኑትን ፋይዳዎች ሁሉ በሙሉ ከባዕዳን በተለይም ከጎረቤቶቻችን የአረባውያንን ሥልጣኔ እንዳለ የቀዳን ወይም የወሰድን አድርገው ብዙዎች እንደሚያስቡትና እንደ ጻፉትም ሳይሆን እውነቱ የዚህ ተቃራኒ ነው።

የሰው ዘር ታሪክና ሥልጣኔ ምንጭ ከሆነው ከአፍሪካ አህጉር ወይም ምድር የመነጨ ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ ነው። በዚህ ረገድ ብዙ ለማቅረብና ብዙ ለማለት ሲቻል አርዕስቱን ላለመሳትና ላለማንዛዛት እቆጠባለሁ።

ይህንን ስል ግን ከጥንታዊው ዓለም ስልጡን አገሮችና ሕዝቦች ማለትም ከቅርብ ጎረቤቶቻችን ከኩሻይት፣ ኑባይት፣ ከጥንታዊ ግብፃውያን፣ ከሮማውያን፣ ከባቢሎናውያን፣ ከፋርስ፣ ከሕንድ፣ ከቻይናና በተለይም ግሪኮችና ሮማውያን እየተፈራረቁና በሕብረትም ከ700 ዓመታት በላይ ጎረቤታችንን ግብጽንና አካባቢውን ማለትም እሥራኤልን ጨምሮ ማዕከላዊ ምሥራቅን ተቆጣጥረው በነበረበት ጊዜ በቀይ ባሕር፣ በአፍሪካ ቀንድና በአባይ ሸለቆ ላይ የነበራቸው አፍራሽም ሆነ ገንቢ ተፅዕኖ የሚዘንጋና ተቃሎ የሚታይ አይደለም።

እነዚህ አገሮችና ኃይሎች ከጥንታዊቱ ኢትዮጵያ የኩሻይት፣ የፑንት፣ የዳማትና የአክሱም ስርወ-መንግሥታት ጋር በነበራቸው የንግድ፣ የባህል፣ የፖለቲካና እንዲሁም የጋራ ደህንነትን የመሳሰሉ ብሔራዊ ጥቅማ ጥቅሞች ትብብር፣ ውልና ቀረቤታ ምክንያት ቀደም ሲል በመቅድሙ ላይ የአገራችን ኢትዮጵያ የጥንታዊው የሰው ልጅ ሥልጣኔ አጋሪና ተጋሪ ነበረች ስል እንደገለጽኩት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ባለ ብዙ ፈርጅ የአገሮችና የሕዝቦች ግንኙነቶች በሚፈጥሯቸው ሁኔታዎች የተለያዩ ጥበብና ዕውቀቶችን፣ ልምድና ተመክሮዎችን አንዱ ከሌላው መቅሰሙ፣ መማርና ሰጥቶ መቀበል ወይም መወራረስ የማይካድ ሀቅ ነው።

የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ አነሳስ ምን ነበር ብለን ስንጠይቅ ከምንም በፊት መታወቅ ያለበት የኢትዮጵያ መልካምድር አቀማመጥ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ልምላሜና የአየር ንብረቷ በጊዜው የነበረውና የምድሯ ባለቤት የሆነው ሕዝብ ማህበራዊ ንቃትና ድርጅት ዋና ዋናዎቹ ቀዳሚ መሰረቶች መሆናቸውን ነው።

ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ባለው መልካምድር፣ የተደላደለ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሕዝብ ንቃትና ድርጅት ስል ዋናው ተዋናይ ሕዝብ፣ አመራሩና የሥርዓተ-ማህበሩ መስተጋብራዊ ሚና ከምንምና ከማንም በላይ ወሳኝነት አላቸው ማለቴ ነው።

እነዚህ በአንድ ሃገርና ሕዝብ ህልውናና ብሎም እድገት ወሳኝ ቁልፍ ፋይዳዎች አክሱማውያን በእነሱ ጊዜ ብቻ የፈጠሯቸው ግኝቶች አይደሉም። በቅድሚያ የኢትዮጵያ መልካምድርና አቀማመጥ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ልምላሜና የአየር ንብረቷ ብለን ያመለከትናቸው የቁሳዊው ዓለም አካል የሆኑት ማንም ያልፈጠራቸው፣ የማይፈጥራቸው፣ ምን ጊዜም የነበሩ ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው።

የሕዝቡ ማህበራዊ ንቃትና ድርጅት ወሳኝ የሚሆነውም ሁልጊዜ፣ የትም ቦታ፣ የሰው ልጅ ሀሳቦች አመለካከቶችና አቋሞች ሊያድጉና ሊዳብሩ የሚችሉት ከሰዎች ያላቋረጠ ጥረትና ከዕለት ዕለት ተግባር በመሆኑ ነው። የሰው ልጅ እውቀቱን በየጊዜው እየመረመረና እያስፋፋ ያንንም ለምርትና ለምርት ኃይሎች ግንባታ ካዋለው እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ ላይ ሁሉም ደግሞ በጠቅላላው ሕብረተሰብ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጡ ስለሚችሉ ነው።

ከዚህ መሠረተ ሀሳብ ስንነሳ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ ኢትዮጵያዊ የተባለውን ሕዝብና ኢትዮጵያ የተባለችውን አገራችንን ከቀረቀሩት ጥንታዊዎቹ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጀምሮ ከአክሱማዊያን በፊት የነበሩት ተከታታይ ትውልዶችና ስርወ-መንግሥታት ለረጅም ጊዜ ያደረጓቸው የግንባታ ጥረቶችና የፈጠራ ውጤቶች ናቸው።

ከእነዚህ ቀዳሚና ዋናዋና መሰረታዊ ጉዳዮች ጋር እንዲሁ በቀዳሚነትና በወሳኝነት ሚናቸው መታዬት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች፣ ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ የምትገኝበት የአካባቢው ጂኦፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታዎችና ሂደት በየወቅቱ የተከሰቱ ክስተቶቹ ናቸው። እነዚህን በጣም ጠቅለል አድርጌ ያቀረብኳቸው ጉዳዮች በጥቂቱና በአጭሩ ዘርዘር አድርገን ስንመለከት:-

1ኛ/ የአክሱም ባሕርታዊና ዘውዳዊ መንግሥት የነበረበት የሕብረተሰብ የእድገት እርከን ወይም ምጣኔያዊ ሀብታዊ ንድፈ ሀሳብ አኳያ ይመራበት የነበረው የባሪያና የጉልታዊ ሥርዓተ-ማህበር ሥልተ-ምርት ነበር።

2ኛ/ የፖለቲካ ሥርዓቱ አካልና የአገዛዙ ዋና ዋና ማህበራዊ መሰረቶች የተገነቡት፣ በባሪያዎች፣ በገባር አርሶ አደሮች፣ በእደ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ በነጋዴዎች፣ በጊዜው የአገሪቱ ምሁራን፣ የቤተ ክርስቲያን ካህናትና የመከላከያ ሠራዊት ነበሩ።

3ኛ/ የአክሱማውያን የኢኮኖሚ አውታር በመሆን ለአገሪቱ እድገት፣ ለመንግሥቱ ጥንካሬ ብሎም ገናናነት ወሳኙን አስተዋጽኦ ያደረጉት፣ የገበሬው፣ የእደ-ጥበቡና የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚዎች በተጠናከረ ሁኔታ መደጋገፍ ነው።

የእነዚህ ዘርፎች የየግል እድገትና ጥንካሬ፣ በየፊናቸው ያበረከቱትንና አንዱ ከሌላው ጋር የነበረውን መደጋገፍ መመልከቱ፣ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ መንስኤው ምንድነው ለሚለው ጥያቄ ተገቢውን መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። የአገሪቱ ለም አፈርና የአየር ንብረት አመቺ ሁኔታ የፈጠሩለት ብቻ ሳይሆን የእደ-ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚ ለታታሪው ገበሬ በጊዜው ዘመናዊ የተባሉ የማምረቻ ወይም የግብርና መሣሪያዎችን በዓይነትና በመጠን አምርቶ የማቅረብ አቅምን ገንብቶ ነበር።

የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ፣ በምግብ እህሎች፣ በጥራጥሬ፣ በቅባት እህሎች፣ በቅመማ ቅመም፣ በእጣን፣ በከርቤ፣ በዝባድና በጠቅላላው የደን ውጤቶች፣ የቤት እንስሶችና የዱር አራዊቶችን በቁማቸውና እንዲሁም ውጤቶቻቸው ከአገሪቱ የውስጥ ፍላጎት ፍጆታ በላይ የተትረፈረፈ ምርት በማምረት በአካባቢው ካሉት አፍሪካዊና አረባዊ አገሮች ሌላ ለእስያና ለአውሮፓ አገሮች ጭምር ማቅረብ ተችሎ ነበር።

ከማዕድኑ ክፍለ ኢኮኖሚም የወርቅና የተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች ምርት ለውጭው ንግድ ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚናቅ አልነበረም። በሜድትራኒያን፣ በቀይ ባሕር፣ በሕንድ ውቅያኖስ በአባይ ሸለቆ የባሕር፣ የወንዝና የየብስ መንገዶች የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ የደራ ነበር።

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሆኑት የአውሮፓ፣ የእስያና የአፍሪካ አህጉራት አገሮች ጋር በነበራት ሁለገብ ግንኙነትና በተለይም የዓለም አቀፍ ንግዷ መስፋፋት ታላቁን አስተዋጽኦ ያደረጉት፣ ዓለም አቀፉ ወደብ አዱሊስና የእደ-ጥበቡ ባለሙያዎች ግምባር ቀደም ናቸው ለማለት ይቻላል። በአክሱማዊያን ጊዜ በእደ-ጥበቡ በኩል የታየው እርምጃና ለአገሪቱ እድገት ያደረገው አስተዋጽኦ በዚያን ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከሺህ ዓመታቶችም በኋላ ዛሬ ላለነው ትውልዶች ጭምር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በዚህ ረገድ እጅግ ብዙ ማለት ሲቻል ለአብነት ያህል ከግብርና መሣሪያዎች፡ ሞፈርና ቀንበርን፣ እርፍና ድግርን፣ ማረሻና ወገልን፣ ምራንና ቅርቃርን ብቻ አቀርባለሁ። ከታሪክ እንደምንማረው ጥንታዊዎቹ የግብጽ ፈርኦናዊያን፣ የግሪክ ነገሥታትና የሮም ቄሳሮች ወዘተ አገራቸውን የገነቡትና ራሳቸውን አንቱ ያሰኙት በባሪያዎች ጉልበት ነበር። የእኛዎቹም የአክሱም አፄዎች እንደዚሁ።

ጥንታዊዎቹ የባሪያና የጉልታዊ ሥርዓተ-ማህበር አራማጅ መንግሥታት ባርያዎችን በተለያዩ የእደ-ጥበብ ሙያዎች በወል አደራጅተዋቸው በየጊዜው ተፈላጊ የሆኑትን የተለያዩ ቁሳቁሶችን በአጠቃላይና በተለይ፣ ገንዘብን፣ የጦር መሣሪያዎችን፣ ትጥቆችን፣ ለነገሥታቱ ለመሣፍንቱና ለወይዛዝርቱ፣ ለመኳንንቱና ለካህናቱ ወዘተ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጡንና በጠቅላላው የማምረቻና የቤት እቃዎችን ወዘተ ያስመርቷቸው ነበር።

የብረት፣ የእንጨት፣ የቀርከሃ፣ የቀንድ፣ የቆዳ፣ የጭራ፣ የፀጉር፣ የቃጫ፣ የዘንባባ፣ የአለላ፣ የሸክላ ሥራዎችን ወዘተ ከሽመና ጋር በዘመኑ የቴክኖሎጂና የፈጠራ አቅም አንፃር

በጣም ዳብረው እንደነበር ይታወቃል። ከ16ኛው እስከ 18ኛው ምዕት-ዓመታት መባቻ ድረስ በምዕራብ አውሮፓ በጉልተኞችና በቡርዧዎች መካከል የመደብ ሹም ሽር ወይም ስርነቅል ማህበራዊ ትግል እንደተደረገ ይታወቃል።

ቡርዧዎች በጉልተኞች ላይ ድልን ተቀዳጅተው የፖለቲካ ሥልጣን እንደተቆናጠጡ የወሰዱት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እርምጃ በእደ-ጥበብ ሙያ ሰልጥነውና በልዩ ልዩ የማምረቻ እርሻዎች ውስጥ ተደራጅተው ለጉልተኞች ሲያገለግሉ የነበሩት ባሪያዎችና ገባሮችን ነፃ በማውጣትና ምንዳ በመክፈል የካፒታሊስት ሥልተ-ምርት እምብርት ወደሆነው ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ግንባታ መውጣጫ እርካብ አድርገው መጠቀምን ነበር።

በታሪክ የዓለም የሠራተኞች መደብ እርሾ የሆኑት የመጀመሪያዎቹ የኢንዱስትሪ ወዛደሮች እነዚህ በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓት የነበሩት የእደ-ጥበብ ባለሙያዎቹ ናቸው። የአክሱም ባሕርታዊ የአፄዎቹ መንግሥት በጊዜው ስልጡን ከሚባሉት መንግሥታት ጋር በብቃት በመወዳደር በአካባቢው የኢኮኖሚና ወታደራዊ ኃይል ከመሆን አልፎ ከእደ-ጥበቡ ክፍለ ኢኮኖሚ በሚፈለጉ ልዩ ልዩ የማምረቻና የመገልገያ ቁሳቁሶች ረገድ ራሱን ከመቻሉ በላይ የመከላከያ ሠራዊቱን በመገንባትም የአካባቢውን ወታደራዊ ኃይል ሚዛን በመድፋቱ ዓለማቀፋዊ ኃይል ሆነ።

አክሱማውያን በዘመኑ የባሕር ቴክኖሎጂ የደረሱበት የእድገት ደረጃ ከፍተኛውና ለኃያልነታቸውም ትልቁን አስተዋጽኦ እንዳደረገ እሙን ነው። የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መሀንዲሶች ጥልቅ ባህሮችን ለመቅዘፍ የሚችሉ፣ የተለያየ መጠንና አገልግሎት ያላቸውን የሰውና የሸቀጥ ማጓጓዣዎችን፣ ለአገሪቱ የባሕር ኃይል የውጊያ መርከቦችን ለማምረት መብቃት ታላቅ የእድገት እምርታ ነበር።

ለማጠቃለል፣ እነዚህ ከዚህ በላይ በጥቂቱ የጠቃቀስኳቸው የተከታታይ ትውልዶችና ጥረቶች በመጨረሻ አክሱማውያን ከደረሱበት እድገት ጋር ተዳምረው የአክሱምን መንግሥት፣ በአፍሪካ ቀንድ፣ በአባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባሕርና በደቡብ አረቢያ የግዛቱን ክልል ለማስፋፋት አስቻሉት። በዚህም ብቻ ሳይወሰን የዓለም ታሪክ በተጀመረባቸው፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ፍልስፍና በመነጨባቸው የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት ሕዝቦችና ኃይሎች መገናኛ ጎዳናና ድልድይ በመሆን ታላቅ ዓለማቀፋዊ ስትራቴጂ ጠቀሜታ ባለው ስፊ ክልል ላይ የራሱን ሥርዓት በመዘርጋት ተጽእኖውንና ተደማጭነቱን ያረጋገጠ አንድ የዓለም ልዕለ-ኃያል አፍሪካዊ መንግሥትና ሥልጣኔ ለመሆን ቻለ።

## ኢትዮጵያ በመካከለኛው ዘመን: የአክሱም መንግሥት ፍፃሜና የዛጉዌ መንግሥት አነሳስ

የአይሁዶች እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት እስከ አራተኛው ምዕት ዓመት ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ መንፈሳዊ እምነት ወይም ሃይማኖት በመሆን ስር ሰዶ መኖሩ የታወቀ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት በጁዳይዝም ፋንታ ክርስትናን ተቀብሎ የአገሪቱ እምነት እንዲሆን በሕግ ከደነገገበት ጊዜ ጀምሮ የክርስትናን እምነት አንቀበልም ብለው በአሪታዊ እምነታቸው የፀኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች በመንግሥት ትዕዛዝ የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ አክሱምንና አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ በመደረጉ፣ በጎንደር፣ በጎጃምና በወሎ ክፍለ

አገሮች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አውራጃዎች ውስጥ ተበታትነው ለረጅም ጊዜ ሲኖሩ ፈላሻ ወይም ፈላሽ እየተባሉ እስከ ዛሬም እንደሚጠሩ ይታወቃል።

ፈላሾችን ስደቱ፣ እንግልቱና በተቀረው ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ ተደርገው በመገለል መኖራቸው ምንኛ እንደሚያሳዝናቸው ለመገንዘብ አያዳግትም። የአክሱም መንግሥት ፈፅሞ በተዳከመበት በ9ኛው ምዕተ ዓለም ላይ ለበቀልና የፖለቲካ ሥልጣን ይዘው የአይሁዶችን እምነት መልሰው ለመትከል ተንቀሳቀሱ።

ከፈላሻ ሕብረተሰብ የምትወለደዋ ዮዲት ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ፈላሻዎችን፣ የባለቤቷ ወገን የሆኑትን አገዎችንና ሌሎችንም የአክሱማውያንን ሥልጣን ተቀናቃኞች የሆኑ ኃይሎችን ሁሉ አስተባብራ በአክሱም መንግሥት ላይ በመዝመት በቀላሉ ድልን አግኝታ ዘውድ በመቀዳጀት የኢትዮጵያ ንግሥት ለመሆን በቃች። ከአክሱም መንግሥት ፍፃሜ በኋላም ኢትዮጵያን ለ40 ዓመታት መራች።

ስለንግሥት ዮዲት ሥልጣን አያያዝና ስለመንግሥት አመራሯ ዘመን እንደሚደመጡት አፈ ታሪኮችና በክርስቲያን ዘጋቢዎች እንደተጻፉ ታሪኮች ከሆነ፣ ታሪኳ በሙሉ ገደብ አልባ ጭካኔዋንና አፍራሽነቷን እንጂ ስላለማችው ወይም ስለገነባችው ግንባታዎችና ስለበጎ ጎኗ አንዳችም የሚደመጥና የሚነበብ ነገር የለም።

የንግሥት ዮዲት የጥቃት ዘመቻ በአክሱም የፖለቲካ አመራር አካላት ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ አሻራዎች፣ ቅርሶችና እንዲሁም የክርስትና ባህልን ለማውደም የተነሳች እንደሆነ ነው ታሪክ የሚመዘግበው።

ከአራት ምዕት ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ሥር ሰዶ የቆየውን የክርስትና እምነትና ባህል እንደገና መልሳ በአይሁዶች እምነት ለመተካት ያደረገችው ጥረት የተሳካ አልነበረም። የኦሪትን ሕግ አራማጅ በሆኑና የክርስትና እምነት አማኝ በሆኑ የአንዲት ሃገር ልጆች መካከል ለ40 ዓመታት ሲካሄድ የነበረው ልማትና ግንባታ ሳይሆን ጥፋትና ሽብር ብቻ ነበር ነው የሚባለው።

በዘመነ አክሱም የተፈጠረ የፈላሻዎች ችግር እስከ እኔ ትውልድ ጊዜ ድረስ መፍትሄ ሳያገኝ ቆይቶ ነበር። እንደሚታወሰው ፈላሻዎችን ማግለልም ሆነ መበደል በፅኑ የተወገዘውና በሕግ የተከለከለው በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ነው።

በኢትዮጵያ አብዮታዊያን እምነት ወይም አስተሳሰብ ፈላሻ ማለት ስሙ እንደሚያመለክተው ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ የፈለሰ ወይም የተሰደደ ማለት ብቻ ነው። እስላምና ክርስቲያን እንደ ማለት ሁሉ፣ በፈላሾችና በተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለው ልዩነት የእምነት እንጂ የዘር ሊሆን አይችልም። ሆኖም ፈላሾች (አይሁዶች) ናችሁ ተብለው ወይም እነሱም እራሳቸው አምነውበትና ነን ብለው ከአገራቸው ከኢትዮጵያ በየጊዜው ወደ እሥራኤል ሃገር ዳግም ሲሰደዱ ይታያሉ። በእርግጥ ፈላሾች የሚሸሹት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው ወይስ ድህነትን? መልሱን ለእነሱ እተዋለሁ።

ከንግሥት ዮዲት እረፍት በኋላ የአክሱም መንግሥት አልጋ ወራሽነን የሚሉ ከተሰደዱበት ከሸዋ እየተመለሱ በተከታታይ ሥልጣን ለመቆናጠጥ ያደረጓቸው ሙከራዎች ስኬታማ አልነበሩም።

የመጨረሻው የአክሱም ንጉሥ ድልነዓድን በ912 ዓ.ም ገደማ መራ ተክለኃይማኖት የተባለ የጦር አበጋዝ በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ነጥቆ መንግሥቱን ዛጉዌ አሰኝቶ ነገሰና የአክሱም ፍፃሜን አበሰረ።

አዲሱ የዛጉዌ መንግሥትም መናገሻ ከተማውን በወሎ ክፍለ ሃገር በላስታ አውራጃ ውስጥ አደረገ። ከ912 ዓ.ም እስከ 1245 ዓ.ም ድረስ አስራ አንድ የዛጉዌ ስርወ መንግሥታት እየተፈራረቁ ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን መርተዋል። ዛጉዌዎች በመጀመሪያ መንግሥታቸውን በሚያቋቁሙበት ጊዜና በኋላ ስልጣናቸውን በተነጠቁበት ጊዜ ከገጠማቸው ችግርና ሁከት በስተቀር የተቀረውን ዘመነ መንግሥታቸውን በሰላም ኖረዋል።

የዛጉዌ ሥርወ ነገሥታት በሙሉ ማለት ይቻላል በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ በፅኑ ስለሚያተኩሩ የአክሱም መንግሥት በጣም በተዳከመበት የመጨረሻ ዘመኑና በንግሥት ዮዲት ትርምስ የአገዛዝ ዘመን የተበታተኑትን ሕዝቦችና የአፄዎች ግዛቶች እንደገና መልሶ ለማሰባሰብ ምንም አይነት ሙከራ ሳያደርጉ በተወሰኑ ሰሜናዊ ክልሎች ብቻ ራሳቸውን አቅበው ስለኖሩ በሃገር ውስጥ ምንም አይነት ተቃውሞ ለብዙ ጊዜ አልገጠማቸውም።

በእነሱ የአገዛዝ ዘመናት በሙሉ እለማቀፋዊ የእስልምና እምነት አራማጅ ኃይሎችና በዓለም አቀፋዊ የአውሮፓ ክርስቲያናዊ ኃይሎች መካከል የመስቀል ጦርነት ይካሄድ የነበረ ከመሆኑም በላይ የዛጉዌ መንግሥት አመራር አካላት ኢትዮጵያን ከዚህ ጦርነት ገለልተኛ በማድረጋቸው ከውጪ የተፈጠረ ችግርና የተሰነዘረ ጥቃትም አልነበረም።

ከማንም ሳይወግኑ ኢትዮጵያን ከመስቀል ጦርነት ገለልተኛ ማድረጋቸው የአስተዋይነት እርምጃ ሲሆን፣ ባገኙት ሰላም የሰፈነበት ሦስት መቶ ዓመታት ረጅም ጊዜ በኢኮኖሚ ልማትና በሃገር ግንባታ ረገድ ይህንን አደረጉ ተብሎ የሚነገር ነገር የለም።

እንዲታሰቡ የሚያደርጋቸው ለሃገር የተደረጉ አስተዋጽኦዎች ቢኖሩ ንግሥት ዮዲት ያቃጠለቻቸውን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ በመገንባት፣ ባሁኑ ጊዜ በዓለም ተደናቂ የፈጠራ ሥራዎች አንዱ የሆነውን ከአንድ ቋጥኝ ድንጋይ የተፈለፈሉ ቤተክርስቲያኖችን በላስታ ማሰራት፣ የክርስትናን እምነት ማጠናከርና አንዳንድ የአስተዳደር ጉዳዮች ለማሻሻል ያደረጓቸው ጥረቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ዙሪያዋን ተከባ፣ ከውጭው ዓለም ጋር ያገናኟት የነበሩት መርከቦቿ በነደዱበትና ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ውጭ ለመንቀሳቀስ በተሳናቸው ጊዜ፣ በአባይ ሸለቆና በቀይ ባሕር ጠረፎች በተለይም በዘይላና በታጁራ በሮችና ወደቦች አረቦች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ያሻቸውን ሲያደርጉ የገታቸው ነገር አልነበረም።

ከዘመነ አክሱም የመጨረሻ ጊዜ ጀምሮ በንግሥት ዮዲትና በዛጉዌዎች ዘመነ መንግሥት ለአራት መቶ ዓመታት ያህል የአረብ ነጋዴዎችና የእስልምና እምነት አስፋፊ መንፈሳዊ የአረብ ምሁራን በፈለጉበት ጊዜ ሲገቡና ሲወጡ በአንድ ሉዓላዊ መንግሥት ሃገር ውስጥ ስለሚያከናውኑት ተግባር ለማወቅና ለመቆጣጠር ቀርቶ ያስተዋላቸውም እንኳን ያለ አይመስልም።

ስለሆነም ከማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ውጪ ከሆኑት የአገሪቱ ሰሜን ምሥራቅ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብና ደቡባዊ ምዕራብ ክልሎችና እንዲሁም በመሃል ሸዋ ደቡብና ምዕራብ አውራጃዎች ነዋሪ የሆነው ሕዝብ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆኑ ከአረቡ ዓለም ጋር የደራ ንግድ ባላቸው አሚሮችና ሱልጣናት አመራር ስር የተደራጁ መንግሥታት ተፈጠሩ።

በዚህ ሁኔታ በአመራር ላይ የቆዩት የዛጉዌ ነገሥታትም በተራቸው ከውስጥ ከደቡብና ከሰሜን የሥልጣን ተቀናቃኞች ስለተነሱባቸው ለመከላከልና ህልውናቸውን ለማቆየት ቢታገሉም የመጣባቸውን ተቃዋሚ ኃይል ለመመከት አልቻሉም።

በመካከለኛ ሠራዊት አደረጃጀትና ግንባታ በኩል ዝንጉ ስለነበሩ በ1119 ዓ.ም የዛጉዌ የመጨረሻው ንጉሥ ነአኩቶለአብ ከሸዋ በተነሳ ይኩኖ አምላክ (ተስፋ እየሱስ) በተባለ መሥፍን ሥልጣኑን ስለተነጠቀ የዛጉዌ መንግሥት ፍጻሜ ሆነ።

# ከዛጉዌ በኋላ የመጡ ሥርወ መንግሥታት የጠቢቃቸው ሥራና የገጠሟቸው ፈተናዎች

የዛጉዌ መንግሥት ወድቆ አፄ ይኩኖ አምላክ ሥልጣነ መንግሥቱን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ መንበረ መንግሥቱ በሸዋ ክፍለ ሃገር ሆነ። ስለአክሱማውያን መንግሥት መዳከምና ብሎም መውደቅ ከውጭ አብይ አስተዋፆ ያደረጉት የአፍሪካ ቀንድ፣ የአባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕር አካባቢና አጠቃላይ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችና የኃይል አሰላለፎች ቢብሱ እንጂ ኢትዮጵያን በሚበጅ ሁኔታ ያሳዩት ለውጥ ወይም መሻሻል አልነበረም።

በኢትዮጵያ ውስጥ አዲሱን አመራር በእጅጉ የሚያሳስቡና አገሪቱን ይበልጥ የሚያዳክሙ ሁኔታዎች ተከስተዋል። የአገዎችና የፈላሻዎች መንግሥት የክርስትናውን እምነት አዳክሞ የአይሁዶችን እምነት መልሶ ለማስፋፋት ያደርጉ የነበረው ጥረት ለአርባ ዓመታት ያከናወነው ጥፋት እንጂ ልማት አልነበረም።

ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ በአመራር ላይ የቆዩት የዛጉዌ ሥርወ መንግሥታት ያከናወኗቸው አንዳንድ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ፋይዳዎች ቢኖሩም፤ ከውጪው ዓለም ጋር በሰላም የመኖር መርሆ ቢመሩም፤ የኢትዮጵያን አንድነት፣ ማህበራዊ ደህንነትና አብይ የሃገር ግንባታ ሥራን ሳያከናውኑ ለተተኪው መንግሥት አስረከቡ። በአክሱም መንግሥት መዳከም ከማዕከላዊ መንግሥት አመራር ካፈነገጡት ክልሎች ሌላ በዘመነ ዮዲትና በዛጉዌ ሥርወ መንግሥታት ጊዜ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑት ክልሎች እየበዙ መሄዳቸው ብቻ ሳይሆን በእነዚህ ክልሎች ነዋሪ የሆነውም ሕዝብ የነቢዩ መሐመድ ተከታይም ሆኗል።

በሌላ አነጋገር፣ ባሕርታዊና መደባዊት ኢትዮጵያ፣ በብሉይ፣ በአዲስ ኪዳንና በቁራን የሚመሩና በተለያዩ አማልክት የሚያመልኩ ሕዝቦችን የማሰባሰብና የማስተዳደር ብቃት ያለው አመራር የሚያስፈልግበት ጊዜ ተከስቷል። እየተካሄደ ባለው ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ጦርነት ውስጥ ባለመግባትና ለማንም ላለመወገን የተከተሉትን መርሆ አጥብቆ ከመቀጠል ባሻገር፤ ኢትዮጵያ የከበባትን አጥር ጥሳ በመውጣት ከዓለም ጋር እንደገና የምትገናኝበትን ስልትና ስትራቴጂ በመጠቀም ክብርና ሞገሷን ለማደስ የሚችል ብርቱና ብልህ አመራር የሚጠይቅ ጊዜ ነበር።

ከጥንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር እንደሚጠበቀው የሸዋ ሥርወ ነገሥታት የትኩረታቸው መጀመሪያ አድርገው ቅድሚያውን የሰጡት ከማዕከላዊ መንግሥት አመራር ውጪ በመሆን የተነጠሉት ክልሎችና የተበታተነውን ሕዝብ መልሶ የማሰባሰብ ተግባር ነበር።

በአንድ አፍራሽ ገጠመኝ ወይም ታሪካዊ ወቅት የተበታተነውን፣ አዲስ እምነት አዲስ ባህልና ልማድ የሰረፀበትን ሕዝብ እንደገና አሰባስቦ በማቻቻልና በማስተባበር፣ በአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ጥላ ስር ሆኖ የጋራ አገሩን መልሶ በጋራ እንዲገነባ የተደረገው ጥረት ያለ መሪር መስዋዕትነት በቀላሉና በሰላም ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም።

አጼሱን የእስልምና እምነት አራማጅ የሆኑትና በከፊልም አረባዊ ደም ያላቸው አሚሮችና ሱልጣናት መካከል የተወሰኑት በተለይም በዳር ሃገር ያሉት ቆለኞች ከአንድነት ይልቅ መነጣጠልን፣ ከሰላማዊ መፍትሔ ይልቅ ኃይል መጠቀምን መርጠው ስለነበር ከ13ኛው እስከ 14ኛው ምዕት-ዓመት ድረስ ያለው ጊዜ ለሰላምና ለግንባታ የዋለ ጊዜ ሳይሆን ዳግም የሽብርና የጦርነት ጊዜ ሆነ።

ከአንድ ምዕት-ዓመት ትግል በኋላ ማዕከላዊ መንግሥት በርትቶ የአመፀኞችን ጥቃት በመመከት እንደ አስፈላጊነቱ ኃይልንም ሰላማዊ መፍትሔም እየተጠቀመ ጥቂቱን የጥንቱን የአክሱም መንግሥት የአስተዳደር ክልሎች መልሶ ለማሰባሰብ በመቻሉ ቢያንስ አንፃራዊ ሰላምና የግንባታ ጊዜ ማግኘት ይቻላል ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ነበር።

ሆኖም በውጪ የአካባቢው ኃይሎች ግፊትና በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ደገኛውና ወይናደገኛው ሕዝብ አሁንም በዳር ሃገር በከብት እርባታና በንግድ የሚተዳደሩት በተለይ አፋርኛና ሶማሊኛ ተናጋሪ የሆኑትን ቆለኞች የሚመሩት ሱልጣናትና ሌሎችም አምርረው በአመፃቸው ወደ መቀጠሉ አመሩ። በመንግሥት በኩል የሰላሙ ጥረት እንደቀጠለ ስለነበር አንዴ መግባባት በመፈጠሩ የሰላም መፍትሄ ተገኘ ተብሎ ተስፋ ሲደረግ፣ ሰላሙ ይደፈርስና እነበረበት ሲመለስ፣ ተብ እረገብ እያለ የእርስ በእርስ ጦርነቱ ከ250 ዓመታት በላይ ያለማቋረጥ ቀጠለ።

ይህም ቢሆን በታሪክ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ዜጎች አብረው በአንድ ሃገር ብሔራዊ አንድነት፣ ነፃነትና ሰላም ተቻችለው የሚኖሩበት ሃገር ጥንታዊት ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች። የኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔታ በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በዚህ መልክ እያለ በአካባቢውና በዓለም አቀፍ ከወትሮው የተለየ አዲስ የኃይል አሰላለፍ ተፈጠረ። ከ7ኛው ምዕት-ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ በአረቦች የጦር ሜፍነት ከማዕከላዊ ምሥራቅ ተነስቶ በሰይፍ ወረራና ዘረፋ በሰሜን አፍሪካ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ አውሮፓና በሕንድ ወዘተ ለሦስት መቶ ዓመታት ከአቅማቸው በላይ በሦስት ሰፋፊ አህጉራት የተንሰራፉት እስላማዊ ኃይሎች ከአውሮፓና ክርስቲያናዊ ኃይሎች በአፀፋው ወይም በበቀል የደረሰባቸውን መልሶ ማጥቃት መመከት ቢችሉም ለረጅም ጊዜ በተካሄደው ጦርነት ሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች በእጅጉ መዳከማቸው እሙን ነው። ከዚህም ሌላ አብዛኛው አረባዊ ኃይሎች በመካከለኛው ምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ ክልሎች ቋሚ ሰፈር በማድረግ ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ አገሮችና ሉዓላዊ መንግሥታት እየመሰረቱ በመኖር ሲመናመኑ፣ ንቅናቄውም ጨርሶ ወደ መቆሙ አመራ።

ጥንት በግሪኮችና በሮማውያን ፈረቃ በመጠቃቱ ተዳክሞ የነበረው የቱርክ አፄዎች መንግሥት እንደገና አንሰራርቶ በመነሳት ለዚያን ጊዜ በጣም ዘመናዊ የሆኑ የጦር መሣሪያዎችና መርከቦች ባለቤት በመሆን አውሮፓውያኑን ድል በመምታትና አረቦችን በመተካት በ15ኛው ምዕት ዓመት በቀይ ባሕር፣ በፋርስ ባህረ ሰላጤ፣ በሕንድ ውቅያኖስና በአካባቢው ብቸኛ ኃያል መንግሥት ሆኖ ብቅ አለ።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ዘመናዊ የጦር መሣሪያና መርከቦች የታጠቀ የፖርቹጋል መንግሥት የአውሮፓውያንን ኃይሎች ተክቶ የቱርክ ባላንጣ በመሆን ተነሳ። የፖርቹጋል ኃያል መንግሥት በአጠቃላይ የእስያን አህጉርና በተለይም ከሕንድ፣ ከሴሎንና ከቻይና፣ ከማዕከላዊ ምሥራቅ ከሰሜን አፍሪካና ከአፍሪካ ቀንድ በቀይ ባሕር ወደ ደቡብ አውሮፓ የሚሄደውን ሸቀጣሸቀጥ በሕንድ ውቅያኖስ፣ በደቡብ አፍሪካ

ጠርዝና በአትላንቲክ ውቅያኖስ በኩል ወደ ምዕራብ አውሮፓ እንዲሄድ ለማድረግ በእነዚህ ቀበሌዎች በጦር አሰላለፍ ተሰማራ።

እዚህ ላይ እንደሚታየውና በሌሎችም ስፍራዎችና ጊዜያቶች በተከናወኑ ውጊያዎችና ጦርነቶች መንግሥታት፣ አገሮችና የተለያዩ ኃይሎች ሃይማኖትን ሽፋን ወይም መሣሪያ አድርገው እየተጠቀሙበት እንጂ ከዚህ ጀርባ ያለው ዋና ግባቸው፣ ግዛትን ማስፋፋትና ቁሳዊ ወይም ኢኮኖሚ ጥቅማጥቅሞችን ለማግበስበስ መሆኑን ጥንትም ሆነ ዛሬ ታሪክ ደጋግሞ ያሳየን መሆኑን ነው።

ለብሔራዊ ጥቅማቸው ሲሉ ክርስቲያኖች ክርስቲያኖችን፣ እስላሞች እስላሞችን የወጉ ወይም የሚወጉ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ እስላሙ ከክርስቲያኑ ጋር ክርስቲያኑም ከእስላሙ ጋር በመሆን ዘሩንና የእምነት ተጋሪውን ሲወጋ ተመልክተናል። የፖርቱጋሎችና የቱርኮች በሕንድ ውቅያኖስና በቀይ ባሕር ስትራቴጂያዊ ቀበሌዎችና ባህሮች ላይ ትንቅንቅ ዋና ምክንያት የሃይማኖት ጉዳይ አስመስለው ሁለቱም በየፊናቸው የትግል አጋር ለማግኘት እንደሚሞክሩትና እንደሚናገሩት ሳይሆን ለኢኮኖሚያዊ ጥቅማጥቅም ነበር።

በፖርቱጋሎችና በቱርኮች የትንቅንቅ ዘመን የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት የአፄ ልብነድንግል መንግሥት ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር በተደጋጋሚ ያደርግ የነበረው ግንኙነት ከቱርኮችና ከአረቦች የተሰወረ አልነበረም። ስለሆነም ውሎ አድሮ ለሚፈጠረው ሁኔታ እራስን ለማዘጋጀት ይመስላል የቱርክ መንግሥት በ1516 ዓ.ም ግብጽን ወሮ የቀይ ባሕርን ክልል በመቆጣጠር በፖርቱጋል ላይ ውጊያ ከፈተ። የቱርኮች እንቅስቃሴ በፖርቱጋሎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያም ላይ ያለመ መሆኑን የሚያስገነዝበው የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ወደብ ምፅዋን መያዛቸው ነው።

ይህ በጣም ግልፅ የሆነ አደጋ ምልክት ወይም ማስጠንቀቂያ ሆኖ ሳለ በፖርቱጋል መንግሥት የመመካት ይመስላል አፄ ልብነድንግል በአካባቢው ካሉ የእስላም አገሮች ጋር የነበራቸውን ጤናማ ግንኙነት በማቋረጥ ሁለገብ የስምምነት ውል በመዋዋል በፀረ-እስላም ግምባር ኢትዮጵያ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ወግና እንድትሰለፍ ተወሰነ። ይህ ሁኔታ እንደ ተለመደው በሃይማኖት ሽፋን በቱርክ መንግሥት አስተባባሪነት የአካባቢው እስላማዊ ኃይሎች ከኢትዮጵያውያን እስላሞች ጭምር በአፀፋው ፀረ-ኢትዮጵያ ግምባር አቋቁመው ታላቅ ጥቃትና ጥፋት የሚያስከትል ሴራ አቀዱ።

## ኢማም አህመድ ግራኝ የመራው አመፅ፣ የእስላም አገሮችና የፖርቱጋሎች በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ሃይማኖት መሣሪያ ወይም ሽፋን እንጂ ሃይማኖትን ሰበብ አድርገው በሚነሱ ተፋላሚዎች መካከል የሚደረጉ ጦርነቶች ዋና ምክንያት አይደለም።

ሃይማኖት ሽፋን ነው። ጠቡና መሠረታዊ ቅራኔ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑትን የሕብረተሰብ ክፍሎች እንመራሃለን ወይም እናስተዳድርሃለን በሚሉት ገዥ መደቦች የሚነሳ የሥልጣንና የኢኮኖሚ ጥቅም ጥያቄ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ የሚተዳደርበት እጅግ ኋላቀር የሆነው ጉልታዊ ሥርዓተ-ማህበርና የሕዝቡ ማህበራዊ ንቃት የቅራኔ፣ የጥላቻ፣ የቀውስ ወይም የጠብ ምንጮች ናቸው። በሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ እንደሚፈፅመው ሁሉ ጉልታዊው

ገዥ መደብ የእስልምና እምነት ተከታዩን የሕብረተሰብ ክፍል ግብር ለማስከፈልና ፀጥታ ለማስከበር የሚሰማራው በክተት ጥሪ ከየስፍራው የሚሰበሰብ ፊውዳል ሠራዊት በየጊዜው እየሄደ ደሃውን ገበሬና ነጋዴ ማርና ቅቤ አዝንብ፣ ሰንጋና መሰና ውለድ እያለ በአደባባይ በሚስቱና በልጆቹ ፊት ሲያዋርደው፣ ሲደበድበው፣ ጎተራና ድምኝቱን ሲደፋበት፣ መኖሪያ ጎጆውንና መፀለያ መስጊዱን ሲያቃጥልበት መረር ጥላቻና የማይታረቅ ቅራኔ ፈጥሮ ነበር።

እንዲህ ያለው እኩይ ድርጊት ሲበዛና ሲደጋገም፣ እንቢ ማለትና እራስን መከላከል የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆናቸው የሚያደርጉት ሳይሆን የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባህሪ ነው። የእስልምና ተከታዩ ህብረተሰብ ከሌላው የሚለየው ነገር ቢኖር ከኢትዮጵያ ውጪ በአካባቢው ያሉት የእስልምና እምነት አራማጅ አገሮች ተቆርቋሪ በመምሰል ቅራኔውን እያባባሱ ለጥፋት መገፋፋታቸውና ኢትዮጵያዊያን እርስ በእርሳቸው የሚጋደሉበት መሣሪያ ማቅረባቸው ነበር።

በወቅቱ በኢትዮጵያና በፖርቹጋል መንግሥት መካከል በተፈጠረው ውል ምክንያት በእስልምና ኃይሎች ወገንም ከ1517 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1519 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ፀረ-ኢትዮጵያ ግምባር ተቋቋመ። በኢትዮጵያ ክርስቲያን ገዥ መደቦችና በኢትዮጵያውያን የእስልምና እምነት ተከታይ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን ቅራኔ መሠረት አድርገው በቱርኮች የሚመሩት የአካባቢው እስላማዊ አገሮች ባወጣጡት ገንዘብና ቁሳቁስ፣ ትጥቅና የሰው ኃይል ድጋፍ የተጠናከረና፣ ኢማም አህመድ ግራኝ በተባለው ኢትዮጵያዊ የሚመራ ኢትዮጵያዊ የእስልምና ተዋጊ ሠራዊት በማቋቋም በ1519 ዓ.ም ጂሃድ የሚባለው በሰይፍ ጥረግ ዘመቻ በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክልል ተጀመረ።

ስለ ግራኝ የፖለቲካ ሰውነትና ወደር የሌለው የጦር አመራር ችሎታ በፀረ-ክርስቲያን አቋሙ ስላስፈፀመው ቀፋፊ የጭካኔ ተግባርና ከሃገር አውዳሚነቱ ሌላ ስለተክለ ሰውነቱ፣ ስለሚታጠቀው ሰይፍ ወይም ጎራዴ መጠን ሳይቀር ከሰው የተለየ ልዩ ፍጡር ተደርጎ በአፈ ታሪክ ተራኪዎች ብዙ ተብሏል።

ስለ ንግሥት ዮዲት ባጭሩ ስተርክ ፀረ-አክሱማዊው ዘመቻ የፖለቲካ ሥልጣን ለመቀዳጀት በአክሱም መንግሥት አመራር ማዕከልና አካል ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ ቅርስና አሻራ፣ እንዲሁም የክርስትና ባህልን ለማጥፋት ስለነበረ በአውዳሚነቷ በኢትዮጵያ ታሪክ ወደር አይገኝላትም ተብሏል ማለቴ ይታወሳል።

ከዮዲት ጊዜ ከስድስት ምዕት ዓመት በኋላ የእስልምና እርማ እንግቦ ከምሥራቅ ብቅ ስላለው ግራኝ ከማንም በተሻለ ሁኔታ ጠለቅ ባለ ጥናትና ሰፋ ባለ ይዘት በማቅረብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ የሆኑት አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ በጽሁፋቸው መግቢያ የሰጡትን አስተያየት ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ። “ፈላሻዋ ዮዲት የቆየችው አርባ ዓመት ነው የሚለውን መሠረት ያደረግን እንደሆን በዘመን እርዝማኔ አሥራ አምስት ዓመት የቆየው የግራኝ አህመድ የወረራ አገዛዝ የእሷ ስለሚረዝም በዚያው መጠን በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ የመከራው ጊዜ በርካታ ይሆናል። ነገር ግን ዮዲት ከተነሳችበት ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የግራኝ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ወረራ ያመጣውን ያህል የጦርነትና የእልቂት መከራ በኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ ምንጊዜም ደርሶ አያውቅም። የኢጣሊያ የአምስቱ ዓመት ወረራና ስቃይ፣ የየካቲት 12 ቀን እልቂት ተጨምሮ የ15 ዓመቱን የግራኝን ወረራና እልቂት አይተካከለውም።”

የግራኝን የዘር ሀረግ በተመለከተ ከተለያዩ ጸሃፊዎች ያገኙሁት መረጃ የሚገልፀው፣ ከአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመን መንግሥት ጀምሮ በይፋትና በአዳል ባላባትነት ለረጅም ጊዜ ከሚታወቁና ከአብዛኛው የሸዋ ሥርወ ነገሥታት ጋር መረር ጥላቻና ቅራኔ ካላቸው ከአመር ወልስማ ተከታዮች ከሚወለደው ከግራኝ ኢብራሂምና ስሟ በታሪክ ካልታወቀው አንዲት ሶማሊኛ ተናጋሪ ሴት መወለዱን ነው። በተለያዩ ሥርወ ነገሥታትና በቆለኞቹ ሱልጣናት መካከል ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ የተደረጉት ፍልሚያዎች ለግራኝ አህመድ የቅርብና ስጋ ዘመዶች፣ የባለቤቱን አባትና ታላቅ ወንድሙን ጨምሮ አያሌ የእሱ ጎሳ አባሎች ተሰውተዋል ይባላል።

ይህንን በመሰለ የብቀላና የጥላቻ መንፈስ ወላጆቹ ግራኝን ኮትኩተው ያሳደጉት ይመስላል። እሱም በበኩሉ በትግሉ ውስጥ መሳተፍ የጀመረው በለጋ የወጣትነት ዘመኑ ነው። እሱ ከመራው የጂሃድ ውጊያ ለበርካታ ዓመታት ቀደም ብለው እሱና እሱን መሰል ግብራበሮቹ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ባህሪው በጎላ መልኩ ሳይፈካ ከቆላው ክልል እየተንደረደሩ በአገሪቱ ምሥራቃዊ ክልል ሰፍሮ በሚገኘው የመንግሥቱ ሠራዊት ላይ አዘውትረው በሚጥሉት አደጋና እንዲሁም በደገኛው አምራች ገበሬ ላይ በሚያካሄዱት ወረራና የዘረፋ ተግባር ግራኝ ጥሩ የውጊያ ልምምድ እንዳገኘና የጦር አመራር ስልትም እንደቀሰመ አያጠያይቅም። በጊዜ ሂደትና ባገኘው ተመክሮ ከተራ ተዋጊነት ተነስቶ በተለያዩ ጊዜያቶች፡ በተለያዩ ደረጃ እና እርከን ላይ ሲደርስ፣ የፖለቲካ ብስለትም በማግኘቱና ባገኘውም በራስ የመተማመን ስሜት ይመስላል የክርስቲያኑን ማዕከላዊ መንግሥት ወግቶ መጣል ኢትዮጵያን የእስልምና ተከታዮች ሃገር ብቻ የማድረግ ምኞት እንዳደረበት እሙን ነው። ያለጥርጥር ለዚህ እምነቱ ማስረጃ የሚሆነው ወረራውን ከጀመረ በኋላ በውጊያው ሂደት ውስጥ ባጋጠሙት ተደጋጋሚ የጦር ሜዳ ድሎች ተኩራርቶና ተብቶ እጅህን ስጥ ሲል ለአፄ ልብነድንግል ከዚህ በታች የተመለከተውን ደብዳቤ መፃፉ ነው። “ኢትዮጵያ የእስላም ግዛት እንድትሆን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለሆነ ከላይ የተቆረጠውን ውሳኔ መቃወም ከንቱ ነገር ነው።”

የግራኝን ማንነት በውል የተረዱት ቱርኮችና አረቦች የነሱን የቆየ ስትራቴጂያዊ ዓላማ ተግባራዊ ያደርግላቸው ዘንድ የእሱን ፀረ-ክርስቲያን የበቀል ፍላጎት ማሳካት በሰለጠነ ተዋጊ የሰው ኃይል፣ በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በሌሎችም ለጦርነቱ አስፈላጊ በሆኑ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፎች ሠራዊቱን አደራጅተው ለጂሃድ ዘመቻ ሲያዘጋጁት በነአፄ ልብነድንግል የሚመራው ማዕከላዊ መንግሥት ስለሚደገስለት የመከራ ድግስ መረጃ የሌለው ይመስላል። ለውጊያም የተዘጋጀ አልነበረም።

በአካባቢው የእስላም አገሮች ሕብረትና በቱርኮች አስተባባሪነት ዋናው መሠረት የኢትዮጵያ እስላሞች ሆነው በቱርኮች፣ በአረቦችና በጥቂት እስላማዊ ሕንዶች ጥምር በተደራጀውና በኢማም አህመድ ግራኝ በተመራው በእስላማዊ ሠራዊትና በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት መካከል በሸዋ ክፍለ ሃገር ሽንብራ ኩሬ በተባለ ስፍራ መጋቢት 2 ቀን 1521 ዓ.ም ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ይህ ውጊያ የዚያን ጊዜይቱን ኢትዮጵያ ዕድል የሚወስን ታላቅ ውጊያ ሆኖ ሳለ በንቀት ወይም ያለ ዕውቀት የተደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ባይኖረንም የንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት የጠላቱን ዓላማ፣ መጠን፣ የውጊያ ስልትና የታጠቀውን የትጥቅ አይነት ቀደም ብሎ በውጊያ መረጃ ያለመገምገምና ያለመገንዘብ ድሉ የእስላማዊው ሠራዊት ሆነ።

ከሽንብራ ኩሬ ታላቅ ውጊያ በኋላ የተደረጉትን አብዛኛዎቹን አውደ ውጊያዎች ግራኝ ራሱና ጥቂቱን ከፍተኛ ተዋጊ የጦር መኮንኖቹ በመሯቸው በባሌ፣ በሲዳሞ፣ በሸዋ፣ በወሎና በትግራይ ብቻ በተደረጉ አሥራ አንድ አውደ ውጊያዎች መላውን ኢትዮጵያ ለመቆጣጠር

የተደረገውን ጥረት ለመከላከልና ለማክሸፍ እስከ 1525 ዓ.ም ድረስ በተደረገው ትግል የመንግሥቱ ሠራዊት በተከታታይ በደረሰበት ሽንፈት፣ ምርኮ፣ በመቁሰልና በመሰዋት በመመናመኑና በመበታተኑ በሰሜኑ የአገሪቱ ክልሎች በተለይ ከተንቤን ውጊያ በኋላ የግራኝን ሠራዊት በተደራጀ መልክ ፊትለፊት ቆሞ የሚዋጋ የንጉሡ ሠራዊት አልነበረም ማለት ይቻላል።

ከተጠቀሱት ውጊያዎች በኋላ በንጉሡና በግራኝ ሠራዊት መካከል የተደረገ መደበኛና ጠጣር ውጊያ ቢኖር፤ ነገሥታቱ በሚያስገርም ጭካኔና እራስ ወዳድነት ለሥልጣናችን እስጊ ይሆናል በሚል አጉል ጥርጣሬና ስጋት ከአብራካቸው የወጡ ልጆቻቸውን በለጋው የወጣትነት እድሜያቸው በግዞት አኑረው በግዞት የሚገሉባቸው ተራሮች ላይ የተሰሩ የወጣት መሣፍንት ወህኒ የተደረጉት ናቸው። ግራኝ ከግሼ አምባ ውጊያ በኋላ ለተከታታይ ዓመታት በማጥቃትም ሆነ በመከላከል በተደራጀ መልክ የገጠመው የንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ስላልነበረ ዋናና ዓይነተኛ ዓላማው አድርጎ ያከናወናቸው እኩይ ተግባሮች፡-

1ኛ/ አፄ ልብነድንግልን በመከታተል የገቡበት ገብቶ በሕይወት መያዝ ባይቻል መግደል፣

2ኛ/ ሠራዊቱን በተለያዩ ክፍለ ሠራዊት ከፋፍሎ በመላ አገሪቱ የተለያዩ ክልሎች፣ አውራጃዎችና ወረዳዎች በማዝመት ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን ማጥፋት፣ አገሬውን መዝረፍና መግፈፍ፤ በሰይፍ አስገድዶ ማስለም፣ በአገሪቱ ያሉትን የቀንድና የዳልጋ ከብቶች ወደ አረብ አገሮች መንዳት፤

3ኛ/ ወጣቶች በአማካኝ የጎልማሳነት እድሜ ክልል ውሰጥ ያሉትንና ጤናም የሆኑትን ወንድና ሴት የአገሪቱን ዜጎች በባርነት ወደ ተለያዩ አረብ አገሮች መንዳት የመሳሰሉት ናቸው።

የጠላውን ወይም ተፋላሚውን ገዥ መደብ ወይም መንግሥት በመበቀል ታግሎ መጣልና ብሎም የፖለቲካ ሥልጣን በመቆናጠጥ አገሪቱን የእስልምና እምነት ተከታዮች ሃገር ብቻ ማድረግ አንድ ነገር ነው። የእናት አገሩን ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት እየጠራረገ ወደ አረብ አገሮች መላክ ያነሰ ይመስል ወገኖቹን አስገድዶ ከአገራቸው በማስወጣት በባርነት ወደ ባዕድ ሃገር መላክ ግን ማንኛውንም እምነት ወይም ሃይማኖት ተከታይ የሆነ የሰው ልጅ ህሊና የማይቀበለው እጅግ ወራዳ ድርጊት ነው። እናም እውን ግራኝ እንደሚናገረው ለአላህና ለእስልምና ታማኝ ሰው ነበረ ወይ? የሚያሰኝ ነው።

ከጎረቤቶቻችን ከአረቦችና ከቱርኮች ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ለመግባት ምክንያት የሆነው የፖርቹጋል መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የሰጠው አንዳችም ድጋፍ ባለመኖሩ አፄ ልብነድንግል ሕይወታቸውና ንጉሠ ነገሥታዊ ክብራቸው በግራኝ እጅ እንዳይወድቅ ካንዱ ቦታ ወደ ሌላው ሲሸሹ በመንገላታት ጤንነታቸው ታውኮ በ1532 ዓ.ም በደብረዳሞ ገዳም አርፈው ልጃቸው ወጣቱ ገላውዲዎስ ተተኩ። አፄ ገላውዲዎስ ከነገሱ በኋላ ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣትና አገሪቱን ከወራሪው ሠራዊት ለማፅዳት ያስችላሉ ብለው ያተኮሩባቸው የትግል ስልቶች ሁለት ነበሩ፡-

1ኛ/ የነበራቸውን አነስተኛ ሠራዊት በጣም አነስተኛ በሆኑ የተለያዩ ተዋጊ ቡድኖች አደራጅተውና የሚዋጉባቸውን የውጊያ ቀጠናዎች ለይተው በመስጠት አሰማርተው ያላቋረጠ የደፈጣ ውጊያ በማካሄድ የግራኝን ጦር እረፍትና ፋታ ነስቶ በመቆናነስና በማዳከም የውጊያ ሞራሉን አላሽቆ በተቃራኒው የወገንን ሞራልና የውጊያ ብቃት መልሶ መገንባት፣

2ኛ/ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለወሳኙ ትግልና ብሎም ድል በመቀስቀስና በማነሳሳት አዲስ ተዋጊ የጦር ኃይል መልምሎ በማሰልጠንና በማደራጀት ጠንካራና መጠነ ሰፊ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ለመውሰድ መደበኛ ብሔራዊ ጦር ማዘጋጀት ነበር።

በአፄ ገላውዲዎስ በሚመራው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ሠራዊት ጎን ተሰልፈው ለመዋጋት በ1533 ዓ.ም በክርስቶፎር ደጋማ የሚመሩና ዘመናዊ ትጥቅ ያላቸው አራት መቶ ወታደሮች ከፖርቹጋል መንግሥት ተልከው በምፅዋ በኩል ኢትዮጵያ በመግባት በሰሜኑ የአገራችን ክልል ከንጉሡ እናት ከእቴጌ ሰብለወንጌል ጋር ተገናኙ።

አፄ ገላውዲዎስ በዚህን ጊዜ በሸዋ ከግራኝ ሠራዊት ኋላ የደፈጣ ውጊያ ይመሩ ስለነበርና ወቅቱም ክረምት በመሆኑ ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር መገናኘት ባይችልም ወጣቱ የፖርቹጋል መኮንን በአካባቢው ከነበሩት ጥቂት የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር ተጠናክሮ በትግራይና በወሎ ሰፍሮ በነበረው የግራኝ ጦር ላይ ሁለት የማጥቃት ውጊያዎችን ሰንዝሮ አመርቂ ድሎችን ለማግኘት ችሎ ነበር።

ከዚህ በኋላ ከንጉሡ ነገሥቱ ተገናኝቶ በተቀናጀ ኃይል ብርቱ ጥቃትን ለመሰንዘር የሚቻልበትን ጊዜና ሁኔታዎች ሁለቱም ሲፈልጉና ሲጠብቁ በባከነው ጊዜ ተጠቅሞ ግራኝ ተጨማሪ የቱርክ፣ የአረብና የሕንድ ቅጥረኛ ተዋጊዎች፣ መድፎችና ነፍጦችን አስመጥቶ ክርስቶፎር ደጋማ በሚመራቸው የፖርቹጋልና የኢትዮጵያ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ተዋጊዎች ላይ በሰነዘረው ከባድ የማጥቃት ውጊያ አብዛኛው የኢትዮጵያና የፖርቹጋል ወታደሮች በሞትና በመቁሰል ከውጊያ ውጭ ሲሆኑ መሪያቸው ክርስቶፎር ስለተሰዋ ድሉ የእስላማዊው ወራሪ ሠራዊት ሆነ።

ከክርስቶፎር ደጋማ ሞት በኋላ ግራኝና ሠራዊቱ በእነሱ አሸናፊነት ትግሉ እንደተደመደመ ገምተውና አምነው አብዛኛውን የቱርክ፣ የአረብና የሕንድ ምንደኛ ተዋጊዎችን ወደ አገራቸው በመመለስ ማዕከላዊ የውጊያ መምሪያ ጠቅላይ ሰፈራቸውን ውብና ነፋሻ በሆነው በጣና ሐይቅ አካባቢ አድርገው በሚዝናኑበት ጊዜ አፄ ገላውዲዎስ ለመልሶ ማጥቃት የሚያስፈልጋቸውን ዝግጅት አጠናቀቁ።

በንጉሠ ነገሥቱ ቀደምት እርምጃ ወሳጅነት የካቲት 28 ቀን 1535 ዓ.ም በገላውዲዎስና በግራኝ ሠራዊት መካከል በዘንተራ በር ላይ ታላቁና የመጨረሻው ውጊያ ተደርጎ ግራኝ አህመድ ውጊያው ላይ ሕይወቱን ሲያጣ የእስልምና እምነት አራማጅ የሆነው ወራሪ ሠራዊት ተበታተነ።

በዚያን ዘመን የዓለም ልዕለ ኃያላን የነበሩት የቱርክና የፖርቹጋል መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካ ቀንድ፣ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቂያኖስ ስትራቴጂያዊ ክልሎች ለወታደራዊ የኃይል ሚዛን የበላይነት፣ ለገበያና ለፖለቲካ ጥቅማቸው በሃይማኖት ሰበብ ለሚያካሄዱት ፍልሚያ የእነሱ መናኸ በማድረግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሱት እልቂትና በሃገር ላይ የፈፀሙት ጥፋት ለመጪው ተከታታይ የኢትዮጵያ ትውልዶች ትምህርት ሊሆን የሚገባ ነው።

## የኦሮሞ ማህበረሰብ ፈለሳና ወረራ

እነዚህን በጣም የተጨመቁ የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳሮችና አበይት ክስተቶች ወደ አብዮቱ ታሪክ መንደርደሪያ መሆን በሚችሉ መልካቸው ስጀምር፣ ዓላማዬ የኢትዮጵያን

ታሪክ ለመተረክ እንዳልነበረ ሁሉ፣ አሁንም ዓላማዬ የኦሮሞን ብሔረሰብ ታሪክ ለመተረክ አይደለም።

ስለ ኦሮሞ ብሔረሰብ ታሪክ አንዳንድ ፀሃፊዎችና አፈ-ታሪክ ተራኪዎች የኦሮሞ ማህበረሰብ ከእስያ ወይም ከማዳጋስካር ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚሉት መላምት የኔ ትኩረት አይደለም። የሰው ልጅ ምንጩ አፍሪካ ከመሆኑ ባሻገር ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላው መንቀሳቀስ፣ መፍለስና መሸጋሸግ የእድገቱ ሂደት የሚያስከትለው ባህሪውም ታሪኩም ነው። በዚህና በሌሎችም አያሌ ምክንያቶች የኦሮሞ ማህበረሰብ ንቅናቄ በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የጎላ ስፍራ አለው። የኦሮሞ ፍለሳ የፈጠረውን የዘር መከላለስ፣ መሰባጠር፣ ተመሳሳይ አገራዊ ስነልቦና መፍጠር፣ የጋራ ባህል መላበስና ቋንቋን መወራረስ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ የነበሩ የተለያዩ ማህበረሰቦችን የሰው ኃይል መጠን፣ በመሬት ይዞታ ወይም አሰፋፈር ታሪክ ላይ ያስከተለውን መሰረታዊ ለውጥ ሳልገልፅ ባልፍ የታሪኩን መንደርደሪያ የተሟላ አያደርገውም።

ጥንታዊው የሰው ልጅ ታሪክና እንዲሁም የሕብረተሰብ እድገት ሕግጋት እንደሚያስተምረን ምርትና የምርት ኃይሎች ባልዳበሩበትና የሰው ልጅ በጥንታዊው የከብት እርባታ ደረጃ የዘላን ሕይወት በሚኖርበት ጊዜ የሃገር ድንበር ወይም ወሰን የሚባለውን ገደብ አያውቀውም። ቋሚ የመኖሪያ ስፍራና የመኖሪያ ቤትም የለውም። ቤቱና ንብረቱ፣ በአጠቃላይ የመኖር ዋስትናው የከብት ሀብቱ ስለሆነ ለከብቱ ግጦሽ የሚሆን ለምለም ሳርና በቂ ዝናብ ያለውን የአየር ንብረት ክልል ሲፈልግና የከብቱን ጭራ ሲከተል የሚኖር ሕዝብ ነው።

በዚህ የእድገት ደረጃ ላይ የነበረው የኦሮሞ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ሰሜን ከአፍሪካ ቀንድ ተነስቶ አያሌ ዘመናትን በጠየቀ ጊዜ ውስጥ ቀስበቀስ እየተንቀሳቀሰ በኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ዛሬ ቦረና ብለን በምንጠራው አካባቢ ለብዙ ጊዜ ሰፍሮ ኖረ። በ16ኛ ምዕት ዓመት እንዲሁ ከቦረና ቀስበቀስ በመንቀሳቀስ በጋሞ ጎፋና በሲዳሞ ክፍለ ሀገሮች መካከል በሚገኙት በጫሞ፣ በአባያታ፣ በአዋሳና በዝዋይ ሀይቆች አካባቢ ባለው እጅግ ለምና ሰፊ የከብት ግጦሽ ባለበት ክልል ድረስና እንዲሁም ታቹን በባሌ ክፍለ ሃገር ውስጥ በተለይ በገናሌ በወይብና በዋቢ ወንዞች ሸለቆዎችና አካባቢዎች ድረስ ተስፋፍቶ በሰላም፣ በምቾትና ድሎት የሚኖር ሰላማዊ ማህበረሰብ ነበረ። የኦሮሞ ፈለሳ እየተባለ የሚነገርለትም ከዚህ በላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ክልሎች ቀድሞ ከነበረበት የአፍሪካ ቀንድ ቆላማ ስፍራ ተነስቶ ወደ ደጋማዎቹ ክልሎች ያደረጋቸው ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ከ250 ዓመታት በላይ የእርስ በእርስ ጦርነትና ከ15 ዓመታት የግራኝ አመጽ በኋላም የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ፣ ክርስትያኑ ሕብረተሰብ በተለይ ጦርነቱ ካደረሰበት ጉዳት ያላገገመ ብቻ ሳይሆን ትግሉም ገና አላባራም ነበር። የግራኝ አመጽ በሰው ላይ ባደረሰው እልቂት፣ በአገሪቱ ላይ ባስከተለው ታላቅ ውድቀት በብርቱ የተጎዳውና የተዳከመው ደገኛው ሕዝብ የዳልጋና የቀንድ ከብቶቹ የወራሪው የግራኝ ሠራዊት ቀለብ ከመሆናቸው ሌላ የተረፉትም ተጠራርገው ወደ አረብ አገሮች ተነድተዋል። አብዛኛው ደጋማው የእርሻ መሬት ለብዙ ዓመታት ባለመታረሱ በመላ አገሪቱ ረሀብና በሽታ በተስፋፋበት ጊዜ ሰላማዊ የነበረውና ከመንግሥት ቀርቶ ከተቀሩትም የአካባቢው የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ምንም አይነት ቅራኔ ያልነበረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ባህሪውን በመለወጥ የውጊያ ትጥቅ አምርቶና ተዋጊ ሠራዊት አደራጅቶ በ16ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የአገሩን ደጋማ ክልሎች መውረር ጀመረ።

በመንገዱ ላይ የሚያገኛቸውን በአገሪቱ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅና እንዲሁም መሃል ሃገር ነዋሪ የሆኑትን የተለያዩ ነባር ማህበረሰቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች እየወረረ በገዳ ሥርዓት ተዳዳሪ፣ የጎሳ ማህበር አባልና የኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ አደረጋቸው። በዚህ ሁኔታ የሰው ኃይሉን ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እያዳበረ እስከ ሰሜኑ የአገራችን ክልሎች ሸዋ፣ ወሎና ጎጃም ብሎም እስከ ትግራይ ድንበር ድረስ የአገሪቱን አንድ ሦስተኛ የቆዳ ስፋት ብቻ ሳይሆን ምሥራቅ አፍሪካንም አጥለቀለቀ።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው ግራኝ ከምሥራቃዊው አገራችን ክልል ተነስቶ መላውን ኢትዮጵያ የወረረው በክርስቲያን ገዥ መደቦችና በእስላሙ ሕብረተሰብ መካከል የነበረውን ቅራኔ ተጠቅመው የቱርክ አረባዊና የፖርቹጋል መንግሥታት የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ መንግሥት ጥሎ የእስላም መንግሥት ለማንሳት የተደረገ ሀይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማ ያለው ብቻ ሳይሆን በቂምበቀልም የተደረገ አመጽ ነው። የኦሮሞ ማህበረሰብ እንደ ሶማሊያና የአፋር ማህበረሰቦች ከአካባቢው የአረብ አገሮች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበረውም። ከማዕከላዊ መንግሥት ወይም ከተቀሩት የሕብረተሰብ ክፍሎች በመንፈሳዊ እምነት፣ በአስተዳደር ጉድለትም ደረሰብኝ የሚለው በደልና ብሶት አልነበረውም።

ጥንት በሶማሊያዎችና በባንቱ ማህበረሰቦች ከሚደርስበት ጥቃት፣ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ 300 ሚ/ሜትር በታች በሆነበት እጅግ ሞቃታማና ደረቅ መሬት ላይ ሆኖ መኖሩ ቀርቶ እስከ 2,000 ሚ/ሜትር ዓመታዊ የዝናብ መጠን ባለው እጅግ ለምና ሰፊ የግጦሽ መሬት ላይ ሰፈረ። እናም የተመቻቸና የተደላደለ የዘላን ኑሮ በመኖሩ ደስተኛነቱና ሰላማዊነቱ የሚነገርለት ማህበረሰብ ጦረኛና ወራሪ የሆነበት ምክንያት ምን እንደሆን የአያሌ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ ለሚያጠኑ ባዕዳንም ያልተመለሰ ጥያቄ ነው። ስለ ኦሮሞ ፈለሳና ወረራ፣ እንዲሁም ስለ ኦሮሞ ታሪክ የጻፉ ሰዎች ሁሉ ንቅናቄው ፖለቲካዊ ይዘት እንዳልነበረው ሲያምኑና ሲስማሙ ጥያቄውን አንስተው ምክንያቱን ግን ያብራሩ የሉም። የኦሮሞ ማህበረሰብ ይህንን የመሰለ ታላቅ ወረራ ለማድረግ የተነሳበትም ምክንያት በአገሪቱ ደቡባዊ ክፍል ደጋማና ወይና ደጋማ ለምለም መሬት ላይ ሰፍሮ ባገኘው ተድላና ደስታ ከብቱም ሰውም በከፍተኛ መጠን በመራባታቸውና ከፍተኛ የመሬት ጥበት በመፈጠሩ ለመስፋፋት ሲባል የተደረገ ወረራ ነው የሚሉን እቶ ይልማ ደሬሳ ብቻ ናቸው። ይህንን አስተያየት አብዛኛው የኦሮሞ ብሔረሰብ አባል የሆኑ ምሁራን የዚህን ታሪክ ደራሲ ጨምሮ አያሌ ኢትዮጵያውያን አይቀበሉትም። ይህንን የምንልበት ምክንያት እንኳንስ በ15ኛውና በ16ኛው ምዕተ ዓመታት ቀርቶ ዛሬም በደቡብ ኢትዮጵያ ለጦርነት የሚዳዳ የግጦሽ መሬት ችግር ያለመኖሩን ስለምናውቅ ነው።

ምክንያቱ የኦሮሞ ማህበረሰብ ቁጥር መብዛትም አይደለም። ችግሩ ይሄ ቢሆን ኖሮ የግጦሽ መሬት ለማግኘት ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ባለበትና የመሬት ጥበት ችግር ወዳለበት የመሃልና የሰሜናዊ የአገሪቷ ክልሎች መሄድ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። በአጭሩ አብዛኛው ሸዋና በአገሪቱ ሰሜናዊ ክልሎች ያለው መሬት ከደቡብ፣ ከምዕራብና ከምሥራቁ ክልሎች መሬት መጠን አነስተኛ ሲሆን፤ ከየትኛዎቹም ክልሎች ሰው በብዛት ለአያሌ ምዕት ዓመታት የሰፈረበትም ሲሆን፤ አብዛኛው ለእርሻ ጥቅም የዋለ በመሆኑም ከብት አርብቶ ለሚኖር ዘላን ሕብረተሰብ በቂም አመችም አልነበረም።

የመሬት ችግር ነበር የተባለውን አስተያየት ደግፈንና ከአምስት አገሮች በላይ የሚያካትተውን የምሥራቅ አፍሪካን እጅግ ሰፊ የኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች መሬትም እንደሌለ አድርገን የመሬት ችግር ነው ብለን እንደ ምክንያት ብንቀበል እንኳን፡ በአይነትም

ሆነ በመጠን ወይም በልምላሜ በዚያን ጊዜ ወደር የሌለውን ቦረናን፣ ሲዳሞን፣ ጋሞን፣ ባሌን፣ አርሲን፣ ሸዋንና ሐረርጌን አልፎ ወሎንና ጎጃምን መውረር ጠብ ፍለጋ እንጂ መሬት ፍለጋ ሊሆን አይችልም። የኦሮሞ ማህበረሰብ በ16ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ አገሩን ለመውረር ያነሳሳቸውን ምክንያት ኢትዮጵያውያን ምሁራን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

1ኛ/ ገዳ የሚባለው የጎሳዎች ማህበር አደረጃጀትና ድርጅቱ የሚመራበት ሥርዓት ሲሆን

2ኛ/ በዚሁ ምዕት ዓመታት መጀመሪያ ላይ የሶማሊያና የአዳል ማህበረሰቦች በብዛት የተሳተፉበት የኢትዮጵያ የእስልምና እምነት ተከታዮች በጎሳ ማህበርና በሃይማኖት ሽፋን ባካሄዱት አመፅና ወረራ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ወግተው በማሸነፍ መላውን ኢትዮጵያ መቆጣጠር ከቻሉ እኛስ ኦሮሞዎቹ ይህንን ለማድረግ ምን ይሳነናል የሚል ስሜት በኦሮሞ የገዳ መሪዎች ህሊና ስለተሰረፀ ነው የሚሉት።

ገዳ በተባለው የጎሳ ማህበራዊ ድርጅት ደንብ መሠረት ወንድ ልጆች በእድሜ ቅደም ተከተል በየስምንት ዓመታቱ የተለያየ ደረጃ በጎሳው ማህበራዊ ድርጅት ውስጥ በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች የሚደለደሉ ሲሆን፣ ከ40 እስከ 48 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ጎልማሶች ሉባ በተሰኘ ስም የጎሳውን ማህበራዊ ድርጅት አስተዳደር፣ የፍርድና የጦር አመራር ኃላፊነት የሚረከቡበት ድርጅታዊ መዋቅርና የጎሳው ማህበር የሚመራበት ሥርዓት ነው።

ገዳ በአጠቃላይ ባህሪው ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ ሳለ በየስምንት አመታቱ በሚደረገው ሕዝባዊ ምርጫ ወደ ከፍተኛው የጎሳ ማህበራዊ ድርጅት የአስተዳደር፣ የፍርድና የጦር አመራር ኃላፊነት ላይ የሚወጡት የአመራር አካላት በሕዝቡ ዘንድ አንድ ቡድን ወይም ሉባ ከሌሎቹ ተሽሎ ለመታየት፣ መልካም ዝና ለማትረፍና ታሪክ ለመሻት ሲል በሚፈጥረው ውድድር በየተራቸው አንዱ ወሮ ከያዘው ወይም ከተቆጣጠረው ክልል አልፎ በበለጠ ሌላ ክልል በመውረር ለሉባው ወይም ለጎሳው ማህበራዊ ድርጅት መልካም ስምና ጀብዱ አስገኘን ብለው በማመን መሪዎቹ ሰላማዊውን ሕዝብ ጦረኛና ጀብደኛ አደረጉት።

ይህን የጀብደኝነት ወረራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ እንዲከፍል በተገደደው አስፈላጊ ያልሆነ መሪር መስዋዕትነት አስከፊነቱና ሰላም አልባነቱ ምክንያት የገዳ ሥርዓት በሕዝቡ ዘንድ የተጠላ እንጂ የተወደደ አልነበረም። የየጎሳው ተዋጊ ሠራዊት ወደ መሃል ሃገርና የተዋጊነት ባህሉ ጠንካራ ወደሆነበት የሕብረተሰብ ክፍል በተጠጋ ቁጥር ከሚደርስበት ብርቱ ተቃውሞ ሌላ የንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ሠራዊት በጥንካሬ ከመከላከል ባሻገር በየጊዜው እየተጎላበተ ባደረገው መልሶ ማጥቃት የኦሮሞው ሠራዊት እንቅስቃሴ መገታት ብቻ ሳይሆን በታላቅ ተጋድሎ ወሮ የያዘውን ክልል እየጣለ እንዲያፈገፍግ ይገደድ ጀመር። በዚህ ሁኔታ ውጊያው ተብ እረገብ እያለና በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋናው ችግር መሬት ሳይሆን ሰላም ስለነበረና ኦሮሞዎች ወደ መጡበት ይመለሱ የሚል የበቀል ፍላጎትና ግፊትም ስላልነበረ ቀስበቀስ ሰላምና መረጋጋት ተፈጠረ። ፈለሳውና ወረራው በዚህ ሁኔታ ለአንዴና ለመጨረሻ ከቆመና የገዳ ሥርዓትም ከከሰመ በኋላ የኦሮሞ ማህበረሰብ ዘላናዊ ኑሮውን እየተወ በገዳ ሥርዓት ግፊት እየተነዳ በየደረሰበት ክልልና አካባቢ በቋሚነት ሰፍሮ በግብርናው ተግባር አዲስና ሰላማዊ ኑሮውን ጀመረ። የሚያሳየውም ማህበራዊ ባህሪ፣ የጥንቱንና የራሱ የሆነውን ሰላማዊነትንና በአዲስ ሕይወቱም አምራችነትን፣ ቅንነትንና ሃገር ወዳድነትን ነው። ከገዳ መክሰም በኋላ የኦሮሞ ብሔረሰብ በረጅም ታሪኩ በጎ ማህበራዊ ለውጥን ደጋፊና መሻሻልን የሚፈልግ እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የብሔረሰቡ አባላት ወይም አካላት የኢትዮጵያ እድገት ደንቃራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ጠንቅ የሆኑበት ጊዜ የለም።

የኦሮሞ ሕዝብ ነፃ አውጪነን የሚሉን ጥቂት የኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደሚገምቱትና እንደሚፈልጉት ኦሮሞ በመጠኑም ሆነ በባህሪው እንዲሁም በታሪኩ ጎጠኛና ዘረኛ አይደለም፤ ምክንያቱም በባህሉም ሆነ በደሙ የብዙ ማህበረሰቦች ቅምር ሕዝብ ነውና። የኦሮሞ ማህበረሰብ ወይም ነገድ ምናልባት አንድ ወጥ ደም ወይም ዘር የነበረው ጥንት በቅድመ ገዳ ሥርዓት እንደሆነ እንጂ በድህረ ገዳ እንደ አማራው፣ ትግሬውና ጉራጌው ወዘተ የአንድ ቋንቋ ቤተሰብ እንጂ የአንድ ወጥ ዘር አይደለም። ስለዚህም ስሙም ሆነ መለያው ኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ነው።

# የሥርዓት አልበኞች መሣፍንት ዘመን

በታላቁ የዛንታር በር ውጊያ ድል የግራኝ ሠራዊት አከርካሪውን ተመቶ ከውጊያ ውጭ በመሆን ከተበታተነና ግራኝም በዚሁ የጦር ሜዳ ከሞተ በኋላ የአገሪቱ ሰሜናዊ ክልሎች በሙሉ ከጠላት ጦር ቅሪቶች ቢጸዱም የተቀሩት የደቡብ ክልሎች ለብዙ ጊዜ በማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ስር አልነበሩም።

የምሥራቁን ክልል የሚቆጣጠረው የእስልምና እምነት አራማጅ ሠራዊት ወደ መሃል ሃገር እየሰረገ፣ የኦሮሞም ማህበረሰብ ሠራዊት እንዲሁ ከደቡብ ወደ መሃል ሃገር እየጠለቀ ከንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ጋር ሁለቱም በየፊናቸው ይዋጉ ስለነበር የሸዋ ክፍለ ሃገር ለብዙ ጊዜ የውጊያ አውድማ ሆኖ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከዛጉዌ መንግሥት ውድቀት በኋላ ሸዋ የአገሪቱ ርዕሰ ከተማ ሆኖ እንደመቆየቱ መጠን የማዕከላዊው መንግሥት ማገርና ግርግር የነበረው ሠራዊትና የሸዋ ሕዝብ ግምባር ቀደም የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ ስለነበሩ በትግሉ አፍላ ሂደት ቀደም ብለው ከተመሰቃቀሉና ከተናዱ ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት የፀጥታው አስተማማኝ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን መሠረተ ልማቶች፣ አብያተ ክርስቲያናትና ቤተ መንግሥቶች ሁሉ ስለወደሙ መንበረ መንግሥቱን ወደ አገሪቱ ሰሜን ምዕራብ ክልል እራቅ ማድረግ አስፈልጎ ነበር።

የሰሜኑ ክልሎችም ቢሆኑ ከግራኝ ወረራ የዳኑ ባለመሆናቸው በመሠረተ ልማት በኩል የነበረው ሁኔታ ከሸዋ ባይሻልም በፀጥታው ረገድ በነበራቸው አስተማማኝነት ጎንደርና ጎጃም በአጠቃላይ፣ የባሕር ዳርና ደብረ ታቦር አውራጃዎች በተለይ በጊዜያዊ ጠቅላይ የጦር መምሪያነት ለተወሰነ ጊዜ አገልግለዋል።

በግራኝ ምትክ አሊ ኑር የተባለ የሐረር አሚር ግራኝ ከሞተ በኋላ እስላማዊ ጦሩን እንደገና መልሶ በማቋቋምና በማደራጀት የግራኝን ደም ለመበቀልና ቢቻልም የንጉሠ ነገሥቱን ብሔራዊ ጦር እንደገና ለመፈተን ወደ ሸዋ መጥቶ ከአፄ ገላውዲዎስ ጋር ውጊያ ገጥሞ በሁለቱ ኃይሎች መካከል ታላቅ ውጊያ ከተደረገ በኋላ አፄ ገላውዲዎስ ውጊያው ላይ ወደቁ።

አሊ ኑር የተመኘውን ግን በዚያ ሁኔታ ይሆናል ብሎ ያልጠበቀውን ታላቅ ድል ስለተጎናጸፈ... ሕዝቡ ጋር በደስታ ካከበረ፣ ሠራዊቱም ካገገመና በውጊያው በተሰዋውና በተጎዳው የሰው ኃይል ምትክ ካሟላ በኋላ ዳግም ለመዋጋት ወደ ሐረር ሲመለሱ መንገድ ላይ አድፍጦ ይጠብቀው የኦሮሞ ሠራዊት እንደገና ለማንሰራራት በማይችልበት ሁኔታ እስከ ሐረር ከተማ ድረስ እያሳደደ ለአንዴና ለመጨረሻ ደመሰሳቸው። ማዕከሉን በሐረር ከተማ አድርጎ ከ15 ዓመት በላይ የተዋጋው የእስልምና እምነት አራማጅ ሠራዊት ህልውናም በዚሁ አከተመ።

የኦሮሞ ሠራዊት ወረራ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ተገቶ ውጊያው ከቆመና እንዲሁም ሰላምና እርቅ ከወረደ በኋላ ማዕከላዊው መንግሥት የአገሪቱን ማዕከልና አካባቢውን ቢቆጣጠርም መንበረ መንግሥቱን በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ማቆየት ስለታመነበት አፄ ፋሲል በ1672 የዛሬውን የጎንደርን ከተማ ከቀረቆሩ በኋላ ጎንደር ከ17ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ ከ200 ዓመት በላይ የኢትዮጵያ ርዕስ ከተማ ሆነች።

በአገሪቱ ሰሜን ምዕራብ ዳርቻ በጎንደር ከተማ መልሶ ለተቋቋመው መንግሥት ስፍራው መላውን ኢትዮጵያ አማክሎ በመቆጣጠር ጠንካራና የቅርብ አመራር ለመስጠት አመቺ አልነበረም። ከዚህ ሌላ በመንግሥቱ የአመራር አካላት ውስጥ የነበሩት አማርኛ፣ ኦሮምኛና ትግርኛ ተናጋሪ የነበሩ አንጃ ቡድኖች ያደርጉት በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ፣ አንዱ በሌሎች ላይ በሚፈጥረው አሻጥርና ይህም በሚፈጥረው ቅራኔ የተወጠሩ ነበሩ።

በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተዳከሙት ነገሥታት ከጎንደር መንበረ መንግሥት መመስረትና በግራኝ ወረራ የተፈጠሩ ቀውሶችና እነሱም ባስከተሉት ድክመቶች ተበታትነውና ተረስተው የነበሩትን ክልሎች መልሶ በማሰባሰብ ጥንታዊቷንና ታላቂቱን ኢትዮጵያ ማደስ ቀርቶ አህመድ ግራኝ ያነኮራትን ኢትዮጵያን እንኳን በማረጋጋት መልሶ ለማቋቋም የሚበቁ አልሆኑም።

ነገሥታቱ ሲሆን እራሳቸው ባይሆን ወኪሎቻቸውንና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እየላኩ እናስተዳድራታለን የሚሏትን ሃገር መጎብኘት፣ የየክልሉን ሕዝብ መገናኘት፣ ሠራዊታቸውን አዘውትረው ማንቀሳቀስና የየክልሉ ገዥ መሣፍንቶች ሕዝቡን በትክክል ማስተዳደራቸውንና ለዙፋኑም ታማኝ መሆናቸውን ከመከታተልና ከመቆጣጠር ፋንታ በጎንደር ቤተመንግሥት ተቀምጠው ለግል ደስታቸውና ለቅንጦት ኑሯቸው ብቻ የሚያስቡ በመሆናቸው ከሠራዊታቸው እራቁ፤ በሕዝቡም ዘንድ ተናቁ።

ይህንን የመሰለውን የነገሥታቱን ድክመት በቅርብ የሚያውቀው ራስ ስዑል ሚካኤል የተባለ መሥፍን በ17ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ አፄ እዩአስን በመፈንቀል መንግሥት አስወግዶ በኃይሉ ፈላጭ ቆራጭ የእንደራሴነት ሥልጣን በመያዝ ከመሣፍንት ወህኒ አንባ የፈለገውን እስረኛ መሥፍን እያወጣ አሻንጉሊት ንጉሥ ሿሚና ሻሪ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ እስከ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ድረስ ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት አልባና የሥርዓት አልበኞች መሣፍንት መራኮቻ ሆነች።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ነገሥታቱ መናቅና ተደማጭነት ማጣት፣ ከዚህም አንፃር የመሣፍንቱ ማን አለብንና ማን አህሎን ስሜት እያደገ መጥቶ የየክልሉና የየአውራጃው ትልልቅ መሣፍንቶችና ባላባቶች ለነገሥታቱ ብቻ ሳይሆን በኃይላቸው ለሚመኩትና ነገሥታቱን አሻንጉሊት ላደረጉት የማዕከሉ እንደራሴ አውራ መሣፍንቶችም አንታዘዝም፤ አንገብርም በማለት አመጹ።

ብርቱዎቹ መሣፍንቶች በደካሞች ጎረቤቶቻቸው ላይ የበላይነትን ለማግኘት፣ አንዱ ሌላውን በመግፋት ጉልት ለማስፋፋትና ሀብት ለማካበት ሲሉ በመላው ኢትዮጵያ ክልሎች ዘረፋ፣ ሽብርና ጦርነት ማካሄድ ጀመሩ። ከዚህ ሁሉ በላይ የተመኙና ይበልጥ ኃይል የተሰማቸው፣ ዘውድ ለመቀዳጀትና እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው የኢትዮጵያ መሪ ለመሆን በሚጭሩት ውጊያ አገሪቱን የጦርነት አውድማ አደረጓት።

እያንዳንዳቸው የኢትዮጵያ ንጉሥ ለመሆን ከመመኘት አልፈው ለመሆን በመዘጋጀት ላይ የነበሩት ከውጪ መንግሥታት ጋር ለመወዳጀትና ርዳታ ለማግኘት በሚፃፃፉበት ጊዜ ራሳቸውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እያሉ፣ እርስ በርሳቸው ሳይተዋወቁ ለአንድ

የባዕድ ሃገር መንግሥት ቁጥራቸው ከሁለትና ከሦስት በላይ የሆኑ ይፅፉ ስለነበረ፣ ወዳጅ ተብለው በሚፃፍላቸው መንግሥታት ዘንድ ትዝብትና መገረምን ፈጥሮ ነበር። ይህም እንግሊዝና ፈረንሳይን ለመሳሰሉት ቀንደኛ የቅኝ ግዛት ጥመኞች ኢትዮጵያ በሥርዓተ አልበኛ መሣፍንቶች የተከፋፈለች መሆኗን የሚያስረዳ በሚልዮን ብር የማያገኙትን መረጃ እቤታቸው ድረስ ይልኩላቸው ነበር።

በዚህ ዘመነ መሣፍንት እየተባለ በሚጠራው ዘመን አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የሰሜኑ ክልል ሕዝብ እየተገደደ የመሣፍንቶች ፍላጎት አስፈፃሚ በመሆን ተንቀሳቅሷል፤ ተተራምሷል፤ ተጨራርሷልም። የአንዱ ክልል ወይም አውራጃ ሕዝብ በሌላው ላይ በመዝመት የፍጅቱ፣ የዘረፋውና የጥፋቱ ተካፋይም ሆኗል። ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት በተከታታይ በደረሰባት የውጪ ጥቃት፣ የውስጥ እርስ በእርስ ጦርነቶችና ቀውሶች እጅግ ተዳክማ አቆልቁሎ ጉዞውን ከተያያዘችው የቆየች ብትሆንም ዘመነ መሣፍንትን የመሰለ ህልውናዋን እጅግ በሚያሰጋ አደጋ ላይ የጣለ ፈተና በታሪኳ ገጥሟት አያውቅም።

ይህ ጊዜ በኢንዱስትሪ የተደራጁና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቁ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች መላውን ታዳጊ ዓለም አፍሪካን፣ እስያንና ደቡብ አሜሪካን ለመቀራመት የተነሱበትና ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በውስጥ ችግሯ ተዳክማና ተከፋፍላ ለእነዚህ ኃይሎች ወረራ የተጋለጠችበት ጊዜ ነበር። በአፍሪካ አህጉር ኢትዮጵያን የምትቀናቀነው፣ ታላቁ የአባይ ጅረትና እየጠረገ የሚወስደው ለም አፈር ቢቋረጥ ህልውናዋም የሚቋረጠው፣ ምንም እንኳን ከጥንታዊዎቹ ስልጡኖችና በእድሜ አንጋፋ ከሆኑ አገሮች አንዷ ወይም ቀደምቷ ብትሆንም ኢትዮጵያን ደፍራ የማታውቀው፤ ፋርሶች፣ ግሪኮች፣ ሮማውያን፣ አረቦች፣ ቱርኮች፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ በወረራ ሲፈራረቁባት የኖረችው ግብጽ የኢትዮጵያን መዳከም በመገንዘብ ሁለቱን የአባይ ጅረቶች ከምንጫቸው ለመቆጣጠር የፈለገችውና የአፍሪካን ቀንድ ከምሥራቅ አፍሪካና ከሱዳን ጋር ቀላቅላ ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ የተመኘችው በዘመነ መሣፍንት በመዳከማችን ነበር።

ይህንን የሚያነብ፣ ድንቢጥ አይጥን ለመዋጥ የፈለገች መስሎ ቢታየውም ግብጽ እራሷ የቱርክ ከፊል ቅኝ ሆናና በቅኝ ገዥዋ እየተገፋችና እየተረዳች ምኞቷን ለመተግበር ከሱዳን ሌላ ለሱዳን ቅርብና ድንበርተኛ የሆነውን የኢትዮጵያን ሰሜን ቆላማ ክልል ከረንን ጨምሮ፡ የምፅዋንና የዘይላን ወረዳዎች፣ የዛንዚባርን ደሴትና ወደብ የመሳሰሉትን ለወረራ መንደርደሪያነት የሚያስፈልጓትን ስትራቴጂ ስፍራዎች ለመቆጣጠር ችላ ነበር።

ሥርዓተ አልበኛ መሣፍንቶች የመሩት ረጅም የርስ በእርስ ጦርነት ወደ መጨረሻው በተቃረበበት ጊዜ አብዛኛዎቹ መሣፍንቶች በጥቂቶቹ አውራና ብርቱ መሣፍንቶች ክንድ እየተመቱና እየተደመሰሱ ወይም ሽንፈታቸውን በመቀበል ለአሸናፊዎቹ እየገበሩና እያደሩ፣ በጎንደር ራስ አሊ፣ በትግራይ ትግሪኛ ደጃዝማች ውቤ፣ በጎጃም ደጃዝማች ብሩና በሸዋ ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ወደ ኋላ የቀሩ ተፎካካሪዎች ነበሩ።

ወሎ የራስ አሊ ትውልድ ሃገር ስለነበረ፣ የየጁ፣ የዋግና የላስታ መሣፍንቶች ለማዕከላዊ መንግሥት አድረው ነበር ማለት ይቻላል። የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ከ16ኛው ምዕት ዓመት በፊት በነአፄ አምደፂዮን፣ በነአፄ ይስሃቅ፣ በነአፄ ዘርዓያቆብ ወዘተ መንግሥት የነገሥታቱ ግዛት አካል ሆነው ሲኖሩ መንበረ መንግሥቱ ወደ ጎንደር ከተዘዋወረ በኋላ ነገሥታቱም መሣፍንቱም እርስ በርስ ጎራ እየለዩ በመዋጋት ስለተዳከሙ ከአክሱም ጀምሮ በማዕከላዊ መንግሥት ስር የነበሩት ቤናድር (የዛሬው የሶማሊያ ሪፓብሊክ)፣ አዳልና ኢሳ (የዛሬው የጂቡቲ ሪፓብሊክ)፣ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ሲዳሞ፣ ቦረና፣ ከፋ፣ ጎፋ፣ ሊሞ፣

እሩሲ፣ ወለጋና ኢሉባቡር ከማዕከላዊ መንግሥት አመራር ተነጥለው በኢኮኖሚውና በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዬች መተሳሰሩ ባይቀርም በአስተዳደር በኩል እንደ አንድ ነፃ ሃገር በየራሳቸው ባላባቶች ይተዳደሩ ነበር።

በዚህ ጊዜ ነበር ጎንደር ውስጥ ደንቢያ ከምትባል ወረዳ ውስጥ ከምትገኝ ቋራ ከምትባል ስፍራ ከተራ ገበሬ ቤተሰብ የሚወለድ ካሳ ኃይሉ የሚባል ሰው ወደ ትግሉ መድረክ ብቅ ያለው። ቋረኛው ካሳ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ጥሩ የደፈጣ ውጊያ ልምድ ባላቸው ጥቂት የፋኖዎች ስብስብ ያደራጁት በቁጥር እጅግ አነስተኛ የነበረ ግን በትግሉ ሂደት የዳበረውንና የጎለበተውን ጦር በመምራት መሣፍንቱን ከነሠራዊታቸው ተራ በተራ ደምስሰው ንጉሠ ነገሥት በመሆን እንደገና ኢትዮጵያን አማከሏት።

አፄ ቴዎድሮስ ሥርዓተ አልበኛ መሣፍንቶችን ከመደምሰስ፣ ቱርኮችን ረግጦ ከኢትዮጵያ ከማስወጣት፣ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ከመመስረትና የኢትዮጵያን አንድነት በአስተማማኝ መሠረት ላይ ከማቆም ባሻገር የራቀ ዓላማ ነበራቸው። አገራቸውን ከደረሰባት ረጅም የእርስ በእርስ ጦርነት፣ ሁከት፣ ፍጅትና መከፋፈል አድነው በአያሌ ምዕተ ዓመታት ጉልታዊ ሥርዓት የታሪክ ሂደት ውስጥ ከወደቀችበት ኋላቀርነት መንጥቆ የማውጣት እቅድ ነበራቸው።

አገሪቱ የጥቂት መሣፍንትና መኳንንት የግል ጉልት ሰፊው ሕዝብ በጠቅላላ ማለት ይቻላል ባሪያ፣ ሎሌና ገባር በሆነበት ሕብረተሰብ ውስጥ፣ በየክፍለ ሃገሩ፣ በየአውራጃውና በየወረዳው ፈላጭ ቆራጭ ገዥ የነበሩትን ጉልተኛ መሳፍንትና ባላባቶች ደሞዝተኛና የመንግሥት ሠራተኛ በሆኑ አስተዳዳሪዎች የመተካት፣ ሕዝቡን የሚረግጡ፣ የሚነጥቁና የሚገፉ የየመሣፍንቱን የግል ፊውዳል ሠራዊት አስወግዶ፣ በደሞዝና በሕግ እየተዳደረ ሕዝብ የሚያገለግል ብሔራዊ የሃገር መከላከያ ሠራዊት ከማደራጀት ባሻገር የጉልተኛ መሣፍንቶች፣ መኳንንቶችና የቤተ ክርስቲያን ይዞታ የሆኑትን ጉልቶች የደሀው ገበሬ ይዞታ የማድረግ እቅድ የጉልተኞችን አከርካሪ የሚሰባብርና ፊውዳላዊ ሥርዓተ ማህበሩንም የሚያፈራርስ፣ የዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ሥርነቀል ለውጥና አብዮት ነበር።

የእንግሊዝን ሕዝብ በአንድ ዘውዳዊ መንግሥት አመራር እንዲማከል ያደረገውና ብሎም የእንግሊዝን ሕዝብ አብዮት የመራውና የጉልተኞቹን አከርከሪ በመምታት እንግሊዝ በዓለም የመጀመሪያዋ የካፒታሊስት ሥልተ ምርት አራማጅና የኢንዱስትሪ ሃገር ትሆን ዘንድ መንገድ የጠረገው ክሮምዌል ከወሰደው እርምጃ የቴዎድሮስ የሚያንስ አልነበረም።

ክሮምዌል በነቃ የእንግሊዝ ሕዝብ መካከል በመወለዱ በወገኖቹ ብቻ ሳይሆን በዓለም ሕዝብ ዘንድ ሲመሰገንና ሲወደስበት ኢትዮጵያዊው ቴዎድሮስ በኋላ ቀር ሕዝብ መካከል ያለ ጊዜያቸው ተወልደው ለሃገርና ለወገን ብለው የሰሩት ሥራ ሕይወትን ያህል ነገር ለሚያስከፍል መስዋዕትነት ዳረጋቸው።

የቴዎድሮስን ዓላማ፣ የቴዎድሮስን ማንነትና በኋላም በአጭሩ የተቀጩበትን ምክንያት የተጋደሉለት የእሳቸው ትውልድ ቀርቶ የዛሬውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ለማለት አያስደፍርም። ሰፊው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከምሁራኑም ወገን ለቴዎድሮስ ያላቸው ክበሬታና አድናቆት ለአንድነትና ለነፃነት ከተደረገው ተጋድሎ፣ ከመቅደላው መስዋዕትነትን የጀግንነት አርዓያነት የሚያልፍ አይደለም።

አፄ ቴዎድሮስ የታገሉለት የራሳቸው ትውልድ ለወራሪው የእንግሊዝ ሠራዊት ቀለብና ፍሪዳ እያቀረበ፣ መንገድ እየሰራና እስከ መቅደላ እጅቡ ከማምጣት ባሻገር የመቅደላን ምሽግ ዙሪያ ከብቦ ቴዎድሮስንና ሠራዊታቸውን መፈናፈኛ በማሳጣት ያንን መሪር ውሳኔ

እንዲወስኑ አስገድዷቸው በራሳቸው ላይ ሲፈርዱ አፅማቸውን ባይሆን ስማቸውን ከትቢያ አውጥቶ ተገቢውን ክብር ሊሰጣቸውና ሊያሞካሻቸው የሞከረው የእኛ አባቶችና የእኛ ትውልድ ነው።

መሃከላዊ ዘመን እያልን የምንጠራው ከ10ኛው ምዕት ዓመት ወዲህ እስከ ዘመነ መሣፍንት ፍፃሜ ድረስ ያለውን የ700 ዓመታት ታሪካችንን ስንመለከት በአክሱም መንግሥት የመጨረሻው ውድቀት የመጨረሻው ምክንያትና ሥልጣን ተረካቢ የሆነው የአርባ ዓመታት የዮዲት ዘመነ መንግሥት ቅጥ አምባሩ የጠፋ የውዥንብር፣ የሽብርና የጥፋት ጊዜ፤ መረጋጋት በፍፁም ያልታየበት፣ መረጋጋትም የማይቻልበት የሽግግር ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከዮዲት ውድቀት በኋላ መንበረ መንግሥቱን የወረሱት የዛጉዌ ሥርወ ነገሥታት በእመራር ላይ በቆዩበት 333 ዓመታት ውስጥ መላው የአውሮፓ መንግሥታት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመላው የአረብና የእስላም መንግሥታት ጋር በማዕከላዊው ምሥራቅ የመስቀል ጦርነት የሚካሄድበት ጊዜ ነበር። በወቅቱም ከአጎራባች አገሮችና ከውጭ የተሰነዘረ ጥቃት ካለመኖሩ ሌላ በውስጥም አንዳችም አፍራሽ እንቅስቃሴ ስላልነበረ ሰላም የሰፈነበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን ይህንን መልካም አጋጣሚ ለልማትና ለሃገር ግንባታ አልተጠቀምንበትም።

ከዛጉዌ መንግሥት ማብቂያ ከ1245 ዓ.ም እስከ 18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ማለትም አፄ ቴዎድሮስ እስከነገሱበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ባለማቋረጥ ለአራት መቶ ዓመታት ሙሉ በእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ነበረች። በአጭሩ ከአክሱም መንግሥት ውድቀት በኋላ በኢትዮጵያ በተከታታይ የታየው ሁኔታ በአመዛኙ ጦርነትንና ቀውስን በማስፈኑ አገሪቷ እጅግ አስከፊ ውድቀት ውስጥ ወደቀች። በኢትዮጵያ ገንዘብም ጠፍቶ አሞሌ ጨው መገበያያ ገንዘብ ሆነ።

## ዘመነ ኢምፔሪያሊዝም

በ12ኛው ምዕት ዓመት ገደማ በምዕራብ አውሮፓ ጥንታዊ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ማህፀን ውስጥ ተፀንሶ በአዝጋሚ ሂደት የተወለደው የከበርቴ (የቡርዧ) መደብ በ16ኛው ምዕት ዓመት ጎልብቶ ጉልተኞችን ታግሎ በመጣሉ የካፒታሊስት ስልተ ምርት ችግኝ ማቆጥቆጥ ጀመረ።

ከምዕራብ አውሮፓ አገሮች እንደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ኢጣሊያ፣ ስፔንና ፖርቱጋል ያሉት ከሌሎች ቀደም ብለው ከዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች እንደ ባሩድ፣ ጠመንጃ ወይም ነፍጥ፣ መድፎችና መርከቦችን ለማምረት በመብቃታቸው፣ በቆዳ ስፋታቸውና በተፈጥሮ ሀብታቸው ማራኪ የሆኑትን አሜሪካንና አውስትራሊያ የተሰኘ ስም የሰጧቸውን አዳዲስ አህጉራት በጦር ኃይል እየወረሩ በእህጉሮቹ ነዋሪ የነበሩትን ጥንታዊ ነባር ሕዝቦች አብዛኛውን በማጥፋት፣ በሕይወት የቀሩትን ጥቂቶቹን በባርነት ረግጠው ጉልበታቸውንና ሀብታቸውን መመዝበር ጀመሩ። በዘረፋ የተገኘውን ነፃ የሰው ጉልበት፣ ማዕድንና የግብርና ውጤት በአውሮፓ ካለው የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ካፒታል፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር ስላቀናጁት በማቆጥቆጥ ላይ የነበረው የካፒታሊስት ሥልተ ምርት በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ስር እየሰደደ በመሄዱ ምርትና የምርት ኃይሎች አደጉ።

ከጥንታዊ ጉልታዊው ሥርዓት ጋር ሲነፃፀር ካፒታሊዝም በአጭር ጊዜ ውስጥ እየፋፋ በመሄዱ አውሮፓውያን 18ኛውን ምዕት ዓመት የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን አሉት።

የካፒታሊዝም ዋና ባህሪ የሆነው በተለያዩ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አገሮች የኢንዱስትሪ ውጤቶች ገበያ የመድራቱን ያህል በካፒታሊስቶች መካከል ውድድሩም ተጧጧፈ።

ካፒታሊዝም በገበያ ኃይሎች እንጂ በእቅድ ስለማይመራ በገበያ ሽሚያና በትርፍ ላይ ብቻ ያተኮረው የምርት አመራረትና የምርት አቅርቦት ሂደት በባህሪው ሥርዓተ አልበኛ በመሆኑ ቀውስ እንደማይለየው የታወቀ ነው። እያንዳንዱ የካፒታሊስት ሃገር የሚመረተው የኢንዱስትሪ ምርት የሚያስፈልገውን ጥሬ እቃ በአይነትና መጠን ያለማግኘት፣ በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው አውሮፓ አጥጋቢ ገበያ ያለመኖርና ምንም እንኳን በኢንዱስትሪ ቀድሞ ገንብታ ብትገኝም አውሮፓ የሚያስተማምን የተፈጥሮ ሀብት የሌላትና ጠባብ ሆና በምርት ግን መጋሸብ፣ በሥራ አጥ ቡዜኦች መከማቸትና በወንጀለኞች ብዛት ክፉኛ ተጨናንቃ ነበር።

በኢንዱስትሪ አብዮት ያልተጠበቀ ፈጣን እድገት ብዙ ሳይራመድ የገጠመውን ቀውስ ለማስወገድ የተመረጠው ዘዴና የተወሰደው እርምጃ በቀውሱ የተጎዱትንና የቆሰሉትን የኢኮኖሚ ህሙማን ከገበያ ውድድር በማውጣት መግደልና ጨፍልቆ መዋጥ ነበር።

በካፒታሊስቶች ዓለም አንዱ ሲታመም ሌላው እስታሞና አሳክሞ አያድነውም። ያንዱ መሞት የሌላው ሕይወትና ብሎም እድገት ነው። ብርቱዎቹ ደካሞችን፣ ጤናማዎቹ ህሙማኑን እንደ ዓሳዎች እየበሉ የሚኖሩና በዚህም የሚደልቡ ጉዶች ናቸው።

እንደነሱ አባባል ይህንን የመሰለው የኢኮኖሚ አስተዳደር፣ አመራርና የእድገት ግፊት ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ይባላል። ይህንን የሩሲያው አብዮታዊ ምሁርና የጥቅምቱ ታላቁ አብዮት መሪ ቭላድሚር ኤሊች ሌኒን የካፒታሊዝም ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ይለዋል።

ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወይም ኢምፔሪያሊዝም አምስት ኢኮኖሚያዊ ገፅታዎች አሉት። እነሂህም:-

1ኛ/ የምርትና የካፒታል ክምችት፣

2ኛ/ በባንክና በኢንዱስትሪ ካፒታል ጥምረት የፋይናንስ ካፒታልን መፍጠር፣

3ኛ/ ካፒታልን በማንቀሳቀስ ወደ ውጭ ማውጣት (ኢንቨስትመንት)፣

4ኛ/ የሞኖፖሊስቶች ማህበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ማደራጀትና

5ኛ/ ርካሽ የሰው ጉልበት፣ ሰፊና የማይነጥፍ ገበያና አጥጋቢ ትርፍ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ እያንዳንዱ ሞኖፖሊስትና ድርጅቱ የአገሩን ክልል ወይም ብሔራዊ ድንበር ጥሶ በመውጣት በዓለም አቀፍ የሞኖፖሊስቶች ማህበር አማካኝነት ዓለምን በወታደራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ስር ማኖር ናቸው።

ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ጊዜና በእነዚህ መሰረታዊ ንድፈ ሃሳቦች እየተመራ ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብትና ነፃ ወይም ርካሽ የሰው ጉልበት ዘረፋ ዘመቻውን ትኩረት በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በማዕከላዊና በደቡባዊ አሜሪካ አህጉራት ላይ በማድረግና ዓለምን በቅኝ ግዛት ክልሎች ከፋፍሎ በወታደራዊ ኃይል፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተፅዕኖ ስር ለማድረግ ቻለ።

# የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና የአካባቢው ባዕዳን ተስፋፊዎች በኢትዮጵያ ላይ ያደረጓቸው ከበባዎችና ብሎም ወረራዎች

በጥንታዊት ኢትዮጵያ ላይ በታሪክ የመጀመሪያ የውጭ ጥቃት የተሰነዘረው ከ7ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ በተከታታይ ለሦስት መቶ ዓመታት በተካሄደው ዓለም ዓቀፍ የእስልምና ኃይሎች ወረራና ዘረፋ ሲሆን፣ አረቦች የዳህላክን ደሴት ተቆጣጥረው መንደርደሪያቸው በማድረግ የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ወደብና የወደቡን ከተማ ካፈራረሱ በኋላ ሉዓላዊነታችንን ለመዳፈር ባይሞክሩም ከበባቸውን ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ አጠናከሩ።

## የቱርኮች ከበባና ወረራ

ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብና ምሥራቃዊ ድንበራችንን በመያዝ በ16ኛው ምዕት ዓመታት አረቦችን ተክተው የከበቡን ቱርኮች ናቸው። ከአረቦች በኋላ በእስልምና አርማ የተነሳው የቱርክ መንግሥት ከ15ኛ ምዕት ዓመት ጀምሮ መካከለኛውን ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካን እንደያዘ አከታትሎ በ15ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ ከምፅዋ ወደብ በመጀመር የአባይ ሸለቆን መገናኛ በሮችና የዘይላን ወደብ ተቆጣጠረ። ከዚያም የአፍሪካን ቀንድ ከከበበና በተለይም በሰሜኑ ደጋማ የአካለጉዛይ፣ የሀማሴን፣ የሰራኤንና የከረን አውራጃዎች ላይ ለረጅም ጊዜ ተደጋጋሚ ጥቃትና ወረራ አካሄደ። በዘመኑ የኢትዮጵያ ጀግኖች ጽናት፣ መከላከልና መልሶ ማጥቃት በአፍሪካ ቀንድ ለመስፋፋት የነበረውን እቅድ ለማክሸፍ ተቻለ።

## የግብፅ መንግሥት ያደረገው ከበባና የሰነዘረው ወረራ

የግብጽ መንግሥት ራሱ የቱርክ ቅኝ ሆኖ፣ የአባይን ጅረት ከምንጩ ለመቆጣጠርና ሰፊ ቅኝ ግዛት ለማግኘት ታጥቆ ለተነሳው ተስፋፊ የግብጽ መሪ ለእስማኤል ፓሻ ቱርኮች በ1866 ዓ.ም የምፅዋን ወደብ አስረከቡት።

እስማኤል ፓሻ የአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን መላውን የምሥራቅ አፍሪካ ክልል ከነጭ አባይ ማዶ እስከ ታላቁ የአፍሪካ ሐይቅ (ዛንዚባር) ድረስ ያሉትን አገሮች ከሱዳን ጋር ቀላቅሎና ጠቅልሎ የመግዛት ግዙፍ ዓላማ ነበረው። ይህ ዓላማ የእስማኤል ፓሻ ብቻ ሳይሆን የአባይ ጅረት የሕይወታቸው እስትንፋስ የሆነው፣ ዛሬም ያሉት ሆነ ወደፊትም የሚወለዱት የግብፃውያንና የመሪዎቻቸው ዓላማ ነው።

ይህን አዳጋችና ግዙፍ የሆነ ምኞታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ አቅም ቢያንሳቸውም የኢትዮጵያ ተከታታይ ትውልዶችና መሪዎቻቸው የአባይ ገባር ወንዞችን ለሃገር ልማት አውለው ኢኮኖሚያቸውን ለማዳበርና አንድነታቸውን እንዲሁም የመከላከያ ኃይላቸውን ለማጠናከር እንዳይችሉ በተቻላቸው መንገድ መቦርቦርና ማዳከም ሌላው ተለዋጭ አላማቸው ነው።

በአሁኑ ጊዜ በእነሱ አደራጅነት፣ ያላቋረጠ ድጋፍና የእጅ አዙር ጦርነት ሻዕቢያና ወያኔ ምኞታቸውን በከፊል ተግባራዊ አድርገውላቸዋል። አረቦች ዛሬ የባሕር በር አልባ ኢትዮጵያን ዳግም ለመክበብና ለመቆጣጠር ችለዋል። በእስማኤል ፓሻ ይመራ የነበረው የግብጽ መንግሥት ኢትዮጵያ በግራኝ አህመድ ወረራና በዘመነ መሣፍንት የእርስ በእርስ ጦርነት መዳከሟንና መላዋን ኢትዮጵያ በሚገባ የሚያማክል ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትም

ገና ለማቋቋም እንዳልቻለች በመገንዘብና ይህም መልካም አጋጣሚ ሳያመልጠው ሊጠቀምበት ወሰኗል።

ግብጽ ለቅኝነት የምትመኛቸውን አገሮች የራሳቸው ቅኝ ለማድረግ ዓላማ ያላቸው እንግሊዝና ሌሎች የቅኝ ገዢ ኃይሎች የጥቁር ሕዝብ የነፃነት እርዓያና ምልክት የሆነችባቸውን ኢትዮጵያን ይበልጥ በማዳከምና አፍሪካን በማንኮር ለወረራ ያመቻቸው ዘንድ ወዳጅ መስለው ግብጽ በመስፋፋት ዓላማዋ እንድትገፋበት ከማበረታታት በላይ ወረራውን በማዘጋጀትና ወታደራዊ እቅድ በማውጣት ጭምር ተባብረዋል። አፄ ቴዎድሮስ ያሰሯቸውን እንግሊዛዊያንና ሌሎች አውሮፓውያን እስረኞችን ለማስፈታት ይደረግ በነበረው ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያም የአውሮፓውያንም ወዳጅ በመሆን መኖሪያውን ምፅዋ ወደብ ላይ አድርጎ ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያን ሲያጠናና ሲሰልል የኖረው በኋላም የእንግሊዝ ሠራዊት ቴዎድሮስን ለመውጋት ከሕንድ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ተቀብሎ ስንቅ አቅራቢ፣ መንገድ መሪና የፖለቲካ አማካሪ በመሆን እስከ መቅደላ የመጣ፣ በትውልዱ ስዊዝ የሆነ የእንግሊዞች ሰው ሙንሲንጀር በግብጽ መንግሥት ለተያዘው የምፅዋ ወደብ፣ የወደቡ ከተማና ለአካባቢው ገዥ ሆኖ ተሾመ።

ይህ ግለሰብ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ለረጅም ጊዜ ሲያጠናና ሲሰልል እንደመኖሩ መጠን ደህና አድርጎ የሚያቀን ብቻ ሳይሆን በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩትን አፄ ዮሐንስ ራሳቸውን የረጅም ጊዜ ወዳጅ መስሎ ሲሰልላቸው የኖረና ግብፆች በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ያቀዱትን ወረራ አስፈፃሚ ዋና መሣሪያ ሆነ።

የግብጽ መንግሥት በውጭ ሃገር ባዕዳን ወታደራዊ ባለሞያዎች እየተረዳ ያሰለጠናቸውና ዘመናዊ ትጥቅ ያስታጠቃቸው ሠላሳ ሺህ ወታደሮች ግብፃዊ ባልሆኑ ባዕዳን መኮንኖች እየተመሩ ከካይሮ ተነስተው ምፅዋ ገቡ። ጦሩ ምፅዋ እንደገባ የሚያስፈልገውን አቀባበልና መስተንግዶ ያደረገው ከፍ ብዬ የጠቀስኩት ሙንሲንጀር የተባለ ግለሰብ ከምፅዋ ክልል አስተዳዳሪነት ወደ ጦር አዛዥነት ተዛውሮ ከምፅዋ በመነሳት የግብጽን ወራሪ ጦር እየመራ የበገስን (የዛሬውን ከረን) አውራጃ፣ ሀባብንና መንሳን በ1864 ዓ.ም ወረረ።

በዚህ ጊዜ ውስጥ በጎንደር ክፍለ ሃገር አስተዳደር ስር ያሉትን የጠረፍ ወረዳዎች መተማን፣ አብዱራፊን፣ ቋራንና ደንቢያን ሌላው የግብጹ ጦር ከሱዳን እየተወረወረ ወረረ። ቀጥሎም በአሥመራ ከተማና በምፅዋ ወደብ መካከል በመንገድ ላይ የሚገኘውን ትንሽ ከተማ ጊንዳን በ1865 ያዘ። የሰሜንና የሰሜን ምዕራቡን የጠረፍ ወረዳና አውራጃ አስተዳደሮች ግብፃውያን በኃይል ወርረው በመያዝ ሕዝቡን በመበደል እንዳሻቸው ሲያደርጉና ሲያስገብሩ አፄ ዮሐንስ ሥልጣን የያዙበት አፍላ ጊዜ ከመሆኑ ሌላ ሥልጣናቸውን ያልተቀበሉና ያመጹ አንጃ መሣፍንቶችን የማንበርከኩና የማሳመኑ ትግል ብቻውን አድካሚ ስለነበር የግብጹን ሠራዊት እንቅስቃሴ ለመግታት የተወሰደ ፈጣን እርምጃ አልነበረም። የኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት ምንም አይነት እርምጃ ሳይወስድ ፀጥ ማለቱ በግብጾች በኩል የተንኮል ወይም የድክመት መሆኑን ለመረዳት ስላስቸገራቸው ያደርጉት በነበረው ጥናትና ጥንቃቄ ለማዝገም መገደዳቸው ለአፄ ዮሐንስ ጊዜ የሰጣቸው ይመስላል።

በተገኘው ጠቃሚ ጊዜ የጦርነት መሰናዶ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ችግሩን ያለጦርነት በሰላም ለመፍታትም ታላቅ ጥረት አድርገዋል። አፄ ዮሐንስ ችግሩን በሰላም ለመፍታት እንዲቻል ከተለያዩ የጊዜው ኃያላንና ተደማጭ የአውሮፓ መንግሥታት ጋር እየተፃፃፉ በሽምግልና እንዲረዷቸው በሚጠይቁበት በ1867 ዓ.ም ግብጾች በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክልል የሚገኘውን ዘይላ የሚባለውን ሌላውን ወደብ ከያዙ በኋላ በዚያ ተረማምደው

የሐረርጌን ክፍለ ሃገር በከፊል ተቆጣጠሩ። ከዚህ በኋላ ዋናውንና ጠቅላላውን ወረራ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ መሃል ለመጥለቅ ከዚህ የሚከተለውን ወታደራዊ እቅድ ነደፉ። እቅዱም፡-

1ኛ/ ከምፅዋ መንቀሳቀስ የጀመረው ዋናው አጥቂ ጦር ካለበት ስፍራ ተወርውሮ መላውን የሰሜን ደጋማ አውራጃዎች ከተቆጣጠረ በኋላ በዚህ ጊዜ የአገሪቱ መንበረ መንግሥት ወዳለበት ወደ ትግራይ ክፍለ ሃገር ማምራት፤

2ኛ/ የአገሪቱን ምሥራቃዊ ክልል የተቆጣጠረው ወራሪ ጦር ከዘይላ ወደብ በመነሳት በሐረርጌ በኩል ወደ መሃል ከማምራት ይልቅ በወሎ በኩል ወደ ትግራይ ለመግባት አጭርና አቋራጭ መንገድ መምረጥ። ከዚያም ከታጁራ ወደብ በመነሳት የአውሳን አውራጃ መቆጣጠርና ትግራይን ወደሚያዋስነው ወሎ ክፍለ ሃገር እንዲያመራ ሆኖ ትግራይን ከመሃል ሃገር መቁረጥ። እናም ከደቡብና ከሰሜን ከሁለት አቅጣጫ በመንቀሳቀስ አፄ ዮሐንስን መቀሌ ላይ እንደተጠነት ለመንከስ የታቀደ ማጥቃት ነበር።

በዚህ እቅድ መሠረት ለሚከናወነው አውደ ውጊያ የሰሜኑን ወራሪ ጦር የሚመራው የዴንማርክ ተወላጅ የሆነው መኮንን ኮሎኔል ኤረንድሮፐ የሚባል ሲሆን፤ የምሥራቁን ወራሪ ጦር የሚመራው ታዋቂው ሙንሲንጀር ፓሻ ነበር። ፓሻ የግብጽ መንግሥት የሰጠው ከፍ ያለ የማዕረግ ስም ነው። የሰሜኑ አጥቂ ጦር ከምፅዋና ከአካባቢው ተነስቶ ጥቅምት 14 ቀን 1868 ዓ.ም በቅደም ተከተል ዶጋሊን፣ ሳህጤንና ጊንዳን በማለፍ የአካለጉዛይን አውራጃ ወረረ። አፄ ዮሐንስ ህዳር 2 ቀን 1868 ዓ.ም ከአድዋ ቁጥሩ ከሃምሳ እስከ ሰባ ሺህ የሚገመት ሠራዊት ይዘው ወደ አካለጉዛይ አውራጃ በመንቀሳቀሳቸው የግብጽና የኢትዮጵያ ሠራዊቶች ጉንደት ላይ ተገናኝተው ተፋጠጡ።

በኢትዮጵያውያን የማጥቃት ቀደምትነት ውጊያው ተጀምሮ በመጀመሪያው ቀን ከስድስት ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በግብጽ ሠራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰበት በሽሽት አፈግፍጎ ጉንዳ ጉንዲ ላይ ሌላ የመከላከያ ስፍራ በመያዝ የመጨረሻውን የመከላከል ጥረት አድርጎ አብዛኛው ጦር በመደምሰሱ የጠላት ሠራዊት ተሸንፎ ውጊያው ሲያበቃ የጦሩ አዛዥ ኮሎኔል ኤረንድሮፐ ውጊያው ላይ ተሰውቶ ብዙዎቹ ወታደሮች ሲማረኩ በጣም ጥቂቱ ሸሽተው በማምለጥ ምፅዋ ሊገቡ ቻሉ።

በምሥራቅ በኩል የሚያጠቃውና የማጥቂያ መስመሩ ታጁራን ያደረገው ወራሪው የግብጽ ጦር በጥቅምት ወር በዝያው ዓመት የአውሳን አውራጃ ለመቆጣጠር ከታጁራ ምሳ ኪሎ ሜትር ተጉዞ ጊዜው በመምሸቱና ሠራዊቱም በመድከሙ ለማደር የሽለብታ ስፍራ በመያዝ እረፍት ባደረገበት ሌሊት በአውሳ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ የአፋር ብሔረሰብ ታጣቂዎች ባደረሱት ባልተጠበቀ ድንገተኛ ጥቃት አብዛኛው የግብጽ ሠራዊት ሲደመሰስ 73 የግብጽና የሱዳን ተወላጅ የሆኑ ወታደሮች ከአራት ባዕዳን መኮንኖች ጋር በሽሽት ታጁራ ገብተው መትረፍ ቻሉ። በሰሜንና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ጠቅላላ ወረራ የሰነዘረው የግብጽ ሠራዊት ላይ የተሟላ ድል ቢገኝም ከኢትዮጵያ ሠራዊት ወገን ዘመናዊ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ የታጠቀው ከአስር አንድ ብቻ ሲሆን አብዛኛው የተሰለፈው ጥንታዊውን የባህል መሣሪያዎች እንደ ጎራዴ፣ ጦር፣ ቀስትና ዱላ በመታጠቅ ስለነበር ድሉ የብዙ ኢትዮጵያውያንን መሪር መስዋዕትነት ያስከፈለ ነበር።

ከዚህ መስዋዕትነት ሌላ አያሌ ችግሮች ስለነበሩ አፄ ዮሐንስ የተገኘውን ድል ለማስፋፋት ግብጾችን ከምፅዋ ለማውጣት ቀርቶ ከቦጎስ፣ ከሀልሀልና ከመንሳ እንኳን ለማስለቀቅ ሳይሞክሩ ወደ ሰላሙ ድርድር አመሩ። በግብጾች በኩል በደረሰባቸው ሽንፈት፣

በሠራዊቱ እልቂትና በጦር ሹማምንቶቻቸው ሞት እጅግ ከመደናገጣቸውና ይበልጥም በማፈራቸው የውጊያውን ውጤት የግብጽ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው ዓለም እንዳይሰማ ሰውረውና ባጣዳፊ አዲስ የጦር ኃይል አደራጅተው በዳግም ውጊያ ኢትዮጵያን ተበቅለው የእነሱን ድል ለማብሰር ወሰኑ።

ኢትዮጵያ ላይ ሌላ ሁለተኛ ጥቃት በመሰንዘር ያለፈውን ሽንፈት ሽሮና ተበቅሎ የግብጽን ሠራዊት የተዋጊነት ዝና ለማደስ ከፍ ያለ የጦር ኃይል ዝግጅት ወዲያው ጀመሩ። ለዳግም ውጊያና ለብቀላ ለሚዘምተው አዲስ ጦር አዛዥ የግብጹ የጦር ኃይል ጠቅላይ አዛዥ መሐመድ እራቲብ ተሾመ። በዚህ አይነት ካይሮ ላይ የተደራጀውና የተዘጋጀው ሁለተኛው ወራሪ የግብጽ ሠራዊት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 5 ቀን 1875 ዓ.ም ምፅዋ እንደገባ ሳይውል ሳያድር ወደ ደጋው ምድር ወጥቶ ጉራእ ላይ ሰፈረ። ጉራእ ከአሥመራ ከተማ የሚርቀው ወደ 40 ኪሎ ሜትር ያህል ነው።

አፄ ዮሐንስ እንደተለመደው የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ለሁለተኛ ጊዜ በእብሪት ለወረራ የመጣውን የእስማኤል ፓሻ ሠራዊት ዳግም አሳፍረው ይመልሱ ዘንድ አስፈላጊውን ቅስቀሳ በማድረግ ቁጥሩ ከ50,000 የማይበልጥ ሠራዊት በአዋጅ አስከትለው ከአድዋ በመነሳት ወደ ጉራእ ዘመቱ። አዲሱ የግብጽ ሠራዊት በቁጥሩ ከ20,000 ባይበልጥም እጅግ ዘመናዊ የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያ የታጠቀና በ40 መድፎች የተደገፈ ነበር። ይህም ሆኖ ከካይሮ ለበቀል የመጣውን የግብጽ ጠቅላይ የጦር ኃይል አዛዥ ከጉራእ ሳይንቀሳቀስ በመከላከል የውጊያ ስልት መሽጎ ስለተቀመጠ በሁለቱ ሠራዊቶች መካከል ለብዙ ቀናት መፋጠጥ ብቻ ሆነ።

በውሃና ስንቅ አቅርቦት ረገድ ግብጾች ከፍ ያለ ችግር የነበራቸው ከመሆኑ በላይ ከምፅዋ ጋር የሚያገናኛቸው መንገድ በኢትዮጵያ ሠራዊት ቃፊሮች የሚጠበቅና ዙሪያውንም የተከበቡ ስለሆነ ከምሽግ እየወጡ የኢትዮጵያን ሠራዊት ለውጊያ መጋበዝ ጀመሩ። በኢትዮጵያ ሠራዊት የማጥቃት ቀደምትነት መጋቢት 7 ቀን 1868 ዓ.ም ውጊያ ተጀምሮ ከምሽግ ወጥቶ ለግማሽ ቀን በተዋጋው የግብጽ ሠራዊት ላይ እሁንም በደረሰበት ከባድ ጉዳት በሽሽት እያፈገፈገ ተመልሶ ወደ ምሽጉ በመግባት ይከተለው በነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ በመትረየስና በመድፍ ተኩስ ከባድ ጉዳት ስላደረሰ ምሽጉን ሰብሮ ለመግባት አዳጋች በመሆኑ ውጊያው ቆመና እንደገና መፋጠጥ ሆነ።

ከምሽጋቸው ወጥተው ዳግም ለመዋጋትና ከበባውን ሰብሮ ለመውጣት በእነሱም በኩል ፍፁም የማይቻላቸው ስለሆነና ውጊያውን አቁመው የሰላም ድርድር በመጠየቃቸው የጉራእ ውጊያ በዚሁ ተፈፀመ። ከካይሮ እስከ ዛንዚባር ድረስ የታቀደው የግብጾች ቁሳራዊ ግዛት የማስፋፋት ዓላማ ከመክሸፉም በላይ አፄ ዮሐንስን ለመበቀልና ለሠራዊታቸው የማይረሳ ትምህርት እሰጣለሁ ብሎ በመፎከር የመጣውን የግብጽ ሠራዊት ለሁለተኛ ጊዜ ራሱ የማይረሳ ትምህርት ስላገኘ ሦስተኛ ወረራ አላማረውም። ቱርክን ተክቶ የምፅዋን ወደብና አካባቢውን ለመቆናጠጥ በምሥራቅ አፍሪካ ለመስፋፋት ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ያላቸውን በኢትዮጵያ ላይ ሁለት ያልተሳኩ ወታደራዊ ወረራዎችን ሰንዝሮ ከሸፈበት።

ይህ ተደጋጋሚ ወታደራዊ ሽንፈት እስማኤል ፓሻ በአገሩ የነበረውን የሕዝብ ድጋፍና የፖለቲካ ጥንካሬ በእጅጉ ሸረሸረበት። ካለበቂ ጥናት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ካፒታል ከአቅም በላይ የወጠናቸው የኢኮኖሚ ልማቶች ያለመሳካትና ለመስፋፋት ዓላማው በተለያዩ ግንባሮች ያለአቅሙ ያሰማራው ሰፊ ሠራዊት ፍጆታና ወጪ ታላቅ ውድቀት አደረሱበት። አባይን ከምንጩ በመቆጣጠር ብቻ ሳይወሰን ምሥራቅ አፍሪካን ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ

የተመኘው ዋናው የኢትዮጵያ ጠላት ራሱ በእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም ቁጥጥር ስር ውሎ ቅኝ ተገዥ ሆነ።

ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ብሎ በወረራ የያዘውን ሱዳንን ነፃ የማውጣት ዓላማ አንግቦ የተነሳው የመህዲስቶች ንቅናቄ የጀመረውን ለነፃነት የሚደረገውን አመፃዊ ተጋድሎ የእስማኤል ፓሻ መንግሥት ሊገታውና ሊቆጣጠረው እንደማይችል የተገነዘበው የእንግሊዝ መንግሥት በግብጽ መንግሥት ላይ ተደርቦ በግብጽ ወታደሮች ደም እየተጠቀመ ሁለቱንም በማዳከም ሱዳንን ከግብጽ ጋራ አጠቃሎ የቅኝ ግዛቱ ለማድረግ በሚጥርበት ጊዜ፤ የግብጽ መንግሥት ቀድሞ የጦር ሠራዊቱንና የሲቪል አስተዳደሩን በሙሉ በሰላም ከሱዳን አውጥቶ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወደ ግብጽ ለማሳለፍና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር እርቅ ለማድረግ መፈለጉንና በዚህ ረገድ አፄ ዮሐንስ ከዚህ በፊት ያቀረቡትን የእርቅ ቅድመ ሁኔታዎች ለመቀበል መዘጋጀቱን አሳወቀ።

አፄ ዮሐንስ ምንም እንኳ ሁለት ጊዜ የግብጽን ጦር በጉንዳጉንዲና በጉራእ የጦር ሜዳዎች ድል አድርገው ቢመለሱም የግብጽን አገዛዝ ከምፅዋ፣ ከአካባቢውና ከቦገስ ማስወጣት ስለተሳናቸው የእርቁን ሐሳብ ለመቀበል የተገደዱ ይመስላል። የእንግሊዝ መንግሥትም በአፍሪካ የቅኝ ግዛቱን የማስፋፋት ዕቅዱ ግብጽን የሚረዳ በመምሰል ከሱዳን ከማስወጣት በላይም የራቀ ዓላማ ስለነበረው፤ የግብጽና የኢትዮጵያን መንግሥት የፈለጉትን እርቅ ሊጠቀምበት ስላሰበ፤ የታወቀውን ጀብደኛ እንግሊዛዊ መኮንን ጄነራል ጆርጅ ቻርለስ ጎርደንን በሸንጋይነት እንዲያገለግል መርጦ ለግብጽ መንግሥት ጠቆመ። የግብጹ መሪ እስማኤል ፓሻ ይህንን መኮንን የሱዳን አስተዳዳሪ፣ በሱዳን የእንግሊዝና የግብጽ ጦር ጠቅላይ አዛዥና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋርም ለሚደረገው የእርቅ ድርድር ግብጽን እንዲወክል ሥልጣንና ውክልና ሰጠው። በዚህ ሥልጣንና ውክልና መሠረት ጎርደን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በ1871 ዓ.ም ከአፄ ዮሐንስ ጋር ተገናኝቶ ነበር። ሆኖም የኢትዮጵያን አቋምና ጥያቄ ሳይረዳ የአገሩን የእንግሊዝንና የቀጠረውን የግብጽን መንግሥት ጥቅምና ፍላጎት ብቻ ለማራመድ በመሞከሩ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ሊግባባና ተልዕኮውን በአግባቡ ሊያከናውን ሳይችል ቀረ። ወደ ግዛቱ ወደ ሱዳን ተመልሶ በዘዴ ግብጽን ከሱዳን አስወጥቶ የእንግሊዝ ቅኝ የሆነ ሱዳንን ለመፍጠርና የዚህ ፍላጎቱ እንቅፋት የሆነበትን የሱዳኑን አመፅ መሪ ኤልመህዲን የሚቃወሙ አንጃዎች ፈጥሮ በመከፋፈልና በማዋጋት አመፁን አከሽፋለሁ ብሎ ሲያወናብድ የኤልመህዲ ሠራዊት መኖርያ ቤቱ ድረስ ሄዶ በሰይፍ አንገቱን በመቅላት ገደለው። እርሱም የሚያዛቸው የግብጽና የእንግሊዝ ሠራዊት፣ ሰላማዊ ሠራተኞች አብዛኞቹ ከመህዲስቶች ጋር በተደረገው ፍልሚያ ተሰውተውና ተማርከው አብዛኛው የሱዳን የአስተዳደር ክልሎች በመህዲስቶች ቁጥጥር ስር ዋለ። ከዚያም አስተዳዳሪዎቹና የጦር ሹማምንቶቹ እጃቸውን ሲሰጡ የተቀሩት ጥቂቱ ተከበው ራሳቸውን ይከላከሉ የነበሩ የግብጽ የጦር ክፍሎች በኢትዮጵያና በሱዳን ወሰን ላይ በገለባት፣ በከሰላና በአካባቢው ብቻ የነበሩት ናቸው።

መህዲስቶቹ የሚያካሄዱት አመፅ እንግሊዞች እንደገመቱትና እንደፈለጉትም ግብጾችን ከሱዳን የሚያስወጣና የእነሱን ቅኝ ገዥነት የሚያመቻች ሳይሆን ከጄነራል ጎርዶን ጋር እያሉ እንግሊዛውያንና ሌሎችም አውሮፓውያን በመታረዳቸውና ብዙዎች ሕይወታቸውን ለማዳን ሲሉ በመስለማቸው ታላቅ ድንጋጤ ተፈጠረ። በዚህ ጊዜና አካባቢ ለእንግሊዞችም ሆነ ለግብጾች ረዳት ለመሆን የምትችል ሃገር ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች የግብጽ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር እርቅ ሊፈጥር የሚችልበትን ለማሳካት በሕንድ የእንግሊዝ መንግሥት የባሕር ኃይል ምክትል አዛዥ ሬር አድሚራል ዊልያም ሂዊት ሸንጋይ እንዲሆን ስለተመረጠ

ግንቦት 26 ቀን 1876 ዓ.ም ወደ አፄ ዮሐንስ መጥቶ ተገናኛቸው። አፄ ዮሐንስ ከሬር አድሚራል ሂዌት ጋር ተገናኝተው ከግብጾች ጋር ለመታረቅ የተግባቡባቸው ውሎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፡-

1ኛ/ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በምፅዋ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡም የሚወጡም እቃዎች ሁሉ የጦር መሣሪያዎች ጭምር በእንግሊዝ ውክልና በነፃ እንዲያልፉ፣

2ኛ/ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1877 ዓ.ም መስከረም ወር ጀምሮ ቦገስ የሚባለው አውራጃ ለአፄ ዮሐንስ መንግሥት ተመልሶ እንዲሰጥ፣

3ኛ/ አፄ ዮሐንስ በከሰላና በገለባት መሀዲስቶች የከበቡትን የግብጽ ሠራዊት ከከበባው አውጥተው በምፅዋ በኩል ወደ አገራቸው ወደ ግብጽ ይመለሱ ዘንድ እንደሚረዱ፣

4ኛ/ የግብጽ መሪ የተከበሩ እስማኤል ፓሻ አፄ ዮሐንስ የሚፈልጓቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚልኩ፣

5ኛ/ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሊሆን ስለሚገባው የወንጀለኞች ልውውጥ ነበር።

በእንግሊዙ አድሚራል ገላጋይነት ከግብጾች ጋር የተደረሰበት እርቅና የመግባባት ውል ከቦገስ በስተቀር ምፅዋንና የተቀሩትንም የኢትዮጵያ የመሬት ጥያቄ ባያካትትም አፄ ዮሐንስ በውሉ የተደሰቱ ይመስላል። ይህም ስሜታቸው ለእንግሊዝ ንግሥት ውሉን አስመልክተው በጻፉት የምስጋናና የአደራ ደብዳቤያቸው ላይ ተንጸባርቋል። በውሉ መሠረት በራስ አሉላ የሚመራ አስር ሺህ የኢትዮጵያ ጦር ተልኮ በከሰላና በአካባቢው በመሀዲስት ጦር የተከበበውን የግብጽ ጦር ከፍ ያለ መስዋዕትነትን በጠየቀ ውጊያ ከበባውን በመስበር ከመደምሰስ አድነው፣ በእንክብካቤ አጓጉዘው በምፅዋ ወደብ አስወጥተው ለአገራቸው በማብቃት አፄ ዮሐንስ ግዴታቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ተወጡ።

## የአውሮፓ መንግሥታት ግብፆችን ተክተው በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ከበባና ወረራ

በዘመነ ኢምፔርያሊዝም ተከታታይነት ያላቸው ጥቃቶች የተሰነዘሩብንና ለአራተኛም ጊዜ የተከበብነው እንግሊዞች ፈረንሳይን፣ ኢጣሊያኖች ቱርኮችንና ግብፆችን ተክተው መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ሰሜን አፍሪካን፣ ቀይ ባሕርንና የአፍሪካ ቀንድ የአባይ ሸለቆን በተቆጣጠሩበት ጊዜ ነው። በ19ኛ ምዕት ዓመታት መገባደጃ የካቲት 26 ቀን 1877 ዓ.ም በተወሰኑ የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት አገሮች መካከል በጀርመን ርዕሰ ከተማ በርሊን ላይ ስብሰባ ተደርጎ እርስ በእርሳቸው ሳይቀናኑና ሳይጋጩ ተባብረው ጨለማው ዓለም እያሉ የሚጠሩትን የአፍሪካን አህጉር ለመቀራመት በተስማሙበት ውል መሠረት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ስፔን፣ ፖርቱጋልና ቤልጂም በተለያየ ጊዜና በተናጠል አፍሪካን ወረሩ።

በዚህ ዘመን በተለይም ከስዊዝ ቦይ መከፈት በኋላ ኢትዮጵያን ለመውረር በመንደርደሪያነት የሚያገለግሏቸውን በኢትዮጵያ ሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅና ምሥራቅ ክልሎች የሚገኙትን ስምንት ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያላቸውን የባሕር በሮች ተከፋፍለው በመክበብ አፈኗት። ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪካ፣ የአፍሪካን ቀንድ፣ ቀይ ባሕርን፣ የሕንድ ውቅያኖስንና የዓባይ ሸለቆን የተቆጣጠረውን የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም ተቀናቃኝ የሆነው የፈረንሳይ መንግሥት ጣልቃ እንዳይገባበት አፄ ዮሐንስን ወዳጅ መስሎ ከግብጽ ጋር

አስታርቃለሁ በማለት ደልሎ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር መወዳጀትን ስለፈለገ ግብጽን በማስወጣት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1877 ዓ.ም የምፅዋን ወደብ አስረከበው።

## የኢጣሊያ መንግሥት ወረራ

የኢጣሊያ መንግሥት ለብዙ ጊዜ የተመኘውን የምፅዋ ወደብ ያለ ድካምና ደም በእንግሊዝ እና በግብጽ መንግሥታት ትብብር ከተቆናጠጠ በኋላ ለቀጣዩ ወረራ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ከማመቻቸቱ ጋር ተጨማሪ ጦር በየጊዜው ከኢጣሊያ እያመጣ አካበተ። በሰላይነትና በመንገድ መሪነት ብቻ ሳይሆን በተወለዱበት ሃገር፣ በሚያውቁት ያአየር ንብረትና ምድር ምናልባትም ከኢጣሊያኖቹ የተሻለ በውጊያ ሊያገለግሉትና የጦር ኃይሉን ሊያጠናክሩለት በሚያስችል መጠን የሃገር ተወላጅ ባንዳዎችን እየመለመለ በገፍ አሰለጠነ።

ወረራውን በመጀመር ከሃገር ተወላጅ ባንዳዎች ጋር የተቀየጠና በአንድ መድፍ ሻለቃ የተደገፈ እግረኛ ሻለቃ ጦር ከምፅዋ በማንቃንቅ 30 ኪ.ሜ ያህል አንጉዞ ዶጋሊን በማለፍና ሰሀጤን በመያዝ መሽጎ ተቀመጠ። በጥር ወር በ1879 ዓ.ም ቁጥሩ አምስት ሺህ የሚሆን የራስ አሉላ ጦር ሰሀጤን ላይ የመሸገውን የኢጣሊያን ጦር ከኋላ የእደላ መስመሩን ዶጋሊ ላይ ቆርጦ ስለከበበው፤ ከበባውን ሰብሮ የሚያወጣው ረዳት የኢጣሊያ ጦር ከምፅዋ እንዲላክለት ጠየቀ።

ምሽግ ውስጥ እንዳለ የተከበበውን ጦር ከበባውን ሰብሮ እንዲያወጣ በጥር ወር ከምፅዋ የተላከውን ኮሎኔል ክርስቶፎር የተባለ መኮንን የሚመራውና በአስር መድፎች የተደገፈ አንድ ሌላ እግረኛ ሻለቃ ጦር ከምፅዋ ተነስቶ ዶጋሊ ሲደርስ አድፍጦ ይጠባበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር የተኩስ ዝናብ በማውረድ አብዛኛውን ጦር ከደመሰሰ በኋላ በጨበጣ ውጊያ ጠቅላላውን ስለጨረሰው ከኋላ የመድፎችን ተኩስ ሲመራ የነበረው የመድፈኛው አዛዥ መኮንን ብቻ ከጥቂት ወታደሮች ጋር አምልጦ ምፅዋ ሊገባ ቻለ።

ከዚህ በኋላ ኢጣሊያ በዶጋሊ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል ብቻ ሳይሆን አንድ የተሟላ አውደ ጥቃት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ደጋማ አውራጃዎች ላይ ለመሰንዘር በማቀድ ጄነራል ሳንማርሳኖ በተባለ መኮንን የሚመራ ሀያ ሺህ የሆነ በመድፈኛና በመሀንዲስ ክፍሎች የተጠናከረ ጦር ከምፅዋ ተንቀሳቅሶ ሰሀጤን ለሁለተኛ ጊዜ በመያዝ መሽጎ ተቀመጠ።

የኢጣሊያ መንግሥት ይህንን እያደረገ ለአፄ ዮሐንስ አዘውትሮ የሚገልፀው በምፅዋ ወደብ አማካኝነት በሁለቱ አገሮች መካከል ንግድ ከመለዋወጥ በስተቀር በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ዓላማ ፈፅሞ የለንም በማለት ነበር። በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው የእንግሊዝ መንግሥት ምፅዋን በኢጣሊያ ሠራዊት ለማስያዝ የሰራው ሸፍጥ ያነሰ ይመስል፣ የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር መሰናዶ ማድረጉን እያወቀ እንዳላወቀ በመሆን የቤራው አባሪ ተባባሪ ሆኖ "በሰላምና በወዳጅነት ከኢትዮጵያ ጋር ንግድ ለመለዋወጥና ሃገር ለማልማት በመጡ ሰላማዊ ኢጣሊያውያን ላይ ራስ አሉላ የፈፀሙት ጭፍጨፋ በጣም የሚያሳዝን ነው" በማለት ራስ አሉላን የሚነቅፍና የሚያወግዝ ስሞታ ለአፄ ዮሐንስ አቀረበ።

አፄ ዮሐንስም እንግሊዞችና ኢጣሊያኖችን በራስ አሉላ ላይ ያቀረቡትን ክስ እውነት ነው ብለው በማመን ሰላም ይገኝ መስሏቸው እንግሊዞችን ለማስደሰት ሲሉ ራስ አሉላን ከሥልጣናቸው አውርደው በማሰርና ለውጊያ ያሰባሰቡትን አንድ መቶ ሺህ የሚገመት ሠራዊት ወደ ቤቱ መልሰው ወደ ሰላሙ ድርድር አመሩ።

በኢጣሊያ በኩል ያለው ሁኔታ ከዚህ በጣም የተለየ ነበር። ጄነራል ሳንማርሳኖን "ጦሩን ከሰሀጢ ምሽግ አስወጥተህ ለውጊያ በተሰለፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ከባድ የብቀላ እርምጃ ወስደህ ለኢጣሊያ መንግሥትና ሕዝብ አንድ አስደሳች የድል ብሥራት ታበሥራለህ" ብለን እንጠባበቃለን በማለት ሮም ያሉት የኢጣሊያ የጦር ኃይል ጠቅላይ አዛዥ የመከላከያ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ ግፊት አደረጉበት። እርሱም "እናንተ ሮም ሆናችሁ የምትመኙትን ድል እዚህ በኢትዮጵያ ምድር ከኢትዮጵያ ተዋጊዎች ጋር ለተፋጠጥነው ወታደሮች በቀላሉ ለማድረግ የሚቻል ነገር አይደለም። ከዶጋሊ የባሰ ጉዳትና ውርደት ሊያስከትል የሚችል ጀብደኛ እርምጃ እንድወስድ አትገፋፉኝ፤ ይህንን የማደርግበትን ቦታና ጊዜም ለኔ ተውሉኝ" በማለት ከምሽጌም አልወጣም ስላለ በበላዮቹ ተንቅፎ ከአዛዥነቱ በመነሳት ወደ ኢጣሊያ እንዲመለስ ተደረገ። ይህን የሰሙት አፄ ዮሐንስ የሳቸው የሰላም ፍላጎትና ጥረት መንገድ የያዘላቸው መስሏቸውም ነበር።

ሠራዊቱ ለውጊያ መፋጠጥና የፖለቲካ ውጥረት ያልተለየው የምፅዋ ግምባር በዚህ ሁኔታ ላይ መሆኑን የተገነዘበውና በአፄ ዮሐንስ ላይ የበካ ቂም ያለውና በመሀዲስቶች የሚመራው የሱዳን መንግሥት ዳግም ለሁለተኛ ጊዜ ጎንደርን ለመውረር ተንቀሳቀሰ። ይህ መልዕክት ከጎንደር የደረሳቸው ንጉሠ ነገሥቱም ሰሀጢ ላይ ለመሸገው የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት አንዳችም መፍትሄ ሳይፈጥሩና ተከላካይ ጦርም ሳያስቀምጡ ወደ መተማ በመዝመት ውጊያው ላይ በመሀዲስቶች እጅ ተሰዉ። ኢጣሊያኖችም ያላንዳች ተቃውሞና ድካም የሰሜኑን ደጋማ አውራጃዎችና የአሥመራን ከተማ ለመውረር አስቻላቸው።

ቀደም ብሎ ሰሀጢን ወሮ በመመሸግ ከአፄ ዮሐንስ ሠራዊት ጋር የተፋጠጠው የኢጣሊያን ጦር አዛዥ ጄነራል አንቶኒዮ ባልዲሴራ ከበላዮቹ ብርቱ ግፊት ስለተደረገበት ከሰሀጢ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ ወደ ፊት በመሄድ ጊንዳ ላይ መሸገ። ከዚያም ጥርጣሬና ፍርሀት በተሞላው ስሜት ስለአፄ ዮሐንስ ሞትና ስለ ሠራዊታቸው መበተን በእርግጠኛነት በማጣራት ላይ እንዳሉ ቀደም ብለው የአፄ ዮሐንስን ሥልጣን በመቀናቀን ተዋግተው ከትግራይ ወደ ኢጣሊያ መንግሥት የገቡና ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ዘውድ ወራሽ የሆኑት የራስ መንገሻ ባላንጣ የትግራይ መሣፍንቶች አገራቸውን ከድተው ለኢጣሊያ በመወገን ጄነራል ባልዲሴራን አበረታተውና ሰበው አሥመራ ከተማ አመጡት። አካባቢው የነበሩ የየአውራጃው ገዥዎችም ያላንዳች ተቃውሞ ተቀብለው በማስተናገድ ተገዥነታቸውን አረጋገጡለት።

የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በዚህ ሁኔታ የያዛቸውን አውራጃዎች ወይም ከመረብ ወንዝ ወዲያ ያለውን የኢትዮጵያ ግዛት ሕጋዊ ይዞታው እንዲያደርገው ሚያዚያ 25 ቀን 1888 ዓ.ም በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ውጫሌ ላይ በተደረገው ጠንቀኛ ውል ዳግማዊ ምኒልክ አፀደቁለት።

አሥመራ ከተማንና አካባቢውን ከተቆጣጠረ፣ ለቀጣዩ ወረራ ከተደራጀና ከተዘጋጀ በኋላ ተከታታይ ወረራዎችን በማድረግ ከኩአቲት ጀምሮ ሰንአፌን፣ ደብረኃይላን፣ አዲግራትን፣ መቀሌንና አምባላጊን ያዘ። ዳግማዊ ምኒልክ የውጫሌን ውል ቢዋዋሉም የኢጣሊያን ፍላጎትና ዓላማ ቀደም ብለው የተገነዘቡ ይመስላል፣ የጦር መሣሪያ እየገዙ በማካበት የኢትዮጵያን ተዋጊዎች አስታጥቀውና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባብረው በመሩት ፀረ-ኢጣሊያን ዘመቻ ከአምባላጌ ጀምረው ወራሪውን የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ኋላ መልሰው በመንዳትና አድዋ ላይ ድባቅ በመምታት በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት የጀመረውን ወረራ ለጊዜው ከመረብ ምላሽ ገቱት።

የአውሮፓ መንግሥታት በርሊን ከተማ ላይ በተስማሙበት የአፍሪካን አህጉር የመቀራመት ውልና ዘመቻ ዘመን በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ የተፈራረቁት ነገሥታት ሦስት ሲሆን እነሱም አፄ ዮሐንስ፣ ዳግማዊ አፄ ምኒልክና አፄ ኃይለሥላሴ ናቸው።

ሦስቱም ነገሥታቶች በዘመነ ኢምፔርያሊዝም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ በመገኘት ብቻ ሳይሆን በየተራቸው በአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና በአካባቢው ተስፋፊዎች የመከበብ፣ የመፋጠጥና ብሎም የመፋለም እጣ ገጥሟቸዋል። ከእነዚህ ሦስት ነገሥታት በፊት በዘመነ መሣፍንት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ብቅ ያሉት አፄ ቴዎድሮስ በብርቱ ያሰጋቸውና እንቅልፍ የነሳቸው አብይ ጉዳይ የአገሪቱ የተወሰኑ ክልሎች በቱርኮች መያዝ ነበር። ስለሆነም የውጭ ወራሪዎችን በብቃት ለመመከት ብሎም ረግጦ ከሃገር ለማስወጣት የሚቻለው አንድነቱ የጠነከረና በአንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የተማከለ ሕዝብ ሲኖር ብቻ ነው ብለው ያምኑ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ መላውን የሥልጣን ዘመናቸውን ያሳለፉት ከውስጥ ከፋፋይና ሥርዓተ አልበኛ መሣፍንቶች ጋር በመቀጣቀጥ ነው። ለነፃነት፣ ለአንድነት፣ ለጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የመመስረት ዓላማ ተግባራዊነት እየታገሉ የጉልተኛ መሣፍንቶችንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረት በማፈራረስ ማዕከላዊውን መንግሥት፣ የመከላከያውን ተቋምና የሕዝቡን አስተዳደር በዘመናዊ ሥርዓት ለመገንባት በመጣር ላይ እንዳሉ በአካባቢው መሣፍንቶች፣ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናቶችና በውጭ ተፃራሪ ኃይሎች የተቀነባበረ ጥቃትና ሴራ በአጭሩ ተቀጩ። የዘመነ መሣፍንትን አፍራሽ ቅሪቶችን አፄ ቴዎድሮስ ከአቅም መወሰንና በጊዜ እጥረት ምክንያት ያላስወገዷቸውን አብይ ብሔራዊ ችግሮች የተረከቡት አፄ ዮሐንስ ነበሩ። አፄ ዮሐንስም ሥልጣን ከተቀዳጁበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወታቸውን እስከ ማጣት የታገሉት ከውጭ ወራሪ ኃይሎች ጋር ነበር። በቅድሚያ ከግብጾች ጋር ቀጥሎም ከኢጣሊያኖች፣ በመጨረሻም ከመሀዲስቶች ጋር ለመዋጋት የተገደዱበትና ሥልጣናቸውን በእጅጉ ከመፈተን እስከ መሰዋት ያደረሷቸው ፈተናዎች ተደራርበውባቸዋል። በዚያ ኢትዮጵያዊ ሕብረት፣ ከብረት የጠነከረ የዓላማ ፅናትና መስዋዕትነትን በሚጠይቅ ለህልውና ለሚደረግ የተጋድሎ ዘመን የኢትዮጵያ መሣፍንቶች ቀርተው የስጋ ዘመዶቻቸው የሆኑ የትግራይ መሣፍንቶች እንኳን ሁሉም አላበሩላቸውም። ሰፊ ግዛት፣ የተካበተ ሀብትና በርካታ ሠራዊት ያላቸው ንጉሥ ምኒልክ ቀንደኛ የዘውድ ባላንጣቸው ስለነበሩም መላውን ኢትዮጵያ ሊቆጣጠሩ ቀርቶ ሸዋን እንኳን በእግራቸው ሊረግጡ አልቻሉም። አፄ ዮሐንስ ሃገርን ከውጭ ወራሪዎች ከመከላከል ባሻገር ሰላም የሰፈነበት አመቺና በቂ ጊዜ አግኝተው ሃገርን ለማዘመንና የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል አልቻሉም፤ አልታደሉምም።

በዘመነ መንግሥታቸው አልፎ አልፎ ባገኟቸው አነስተኛና አንጻራዊ ሰላምና የሥራ ጊዜም ያተኮሩት በልማትና በግንባታ ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ነበር። እሳቸው በነበሩበት የጊዜ ክልል በኢትዮጵያ ቀርቶ በቀሩትም አህጉሮችና አገሮች 'ሃገር የጋራ ሃይማኖት የግል' ስለመሆናቸው በሕዝቡም ዘንድ ሆነ በአመራር አካሎች በቂ ግንዛቤ ስላልነበረ ከአክሱም መንግሥት ውድቀት በኋላ በተለያዩ ጊዜያቶችና ክልሎች በፈቃዳቸው የእስልምና እምነትን የተቀበሉትንና በኋላም በግራኝ አስገዳጅነት በሰይፍ ያሰለሙትን ኢትዮጵያውያን ምርጫውን ለነሱ መተው ሲገባ እንደገና ወደ ክርስትና እምነት እንዲመለስ ያደረጉት ጥረት በባህሪው ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ አልነበረም። ድርጊቱ ከራሱ ከሕዝቡ ፍላጎትና ፈቃድ የመነጨ ባለመሆኑ ስኬታማ ሳይሆን ብርቱ ጠላቶችን በማፍራት ከመሀዲስቶች ጋር በጦር ሜዳ ለመሰለፍና ለሕይወታቸው ማለፍ ምክንያት ሆኗል።

በገጠሟቸው ውስብስብ ብሔራዊ ችግሮች ጊዜም አቅምም አግኝተው አመርቂና ዘላቂ መፍትሄ ያላገኙላቸው ግን ያለ እረፍት እንደታገሉ በጦር ሜዳ ላይ የመውደቅ እጣ ስለገጠማቸው የእሳቸው ተተኪ የሆኑት አፄ ምኒልክም በፈንታቸው እንደዚሁ ውስብስቦቹን ብሔራዊ ችግሮችና ከባድ የሥራ ውዝፎችን ተረክበዋል። ዳግማዊ ምኒልክ የተረከቧት ኢትዮጵያ እንግሊዝን፣ ፈረንሳይንና ኢጣሊያን በመሰሉ የአውሮፓ የቅኝ ገዥ ኃይሎች የተከበበችና የታፈነች ሃገር ነበረች። እንግሊዞች ቀደም ብለው የኢትዮጵያ አጎራባች የሆኑትን አገሮች ሱዳንና ኬንያን ቅኝ ግዛቶቻቸው ከማድረግ ሌላ የኢትዮጵያ አካል የነበረውን የዛሬውን ሰሜን ሶማሊያ የእንግሊዝ ሶማሊያ የተሰኘ ስም በመስጠት፣ የፈረንሳይ መንግሥት በዛሬው የጂቡቲ ሪፑብሊክ መንግሥት ግዛት ውስጥ ካሉት ጥንት ታጁራ በመባል የሚታወቀውን ወደብና በኋላም ጂቡቲ የተባለ ስም የሰጡትንና ጥንት አቦክ የሚባለውን ወደብ፣ ኢጣሊያ በቅድሚያ አሰብን፣ በተከታታይ ቤሉልንና የምፅዋ ወደብን በማጠቃለል ኤርትራ የተባለ ስም ከሰጠችው መላው የሰሜንና የሰሜን ምሥራቅ ክልል በተጨማሪ መላውን ደቡብ ሶማሊያን በመቆጣጠርና የኢጣሊያ ሶማሊያ በማለት ተቀራመቱ። እነኝህ ቅኝ ግዛት የተጠሙ የአውሮፓ ኃያል መንግሥታት እነዚህን የኢትዮጵያ ድንበሮችና መውጫ መግቢያ የባሕር በሮች ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ልብ የሚጠልቁበትን ጊዜና አመቺ ሁኔታ ይጠብቁ ነበሩ።

አፄ ምኒልክ ከተረከቧቸው አያሌ ችግሮች ታላቁና አንገብጋቢው የኢጣሊያ መንግሥት የአፍሪካ ቀንድ ይገባኛል ከሚል ዓላማ በመነሳት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ከመረብ ወንዝ ወዲያ ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ በመላው ኢትዮጵያ ለመስፋፋት በገሀድ የጀመረው ወረራ ነው። ዳግማዊ ምኒልክ የኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት በአድዋ የጦር ሜዳ ለጊዜው ከመረብ ወንዝ መለስ ከማቆም በስተቀር ከኢትዮጵያ ፈጽሞ በማስወጣት የቅኝ ግዛትን ስጋት ስላላስወገዱ ችግሩን በፈንታቸው ለተከታያቸው ለአፄ ኃይለሥላሴ አስረከቡት። የአፄ ምኒልክ ዘመን መንግሥትን ከአመራር አባቶቻቸው ከአፄ ቴዎድሮስና ከአፄ ዮሐንስ ጋር ስናነጻጽር አፄ ምኒልክ በጣም እድለኛ ናቸው ለማለት ይቻላል። ከሁሉ በፊት ጥቅጥቅ ያለውን የጎጠኞችና ሥርዓተ አልበኞች መሣፍንቶች ደን አፄ ቴዎድሮስ መንጥረው ያረሱትንና አፄ ዮሐንስ ያለሰለሱትን ሃገር ስለተረከቡ የውጭ ጠላት እንጂ የውስጥ ጠላት አልነበረባቸውም።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብና መሣፍንቱ በሙሉ ያበረላቸው በመሆኑ፡ አንፃራዊ ሰላም በሰፈነበት ሁኔታ ከአርባ ዓመታት በላይ በንጉሥ ነገሥትነት ለመምራት ችለዋል። የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ኢትዮጵያን ዙሪያዋን መክበብ ብቻ ሳይሆን ወደ አገሪቱ ልብ ለመግባት ሲያደቡ አፄ ምኒልክ ፈጥነውና ቀድመው በመንቀሳቀስ ክግራኝ ወረራና በዘመነ መሣፍንት ሁከት የተበታተነውን ሕዝብ መልሰው ከማሰባሰብ ባሻገር ከቅኝ ገዢ ኃይሎች ወረራ አድነውታል። በአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት በተጧጧፈበት ወቅት ከብረት ዘሮች ሳንቲም ማስቀረፅና ከወረቀት ገንዘብ ማሳተም ተስኖት በእህል፣ በጥራጥሬ፣ በተለያዩ ቁሳቁሶችና በከብትና እንስሳት ልውውጥ እንዲሁም በጥይትና በአሞሌ ጨው ይገበያይ የነበረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በምስላቸው ገንዘብ አስቀርጸው ከሺህ ዓመታት በኋላ በሕጋዊ ገንዘብ ተገበያይና ተጠቃሚ አድርገውታል።

አፄ ምኒልክ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባብረው የኢጣሊያን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በአድዋ የጦር ሜዳ ድባቅ በመምታት ኢጣሊያ በመላው ኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት የጀመረውን ወረራ ከመረብ ምላሽ ገተዋል። ዓለም እረስቷትና እሷም ዓለምን እረስታ ለሺህ ዓመታት ብቻዋን በጨለማ ውስጥ የኖረችውን ኢትዮጵያን ከዓለም ጋር

በማስተዋወቅና ከተለያዩ የውጭ መንግሥታት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመመስረት እንደገና የዓለም ሕብረተሰብ አካል አድርገዋታል። ከሰማው ዓለም ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ኃይል በጥቂቱም ቢሆን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት፣ የጤና፣ የመገናኛ፣ የባንክ፣ የንግድ፣ የመሠረተ ልማትና የፋይናንስ ዘመናዊ አገልግሎትን ጥቅም አስተዋውቀዋል።

የመንግሥታቸውን አመራር አካላት በዘመናዊ መልክ በማዋቀር የሥራ ክፍፍል ያለበት የሃገር አመራር ለመመስረትም ሞክረዋል። በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች አፄ ምኒልክ የአዲሲቱን ኢትዮጵያ አናዊ መሃንዲስ ቢባሉ የሚበዛባቸው አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዳግማዊ ምኒልክ ለረጅሙ ዘመን መንግሥታቸውና በጦር ሜዳ ላገኟቸው ድሎች በመድማትና በመሰዋት አመራራቸው ስኬታማ እንዲሆን ከማድረግ ባላይ ለረጅም ዘመናት ሳያስከፋቸው እምዬ ምኒልክ እያለ አቅፎና ደግፎ አቆያቸው። እላቸው ቢያንስ ሕጋዊና ፍትሃዊ አስተዳደር መስርተው ከአያሌ ችግሮቹ ጥቂቱን እንኳን ላይቀርፉለትና ሳያቃልሉለት፡ ይልቁንም ጸሮቹ ከሆኑት መሣፍንትና መኳንንት ጋር እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ወግነዋል።

አፄ ቴዎድሮስ ያፈራረሱትን የመሣፍንቱን መደብ መልሶ መገንባት ብቻ ሳይሆን የባርያና የገባር ሥርዓቱን ከምንግዜውም በላቀ ሁኔታ እንዴት እንዳጠናከሩት ከዚህ በታች እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ሳታጣ ያጣች የዓለም ኋላ ቀር ሰልፈኞች ጭራ የሆነችበት ምክንያት ጥንታዊውና ከኋላ ቀሩ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ያለመላቀቋ ነው፣ በማለት አበክረን ስንጭትና በብሶት የምንኮንነውን የፖለቲካ ሥርዓት ባህሪ መዳሰሱ የሥርዓቱ ነጸብራቅ የሆነውን የአገሪቱን የተለያዩ አሳፋሪ ገፅታዎችና የሕዝቡን እጅግ አሳዛኝ ሕይወት ለመመልከት ያስችለናል። ኢትዮጵያ የብዙ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች ሃገር ከመሆኗ ይልቅ ከአብራኳ የወጡና ራሳቸውን ግን ከሕዝብ የነጠሉ ጉልተኛ መሣፍንትና መኳንንት ሃገር ሆና ኖራለች።

ከጥንታዊው የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር በመውጣት ወደ ጉልታዊው የመደብ ሕብረተሰብ ከተሸጋገርንበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ሕብረተሰቡ አሰፋፈርና እንደ ጉልታዊው ሥርዓት አስተዳደር ተዋረድ ከመንደር ጀምሮ እስከ ክፍለ አገሮች ድረስ ለአያሌ ምዕተ ዓመታት አስተዳዳሪ የሚባሉት በሕዝቡ የተመረጡ፣ ለሕዝቡ ፈቃድና ለሕግ የሚገዙ የሕዝብ አገልጋዮችና አስተዳዳሪዎች አልነበሩም። ከሕዝቡ የተለየንና በተፈጥሮ ሕዝብን እረግጠንና መዝብረን እንድንገዛ የተመረጥን ነን ብለው የሚያምኑ፣ የዘር ሀረግ እየቆጠሩ፣ በመሬቱ ላይና በመሬቱ ከርሰ ማህጸን ውስጥ ያለውን ማናቸውንም የተፈጥሮ ሀብትና ሕዝቡን ራሱን እንደ ቁሳቁስ እየተወራረሱ የግል ንብረታቸውና የኪስ ገንዘባቸው አድርገው እንዳሻቸው የሚያዙበትና የሚጠቀሙበት አፄ በክንዱ ናቸው። እስከ አፄ ምኒልክና በኋላቸውም ዘመነ መንግሥት የየክልሉ ጉልተኛ ገዥዎች ማዕከላዊ መንግሥት ከሚባለው ጋር ያላቸው ግንኙነት ተመጥኖ የተሰጣቸውን ዓመታዊ ግብር እንደ ሁኔታው በእህል፣ በከብት፣ በማርና በቅቤ፣ ወደ ኋላም በጥሬ ገንዘብ ከመክፈል ሃገርን የሚወር የውጭ ጠላት ሲመጣ ወይም የአገሪቱን ሰላም የሚያደፈርሱና ለማዕከላዊ መንግሥት አንገብርም የሚሉ የውስጥ አመጸኞች ሲፈጠሩ በሚሰጣቸው የክተት ትዕዛዝ መሠረት ተንቀሳቅሰው ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዙትን ሃገርን የመከላከልና የውስጥ ፀጥታን የማስከበር ተግባር አከናውነው ወደ የክልላቸው መመለስ ሲሆን ከዚህ ቢያልፍ እንደየአቅማቸውና ፍላጎታቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ፍቅርና ቀረቤታ ለማግኘት ገጸ በረከት ማቅረብን በመሳሰሉ ጉዳዮች ነው።

በአንድ ንጉሠ ነገሥት በምትመራና በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ጥላ ስር በምትተዳደረው ጉልታዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የአስተዳደር ክልሎች ለማዕከላዊ መንግሥት የተወከለ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት፣ ሕግ አስከባሪ ፖሊስ፣ ዳኛና ፍርድ ቤት ወይም የሕግና የፍትህ ተቋም ብሎ ነገር አልነበረም። የየክልሉ ገዥ ጉልተኞች የየራሳቸውን ክልሎች እንዳሻቸው የሚረግጡበት የየራሳቸውን ልማዳዊ የአገዛዝ ዘይቤ፣ የጥቅማቸው፣ የሥልጣናቸውና የየግላቸው ፀጥታ አስከባሪ የሚባል ግን ዘራፊና ገፋፊ የገበሬ ፀር የሆነ የግል ሠራዊት ያላቸው ናቸው። እንዳሻቸውና እንደልማዳቸው በሕዝቡ ሀብት፣ ጉልበትና ሕይወት ጭምር የሚያዙና የሚፈርዱ የሚያስፈልጓቸውን ባለ ሥልጣኖች በዘር ሀረግ ላይ ተመስርተው በስጋ የሚዛመዷቸውን የሚሾሙም የሚሽሩም ናቸው።

በሕዝቡ ላይ ምንም አይነት ግፍና በደል ቢፈጽሙ ተከሳሽነትና ተጠያቂነት የሌለባቸው፣ የማይገሰጹና የማይከሰሱ፣ የሁሉም ነገር ባለቤት ሆነው እንደመሰላቸው ለአገልጋዮቻቸው እርስትና ማደርያ መሬት እየሸነሸኑ የሚተክሉና ሲያስፈልጋቸውም የሚነቅሉ ፈላጭ ቆራጭ፣ ገዥም፣ ዳኛም ሕግም ናቸው። ገባሩ የሚገብረው ለዋናው ጉልተኛ ወይም ለክልሉ ገዥዎች ብቻ ሳይሆን አስገባሪው ብዙ ነው።

እንደ ክልሉ ወግና ልማድ ራስ፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች፣ የጭቃሹም፣ ምስለኔ ወዘተ የሚባሉና በገባሩ ላይ የሚሾሙ እያሌ የማዕረግ ደረጃ ያላቸውና የሠራዊቱ ሹማምንቶች እስከ ምንዝሩ ወታደር ድረስ ሁሉም አስገባሪ ናቸው። ለአገዛዙ የሚከፈል አሥራትና እርቦ፣ ለቤተክርስቲያንና ለካህናት፣ ለጦር አበጋዞችና ለወታደር የሚከፈል ድርጎ ወዘተ እየተባለ የሚጠራ በጽሑፍ የሰፈረና በሕግ የተደነገገ ሳይሆን በዘፈቀደና በልማድ በየክልሉ የሚሰራባቸው የግብር አይነቶች ብዙ ናቸው። ከዚህ ውጪ ከላይ እስከ ታች በተዋረድ ለእያንዳንዱ ጉልተኛና ሹመኛ ከብቶች በመጠበቅና በማርባት፣ ጊደሮች ወይም ላሞች ሲወልዱ ጥገቶቹን ለጉልተኛው ወይም ለሹመኛው ማስረከብ፣ ታልበው ሲነጥፉ ከነጥጆቹ መልሶ በመውሰድ ዳግም እስኪያረግዙ እንዲሁ በመጠበቅና በመንከባከብ ወይፈኖች ተኮላሽተው በተለየ እንክብካቤ እየተቀለቡ የሰቡ ሰንጋዎችንና እንዲሁም የበግና የፍየል ሙክቶችን ማቅረብ የእያንዳንዱ ገባር ግዴታ ነው። ገበሬውና ልጆቹ የሚጠጡት የምንጭና የወንዝ ውሃ፣ የሚመገቡት ሽሮና ጎመን ሲሆን በአዘቦቱ ቀን አንጓትና አሬራ፣ በአውዳመት መረቅና ስጋ የሚያገኙ የገበሬ ቤተሰቦች እድለኞች ናቸው።

ለፋሲካ፣ ለገናና ለዘመን መለወጫ ዓውዳመቶችና በዓሎች፣ ጉልተኛውን እጅ መንሳት ቋሚ ሕግና ባህል ነው። ይህንን ሁሉ ግብርና የእጅ መንሻ ስጦታ እንደ ጉልቱ ስፋትና ርቀት፣ እንደ ግብሩ ብዛት ገባሮቹ ጭነው ለጉልተኛው ሲያመጡ አመስግኖ በጸጋ የሚቀበላቸው በማጣት ስንቃቸውን ጨርሰው ግብር ለማቅረብ ደጅ በመጥናት የሚጉላሉም አሉ። የአየር ንብረት ይቃወስና፣ የሰብል ፀር የሆኑ ተባዮች ይፈጠሩና፣ ሰብሎች በዋግ፣ በከባድ ዝናብና በበረዶ ይመቱና፣ የከብት በሽታ ይከሰትና ገባሩ ከአቅሙና ከቁጥጥሩ ውጪ የሆኑ ችግሮች ገጥመውት ለጉልተኛው የሚያቀርበው ግብር ቢታጎል፣ መጠኑ ቢያንስ ወይም ጥራቱ ቢቀንስ ገባሮቹ የሚደርስባቸው ቅጣት ከፍ ያለ ነው።

ያለማጋነን አንዳንዶቹ ጉልተኞች በዚህ የተነሳ ገባሮቻቸውን የሚያስሩ፣ የሚገርፉና ከጉልታቸውም እስከ መንቀል የሚደርሱ አሉ። አልፎ አልፎ በሚከሰቱ እንኚህን በመሳሰሉ ችግሮች ገባሮች ለጉልተኞች የሚያቀርቡት ቀርቶ እራሳቸውም የሚመገቡትና ለዘር የሚያውሉት እየጠፋ ከጉልተኛው በአራጣ ለምግብና ለዘር እህል የሚበደሩበትም ጊዜ አለ።

ይህንን የመሳሰለው መከራ እንዳይደርስባቸው፣ ቢደርስ ለከፋ አደጋ እንዳይዳርጋቸው ዘለዓለም በስጋት የሚኖሩት ገባሮች ሳይሰሩ በእነሱ ጀርባ ታዝለው ደማቸውን እየመጠጡ የሚኖሩትን ጉልተኞችና ባለጊዜ ሹመኞች ለማስደሰትና ርህራሄ ለማግኘት ከመጣር ሌላ አማራጭ የሌላቸው የመኖር ግዴታ ስለሆነ ዓመት የደከሙበትን ምርት አካፋፍለው እነሱ ምርት ካበራዩበት አውድማ ግርድ ከአፈር ጋር በችፍርግ ጠርገው ወደ ጎጆዋቸው ሲገቡ ለተመለከተ የሚያስለቅስ ነው። የገበሬው ልጆች አባታቸው ያዘመረውን እሸት እንዳይቀጥፉ፣ ከምር ዘርጥጠው እንዳያሹና እንዳያነኩቱ ሌትተቀን በአይነ ቁራኛ የሚጠብቋቸው የጉልተኞች ወኪል የሆኑ ሰላዮች ይሰማሩባቸዋል።

የቀን ሀሩር፣ የሌሊት አመዳይና የንጋት ቁር እየተፈራረቁባቸው ቀን ከብት የሚያግዱ፣ ማገገ ላይ ተሰቅለው ሰብሎችን ከአዕዋፍ የሚጠብቁ፣ ለሊት ከአራዊት የሚከላከሉ፣ ምርት ደርሶ አባታችን ጨርቅ ይገዛልናል ብለው የሚቋምጡ የገበሬ ልጆች፣ የጉልተኞችና የሹማምንት ሚስቶች የሚዋቡባቸውን አልባሳት፣ ጌጣጌጥና ሽቶ ሳይመኙ ቀን ሲያርሙና ሲጎለጉሉ፣ ለሊት ሲፈጩና ሲጋግሩ የተቆራመደ ፊታቸውን የሚያብሱበት ዘይት እንደ ብርቅ የሚመለከቱና የሚመኙ የገበሬ ሚስቶች ብዙ ናቸው።

ዳግማዊ ምኒልክ ይህንን በመሰለ አሰቃቂ ኑሮ ሲሰቃይ የኖረውን የሰሜኑንና የመሃል አገሩን ገባር ስቃይ ከማቃለል ፋንታ አንፃራዊ ነፃነት፣ የተሻለ የኑሮ ደረጃ፣ ሰላም፣ ለምና ልሙሬ ርስት በነበረው በደቡብ ሕዝብ ላይ የተለየ የመሬት አስተዳደር ደንብ በማውጣት የገባር ገበሬዎችን ችግር ማዛመት ብቻ ሳይሆን በከፋ ሁኔታ አባብሰውታል።

ፀረ-ገበሬ የሆነውን የመሣፍንቱን የየግል ፊውዳል ሠራዊት በደቡብ ገበሬ ላይ በማሰማራት ያላንዳች ሕግና ሥርዓት መረን ለቀው የገባር ሥርዓቱን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ጥንታዊውን የባርያ ሥርዓት መልሰው በመገንባት ከምንጊዜውም በላቀ ሁኔታ በኢትዮጵያ የባርያውን መደብ ቁጥር አበራክተውታል። አፄ ምኒልክ የአውሮፓን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት የዓለም ኋላ ቀር የሆነችውን ሃገር ለማዘመንና የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ሲያደርጉት በነበረው የአዲስ ሀሳብና የመሻሻል ተግባር ተፃራሪ የሆነውን የመሣፍንት መደብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም በመካብ፣ የአገሪቱ ምሰሶ የሆነውን አምራች ገበሬ መደብ በመበደል ከራሳቸው ጋር ሲጣሉ ኖረዋል።

ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ በቅርቡ በተለይም በዘመነ ኢምፔርያሊዝም በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ ከተፈራረቁት ነገሥታት የመጨረሻ የሆኑት አፄ ኃይለሥላሴን የ20ኛው ምዕት ዓመት መሪ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በብዙ ምክንያቶች ከቀደምቶቻቸው ጋር ማነፃፀር ተገቢ አይሆንም።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አስተዳደግ፣ በዘመነ መንግሥታቸው የነበረችው ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከ19ኛው ምዕት ዓመት ጠቅላላ ሁኔታዎች ጋር ስናስተያየው በጣም የተለያዩ ናቸው። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ልደትና እድገት በተመለከተ ራሳቸው ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ብለው ባጻፉት ግለ ታሪክ ላይ እንደገለፁት በተፈጥሮ ብልህነታቸው፣ በአስተዳደርና በጦር አመራራቸው ምስጉን ከሚባሉትና ከአንዴም ሁለቴ ከኢትዮጵያ ውጪ ተልከው የአውሮፓን ክፍለ ዓለም ዕድገትና ሥልጣኔ ከተመለከቱት አባታቸው ከልዑል ራስ መኮንን ትምህርትና ተመክሮ ያገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ የተፈራረቁት ነገሥታቶቻችን በሙሉ የአገራቸውን ባህላዊ ወይም የቤተክህነት ትምህርት ተምረው ምናልባት ማንበብና መጻፍ ይችሉ እንደሆን እንጂ ዘመናዊ የሚባለውን የውጪ ሃገር ትምህርት የቀሰሙ እንደሌሉ ሲታወቅ ቀዳማዊ

ኃይለሥላሴ ግን የውጪውን ሃገር ቋንቋና የቀለም ትምህርት አባታቸው በቀጠሩላቸው የቤት መምህራንና በኢትዮጵያ የመጀመሪያ በሆነው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከአገራቸው ወጥተው ሌላውን ዓለም ለመጎብኘት እድል ያገኙ ነገሥታት እንደሌሉን ሲታወቅ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግን ከእንደራሴነታቸው ጀምሮ እስከ ሕይወተ እረፍታቸው ዓለምን በብዛት ከጎበኙት የዓለም መሪዎች አንዱ ናቸው።

በልጅነታቸው የቀለም ትምህርታቸውን ከመከታተል ጋር በአባታቸው ቤትና በአፄ ምኒልክ ቤተመንግሥት ውስጥ በመኖርና ፍርድ አደባባይ በመዋል የአገራቸውን ፖለቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮችን በቅርብ የተከታተሉ ብቻ ሳይሆን በጎውንም ተንኮሉንም እንደተማሩ ገልጸዋል። ከአሥራ ሦስት ዓመት እድሜያቸው ጀምሮ በአባታቸው ወዳጅ ሹማምንቶችና በሞግዚት መካሪዎች እየታጀቡና እየታገዙ በተለያዩ አውራጃዎችና ክፍለ አገሮች አስተዳዳሪ በመሆን የሕዝቡን ኑሮ ለማስተዋል ታድለዋል። አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ ጭምር የባዕድ ቋንቋ በቃል ወይም በጽሑፍ የሚተረጉምላቸው፣ በውጪ ሃገር የሚወክሏቸውና የሚላላኳቸው ኢትዮጵያውያን አጥተው በተቸገሩበት ሃገር፥ አፄ ኃይለሥላሴ የተለያዩ ሙያዎች ባላቸው አያሌ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ተከበው መኖራቸው ብቻ ከቀደምቱ ነገሥታት በጣም የተለዩ ያደርጋቸዋል።

የሸዋ መሣፍንት፣ መኳንንትና ካህናት ልጅ እያሱን በአድማ ወንጅለው ከሥልጣን በማውረድ ልዕልት ዘውዲቱን ንግሥት እርሳቸውን ደግሞ አልጋ ወራሽና እንደራሴ አደረጓቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የተነሱባቸው የሥልጣናቸው ባላንጣዎችና ወግ አጥባቂ አንጃዎች ክፉኛ ቢታገሏቸውም፥ በአንፃሩ ቅን ልቦናና አስተዋይ ህሊና የነበራቸው አያሌ ሃገር ወዳዶች፣ የነጋዴው ሕብረተሰብና በተለይም የአገሪቱ ምሁራን ከተፈሪ መኮንን የሚሻል ሰው የለም በማለት ታግለው ለዙፋን ባለቤትነት አብቅተዋቸዋል።

አፄ ኃይለሥላሴ እንደ ተጠበቀባቸውም ከአመራር አባቶቻቸው በተሻለ በጎና ገንቢ ተግባሮችን አከናውነዋል። የአገራችን ኋላ ቀርነት ዓብይ ምክንያት የሕዝቡ አለመማርና የመሪዎቹም ማይምነት መሆኑን በመገንዘብ የትምህርት ሚኒስትርነቱን ደርበው በመያዝ በአገሪቱ ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ያደረጉት ሙከራ እጅግ ከፍተኛ ነው። የጤና አገልግሎቶችን ችግር ለማቃለል ከመሞከር ጀምሮ በአገራችን የህክምና ባለሙያዎችን በተለይም ሀኪሞችን የማፍራት ጅምራቸው የሚናቅ አይደለም። የመስተዳድሩን ተቋም በዘመናዊ መልክ በማደራጀት ትምህርትና እውቀት ያላቸውን ዜጎች ለማሰባሰብ ያደረጉት ጥረት የሚያስመሰግናቸው ነው።

የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች በዓለም ላይ በተንሰራፉበት ዘመን ኢምፔርያሊዝም አፍሪካዊያን በባርነት ቀንበር በተጠመዱበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያን የነፃዎቹ መንግሥታት ሊግ አባል ማድረጋቸው በዘመነ መንግሥታቸው የተከናወነ ታላቅ የፖለቲካ እርምጃና እምርታ ነበር። ታሪኳን በሙሉ በጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ በመማቀቅ በጦርነት፣ በሥርዓተ አልበኝነት፣ በሽብርና በሁከት ለኖረች የሰላም እጦት ብቻ ሳይሆን ሕግና ፍትህ አልባ የባርያዎች፣ የሎሌዎችና የገባሮች ሃገር ለሆነችው ኢትዮጵያ የ1923 ዓ.ም የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ይዘቱ ባዶ ባይሆን ኖሮ ሌላው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ታላቅ የፖለቲካ ክንዋኔ በሆነ ነበር። "ማንም ሳይጠይቀንና ሳያስገድደን ለምንወደውና ለሚወደን ሕዝባችን በፈቃዳችን ሰጠነው" የተባለው ሕገ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳያስተውል አውሮ፣ እንዳያስብ አደንቁሮ፣ እንዳይራመድና እንዳይሰራ እጅ እግሩን አስሮ

የኖረውን ጉልታዊ የፖለቲካ ሥርዓትና ሥልተ ምርት ሊያሻሽል ቀርቶ የኢትዮጵያዊያንን ተራ ሰብዓዊ መብትና የህሊና ነፃነት እንኳን የማይገልፅ፣ ለንጉሡ ነገሥቱ መለኮታዊ ሥልጣን ለመዋፍንቱ ጥቅም ሕጋዊ መደላደል የሆነ ሰነድ ነበር።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቀደም ብለን በተመለከትናቸው ብዙ ምክንያቶች ከቀድሞ ነገሥታት ሁሉ የተሻለ አጋጣሚና ግንዛቤ ያገኙ በጣም የተሻሉ ተግባሮችን ስላከናወኑ ምስጋና ሊነፈጋቸው አይገባም ብንልም የተረከቧት ኢትዮጵያ ወሳኝ አደጋ ያንዣበበባት እንደነበረችም መዘንጋት የለበትም።

ከመረብ ወንዝ ወዲያ ባለው የአገራችን ሰሜናዊ ክልልና በሶማሊያ መሸጋ የተቀመጠችው ኢጣሊያ የማጥቂያ መዣሪያዎቿንና ዘመናዊ አየር ኃይሏን በሚገባ አደራጅታ በአድዋ የደረሰባትን ሽንፈትና ውርደት ለመበቀል ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ለኔ ትገባኛለች ብላ የተነሳችበትን ዓላማ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለሚያደርግ ወረራ ተዘጋጅታ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባገኙት የ22 ዓመታት ረጅምና አንፃራዊ የሰላም ጊዜ እንደ ኢጣሊያ መንግሥት የመከላከያ ኢንዱስትሪ አደራጅተው ከኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ትጥቅ ጋር የሚገማመት የጦር መሳርያ ለማስመረት የአገሪቱ አቅም ፈፅሞ የማይችል ቢሆንም፣ የዓለም መንግሥታትን ሊግ ያቋቋሙት መንግሥታት እራሳቸው የማያምኑበትንና የማያከብሩትን የማህበሩ ሕግ የጦር መሳርያና የመከላከያ ሠራዊት ሆኖ ከወረራ ያድነን ይመስል በማህበሩ ተማምነውና ተመክተው አፄ ምኒልክ ከአርባ ዓመታት በፊት አገራቸውን ለመከላከል ያደረጉትን ያህል እንኳን ዝግጅት ያለማድረጋቸው የሚያሰገርም ነው።

እንደሚታወቀውና እንደሚጠበቀው ቅኝ ግዛት የተጠማው ፋሽስት የኢጣሊያ መንግሥት የወረራ ጅምሩን ህዳር 14 ቀን 1927 በወልወል ግጭት አማካኝነት ለኢጣሊያ ሕዝብና እንዲሁም ለመላው ዓለም አበሰረ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት አዛዥ በሆነው ጀነራል ግራዚያኒ የሚመራው እግረኛና ብረት ለበስ ቅምር ጦር ከደቡብ ሶማሊያ ወይም ኢጣሊያ እንደምትለው "ከኢጣሊያ ሶማሊያ" እየተወረወረ የኢትዮጵያን ደቡብና ምሥራቃዊ ክልሎች መውረር ያዘ። ኦጋዴን አቋርጦ ወደ መሃል ኢትዮጵያ ሲያመራ አካባቢው በርሃ ስለሆነ የውሃ ችግር እንዳይገጥመው በመሃል ኦጋዴን ብቸኛ የከርሰ ምድር ሀይቅ ያለበትን የወልወልን ወረዳ ከዋናው ወረራ በፊት በጥቂት ምንደኛ ባንዳ ጦር ተቆጣጠረ።

ወልወል በመሃል ኦጋዴን በአውላላ ሜዳ ላይ የሚገኝ ከዋርዴር አውራጃ ወረዳዎች አንዱ ሲሆን፣ በ14ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ አፄ ዘራያዕቆብ በርካታ ሠራዊት ይዘው በዚያን ጊዜ ቤንያድር አሁን የሶማሊያ ሪፓብሊክ የሚባለውን ክልል በሙሉ እስከ ቀይ ባሕርና የሕንድ ውቂያኖስ ዳርቻ ድረስ ታሪካዊ ቅኝትና ጉብኝት ባደረጉበት ጊዜ በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ጥያቄ 359 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን ያስቆፈሩበት ስፍራ ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግሥት ወሰን ከሚባለው መስመር 90ኪ.ሜ እርቀት ላይ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኘው የወልወል ወረዳ በአጠቃላይ የከርሰ ምድር ሀይቅ ነው ለማለት ይቻላል። የወልወል የከርሰ ምድር ውሃ በየትኛውም የኦጋዴን አውራጃዎች የማይገኝ ጨውና ኖራ አልባ የሆነ፣ ለአፍ የሚቀልና ሲጠጡት የሚጥም ጣፋጭ ውሃ ሲሆን እያንዳንዱ ጉድጓድ ጥልቀት 50 ሜትር ነው።

ከኤርትራ እየተነሳ በኢትዮጵያ ሰሜን የሚገባው የኢጣሊያ ወራሪ ጦር መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም በሦስት አቅጣጫ የመረብን ወንዝ እየተሻገረ ወሰን ሲጥስ፣ ከሶማሊያ የሚነሳው ወራሪ ጦር በሐረርጌና በሲዳሞ ክፍለ አገሮቻችን ጠረፎች በሦስት አቅጣጫ፣

በጠቅላላው በሰድስት አቅጣጫዎች ወሰናችንን በመጣስ ወረው በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን፣ መንግሥታዊ ህልውናውንና ክብሩን ተገፈፈ።

እንደዚህ አይነቱ ጥቃት ሲሰነዘር የኢትዮጵያ ሠራዊት ከጠላቱ የተሻለ ጥቅም የሚኖረው በሚኖርበት የአየር ንብረት፣ በተወለደበት ሃገርና መግቢያ መውጫውን በሚያውቀው ምድር ላይ መዋጋቱ ነው። ሌላው ጥቅሙ አፄ ምኒልክ በአድዋ እንዳደረጉት ቁጥሩ ከኢጣሊያ ሠራዊት እጅግ የላቀ የሰው ኃይል ማሰለፍ መቻሉም ነው። በዚህ ሁለተኛው ከኢጣሊያ ጋር በተደረገ ውጊያ ግን ሁሉንም አልተጠቀምንበትም።

የኢጣሊያ እጅግ ከፍ ያለ የመሣሪያ የበላይነትን መዝኖ ለመገኘት ይቻል የነበረው ከሰው ኃይል ብዛት ባሻገር፣ የጀግንነት ባህልና ፅኑ የሃገር ፍቅር ያለውን ተዋጊ ባለው መሣሪያ አሰልጥኖ ጥራት ያለው ሠራዊት ማሰለፍም አልተቻለንም። ቁጥራቸው 25,000 ነው የሚባሉት የንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ጦር በስተቀር ተዋጊው ኃይል ከዘጠና በመቶ በላይ የሆነው ምንም ዓይነት ሥልጠና የሌለው ገበሬ ነበር። በጦር መሪዎቹም ረገድ ከትልልቆቹ ከራሶቹ ጀምሮ በየእዙ ተዋረድ አመራር ላይ የተቀመጡት ስምና ማዕረግ እውቀት ይሆን ይመስል በጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ደንብ በሚያዙበት ክልል የሚያስተዳድሩትን የታጠቀ ገበሬ ይዘው የዘመቱ እንጂ ከጦርነቱ ባህሪ፣ ከሚገጥማቸው ጠላት አይነትና ትጥቅ አንፃር በተቃርኖ ለመፋለም ወይም ለመምራት የሚያስችል የጦር ትምህርት የሌላቸው መሣፍንትና መኳንንት ስለሆኑ የአመራር ድክመት ለሠራዊቱ ውድቀት ዋናው ምክንያት ነበር። አንድን የጦር መሪ በጦር ሜዳ የድል ባለቤት የሚያደረገው በጦር ሜዳ ላይ ሠራዊቱን ለማጋፈር ከመሠማራቱ በፊት ጠላቱ ማን እንደሆነ፣ መጠኑንና አይነቱን፣ የሚዋጋበትን የመሣሪያ አይነት የሚጠቀመውን የውጊያ ስልትና ስትራቴጂ በቅድሚያ አውቆና በዚህ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ እንደሆነ ብቻ ነው።

የእኛ ጀግና ሠራዊትና መሪዎቹ ወደ ማይጨው የጦር ሜዳ ከመሄዳቸው በፊት በንጉሡ ነገሥታቸው ፊት በፅኑ የሃገር ፍቅር ስሜትና በልበ ሙሉነት ጎራዴያቸውን እየመዘዙ፣ "ለአስር ለሃያ የኢጣሊያ አንገት ተዋሰኝ" እያሉ በሚያቅራሩና በሚፎክሩበት ጊዜ የሚላኩበት የጦር ሜዳ ከሰማይ የቦንብ ናዳና የጋዝ መርዝ ዝናብ የሚወርድባቸው መሆኑን ያውቁ ነበር ተብሎ አይታሰብም።

የጦር ሜዳ ድል ከጦርነቱ በፊት በሰላሙ ጊዜ በብርቱ የተደከመበትና ከፍ ያለ ገንዘብም የወጣበት የመረጃ ውጤት ነው። በኢጣሊያኖች በኩል ስለማናቸውም የኢትዮጵያ ሠራዊት ለማወቅ የመረጃ ችግር አልነበረባቸውም። በኢጣሊያኖች ሰፈር ከነበረው ቁጥር ከመቶ ሺህ በላይ ከሚገመተው የሃገር ተወላጅ ምንደኛ ባንዳ ሌላ በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት የአውሮፓ ዲፕሎማቶች፣ የአረብ፣ የሕንድ፣ የአርመንና የግሪክ ነጋዴዎች ወንጌል ሰባኪ ነን ከሚሉ ሚሲዮናዊያን ሌላ ከኢትዮጵያ ታላላቅ መሣፍንትም ውስጥ የኢጣሊያ መንግሥት የመረጃ ወኪሎች ነበሩ።

የንጉሡ አማች ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳን የመሳሰሉት ግለሰቦች ከኢትዮጵያ ወገን የተዘጋጀውን የውጊያ እቅድና የዘመቻውን ትዕዛዝ ሳይቀር ከነዘመቻ ካርታው ከቤተ መንግሥት እየወሰዱ ለኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ከመድረሱ በፊት ለኢጣሊያ የጦር መሪዎች ይሰጧቸው ነበር።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ሠራዊት በኩል የነበረው ታላቅ ችግር ስለጠላት ለማወቅ ያለመቻልና የውጊያ መረጃ ድህነት ብቻ ሳይሆን የራስን የጦር ገበናና ምስጢር ለመጠበቅ ያለመቻል ድክመት ጭምር ነበር። በኢትዮጵያ ሠራዊት ተቋም ውስጥ ባለው የእዝ ጠገግ

ላይ ያሉት የጦር መሪዎች ጦራቸውን የሚያስተባብሩበት፣ ማናቸውንም ትዕዛዝ በተዋረድ ለየጦር ክፍሉ የሚሰጡበትንና የሚቀበሉበት የመገናኛ መሣሪያ አልነበራቸውም። በሌላ አነጋገር በጦር ሜዳ ላይ ጦሩን እንዲመሩ የተሰማሩ መሪዎች ይመሩታል በሚባለው ሠራዊት ላይ እዝና ቁጥጥር የላቸውም።

የሚዋጋበትን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ራሱ ከሚያመርት አንድ የአውሮፓ ኃያል መንግሥት ከሆነ ጠላቱ ጋር ለነፃነቱና ለህልውናው የሚታገል መንግሥት ታንክና ተዋጊ አውሮፕላኖች ማምረት ወይም ማግኘት ባይችል የእነዚህን ፀሮች መከላከያ ማሳሪያ ማግኘት ግን ከአገሪቱ አቅምና ችሎታ በላይ ሆኖ አይታየንም።

በስንቅ አቅርቦት ድክመት ከብረት ጋር የሚታገለው ሠራዊት በጠላቱ ተኩስ ሳይሆን ለአጭር ጊዜ ውስጥ በርሃብ መሰቃየቱና መፈታቱ በጣም የሚያሳዝን ነው። ለሠራዊቱ ሽንፈት ምክንያት የሆኑት ሰበቦች እነዚህ ብቻ አልነበሩም። የጊዜው የኢትዮጵያ ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታ ይመስላል የኢትዮጵያ መሣፍንቶች ለአፄ ምኒልክ እንዳደረጉት አፄ ኃይለሥላሴን አልተባበሯቸውም።

አንዳንዶቹ መሣፍንትና መኳንንት ከጠላት ወግነው በመሰለፍ ወግተዋቸዋል። ወደ የጦር ግምባሮቹ ከዘመቱት የጦር መሪዎች ውስጥ ትልልቆቹ ራሶች የሚናናቁና የማይግባቡ ወይም የማይስማሙ ነበሩ።

የጀግናውና የብልሁ የራስ ሙሉጌታ ከመከላከያ ሚኒስትርነት ተነስቶ የቂሉ የራስ ካሳ መተካት ለመሣፍንቶቹ መጥመምና ያለመግባባት ዋና ምክንያት ነበር። ለዚህም ማስረጃው፣ ዋናውን የሰሜን ግምባር ወሳኝ ፍልሚያ ተፋለሙ ማለት የሚቻለው ልዑል ራስ እምሩና ራስ ሙሉጌታ ብቻ ናቸው። ይህ የኔ ምስክርነት ሳይሆን የጠላት የጦር መኮንኖች ያረጋገጡት ሐቅ ነው።

ከጦርነት በፊት፣ በጦርነቱ ሂደትና ከጦርነቱም በኋላ የመሣፍንቶቹ መክዳት ለፋሽስቱ ድልና መጠናከር ታላቅ አስተዋፆ አድርጓል። በአጠቃላይ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ጋር የተደረገው ተጋድሎ በጥልቀትና በዝርዝር ለመረመረው ትግሉ ከኢጣሊያኖች ጋር ብቻ ሳይሆን የኢጣሊያ ምንደኛ ከሆኑት የሃገር ተወላጆች ጋር እንደነበር የሚያከራክር አይደለም።

የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የተባበረው የእንግሊዝ መንግሥት ሠራዊት አመራር ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ በ1933 ዓ.ም ስለጦርነቱ ባወጣው መግለጫ ለማወቅ እንደተቻለው ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው ጠቅላላ ሦስት መቶ ሃያ ሺህ የኢጣሊያ ሠራዊት ውስጥ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብቻ ኢጣሊያኖች ሲሆኑ፣ ሰላሳ ሺህ የሶማሊያና የሊቢያ ዜጎች ወታደሮችና የተቀሩት አንድ መቶ ሰባ ሺህ ሠራዊት ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ።

ይህ ቁጥር አምስት ዓመት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በተደረገው ውጊያ የተሰዋው፣ የቆሰልና በተለያዩ ምክንያቶች ከውጊያ ውጭ የሆነውን ሁሉ በመቀናነስ በመጨረሻ የፋሽስት ሠራዊት እጁን ሲሰጥ የተገኘ ቁጥር ወይም ዘገባ ስለሆነ የኢትዮጵያኑ ምንደኞች ቁጥር ከዚህ የላቀ መሆኑ አያጠያይቅም።

በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል ከአድዋ በኋላ በተደረገው ሁለተኛው የማይጨው ጦርነት አይበገሬዎቹን የኢትዮጵያ ጀግኖች ለመበቀልም፣ ለመርታትም የኢጣሊያ መንግሥት ለአርባ ዓመታት ያደረገው የውጊያ ዝግጅትና በህገወጥ መሳርያ መጠቀሙ

በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ያደረሰው የንብረት፣ የአካልና የመንፈስ ጉዳት እጅግ ከባድ ነበር። ሆኖም ግን በኢትዮጵያም በኩል ባለው አቅም ተገቢው የውጊያ ዝግጅት ተደርጎ ቢሆንና ኢጣሊያንን ለመመለስ በሚበጅ ዘመናዊ የጦር ስልት ብንጠቀም ኖሮ ኢትዮጵያ ወራሪውን ለመመከት ትችል እንደነበር ይታመናል። ይሄም የኢትዮጵያ አርበኞች ከጠላታቸው በነጠቁት መሣሪያ ያከናወኑት ተግባር ራሱ ማስረጃ ከመሆኑ በላይ አማካሪ የነበሩ የኢትዮጵያ ወዳጆች ባዕዳን መኰንኖችና ወታደራዊ ጠበብቶች ያመኑበት ጉዳይ ነው።

የጦርነቱን ጊዜና ውጤቱንም በዚያ ሁኔታ የወሰነው የኢጣሊያኖች ጀግንነትና የመሣሪያ የበላይነት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ በኩል የነበረው የውጊያ መሰናዶ ጉድለት፣ የጠላትን ኃይልና አወጋግ ተመልክቶ የውጊያ ስልት ለውጥ ለማድረግ ቀርቶ ሠራዊቱን ማዘዝና መቆጣጠር እስከለመቻል ድረስ የአመራር ድክመት መኖሩም ነው።

የዓለም መንግሥታት ማህበር አንዱ አባል ሃገር ሌላውን አባል ሃገር ሊያጠቃው ስለማይችል ኢጣሊያ አትወጋንም የሚል አስተሳሰብ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ በኢትዮጵያ መሪዎች ሁሉ ስለተሰረፀ ሰርገኛ መጣ እንዲሉ ለውጊያ ዝግጅት ማድረግ የተጀመረው የከበቡን የኢምፔርያሊስት መንግሥታት የመሣሪያ ማዕቀብ ካደረጉብን ከ1927 ዓ.ም የወልወል ግጭት በኋላ ነው። ይህንንም ለጦርነቱ በአማካሪነት ከተለያዩ አገሮች የተቀጠሩ የጦር መኮንኖች በጻፏቸው መጻሕፍቶቻቸው ላይ ስለጦርነቱ ያዩትን፣ የታዘቡትንና ስለውጤቱም ሲገልጹ በኢትዮጵያ ወገን ከኢጣሊያ ጋር የሚያስልፈን ዝግጅት እንዳላደረግን አረጋግጠዋል።

የመጨረሻው ውጤትም ኢትዮጵያና ሕዝቧ ያለ ምንም ተቃውሞ ከትግራይ እስከ አዲስ አበባ መንገድ እየሰሩ በመጡ ፋሽስቶች መዳፍ ውስጥ መውደቅና ንጉሠ ነገሥቱም ለዚያው ላመለኩበት የመንግሥታት ማህበር ሊያመለክቱ አገራቸውን ለቀው እንዲወጡ መገደድ ሆነ። ለአንድ ሃገር፣ ለአንድ ሕዝብና ለአንድ መሪ ከዚህ የከፋ ነገር ያለ አይመስለኝም። በስደት ለአምስት ዓመት አውሮፓ ከግዞት በማይሻል ሁኔታ መቀመጥ የአካልና የአእምሮ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የኃዘንና የሰቆቃ ጊዜ ቢሆንም ስለ ጊዜው የዓለም ፖለቲካ ብዙ የተማሩበትና ታላቅ ግንዛቤ ያገኙበት ጊዜ እንደነበር አያጠያይቅም።

በእጅጉ የሚያምኑበትና የሚመኩበትን የመንግሥታቱን ማህበር እንዳሻቸው የሚያሽከረክሩት መንግሥታት እራሳቸው ወራሪዎችና የቅኝ ግዛት ኃይሎች እንደመሆናቸው፣ የእነኙህ ጥርቅም የሆነው ሊግ ወራሪዋ ፋሽስት ኢጣሊያ ከጀርመን ወግና ብሔራዊ ጥቅማቸውን እንዳትጋፋ ለማስደሰት በኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ህልውና ብቻ ሳይሆን በደሙና በሕይወቱ የፖለቲካ ቁማር ሲጫወቱ ለማስተዋል ችለዋል።

ኢጣሊያኖች በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረው የያዙት ባጭር ጊዜ መሰናዶና በቀላሉ ተዋጊ ኃይል በመርከብ ጭነው በመላክ ብቻ አልነበረም። በ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ በቪክቶር አማኑኤል ርዕሰ ብሔርነት የሚመራ ዘውዳዊ መንግሥት በመቋቋም የተበታተነውን የኢጣሊያ ሕዝብ መልሶ ለማሰባሰብና ለማቋቋም ቢሞክርም ድህነትን ሥራ አጥነት፣ ከዚያም የሚመነጨው የሕዝብ ተስፋ መቁረጥን የመሳሰሉ ከባድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመላው ኢጣሊያ ሰፍነው ነበር።

በ1857 ዓ.ም በተደረገው የጠቅላይ ሚኒስቴር ምርጫ የርዕሰ መንግሥቱን አመራር ለመያዝ የቻለው ካሚዩ ካቮር "በኢኮኖሚ እጅግ የተዳከመችውና በቆዳ ስፋቷም የኮሰመነችውን ኢጣሊያ እንድታንሰራራና መልሳ እንደትቋቋም ለማድረግ የሚቻለው ከ16ኛ

ምዕት ዓመት ጀምሮ በተራቸው እንደገነኑት የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት እኛም በአፍሪካ አህጉር ቢያንስ አንድ በቆዳ ስፋቱና በተፈጥሮ ሀብቱ የታወቀ ሃገር በቅኝነት ለመያዝ የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው። ቅኝ ግዛታችንን በአፋጣኝ በማልማት ለአገራችን ለኢጣሊያ ምንጊዜም የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ የሚገኝበት፣ በሚሊዩን የሚቆጠሩ የአገራችንን ሥራ አጦች የምናስፍርበትና ንግዳችንን በማስፋፋት ሸቀጦቻችንን እንዳሻን የምናስራጭበት ሁኔታዎች መፍጠር አለብን” በማለት በኢጣሊያ ሕዝብ ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ የቅስቀሳ ንግግር አደረገ።

ካሚዩ ካቮር ይህንን የመሰለ ቅስቀሳ በይፋ ያደረገው ከራሱ ግላዊ ምኞትና ፍላጎት ብቻ ከመነሳት ሳይሆን በምክር ቤቱ ውስጥ የነበሩት የቀኝ ክንፍ የፖለቲካ የአመራር አካላት በሙሉ የሃሳቡ ተጋሪ ስለነበሩ ነው። የኢጣሊያ ፋሽስቶች ብቻ ሳይሆን ከግራ የፖለቲካ የአመራር አካላት በስተቀር መላው የቀኝ ክንፍ የፓርቲ አመራር አካላትን ያስከራቸው የቅኝ ግዛት ምኞት መንስኤም ነበረው። ይኸውም የስዊዝ ቦይ ከመከፈቱ በፊት በ1830 ዓ.ም እነጁሲፔ ሳፔቶ ወደ ኢትዮጵያ ከተላኩበት ጊዜ ጀምሮ በራሳቸው አነሳሽነት፣ በመንግስታቸው ትዕዛዝ፣ በሮም ሊቃነ ጳጳሳትና በቫቲካን ድርጅት ድጋፍና ግፊት ወደ ኢትዮጵያ በጉብኝትና በንግድ ሰበብ፣ በወንጌል ሰባኪነት ከሚላኩት ኢጣሊያውያን ሌላ ከተለያዩ የአውሮፓ አገሮች በኢጣሊያ መንግሥት እየተመለመሉ ይሰማሩ ነበር። የዓባይን ጅረት መነሻ ለማወቅ የመጣን የአፈር፣ የውሃ፣ የእዕዋፍና የእፅዋት ተመራማሪዎች ነን የሚሉት እነኚህ ሰላዮች ኢትዮጵያን ከዘጠና ዓመት በላይ እየሰለሉ “ይህች የምድረ ገነት እንዳታመልጠን” በማለት በተለይ የኢጣሊያ ተወላጆች የኢትዮጵያን ለምነትና የተፈጥሮ ሀብት ክምችት በማጋነን መንግሥታቸውን ለወረራ ሲቀሰቅሱ ኖረዋል።

በእነኚህ የሃገር ሰላዮች አማካኝነት የኢጣሊያ መንግሥት ስለኢትዮጵያ ጠቅላላ ተፈጥሮ፣ ስለመልካምድራዊ አቀማመጧ፣ ስለ አየር ንብረቷ በምድሯ ላይና በምድሯ ከርሰ ማህፀን ውስጥ ስላሉ የተፈጥሮ ሀብቶቿ፣ የአገሪቱን የማህበረሰቦችንና የብሔረሰቦች ቋንቋ፣ ባህልና መንፈሳዊ እምነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ቅራኔ ወይም ልዩነት በሕዝቡና በገዥው መደብ መካከል ያለውን ግንኙነት፣ አጠቃላዩን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ሥርዓትና ሥልተ-ምርት፣ በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ያሉት የመደቦች አሰላለፍ ወዘተ የመሳሰሉ ዝርዝር መረጃዎችን ሲሰበስቡ ቆይተዋል። የተሰበሰቡትን መረጃዎች የሚያበጥር የሚተነትን፣ የሚተረጉምና እንዴትና ለምን ጉዳይ እንደሚጠቅም ሀሳብ የሚያቀርብ አንድ ራሱን የቻለ ልዩ ስለ ኢትዮጵያ የሚያጠና የምርምር ተቋም በሮም ከተማ ተቋቁሞ ይሰራ ነበር።

የኢጣሊያ ፋሽስት መንግሥት ኢትዮጵያን ወሮ ርዕሰ ከተማዋ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ሙሶሎኒ “የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ድል አድርጎ ይዟል! ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቄሳር ግዛት መሆኗን ለዓለም እናስታውቃለን!” ካለ በኋላ፣ አንዴ ጠቅላይ ሚኒስትር ካሚዩ ካቮር በኢጣሊያ የገቢ ምንጭ ለማድረግ ከፍ ያለ ገንዘብ በማፍሰስና አያሌ ሰላዮችን በማሰለፍ የተሰበሰበውን መረጃና ጥናት በሚገባ ተጠቀመበት። በዚህ የመረጃ ስብስብና ጥናት ላይ ተመስርቶ “የኢጣሊያ ሠራዊት ወራሪ አይደለም እናንተን ነፃ አውጪ እንጂ፣ የኢጣሊያ ሠራዊት አፍራሽ አይደለም የእናንተን ኑሮ ለማሻሻልና ኢትዮጵያን ለመገንባት የመጣላችሁ እንጂ” በማለት ይነዛ በነበረው መሰሪ ፕሮፖጋንዳ ያላመነና ያልተታለለ አልነበረም ለማለት ያዳግታል።

በዘር፣ በቋንቋና በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በአስተዳደር ክልላዊ ሥነ-ልቦናና በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ስለከፋፈለው አገሩንና ነፃነቱን ይወጋ የነበረው ምንደኛ ባንዳ ቁጥር

ከአርበኛው ቁጥር የላቀ ነበር። የኢትዮጵያ ጉልተኛ የገዥ መደብ የመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት በጦር ሜዳ ተሸንፎ፣ በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ የቅኝ ገዥው መደብ የመራው አካል በመኮታኮቱ ማህበራዊ ሥርዓቱም አብሮ ፈርሷል። የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን ጉልታዊውን ሥልተ-ምርት በካፒታሊስት ሥልተ-ምርት ለመተካት የሚያስፈልገውን እቅድና ቅድመ ሁኔታ ያዘጋጀው ቀደም ብሎ በዚያው በኢጣሊያ ከጦርነቱ በፊት ስለነበረ ግንባታው በሚያስደንቅ ፍጥነት ሰመረ።

በጦርነቱ ሂደት ውስጥ ተጀምሮ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ የተካሄደው የመሠረተ ልማት፣ የዘመናዊ ግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የማዕድን ልማትና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ተቋማት ግንባታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልጠበቀውንና በታሪኩ አይቶት የማያውቀውን የሥራ ዕድል ከፈተለት። በኢትዮጵያ ጉልታዊው ሥርዓት ባሪያና ሎሌ የነበረውና እንዲሁም ቀማኛና በዘኔ ሥራአጥ የሕብረተሰብ ክፍል በኢጣሊያ የካፒታሊስት ሥልተ-ምርት ግንባታ ጅምር ወደ ወዝ አደር መደብ ሲለወጥ፣ የጉልተኞች ገባር የነበረው ደሃ ገበሬ ባለ ርስት ስለሆነ የፋሽስት ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ማወደስ ተጀመረ።

ከዘመናዊው ምሁርና ከካህናቱም ወገን የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ኃያልነትና ለጋስነትን ያወደሱ፣ የዘመሩ፣ የገጠሙና የተቀኙም ነበሩ። እንደሚባለውም ከሰፊው ሕዝብ ወገንም ለኢጣሊያ ወታደሮች "ኢጣሊያ ለዘላለም ትኑር" እያለ መፈክር የሚወረውረው ቁጥር ጥቂት አልነበረም። ታሪኩን በሙሉ በዚያ በከፋ ጨቋኝ ጉልታዊ ሥርዓተ-ማህበር ውስጥ የተሰቃየና የተንገፈገፈ ሕዝብ ባጠቃላይ፣ ባርያው ሎሌውና ገባሩ በተለይ ከምንዳ ወዝ አደርነት ወደ ባለመሬትነት መለወጡ ቢያስደስተው የሚያስደንቅ ሊሆን አይገባም።

ሕዝቡ ለአያሌ ምዕተ-ዓመታት ካሰቃየው ጉልታዊው ሥርዓት የኢጣሊያኖች የፕሮፖጋንዳ ናዳና ከሕዝቡ ድህነትና በጣም ዝቅ ያለ ማህበራዊ ንቃት አንፃር በቅኝ ግዛት አስተዳደር መደሰቱ ባያስደንቅም ቤኒቶ ሙሶሎኒ ለኢትዮጵያ ያቀደው ግን በሌሎች አገሮች ሲደረግ የምናየው አይነት የቅኝ ግዛት አስተዳደር ሳይሆን ኢትዮጵያን የኢጣሊያውን አፅመ ርስት ወይም ሁለተኛዋ ኢጣሊያ ለማድረግ ነበር።

ሰኔ 20 ቀን 1928 ዓ.ም ለቀምት ከተማ ላይ የጥቁር አንበሳ አርበኞች ከአሥራ አንድ የኢጣሊያ የጦር መኮንኖች ጋር በኢትዮጵያ የኢጣሊያ የአየር ኃይል አዛዥ የነበረውን ማርሻል ማልቲኮን ገድለው ሦስት አውሮፕላኖችን ባጋዩበት ጊዜ በእጅጉ የተናደደው ሙሶሎኒ ለማርሻል ግራዝያኒ በጻፈው መልዕክት "ግራዝያኒ የእስከ ዛሬዎቹን የኢጣሊያ ግዛቶች ሊቢያንና ሶማሊያን አንተ ከማንም የተሻለ ደህና አድርገህ ታውቃቸዋለህ፤ በእነዚህ አገሮች ከመክሰር በስተቀር ያገኘነው አንዳችም ነገር የለም። ሁለቱም ምንም ነገር የሌላቸው የአሸዋ ክምሮች ናቸው። እዚያ የከሰርነውን የምንካሰው በኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ የምድር ገነት ነች። እንግሊዞች በሰሜንና በማዕከላዊ አሜሪካ፣ በአውስትራሊያ በኒውዚላንድ እንዳደረጉት ቢያንስ ከፊሉን የኢጣሊያ ሕዝብ አስፍረን ዘላለማዊ ርስት በመስጠት አንድ ሌላ ኢጣሊያ በአፍሪካ ለመፍጠር እየተዘጋጀን ባለንበት ጊዜ የኢትዮጵያ ባላገሮች የሮማን መኮንኖች ገደሉ የሚባል ዜና እኔና የኢጣሊያ ሕዝብ እንዴት እንስማ? የኢጣሊያ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን ዘመናዊና አውዳሚ መሣሪያዎች በገፍ ሰጥቼሃለሁ። ቢያስፈልግም አሁንም ከሠራዊት ጋር እጨምርልሃለሁ። ተጠቀምባቸው።" ብሎት ነበር።

ግራዚያኒም ለሙሶሎኒ ትዕዛዝ የሰጠው መልስ: "ስህተቱ የማርሻል ማልቲኮ ነው። ያለጥንቃቄ ያለበቂ ጥበቃ ሽፍቶች ባሉበት ስፍራ በድፍረት ስላረፈ እሱን የመሰለ መኮንንና ሌሎችም ከማጣታችን ይልቅ የእርስዎን የታላቁን መሪዬንና የአገሬን የኢጣሊያንን ክብር

የሚነካ ነገር በመፈጸሙ ሀዘኔ ወሰን የለውም። እርስዎ የሰጡኝ ተልዕኮ የተሳካ እንዲሆን ሁሉንም ነገር ከመስጠትና ከማመቻቸት በስተቀር የተነፈግኩት አንዳችም ነገር የለም። የሰጡኝን ትዕዛዝ በሚገባ እፈፅማለ። ኢትዮጵያን ቢቻል ከነሕዝቡ ባይቻልም ያለሕዝቡ ለዱቼ ለማስረከብ ቃል እገባለሁ።” የሚል ነበር። እዚህ ላይ አንባቢ ሊያጤነው የሚገባ ነገር፣ “ቢቻል ከነሕዝቡ፤ ባይቻል ያለሕዝቡ አስረክባለሁ” የሚለውን ቃል ነው። የኢጣሊያን ሕዝብ ወረራውን እንዲደግፍ ሲባል የተፈጠረ መላ ይሁን ወይም በኢትዮጵያ ረጅም ጊዜ በስለላ ሥራ የቆዩት ስላዩች የግል ምኞታቸውን ለማሳካትና ባለታሪክ ለመሆን ሲሉ ስለ ኢትዮጵያ ልምላሜና ሀብቷ ከመጠን በላይ እያጋነኑ በመናገር የኢጣሊያን ፖለቲከኞችና የጦር መሪዎች ሁሉ አሳምነው እንደሆነ መንስኤው በውል ባይታወቅም ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ሕዝብ ዘንድ ልዩ ስሜት ፈጥራለች፣ ልዩ ትኩረትም አግኝታለች።

ሙሶሎኒ የምድር ገነት እያለ ሲናገር በተደጋጋሚ ተደምጧል። ገነት የሚባል ነገር ካለ ምን እንደሚመስል ባላውቅም ሙሶሎኒ ስለኢትዮጵያ ነፋሻነት፣ ውበትና ልምላሜ የተናገረው ከእውነት የራቀ አልነበረም። እኛ ኢትዮጵያውያን አያያዝና አጠቃቀሙን ባለማወቃችን አገራችን የተላበሰችውን የተፈጥሮ ፀጋ በመግፈፍ አወደምናት እንጂ ጥንታዊ ግሪኮችና ግብፃውያን የአገራችንን ነፋሻ የአየር ንብረት፣ ውበትና ልምላሜ በማድነቅ የአዝርዕት፣ የእጽዋት፣ የእንስሳትና የቅመማ ቅመም ሃገር እያሉ ሲያወድሷት እንደነበር ሁሉ በመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኙ አውሮፓውያን በሙሉና ለማስረጃም ያህል አፍሪካን በውል የሚያውቁት እነዶክተር ዴቪድ ሊቪንግስተንና እነጀምስ ብሩስ “የአፍሪካ የውሃ ገበቴና የዳቦ ቅርጫት” በማለት አሞካሽተዋት ነበር።

እንደ ዛሬው የለማኞችና የችጋር ሃገር ሳትሆን የእንግዳ አስተናጋጅና የደግ ሕዝብ ሃገር ነበር የምትባለው። ሙሶሎኒ ለሂትለር በመወገን የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቀውስ ውስጥ ገብቶ በተወጠረበት ጊዜ የኢጣሊያ ኮሚኒስቶች ገድለው ዘቅዝቀው በመስቀል በአጭሩ ባይቀጩትና ምኞቱ ቢሳካለት ኖሮ ሌላዋ ኢጣሊያ እናደርጋታለን የሚላት የኢትዮጵያ እድል ምን ሊሆን እንደሚችል ለማሰብም ሆነ ለመተንበይ የሚያስቸግር ነው።

## ድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ

ፋሽስት ኢጣሊያ በጦር ሜዳ ድል ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊመለስ የቻለው የጀርመን፣ የኢጣሊያ እና የጃፓን ሕብረት ጎራ ለመውጋት የተባበሩት የቃል ኪዳን አገሮች መንግሥታት ለኢትዮጵያ በነበራቸው ወገናዊነትና ርህራሄ ሳይሆን የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት እነሱን በመክዳት ከጀመርን ወግኖ ስለወጋቸው ነው። የኢትዮጵያ አርበኞች ከወራሪው የፋሽስት ኢጣሊያ ሠራዊት ጋር የሚያካሂዱትን ትግል እንደግፋለን በማለት አፄ ኃይለሥላሴን ይዘው የመጡት የእንግሊዝ መኮንኖች የግብጽ መሪ እንደነበረው ፋሩቅ በኢትዮጵያም አፄ ኃይለሥላሴን በአሻንጉሊትነት አስቀምጠው የራሳቸውን ወታደራዊ አስተዳደር በመትከል ቅኝ ሊያደርጉን ያልሞከሩት ነገር የለም።

ይሀ ግን ከእንግሊዝ መንግሥት ማዕከላዊ የአመራር አባላትና ወደ ኢትዮጵያ ከተላኩትም መኮንኖች መካከል ጥቂትም ቢሆኑ የነበራቸውን ቅን አመለካከትና የፈፀሙትንም በጎ ተግባር በውለታ ቢስነት ለመካድና ሁሉንም በጅምላ ለመኮነን አይደለም። ጥቂቱን እንደ ቁም ጠንካራ አድርጎ ለኢትዮጵያ ነፃነት የበኩላቸውን በጎ አስተዋፆ ለማድረግ ያስቻላቸው ግን የአርበኞቻችን ጥንካሬና ሕዝባችን ለነፃነቱ የነበረው ቀንዓዊነት ነው።

በዚያን ጊዜ በአገራችን እንግሊዞች በሁለት አንጃ የተከፋፈሉ ነበሩ። በየደረሱበት በአያሌ ታዳጊ አገሮች ውስጥ ያደርጉ እንደነበረው ሁሉ የኢትዮጵያ አርበኞች ባይኖሩ ኖሮ በፈቃዱ የሚገዛ ሕዝብ አገኘን በማለት መንግሥታቸውን አሳስተው እነሱ በፈላጭ ቆራጭነት የሚንደላቀቁባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ቆርጠው የተነሱ መኮንኖችን ያሰባሰበ ቡድንና በተቃራኒው በሃቅ የኢትጵያን ሕዝብ ነፃነት የሚደግፉ ያካተተ ሌላ ቡድን፤ በኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች በሱዳን፣ በሶማሊያ፣ በኬንያና በዩጋንዳ የነበሩ የእንግሊዝ ወታደራዊ የበላይ ሹማምንቶች ብቻ ሳይሆኑ ሲቪል ፖለቲከኞችም ጭምር ይህችን ከዓለም ጥቁር ሕዝብ ብቻዋን የነፃነት ደሴት ሆና የምትታይ ጥንታዊት ሀገር ከምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቻቸው ጋር ቀላቅለው አንድ ሰፊና ኩታገጠም ክልል ለመፍጠር በኢትዮጵያ ከነበረው አንጃ ግብራበራቸው ጋር ግምባር ፈጥረው የእንግሊዝን ማዕከላዊ አመራር አሳስተው ስለሚያሳምኑበት መላምት በተለያዩ ስፍራዎችና ጊዜዎች እየተገናኙ ይዶልቱ ነበር።

በኢትዮጵያ የነበሩት የቅኝ ግዛት ዓላማ አራማጆች ከንጉሠ ነገሥቱም ሆነ ከሌላ የኢትዮጵያ አመራር አካል ጋር ሳይመክሩና ሳያስታውቁ አርበኛውን ቀድመው አዲስ አበባ በመግባትና ንጉሠ ነገሥቱ ከነጃም ወደ አዲስ አበባ እንዳይመጡ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር አዘግይተው ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ለአመራሩ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ ወታደራዊ የቅኝ አገዛዝ መሰረቱ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ የሚያውቀውንና የሚወደውን የራሱን ገንዘብ እንዳይገበያይበት አግደው የእንግሊዝ መንግሥት በምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቹ የሚገለገልበትን የምሥራቅ አፍሪካ ሽልንግ ብቻ እንዲሰራ ታላቅ ተፅዕኖ አደረጉ።

የጠላት ስሪትና ቅሪት በሆኑ በማናቸውም ንብረቶችና ህንፃዎች አዛዥና ናዛዥ ሆነዋል። በተለይ የጠላት ንብረትን በተመለከተ እነሱ ብቻቸውን ተዋግተው ከጠላት የነጠቁ ወይም ያስጣሉ ይመስል ያገኙትን ሁሉ የጦር ምርኮ ንብረት ነው በማለት እየሰበሰቡ የራሳቸው አድርገዋል። ከየትኛውም የኢትዮጵያ የበላይ አካል ሳይመክሩ አርበኞች በውጊያ ከጠላት የማረኳቸውን ከባድ መሣሪያዎች በእናንተ እጅ እንዲቆይ አይፈቀድምና አስረክቡን በማለት በአርበኞች ላይ የኃይል እርምጃ እስከ መውሰድ ቃጥቷቸዋል።

ንጉሠ ነገሥቱ የፈረሰ መንግሥታቸውን መልሰው ለማደራጀት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋም በጀመሩ ጊዜ የምክር ቤቱን መቋቋም ከመቃወም ሌላ እኛ ሳናውቅና ሳንፈቅድ ምንም አይነት ተቋም መፍጠር፣ የሲቪልም ሆነ ወታደራዊ ባለሥልጣኖችን መሾም፣ መሻርና በአገሪቱ በየትኛውም ክልል ጦር ማዘዋወር አይችሉም ለማለት በቅተዋል። በርዳታ ስም የመጣ አንድ ባዕድ ኃይል ይህንን ለማድረግ መቻሉ ቀርቶ ካሰበም ቅኝ ግዛት ከዚህ የተለየ ቦታ የለውም። በመጨረሻም አርበኛው እንደ ማይንበረከክላቸውና ሕዝቡም እንደማይገዛላቸው በተረዱ ጊዜ የኢጣሊያ ስሪትና ቅሪት የሆኑትን ኢንዱስትሪዎች፣ ልዩ ልዩ የቴክኒክና የጥገና አገልግሎት መስጫ ማዕከሎችንና ሆርሻዎችን፣ መሣሪያዎችንና በጠቅላላ ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ንብረቶች፣ የውሃ ማከፋፈያ ቧንቧዎችና የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች ሳይቀሩ እየነቃቀሉ ወደ ሶማሊያ፣ የመንና ሕንድ ሲልኩ ለማጓጓዝ የተሳናቸውን በተለይም የጦር መሣሪያዎችን ሰብስበው ባሕር መጨመራቸውን ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ የነበራቸው ምኞት ባለመሳካቱ የቁን ያህል እንዳስቆጫቸው በግልፅ የሚያስረዳ የበቀል እርምጃ ነው።

እንግሊዞች በዚህ በቀል ብቻ ኢትዮጵያን ከመበደል አልተገቱም። ከኢትዮጵያ መውጣታቸው አይቀሬ መሆኑን ሲገነዘቡ ኤርትራንና ኦጋዴን ላልተጠናቀቀው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወታደራዊ ጥቅም ስለሚያስፈልጉን በኛ የቅኝ ግዛት ይዞታ ይቆያሉ በማለት

ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዳይመለሱ ከለከሉ። በእነዚህ ሁለት ክልሎች ውስጥ በቆዩበትም ጊዜ የኤርትራን ደጋማ ክልል ከትግራይ ጋር ቀላቅለው ከኢትዮጵያ በመገንጠል ትግራይ ትግሪኝ የተባለ ሃገርና መንግሥት ለማቋቋም፣ የኤርትራን ምዕራባዊ ቆላማ ክልል የቅኝ ግዛታቸው ከነበረው ከሱዳን ጋር በመቀላቀል ኢትዮጵያን ለማኮስመንና ለማዳከም ታላቅ ጥረት አድርገዋል።

ይህንን መሰሪና እኩይ ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባር ኢጣሊያኖችም ያሉበት ሲሆን የባዕዳኑን ዓላማ የራሳቸው ዓላማ ያደረጉትና አፄ ኃይለሥላሴ የየክልሉን መሣፍንቶች የፖለቲካ ሥልጣን በማዳከም ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚያደርጉትን ጥረት የሚቃወሙ ጥቂት የትግራይ ጉልተኛ መሣፍንቶችና በኤርትራ የነበሩ የኢጣሊያ ምንደኞች የተለያዩ ችግሮችና ብሶቶች ያሏቸውን ደሃ የትግራይ ገበሬዎችን በማሳሳት የቀሰቀሱትን የመገንጠል አመፅ፣ የዛሬዎቹ ወያኔዎች በአገራችን ታሪክ የመጀመሪያው ፀረ-ፊውዳል የትግራይ ገበሬዎች አብዮት ነበር ይሉታል። ለዚህ እኩይ ተግባር ተቀስቅሰውና ተደልለው የጥፋት ሰለባ የሆኑት የትግራይ ክልል የሕብረተሰብ ክፍሎች ከትግራይ ክፍለ ሃገር በጣም ጥቂቱ በመሆናቸውና አብዛኛው ለእናት አገሩ አንድነትና ሰላም በመሰለፉ አደገኛውን ሴራ ባጭሩ ለመቅጨት ተቻለ።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በዚህ የጊዜ ክልል በተመሳሳይ ሁኔታ ሶማሊያ የነበሩ የእንግሊዝ ወታደራዊ የበላይ ሹማምንቶችና የሲቪሉም ፖለቲከኞች ኢትዮጵያን ለመበቀል ታላቋ ሶማሊያ የተባለውን ምኞታዊ መፈክር ፈጠሩ። ጥቂትና ግብዝ ባላባቶች በመደለል ቀስቅሰው ያቀጣጠሉትን የኦጋዴን ክልል ከሶማሊያ በመቀላቀል ከኢትዮጵያ የመገንጠል ዓላማ ያለው አመፃዊ ውጊያ ሰሜን ኦጋዴን ያለውን ሕዝብ አምሶና አተራምሶ ወደ ደጋማው ክልል በማምራት ጉርሱም አውራጃ ሲደርስ የማህል ሃገር ኢትዮጵያ አርበኞች ዘምተው በአጭሩ ቀጩት።

እንግሊዞች በርዳታ ስም ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ ደባዎችን በሚፈጽሙበት ጊዜ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አላበቃም፤ የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ፈርሷል፤ አዲሱ የዛሬውም አልተቋቋመም፤ የእንግሊዝን የጦር ኃይል የሚመሩ መኮንኖች በያንስ በአብዛኛው በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በአጠቃላዩ በእስያ አህጉራት ማንም የማይጠይቃቸውና የማይጋፋቸው ፍፁም ፈላጭ ቆራጭ ኃይል ነበሩ። በጦርነቱ የቃል ኪዳን አገሮችን ሠራዊቶች አሰላለፍ በተመለከተ፣ የመጨረሻ ግባቸውን የጀርመንን ርዕሰ ከተማ በርሊንን አድርገው ከሁለት አቅጣጫ ወደ ጀርመን የሚንደረደሩት መጠነ ሰፊ አጥቂ ሠራዊቶች ሁለት ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው የሰሜን አሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የካናዳ፣ የአውስትራሊያ፣ የኒውዚላንድ፣ የፈረንሳይና የፖላንድ ስደተኞችን ያካተተና በአሜሪካዊው ጄነራል አይዘንሃወር የበላይ መሪነት የተመራው ሕብረብሔር ሠራዊት ነበር።

ይህ ሠራዊት በቅድሚያ በጀርመናዊው በማርሻል ሮሜል የሚመራውን የጀርመን የአፍሪካ ኮር ከሰሜን አፍሪካ በማስወጣት፣ ቀጥሎም ፈረንሳይን ነፃ የማውጣት ተግባሩን ከከናወነ በኋላ በተቀረው የምዕራብ አውሮፓ ክልል በተለይም በኢጣሊያ ውስጥ የመሸጉትን የኢጣሊያና የጀርመን ሠራዊቶች ደምስሶ ንቅናቄውን በመቀጠል በርሊንን የመያዝ ግዳጅ የተሰጠው ነው። ሁለተኛው፣ በሩሲያዊው ማርሻል ዡኮቭ የተመራው የሶቭየት ሕብረት ቀይ ሠራዊት ከሩሲያ ተነስቶ በምሥራቅ አውሮፓ የነበረውን ዋናውን የጀርመንን ሠራዊት በመምታት አካባቢውን እያጸዳ ወደ ጀርመን በማምራት በርሊንን የመቆጣጠር ግዳጅ የተሰጠው አንድ ወጥ ሠራዊት ነው።

ከእነዚህ ሌላ ግን ስትራቴጂያዊ የዓላማና የተግባር ቅንጅት ያላቸውና ግዳጃቸው የተለያዩ ሁለት ሠራዊቶች ነበሩ። አንደኛው አብዛኛውን የፓስፊክ ውቅያኖስ ክልሎች፣ የባሕር መንገዶችና የሩቅ ምሥራቅ አገሮችን የወረረውን የጃፓንን ወራሪ ሠራዊት በያለበት እየመታ አካባቢውን በማጽዳት የመጨረሻ ግቡ ጃፓንን ራሱ የመቆጣጠር ግዳጅ የተሰጠውና በጄኔራል ዳግላስ ማካርተር የተመራው የሰሜን አሜሪካ አንድ ወጥ ሠራዊት ሲሆን፣ ሁለተኛውና ከዚህ ሠራዊት ጋር ተመሳሳይ ግብር ግን የተለየ ግብ ያለው በሰሜን አፍሪካ፣ ማዕከላዊ ምሥራቅ፣ በአፍሪካ ቀንድ፣ በቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ የባሕር መንገድ ለወገን ሠራዊት ለተቀረውም ሰላማዊ ተግባርና አገልግሎት ክፍት አድርጎ በአስተማማኝ ሁኔታ በማስከበር የእንግሊዝ መንግሥት፣ በኒውዚላንድ፣ በአውስትራልያና በደቡብ እስያ ያለውን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ግዳጁ የሆነው የእንግሊዝ ግበረ ኃይል ነበር።

በባለ ቃል ኪዳን አገሮች ሠራዊቶች መካከል የውጊያ እቅድን አስመልክቶ ስለ ነበረው ሕብረትና ቅንጅት ለጊዜው የሶቭየት ሕብረትን ቀይ ሠራዊትና እንዲሁም በፓስፊክ ውቅያኖስ አቅጣጫ የዘመተውን የሰሜን አሜሪካ ሠራዊት ወደ ጎን ትተን የተቀሩትን ከእንግሊዝና ከደቡብ አፍሪካ በመንደርደር በተቀረው አፍሪካ፣ በሜድትራኒያን ባሕርና በምዕራብ አውሮፓ ለሚደረገው ዘመቻ የተሰለፉትን ሕብረብሔር ሠራዊቶች ስንመለከት በአንድ ወታደራዊ እቅድ ማዕቀፍ ውስጥ በተቀነባበረ ሁኔታ የሚመሩ ነበሩ።

የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት የተካፈሉ አገሮችና ሠራዊቶቻቸውን እስከ ዓላማና ተግባራቸው በአጭሩም ቢሆን መዳሰስ ያስፈለገበት ምክንያት የውጊያ እቅዳቸውንና አፈፃፀሙንም ስንገመግምና የእንግሊዝ ጦር ለኢትዮጵያ ትግል ድጋፍ ለመስጠት መጣ ስንል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ሲባል የተለየ እቅድ ተሰርቶለትና የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት የተካናወነ ውጊያ ሳይሆን የጦርነቱ የጦር ጫፍ ከየአቅጣጫው ወደ ጀርመንና ወደ ጃፓን ምድር እያመራ ባለበት ጊዜ ከኋላ በአፍሪካ ቀንድ ወይም በኢትዮጵያ የጠላት ቅሪት ትቶ ላለመሄድ የግድ የቃርሚያ ውጊያ መደረግ ስለነበረበት የተደረገ ወታደራዊ ጽያጄ ተግባርና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት እቅድ አካል መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ መላው ሶማሊያ እንኳን ቢቀር ኤርትራንና ኦጋዴን ወዲያው ለኢትዮጵያ መንግሥት ለመመለስ የእንግሊዝ መንግሥት የሚሳነው ነገር አልነበረም። እነዚህ ክልሎች ለኢትዮጵያ እንዳይመለሱ የጠመመው የእንግሊዝ መንግሥት ሳይሆን ወደ አፍሪካ የተላኩት የጦር መኮንኖች ናቸው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው፣ አፄ ኃይለሥላሴ ከነፃነት በኋላ በግብጽ በኤሌክሳንደሪያ ወደብ መርከብ ላይ የአሜሪካንን ፕሬዝዳንት ሩዝቬልትን በተገናኙበት ጊዜ፣ በአጋጣሚ እንደዚሁ የእንግሊዙን ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችልንም በዚያው ተገናኝተው የኦጋዴን ክልል ጉዳይ ሲያነሱለት መኮንኖቹ እንደሚሉት የኦጋዴን ክልል ላልተጠናቀቀው የዓለም ጦርነት ለእንግሊዝ መንግሥት እጅግ ጠቃሚነት ያለው መሆኑ ቀርቶ ኦጋዴን የሚባለው ሃገር ከነስሙ ምን እንደሆነና የትስ እንደሚገኝ ባለማወቁ በንግግሩ ላይ አብረው ወደ ነበሩት የሥራ ጓደኞቹ ፊቱን አዙሮ "እኝህ ሰው ኦጋዴን የሚሉት ነገር ምንድን ነው? የትስ ነው የሚገኘው?" ብሎ መጠየቁና በአጋጣሚውም መኮንኖቹ መጋለጣቸው ነው። ከታሪክ እንደተረዳነው በአጠቃላይ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ዓለምን በተቀራመቱበትና በገዙበት ረጅም ጊዜያቶችና በኋላም በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች ዘመን የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም ቅኝ ግዛቶች በተመለከተ ብዙና ታላላቅ ውሳኔዎች ይሰጡ የነበሩት በማዕከላዊ አመራሩ ከለንደን ሳይሆን ፈላጭ ቆራጭ ሆነው በዓለም ላይ ሲዘባነኑ በኖሩትና የቅኝ ግዛት ኑሮ በእጅጉ በጣማቸው ጄኔራሎቻቸው ነበር።

ጊዜው የዓለም ጦርነት የሚካሄድበት በመሆኑና የእንግሊዞች የቅኝ ግዛት በጣም ሰፊ ከመሆኑም በላይ በሰፊው የቅኝ ግዛት ክልሎች የተሰማሩት የጦር መኮንኖቻቸው መረን ለቀቅ ያለ መንግሥታቸው እውቀትና መንግሥታቸውንም በማሳሳት የግል ጥቅማቸውን፣ ጊዜያዊ ፍላጎትና ምቾታቸውን በሚያመቻችላቸው ሁኔታ የብዙ ታዳጊ ሃገር ሕዝቦችን እድል ሊወስኑ መኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ አዲሱንና ነፃውን መንግሥት መልሶ ለማቋቋም ይደረግ የነበረውን ጥረት እጅግ አዳጋች ያደረጉት ምክንያቶች ለመከላከያ ሠራዊቱና ለሰላማዊ የመንግሥት ሠራተኛ ደሞዝና ጠቅላላ ለመንግሥቱ ሥራ ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ ችግር፣ ሥራውን የሚመራ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የእንግሊዝ ወታደራዊ ቅኝ ገዥዎች ሥልጣናቸውን ለማሳየት የሚፈፅሙት ሻጥርና እብሪት፣ በትግራይ በኦጋዴንና በምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም በአዳልና ኢሳ አውራጃ ከ1933 እስከ 1937 ዓ.ም ድረስ በነበሩበት የመጀመሪያዎቹ የሽግግር ዓመታቶች የተከሰቱት የትጥቅ አመፆች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከእነዚህ ችግሮች ሌላ በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በስደተኛ፣ በአርበኛ፣ በባንዳዎች ጎራና በእነዚህ መካከል ባለው መሃል ሰፋሪ የሕብረተሰብ ክፍል የተከፋፈለበት፣ መረጋጋት ያልነበረበትና ውዥንብር የሰፈነበት ሁኔታ ነበር። ሆኖም እነዚህ ሁሉ ችግሮች ቢከሰቱም በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ላይ በተገኘው የጦር ሜዳ ድልና ድሉም በአስገኘው ነፃነት በሕዝቡ ህሊና የሰረጸውን የደስታ ስሜት ሊደፍቁት አልቻሉም።

ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ አፄ ኃይለሥላሴ በእንደራሴነት ዘመናቸውና ከነገሡም በኋላ ሁሉንም ነገር ጠቅልለው በመያዛቸው መሣፍንቶቻቸውና መኳንንቶቻቸው ጠቅል የተባለውን የፈረስ ስም በሰጧቸው ጊዜ የነበራቸው ድጋፍ ሲገመገም ጥሩ ነው የሚባል አልነበረም። ዋና የኃይላቸው ምንጭና ማህበራዊ መሰረታቸው አባታቸው ልዑል ራስ መኮንን ያደራጁት በመጠኑ ብዛትና በይዘቱ ጥራት የነበረው የሐረርጌው ጦር፣ የክብር ዘበኛው ሠራዊት፣ የሸዋ ካህናት፣ የነጋዴው ሕብረተሰብ፣ የአገሪቱ ምሁር፣ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የውጭ ሃገር ሰዎችና የዲፕሎማቲክ ኮር ድጋፍ ነበር።

የየክልሉን መሣፍንቶች የፖለቲካ ሥልጣን በማዳከም ማዕከላዊ መንግሥትን ለማጠናከር ያደርጉ የነበረው ጥረት በየክልሉ መሣፍንቶች ዘንድ የተወደደና የሚደገፍ አልነበረም። ከዚህ ሌላ በቅድሚያ ልጅ እያሱን፣ በኋላም ንግሥት ዘውዲቱን ከሥልጣን ለማስወገድ ባደረጉት ትግል ታላቅ ቅራኔ ውስጥ የገቡ ብቻ ሳይሆን ከወሎና ከጎንደር ሕዝብ ጋር ደም ተቃብተዋል። በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች በሰሜንም ሆነ በደቡብ ሕዝብ ዘንድ የተወደዱና አስተማማኝ ድጋፍ የነበራቸው ሰው ናቸው ለማለት ያስቸግራል። ከስደት ተመልሰው በመንበረ መንግሥታቸው ላይ በተቀመጡበት በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ሕዝብ ለሳቸው ያለውን አስተያየትና የሰጣቸውን ድጋፍ ያስተዋሉና የገመገሙ “ሳይደግስ አይጣላም” የሚለውን አነጋገር በትክክል ለአፄ ኃይለሥላሴ ገጥሟል ስርቷልም ይላሉ።

በአምስት ዓመታት በአርበኛነቱ ተጋድሎ በዱር በገደል ሲንገላቱ የነበሩት፣ በገዛ አገራቸው ስደተኛ የሆኑት፣ በፋሽስቶች የተረገጡትና አያሌ ወገኖቻቸውን ያጡት፣ ነፃነት የተጠማውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ “አፄ ኃይለሥላሴ ለአንተ ነፃነት ሲሉ አገራቸውን ጥለው ተሰደው በዓለም መንግሥታት ሸንጎ ተሟግተው፣ የታላቋ እንግሊዝ ረዳት ጦር ይዘውልህ መጡ” እየተባሉ ስለተነገራቸው “ታላቅ ባለውለታችን ንጉሥ” እና “ነፃ አውጪ ንጉሥ” ከማለትም አልፎው “ፀሃዩ ንጉሥ፣ ፀሃይ አወጣልን” በማለት ከዳር እስከ ዳር ድጋፉን ሰጧቸዋል።

ኢጣሊያኖች እየተዋጉ በአምስት ዓመት በኢትዮጵያ ያለሙትንና የገነቡትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተመለከተ ባደረበት ቅናትና በተሰረጸበት ማህበራዊ ንቃት ለመማር፣ ለመሻሻል፣ ለመሥራትና አገሩን ለመገንባት በጣም የተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን በጣም የጓጓ ሕዝብ ነበር። በጦርነቱ በልማቱና በግንባታው ተሳታፊ ስለነበረ በተለያዩ የልማት፣ የግንባታና የሙያ መስኮች በተለያየ ደረጃ የማይናቅ እውቀትና ልምድ የቀሰሙ ኢትዮጵያውያን ቁጥር የሚናቅ አልነበረም።

መልሶ የሚቋቋመው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት እንደ አዲስ ጎጆ ወጪ ሳይቸገር ከጠላት ወረራ በፊት ምንም ነገር በሌለባት ሃገር፣ የሌሎና ዘመናዊ መሠረተ ልማቶችን፣ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋሞችንና ድርጅቶችን ከእንግሊዞቹ ቅርምት የተረፈውን ከኢጣሊያኖች ተረክቧል።

ፋሽስቶች መጠኑ እስከ ዛሬ በውል ያልታወቀ ወደ አንድ ትውልድ ቁጥር የሚጠጋ ወገኖችንን መፍጀት ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የሙሶሎኒ ሕይወት በአጭሩ ተቀጨ እንጂ ኢትዮጵያን ሁለተኛዋ ኢጣሊያ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ታጋዩን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማጥፋት አቅዶ ነበር።

በዚህ አጋጣሚ ሳይገለጽ መታለፍ የሌለበት ብቻ ሳይሆን ሊጤን የሚገባው ነገር በደኖቻችን ላይ ያደረሰው ሊተካ የማይችል ታላቅ ጥፋት ነው። የአገራችን ገበሬ በነጋ በጠባ ዛቢያና መጥረብያውን በትከሻው አንግቦ ከቤቱ እየወጣ የማይተካውን ደን ሲጨፈጭፍ ቢኖርም በአብዮቱ ወቅት በግብርና ሚኒስቴር የደን ልማትና የዱር አራዊት ጥበቃ መምሪያ ባደረገው የሃገር አቀፍ ሴሚናር ላይ ከስዊድን የግብርና ባለሙያዎች ጋር በትብብር ያቀረበው ጥናት ያስረዳው፣ በ20ኛው ምዕተ-ዓመት መባቻ ላይ ኢትዮጵያ ምድር ስልሳ በመቶ የሚሆነው ችምችም ባሉ ደኖች የተሸፈነ እንደነበረ ነው።

በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አውቶማቲክ መጋዝ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በኢጣሊያኖች ከወራሪው ሠራዊት ጋር ነው። ተጠቃሹ የግብርና ሚኒስቴር ጥናት "ፀረ-ደን ሠራዊቱን ዘመናዊ መጋዝ በማስታጠቅ አዝምቶ በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሃያ በመቶ የሚሆነውን የአገራችንን የደን ሀብት በመጠራረግ እንዳልነበረ አደረገው" ይላል።

ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያ በቆዩበት ጊዜ ውስጥ የአገራቸውን የኢጣሊያን ሕዝብና ኢንዱስትሪዎች ፍላጎትን ፍጆት አሟልተው ከኢትዮጵያ ደኖች ለልዩ ልዩ የግንባታ ተግባሮች፣ በጥሬ እቃነት ለወረቀት ኢንዱስትሪዎች ወዘተ የሚያስፈልጉ የጥድ፣ የዝግባ፣ የወርካና የዋንዛ ወዘተ የዛፍ ግንዶችን፣ የቡና ምርት ለአውሮፓ ገበያዎች አቅራቢ ሆነው ነበረ። በዚህ አጋጣሚ ሌላው መታወቅ ያለበት በጣም አሳዛኝ ነገር፣ የአገራቸውን ጥፋት ከኢጣሊያኖች የተማሩ የኢትዮጵያ ትልቶቻችና የመሬት ከበርቴዎች በሸዋ፣ በሲዳሞ፣ በከፋ፣ በወለጋ፣ በባሌና በሐረርጌ ኢጣሊያኖች አቋቁመዋቸው ያገሪቱን ምርጥ የዛፍ ዘሮች እየቆረጡ ለውጭ ገበያ ሲያቀርቡ የነበሩ ድርጅቶችን ከነመሣሪያቸውና በድርጅቱ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ኢጣሊያውያንን ተረክበው ባካሄዱት የጥፋት ዘመቻ በሰላሳ ዓመት ውስጥ ከመቶ ሠላሳ በላይ ጠርገው በማጥፋታቸው በአብዮታችን ወቅት የተረከብነው አራት በመቶ ብቻ እንደነበረ የተጠቀሰው ጥናት ያስረዳል።

በሰው ሕይወትና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የደረሰው ጥፋት ሲነገር ለጆሮ የሚቀፍ ቢሆንም የኢጣሊያኖችን ሌላውን ግብራቸውን ደግሞ በጥሞና ላስተዋለ በአገራችን ያከናወኑትን ልማትና ግንባታ እኛ ለመካድ ብንፈልግ ሥራቸው ይመሰክራል። በእኛ ትልታዊ ገዥ መደብ አመራር፣ ፈጠራ፣ የማቀድና የማስፈጸም ችሎታና ቴክኖክራሲያዊ ይሞከር ቢባል

በአምስት ዓመት ቀርቶ በሀምሳ ዓመታት ይቻል ነበር ብሎ ለማሰብ በጣም ያስቸግራል። የዚህን እውነታ ለመረዳት ቢያስፈልግ ኢጣሊያኖች በአምስት ዓመት ገንብተው ያስረከቡንን ህንፃዎች ላለፉት ሀምሳ ዓመታት እየጠገንን ለመገልገል ተስኖን በመፈራረስ የጠፉትንና በመፈራረስም ላይ ያሉትን የሚያሳየውን አሳዛኝና አሳፋሪ ትርዒት ሐረርጌ፣ ከፋ፣ ወሎ፣ ጎንደር፣ ትግራይና ኤርትራ ሄዶ መመልከት ይቻላል።

ከዚህ በላይ በጠቃቀስኳቸው የጠላት ስራቶችና ቅሪቶች ተጠቅመው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ወታደራዊ ተቋሞችንና አልግሎቶችን እንደገና ከመወጠን ጋር የእንግሊዞችን ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ በማንሳት ኢትዮጵያን የአዲሱ ዓለም መንግሥታት ማህበር መሥራች አባል ለማድረግ መቻሉም ታላቅ እምርታ ነው። በተለይም የአጋዴን ብሎም የኤርትራን ክፍለ ሃገር ሕዝብ ከወገኑ ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መልሶ መቀላቀሉ፣ አፍሪካውያን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለትግል ታሪኩ ባላቸው አክብሮት አዲስ አበባን የድርጅታቸው ቋሚ ጽሕፈት ቤት መኖሪያ አድርገው በመረጡ ጊዜ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ኃላፊነቱን ወስዶ የአገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸትና ከማዘጋጀት ባሻገር በንጉሡ ነገሥቱ ሊቀመንበርነትና ኢትዮጵያዊ በሆነ ጊዜያዊ ኃፊነት የድርጅቱን መሥራች የመሪዎች ጉባዔ በተሳካ ሁኔታ ማስተናገድ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከተከናወኑት ገንቢ ተግባሮች ሁሉ የላቀ የፖለቲካ ክንውን በመሆኑ የሚያስመሰግናቸው ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ማህበር መሥራች አባል ከመሆናችን ጋር ተያይዞ የመጣ ድርጅቱ ላይ አፄ ኃይለሥላሴ የነበራቸው እምነት አሁንም ለቀድሞው ሊግ ከነበራቸው እምነት የተለየ አልነበረም። እርሳቸው አንዳንድ ወቅታዊ ክስተቶችን ፍፁምና ዘላለማዊ አድርጎ የመውሰድ ወይም የማመን ልዩ ፀባይ አላቸው። በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ወታደራዊ ቅኝ ገዥ መኮንኖች ሥልጣናቸውን ለመውረስና ንጉሠ ነገሥታዊ ክብራቸውን ለማኮሰስ ዱጅቱ የተፈታተኗቸው በመሆኑ በተሰማቸው ብሶት ከእነሱ ለአንዴና ለመጨረሻ ለመገላገል ሲሉ የሰሜን አሜሪካንን መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት አጋርና በግላቸውም ልባዊ ወዳጃቸው አድርገው በማሰብ የሙጥኝ አሉ።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ላይ ከሰፈሩት አያሌ ለጆሮ የሚጥሙ ኃይለ ቃሎች አንዱ "የማህበሩ አባል አገሮች የጋራ ደህንነት በፍፁም እኩልነት ይከበራል" የሚለውን ቃል የተባበሩት መንግሥታት አባል የሆነን መንግሥት ብርቱም ሆነ ደካማ፣ ደሃም ሆነ ሌላ ጸጋ ሌላው አባል ኃይል አለኝ ብሎ ቢያጠቃው በዚህ የሕግ አንቀጽ መሰረት ማህበሩ ያድነዋል ወይም ይጠብቀዋል የሚል ፍጹም የሆነ እምነት ነበራቸው። በሕጉ ማመን ብቻ ሳይሆን ቃሉንም ከመውደዳቸው የተነሳ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ንግግር ባደረጉ ቁጥር አብዛኛውን ጊዜ እንደ ጸሎት ሲደጋግሙት ይደመጡ ነበር።

ሌላው አስገራሚ ነገር በሰሜን አሜሪካ መንግሥት ላይ ያላቸው ፅኑ እምነት ነው። አሜሪካኖችን ማመን ብቻ ሳይሆን ከማፍቀራቸውም የተነሳ ምንም ነገር ይሁን አሜሪካኖች ያሉት ሁሉ መደመጥ አለበት፤ አሜሪካኖች የፈለጉት ሁሉ መፈፀም አለበት የሚሉ ነበሩ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ከነበሩት ከአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እና ከፀሃፊ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስ ጋር ብዙ ጊዜ ያለመግባባት የሚፈጠረው በዚህ አመለካከታቸው ነበር። በዚህ አስተያየታቸው ይመስላል የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና የዓለም ማህበራዊ ኃይሎች የመደብና የርዕዮተ ዓለም ትግል ነፀብራቅ በሆነው ወታደራዊ ቀውስ ውስጥ ገብተው መናጆ በመሆን በሰሜን አሜሪካ ወራሪ ሠራዊት በግፍና በእብሪት የተወረረው

የታዳጊው ዓለም አባልና አካል የሆነው የኮሪያ ሕዝብ በተከላካይነት ለነፃነቱ፣ ለአንድነቱና ለማህበራዊ እድገቱ የሚያደርገውን ተገቢና ሕጋዊ ትግል ለማሰብና ለማመዛዘን ተስኗቸው ከወራሪው ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር ወግነው ለመውረር አንድ ሻለቃ እግረኛ ጦር በመላክ ጦርነቱ ውስጥ የተዘፈቁት።

እራሷ ለነፃነቷና ለአንድነቷ በመታገል ላይ ያለች ሃገር በመሆኗ የሞራልና የመርህ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ውሎ አድሮ ለህልውናዋና ለአንድነቷ እጅግ አደገኛ ጠንቅ በመሆኑ ኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት ውስጥ በፍጹም መካተት አልነበረባትም።

ለወጉ የገለልተኛ አገሮች መንግሥታት ንቅናቄ መሥራች አባል ሆነናል። በመሪያችን አሜሪካንን አፍቃሪነት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተለጣፊ የተሰኘ ስም የተሰጠን ብቻ ሳንሆን ገለልተኛም ስላልነበርን በገለልተኝነት ንቅናቄ፣ መርሆ ያምናሉ ብሎ ከቁም ነገር የሚፅፈን ሃገር አልነበረም።

ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያ በወረረችበት ጊዜ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከኢጣሊያን ከተቀሩትም የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር አብሮ የኢጣሊያ ወረራ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ለመርዳት በተጠቂዋ ኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብ ከማድረጉም ሌላ አፄ ኃይለሥላሴ ከእንግሊዝ ወደ አሜሪካ ለመግባት ሲጠይቁ እስከ መጨረሻው ሳይፈቅድላቸው ቀርቷል።

አሜሪካንን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመጎብኘት የቻሉት በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በ1940 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነበር። ይህ ጉብኝት በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የተደከመበት፣ ለብዙ ጊዜ የተጠበቀና በእንግሊዞች ላይ የተገኘ ድል ሆኖ ከመታዩቱም በላይ ለኢትዮጵያ እድገት በር የሚከፍት ሆኖ ተገምቷል።

ከጊዜው አንፃር ከኢትዮጵያ ድህነትና ውስብስብ ችግሮች አኳያ አዲስ በር ከፋች መስሎ ቢታይም አያስደንቅም። በጉብኝቱ ጊዜ በዋሽንግተን በነጩ የአሜሪካኖች ቤተ መንግሥት ውስጥ በጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ለአብዛኛው መልስ የሰጡት እሳቸው ሳይሆኑ አስተርጓሚያቸው የነበሩት ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ነበሩ ለማለት ያስደፍራል።

ይህንን ለማለት ካስገደዱኝ ብዙ ጥያቄዎች ሁለቱን ብቻ ላቅርብ። አንዲት አሜሪካዊት ጋዜጠኛ “በሃገርዎ ምን አይነት የመጓጓዣ አገልግሎቶች እንዳሉ ሊገልፁልኝ ፈቃድዎ ነው?” ስትል ጠየቀች። ሴትየዋ ቀደም ብላ ኢትዮጵያን የጎበኘች ወይም ስለ ኢትዮጵያ ያነበበች እና ጥያቄውም ለማወቅ የቀረበ ቅን ጥያቄ ሳይሆን አሽሙር አዘል ነበር። ንጉሡም ጥያቄውን ትንሽም ሳያስቡበት “ጥቂት ካሚዮኖች ቢኖሩንም ዋናዎቹ መጓጓዣዎቻችን የጋማ ከብቶች ማለትም እህያ፣ በቅሎና ፈረሶች በብዛት አሉን” ብለው በአማርኛ የተናገሩትን ልጅ እንዳልካቸው ሲተረጉሙ፣ “እያደገ በመሄድ ላይ ላለው ኢኮኖሚያችንና እንዲሁም ሕዝባችን ፍላጎት በቂ ነው ባንልም፣ የየብስ፣ የአየርና የባሕር መጓጓዣ አገልግሎቶች አሉን” በማለት ለጋዜጠኛዋ በእንግሊዝኛ መለሱ። ድንቅ መልስ!

በመጨረሻ ሌላው ጋዜጠኛ “ከጥቁር ሕዝብ መሪዎች በአሜሪካ ነጩ ቤተመንግሥት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እርስዎ ለመግባት በመቻልዎ ምን ይሰማዎታል?” የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረበላቸው። ጥያቄው ብርቱ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነበር። በዚያን ጊዜ ከነበራቸው ከፖለቲካ ንቃት የተነሳ የረባ መልስ የሰጡ መስሏቸው ወይም አውቀው ከኃላፊነት ስሜት ጉድለት፣ “እኛ ከንጉሥ ሰለሞን ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ቤተሰብ የምንወለድ አይሁድ ነን እንጂ ጥቁር አይደለንም” ብለው መለሱ። ልጅ እንዳልካቸው ቀደም ብለው ሲያደርጉት እንደነበረው ሁሉ ሲሆን ፍፁም ለውጠው ተገቢ መልስ መስጠት ባይቻላቸውም በመጠኑ

አለዝበው መተርጎም ሲገባቸው ንጉሡን ፈርተው ወይም የልጅ ልጅ ናቸውና እሳቸውም አይሁድ ነኝ ብለው በማመን በንጉሡ መልስ ተስማምተው እንደሆነ አይታወቅም ንጉሡ የሰጡትን መልስ እንዳለ ጥሬውን አስቀመጡት። ይህንን የሰሙ አፍሪካዊያን፣ የካሪቢያን ጥቁሮች በተለይም መላው አፍሪካ አሜሪካዊያን ከዚያ በፊት ለረጅም ዘመን "የጥቁር ሕዝብ ተስፋ፣ የጥቁር ሕዝብ አንጸባራቂ ኮከብ፣ የነፃነት አርዓያ" ይሉን የነበሩ ሁሉ ተገፈርና በማዘን በተለይ አሜሪካውያኑ ያገኙትን ኢትዮጵያዊ ሁሉ "ንጉሣችሁ ጥቁር አይደለሁም አለ፣ አንተ ጥቁር ነኝ ብለህ ታምናለህን?" እያሉ ያቀረቡልን ለነበረው ጥያቄ በበኩሌ ለማስተባበል ሞክሬ መልሱ እኔኑ ስላሳፈረኝ ጥያቄው ሲነሳ ፊቴን አዙሬ መሸሽ እመርጥ ነበር። መሸሹም ስለታከተኝ እንዲህ አይነት ጥያቄ ሲቀርብልኝ እስቲ ተመልከተኝ ምን መስዬ እታይሀለሁ በማለት መልሼ አፈጥና እቆጣ ነበር።

ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ የተከታተሉ ብቻ ሳይሆኑ ዜናው በመዛመቱ ወሬውን እሱ ሲባል የሰሙ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ሕዝቦች ሁሉ ለማለት ያስደፍራል ጥቁር አይሁዶች የሚል ስም በመስጠት ከአይሁዶች ቀጥሎ ሁለተኛ ጠላታቸው አድርገው ይመለከቱን ጀመር። ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔርያሊዝም ወገንን የኮሪያን ሕዝብ በመውጋታችን መላው ሕብረተሰባዊ አገሮች፣ መላው የዓለም ተራማጅ ኃይሎች፣ የሠራተኛ ንቅናቄዎች፣ ዲሞክራቲክ መንግሥታትና ድርጅቶች በአፄ ኃይለሥላሴ የምትመራዋ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አብዮት ብቻ ሳይሆን ለዓለም ማህበራዊ ዕድገት ጠንቅ ነች የሚል ስም የተሰጣትና የተራማጁ ዓለም ፍፁም የተገለለች ሃገር መሆን ብቻ ሳይሆን የእነዚህ ሁሉ የጥቃት ኢላማ ሆነች።

ከማንም ቀድሞ የሰለጠነውንና በልዕለ ኃያልነትም እጅግ ገናና የነበረውን ጥንታዊውን የግሪክ መንግሥት ስፍራ በመውረስ በዓለም ላይ በተንሰራፉት ሰፋፊ ቅኝ ግዛቶቹ፣ በግዙፍ የመከላከያ ሠራዊቱ በዘረፋና በገፈፋ በተሰበሰበ ሀብቱ አቻ ያልነበረው የሮም ቄሳሮች መንግሥት እንደነበር የታወቀ ነው።

ከሮም ቄሳሮች ውድቀት በኋላ በተለያዩ ጊዜያቶች፣ ከተለያዩ አገሮችና አህጉሮች በፈረቃ እየተነሱ በመግነን ከፊሎቹ በሚኖሩበት አካባቢ የተቀሩት ከዛም በሰፋና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ላይ የተስፋፉና በተራቸው ተመልሰው የከሰሙ መንግሥታት እንዳሉ ከታሪክ ማህደር እንረዳለን። ከመካከለኛው ዘመን መገባደጃና በተለይም ከካፒታሊስት ሥልተ ምርት መፋፋትና ዕርዮት መስፋፋት ጋር በተሳሰረ ሁኔታ እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ድረስ ከሞላ ጎደል ዓለምን የተቆጣጠረ ሌላው ወደር አልባ ልዕለ ሃያል የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም ነበር።

እያሌ አብዮታዊ ምሁሮች የኢምፔርያሊዝም ጭንቅላት እንግሊዞች ናቸው ይላሉ። ይህ አባባል ከእውነት የራቀና ያለ ምክንያት የተነገረ አይደለም። እንግሊዞች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን በአፍራሽም ሆነ በገንቢ ዓለማችንንም ለውጠዋል። ለረጅም ዘመን እረግጠው ሲገዟቸውና ሲመዘብሯቸው በነበሩት ሁለቱ ታላላቅ አህጉሮች በእስያና በአፍሪካ ሕዝብ ላይ የፈጠሩትን አፍራሽም ሆነ ገንቢ ተፅዕኖ የማመዛዘኑን ፍርድ ለአንባቢ ብተው የተቀሩት አዲሶቹ አህጉራት ማዕከላዊው ሰሜን አሜሪካና አውስትራሊያ የእንግሊዝ ፍጥሮች ናቸው።

የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም በዓለም ላይ እንደዚያ መንሰራፋቱ ያከተመበትን የምዕራቡን ዓለም ምህዋር ማሽከርከሩ ቀርቶ የመሪነቱን ስፍራ ለሰሜን አሜሪካ ኢምፔርያሊዝም ማስረከብ የተገደደው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላና ቅኝ ግዛቶቹን እያጣ በሄደበት በ20ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ የጊዜ ክልል ውስጥ ነው። የእንግሊዝ ቅኝ

የነበረው ሰሜን አሜሪካ በጣም ባጠረ ጊዜ ማለትም ሁለት መቶ ዓመት እንኳን ባልሆነ ጊዜ ውስጥ በሚያስደንቅ ሕዝቡ አገሩን አልምቶና ገንብቶ በከፍተኛ የእድገት እርከን ላይ ሊገኝ የቻለው አገሪቷ ከታደለችው የተፈጥሮ ሀብት ሌላ ከአውሮፓ በሄደ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ቴክኖሎጂ፣ ካፒታልና ከአፍሪካ በሄደ ነፃ የባርያ ጉልበት ነበር።

ከዚህ ሌላ ለአሜሪካ አጠቃላይ የተፋጠነ እድገት ዋናውን አመቺ ሁኔታ የፈጠረው መንግሥቱ ህልውናውን ከመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ከውጪ ጥቃትና ወረራ ያልተሰነዘረበት፣ በአካባቢውም የእድገት አደናቃፊ የሆነ ውጊያ ወይም የተፈጥሮ ችግር ባልተከሰተበት፣ በተረጋጋና ሰላም በሰፈነበት ሁኔታ መኖሩ ነው። በሰሜን አሜሪካ ታሪክ የሰላም መታወክ ችግር ደረሰ ቢባል አፍሪካ አሜሪካዊያንን አስመልክቶ በደቡብና በሰሜን ሕዝብ መካከል ለጥቂት ዓመታት የተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነትና በሁለኛው የዓለም ጦርነት አጥቢያ የጃፓን ወታደራዊ መንግሥት በፐርል ወደብ ላይ የፈጸመው ወታደራዊ ትንኮሳ ብቻ ነው።

ከሜክሲኮ ጋር የተደረገው ውጊያም እንዲሁ ብዙ ጊዜ ያልወሰደ ከመሆኑም በላይ በሜክሲኮ ኪሳራ አሜሪካ በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበት እንጂ በሰውም ሆነ በቁሳቁስ በብሶት ደረጃ የሚነገርለት ጉዳት ያልደረሰና የአሜካንን የእድገት እንቅስቃሴ መግታት ቀርቶ ያደናቀፈ አልነበረም። አውሮፓውያን ከዓለም ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ ከመሆናቸው ሌላ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝት በእነዚህም መሣሪያነት በተካሄደው ልማትና ግንባታ ዓለምን በመቅደም ብዙ ዘመናት ያስመዘገቡ ቢሆንም ከመሬት ጥበትና ከተፈጥሮ ሀብት እጥረት ሌላ ታሪካቸውን በሙሉ ማለት ይቻላል ለሰላም አልታደሉም።

የቅርቡና የመጨረሻው የአውሮፓ እጅግ አስከፊው ጦርነት የሌሎቹንም አህጉራት ሕዝቦች ያካተተውና መጠኑን በገንዘብ ለመተመን ያዳገተ፣ አያሌ ሀብትና ንብረት፣ የሰው ልጅ ፈጠራና ሥልጣኔ ያወደመና ከ70 ሚሊዮን በላይ የሰው ሕይወት የጠፋበት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ነው። አሜሪካ ብዙ ስታመንታና እግሯን ስትጎትት ቆይታ ጦርነቱ ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ የጦርነቱ ተሳታፊ በመሆን በሰው መጠንና በትጥቅ ጥራት የጎላ አስተዋፅዖ በማድረጓ የምዕራቡን መጠን ሰፊ ሕብረብሔር ሠራዊት የመምራቱን ሚና መጫወት ብቻ ሳይሆን በጦርነቱ ብዙ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ አልነበረችም።

በጦርነቱ ተሳታፊ መንግሥታት ሁሉ ሶቭየት ሕብረትን ጨምሮ ለመሣሪያ፣ ለመከላከያ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ እቃዎች፣ የየብስ ተሽከርካሪዎች፣ የመለዋወጫ እቃዎች፣ ትጥቆችና በጠቅላላ ለጦርነቱ ሂደትና የድል ውጤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን አቅራቢ በመሆኗ ጦርነቱ ከሰላሙ ጊዜ በጣም የተሻለ ገበያ ስለሆናት ዛሬ ላለችበት አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገትና የረቀቀ ወታደራዊ ቴክኖሎጂ ባለቤት ለመሆን አበቃት። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተባበሩት የጀርመን፣ የኢጣሊያ፣ የጃፓንና የሌሎችም ተባባሪዎች ሕብረብሔር ሠራዊት ጋር ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በመዋጋት ከባዱ የጦርነቱ ሸክም የወደቀባቸው ሶቭየት ሕብረትና እንግሊዝ ነበሩ።

እንደሚታወቀው በምድራችን አቻ የሌለውን የሶቭየት ሕብረት የተፈጥሮ ቅምጥ የሀብት ክምችት በአጠቃላይ፣ ለምግብ የሚሆኑ ጥራጥሬዎችን፣ እንደ ድንጋይ ከሰል፣ ብረት፣ ኒኬል፣ አሉሚንየም፣ መዳብ፣ የደን ውጤቶችን፣ ጋዝና የነዳጅ ዘይት የመሳሰሉትን በተለይ ጀርመኖች እየተጠቀሙ ጦርነቱ የፈጀውን ያህል ጊዜ ቢፈጅም ለሠራዊታቸው የሚያስፈልገው የሎጅስቲክ አቅርቦት ምንም አይነት እጥረት ሳይገጥመው በጦርነቱ የድል ባለቤት ለመሆን ያቀዱት በቅድሚያ ሶቭየት ሕብረትን ወረው በመያዝ ለመበዝበዝ ስለነበር

ከእንግሊዝም በላይ የላቀ የጀርመን መንግሥት ከባዱን ክንዱን ያሳረፈው በሶቭየት ሕብረት ላይ ነበር።

ይህም በመሆኑ ሶቭየት ሕብረት ለትግሉ ከሃያ ሚሊዮን በላይ የሰው ሕይወት የጠፋባትና ታላቅ ውድመት የደረሰባት ቢሆንም ቀዩ አብዮታዊ ሠራዊት የጀርመኖችን ምኞትና ጥረት በማምከን በመጨረሻ የጦርነቱ ውጤት ሕብረተሰባዊ ሥርዓተ ማህበር ዓለም ላይ የተስፋፋበት፣ ሶቭየት ሕብረት ገንና በአኩሪ ድል የወጣችበት ሁኔታ ተፈጠረ። ቀዝቃዛው ጦርነት የተፈጠረውና ዓለም በሁለት የመደብና የርዕዮተ ዓለም ተከፍላ እጅግ አስፈሪ የኬሚካል፣ የባዮሎጂካልና የኒውክለር መሳሪያ የታጠቁ ሠራዊቶች ፍጥጫ የተጀመረው ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር።

ጀርመኖች የከፈቱትን የዓለም ጦርነት የሶቭየት ሕብረትን ሕዝብ ሀብት ተጠቅመው በድል ለመወጣት ከነበራቸው እቅድ የተነሳ ባደረጉት የውጊያ ትኩረትና ቀዩ ሠራዊት ወረራውን ለመመከት ባደረገው ብርቱ የመከላከል ጥረት የሶቭየት ሕብረት አስተዳደር አካል የሆኑት የዳር አገሮች ከሁለቱም ወገን በሚወረወር የአውሮፕላን ቦንብ ናዳና የመድፍ በስብ ተኩስ እንዳልነበሩ ሆኑ።

ዩክሬን፣ ቤላሩስ፣ ስቶኒያ፣ ላትቪያ፣ ሞልዶቪያን የመሳሰሉት ዳር አገሮች ሰማንያ በመቶ በላይ ሲወድሙ ከመሃል ሃገርም ከርዕሰ ከተማው ከሞስኮ ጀምሮ ታላላቆቹ የሕዝብ፣ የባህልና የኢንዱስትሪ መናኸሪያ ከሆኑት ታሪካዊ ከተሞች እንደ ሌኒንግራድና ቮልጎግራድን የመሳሰሉት ከመቶ ስልሳ እጅ ፈራርሰዋል። ወደ ሶቭየት ሕብረት መቃረቢያ ከሆኑት አገሮችም ላይ የደረሰው ጥፋት ቢብስ እንጂ የተሻለ አልነበረም። ፖላንድ፣ ቼኮዝሎቫኪያና ፊሱ ጀርመን በጀርመኖች ማጥቃት፣ በሶቭየት ሕብረትና በምዕራባዊያን ሕብረብሔር ሠራዊት የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ኢላማ በመሆናቸውና የጦርነቱን የመጀመሪያውን ገፈትና የመጨረሻውንም አሣር ለመጠጣት በመገደዳቸው ከሰባ በመቶ በላይ ወድመዋል።

እዚህ ላይ በጣም የሚደንቀውና በምሳሌነቱም ለሌሎች ትምህርት ሊሆን የሚችለው ጦርነቱ እንዳለቀ ወዲያው የተጠራ የሶቭየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ ያሳለፈው ውሳኔ መሠረትና በሶቭየት ሕብረት መንግሥት መሪነትና አስተባባሪነት መላውን የምሥራቅ አውሮፓ ሕዝብ በማንቀሳቀስ ከታላቅ የመልሶ ግንባታ ተግባር ባሻገር ባጭር ጊዜ ውስጥ የተጀመረው የልማት ተግባር ነው።

ጀርመንን ለመውጋት የተባበሩት ሁለቱ የምዕራቡና የምሥራቁ ግዙፍ ሠራዊቶች መካከል ፍጥጫ የመጀመሩ አይነተኛ ምክንያት የሆነው ሁለቱም በየአቅጣጫቸው በድል አድራጊነት በጀርመን ርዕሰ ከተማ በበርሊን የመገናኘታቸው ብቻ ሳይሆን ፀረ-ሶቭየትና ፀረ-ሕብረተሰባዊነት የሆነው ወታደራዊ ተቋም የሰሜን አትላንቲክ አገሮች ቃል ኪዳን ድርጅት ወይም ኔቶ በአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም መሪነት በመቋቋሙ ምክንያትና ሕብረተሰባዊ አገሮችም ራሳቸውን ለመከላከል በሶቭየት ሕብረት መንግሥት መሪነት የዋርሶን የመከላከያ ወታደራዊ ድርጅት በማቋቋማቸው ነበር።

ከዚህ ሁሉና እንደውም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በአውሮፓ ገዥ መደቦች ንቃት፣ የኢኮኖሚ ውድቀትና ጅምላ ሥራ አጥነት የተማረረው የምዕራብ አውሮፓ የሠራተኛ መደብ፣ ምሁራንና ዝቅተኛው ንዑስ ከበርቴ፣ ወጣቱና የደሃው ሕብረተሰብ ክፍል በጠቅላላ ሩሲያና በቻይና የሚካሄውን ሕዝባዊ አብዮት በቅርብና በተመስጦ ስለሚከታተሉና ስጋታቸው ስለተሳበ በእጅጉ የሰጉ የአውሮፓ ገዥ መደቦች ናቸው ፋሽዝምን የፈጠሩትና ጦርነቱን የጀመሩት።

ጦርነቱ እንዳበቃ በሕብረተሰባዊ አገሮች የተጀመረው የመልሶ ግንባታና የልማት እንቅስቃሴ፣ ቀድሞም የነበረው አብዮታዊ ዝንባሌ ከመጠንከሩ ጋር ጦርነቱ ባስከተለው ጠቅላላ ሁለንተናዊ ጥፋትና ውድመት ሰለባ የሆነው የምዕራብ አውሮፓ ሰፊ ሕዝብ በደረሰበት ረሀብ፣ ሥራ አጥነት፣ የመጠለያ እጦት፣ እርዛትና በሽታ ምክንያት በሆኑት ገዥ መደቦችና በሚያራምዱት ሥርዓተ ማህበር ላይ ማመፅ ጀመረ። እንደሚታወቀው አፈናው፣ እመቃውና ብሎም ግድያው እጅግ የከፋ ቢሆንም የአውሮፓ ኮሚኒስቶች በህዕቡም በግልፅም በብዛት ተደራጅተው መላውን የሠራተኛ መደብ ከጦርነቱ በፊት፣ በጦርነቱ ሂደት ውስጥና ከጦርነቱም በኋላ ሕዝባዊውን አመፅ ለማቀጣጠል ችለው ነበር።

በመላው ምዕራብ አውሮፓ ጎልቶ ከታየው የሕዝቦች አመጽ ጅምር ባሻገር በግሪክ፣ በስፔን፣ በኢጣሊያና በፈረንሳይ ኮሚንስቶች ወደ ፖለቲካ ሥልጣን ማማ የተቃረቡበት ሁኔታ እየታየም ነበር። በኮሚንስቶች እንቅስቃሴ ከማንም በላይ በብርቱ የሰጉት የኢምፔሪያሊስት ጭንቅላት የተባሉት የእንግሊዝ መሣፍንቶችና ቡርዥዎች ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ክፉኛ ስላዳሸቃቸው በእነሱ አቅምና የኢኮኖሚ ደረጃ ምንም ለማድረግ በማይችሉበት ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በማተት የሰሜን አሜሪካ መንግሥትና መላው የአሜሪካን ከበርቴዎች ከፍ ያለ የገንዘብ ድጋፍ በልግስና፣ በብድርና እንዲሁም በመዋዕለ ንዋይ ባጣዳፊ ይዘው ካልመጡና ከዚሁም ጋር የወታደራዊ ጣልቃ ገብነትም እርምጃ ካልወሰዱ ምዕራብ አውሮፓ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሶሻሊስት አብዮት የምትጥለቀለቅ መሆኗን የሚያስረዳና የካፒታሊስት ሥርዓትን ከውድቀት ማዳን ስላለባቸው ሁኔታ በብርቱ የሚያሳስብ ምስጢራዊ ሰነድ ለአሜሪካን ገዥ መደብ አቀረቡ።

የእንግሊዞች ስጋት ምን ያህል እውነትነት እንዳለው እንዲያጣራ በፕሬዝዳንት ትሩማን ታዞ የነበረውም የአሜሪካ መንግሥት የውጭ የስለላ ድርጅት በምዕራብ አውሮፓ እየተዘዋወረ ጥናት ካደረገ በኋላ የእንግሊዞች ስጋት እውን መሆኑን በማረጋገጥ ሰፊ ሪፖርት አቀረበ።

እነኚህ ስጋቶችና ብሎም ማሳሰቢያዎች ማርሻል ኘላን በመባል የሚታወቀውንና አሜሪካ በገሀድ የምዕራብ አውሮፓ መሪ ብቻ ሳትሆን በዚያን ጊዜ ያለማጋነን አስተዳዳሪም መሆኗን ይፋ የከሰተው ፖሊሲ በተግባር መገለፅ ጀመረ። ኘላኑ የተሰየመው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጥር ወር 1947 ዓ.ም የአሜሪካን መንግሥት የውጭ ጉዳይ ምኒስተር በሆነው በጄነራል ጆርጅ ማርሻል ስም ነበር።

ጆርጅ ማርሻል በምዕራብ አውሮፓ የካፒታሊስት ሥርዓት-ማህበርን ከጥፋት ለማዳንና ሕዝባዊውን አብዮት ለመግታት የሚያስችል ብቸኛና አስቸኳይ መፍትሔ በማለት ለፕሬዝዳንት ትሩማን የቀረበውን ሃሳብ የአሜሪካ ምክር ቤት አፀደቀው፡። የማርሻል ኘላን አብይ አካል የሆነውን የሶሻሊስት አብዮትን ለመገደብ በምዕራብ አውሮፓ የአሜሪካ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል የሚለውን የእንግሊዞች ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው የሰሜን አትላንቲክ የቃል ኪዳን ድርጅት መጋቢት 4 ቀን 1949 ዓ.ም (እ.አ.አ) ተመሠረተ።

የማርሻል ኘላን ዓላማና ተልዕኮ በምዕራብ አውሮፓ እየተቀጣጠለ የነበረውን ሕዝባዊ አብዮት በእንጭጩ ለመቅጨት የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማህበር አጥር የሆነውን ወታደራዊ ድርጅት ለማቋቋም ሆኖ ሳለ የዚህ እቅድ ሽፋን ሆኖ የተነገረው “በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጎዱ የምዕራብ አውሮፓ አገሮችን በመልሶ ግንባታው የአሜሪካን መንግሥት ሕዝብ ትብብርና ልግስና ኘሮግራም ነው” በማለት ነበር።

በጦርነት የተጎዱትን አገሮች መልሶ ለመገንባት ከሆነ ከጀርመን ጋር የወገነው የኢጣሊያ ፋሽስት መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጉዳት በምዕራብ አውሮፓ አገሮች ላይ ከደረሰው ቢበልጥ እንጂ የሚያንስ ስላይደለ በማርሻል ፕላን ውስጥ መካተት አለብን ብለው ከጠየቁ ጥቂት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች። የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎት አግባብነት ያለው ቢመስልም በፕላኑ ውስጥ ለመካተት መጠየቅ ግን የፕላኑን ዓላማ ካለመገንዘብ መሆኑ ግልፅ ነው። የእንግሊዝ መንግሥት የጀመረውን የካፒሊስቱን ሥርዓት ደህንነት ለመጠበቅ ለሰሜን አሜሪካ መንግሥት ምክሮችን በማቅረብ ግፊት ማድረጉን ማርሻል ፕላን ብቻ አላበቃም። በምዕራብ አውሮፓ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አብዮት በእንጭጩ መቅጨትና ካፒታሊዝምን ከውድቀት ለማዳን ብሎ ያቀረበውን ሀሳብ በአሜካን ገዥ መደቦች ተቀባይነት ማግኘቱን ከተረዳ በኋላ አዲሱ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስልትና ስትራቴጂ የተሰኘ ሀሳቡን በቅድሚያ ለሰሜን አሜሪካ ገዥ መደቦች ቀጥሎም የቅኝ ግዛት ኃይሎች ለነበሩት መንግሥታት ሁሉ አቀረበ።

የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አዲሱ የእጅ አዙር ቅኝ አዛዝ ስልትና ስትራቴጂ ያቀረበው መሰረታዊ ሀሳብ በአጭሩ ከዚህ የሚከተለው ነበር። በአፍሪካ፣ በእስያና በደቡብ አሜሪካ ስር ሰዶ የቆየው ድህነት፣ በዚያም ላይ በታከለው ቅኝ ተገዥነት ጋር ተጠናክሮ የቀረበልንን የነፃነት ጥያቄ በወቅቱና በአግባቡ ለማስተናገድ ዳተኛ ብንሆንና ብንዘገይ የኮሚኒስት ሥርዓት በዓለም ላይ እንዲለማ የለሰለሰ ለም መሬት ከማዳበሪያ ጋር እንደመስጠት ወይም እንዳስረከብን ነው የሚቆጠረው።

ሳንቀደም የቅኝ ግዛቶቻችንን በሰላምና በመግባባት ፈጥነን ነፃነታቸውን መስጠት አለብን። ነፃነታቸውን ከስጠንም በኋላ ጥለናቸው መውጣት ሳይሆን በጋራ የልማት ሕብረት ትስስር ያለፈ ቂማቸውን በመርሳት ከእኛ ጋር አብረው በመኖር የሚገኘውን ጥቅምና ተስፋ ለማሳየት መቻል አለብን የሚል ነበር። በዚህ ሀሳብ ከቅኝ ገዥዎቹ አገሮች በጣም ደሀ የነበሩት ቤልጄም፣ ፖርቹጋልና እስፔን በመጠኑ የመንገታገት አዝማሚያ ከማሳየታቸው በስተቀር በተለይ የሰሜን አትላንቲክ የቃል ኪዳን አገሮች ማህበር አውራ የሆኑት የሀሳቡን አቅራቢ እንግሊዝን ጨምሮ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ኢጣሊያ በሙሉ ተስማሙ።

የአዲሱን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስልትና እስትራቴጂ የሰሜን አሜሪካ ገዥ መደቦች፣ መስተዳደሩና ምክር ቤቱ ሙሉ በሙሉ ተቀብለው በማፅደቅ ፖይንት ፎር በመባል የሚታወቀውን ፕሮግራም ሰኔ 24 ቀን 1949 ዓ.ም (እ.አ.አ) አወጁ። ለተለያዩ አገሮች የአሜሪካ መንግሥት የሚሰጠው ርዳታ፣ ብድር፣ መዋዕለ ንዋይ መጠን፣ አይነት፣ ምክንያቱና የአቀራረብ ስልቱ ይለያይ እንጂ በዓላማ የፖይንት ፎር ፕሮግራምና ማርሻል ፕላን ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ የተሰጠው ሽፋንና በተለይም በፕሬዝዳንት ትሩማን በራሱ የተሰጠው መግለጫ "ታዳጊ አገሮችን የአሜሪካን መንግሥትና ሕዝብ በቴክኒክና በመዋዕለ ንዋይ ለመርዳት የታቀደ የልግስና ፕሮግራም" በማለት ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎትና ጥያቄም መልስ ማግኘት የነበረበትና የተካተተው በዚህ በፖይንት ፎር ፕሮግራም ውስጥ ነበር። እነኚህ እቅዶችና ፕሮግራሞች በሚካሄዱበት የጊዜ ክልል ውስጥ የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም በአፍሪካ ቀንድና በቀይ ባሕር ላይ ከነበረው ትኩረትና ብሔራዊ ጥቅም አንፃር ኢትዮጵያ ያለችበት መልካ ምድር በስትራቴጂያዊ አመለካከት ቁልፍ ስፍራ ነበር። በአካባቢው ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ጠላቶች ለማፍራት ምክንያት የሆነውን የአሜሪካ ኢምፔርያሊዝምን ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በመፍቀዷ ከፖይንት ፎር ፕሮግራም የሚሰጠውን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ የአንበሳ ድርሻ ለማግኘት ትችል ነበር። ብሔራዊ የሃገር ልማትና ግንባታ እቅድ ቀርቶ ለአንዳንድ

ጥቃቅን ኢኮኖሚያዊ ተግባር የሚውል ብድር ለመጠየቅ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች እንኳን ሊሰሩና ሊያቀርብ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል ስላልነበራት በፖይንት ፎር ፕሮግራም ተጠቃሚ ሳትሆን ቀርታለች። የኢትዮጵያ ከፖይንት ፎር ፕሮግራም ፍርፋሪ አግኝታለች ቢባል በአሜሪካዊያን በራሳቸው ባለሙያዎች ርዳታና ግፊት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ባንክ፣ የኢትዮጵያን ሲቪል አቪዬሽንና የአየር መንገድ፣ የአውራ ጎዳና ግንባታ ባለሥልጣንንና የውሃ ልማት ተቋምን ለማቋቋም መቻሉ፣ በአሜሪካ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች የከፍተኛ ተቋም የትምህርት እድል መከፈቱና በጣም መናኛና አነስተኛ የመከላከያ ድጋፍ መገኘቱ ብቻ ነው።

ለአርባ ሺህ ሠራዊት በመከላከያ ድጋፍ ስም የቀረቡልን የጦር መሣሪያዎች ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተዘጋጁና እጅግ በመፋጠን ላይ ከነበረው የዓለም ወታደራዊ ቴክኖሎጂ ወደኋላ የቀሩ በመሆናቸው ለአሜሪካ ለራሷ የማያስፈልጓትና ለኢንዱስትሪ ግብዓት በጥሬ እቃነት ወደ ብረት ማቅለጫ ይላኩ የነበሩት አሮጌ መሣሪያዎችን ቀለም እየቀቡ ነበር የላኩልን። በውሃ ልማት ተቋም መፈጠርና በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት በወረት አሜካዊያን ባሳዩት ንቅናቄ ኢትዮጵያ ትለማ ይሆናል በሚል ተፈንጥቆ የነበረው የተስፋ ጮራ ወዲያው ጨለመ። የኢትዮጵያን ድክመትና ውድቀት ጥቅማቸውና እድገታቸው አድርገው የሚመለከቱት አረባውያን በተለይም ግብጽና ሱዳን ለአሜሪካ መንግሥት ባቀረቡት ምልጃና ከዘይት አምራች አረባዊ መንግሥታት ጋር ተደጋግፈው ባደረጉት ተፅዕኖ የአሜሪካ ባለሙያዎች የጀመሩትን የውሃ ልማት ጥናት ሥራቸውን ጥለው ሄዱ።

ይህንን የተመለከቱ ለኢትዮጵያ ቅንና በጎ አመለካከት የነበራቸው የስዊድን፣ የካናዳ፣ የኢጣሊያና የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው በአንድ እጅ ጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች ይችን ጥንታዊና የታጋይ ሕዝብ መኖሪያ ሃገር እንርዳት በማለት ሰሜን አሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ ከበርቴዎች ቴክኖሎጂና መዋዕለ ንዋይ ይዘው እንዲገቡ ለማድረግ ሲሉ በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የልማት ትዕይንት በጥንቱ የአውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ በነበረ ሰፊ ሜዳ ላይ በማዘጋጀትና የኢትዮጵያን ለም አፈር፣ የውሃ ሀብት፣ ልምላሜና ሌሎች ቅምጥ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማስተዋወቅ ጥረት አድርገው ነበር።

በትዕይንቱ ላይ ለመሳተፍ የመጡት ከበርቴ ግለሰቦችና ድርጅቶች መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ ኢትዮጵያ የቱን ያህል ምቹ ነች? መዋዕለ ንዋይ ለመቀበል የሚያስችሏትን ቅድመ ሁኔታዎች በማዘጋጀት ረገድ በእንዴት ያለ ደረጃ ላይ ትገኛለች? ለተሰኙ ጥያቄዎቻቸው ፈጣን መልስ ለማግኘት ሲሉ በየፊናቸው በወልና በግል ከትዕይንቱ በኋላ በኢትዮጵያ ሰንብተው አጭርና ግርድፍ ጥናት አድርገው ነበር።

ጥናታቸው ያስገነዘባቸው በአጭሩ በኢትዮጵያ የተለያዩ ልማቶችን ለማካሄድ ይቻላቸው ዘንድ የሚያንቀሳቅስ የአየር፣ የባሕርና የየብስ ተሽከርካሪዎችን የሚያንቀሳቅስ ሁኔታ ወይም የመገናኛና የትራንስፖርት አገልግሎት ጨርሶ ያለመኖሩን፣ ከጉልበት ሠራተኛ በስተቀር በልማቱ ተግባር በብዛት ለመሳተፍ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል እንደሌለ፣ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ልማት ለመሳተፍ ፍላጎት ላለው መዋዕለ ንዋይ አቅራቢ የሚያስፈልጋቸው ቀላልና መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎች እንኳን በግብርናውና በመዓድኑ ዘርፍ ጨርሰው እንደሌሉ ነበር። መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾቹ እራሳቸው ለልማቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች የማሰባሰቡን ተግባር ቢያመቻቹና ቅድመ ሁኔታዎችን ቢፈጥሩ እንኳን ልማቱን ለመጀመር ከሚያስችሉ የመገናኛ ችግሮች ሌላ በኢንዱስትሪው መስክ አነስተኛ የብረታ ብረት ሥራዎችን ለመሥራት አስር ኪሎ ግራም ብረት ለማቅለጥ የሚያስችል ማቅለጫና የኤሌትሪክ ኃይል እንኳ አልነበረንም።

መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾቹ ባደረጉት አጭርና ግርድፍ እንዲሁም አጠቃላይ የልማት ጥናት ውስጥ በተለይ ገበያን አስመልክቶ ያገኙት መረጃ የሚያመለክተው መለስተኛ የጨርቃ ጨርቅ፣ የምግብና የመጠጥ ኢንዱስትሪዎችን አቋቁመው ቢያመርቱ ሕዝቡ የቆመው በድህነት ወለል በታች ስለሆነ ሌላው ቀርቶ ኮካኮላ ገዝቶ ለመጠጣት የመግዛት አቅም የሌለውና ለጎጆ ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ እንኳን ያልተጋለጠች ሃገር ገንዘብ የምናፈሰው ለጽድቅ ነው ወይስ ለትርፍ በማለት ወደ የአገራቸው ተመለሱ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነቱ ማኘት የተሰማው ደስታና የፈንጠዝያው ጊዜ እያለቀ ሲሄድና በተከታታዮቹ ዓመታት የተከሰቱት አፍራሽ ችግሮች ከፋሽስቶች የቅኝ አገዛዝ እየከፉ መሄድ ጀመሩ። ንጉሡ የኢትዮጵያን ጉልተኛ መሣፍንቶች መደብ በጦርነቱ መደምሰሱና ሠራዊታቸውም የመፍረሱን አጋጣሚ ተጠቅመው፣ የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ገፈው፣ ጥርስና ጥፍር የሌለው ነብር አደረጓቸው። ዳግማዊ ምኒልክ አፄ ቴዎድሮስ ያፈረሱትን የመሣፍንት መደብ መልሰው እንደገነቡት ሁሉ፡ ኢጣሊያኖች ያፈረሱትን መደብ አፄ ኃይለሥላሴ መልሰው ለመገንባት ሲሉ የኢኮኖሚ ኃይላቸው እንዳይነጥፍ በጦርነቱ የተረፉትን መኳንንትና መሣፍንት በሙሉ በየጉልታቸውና በየአባቶቻቸው ጉልት መልሰው ስለተከሏቸው በአምስቱ የፋሽስት ኢጣሊያ አገዛዝ ዓመታት ባለመሬት የነበረው ገበሬ፣ በሰላሙ ጊዜ በነፃነቱ አገሩና በራሱ መንግሥት አመራር ተመልሶ የጉልተኞች ጭሰኛ፣ ጥሰኛና ሎሌ ሆነ። በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የአፄ ኃይለሥላሴ የጉልት አተካከል ከቀድሞው ለየት ባለ ሁኔታ ወትሮ ጉልተኞች ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ የመጣና ርስት ሀረጋችን ላይ የተመሠረተ መብታችን ነው በማለት ሲከራከሩ በነበረበት ሁኔታ አልነበረም።

ህገ መንግሥቱ በሰጣቸው ፈላጭ ቆራጭ መለኮታዊ ሥልጣን ፍፁም ተገዥ፣ ሎሌ ደጋፊያቸውና አገልጋያቸው ለሆነ ሰው የሚለግሱና በፈለጉም ጊዜ ሊነቅሉ የሚችሉ መሆናቸው መሣፍንቱ በሙሉ ለንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድና ችሮታ በአድርባይነት ለመኖር ተንበርክከላቸዋል። በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የጉልተኞችና የገበሬው ግንኙነት፣ የገበሬው ኑሮና የመሬቱ ይዞታ በአጭሩ ይህንን ሲመስል በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፈረንሳይ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር መቋቋም ምክንያት በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው የሠራተኛው መደብ ቁጥሩ በተፋጠነ ሁኔታ ሊያድግ የቻለው ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ በገነቡት ጅምር የካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር ነው። የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ በጀመረው የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ የማዕድን፣ የኢንዱስትሪና የዘመናዊ እርሻ ልማት፣ በመገናኛና ትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚው፣ በገንዘብ፣ በጤና፣ በሆቴሎችና በልዩ ልዩ ሰበንክ አገልግሎቶች የሥራ መስኮች ውስጥ በተፈጠሩት የሥራ እድሎች ነበር።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በተለይም በመጀመሪያዎቹ የሽግግር ዓመታት በተከሰቱት መንግንብሮችና ቀውሶች፣ ባለቤትና አመራር እጦት፣ ካፒታልና ሥራ ማስኬጃ የገንዘብ እጦት፣ በኤሌትሪክ ኃይል እጦት አምራቾችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተግባራቸውን አቆሙ። በነፃነት ማኘቱ የፈነጠዘው የሠራተኛ መደብ ሰላም በሰፈነበትና የራሱ ነፃ መንግሥት መልሶ በተቋቋመበት ጊዜ ሥራአጥ ቦዘኔ ሆኖ ለመጠለያ፣ ለዕለት ጉርሱና ለብሱ ባለመብቃቱ ወደ ወንጀል ተግባር ተሰማራ።

# የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና አይበገሬ አርበኝነት

እስከ ቅርቡ የሶማሊያ የመስፋፋት ወረራ ድረስ በኢትዮጵያ ጀግኖች የተደረጉትን የመከላከል የአርበኝነት ተጋድሎ ስናሰላቸው ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ የተለያዩ ባዕዳን ኃይሎች ኢትዮጵያን በቅኝነት ለመያዝ ወይም ለመስፋፋት ሞክረው አንዳቸውም አልተሳካላቸውም። ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ ታሪኳን በሙሉ ከውጭ በተቃጣባት ጥቃትና ወረራ ተሸንፋ አታውቅም።

የዚህን እውነታነት እኛ ኢትዮጵያውያን ሳይሆን አጥቂ ጠላቶቻችን ይመሰክራሉ። ዓመተ ዓለም እየተባለ ይጠራ ከነበረው ከ336 የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ እናት በምትባለዋ በግሪክ የነገሠውና ዓለምን የገዛው ታላቁ አሌክሳንደር ኢትዮጵያን ለመውረር የነበረውን ምኞትና ስለ ኢትዮጵያም ያለውን አመለካከት ኩዌንተስ ኩሪቲወስ የተባለው ግሪካዊ የጊዜው ፀሃፊና የታሪክ ምሁር "ወጣቱ ንጉሥ አሌክሳንደር ከመቄዶንያ በመነሳት ሠራዊቱን እየመራ የመጀመሪያውን ወረራ ሲጀምር ዝቶ የተነሳው በዚያን ጊዜ በአፍሪካ ገናና የነበሩትን ታላላቅ የግብጽና የኢትዮጵያ መንግሥታት ለመውረር ነበር" ሲል ግዛቱን ለማስፋፋት መነሳቱን ገልጾ ነበር።

"ግብጽን ታግለን ከያዝን በኋላ ኢትዮጵያን ለመውረር ብንሄድ እንደ ግብጽ አይቀናንም። ኢትዮጵያኖች የማይሸነፉ፣ ወደር የሌላቸው ተዋጊዎች ስለሆኑ ብንገጥማቸው ብዙ ያስከፍሉናል ያም ሆኖ ስለማንረታቸው ከነሱ ጋር ከመጣላት መወዳጀቱ ይሻላል ብለን መክረነው ነበር። ለጊዜው እኛን አላዳምጥ ብሎ ራሱን ሌላ ሰው በማስመሰል ሰውሮ ከጥቂት ሰላዮቹ ጋር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ በመሰለል የኢትዮጵያውያንን ማንነት ከተረዳ በኋላ ከግብጽ ጀምሮ እስከ ሕንድ ድረስ አያሌ አገሮችን እየወረረ ሲያስገብር በእነዚህ አገሮች መካከል ካለችው ኢትዮጵያ ጋር ግን እንደመከርነው መወዳጀትን መረጠ" ብሏል።

ኩዌንተስ ኩሪቲወስ ከግሪክ ሠራዊት ጋር አብሮ በመዝመት የአሌክሳንደርን አመራርና የጦርነቱን ታሪክ ዘጋቢ ነበር። በ29 ዓመተዓለም የሮም ቄሳር የነበረው አውግሥቶስ ኢትዮጵያን ለመውረር አስቦ ስለወረራው ከጦር መሪዎቹ ጋር በሚወያይበት ጊዜ ከጦር መሪዎቹ አብዛኛው "ኢትዮጵያውያን የማይበገሩ ተዋጊዎች ስለሆኑ የሚሻለው ከእነሱ ጋር ባንዋጋ ነው። እንድንዋጋ የአንተ የጌታችን ፅኑ ፍላጎት ከሆነ የኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ረጅም የውጊያ ልምድ ያለው አደገኛ ሠራዊት ከመሆኑም ሌላ መልካ ምድሩም ለእኛ አመቺ ስላልሆነ በእግረኛ ሠራዊት በመሬት ላይ ብንፈትናቸው ይሻላል የሚል ምክር ስለሰጡት ሀይሎስ ጋሎስ በሚባል ዝነኛ ጄነራል የሚመራ መጠነ ሰፊ ፈረሰኛና እግረኛ ሠራዊት ከግብጽ በማስነሳት በሱዳን በኩል ላከ። ሮማውያን የሚያደርጉትን የወረራ እንቅስቃሴ ቀድመው ያወቁት ኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ድንበራቸውን አልፈው ሱዳን ምድር ላይ በመጠበቅ ብዙ ጊዜ በወሰደና የብዙ ሰው እልቂት ባደረሰ ውጊያ ኢትዮጵያውያን ጠላቶቻቸውን እረተው መልሰዋል።

አጉስቶስ ቄሳር ላይ የደረሰውን ሽንፈትና ውርደት ለመበቀል ከሰላሳ ዓመት በኋላ በ54 ዓመተዓለም ኔሮ የተባለው ሌላው የሮም ቄሳር የአባቶቹን ምኞት ለመፈፀም የአባይን ምንጭ የሚፈልጉ ናቸው ብሎ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ደብዳቤ ጽፎ ሰላዮቹን ወደ ኢትዮጵያ ላከ። "የተላከነው ሰላዮች ኢትዮጵያ ውስጥ ከርመን ስንመለስ ሕዝቡ በሙሉ ጦረኛ መሆኑንና ወደ ኢትዮጵያ ጦር መላክ እንደማያዋጣ ነበር። በዚህ የስለላ ተልዕኮ አጋጣሚ ለመረዳት የቻልነው የሕዝቡን ጀግንነትና አይበገሬነት ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን እጅግ ውብነትና ልምላሜ ጭምር ነበር" ሲል የስለላው ቡድን አባልና የጊዜው ታሪክ ፀሃፊ

የበረው ሴኔካ ጽፏል። ሌላው ታዋቂ ኢጣሊያዊ ሃገር ጎብኚ ማርኮ ፖሎ በ1298 ዓ.ም የሕንድ ጉዞዬ ብሎ በጻፈው መጽሃፉ ስለኢትዮጵያውያን ጀግንነትና አይበገሬ አርበኝነት ሲገልጽ "ዓለም ሊያውቀው የሚገባ ነገር አለ። በሐበሻ ምድር ምርጥ የሆኑ ጀግና ወታደሮች አሉ። አብዛኛዎቹ ወታደሮችም ፈረሰኞች ናቸው። ፈረስም በብዛት አላቸው። በዚህም ምክንያት ተዋጊዎችና ኃይለኞች ናቸው። በሕንድ ሃገር ስላሉትና በእጅጉ ከምናደንቃቸው አውቅ የሕንድ ወታደሮችም ኢትዮጵያኖቹ የላቁ ናቸው" ብሏል።

የሰው ልጆችንና የአገሮችን ህልውና፣ ነፃነት፣ መብትና ሰላም የሚያስከብር፣ የሚያስተባብር ወይም የሚዳኝ ምንም አይነት ዓለማቀፋዊ ማዕከል በሌለበት ዓመተዓለም እየተባለ በሚጠራው ጥንታዊ ጊዜ የሰው ልጅ ይተዳደር የነበረው ከአራዊቶች ባልተሻለ ሁኔታ ነበር። በአራዊቶች ዓለም አቅመ ደካማውና አካለ ኮሳሳው ከግዙፍ ፍጡርና ከኃይለኛው በመሸሽ በመራቅና በመሰወር ፈርቶ፣ ተሸማቆና ተንበርክኮ ከመኖር ባሻገር ስጋ ለባሙ ቅጠል በላውን እየተመገበ ይኖራል። የአራዊቱ ዓለም የሁሉም ሳይሆን የኃይለኞችና የጉልበተኞች ዓለም ነውና።

የሰው ልጅ አኗኗርም ከዚህ ብዙ የሚሻል አልነበረምና ጥንታዊቷ ዓለም የኃይለኞችና የጉልበተኞች ነበረች። በሰው ብዛት፣ በሀብት ምጣኔና በጦር ኃይሉ ጥንካሬ የተበተው ሃገር በሌላው ላይ ለመስፋፋትና ሌላውን ቅኝ አድርጎ ለመግዛት መውኃትና መውረር እንደ በጎ ነገር፣ እንደ ጀግንነት፣ ታላቅነትና አስተዋይነት እየተቆጠረ የወራሪው ሃገር መሪ ታላቁ እየተባለ በሚሞካሸበትና በሚወደስበት ዓለም ደካሞች በሰላምና በነፃነት የመኖር ተስፋ አልነበራቸውም። የኃይለኞችና የጉልበተኞች በነበረችው ዓለም ህልውናቸውን አጥተው እንደ አንድ ሕዝብ ወይም ሃገር በሉዓላዊነት የመኖር እድላቸው አክትሞ ከጥፋት ተርፈው ቢሆን በአንድ ነፃ ሕዝብነትና ሃገርነት ከሚታወቁት ሁሉ የመወረርና የቅኝ ተገዥነት እጣ ፈንታቸው ያመለጡ በአንድ እጅ ጣት የሚቆጠሩ ጀግኖችና አይበገሬዎች ናቸው።

በዚህ ረገድ በመቶዎች የሚቆጠሩ የወራሪና የተወራሪ አገሮች ዝርዝር ማቅረብ ቢቻል ለአብነት ያህል ሦስት አገሮችን ብቻ እጠቅሳለሁ። ከ16ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ 19ኛ ምዕት ዓመት መገባደጃ ድረስ በቅኝ ግዛት አገሮቿ ብዛትና ስፋት ወደር ያልነበራት የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም በጥንቱ ጊዜ የኢጣሊያ ቄሳሮች ቅኝ የነበረች ስትሆን የዛሬው ዓለማችን ብቸኛ ልዕለ ኃያላን የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም በቅርቡ የእንግሊዝ ቅኝ ነበር። ከእነዚህ አይበገሬ ታሪከኛ በጣም ጥቂት ጥንታዊ አገሮች የኛ ሃገር ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች።

ኢትዮጵያ በጀግኖቿ የአርበኝነት ተጋድሎዋ በነፃነት መኖር ብቻ ሳይሆን በዓለም የታፈረችና የተከበረች ነች። የኢትዮጵያ መልካ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ለም አፈሯ፣ ድንግል የተፈጥሮ ሀብቷ፣ ንፁህና ነፋሻ አየሯ ከጥንታዊዎቹ ኃያላን ግሪኮችና ከሮማውያን ምኞትና ውጪ ሌላ በየጊዜው ኃይል የተሰማቸው፣ የቅኝ ግዛት ምኞት ያሰከራቸው ወራሪዎችና ተስፋፊ ጠላቶቿ ኢላማ አድርገዋታል።

ባለፉት ሁለት ሺ ዓመታቶች ውስጥ በፈረቃ ፋርሶች፣ አረቦች፣ ቱርኮች፣ ግብጾች፣ ሱዳኖች፣ ዳግም ኢጣሊያኖች ሦስት ጊዜ በመጨረሻም ሶማሊያዎች ከፊሉ ቅኝ ግዛታቸው ሊያደርጉን የተቀሩት ለመስፋፋት ሞክረው ሁሉም እየተቀጡ ተመልሰዋል። ያለፈውን የኢትዮጵያውያንን የጀግንነትና አይበገሬ አርበኝነት ታሪክ ቆንጥሬ ለማቅረብ የሞከርኩበት ዋናው ምክንያት ስለአኩሪ መንፈሳዊ ቅርሳችን በማውሳት የአገራችንን የጥንቱንም የቅርቡንም ጊዜ ጀግኖች ለማስታወስ ያህል ነው።

የኢትዮጵያ ታሪክ በአገራችን የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ድህነትና የኋላ ቀርነት ምክንያት የተመራንበት የፖለቲካ ሥርዓት ችግር እንጂ አገራችን ኢትዮጵያ አይደለችም። የኢትዮጵያ ጀግኖች አይበገሬ የአርበኝነት ተጋድሎ ገድል የሚያስረዳን አንድነት ኃይል መሆኑን፣ አንድነት ታላቅነት መሆኑን ነው። የዚህች የጥንታዊት አይበገሬ ነፃና አኩሪ ሃገር ባለቤት ለመሆን የቻልነው በአንድነታችንና በሕብረታችን ነው። አገራችን ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ የየዘመኑ ተከታታይ ትውልዶች በፈረቃና ባላቋረጠ መሪር መስዋዕትነት ያቆዩንን ሃገርና ያወረሱንን አኩሪ የታሪክ ቅርስ እኛም በፈንታችን ለተከታዩ ትውልድ እናወርሳለን ወይስ እናፈርሳለን ብሎ የዛሬው ትውልድ ራሱን መጠየቅ አለበት።

ከዚህ ሌላ ስለ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ጀግኖች አይበገሬ የአርበኝነት ተጋድሎ ታሪክ አረምና አፈር መልበስ ብቻ ሳይሆን በዘመናችን ከህዲዎች መንኳሰስና መርከስ ስንቆጭ የትናንቱን የኛን አባቶች ፀረ-ፋሽስት ተጋድሎ ባዕዳንና በተለይም ጠላቶቻቸው የጻፉላቸውን ያህል እንኳ ለመጻፍ ያለመብቃታችንን ማስታወስም ተገቢ ነው። በየዘመናቱ የተከሰቱ የአገራችን አበይት ታሪካዊ ክስተቶችን ለመጻፍ በመረጃነትና በዋቢነት የሚያገለግሉኝን መጻህፍት ሳገላብጥ የትናንቱን የፀረ-ፋሽስት ተጋድሎ ቢያንስ ከአህመድ ግራኝ ወረራ ታሪክ ባላነሰ ለመጻፍ ምኞቴ ነበር።

ስለሆነም በዚህ ረገድ የምረዳበት መረጃ ለማግኘት ስል ይህ ቅፅ አንድን ለማሳተም በማዘግየት ብዙ ደክሜ በሰነድ የሰፈረ አነስተኛ መረጃ ላገኝ የቻልኩት በመሃል ሃገር በሸዋ፣ በወለጋ፣ በኢሊባቡርና በጥቂቱ በከፋ ክፍለ አገሮች ብቻ የተደረገውን ፀረ-ፋሽስት ትግል በመሆኑና በተቀሩት ኤርትራ፣ በትግራይ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በወሎ፣ በሐረርጌ፣ በሲዳሞ የነበሩ አርበኞችን ተጋድሎ የማያካትት በመሆኑ ቁንፅል ነገር ከመጻፍ ተቆጥቤያለሁ።

የትናንት ፀረ-ፋሽስት አርበኞቻችን የታገሉት እንደ ጥንቱ ተመሳሳይ መሣሪያ ታጥቆ ከመጣ ጠላት ጋር በክንድ መሣሪያ ሳይሆን በሰው ልጅ ታሪክ ታይቶ ከማይታወቅ፣ እጅግ ከተራቀቀ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጋር እና በዓለም ሕግ የተከለከለ የመርዝ ጋዝ ዝናብ እየዘነበባቸው ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከአየር በአውሮፕላን የሚጣል ወይም የሚወረወር የቦንብ ናዳ የተጠቀመችው ብቸኛ ሃገር ፋሽስት ኢጣሊያ ስትሆን የመጀመሪያዎቹ ተጠቂዎች ኢትዮጵያና ሊቢያ ነበሩ። ከዚህ ሌላ የፀረ-ፋሽስት አርበኞቻችንን ጀግንነትና መስዋዕትነት ከሌላው ጊዜ ልዩና ተደናቂ የሚያደርገው እንደሚታወቀው በ1928 ዓ.ም ወራሪውን የፋሽስት ሠራዊት በሃገር ደረጃና በመንግሥት አመራር የተደረገው የመከላከል ሙከራ ባለመሳካቱና በመወረራችን ለነፃነት የተደረገው የአምስቱ ዓመታት ፀረ-ፋሽስት የአርበኝነት ትግል ግምባር ቀደም የነበሩትና በኋላም በሂደት ትግሉ የወለዳቸው ጀግኖች ለትግል የተሰማሩት በማንም አሳሳቢነት፣ ቀስቃሽነት ወይም ትዕዛዝ ሳይሆን በየአንዳንዱ ጀግና በራሱ አነሳሽነት ነው።

ለደሞዝ፣ ሹመትና ለሽልማት ወይም ለቁሳዊ ጥቅም ሳይሆን ለመስዋዕትነት ነው። የዚህ ክልል ሰው የዚያ ጎሳ አባል ብለው ሳይከፋፍሉ ሁሉም በያሉበት ክልል ተደራጅተው ያላንዳች አገራዊ የማዕከል መሪ ወይም አስተባባሪ፣ ያላንዳች ፖለቲካዊና ወታደራዊ ማዕከል፣ በገንዘብ፣ በትጥቅና ቁሳቁስ ማንም ሳይረዳቸው በትግሉ ጥለው እየወደቁ ከጠላት በሚነጥቁት መሣሪያ ለአንዲት ኢትዮጵያ ነፃነትና ሉዓላዊነት ነው የተፋለሙት። በእንደዚህ ያለ እጅግ ፈታኝና ውስብስብ ሁኔታ ታግለውና አታግለው ስደተኛውን ንጉሥ ተቀብለው

መንበረ መንግሥታችን ላይ መልሶ ማስቀመጥን የሚያክል ታላቅ ተግባርና ለአንድ መሪ የሚደረግ ውለታ በላይ ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም።

በደሙላትና በተሰውላት አገራቸው፣ በአዲሲቱና ነፃይቱ ኢትዮጵያ ሌላው ነገር ሁሉ ቀርቶ ቢያንስ ፍትሀዊ አስተዳደር ሲጠብቁ፣ ስደተኛና ባንዳ ግምባር ፈጥረው የንጉሡና የመንግሥታቸው ባለሟልና ባለጊዜዎች በመሆን ለሹመቱ፣ ለሽልማቱና ለጥቅማ ጥቅሙ መጀመሪያው ረድፍ ተሰለፉ። አርበኛ ለአገሩና ለመንግሥቱ ባይተዋርና የበይ ተመልካች መሆኑ ባሻገር ጥቂቶቹ ስመጥር አውራ አርበኞች በመገደላቸው፣ በመታሰራቸውና መጋዛቸው መላው አርበኞች ክፉኛ አዝነው "አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!" አሉ።

እንደ ባህል ተወስዶ ወይም የታሪክ ገጠመኝ ሆኖ ዳግም የሚያሳዝነው በአባቶቻችን የደረሰው የእኛም እጣ ሆኖ ዛሬም በእኔ ትውልድ በኢትዮጵያ የሚንደላቀቁት ለኢትዮጵያ የደከሙላት፣ የሞቱላት ለሕዝቡ የተፋጠነ ማህበራዊ እድገት፣ ለአገሪቱ አንድነትና ታላቅነት የታገሉ ልጆቿ ሳይሆኑ፣ የከዷት፣ የወጓት፣ ያስገነጠሏት፣ ያደሟትና የገደሏት አጥፊዎቿና ጠሮቿ መሆናቸው ነው።

ለአፄ ኃይለሥላሴ ተስፋና የፖለቲካ ምርኩዝ ሆኖ በዓለም መንግሥታት ሸንጎ ቆመው መናገር ያስቻላቸውና የእንግሊዝን መንግሥት ወታደራዊ ድጋፍ ያስገኘላቸው የኢትዮጵያ ፀረ-ፋሽስት አርበኞች ተጋድሎ ነው። የኢትዮጵያ አርበኞች ባይታገሉና ሕዝቡም ቅኝ ተገዥነትን አሜን ብሎ ቢቀበል ኖሮ ከሁሉ በፊት በዓለም መንግሥታቱ ሊግና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል ቅራኔ ባልተፈጠረና ኢጣሊያ በተቃርኖ ከጀርመን ጋር ባልተሰለፈችም ነበር። ከእንግሊዝ ኢትዮጵያን ለመደገፍ የተላከውን የጦር ኃይል የመሩት መኮንኖች የኢትዮጵያን አርበኞች ጀግንነትና አይበገሬነት ባይመለከቱ ኖሮ ኢትዮጵያን በሰላም ለቀው መውጣታቸው በእጅጉ አጠራጣሪ ነበር።

ፋሽስታዊው ወራሪ ሠራዊት አዲስ አበባ በገባ ማግሥት የኢጣሊያ ፋሽስት መሪ ዱቼ ሙሶሎኒ "ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር የሮም ቄሳሮች ቅኝ ግዛት መሆናን እናስታውቃለን" ብሎ የደነፋውን ድንፋታ የሰማ ኢትዮጵያዊ ልብ ሁሉ እንደሚደማ አያጠያይቅም።

ሆኖም ዱቼ እንዳለው ሳይሆን አብዛኛው የፋሽስት ሠራዊት ከድንኳን መጠለያው ሳይወጣና ጫማውን ሳያወልቅ እንደተለመደው አራውጠው በማባረር በአጭር ጊዜ ውስጥ አገራችንን ነፃ ያደረጉት ጀግኖች አብዛኛዎቹ ከዚህ ዓለም ተለይተው የተረፉት የእድሜ ባለጸጎች በእርጅናቸው ዘመን በቀድሞ ባንዳዎች ልጆችና በአዲሶቹ ባንዳዎች የቅኝ ግዛት አስተዳደር አረንቋ ውስጥ ከመውደቃቸው ባሻገር የደሙላትና የሞቱላት ኢትዮጵያ ዳግም የባሕር በር አልባ ሆኖ በጎጥ በመከፋፈሏ ያለቅሳሉ።

ለማጠቃለል፣ ይህ ሰው የተነሳው መርዶ ለመናገር ብቻ ነው ባልባል በመንፈሳዊ ቅርፅ ረገድ ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ዛሬ እንደ ቁሳዊ ሕይወታችን አቆልቁሎ ጉዞ ብቻ ሳይሆን አቆልቁሎ እሩጫውን ተያይዘነዋል ለማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያን ዛሬ ጀግና ብቻ ሳይሆን ሰው አልባ ምድረ በዳ እየሆነች ነው። ዛሬ ሰው የሆኑላቸው ኢትዮጵያዊያን አንድም ተገለዋል፣ አንድም ተሰደዋል፣ አብዛኛውም በወያኔ እስር ቤቶች ታጉረዋል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚዋጋና የሚታገል ቀርቶ የሚናገርም የለም።

ከዚህ እጅግ ከከፋና ከከረፋ ጨቋኝና ጎታች ጉልታዊ ሥርዓት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ያወጡት አብዮታዊያን መሪዎችና የአገሪቱ ወጣቶች በወያኔ እስር ቤቶች በረት የተዘጋባቸው መሆናቸውን እያስተዋለ ሁሉም ዝም ብሏል።

በየጊዜው የተሞከረብንንና የተቃጣብንን የእብሪተኛ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና ተስፋፊዎችን ወረራ በመመከት እያሳፈረ ተከብሮ የኖረ ሕዝብ የወያኔ ቅኝ ሆኗል።

## ክፍል ፩

# ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት
# መቃረቢያ፣ ዋዜማና አጥቢያ

# ምዕራፍ አንድ

# የአብዮቱ መቃረቢያ

በመግቢያው ላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያቶች ከውጪ ከተሰነዘሩባት ጥቃቶችና ወረራዎች ይልቅ ከፋኛ የተፈተነችው፣ ለብዙ ዘመናት ሰላም እልባ የሆነችውና ሕዝቡን ለመሪር ስቃይ የዳረጉት ሁኔታዎች በተደጋጋሚ የተከሰቱት በሃገር ውስጥ በየአካባቢው መሣፍንቶችና ባላባቶች አንዱ በሌላው ላይ ለመስፋፋት፣ አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠር፣ ለማስገበርና ለማጠቃለል በሚያደርጉት መራኮት ነበር።

ኢትዮጵያ ጀምራው በነበረው ልማት፣ ግንባታና ለጥንታዊ ሥልጣኔዋ መክሰም ምክንያት ይሁኑ እንጂ በታሪክ በባዕዳን ቀጥተኛ ወረራ የተሸነፈችበት፣ ህልውናዋ የተፈተነበትና ነፃነቷን የተገፈፈችበት ሁኔታ አልተፈጠረም። በ19ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ ኢጣሊያ ለቅኝነት የተመኘችንና ብሎም ለአምስት ዓመታት ህልውናችንን የገሰሰችበት ሁኔታ የተፈጠረው ከውስጥ በመነጨ የራሳችን ችግርና ድክመት እንጂ በኢጣሊያ ብርታት አልነበረም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ታታሪነቱ በሥራ ባህሉ ጥሮና ግሮ ያፈራውን ጥሪትና አገሩ በተፈጥሮ የታደለችውን የጋራ ሀብት ለልማትና ግምባታ አውሎ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ባለቤትና ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም። በርካታ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች በየጊዜው እየተከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶችን በማሰናከልና በመግታት የረጅም ዘመን ታሪኳን ያህል እንዳታድግ አቀርቅዟታል።

በሌሎች አገሮች እንደታየው በኢትዮጵያ ያለውን የሰውና የቁሳቁስ ኃይል አሰባስበውና አቀናጅተው በመምራት ለአገሪቱ ሥልጣኔና እድገት ፋናወጊ መሆን የነበረባቸው የሕዝቡ መሪዎች ነን የሚሉት መሣፍንት፣ መኳንንትና ካህናቱ የአገሪቱ አንድነት፣ ሰላምና የሕዝቡ ማህበራዊ እድገት እክል መሆን ብቻ ሳይሆን የአዲስ ሀሳብ፣ የመሻሻልና የለውጥ ተፃራሪ ናቸው።

ከዚህ አሳዛኝ ሁኔታ አኳያ በአንፃራዊ አመለካከት ሲታይ የዳግማዊ ምኒልክ ዘመን መንግሥት ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ያልታየ የሰላም፣ የፀጥታና የመረጋጋት ዘመን ነበር። የዘመነ መሣፍንት የሁከት፣ የሽብርና የሕዝብ ሰቆቃ ዘመን አልፎ የኢትዮጵያ ሕዝብ በውስጥ ሥርዓት አልበኞችና በውጭ ወራሪዎች ላይ አኩሪ ድል ተቀዳጅቶ ደህንነቱንና ሰላሙን ለማስከበር መብቃት ብቻ ሳይሆን በፅኑ መሠረት ላይ አንድነቱን ያጠናከረበት አስተማማኝ ማዕከላዊ መንግሥት ለመመስረት የቻለበት ጊዜም ነበር።

የአገሪቱ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ የግዛት አንድነት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና አግኝቶ የተከበረበት፣ ከዘመኑ የዓለም መንግሥታት ጋር ከሺህ ዓመታት በኋላ አዲስ ግንኙነት የፈጠረበትም ጊዜ ነበር። በጉልታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የካፒታሊስት

ጠባላት ከነበሩት መሣፍንት ጋር ሲመዘኑ የአገሪቱን ዘመናዊ ምሁራን ሀሳብ የሚደግፉና የሚቀበሉ የለውጥ አራማጅ ስለነበሩ ከልጅ እያሱና ከንግሥት ዘውዲቱ ጋር ባደረጉት የሥልጣን ትግል ዘመናዊው ምሁራን በአብዛኛው ለእሳቸው ወግነው ለድል አበቋቸው።

በሃገር አቀፉ ፀረ-ፋሽስት የአርበኝነት ተጋድሎ የገነት የጦር ትምህርት ቤት ምሩቅ መኮንኖች፣ እጩ መኮንኖችና የአገሪቱም ሲቪል ምሁራንን አጣምሮ ጥቁር አንበሳ በመባል የተመሠረተው፣ በዘመናዊ የደፈጣ ውጊያ ስልት በአፍሪካ የመጀመሪያው የሆነው የአርበኞች ጦሩ ከፀረ-ፋሽስት ትግሉ ጋር ኢትዮጵያ የሪፐብሊክ መንግሥት አመራር የምትቀዳጅበትን ዓላማ አንግቦ የተነሳ ቢሆንም በትግሉ ሂደት አብዛኛዎቹ አርበኞች በመሰዋታቸውና ፋሽስት ኢጣሊያም በመሸነፉ ከሞት የተረፉት ቀደም ብለው ለአፄ ኃይለሥላሴ ሲሰጡ የነበረውን ድጋፍ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያም ቀጠሉ።

የኢትዮጵያን ህልውና፣ ሰላምና ደህንነት፣ ልማት፣ ግንባታ፣ አጠቃላይ እድገትና ሥልጣኔ ከማዕከላዊ መንግሥት ህልውናና ጥንካሬ ጋር አስተሳስረው የሚያዩት የኢትዮጵያ ዘመናዊ ምሁራን በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብዙ ጠብቀው ነበር። የአውሮፓን ሕዝብ የኑሮ እድገት ባጠቃላይ የእንግሊዝ መንግሥት የሚመራበት የካፒታሊስት ሥርዓት በተለይ ለአምስት ዓመታት በቅርብ ሲከታተሉ የቆዩ በመሆናቸው፣ የቤተመንግሥቱን ወግና ልማድ አድናቂ በመሆናቸው፣ የዘውዳዊውን የቡርዥዋ ዲሞክራሲያዊ አመራር ይከተላሉ፣ ርዕሰ ብሔርነታቸውን ይዘው መስተዳድሩን ለሕዝቡ ይሰጣሉ የሚል ግምት ነበራቸው።

የሚያሳዝነው እንደተጠበቀው ሳይሆን ኢጣሊያኖች ያፈረሱትን የጉልታዊ ሥርዓት ጥና አቀንቃኝ የሆነውን የመሣፍንቱን መደብ ከያለበት እየፈለጉ በየጉልቱና በየአባቱ ጉልት መልሰው ሲተክሉት ያስተዋለው፣ ወገኑን ከአሳፋሪው ድህነት፣ አገሩን ከኋላ ቀርነት ለማውጣት በታላቅ ጉጉትና ስሜት የተነሳሳው ኢትዮጵያዊው ብሔርተኛ ምሁር በሙሉ ወጅጉ አዝኖ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ወደ ኋላ ተመልሶ የጉልተኛ ገባር፣ ጢሰኛና ጭሰኛ ከሆኑት ገበሬዎች ሥራ አጥ ሆኖ ስለበዘነ ከየቤቱና ከየጎዳናው በወታደር እየታፈነ ወደ አዶላና ወደየመሣፍንቱ እርሻ የግዴታ ሥራ ከተጋዘው ሠራተኛ መደብ፣ ስደተኛና ባንዳ ሊሾምና ሲሸለም በደማላትና በሞተላት ሃገር ባይተዋር የበይ ተመልካች ሆኖ ከተገለለው አርበኛ ጋር አንገቱን ደፋ።

በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ የተፈራረቁትን መሪዎቻችንን አንዱን ከሌላው ማነፃፀር ከተፈለገ ጊዜ በታና የተለያዩ ሁኔታዎች ፈቅደውላቸው በእያሌ ምሁራን በመከበባቸው፣ በባዕዳን አማካሪዎች ከመረዳታቸውም ሌላ በራሳቸው አነሳሽነትና የግል ጥረት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለአገራቸው ብዙ ቁም ነገሮችን አከናውነዋል። በእሳቸው አመለካከት ለራሳቸው ያላቸው ግምት ግን ሌላው ሰው ከሚሰጣቸው እጅግ የላቀ ነው። ይህ አመለካከታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዘመነ መንግሥታቸው አከናወንኩ ከሚሏቸው ሥራዎች ሁሉ የላቀውን ግምት የሚሰጡትና አዘውትረው የሚናገሩት 'በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንም ያላደረገውን፣ ማንም ሳይጠይቀን በፈቃዳችን ሕዝባችንን ሕገ መንግሥት ለግሰነዋል' ለሚሉት ነው።

ይህ በእጅጉ የሚኮሩበት የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ በመሆኑና እንዲሁም በሕገ መንግሥትነቱ ሊሰጠው ከሚገባው ግምት ብቻ ሳይሆን በዚህ 'ሕገ መንግሥት አማካኝነት አሮጌውን ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር አፍርሼ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሰለጠኑት የዓለም ሕዝቦች ተራ በማሰለፍ የዘመናዊ አስተዳደርና

ዲሞክራሲ ባለቤት አድርጌዋለሁ' ብለው በማመን ነው። ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ሕገ መንግሥት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ሁሉ ስለ ህገ መንግሥቱ ያለው አስተያየት አንድ ወይም ተመሳሳይ ነው ባይባልም ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አስተያየት ጋር በእጅጉ የተራራቀ ነው።

ከፊሉ ባርነትንና የባርያ ንግድን የሚያወግዝ፣ የማዕከላዊ መንግሥትን ሥልጣን የሚያጠናክርና በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነትን የሚፈጥር እስከሆነ ድረስ የተጠበቀውን ያህልም ባይሆን መሻሻል አስገኝቷል በማለት መለስተኛ ድጋፋቸውን ሲሰጡ የተቀረው በተለይም ምሁራኑ ከደጃዝማችነት ማዕረጋቸው ጀምሮ አፄ እስከ ተባሉበት ጊዜ ድረስ ብቸኛ ተራማጅና የለውጥ አራማጅ መሥፍን በማለት ከጎናቸው ተሰልፎ የታገለው ክፍል በጣም አዝኖ ተስፋ በመቁረጥ ፊቱን ያዞረባቸው፣ 'እኛን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድተው ህገ መንግሥቱን ለራሳቸው መለኮታዊ ሥልጣን፣ ለመሣፍንቱና መኳንንቱ መደባዊ ጥቅም ሕጋዊ መደላድል አደረጉት' በማለት ነበር።

በ1943 ዓ.ም አፄ የተባሉበትን ሃያኛውን የንግሥ በዓላቸውን ባከበሩበት ዕለት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር፣ "አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከቀድሞው በተሻለ አዲስ ሕገ መንግሥት ትመራለች" በማለት ቀስቃሽ አበረታችና ተስፋ የፈነጠቀ ንግግር በማድረጋቸው እነዚህ ቃላቶች ወደ ተግባር ተለውጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሻሻልበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል በማለት ሕዝቡ በአጠቃላይ ምሁራኑ በተለይ በከፍተኛ ጉጉትና ትዕግሥት ይሻሻላል የተባለውን ሕገ መንግሥት ለአምስት ዓመት ጠበቀ።

አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከቀድሞው በተሻለ አዲስ ሕገ መንግሥት ትመራለች በማለት ለሕዝብ ቃል ከገቡበት ጊዜ አምስት ዓመት በኋላ በ25ኛው የብር እዮቤልዩ የንግሥ በዓላቸውን ምክንያት በማድረግ የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ከወጣበት ከ25 ዓመት በኋላ ማንም ሳይጠይቃቸው በራሳቸው መልካም ፈቃድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀድሞው የተሻለ አዲስ ሕገ መንግሥት ለገሱት።

እዚህ ላይ በቅድሚያ አፄ ኃይለሥላሴ እንደሚሉት 'በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ በሆነው የሐምሌ 16 ቀን 1923 ዓ.ም ሕገ መንግሥት አማካኝነት አሮጌውን ትልታዊ ሥርዓት አፈራርሼ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሰለጠኑት የዓለም ሕዝቦች ተራ በማሰለፍ የዘመናዊ አስተዳደርና ዲሞክራሲ ባለቤት አድርጌዋለው' ስለሚሉት ጉዳይ እውነትነት የህገ መንግሥቱን የተወሰኑ አንቀጾች አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ መዳሰስ ያስፈልጋል።

እንዲሁም ይህንን ሕገ መንግሥት አምርረው የተቃወሙ ምሁራን 'እኛን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድተው ለራሳቸው መለኮታዊ ሥልጣን፣ ለመሣፍንቱና ለመኳንንቱ መደባዊ ጥቅም የሕግ መደላድል አደረጉት' ያሰኛቸው ምክንያት በእውነት በህገ መንግሥቱ ውስጥ ተንፀባርቆ ከሆነ ይህ እንከን በሁለተኛው ሕገ መንግሥት ውስጥ ምን ያህል ተሻሽሏል ብለን ለምናነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይኖርብናል።

በቅድሚያ አፄ ኃይለሥላሴ ማንም ሳይጠይቃቸው በራሳቸው መልካም ፍቃድ ሐምሌ 16 ቀን 1923 ዓ.ም ልደታቸውን ምክንያት በማድረግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የለገሱት የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት እሳቸው እንደሚሉት የቱን ያህል ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት እንደሆነና የህገ መንግሥቱ ባለቤት የሆኑት ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ራሱ ምን ያህል ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እንደነበር ለማወቅ የተቋቋመውን የሕዝብ ምክር ቤት ተብዬውን ፓርላማ ይዘት እንመልከት፦

1ኛ/ ህገ መንግሥቱንና የሱም አካል የሆኑትን ማናቸውንም መሰረታዊ ጉዳዮች ለማጽደቅም ሆነ ለመሻር መብትና ሥልጣን የንጉሠ ነገሥቱ ብቻ መሆኑን የሚያብራራው አንቀጽ 6 የዘውዱን አወራረስ በተመለከተ "በሕዝቡ መካከል ያለመግባባትን ለማስወገድና አገሪቱን ከጥፋት ለማዳን ዘውዱ ለዘላለም ከአፄ ኃይለሥላሴ ቤተሰብና ዘር እንዳይወጣ" በህገ መንግሥቱ የተወሰነ መሆኑን ይገልጻል።

2ኛ/ ፓርላማው በውስጡ ሁለት ንዑሳን ምክር ቤቶች አሉት። እነዚህም፣ አንደኛው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ሲሆን ሁለተኛው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት የሚባለው ነው። የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 59 'የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አባላት ሀሳብ ይበልጥ ተቀባይነትና ተደማጭነት ስላለው ምክር ቤት የላቀ' የበላይ ምክር ቤት መሆኑን ያብራራና 'የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ተመራጮች ከልዑላንና ከመሣፍንቱ' ማዕከል ብቻ መሆናቸውንና እነሱም የሚመረጡት 'በንጉሠ ነገሥቱ ብቻ' መሆኑን ይገልፃል።

3ኛ/ የዝቅተኛው ማለትም የሕግ መምሪያው ምክር ቤት አባላት ስለሚሆኑት ተመራጮችና እንዲሁም መራጮች የሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 ሲያብራራ፣ 'ሕዝቡ ራሱን ችሎ ተወካዮቹን በቀጥታ መምረጥ እስኪችል ድረስ የመምረጥ መብቱ በየአካባቢውና በየአጥቢያው ላሉ መኳንንት፣ ካህናትና የጦር አበጋዞች ወይም ሹማምንት' የተሰጠ መሆኑንና በዚህ ሁኔታ የሚመረጡት የሕግ መምሪያው ምክር ቤት አባላት 'ለንጉሠ ነገሥቱና ለመራጮቻቸውም ለሚኖራቸው ታማኝነት ዋስትና ይሆን ዘንድ ለምርጫ ተወዳዳሪው ግለሰብ የመሬት ከበርቴ መሆን እንዳለበት' ይደነግጋል።

4ኛ/ በዚህ ሁኔታና መስፈርት ለሁለቱም ንኡሳን ምክር ቤቶች የተመረጡት አባላት በግልም ሆነ በወል፣ ለአስቸኳይም ሆነ መደበኛ ስብሰባ ለመጥራት ሥልጣን እንደሌላቸውና ይህ ሥልጣንና መብት 'የንጉሠ ነገሥቱ ብቻ' መሆኑን ያስረዳል።

የህገ መንግሥቱን የተለያዩ ክፍሎች ገላልጦ በዝርዝር ማየት ሳያስፈልግ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው አንቀጾች የሚያስገነዝቡን አፄ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያን ሕዝብ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ባለቤት ማድረጋቸውን ሳይሆን የቱን ያህል እንደናቁትና እንደካዱትም ነው።

ዋናው ጥያቄ ከ25 ዓመታት በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የለገሱት ሁለተኛው ሕገ መንግሥት ከመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ምን ያህል ተሻሽሏል? ነው። አዲሲቱ ኢትዮጵያ የምትመራበት የተሻሻለ ተብሎ ከ25 ዓመታት በኋላ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተሰጠው ሕገ መንግሥት ከመጀመሪያው የተሻለ የተባለበት ዓብይ ምክንያት፣ ሕዝቡ በእጅ አዙር ፊውዳል ጌቶቹና ገዥዎቹ ተወካይ ተብለው የሚመርጡበት ሁኔታ ታርሞ የምርጫው ሕግና የተመራጮቹም መመዘኛ ሳይሻሻል ሕዝቡ ራሱ ተወካዮቹን እንዲመርጥ የተፈቀደለት መሆኑ ነበር።

በመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ለሕዝቡ የሚመርጡለት ተወካዮቹ መሆናቸው ቀርቶ ራሱ እንዲመርጥ መብት የተሰጠው ቢመስልም፤ በተመራጮች መመዘኛ ሕግ መሠረት መመረጥ ያለበት የታወቁ የመሬት ከበርቴዎች እስከሆኑ ድረስ ለሕዝቡ የተፈቀደው የሚፈልጋቸውን ተወካዮች እንዲመርጥ ሳይሆን ፊውዳል ጌቶቹን ነበር።

የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሻሻለ ለተባለው ሁለተኛው ሕገ መንግሥት የነበራቸው አስተያየት እንደ መደብ ጀርባቸውና እንደ ማህበራዊ ንቃታቸው የተለያየ ነበር። ከጉልተኞች ገዥ መደብ የሚወግነው ወግ አጥባቂና ኋላቀሩ የሕብረተሰብ ክፍል በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱ ተወካዮቹን የመምረጥ መብት ማግኘቱን ታላቅ የፖለቲካ ለውጥ

አድርገው በማየት ያደነቁ እንደነበሩ ሲታወቅ የተሻለ ማህበራዊ ንቃት ያላቸው ጥቂ
አርበኞችና ምሁራን ደግሞ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአፄ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ በአመጽ
ወደ ማስወገዱ አቅጣጫ አመሩ።

ከእነዚህ መካከል አንዳንድ ደፋሮች ንጉሡን፡ “ንጉሡ ነገሥትነትዎና ርዕሰ
ብሔርነትዎ እንደተከበረና እንደተጠበቀ ሆኖ መስተዳደሩን ለሕዝቡ በመስጠት እርስዎ
ለሕግ ተገዝተው ይኑሩ” በማለት በገሃድ ጠይቀው ውጤቱ ግን ዘብጥያ መወርወር ሆነ።

በአፄ ኃይለሥላሴ ፍትህ አልባ አስተዳደር በመበደላቸው ብቻ ሳይሆን ተሻሻለ
በተባለው የሕገ መንግሥት ይዘት የተበሳጩ አርበኞችና ሃገር ወዳድ ምሁራን በተለያዩ
ጊዜያቶች የተለያዩ ግን ያልተሳኩ አመጾችን ሞክረው በሞት፣ በእሥራትና በግዞት
ቢመናመኑም ውሎ አድሮ የእነሱ ጥረትና መስዋዕትነት የ1953 ዓ.ም ወታደራዊውን
አመጽ አስከተለ።

በታህሣስ 1953 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብራዚልን ሲጎበኙና በአዲስ አበባም
እነጀነራል መንግሥቱ ነዋይ የመፈንቅለ መንግሥት አመጽ ሲያደርጉ እኔ የሃያ ዓመት
ምክትል የመቶ አለቃና በኦጋዴን ክልል በዋርዴር አውራጃ ይኖር የነበረው የዘጠነኛ እግረኛ
ሻለቃ ጥብቅ የዘመቻና የትምህርት መኮንን ነበርኩ።

የእኔ ሻለቃ የበላይ አካል የሆኑት ከሦስተኛው ክፍለ ጦር መምሪያ ከዘጠነኛው እግረኛ
ብርጌድ መምሪያ አዲስ አበባ ስለተጀመረው አመጽ አንዳችም ነገር ሳይገልጹልን ጦሩ
‘በአንደኛ ደረጃ ተጠንቀቅ ተዘጋጅቶ ትዕዛዝ እንዲጠባበቅ’ የሚል መልዕክት ብቻ ደረሰን።

ይህ መልዕክት በአዲስ አበባ ስለተጀመረው አመጽ ወይም በኦጋዴን ግምባር የሶማሊያ
መንግሥት ሊፈጥር ስለሚችለው ችግር ስለመሆኑ በግልጽ የተረዳነው ነገር አልነበረም።
በአዲስ አበባ አመጹ በተጀመረበት ዕለት እንደተለመደው ማለዳ ተነስቼ የሻለቃው ተነጣይ
ሻምበሎችንና የመቶዎች ጥበቃ ከሚያካሄዱባቸው ከገላዲንና ከቦህ ወረዳዎች እንዲሁም
አስማአኔ ከሚባለው ስፍራ በሰላም ማደራቸውን በየዕለቱ በወታደራዊ ራዲዮ ሪፖርት
ስለሚያደርጉ እነዚህን ሪፖርቶች ለመመልከት ጽሕፈት ቤቴ ገባሁ። ከሻለቃው የመገናኛ
ኃላፊ የበታች ሹም መልዕክቶችና ከአጎራባች የወገን ጦር ክፍሎች የምንለዋወጣቸውን
መረጃዎች እንዲያቀርቡልኝ ስጠይቅ፡ “በአዲስ አበባ የምድር ጦር መገናኛ መምሪያ የሌሊት
ተረኛ ከሆነ ጓደኛዬ ጋር ግንኙነት አድርጌ ነበር፤ የአዲስ አበባ ሁኔታ ጥሩ አይደለም።
የክብር ዘበኛ ሠራዊት ከተማውን በከፊል በቁጥጥሩ ስር አድርጎ አያሌ የመንግሥቱን
ባለሥልጣኖች ከእነአልጋ ወራሹ ጭምር አስሯል እየተባለ ይወራል። የጦር ንቅናቄና
የሕዝብ ትርምስ ይታያል ብሎ ነገረኝ” ካለ በኋላ የጠየኩትን መረጃዎች አቀረበልኝ።

የጠዋቱን የራዲዮ ፕሮግራም ጠብቄ ስከፍት በወታደራዊ ሙዚቃ ታጅቦ አንድ ሰፋ
ያለ አስተያየት ስለኢትዮጵያ ድህነት፣ የፍትህ ጉድለት፣ የመንግሥቱን ባለሥልጣኖች
ንቅዘት፣ የንጉሠ ነገሥቱን ድክመትና የአመራር ጉድለት የሚተነትን መግለጫ ካቀረበ በኋላ
ተከታታይ ዜናዎችንና መግለጫዎችን ሕዝቡ በንቃት እንዲከታተል አሳስቦ በወታደራዊ
ሙዚቃ የጠዋቱ ዜና አበቃ።

የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ የተነተነውና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አመራር በከባድ
የነቀፈው መግለጫ ምን ለማድረግ እንደ ታቀደ የሚያብራራ ስላልነበረ የሚከተለውን
መግለጫ ከመጠበቅ በስተቀር አንድ የተቋጨ ሀሳብ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ቢሆንም
የመግለጫው ይዘት መፈንቅለ መንግሥት እንደሆነ ለመረዳት አልተሳነንም።

የሻለቃውን አዛዥ "ራዲዮ አዳምጠዋል ወይ?" ብዬ ለመጠየቅ ወደ ጽሕፈት ቤታቸው ስሄድ መኖሪያ ቤታቸው ሆነው እንዳዳመጡ ተገነዘብኩ። በሰባት ሰዓቱ ዜና፡ ልጋ ወራሹ የአባታቸውን ሥልጣን እንደወረሱ፣ ሹመትና ሽረቱ ሌላው ሁሉ በተከታታይ ጋጸ በጦር ኃይሉ የእዝ ጠገግና የግንኙነት መስመር ስለሁኔታው የሚያስረዳ ከበላይ ላ የደረሰን አንዳችም ነገር አልነበረም።

ስለዚህም አልጋ ወራሹ በራሳቸው አነሳሽነትና መሪነት የሚያካሄዱት መፈንቅለ ንግሥት ወይስ የመገናኛ ባለሙያዎቹ እንዳሉት ታስረውና ተገደው የሚናገሩት ይሆን? ጊሉ ጥይቄዎች ነበሩን። መግለጫውን የሚሰጡትና መፈንቅለ መንግሥቱን የሚያራምዱትስ ግን ናቸው? በመፈንቅለ መንግሥቱ ውስጥ መላው የጦር ኃይል አካላት አሉበት ወይስ ቦር ዘበኛው ሠራዊት ብቻ? ይህ ደግሞ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ቅርብ ጓደኞቼ ጋር ስናውጠነጥን ነበር።

በአገራችን የመንግሥት ለውጥን ያህል ነገር ሲደረግ በጦር ኃይሉ የእዝ ጠገግ ንም ነገር ያልተገለጸልን መከፋፈልና ምናልባትም የሥልጣን ትግል ተፈጥሮ የጦር ኃይሉ ሬዎች ተቃውሟቸውን ወይም ድጋፋቸውን መግለጽ በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኙ ናል ወደሚልም ሀሳብ አምርተን ነበር።

አብረውን ያሉት የጦር አለቆቻችን የበላይ አካልን ጠይቀውም ሆነ በእራሳቸው ግምት ኮንኖችም ሆነ ለጦሩ አንዳችም ነገር ለመተንፈስ ፈቃደኞች አልነበሩም። ይህም ዝምታ ጸ ግልጽ ስላይደለ ወይም እራስን ለመጠበቅ ሲባል ከፍርሀት የመነጨ ጥንቃቄ መሆኑ ለመኮንኖቹ ግልጽ ቢሆንም ለጦሩ ግልጽ ስላልነበረ አዛዦቻችን እንዴት አያነጋግሩንም ጊል ጥያቄ አንስቶ ነበር።

ከወታደራዊ ራዲዮ መገናኛ በስተቀር በኦጋዴን የስልክ መስመር ስለሌለ እንደሌሎቹ ር ክፍሎች ከመሀሉ ሃገር ቀርቶ በኦጋዴን ካለው አጎራባች ጦር ጋር የምንገናኝበት ሁኔታ አልነበረም። በአገሪቱ ራዲዮ መፈንቅለ መንግሥት አራማጆቹ የሚሰጧቸውን መግለጫዎች ያዳምጠው ጦር የመግለጫዎቹ ይዘት እንከን የማይወጣላቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ዲሱ መንግሥት ለሠራዊቱ ደሞዝ ስለጨመረ ለውጡን ሠራዊቱ በመደሰት ደግፏል።

በዚህ መካከል የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን፣ የገነትና ሐረር የጦር አካዳሚ መኮንኖችና እጩ መኮንኖች 'ለአዲሱ መንግሥት ድጋፋቸውን ጡ' የሚል መግለጫ ሲነገር የኔ ሻለቃ መኮንኖችና ጦሩ ተቅበጠበጡ። በእንዲህ ያለ ኝ የፖለቲካ ጉዳይ በሚደመጠው መደሰት ብቻ ሳይሆን ያንን ተግባር ለሚያከናውነው ችም ግልጽ ድጋፍ መስጠት ወሳኝነት ስለነበረውና እኛ ግን ይህንን ማድረግ ባለመቻላችን ጨነቅን።

የሻለቃው የመገናኛ ሠራተኞችና ምስጢር ፈቺዎች በእኔ እዝ ስር ስለነበሩ በምስጢር ኦጋዴን ካሉ አጎራባች የጦር ክፍሎች ጋር ባደረግነው ግንኙነት እንደተረዳነው በኦጋዴን ሰፈረው ጦር በሙሉ የለውጡ ደጋፊ ነበር። በአዲስ አበባና በአካባቢው ካሉት በስተቀር ተቀረውም ጦር አቋም ከኛ የተለየ አልነበረም።

የ1953 ዓ.ም ንቅናቄ ታሪክ እስከ ዛሬ ምስጢር ሆኖ የቀረና ከነጄነራል መንግሥቱ፣ ቶ ግርማሜና እንዲሁም ከእድምተኞቻቸው ጋር የተቀበረ ይመስለኛል። መፈንቅለ መንግሥቱን የወጠኑት ጄነራል መንግሥቱና ጥቂት የክብር ዘበኛ መስመራዊ መኮንኖች ቻ ናቸውን? ሌሎች የጦር ኃይሉ ከፍተኛ መኮንኖች አመጹን አብረው ወጥነው የክብር ኛ መኮንኖችን የማይወጡበት ወጥመድ ውስጥ ከተቷቸው ወይስ በሥልጣን ክፍፍል

ከዴቸው? ጀነራል መንግሥቱ ነዋይ ብቻቸውን አንድ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ብቻ ይዘው ያለ ኢትዮጵያ የጦር ኃይልና ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ሥልጣን ማማ ላይ ወጥቼ እቀመጣለሁ ብለው ያስባሉን? የልዑል ራስ እምሩ ጠቅላይ ሚኒስትርነትና የጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ የመከላከያ ሚኒስትርነት እንደ አልጋ ወራሹ በመሣሪያነት ለመጠቀም ወይስ ለይስሙላ የተደረገ ይሆን?

መፈንቅለ መንግሥቱ ሲደረግ በቅድሚያ ለውጡን ተግባራዊ የሚያደርጉት የአገሪቱ የጦር ኃይሎች ሲሆን በሙሉ ባይሆን በከፊል እንኳን የማስተባበር ሥራ እንዴት ሊቀር ወይም ሊዘነጋ ይችላል? የጦር ኃይሉ በከፊል እንኳን ሳይተባበር በአንድ ያውም 'የንጉሥ ተቀላቢ' እየተባለ በሚጠላ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር እንዴት ብልሁ ጀነራል መንግሥቱና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ግርማሜ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት መገርሰስ ይቻላል ብለው ይህንን ያህል ስህተት ይሰራሉ?

በረቀቀ ስልት፣ በሰለጠነ አነስተኛ ሠራዊትና በሕዝብ ድጋፍ ይህንን ተግባር መፈጸም ይቻላል። እነጀነራል መንግሥቱ በዚህ መልክ ለውጥ ለማምጣት አስበው ከነበረ ለምን በአዲስ አበባ ከተማ ተበታትነው የሚኖሩትን ተቃዋሚ የጦር ኃይሉን ከፍተኛ መኮንኖች በቅድሚያ ለቃቅመው አላሰሩም?

ጀነራል ፅጌ ዲቡ የእድሜያቸውን አጋማሽ ያገለገሉበትን የጦር ሠራዊት አይነት፣ መጠንና ገበና በሚገባ የሚያውቁ ጀነራል ሆነው ሳለ ጥቂት ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ይዘውና አሰልፈው እንዴት ከነጀነራል መንግሥቱ ጋር ወገኑ?

የክብር ዘበኛ መኮንኖች ጥቂቱን ሠራዊታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ አደባባዮችና ጎዳናዎች ላይ ከማንሸራሸር ይልቅ ባነስተኛ ጦር እንደ ኮብራ እባብ ተወርውረው ደብረ ዘይት የሚገኘውን የአየር ኃይል ሠራዊት በመቆጣጠርና በማንቃነቅ በናዝሬት ከተማ አውላላ ሜዳ ላይ የቆሙትን ታንኮች ለምን አላስደበደቡም?


ጥቂት የክብር ዘበኛ መስመራዊ መኮንኖች ከብዙሃኑ የጦር ኃይሉ ጀነራሎች ጋር በተፋጠጡበት ጊዜ በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር የነበረው ኮሪና ፓትርያኩ በሁለቱ ጎራዎች መካከል እየተመላለሱ ለማደራደር ያደረጉት ሙከራ በምን የግልግል መሠረተ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነበር?

ፓትርያኩ ወዲያው አቋማቸውን ለውጠው ከጦር ኃይሉ ጋር በመሰለፍ የክብር ዘበኛውን ሠራዊት ሲያወግዙ አምባሳደር ኮሪ ንጉሥ ነገሥቱ እንደተመለሱ ከኢትዮጵያ አምባሳደርነቱ ብቻ ሳይሆን ከመንግሥት ሥራውም ለምን ተባረረ? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች እስከ ዛሬ መልስ አላገኙም።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት መፈንቅለ መንግሥቱ በተጀመረበት ዕለት ከሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያና በስሩ ላሉ እግረኛ ብርጌዶችና ሻለቆች ትዕዛዝ ሲሰጥ ለእኔም ለዘጠነኛ እግረኛ ሻለቃም በደረሰን 'በአንደኛ ደረጃ ተጠንቀቅ ላይ ሆናችሁ ትዕዛዝ እንድትጠባበቁ' በተባለው መሠረት ጦራችን በአንደኛ ደረጃ ተጠንቀቅ ላይ ነበር።

የክፍሉ የዘመቻ መኮንን እንደመሆኔ ቀንም ሆነ ሌሊት ከበላይ አካል ትዕዛዝ ሊመጣ ስለሚችልና የሻለቃ አዛዤን ከማንቃት ባሻገር ከተፈለገ በሚሰጠኝ ትዕዛዝ መሠረት ጦሩን ወደ ተፈለገበት በአስቸኳይ ለማንቀሳቀስ ይቻል ዘንድ አዳሬ በዘመቻው ጽሕፈት ቤት ነበር።

ረዳቶቼ የዘመቻውና የመገናኛው የበታች ሹሞች፣ የመገናኛ ምሥጢር መስጣሪውንና ፈቺውን ባለሙያ ጨምሮ የሚያድሩት ከኔው ጋር በዘመቻ ጽሕፈት ቤት አካባቢ ነበር።



ጄነራል መንግሥቱ እና ወንድማቸው አቶ ግርማሜ ንዋይ

መፈንቅለ መንግሥቱ እስከ ከሸፈበት ጊዜ ድረስ ሌሊትም ሆነ ቀን አብዛኛው ሥራችን መፈንቅለ መንግሥቱ ምክንያት የአገሪቱ የጦር ኃይል አካል የሆኑ የተለያዩ የጦር ክፍሎች የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች፣ አንዱ የጦር ክፍል ከሌላው ጋር የሚያደርጓቸውን የራዲዮ ግንኙነቶችና ከፀረ-መፈንቅለ መንግሥቱ የዘመቻ መምሪያ ለበታች ክፍሎች የሚተላለፉትን ትዕዛዞች እየጠለፍንና የተመሰጠሩባቸውን ቁልፎች እየሰበርን ማናቸውንም ሁኔታዎች በዝርዝር እንከታተል ስለነበረ መፈንቅለ መንግሥቱ የከሸፈበትን ሁኔታና የአማጺያኑን ውድቀት ለመረዳት ችለናል።

መፈንቅለ መንግሥቱን ለማክሸፍ የተሰለፈውን የጦር ኃይል የሚመሩት ሌ/ጄነራል መርዕድ መንገሻ የእዝ መምሪያ ማዕከል ወደ ማጥቃት ከመሸጋገሩ በፊት በክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ቢጠቃ ጥቃቱን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ደቡባዊውን የአዲስ አበባ ክልልና እንዲሁም የጦር ኃይሉን ድርጅታዊ ተቋሞች ለማስከበር ከአዲስ አበባ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች የተውጣጣ አንድ ግብረኃይል አደራጅቶ በመከላከል ለውጊያ ስልት እንዳሰለፈ፣ ከዚያም በሁለተኛ ምዕራፍ ከነገሌና ከጅማ ወደ ደብረ ዘይት በአየር ኃይሉ የመጓጓዣ አውሮፕላኖች፣ ከድሬዳዋ በምድር ባቡር ወደ ደብረ ዘይት ጦር መንቀሳቀሱን እናውቅ ነበር።

መፈንቅለ መንግሥቱ እንደተጀመረ ሁለቱ ተፃራሪ ኃይሎች አንዱ ሌላውን አማጺ፣ ከሀዲና ወንበዴ እያሉ ስለሚጠሩ ማን በማን ላይ እንዳመጸ ለማወቅ የነበረብን ችግርም የተፈታው የጄነራል መርዕድ ማዘዣ ከበታች ክፍሎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት፣ በሚሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ አማካኝነት ነበር።

የጄነራል መንግሥቱ ነዋይ የእዝ መምሪያ የጦር ኃይሉ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ማወቁን ወይም የሚከታተል መሆኑን በጣም እጠራጠራለሁ። ቢያውቅም በአየር ኃይልና ሞተራይዝድ በሆነው የምድር ጦር ጣልቃ የመግባትና የመግታት አቅም ስላልነበረው ምንም

ለማድረግ አይችልም ነበር። በእነኚህ ምክንያቶችና ለመሰናዶ ባገኙትም በቂ ጊዜ ተጠቅመው እነጄነራል መርዕድ ከየክልሉ አጓጉዘው ደብረ ዘይት ላይ ያካበቱትን እግረኛና ታንከኛ ጦር ወደ አዲስ አበባ ካመጡ በኋላ አዲስ አበባ ከነበረው ግብረ ኃይል ጋር በማቀናጀት በሁለቱ ግብረ ኃይሎች ሁለት የተለያዩ የማጥቃት እቅድ ነደፉ።

በአመዛኙ ቀላል የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎችን የታጠቀውና መጠነ ሰፊ የሆነውን የአዲስ አበባ ግብረ ኃይል፣ በአዲስ አበባ ከተማ የተለዩ ክልሎች ለጥበቃ የተሰማራውን የክብር ዘበኛ ጦር እያደነ ሲያጸዳ፣ በአየር ኃይል በከባድ መሣሪያዎችና በታንኮች የተጠናከረው ግብረ ኃይል እነጄነራል መንግሥቱ የእዝ መምሪያቸው አድርገውታል፣ ብዙ የክብር ዘበኛ ሠራዊት መሽጎበታል ወደተባለው ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት በማምራት ጥቃት ሲሰነዝር በጣም ጥቂት ግን ቆራጥ ጀግኖች መሪዎቻቸውን ትተው ላለመሄድ በያዙት ቀላል መሣሪያ ታንኮችን ለመከላከል ካደረጉት ሙከራ በስተቀር አጥቂው ግብረ ኃይል ገቺ ኃይል ሳይገጥመው ቤተ መንግሥቱን ስለተቆጣጠረው የአማፂያኑ ህልውና እዚሁ ላይ አበቃ።

ቀደም ብሎ የጄነራል መንግሥቱን ወታደራዊ ስልት በጥያቄ መልክ ላስቀምጥ እንደሞከርኩት መፈንቅለ መንግሥቱ ተሳክቶ የድል ባለቤት ይሆኑ ነበር ለማለት በጣም የሚያስቸግር ቢሆንም ከአዲስ አበባ በሃምሳና በመቶ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኙትን የአየር ኃይሉንና የታንከኛውን የጦር ሰፈሮች ቀድመው ተቆጣጥረው ቢሆን ኖሮ የነገሌውና የጅማው ጦሮች በየብስ ተሽከርካሪ ተጓጉዘው አዲስ አበባ እስኪገቡ ድረስ ህልውናቸው ለሳምንታት ሊቆይ ከመቻሉ ሌላ ተቃዋሚዎቹን መሣፍንታዊ ጄነራሎች በቅድሚያ ለቃቅመው ቢያስሩ ኖሮ ወታደራዊው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካውም ይዘት ተለውጦ ሌላ ታሪክ በተከሰተ ነበር።

የዘውዱ ደጋፊ የሆኑት መሣፍንታዊ ጄነራሎች የሚመሩት የጦር ኃይል መፈንቅለ መንግሥቱን ማክሸፉ ታወቀ። ወዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ አሥመራ ከተማ ገቡ የሚል ዜና ሲሰማ እኔ በነበርኩበት የኦጋዴን ክልል በተለይ በዋርዴር ከተማ አንድ ያልታሰበና ያልተጠበቀ አስገራሚና አስተዛዛቢ ሁኔታ ተፈጠረ።

በዋርዴር የነበሩ ጥቂት የፖሊስ መኮንኖች፣ ሰላማዊ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ከነጋዴው ሕብረተሰብ ከበርቴ የሚባሉ ጥቂት ግለሰቦችና ከሠራዊቱም ጥቂት ነባር መኮንኖች የሻለቃ አዛዦችንን ጨምሮ አንድ ግምባር ፈጥረው የተቀረውን በተለይም የዋርዴር አውራጃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን በምሥራቅ አፍሪካ የአንበጣ መከላከያ ዘመቻ ማዕከል የአመራር አባላት የነበሩ ምሁራንና የሠራዊቱን ወጣት መኮንኖች መፈንቅለ መንግሥቱን የደገፉ ከሀዲዎች ናቸው ተባለ። እንዳንዶቻችንን ደግሞ በስም እየጠቀሱ ወሬ ማስወራት ስለጀመሩ በመሃከላችን መከፋፈል፣ ጥላቻና አደገኛ ውዝግብ ተፈጠረ።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ውስጥ እያለን የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት በዘውድ አገዛዝ አፍቃሪነታቸው የታወቁትና በዚህም ምክንያት የምንፈራቸው ብ/ጄነራል ድረሴ ዱባለ በጄነራል ፅጌ ዲቡ ምትክ የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሲሆኑ ብ/ጄነራል አማን አንዶም የሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው ተሾሙ።

በቅርቡ ነፃነቱን ያገኘው አዲሱ የሶማሊያ መንግሥት ራዲዮ 'የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ኃይለሥላሴን በመቃወምና በመደገፍ ተከፋፍለው በመዋጋት እየተላለቁ ነው' የሚል መሠረተ ቢስ ዜና ሲያሰራጭ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ 'አገራችን ውስጥ የተፈጠረውን ጊዜያዊ ሁኔታ በመጠቀም አዲሱ የሶማሊያ መንግሥት የአገራችንን ሰላም ለማደፍረስ ሰርጎ ገቦችን ወደ አገራችን በማስገባት ችግር ሊፈጥር ስለሚችል አንደኛ ደረጃ

ጠንቀቁ እንደተጠበቀ ሆኖ መላው ትኩረታችሁ ወደ ጠረፋችን እንዲሆን’ የሚል ትዕዛዝ ኦጋዴን ላሉ የጦር ክፍሎች ሁሉ ሲሰጥ ለእኔም ሻለቃ ደረሰ።

የእኔ እናት የጦር ክፍል የሆነው ዘጠነኛ እግረኛ ሻለቃ በማዕከላዊ ኦጋዴን ውስጥ 200 ኪ.ሜ ከባቢ (ሬዲየስ) በላይ ለሆነ ክልል የጥበቃ ኃላፊነት ያለው ክፍል ነበር። ሶማሊያ መንግሥት የዜና ማሰራጫ ‘የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች እርስ በርሳቸው እየተላለቁ ነው’ የሚል መግለጫ ካወጣ ከአንድ ሳምንት በኋላ ታህሣሥ 17 ቀን 1953 ዓ.ም ወደ አንድ ብርጌድ ሠራዊት የሚገመት ቅይጥ ጦር ጨርቅ በማልበስ የዘጠነኛ እግረኛ ሻለቃ የጥበቃ ቀጠና በሆነው ክልል በዳኖት ወረዳ አስርጎ በማስገባት ድንገተኛ አደጋ ጣሉ የወረዳውን ሃያ ፖሊሶች በመፍጀቱ ምክንያት ከእኛም ሠራዊት በቃኚ ብረት ለበስ ውጊያ ተሽከርካሪዎች የተጠናከረ አንድ ብርጌድ የሚያህል ጦር ተሰማራ። በተካሄደውም ውጊያ ከኢትዮጵያ ወገን ፖሊሶቹን ጨምሮ 65 ሰው ተሰውቶ ይህንን ያህል ሲቆስልብን ሶማሊያ ወገን ከሦስት መቶ በላይ በውጊያው አውድማ የተሰው የቆጠርን ሲሆን፡ ከዚህ ላይ እንደቆሰለ ሲገመት በርካታ ቁስለኞቻቸውን በማግለል አፈግፍገው ወደ ግዛታቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ‘የሶማሊያ መንግሥት ጦር ዓለም አቀፍ ወሰናችንን ጥሶ መግባትና በመውረር ከፍያለ ጉዳት አደረሰብን’ ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት ለፀጥታው ምክር ቤት ሲያመለክት የሶማሊያ መንግሥት ደግሞ በበኩሉ ‘ዳኖት ላይ የተካሄደው ውጊያ ሶማሊያ መንግሥት ሠራዊትና በኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት መካከል ሳይሆን ከሐበሻ ኢምፔርያሊዝም ቅኝነት ነፃ ለመውጣት በሚታገሉ አርበኞችና በመንግሥቱ ወታደር መካከል ነው’ በማለት አስተባበለ።

እኔ ከጄኔራል አማን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘሁትና የተዋወቅነው በዳኖት ውጊያ ምክንያት ሲሆን ከዚያ በኋላ በቅድመ አብዮትና በድህረ አብዮት በተፈጠሩ አያሌ ሁኔታዎች በጣም ለመቀራረብ በመቻላችን በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ማግስት ጄኔራል አማን ከጡረታ ተጠርተው የአብዮቱ ተሳታፊ ከመሆን ባሻገር በተለያዩ ታላላቅ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ መቀመጥ የቻሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ጄኔራል አማን የደርግ አባልና የመከላከያ ሚኒስትር ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ካረፉም በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ ጥቂቶች ያለ ትክክለኛ መረጃ የራሳቸውን የተሳሳተ ግምትና አስተያየት ጽፈዋል፣ አውርተው አስወርተዋልም። እውነታውን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚቀርብ በመግለጽ ወደ አርእስቴ እመለሳለሁ።

በጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ የተመራው የ1953 ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥት ስኬታማ ቢሆን ኖሮ ዘውዱን አስወግደው ኢትዮጵያን ወደ ሪፓብሊካዊ መንግሥት አመራር እንደሚወስዱን ሲገመት ይህንን ማድረግ ቢሳናቸው ደግሞ ዘውዳዊውን መለኮታዊ ሥልጣን በሕግ ገድበው በዲሞክራሲያዊ የሕዝብ ምክር ቤት እንድንመራ ያደርጉ ነበር ብዬ እምናለሁ።

ከዚህ አንፃር የአመጹ ውጤት ከተከፈለው መስዋዕትነት ጋራ የማይመዛዘን መሆኑ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ታላቅ ታሪካዊ እድል እንዳመለጠው ግልጽ ነው። ቢሆንም ግን የተከፈለው መስዋዕትነት ከንቱና ፍሬ አልባ አልነበረም።

ሙከራው በዚያ ይዘት ከዚያ በፊት ያልተሞከረና በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያው ታላቅ የፖለቲካ እርምጃ ነበር። አይሞከርም፣ አይደፈርም ሲባል በነበረው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ እንደመብረቅ ወርዶ ማናጋት ብቻ ሳይሆን የጉልተኞችንም ኃይል አመናምኗል። ሕዝቡን በመቀስቀስ ዓይኑን የገለጠለት ብቻ ሳይሆን በጦር ኃይሉ

ውስጥ ያሉት የለውጥ አቀንቃኝና የሕዝብ ወገን ለሆኑ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አርአያ ከመሆን ባሻገር ጠቃሚ ትምህርትም ሰጥቶ ያለፈ ተጋድሎ ነበር።

## በጉልታዊት ኢትዮጵያ፡ ትምህርትና ተማሪው እንዲሁም አዲሱ ምሁር

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ለትምህርት ወደ አውሮፓ ተልከው የተለያዩ ሙያዎችን እየቀሰሙ በመመለስ አገራቸውን ለማገልገልና ወገናቸው ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እውቀት ለመፈንጠቅ በቅን ልቦና፣ በአንድነትና በጠንካራ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ሲታገሉ የነበሩትን ምሁራን ከቀደምቱና ከጥንቱ የቤተ-ክህነት ምሁራን ለመለየት ስል ዘመናዊ ምሁራን ማለቴ ይታወሳል።

አሁን ደግሞ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሰሜን አሜሪካና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በተደረገው የተራድኦ ውል መሠረት በተገኘው የትምህርት እድል፣ከአሜሪካና ከአውሮፓ እየተማሩ የተመለሱትንና፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲና ከተቀሩትም የአገራችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁትን ዘመናዊ ካልኳቸው ከቀድሞ ምሁራን ለመለየት አዲሱ ምሁራን ብያቸዋለሁ።

ከጥንቱ ከቤተ-ክህነት መንፈሳዊ ትምህርት በስተቀር ዘመናዊ ወይም ዓለማዊው የምንለው የአውሮፓውያን ትምህርት ጨርሶ ባልዳሰሳት ጉልታዊት ኢትዮጵያ የአውሮፓን ትምህርት ለማስገባት የተሞከረው 19ኛው ምዕተ-ዓመት መባቻ ላይ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው።

ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ ጉልታዊ ገዥ መደቦችና ቤተ-ክህነቱ የአውሮፓዊያኑን ትምህርት ከመናቅም በላይ ሃይማኖትንና መንፈሳዊ እምነትን የሚበክል የአሕዛቦች ሰይጣናዊ ትምህርት ነው በማለት ሲጠሉትና ሲያጥላሉት እንደቆዩ ይታወሳል።

የመጀመሪያው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ የተቋቋመውና ዛሬም ያለው አንጋፋው የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው። ከዚህ ሌላ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ በኤርትራና በሐረርጌ ጥቂት የአውሮፓ ሚሲዮን ትምህርት ቤቶች እንደነበሩ ይነገራል።

በግብፃውያን መምህራን በተቋቋመው የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው መማር የጀመሩት ተማሪዎች ጥቂት የመሣፍንትና የመኳንንት ልጆች ብቻ ቢሆኑም የትምህርቱ ዓላማ፣ የትምህርቱ አይነት፣ የትምህርቱ አሰጣጥ ይዘት መምህራኑን ጨምሮ ለዘለቄታው ለኢትዮጵያ እድገት የማይጠቅም የባዕዳን ባህልና ቋንቋ ቅኝ ያደረገን ብቻ ሳይሆን ዛሬ ለምንዳክርበት ኋላ ቀርነታችን አንዱ ምክንያት ቢሆንም ባለማወቅና በቅን ልቦና የተወጠነ ስለሆነ ዳግማዊ ምኒልክ የአዲስቱን ኢትዮጵያ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ተካይ ከሚያደርቸው አያሌ አስመስጋኝ ተግባሮቻቸው አንዱ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1908 ዓ.ም እንደራሴ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ለሃገር ውስጥ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት ቤቶች በጥቂት የአገራችን ክልሎችና በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ማስፋፋታቸውና ወደ ውጭ ሃገር ለከፍተኛ ትምህርት የሚላኩ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ቁጥር ለመጨመር የሰጡት ትኩረት ያስመሰግናቸዋል።

ይህንን ጅምር የእድገት አዝማሚያ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ቢያጨናግፈውም ከነፃነት ግኝት በኋላ የፋሽስቶች ስሪትና ቅሪት በሆኑ ህንፃዎች ድጋፍ ትምህርት ቤቶችን

መልሶ ለማቋቋምና ለማስፋፋት የተደረገው ጥረት አገሪቱ ለአያሌ ምዕተ ዓመታት ከቆየችበት ድቅድቅ የድንቁርና ጨለማ ጊዜ ጋር ሲነፃፀር ተቃሎ የሚታይ አልነበረም።

ሆኖም አጀማመሩ መልካም መስሎ ቢታይም በሂደት እየጎላና እየከፋ የመጣው ችግር፣ የትምህርት ቤቶች ስርጭትና እድገት ከሕዝቡ የመጠን እድገት፣ ከትምህርት ጥማትና ከአገሪቱ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር ሊጣጣም ቀርቶ ሊቀራረብ ያለመቻሉ ነበር።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአገሪቱ ለትምህርት ገበታ ከደረሱት ሕፃናት መካከል አስር በመቶውን እንኳን ለመቀበልና ለማስተናገድ ያለመቻላቸው፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁትን መቀበል ያለባቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እጥረት ብቻ ሳይሆን የነበሩትም ጥቂቶች የሚገኙት ከጠቅላላው ተገልጋይ ሕዝብ እርቀው በጥቂት የክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተሞች ውስጥ ብቻ መሆናቸው ነው።

በዚህ ምክንያት ነው በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ማግሥት የአገሪቱ መሃይማን መጠን በጥናት ሲሰላ ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘጠና ሰባት በመቶ መሃይማን ሆኖ የተገኘው። ከመደበኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሌላ ወጣቶችን ተቀብሎ በማስተናገድ በመጠኑም ቢሆን የሕዝቡን ችግር ያቃልሉ የነበሩት መለስተኛ የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ነበሩ።

እነሱም የአዲስ አበባውና የአሥመራው ተግባረዕድ ትምህርት ቤቶች፣ የእቴጌ መነን የእደጥበብ ማሰልጠኛ፣ የአዲስ አበባ የንግድ ሥራ ማሰልጠኛ፣ የአምቦውና የጅማው መለስተኛ የግብርና ኮሌጆች፣ የአዲስ አበባው፣ የሐረሩ የአሥመራውና የደብረ ብርሃኑ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ የአየር መንገድና የሲቪል አቬሽን የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ የፖሊስና የጦር ኃይሎች አካዳሚዎች ነበሩ።

ከእነዚህ ከፍ ያሉትና በዲግሪ የሚያስለጥኑት የዓለማያ ግብርና ኮሌጅ፣ የጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ፣ የባሕር ዳር መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ እና በአዲስ አበባ የተቋቋመው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነበሩ።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ሕዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ከመቀላቀሉ በፊት በዘረኛው የፋሽስት የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዲማሩ ስለማይፈቀድ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ሕፃናትና ወጣቶች በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት ቤቶችና በሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እየገቡ የሚማሩት በትግራይ፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በሸዋና እንዲሁም በተቀሩት ክልሎች ነበር።

ኢትዮጵያዊያን በአንዳንድ የውጭ አገሮች በተለይም ወደ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ካናዳ፣ ሜክሲኮ፣ ግብጽና ሊባኖስ ዩኒቨርሲቲዎች ለከፍተኛ ትምህርት መላካቸው እንደቀጠለ ሆኖ ሰሜን አሜሪካ በርከት ያሉ ተማሪዎችን መቀበል ስትጀምር የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችና የሶቭየት ሕብረትም ድጋፍ እንዲሁ ስለጨመረ በኢትዮጵያ ለምሁራን መበራከት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፈተ።

ዩኒቨርሲቲው በተቋቋመ ዓመት በጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራውን ፀረ-መንግሥት አመጽ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሰልፍ አደባባይ ወጥተው ለአማጺያኑ ድጋፋቸውን ሰጡ። ይህ ድርጊት በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ ከመሆኑም ባሻገር 'ተማሪ እንጀራው ሳሳ፣ ዳቦው አነሰ እና ወጡ ቀጠነ' ከማለት አልፎ 'በማህበር እንደራጅ፣ መማሪያና የሃሳቦች መግለጫ የሚሆን መፅሔቶችን እናዘጋጅ፣ መብት ይኑረን' ብሎ መጠየቁ በመንግሥት በኩል እንደ

ትልቅ ችግር በሚታይበት ሃገር ተማሪ በይፋ አደባባይ ወጥቶ መንግሥትን መቃወም ለጉልታዊው ሥርዓት አራማጅ ገዥ መደብ አስደንጋጭ ዱብ ዕዳ ሆነ።

የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ከሽፎ ንጉሡ ከተመለሱ በኋላ መፈንቅለ መንግሥቱን አስመልክተው ባደረጉት ሰፋ ያለ ንግግራቸው በተለይም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በተመለከተ "በብዙ ድካም ለፍተው የተከሉት ዛፍ ፍሬ ያለመስጠቱ እጅግ የሚያሳዝን ነው" በማለት ያደረጉት ንግግር ጥልቅ ቅሬታቸውን የገለፀ ነበር።

ከተማሪዎች የምረቃ በዓል ሌላ የዩኒቨርሲቲ ቀን እየተባለ በሚዘጋጀው በዓል ንጉሡ የዩኒቨርሲቲው ቻንስለር በመሆናቸው ከአገሪቱ ታላላቅ ባለሥልጣኖችና ከንጉሣዊያን ቤተሰብ ጋር በዩኒቨርሲቲው እየተገኙ ከተማሪውና ከምሁራኑ ጋር ለመቀራረብ ሙከራ ያደርጉ ነበር።

በጊዜ ሂደት ተማሪው የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ አስተዳደርና የትምህርቱን አቅርቦት ከመተቸትና ብሎም ከመቃወም አልፎ ከመንግሥት ጋር መጎናተል ጀመረ። የታህሣሱን ፀረ-መንግሥት አመጽ አደባባይ ወጥቶ በይፋ ከደገፈ በኋላ ተማሪው በአንዳንድ የሃገር ጉዳዮችም እየገባ 'ትምህርት ለሁሉም' በማለትና በአዲስ አበባ የአፍሪካ መሪዎችና ሚኒስትሮች በተሰበሰቡ ቁጥር ከጎዳና እየታፈሱ የሚጋዙትን አቅመ ደካሞችን፣ ደሃና ሕፃናትን አስመልክተው 'ድህነት ወንጀል ነው ወይ?' የተሰኘውን ተቃውሞ መሰንዘርም ጀመረ።

አብዛኛው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ከአውሮፓ እና ከሰሜን አሜሪካ አገሮች የመጡ ምሁራን ነበሩ። በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲማሩ፣ አገሩንም እንዲቃኙ የተላኩት ወጣት ተማሪዎች የካፒታሊስቱን ሥርዓተ-ማህበር ከጉልታዊው ሥርዓት ጋር ለማዳቀል የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎችና የሚሰነዝሯቸውን ትችቶች በቀላሉ ማስተናገድ የሚጎዳም የሚገድም አልነበረም።

ችግሩ ንጉሡንም ሆኑ መሣፍንቱና መኳንንቱ ለእንዲህ ያለው ሁኔታ የስነ ልቦና ዝግጅት የሌላቸው መሆናቸው ነው። እንደ ጥንቱ የቆሎ ተማሪ በኩርኩምና በአለንጋ የአዲሱን ተማሪና ወጣት ምሁር ስሜትና ፍላጎት መግራት ስላልተቻለና ተማሪው አምርሮ ስለታገለ በ1956 ዓ.ም በየኮሌጁ ተከፋፍለው ማህበር ያቋቋሙት ተማሪዎች ተሰባስበው በሃገር አቀፍ ደረጃ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርን በመሠረተው ጉባዔያቸው መዝጊያ ላይ ባወጡት የአቋም መግለጫ፣ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነ የተማሪው አመለካከት ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ አለ።

መወደስን እንጂ ሂስን ያልለመዱት ንጉሥና የተቀሩትም የገዥ መደብ አካላት ቀስ በቀስ ራሳቸውን ከዩኒቨርሲቲው ሕብረተሰብ ማግለል ጀመሩ። የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የኢትዮጵያ አርሶ አደር ጠበቃ በመሆን ታሪካዊውን የመሬት ለአራሹ ጥያቄ በጽሑፍ ለአገሪቱ ፓርላማ ከማቅረብ ሌላ በሰልፍ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እየዘመሩ ለአያሌ ምዕት-ዓመታት ስር ሰዶ የኖረውን ጉልታዊ የመሬት ስሪት በገሃድ አደባባይ አወጡት። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ጉልተኛው ተማሪውን በጠላትነት ፈረጀው።

የተማሪው ጥያቄ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ሥልጣን የሚያሳስብ ሳይሆን የሚያንቃ በጎና ወቅታዊ ጥቆማ ስለነበር ጥያቄው የተማሪ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን አጢኖ ተገቢውን መፍትሄ በመፈለግ ፋንታ እንዴት ተደፈርን በማለት የተማሪው ማህበር መሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዲባረሩ ተደረገ።

በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ቀድመው የተደራጁት የኢትዮጵያ ተማሪዎች በማህበራቸው አማካኝነት የሃገር ቤቶቹን ተማሪዎች የመሬት ለአራሹን ጥያቄ በመደገፍና በጥያቄው ምክንያት በተማሪዎቹ ማህበር መሪዎች ላይ መንግሥት የወሰደውን እርምጃ በማውገዝ ጠጠር ያሉ መግለጫዎችን አወጡ። የሃገር ቤቶች ተማሪዎችም መሪዎቻችን ወደ ትምርት ገበታ ካልተመለሱ አንማርም በማለት ትምህርት አቋረጡ።

በብዙ ውዝግብና በተማሪው ጽኑ አቋም የተባረሩት የተማሪው ማህበር መሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ መንግሥት ቢፈቅድም በየምክንያቱ ተማሪው በሚያነሳው ጥያቄና መንግሥትም በሚወስደው አፀፋዊ እርምጃ ዩኒቨርሲቲው ብቻ ሳይሆን የተቀሩትም የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች አንማርም ሲሉ አድማ አዘወተሩ።

በ1959 ዓ.ም የተካሄደው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ዓመታዊ ስብሰባ ሲዘጋ ያወጣው የአቋም መግለጫ የተማሪውን ማህበራዊ ንቃት እድገትና የርዕዮተ ዓለም አቅጣጫ የገለጸ ነበር። በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሆነ በውጪ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የተማሪዎች ማህበር ዓመታዊ ስብሰባ ላይ የሚወጡት የአቋም መግለጫዎች ሁሉ አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ ያዘሏቸው ፍሬ ሃሳቦች ሲገመገሙ 'የኢትዮጵያ ጉልታዊ ሥርዓት ያረጀና የመጨረሻ የውድቀት እርከን ላይ ደርሶ ለመሞት የተቃረበ መሆኑን የሚገልፁ፡ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ የመደብ አሰላለፍ የሚተነትኑና የወቅቱን ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች የሚዳስሱ ነበሩ።

ተማሪው ጉልታዊውን ሥርዓት ማጋለጡንና መቃወሙን እያጠናከረ መሄዱን በመመልከት ተማሪውን እንደ አንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት በማየት መንግሥትና ተማሪ ዓይንና በርበሬ የሆኑበት ሁኔታ ስለተፈጠረ በዚያው በ1959 ዓ.ም መንግሥት የተማሪውን እንቅስቃሴ ለመግታት ስለ ሰላማዊ ሰልፍ አዲስ ሕግ አወጀ።

የታወጀው ሠላማዊ ሰልፍን የሚከለክለው ሕግ ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ በፊት ተማሪው ተቃውሞውን ለመግለጽ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ በተሰበሰበበት የመንግሥት ፀጥታ አስከባሪዎች ገብተው በወሰዱት የኃይል እርምጃ ብዙ ተማሪዎች የአካል ጉዳት ሲደርስባቸው ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ በርካታ ተማሪዎች ወደ ፖሊስ ጣቢያዎች በመጋዝ ታሰሩ።

ከእስር ያመለጡት አብዛኞቹ እንደተለመደው 'የታሰሩት ካልተፈቱ አንማርም' በማለት ከትምህርት ገበታቸው ራሳቸውን አግልለው በመላ አገሪቱ ባካሄዱት ቅስቀሳ የተማሪውን ንቅናቄ ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ወደ አገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አዛመቱት።

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ያቀራረባቸውና የመላውን ተማሪና መምህራን አመጽ የቀሰቀሰው የሥርዓተ ትምህርት ግምገማ ተብሎ በ1960 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የወጣው እቅድ ወይም ሴክተር ሪቪው ነበር።

ይኸውም የደሃ ገበሬና የሠራተኛውን ልጆች ወደሚመኙት የትምህርት ግብ የሚጓዙበት ጐዳና በእጅጉ እየጠበበ በመሄዱ የተማሪውንና የመምህራኑን ብቻ ሳይሆን የወላጆችንም ተቃውሞ ጋበዘ። በዚህም ጊዜ በአዲስ አበባ የአፍሪካ መሪዎች ዓመታዊ ስብሰባ የሚካሄድ በመሆኑ መንግሥት ከፖሊሱ ኃይል በተጨማሪ የክብር ዘበኛውን በዩኒቨርሲቲው፣ በተቀሩትም መደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ ለኤምባሲዎች ጥበቃና እንዲሁም ለጠቅላላው የከተማ ፀጥታ በየጎዳናው በማሰለፉ ሁኔታው የውጭ ዜና ማሰራጫዎችን ትኩረት ሳበ።

ይህ ደግሞ በተማሪው ዘንድ 'ዓለም አቀፋዊ ትኩረትን አገኘን' በሚል እንደታላቅ ድል ተቆጠረ። በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ የሚበተኑት በራሪ ጽሁፎችም የጉልታዊው ሥርዓት ቁንጮ የሆኑትን ንጉሡ ነገሥትና በመንግሥታቸው ላይ ያተኮሩና ሕዝቡን ለጠቅላላ አመጽ የሚጋብዙ ነበሩ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በእጅጉ የቆረቆራቸው 'የሬውዶ ፋሽስቱ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ለአፍሪካ አብዮት ጠንቅ ነው' የሚለው ጽሑፍ በአፍሪካ አዳራሽ በተሰበሰቡት መሪዎች እጅ እየገባ መነበቡ ነበር። የመሪዎቹ ስብሰባ ተጠናቆ እንግዶቹ ከተሸኙ በኋላ፡ ከ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪውን ተቃውሞ አስመልክተው ንጉሡ መረር ያለ ንግግር አደረጉ። ከንግግራቸውም ውስጥ 'የተማሪዎቹ ድርጊት ጋጠወጥ ብልግና ብቻ ሳይሆን የሚያመዛዝን ጭንቅላት ማጣትና ጨቅላነትም ነው፤ ራሳቸውን ለማዘዝና ለመቆጣጠር የተሳናቸው ባለጌዎች ጥብቅ የሕግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያስፈልጋል" የሚል ነበረበት። ይህም ደግሞ የተማሪውን ተቃውሞ ያለዘበና የሕዝብ ድጋፍ ያስገኘላቸው ሳይሆን በተቃራኒው ተማሪዎች እንደ ተነበዩት የጉልታዊው ሥርዓት ማርጀት ነበር።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተማሪው ላይ መንግሥት የሚወስደው እርምጃ እጅግ እየጠበቀ በመሄዱ የተማሪው ማህበር መሪ የነበሩትና ግምባር ቀደም የለውጥ አቀንቃኞች ከሃገር በመውጣት የውጪውን ተማሪ ንቅናቄ ሲያጠናክሩ የሃገር ውስጥ ተማሪዎች ፀረ-መንግሥት እንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ ረገብ ያለ መስሎ ነበር።

የተማሪው ሰላማዊ ሰልፍ በሕግ በመገታቱ፤ አብዛኛዎቹ የተማሪው መሪዎች መታሰራቸው፤ መገደላቸውና ብሎም መሰደዳቸው የተማሪውን እንቅስቃሴ ረገብ ያለ ቢያስመስለውም የተቀሩት ተማሪዎች ግን መንግሥት በያዘው የመረረ አቋም አንጻር ትግሉ በምን ሁኔታ ይቀጥል የሚል መላ ሲፈልጉ ነበር።

እነዚህ ወጣት አዲስ ምሁራን ተማሪዎች ይህንን እንቅስቃሴያቸውን የጀመሩበት ጊዜ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፋሽስቶችን ድባቅ በመምታት የዓለምን የሶሻሊስትና የሰላም ኃይሎች፤ የሠራተኛውን ንቅናቄና ብሔራዊ የአርነት ትግሎችን በማጠናከር፤ የሶሻሊዝም ድንበር በማስፋት የሶቭየት ሕብረት መንግሥት፤ የምሥራቅ አውሮፓ ሶሺሊስት መንግሥታትና ሕዝባዊት ቻይና የገነኑበት ጊዜ ነበር።

እነዚህ ኃይሎች የዓለም ሠራተኞች ንቅናቄ የጀርባ አጥንት ከመሆናቸው ባሻገር ለዓለም ብሔራዊ የአርነት ትግሎች ተስፋና የተፈጥሮ የትግል አጋር በመሆን በሚሰጡት የቁሳቁስ፤ የሞራልና የፖለቲካ ድጋፍ የዘር መድሎ አራማጆችና የቅኝ ግዛት ኃይሎችን በማንኮታኮት ላይ ነበሩ።

ኢምፔሪያሊዝም የሰውን ልጅ ለመርገጥና ለመመዝበር በማን አህሎኝነትና በጦርነት በተሰማራባቸው የዓለም ልዩ ልዩ ክፍሎች ሁሉ የሽንፈት ጽዋ እየተጎነጨ የሚያፈገፍግበት፤ ከዓለም ሕብረተሰብ የተገለለበት፤ በምሥራቅ አውሮፓ፤ በመካከለኛውና በደቡብ አሜሪካ፤ በእስያ፤ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ንቅናቄና ማህበራዊ አብዮቶች እንደ እንጉዳይ የፈሉበት፤ ጊዜው የሶሻሊዝምና የሠራተኛው መደብ ነው ተብሎም የተዘመረበት ነበር።

የቅኝ ግዛት ኃይሎች በአፍሪካ አብዛኛውን ቅኝ ግዛታቸውን በግድ እየለቀቁ በመሄዳቸው የነፃነት ዳንስ የሚደነስበትና አዲሶቹ የነፃዎቹ አፍሪካ አገሮች መሪዎች እስከ መጨረሻ ባይዘልቁም ለጊዜው በወረት ጠጠር ያለ ብሔርተኝነትና ፀረ-ኢምፔርያሊስት አቋም ያንፀባረቁበት ጊዜ ነበር። ከቅኝ ተገዥነት ቀንበር ያልወጡ እንደ ኮንጎ ኪንሻሳና

ኮንጎ ብራዛቪል፣ ኬኘቬርዴ፣ ጊኒቢሳኦ፣ ሳኦቶሜ፣ ቤኒን፣ አንጎላ፣ ሞዛንቢክ፣ ዝምባቤ እና ናሚቢያ የመሰሉት አገሮች ከቅኝ ተገዥነት ቀንበር ለማውጣት ብቻ ሳይሆን ኢምፔሪያሊዝምን ዕርዮትና ሥልተ ምርት ለመንቀል ቆራጥ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱበት ጊዜ ነበር።

በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ቀደም ብለው ነፃነታቸውን ካገኙት አገሮች መካከል ጋና፣ ግብጽ፣ ጊኒ ኮናክሪ፣ ታንዛንያ፣ ዛሚቢያ፣ ሱዳን፣ አልጄሪያ፣ ሶማሊያ፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ ሊቢያ፣ ደቡብ የመንና ማዳጋስካር ጠንካራ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አቋምና ግራ ዘመም የውጭ ግንኙነት መርሆ የሚከተሉ አገሮች ነበሩ።

ከእስያ በበርማ፣ በኢንዶኔዥያና በማሌዥያ አብዮተኞች ለሥርነቀል ማህበራዊ ለውጥ የትጥቅ ትግል የታጀበ የመደብ ትግል ሲያካሂዱ፣ በቬትናምና በካንፑቺያ የሚካሄደውን ሕዝባዊ አብዮት ለመቀልበስ በሰሜን አሜሪካ ኢምፔርያሊዝም በጫረው ጣልቃገብ ጦርነት በሁሉም ወገን በሚልዮን የሚቆጠር ሕይወትን የጠየቀ ውግያ የሚካሄድበት ጊዜ ነበር።

ኢምፔርያሊዝም ቀደም ብሎ በኮሪያ የጫረው ጦርነት በሰሜን ኮሪያ ሕዝብ አይበገሬነት የተኩስ የማቆም ውል ለጊዜው በመገታቱ ምክንያት በተገኘው አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት ሰሜን ኮሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን አጠናቆ ሶሻሊስት ሕብረተሰብና በከባድ ኢንዱስትሪ የተጠናከረ የኢኮኖሚ ግንባታውን በሚያስደንቅ ሁኔታ ያካሂድ ነበር።

ከሩሲያና ከቻይና ሕዝባዊ አብዮት ቀጥሎ የነበረውና፣ በምዕራብ አውሮፓውያንና ሰሜን አሜሪካ አድህሮት ርብርብ ከከሸፈው የስፔን ሕዝብ አብዮት ጋር ጎን ለጎን ይካሄድ የነበረው የሚክሲኮ ሕዝብ አብዮት ከከሸፈ ብዙ ዓመታት በኋላ በደቡብ አሜሪካ እንደገና የተቀጣጠሉ አብዮቶች፣ በኩባ ሶሻሊስታዊ መንግሥት ሲመሠረት፣ በቺሌ፣ በጓቲማላ፣ በኤልሳልቫዶርና በኒካራጉዋ ፍልሚያ የተፋፋመበትም ጊዜ ነበር።

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የበቀሉ ጥቂት የአብዮት እንቡጦች ወቅታዊውን ጠቅላላ የዓለም ሁኔታና በተለይም ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን አገሮች ዜና መስማትና የትግል ፈለግ በመከተል ኢትዮጵያን ከጉልታዊ ሥርዓት ማላቀቅ የሚቻለው በሥርነቀል ማህበራዊ አብዮት ብቻ ነው ወደሚለው ድምዳሜ አመሩ። እነዚህ በሃገር ቤት በነበሩበት ጊዜ ጅምላውን ተማሪ በፀረ-መንግሥት አቋም አሰልፈው ሲያደራጁ የነበሩ [illegible]ደተኛ ወጣት ምሁራን በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በነበራቸው ነፃነትና አጠቃላይ የተማሪዎች ማህበር ጃንጥላ ተጠልለው በጥቂት ቁጥር እየተቧደኑ ራሳቸውን ለአብዮት ማሰናዳትና ማደራጀት ጀመሩ።

ወጣቱ ተማሪ በግምባር ቀደምትነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር መፍትሄ ፈላጊ መሆን የአገሪቱን ጅምላ ኋላቀርነትና የሕዝቡን ማህበራዊ ንቃት ጉድለት ወይም የፖለቲካ [illegible]ል ድህነትን እንጂ እድገትን የሚያመለክት አልነበረም። ይህ ባይሆን ኖሮ የሌሎች ሕዝቦች አብዮታዊ ታሪክና የትግል ተሞክሮ እንደሚያስተምረን ወጣቱ መመራት የነበረበት በሠራተኛው ግምባር ቀደም አብዮታዊ ፓርቲ ነበር።

እዚህ ላይ የሚያሳዝነው ነገር ኢትዮጵያ የሠራተኞች ሃገር ሳትሆን የፊውዳሎች መሆኗ ወጣቶች ለመሸፈን የሞከሩት ይህንን የታሪክ ቀዳዳ ነው። በዚህ የአብዮቱ መቃረቢያ የጊዜ ክልል ውስጥ በተለይም በማህበር ተደራጅተው የነበሩት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በማህበራቸው አማካኝነት ለፀረ-መንግሥት አቋም የተባበሩ ቢመስሉም በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍልና መደብ በእጅጉ የተዥጎረጎረ ባህልና አመለካከት እንደነበራቸው አይካድም።

የንጉሣዊያን ቤተሰቦች ተወላጆች፣ የጉልተኛ መሣፍንትና መኳንንት ልጆች፣ ከደሃው ሕብረተሰብ አብራክ የወጡ ነገር ግን ፊውዳላዊው አሮጌ ባህል ያጣመማቸው ወግ አጥባቂዎች፣ በአመለካከታቸው ወይም በንቃተ ህሊናቸው ገና ከጎሳና ከጎጥ ያልወጡ ጠባቦች ትምክህተኞች፣ ከትልቅ የሃገርና ብሔራዊ ስሜት እርከን አልፈው ወደ ዓለማቀፋዊነት የመነጠቁ አብዮታዊያን፣ ግራ ቀደሞችና ሥርዓተ አልበኞች ጥርቅም ስለነበሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ሊመሩ ቀርቶ የተማሪ ማህበራቸውን እንኳን በሕይወት ለማቆየት የማያስችላቸው ውስብስብ ቀውስ ውስጥ ወደቁ።

ችግሩም ተራና ውስጣዊ የተማሪ ቅራኔ ብቻ ሳይሆን አዲሱ ምሁር ብዮ ከቀድሞዎቹ ዘመናዊ ካልኳቸው ሃገር አፍቃሪና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ ምሁራን እንድለያቸው ያስገደደኝ ምክንያት ማለትም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር መፍትሄ ፈላጊ ከመሆን ፋንታ የነበሩ ችግር አካልና በተጨማሪ ለአገሪቱ አዲስ ችግር ፈጣሪ ወዳደረጋቸው ሁኔታ አመሩ።

ካረጀውና ካፈጀው እጅግም ኋላቀር ከሆነው ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ለመላቀቅ ሥርነቀል ማህበራዊ አብዮት ያስፈልጋል የሚሉትን አብዮታዊያን አቋም ስንመለከት “የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ችግሮች በሙሉ የሃይማኖትና የብሔር ብሔረሰቦችን ችግር ጨምሮ የሚመነጨት ከፊውዳል ሥርዓት-ማህበርና እንዲሁም ከቅኝ ግዛት ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ነው። ከዚህም ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገል መፍትሄው ሥርነቀል ማህበራዊ አብዮት ነው። አብዮታዊ ትግል ደግሞ በባህሪውም ሆነ በተልዕኮው በዘር፣ በቋንቋና በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ሰው በሰው እንዳይጨቆን መድሎ እንዳይደረግበትና እንዳይበዘበዝ በሚከላከለው በመደብ ላይ የተመሠረተ ትግል ነው። ሕዝባዊ አብዮትን የሚመራ አብዮታዊ ፓርቲ አግኝቶ፣ በአብዮታዊ ፓርቲ አመራር፣ በሠራተኛው መደብ ግምባር ቀደምትነት በገበሬው መደብ የትግል አጋርነትና በተቀሩት ተራማጅና እንዲሁም ጭቁን የሕብረተሰብ ክፍሎች ተባባሪነት በሚካሄደው የመደብ ትግል ብቻ ነው። ማናቸውም የዘር መድሎ፣ ጭቆናና የሰውን በሰው መበዝበዝ ማቆም የሚቻለው” ባዮች ናቸው።

የግራ ቀደምቶችንና ሥርዓት አልበኞችን አቋም ስንመለከት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የሚፈታው በሥርነቀል ሕዝባዊ አብዮት ነው የተባለው መሠረተ ሃሳብ ከአብዮተኞች ጋር ተመሳሳይ አቋም ቢኖራቸውም አብዮታዊ ፓርቲና አብዮት በሌሉበት ‘ከፈረሱ ጋሪው’ እንዲሉ ከእያሌ መሰረታዊ የሕዝቡ ችግሮች አንዱን ዘለላ ብቻ በመምዘዝ በብሔረሰቦች ጉዳይ ላይ ያተኩራሉ።

የዓላማና የተግባር አንድነት፣ በሕዝቡ ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት ያለው መሪና አብዮታዊ ድርጅት አግኝተው ጉልታዊው ሥርዓትና የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጣልቃ ገብነትና ወረራ የፈጠሩትን ቅራኔና ቀውስ የተሞሉ ሁኔታዎች ከመለወጥ ፋንታ ራሳቸውን ለእነኚህ ቀውሶች አስገዝተው ‘የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል’ የተባለውንና መነሻና መድረሻውን በውል ያላጤኑትን መርህ ያለጊዜውና ያለቦታው አንስተው ተማሪውንና ሕዝቡን ከመከፋፈል ባሻገር አገሪቱንና ራሳቸውንም እጅግ አሳዛኝ ለሆነ ከፍተኛ ቀውስ ዳረጉ።

እነዚህ ግራ ቀደምትና ሥርዓት አልበኞች ‘ካብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ’ እንዲሉ በሌሉበትና ያላንዳች ሃፍረት ራሳቸውን አብዮተኛና የሕዝቡ መሪ አድርገው ‘አብዮቱን ወታደሩ ጠለፈው።’ ብሎም ‘ቀለበሰው።’ በማለት የሃገር አንድነትና የአብዮት ፀር ሆነው በአምስተኛ ረድፍ ተሰለፉ።



የኢትዮጵያ አብዮት የተጀመረው በወደቀው ሥርዓት ላይ ታላላቅ ሰላማዊ ሠልፎች ከተደረጉ በኋላ ነበር

በማህበራዊ ንቃታቸው ከጎሳና ከጎጥ አጥር ያልወጡት ጠባብ ብሔርተኞች ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ነን በማለት በተማሪው ማህበር ሽፋን ለመምሰልና ለማስመሰል ቢሞክሩም በሂደቱ ተግባራቸውና ብሎም ታሪካቸው በገሃድ ማንነታቸውን እንዳሳየን የሚሉትን አልነበሩም።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ተብትበው የያዙት ባለብዙ ፈርጅ መሰረታዊ ችግሮችና ቅራኔዎች የሚመነጩት ከጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር መሆኑን አይገነዘቡም። ለማመንና ለመቀበልም አይፈልጉም። ስለ ሥርዓተ-ማህበር ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለ ሕብረተሰብ እድገት ታሪክና ሕግጋት ያላቸው አመለካከት በጎሳና በጎጥ አጥር የተከለለና የተወሰነ በመሆኑ በሥርነቀል ማህበራዊ ለውጥ መፍትሄነት፣ በሕዝብ አንድነትና በአንድ ታላቅ ሃገር ሉዓላዊነትም አያምኑም።

በእነሱ ኋላቀርና ጠባብ አመለካከት የብሔር ብሔረሰቦች ችግር ከኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ችግር የተለየ ከመሆኑ ሌላ የችግሩ ምንጮችም የቅኝ ግዛት ኃይሎች ወረራና ጉልታዊው ሥርዓት ሳይሆን፣ 'የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና የአማራው ብሔረሰብ ናቸው' ስለሚሉ የተማሪውን አንድነትና ማህበሩን ካፈራረሱ በኋላ ከኢትዮጵያ ፀሮችና ታሪካዊ ጠላቶች መሣሪያ እየተቀበሉ በገንጣይና አስገንጣይነት ሃገር ወደማፈራረሱ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ወደ ማጥፋቱ ተግባር አመሩ።

# በአብዮቱ መቃረቢያ የጊዜ ክልል ውስጥ የነበረው የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የኢጣሊኖች የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ጅምር ግንባታ የፈጠራቸው የግብርና፣ የማዕድን ፍለጋና ቁፈራ፣ መለስተኛና አነስተኛ የሆኑ የምግብና ጥቃቅን የፍጆታ እቃዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴና የማምረት ሂደት ከነፃነት ግኝት በኋላ የመጀመሪያው የሽግግር ወቅት በፈጠረው የአሰሪና የካፒታል፣ የጥሬ እቃና የኃይል ማመንጫ እጥረትና የሌሎችም ጊዜያዊ እክሎች አብዛኛዎቹ የማምረት ሥራቸውን እንዲያቆሙ አስገደዳቸው። ስለዚህም ከ1933 እስከ 1950 ዓ.ም በመንግሥት፣ በሕዝቡና በግለሰቦች በኩል የተደረገው ጥረት አዲስ የኢኮኖሚ ግንባታ ሳይሆን በአመዛኙ የነበሩትን የፋሽስት ኢጣሊያ ጅምርና ቅሪት የሆኑ የማምረቻ ተቋሞችን እንደገና በሙሉ ኃይላቸው የማምረት ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ መንግሥት ያደረገው ሌላ ሙከራ ቢኖር በአንዳንድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጃዊ ስሜትና በጎ ምኞት በነበራቸው ባዕዳን ግለሰቦች ትብብር የተለያዩ የአገሪቱን ቅምጥ ሀብቶች በጋራ ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል ሁኔታ ባዕዳን ከበርቴ ድርጅቶችና ግለሰቦችን መዋዕለ ንዋይ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በልማት ይሳተፉ ዘንድ ያደረጉት ያልተሳካ ጥረት ነው።

ከዚህ በኋላ ነው ብዙና በቂ ባይሆንም መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች የሚፈልጓቸው አንዳንድ መረጃዎችንና እንዲሁም ለጋራ ልማቱ የሚበጁ ቅድመ ሁኔታዎችን ከማዘጋጀት ጋር ከ1950 እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ በዩጎዝላቪያ የኢኮኖሚ ጠበብቶች ርዳታ በተሰራ ሁለት የአምስት ዓመት የልማት ጠቋሚ እቅድ በመታገዝና በመመራት ከውጭ መዋዕለ ንዋይ ለሁለተኛ ጊዜ ለመጋበዝ የተሞከረው።

በውጭ መዋዕለ ንዋይ ላይ ብቻ ማተኮሩ ግድ የሆነበት ምክንያት ለጠቅላላ አስተዳደርና ማህበራዊ ጉዳዮች፣ ለሃገር ደህንነት ጥበቃና ለመከላከያ ድርጅቶች ከሚደረጉ ወጭዎች ተርፎ ከ1950 እስከ 1960 ዓ.ም ብቻ ለሁለት አምስት ዓመታት ጠቋሚ የልማት እቅድ ተግባራዊነት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ወይም የልማት ካፒታል ከሃገር ውስጥ የምርት ውጤት፣ የንግድ አገልግሎት፣ ከጠቅላላ ግብርና ቀረጥ በሚገኝ የሃገር ውስጥ ገቢ መሸፈን ፈፅሞ ባለመቻሉ ነው።

ይህም ሆኖ የውጭ መዋዕለ ንዋይ ቢገኝ የዩጎዝላቪያ የኢኮኖሚ ጠበብቶች በእቅድ ዝግጅቱ ሥራ ቢተባበሩም፣ ኢትዮጵያን ከባዕድ ጥገኝነትና ብዝበዛ፣ ከዓለም ኋላቀር ስልፈኝነት ተራ የሚያወጣትና ነፃ የሚያደርጋት ጠንካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችሉ መሣሪያዎችንና ለልማትና ለእድገት የሚበጁ ስትራቴጂያዊ ቁሳቁሶችን ለማምረት ማሰብና ማቀድን የመሰለ አመለካከትና እርቆ የማስተዋል ቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ እውቀት በገዥዎቻችን ዘንድ ስለሌለ የውጭ መዋዕለ ንዋይ የሚፈልገውን የውጭ ምንዛሬ አውጥተን ለፍጆታ የምንገዛቸውን አላቂ እቃዎች አልባሳት፣ ምግብና መጠጥ የሚያመርቱ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን በሃገር ውስጥ ለማቋቋም ነበር።

እንደዚህ ባለው ሁኔታና አመለካከት የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ ፍለጋ ውጤት ሆላንዶችን በስኳር ኢንዱስትሪ፣ ጃፓንና ሕንዶችን በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ፣ ኢጣሊያኖችን በብረታ ብረት፣ በእንጨት በምግብና በመጠጥ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአዲ

ለበ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ከሁሉም በላይ በኃይል ምንጭ ግንባታ ማሳተፍ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጠረ።

እነዚህ ከግብርናው ጋር በጽኑ የተሳሰሩት ቀላል ወይም አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ሆነው ሳለ በአገሪቱ አንድም የተገለበተ የሃገር ተወላጅ ወይም ብሔራዊ ከበርቴ ባለመኖሩ ከጠቅላላው ኢኮኖሚ 15 በመቶ ድርሻ ያለው የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ባለቤቶች በሙሉ ባዕዳን ነበሩ።

በኢትዮጵያ አቅምና የእድገት ደረጃ በሃገር ውስጥ አሉ የሚባሉት ብሔራዊ ከበርቴ ቀዛዙዎች በአመዛኙ የሚያተኩሩባቸው የሥራ ወይም የልማት መስኮች ከስጋ ከብቶች፣ ከእህልና ጥራጥሬ ንግድ፣ ከአነስተኛ የምግብ ቤቶችና የመሸታ ቤቶች አገልገሎትና ከደን ምንጠራ ያለፈ አልነበረም።

ከአገሪቱ የእድገት ደረጃ አንፃር መታዬት ካለባቸው ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መመዘኛዎችና የልማት ቅደም ተከተሎች፣ በእነዚህም መረጃዎች ላይ ተመስርተው የዩጎዝላቪያ የኢኮኖሚ ጠበብቶች ከሰጡት ጥቆማ አኳያ በጠቅላላው የብሔራዊ ልማት እቅድ ውስጥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ መሆን ሲገባ የአገራችን ጉልታዊ የመሬት ስሪት መንግሥትም ሆነ ሃገርን ለማልማት የሚፈልጉ ግለሰብ ከበርቴዎች መሬትን ለመጠቀም ስለማይችሉ፣ የአገሪቱ ጉልተኞች እራሳቸው ያለመሥራት ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ስለማያሰሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት እስኪፈነዳ ድረስ መሬትን ለመጠቀም አልተቻለም ነበር።

የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ በተጠቀሱት ሁለት የእቅድ ዘመኖች የተሞከረ የመሬት ልማት ቢኖር ባዕዳን ድርጅቶችና ግለሰቦች በብላቴን ወንዝ ዳርቻ በመስኖ የጀመሩት የትንባሆ ተክል ዘመናዊ እርሻ፣ በመተሐራ በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ የተጀመረው የአባድር የመስኖ ፍራፍሬና የአትክልት እርሻ፣ በአዋሳ ከተማ ዳርቻ የምግብ ዘይት ለመጭመቅ የተዘጋጀው ዘመናዊ የበቆሎ ሰብል እርሻና የቃጫ ተክል እርሻ፣ ለስኳር ፋብሪካዎች ጥሬ ምርት የሚሆን በናዝሬት በመስኖ የለማው የሸንኮራ አገዳ እርሻና እንዲሁም ጥጥ ለማምረት በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ በተንዳሆ የለሙት እርሻዎች ነበሩ።

በፋሽስት ኢጣሊያ የቅኝ አገዛዝ ዘመን በተሞከረው የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ ምክንያት በተፋጠነ ሁኔታ ቁጥሩ አድጎ የነበረው የኢትዮጵያ ወዝ አደር ከነፃነት ማግኘቱ በኋላ በሽግግሩ ጊዜ በተከሰቱ የተለያዩ ችግሮች ተመናምኖ ከቆየ በኋላ መልሶ የማደግ አዝማሚያ ያሳየው ከዚህ በላይ በገለፅኳቸው የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ዘመናዊ እርሻዎች ከ1950 እስከ 1966 ዓ.ም ማለትም እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ነበር።

በማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው ዘርፍ በዶማና በግዴታ በሚሰራ ደሀ ወዝ አደር ጉልበትና እጅግ ኋላቀር በሆነው የአመራረት ዘይቤ በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በክብረ መንግሥት ይመረት ከነበረው የወርቅ ማዕድን ሌላ በሐረርጌ ክፍለ ሃገር በኦጋዴን ክልል ሲንክለር የሚባለው የሰሜን አሜሪካ የነዳጅ ዘይት ፈላጊና ቆፋሪ ድርጅት ጀምሮት ያልጨረሰው የነዳጅ ዘይት ቁፈራ ሥራም ነበር።

ከአረቦች ጣልቃ ገብ አሻጥር ባሻገር የዘይት ማዕድን ምልክት የታዬበት ብቻ ሳይሆን በቂ ክምችት አለበት ተብሎ የታመነበት ስፍራ ነዳጅ ዘይትን ለማምረት የግድ የሚያስፈልገው ጥልቅ የባሕር ዳርቻ በጣም የራቀ በመሆኑ ከ1500 ኪ.ሜ እርቀት በላይ ድፍድፉን ወደ አሰብ አጓጉዞ ለማንጠር ኢኮኖሚያዊ ባለመሆኑ የቁፈራው ሂደት እስከ አብዮታችን ፍንዳት ድረስ መቆሙ የሚታወቅ ነው፤ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ ናቸው ባልናቸው በዩጎዝላቪያ ባለሙያዎች ርዳታና ትብብር በተዘጋጁት ሁለት የአምስት ዓመታት

የልማት ጠቋሚ እቅዶች በመመራት የውጭ መዋዕለ ንዋይ ለጋሾችን ለመሳብ ያስቻለው ቅድመ ሁኔታና ብሎም የተለያዩ አነስተኛ ወይም ቀላል ኢንዱስትሪዎች ግንባታ ስኬታማነት ወሳኙን ሚና የተጫወተው የኢጣሊያ መንግሥት የቆቃን ወንዝ በመገደብ 130 ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ኃይል ለማመንጨት በለገሰው የገንዘብና የቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ ነበር።

ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ወርረው አዲስ አበባን እንደተቆጣጠሩ በዱከም ወረዳ ውስጥ በሚገኘው አባ ሳሙኤል በመባል የሚጠራውን አነስተኛ ወንዝ ገድበው 12 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ሲገለገሉበት የነበረው ተርባይን በማርጀቱና ግድቡም በደለል በመሞላቱ ኃይሉ እቀልቀሎ ወርዶ ለአዲስ አበባ ከተማ ብርሃን መስጠት ስለተሳነው ሕዝቡ ኩራዝና ሻማ ይገለገል ስለነበረ የቆቃው ግድብ ባይገነባ ኖሮ የአገሪቱ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወት ምን ሊመስል እንደሚችል ግልፅ ይመስለኛል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የአብዮቱ ዋዜማ

የአብዮቱ ዋዜማ ከጥር 4 ቀን 1960 ዓ.ም በደቡብ ኢትዮጵያ ሰፍሮ የሚገኘው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር ካመፀበት እስከ የካቲት 21 ቀን 1966 ዓ.ም ሠራዊት ሳያመርጣቸው በመጠራራት ራሳቸውን መርጠው በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ በመሰብሰብ የጦር ኃይሉን አንደኛውን ዙር ንቅናቄ የመሩት በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ያሉ ከፍተኛ መኮንኖች የአቶ አክሊሉ ሀብተወልድን መንግሥት አፍርሰው የልጅ እንዳልካቸው መኮንን መንግሥት እስካቋቋሙበት ያለው የጊዜ ክልል ነው።

የአንድ ስር ነቀል ማህበራዊ አብዮት ዋዜማ ማለት አንድ ሕዝብ የሚተዳደርበት ማህበራዊ ሥርዓት አርጅቶና ገልምቶ ሂደቱ ሲገታና ጠቀሜታው ሲያበቃ የሕዝቡም እርምጃና እድገት እንደዚሁ ይገታና እያደር መቆርቆዝ፣ ኋላ ቀርነት፣ ድህነት ጭቆናና መድሎ፣ ፍትህ አልባ አስተዳደርና የእነዚህ ሁሉ ውጤት የሆነው ኃዘንና ሰቆቃ በገዥው መደብና በሕዝቡ መካከል የሚፈጥረው ቅራኔ እጅግ ይከርና ሕዝቡና የገዥው መደብ የማይታረቁበት ደረጃ ላይ ደርሰው የሕዝቡ ትዕግሥት ተሟጦ፣ በቃኝ አሻፈረኝ በሚልበት ቁጣው ከአፍከገደፉ አልፎ የሚፈስበት ጊዜ ማለት ነው።

ማህበራዊ ሥርዓት ማለት በሕብረተሰብ ዕድገት ሕግጋት የሚመራ የተለያየ ባህሪ ያለውና የአንድ ሕዝብ ወይም ሀገር ሁለንተናዊ ይዘትና የዕድገት እርከን ወይም ደረጃ ገላጭ ነው። እያንዳንዱ ማህበራዊ ሥርዓት እድገትና ጠቀሜታው እስከሚያከትም ድረስ የየራሱ የሆኑ የሚሞካሽበት ፋይዳዎች ወይም ግኝቶች አሉት። አርጅቶና አፍጅቶ እድገቱና ጠቀሜታው ሲያበቃ መሻሩና በሌላ አዲስ የተሻለ ታዳጊ ሥርዓት መለወጡ አይቀሬ የታሪክ ግዴታ ነው።

ይህ ለውጥ እንደ የአገሩ ሕዝብ እድገትና ተጨባጭ ሁኔታ፣ ፍላጎትና ማህበራዊ ንቃተ ህሊና ሊለያይ ቢችልም፣ ለውጡ በአዝጋሚ፣ በጥገና ወይም ፈጣን በሆነ ሥር ነቀል ማህበራዊ አብዮት ሊሆን ይችላል።

በአብዮቱ ዋዜማ፣ አጥቢያና ማግስት በኢትዮጵያ አብዮታዊያን ለአያሌ ምዕት ዓመታት ተካብቶ የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ ዓላማ ቢስና ሥርዓት አልበኛ በመሆን ውጤቱ ባዶ ሽብርና ውድመት እንዳይሆን፣ ሕዝባዊ ዓላማና ግብ ያለው ሥርነቀል ማህበራዊ አብዮት አቅጣጫ እንዲይዝ ታላቅ ጥረትና መስዋዕት ከፍለዋል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሺህ ዓመታት ታሪክ ከእድገትና ከልማት ሂደት አኳያ ስንመለከተው ለዘመናት ብዙ አልተራመደም። የፋሽስት ኢጣሊያ የአምስት ዓመት በጉልታዊት ኢትዮጵያ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ ጅምር መሠረት በማድረግ በጃፓንና

በህንድ፣ በሆላንድና፣ በኢጣሊያ ከበርቴዎች መዋዕለ ንዋይ፣ በሰሜን አሜሪካና በስዊድን መንግስታት ርዳታ ተደግፈን ከ1950 እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ በአስር ዓመታት በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ ዘመናዊ ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ጀምረን ነበር።

ከ1961 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ በተለያዩ በርካታ ምክንያቶችና ቀውሶች እንደተለመደው ባለህበት ሂድ ብቻ ሳይሆን ተመልሶ ወደ ኋላ መሄድ ተጀመረ። ቀውሶቹ ወይም ችግሮቹ ባለብዙ ፈርጆች ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ ባጠቃላይ አነጋገር ሁለንተናዊ ነበሩ።

ሰው ሰራሽ ብቻ ሳይሆኑ ተፈጥሮ ያመጣቸውም፣ ከሃገር ውስጥ ብቻ የመነጩ ሳይሆኑ ከውጭም ወደ ውስጥ የፈሰሱ የአካባቢውና በአጠቃላይም የወቅቱ ዓለማቀፋዊ ክስተቶች ነጸብራቅ ጭምር ነበሩ።

የአብዮቱ ዋዜማ ባልኩት የጊዜ ክልል ውስጥ ከ1961 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ በአንድ ጊዜ ተሰባስበውና ተሳስበው የመጡትን ቀውሶች መንስዔና ባህሪያት በጥቂቱም ቢሆን ገላልጦ ማየት አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደርበትና ከመቶ ዘጠና በላይ የመንግሥት የተለያዩ ዓመታዊ የገንዘብ ገቢዎች የሚገኙት ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው። የግብርና ኢኮኖሚ ባህሪው በጣም ውስብስብ፣ ሥራው አድካሚ፣ ከመሆኑም በላይ በተፈጥሮ ከባድ ተፅዕኖ ስር ያለ፣ የተፈጥሮ ባህሪያትና የአየር ንብረቶች ሲለዋወጡ አብሮ የሚለዋወጥ፣ ቋሚና አስተማማኝ ሂደትና የተረጋጋ ባህሪ የሌለው፣ በተለይ ኢትዮጵያን በመሰለ ኋላቀር ሃገር ያለማቋረጥ በሚከሰቱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አመጣሽ ቀውሶች ሂደቱና ምርታማነቱ የሚታወክ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላም የሚሄድ ኢኮኖሚ ነው።

በተረጋጋ ባህሪና በማያቋርጥ ሂደት ምርትን፣ ምርታማነትን፣ የምርት ኃይሎች እድገትን የሚፈጥርና ከተፈጥሮ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በአስተማማኝ ሁኔታ በሰው ልጅ የሚመራ ኢኮኖሚ የታዩው የኢንዱስትሪ አብዮት እየተባለ በታሪክ የሚታወቀው መጀመሪያ በእንግሊዝ ከዚያም ቀጥሎ በሌሎች የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አገሮች የታየው ኢንዱስትሪያዊ ኢኮኖሚ ነው።

ከዚህ ታሪካዊ ልምድና ግንዛቤ አንፃር የኢትዮጵያን የግብርና ኢኮኖሚ ጠቅላላ ሁኔታ ስንመለከት የገበሬው የግብርና መሣሪያዎች በሰው ልጅ ጥንታዊ አፍላ የሥልጣኔ ዘመን በተገኘ የፈጠራ ችሎታ ከሺህ ዓመታ በፊት የተፈጠሩ ከኋላ ቀሮችም ኋላ ቀር ናቸው።

በእነዚህ እጅግ ኋላቀር የግብርና መሣሪያዎች እየተገለገለ ,ነው የኢትዮጵያ ገበሬ ታሪኩን በሙሉ የአገሬቷን ጉልተኛ መሣፍንት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ አባት፣ መሪና መምህር ነን የሚሉትን ካህናት ሁሉ አዝሎ የተቀረውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲመግብ የኖረው።

የአርሶ አደሩ ሸክሞች እሱ ሲራብና ሲከሳ እነሱ የሚሰቡት ጉልተኞች ገባር ጭኖ ያቀረበላቸው አልበቃቸው ብሎ እደሳሳ ጉጀው እየገቡ ሚስቱንና ልጆቹን የሚደፍሩ ለዕለት ጉርስና ለአመት ዘር ብሎ ያስቀመጠውን እህል ከጐተራና ከድምኝት የሚዘርፉ ፊውዳል የየመሣፍንቱ፣ ታጣቂ ሎሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ዱር ቤቱ ብለው በቅሚያና ዘረፋ የሚኖሩ ፋኖዎች ወይም ሽፍቶች፣ ተፈጥሮ፣ አዕዋፍ፣ አራዊትና ተባዮች ሁሉ ፀሮችና ሸክሞቹ ናቸው።

የተፈጥሮና የመደብ አጋሩ ከሆነ ከሠራተኛው መደብ ጋር ተቀናጅቶ በመንቃት፣ በመደራጀትና በመታጠቅ አምፆ የፖለቲካ ሥልጣን ከጉልተኞች ካልነጠቀ በስተቀር ከዚህ መከራ የሚያወጣው ምንም ዓይነት ተዓምር የለም።

መጋቢት 4 ቀን 1959 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመሬት ለአራሹን ጥያቄ አደባባይ ይዘው በመውጣት ለፓርላማው ሊያቀርቡም ጉልታዊውን የመሬት ስሪት መለወጥ ቀርቶ ሊታሰብም የማይቻልበት ጊዜ ስለነበረ የገበሬውን ሸክም በጥቂቱ እንኳን ለማቃለል ይቻል እንደሆን ተብሎ በፓርላማው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት በተከታታይ በ1959፣ 1960፣ 1965 ዓ.ም ለሕግ መወሰኛው ምክርቤትና ለንጉሡ ያቀረቧቸው መናኛ የጥገና ሀሳቦች ተቀባይነት ሳያገኙ ቀርተዋል።

በየአጋጣሚው ሲያልፉና ሲያገድሙ የአውሮፓንና የሰሜን አሜሪካን ዘመናዊ እርሻዎች እየተመለከቱ የኢትዮጵያ ጉልተኞችና የመሬት ከበርቴዎች ገባሩና ጢሰኛው አገልጋያቸው ገበሬ ችግር ያነሰ ይመስል፣ በሲዳሞ፣ በባሌ፣ በአርሲ፣ በከፋ፣ በወለጋና በሸዋ ወዘተ ደሀውን ገበሬ ለእያሌ የትውልድ ዘመን ከኖረበት መሬት እየነቀሉ አባረው ትራክተሮች ማሰማራት የጀመሩት በአብዮቱ ዋዜማ ነበር።

የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ይህንን የመሰለ ግፍና በደል የሚፈጽምበት ደሀ ዜጋ በሕግ ከመጠበቅ ፈንታ ከፍ ብዬ የጠቀስኳቸውን ወይም ሕዝቡ የሰንበት አራሾች እያለ የሚጠራቸውን መሣፍንትና መኳንንት ከማበረታታት አልፎ የጦር ኃይሉና የፖሊስ ሠራዊቱ ከፍተኛ መኰንኖች ሳይጠይቁ ወይንም ሳይለምኑ እየጠራ ድሃ ገበሬዎች በሚያርሱት የእርሻ መሬት ላይ እየመራ የሰንበት አራሾችን በማበራከት የድሃውን ችግርና ሰቆቃ የበለጠ አስፋፋው።

እስካሁን ለመግለጽ የሞከርኩት በአመዛኙ በግብርናው አዝመራና በገበሬው የማምረት ጥረት ጣልቃ እየገቡ ቀውስና ችግር ሲፈጥሩ የኖሩትንና አሁንም እየፈጠሩ ያሉትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አመጣሽ የሆኑ ችግሮችን ነው።

ከዚህ በታች ለማሳየት የምሞክረው የኢትዮጵያን ግብርና በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ኋላ ቀር ሆኖ የሚታየው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ባለመደገፉ ብቻ ሳይሆን ሌላውን የኋላ ቀርነታችንን ምክንያት ግጥጥ አድርጐ የሚያሳየንን የሕዝባችንን አሰፋፈርና የመሬት አጠቃቀም ነው።

ከዚህ በፊት ግን አንባቢ እንዲያጤነው የምፈልገው በአፍሪካ ወደር በሌላቸው ታላላቅ ወንዞች፣ ጅረቶችና ሀይቆች አገራችን ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዳቦ ቅርጫትና የውሃ ጎተራ ትባል የነበረ መሆኗን ነው።

በኢትዮጵያ ምድር ከባሕር ወለል በላይ ከፍተኛው በአማካኝ እስከ ሁለት ሺ ሜትር የሚደርሰው አካባቢ ዝቅተኛ መሬት ወይም ቆላማ ክልል የምንለው ሲሆን፣ ከፍተኛው ከባሕር ወለል በአማካኝ ወደ ላይ ከሁለት ሺ እስከ አራት ሺ ሜትር የሆነውን ደጋማ ክልል የምንለው ነው።

ከእነኝህ ከባሕር ወለል በላይ ከዜሮ እስከ አራት ሺ ሜትር ከፍታ ባላቸው ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላማ በምንላቸው የተለያዩ ከፍታዎች 26 ያህል የግብርና አየር ንብረት ክልሎች ይገኛሉ።

የግብርና የአየር ንብረት ክልሎች ማለት በተለያየ ከፍታነታቸው ምክንያት የተለያየ ቅዝቃዜና ሙቀት፣ የተለያየ የንፋስ መጠንና ፍጥነት፣ የተለያየ የዝናብ መጠንና ስርጭት

እንደ ክልሉ መጠን ባይበዛም የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች ስላሏቸው የተለያዩ እፅዋትና አዝዕርትን የሚያበቅሉ ወይም ለተለያዩ እንስሳት እርባታና ኑሮ የሚያመቹ ወዘተ ማለት ነው።

ከኢትዮጵያ ጠቅላላ 1,250,282 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት 769,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 61 ከመቶ ዝቅተኛው መሬት ሲሆን 482,282 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 39 ከመቶው የሆነው ከፍተኛ መሬት ነው።

በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በግምት 40 ሚሊዮን ሲሆን 93 ከመቶ የሚሆነው ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት በ482,282 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 39 ከመቶ በሆነው እጅግ አናሳ ደጋማ መሬት ላይ ብቻ ሰፍሮ በግብርና ሲኖር፣ ሦስት ሚሊዩን ወይም ሰባት ከመቶ የሚሆነው እጅግ አናሳ የሆነው በከብት እርባታ የሚኖረው ዘላን ሕብረተሰብ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 769,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም 61 ከመቶ በሆነው እጅግ ሰፊ መሬት ላይ ሰፍሮ ይኖራል።

በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ልማዳዊ አነጋገር የሕዝቡ አሰፋፈርና የመሬት አጠቃቀም በዚህ ሁኔታ የተዛባበት ምክንያት ሕዝቡ የቆላውን ሙቀትና የተለያዩ በሽታዎች በመፍራት ነው ቢሉም እውነቱ ግን የአፍሪካ የውሃ ጉተራ ያስኙንን ከፍተኛ የውሃ ሀብቶቻችንን ለሰውና ለእንሰሶች መጠጥ፣ ለግብርናው ልማትና እንዲሁም ለመጓጓዣነት ይሆኑን ዘንድ ከከፍተኛው ወደ ዝቅተኛው መሬት ማፍሰስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ስለሌለንና ለም አፈራችንን አግበስብሰው ወደ ባዕድ ሃገር የሚሄዱትን ወንዝና ጅረቶቻችንን ገምሰን ወይም ቀልብሰን ለመስኖ እርሻ ለመጠቀም ባለመቻላችን ብቻ ነው። ይህንን ከመሰለው እጅግ የተዛባ የሕዝብ አሰፋፈር፣ ኋላቀር ግብርናና የመሬት አጠቃቀም ከሚጠቀመው ደገኛው ሕዝብ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ በኤርትራ፣ በትግራይ፣ በወሎ፣ በጐንደር፣ በሰሜንና በደቡብ ሸዋ የሕዝቡ የመጠን ዕድገት ከሚታረሰው የመሬት መጠን ጋር ፍፁም ባለመመጣጠኑ ሕዝቡ ለአያሌ ዘመናት ተጨናንቆ ኖረ።

ይህንን ከመሰለው የመሬት ጥበትና ብሎም ጭንቀት ሌላ ተፈጥሮና የአየር ንብረት ቀውስ በሚያስከትሉት የዝናብ እጥረትና ብሎም ድርቀት የሰሜኑ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ካለበት አሳፋሪ ድህነት ባሻገር በችጋር መሞትና ክልሉን እየጣለ ወደ ደቡብ መሰደድ ከጀመረ አያሌ ዘመናት ቢቆጠሩም፣ በጉልታዊት ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ ሲፈራረቁ የኖሩት ገዥ መደቦች እንዳቸውም የፈየዱት ነገር የለም።

በዚህም ምክንያት በባህላቸው ብርቱ አምራቾች ከነበሩት ከኤርትራ፣ ከትግራይና ከወሎ ሕዝብ ከፊል የሚሆኑት ወደ ለማኝነት ከተሸጋገሩ ሰንብተዋል።

በግብርና የኢኮኖሚ ዋልታ የተዋቀረችው ሀገር ዘጠና ከመቶ የሚሆነው በተለያየ መልክ ለመንግሥት ገቢ የሚሆነው የገንዘብ ምንጭ መድረቅ ከጀመረ ቆይቶል።

የመሣፍንቱንና የመኳንንቱን የቅንጦትና የፍጀት ኑሮ፣ የአገሪቱን ላእላይ መዋቅር ያለእቅድና ገደብ ከላይ ወደታችና ወደጐን በሰፊው የተዘረጋውን ቢሮክራሲ የገበሬው ጫንቃ መሸከም ከተሳነው ዘግይቷል።

በአገሪቱ ሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምዕራብና ደቡብ በሰፊ ዝቅተኛ መሬት ላይ የሰፈሩትና በከብት እርባታ የሚኖሩት ዘላን የሕብረተሰብ ክፍሎች ምንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት ሳይቀርብላቸውና ሳይገነባላቸው ከአገሪቱ ሕዝብ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን በከፊል ጥንታዊና የጋርዮሽ ሥርዓት

ውስጥ ቢኖሩም፣ በሃገር ውስጥ ፍጆትና ለውጭ ገበያ ቁም የሰጋና የወተት ከብቶችን በማቅረብ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።

ሆኖም የአብዮቱ ዋዜማ ባልኩት የጊዜ ክልል ውስጥ በአገራችን ያለማቋረጥ በደረሰው የዝናብ እጥረትና ብሎም የለየለት ከባድ ድርቅ ሰው ብቻ ሳይሆን ከብቱም በማለቁና ከብት አርቢው ለከተሜው ከመስጠት ይልቅ ወደ ምግብ ተመፅዋችነት በመዘዋወሩ፣ በምግብ እጥረት ረገድ በአገሪቱ ከቡና ቀጥሎ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ አሳጣት።

ለሃገር ውስጥ ፍጆትና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡት ከከብትና የከብት አስተዋጽኦዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ወሳኝነት ያላቸው እንደ ቡና፣ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶችም በድርቁ ምክንያት መጠናቸው ከመውረዱ በላይ በወቅቱ የዓለም ገበያ ላይ ዋጋቸው ክፉኛ ወድቆ ነበር።

የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ቀውሶችና ችግሮች ብዙ ስለሆኑ ሁሉንም ለመዘርዘር አዳጋች ከመሆኑ ባሻገር አንባቢንም የሚያሰለች ነው የሚሆነው። የኢትዮጵያ ገበሬ ንቃት፣ የግብርናው ዕውቀት ደረጃውና ከዘመናዊ የግብርና ጥበብና ከቴክኖሎጅ ጋር ያለመተዋወቅ ለግብርናው ኢኮኖሚ ውድቀት ያደረጉት አስተዋፆ ከፍተኛ ነው።

ገበሬው ለግብርና የተመቻቸውን፣ ለሙን፣ ዝርግና ሰፊ መሬት ለመጠቀም አለመቻሉ በደጋማ ክልሎች ውስጥ የሚገኙትን ከፍተኛ መሬቶች፣ ኮረብታዎችና ተራሮች ላይ የሚገኙትን ደኖችና ዛፎች በመመንጠር፣ ዘብጣማና ገደላማ የሆነውን ምድር በማረስ ለም አፈር በነፋስ ስለሚከላና በዝናብ ስለሚታጠብ፣ ገበሬው ራሱ ተፈጥሮን በማቃወስ አገሪቱን ወደ በረሃነት ለመለወጥ የሚያከናውነው አፍራሽ ተግባር በእስቾኳይ ካልታረመና ካልተገታ ለነገው ትውልድ የምናስረክበው፣ እነ ቤኒቶ ሙሶሎኒ የምድር 'ገነት' ያሏትን፣ እነ ጀምስ ብሩስ 'የአፍሪካ የውሃ ጉተራና የዳቦ ቅርጫት' ያሏትን ኢትዮጵያ ሳይሆን ምድረ በዳ መሆኑን የማያጠያይቅ ነው።

በአገራችን ዘመናዊ ወይም ኬሚካል የአፈር ማዳበሪያ እስከ 1950 ዓ.ም አጋማሽ ወይም እስከ ሁለተኛው የልማት ጠቋሚ እቅድ ዘመን ድረስ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠር ጥቅሙ ቀርቶ ስሙም አይታወቅም።

የአፈር ማዳበሪያና የሰብል ተባይ መከላከያ ንጥረ ነገሮች ወይም ኬሚካሎች ወደ አገራችን የገቡትና ጥቅም ላይ የዋሉት በአዋሽ ሸለቆዎች በውጭ ከበርቴዎች የሸንኩራና የጥጥ እርሻዎች በተጀመሩበት ጊዜ ሲሆን የዓለማያ ግብርና ኮሌጅ ተቋቁሞ የተለያዩ የግብርና ባለሙያዎችን አፍርቶ በአገራችን የግብርና ምርምር ከተጀመረና በስዊድን መንግሥት ርዳታ በወላይታ ሶዶ፣ በአርሲ ጭላሎና በትግራይ ሽሬ የግብርና ቴክኒክ አገልግሎት አቅርቦት ለጥቂት ገበሬዎች መስጠት ከተጀመረ በኋላ ነው።

እዚህ ላይ በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ነገር ከፍ ያለ ችግር ያለበትን የትግራይን ገበሬ በተለይም የሰሜኑ ክልል አርሶ አደር በአጠቃላይ ለመርዳት አማካኝ ማዕከል ነው በማለት በሽሬ የተቋቋመውን የግብርና ቴክኒክ አገልግሎት አቅራቢ ተቋም መሣሪያዎች በማቃጠልና በመዝረፍ፣ ቤተ ምርምሮችንና የምሁራኑን መኖሪያ በማፈራረስ እንዳችም አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ከማውደም ባሻገር ወያኔ የግብርና ምሁራኑን መረሸኑ ነው።

በዘመናዊ የግብርና ጥበብና ምርታማነት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ እንኳን እንደ ግብጽ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ዝምቧቤ፣ ናሚቢያ፣ ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ጋና፣ ሞሮኮና አይቬሪኮስትን ከመሳሰሉት አገሮች ብዙ ወደ ኋላ የቀረች ነች።

ለተለያዩ ዕፅዋት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ቀርቶ ጥራጥሬን ለመሳሰሉት የምግብ እህሎች የሚሆኑ የዘር ዓይነቶች እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በሃገር ውስጥ ለማምረትና ለገበሬው ምርጥ ዘር ለማደል ያልበቃች ሃገር ነች።

በድህረ አብዮት የመጀመሪያዎቹ ዓመቶች የአገሪቱን የግብርና ኢኮኖሚ በአጣዳፊ ለማጎልበት ስንል በአስቸኳይ ያቋቋምናቸው ሦስት ተቋሞች ማለትም የግብርና ምኒስቴር፣ የመንግሥት እርሻ ሚኒስቴርና የቡና፣ የሻይ፣ የፍራፍሬና የቅመማ ቅመም ልማት ሚኒስቴር ምርጥ ዘር ያስመጡ የነበረው ከኬንያ፣ ከእሥራኤልና ከሌሎች የአውሮፓ አገሮች ነበር።

ስለ ግብርና የአየር ንብረት ክልሎች ለመግለጽ እንደሞከርኩት በተለያዩ የአየር ንብረት ክልሎች የተለያዩ እፅዋትና አዝርዕት ይበልጥ የመመቸት ባህሪ ስላላቸውና አፈሮቹም የተለያዩ ስለሆኑ በአፈሮች ጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ አፈር ማዳበሪያዎች ሊኖሩ ይገባል።

በኢትዮጵያ እስከ ዛሬም ይህ አልተደረገም። በአሁኑ ጊዜ ስማቸውን ለማስታወስ የተሳነኝ የአለማያ ግብርና ኮሌጅ መምህር የነበሩ አሜሪካዊ የግብርና ምሁር በራሳቸው አነሳሽነትና ፍላጎት አገራችን የተለያዩ የአፈር አይነቶች በአንዱ ላይ ብቻ ምርምር አድርገው ለአገሪቱ ያበረከቱት አንድ ዳፕ በመባል የሚጠራ ኬሚካል የአፈር ማዳበሪያ በስተቀር ሌላ ስለማይታወቅ እስከ ዛሬ ከውጭ የሚገዛው ይህ ማዳበሪያ ለአንድ አይነት የአገራችን አፈር የሚያገለገል ብቻ ነው።

በመሰረቱ የማዳበሪያ ጥቅምን ባለማወቅ፥ ቢያውቅም የመግዛት አቅም ከማነስ፥ የመግዛት አቅምና ፍላጎትም ቢኖር ማዳበሪያ ከሚያቀርቡት የግልና የመንግሥት ተቋሞች አቅም ውስንነትና ከእነዚህ ሁሉ በላይ አገሪቱ ባለባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት አብዛኛው የኢትዮጵያ ገበሬ በማዳበሪያ ተጠቃሚ አይደለም።

ለአንድ አይነት አፈር ብቻ የሚያገለግለው ዳፕ በመባል የሚጠራው ማዳበሪያ ተገልጋይ ገበሬ ከመላው የኢትዮጵያ ገበሬ አስር ከመቶ እንኳን ካለመሆኑ በላይ በሚጠቀመው የማዳበሪያ መጠንም በአፍሪካ ደረጃ እንኳን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው።

ከዚህም መካከል ምናልባት ከፊሉ ከሚያርሰው አፈር ጋር የማይጣጣመውን ወይም የማይጠቅመውን ማዳበሪያ ነው የሚገለገለው ለማለት ይቻላል። የግብርናውን ኢኮኖሚ ነባር ችግሮችና በአብዮቱ ዋዜማ የተከሰቱትን ቀውሶች አጠርና ጠቅለል ባል ሁኔታ ለማጠቃለል፣ በሰሜንና በመሃል ሃገር የመሬት ጥበት፥ እጅግ የተዛባ የመሬት አጠቃቀምና አጠቃላይ የግብርና ዘዴ ኋላ ቀርነት የእነኝህ ጠቅላላ ውጤት የሆነው ረሃብ ወይም አሳፋሪ ድህነት ያገሪቱ አስከፊ ገጽታዎች ናቸው።

የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ የፋሽስት ኢጣሊያ ቅሪት የሆኑ ጥቂት አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የቆቃ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ መሠረት ሆነው በኢጣሊያና በህንድ፥ በጃፓንና በሆላንድ ወዘተ ከበርቴዎች መዋዕለንዋይ ፍሰትና እንዲሁም በሰሜን አሜሪካና በስዊድን መንግሥት እርዳታ አገሪቱ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናዊ ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ረገድ ዳዴ ማለት መጀመሯ ተገልጿል።

በተጠቀሱት አገሮች ከበርቴዎች ቴክኖ-ካፒታል አቅርቦት የተለያዩ አላቂ የኢንዱስትሪ ርቶችን ከውጭ ለመግዛት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለመቆጠብና ብሎም ወደ ንዱስትሪ ግንባታ ለመሸጋገር ተብሎ በአገራችን የተተከሉት ጥቂት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ዝቡ ዘንድ የእድገት ተስፋ ከመፈንጠቃቸው በላይ የሕዝቡን አንዳንድ የአላቂ እቃዎች ጎት በማሟላትና ለጥቂት ዜጎቻችን የሥራ እድል በመክፈት ቢያገለግሉም በብዙ ሰው ች ችግሮች የተጠላለፉ ስለነበሩ የተጠበቀውን ምርትና ገቢ ሊያስገኙ አልቻሉም።

በቅድሚያ ለአገሪቱ አዲስና ብርቅዬ የሆኑትን ቀላል ኢንዱስትሪዎች በሃገር ውስጥ ትክል የነበረው ከፍያለ ጉጉትና የመዋዕለንዋይ ባለቤት የሆኑ የውጭ ከበረቴዎችን ገብ ተብሎ ኢንዱስትሪዎቹ በሃገር ውስጥ ተተክለው ምርት መስጠት ከሚጀምሩበት ጀምሮ ለተከታታይ አስርና አሥራ ሁለት ዓመታት ለአገሪቱ መክፈል ያለባቸውን ለያዩ ግብሮች እንዳይከፍሉ ከመደረጋቸው በላይ በውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም በኩልም ደዚሁ መረን የተለቀቁ ነበሩ።

በወቅቱ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከውጭ ከበርቴዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ድ በጣም ካደሉ ለጋስ ውለታዎች አንዱን ብቻ ላቅርብ። በአዋሽ ሸለቆዎች ለሸንኮራ ዳ፣ ለጥጥ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬዎች ማምረቻ ለባዕዳን ከበርቴዎች የተሰጠው ወደ ባ ሺ ሄክታር የሚሆን ለምና ውሃ ገብ መሬት ግብር በአንድ ጋሻ መሬት በዓመት አንድ ትዮጵያ ብር ነበር።

እንዲህ ያለ ግብር ይህንን ለሚያክል መሬት በነፃ ተሰጠ እንዳይባል ብቻ ተብሎ ደተደረገ አንባቢ ሊረዳ ይችላል። የተተከሉት ቀላል ኢንዱስትሪዎች በሙሉ የውጪ ክኖሎጂ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከዚህ በላይ በገለጽኩት እጅግ ለጋስ በሆነ ውል ረት የተተከሉ ስለነበሩ የሚያስፈልጋቸውን የመለዋወጫ እቃዎችና ለምርቱ ግብአት ሆኑ ጥሬ እቃዎች ከውጪ የሚያስመጡት በአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ስለነበረ መንግሥት ቀደው የውጪ ምንዛሬ ቁጠባ እንደተጠበቀው ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም።

በገበያ ልውውጥ ላይ የተመሠረተ የካፒታሊስት ሥልተ ምርት በሠራተኛውና በርቴው መደቦች የተዋቀረ እድገትን ከብዝበዛ ጋር አጣምሮ የያዘ ማህበራዊ ሥርዓት ገራችን ጉልታዊ ሥርዓት ጋር ተዳቅሎ የኢንዱስትሪ ግንባታ ልምድን፣ የቴክኖሎጂ ችትንና ለሃገር ግንባታ የሚውል የሃገር ውስጥ ካፒታል ክምችትን ከማስገኘቱ በፊት ለቱ ጠቋሚ የእቅድ ዘመኖች ከ1950 እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ ከራሱ ባህሪያት ነጨና ከውጪ በተጨመሩ የተለያዩ የኢኮኖሚ ቀውሶች በመጠላለፉ አቆልቁሎ ወደ ውረዱና ምርታማነታቸውን ከመቀነስ አልፎም አንዳንዶቹ የማምረት ተግባራቸውን ወደ ገታትና ሠራተኛውን ወደ ማባረር አመሩ።

ቀውሱ በዚህ ሁኔታ የተባባሰው በ1959 ዓ.ም የእሥራኤልና የአረቦች ጦርነት ቀስቅሶ የስዊዝ ካናል ወይም የመርከቦች መተላለፊያ መንገድ በመዘጋቱ ምክንያት የቀይ ሕር፣ የአፍሪካ ቀንድና የአባይ ሸለቆ አካባቢ አገሮች የገቢና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ጠቅላላ ከመታወኩ ባሻገር ነዳጅ አምራች የአረብ መንግሥታት ነዳጅን ለጦርነቱ መሣሪያ ገድረግ በነበራቸው ዓላማ በነዳጅ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ ማድረጋቸው ነው።

"በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ በተለያዩ ቀውሶች ምክንያት ሲጥመለመል በረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የውጭ ንግዱ የደረሰበት ያልተጠበቀ ድንገተኛ አደጋ ውሱን አባባሰው። ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ቀጥሎ የመንግሥት አብይ የሃገር ውስጥ ቢ የነበረው የንግድ ግብር በአስደንጋጭ ሁኔታ አሽቆለቆለ።

የግብርናው፣ የኢንዱስትሪውና የውጪ ንግዱ ይህንን በመሰለ ውድቀት ላይ እያሉ ስልሳ ከመቶ በላይ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የነበረው የቡና ምርት ዋጋ በዓለም ላይ መውደቁ ኢኮኖሚውን ጨርሶ አላሽቀው።

የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ መንግሥት ይህንን የተወሳሰበ የኢኮኖሚ ቀውስ በጥቂቱም ቢሆን ለማቃለል ወይም ለመቀነስ በማለት ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ የበጀት ቁጠባ እቅድ አውጥቶ በተከታታይ ዓመታት ተግባራዊ ለማድርግ ሞከረ።

ሙከራውም፣ ማናቸውም በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት ተቋማት ቀድሞ ከነበራቸው ሌላ ተጨማሪ ባጀት እንዳይጠይቁ፣ ሠራተኛ እንዳይቀጥሩ፣ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውንም የልማትና የግንባታ ሥራ እንዳያቅዱም፣ እንዳይሰሩም፣ ካልተፈቀደ በቀር ከውጭ የእቃ ግዢ እንዳይደረግ የተሰኙ የቁጠባ ዘዴዎችን በተግባር ላይ ማዋል ነበር።

እዚህ ላይ የሚያስገርመው ይህንን የመሰለ የቁጠባ እርምጃ በመውሰድ ላይ ያለ መንግሥት በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለካቢኔ ሚኒስትሮች ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ ማድረጉ ሲሆን ይህ በጠቅላላው ሕብረተሰብ ዘንድ ማለት ይቻላል አሉታዊ ስሜትና ከፍተኛ ነቀፋ አስከትሎ እያለ በዓለም አቀፍ ደረጃ አረቦች የጨመሩትን የነዳጅ ዋጋ ለማካካስ ብሎ ባገር ውስጥ የነዳጅ ዋጋ መጨመሩ የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉን መንግሥት ውድቀት አፋጠነው።

በአብዮቱ ዋዜማ የአገሪቱ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ አጠር ባለ ሁኔታ ይህንን ያህል ካልኩ፣ ወቅታዊውን የፖለቲካ ሁኔታ ደግሞ በጥቂቱ ለመቃኘት ብሞክር በኃላ ሁኔታ የሕዝቡ ትኩረቶችና የልብ ትርታዎች ከነበሩት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የደቡብ ኢትዮጵያ የመሬት ይዞታ፣ የብሔረሰቦችና የሃይማኖት ጥያቄ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ለብዙ ጊዜ የቆየው የመሬት ጥበትና ያስከተለው ስደት፣ ዓለምን ያስደነገጠው የትግራይና የወሎ ሕዝብ በርሃብ እልቂት፣ በኤርትራ፣ በኦጋዴን፣ በባሌ፣ ወዘተ የተቀሰቀሱት የትጥቅ ትግሎችና ያስከተሉት ጉዳት በጠቅላላውም በሕዝቡና በገዥው መደብ መካከል እያደገ የመጣው ቅራኔና የሕዝቡ ብሶትና ቁጣ ከአፍ እስከ ገደፉ መድረስ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው። የአገሪቱን አንድነት የሕዝቡን ማህበራዊ ደህንነትና የዳር ድንበር መከበርን የሚያካትተው የአገሪቱ የመከላከያ ጉዳይ ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ቢብስ እንጂ የሚሻል አልነበረም።

የጎረቤቶቻችን የሱዳንና የሶማሊያ መንግሥታት የጦር ኃይሎች እጅግ ዘመናዊ የሆነውን የሶቭየት ሕብረት ስሪት የዋርሶ መሣሪያ እስከ አፍንጫቸው የታጠቁበት ጊዜ በመሆኑ የአፍሪካ ቀንድ ወታደራዊ ሚዛን ኢትዮጵያን እጅግ በሚያሰጋ ሁኔታ ከተዛባ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በሱዳን የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የተፈራረቁ መሪዎችና መንግሥቶቻቸው አረቦች ለኤርትራ ገንጣዮች በገፍ የሚልኩትን መሣሪያ፣ ትጥቅ፣ ስንቃ ስንቅና መድሃኒት ወዘተ እየተቀበሉ በማካበት፣ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ለገንጣዮቹ የስልጠናና የህክምና ድጋፍ በመስጠት መውጫ መግቢያ በር ሆነው ኢትዮጵያን ማድማትና መበርበር ከጀመሩ ብዙ ጊዜ ሆኗል።

የሶማሊያ መንግሥት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በተባበሩት መንግሥታት ማህበር፣ በአረብ ሊግ፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት መድረኮች ወዘተ ላይ በየአጋጣሚው ሁሉ 'አንድ አምስተኛው የኢትዮጵያ ግዛት አለኝታዬ ስለሆነ ለእኔ ይገባኛል' ከማለት ባሻገር ይህንን

ምኞቱንና ፍላጎቱን በኃይል ተግባራዊ ለማድረግ የጦር ኃይሉን በጋራ ድንበራችን ላይ አሰልፎ ለውጊያ ከተዘጋጀ ሰንብቷል።

በ1953 ዓ.ም በኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር በሚመራው የግብጽ መንግሥት ግፊትና አደራጅነት ራሱን የኤርትራ ነፃ አውጪ ግምባር ወይም በአረብኛ ቋንቋ 'ጀብሃ' እያለ የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት ካይሮ ላይ ከተቋቋመና በኤርትራ ክፍለ አገራችን የትጥቅ ትግል ከጀመረ በኋላ የእሱን አርዓያነትና ፈለግ በመከተል በተለያዩ ጊዜያቶች በተከታታይ በዚያው በኤርትራ ክፍለ ሃገር ራሱን የኤርትራ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ወይም በአረብኛ ቋንቋ 'ሻዕቢያ' ብሎ የሚጠራ ድርጅትና ለተመሳሳይ ዓላማ በተመሳሳይ ሁኔታ በአረብ መንግሥት በተለይም በሱዳንና በሶማሊያ የሚረዱ፣ የኦሮሞ፣ የእስላማዊ ኦሮሞ፣ የአፋር፣ የምዕራብ ሶማሊያ፣ ሶማሊያ አቦ፣ የአደሬ፣ የሲዳማ ወዘተ ነፃ አውጪ በማለት ራሳቸውን የሚጠሩ የኢትዮጵያ ማህበረሰብና ብሔረሰብ ድርጅቶች ተቋቁመው በተለያዩ የአገሪቱ ማዕዘናት የመከላከያ ሠራዊታችንን ይወጉ ነበር።

እነኝህ ሁሉ የታጠቁት እጅግ ዘመናዊ የሆነ የዋርሶ መሣሪያ ስለነበረ በብዛታቸው ብቻ ሳይሆን በትጥቅ ጥራትም የአገሪቱን የምድር ጦር ልቀው ሄደዋል። በጦር ኃይሎቻችን የበላይ መኮንኖች ግፊትና ጉትጎታ አፄ ኃይለሥላሴ ወደ ዋሽንግተን ሄደው የአገሪቱን ውስጣዊ፣ የአፍሪካን ቀንድ ክልል አጠቃላይና ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታና በአካባቢያችን ያሉ የአረብ መንግሥታትን የጦር ኃይል ግንባታ፣ በዚህም ምክንያት የተፈጠረውን ስጋትና አደገኛ ሁኔታ በማስረዳት ተመዛዛኝ የሆነ መሣሪያ እንዲቀርብልን የሰሜን አሜሪካንን መንግሥት ጠይቀው ነበር።

በዚህ ጊዜ አሜሪካ በቬትናም ጦርነት ዳሽቃ ለሽንፈት ከመቃረቧ ጋር ለተዋዋለችው የወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ተራድዖ ውለታ ዋና ምክንያት የነበረው በአሥመራ የኔቶ ወታደራዊ የመገናኛ ተቋም በሳተላይት ቴክኖሎጂ ግኝት ምክንያት ጥቅም አልባ ሆኖ ስለነበረ ለንጉሡ የተሰጣቸው መልስ "አሜሪካ ኢትዮጵያን የመከላከል ግዴታ ስለሌለባት ከእንግዲህ ወዲያ የምትሰጠው ነገር የለም" የሚል ነበር።

እንባቢ እንደሚያስታውሰው ኢትዮጵያ የዓለም አቀፋዊው ሶሻሊስቱ ጎራና የአረቡ ዓለም የጥቃት ዒላማ የሆነችው ከአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ጋር ወግና የኮሪያን ጦርነት ተካፋይ በመሆናና በአሥመራ በኤርትራ ክፍለ አገራችን ርዕስ ከተማ በሰሜን አሜሪካ መንግሥት ለሚመራው የምዕራቡ ዓለም ወታደራዊ ቃል ኪዳን ድርጅት ለኔቶ በአፍሪካ ቀንድ፣ በአባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቂያኖስ እንዲሁም በሰሜን አፍሪካ በመላው ማዕከላዊ ምሥራቅ፣ የአየርና የባሕር ወታደራዊ ቅኝት ለማድረግና ለኤሌክትሮኒክ ወታደራዊ ስለላ መሣሪያ መደብነት የሚያገለግል ስትራቴጂያዊ የሆነ ጠቃሚ ስፍራ በመስጠቷ ነው።

አገራችን በውስጥ የመከላከያ ሠራዊታችንን በሚወጉ አስር የብሔረሰብ ድርጅቶች ተወጥራ፣ በውጪ የዓለም አቀፋዊው ሶሻሊስት ጎራና የአረቡ ዓለም ድጋፍ ባላቸው ተስፋፊዎች ተከባ ባለችበት ጊዜ "የራሷ እያረረ የሰው ታማስላለች" እንዲሉ ጀብሃና ሻዕቢያ እያሉ ራሳቸውን የሚጠሩ ሁለቱ የኤርትራ ገንጣይ ድርጅቶች በሠራዊታችን ላይ የሚያደርሱት ጥቃት በተስፋፋበት ወቅት በኛ እየተረዳ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ለነፃነቱ ይታገል የነበረው የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ወይም አንያንያ በመባል የሚታወቅ የደፈጣ ተዋጊ ድርጅት 16 ዓመት ተዋግቶ ግቡን ሊመታ ሲቃረብ እንዳይዋጋ አድርገው በማኮላሸት አፄ ኃይለሥላሴ ለካርቱም መንግሥት አሳልፈው ሰጡት።

ለማጠቃለል በአብዮቱ ዋዜማና አጥቢያ የነበሩት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለጊዜው ወደ ጎን ትተን ጊዜ የማይሰጠውን ለኢትዮጵያ የሞት ሽረት ጉዳይ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ደህንነት፣ የአገራችንን አንድነትና የዳር ድንበራችንን አስከፊ አደጋ ላይ መውደቅ፣ ሕዝቡ እርስ በእርሱ ሆድና ጀርባ ከመሆኑ ሌላ ከገዥው መደብ ጋር የደረሰበትን እጅግ የከፋ ቅራኔ መለስ ብሎ በአይነ ህሊናው መመልከት ለቻለ ኢትዮጵያዊ በ17ኛውና በ18ኛው ምዕት ዓመት አገራችን ከገጠማት ከዘመነ መሣፍንት ጊዜም የበለጠ አደገኛ ጊዜ ነበር።

ከዘመነ መሣፍንት የበለጠ አደገኛ ጊዜ ነበር ማለቴ ለማጋነን አይደለም። መሣፍንቱ እርስ በራሳቸው ሲዋጉ አገራቸውን ከፋፍለውና አዳክመው ለውጪ ጠላቶች ወረራ ማጋለጣቸው ለወረራ ማመቻቸታቸው ከእኛ ዘመን ገንጣይና አስገንጣዮች ጋር በግብር ቢያመሳስላቸውም መሣፍንቶቹ እርስ በእርሳቸው ይዋጉ የነበረው ሃገርን የመገንጠልና የማስገንጠል፣ ብሎም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዓላማ አንገበው በመነሳት ሳይሆን አንዱ በሌላው ላይ ለመስፋፋትና የበላይነትን ለመቀዳጀት አንዱ ሌሎችን ለማጠቃለልና አንዲት ኢትዮጵያን ለማማከል ነበር።

በድህረ አብዮት ታሪክና ተግባራቸው ማንነታቸውን ስለገለጠልን ገንጣይ አስገንጣይ ብለን የምንጠራቸው፣ ራሳቸውን የየማህበረሰቡ ወኪልና ነፃ አውጪ ያደረጉት ድርጅቶች አካላትና አባላት በቅድመ አብዮት እንደተቀረ ነው። ኢትዮጵያውያን ቅራኔና ጠባቸው ከፉልታዊው ሥርዓት ማህበርና ሥርዓቱን ከሚያራምደው የአፄ መንግሥት ጋር ነው ብለን በመገመት እየወጡንም የሕዝቡ አመፃዊ ቁጣ አካል አድርገን እንመለከታቸው ነበር።

የሕዝቡ አመፅና ቁጣ የሚወልደው ማህበራዊ አብዮት ተስፋ፣ ቅምጥ ኃይልና ማህበራዊ መሠረት አድርገን የተመለከትናቸው ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ጥቂት አልነበረም። በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ላይ ለአያሌ ምዕት-ዓመታት ቤታቸውን ሰረተው የቆዩ ነባር ችግሮችና በቅርቡ የተፈጠሩትን ቀውሶች ለማስገወድ አማራጭ የሌለው አንድና ብቸኛ መፍትሄ ሥርነቀል ማህበራዊ አብዮት ነው የሚል አቋም ከወሰድን ብዙ ቆይተናል።

በህብረተሰቡ እድገት ታሪክና በሰው ልጆች ማህበራዊ ሕይወት ሂደት ከሚከሰቱ አያሌ ቅራኔዎች ዋናውና ትልቁ የመደብ ቅራኔ ነው። ከዚህ በመለስ የመደብ ሕብረተሰብ የሚፈጥራቸው፣ እንደ የዘር፣ የሃይማኖትና የፆታ መድሎ፣ ሰው በሰው መበዝበዝን የመሰሉት ቅራኔዎች በመደብ ትግል የሚፈቱ ናቸው።

በአንድ ሃገር ሕዝባዊ አብዮት ፈንድቶ ትክክለኛ ታሪካዊ አቅጣጫውን ከያዘና የመደብ ትግሉ ፈሩን ሳይለቅ ከሰመረ፣ የግለሰቦች፣ የቤተሰቦች፣ የማህበረሰቦችና የብሔረሰቦች ቅራኔዎች ስለሚፈቱ የኛዎች የየብሄረሰቡ ወኪልና ነፃ አውጪ ነን የሚሉን ድርጅቶች አመፃቸውን ከሕዝቡ አመፅ ጋር ማቀናጀታቸው አይቀሬ ነው የሚል ዕምነት ነበረን። በኢትዮጵያ ማህፀን ውስጥ የተረገዘው የአብዮት ሽል ሲወለድ የውስጥ ቅራኔዎችንና ከነሱም የሚመነጩት ችግሮቻችን ብቻ ሳይሆኑ በላያችን ላይ እያንዣበቡት ያሉት ከውጪ የሚወረወሩ አደጋዎች ወይም በአካባቢውና በሩቅ ጠላቶቻችን ዘንድ በእኛ ላይ እየተሸረቡ ያሉትን ሴራዎችና ዙሪያ ከበባዎች ሁሉ ያስወግድልናል፣ በአጠቃላይ አነጋገር አብዮት ኢትዮጵያን ከህመሞቿ የሚፈውሳት ብቸኛ መድሃኒት ነው ብለን ካመንን ቆይተናል።

ዓለም አቀፋዊው አመለካከታችን ከሌሎች አገሮችና ሕዝቦች ጋር የምንገናኝበት የውጪ ግንኙነት መርሖዋችንና የእድገት አቅጣጫ መመሪያችን ሕብረተሰባዊነት ወይም ሶሻሊዝም በመሆኑ ፀረ-ኢምፔርያሊስት ነን ከሚሉትና ግን እኛን ከሚተናኮሉት ያካባቢው

ግራ ዘመም መንግሥታት ጋር ሶማሊያንና ሱዳንን ጨምሮ ሰላምና መልካም ጉርብትና መፍጠር ይቻላል ብለን ተንብየናል።

ሰላምና መልካም ጉርብትና ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ሄደን በንግድ ልውውጥ ጋራ ልማትና ተፈጥሮ ባደለን የጋራ ሀብት በመረዳዳት በአፍሪካ ቀንድ ሰላማዊ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ፣ የሕዝቦች ግምባር ወይም ሕብረት የመፍጠር ምኞትና የህልና ዝግጅትም ነበረን።

በአካባቢያችን ያሉ አብዛኞዎቹ ግራዘመም የሆኑ አገሮች ዓለም አቀፋዊ ከሆኑት ሕብረተሰባዊ ኃይሎች ጋር ፀረ-ኢምፔርያሊስት ግምባር ወይም ሕብረት የፈጠሩ ስለሆነ መላው የዓለም ተራማጅ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሕዝባዊ ቻይናና በተለይም ታላቋ ሶቭየት ሕብረት በዋርሶ መማሪያ እንድንጠቃና የኢትዮጵያ አብዮት ሳይፈነዳ እንዲዳፈን ለማይፈልጉ የእኛ ባላጋራ በሆኑትና በእነሱ የሚረዱት የውጭና የውስጥ ጠላቶቻችን መካከል ያለው ቅራኔ ወደ ለየለት ጥፋትና ጦርነት እንዳያመራ ገንቢ ተጽዕኖ ያደርጋሉ የሚል እምነት ነበረን።

የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ባልደረባ የሆንን ሃገር ወዳዶች፣ ዲሞክራቶችና አብዮታዊ ዲሞክራቶች ለአገራችን ይህንን አብዮታዊ አቅጣጫ ስንመርጥ ወይም ማህበራዊ ሥርዓት ስንመኝ አብዮታችንን ከአንድነታችን፣ ሰላምን ከሶሻሊዝም በመለየት ተመልክተን አናውቅም።

በቅድመ አብዮት በተለይም በአብዮቱ ዋዜማ ኢትዮጵያን ሳይሆን ጉልታዊውን ሥርዓት የሚገዘግዙ የአብዮት ወገንና ቅምጥ ኃይል አድርገን ስንመለከታቸው የነበሩና ድህረ አብዮት ገንጣይና አስገንጣይ ሆነው ያገኘናቸው ድርጅቶች በተለይ ጀብሃና ሻዕብያ ሰሜኑ የአገራችን ክልሎች የሚያካሄዱትን ጥፋትና ሽብር "ሕዝባዊ አብዮት እያካሄድን ነው" እያሉ የሚነግሩንን እምነን ለመቀበል ዳድተን ነበር።

በዚህ ወቅት ወይም የጊዜ ክልል ውስጥ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር በተለይም በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የነበሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አመራር አካላትና አባላት ከጀብሃና ከሻዕቢያ ጋር የፈጠሩት ግንኙነትና የነበራቸው አስተያየት ለኛ የተሳሳተ ግምት አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከሰሜኑ ሠራዊታችን በምናገኘው መረጃ የተረዳነው ነገር ገንጣዮቹ የምናራምደው አብዮት ነው እያሉ በአንደኛ ደረጃ ፀራቸውና ጠላታቸው አድርገው የሚመለከቱትና የጥፋት ዒላማቸው ያደረጉት የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትና ኢትዮጵያዊውን ብሔራዊ ስሜት ነው።

"ኢትዮጵያ ወይም ሞት" በማለት ታግለውና አታግለው የኤርትራን ክፍለ ሀገር ሕዝብ መልሰው ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያቀላቀሉትን ሃገር ወዳድ አርበኞች በነቂስ እየመረጡ የሚረሽኑ መሆናቸውን ነው።

አርበኞቹን እየመረጡ በመጨፍጨፍ ካገባደዱ በኋላ ማለት ይቻላል እነሱ እንደሚሉት አብዮታዊ ተግባር አድርገው የተያያዙት መላውን በክፍለ አገሩ ያሉትን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኞች ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ነው።

በዚህ እጅግ አሳዛኝ በሆነ የጊዜ ክልል ውስጥ አርበኞቹና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው ሕዝብ የገንጣዮች ሰለባ በሆኑበት ጊዜ በክልሉ የተሰማሩት የመንግሥቱ ሠራዊትና ሕግ

አስከባሪ ፖሊሶች ሕዝቡን ከጥቃት ሊከላከሉ ቀርቶ የራሳቸውንም ወታደራዊ አዛዦች ሊያድኑ አልቻሉም ነበር።

በዚህ የተነሳ አብዛኛው ደገኛው ማለትም የሀማሴን፣ የአካለ ጉዛይና የሰራኤ አውራጃ ነዋሪዎች የሆኑት ከተሜውም ገጠሬውም መኖሪያ ክልሉን እየለቀቀ ነፍሱን ለማዳን ወደ ትግራይ፣ ወሎ፣ ጎንደርና ወደ መሃል ሃገር ሲሰደድ፣ ቆለኛው ወደሚቀርበው ወደ ሱዳን ሄደ።

በራሱ አነሳሽነትና ጥረት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከተሰደደው ሌላ በተደራጀ መልክ መንግሥት በወል እያንቀሳቀሰ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በሸዋና በከፋ የመንግሥት መሬት ላይ ያሰፈራቸው የኤርትራ ገበሬዎች ብዙ ናቸው።

ከቤተሰቦቻቸው ብዛትና ከአቅማቸው ውስንነት እርቀው በመሄድ ወደ መሃል ሃገር ለመጓጓዝ ያልቻሉትና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኤርትራ ገበሬዎች ወደ ትግራይ ሽሬ፣ አክሱም፣ ተንቤን፣ አድዋና አጋሜ ወዘተ በመምጣት በድህረ አብዮታዊ ሠራዊታችን አብዛኛውን የኤርትራ ክፍለ ሃገር አውራጃዎች ከገንጣዮች እስኪያጸዳ ድረስ ለዓመታት በመጠለያ እየኖሩ በመንግሥት ይረዱ ነበር።

በዚህ የጥቃት ምሬት ምክንያት አብዮታዊ ሠራዊታችን አብዛኛውን የኤርትራ ምድር ከተቆጣጠረም በኋላ ፀና ድንግል የሚባለው የአንድ ወረዳ ሕዝብ መንግሥት ካላስታጠቀን በቀር ከአክሱም መጠለያ አንሄድም በማለታቸው እንዲታጠቁ ማድረጋችንን አስታውሳለሁ።

ሻዕቢያ በአምሳሉ ፈጥሮ፣ ኮትኩቶ በማሳደግ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ሱሪም አስታጥቆ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያስማራቸው ወያኔዎች በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈፀሙት፡ ጀብሃና ሻዕቢያ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የፈፀሙትን ነው። ስለዚህም ነው የኤርትራን ሕዝብ ከሻዕቢያ፣ የትግራይን ሕዝብ ከወያኔ ማገናኘት ታላቅ ስህተት ነው የምንለው።

የቅርብና የሩቅ ጠላት ከምንላቸው ኃይሎች አሰላለፍ ጋር ወቅታዊውን የፖለቲካ ሁኔታ በማስላት፣ መጭውን ጊዜ በጎና የተሻለ አድርገን በመመልከት ራሳችንን በማፅናናት ኢትዮጵያ ያረገዘችው አብዮት መወለድ አለበት፣ አገራችንንም አብዮቱንም በአንድነት ለማዳን ማናቸውም መስዋዕትነት መከፈል አለበት ብንልም ለምኞታችን ተግባራዊነት ፍፁም እርግጠኞች ነበርን ብንልም ስጋትና ፍርሀታችን ተወግዷል ማለት ግን አልነበረም። በአብዮቱ ዋዜማ ላይ በጦር ኃይሉ በኩል የነበረው መሠረታዊ ስጋት ለወረራ አሰፍስፎ በጋራ ድንበራችን ላይ አመቺ ጊዜ የሚጠባበቀውን ወራሪ ሠራዊትና ተስፋፊ የሶማሊያ መንግሥት የኛን ሰላም ፈላጊነትና አብዮታዊ ምኞት ተጋሪ ያለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የቆየ በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ ከአሁን የተሻለ ጊዜ የለም በሚል አቋም ለወረራ ነበር የሚጠባበቁት።

ሌላው ጎረቤታችንና በተዘዋዋሪው ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በበለጠ እያደማን ያለው የሱዳን መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት የሚወስደን የመሬት ጥያቄ አለ ብለን በእኛ በኩል በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ባንመለከተውም ባልተለመደ ሁኔታ በጋራ ድንበራችን በተሰኔ፣ በሁመራ፣ በመተማና በአብዱራፌ በከባድ መሣሪያዎችና በአየር ኃይል የተደገፉ ሜካናይዝድ የጦር ክፍሎች አሰልፎ ነበር።

ከዚህ በተረፈ ሌሎች ችግሮችም የሉም ባይባሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚ ግንባታ ጎልብቷል፣ የፖለቲካ ንቃቱ አድጓልና የአብዮቱ መወለድ የሚያስፈልጉ መንፈሳዊና

ቁሳዊ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፤ ሕዝቡን የሚያስተባብርና የሚያታግል አብዮታዊ ፓርቲ ተመስርቷል ባይባልም ሕዝቡ የለውጡ ተዋናይ መሆኑን ከጀመረ ቆይቷል።

የየማህበረሰቡና የየብሄረሰቡ ወኪል፤ ነፃ አውጪና ለውጥ አምጪ አብዮተኞች ነን የሚሉን ድርጅቶች ተግባራቸው ከቃላቸው ጋር የተጣላ ሆኖ ስለተቸገርን የእነኝህ ኃይሎች አፍራሽ ዓላማ አስለውጠን በመጪው ሕዝባዊ አብዮት ውስጥ እንዴት ማካተት ወይም ክንፋችን ማሰለፍ ይቻላል? አብዮቱ ሲፈነዳ የእነዚህ ድርጅቶች አቋም ምን ሊሆን ይችላል? የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩን።

በዚህ ጊዜና በዚህ ምክንያት ነው የምሥራቁ ሠራዊት አብዮታዊ ኮሚቴ ልኮኝ ኤርትራ ያለውን የፖለቲካ ቀውስ አነሳስን መፍትሄውንም አውቃለሁ እያሉ ሲነግሩኝ የነበሩ የቀድሞው የክፍለ ጦር አዛዡና በግል ወዳጄና ባለውለታዬ የሆኑትን ሜ/ጄነራል አማን ሚካኤል አንዶምን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ እየመጣሁ ለሦስት ጊዜ ያህል በአዲስ አበባ ቤታቸው የቅርብ ጓደኛዬና የአመለካከቴ ተጋሪ ከነበረው ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ጋር ሆነን ያነጋገርናቸው።

ከጄነራል አማን ጋር ያደረግናቸውን የውይይት ይዘቶች ብቻ ሳይሆን ስለጄነራል አማን ጠቅላላ ማንነት ከዚህ በሚቀጥለው የመጽሐፍ ክፍል በዝርዝር ለአንባቢ እንደማስረዳ በመግለጽ ወደ ዋናው ርእስ እመራለሁ።

ሃገርን ለውጭ ወራሪዎች ጥቃት ማመቻቸት፣ ከአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶችና የመሬት ባላንጣዎች ጋር መተባበር፣ ሃገርን መገንጠል ማስገንጠልና አንዱን ሕዝብ በጎጥ በሃይማኖት መከፋፈል፣ የሕዝቡን የጠነከረ የሃገር ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት ከመሸርሸር ባሻገር ኢትዮጵያዊ ብሔርተኞችንና አብዮተኞችን ስምና ታሪክ ማጥፋትና መፍጀት ኢትዮጵያዊነትን ከማጥፋት በስተቀር ሌላ ትርጉም ለመስጠት ስለማይቻል ቢቻላቸው ወይም ቢሳካላቸው የጎጠኞች ዓላማና ግብ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነት ማጥፋት ነው ብለን አበክረን ስንናገር የነበረው ለዚህ ነው።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሰፍሮ ለአገሩ የጠረፍ ጥበቃ ተግባር ሲያከናውን የነበረው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር ለጉብኝት የሄዱትን ሌ/ጄነራል ድረሴ ዱባለ የሚባሉትን የምድር ጦር አዛዥ በቁጥጥር ስር አውሎ ጦሩ በዚያን ጊዜ ይኖር የነበረውን አስከፊና ጎስቋላ ኑሮ እንዲያዩ በማድረግ የጀመረውን አመፅ በድህረ አብዮት የአራተኛውን እግረኛ ብርጌድ ጦር የአብዮት ፋና ወጊ የተሰኘ ስም አሰጥቶታል።

ከአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር የአብዮት ፋና ወጊ አመጽ በኋላ በኢትዮጵያ ጉልታዊ ገዥ መደቦች መካከል የሚታየው አባዜ መደባቸውንና ሥርዓት-ማህበራቸውን ሊያጠፋ የተቃረበ አደጋ የሚያንዣብብባቸው መሆኑን ካለመገንዘብ ይመስላል ንጉሡ ስላረጁና ስለተዳከሙ ዙፋኑን የሚወርስ ማን ነው? በሚል ጥያቄ ታላቅ የሥልጣን ትግል ተጀምሮ ነበር።

ለሥልጣን ይታገሉ ከነበሩት ቡድኖች መካከል የመጀመሪያው በሥልጣን ላይ ያለው የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ቡድን ሲሆን ዓላማው፣ ከዚህ በየተራ የሚጠቀሱትንና የሱ ተጻራሪ የሆኑትን መሣፍንታዊ ቡድኖች ሴራ ተቋቁሞ ድል በመንሳት ህገ መንግሥቱ በሚደነግገው ሕግ መሠረት የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንን ወራሽነት ማጽናትና የአስተዳደሩን ሥልጣን አጠናክሮ የመቀጠል ሲሆን ያልጋ ወራሽ ደጋፊ የሆኑ ጥቂት መሣፍንት ያሉበት፣ በአያሌ መኳንንቶች የተበረዘ የነባሩ የኢትዮጵያ ቢሮክራሲያዊ ቡድን ነበር።

ሁለተኛውና ከሌሎች ቡድኖች ጋር ሲነፃፀር አንፃራዊ ጥንካሬ የነበረው የወጣት መሣፍንትና መኳንንት እንዲሁም ቢሮክራቶች ጥርቅም የሆነው የልጅ እንዳልካቸው መኮንን ቡድን ሲሆን እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ቡድን የአፄ ኃይለሥላሴን ሥልጣንና እንዲሁም የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንን ዘውድ ወራሽነት በመደገፍ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉን ፈንቅሎ መስተዳድሩን በመቆጣጠር ጥገናዊ የፖለቲካ ለውጥ ለማድረግ የተነሳ ቡድን ነበር።

ሦስተኛው የልዑል እሥራተ ካሳ የመሣፍንትና የመኳንንት ጥምር ቡድን ወጣቱን ልዑል ወሰንሰገድ መኮንን አንግሦ የገዥ መደብነቱን ሥልጣን በተወሰነ የጥገና ለውጥ አሻሽሎ ለመቀጠል የተዘጋጀ ቡድን ነው።

አራተኛውን በኔ መረጃ የመጨረሻው የዘውድ ሥልጣን ተቀናቃኝ የልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለሥላሴ ቡድን ነው። ይህ ቡድን የአፄ ኃይለሥላሴ ደጋፊ የሆነውን መላው የአማራ ሞጃ ያቀፈው ነው እያሰኘ ቢያስነግርም የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንን የዙፋን ወራሽነት የማይቀበል፣ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አያሌ አድርባዮችን በማሰባሰብ ሌላውን የንጉሡን የልጅ ልጅ ወጣቱን የኢትዮጵያ የባሕር ኃይል አዛዥ አድሚራል እስክንድር ደስታን ለማንገስ የሚታገል ብቻ ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ  ፅኑ ተቃዋሚ የሆነና ከውጭም የአሜሪካን፣ የእንግሊዝና የሌሎችም የምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት ድጋፍ አለኝ እያለ የሚያወራ ቡድን ነው።

እነዚህ የዘውድ ሥልጣን ተቀናቃኝ የሆኑ አራት የጉልታዊት ኢትዮጵያ ገዥ መደቦች አንዱ ሌላውን በመፍራትና በመጠበቅ ከሚያደርጉት ጥንቃቄ የተሞላው ህቡዕ እንቅስቃሴና ታላቅ ምኞት ባሻገር በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዘንድ ታዋቂነትና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው የሚያሰኝ ተጨባጭ መረጃ የለንም።

ንጉሡ በዚህ ጊዜ ሁሉንም እያስተዋሉ ከአንዱም ጋር ያለመወገንና አንዱንም ያለመኮነን አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ  እስኪወድቁ ድረስ የመሃል ሰፋሪነት ሚና ለመጫወት የወሰኑ ይመስላል።

በኢትዮጵያ ረጅም የጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ታሪካዊ ሂደት የፖለቲካ ሥልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ሳይሆን ከኃይል ወይም ከጠመንጃ አፈሙዝ ስለሆነ እነዚህ ቡድኖች የጦር ኃይሉን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ የጦር ኃይሉን ከፍተኛ መኮንኖች ለማስወገን በመቀራመት ያደርጉት በነበረው ጥረት የሠራዊቱን አዛዦች ፍፁም ከፋፍለዋቸው ነበር ለማለት ይቻላል።

የጦር ኃይሉ ከፍተኛ መኮንኖች አብዛኞዎቹ ማለት ይቻላል'የአፄ ኃይለሥላሴ ታማኝ ሲሆኑ ከእሳቸው በኋላ ስለሚሆነው ነገር በአቋም እንዲለያዩ ያደረጋቸው የልዑል አልጋ ወራሾች አስፋወሰን የጤና መጓደል ነው ተብሎ ይታመናል።

እዚህ ላይ የሚያስገርመው የጦር ኃይሉ ከፍተኛ መኮንኖች ከተለያዩ ጉልታዊ ገዥ መደቦች ጋር ሲወግኑና የየራሳቸውን ምርጫ ሲወስኑ የሚመሩትን ሠራዊት የፖለቲካ አቋምና ምርጫ አለማወቃቸው ነው።

አብዛኛው የጦር ኃይሉ ወጣት መኮንኖች በነበረን መረጃ ከከፍተኛ መኮንኖቻችን መካከል ፊውዳላዊውን የገዥ መደብ አካላት ገፍተው የፖለቲካ ሥልጣን የመያዝ ምኞትና ፍላጎት አላቸው የምንላቸውና የምንከተላቸው ግለሰቦች አልነበሩም። እንደሚታወቀው በእኛ ትውልድና በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት ለፊውዳሉ ገዥ መደብ የቀረቡ የፖለቲካ

ጥያቄዎች ቢኖሩም አንዱና ዋናው የጄነራል መንግሥቱ ነዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሲሆን ሁለተኛው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያቀረቡት የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ነበር።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ አንድም የሕብረተሰብ ክፍል ወይም መደብ በግልና በቡድን፣ በተለያየ መልክ አመጽ ከመሞከርና በተለያየ መልክ ስሞታ ከማቅረብ፣ ብሶትን ከመግለጽና መንግሥትን ከማማት አልፎ በተደራጀ መልክ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ለማቅረብ የበቃ የለም።

በቂ ሕዝባዊ የፖለቲካ ንቃትና መሪ የፖለቲካ ድርጅት በሌለበት ሃገር የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ለማቅረብ ቀርቶ ለማሰብም ያዳግታል። ይህም በመሆኑ አገራችን በነበረችበት አብዮት መቃረቢያ መጨረሻ ጊዜ ገደማና በአብዮቱ ዋዜማ በታዬው ድፍርስ ባለ ሁኔታ ውስጥ ንጉሡ ቢያርፉ የፖለቲካ ወና ወይም ሥርዓተ አልበኝነት ተፈጥሮ አገራችን ለውስጥ ርቢሪዎችና ለውጭ ወራሪዎች ጥቃት ከመጋለጧ በፊት ሁኔታዎችን ተቆጣጥሮ የተረጋጋ ሰላማዊ የሽግግር ጊዜ ለመፍጠር የጦር ኃይሉን አስተባብሮ ሊመራ የሚችል መኮንን ማንነው እየተባለ በሠራዊቱ ዘንድ ሰው ሲፈልግ ነበር።

በየጦር ክፍሎች ውስጥ በሀሳብና በውይይት ደረጃ በአማራጭ ስማቸው ከሚነሳ ጄነራል መኮንኖቻችን እነጄነራል ከበደ ገብሬ፣ አሰፋ አያና፣ አበበ ገመዳ እና አማን ሚካኤል አንዶም ነበሩ። እነዚህ መኮንኖች የረጅም ጊዜ የሥራ ልምድ፣ የፖለቲካ ተሞክሮ፣ የሃገር ፍቅርና በሠራዊት አመራርም መልካም ስም ያተረፉ በመሆናቸው እንያንዳንዱ ወጣት መኮንን ከነዚህ መካከል የየራሱ ምርጫ ቢኖረውም ወደ ኋላ መሸ በማለት ይመስላል ሠራዊቱ ካስቀመጣቸው ክቡር ስፍራ እየወረዱ ወደ ግል ጥቅም ብቻ ስላደሉ የእኔ እናት የጦር ክፍል በሆነው በአንበሳው ሦስተኛ ክፍለ ጦር ወጣት መኮንኖች በኩል አስፈላጊ ከሆነ ታሳቢ ያደረግናቸው ጄነራል አማንን ብቻ ነበር።

ከንጉሡ እረፍት በኋላ ራሳቸውን ለሥልጣን በማጩት የተደራጁ ቡድኖች ሁሉም ማለት ይቻላል ከንጉሡ እረፍት በፊት ከወዲሁ መስተዳድሩን ለመቆጣጠር ይቻላቸው ዘንድ እያንዳንዳቸው በጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ መንግሥት ላይ በማሴር አንዳንድ ደባና አሻጥሮችን ይሰሩ ነበር።

ለማስረጃ ያህል ከብዙዎቹ ጥቂቱን ብጠቅስ ሰላም ለማስከበር በተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት ጥያቄ ከኢትዮጵያ ወደ ኮንጎ ተልኮ የነበረው የጠቅል ብርጌድ በመባል የሚታወቀውን የጦር ክፍል አባላት የተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት የከፈላችሁን የአገልግሎትና የደም አበል የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ መንግሥት ወስዶባችኋል በሚል የሐሰት ክስ ጦሩ የአበል ጥያቄ ያቀረበው እንዳልተከፈለው አምኖ በራሱ አነሳሽነት ሳይሆን የመሳፍንቱ ቡድን አቶ አክሊሉን ከጦር ኃይሉ ጋር ለማቃቃር ብሎ የፈጠረው ሴራ ነበር።

በሰሜን ኢትዮጵያ ሰፍሮ የሚገኘው የሁለተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት የአራተኛውን እግረኛ ብርጌድ ጦር ፋና ወጊነት በመደገፍ በበኩሉ የክፍለ ጦሩን አዛዥና ምክትል አዛዥ፣ ከሻለቃ ማዕረግ በላይ ያሉትን ከፍተኛ መኮንኖችና የክልሉን ሲቪል ባለሥልጣኖች በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የካቲት 19 ቀን 1966 ዓ.ም ለንጉሡ ያቀረበው አብይ ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድ ከሥልጣናቸው እንዲነሱ ነው።

ከዚህ በኋላ የተቀሩት የጦር ኃይሎችና የተለያዩ የጦር ክፍሎች በተለይም የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይልና የአራተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት የሰሜኑን ጦር ጥያቄና

ንቅናቄ እንደሚደግፉ አሳውቀው ሲነሱ መንግሥት ሁኔታውን ሸንግሎ ለማብረድ ሲል የካቲት 20 አራት ከፍተኛ ጄነራሎች ያካተተ ልዑካን ላከ።

ልዑካኑ አሥመራ እንደደረሱ ሠራዊቱ እንደተለመደው ተቀብሎ ማረፊያ ቤት አስቀምጦ የመጡበትን ጉዳይ ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ልዑካኑን ለሁለት ከፍሎ አንዱን ክፍል በመያዣነት ይዞ ሌላውን ክፍል ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው 23 ተራ የያዙ ጥያቄዎችን አስይዞ በመመለስ ወደ አዲስ አበባ ላካቸው።

በዚህ ጊዜ ውስጥ የሁለተኛውን እግረኛ ክፍለ ጦር በመደገፍ የባሕር ኃይል አዛዦቹን በቁጥጥሩ ስር ሲያደርግ የተመለከቱትና ለንጉሥነት የታጩት የባሕር ኃይሉ ዋና አዛዥና ምክትል አዛዥ በአንዲት ጀልባ ተሳፍረው በማምለጥ ቀይ ባሕርን ቀዝፈው በጂቡቲ በኩል አዲስ አበባ ገቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ የወቅቱን የአገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታ በማመዛዘንና ልዑካኑ ጄነራሎች ከሰሜኑ ሠራዊት ተቀብለው ያመጡትን የፖለቲካ ጥያቄዎች በመመልከት ንጉሡ ከሥራ እንዲያሰናብቷቸው ጠየቁ።

የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉን ከሥራ ስንብት ጥያቄ ንጉሡ አልቀበልም አሉ ተብሎ በአገሪቱ የብዙሃን ማሰራጫ ዜናው ሲናኝ በአገራችን ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ አዲስ ክስተት ስለነበረ ማንንም ያስገረመ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጉልታዊ ሥርዓትና የገዥ መደቦቹ ቤተመንግሥት ለመፍረስ እየነቃቃ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነበር።

ይህንን አመጽ የስር ነቀል ለውጥ አቀንቃኝ የሆኑ ወጣት መኮንኖች ሳይጠቀሙበት ቅደሙ ተብለው በመጣፍንቱ የተገፉ ከፍተኛ መኮንኖች ሠራዊቱ ሚይመርጣቸው ሠራዊቱ ለንጉሡ ያቀረባቸውን ጥያቄዎችና የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉን ከሥልጣን መነሳት እናስተናግዳለን ብለው በመጠቃቀስና በመጠራራት በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ተሰበሰቡ።

በነበረው ጠቅላላ የፖለቲካ ውዥንብር የእነዚህን ከፍተኛ መኮንኖች ዓላማ በውል ያጤነውና ከሠራዊቱ ወገን የደገፈም የነቀፈም አልነበረም።

ይህ የጊዜ ክልልና መኮንኖቹ ሊሰጡ የሞከሩት አመራር አንደኛው ዙር የጦር ኃይሎች ንቅናቄ በመባል ሲታወቅ ያከናወኑት ተግባር ለሠራዊቱ ደሞዝ ማስጨመርና አቶ አክሊሉን አስነስቶ ልጅ እንዳልካቸውን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መተካት ነበር።

## ምዕራፍ ሦስት

# የአብዮቱ አጥብያ

የአብዮቱ አጥብያ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ከሥልጣናቸው ወርደው ልጅ እንዳልካቸው ከተተኩበት ጊዜ ጀምሮ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ እስከ ተቋቋመበት ወይም የጦር ኃይሎች ሦስተኛውና የመጨረሻው አብዮታዊ ንቅናቄ በመባል የሚታወቀውን ከየካቲት 21 እስከ ሰኔ 21 ድረስ ያለውን የጊዜ ክልል ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ መንግሥት ፈርሶ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት እስኪቋቋምና ከተቋቋመም በኋላ ከየካቲት ወር መገባደጃ እስከ ሚያዝያ ወር አጋማሽ አገሪቱን የሚመራ መንግሥትም ሆነ አንድ ማዕከል ነበር ለማለት ያስቸግራል።

የጉልታዊው ሥርዓት አራማጅ ገዥ መደብ ጋሻና መከታ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ ዋነተኛ መሣሪያ ከነበሩት ተቋማት ዋናዎቹ የአገሪቱ የጦር ኃይሎች በገሃድ በሥርዓቱ ላይ አምጸው መነሳታቸውን ያስተዋለው ሕዝብ እንግዲህ ወዲያ ማን ሊፈራ በማለት የአያሌ ዘመናት ብሶቱን በማሰማትና በማሳወቅ ያለማቋረጥ በየፈርጁ በፈረቃና በሕብረት በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የተቃውሞ ሰላማዊ ሠልፍና የሥራ ማቆም አድማ ያደረገበት ጊዜ ነው።

የመንግሥቱ ፀጥታ አስከባሪ የሆነው የፖሊስ ሠራዊትና የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ኃይሎች የሕዝቡን አባዜና የጊዜውን አደገኝነት በመመልከት ይሁን ወይም ከሕዝቡ በመወገን ለሕዝቡ አመፃዊ እንቅስቃሴ ጣልቃ ሳይገቡ እንደማናቸውም የህብረተሰቡ ክፍሎች ዳር ቆመው እንደ ታዛቢ መመልከቱን መርጠው ነበር።

በኃላፊነት ስሜትና በድፍረት እንደ ወትሮው ከየትኛውም የበላይ አካል በግልም ሆነ በወል ትዕዛዝና አመራር የሚሰጥ አልነበረም።

አዲሱ የልጅ እንዳልካቸው ካቢኔ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በዚያ ፈታኝ በሆነ ቀውጢ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ሊሰራ እንደሚችል የራሱን ሁኔታ ማረጋገጥ፣ በዚህ ቀውጢ ሁኔታ ውስጥ ሊሰራ የሚችል የሰው ኃይል ማሰባሰብ፣ በአገሪቱ ውስጥ ከሚታዩው ቀውስ የተሞላው አስቸጋሪ ሁኔታ ጋር የሚመጥን አዲስ ዘዴና የሥራ መመሪያ መንደፍና ራሱን ብቁ ማዘጋጀት ነበረበት።

የአገሪቱ የጦር ኃይሎች፣ ፀጥታ አስከባሪዎችና የደህንነት ክፍሎች የፀጥታውን ችግር የሚያቃልሉ ሳይሆኑ ከሬሉ ዳር ቆመው እንደ ታዛቢ ሲያስተውሉ ከሬሉ በአመጹ ግምባር

ቀደም ስለሆኑ የእነኝህን ኃይሎች ድጋፍና ትብብር ለማግኘት ጊዜ ሰጡን እያሉ መለመንና መማጠን ነበረበት።

ሆኖም ጊዜው የአመጽና የነውጥ ጊዜ ስለነበር መስማማት ቀርቶ መደማመጥም አልነበረም። ከሥልጣን የወረደው የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ካቢኔ አባላትና መላው እድምተኞቻቸው የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ድል ተመትቶ ከአገራችን ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ይህችን ሃገር እንደ ሃገር ለማቆምና አሁን ያለችበት ደረጃ ላይ ለማድረስ እንዳልደከምን፣ ንጉሡን ጨምሮ ሁሉም ከእኛ ጋር እንዳልነበሩ ሁሉ ዛሬ ለደረሰው የአገሪቱ ችግር እንዴት እኛ ብቸኛ ኃላፊዎችና ተጠያቂዎች ሆነን በጦር ኃይሉ፣ በሕዝቡና በእንዳልካቸው መንግሥት እንወዛለን? እንዴትስ እንደ ወንጀለኛ ለፍርድ ይቅረቡ እንባላለን? እነሱ ማን ሆነው ከእኛስ በምን ተሽለው ነው? በማለት በተቻላቸው ሁሉ ፀረ-እንዳልካቸው ትግል ጀምረው ነበር።

የጦር ኃይሎች የእዝ ሰንሰለት በየክልሉና በየጦር ክፍሉ ተሰብሮ ወይም ተቆርጦ ሠራዊቱ የሚመራው በጊዜያዊ ህቡዕ ኮሚቴዎች ነበር።

በመላ አገሪቱ ባሉ የተለያዩ የማምረቻ፣ የአገልግሎት መስጫና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የሚሰሩ ሠራተኞችም እንደ ሠራዊቱ ከአሰሪዎችና ከበላይ አመራር አካላት ጋር የነበራቸውን መደበኛ የሥራ ግንኙነትና የእዝ ሰንሰለት ቆርጠው የየራሳቸውን ሕዝባዊ የአመራር ኮሚቴ አቋቁመዋል።

በዚህ ሁኔታ የአገሪቱ ገዢ መደብ እንደ መንግሥት አንዳችም ነገር ለማከናወን በማይችልበት፣ የአገሪቱ ዕለት ተለት አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ፈጽሞ የተገቱ ብቻ ሳይሆን፣ በኤርትራ፣ በኦጋዴንና በባሌ የሚካሄዱት የፖለቲካ ቀውሶችና አጠቃላይ የአገሪቱ ዳር ድንበር፣ አንድነትና የመከላከያ ጉዳይ ባለቤት ያጣበት ጊዜ ነበር።

የአገሪቱ መላ ተማሪዎችና በየትኛውም ደረጃ ያሉ መምህራን የአዲስ አበባን ዩኒቨርሲቲ ጨምሮ ለሕዝባዊው አመጽ የበለጠ ግፊት ለመስጠት ይመስላል የመማርና የማስተማሩን ሥራ አቁመዋል።

የአገሪቱ የሠራተኛ ማህበር ማዕከላዊ አመራር በየክልሉ ያሉትን የሠራተኛ ማህበር ቅርንጫፎችና ዘርፎች የአመራር አካላት ከያሉበት ወደ አዲስ አበባ ጠርቶ ከየካቲት 16 እስከ 22 በአዲስ አበባው የማህበሩ ምክር ቤት ሲዶልት ሰንብቶ 16 ተራ የያዙ ጥያቄዎችን ለአዲሱ መንግሥት በማቅረብ ለጥያቄው ተገቢው መልስ እስከ የካቲት 28 ቀን ድረስ ባይሰጠው ሃገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ እንደሚጀምር አሳውቆና አስጠንቅቆ ተበተነ።

የጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መንግሥት በዚያ አስቸጋሪና አጭር ጊዜ ውስጥ በሕዝቡና በሠራዊቱ ዘንድ ድጋፍና ተቀባይነት ለማግኘት ያደረገው ጥረትና የተጠቀመው ስልት ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም።

በየካቲት ንቅናቄ በአራተኛ እግረኛ ብርጌድ የአመጽ ፋና ወጊነት የተጀመረውን የተለያዩ የጦር ክፍሎች እየተቀባበሉ አመጹን ያስፋፉት ቢሆንም በአከናወኑት አመጻዊ ተግባር ሁሉም የሚያምኑ፣ የዓላማና የተግባር አንድነት ወይም ፍፁም ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው ማለት አልነበረም።

እንደ ተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ሠራዊቱም በመደብ የተከፋፈለ ሕብረተሰብ ነበር። አብዛኛዎቹ የሠራዊቱ ከፍተኛ የአመራር አካላት ከጉልታዊው ገዥ መደብ ጋር በደም፣ በጋብቻና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው።

በደምና በጋብቻ የተሳሰሩ ባይሆኑም ንጉሡ እራሳቸው የግለሰቦቹን አቋም ከጠዋቱ ከመጣትነታቸው ጊዜ ጀምሮ በሚገባ እያጠኑና እየተከታተሉ መርጠውና ኮትኩተው ያሳደጓቸው ማደጎዎች ስለሆኑ ከደረሱበት የእድሜ ክልልና የማዕረግ ደረጃ አኳያ ኑሮና የመደፊት እድላቸውን ከንጉሡ ሕይወት ለይተው የማይመለከቱ ፍፁም ታማኞች ናቸው ማለት ይቻላል።

እንዲህ ያሉ የጦር አመራር አካላት በበዙበትና ለብዙ ዘመን በመሩበት ሃገር በዝቅተኛ መኮንኖችና በሰፊው ሠራዊት ውስጥ ያለው ማህበራዊ ንቃትና ፖለቲካዊ ግንዛቤ የበላይ አመራሩ ነጸብራቅ ከመሆን እምብዛም እንደማያመልጥ የታወቀ ነበር።

የሠራዊቱን ምንነት፣ የአገሪቱን እጅግ ኋላ ቀርነትና የሕዝቡን አሣፋሪ ድህነት በሚገባ የተገነዘቡና ሥርዓቱ እንዲለወጥ የሚፈልጉ አብዮታዊ ዲሞክራት መኮንኖች ቁጥር ከሠራዊቱ መጠን አንጻር ሲታይ እጅግ ዝቅተኛ ነበር።

እምብዛም ለለውጥ የማይታገሉ ወይም መጋፈጥ የማይፈልጉ ግን ከሥርዓቱ መውደቅ ምንም የማያጡ፣ ከድሃው ሕብረተሰብ አብራክ የወጡና በፖለቲካ አመለካከታቸው ሊበራል የሆኑ የሠራዊቱ አባል ቁጥር ግን ከፍተኛ ነበር።

አብዮታዊያን ለሚያደርጉት ቅስቀሳ ፈጥነው ጆሯቸውን በመክፈት ለለውጡ ሕይወትና ግፊት በመስጠት አመጹን ለሚያራምደው ሠራዊት የጀርባ አጥንት የሆኑት እነዚህ ክፍሎች ናቸው።

ጀነራል መኮንኖች በመሩት አንደኛ የጦር ኃይሎች ንቅናቄ ለሠራዊቱ ደሞዝ ከመጨመሩ ባሻገር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥት ለማስለወጥ መቻሉ እንደ ሥርዓት ለውጥ ተደርጎ በመታየቱ በዚህ የረኩና ልጅ እንዳልካቸው ፋታ ስጡን እያሉ ለሚያሰሙት ጩኸት ጆሯቸውን የሰጡ የጦር ኃይሉ አባላት ቁጥር ቀላል አልነበረም።

ልጅ እንዳልካቸው በዚህ ሁኔታ ተጠቅመው አብዮቱን ለማዳፈን ይችላሉ ብለው የገመቷቸውንና በሠራዊቱም ዘንድ እስከዚያ ጊዜ ድረስ መልካም ስምና ታዋቂነት ያላቸውን ቁልጣብልጥ የሆኑ ከፍተኛ መኮንኖችን መመልመሉ የሥራቸው መጀመሪያና ዋናውም ነበር።

ምልምል መኮንኖቹ "ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ፋታ እንስጣቸው፣ የንጉሣዊያን ቤተሰብ በመሆናቸው ብቻ በስሜት ከምንጠላቸው እንዲሰሩ እድሉን ሰጥተን በተግባር እንመዝናቸው" በሚል በመላው ሠራዊት ውስጥ ቅስቀሳ ጀምረው ነበር።

ቅስቀሳውን ለማካሄድ መሣሪያ የሆናቸውና ለአጭር ጊዜ በከፊልም ቢሆን እንዲደመጡ ያደረጋቸው አዲስ ሕገ መንግሥት ይረቀቅ ዘንድ በአጣዳፊ ሕገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔን ያቋቋመውና ያላግባብ የበለፀጉ፣ በፖለቲካ ሥልጣናቸው የባለጉ፣ በተለያየ መንገድ ሕዝብን የበደሉ የቀድሞ ባለስልጣኖችን ወንጀል መርምሮ ለፍርድ የሚያቀርብ መርማሪ ኮሚሽን እንዲቋቋም ይደርጋል የሚለው የእንዳልካቸው የፖለቲካ ፕሮግራም ነው።

ልጅ እንዳልካቸው ይህንን የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ካወጡ በኋላ የጦር ኃይሉን በተመለከተ የወሰዱት ሌላው እርምጃ በሠራዊቱ ውስጥ አጠቃላይ የአመራር ለውጥ ተደርጎ የጀነራል አብይ አበበና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምልምል መኮንኖች ከመከላከያ ሚኒስትርነት ጀምሮ ቢያንስ እስከ ክፍለ ጦር ደረጃ ያሉትንና በአንዳንድ ቦታዎች ከዚያም ባለፈ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ የሥልጣን ቋካዎችን በአዛዥነትና በምክትል አዛዥነት ማስያዝ ነበር።

እነዚህ ምልምል መኮንኖች በየተሾሙባቸው የጦር ክፍሎች እንደደረሱ፣ የልጅ እንዳልካቸውን አዋቂነት፣ የሥራ ልምድና ብቃት ጋር ከፍ ብዬ የገለጽኩትን የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ይዘት እያጎሉና እያጋነኑ በማዳነቅ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ድጋፍ ከማሰባሰብ ባሻገር እነሱም በበኩላቸው በዝቅተኞቹ የጦር ክፍሎች ውስጥ እነሱን የሚወክሏቸውን ምልምሎች መምረጥ ጀምረው ነበር።

በዚህ የአጭር ጊዜ ሂደት በየጦር ክፍሉ ውስጥ እንዳልካቸውን በመደገፍ የታወቁትንና እንደበተ ርቱዕ የሆኑትን መኮንኖች የበታች ሹማምንቶች ጦር ሳይሆን ምልምል አዛዦቹ እራሳቸው በኮታ መርጠው ጦሩን ወክለው አዲስ አበባ አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ እንዲሰበሰቡ ተደረጉ።

ጦሩ በተሰበሰበበት የሰልፍ ሜዳ ወጋዊ ዝግጅት በማድረግ ልጅ እንዳልካቸው ተጠርተው ለተሰበሰበው ሠራዊት የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን፣ ከፕሮግራሙ የሚመነጩ ሌሎች ዝርዝር አጀንዳቸውንና ፕሮፖጋንዳቸውን ከነሰነሱ በኋላ ያቀዱትን በተግባር ለመተርጎም ፋታ ብቻ ሳይሆን የጦር ኃይሉን ሙሉ ድጋፍ ጠየቁ።

ይህ በሆነ በበነጋታው የአገሪቱን መለዮ ለባሽ ወክለው መጡ የተባሉት መኮንኖችና የበታች ሹማምንቶች በሙሉ በሰልፍ እየተነዱ ወደ ቤተመንግሥት ተወስደው ንጉሡ ዘንድ በመቅረብ እነሱ የሚወክሉት የአገሪቱ መለዮ ለባሽ በሙሉ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ለልጅ እንዳልካቸው መንግሥት የማይናወጥ ታማኝነቱንና ታዛዥነቱን ገለጸ ተብሎ በተቀነባበረ ሁኔታ ዜናው በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለሕዝብ ተደጋግሞ እስኪያሰለች ለሳምንታት ያህል ቀረበ። ይህንን ያስተዋለው ሕዝብ በመገረምና በማዘን "ወታደሩ በጠመንጃው ለራሱ ደሞዝ አስጨምሮ፣ በእውቀቱና በጥረቱ ያደገውን የደሀውን ልጅ አክሊሉን በማውረድ የንጉሡን የልጅ ልጅ ተክቶልን እኛን ጥሎና ታማኝነቱን ገልጾ ወደ ጦር ሰፈሩ ተመለሰ" የሚለው ስሞታና ወቀሳ በየቤቱ፣ በየመሥሪያ ቤቱና በየጎዳና የሕዝብ መወያያ አጀንዳ ሆነ።

ይህ ሁኔታ በሠራዊቱ ውስጥ "እኛ መቼ ነው እነዚህን የመረጥነውና የአገሪቱን መለዮ ለባሽ ወኪሎች ናቸው እየተባለ የሚነገረው?" የሚል ጥያቄዎች ተነስቶ አዛዦቹ ሁሉ ከሚያዟቸው ጦሮቻቸው ጋር ተፋጠጡ።

በዚህ ወቅት በአዲስ አበባ ይበተኑ ከነበሩት እያሌ ፀረ-መንግሥት በራሪ ወረቀቶች አንዱ የሠራዊቱን ታማኝነት አስመልክቶ፡ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! አብዮቱ መዳፈኑ ነው። የንጉሡና የልጅ ልጃቸው የወቅቱ መርህ ለወታደሩ ብር ለሕዝቡ ሽመል የሚል ስለሆነ ለዚህ ትግልና ፈተና ተዘጋጅ። ሕብረትህንም አጠንክር።" የሚል ነበር።

በሠራዊቱ የተጀመረው ለንጉሡና ለአዲሱ ካቢኔ ታማኝነትን መግለጽ ወደ ሕዝቡም እንዲያመራ ተደርጎ በግለሰብ፣ በድርጅትና በክልል ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ለአዲሱ ካቢኔ የታማኝነትና የድጋፍ መግለጫ መልዕክቶች መጉረፍ ጀመሩ።

ይህ ሁሉ ሲሆን በሰፊው ሕዝብ በኩል በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞውን መግለጡና የሥራ ማቆሙ አድማ እንደቀጠለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሚታዩው ትያትር የሕዝቡ ቁጣ ከረረ። በመንግሥትም በኩል የጦር ኃይሉ ድጋፍና ትብብር ተገኝቷል በሚል ድምዳሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በወቅቱ በአገሪቱ ላይ ለደረሰው ቀውስ የቀድሞው ባለሥልጣኖች ዳተኝነትና ለተሰጣቸው ኃላፊነት ብቁ ሆነው ያለመገኘት ነው ብንልም ዋናው ችግር የመነጨው ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጪ በሆነው የተፈጥሮ የአየር ንብረት ቀውስ ባሻገር

የባዕዳን ጠላቶቻችን እጅ ያለበት ነው በሚል ሰፋ ባለ ሃተታ የታጀበ የሕዝቡን እንቅስቃሴ የሚያምቅ አዋጅ ወጣ።

አዋጁን የሚያስከብ ከወትሮው መደበኛ የፀጥታ ማስከበር ተግባር በተለየ ሁኔታ የልጅ እንዳልካቸውን መንግሥት በሚደግፉ ሰዎች ወይም ምልምሎች የተቃመረ ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን ተቋቋመ።

ከኮሚሽኑ ጋር ሁለተኛው የጦር ኃይሎች እንቅስቃሴ በተሰኘ ስም በኮሎኔል የዓለምዘውድ የአየር ወለድ ሠራዊት አዛዥ ሰብሳቢነት ወይም መሪያነት በልጅ እንዳልካቸው የሚመራ ወታደራዊ ኮሚቴ ተቋቋመ።

ይህ ወታደራዊ ኮሚቴ እንደተቋቋመ ለምርመራ የሚፈለጉትን የቀድሞ ባለሥልጣኖች እያደነ ማሰር የጀመረ መሆኑንና የሚታሰሩትም ግለሰቦች ስም በዜና ማሰራጫ ሲቀርብ ወታደራዊ ኮሚቴው የሕዝቡ ወገን ነው የሚያሰኝ ስም ስላሰጠው ለተወሰነ ጊዜ በሠራዊቱ በኩል ለመቃወምም ሆነ ለመደገፍ የሚያስቸግር ሁኔታና ውዥንብር ፈጠረ።

ኮሚቴው የሚያድነውና የሚያስረው የቀድሞ ባለስልጣኖችን ብቻ ሳይሆን የሥራ ማቆም አድማና ለመንግሥት ተቃውሞ ሰልፍ ወዘተ ህብረተሰቡን ቀስቃሽ ናቸው የተባሉትን ሰላማዊ ዜጎች ሁሉ ከመሆኑ ሌላ በአየር ኃይላችን ሠራዊት ውስጥ የነበሩትን ተራማጅ ግለሰቦች በነቂስ እየለቀመ በወታደር እስር ቤት የማጎሩ ጉዳይ በተጨማሪና በእጅጉ ሠራዊቱን አደናገረ።

በዚህ ጊዜ ነበር በአጋጣሚ የሥራ ተልዕኮ ወደ አዲስ አበባ ተልኬ ከማንም ሳልገናኝ በቅድሚያ በአዲስ አበባ የሲቪል ምህንድስና ኮሌጅ ትምህርቱን ይከታተል የነበረውን፣ የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ባልደረባ ከመሆኑም ሌላ ለእኔም እጅግ የቅርብ ጓደኛዬ የነበረውን ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብን የተገናኘሁት።

እንደሚታወቀው የመማርና የማስተማር ተግባር በሃገር አቀፍ ደረጃ ቆሞ ስለነበረ ሻለቃ ተፈራ ያለ ትምህርትና ያለ ሥራ ባገኘው ሰፊ የእረፍት ጊዜ በአዲስ አበባ በሚካሄደው የተማሪውና የመለዮ ለባሹ ንቅናቄ ቀንደኛ አባልና አካል ሆኗል።

ጓደኝነታችን ከልጅነት ከትምህርት ቤት ጊዜ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አገራችንን በተመለከተ የፖለቲካ ጉዳይ ተመሳሳይ አመለካከት ስለነበረን እኔ በአገራችን ምሥራቃዊ ክልል ያለውን ሁኔታ ሳስረዳው እሱም በበኩሉ ስለወቅታዊው የአዲስ አበባ ሁኔታ፣ በሲቪሉ ሕብረተሰብ፣ በወዛደሩና በወታደሩ ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች በመዘርዘር ጠቃሚ መረጃዎችን ሰጠኝ።

ከተወያየንባቸው አያሌ ጉዳዮች ውስጥ ዋናውን ትኩረት የሰጠነውና የመጀመሪያው ኮሎኔል የዓለምዘውድ የሚመሩት ወታደራዊ ኮሚቴ በሠራዊቱ ስም ሠራዊቱን ከሕዝቡ ማጋጨት ብቻ ሳይሆን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለልጅ እንዳልካቸው ፋታ ይሰጣቸው በተሰኘ ዓላማ አብዮቱን እያዳፈኑ ስለመሆኑ፤ ሁለተኛው ሶማሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር በደቡብና በምሥራቁ የጋራ ድንበራችን ላይ ያሰፈረችው ወራሪ ሠራዊት በአገራችን ላይ ሊያደርስ ስለሚችለው ጥቃትና ከዚህም አኳያ የአብዮቱ ሁኔታ፤ ሦስተኛውና የመጨረሻው በጊዜው ከሚታዩት የብሔረሰብ ንቅናቄዎች በተለይ የሰሜኖቹ ገንጣዮች 'አሁንም ሆነ ወደ ፊት የአብዮቱ ወገን ይሆናሉ ወይስ ፀሩ?' በተባሉት ጥያቄዎች ላይ ነበር።

ቀድሞ የአንበሳው ሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩትና በዚህ ጊዜ ከሠራዊቱ በጡረታ ተገልለው የዘውድ ምክር ቤት አባል በመሆን የሚሰሩትን ሜ/ጀነራል አማንን

በማናቸውም አጋጣሚ አዲስ አበባ በተገኘሁ ጊዜ መኖሪያ ቤታቸው እየሄድኩ እንጠየቸው ነበር።

ይህንንም ሻለቃ ተፈራ የሚያቅ ከመሆኑ ሌላ እሱም የሚያደርገው ስለሆነ "ከጄኔራል አማን ጋር ቀጠሮ ይዘን እንደተለመደው እንንብኛቸውና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የእሳቸውንም አስተያየት ብንዘክር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል" አለኝና ቀጠሮ ይዘን በሰንበቱ የእረፍት ጊዜያቸው ቤታቸው በመሄድ ተገናኝተን ከአራት ሰዓት በላይ ለሆነ ጊዜ ተወያየን።

እኔና ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ከገነት የጦር ትምህርት ቤት ተመርቀን በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር እዝ ስር ለአገራችን ወታደራዊ አገልግሎት መስጠት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ለ15 ዓመታት በሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥነት ሰባት ጄኔራሎች ተፈራርቀዋል።

ጄኔራል አማን በችሎታቸው፣ በንቁ ወታደራዊ አመራራቸውና ከሁሉም በላይ በሙስና ፍፁም በማይጠረጠረው ንፅህናቸው በሚያዙት ሠራዊት በተለይ ከወጣት መኮንኖች ከፍ ያለ አክብሮትና ፍቅር ያተረፉ መኮንን ነበሩ።

እኔ በማከናውነው የሥራ ባህሪ ምክንያት በቀጥታ ከሳቸው ትዕዛዝ የምቀበልና የሚያቀርቡኝ ስለነበረ ጦር በሚጎበኙበት ጊዜያቶች ሁሉ ከሳቸው የተለየሁበት ጊዜ ስላልነበረ በሚያደርጉት፣ በሚናገሩትና በጠቅላላ ሁኔታቸው እንከን የማይወጣላቸው ሃገር ወዳድ፣ ለውጥ ፈላጊና የኢትዮጵያን መሻሻል ከልብ የሚመኙ መኮንን ናቸው ብዬ እልቤ ከትቻቸዋለሁ።

ውጊያ ሲመሩ ባላስተውልም ጥሩ አዋጊ ጄኔራል ይመስሉኛል። ጥሩና የወጣላቸው አስተዳዳሪ ግን አልነበሩም። በአስተዳዳር ጄኔራል አበበ ገመዳን አደንቃለሁ። ሰው ፍፁም አይደለምና የጄኔራል አማን አንዱ እንከንና ድክመት ግን አህሎኝ በማለት ለራሳቸው ያላቸው ከፍተኛ ግምት ነበር።

አልፎ አልፎ ኃይልና እብሪት ይታይባቸዋል። ሰው ሲወዱ ለማመስገን ለጋስ የመሆናቸውን ያህል ሰው ሲያዋርዱና ሲሰድቡ አያድርስ ነበር። ምቀኛ፣ ነገር ሰሪ፣ ሸፍጠኛና መሰሪ ግን አልነበሩም፤ ቅን፣ ግልፅና ቀጥተኛ ሰው እንጂ።

አንድ ጄኔራል ከሚገቡት ችሎታና ባህሪያት አብዛኛውን አካተው የያዙ በመሆናቸው ጉድለታቸው ላይ እንዳናተኩር አድርገውናል። አብረን በሰራንበት ጊዜ ሁሉ እኛ የምናውቀውና ያስተዋልነው የጤንነት ችግርም አልነበራቸው።

ከእቻዎቻቸውና ከበላዮቻቸው የአገሪቱ ጄኔራሎች ጋር በእድሜ ሲነፃፀሩ ልጅ እግር ሆነው ሳለ በጡረታ መገለላቸው አብዛኛዎቻችንን ቅር ያሰኘን ብቻ ሳይሆን በወታደር የሚወደድ አዛዥ በአገሪቱ ገዥ መደብ አይወደድም ወደሚል ድምዳሜ ደርሰን አጋጣሚው ቢገኝ ወደ ሠራዊቱ የመመለስ ፍላጎት ነበረን።

ስለሆነም ከሠራዊቱ በጡረታ ተገልለው የዘውድ ምክር ቤት አባል ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ ፍቅራቸውንና አክብሮታቸውን ለመግለጽ አልፎ አልፎ ከሚጎበኟቸው የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መኮንኖች አንዱ ነበርኩ። ጓደኛዬ ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብም እንደዚሁ።

ከፍቅርና ከአክብሮት ባሻገር በ1966 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ጄኔራል አማንን መጎብኘት ያስፈለገበት ዓብይ ምክንያት የኤርትራ የወቅቱ ጉዳይ ነበር። ከጄኔራል አማን ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ተገናኝተን የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጥንና እንዲሁም ስለ ሥራቸውና ጤንነታቸው ከጠየቅናቸው በኋላ ወደ ውይይቶቻችን ነጥቦች ያመሩት እሳቸው ነበሩ።

የመጀመሪያ ጥያቄያቸው በቀጥታ ያተኮረው እኔ ላይ ነበር። ጥያቄያቸውም "ከክፍለ ጦሮች ሁሉ ስመ ጥርና ግዙፍ የሆነው ሦስተኛ ክፍለ ጦር በአሁኑ ጊዜ ከመላው ሠራዊት መለየት ፀጥ ያለበት ምክንያት ምንድነው?" የሚል ነበር።

የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ አይከታተልም፤ ከሌሎች የጦር ክፍሎች ጋር ግንኙነት የለውም ወይም እስከ አሁን ለሆነው ሁሉ ድጋፉን አልሰጠም ማለት ሳይሆን የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል አገራችንን ለመውረር የሚያደርገው መሰናዶ በጣም እንዳሰጋንና ሀሳባችንን እንደከፈለው ገለጽኩላቸው።

"የሶማሊያ መንግሥት የወረራ ዝግጅት ሁላችንንም እንደሚያሰጋ ግልጽ ነው። ሆኖም አንተ እንዳልከው በማናቸውም ወራት፣ ቀናትና ሰዓት አይወረንም። ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመበርነቱን ከማስረከቡ በፊት ወረራ እንደማይሰነዝር ለእኔ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱ መሪዎችም ግንዛቤ ስለሆነ ቢያንስ አንድ አመት ያህል ጊዜ እንዳለን በእርግጠኝነት ለጦሩ መግለጥ ትችላለህ" አሉኝና ወደ ሌላው ነጥብ አመራን።

ጄነራል አማን በኤርትራ ክፍለ ሀገር በመወለዳቸው ብቻ ሳይሆን የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ ከፋሽስት ኢጣሊያ ድል መመታት በኋላ ለአንድነት ትግል ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ የመገንጠል አመጽ እስከተጀመረበት ጊዜ ድረስ ያለውን ዝርዝር በሙሉ በመከታተል የሚያውቁና ስለተፈጠረውም ሁኔታ ይቆረቆሩ ስለነበር ነው በኢትዮጵያ መሃፀን ከተረገዘው አብዮት ጋር አጣምረን የሳቸውን አስተያየት ማወቅ የፈለግነው።

እኔና ሻለቃ ተፈራ ባልጠበቅነው ሁኔታ የኤርትራን ችግር በጣም አቃለው በእሳቸው አነጋገር "በረሀኞቹ የሚወጉት ሥርዓቱን እንጂ የኢትዮጵያን አንድነት አይደለም። የእናንተ ጥያቄ 'ለአብዮቱ ወግነው ከእኛ ጋር ይቀላቀላሉ ወይስ የአብዮቱ ፀር ሆነው ይወጉናል?' ነው። የእኔ መልስ ደግሞ 'በረሀኞቹ አብዮት ማካሄድ ከጀመሩ ሰንብተዋል፤ የትኛው የመሃል አገሩ ታጋይ ነው' ባይ ነኝ" አሉን።

ንግግራቸውን በመቀጠል "እኔ ቢያንስ የበረሀኞቹን መሪዎች ወላጆችና ቤተሰቦች አውቃለሁ፤ ከውጭም የሚተባበሯቸውን የሱዳንን የጦርና የፖለቲካ አመራር አካላት አውቃለሁ፤ እናንተ ሠራዊቱን ለለውጥ ማቆም ከቻላችሁ የኤርትራን ጉዳይ ለእኔ መተው ትችላላችሁ።" ሲሉ አርኪና አስመኪ መልስ ስለሰጡን ሌላ ጥያቄ ማቅረብም አላስፈለገንም።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የውይይት ነጥባችን የአዲስ አበባው መለዮ ለባሽ ከሚያዝያ ወር መጀመሪያ ጀምሮ ስለሚያሳየው አስጊና አፍራሽ አዝማሚያ ነበር። ይህንን ጉዳይ ጄነራል አማን ቀድመው በማንሳት "እንዴት አንድ ኮሎኔል ያውም የአንድ ሻለቃ አዛዥ ይህንን ሊያደርግ ይችላል? በእኔ አስተያየት ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ ባለው ጦር ለአስቸኳይ መገሠጥና ከአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥነቱም መነሳት ያለበት ሰው ነው" በማለት በቀጥታ መልክ ፈርጠም ብለው የዓለምዘውድ የመሣፍንቱ መሣሪያ ሆኖ ሠራዊቱን እያሳሳተ መሆኑን ገለጹ።

በአዲስ አበባ መለዮ ለባሽ የሚከናወነውን ጉዳይ በተመለከተ የተሻለ መረጃ ያለው ብቻ ሳይሆን በተግባርም ተሳታፊው ሻለቃ ተፈራ ስለሆነ ለቀረበው ጥያቄ አስተያየቱን እንዲሰጥ እኔ ጠየቅሁ። ሻለቃ ተፈራም በአዎንታ ፈቃደኝነቱን ገልጾ ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት ሰጠ።

"የኮሎኔል የዓለምዘውድና የግብራበሮቻቸው ብቻ ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸውም በሥልጣን ላይ የመቆያ ጊዜ በጣት የሚቆጠር ይመስለኛል። የኮሎኔል

የዓለምዘውድ ዓላማና የሚጫወቱት ሚና በመላው የአዲስ አበባ ክልል መለዮ ለባሾች ብቻ ሳይሆን በሚያዙት በአየር ወለዱ ሻለቃ ጦርም ጭምር በሚገባ ታውቋል። አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አብዛኛው የአዲስ አበባ ክልል ልዩ ልዩ ክፍሎች፣ ሠራዊቶችና የምድር ጦር ከእነሱ አመራር አፈንግጠው በእነሻለቃ አጥናፉ አባተ የሚመራ የራሳቸውን ህቡዕ አመራር ፈጥረዋል።

የኮንጎ ዘማቾች ተወካይ ኮሚቴም ከኮሎኔል የዓለምዘውድ ኮሚቴ ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብቷል። አብዛኛው የከተማው ነዋሪ ሕዝብ፣ በተለይም ተማሪውና ምሁሩ የልጅ እንዳልካቸውን መንግሥት ተቃዋሚ በመሆን 'ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም' እና 'ትሻልን ፈትቼ ትብስን አገባሁ' በማለት ሕዝቡ እያፌዘና እየተሳለቀበት ስለሆነ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ ለውጥ ይፈጠራል ብዬ እገምታለሁ አለ።

'ምን አይነት ለውጥ ነው የሚመጣው?' 'መቼና እንዴት?' ከተሰኘው የታክቲካዊና ቴክኒካዊ ጥያቄ በስተቀር በመጭው ጊዜ ሊሆን ስለሚችለው ግምት የተለያየን አልነበርንም። ሆኖም ጄነራል አማን በአዲስ አበባ ክልል የጦር ክፍሎች ላይ እምነት ያጡ ይመስላል "በእኔ አስተያየት ከአዲስ አበባ ውጭ ያለው ጦር በአዲስ አበባዎቹ ላይ ብርቱ ተጽዕኖ ካላደረገና ይህን መንግሥት ካላንበረከከ ለውጥ ይመጣል ብዬ ለማሰብ ይቸግረኛል" አሉ።

የጄነራል አማን አስተያየት 'እስካሁን ያልተንቀሳቀሰውን ሦስተኛውን ክፍለ ጦር አንቀሳቅሱት' የሚል ነበር። በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የጄነራሉን አቋም በሚገባ ስለተገነዘብንና በተለይም ከእሳቸው ጠብቀነው በነበረው የኤርትራ ችግር የሰጡን አስተያየት ያረካን ስለነበረ ከተቀሩት የእምነታችን ተጋሪ ከሆኑት ወንድሞቻችን ከሰፊው ሠራዊት ጋር መክረን ለኢትዮጵያ የሚበጃትን ሁሉ ለማድረግ እንሞክራለን በማለት ተለየናቸው።

በዚያው ቀን ከቀትር በኋላ ሻለቃ ተፈራ አቅዶት የነበረው ፕሮግራም በእሱ መኖሪያ ቤት እኔንና ሻለቃ አጥናፉ አባተን ማገናኘትና ማስተዋወቅ ነበር። እኔ ከዚያ በፊት ሻለቃ አጥናፉን በመልክም ሆነ በስም አላውቀውም፤ እርሱም አያውቀኝም ነበር። የ17ኛው የገነት የጦር ትምህርት ቤት ምሩቅና በወቅቱ ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በምሽት የሕግ ትምህርት በመከታተል ላይ የነበረ መኮንን ነው።

ለእኛ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ሻለቃ አጥናፉ በቀጠሮው መሠረት መጥቶ ልንገናኝ አልቻልንም። ከቀትር በኋላ ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ጠብቀነው ስለቀረ ምክንያቱን ለመረዳትና የሚቻልም ከሆነ በዚያው ምሽት ለእሱ ባመቸው ጊዜና ቦታ ሌላ ቀጠሮ ይዘን እንድንገናኝ ስልክ እንድንጠቀም ሻለቃ ተፈራን ስጠይቅ በሁለቱም መኮንኖች መኖሪያ ቤት ስልክ እንደሌላቸው ተረዳሁ።

በበነጋው እኔ ወደ ሐረር መመለስ ስለነበረብኝ እኔና ሻለቃ አጥናፉ ብንገናኝ ኖሮ በውይይታችን ላይ ይነሱ የነበሩ ዋና ዋና ጉዳዮች፡

1ኛ/ ከአንድም ሁለት ጊዜ ከጉልታዊው ሥርዓት ጋር የተሳሰሩ ከፍተኛ መኮንኖች በሠራዊቱ ሳይመረጡ በሠራዊቱ ስም ሕዝብን ከማወናበዳቸው ባሻገር አሁን ወደ ኋላ እንደሚታዩው ሠራዊቱን ከሕዝቡ አጋጭተው አብዮቱን ለማዳፈን እያሴሩ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲያ መመራት ያለብን የሻለቃ ማዕረግና ከዚያ በታች ባሉ ወጣት መኮንኖች ነው በማለት የአዲስ አበባ ክልል መለዮ ለባሾች ስለያዙት አቋም፣

2ኛ/ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር እና በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መካከል አንድ ምስጢራዊና ቋሚ የመገናኛ ድር ወይም አገናኝ የሚሆን ሁነኛ ሰው በአዲስ አበባ እንዲኖር ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ለመነጋገር ነበር።

በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተውን ሀሳብ እንደተባለው የአዲስ አበባ ክልል ሠራዊት በሙሉ ያመነበትና የማያወላውል ፅኑ አቋም የያዘ ከሆነ የሦስተኛው ክፍለ ጦርም ሠራዊት የሚቀበለው መሆኑን ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ለሻለቃ አጥናፉ አመራር አካል በገጽ ተገናኝቶ ሦስተኛ ክፍለ ጦርን በመወከል እንዲያስረዳ፤ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተውን ሻለቃ ተፈራ ራሱ ከአራተኛ ክፍለ ጦር ጋር ብቻ ሳይሆን ከአንደኛ ክፍለ ጦር፣ ከአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ክፍሎች፣ ከአየር ኃይልና ከምድር ጦር አየር ክፍል ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ሦስተኛ ክፍለ ጦርን ወክሎ ተጠሪና አገናኝ እንዲሆን ተስማምተን በበነጋታው እኔ ወደ ሐረር ተመለስኩ።

ወደ ሐረር የምመለሰው እየነዳሁ ስለነበር በናዝሬት ከተማ በማደር የምድር ጦር ታንከኛ መምሪያ የትምህርትና የዘመቻ መኮንን የነበረውን ሌላውን የቅርብ ጓደኛዬን ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳንን በማግኘት አንድ ምሽት እሱ ቤት በማደር ከጄነራል አማን ጋር የተደረገውን ውይይት፣ በአዲስ አበባ ቆይታዬ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች፣ የተገናኘኋቸውን መኮንኖችና ከአራተኛ ክፍለ ጦር ጋር ካደረግናቸው ትብብሮች ጋር ከሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ጋር የወሰድናቸውን አቋሞች በዝርዝር ተወያይተንና በእሱም አማካኝነት በሦስተኛ ክፍለ ጦርና በታንከኛ ሠራዊት መካከል መኖር ስላለበት ግንኙነትና ሕብረት ተስማምተን በበነጋታው ጉዞዬን ቀጠልኩ።

ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን የ19ኛው የገነት የጦር ትምህርት ቤት ምሩቅና ለእኔ በእጅጉ የቅርብ ጓደኛዬ ሲሆን፣ በአብዮቱ የታንከኛን ሠራዊት በመወከል የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ አባልና የመከላከያው ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ በድህረ አብዮት ወይም በአብዮቱ ሂደት የፓርቲያችን የፖለቲካ ቢሮ አባልና የሃገር መከላከያ ሚኒስትር የነበረ ጓድ ነው።

ሐረር ተመልሼ ለምሥራቁ መለዮ ለባሽ ህቡዕ ኮሚቴ ሪፖርት ባቀረብኩባቸው ነጥቦች ላይ በዝርዝር በተወያየንበት ጊዜ ኮሚቴው ያተኮረበት አብይ ጉዳይ ጄነራል አማንን በምን ሁኔታ ወደ ሠራዊቱ መመለስ ይቻላል በተሰኘው ጉዳይ ላይ ነበር።

የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ለጄነራል አማን ካለው በጎ አመለካከትና ፍቅር ባሻገር ታላላቆቹ የአገሪቱ የጦር ኃይል መሪዎች አብዛኛዎቹ ባለፈው ተግባራቸው እየተወነጀሉ በልጅ እንዳልካቸው መንግሥት ትዕዛዝ'የታሰሩ በመሆናቸው የመከላከያው ላዕላይ መዋቅር አመራር አልባ ስለነበረና እኚህ ሰው የተፈጠረውን ክፍተት ሁሉ ባይሞሉም በዚህ አሳሳቢ ጊዜ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹምነቱን ቦታ ይዘው ቢሰሩ እንደሚጠቅሙ ታመነበት።

ጄነራል አማን ወደ ሠራዊቱ ተመልሰውና የተጠቀሰውን ኃላፊነት ተረክበው እንዲመሩ በሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ለመንግሥት ጥያቄ ከማቅረብ በፊት በተቀረውም ሠራዊት ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በቅድሚያ የግለሰቡን ማንነት ለመላው የአገሪቱ ሠራዊትና እንዲሁም ለሕዝቡ ማስተዋወቅ ይገባል ብለን ወሰንን።

በዚህም ውሳኔ መሠረት በሚያዝያ ወር መገባደጃ ላይ 'አማን ኮዳ ትራሱ' የሚል የቁልምጫ ስም በመስጠት "የጄነራል አማን ጭንቅላት የኬኘ መሸከሚያ አይደለም" የሚል አንድ አጭር ሀተታ ጽፌ በዚያን ጊዜ የዛሬዩቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጅ ለነበረው ለአቶ ጳውሎስ ኞኞ ልኬለት በጋዜጣ ግምባር አምድ ላይ አወጣው።

ጊዜውና ወቅቱ ጋዜጣ አንባቢዎችን አበራክቶ ስለነበረና በስፋት ስለተነበበ የጄኔራል አማን ስም የሠራዊቱና የሕዝቡ መወያያ አጀንዳ ሆኖ ሰነበተ። የጽሁፉ አድራሻ ከምሥራቅ ህቡዕ መለዮ ለባሽ ኮሚቴ ስለሚልም ያነበበው ሁሉ የየራሱን ፖለቲካዊ ትርጉም ሰጠው። ለጄኔራል አማን ስልክ እየደወሉ "በዛሬው ጊዜ ከሠራዊቱ አንድ ጄኔራል እንዲህ ያለ ፍቅርና አክብሮት ማግኘት ታላቅ እድል ስለሆነ እንኳን ደስ ያለዎት" ያሏቸው ሰዎች ብዙ ነበሩ። በቅደመ አብዮት፣ በድህረ አብዮትና አብዮቱ ተቀልብሶ ኢትዮጵያ የወያኔ ቅኝ ከሆነችም በኋላ ጄኔራል አማንን ምናልባት በስምና በመልክ ካልሆነ በስተቀር ጨርሶ የማያውቋቸው ሰዎች 'ወደር የሌላቸው የጦር ሜዳ ጀግና ናቸው፤ የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት አዳሽቀው ከመመለስ ባሻገር በማሳደድ እስከ ሃርጌሣ ድረስ ሊገቡ ሲሞክሩ ንጉሡ ራሳቸው በመገሰጽ መለሷቸው' በማለት የፈጠራ ታሪክ የተረኩላቸው ሰዎች አሉ።

ጄኔራል አማን ሠራዊቱን በማሰልጠንና በማዘመት፣ የሚያዙት ሠራዊት ሞራል ከፍ ያለ እንዲሆንና የክፍል ቅናት እንዲሰርፅበት ከማድረግ ጋር ከሙስና የፀዱ ነበሩ እንጂ የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በእኛና በሶማሊያ መንግሥት መካከል ምንም አይነት ውጊያ አልነበረም፣ በውግያም አልመሩንም፣ እሳቸውንም የጦር ሜዳ ጀግና የሚያሰኛቸው ምንም ነገር አልተፈፀመም።

እንደውም በ1953 ዓ.ም እሳቸው በአዛዥነት ወደ ሦስተኛ ክፍለ ጦር እንደተዛወሩ ዳኖት በተባለችው የጠረፍ ወረዳ ላይ እኔ በጥብቅ የዘመቻና የትምህርት መኮንንነት አገለግለው የነበረው ዘጠነኛ እግርኛ ሻለቃ ጦር ከሶማሊያ ሰርጎ ገብ ጠብ አጫሪዎችና ሽብር ፈጣሪዎች ጋር ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ከእኛ ወገን 65 ሰዎች በተሰውበት የሦስት ቀን ውጊያ ጦሩን የመሩት የሻለቃው ጥብቅ አዛዥ የነበሩት ሻለቃ ይስፋህ ደስታ የሚባሉ መኮንን ነበሩ።

ሰርጎ ገቦቹ በሰው ኃይል ልቀውን ከፍ ብዬ የጠቀስኩትን ያህል ጉዳት በማድረሳቸው ተጨማሪና አጠናካሪ ጦር በማንቀሳቀስና ቦታው ላይ ተገኝተው አመራር በመስጠት ውጊያው በእኛ ድል አድራጊነት እንዲደመደም ያደረጉት በዚያን ጊዜ የክፍለ ጦር የትምህርትና የዘመቻ መኮንን የነበሩት ኮሎኔል ምህረተአብ ተድላ ናቸው።

ጄኔራል አማን ዳኖት የተገኙት ግን ውጊያው ካለቀ በኋላ ሠራዊቱን ለማመስገንና ለማነቃቃት ነበር። በዚህ ሁኔታ አመራር መስጠት የጦር ሜዳ ጀግና የሚያስኝ ከሆነ ጀግናው ምህረተአብ እንጂ አማን አልነበሩም።

ከውጊያው በኋላ የዳኖት ጀግና ተብሎ የጀግና ሜዳልያ የተሸለመው የክፍለ ጦሩ ቃኚ ሻምበል አዛዥ የነበረው የመቶ አለቃ ደጀኔ ስሜ የሚባል መኮንን ነበር። የመቶ አለቃ ደጀኔ (በድህረ አብዮት ሻለቃ) ለምሥራቁ የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ዝግጅት ከናዝሬት የታንከኛውን ሠራዊት እያስታጠቀና እያደራጀ ሌሊት በባቡር በሚያጓጉዝበት ጊዜ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ እያለ ይጠራ የነበረው ድርጅት ገድሎታል።

የሶማሊያ መንግሥት በሶቭየት ሕብረት ርዳታ ዘመናዊ የጦር ኃይል ከመገንባቱ በፊት የደፈጣ ተዋጊዎችን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አስርጎ ከማስገባት ባሻገር የደገሐቡር አውራጃ ባላባት የነበረ ደጃዝማች መቅተል ጣሄር የሚባል ሰው አገሩን ኢትዮጵያን ከድቶ የሶማሊያ መንግሥት ምንደኛ በመሆን የጎሳ አባሎቹን አስከትሎ በማመጽ ሠራዊታችንን መውጋት በጀመረበት ጊዜ የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ጄኔራል አማንን የተኩት ጄኔራል አበበ ወ/መስቀል ነበሩ።

ከሶማሊያ መደበኛ ሠራዊት ጋራ ቶጎጫሌ፣ ኢነጉሀና ደበጉርያሌ ተብለው በሚጠሩት ሁለቱ አገሮች ወሰን ላይ በሚገኙ የጠረፍ ከተሞች የተደረጉትን ውጊያዎች የመሩት ጄነራል አበበ ወ/መስቀልን የተኩት ደግሞ በዚያን ጊዜ ሜ/ጄነራል ወ/ሥላሴ በረካ ናቸው።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሶማሊያ ሠራዊት ጋር የተደረገ ዓውደ ውጊያ አልነበረም። አንዳንድ ግጭቶች እንኳ ቢደረጉም የተመሩት ጄነራል ወ/ሥላሴን በተኩት በጄነራል አበበ ገመዳ ነበር።

ሆኖም ጄነራል አማንን ከሠራዊቱ ጋራ በማስተዋወቅ ተቀባይነት እንዲያገኙ ብዬ "ከዳ ትራሱ" የተሰኘ የቁልምጫ ስም ስለሰጠኋቸው ብቻ ብዙ ሰዎች ምናልባት ከጦር ሜዳ ጀግንነት ጋር እያይዘውት ይመስለኛል የእኛን ፍላጎት ከጠበቅነው በላይ በፈጠራና በግጋነን አስተናግደውልናል።

ጄነራል አማንን ለማስተዋወቅ የተደረገው ሙከራ ከተጠበቀው በላይ የሰመረ ሆኖ ሳለ በኋላ ላይ ግን ትንሽ ችግር ፈጠረ። በወቅቱ የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ በተከሰተው መናጋት የተፈጠረውን ክፍተት በእሳቸው የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹምነት እንደሚሰጣቸው ያለሙ ይመስላል። በእኔ በኩል ጄነራል አማንን ወደ ሠራዊቱ መልሶ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት አሳስቧቸው ኖሮ፣ ሰላዮቻቸው አማካኝነት ይድረሱበት ወይም በራሳቸው ግምት አላውቅም ጽሕፈት ቤታቸው ጠርተው "መንግሥቱ ኃይለ ጄነራል አማን በስተቀር የተቀረነው ሰዎች ጭንቅላት የኬፕ መሸከሚያ ነው' ብለህ የምታስብ ሰው መሆንክን አላውቅም ነበር" በማለት ቅሬታቸውን ገለጹልኝ።

በበኩሌ ሳልከድና ሳላስተባብል ወቀሳቸውን ተቀብዬ እኔ ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ የጻፍኩ እርስዎን የመሰለ ጄነራል ጨርሶ አይመለከትም በማለት ቅሬታቸውን ለማለዘብ ሞከርኩ "እኔን የማይመለከት ቢሆን ኖሮ በሠራዊቱ ውስጥ ሰው እንደሌለ ወይም እንደ ጠፋ ሁሉ ጄነራል አማንን ከጡረታ የሚያስጠራ ምክንያት አይታዬኝም" አሉኝ።

ንግግራቸውን በመቀጠል "ስማ እኔ ከአገሬ እድገትና መሻሻል የማስቀድመው ነገር የለኝም። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሥልጣን በስተቀር በተቀረው ሁሉ ከእናንተ የተለየሁ ሰው አይደለሁም። አትራቁኝ፤ ምንም ነገር አትደብቁኝ፤ በእኔ አቅም ለሚደረግ ማናቸውም ነገር ገንዘብ ሆነ ሌላ ይነገረኝ" ብለው አሰናበቱኝ።

ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በብዙ ጉዳዮች ላይ ተባባሪ በመሆን ከኮሚቴው ጋር ስለሰሩና ከሳቸው ጋር ያለጊዜው ላለመጋጨት ጄነራል አማንን ወደ ሠራዊቱ የመመለሱ ጉዳይ ለጊዜው አመቺ ሁኔታ እስኪፈጠር እንዲዘገይ በኮሚቴው ተወሰነ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን በዚያው በሚያዝያ ወር መገባደጃ ላይ አዲሱ የመከላከያ ሚኒስትር ሌ/ጄነራል አብይ አበበ በምሥራቅና በደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች የሰፈረውን ሠራዊት ያለበትን ሁኔታ አጥንቶ ሪፖርት የሚያቀርብላቸው በአንድ ከፍተኛ መኮንኖች የተቀመረ መርማሪ ቡድን ወደ ሦስተኛ ክፍለ ጦር ተልኮ መጣ። የቡድኑ አባላት ዝርዝርም ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፦

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ሜ/ጄነራል መርዕድ ግዛው[1] | የቡድን መሪ |
| 2ኛ/ ብ/ጄነራል ወርቁ ገብረማርያም | አባል |
| 3ኛ/ ብ/ጄነራል አሰፋ ገብረማርያም | አባል |

1 የጦር ኃይሎች ኢንስፔክተር መኮንን

4ኛ/ ብ/ጄነራል ወርቁ መኮንን አባል

5ኛ/ ሌ/ኮሎኔል አበበ ደጋጋ አባል

6ኛ/ ሻለቃ መሥፍን ገብረቃል[2] አባል

7ኛ/ አሁን ስሙን ለማስታወስ የተሳነኝ የጦር ኃይሎችን የመረጃ መምሪያ የወከለና የሻምበል ማዕረግ ያለው መኮንን ነበር።

በትዕዛዙ መሠረት ጉብኝታቸውን ለመጀመር ሐረር ሦስተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ በደረሱ ጊዜ እኔም የቡድኑ አባል እንድሆን ተወሰነ። እኔ የቡድኑ አባል እንድሆን የተደረገበት ምክንያት የምሥራቁና የደቡብ ሠራዊት የተፋጠጡበት ከአንድ ጠላት ማለትም ከሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ጋር ለአንድ ዓላማና ተግባር በመሆኑ ውጊያ ቢከፈት ሁለቱ ክፍሎች በአንድ እዝ አመራርና ቁጥጥር ስር ሆነው በቅንጅት ቢዋጉ የተሻለ ውጤት ይገኛል ተብሎ በመታመኑ አራተኛ እግረኛ ብርጌድ ከአራት ክፍሉ ከአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር የአስተዳደርና የሎጂስቲክ ድጋፍ እያገኘ በዘመቻ በኩል በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ እንዲመራ ቀደም ብሎ የተደረገ በመሆኑ የክፍለ ጦሩን አዛዥ ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝን ወክዬ ነበር።

ጉብኝቱን ከምሥራቅ ግምባር ጀምረን በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር እዝ ስር ያሉትን እግረኛ ሻለቆች ለማየት ቢሞከር ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ በመታመኑ ጎዴ፣ ቀብሪደሐር፣ ደገሀቡርና ጅጅጋ ያሉትን የየብርጌዶቹን ጠቅላይ ሰፈር፣ አካባቢ ያሉትን እግረኛ፣ መድፈኛና ታንከኛ ክፍሎች ያሉበትን ሁኔታ በዝርዝር ከመመልከት ባሻገር የየብርጌዱ አመራር አካላት የሚሰጡንን ገለጻ ካዳመጥን በኋላ ውይይቶች ይደረግ ነበር።

የምሥራቁ ጉብኝት ተጠናቆ ወደ ደቡብ ስናመራ ጉብኝቱን የጀመርነው ከላይ ሳይሆን ከታች ተዋጊ እግረኛ ሻለቆች ካሉባቸውና ታላቁ የጁባ ወንዝ ከሚያቋርጣቸው ባሬና ዶሎ ከሚባሉት ሁለት የጠረፍ አውራጃዎች ነበር።

በየትኛውም ስፍራና የጦር ክልሎች የተመለከትነው የሠራዊቱ ችግሮች ተመሳሳይ ቢሆንም የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ የጥበቃ ቀጠና በተለይ በዶሎና በባሬ የጠረፍ አውራጃዎች የሰፈሩትን ሻለቆች በተመለከተ አራተኛ እግረኛ ብርጌድ በምን ምክንያት ከተቀረው ሠራዊት ሁሉ ቀድሞ ለማመጽ እንደተገደደ መረዳት ያስችላል።

በየግምባሩ ለውጊያ አሰፍስፎ ትዕዛዝ የሚጠባበቀው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር የተፋጠጠው የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰው ኃይል መጠንም ሆነ በመሣሪያ ብዛትና ጥራት ከፍተኛ ልዩነት የሚያመለክተው ነፃነቷን ካገኘች አሥራ አምስት አመት ያልሆናት ሶማሊያ የቁን ያህል ልቃ እንደ ሄደችና በአንፃሩ አገራችን ኢትዮጵያ የቁን ያህል በማንቀላፋት ላይ እንዳለች የሚያሳይ ነው።

በበኩሌ አብዮቱ ብዙ በጣም ብዙ ዘግይቷል የሚያሰኝ ስሜት ተሰምቶኝ ነበር፤ የግንባሩ ጉብኝት በመጠናቀቁ ከዚያ በኋላ ያመራነው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ መምሪያና ጠቅላይ ሰፈር ወዳለበት ወደ ነገሌ ነበር።

---

2 ሻለቃ መሥፍን ገብረቃል በድህረ አብዮት ወይም በአብዮቱ ሂደት በሜ/ጄነራል ማዕረግና በምክትል ኢታማጆር ሹምነት የአብዮታዊ ጦር ኃይል የትምህርትና የክተት ሠራዊት መምሪያ ኃላፊና የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሲሰራ በግንቦት ስምንት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ከእኔ ጋር በምሥራቅ ጀርመን ከነበሩት መኮንኖች አንዱ ነው።

የብርጌዱ አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ፍቅሩ ወ/ተንሣይ አዲስ አበባ ተጠርተው ሄደዋል ተብሎ ተቀብለው ያስተናገዱን ምክትል አዛዡ ነበሩ። በነገሌ ከተማ የነበሩ የጦር ክፍሎች፣ የብርጌዱ አካል ክፍሎች፣ የብርጌዱ ጠቅላይ ሰፈር ሻምበል፣ የብርጌዱ አጋዥ መሣሪያ ሻምበል፣ ከአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ተነጥሎ ለብርጌዱ የተደረበ አንድ መድፈኛ ሻለቃና ድህረ አብዮት የአብዮታዊ ሠራዊታችን ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም አድርገናቸው የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም "የኢትዮጵያ ነፃ መኮንኖች ንቅናቄ" በተሰኘ ስም በምንደኝነት ያደራጀው ፀረ-አብዮት አድሃሪ ድርጅት ወኪል ሆነው ከሻዕቢያ፣ ከወያኔና ከኦነግ ተባብረው የግንቦት ስምንት የአብዮት ቅልበሳ ሙከራ ካደረጉት አድሃሪ ከፍተኛ መኮንኖች መካከል ቀንደኛ መሪ የነበሩት ሜ/ጄነራል በዚያን ጊዜ ሌ/ኮሎኔል መርዕድ ንጉሴ የሚባሉት መኮንን የሚያዙት አንድ እግረኛ ሻለቃ ነበር።

በብርጌዱ መምሪያ ጽሕፈት ቤት በብርጌዱ ምክትል አዛዥና በተቀሩት የብርጌዱ መምሪያ መኮንኖች ስለ አካባቢው ጠቅላላ ሁኔታ፣ ስለ ጠላትና ስለ ወገን ሰፌ ገለፃ ተደረገልን።

ከጎዴ ጀምሮ እስከ ነገሌ የሠራዊቱ ስጋትና ትኩረት አንድና ተመሳሳይ ሲሆን፤ ይኸውም በማናቸውም ቀንና ሰዓት የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ስለሚዘጋጁበት ወረራ ነበር። አዲሱ መንግሥት ፕሮፓጋንዳ፣ ሠራዊቱን ለማለዘብና ለማግባባት ይጠቅም እንደሆነ እንጂ የቡድኑ አባላት ቀድሞ ከምናውቀው ነገር የተለየ አዲስ ነገር አላጋጠመንም።

በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥነት የተፈራረቁ አዛዦች ሁሉ እስከ ጄኔራል ነጋ ተገኝ ድረስ ስለ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ የጦር ኃይል ድርጅትና የወረራ ዝግጅት በዝርዝር ያላመለከቱትና ያላሳሰቡት ነገር የለም።

ያዛዦቹን የተደጋገመ ሰፊና ጥልቅ ሪፖርት ተመልክቶና ተጠቅሞ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ሲገባ ያንኑ ነገር በየጦር ክፍሉ እየተዘዋወርን እንድንሰማ መደረጉ ለአብዛኛው የቡድኑ አባላት ጠቃሚ ነገር አከናወንን የሚል ስሜት አልሰጠንም።

በአጣዳፊ የሚፈለገውን የጦር መሣሪያ የሰሜን አሜሪካ መንግሥት "እጅ በእጅ የምትከፍሉ ከሆነ በሽያጭ ይፈለግላችኋል። ከዚህ በተረፈ በዱቤና ያለ ክፍያ በርዳታ የመስጠት ግዴታ የለብንም" ብሎ ነግሮናል።

እጅ በእጅ ክፍሎ የመግዛት አቅምና ሌላ የጦር መሣሪያ ምንጭ ወይም አማራጭ የሌለን ብቻ ሳይሆን ቢኖርም እንኳ በሕዝብ የተቃውሞ አመጽ በመናወጥ ላይ ላለና የራሱ ሕዝብ ያልተቀበለውን መንግሥት ባዕዳኖች ሊቀበሉና በአመኔታ ሊዋዋሉ ስለማይችሉ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት በዚያ ወቅት የሚፈለገውን መሣሪያ አይነት፣ መጠንና የሚፈለግበት ጊዜና ፍጥነት ለማግኘት እንደማይችል ለብዙዎቻችን በጣም ግልጽ ነበር።

ጉብኝቱ ከሁለት ሳምንት በላይ የሆነ ጊዜ ወስዶ ከነጌሌ እንደገና ተመልሰን ወደ ሐረር በመሄድ በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ጽሕፈት ቤት ውስጥ አጠቃላይ ገለጻ በመስማት ከክፍለ ጦሩ አመራር አካላት ጋር በመወያየት ጉብኝቱን ቋጨንና ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

በዚህ ታሪካዊ በሆነ መልካም አጋጣሚ እኔ በግሌ በየደረስንበት የጦር ክፍል የማውቃቸውና ከማምናቸው መኮንኖች ጋር ስለ አገራችን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ስለ ሠራዊታችን አቋምና አስተሳሰብ በግልጽነትና በዝርዝር የመወያየት እድል ገጥሞኝ ነበር።

በጉብኝቱ ካጋጠሙኝና ካስተዋልኳቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያስገረመኝና እንግዳም የሆነብኝ ነገር ሠራዊቱ ሁሉ በፖለቲካ ስሜት ገንግኖና የሥር ነቀል ለውጥ አቀንቃኝ ሆኖ መገኘቱ ነበር። ያለአንዳች ፍርሀትና ስጋት የአገራቸውን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በገሀድ ይወያዩም፣ የአገሪቱንም የገዢ መደቦች በግልም ሆነ በወል ይተቹም ነበር።

ከተገናኘኋቸው መኮንኖች የብዙዎቹ ቁጭትና ጥያቄ የምሥራቁ ሠራዊት ከሌሎች ግምባር ቀደም ሆኖ ለተፋጠነ ለውጥ መሥራትና መነቃነቅ ሲገባው ዳር በመቆም ሌሎችን ተመልካችና ተከታይ የሆነው በምን ምክንያት ነው የሚል ነበር።

እናንተ ከእኛ የተሻለ መረጃና ለሁሉም ነገር ቀረቤታ ያላችሁ የክፍለ ጦሩ መምሪያ መኮንኖች "ለምንድን ነው አመራር የማትሰጡን" የሚል ጥያቄ አብዛኞዎቹ መኮንኖች ያቀርቡልን ነበር። አመራር ይሰጡናል ተብለው ለሚገመቱ የክፍለ ጦሩ መምሪያ መኮንኖች መልዕክታቸውን የማደርስ መሆኔን ቃል በመግባት 'በእኛ በኩል ከብዙ ነገር እንድንቆጠብ ያደረገን በተስፋፊው ሶማሊያ መንግሥት በኩል እየተደገሰልን ላለው የጥቃት ወረራ ቅድሚያውን በመስጠት እንደነበርና ነገር ግን ከጥቂት ሳምንት በፊት አዲስ አበባ ተገኝቼ ከብዙ ሁነኛ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ እንደተረዳሁት የሶማሊያው መሪ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበርነቱን ከማስረከቡ በፊት ወረራ ሊሰነዝር ስለማይችል ቢያንስ የአንድ ዓመት ያህል የሰላም ጊዜ ሊኖረን ስለሚችል በግሌ የነበረኝ ስጋት ተቃሏል' የሚል ነበር።

በ1953 ዓ.ም እነጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ ያቀዱትን አመጽ በማስታወስ የጦር ኃይላችን ሁነኛ አመራር ባለማግኘቱ ብቻ ሳይፈልግ የፊውዳሎች መሣሪያ በመሆን እንዳከሸፈው ሁሉ ዛሬም ተመሳሳይ ድርጊት ለመፈፀም የተወሰኑ ከፍተኛ መኮንኖች እያሴሩ በመሆኑ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ያሉ የጦር ክፍሎች በሙሉ ከእንግዲህ ወዲያ የሻለቃ ማዕረግ ባላቸውና ከዚያም በታች በሆኑ ወጣት መኮንኖች ነው መመራት ያለብን የሚል አቋም ስለመያዛቸው አስረድቼ በዚህ ርዕስ ላይ በመጠኑ ያከራከረ ውይይት ከተደረገ በኋላ ሀሳቡን ተቀበሉት።

ከዚህ በኋላ የእኛ ክፍለ ጦር የሚታዘዘው የንጉሡ አማች በመሆን ራሳቸውን የንጉሣዊያን ቤተሰብ አድርገው በሚያዮት የጄኔራል ነጋ ተገኝ መሣሪያ በሆኑ የተወሰኑ የክፍለ ጦሩ አባላትና አካላት ክፍለ ጦራችን በተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይመራ የሚያነቃና የሚያስተባብር ህቡዕ ኮሚቴ በክፍለ ጦሩ መምሪያ እንደ ተቋቋመ አስረድቼ አሁን ባሳሰባችሁት መሠረት ከእንግዲህ ወዲያ አንበሳው ክፍለ ጦር መሪ እንጂ ተከታይ እንዳይሆን በትጋት እንሰራ ዘንድ በየክፍሉ ተመሳሳይ ኮሚቴ ተቋቁሞና መገናኛ የሚሆን የምሥጢር ቁልፍ ተፈጥሮ እየተገናኘን መሥራት ወሳኝነት አለው ብዬ ባቀረብኩት ሀሳብ መሠረት በየብርጌዱ ህቡዕ ኮሚቴ እንዲቋቋምና የኮሚቴ አባልና አመራር አካል የሚሆኑት መኮንኖች ከሻለቃ ማዕረግ በላይ እንዳይሆኑ ተወሰነ።

የመኮንኖች ማዕረግ ከሻለቃ በላይ እንዳይሆን የተወሰነው ብዙ ካነጋገረና ካከራከረ በኋላ ሲሆን እዚህ ውሳኔ ላይ የተደረሰውም ከሻለቃ በላይ ያሉትን መኮንኖች ሁሉ ባለማመንና እስከ መጨረሻው ለማግለል ታስቦ ሳይሆን የለውጡን ውጥን በእጭሩ እንዳይከሽፍ ሲባል ለጥንቃቄ ለመጀመሪያው የአብዮቱ አፍላ ጊዜ ማስፈለጉን ሁሉም ካመነበት በኋላ ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ በዶሎ፣ በባሬና በነገሌ ከመኮንኖች ጋር ተመሳሳይ ውይይት ተደርጎ ተመሳሳይ ውሳኔ ላይ ተደረሰ። የአራተኛ እግረኛ ብርጌድና የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት በአንድ እዝና ቁጥጥር ስር ሆነው እንዲዋጉ መደረጉ ብቻ አይበቃም። በወቅቱ

አገራችን ሁኔታ ላይም የጋራ ግንዛቤ፣ የጋራ ዓላማና የተግባር ትብብር ያስፈልገናል ብዬ ያቀረብኩትን ሃሳብ ተቀብለው ወደ ውሳኔ ከማምራታችን በፊት ሌ/ኮሎኔል መርዕድ ንጉሴን እናማክራቸው አሉኝ።

ከመኮንኖቹ ሁኔታ ለመገመት እንደቻልኩት ያለፈውን አመፅ የመራው ኮሚቴ እንደሆነና ኮሚቴውንም በህቡዕ የመሩት ሌ/ኮሎኔል መርዕድ መሆናቸውን ነበር። እንደሚታወሰው የጦር ኃይሉ ሦስተኛው ንቅናቄ በሻለቃና ከዚያ በታች ባሉ መኮንኖች ይመራ ሲል፣ አብዛኛው የመሃል አገሩ መለዮ ለባሽ ከያዘው አቋም ጋር ለማስተባበርና ይህም ርዕስ ላይ ከሌ/ኮሎኔል መርዕድ ንጉሴ ጋር መነጋገሩ በኔ በኩል አስቸጋሪ ሆነ።

በብርጌዱ ሠራዊት የሚወደድና የሚከበር፣ ያለፈውንም አመጽ ከነሌ/ኮሎኔል መርዕድ ጋር በወል የመራ ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ የሚባለው መኮንን በግል ችግሬን ስለገለጽኩለት "ይሄ አያሳስብህ እኛ አንተ በሌለህበት የራሳችንን ስብሰባ አድርገን የተቀሩት የጦር ክፍሎች እዚህ ውሳኔ ላይ እንዴት መድረስ እንደቻሉ አስረድተን እናሳምናቸዋለን" አለኝ። እንዳለውም አድርጎ አራተኛ ብርጌድ የተቀሩትን ሠራዊቶች አቋም ያዘ።

ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ የጦር ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ሲቋቋም የአራተኛ ብርጌድ ጦርን በብቸኝነት ወክሎ አባል የሆነ መኮንን ነው። በድህረ አብዮት በሥነ ሥርዓት ጉድለት ተነቅፎ ከደርግ አባልነት ወደ ሠራዊቱ በመመለስ በሰሜን ኢትዮጵያ ሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት ውስጥ በብ/ጄነራል ማዕረግ የኮር ምክትል አዛዥ ሆኖ የሚሰራበት ጊዜ ከጄነራል መርዕድ ንጉሴ ጋራ በነበረው የቆየ ትውውቅና ግፊት ይመስለኛል የኢትዮጵያ ነፃ መኮንኖች ንቅናቄ በተሰኘ ስያሜ የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ያቋቋመው ምንደኛ ፀረ-አብዮት ድርጅት አባል ሆኖ ከገንጣዮችና ከአስገንጣዮች ጋር በመወገን አብዮት ለመቀልበስና ሃገር ለማፍረስ ሲሞክር በመያዙ በአብዮታዊ ሠራዊት ተወግዷል።

የጦር ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት ሦስተኛ ክፍለ ጦር ከሌሎች የጦር ክፍሎች ጋር ባደረገው ውልና ትብብር መሠረት፣ አራተኛ እግረኛ ብርጌድን በመወከል ከሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ህቡዕ ኮሚቴ ጋር አገናኝ የነበረው ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ፣ የምድር ጦር ታንከኛን መምሪያ በመወከል ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ የሰሜኑን ሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር በመወከል ሻለቃ ነሲቡ ታዬና ሦስተኛ ክፍለ ጦርን በመወከል አዲስ አበባ ተቀምጦ የአዲስ አበባን አካባቢ የጦር ክፍሎችና የኢትዮጵያን አየር ኃይል ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ህቡዕ ኮሚቴ ጋር አገናኝ የነበረው ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ነበሩ። ሻለቃ ነሲቡ ታዬ ንውስ ደርግ የምንለው ተቋም እስኪፈርስ ድረስ የሰሜኑን ሠራዊት ንውስ ደርግ በሊቀመንበርነት የመራና በድህረ አብዮት በቅድሚያ በሶሻየት ሕብረት የኢትዮጵያ መንግሥት አምባሳደርና በኋላም በሚኒስትር ማዕረግ የአገሪቱ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረ ጓድ ነው።

በሜ/ጄነራል መርዕድ ግዛው የተመራው የጦር ኃይሎች ኢንስፔክተር ቡድን ሥራውን አጠናቆ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ ለመከላከያ ሚኒስትሩ በሚቀርበው ሪፖርት ውስጥ የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ስጋቶችና ከመፍትሄ አንፃርም የሚያቀርቧቸው ሀሳቦች በሚገባ ይንጸባረቁ ዘንድ አስተዋፅኦ እንዳደርግ አዛዡ ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝ ከቡድኑ ጋራ አብሬ ወደ አዲስ አበባ እንድሄድ ስላዘዙኝ ከጉብኝቱ በኋላ ለጥቂት ቀናት አዲስ አበባ ተገኝቼ ነበር።

አዲስ አበባ በደረስን በበነጋታው እነጄነራል መርዕድ ግዛው ዘንድ ቀርቤ የትና እንዴት ከቡድኑ ጋር ልሰራ እንደምችል መመሪያ ይሰጡኝ ዘንድ ስጠይቅ "አንተ የቡድናችን አባል

የሆንከው ሦስተኛ ክፍለ ጦርን በመወከል እንጂ መከላከያ ሚኒስቴርን ስላይደለ ለጊዜው አታስፈልገንም" ስለተባልኩ የሰራሁት ሥራ አልነበረም። ይህንኑ ለክፍለ ጦሬ አዛዥ ለጄኔራል ነጋ ካሳወኩ በኋላ በአዲስ አበባና በተለይም በመከላከያ ሚኒስቴር አካባቢ ስላለው ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ተረድቼ ለመመለስ የሳምንት ፈቃድ ጠይቄ ተፈቀደልኝ።

በተሰጠኝ የአንድ ሳምንት የጊዜ ክልል ውስጥ ናዝሬት ያለውን የታንከኛውን መምሪያ፣ ደብረ ዘይት ያሉትን የአየር ኃይሉንና የአየር ወለዱን ጦር ሰፈር፣ የምድር ጦር የአየር ክፍሉን እና የገነት የጦር ትምህርት ቤትን በተለያዩ የሥራ ሰበቦች ከሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ጋር ሆነን በመጎብኘት ከብዙ ሰዎች ጋር ተገናኘን።

ደህና አድርጌ ከማውቃቸው ከአንዳንድ ሲቪል ምሁራኖችም ጋር ተገናኝተን የተለያዩ ሀሳቦችን ተለዋወጥን። በዚህ መረጃ በማሰባሰብና የተለያዩ ሰዎችን አስተያየት በመቃረም ጥረት ካገኘኋቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው የአየር ኃይል ሠራዊታችን የነበረበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ነበር።

በ1953 ዓ.ም በነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከተደረገበት ጊዜ በስተቀር የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በሃገር ውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ የአገሪቱን የጦር ኃይሎች በጥቅል ወይም የጦር ኃይሎች አካል የሆኑትን የጦር ክፍሎች በግልና በስም ጠርቶ የወቀሰበት ወይም የኰነነበት ጊዜ አይታወቅም። በዚህ ረገድ የመለዮ ለባሹ አካላት የሆኑ ግለሰቦች የተከሰሱ ቢኖሩ በበኩሌ የሚታወሰኝ ሜጫና ቱለማ በመባል የሚጠራው የጥቂት የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት እንቅስቃሴ ለአመፅ መርታችኋል ተብለው የተወነጀሉት ጄኔራል ዳዊት አብዲ፣ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩና ሻምበል ማሞ መዘምር ነበሩ።

በሜጫና ቱለማ እንቅስቃሴ ጊዜ ሌሎችም በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የጎጃምን ክፍለ ሃገር ጨምሮ የመገንጠልና የመንግሥት ተቃውሞ አመጾች መካሄዳቸው እየታወቀ መንግሥቱም ሆነ የመንግሥቱ ብዙሃን ማሰራጫዎች ለሕዝብ አንዳችም ነገር ገልፀው አያውቁም። እነዚህ ሁኔታዎች በነበሩበት የጊዜ ክልል ውስጥ ለማናቸውም የሃገር ውስጥ የፖለቲካ ችግሮችና ሕዝባዊ አመጾች በምክንያትነት የሚከሰሱት የአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ብቻ ነበሩ።

ከ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ጀምሮ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ማህበርን፣ በተለይ ደግሞ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርን የመንግሥቱ አንጃ የፖለቲካ ድርጅት አድርጎ ይመለከታቸው ስለነበረ የብዙሃን ማሰራጫዎቹም ትኩረት በተማሪው ላይ ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል።

የአገሪቱ የጦር ኃይሎች አካል የሆኑትን ክፍሎችና የጦር አባላት በሃገር ውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ በገሀድ መወንጀል የተጀመረው ከየካቲት 1966 ዓ.ም ጀምሮ በልጅ እንዳልካቸው መስተዳድር ነበር።

እንደሚታወሰው ለአያሌ ምዕት ዓመታት ተዳፍኖ የኖረውን የሕዝብ ቁጣ የቀሰቀሰውና ወደ አመፅ ያመራው ብቻ ሳይሆን ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድን ከሥልጣን ያወረደው የጦር ኃይሉ ስለነበር፣ ልጅ እንዳልካቸው በንጉሡ ትዕዛዝ አቶ አክሊሉን ተክተው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንደሆኑ ከማንምና ከምንም በላይ የፈሩት የጦር ኃይሉን ነበር። ስለሆነም ከሥራቸው ሁሉ ቅድሚያውን የሰጡትና በብርቱ ያተኮሩበት ጉዳይ የጦር ኃይሉን ድጋፍ ለማግኘት በሚያስችሏቸው ተግባሮች ላይ እንደነበረ ገልጫለሁ።

በምልምል መኮንኖች አማካኝነት በዚህ ወቅት ለሠራዊቱ ጆሮ ይጥማሉ ያሏቸውን ቅስቀሳዎች ካደረጉና ጥገናዊ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ካሰራጩ በኋላ የመላውን የጦር ኃይል የሚወክሉ ናቸው ያሏቸውን ግለሰቦች ከየጦር ክፍሉ ጠርተው አዲስ አበባ በማስመጣትና በሰልፍ እየነዱ ንጉሡ ፊት በማቅረብ 'ለዙፋኑና ለልጅ እንዳልካቸው መስተዳድር ታማኝነታቸውን ገለፁ' ብለው የመንግሥቱ የብዙሃን ማሰራጫዎች ገለጹ።

መልካም ስምና ከተቀሩት ጦር ክፍሎች ሁሉ የላቀ ስልጠናና ዕውቀት ያለውን የአየር ወለድ ሻለቃ ጦርና የዚሁ ሻለቃ አዛዥ በነበሩት በኮሎኔል የዓለምዘውድ መሣሪያነት ልጅ እንዳልካቸው እራሳቸው የሚመሯቸው በወታደራዊ ኮሚቴ እየተረዳ የሚሰራ የብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን የተባለ ሁለት አብዮት ቀልባሽ ተቋማትን መሰረቱ።

እነዚህ ተቋማት ቀዳሚና አብይ ትኩረት አድርገው የሚያሳድዷቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የአየር ኃይል ሠራዊት አባል ተራማጅ መኮንኖች፣ የሃገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ መርተዋል የሚባሉ የአገሪቱ የሠራተኛ ማህበር አመራር አካላት እና ወትሮም የመንግሥቱ ጥቃት ዒላማ የሆነው የተማሪው ማህበር የአመራር አካላትና አመራሩን ነበር።

ኮሎኔል የዓለምዘውድ በአየር ኃይሉ ውስጥ እውቅ በራሪ ተዋጊ መኮንኖችንና ከበታች ሹማምንቱም ቀልፍ የቴክኒክ ሙያ ያላቸውን አባላት እያሳፈኑ በምድር ጦር ወታደር ፖሊስ በሚጠበቀው ወህኒ ቤት ያጉሯቸው ጀመር። ከአየር ኃይሉ ሠራዊት ውስጥ 'አገራቸውን በመክዳትና በግል ጥቅም በመታወር የኢትዮጵያ ጠላት ለሆነችው ለሊቢያ መንግሥት የተገዙ አሉ' ከማለት ሌላ 'የአዲስ አበባን ከተማና ቤተ መንግሥቱን በቦንብ ለመደብደብ ያቀዱት እቅድ ተደረሰበት' በማለት የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት በአየር ኃይላችን ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ጀመረ።

ይህን በመሰለ ዘመቻ መልካም ስማቸው የተበከለባቸውና እፈናውን የፈሩ መኰንኖች አየር ኃይሉን እየጣሉ በመሔድና በመሰወር ላይ መሆናቸውን ከመስማት ባሻገር ደብረ ዘይት ድረስ ሔደን ማረጋገጥ ቻልን።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል፣ የሰው ኃይሉ ከማነሱና ከትጥቁ መናኛነት በስተቀር በውጊያ ብቃት ደረጃው ሠራዊቱ ለአገሩ ባለው ፍቅርና ለክፍሉ ባለው ቀንአዊነትና በወታደራዊ ሞራሉ ኩራተኝነት በምድር ጦር ሠራዊቱ ዘንድ የተወደደ ሲሆን በተለይ በሦስተኛ ክፍለ ጦር በኩል ለማይቀረው ከሶማሊያ ውጊያ አለኝታችን አድርገን የምንመለከተው ኃይል ነው።

አገራችን የአረብ ሊግ አባል በሆኑና የዋርሶን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በታጠቁ ጠላቶቻችን ከመከበቧ በላይ በሃገር ውስጥ ከሀዲዎችና ገንጣዮች ሽብር እየደማች በመሆኗ ራሳችንን የምንከላከልበት መሣሪያ አፄ ኃይለሥላሴ የሰሜን አሜሪካንን መንግሥት ለመለመን ዋሽንግተን ሄደው በሃፍረት ባዶ እጃቸውን እንደተመለሱ እናውቃለን። በዚህ ሁኔታ ባለው የሃገር መከላከያ ሠራዊት ችግር ከመፍትሔ መፈለግ ፋንታ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት የሠራዊቱን ስም በማጥፋት፣ ከፋፍሎ ለማዳከምና ብሎም ለማፍረስ የሚደረገውን አደገኛ ጥረት በዝምታ መመልከት የለብንም በማለት ወደ ሐረር ተመልሼ ለህቡዕ ኮሚቴው ስላመለከትኩኝ ጊዜ ወስደን በስፋትና በጥልቀት ተወያየንበት።

የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት የወረራ መሰናዶ፣ በአገሪቱ ሰሜንና ደቡብ ክልሎች የሚካሄደውን የሃገር ውስጥ ሽብርና የመገንጠል ሴራ፣ በአየር ኃይል ሠራዊታችን ላይ የተጀመረውን አደገኛ የማፍረስ ተግባር፣ ከወቅቱ ሕዝባዊ አመፅና ከአጠቃላይ አገራዊ ሠላምና ደህንነት ጋር እያገናዘብን በምንወያይበት ጊዜ ከኮሚቴው አባላት መካከል አንዳንዶቹ እራቅ ብለው በመሔድ "እነዚህን የእኛን ስጋቶች የልጅ እንዳልካቸውን

መንግሥት ይጋራናል ብላችሁ ታስባላችሁ? በማለት ይጀምሩና እኛ እንጨነቅ እንጂ በሕዝብ ቁጣና አመፅ በመናወጥ ላይ ያለው የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት የተገንጣዩቹን ሴራና የሶማሊያን ወረራ የሱ ችግር አድርጎ ይመለከታቸዋል የሚል ግምት የለንም" አሉ።

ጓዶቹ ጉዳዩን በየተራ እየተቀባበሉ የእንዳልካቸው መንግሥት ከገባበት የፖለቲካ ማጥ ለመውጣት የሕዝቡን ቁጣ እንዲያበርድለትና የትኩረት አቅጣጫውንም የሚለውጥለት ከመሆኑ በላይ ይህንን አምርሮ የሚጠላውንና የሚፈራውን የጦር ኃይል በአገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት በቀውጢ ውጊያ ሲወጠር እሱ ፋታ ስለሚያገኝ በአሁኑ ጊዜ የአገሪቱ የውጭና የውስጥ ጠላቶች በጦር ኃይላችን ላይ የሚሰነዝሩትን ጥቃቶች የእንዳልካቸው መንግሥት አይፈልጋቸውም ወይም የሶማሊያንም ሆነ የሱዳንን መንግሥት ጣልቃ ገብነት አይጋብዝም ብሎ ማሰብ የዋህነት ሲሆን፣ የውጪም የውስጥም ጠላቶቻችን ደግሞ በበኩላቸው ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከዚህ ጊዜ የተሻለ አጋጣሚ የለም በማለት ተጠራርተው በእርዳ ተራዳ አይረባረቡብንም። ማለት ታላቅ ስህተት ነው በማለት የኮሚቴውን አባላት ትኩሳት ይበልጥ ከፍ አደረጉት።

እዚህ ላይ ታሪክ ወደኋላ እንደሚያሳየን የኮሚቴው ትንበያ ፍፁም ትክክል ነበር። ምክንያቱም አንባቢ እንደሚያውቀው ወይም እንደሚያስታውሰው በድህረ አብዮት የኢትዮጵያ ሕዝብ የገጠመው ፈተና ይሔው ነበርና። በዚህ ሁኔታ የተካሄደው ውይይት እልባት ወይም ውጤት፣ ጠቅላይ ምኒስትሩ እንዳልካቸውና የመከላከያ ምኒስትሩ ጄነራል አብይ በአስቸኳይ ሐረር መጥተው እየተደገሠልን ያለውን የውጭ ወረራና ሃገር የመገንጣጠል ወይም የማፍረስ ትግል ለመመከትና ብሎም ለማክሸፍ ምን ዕቅድና ዝግጅት እንዳላቸው በገፅ ቀርበው ለሠራዊቱ ያሥረዱ ዘንድ እንጠይቃቸው የሚል ሆነ።

የጥያቄ አቀራረብ በኃይል የተመረኮዘ ህገወጥ ሳይሆን በዕዝ ጠገጋችን የክፍለ ጦር አዛዦችን እንዲያቀርቡ ስንወስን ጄነራል ነጋ በተደጋጋሚ "እኔ ከእናንተ የተለየ ዓላማና ፍላጎት ስለሌለኝ አትራቁኝ ምንም ነገር አትሰውሩኝ ተባባሪያችሁ ነኝ" ብለው የተናገሩትን ቃል ተግባራዊ ለማድረጋቸው መፈተኛም ይሆነናል ብለን በማሰብ ጥያቄያችንን አቀረብንላቸው።

ጄነራል ነጋ የአገራችን ምሥራቅና ደቡባዊ ክልሎችን ወሰኖች ጥበቃ ሃላፊነት ያለበት ክፍለ ጦር አዛዥ እንደ መሆናቸው መጠን የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ለወረራ ዝግጅት ለአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ደጋግመው ማስረዳት የሚያስደስታቸው ጉዳይ ቢሆንም የኮሚቴው ጥያቄ ከባድና ዱብዕዳ ሆኖባቸዋል።

ሆኖም ደግም ምንም ነገር አትሠውሩኝ ስለአሉ ይህንን የመሰለ ከባድ ጥያቄ በግልፅነት ከማቅረባችን ባሻገር፣ ጥያቄያችን ሕጋዊነትንና የዕዝ ጠገግ ተከትሎ በእሳቸው አማካኝነት እንዲቀርብ መጠየቃችን፣ ጄነራል ነጋ አሁንም ሦስተኛ ክፍለ ጦርን በቁጥጥሩ ስር እንዳደረገ ነው የሚያሰኝ ስም ስለሚሰጣቸው መደሰታቸውን ለማንበብ ችለናል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩንና የመከላከያ ሚኒስትሩትን በአንድነትና በአስቸኳይ ሐረር ይምጡ ብሎ መጠየቁ እጅግ የከበዳቸው መሆኑን ግን ሊሸሽጉን አልቻሉም። ሁሉም ራሱን ለመጠበቅ ሲል ፈርቶ በሚኖርበት ጊዜ ይህንን ጥያቄ ማቅረብ በበላይ አለቆቻቸው ዘንድ እንደማይወደድላቸውና ተቀባይነትም እንደማያገኝ በመገመታቸውና በመፍራታቸው "የአገሪቱ ከፍተኛ የሲቪል የጦር ባለሥልጣኖች በወታደሩ እየተያዙ በሚታሰሩበት በአሁኑ ጊዜ ልጅ እንዳልካቸው ይህንን ጥሪ ይቀበላሉ ብላችሁ ታስባላችሀ?" ብለው ላቀረቡልን ጥያቄ የእኛን ፍርጥም ያለ አቋም ሲመለከቱ ትንሽ ለዘብና ጠንቀቅ ብለው "የእነሱን እቅድ

ለመረዳት ከሆነ እነሱን ከመጥራት ፋንታ እኛ ለምን ወደነሱ አንሄድም? ይህንን ማድረግ እንችላለን?” ሲሉ መልሰው ጥያቄ አቀረቡልን።

የእኛ ጥያቄ እቅዳቸውን በገፅ ቀርበው ለሠራዊቱ እንዲያስረዱ ስለሆነ የእነሱ መምጣት አስፈላጊ ነው ስንላቸው ይሄ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ትተን የመከላከያ ሚኒስትሩንና ጠቅላይ ኢታማጆሩን ብቻ እንዲመጡ እጠይቅ ዘንድ እባካችሁ ተባበሩኝ በማለት አጥብቀው ስለለመኑ ሃሳባቸውን መቀበል ግድ ሆነና የመከላከያ ሚኒስትሩን አነጋግራለሁ ብለውን ወደ አዲስ አበባ ሄዱ።

በእሳቸው የአዲስ አበባ ቆይታ ጊዜ ሐረር የሚገኘው ወታደራዊ ኮሚቴ በየብርጌዱ ውስጥ ላሉ ንዑሳን ኮሚቴዎች በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያለብንን የሃገር ድንበርና ክብር የማስጠበቅ ሃላፊነታችንን ከዚህ አንፃር ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት እስከዛሬ ካከናወነው የጦር ኃይል ግንባታና ከሚያደርገው የወረራ መሰናዶ አንፃር መንግሥታችን በበኩሉ ምን እቅድና መሰናዶ እንዳለው ለመጠየቅ ቢቻል ጠቅላይ ሚኒስትሩን ባይቻል የመከላከያ ሚኒስትሩን ሐረር ጠርተን ለማነጋገር የወሰንን መሆናችንን ስለገለጽንላቸው ታላቅና ተገቢ እርምጃ ነው ሲሉ ሀሳቡን ከአድናቆት ጋር የሚደግፍ መልዕክት ላኩልን።

የሠራዊቱን የድጋፍ መልዕክት ያውቁት ዘንድ ለጄነራል ነጋ አዲስ አበባ ደውዬ ስገልጽላቸው በጣም በመደንገጥ “የእኔን ተልዕኮ ውጤት ሳታውቁ ለሠራዊቱ መግለጻችሁ ትክክል አይደለም፤ በጣም የቸኮላችሁ ብቻ ሳይሆን እኔንም አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ነው የሰራችሁት” በማለት ቅሬታቸውን ገለጹልኝ።

አዲስ አበባ ሄደው ከነማን እንደተገናኙና ምን መልስ እንዳገኙ በበኩሌ የማውቀው ነገር አልነበረም። ከአዲስ አበባ ተመልሰው ያሳወቁን “የሠራዊቱ ጥያቄ ነው በማለት ለመከላከያ ሚኒስትሩና ለጠቅላይ ኢታማጆሩ የተፋጠነ የጉብኝት ጥያቄ አቅርቤያለሁ። ሆኖም እጅግ የበዛ የሥራ ጫናና የፖለቲካ ውጥረት ያለባቸው ስለሆነ ቁርጥ ያለ መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም። ጉዳዩን አጥንተንና ለሠራዊቱም ጥያቄ ተሰናድተን መልሱን ወደ ፊት እንገልፃለችኋለን ነው የተባልኩት” በማለት ውልና ገደብ የሌለው ነገር ነው የነገሩን።

የጉብኝቱ ጥያቄ ለሠራዊቱ የተናኘ ስለነበረ የተጠሩት ባለሥልጣኖች መቼ ነው የሚመጡት? ሐረርን ብቻ ነው ወይስ ኦጋዴንም ይጎበኛሉ ወዘተ በማለት ከሠራዊቱ ለሚቀርቡልን ጥያቄዎች የምንሰጠው አጥጋቢ መልስ አልነበረም። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ይሄ ጥያቄ ለምን ቀረበ? ቀና ጥያቄ ነው ወይስ ተንኮል አለበት? እነማናቸው የዚህ ጥያቄ አመንጪዎችና ቀስቃሾች ወዘተ ለተሰኙ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ይመስላል የሐረር ከተማ በተለያዩ የመንግሥቱ ሰላይ ቡድኖች ተወረረች።

ስለ አቀረብነው ጥያቄ ከአዲስ አበባ ምንም አይነት መልስ ሳይሰጠን ቀናትና ሳምንታት ተቆጠሩ “ጥያቄያችን መልስ ሳያገኝ ይህንን ያህል ጊዜ የወሰደው እንደ ሌላው ሠራዊት ሳናምፅ ሕጋዊ በሆነ መንገድና በአግባቡ የእዙን ጠገግ ተከትለን በመጠየቃችን ነው።” የሚሉት የሠራዊቱ አባላት እየበዙ ሄዱ።

የክፍለ ጦሩ አዛዥ በጉዳዩ ቢጨነቁም ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም። በመጨረሻ የግንቦት ወር በሌ/ጄነራል ወ/ሥላሴ በረካ የሚመራ የጄነራል መኮንኖች ቡድን በጥያቄው መሠረት በሐረር ከተማ ዙሪያ ያለውን ጦር ለመጎብኘት እንደሚመጣ ተገልፆ ቡድኑ በሐረር ዙሪያ ያሉትን የጦር ክፍሎች በየጦር ሰፈራቸው እየተዘዋወረ በተራ የሚያነጋግር እንጂ መላውን ሠራዊት በመሰብሰብ በአንድ ላይና በአንድ ስፍራ ለማነጋገር የማይችል መሆኑን በማሳወቅ ቅድመ ሁኔታዎችን ደረደረ።

ሠራዊቱ የሚጠብቀው፣ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ካልተቻል ከዚያ በመለስ ቢያንስ የመከላከያ ሚኒስትሩን ሆኖ ሳለ ጄኔራል ወ/ሥለሴ መላካቸው ትክክል እንዳልሆነና ያም ሆኖ ደግሞ ሠራዊቱን በወል የማያነጋግሩ ከሆነ መምጣታቸው እንደማይፈለግ አዛዡ በመደበኛ የመገናኛ መስመር በኩል ለመከላከያ ሚኒስቴር ያስታውቁ ዘንድ ኮሚቴው አሳሰበ። አዛዡም ይህንን ገልፀው ሳለ ከአዲስ አበባ የመጣው መልስ ግን ቡድኑ ሐረር የሚደርሰው ግንቦት 11 ቀን በሦስት ሰዓት ገደማ ይሆናል የሚል ነበር። ኮሚቴው ይህንን ሁኔታ በራሱ የመገናኛ ዘዴ በየብርጌዱ ላሉት ንዑሳኖች ኮሚቴዎች ስላሳወቀ ዜናው ወዲያው ለሠራዊቱ ተዳረሰ። በዚህም መሠረት ከየብርጌዱ የተላከልን መልእክት ጠቅላላ ይዘት እንደሚከተለው ሆነ።

"በክፍለ ጦራችን ውስጥ ለረጅም ዘመን በዳበረው የወታደራዊ ጨዋነት ባህላችንና ስነ-ሥርዓት አክባሪነታችን በቅንነት፣ ለአገራችን ባለን ፍቅርና የሃላፊነት ስሜት ያቀረብነውን አነስተኛ ሰላማዊ ጥያቄ መንግሥታችን የማይቀበል ከሆነ በጄኔራል ወ/ሥላሴ በረካ የሚመራውን የጄኔራል መኮንኖች ቡድን በቁጥጥር ስር አውላችሁ ባቀረብነው ጥያቄ መሠረት የተፈለጉት ባለሥልጣኖች መጥተው እንዲያነጋግሯችሁ ጠይቁና የሚሰጠውን መልስ አስታውቁን" የሚል ነበር።

ከንዑሳን ኮሚቴዎች የመጣውን ውሳኔ ሐረር ያለው ዋናው ኮሚቴ ቀድሞ ያሰበበት ስለነበረ የጄኔራሎቹ ቡድን ከመምጣቱ በፊት በቁጥጥር ስር እንዲውል ከሚደረግበት ወታደራዊ እቅድ ሌላ በዚሁ አጋጣሚ ለንቅናቄው ሕዝባዊ የፖለተካ ይዘት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ሰፋ ብሎ እንዲታቀድ ተወሰነ።

በዚህም ውሳኔ መሠረት በእቅዱ ውስጥ ከተካተቱት አብይ ጉዳዮች ወይም መሰናዶዎች ጥቂቶቹንና ዋና ዋናዎቹን ከዚህ እንደሚከተለው ለመግለፅ እወዳለሁ። የዓለማያ የግብርና ኮሌጅን ተማሪዎችና መምህራንን የሚወክሉ፣ የሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ተማሪዎችና መምህራንን የሚወክሉ፣ የመድሃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ተማሪዎችና መምህራንን የሚወክሉ፣ በሐረር ከተማ ነዋሪ በሆነው የሕብረተሰብ ክፍል የታወቁና የሚደመጡ ተራማጅ ግለሰቦችን ያጣመረ አንድ ቡድን በህቡዕ ተቋቁሞ በክፍለ ሃገሩ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ የሕዝባዊ ሰልፍ ጄኔራሎቹ በታሰሩ ማግሥት እንዲካሄድ ተወሰነ።

የሰልፉን ሕዝባዊነት አጉልተው የሚያሳዩና ሥርነቀል የፖለቲካ ለውጥ በሚጠይቁ በራሪ ወረቀቶች፣ ስሌዳዎችና ሥዕሎች ሰልፉ እንዲታጀብ የሐረር ራዲዮን ማቢያን በመጠቀም ለሕዝቡና ለሠራዊቱ የተቀናጀ የንቅናቄውን ዓላማና ግብ፣ ሥርነቀል የፖለቲካ ይዘት ያላቸውን ቅስቀሳዎች፣ ወታደራዊ ማርሾች፣ ባህላዊ ፉከራና ቀረርቶዎችን ከመዝናኛ ኘሮግራሞች ጋር ማሰራጨትን የመሳሰሉት ከመሰናዶዎቹ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

ሕዝባዊ ሰልፉ በሐረር ከተማ ብቻ ሳይሆን በሐረር በተደረገ ማግሥት በተመሳሳይ ሁኔታ በድሬዳዋ ከተማም ይከናወን ዘንድ በሁለቱ ከተሞች መካከል በቅንጅት ሕዝቡን ለማስተባበር ታቅዷል። የሐረር ክፍለ ሃገር ፖሊስ ሠራዊት አባላት የሆኑ በርካታ ሃገር ወዳድና ዲሞክራት መኮንኖች በቅንጅቱ ውስጥ ስለነበሩ ሕዝቡን የሚያሰጋና ለአደጋ የሚዳርግ ችግር እንደማይፈጠር ለሕዝቡ ተነግሮታል።

በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት በኩል የሚከናወነውን ጉዳይ በተመለከተ የጄኔራል መኮንኖችን ቡድን በቁጥጥር ስር የሚያውልና እስከ ተፈለገ ጊዜ ድረስ ለእነሱ የሚደረገውን የጥበቃ ተግባር የሚያከናውን፣ አጋጣሚውን በመጠቀም የከተማው ወሮበሎች ሕዝቡን እንዳይዘርፉትና ሰላሙን እንዳያደፈርሱ ከፖሊስ ጋር በቅንጅት የከተማውን

ፀጥታ የሚያስከብር፣ እንደ ባንክና ሆቴል፣ የሕዝብ መኖሪያዎችን ገበያዎችንና ሱቆችን በቋሚነት በተነቃናቂነት የሚያስከብሩ፣ የሠራዊቱ ወገን ተቃዋሚ አንጃ ተፈጥሮ ኃይል የሚጠቀም ቢሆንና ወይም መንግሥት ፀጥታን በማስከበር ሰበብ ከውጪ የሚወረወረውን ኃይል የሚመክት በጠቅላላውም ከሦስት በላይ የታጠቁ ግብረኃይሎች ተዘጋጅተዋል።

ጄነራሎቹ በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ በመሪያቸው በሌ/ጄነራል ወ/ሥላሴ በረካ አማካኝነት ለንጉሡ በቀጥታ በስልክ የሚቀርቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ተዘጋጅተዋል። የእነዚህ ጥያቄዎች ተግባሮች ቅድመ ተከተል በሥራና በሰው ኃይል አመጣጠንና የአመራራቸውን አካል የሚተነትን የጊዜ ሰንጠረዥ ከአፈፃፀማቸው ስልትና ቴክኒክ ጋር ለየአመራር አካላቱ ታድሏል።

በጠቅላላው ማን፣ መቼ፣ የት፣ ምን እና እንዴት እንደሚሰራ ያውቃል። ጄነራሎቹ በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ በጄነራል ወ/ሥላሴ አማካኝነት በስልክ በቀጥታ የሚቀርቡትን ጉዳዮች ቢቻል በፈቃዳቸው ባይቻል በማስገደድ እንዲያስፈፅሙ ሃላፊነት የተሰጣቸው የበታች ሹሞች የሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋውና የሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው ነበሩ። በአብዮቱ ሂደት የሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋው በሻምበልነት ማዕረግ የፓርቲያችን የፖለቲካ ቢሮ አባል፣ የሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው ደግሞ በሻለቅነት ማዕረግ የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ ተለዋጭ አባል ለመሆን በቅተዋል።

ይሄ ሁሉ ሥራ ሲሰራ በሚያስገርም ሁኔታ ምስጢራችን የተጠበቀ ሆኖ በሐረር የሚደረገውንና የተደረገውን ሁሉ በእያንዳንዱ ሰዓት በተዋረድ ላሉ የጦር ክፍሎች በሙሉ በፈጠርነው የመገናኛ ዘዴ እናስተላልፍላቸውና እነሱም በየበኩላቸውና በየክፍላቸው ስላለው ሁኔታ በዚሁ መልክ በየሰዓቱ ያሳውቁን ነበር።

አንባቢ ሊገምት እንደሚችለው መገናኛችን እንደ ደምሥራችን የሚቆጠር ነበር። ይህንን ተግባር በትጋትና በብቃት ለማከናወን ለንቅናቄው ስኬታማነት የክፍለ ጦሩ የመገናኛ አዛዥ መኮንንና የሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋው አስተዋፆ ታላቅና የማይረሳ ነው።

በጄነራል ወ/ሥላሴ በረካ የሚመራው የጄነራል መኮንኖች ቡድን በወታደራዊ የአየር መጓጓዣ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ድሬዳዋ አውሮፕላን ማረፊያ ከደረሰ በኋላ ወደ ሂሊኮፕተር ተጋብቶ ሐረር ከተማ የገባው ግንቦት 11 ቀን 1966 ዓ.ም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ገደማ እሁድ ቀን ነበር።

ቡድኑ ከሄሊኮፕተር እንደወረደ ያመራው ወደ ክፍለ ጦሩ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ስለነበረ ከክፍለ ጦሩ አዛዥ ጋር ተገናኝቶ ስለ እለቱ የጉብኝት ፕሮግራም ሲነጋገር የአንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ፈጅቷል። የቡድኑ መሪ ሌ/ጄነራል ወ/ሥላሴ በረካ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት በሐረር ዙሪያ ያሉትን የጦር ክፍሎች እየተዘዋወሩ ለመጎብኘት ቢታቀድም ሠራዊቱ የተዘጋጀው እነሱን በቁጥጥር ስር አድርጎ እነሱ ያለመጠራታቸውንና ያለመፈለጋቸውን በማስረዳት በእነሱ አማካኝነት ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩንና የመከላከያ ሚኒስትሩን በአንድነት ይህ ባይቻል ጄነራል ነጋ ተገኝ አሳስብያለሁ ባሉት መሠረት የመከላከያ ሚኒስትሩንና ጠቅላይ ኢታማጆሩን ለማስመጣት ነበረ።

ጄነራል ነጋ የሠራዊቱን እቅድ ስለሚያውቁ በሚሰጡት መልክት እዚያው ቢሯቸው ያለና ልዩ ረዳታቸው የሆነ መኮንን ሁኔታውን ከስብሰባው አዳራሽ ወጣ እያለ በስልክ በየደቂቃው ያስታውቀን ነበር። ይህ መኮንን በድህረ አብዮት በሶቭየት ሕብረት የፖለቲካ ትምህርቱን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በጦር ኃይላችን ውስጥ በወታደራዊ ካድሬነት ባሳየው

ከፍተኛ ንቃትና የሥራ ትጋት የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የአንድ ክፍለ ሃገር ፓርቲ አንደኛ ፀሃፊ ለመሆን የበቃ ጓድ አሳየ ብርሃኑ ይባላል።

ከጠዋቱ አራት ሰዓት ገደማ ክፍለ ጦሩ አዛዥ ጽሕፈት ቤት ጄኔራሎቹ የሚያደርጉትን ውይይት መጨረሳቸው በዚሁ መኮንን ማለትም በመቶ አለቃ አሳየ ብርሃኑ አማካኝነት በስልክ ሲገለጥልን ስድስት ቀላል መትረየስ የጠመዱ ጂፕ ተሽከርካሪዎችን የሚጠቀሙ ሀያ ወታደሮችና የበታች ሹማምንቶች በሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው እየተመሩ ክፍለ ጦሩ መምሪያ ቅጥር ግቢ ሰተት ብለው በመግባት በቅድሚያ ጄነራሎችን ከአዲስ አበባ አጅበው የመጡትን የታጠቁ የምድር ጦር ወታደር ፖሊስ ክፍል ባልደረቦች ትጥቅ ሳያስቡት በቅጽበት ካስፈቱ  በኋላ ጄነራሎቹ ወደ ተቀመጡበት አዳራሽ የሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው ገብቶ ያክብሮት ሰላምታ ካቀረበ በኋላ፣ ኮስተር ባለ ወታደራዊ ሁኔታ "የክፍለ ጦሩ ሠራዊት ተሰብስቦ እናንተ እንድታነጋግሩት ወደሚፈልገው ቦታ እንድወስዳችሁ ስለታዘዝኩ ልወስዳችሁ መጥቻለሁ። ተሽከርካሪዎች ላይ እንድትሳፈሩ በአክብሮት እጠይቃለሁ" በማለት በሦስት ላንድሮቨር ተሽከርካሪዎች አሳፍሮ እሱ ከኋላ በመሆን የእሱ ምክትል ተሽከርካሪዎቹን እየመራ አምጥተው ለተወሰነ ጊዜ እንዲጠበቁበት በተሰናዳው በኔ ጽሕፈት ቤት በማስገባት አስጠበቃቸው።

የሻምበል ባሻ ደመቀ ባንጃው በድህረ አብዮት ሻለቃ የአካልና የመንፈስ ብርቱ ጥንካሬ ያለው፣ በፈጣንነቱ፣ በቀልጣፋነቱ፣ በድፍረቱና በጀግንነቱ ወታደር ሆኖ የተፈጠረ ነው የሚያሰኝና ቢያምኑት የማይከዳ ሰው ነበር።

በቅድመ አብዮት እኔ የማዝዘው የጦር ክፍል ባልደረባ ሆኖ ሲሰራ ለ15 ዓመታት ያህል አውቀዋለሁ። በድህረ አብዮት ለ17 ዓመታት ለደህንነቱ ጠባቂ በመሆን በቅርብ ሲረዳኝ ከመኖሩ በላይ የትግል አጋርና ጓድ ያልኳቸው ለስደት ሲወረውሩኝም እስከ ኬንያ ድረስ አልተለየኝም።

የእኔን ደህንነት ከመጠበቅ ሌላ ምንም አይነት ነገር ለመወሰን ወይም ለማስወሰን የሚያስችለው ሌላ የሥራ ኃላፊነትና የፖለቲካ ሥልጣን ያልነበረውን ሰው ወያኔ ከደርግ አባላት ለይቶ ብቻውን ጨለማ ቤት ዘግቶ ለዓመታት ካሰቃየው በኋላ ገድሎታል።

ጄነራሎቹ በሠራዊቱ ቁጥጥር ስር መዋላቸውን በክፍለ ጦሩ ሕጋዊ የመገናኛ መስመር በኩል የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት እንዲያውቅ አደረግን። የጄነራሎቹ መታሰር በተሰማ ጥቂት ሰዓት ውስጥ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና በሐረር የልጅ እንዳልካቸው መኮንን ምልምልና ደጋፊዎች ባደረጉት የስልክ ግንኙነትና እንዲሁም ቅስቀሳ በሐረር የጄነራሎቹን መታሰር ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን የሠራዊቱን ንቅናቄ የሚቃወም አንድ ወጣ አጥባቂ የመኮንኖች አንጃ ቡድን ተፈጥሮ ሠራዊቱን የመከፋፈልና የሐረር ከተማን ነዋሪ ሕዝብም የሚያሳስቱ ጽሁፎችን መበተን ጀመረ። ለሃገር ለውጥ የቆሙና የሠራዊቱንም ንቅናቄ የሚደግፉት ብዙሃን መኮንኖችም "በሠራዊቱ ስም እንዲህ ያለ እርምጃ ሲወሰድ እኛ እንዴት አላወቅንም?" "ለእኛ እንዴት ምስጢር ሊሆን ቻለ?" ወዘተ በማለት ከመቆጣታቸው ባሻገር አመጹ።

እንዴት በበታች ሹማምንቶች እንዲመራ ተደረገ በሚል ግንፍል ስሜትና በንቃትም ጉድለት ከወጣ አጥባቂው አንጃ ጋር የመወገንና አደገኛ ሁኔታ የመፍጠር አዝማሚያ በማሳየታቸው ለአመጹ ስኬታማነት ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ሕዝብ ሰላም፣ ለሠራዊቱ ደህንነትና አንድነት ሲባል ኮሚቴው ለአጭር ጊዜ በሐረር ከተማ ዙሪያ ያሉ የጦር መኮንኖች ሁሉ በቁጥጥር ስር እንዲሉ ወሰነ።

በውሳኔውም መሠረት ለዚሁ ተግባር ተሰናድቶ ከነበረው መቺ ግብረ ኃይል የተከፈለ ኃይል ተሰማርቶ መኮንኖቹን በተገኙበት ቦታ ማለትም በሥራ ቦታ፣ በመኖሪያ ቤታቸው፣ መዝናኛ ስፍራዎችና ከንዳናም እያደነ በመሰብሰብ የክፍለ ጦር ኦርኬስትራ አባላት ዳንስና ውዝዋዜ በሚለማመዱበት መለስተኛ አዳራሽ ውስጥ በክብር እንዲጠበቁ በመደረጉ ሴራውን ማክሸፍ ተቻለ። ብዙሃኑ መኮንኖች ከማስጠበቅና ከመቆጣጠር ጋር በነሱም ፍላጎት መሠረት እንደ አልባሳት፣ መኝታ፣ ምግብና ውሃ የመሳሰሉትን በማቅረብ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ሁለገብ ግብረኃይል ተመድቦ በሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ እንዲመራ ተደረገ።

የሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ በሠራዊቱ ውስጥ አንፃራዊ ንቃት የነበረውና አስተዋይ የበታች ሹም ነበር። በአብዮቱ ፍንዳታ በአዲስ አበባ የጦርኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ሲቋቋም ሦስተኛ እግረኛ ክፍለጦርን ከወከሉት አንዱ የነበረና በድህረ አብዮት በንቃቱ፣ በሥራ ትጋቱና በታጋይነቱ የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የአንድ ክፍለ ሃገር አስተዳደር ፓርቲ ኮሚቴ አንደኛ ጸሃፊ ሊሆን የበቃ ጓድ ነው።

በጥቂት ወግ አጥባቂ መኮንኖች ቅስቀሳ በመገንፈል ተነሳስተው ከበታች ሹማምንቱ ጋር ከመጋጨታቸው በላይ ሠራዊቱን ለመከፋፈልና ብሎም ደም ለማፋሰስ በመሞከራቸው ምክንያት ያለ እቅድና ያለ ፍላጎት ኮሚቴው መኮንኖችን ማሰሩ በሁላችንም ላይ የመንፈስ ጉዳት ያደረሰ ብቻ ሳይሆን ለአጭር ጊዜም ቢሆን ከንቅናቄው ፍፃሜም በኋላ በመኮንኖች መካከል ስር የሰደደ ጥላቻና መከፋፈልን ሊፈጥር ችሏል።

በጄነራል ወ/ሥላሴ ከተመራው የጄነራል መኮንኖች ቡድን ጀምሮ ከእቅድ ውጪ በአስገዳጅ ሁኔታ የክፍለ ጦሩን መኮንኖች በቁጥጥር ስር እስከ ማዋል ድረስ የተከናወነው ተግባር ከቀኑ በአስር ሰዓት ገደማ ስለተጠናቀቀ ለኦፕሬሽኑ አፈፃፀም የተሰናዳውን ጠቅላላ እቅድና እንዲሁም የጽሑፍ መመሪያ በበነጋታውም ከሚከናወነው ሥራ ጋር ለበታች ሹማምንቱ በማስረከብ የኮሚቴው አባልና የአመራር አካል የነበርን መኮንኖች በሙሉ ራሳችንን በማሰር ከታሰሩት ብዙሃን መኮንኖች ጋር ተቀላቀልን።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ የተከናወነው ተግባር ያለአንዳች እንከን በተቀላጠፈ ሁኔታና በእቅዱ መሠረት የሰመረ ቢሆንም ከዚህ በኋላ አንባቢ ሊረዳው እንደሚችለው በመኮንኖች ያልተጠበቀ ድንገተኛ አፍራሽ እንቅስቃሴ ምክንያት መታሰርና ሠራዊቱ አመራር አልባ መሆን በቁጥጥር ስር ያልዋሉት ተቃዋሚ መኮንኖች ሴራ፣ የመደራደሩ ሥራ በተሰጣቸው ሁለት የበታች ሹማምንት ላይ የጄነራሎቹ ክብደት፣ ከልዑካኑ የጄነራል መኮንኖች ቡድን ጋር አብረው የታሰሩት የክፍለ ጦር አዛዥ የአመፁ እድምተኛ ላለመምሰል ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከነጄነራል ወ/ሥላሴ ጋር አብረው የበታች ሹማምቱን በመጫን የሠራዊቱ ጥያቄ ዓላማውን እንዲስት በማድረጋቸው የንቅናቄውም ዓላማ ሊከሽፍ ችሏል።

ከጄነራሎቹ ሌላ ብዙሃኑ በክፍለ ጦሩ መምሪያ ውስጥና በሐረር ዙሪያ ያሉ መኮንኖች በበታች ሹማምንቶች መታሰራቸውን የሰሙ በጅጅጋ፣ በጉርሱም፣ በባብሌና በድሬዳዋ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የአንጃው ወገኖች ወደ አዲስ አበባ እርስ በእርሳቸው ስልክ እየተደዋወሉና በወታደራዊ ራዲዮ እየተገናኙ ወሬውን በጥቂት ሰዓት ውስጥ በሃገር አቀፍ ደረጃ አዛመቱት።

በአዲስ አበባ ከሚገኙት የጦር ኃይሎች ከፍተኛ የአመራር አካሎች ጋር በስልክ እየተማከሩ የበታች ሹማምንቱ የመከላከያ ሚኒስትር ልዑካን የሆኑትን ጄነራል መኮንኖችና የክፍለ ጦሩን መኮንኖች በአስቸኳይ ፈትታችሁ በመልቀቅ ወደ ሕጋዊ አመራር ባትመልሱ በአየር ኃይል እናስደበድባችኋለን፣ አየር ወለድ ሠራዊት እናወርድባችኋለን፣ ድሬዳዋ የሚገኘው ከባድ መድፍ እናስደበድባችኋለን በማለት ማዋከብና ማስፈራራት ጀመሩ።

በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ከላይ እስከ ታች ያሉትን መላውን መኮንኖች በማሰር ሠራዊቱን አመራር አልባ አድርጎ ከመንግሥት ሥርዓትና ቁጥጥር ውጪ ሆኗል የሚል መረጃ የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ስለደረሰው የተፈጠረለት መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም በስሜን ሶማሊያ በኩል መጠኑ በውል ያልታወቀ ታንከኛ፣ ሜካናይዝድና እግረኛ ሰፊ ሠራዊት ድንበራችንን በመጣስ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባት ላይ እንደሚገኝ ከስትራቴጂ የመረጃ ምንጫችን የደረሰን ስለሆነ መኮንኖችን በአስቸኳይ ፈታችሁ ባትለቁ አገራችንን ለጠላት አሳልፋችሁ መስጠታችሁን እወቁ የሚሉና ሌሎችም ይህንን የመሳሰሉ አሸባሪ መልዕክቶች ያለማቋረጥ ስለሚደርሳቸው የበታች ሹማምንቱ በመደናገጣቸው የተፈለጉትን ባለሥልጣኖች ለማስመጣት ተሳናቸው።

ከዚህ በተረፈ ሊያስፈፅሙ የቻሉት ነገር ቢኖር ከጄነራል ነጋ ተገኝ በፊት ለጥቂት ዓመታት የክፍለ ጦሩ አዛዥ የነበሩት ሜ/ጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ በሥልጣናቸው እጅግ የባለጉና ያለአግባብ የበለፀጉ በመሆናቸው ከጦር ኃይሎች ምክትል ኢታማጆር ሹምነታቸው ወርደው ከመሰሎቻቸው ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር እንዲታሰሩ ማድረግ ነበር። የመከላከያ ሚኒስትሩን ሐረር ለማስመጣት ያለመቻል የክፍለ ጦሩ ሠራዊት ንቅናቄ ፍሬ አልባ ሆነ ማለት አልነበረም።

የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት አቋም ምንድነው? ከልዑላን ቤተሰብ ጋር በጋብቻ በተዛመዱት አዛዥ አማካኝነት በቤተ መንግሥቱ ተፅዕኖ ስር ወደቀ ወይ? እያሉ በጥርጣሬ ለሚመለከቱ የጦር ክፍሎች ማንነቱን ከማስታወቅ ባሻገር መላውን የጦር ኃይል በመቀስቀስ ለአብዮቱ ፍንዳታ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ነው ተብሎ በታሰበው መሠረት በኢትዮጵያ ሕዝብ በሰፋት ባይታወቅም ዝርዝር ይዘቱ በጦር ኃይሎች የመገናኛ ድሮቻችን አማካኝነት ለመላው መለዮ ለባሽ ተዳርሷል።

በዚህ ሁኔታ የዕለቱ ጀንበር ትጠልቅና ወደ ምሽቱ ጊዜ እናመራለን። ቀደም ብዬ ለአንባብያን እንደገለፅኩት ቀኑ እሁድ ስለነበር ፀጥታ ለማስከበር ከተሰማሩት ግብረኃይሎች መጠን የላቀ ሠራዊት እለቱን እንደ አንድ ልዩ የፖለቲካ በአል ቀን አድርጎ በመቁጠር በገፍ ወደ ከተማ ተሰማርቶ ያመሸው ሁሉ በመጠጥ ስሜት እየተገፋ ጄነራል መኮንኖቹ ወደ ተጠበቁበት ስፈራ በመሄድ ጄነራሎቹን እኛ እናነጋግራቸዋለን የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ አመራር ላይ ያሉት ሹማምንት ይህንን ማድረግ አይቻልም የሚል መልስ ስለሰጧቸው ከፍተኛ ሁከት ይፈጠራል። ጄነራሎቹ በተጠበቁበት ጽሕፈት ቤት የመስኮት መስታዋት አሻግረው የሠራዊቱን ብዛትና የተፈጠረውን ሁከት ይመለከቱ ነበር።

ከነሱ ጋር የታሰሩት ጄነራል ነጋ ሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃውን በመጥራት "ሠራዊቱ በመጠጥ ተፅዕኖ በሚያሳየው ሥርዓት አልበኝነት የተሰማቸውን ስጋት አስረድተው ሁኔታው ከእናንተ አቅምና ቁጥጥር በላይ ስለሆነ የኮሚቴው የአመራር አካል የሆኑትን መኮንኖች ጠርታችሁ ይህ ሠራዊት እንዲመለስ ታደርጉ ዘንደ በጥብቅ አሳስባለሁ" በማለት ያዙታል።

የሃምሳ አለቃ ደመቀ የጄነራል ነጋን ሀሳብ ለሥራ ጓደኞቹ ሲያማክራቸው "በጣም ትክክል ተናግረዋል። እንደውም ዘግይተናል። አሁን ሄደን ሻለቃ መንግሥቱን እንጥራ" ብለው በመምጣት ከብዙ መኮንኖች መካከል ጠርተው 'ለጥያቄ ይፈለጋሉ' በማለት ይዘውኝ ይወጡና በተሽከርካሪ ወደ መሥሪያ ቤት አምርተን ወደ ግቢው ስንቃረብ ያስተዋልኩትን ለማመን አልቻልኩም።

በዚያ አደንቋሪ ጩኸትና ሁካታ መካከል እንደምንም ቀድጄ በማለፍ አንድ ከባድ የሠራዊት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ላይ ቆሜ የሠራዊቱን መንጋ ዝም ለማሰኘት ስጮህ ጄነራሎቹ

ይመለከቱኝ ኖሯል። ከሠራዊቱ ጋር ለመደማመጥ ከተቻለ በኋላ በሚገባቸው ቋንቋ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥቼ ወደየመኖሪያ ቤታቸው ለመመለስ ከቻልኩ በኋላ ጄነራሎች ይመለከቱኝ እንደነበር ተረዳሁ።

ከዚህ በኋላ ተመልሼ ወደ ብዙሃኑ መኮንኖች ሄጄ እራሴን ማሰር ግመል እየጎተቱ ለመደበቅ እንደሞሞከር ስለሆነ ወደ መኖርያዬ ሄጄ አረፍኩ።

ጥቂት ካረፍኩ በኋላ የክፍለ ጦሩን ህቡዕ ኮሚቴ የአመራር አካላት ከመኮንኖቹ መካከል አስጠርቼ በዚያው ምሽት በኔ መኖሪያ ቤት ተሰብስበን ስለእለቱ የሥራ ክንዋኔ ግምገማ አደረግን። በግምገማችንም በፕሮግራማችን ውስጥ አብዬን ስፍራ የያዙትን አብዛኛውን ተግባሮች ለማከናወን ችለናል ብለን አመንን። መንግሥትም ሆነ የመከላከያው አመራር አካላት ለጥያቄያችን ተገቢውን መልስ መንፈግ ብቻ ሳይሆን ብዙ ስለተፈታተኑንም ጄነራሎቹን በቁጥጥር ስር ማዋላችን ተገቢና ትልቁ ክንዋኔ ነበር። በአጋጣሚው ሠራዊታችንን ብቻ ሳይሆን የሐረርን ከተማና የክፍለ ሃገሩን ሕዝብ ያነቃነው የቀሰቀስነው መስሎ ታይቶናል።

በእለቱ ለሕዝቡና ለሠራዊቱ በሐረር ራዲዮ የተሰራጩት ፕሮግራሞች ሥርነቀል የፖለቲካ ይዘት ስለነበራቸው ፕሮግራሙን የተከታተሉ ሁሉ እያወደሱ አድናቆታቸውን ገልፀዋል።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የተቀሩት የአገሪቱ የጦር ክፍሎች በአጠቃላይ የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይል፣ አንደኛና ሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ወዘተ የእኛን አቋም በጥርጣሬ ሲመለከቱት የቆዩበትን ችግር በማስወገድ ለመጭው ጊዜ የሚያበረታታ ብቻ ሳይሆን ለአብዮቱ የሚያስተማምን ሁኔታ ተፈጥሯል። በጠበቅነው ዓይነትና መጠን ባይሆንም ንቅናቄው በሃገር አቀፍ ደረጃ የብዙሀን ማስራጫ ሽፋን አግኝቷል። ሠራዊታችን በጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ ላይ በተወሰደው እርምጃ በጣም በመደሰቱ ለወደፊቱም ከእኛ ጋር በፅናት ይቆማል ብሎ ለመገመት ኮሚቴውን አስችሎታል።

በሲቪል ሕብረተሰብ በኩል የታሰበውን በተመለከተ ፀረ-መንግሥቱን የሰላማዊ ሰልፍ ጊዜ ከሳምንት በኋላ እሁድ በአንድ ልቦናና በተጠናከረ ሁኔታ ይከናወናል ብለን አምነናል። ከዚህ ሁሉ በላይ ፕሮግራሙ ያለአንዳች ጉዳትና ደም ጠብታ በሰላም መከናወኑ ታላቅ ድል መሆኑን የኮሚቴው አባላት በሙሉ በአንድ ድምፅና በሕብረት የገለፁ ከመሆናቸው በላይ በሰፊው ሠራዊት ውስጥም ተንጸባርቋል። የሃገር መከላከያ ሚኒስትሩ እራሳቸው የፈለጉ ጄነራል ወ/ሥላሴን የላኩበት ምክንያት ከሶማሊያዎች ጋር ስንዋጋ አዛዣችን የነበሩ መሆናቸው ጦሩንና አገሩን ያውቃሉ ተብሎ ነው።

ጦሩንና አገሩን ከማወቅ ሌላ እንደ ጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ ጥጋብና እብሪት የወጠራቸውና ሙስና ያጠቃቸው ሳይሆኑ ንፁህ፣ ትሁትና ርህሩህ አዛዥ በመሆናቸው ሠራዊቱ ዘንድ ከመከበራቸው በላይ እንደ አባት የሚቆጠሩ ስለነበሩ ከምንም የተሻለ ጦሩን ሊያግባቡ ይችላሉ ተብለው እንደተላኩ ስለምናውቅ ሁኔታው አስገድዶን እንጂ ጄነራል ወ/ሥላሴን ማስቀየም ፍላጎታችን አልነበረም።

በድህረ አብዮት አብዛኛው የአገሪቱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች በሕዝብና በሠራዊት እየተወነጀሉ ሲታሰሩ ጄነራል ወ/ሥላሴ በጣም ጥቂት ከሆኑ መስሎቻቸው ጋር ያላሰርናቸው በዚሁ መልካም ምግባራቸው ነው። ስለሆነም በዚያ ምሽት በኔ ቤት ተሰብስቦ የነበረው ህቡዕ ኮሚቴ በመጨረሻ የደረሰበት ውሳኔ ያሰርናቸውን ጄነራሎችና የክፍለ ጦሩን መኮንኖች በነጋታው ፈተን መልቀቅ ነበር።

ከዚህ በኋላ የሐረርና የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎችና የአካባቢው ሕዝብ ለሚያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ድምቀትና የይዘትም ታላቅነት ልዩ ልዩ የቴክኒክ የቁሳቁስና የደህንነት ጥበቃ ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር መለዮ ለባሹ ከሕዝቡ ጋር በቁርጠኝነት የቆመ መሆኑን ለማስረዳት በሚያስችሉ ዝግጅቶች ላይ ነበር ያተኮርነው።

የሕዝባዊው ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በሰጠው አመራርና ባወጣው ፕሮግራም መሠረት በሳምንቱ እሁድ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ጀምሮ የሐረር ከተማና የአካባቢው ሕዝብ በገፍ በመውጣት የከተማዋ የእግር ኳስ ሜዳ ግቢና ውጭው እስኪጨናነቅ ድረስ ተሰብስበው የሕዝባዊ ሰልፍ ምክንያት፣ የሰልፉ ስርዓታዊ ፕሮግራም የያዙና ሌሎችንም ጉዳዮች ያካተቱ ጽሁፎች በወጣቶች ለሕዝቡ ታደሉ።

ለሕዝቡ የታደሉትና የተበተኑት ጽሁፎች ለሕዝባዊው ሠልፍ ዋና ምክንያት ያደረጉት በወሎና በትግራይ በተደበቀው ረሀብ ያለቁትን ወገኖቻችንን ለማሰብ ሆኖ ሌሎችንም ጉዳዮች እንዲያካትት ሆኗል። ከተካተቱት ጥቂቶቹ የምንተዳደርበት ጉልታዊው ሥርዓተ-ማህበር ያረጀ፣ ያፈጀና ጊዜው ያለፈበት ስለሆነ ተራማጅ ማህበራዊ ሥርዓት የሚያስፈልገን መሆኑንና የእንዳልካቸው መንግሥት ሕዝቡን ማፈን፣ የመከላከያ ሠራዊቱን ማመስና በተለይም አየር ኃይሉን ማፍረሱን በአስቸኳይ እንዲያቆም የሚሉና የአገሪቱን መለዮ ለባሾች በአንድነት ኢትዮጵያን በማስቀደም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መቆማቸውን የሚያስረዱ ነበሩ።

ጽሑፎች በሚታደሉበት ጊዜ የሕዝባዊው ሠልፍ አካል የሆኑ የኪነት ባለሞያዎች መዝናኛ የሆኑ ሙዚቃዎች፣ የባህል ሽለላና ቀረርቶዎችን ወጣቶች ቀስቃሽ የሆኑ አብዮታዊ መዝሙሮችን ካሰሙ በኋላ ሕዝቡ ከስታዲየሙ እየወጣ በመዘመር በመሸለልና የተለያዩ ዜማዎችን እያዜመ ለሰልፉ በተመረጡ የከተማው ጎዳናዎች መትመም ሲጀምር፣ የአለማያ ግብርና ኮሌጅ ተማሪዎችና መምህራን በኮሌጁ ትራክተሮችና ተሳቢ ጋሪዎች ተጎትተው በመምጣት ሠልፉን ከኋላ ማጀባቸው ሕዝባዊውን ሠልፍ ታላቅ ድምቀትና ግርማ ሰጥቶት ነበር።

ሠልፈኛው በተመረጡለት የከተማው አደባባዮችና አውራ ጎዳናዎች ሲተም ቆይቶ ስምንት ሰዓት ሲሆን በመጣበት ሁኔታ በሰላም ወደየመኖሪያ ቤቱ ተመለሰ። በአገሪቱ ማዕከላዊ የብዙሀን ማሰራጫ የሠልፉ ታላቅነትና ታሪካዊነት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰፊው ተናኘ። ሠልፉ ከተጠበቀው በላይ የተሳካ ብቻ ሳይሆን በክፍለ አገሩ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅና ታሪካዊ ሠልፍ ነበር።

በሳምንቱ በድሬዳዋ ከተማ ተመሳሳይ ሕዝባዊ ሠልፍ እንዲደረግ በታቀደው መሠረት የሠልፉ ሥርዓት ተጀምሮ በመካሄድ ወደመገባደዱ ሲቃረብ ሠልፈኛው በከተማው አደባባዮችና በተመረጡ አውራ ጎዳናዎች በመትመም እየዘመረ የምድር ባቡሩ መሥሪያ ቤት ሕንፃ ፊትለፊት ካለው ሰፊ አደባባይ ላይ እንደደረሰ ማንነታቸው ያልታወቀ ፀረ-ሕዝቦች የምድር ባቡሩን የነዳጅ ማከማቻ ጋን በእሳት ሊያቀጣጥሉ ሲሞክሩ ታዩ በማለት ፖሊሶች በሰልፈኛው ላይ ተኩስ ከፈቱ። በተተኮሰው ተኩስ ታላቅ ሕዝባዊ ትርምስ መፈጠሩና ሰልፉ መበተን ብቻ ሳይሆን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ እናቶች፣ ሽማግሌዎችና ሕፃናት ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደረሰ።

ከተኩሱ ብዛት የተነሳ በደረሰው መደናገጥ ሕይወቱን ለማዳን ሕዝቡ ሲሮጥ በተለይ የእህቶቻችን የእግር ጫማና የእጃቸው ቦርሳ በአደባባዩና በየጎዳናው ላይ በብዛት ወድቆ ይታይ ነበር። ይህንን የፈፀሙት ሰዎች ማንነት በውል ባይታወቅም በመንግሥት ትዕዛዝ

የተከናወነ ሻጥር ለመሆኑ ግን አጠራጣሪ አልነበረም። ሆኖም የሕዝቡን የከረረ ጥላቻ ከማትረፍ በስተቀረ መንግሥት ያተረፈው ጥቅም አልነበረም። የድሬዳዋና የአካባቢው ሕዝብ ሰልፍ በተካሄደበት ማግስት ግንቦት 26 ቀን የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝ ምክንያቱ ሳይገለጽላቸው "አዲስ አበባ መከላከያ ሚኒስትሩ ዘንድ ለአስቸኳይ ጉዳይ ስለምትፈለግ ዛሬውኑ እንድትመጣ" የሚል ትዕዛዝ ስለደረሳቸው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ። በአስቸኳይ የተጠሩበት ምክንያት ካለመታወቁም በላይ ከሄዱም በኋላ ከተገመተው ጊዜ በላይ ቆይተው አብሯቸው ያለው ልዩ ረዳታቸው የመቶ አለቃ አሳየ ብርሃኑ ለእኔ ስልክ ደውሎ ከዚህ የሚከተለውን ነገረኝ።

"ጄነራል ነጋ ለእርስዎ ከዚህ የሚከተለውን እንድነግርዎ አዘውኛል" ካለ በኋላ መልዕክቱም "ከጥቂት ወጣት፣ መኮንኖች ጋር ሆኖ የክፍለ ጦሩን የበታች ሹማምንትና ተራ ወታደሮችን በማሳደም እነጄነራል ወ/ሥላሴን ያሳሰረውና ከዚያም በኋላ ክፍለ ጦሩን የሚበጠብጠው ነጋ ተገኝ ነው ተብዬ በመወንጀል ከሠራዊቱ ተነጥዬ የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ እንድሆን ተደርጓል።

ለጃንሆይም ይኸው ስለተነገራቸው እውነት ነው ብለው ያመኑ ይመስላል። እኔ ጥርሴን የነቀልኩት በሠራዊቱ ውስጥ ነው። ሙያዬ ውትድርና ነው፡ ከዚህ የተለየ የሥራ ልምድ የለኝም። እኔን ከእናንተ ለመለየትና ብሎም ነጣጥሎ ለመምታት አንድ መሰናዶ ያለ ይመስለኛል።

ይህንን ለማክሸፍ በእናንተ በኩል የሚደረግ ነገር ካለ ጉዳዩ ከመጠንዛቱ በፊት ጊዜው አሁን ነው ብለህ ንገረው ተብያለሁ። ጄነራል ነጋ እንደሚሉት ከሠራዊቱ ወጥተው ወደ ሲቪል አስተዳደር የተዛወሩበት ምክንያት አንድም ሠራዊቱን አሳድመዋል ያለበለዚያም አድመኞቹን ሊቆጣጠሩ አልቻሉም ተብለው እንደ ተወነጀሉ እኔ ብቻ ሳልሆን ኮሚቴያችንም አልተጠራጠረም።

የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው በሐረር የቆዩት በጣም ለአጭር ጊዜ በመሆኑ ሠራዊቱ ባያውቃቸውም ቅን፣ ግልጽና ትሁት ሰው ስለነበሩ በቅርብ የምናውቃቸው ሰዎች ጥላቻ የለንም።

በፖለቲካ ዝንባሌያችን የማንጣጣም ከመሆናችን ሌላ ከንጉሣዊያን ቤተሰብ ጋር ተጋብቶ ራሱን መጣፍንት አድርጎ የሚያስብ ጄነራል በዚህ ወቅት ከሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥነት አይነሳም ብሎ የመንግሥትን ውሳኔ በመቃወም ሠራዊት ለማሳደም ኮሚቴው ለመፈለጉ ችላ ማለቱን ስለተገነዘቡ እዚያው አዲስ አበባ እያሉ ሐረር ላሉ ወዳጆቻቸው እየደወሉ ብሶታቸውን ይገልጹና አንድ አድማ እንዲጠነሰስ ያደርጋሉ።

የመቶ አለቃ አሳየ ብርሃኑ እንደነገረኝ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥነታቸው ተነስተው የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ከተሾሙ በኋላ ወደ ሐረር ሲመለሱ በመንግሥት የተወሰነውን ውሳኔ አንቀበልም እርስዎም ከሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥነትዎ የትም እንዲሄዱ አንፈቅድም በማለት በጣም ጥቂት መኮንኖች የክፍለ ጦሩን ተዋጊ መሀንዲስ ክፍል የሚጠቀም መኖሪያ ቤታቸውን በታጠቁ ወታደሮች እንዲጠበቅ ያደርጋሉ።

ይሄ በመሆኑ ክፍለ ጦሩን የሚያንቀሳቅሰው ህቡዕ ኮሚቴ ችግር ውስጥ ይወድቃል። ኮሚቴው ችግር ላይ የወደቀባቸው ምክንያቶች በርካታ ሲሆኑ፣ አንደኛውና ቀዳሚው ግለሰቡ በመደብና በአቋም በኢትዮጵያ ማህፀን ከተረገዘው ከኢትዮጵያ አብዮት ጋር አብረው የማይሄዱና የማይጣጣሙ መሆናቸው ዋናው ሲሆን፤ ሁለተኛው ሰውዬው በመንግሥት የተበደሉና ከነበሩበት የሥልጣን ደረጃ የተሻሩ ሳይሆን ከአንድ ክፍለ ጦር አዛዥነት የአንድ

ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪነት ከፍያለ በመሆኑ ለአመጽና ለጣልቃ ገብነት እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ሲሆን፤ ሦስተኛው እንኳንስ አንዱ ነባር አዛዥ ተዛውሮ በሚሄድበትና አዲስ አዛዥ በስፍራው ባልተገኘበት ጊዜ ቀርቶ ከዚያም በፊት ሠራዊቱ ከመደበኛ የዕዝ ጥገግ ውጭ በኮሚቴው የሚመራ በመሆኑ ለዚህ ችግር መፍትሔ የሚፈልግ ሌላ ተቋም ያለመኖሩና፤ የመጨረሻው ጄነራል ነጋ ተነኝ የመላው ሠራዊት አዛዥ እንደነበሩ ሲታወቅ ጥቂት ሰዎች ተነስተው በሠራዊቱ ስም ህገወጥ ተግባር ሲያከናውኑና ሠራዊቱን ሲከፋፍሉ ዝም ብሎ ማስተዋል ያለመቻሉ ነበር።

በፖለቲካ ዓላማና ትግል መመራት ያለብን በስትራቴጂያዊ መርሆ እንጂ በይሉኝታ፣ በጊዜያዊ ጥቅም ወይም ችግር ላይ በመመስረት የሚሰጥ ውሳኔ ሃገርን ስለማያስቀድም ኮሚቴያችን በዚህ ጉዳይ ላይ መክሮ የወሰደው አቋም ያናሳዎቹን የጄነራል ነጋ ደጋፊ የሆኑ አማጽያንን አቋም ማስለወጥ ነበር።

'እናንተ ማንን ወክላችሁ፣ ማንንስ ሆናችሁ ነው ለክፍለ ጦሩ ሠራዊት አዛዥ መራጭና የመንግሥቱን ውሳኔ ተቃዋሚ የሆናችሁት?' 'በክፍለ ጦር ሠራዊት ስም ይህንን ለማድረግ አትችሉም' በማለት ድርጊቱን መቃወም ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ከሆነ ለክፍለ ጦሩ ሠራዊት አንድነትና እንዲሁም ስነ-ሥርዓት ሲባል ኃይልን መጠቀም ወደሚል ውሳኔ ደረስን።

እዚህ ውሳኔ ላይ መድረሳችንን የተገነዘቡት የጄነራል ነጋ ደጋፊዎች ከአቋማቸው አፈግፍገው በጦር አስጠብቀውት የነበረውን የጄነራል መኖሪያ ቤት እየጣሉ ወደ ጦር ሰፈራቸው ስለተመለሱ ጄነራሉም ሁኔታውን በማየት ወደ ታዘዙበት አዲስ ሥራቸው ለመሄድ ዝግጅት ጀመሩ።

ኮሚቴው የጄነራል ነጋን የመጨረሻ ውሳኔ በመደገፍና ከክፍለ ጦሩ ሠራዊት መለየታቸው ምክንያት በማድረግ ሠራዊቱን አስተባብሮ በክፍተኛ ግብዣና የሽልማት ስጦታ አሰደስቶ በመሸኘት የቆሰለውን ስሜታቸውን በጥቂቱም ቢሆን እንዲሽር ለማድረግ ሞከሯል። ግንቦት 11 ቀን በሐረር ራዲዮ ጣቢያ ለሕዝብ በተሰራጨት የአቋም መግለጫዎችና ጠቅላላ ፕሮግራሞች አማካኝነት በአዲስ አበባ ሠራዊት ሳይመርጣቸው ሠራዊቱን እንወክላለን በማለት ሠራዊቱን ከሕዝቡ ጋር የሚያቃቅሩት የአሮጌው ሥርዓት እድሜ እንዲራዘም የሚሞክሩ ስለመሆናቸው ተገልጦ ነበር።

ይህ ዜና ጊዜ ሳይወስድ በአዲስ አበባና በአካባቢው ለሚኖሩ መለዮ ለባሾች ስለተዳረሰ ኮሎኔል የዓለምዘውድ ስልክ ደውለው "በአዲስ አበባ ሠራዊቱ ስለሚያከናውነው ተግባር ያላችሁ መረጃ አንድም የተዛባ ነው ወይም የለውጡ ተፃራሪዎች እያሳሳቷችሁ ይመስለኛል። እውነቱን እንዲያስረዳችሁ ብዬ የክፍሌ ባልደረባ የሆነና የሚታመን ሻምበል አቢኑር የሚባለውን መኮንን ወደ እናንተ ስለላኩት እንደምታዳምጡት ተስፋ አደርጋለሁ" አሉ። እኔ በበኩሌ እሳቸው ለተናገሩት አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ መልስ ሳልሰጥ መልካም ነው መኮንኑ ይምጣና የሚያስረዳንን ነገር ለማዳመጥ ዝግጁዎች ነን ብያቸው ተለያየን።

ኮሎኔል የዓለምዘውድን ለብዙ ጊዜ የማውቃቸው ከመሆኔ ሌላ በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ውስጥ የአምስተኛ ኮማንዶ አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በሥራ አግባብ በጣም ተቀራርበን ስለነበረ ለመኮንኑ መልካም ግምትና አክብሮትም ነበረኝ። እንደተባለው ሻምበል አቢኑር ሐረር መጥቶ ከኔም ከሌሎችም መኮንኖች ጋር ተገናኝቷል። ኮሎኔል የዓለምዘውድ በሚፈፀሙት ተግባር አይስማማ ወይም ሐረር ከመጣ በኋላ ይለወጥ አይታወቅም፡ ስለ ተልዕኮው ፋይዳ ያለው ነገር ሳያስረዳን ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር በመንገር ሲዘባርቅ ሰንብቶ ሳይሰናበተን ሹልክ ብሎ ወደ ደብረ ዘይት ተመለሰ። እሱ ከሐረር በተመለሰ

ጥቂት ቀናት ውስጥ ሰኔ 13 ቀን በአየር ኃይልና በአየር ወለድ ሠራዊት መካከል በደብረ ዘይት ከተማ ውስጥ አምባጓሮ ተፈጥሮ በሁለቱም ወገን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ከመድረሱ ሌላ የአንድ ሰው ሕይወት እንዳለፈ ሰማን። 'የአዲስ አበባ ክልል ሠራዊት አስተያየት' ብሎ ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ በላከልን የጽሑፍ ሪፖርት እንደገለጠው፣ "ልጅ እንዳልካቸው ሠራዊቱን በማንኮር ሰላም የሚያገኙ ስለመሰላቸው በኮሎኔል የዓለምዘውድ መሣሪያነት የሚያከናውኑት ፀረ-አብዮት ሴራ ነው" በማለት ነበር።

የሻለቃ ተፈራ ተክለዓብን ምክንያት አድርጌ ለኮሎኔል የዓለምዘውድ ደብረ ዘይት መደወል ወደኛ የላኩት መኮንን ምንም ሊያስረዳን እንዳልቻለ ከገለፅኩላቸው በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸውን መንግሥት ጠጋግናችሁ ለማቆየት የምታደርጉት ጥረት ለእርስዎና ለታሪክዎ የሚበጅ አይመስለኝም። በእኔ አስተያየት የጦር ሜዳ የውሃ ስንቅዎን በቀዳዳ ኮዳ ውስጥ እየሞሉ ይመስለኛልና ቢያስቡበት ይሻላል' ስላቸው "በጣም ትክክል ነው፣ ተሳስቻለሁ" በማለት ስልኩን ዘጉት። ሠራዊቱ ጥርስ ውስጥ እንደገቡ የተረዱ ይመስለኛል። በዚያው ሰሞን ሥራቸውን ትተውና ይመሩት የነበረውን ኮሚቴ አፍርሰው ከከተማው ተሰወሩ የሚል መረጃ ደረሰን።

ከዚህ በኋላ በአብዮቱ ማግሥት ከሕግና ከሕዝብ ሸሽተው የተሸሸጉ ባለሥልጣኖች እጃቸውን እንዲሰጡ በጠየቅንበት ጊዜ እሳቸውም ከተሸሸጉበት ቦታ በሻምበል ብርሃኑ ባይህ በኩል ለእኔ በመፃፍ እጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀው አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ድረስ በመምጣት በወታደር እያሳደኑ ከአሰሯቸው ባለ ስልጣኖች ጋር ሲቀላቀሉ ማየት የሚያሳዝን ነበር።

ሻምበል ብርሃኑ ባይህ የሐረርን የጦር አካዳሚ ሠራዊት በብቸኝነት በመወከል የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ሲቋቋም አባል የሆነና የደርጉ የእቅድ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ የሕግ ኮሚቴና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር በመሆን እየተዘዋወረ አገልግሎት የሰጠና የፓርቲያችን የፖለቲካ ቢሮ አባል ለመሆን የበቃ ጓድ ነው።

ሦስተኛውን የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች አብዮታዊ ንቅናቄ ለማብሰርና ለንቅናቄውም አስተማማኝ የአመራር አካል ለመፍጠር በታቀደው መሠረት ሰኔ 18 ቀን 1966 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው ያሉ የጦር ክፍሎች የጋራ አብዮታዊ አመራር የአዲስ አበባን ራዲዮና የቴሌቭዥን ጣቢያ በቁጥጥር ስር አደረገ። በዚሁ ቀን በወታደራዊ መገናኛ በሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ አማካኝነት የንቅናቄውን የአመራር አካላት በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ ማቋቋም ይቻል ዘንድ ሦስት ኃይሎች ማለትም የምድር ጦር፣ የአየር ኃይልና የባሕር ኃይል እንዲሁም የፖሊስ ሠራዊት፣ በምድር ጦር አመራር ስር ያሉት እግረኛና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች በሙሉ የሚፈለግባቸውን ተወካዮች መጠንና የማዕረግ ደረጃ በመግለፅ በበነጋታው አዲስ አበባ አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ድረስ ይላኩ ዘንድ ጥሪ ቀረበ።

በተደረገው ጥሪ መሠረት የተለያዩ የጦር ክፍሎች ተወካዮቻቸውን ለመምረጥ የተጠቀሙበት ሥርዓትና ዲሞክራሲያዊ ዘይቤ ቀደም ብለው በደረሱበት የጋራ ውሳኔ መሠረት በመሆኑ በጣም ተመሳሳይነት ሲኖረው ዝርዝር ይዘቱን አንባቢ ይረዳ ዘንድ እዚህ ላይ እኔ የምገልፀው የምሥራቅ ኢትዮጵያ ክልል መለዮ ለባሾች የተጠቀሙበትን ሁኔታ፣ ከምርጫው በኋላ በእኔ የተመራው ልዑክ አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ ሰኔ 21 1966 ዓ.ም የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ እንዴት እንደ ተቋቋመ ነው።

ከዚህ በፊት ግን አንባቢ ማወቅ ያለበት ነገር ቢኖር የብሔራዊ ጦርና የወህኒ ቤት ፖሊሶች የአስተባባሪ ኮሚቴው አባል ይሆኑ ዘንድ ተወካዮቻቸውን እንዲልኩ የተወሰነው ኮሚቴው ከተቋቋመ፣ የአመራር አካላት ተመርጠው የሥራ ሃላፊነታቸውን ከተረከቡና በተፈጠረው የተቋም መዋቅር መሠረት የጠቅላላ የሥራ ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ተመክሮበት መሆኑን ነው። ሐረር የካቲት 19 ቀን 1966 ዓ.ም በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በብ/ ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ጥሪ በክፍለ ጦሩ መምሪያ የስብሰባ አዳራሽ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ በክፍለ ጦሩ መምሪያና በአካባቢው ያሉ መኮንኖች በተሰበሰቡበት ከአዲስ አበባ ለተለያዩ የጦር ክፍሎች ጥሪ ሲቀርብ ለእኛም ክፍለ ጦር፣ አካዳሚውና የክፍለ ሃገሩን ፖሊስ ሠራዊት አዛዥ ለዚህ ስብሰባ መጋበዝ ጠቃሚና አስፈላጊም ይመስለናል' በማለት ሀሳብ አቀረብንና ቤቱ ተስማማበት።

በስምምነቱ መሠረት የተጀመረው ውይይት ለአንድ ሰዓት ያህል ጊዜ እንዲዘገይ ተደርጎ የአካዳሚው አዛዥ ብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ እና የሐረር ክፍለ ሃገር ፖሊስ አዛዥ ኮሎኔል ቃለክርስቶስ አባይ ተጋብዘው በመምጣት ስለተቀላቀሉን እነሱ ባሉበት ውይይቱ ተጀመረ።

የክፍለ ጦሩ አዛዥ ብ/ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ፣ ምክትል አዛዡ ብ/ጄኔራል ግርማ ፈለቀና እንዲሁም የአካዳሚው አዛዥ ወደ ሐረር ተዛውረው ከመጡ አንድ ሳምንት ስላልበለጣቸውና የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ በአዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ በቅርቡ የተከታተሉ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ጉዳዮችና ውሳኔዎች በምድር ጦር መምሪያ ውስጥ እና እንዲሁም በብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን ውስጥ ተሳታፊ በመሆናቸው ባላቸው ግንዛቤ መኮንኖችን በማወያየትና ብሎም ወደ ተገቢው ውሳኔ ለማምራት ብቃቱ የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። በክፍለ ጦሩ አዛዥ የውይይት መድረክ ተከፍቶ በአገራችን ከየካቲት ወር ጀምሮ ሲካሄድ የቆየውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ዳሰው በዚህ ታሪካዊ የሕዝብ ንቅናቄ መለዮ ለባሹ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕዝቡ ያልተለየ ብቻ ሳይሆን የመሪነቱን ሚና እተየጫወተ መሆኑን አስረድተው የተደረገው ጥሪ፣ ለጥሪውም የተሰጠው ምክንያትና ጠቅላላ መግለጫ ዱብ እዳ ነገር ሳይሆን ሲጠበቅ የነበረ መሆኑን በመግለፅ መደረኩን ለመኮንኖች ለቀቁ።

ፍፁም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ እያንዳንዱ መኮንን አስተያየቱን ሰጠ። ራሱንም ገለጠ። አንድም መኮንን ጥሪው ለምን ተደረገ? ወይም ደግሞ መሳተፍ የለብንም የሚል አስተያየት ባለመሰንዘሩ በጥሪው መሠረት ተወካዮቻችንን ልከን እንሳተፍ ወይ? ተብሎ ለቤቱ የቀረበው ጥያቄ በሙሉ ድምፅና በአዎንታ ስለተደገፈ የአገሪቱን ምሥራቃዊ ክልል መለዮ ለባሽ ተወካዮች መላክ አለብን ተብሎ ተወሰነ።

ከዚህ የቀጠለው እንሳተፍ ብለን ከወሰንን በተላከልን ኮታና ጥያቄ መሠረት ሠራዊታችንን የሚወክሉ መኮንኖችና ባለ ሌላ ማዕረጎችን በምንመርጥበት የምርጫ ይዘትና ሥርዓት ስብሰባው እንዲወያዩ የክፍለ ጦሩ አዛዥ ጠይቀው በዚህም ረገድ አስፈላጊው ውይይት ከተደረገ በኋላ የምርጫ ሥርዓት ተደነገገ።

ከዚህ በኋላ በተደነገገው የምርጫ ሕግ መሠረት እያንዳንዱ ተወካይ ወደ ጦር ሰፈሩ ተመልሶ ምርጫውን በማከናወን የተወካዮቹን ዝርዝር ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት እንዲያመለክት ስምምነት ተደርጎ የአካዳሚውና የክፍለ ሃገሩ ፖሊስ አዛዦች ተለዩን። የክፍለ ጦር መኮንኖች ወደ ምርጫው ዝርዝር ጉዳይ ስንገባ አወዛጋቢና አስቸጋሪ ጥያቄዎች

ተነስተው ብዙ ስላነጋገሩ ብዙ ጊዜ ከመውሰዳቸውም ባሻገር በቅደሚያ ያልታሰቡ አንዳንድ ችግሮችም ኀልተው ወጡ።

አስቸጋሪ ከሆኑ ጉዳዮች ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ፤ አንደኛ የተሰበሰብነው መኮንኖች ብቻ በመሆናችን ባለሌላ ማዕረግተኞቹ እንዴትና የት ይምረጡ? ሁለተኛ መኮንኖችም ሆንን የበታች ሹማምንት እዚህ ተገኝተን መወያየት የቻልነውና የምንችለው በሐረር ከተማና በዙሪያዋ ያለነው ብቻ ስለሆንን ከእኛ እርቀው በኦጋዴን ክልል ያሉት የጦር ክፍሎች እንዴት ነው በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ተወካዮቻቸውን መርጠው ሊልኩ የሚችሉት በተሰኙ ጥያቄዎች አጭርና ቀጥተኛ መልስ ለማግኘት አለመቻሉ ነበር።

ለመጀመሪያው ጥያቄ በሐረር ከተማና በዙሪያዋ ያሉትን ባለሌላ ማዕረግተኞች በአንድ ቦታ በማሰባሰብ ማስመረጥ ይቻላል ሲባል ቀላል ሆኖ ያልተገኘው በኦጋዴን ያሉትን የጦር ክፍሎች መቼና እንዴት ማስመረጥ ይቻላል ለሚለው ጥያቄ መልስ ነበር።

ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ተብለው በቀረቡት አማራጭ መፍትሄዎች በጣም ስለተለያየንና ድምፅ ስለተበታተነ ሁላችንንም ወደሚያሳምነን ውሳኔ ለማምራት የማይቻል ሆነ። በስብሰባው ላይ ከተገኙት መኮንኖች አብዛኞዎቹ ያቀረቡት ሀሳብ በክፍለ ጦር አመራር ስር ያሉትን ጠቅላላውን እግረኛ ሻለቆችና ብርጌዶች በያላችሁበት ተወካዮቻችሁን በገፅ አስመርጣችሁ ከዚያም በኦጋዴን ክልል ደረጃ አጠቃላችሁና አጣርታችሁ አቅርቡልን ወደሚል ውሳኔ የምናመራ ከሆነ የአዲስ አበባው ጥሪ አልተቀበልንምና ተወካዮቻችን አይገኙም ብሎ በጊዜው መልስ መስጠቱ የሚሻል ይሆናል።

ምክንያቱም 2,000 ኪ/ሜትር ግምባር ስፋትና ወደ 1,000 ኪ/ሜትር ጥልቀት ባለው የጥበቃ ቀጠና የተሰማራውና ቁጥሩ 10,000 የሚሆነው ሠራዊት ሁለት መኮንኖችና ሦስት የበታች ሹማምንትን መርጦ ለመላክ ቢያንስ የሳምንታት ጊዜ ያስፈልገዋል ብለው አስተያየታቸውን ከሰጡት መካከል አንዱ ነበርኩ።

ታዲያ ምን ይበጃል? በምን ዘዴ ተወካዮቻቸውን እንዲመረጡ ማድረግ ይቻላል? በማለት ከክፍለ ጦሩ አዛዥ ለቀረበው ጥያቄ ብዙሃኑ መኮንኖች የሰጠነው መልስ አዲስ አበባ የሰጠንን አጭር የጊዜ ገደብና መላው ሠራዊት ተወካዮችን በገጽ እንዲመርጥ ቢደረግ የሚጠይቀውን ጊዜና የአሰራሩንም አስቸጋሪነት ኦጋዴን ያለው ሠራዊታችን በሚረዳበት መልክ መግለጽና ያለው አንድና ብቸኛ አማራጭ ሐረር ያለነው የጦር ክፍሎች ከአካባቢያችን ከምንጠቁማቸው ግለሰቦች ድምፅ በመስጠቱ ረገድ ኦጋዴን ያለው ሠራዊት እንዲሳተፍ ማድረግ ብቻ መሆኑን አስረድተን መስማማት ተቻለ።

በዚህም መሠረት ቤቱ መላውን የክፍለ ጦሩን ሠራዊት ለመወከል ይመጥናሉ የሚላቸውን አምስት መኮንኖችና ስድስት የበታች ሹማምንት እንዲጠቁምና የተጠቆሙት ግለሰቦች የስም ዝርዝር ለቤቱና እንዲሁም ኦጋዴን ላሉት የጦር ክፍሎች ሁሉ ቀርቦ ድምፅ እንዲሰጥበት ተደረገ።

ከኦጋዴን የጦር ክፍሎች ወዲያው የተላከልን መልስ እንደሚያስረዳው በጥቆማ የስም ዝርዝራቸው የተላከልንን የበታች ሹማምንት ስለማናውቃቸውና በጭፍን ድምፅ መስጠትም አግባብ መስሎ ስላልታዬን በእናንተ በኩል ቢመረጡ የምንቀበል መሆናችንን እየገለጥን መኮንኖቹን በተመለከተ ግን ምርጫችንን በአክብሮት እንገልፃለን የሚል ነበረ።

ከኦጋዴን፤ ከሐረር ከተማና ከአካባቢው ለተጠቋሚዎቹ የተሰጠው ድምፅ ሲሰላ፡ ካለ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም በስተቀር ለአንዱ መኮንንና ለስድስቱ ሹማምንት የተሰጠው

ድምፅ በምርጫው ሕግ መሠረት የሠራዊቱን ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሊሸፍን ስላልቻለ በተደጋጋሚ እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ ሠራዊቱ ድምፁን እንዲሰጥ ተደርጎ ሳይሳካ በመቅረቱ የምርጫው ሂደትና ጠቅላላ ሥራው ተገታ። "የሐረር ጦር አካዳሚ አዛዥ ብ/ጄነራል ተፈሪና ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የሠራዊቱን ከመቶ ስማንያ በላይ የሆነ ድምፅ ያገኙ ስለሆነ ክፍለ ጦሩን ይወክላሉ፣ እኔንም ሊረዱኝ ይችላሉ የሚላቸውን መርጦ እየመራ እንዲወስድ መብት እንስጠውና ከዚህ አጣብቂኝ እንውጣ" ብለው ያቀረቡት ሀሳብ ድምፅ ተሰጥቶበት ከሁለት ሦስተኛ ድምፅ በላይ ድጋፍ ስላገኘ የተቀሩትን ተወካዮች የመምረጡ ሃላፊነት በሙሉ እኔ ላይ እንዲወድቅ ተወሰነ። ያካሄድነው ውይይትና የተጠቀምንበትን የምርጫ ዘይቤ ፍፁም ዲሞክራሲያዊ ነበር ብልም ፍፁም እንከን አልባ ነበር ማለት ግን አይቻልም። ተወካዮች ሲጠቆሙና የአሥመራጭ ኮሚቴ አባላት ሲመረጡ፣ ለተወካዮች ድምፅ ሲሰጥና በመጨረሻም የምርጫው ሃላፊነት እኔ ላይ ሲጣል የአንዳችንም ፈቃደኝነት ተጠይቆ ሳይሆን በዝምታና በትዕዛዝ መልክ ነው የተወሰነ ማለት ይቻላል።

አንድ ሰው ፈቃዱ ሳይጠየቅ እንዲህ ያለ ነገር እንዴት ይጫንበታል የሚል ጥያቄ ባቀርብ በተቃራኒው እንዴት እንዲህ ያለ ጥያቄ ታቀርባለህ ብሎ ቤቱ ጮኸብኝ። ምንም ማድረግ ስላልተቻለኝ ቢያንስ ለእኔ የተሰጠውን ምርጫ ለመላው ሠራዊቱም እስታውቃችሁ የነሱን ይሁንታ ማወቅ እፈልጋለሁ ብዬ ያቀረብኩት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ለሠራዊቱ ሲገለፅ ሠራዊቱም በዚህ መስማማቱን ወዲያው ስለገለፀ፣ ሁለተኛውን ተወካይ መኮንን በተመለከተ ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሃና የሚባለውን መረጥኩ።

የበታች ሹማምንት ተወካዮችን በተመለከተ አንደኛ የሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃውን፣ ሁለተኛ ሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋውንና ሦስተኛ የሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታን በመምረጥ ለቤቱ አቅርቤ መኮንኖች በሙሉ ስለተስማሙ በዚያው ቀን ምሽት በሁለት ላንድሮቨሮች በበነጋታው ሰኔ 20 ቀን 1966 ዓ.ም ማለዳ አዲስ አበባ ገባን።

በኔ የቡድን መሪነት መላውን የምሥራቅ ኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ወክለን፣

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም | የቡድን መሪ / የጦር ኃይሎች ኢንስፔክተር መኮንን |
| 2ኛ/ ሻለቃ ተካ ቱሉ | የሐረርጌ ክፍለ ሃገር ፖሊስ ሠራዊት ተወካይ |
| 3ኛ/ ሻለቃ ገበረየስ ወ/ሃና | የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ተወካይ |
| 4ኛ/ ሻምበል ብርሃኑ ባይህ | የሐረር አካዳሚ ጦር ተወካይ |

በአዲስ አበባ ማረፊያ በመፈለግና እቃችንን በማሳረፍ የሰዓት በፊቱን ጊዜ ወስደን ከሰዓት በኋላ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ የአዲስ አበባና አካባቢው ጦር ተወካዮች ወደ ተሰበሰቡበት ወደ አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ሄድን።

ክፍል ፪

# አብዮታዊት ኢትዮጵያ፡
# ከትግል ወደ ድል፣ ከድል ወደ ትግል
# የኢትዮጵያ አብዮተኞች ጉዞ

# ምዕራፍ አራት

## የአብዮቱ ማግሥት

የአብዮቱ ማግስት ብዬ የሰየምኩት በአዲስ አበባ ከተማ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ከተቋቋመበት ከሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የመጀመሪያውን የጥቂት ሳምንታት አፍላ ግን ወሳኝ ታሪካዊ የሽግግር ጊዜ ነው።

የምሥራቅ ክልል መለዮ ለባሽ ተወካዮች ከአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው ካሉ የጦርና የፖሊስ ተወካዮች ጋር በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ የስብሰባ አዳራሽ ስንቀላቀል ከአዲስ አበባ እርቀው የሚገኙት የአብዛኛው የጦር ክፍል ተወካዮች አዲስ አበባ አልደረሱም ነበር።

የሰሜኑ ክልል መለዮ ለባሾች፣ የአየር ኃይል ሠራዊት፣ የባህር ኃይል ሠራዊት፣ የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ፣ የብሔራዊ ጦርና የወህኒ ቤት ፖሊስ ተወካዮች አልተገኙም ነበር።

ወደ ስብሰባው አዳራሽ ስንገባ ጉባዔውን የሚመራው ሻለቃ አጥናፉ አባተ የአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ተወካይ ቡድን መሪ ነበር። የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክልል መለዮ ለባሽ ተወካዮች ነን በማለት የተወከልንበትን ደብዳቤ ከሰጠን በኋላ እንድንቀመጥ ተጋብዘን በአንድ መደዳ ተጠጋግተን ተቀመጥን።

በሻለቃ አጥናፉ አባተ የሚመራው ጉባዔ አባላት የተቀሩት የአገሪቱ የጦር ክፍሎች ተወካዮች በሙሉ እስኪከቱ ሳይጠብቁ ሥራ በመጀመር የተለያዩ ውሳኔዎችን መስጠትና የተለያዩ ተግባሮችን ማከናወንና ማስፈፀም ጀምረው ነው ያገኘናቸው።

ጉባዔው ይነጋገርበት የነበረው አጀንዳ፣ ያላግባብ በመበልጸግና በሥልጣን መባለግ፣ ከሕዝብ ክስ የቀረበባቸው ባለሥልጣኖች የስም ዝርዝር ቀርቦ ይነበባል፣ አንዳንድ ተወካዮች እየተነሱ የምስክርነት ቃላቸውን ይሰጣሉ።

በውይይቱ መሠረት ወዲያው እዚያው ውሳኔ እየተሰጠ የታጠቁ ወታደሮችን በማሰማራት ባለሥልጣኖቹ እየታደኑ ይታሰራሉ። ስለሚታሰሩት ባለሥልጣኖች እናውቃለን በማለት ጥቆማ በማካሄድና የባለሥልጣኖቹን ታሪክ በመዘርዘር ዋናውን ሚና የሚጫወቱት የክብር ዘበኛው ክፍለ ጦርና የአዲስ አበባ ፖሊስ ሠራዊት ተወካዮች ነበሩ።

የተቀሩት መለዮ ለባሾች የሚጠቆምባቸውን ባለሥልጣኖችም ሆነ ወንጀላቸውን የሚያውቁ አይመስሉም። በጉባዔው አባላት መካከል ይታይ የነበረው ችግር እርስ በርስ ያለመተዋወቅና መፈራራት ብቻ ሳይሆን ያለ መረጋጋትና አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለቶችም ይታዩ ነበር።

የውይይቱ ይዘትና ሂደት፣ አያያዙና የአሰራሩም ዘይቤ በአንድ ሃገርና በዜጎች እድል ላይ ያንን የመሰለ ውሳኔ ለመወሰን ወግና ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የቅርጽም ሆነ የይዘት ድርጅታዊ ባህሪ አልነበረውም።

ይህም በመሆኑና በመደናገራችን እኛ የምሥራቁ ክልል መለዮ ለባሽ ተወካዮች በስብሰባ አዳራሽ ገብተን ከተቀመጥን በኋላ ጉባዔው ለብዙ ሰዓት ሲካሄድ ከማስተዋል በስተቀር ከመሳተፍ መቆጠብን መርጠን ነበር።

የኛ ራሳችንን ማግለልና ዝምታ በሌሎቹ ተወካዮች ዘንድ ተስተውሎ ኖሮ፡ “ምሥራቆች ምነው ዝም አላችሁ? እንደ ታዛቢ ትመለከቱናላችሁ፣ ለምንድነው ከውይይቱ የማትሳተፉት? ለምንስ ሀሳብ አትሰጡንም?” የሚል ጥያቄ ከቤቱ በተከታታይ ስለተወረወረ በእኛም በኩል መልስ መስጠት አስፈላጊ ስለሆነም ተነሳሁና ወደ ቀረበልን ጥያቄ መልስ ሳመራ፣ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ የምንገኝበትን ታላቅ፣ ታሪካዊ የሽግግር ወቅት ሰፋ ባለ ሁኔታ በማብራራት በዚህ የታሪክ አጋጣሚ በዚያ አዳራሽ የተሰበሰብን መለዮ ለባሾች ታሪክና ሕዝብ የጣለብንን እጅግ ግዙፍ የሆነ ተልዕኮና ከባድ ብሔራዊ ሃላፊነት ለማስገንዘብ ሞከርኩ።

ለጉባዔው አባላት ሌሎች የጦር ክፍል ተወካዮች ከመምጣታቸው በፊት ሥራ ላለመፍታት ኃላፊነትና ቀደምትነትን ወስደው ሲያከናውኑ ስላስተዋልነው በራሴና በምወክለው ልዑካን ስም ካመሰገንኩ በኋላ የውይይታቸው ይዘትና ሂደት፣ የውሳኔው አሰጣጥ፣ የሚታየው ሥነ-ሥርዓትና ወታደራዊ ግብረገብነት ከሚወያዩበት አጀንዳ ጀምሮ ከተልዕኳችን ጋር የሚመጥን ሆኖ እንዳላገኘነው ልንሰውራችሁ አንፈልግም በሚል ግልጽነት ያስተዋልነው ጉድለት ብቻ ሳይሆን በቁጥራቸው ከኛ የሚልቁት ተወካዮች ባልተገኙበት ስለሚሰጠው ውሳኔ ተገቢነትና ሕጋዊነትም በኛ በኩል ችግር እንዳለ ገልጬ ሆኖም እነዚህን ያነሳሁት የማይታለፉ እንከኖች በመሆናቸው እንጂ ለኛ ከተሳትፎ መቆጠብ ምክያንት አለመሆናቸውን አስረድቼ፣ የኛ ከተሳትፎ መቆጠብ ምክንያት መሰረታዊ ጉዳይ የዓላማ ጥያቄ መሆኑን አስረግጬ ለማስገንዘብ ሞከርኩ።

ንግግሬን በመቀጠል ‘እዚህ የተሰበሰብንበት ምክንያት ምንድነው? ተልዕኳችንስ ምንድነው? በአጠቃላይ ዓላማችን ምንድነው? ከሚል ጥያቄ ተንደርድሬ፣ ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የምንመራበትና የምንከተለው ዓላማ ሊኖረን ይገባል የሚል ፅኑ አቋም አለን’ ስል አስረዳሁ።

“ሰው ማሰር ወይም መሾም ሁሉም ከዓላማ ቅስታ በኋላ የሚደረጉና ከዓላማ መመንጨት ያለባቸው ናቸው። ምንድነው ዓላማችን? የእኛ ጥያቄ የዓላማ ብሎም ዓላማ ወደ ተግባር የሚተረጎምበት የድርጅትና የሥርዓት ጥያቄ ነው።

“ይሄ እዚህ ላለነው ለማንኛችንም ልዑካን ግልፅ እስካልሆነና በዓላማ እስካልተመራን ድረስ ከሁሉ በፊት አናብርም ወይም አንተባበርም። ካላበርንና ካልተባበርን ደግሞ የትም አንደርስም” ብዬ ተቀመጥኩ።

ጉባዔው አስተያየቴንና በሂስ መልክ ያቀረብኩትን ሀሳብ ካዳመጠ በኋላ ሀሳቤን በሙሉ ደግፎ እኔ ያቀረብኳቸውን አንዳንድ የሀሳብ ዘለላዎችን እየመዘዘ ሲወያይ አመሸና ጊዜው በመምሸቱ የእለቱ ጉባዔ አብቅቶ ተበተንን።

በዚያው ዕለት፣ በምሽቱና በበነጋታው ያልመጡት ተወካዮች በተከታታይ አዲስ አበባ ገብተው ስላደሩ ሰኔ 21 ቀን ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት ጉባዔው በምላተ ጉባዔ ሥራውን

ረ። ሻለቃ አጥናፉ አባተ ጉባዔውን ከፍቶ የእለቱ አጀንዳ ትናንት ያልተገባደደው ሚታሰሩ ባለሥልጣኖች ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ውይይቱ እንዲቀጥል ጠየቀ።

እኔ በሰጠሁት አስተያየትና ባቀረብኩት ሂስ ደስተኛ አልነበረም። ከዓላማ አኳያም ከአሰራር ጉድለት አኳያ የተናገርኩት ሁሉ የሱን አመራር በመንቀፍ ሥልጣን ፍለጋ ቻ ያካሄድኩ አድርጎ ነው የተመለከተው።

በዚህ ስሜት ይመስላል ትናንት ጉባዔው ከመሸም በኋላ ጊዜ ወስዶ የተወያየበትን ቀ የውይይት ርዕስ የዘነጋ መስሎ ባለሥልጣኖችን የማሰር አጀንዳ ሲያቀርብ፣ ከጉባዔ ባላቱ "ዛሬ ውይይቱ መቀጠል ያለበት ትናንት የምሥራቁ መለዮ ለባሽ መሪ ቡድን ሻለቃ ንግሥቱ ኃይለማርያም ባቀረቡት ሀሳብ ላይ ነው" የሚል ጥያቄ ቀረበ።

"ሻለቃ መንግሥቱ ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ሳይገኝ ሌላ የምንወያይበት ነገር ሊኖር ይችልም፤ ትናንት የቀረበው ጥያቄ ዓላማችን ምንድነው? ነው። ሻለቃ አጥናፉ ይንገሩን ላማችን ምንድነው?" በማለት ጥያቄውን ወደ ሻለቃ አጥናፉ ሲወረውሩት በፊቱ ላይ በስጭትና የቁጣ ስሜት በግልፅ ይታይበት ነበር።

ሻለቃ አጥናፉ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም ሲል የጉባዔው አባላት አንዱ ሌላውን ያየ መፋጠጥና በጉባዔውም ዝምታ ሰፈነ። ሻለቃ ባሻ ማንመክቶት ወንድማገኝ የተባለ ጉባዔ አባል ተነስቶ "ዓላማችን ምን መሆን እንዳለበት የሚነግረን ከሌለ እርስዎ ጠያቂው ለቃ መንግሥቱ ዓላማችን ምን መሆን እንዳለበት ይንገሩን" ሲል ጠየቀ፤ ተሰብሳቢውም ጭብጨባ ደገፈው።

የሻለቃ አጥናፉን ስሜት እንደጎዳሁ ስለተሰማኝ ተነስቼ "ሁላችሁም እንድትረዱልኝ ፈልገው ነገር ትናንት ያቀረብኩት አስተያየት ለሁላችንም ተልዕኮ ስኬታማነትና አገራችን ለውጥ ይጠቅመናልና ከመጀመሪያው ሥራና ተግባራችን ይመር ብዬ እንጂ ማንንም አስተዋጽኦ ለማጣጣልና ለማኮሰስ ዓላማ የሌለኝ መሆኑን ነው። በተለይ ሻለቃ አጥናፉ በዚህ መንገድ ተመልክተኸው ከሆነና ካሳዘንኩህ ይቅርታ አድርግልኝ" ብዬ ስል እንደገና በቤቱ ዝምታ ሰፍኖ ከአጥናፉ የሚሰጠው መልስ ይጠበቅ ነበር።

ይቅርታ ስለጠየቅኩት የተቆጣ ፊቱ በቅጽበት ተለውጦ በፈገግታ ጸዳል "አንተ በተናገርከው ነገር አላዘንኩም። እንዳልከው የተናገርካቸው ሁሉ ለእኛም ለአገራችንም የሚበጁ በመሆናቸው ተደስቻለሁ። አሁንም ጉባዔው በጠየቅከው መሠረት ምክርህን እንድትለግሰን እኔም እጠይቅሃለሁ" ሲልና ቤቱ ሲያጨበጭብ ውጥረቱ የረገበ ስለመሰለኝ እኔም የተጠየኩትን አስተዋፅዖ ለመዘከር አስቻለኝ።

እዚህ ላይ ለአንባቢ መግለጽ ያለብኝ ከመጠየቄ በፊት አስፈላጊ የመሰለኝን ሁሉ አስተዋፅዖ ለማድረግ ቀደም ብዬ የተዘጋጀሁ መሆኔን ነው። ሊቀመንበር ሻለቃ አጥናፉን "ሰፋ ያለ ዝግጅትና መሰናዶ ስላለን የጉባዔው አባላት በሚገባ ሊመለከቱትና ሊገነዘቡት ይችሉ ንድ የማስረዳበት ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ያስፈልገኛል" ብዬ ጠየኩና ሁሉም ቀረበልኝ።

የመጣልኝን ትልቅ ጥቁር ሰሌዳ ሁሉም ሰው ሊመለከት በሚችልበት አቅጣጫ በአዳራሹ መግቢያና መውጫ በር ትይዩ የተዘጋውን በር ከውስጥ በማስደገፍ አቁሜ በጥቁር ሰሌዳው እራስጌ ዳርቻ በትልቅ ጽሑፍ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የተሰኘውን በኢትዮጵያ እስከ ዛሬም የሚወደደውን ገናናውን አብዮታዊ መፈክር ነበር የጻፍኩት።

መፈክሩን ከጻፍኩ በኋላ "ከዛሬ ጀምሮ የአብዮታችን መፈክር 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለው ነው" በሚል ካስረዳሁ በኋላ ከመፈክሩ ቀጥዬ አስተባባሪው ኮሚቴ ከዘውዱና

ከመስተዳድሩ በላይ ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ሊመራ የሚችልበትን የአቋም መዋቅርና በዚያም ላይ የተመሠረተ የሥራ ክፍፍል፣ አጠርና ጠቅለል ያለ የሥራ መመሪያ መሆን አለባቸው የምላቸውን ሀሳቦች በሰሌዳው ላይ ጻፍኩና ጉባዔው ተወያይቶ እንዲያጸድቀው ስለአሳሰብኩ ውይይት ተጀመረ።

እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ሀሳቡን ከመደገፍ በስተቀር አንዳችም አቃቂር ሳይወጣለት በሁሉም ጉባዔ አባላት ተደግፎ ጸደቀ። ከአቋም መዋቅሩና የሥራ መመሪያ ዝርዝሮች መጽደቅ በኋላ ያቀረብኩት ሀሳብ፣ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና ብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰኘው ስም ከዓላማና ተግባራችን ጋር የሚጣጣም ስላልነበረ የተሻለ ስም እንዲፈለግ ነበረ።

በተለያዩ የስም አማራጮች ላይ ውይይት ተደርጎ የኮሚቴው አባል ሳይሆን የኮሚቴ የማስታወቂያ ጉዳይ ሠራተኛ ሪፖርተር በመሆን የውይይቱን ሂደት ይከታተል የነበረው ጓድ ሻለቃ ናደው ዘካሪያስ ደርግ በመባል እንዲጠራ ያቀረበው ሀሳብ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በደርግ ተስማማን።

ከስም ምርጫ በኋላ ያመራነው ባጸደቅነው መፈክር፣ የተቋም መዋቅር፣ የሥራ ክፍፍልና ሥራ መመሪያ መሠረት ከላይ እስከ ታች በየፉካው የአመራር ማዕከሎችንና አካሎችን መምረጥና ኮሚቴዎችን ማቋቋም ነበር።

ሻለቃ አጥናፉም ራሱ በጠየቀኝ መሠረት የኔ አስተዋፅዖ ከሚያቆምበት ጀምሮ በሊቀመንበርነቱ አመራር መስጠቱን መቀጠል ሲገባው እንደ ጀመርክ ጨርስ በማለት ራሱን ከአመራር ስላገለለና ጉባዔውም ዝም ስላለ ስለ ምርጫ ደንብና ሥርዓት ያለኝን ልምድ በበኩሌ አካፍዬና ሌሎችም ጓዶች አክለውበት በዚያ መመሪያነት አሥመራጭ ኮሚቴ መረጥን።

በምርጫ አሥመራጭ ኮሚቴ አመራር ወደ ምርጫው ሥራ ለመግባት እንደ ተዘጋጀን የሻይ ቡና እረፍት ሆነና ከአዳራሹ ወጣን። የቅርብና የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ የሆነው ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን በእረፍት ላይ ሻይ እየጠጣሁ ሳለ ጠጋ ብሎ 'መላው ጉባዔ አባላት ይህንን ከባድ ኃላፊነት አንተ ላይ ለመጫን ተስማምተዋል። እንግዲህ ፅናቱን ይስጥህ' ብሎኝ ጥሎኝ ሄደ።

በጣም ደነገጥኩ። በእውነት፣ በእውነት ነው የምለው እኔ ለዚህ አልተዘጋጀሁም። አልተመኘሁምም። ወደ አዳራሹ ተመልሰን በመሪነት የሚመረጡ ሰዎች መጠሪያ ወይም የማዕረግ ስም ላይ እንድንነጋገር ምርጫ አስመራጩ ኮሚቴ አሳሰበ፣ ፕሬዝዳንት፣ ሊቀ ጉባዔና ሊቀመንበር የተሰኙ አማራጮችን አቅርቦ ሊቀመንበር በተሰኘው ስም ያለምንም ክርክር ተስማማንና ወደ ምርጫው አመራን።

እኔ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ባገኘሁት እድልና ጊዜ ሁሉ ላገኘሁት ሰው አሳስብ የነበረው ሻለቃ አጥናፉ በመሪነቱ እንዲቀጥል ሲሆን ይህ ባይሆን ደግሞ እሱ ምክትል ሊቀመንበር ካልሆነ እኔ ሊቀመንበርነቱን እንደማልቀበል በማያዳግም ቋንቋ አስረድቻለሁ።

ይህንን አቋም የያዝኩት ከአጥናፉ አስተዋፅዖና አጥናፉን ከመካስ ባሻገር እሱ ከሥልጣኑ ወርዶ በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ከአራተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ጋር ለመሥራት ስለማይቻል አብዮቱንም ለማዳን ስል ያደረኩት ነበር።

ምርጫው የደርጉን ሊቀመንበር በመምረጥ ተጀመረና ለኔ ሊቀመንበርነት ድጋፍ ያልሰጠኝ ሻለቃ አጥናፉ ብቻ ነበር። ለምክትል ሊቀመንበርነት ለአጥናፉ ከራሱ

ስተቀር ድምጽ ያልሰጠው ሰው አልነበረምና እኔን በጣም ደስ ቢለኝም አጥናፉ ግን ደስተኛ አልነበረም። ለቀናቶችም ቢሆን ሊቀመንበር ነበረና በበኩሌ ደስተኛ ባለመሆኑ አልተገረምኩም።

የደርጉ ሊቃነመናብርት ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ዋናው ጸሃፊ ምርጫ ስናመራ የደርጉ ዋና ጸሃፊ ከማንም በፊትና በላይ የሊቃነመናብርቱ ረዳትና ሥራ አቀነባባሪ ማለት ነው። ይህ ሥራ ደግሞ የፖለቲካ ተልዕኮ ብቻ ሳይሆን የሙያና የሥራ ልምድ ስለሚጠይቅ በምርጫው ላይ ብርቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስባለሁ ብዬ ተናገርኩ።

ሻለቃ አጥናፉም እዚህ ላይ ሻለቃ መንግሥቱ ያለውን እኔም በጥብቅ እምንበታለሁ በማለት ሀሳቡን አጠናካሪ ድጋፍ ሰጠ። የአስር አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ የተባለ የጉባዔው አባል ተነስቶ "ሊቃነ መናብርቱ የገለጹትን አይነት ሰው ለመምረጥ መቻላችንን በጣም እጠራጠራለሁ። ለምን እነሱ እራሳቸው ሊቃነ መናብርቱ ዋና ጸሃፊውን እንዲመርጡ አንፈቅድላቸውም" ብሎ ያቀረበው ሀሳብ በአብዛኛው አባላት ስለተደገፈ የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ከኔ ቀጥሎ ሁለተኛ ተወካይ የሆነውን ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሃናን መረጥን።

ከዋናው ፀኃፊ ምርጫ በኋላ በፈጠርነው መዋቅርና የሥራ ክፍፍል መሠረት ለየኮሚቴዎቹ አመራር የሚሰጡ ንዑሳን ሊቃነመናብርትን ከዚህ እንደሚከተለው መረጥን፡-

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን | የሃገር መከላከያ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 2ኛ/ ሻለቃ ተካ ቱሉ | የሃገር ደህንነት ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 3ኛ/ የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ | የሃገር አስተዳደር ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 4ኛ/ ሻምበል ሲሳይ ሀብቴ | የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 5ኛ/ ሻለቃ አሥራት ደስታ | የማስታወቂያ፣ የቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 6ኛ/ ሻምበል ብርሃኑ ባይህ | የእቅድ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 7ኛ/ ሻምበል ሞገስ ወ/ሚካኤል | የኢኮኖሚ፣ መሬት ይዞታና ማህበራዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 8ኛ/ ሻምበል ሚካኤል ገብረንጉሥ | የሕግና የፍትህ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 9ኛ/ የመቶ አለቃ ካሳዬ አራጋው | የእስረኞች ጥበቃና አስተዳደር ኮሚቴ ሊቀመንበር |

በአብዮቱ ሂደት ሥራው እየሰፋ በሄደ መጠን የሰው መጠን ብቻ ሳይሆን የመዋቅርና የኮሚቴዎችም አይነትና መጠን ብዙ ጊዜ ተለዋውጧል።

ከሰኔ 19 ቀን ጀምሮ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ስብሰባ አዳራሽ በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው የሚገኙ የጦር ክፍል ተወካዮች በተሰበሰቡበት ጊዜ የነበረውን ልቅ ሁኔታ በመጠቀም የቤተመንግሥቱ ሰላዮችና የልጅ እንዳልካቸው ምልምሎች ብቻ ሳይሆኑ ማንንም የማይወክሉ ሥራ ፈት ወታደሮች ጭምር ከጎዳና ጎራ እያሉ ወደ ስብሰባ አዳራሽ በመግባት ተወካይ ከሆኑት ጋር የተሰበሰበውን መለዮ ለባሽ ስንቆጥረው 120 ሰው ደርሶ ነበር።

የሕጋዊ ተወካዮችን ትክክለኛ መጠን ከማጣራታችን በፊት በተፈጥሮው እጅግ ችኩል የሆነው የማስታወቂያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሻለቃ አሥራት ደስታ ሰውን ቆጥረን አንድ መቶ ሀያ ነን ስንል የሰማውን አሃዝ ወዲያው ጠልፎ ለሃገር ውስጥና ለውጭ ሃገር ጋዜጠኞች በመስጠቱ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የደርጉ ብዛት አንድ መቶ ሃያ ነው እየተባለ እስከ ዛሬ ይነገራል።

የሻለቃ አሥራት ደስታን ችኩልነት በተመለከተ ሌላም አስቂኝ ለአንባቢ መመረቅ እወዳለሁ። ደርግ በተቋቋመበት ቀን የደርጉ አባላት የእኔን አስተዋፅዖ በጠየቁኝ መሠረት ያሉኝን ሀሳቦች ሳቀርብ የመጀመሪያው የደርጉ የፖለቲካ ወይም የትግል መፈክር "ኢትዮጵያ ትቅደም" እንዲሆን ማሳሰቤ ይታወሳል። ጉባዔው መፈክሩን በይሁንታ እንዳጸደቀ ሻለቃ አሥራት ከስብሰባው አዳራሽ ሹልክ ብሎ በመውጣት የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ጋዜጠኞች በመሰብሰብ "የደርጉ የፖለቲካ ፍልስፍና ኢትዮጵያ ትቅደም ይባላል" በማለቱ እስከ ዛሬ በተራማጅ ምሁራን ዘንድ ሲያስተቸን ይኖራል።

ሻለቃ አሥራት በሰሜን አሜሪካ ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነት ሙያ የተመረቀ፣ ጥሩ የሥነ-ጽሑፍ ችሎታ ያለው ከመሆኑም በላይ ሰርቶ የማይጠግብ ታታሪ ሰው በመሆኑ ችኩልነቱን ለመቀነስ አንዳንዴ እግሩንና እጆቹን እየያዝን በሚያፈቅረው ሥራ ላይ ለማቆየት ተገደድን።

ወደ ተነሳሁበት ርዕስ ልመለስና ደርግ ተቋቁሞ፣ መዋቅርና ሥራ ክፍፍል ተፈጥሮ፣ ለሥራውም መመሪያ አውጥቶ በሰው ኃይል በኩል አመራሩና ምንዝሩ በውል ታውቆ ሥራውን ሲጀምር ቅድሚያ የሰጠው ጉዳይ ሕጋዊዎቹን የደርግ አባላት ትክክለኛ መጠን ማወቅ ነበር።

በዚህም መሠረት የእያንዳንዱ ጦር ክፍል ተወካዮች ከሰኔ 19 ቀን ጀምሮ ወደ አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ሲመጡ ለሕጋዊ ተወካይነታቸው ማስረጃ ይሆን ዘንድ የጦር ክፍላቸው የጻፈላቸውን ደብዳቤዎች አፈላልገን ሲመረመሩ፣ ከተሰበሰቡት መካከል የውክልና ማስረጃ ደብዳቤ ይዘው ያልመጡ ስለተገኙና እነዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስለነበሩ በዚያኑ ዕለት ወደየጦር ክፍሎቻቸው ተመልሰው በመሄድ የውክልና ደብዳቤዎችን እንዲያመጡ አዝዘናቸው ሄዱ።

በሠራዊቱ የተመረጡትና የተወከሉት የጎደላቸውን የጽሑፍ ማስረጃ ይዘው ሲመለሱ ያልተመረጡት በዚያው ስለቀሩ ሕጋዊዎቹን የደርግ አባላት ቁጥር በትክክል ማጣራትና ማወቅ ተቻለ።

የሠራዊቱ ተወካይ የነበሩት የደርግ አባላት ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፦

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም | የደርግ ሊቀመንበር |
| 2ኛ/ ሻለቃ አጥናፉ አባተ | የደርግ ምክትል ሊቀመንበር |
| 3ኛ/ ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሀና | የደርግ ጸሐፊ |
| 4ኛ/ ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን | የደርጉ የሃገር መከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 5ኛ/ ሻለቃ ተካ ቱሉ | የሃገር ደህንነት ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 6ኛ/ የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ | የሃገር አስተዳደር ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 7ኛ/ ሻምበል ሲሳይ ሀብቴ | የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 8ኛ/ ሻለቃ አሥራት ደስታ | የማስታወቂያ፣ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 9ኛ/ ሻምበል ብርሃኑ ባይህ | የእቅድ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 10ኛ/ ሻምበል ሞገስ ወ/ሚካኤል | የኢኮኖሚ፣ መሬት ይዞታና ማህበራዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 11ኛ/ ሻምበል ገብረንጉሥ | የሕግና የፍትህ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 12ኛ/ የመቶ አለቃ ካሳዬ አራጋው | የእስረኞች ጥበቃና አስተዳደር ኮሚቴ ሊቀመንበር |
| 13ኛ/ ሻለቃ አባተ መርሻ | አባል |

14ኛ/ ሻለቃ አበበ በላይነህ አባል
15ኛ/ ሻለቃ ፋንታዬ ይህደን አባል
16ኛ/ ሻለቃ ሀሩይ ኃይለሥላሴ አባል
17ኛ/ ሻለቃ ዘለቀ በየነ አባል
18ኛ/ ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ አባል
19ኛ/ ሻለቃ ፍስሀ ደስታ አባል
20ኛ/ ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ አባል
21ኛ/ ሻለቃ ደበላ ዲንሳ አባል
22ኛ/ ሻለቃ መኩሪያ ኃይሌ አባል
23ኛ/ ሻለቃ ደምሴ ደሬሳ አባል
24ኛ/ ሻለቃ አሰፋ መኮንን አባል
25ኛ/ ሻለቃ ግርማ ሀብተገብረዔል አባል
26ኛ/ ሻለቃ ካሳሁን ታፈሰ አባል
27ኛ/ ሻምበል አዲስ ተድላ አባል
28ኛ/ ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ አባል
29ኛ/ ሻምበል እንዳለ ተሰማ አባል
30ኛ/ ሌ/ኮማንደር የኋላሸት ግርማ አባል
31ኛ/ ሻምበል ነጋሽ ተሰፋጽዮን አባል
32ኛ/ ሻምበል ውብሸት ደሴ አባል
33ኛ/ ሻምበል የማነ ገብረንትሥ አባል
34ኛ/ ሻምበል ኃይሌ መለስ አባል
35ኛ/ ሻምበል ተፈራ ደነቀው አባል
36ኛ/ የመቶ አለቃ መለሰ ማሩ አባል
37ኛ/ የመቶ አለቃ አሸብር አማረ አባል
38ኛ/ የመቶ አለቃ ጥሩነህ ኃይለሥላሴ አባል
39ኛ/ የመቶ አለቃ ተሰማ በላይ አባል
40ኛ/ የመቶ አለቃ አሊ ሙሳ አባል
41ኛ/ የመቶ አለቃ በላይ ቢተው አባል
42ኛ/ የመቶ አለቃ በእውቀቱ ካሳ አባል
43ኛ/ የመቶ አለቃ መላኩ ተፈራ አባል
44ኛ/ የመቶ አለቃ ገበያው ተመስገን አባል
45ኛ/ የመቶ አለቃ ስለሺ በየነ አባል
46ኛ/ የመቶ አለቃ ተስፋዬ ተከሌ አባል
47ኛ/ የመቶ አለቃ ግርማ ፍስሀ አባል
48ኛ/ ሻለቃ ባሻ ማንመከቶት ወንድማገኘ አባል
49ኛ/ ሻለቃ ባሻ ኃይሌ ገበየሁ አባል
50ኛ/ ማ.ቴ.ክ. ደምሴ ካሳዬ አባል
51ኛ/ ማ.ቴ.ክ. ገሰሰ ወ/ኪዳን አባል
52ኛ/ የሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ አባል
53ኛ/ ሻምበል ባሻ ግዛው ወ/ሚካኤል አባል
54ኛ/ ሻምበል ባሻ ታደሰ አደራ አባል
55ኛ/ ሻምበል ባሻ ከበደ አሊ አባል


56ኛ/ ሻምበል ባሻ ደሳለኝ በላይ አባል
57ኛ/ ሻምበል ባሻ ጌታሁን አቦዬ አባል
58ኛ/ የሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው አባል
59ኛ/ ሻምበል ባሻ ጎሹ አለማየሁ አባል
60ኛ/ ሻምበል ባሻ ታምራት ፊዬ አባል
61ኛ/ ሻምበል ባሻ አበራ አጋ አባል
62ኛ/ ሻምበል ባሻ አክሊሉ በላይነህ አባል
63ኛ/ ሻምበል ባሻ ተገኝወርቅ ተስፋ አባል
64ኛ/ ሻምበል ባሻ ገ/ሕይወት ገ/እግዚአብሔር አባል
65ኛ/ ሻምበል ባሻ አብርሃም በላይ አባል
66ኛ/ ሻምበል ባሻ ጌታሁን ተ/ማርያም አባል
67ኛ/ ሻምበል ባሻ ደምሴ አብተው አባል
68ኛ/ ፒ.ኦ ታምራት ፈረደ አባል
69ኛ/ ፒ.ኦ ሚካኤል አስገዶም አባል
70ኛ/ የሃምሳ አለቃ ማሞ እጅጉ አባል
71ኛ/ የሃምሳ አለቃ ተፈራ ወ/መስቀል አባል
72ኛ/ የሃምሳ አለቃ ከበደ ከብረት አባል
73ኛ/ የሃምሳ አለቃ እየለ አድማሱ አባል
74ኛ/ የሃምሳ አለቃ ተፈራ ጂፋር አባል
75ኛ/ የሃምሳ አለቃ ገ/ሕይወት ገ/ፃዲቅ አባል
76ኛ/ የሃምሳ አለቃ በቀለ ደጉ አባል
77ኛ/ የሃምሳ አለቃ ለገሰ አሰፋው አባል
78ኛ/ የሃምሳ አለቃ ይልማ ከበደ አባል
79ኛ/ የሃምሳ አለቃ ፍቅሬ ዘርጋባቸው አባል
80ኛ/ የሃምሳ አለቃ ጌታቸው አረጋ አባል
81ኛ/ የሃምሳ አለቃ ጌታቸው ተቀባ አባል
82ኛ/ የአስር አለቃ ከበደ አቢጋዝ አባል
83ኛ/ የአስር አለቃ ስለሺ መንገሻ አባል
84ኛ/ የአስር አለቃ ግርማ አድማሱ አባል
85ኛ/ የአስር አለቃ ንጉሴ ነጋሳ አባል
86ኛ/ የአስር አለቃ አለማሁ አየለ አባል
87ኛ/ የአስር አለቃ በጋሻው አታላይ አባል
88ኛ/ የአስር አለቃ በጋሻው ጉርሜሳ አባል
89ኛ/ የአስር አለቃ ኃይሉ በላይ አባል
90ኛ/ የአስር አለቃ ግርማ ቡርቃ አባል
91ኛ/ የአስር አለቃ መንግሥቱ ገመቹ አባል
92ኛ/ የአስር አለቃ ንጉሴ ወልዴ አባል
93ኛ/ የአስር አለቃ ዳምጤ ገረመው አባል
94ኛ/ የአስር አለቃ ፀጋዬ ጥሩነህ አባል
95ኛ/ የአስር አለቃ ጉዛህኝ ወርቄ አባል
96ኛ/ የአስር አለቃ አምባቸው ዓለሙ አባል
97ኛ/ የአስር አለቃ ሙሉጌታ አብርሃም አባል

| | |
|---|---|
| 98ኛ/ የአስር አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ | አባል |
| 99ኛ/ የአስር አለቃ አራጌ ፀመር | አባል |
| 100ኛ/ የአስር አለቃ ፍስሀ አንደቶ | አባል |
| 101ኛ/ የአስር አለቃ ግርማ አየለ | አባል |
| 102ኛ/ የአስር አለቃ ደጀኔ ወንድምአገኘሁ | አባል |
| 103ኛ/ ጁ.ኤ.ከማን ዮሀንስ ፋታዊ | አባል |
| 104ኛ/ ተራ ወታደር እሸቱ አለሙ | አባል |
| 105ኛ/ ተራ ወታደር ደምስ አላምረው | አባል |
| 106ኛ/ ተራ ወታደር ገ/ጊዮርጊስ ብርሃኔ | አባል |
| 107ኛ/ ተራ ወታደር አለማየሁ ከልካይ | አባል |

ድርጅታዊ ሥራችንንና ምርጫችንን አከናውነን ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም በቀኑ የአገሪቱ የዜና ማሰራጫ ሰዓት በራዲዮ፣ እንዲሁም በምሽቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ጓዶችንንና የተሰበሰብንበትን ስፍራ የሚያሳይ ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ስዕላዊ መግለጫ ሳይታከል አጠር ባለ አጃቢ መግለጫ የደርጉን ህልውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበሰርን።

ካልተገደድንና አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ደም ሳይፈስ፣ የሰፊው ሕዝብ ባተሌ ሕይወት ሳይቃወስ፣ አብዮቱን በሰላም፣ ፍፁም ጥንቃቄ በተሞላው አሰራር፣ በትዕግሥትና በጥበብ ለመምራት ነበር ያቀድነው።

ይህም እቅድ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ለግጭት ምክንያት ወይም መንስኤ የሚሆኑትን ማናቸውንም አደጋዎች በንቃት በመከታተል፣ መለዮ ለባሹ እርስ በርሱና ከሕዝቡ ጋር ፍጹም ሰላምና አብዮታዊ ሕብረት ከመፍጠር ባሻገር በቤተመንግሥቱና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ዘንድ አላስፈላጊ ያልሆነ ስጋትና ፍርሀት እንዳይፈጠር ሰኔ 22 ቀን 1966 ዓ.ም የሚገልጻ አንድ የደርግ የሰላም ልዑካን ቡድን ወደ ንጉሡ ላክን።



አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ደርግ የተመሠረተበት ሕንፃ

ልዑካኑ ለንጉሡ ይዞ የሄደው የደርጉ የጽሑፍ መልዕክት ዛሬ ይህንን ታሪክ ስጽፍ ላስታውስ የቻልኩትን ያህል አጠቃላይ ይዘቱ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፣

አገራችን በተለያዩ ታሪካዊ ጠላቶችና ተስፋፊዎች ተከባ ባለችበት ጊዜ እንዲሁ ከየካቲት ወር ጀምሮ በታሪኳ ገጥሟት በማያውቅ በሕዝባዊ ነውጥ በመናወጥ ላይ ትገኛለች።

በተለያዩ ቀውሶችና ችግሮች በመታወኳና ሕዝቡም በደረሰበት ረሀብ፣ ሞትና ልዩ ልዩ ስቀቃዎች ብሶቱን ባገኘው ጊዜ፣ ቦታና አጋጣሚ ሁሉ ሲገልጽ በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራው ሚኒስትሮች ምክር ቤት ግርማዊነትዎና የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠብቁበትን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ሰላምና እርጋታ በማጣቱ ጊዜና ፋታ ስጡን ሲል በመስማቱ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦርን ከሕዝብና ከመንግሥት ጋር በማስተባበር ለሰላምና ለመረጋጋት የሚሰራና ኢትዮጵያ ትቅደም የሚል ኮሚቴ ስለቋቋምን ኮሚቴው ከግርማዊነትዎ ምክርና አመራር እየተሰጠውና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ጋር እየተማከረ ይሰራ ዘንድ እንዲፈቀድልን እንለምናለን።

የሚል ነበረ። ንጉሡም ሀሳባችንን ተቀብለው ስለፈቀዱ ደርጉን በማንም ዘንድ ተሰሚና ሕጋዊ ህልውና ያለው አደረግነው።

በዚሁ ዕለት በልጅ እንዳልካቸው የተቋቋሙት ወታደራዊ ኮሚቴና ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን ሕዝቡንና መለዮ ለባሹን በአመፅ የቀሰቀሱና የገፋፉ ናቸው ተብለው በመወንጀል የታሰሩትን ግለሰቦች በመፍታት የመንፈስ ተሐድሶ አድርገንላቸው ወደነበሩበት ሥራቸው መመለስ ነበር።

የታሰሩት ግለሰቦች የመለዮ ለባሹና የተለያዩ የሲቪል ሕብረተሰብ አባላት ስለነበሩ የታሰሩትም በተለያዩ ስፍራዎችና ክልሎች ስለነበር ቅድሚያውን የሰጠነው፤ በምድር ጦር ወታደር ፖሊስ በሚጠበቀው እስር ቤት ለታሰሩት የአየር ኃይል አባላት ነበር። ለጓዶቹ ክብርና የሞራል ተሐድሶ ስንል ነፃ መለቀቃቸውን ያሳወቅናቸው የደርጉ ጉባዔ አዳራሽ ጠርተን ነበር።

የቀረቡልን እስረኞች ቁጥር ከ30 የሚበልጥ አልነበረም። በዚህም አጋጣሚ ነበር በአብዮቱ አጥቢያ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት አየር ኃይሉን እያፈረሰ ነው ተብሎ ይነገር የነበረው በጣም የተጋነነ መሆኑን የተረዳነው።

እነዚህ እስረኞች ከታሰሩበት ምክንያት ሌላ በተጨማሪ ሁልጊዜ እንዳስባቸው ወይም እንዳስታውሳቸው ያደረገኝ፣ እስር ላይ በነበሩበት ጊዜ ታጋይነታቸውና አብዮታዊ ወኔያቸው ሳይቀዘቅዝ አርቀው በማሰብ ለአብዮቱ ያዘጋጁት ታሪካዊና በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ተወዳጅ የሆነው፤ ተነሳ ተራመድ የሚለው አብዮታዊ መዝሙራቸው ነበር።

"ተነሳ ተራመድ ክንድህን አበርታ

ላገር ብልጽግና ለወገን መከታ..."

## ምዕራፍ አምስት

# ደርግና የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት

ለንጉሡ ተልኮ የነበረው የደርጉ የሰላም ልዑካን በዚያው ዕለት ከቀትር በኋላ ለተመሳሳይ ዓላማ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተላከ። ልዑካኑ ይዞት የሄደው የደርግ የጽሑፍ መልዕክት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፣

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፡

ከሁሉ አስቀድመን በዚህ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ በሆነ ወቅት በእርስዎና በምክር ቤትዎ አባላት ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጣለባችሁን አደራና የተሰጣችሁን ከባድ ሃላፊነት በብቃት ትወጡ ዘንድ ያለንን ልባዊ ምኞት በመላው የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ስም በአክብሮት እንገልጻለን።

ሁላችንም ያለነው በአንድ መርከብ ውስጥ ስለሆነ ለለውጡ ጉዞ በአንድነት በሕብረት እንቀዝፋለን የሚል ተስፋ አለን። ሰኔ 21 ቀን በይፋ ባሳወቅነው መሠረት መለዮ ለባሹን እርስ በርሱ፣ ሕዝቡን ከመለዮ ለባሹ፣ ሁሉንም ደግሞ እርስዎ ከሚመሩት መስተዳድር ጋር በማቀራረብና በማስተባበር ሕዝቡ ሰላምን አደፍራሽ የሆነ ሕገ ወጥ ተግባር እንዳይፈጽም መንግሥት በሕዝብ ላይ አስፈላጊ ያልሆነ እርምጃ እንዳይወስድ ወይም ኃይልን እንዳይጠቀም በሰላምና በመረጋጋት ያለአንዳች ደም ኢትዮጵያን ለማስቀደም የተነሳንበትን በጎ ዓላማ አስረድተን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የፈቀዱልን ሲሆን ምክር ቤቱን ለማገልገል የተዘጋጀን መሆናችንን ስንገልጽ የእርስዎና የምክር ቤቱ ትብብርና በጎ ፈቃድ እንደማይለየን ተስፋ እናደርጋለን።

እንዳቀድነው ንጉሡንና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከማስደሰት በላይ የነበራቸውን ስጋትና ውጥረት በእጅጉ አረገብነው።

በሃገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ በጦር ኃይሎችና በምድር ጦር መምሪያ ውስጥ የከፍተኛው አመራር አካላት አባላት የነበሩ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ መኮንኖች አብዛኛዎቹ በመታሰራቸው የአገሪቱ የመከላከያ ተቋማት በጣም በሚያሳስብ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን በመገለፅ በሠራዊቱ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሜ/ጄነራል አማን ሚካኤል እንዶም በዚያው ዕለት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ሆነው በንጉሠ ነገሥቱ እንዲሾሙ በልዑካኑ አማካኝነት ያቀረብነውን ጥያቄ ልጅ እንዳልካቸው ወዲያው ወደ ቤተመንግሥት ከልዑካኑ ጋር በመሄድና ጄነራል አማንን በማስጠራት አሾሚቸው።

'ውሾቹ ካለማቋረጥ ይጮሀሉ ግመሎቹ ግን ከጉዟቸው አልተገቱም' እንደሚለው የነገር ምሳሌ እኛ በተነሳንበት ዓላማና ከዓላማችንም በሚመነጨው እቅዳችን መሠረት እንደሚታወሰው በየሰዓቱና በየዕለቱ የምንወስዳቸው አብዮታዊ ርምጃዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ

ሲቅበጠበጡና 'ምን እየተደረገ ነው?' በማለት አዘውትረው ንጉሡን ሲጠይቁ፣ ንጉሡም በበኩላቸው 'ደርጎቹ ታማኞቻችን ስለሆኑ ከነሱ ተባብረህ ሥራ' ሲሉ ለጥቂት ጊዜ አብረን ተራመድን።

ልጅ እንዳልካቸው "ከሻለቃ መንግሥቱና ከሻለቃ አጥናፉ ጋር ተገናኝተን መነጋገር አለብን" በማለት አበክረው ቢጠይቁም የእኛና የሳቸው ግንኙነት ጊዜያዊና ስልታዊ ስለነበረ የተለያዩ ምክንያቶችን በመስጠት አልተገናኘናቸውም።

የሚኒስትሮች ምክር ቤትና ደርግ በአንድ ሃገር ውስጥ በየፊናቸው የሚሰሯቸውን ሥራዎች የሚያስተባብር ከደርግና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተውጣጣ አንድ የጋራ አገናኝ ኮሚቴ እናቋቁምና እንሥራ በማለት ልጅ እንዳልካቸው ያቀረቡትን ሀሳብ ተቀብለን በአገናኝ ኮሚቴ መሥራት ጀመርን።

አገናኝ ኮሚቴው የደርግን ባህሪና የአሠራር ዘይቤ ሲለውጥ ስላልቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ የዓለም ሕዝብ ኢትዮጵያን የሚመለከተው ሁለት መንግሥታት ለሥልጣን የሚታገሉበት ሥርዓተ አልበኝነት የሰፈነበት ሃገር አድርጎ ስለሆነ በውጪ ግንኙነታችንና በዓለም እውቅናችን ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ነውና የሚኒስትሮች ምክር ቤቱን እኩል በኩል ደርግ አባላት ጋራ በውዘን ሥልጣን በመከፋፈል በአንድ ሥልጣን ስር እንሥራ ሲሉ ልጅ እንዳልካቸው ሀሳብ አቅርበው ነበር።

ይህ በእኛ በኩል ፍፁም የሚታሰብ ስላልነበረና ስላልተቀበልናቸው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ልጅ እንዳልካቸው ደርግን በዘዴ ከፋፍለውና ገዝግዘው ወደ መጣሉ ተንኮል አመሩ ማለት ይቻላል።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ በደርግ በኩል የነበረው አቋም፣ ንጉሡና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የራሳቸውን ቆዳ ለማዳን ሲሉ እኛን ሳያስቸግሩ ታማኞቻችን ብለው የራሳቸውን ሥርዓትና ተከታይ አባላት እየገዘገዙ የኛን ሥራ እንዲያቃልሉልን ቢያንስ የአብዮቱ ማግስት የምንለው የሽግግር ጊዜ ሰላማዊ ይሆን ዘንድና እንዲሁም የሕዝቡን ሥነልቦና በሚገባ እስክናዘጋጅ ንጉሡንም ሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማንሳት አልፈለግንም።

አብዛኛው ነገር በቁጥጥራችን ውስጥ ስለነበረ የሚያሰጋንና የሚያጣድፈን ነገርም አልነበረም። ይህንን ጊዜና ሁኔታ ነው ምዕራባዊያን 'የሚድኸው መፈንቅለ መንግሥት' የሚል ስም የሰጡት።

ደርግ ከሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታዮቹ ቀናቶች፣ ድርጅታዊ ሥራዎችንና ምርጫዎችን ካከናወነና ሥራዎችን ለየኮሚቴው አከፋፍሎ ከሰጠ በኋላ መልስ ማግኘት ያለበት አንድ ታላቅና ወሳኝ ጥያቄ ነበር።

ይህም የደርጉ ዓላማ ምንድነው? ምንስ ይሁን? በማለት በምሥራቅ ክልል መለዮ ለባሾች ልውካን የቀረበው ጥያቄ ነበር። እኔም ሆንኩ አንፃራዊ ንቃት የነበራቸው የደርግ አባላት 'ዓላማ' የምንለው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምን ዓይነት ሥርዓተ ማህበር የሚመራ መንግሥት ያስፈልገዋል? ምን ዓይነት የእድገት አቅጣጫ መከተል አለብን? በምንስ አይነት ንድፈ ሀሳብ ወይም ርዕዮተ ዓለም እንመራ? የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ነበር።

ሁላችንም በቅደም ተከተል በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር የስብሰባ አዳራሽ ከተገናኘንና ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን አንዳንድ ቀዳሚ ድርጅታዊ ሥራዎችን ማከናወን ከጀመርን በኋላ አብዛኛዎቹ መኮንኖች የተገነዘብነው ያንን ጉባዔ ዓላማችን ምንድነው? ወይም የምንመራበት የእድገት አቅጣጫ ምን ይሁን? ብሎ መጠየቅ ሳይሆን ዓላማ ፈጥረን

ዓላማ መስጠት ወይም ማስጨበጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።

አንባቢ ሊገምት እንደሚችለው የደርግ አባላት የምንባለውን ሰዎች የሚያመሳስለን ነገር ቢኖር አንደኛውና ምናልባትም ዋናው መለዮ ለባሽነታችን ወይም ወታደርነታችን፣ እንዲሁም ሌላው ከወታደርነታችን ጋር በጥብቅ የተሳሰረው ከሰላማዊው ሕዝብ በጣም በተለየ መልክ ሥነ-ሥርዓት አክባሪነታችን፣ የጋራ የሆነው ወታደራዊ ባህላችንና ወታደራዊ ሥነ-ልቡና መላበሳችን ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ጋራ በሁለተኛ ደረጃ ሊታይ የሚችለው፣ ሁላችንም ከደሀው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተገኘን፣ ለአገራችንና ለሕዝቧ የተፋጠነ እድገትና መሻሻልን የምንመኝና የኢትዮጵያ ጉልታዊ ገዥ መደብ ከነሥርዓቱ ቢፈርስ ወይም ቢገረሰስ እኛ የሚጎድልብንና የምናጣው አንዳችም ነገር ያለመኖሩ ነው።



ልጅ እንዳልካቸው መኮንን - ጠቅላይ ሚኒስትር

ከዚህ በተረፈ በተለያየ የእድሜ ክልል፣ የማዕረግ ደረጃ፣ ከሻለቃ እስከ ተራ ወታደር፣ የተለያየ የትምህርት ደረጃና እውቀት፣ የሥራ ልምድ ወይም ተሞክሮ፣ የተለያየ ፍላጎትና ምኞት እና የተለያየ ማህበራዊ ንቃት ያለን ሰዎች ነበርን።

የሚያመሳስሉንንና የሚለያዩን መሰረታዊ ጉዳዮች ጎልተው የታዩንና በውልም የተረዳናቸው ከተሰባሰብን በኋላ ራሳችንን ለማቋቋምና ለማደራጀት ባደረግነው የጋራ ጥረቶች ጊዜ አንዱ ሌላውን ለማንበብና እንዲሁም ለመገማመት በተገኘው እድል ነበር።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ካገኘነው መሠረታዊ ግንዛቤ ተነስተን 'ዓላማ' በተሰኘ አንድ ኃይለ ቃል ውስጥ የተካተቱትን፣ ሥነ-መንግሥት፣ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ማህበር፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት አቅጣጫ፣ ንድፈ ሀሳብ ወይም ርዕዮት የተባሉ ረቂቅ ጥያቄዎች አንስቶ ለመወያየት፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ መግባባትን ፈጥረንና የጋራ ግንዛቤ አግኝተን አብዮታዊ ዓላማን ለማንገብ፣ ለመቀየስ ወይም ለመቀስት የሚያስችል መድረክ ባለበት ሁኔታ ላይ ነን ወይ? ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ መልሱ፣ የለም አይደለንም ሆነ።

ስለሆነም ከመቋቋምና ከመደራጀት በኋላ የምንመራበትን ዓላማ ለማንገብና ለሚጠብቀን አብዮታዊ ተግባር ብቁ ሆነን ለመገኘት በቅድሚያ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ርዕሶች ላይ በጣም ብዙ በመወያየት ነገሮችን አላምጠን የትግል ስልትና ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልገናል የሚል እልባት ላይ ደረስን።

ከሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም እስከ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ድረስ በነበረን 70 ቀን ውስጥ እየተማርንና እያስተማርን፣ እየነቃንና እያነቃን በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት

ሂደት የተከናወኑትን አብዮታዊ ፋይዳዎች፣ የማፍረሱንና መልሶ የመገንባቱን ተግባሮች ያቀድንበት ጊዜ ነበር።

መጪው ወይም ተከታይ ተግባራችን እየተጠናና እየታቀደ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወሳኙ አብዮታዊ ትግል ጉዞ ይሰናዳ ዘንድ እንዲማርና እንዲነቃ ሲደረግ በፀሮቹ በአድህሮት ላይ አንበርካኪና ተስፋ አስቆራጭ የሥነ-ልቡና ጦርነትና የመንፈስ ውጊያ ከትጥቅ ፕሮፓጋንዳ ጋር እናካሂድ ነበር።

ከዚህ ጋር በየእለቱ አሮጌውን ሥርዓት መሸርሸራችን ስለቀጠለና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግራ እየተጋባ ስለነበረ ደርግና ልጅ እንዳልካቸው የጀመሩት ጊዜያዊ ትብብር እርቆ እንደማይሄድ ለራሳችን ቀርቶ ለሕዝቡም ግልጽ ቢሆንም እንዳልካቸው እዚያ ሥልጣን ላይ የተቀመጡት በራሳቸው ፍላጎትና ጥረት ሳይሆን የየካቲቱ ፖለቲካ ጎርፍ አምጥቷቸው ከመሆኑ ባሻገር ራሳቸውንና ንጉሡን ለማዳን ሲሉ ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር ብቻ ሳይሆን ከአብዛኛው አገሪቱ መሣፍንትና መኳንንትም ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብተው ስለነበር ከሥልጣን ቢወርዱ በሰላምና በክብር ብቻ ሳይሆን ለደህንነታቸው ጥበቃ እስከማድረግ የምናስብላቸው ሰው ነበሩ።

ነገር ግን እኛ ለእርሳቸው የነበረንን በጎ አመለካከት ያለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን የእኛን አብዮታዊና ፖለቲካዊ ስብዕናና ብስለት ተገቢውን ግምት ለመውሰድ የማይችሉ ሰው ሆነው ተገኙ።

በደርጉ እቅዶች መሠረት በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ በአስቸኳይ እንዲጀመሩ የምንፈልጋቸው የሕግና የፍትህ፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የፖለቲካና የመከላከያ ጉዳዮች የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችንና ጥናቶች በልጅ እንዳልካቸው የሚመራው መስተዳድር ይሰራዋል የሚለው ተስፋችን መላሸቁ ብቻ ሳይሆን መተማመንም እንዳይኖር አደረጉ።

ደርግ ሲቋቋም የነበሩት የልጅ እንዳልካቸው ካቢኔ አባላት ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፡-

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን | ጠቅላይ ሚኒስትር |
| 2ኛ/ ሌ/ጄኔራል አብይ አበበ | የሃገር መከላከያ ሚኒስትር |
| 3ኛ/ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴ | የሃገር ግዛት ሚኒስትር |
| 4ኛ/ ልጅ ሚካኤል እምሩ | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር |
| 5ኛ/ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ | የግቢ ሚኒስትር |
| 6ኛ/ ደጃዝማች ተስፋ ዮሃንስ በርሄ | የማዕድን ሚኒስትር |
| 7ኛ/ አቶ በላቸው አሥራት | የፍርድና ፍትህ ሚኒስትር |
| 8ኛ/ አቶ ተክለኝ ገዳሙ | የመገናኛ ሚኒስትር |
| 9ኛ/ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ | የግብርና ሚኒስትር |
| 10ኛ/ ዶክተር ጀማል አብድር ቃድር | የጤና ጥበቃ ሚኒስትር |
| 11ኛ/ ዶክተር ምናሴ ኃይሌ | የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር |
| 12ኛ/ አቶ አህዱ ሳቡሬ | የማስታወቂያ ሚኒስትር |
| 13ኛ/ አቶ በለጠ ገብረፃዲቅ | የመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስትር |
| 14ኛ/ አቶ ሚልዮን ነቅንቅ | የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስትር |
| 15ኛ/ አቶ ታደሰ ተፈራ | የትምህርት ሚኒስትር |
| 16ኛ/ አቶ ነጋሽ ደስታ | የገንዘብ ሚኒስትር |
| 17ኛ/ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ | የባህል ሚኒስትር |

| | |
|---|---|
| 18ኛ/ አቶ ጌታቸው በቀለ | የሥራ ሚኒስትር |
| 19ኛ/ አቶ ብርሃኑ ዋቀዩ | የፕላንና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር |
| 20ኛ/ ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ | በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ም/ዲሬክተ ናቸው። |

ደርጉ የሚመራበትንና ኢትዮጵያ የምትለወጥበትን ቋሚና ዘላቂ ዓላማ ለማለም ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ዓላማ የተባለው ኃይለ ቃል ያካተታቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ጊዜ ወስደን በስፋትና በጥልቀት ማየትና መወያየት ያስፈልግ ነበር።

ከሰኔ 22 እስከ ሐምሌ መባቻ ድረስ በመንግሥት ዓይነቶች፣ በሥነ መንግሥት ንድፈ ሀሳብ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ የእድገት አቅጣጫ እና በርዕዮተ ዓለም ወዘተ ርዕሶች ላይ በመወያየት ጠለቅ ያለ የጋራ ግንዛቤ ለማጎልበት ተሞከረ።

በዚህ አይነት ዓይን ከፋች የእውቀትና የግንዛቤ ማዳበሪያ በሆነ ውይይት ላይ እኔ በየአጋጣሚው "መሰረታዊ ለውጥ" እያልኩ የማነሳው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ያልገባቸው የደርግ አባላት "መሰረታዊ ለውጥ ማለት ምን ማለት ነው?" ብለው ሲጠይቁ፣ ሻለቃ አሰፋ መኮንን የተባለ የደርግ አባል ከመቀመጫው ተነስቶ "አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሀፍ አጠበች ይባላል። እዚህ ከተገናኘንበት ጊዜ ጀምሮ ሻለቃ መንግሥቱ እየደጋገመ መሰረታዊ ለውጥ የሚለው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ መንግሥት እንገልብጥ ማለቱ ነው። ይህ እብደት ነው። ሕዝቡም አይቀበለንም። የላከንም ሠራዊት ይሄንን ቢሰማ ያጠፋናል። ከመሀከላችን ይህንን ሃሳብ የምትከተሉ ካላችሁ እንድትታረሙ በጥብቅ አሳስባለሁ" አለና ተቀመጠ።

አነጋገሩ ብዙሃኑን የደርግ አባላት ሲያስቅ ጥቂቶቹን ውዥንብር ውስጥ በመከተቱ ውይይታችንን ለተወሰኑ ሰዓቶች አደፍርሶብን ነበር።

ሻለቃ አሰፋ መኮንን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዙፋን ተሟጋች ጠበቃ ሆኖ ከመቆሙ ሌላ ስራችንን በየጊዜው እያወከና ውይይታችንን በማደናቀፍ የምንመራበትን ሥርዓት አላከብር ስላለ ወደመጣበት የጦር ክፍሉ እንዲመለስ ሆነ።

የእውቀትና የግንዛቤ ማዳበሪያ የሆነው የውይይት ፕሮግራም ካበቃ በኋላ የደርጉ ጉባዔ ያመራው ኢትዮጵያ ምን ዓይነት መንግሥት ያስፈልጋታል ወደሚለው ጥያቄ ነበር።

ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ አንስተን በምንወያይበት ጊዜ የአብዮቱ ባለቤትና የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ጥያቄ ላይ ፍላጎቱን በነፍስ ወከፍ ይገልፅልን ዘንድ በአገሪቱ ርእሰ ከተማ በአዲስ አበባ የተለያዩ ክልሎችና በየክፍለአገራቱ ርዕሰ ከተሞች የሀሳብ መስጫ ሳጥኖችን አስቀምጠን ነበር።

ያስቀመጥናቸው ሳጥኖች በየእንዳንዱ ቀን ሕዝቡ ሃሳቡን በሰጠባቸው የታሸጉ ደብዳቤዎች እየተሞሉ የሳጥኖች እጥረት ስለተፈጠረ በርካታ ሳጥኖችን በድጋሚ ማሰራትና በብዛት ማሰራጨት አስፈልጎን ነበር።

የሕዝቡን ፍላጎት ተመልክተን በተግባር ላይ ለማዋል ይቻለን ዘንድ የደብዳቤዎችን አቀራረብ በተመለከተ ሃላፊነቱን የሰጠነው የፖስታና መገናኛ ሚኒስቴር ሠራተኞች የሕዝቡን የሃሳብ መስጫ ደብዳቤዎች ከየሳጥናቸው እያወጡ በማሰባሰብ ለደርጉ ጽህፈት ቤት እንዲያቀርቡና በደርግ አባል በሻለቃ ፋንታዬ ይህደጉ የሚመሩት በጣም ጥቂት የጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች ደብዳቤዎቹ የታሸጉባቸውን ፖስታዎች እየከፈቱ በማንበብ ያዘሉት ምርጫ መሰረት እየለያዩ በፈርጅ በፈርጃቸው እንዲያቀር ቡልን ነበር።

በየቀኑ በሄሊኮፕተር ወደ ጽህፈት ቤታችን የሚመጡ የሃሳብ መስጫ ደብዳቤዎች ቁጥር እኛ ከገመትነው በላይ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ በመሆናቸው በጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች አቅም የሚከናወን ስራ ሆኖ አልተገኘም።

ለተወሰኑ ቀናቶች መላው የደርግ አባላት ፋታ የማይሰጠውን መደበኛ ሥራችንን ትተን በስብሰባ አዳራሻችን ውስጥ እያንዳንዳችን የታሸጉ ፖስታዎችን ስንከፍት የታሸጉበት የቁልቋል ወተት ዓይናችንን እየለበለበ ከማስቸገሩ ሌላ ደብዳቤዎቹን ለማንበብ ያደረግነው ሙከራ በደብዳቤዎቹ መብዛት ምክንያት ሊሳካልን ስላልቻለ፣ ከጥቂት ቀናቶች በኋላ የሕዝቡን የመንግሥት አይነት ምርጫ ለመረዳት ያስቻሉንን ያህል ደብዳቤዎች የደረሱን መሆናቸውን ስላረጋገጥን የሃሳብ መስጫ ሳጥኖችን እንስተናል የሚል መግለጫ ለሕዝቡ በመግለፅ የሃሳብ መስጠቱን ሂደት ማቆም ነበረብን።

ይህንንም አድርገን ከሕዝቡ የደረሱንን ደብዳቤዎች ሁሉ ገልጠን ለማየት የሚሞከር ስላልነበረ ከመጡልን ደብዳቤዎች ውስጥ ከመቶ አምስት እጅ ብቻ የሚሆኑትን በናሙና መልክ ለመጠቀም ተገደድን።

ኢትዮጵያ ምን አይነት መንግሥት ያስፈልጋታል ለሚለው ጥያቄ ከሕዝቡ የቀረቡልን ሃሳቦች እንደየግለሰቡ የመደብ ጀርባ፣ እንደየ ማህበራዊ ንቃቱና በተለይም ስለመንግሥት አይነቶችና ልዩነቶች ካላቸው ግንዛቤ አንፃር የተለያዩ ነበሩ።

እጅግ ከፍተኛውን ቁጥር ከያዙት ሃሳብ መስጫዎች፣ በመንግሥት አይነቶች ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ሳይገቡ በ አጫጭር አገላለጦች ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ነው ያሉን ሃሳቡን ከሰጠው ሕዝብ መሀል በግምት ስልሳ በመቶ ያህል ነበሩ።

ዘላቂ ምርጫቸውን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አድርገው፣ አሁን አገሪቱ ባለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ሕዝባዊ መንግሥት ለመመስረት ስለሚያዳግት ለሽግግሩ የሚያስፈልገን ጊዜያዊ መንግሥት ነው ሲሉ፣ ጊዜያዊ መንግሥቱም እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል የገለፁልን በግምት ሃሳቡን ከሰጠው ሕዝብ መካከል አስር በመቶ ያህል ነበሩ።

ኢትዮጵያ ሌላ መንግሥት ሳያስፈልጋት አሁን ያለው የአንድነታችንና የረጅሙ ታሪካችን ቤዛ የሆነው ዘውዳዊ መን ግሥት እንዲቀጥል ሆኖ፣ ግን፣ የእስከ ዛሬው ፍፁም ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣኑ በሕግ ተገድቦ አገሪቱ ሕዝቡን በሚወክለው የሕዝብ ምክር ቤት ወይም ፓርላማ ስር በሚመራ መስተዳድር ብትመራ ይበጀናል ያሉ በግምት ሃያ በመቶ ያህል ነበሩ።

ዘላቂ ምርጫቸውን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አድርገው ደርግ ዘውዳዊውን መንግሥት አስወግዶ ለሽግግሩ ጊዜ የአብዮቱ ጠባቂ ሆኖ ስቪል ምሁራን ከሚመሩት መስተዳድር ጋር አሁን ባለው ሁኔታ ቢቀጥል ይበጃል ብለው ምክንያ ታቸውን የዘረዘሩ በግምት አስር በመቶ ያህል ነበሩ።

በናሙና መልክ ያሰላነው የሕዝቡ አስተያየት ወይም ምርጫ ይህንን ሲመስል፣ ምርጫና እንዲሁም አስተያየታቸውን እጠር ባለ መልክ በነፍስ ወከፍ ካቀረቡልን ብዙሃን ለየት ባለ ሁኔታ ለዘለቄታው ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት መንግሥት አይነት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ነው ብለው ምርጫቸውን ካስቀመጡ በኋላ፣ ለዘላቂው ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ በቅድሚያ መሰራች ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መኖር አማራጭ የሌለው የታሪክ ግዴታ ነው በማለት ሃሳባቸውን ያቀረቡ ሁለት የምሁራን ቡድኖች ነበሩ።

ሃሳባቸውን በወል ያቀረቡ ቡድኖች ያልኩበት ምክንያት ስምና አድራሻቸውን ሳይገልጡ እኛ አገር ወዳድ ምሁራን ብለው ስለፃፉልን ነው። ምሁራን ያልኩበት ምክንያት እነሱ አገር ወዳድ ምሁራን ስላሉ ብቻ ሳይሆን የሃሳባቸው አቀራረብና ይዘቱ የአገራቸውን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ የገመገሙና በውል የተገነዘቡ በሳል የፖለቲካና የሕግ ባለሙያዎች መሆናቸውን የሚያስረዳ በመሆኑ ነው።

ከሁለቱ ምሁራን ቡድኖች በተለይ አንዱና ሰፋ ያሉ ሃሳቦችን ያቀረበው አቀራረብና የተጠቀመባቸው ቃላቶች ወዘተ በሚኒስትሮች ምክር ቤትና ከምክር ቤቱም ውጪ በወልም በግልም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከአወያየናቸው ሰዎች እንደበት በተደጋጋሚ የሰማናቸው ቃላቶችና ሃሳቦች በመሆናቸው ከሚኒስትሮቻችን የተወጣጣ ቡድን ሃሳብ ነው ብዬ ሳምን ሌላው ቡድን ከዩኒቨርስቲው መምህራን ቡድን የተወጣጣ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት ነበረን።

ከሁለቱ ምሁራን ቡድኖች የቀረቡ ሰፋ ያሉ ሃሳቦች አንድ ላይ ሲጨመቁ ያዘሏቸው ፍሬ ሃሳቦች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ። በቅድሚያ የተለያዩ መንግሥታትን አይነት፤ ተልዕኮና የተመሰረቱበትን ታሪካዊ ሁኔታ፤ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ሁኔታ በወጡና ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት በመመስረት በቅድሚያ ያከናወኑትን የሕገ መንግሥት መሰናዶ ታሪክ ልምድና ተሞክሮ በመዳሰስና ከኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም በቅድሚያ ሊመቻቹ የሚገባቸውን በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች በመግለፅ የሽግግር ጊዜ እንደሚያስፈልግና ይህም ጊዜ ባለቤት ወይም የሽግግር መንግሥት እንደሚያሻው ገልፀዋል።

ይህ የሽግግር መንግሥት ግን በአንዳንድ ቡድኖችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲነገር እንደምንሰማውና ከሚበተኑም በራሪ ጽሁፎች እንደምናነበው፣ ከወታደሩ፣ ከምሁሩ፣ ከሠራተኛው፣ ከነጋዴው ኅብረተሰብ፤ ከገበሬው ወዘተ በተውጣጣ ጥንቅር የሚቋቋም ነው የሚባለው ሃሳብ ደርግ ተመርቶ በቡሀ ላይ ቆረቆር እንዲሉ አገሪቱን የማትወጣው ቀውስ ውስጥ እንደማይከታት ተስፋ እናደርጋለን።

እስከ አሁን እንዳየነው ደርግ የዓላማ ጽናትና የተግባር አንድነት ያለው ፍፁም ያበረ ወይም የተባበረ ተቋም በመሆኑ የማይደሰት አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የለም። ደርግ እራሱን አንድ አድርጎ የአገሪቱን መለዮ ለባሽ አንድ አድርጓል። ደርግ እራሱን አንድ አድርጎ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ አድርጓል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ከእጅ ቢወድቅ እንደሚፈርስ እንቁላል ልንጠነቀቅላት ይገባል ብላችሁ እንደ ለሕዝብ የሰጣችሁትን ማስገንዘቢያና የሚሰማችሁን ስጋት እኛም እንጋራለን። ደርግ እስከ አሁን አብዮቱን በመምራት ያሳየው ብስለትና በተጠቀመ መበት የፖለቲካ ስልት የማይደነቅና የማይኮራ የኢትዮጵያ ሕዝብ የለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያምናችኋል ይደግፋችኋልም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምጦ ለወለደው እፍላ አብዮታዊ ትግል ደህንነትና የሽግግር ጊዜ ከደርግ የተሻለ አመራር ሊሰጥ የሚችልና ተቀባይነት ያለው ተቋም ወይም ኃይል አለ ብለን ለማመን የምንቸገር ከመሆናችን በላይ ሁሉንም ባይሆን የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን አቀንቃኞች ፍላጎትና የዓላማ ቅንነት በጣም ስለምንጠራጠር በጣም እንሰጋለን።

በመስተዳደሩ ማለትም በሚንስትሮች ምክር ቤት ውስጥ ያሉትን አንዳንድ እንቅፋቶች አስወግዳችሁ ለአገራቸው ልባዊ ፍቅርና ለስራቸው ብቃት ባላቸው ምሁራን እንዲጠናከር ማድረግ እስከ አሁን ባሳያችሁን ሁኔታና ብልህ አመራራችሁ እንድትቀጥሉበት እንመክራለን የሚል ነበር።

ለማጠቃለል ኢትዮጵያ ምን አይነት መንግሥት ያስፈልጋታል ብለን ላቀረብነው ጥያቄ የብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መልስ በደፈናው ወይም ያለሌላ አማራጭ ሕዝባዊ መንግሥት የሚል ሲሆን የተቀሩት አናሳ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ቢሆኑ ለሽግግር ጊዜ የሽግግር ጊዜያዊ መንግሥት ያስፈልጋል ከማለት በስተቀር ዘላቂ ፍላጎታቸው ዘላቂ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ነው።

ፍላጎቱን ከገለፀው ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለዩት የአገሪቱ የበላይ ሥልጣን ሕዝቡን የሚወክለው የሕዝቡ ምክር ቤት ወይም ፓርላማው ሆኖ ዘውዳዊው መንግሥት ማለትም ንጉሡ በሕግ ተገድቦና ለሕዝቡ ሥልጣን ተገዝቶ በርዕሰ ብሔርነት እንመራ የሚል ምርጫ ያቀረቡት ከጠቅላላው ሕዝቡ ሃያ በመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው።

ሕዝቡ የሚፈልገውን የመንግሥት አይነት በመምረጥ ላይ በነበረበት ጊዜ የደርግ ጉባዔም በበኩሉ ኢትዮጵያ ምን አይነት መንግሥት ያስፈልጋታል በተባለው ጥያቄ ላይ ጊዜ ወስዶ ሰፊ ውይይት አድርጓል።

ስለመንግሥት አይነት ምርጫ በይፋና ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ሕዝቡን ለማወያየትና ፍላጎቱን ለመረዳት ተብሎ የቀረበ ጥያቄ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ማለት ይቻላል በተለይም ተማሪው፣ ሠራተኛውና ተምሯል የሚባለው የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን ገበሬው ጭምር ከየካቲት ወር ጀምሮ የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ በሰሌዳ እየፃፈ በሰልፍ መውጣትን ካዘወተረ ቆይቷል።

ሕዝባዊ መንግሥት ለሕዝቡና ከሕዝቡ አብራክ ለወጡት የደርግ አባላት እንግዳ ጥያቄ ካለመሆኑ ሌላ ደርግን እንድናቋቁም ሠራዊቱ መርጦ ሲልከን ለአብዛኛዎቻችን የተሰጠን ተልዕኮ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም ስለነበር በደርጉ ሸንጎ ስለ መንግሥት አይነት ምርጫ  የተደረገው ውይይት ሽለቃ አሰፋ መኮንንና ጥቂት መሰሎቹ ካነሷቸው ጥያቄዎች በስተቀር ምንም አይነት ችግር አልገጠመንም። ከጠቀስኳቸው የዙፋን ጠበቆች በስተቀር የመላው የደርግ አባላት ምርጫ ያለሌላ ምርጫ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሚል ብቻ ነበር።

ሕዝቡ ፍላጎቱን የገለጠባቸው ደብዳቤዎች ተጠቃለው ከደረሱን በኋላ ተገልጠው ሲታዩ ሀሳቡን ከሰጠው ሕዝብ ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ምርጫው ሕዝባዊ መንግሥት መሆኑን የደርጉ ጉባዔ ከተረዳ በኋላ የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም ከሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ጋር ተከታታይ የአፈፃፀም መርሐ ግብሮችን አቅዶ ያቀርብ ዘንድ ውሳኔ ሰጠ። የደርጉ ተልዕኮ ፊውዳሉን የገዥ መደብ መንግሥት ተክቶ ሥልጣን ላይ ለመቀመጥ ሳይሆን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከማንኛውም አይነት ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ የሚያደርግ፣ ኢትዮጵያን ከኋላ ቀርነትና ከአሳፋሪ ድህነት አውጥቶ የሚያስቀድም የራሱን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚያስፈልጉትን ድጋፍ፣ ጥበቃና አገልግሎት ሰጥተን ወደ ጦር ሰፈራችን መመለስ ነው የተባለውን ውሳኔ የደርጉ ጉባዔ ያሳለፈው ከሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምርጫ በኋላ በዚያው ቀን ነበር። ይህንን የደርጉን ጉባዔ ውሳኔ በአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን ሰፋ ካለ አጃቢ ታሪካዊና ርዕዩተ ዓለማዊ ሀተታ ጋር ለኢትዮጵያ ሕዝብ መግለፃችን ይታወሳል።

ታሪኳን በሙሉ የጉልተኞችና የፊውዳል ገዥ መደቦች ቁንጮ በሆኑ ነገሥታት ስትገዛ በኖረች አገር ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተከታታይ መርሐ ግብሮችን አጥንተንና አቅደን ለውሳኔ እንድናቀርብ በደርጉ

ጠቅላላ ጉባዔ የታዘዘው የደርጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎች የተሰጠን ስራ ከዚያ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ እየታዘዝን ከአከናወንናቸው ተግባሮች ሁሉ የከበደ ነበር። የአብዮቱ የመጀመሪያ ወሳኝ የሽግግር ወቅት ያልነውን አብዛኛውን ጊዜ የወሰደውም ይሄው ስራ ነበር።

ለተሰጠን ተልዕኮ ስኬታማነት ጠቃሚና በጣም አስፈላጊ ናቸው ብለን በቅድመ አብዮት ለአገር ለውጥ በመፈለጋቸው ብቻ የአፄው መንግሥት የጥቃት ሰለባ በመሆን በብዋያ የተጣሉ ሰዎችን ፈትተን ነፃነታቸውን በመስጠት ማነጋገር ነበረብን።

ለኢትዮጵያ መሰረታዊ ለውጥ ይፈልጋሉ፣ አቅማቸው በፈቀደ መጠንም ታግለዋል የሚባሉ እውቅ ተራማጅ የአገሪቱን ምሁራን እያስፈለግን በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴያችን ላይና በግልም ብዙዎቹን አነጋግረናል።

በውጭ አገር የፖለቲካ ስደተኛ የነበሩ ግለሰቦችንና በተለይም በተማሪው ማህበር ንቅናቄ ውስጥ አመራር ሰጭና ንቁ ተሳታፊ ናቸው የተባሉ ግለሰቦች በጠቅላላ ወደ አገራቸው ተመልሰው በመምጣት በአብዮቱ እንዲሳተፉ በመጋበዝና ለደህንነታቸው ዋስትና በመስጠት እየጠራን በተፈለጉበት ወቅት ጥሪያችንን ተቀብለውና ፈጥነው የመጡትን ተቀብለን በማስተናገድ እንዲሁ በብዛት አነጋግረናል።

የዚህ ብዙ ጊዜ የወሰደብን ብዙ ሰዎችን ማነጋገር ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ለአገራችን በቅድመ አብዮት በህቡዕ ተደራጅተው ለለውጡ ሲታገሉ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳሉ ለማወቅና ከአሉም የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ሁሉ በመስጠት፣ በማጎላበትና በማበረታታት ከህቡዕነት ወጥተው ሕዝቡን እንዲያነቁና ለአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ግምባታ እንዲያደራጁት በማሰብ ነበር።

ከኔ ጀምሮ አንዳንድ የደርግ አባላት በርካታ የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት የሚቃወሙና ከዚያም አልፈው አገር ለመገንጠል የትጥቅ ትግል የጀመሩ ድርጅቶች ስለተፈጠሩ ከነዚህ አንፃር ቀና ፍላጎትና በጎ ዓላማ፣ ብሔራዊ ስሜት ያላቸውና ለአገሪቱ ለውጥ የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ወይንም ቢያንስ የፖለቲካ ድርጅት ጥንስሶች ይኖራሉ የሚል ግምት ስለነበረን ምናልባት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም ይቻል ይሆናል በማለት ያልተፈጠሩ ፓርቲዎችን በመብራት በመፈለግ ብዙ ጊዜ አባክነናል። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ የየብሄረሰቡ ነፃ አውጭ ነን ከሚሉ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች ሌላ አገር አቀፍ አመለካከትና ብሔራዊ ዓላማ ያላቸው ብህርታዊ የፖለቲካ ድርጅቶች አልነበሩም።

የፖለቲካ ድርጅቶች ኖሩም አልኖሩ በኢትዮጵያ ስር ነቀል ሕዝባዊ አብዮት በመካሄድ ላይ ስለነበር በምንም መንገድ የማይታለፈውን የፊውዳሉን ሥርዓት ቁንጮ ዘውዱን መገርሰስና የፖለቲካ ሥርዓቱን ላእላይና ታህታይ መዋቅር ማፈራረስ የደርግ አብይና ቀዳሚ ተልዕኮ ስለሆነ ይህን ለማድረግ የሚጠይቀውን ትግል፣ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነትና የጊዜ መጠን ከወዲሁ ለመገመትና ብሎም ለመመጠን  የምንችልበት ሁኔታ አልነበረም።

ጠቅላላውን የሽግግር ጊዜ በሚባለው የመጀመሪያው ወሳኝ የትግል ምዕራፍ መከናወን ያለባቸውን በርካታ ፈታኝና ውስብስብ አብዮታዊ ተግባሮች ትተን የአገሪቱን ጭቁንና ምዝብር ገበሬዎች ከገባርነት፣ ከጭሰኝነትና ከመሬት ከበርቴዎች ሎሌነት ነፃ የሚያወጣውንና በዲሞክራቲክ አብዮት የመጀመሪያው የአብዮታዊያን ተግባር የሆነውን የገጠሩን የእርሻ መሬት ለገበሬው የማድረጉና ሠራተኛውን መደብ ከምንዳ ባርነት ነፃ የማውጣቱ አብዮታዊ ተግባሮች ብቻቸውን የሚያስከትሉትን ትግል፣ ትግሉ የሚያስከፍለውን መስዋዕትነትና

የሚጠይቀውን የጊዜ መጠን ከወዲሁ ገምተን እቅድ ማውጣትና እቅዱም ተግባራዊ የሚሆንበትን መርሐ ግብርና የጊዜ ሰንጠረዥ ለመስራት የሚቻል አልነበረም።

በአገራችን ኋላ ቀርነትና በሕዝቡ የፖለቲካ ባህል ድህነት ምክንያት አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት አካሎች በመፍጠርና በማዋቀር ሕዝባዊ መንግሥቱን የሚያቋቁሙና ብለውም የሚመሩ የፖለቲካ ድርጅቶች አልነበሩም እንጂ ቢኖሩም የፖለቲካ ድርጅቶች መኖር ብቻውን ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም ያስችላል ማለት አልነበረም።

የሕዝባዊ መንግሥት ማህበራዊ መሰረት የሆኑትን የመደብ፣ የሙያና የሕዝቡን ልዩ ልዩ ብዙሃን ድርጅቶች በየፈርጃቸ ው ማደራጀቱ ሕዝባዊ መንግሥቱን ከማዋቀሩ በጣም የላቀ ጥረትና ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ነው ያገኘነው። ያለሕዝቡ ብዙሃን ድርጅቶች መደራጀትና ያለሕዝቡ ተሳትፎ ሕዝባዊ መንግሥት ብሎ ነገር ለኖር አይችልም።

በደርጉ ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ መሰረት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም መዘጋጀት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ከዚያም በኋላ መሰራት ያለባቸውን ተከታታይ መርሐ ግብሮች አቅደን ለአፈፃፀማቸውም ቅደም ተከተልና የጊዜ ሰንጠረዥ ሰርተን ለማቅረብ የተሰበሰብነው የደርጉ ስራ አስፈፃሚና የእቅድ ኮሚቴዎች አባላት ያደረግነው ጥረት ያስገነዘበን ያሮጌውን የፖለቲካ ሥርዓት ላዕላይና ታህታይ መዋቅር ለማፍረስ፣ በአሮጌው ሥርዓት ፍራሽ ላይ አዲሶቹን የፖለቲካ ሥርዓት አካላት ማለትም፣ ፓርቲዎችንና የአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ማህበራዊ መሰረት የሚሆኑትን የሕዝቡን ብዙሃን ድርጅቶች ወዘተ በማደራጀት ለስር ነቀል ማህበራዊ ለውጥ ማዘጋጀት ቀላልና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማከናወን የሚቻል ስራ ያለመሆኑን ነው።

ስለሆነም ለደርጉ ጉባዔ ውሳኔ ያቀረብነው ሃሳብ፣ የመጀመሪያው ወሳኝ የትግል ምዕራፍና የሽግግር ጊዜ በምንለው ከፍለ ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን ማቋቋም እንደማይቻልና ማድረግ የሚቻለውና መደረግ ያለበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን መስራች የሆነ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥትን ማቋቋም ስለሚቻልበት ሃሳብ ነው።

የደርጉ ሥራ አስፈፃሚና የእቅድ ጥምር ኮሚቴ አባላት ባቀረብነው ሃሳብ ላይ የደርጉ ጉባዔ ከተወያየ በኋላ በቀረቡት መሰረታዊ ሀሳቦች ላይ የጋራ ግንዛቤ በመገኘቱና ሁሉም በመስማማቱ ጉባዔው ከዚህ በኋላ ያመራው ኢትዮጵያ ምን አይነት የሽግግር መንግሥት ያስፈልጋታል የተባለውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላሉ ተብሎ በጥምር ኮሚቴው በቀረቡ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት አይነቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን ነበር።

ደርግ ሲቋቋም ሰርገው ወደ ስብሰባው አዳራሽ የገቡ የቤተመንግሥቱን ሰላዮችና የልጅ እንዳልካቸውን ወኪሎች ለማስወጣት ብንችልም በሠራዊቱ ተመርጠው ግን ለገዥው መደብና ለገንጣዮች መረጃ የሚያቀብሉ መሀከላችን ስለነበሩ የስብሰባ አዳራሹን ዘግተን የምንወያይባቸውና የምንወስናቸው ነገሮች ሁሉ በየዕለቱ የሚያቀርቡ ነበሩ።

ወደ የመንግሥት አይነት ምርጫ ከማምራታችን በፊት በተለያዩ ፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለም ጉዳዮች ላይ በምንወያይበት ጊዜ የውይይቶቻችንን ርዕሶችና የውይይቱም ዓላማ ለልጅ እንዳልካቸው ስለደረሳቸው ውይይቱ የተሳካ ውጤት ሳያገኝ ለማክሸፍና ቢቻልም ደርጉን ለማፍረስ ሁለት አደገኛ ሴራዎችን ጠነሰሱ።

አንደኛውና የመጀመሪያው ሴራ፣ ከየካቲት ወር በፊት የአቶ አክሊሉ ሀብተወልድን መንግሥት ከጦር ኃይሉ ጋር ለማጋጨት የተጠቀሙበትን የኮንጎ ዘማች ሠራዊት የአበል ጥያቄ በመቀስቀስና "ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አዘውኝ አበላችሁን ልከፍላችሁ ተዘጋጅቼ



'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለውን አብዮታዊ መፈክር ከአንድ ዓይና የኢትዮጵያ ካርታ ጋር ሠራዊቱ ልጅ እንዳልካቸው ደርግን ለማፍረስና ሠራዊቱን አዋግተው ደም ለማፋሰስ የሞከሩትን ሴራ ለማክሸፍ ሠራዊቱ በአዲስ አበባ ለሕዝቡ ያሳየው ሁብረት

ሳለ የከለከለኝ ደርግ ነው። አሁንም በእናንተ ምክንያት ደርግ ከሥልጣኔ አውርዶ ሊያስረኝ እየተወያየ ነውና የኔም የእናንተም ችግር ሊወገድ የሚችለው ደርግን በጋራ ለማስወገድ የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው" በማለት ሠራዊቱን በደርግ ላይ አሳምፀው ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ በመክተት ሥራችንን ክፉኛ ከማወክ ሌላ በአብዛኛው የኮንጎ ዘማች ያለበትን የክብር ዘበኛውን ክፍለ ጦር በማስተባበር ወደ አደገኛ የኃይል ፍጥጫ አድርሰውን ሴራውን ለማክሸፍ የቻልነው ከሐረርና ከናዝሬት የብረት ለበስና ታንከኛ ጦር ወደ አዲስ አበባ እምጥተን ከአየር ኃይላችን ጋራ በማስተባበር ባሳየነው የኃይል ትርኢት ነበር።

ሌላውን ሁለተኛ ሴራ የሞከሩት ቀደም ብዬ በጠቀስኳቸው ወሳኝ የፖለቲካ ርዕሶች ላይ በጣም የሞቀ ውይይት በምናካሄድበት ዛሬ ቀኑን በማላስታውሰው ማለዳ በደርጉ ድጋፍ ሰጪ ክፍል ውስጥ የወታደራዊውን መረጃ መምሪያ ይመራ በነበረው የሻለቃ ንጉሤ ኃይሉ የስብሰባ አዳራሻችንን በር በኃይል በማንኳኳትና አስከፍቶ በመግባት "በጄኔራል ጃጋማ ኬሎ የሚመራና በበዙ ሺህ የሚቆጠር ብሔራዊ ጦር በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ደርጉን

እንዲደመስስ በንጉሡ ስለታዘዘ ሕይወታችሁን ለማዳን ባስቸኳይ ከዚህ አዳራሽ ወጥታችሁ መበታተን አለባችሁ” ብሎ በመውጣት ራሱን ሰወረ። በእርግጥም አደገኛ ሴራ ነበር።

በተነገረው ነገር የደርጉ አባላት ተደናገጡ። እንደተባለው ከአዳራሹ ወጥተን በመበተን እያንዳንዳች ራሳችንን እናድን ዘንድ የሻለቃውን መረጃ አምነው በምክሩ የተስማሙ ነበሩ። ሆኖም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ደህንነትና ማህበራዊ እድገት ሕይወታቸውን ለመስጠት ቆርጠው የተነሱ ጀግኖች በብዛት ስለነበሩ ሴራው ከሽፈና ውይይታችንን እንደነበረ በሰላም ቀጥለን ካበቃን በኋላ ወደ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ምርጫ አመራን።

ለምርጫው የቀረቡ የሽግግር መንግሥት ዓይነቶች፡

1ኛ/ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን እንዳለ ሆኖ ከአዲሱ ካቢኔ ውስጥም ሆነ ውጭ ያሉትን እንቅፋቶች በማስወገድ መንግሥት ከደርግ ተባብሮ ሥራውን በታሻለ ሁኔታ እንዲሠራ ማድረግ፣

2ኛ/ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የልጅ እንዳልካቸውን መስተዳደር አፍርሶ በሲቪልና በወታደር በተቀመረ መስተዳድር መተካት፣

3ኛ/ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን እንዳለ ሆኖ የልጅ እንዳልካቸውን መስተዳድር በወታደራዊ መስተዳድር መተካት፣

4ኛ/ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘውዳዊ ፈላጭ ቆራጭ መለኮታዊ ሥልጣን በሕግ ተገድቦ አዲስ በሚቋቋም ጊዜያዊ የሕዝብ ምክር ቤት የሚመራ ጊዜያዊ መንግሥት ማቋቋም የተባሉት ነበሩ።

ደርጉ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል ብሎ ወዳመራበት ምርጫ ለማምራት በአማራጮች ላይ የተደረጉት ሰፊና ዲሞክራሲያዊ ውይይቶች ዓይን ገላጭና ብሎም ትምህርት ከመሆናቸውም በላይ በጣም አስደሳችና ምንጊዜም የማይረሳ ትዝታ በእያንዳንዱ የደርግ አባል ህሊና የቀረፁ ናቸው።

የብዙሃኑን የደርግ አባላት ስሜት የሳበውና በከፍተኛ ደረጃ የተደገፈው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የተባለው አማራጭ የመንግሥት ዓይነት ነበር።

በሕዝባዊ ሥርዓት የሚመራውን ሕዝባዊ መንግሥት የተቃወመ ወይንም ድምጹን ያቀበ አንድም የደርግ አባል አልነበረም። የውይይቱ ስልት፣ ዲሞክራሲያዊ ይዘቱና የአማራጮቹ መብዛት ባስገኙት የማንዛቤ ውጤት ኢትዮጵያ ከነበረችበት ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ አንፃር በሕዝባዊ ሥርዓት የሚመራ ሕዝባዊ መንግሥት ወይም ባጠቃላይ አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ካለመዘጋጀታቸው ባሻገር በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ከውጪ የከበቡንን መንግሥታትና እንዲሁም ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል በውስጥ የትጥቅ ትግል የጀመሩትን ምንደኞችና የአብዮት ፀሮች በመከላከልና በመመከት፣ የኢትዮጵያን ድንበር፣ ክብሯንና አንድነቷን ማስከበሩ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ወግ ሲባል የማይታለፍ፣ ከምንም ጋር የማይነፃፀር ከማንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ህልውና ጉዳይ በመሆኑ ይህንን ወሳኝ ተልዕኮ የሚያሟላና ኢትዮጵያን ወደ ሕዝባዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የሚያስፈልጓትን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያመቻች ጠንካራ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በጊዜው ከነበረው ካቢኔ ወይም የምኒስትሮች ምክርቤት ጋር እንዲሰራ ተወሰነ።

ባነገብነው ሕዝባዊ ዓላማና ለዓላማችንም ግብ መምታት መሸጋገሪያ ይሆን ዘንድ በምናቋቁመው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ለሚመራው ሕዝባዊ አብዮት በፍፁም

ታማኝነት፣ ቁርጠኝነት፣ በተግባር አንድነትና በዓላማ ፅናት እንታገላለን በማለት ለምንወዳት አገራችንና ለምናከብረው ሕዝቧ ከዚህ የሚከተለውን ቃል ኪዳን ገባን።

የደርጉ አባላት ቃለ መሀላ

እኔ ______________________ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ አባል፣ ደርጉ ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ በተነሳበት ሕዝባዊ ዓላማ መሠረት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአያሌ ዘመናት አሳፋሪ ድህነት፣ ግፍና በደል፣ ጭቆናና ምዝበራ ነፃ ለማድረግ ኑሮውን ለማሻሻል የግል ጥቅሜንና ሕይወቴን መስዋዕት በማድረግ በፍፁም ታማኝነት አገለግላለሁ።

ደርጉ ኢትዮጵያን ለማስቀደም የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ድንጋጌዎች ሁሉ ያለአንዳች ማመንታትና ማወላለፅ አከብራለሁ አስከብራለሁ።

የደርጉን ዓላማ የሚቃወምና የሚቃረን ሥራ አልሰራም። ምስጢርም አላባክንም። ለእዚህም በጭቁኑ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ። ከገባሁበት ቃል ኪዳን ዝንፍ ብል የኢትዮጵያ ትቅደም ሠይፍ ይረፍብኝ።

ፊርማ ______________________

ኢትዮጵያ ትቅደም

ኢትዮጵያ በታሪኳ ገጥሟት በማያውቅ በዚያ ፖለቲካዊ ነውጥ በመናወጥ ላይ እያለች፣ የጉልታዊው ሥርዓት ማህበር አራማጅ ገዥ መደቦች በሙሉ ማለት ይቻላል የንጉሡ እልፍኝ አስከልካይና አጃቢዎቻቸው ሳይቀሩ በቁጥጥር ስር ውለው ንጉሡ ብቻቸውን በወና ቤተመንግሥት ውስጥ በተቀመጡበት ጊዜ የተሻሻለ አዲስ ሕገመንግሥት አርቃቂ የተባለው ጉባዔ አባላት በተለያዩ የቃላት ቀለማት ብቻ አኾርኩርጉረው የነበረውን የንጉሡን ፈላጭ ቆራጭነት የሚያንፀባርቅ ሕገመንግሥት ማርቀቃቸው የሚያስገርም ነበር።

የደርጉ ጉባዔ ወደ የመንግሥት አይነት ምርጫ ከማምራቱ በፊት እኔ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ሻለቃ አጥናፉ አባተ፣ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ፣ ሻለቃ ደበላ ዲንሳና ሻምበል ብርሃኑ ባይህ ሆነን የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ጉባዔ ላይ ተገኝተን የጉባዔውን ጠቅላላ አባላትና እንዲሁም የአመራር አካላት አነጋገርናል።

አልገባቸውም ወይም ሃሳባችንን አልተቀበሉም እንጂ በመረቀቅ ላይ ያለው ሕገመንግሥት በቅርፁም ሆነ በይዘቱ ፍፁም ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአያሌ ዘመናት ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ የማይመልስና እንደተለመደው የአንድን ሰው መለኮታዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን የሚደራርት ከሆነ በከንቱ ነው የምትደክሙት ብለን በግልፅ አስጠንቅቀናቸው ነበር።

የሕገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔ አባላት የሥም ዝርዝር፡-

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ | የጉባዔ ሰብሳቢ |
| 2ኛ/ አቶ አማኑኤል አምደሚካኤል | የጉባዔ ፀሃፊ |
| 3ኛ/ አቶ ይልማ ደሬሳ | የጉባዔ አባል |
| 4ኛ/ ቢትወደድ አስፍሃ ወ/ሚካኤል | የጉባዔ አባል |

| | |
|---|---|
| 5ኛ/ ቢትወደድ አበበ ረታ | የጉባዔ አባል |
| 6ኛ/ ቢትወደድ አዲስ አለማሁ | የጉባዔ አባል |
| 7ኛ/ ደጃዝማች ግርማቸው ተ/ኃዋርያት | የጉባዔ አባል |
| 8ኛ/ ብላታ ትርፌ ሹምዬ | የጉባዔ አባል |
| 9ኛ/ አፈንጉሥ ቅጣው ይታበቱ | የጉባዔ አባል |
| 10ኛ/ ብላታ ማትያስ ሀለተወርቅ | የጉባዔ አባል |
| 11ኛ/ አፈንጉሥ ታደሰ መንገሻ | የጉባዔ አባል |
| 12ኛ/ አቶ ነፀቶም ጴጥሮስ | የጉባዔ አባል |
| 13ኛ/ ወይዘሪት የዲት እምሩ | የጉባዔ አባል |
| 14ኛ/ አቶ አሰፋ ሊበን | የጉባዔ አባል |
| 15ኛ/ ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ | የጉባዔ አባል |
| 16ኛ/ ቀኛዝማች አብዱላዚዝ ሼክ መሃመድ | የጉባዔ አባል |
| 17ኛ/ አቶ ተፈራ ደገፌ | የጉባዔ አባል |
| 18ኛ/ ቄስ መላከሰላም ተክለብርሃን ወ/እየሱስ | የጉባዔ አባል |
| 19ኛ/ ሀጂ መሐመድ ሳኒ | የጉባዔ አባል |
| 20ኛ/ አቶ ወርቁ ተፈራ | የጉባዔ አባል |
| 21ኛ/ ሀጂ የሱፍ አብዱራህማን | የጉባዔ አባል |
| 22ኛ/ ፊታውራሪ ገ/ሕይወት ወ/ሃዋሪያት | የጉባዔ አባል |
| 23ኛ/ ፊታውራሪ ሀዳድ ከራር | የጉባዔ አባል |
| 24ኛ/ ዶክተር አብርሃም ደሞዝ | የጉባዔ አባል |
| 25ኛ/ አቶ ብርሃኑ ዋቀዩ | የጉባዔ አባል |
| 26ኛ/ አቶ ፍሰሀ ባየህ | የጉባዔ አባል |
| 27ኛ/ አቶ ፍሰሃጽዮን ተክሌ | የጉባዔ አባል |
| 28ኛ/ ዶክተር ኃይሌ ወ/ሚካኤል | የጉባዔ አባል |
| 29ኛ/ አቶ ነጋሽ ወ/ማርያም | የጉባዔ አባል |
| 30ኛ/ ሻለቃ ወንዳየሁ ምህረቱ | የጉባዔ አባል |

ምን አይነት መንግሥት ትፈልጋለህ ብለን የኢትዮጵያን ሕዝብ በገሀድ መጠየቃችንና ሕዝቡም ፍላጎቱን መግለጡን ንጉሡና ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ከመመልከታቸው በላይ ደርጉ "ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል የሚለውን መንግሥት ዓይነት መርጧል። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሥልጣንና የዘውዱ የህልውና ጊዜ በጣት የሚቆጠር ነው" በማለት መሀከላችን ያሉት ወኪሎቻቸው ስላሳወቋቸው በቤተመንግሥቱና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ ድንጋጤና ሽብር ተፈጠረ።

የመንግሥት አይነት ከመምረጣችን በፊት ከሰኔ 21 ቀን ጀምሮ በየእለቱ የምንወስዳቸው ርምጃዎች፣ የምንሰጣቸው መግለጫዎችና ለሕዝቡ የሚደረጉት ቅስቀሳዎች የደርጉን ማንነት በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያስረዱ ቢሆኑም ንጉሡ እንኳ ህን ለማሰብ አልፈለጉም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የንጉሡ እልፍኝ አስከልካይ፣ ከእስር ተርፈው በአካባቢያቸው የነበሩ መሣፍንትና ቤተሰቦች ስጋታቸውን ሲገልጹና የተለያዩ ደርግን የሚከሱባቸውን ስሞታዎች ሲያቀርቡላቸው ደርግ ታማኞችን ስለሆነ ተባብራችሁ ስሩ ይሉ የነበሩት ንጉሥ ደርግ አታሎናል በማለት አማርረው ወደ ተንኮል አመሩ።

"ምን ይደረግ? ይህንን ደርግ የተባለ ነገር እንዴትና በምን ማጥፋት ይቻላል" በማለት ለዙፋኑ ቅርብ የሆኑ ሰዎች፣ ንጉሣዊያን ቤተሰቦች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰኔ ወር መገባደጃ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያቶች በቤተመንግሥቱ በምስጢር እየተሰበሰቡ መዶለታቸው ይደርሰናል። የእኛ መረጃዎች በሙያ የሰለጠኑ ምንደኛ ወኪሎች ሳይሆኑ እኛ የማናውቃቸውና አብዮቱ የመጣላቸው ወይም የሃገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ናቸው።

እንዲህ ያሉ ሰዎች በቤተመንግሥቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በግልና በመንግሥት ተቋማት ወስጥ ብዙ ነበሩን። ደርግን እንዴት እናጥፋ የተባለውን ጥያቄ መልስ ቀላል ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚቻል አልነበረም። ምክንያቱም በዚያ ጊዜ ደርግ ሕዝብ ነው ሕዝብም ደርግ ነው።

ሆኖም ንጉሡና ልጅ እንዳልካቸው ተስፋ በመቁረጥ ከዚህ የሚከተሉትን ሁለት ደርግን የማጥፋት ሙከራዎች አደረጉ።

ከሰኔ ወር ሁለት ያልተሳኩ ሙከራዎች በኋላ በሐምሌ ወር የተሞከረው ሦስተኛው ሙከራ ከምድር ጦር አየር ክፍል፣ ከምድር ጦር ወታደር ፖሊስ፣ ከምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ ክፍሎች ወዘተ የተውጣጡ የልጅ እንዳልካቸው ምልምል መኮንኖች የምድር ጦር መሀንዲስ ክፍልን ዋና መጋሪያና መቺ ኃይል በማድረግ ሐምሌ 2 ቀን ከቀኑ በ7 ሰዓት ላይ የደርጉ ጉባዔ በስብሰባ አዳራሽ ላይ እንዳለ ለመፍጀት ያቀዱትን እቅድ አንድ የመሀንዲስ ክፍል ባልደረባ የሆነ በታች ሹም ከቀኑ በ5 ሰዓት ስብሰባ አዳራሻችን ድረስ መጥቶ እቅዱን አስታወቀን በ6 ሰዓት ላይ አንድ ብረት ለበስ ሻምበል ጦር ስንልክ በርግጥም ሠራዊቱ የመሣሪያ ግምጃ ቤቱን ሰብሮ መሣሪያ ለማውጣት በመንቀሳቀስ ላይ ስለነበረ ከደርጉ ጦር ጋር በተደረገው ግጭት ከመሀንዲስ ጦር አንድ ሰው ተሰውቶና አራት ሰዎች ቆስለው ሴራውን ለማክሸፍ ተቻለ።

አራተኛውና የመጨረሻው ሙከራ በንጉሡ አንጋች ጦር ሹፋን በቤተመንግሥቱ ውስጥ የሚሰራ ሻለቃ ጣሰው ሞጆ በሚባል መኮንን የሚመራ፣ በእሥራኤሎች በአፈናና ግድያ የሰለጠነና በልዩ ተግባር የተካነ ወታደራዊ ቡድን ሐምሌ 10 ቀን በኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት በንጉሡ፣ እኔና ሻለቃ አጥናፉን በ48 ሰዓት ውስጥ ገድሎ ውጤቱን እንዲያመለክት ትዕዛዝ ተሰጠው።

ሐምሌ 11 ቀን ጠዋት በ2 ሰዓት በሰብሰባ አዳራሻችን ውስጥ እንደተገናኘን የመቶ አለቃ ገበያው ተመስገን የተባለ የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ ተወካይ የሆነ የደርግ አባል ጥቂት ዘግየት ብሎ ስለነበር የሮጠ ይመስለኛል ወደ አዳራሹ ሲገባ እያቃሰተና ላቡ እየተንቆረቆረ በኃላ ድምጽ እንድናዳምጠው ጉባዔውን አባላት ከጠየቀ በኋላ "ንጉሡ ራሳቸው በመሩት ስብሰባ ትናንትና ማታ በኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት የደርጉ አመራር አካላት በ48 ሰዓት ውስጥ እንዲገደሉና ደርጉ እንዲበተን ተወስኗል።

የደርጉን አመራር አካላት እንዲገድል የታዘዘው ግለሰብ በዚህ አይነት ግድያና አፈና ሙያ የታወቀው ሻለቃ ጣሰው ሞጆ ነው። አሁን ጉባዔውን በጥብቅ የማሳሰበው ከክፍለ ጦር የመጡትና በየሆቴሉ የሚኖሩት መሪዎቻችን በአስቸኳይ በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ መኖሪያ ቤት ተፈልጎ እንዲሰጣቸውና በጥብቅ እንዲጠበቁ ነው። ይህ አደገኛ ነፍሰ ገዳይ ሻለቃ ዛሬውኑ ተፈልጎ በቁጥጥር ስር እንዲውል እጠይቃለሁ" ብሎ ንግግሩን ሲያቆም በአዳራሹ ውስጥ ሁካታ ተፈጠረ።

ሻለቃ ጣሰው ሞጆን እናውቃለን የሚሉት የፖሊስና የክብር ዘበኛው ክፍለ ጦር አባሎች ናቸው። ከማናችንም በላይ የሰጉትና የተቅበጠበጡትም እነሱ ነበሩ።

ሁሉም ሰው ይናገራል፤ ሁሉም ይጮሀል፤ አንዳንዱ ይፎክራል፤ መደማመጥ አልተቻለም። አዳራሹ ያልጠበቅነው ድንገተኛና የአስገራሚ ትርኢት መድረክ ሆነ። እኔ በበኩሌ እንደተለመደው እኛን ለማሸበር የተደረገ የገጠው መደብ ፈጠራ ወይም ሴራ ነው በማለት የመቶ አለቃ ገበያው ያቀረበውን መረጃ ለማመን ተቸግሬያለሁ።

ከውጪ ወደ ስብሰባ አዳራሽ ለመግባት የሚፈልጉ ሰዎች በሩን ያንኳኳሉ። የዘገዩ ወይም ከአዳራሹ የወጡ የደርግ አባላት እንዳሉ ብጠይቅ ሁሉም በአዳራሽ እንዳሉ ስለተነገረኝ በአዳራሹ ውስጥ የተፈጠረው ሁካታ ሳይቆም ማንም የውጭ ሰው ወደ አዳራሹ እንዳይገባ ስለፈለግሁ በሩ እንዳይከፈት አዘዝኩ።

በሩ በሃይል ተደበደበና በበሩ አካባቢ ያሉ የደርግ አባላት በሩን ለመክፈት ሲሞክሩ፣ አይከፈትም ተመለሱ ብላችሁ ንገሯቸው እንጂ ብትከፍቱ የምትጣሉት ከኔ ነው በማለት በብርቱ ሁኔታ አስጠነቀቅኩ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን አንድ ሁላችንንም በድንገት ክፉኛ የሚያስቅ ነገር ተፈጠረና ስናስተውል የነበረውን ትርኢት በቅጽበት ለወጠው። ለዚህም ምክንያት የሆነው የአስር አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ የሚባለው የደርግ አባል ነበር።

ጴጥሮስ መልካም ቁመና ያለው ግዙፍ ሰው ከመሆኑ ሌላ ድምጹ ጎርናና እና ካልጮኸ ቀስ ብሎ መናገር የማይሆንለት ሰው ነው። አብዛኛው የደርግ አባላት የታጠቅነው ሽጉጥና የተለያዩ አነስተኛ አውቶማቲክ ጠብመንጃዎችን ሲሆን እሱ የታጠቀው አይነት ኤም ዋን የሚባለውን ትልቅ የአሜሪካን ስሪት ጠብመንጃ ከሙሉ ዝናር ጥይት ጋር ነበር።

ከውጪ የበሩ መንኳኳት አላቆመም። በበሩ አካባቢ ያሉ የደርግ አባላት ሊከፍቱ ሲሞክሩ ተመልክቼ በድጋሚ ስናገር የአስር አለቃ ጴጥሮስ ይመለከተኝ ነበርና ከተቀመጠበት ወንበር ተነስቶ በሩን ከውስጥ በመደገፍ ያንን ትልቅ ጠብመንጃ ለመተኮስ የተዘጋጀ ይመስላል ደግሞ፤ "ሁልሽም ያቦካሽውን ሳትጋግሪ ከዚህ መውጣት የለም" ሲል የደርግ አባላቱ ሁሉ በሳቅ አወካን።

እኔ ሳቄን ማቆም ተስኖኝ አይኖቼ እንባ እስኪያቀሩ ድረስ ሳቅሁ። ብዙዎቹም የደርግ አባሎች እንደዚሁ። ቁጣው፣ ሁከቱና ፉከራው በሳቅ ተለውጦ ሳቁም ከቆመ በኋላ በሩ ሲከፈት ያንን ያህል በሩን ሲያንኳኳ የነበረው ከደርጉ ውጪ በሃገር ደረጃ ያቋቋምነውን ጊዜያዊ የሃገር ደህንነት ጥበቃ ኮሚቴ የሚሰበስበው ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ነበር።

ያንን ያህል የደርጉን አዳራሽ በር ለማንኳኳት የተገደደውም የመቶ አለቃ ገበያው ተመስገን ያመጣው መረጃ ለብሔራዊ ደህንነቱ ኮሚቴም መድረሱን ለማሳወቅና ስለሚወስደው እርምጃ መመሪያ ለማግኘት ነበር።

የደህንነት ኃይሎች ሻለቃ ጣሰው ሞጆ እንገባበት ገብተው በዚያኑ ቀን በቁጥጥር ስር እንዲያውሉት ትዕዛዝ ሰጥቼ ሻለቃው እስኪያዝ ድረስ የደርግ አባላት ከአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ እንዳይወጡ አደረግን።

በመቶ አለቃ ገበያው ማሳሰቢያ መሠረት በሆቴል እንኖር የነበርን አባላት ለደህንነታችን ዋስትና ያላቸው መኖሪያ ቤቶች አገኘን። በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በሚያስገርም ቅልጥፍናና ፍጥነት የተንቀሳቀሱት የደህንነት ኃይሎች በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሻለቃ ጣሰው ሞጆን ብቻ ሳይሆን በሱ የሚመሩትን የአፈናና የግድያ ቡድን አባላት በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ ቻሉ።




እኔና ሻለቃ አጥናፉ በ48 ሰዓት ውስጥ እንድንገደልና ደርግ እንዲበተን ትዕዛዝ የሰጡት ንጉሥና ግብረአበሮቻቸው የሻለቃ ጣሰው ሞጆን ገድል ሲጠብቁ ሻለቃው ራሱ መጥፋቱን ሲያውቁ ተሸበሩ።

የንጉሡ እልፍኝ አስከልካይ ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ለልጅ እንዳልካቸው ስልክ ደውለው "ሻለቃ ጣሰው ጠፋብን" ሲሉ ይነግሯቸዋል። ልጅ እንዳልካቸው በከፍተኛ ድንጋጤ "ጄኔራል ምን ሻለቃ ጣሰው ጠፋ ይሉኛል? እኛ በጠቅላላው ጠፋን ይበሉን እንጂ" ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል "ጃንሆይ ይህንን ጉድ ሰምተዋል?" ብለው ሲጠይቁ ጄኔራሉም "አዎን ሰምተው በእጅጉ በማዘንና በመቆጣት እናንተ ተሳስታችሁ እኛንም አሳሳታችሁን በማለት እህል አልቀምስም፤ ሰውም አላይም፤ አላነጋግርም ብለውናል" ካሉ በኋላ ጄኔራል አሰፋም ንግግራቸውን በመቀጠል "ይህንን ያመጣው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ስለሆነ ከእንግዲህ የሚመጣውን ሁሉ ከመቀበል ሌላ ምን ይደረጋል? እግዚአብሔር ያጥናህ። ደህና ሁን" ብለው ስልኩን ሲዘጉ ተደምጠዋል።

ሁለቱም ግለሰቦች የሰሩት ወንጀል የሚያስከትለውን የተገነዘቡ ይመስላል በእስር ቤት በሚገናኙበት ጊዜ ምናልባት እርስበርሳቸው ይወያዩበት እንደሆን እንጂ በስልክ ንግግራቸው የመጨረሻ ነበር።

እኔና ሻለቃ አጥናፉ የሻለቃ ጣሰው ሞጆ ሰለባ ከመሆናችን በፊት ያስጣለን ሕዝብ ነው። ደህንነቱም ሆነ የመቶ አለቃ ገበያው በዚያ ፍጥነት ያንን የመሰለ መረጃ ያገኙት ከሰለጠኑ የመረጃ ወኪሎች ሳይሆን ከሕዝብ ነው።

ደርግ ሕዝብ ነበር፤ ሕዝብም ደርግ ነበር ያልኩት ለመመፃደቅ ወይም ለማጋነን ሳይሆን አብዮቱንም አገሪቱንም ያዳነው በሕዝቡ መረጃና በሕዝቡ ያላቋረጠ ትብብር ስለሆነ

ነው። ጓድ ገበያው ተመስገን ከፍተኛ የሃገር ፍቅር ያለው ሃቀኛ አብዮተኛ፣ እንደበተ ርቱዕ፣ የሚደነቅ ጭንቅላት ወይም ብሩህ አእምሮ ያለው የሥነ ጽሑፍ ሰው ነበር።

ደርጉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይኑን ከፍቶና አንገቱን ቀና አድርጎ በአብዮቱ ወደ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲራመድ ለማድረግ የተደረጉት አብዮታዊ ቅስቀሳዎችና እንዲሁም በፀረ-ሕዝቦች ላይ ያካሄድናቸው የመንፈስ ውጊያዎች፣ የሥነልቦናና የርዕዮተ ዓለም ጦርነቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ የተደነቀባቸው ስለመሆኑ የአብዮቱ ወገኖች ቀርቶ የጠላትም ጎራ የሚክደው አይመስለኝም።

ጓድ ገበያው የደርጉን የማስታወቂያ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ኮሚቴ ከማቋቋም ጀምሮ ያንን የተደነቀ ሥራ ከሰሩት ጥቂት ጓዶች መካከል ግምባር ቀደም ነበር። ይህንን በማወቅ ወይም በመረዳት ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮዊ ፓርቲ በማለት የሚጠራው እምስተኛ ረድፍ የነፍሰ ገዳዮች ድርጅት የማይተካውን አብዮታዊ ወጣት በአጭር ቀጨው።

የጓድ ጴጥሮስ ገብሬ ንግግር በዚያ ዕለት ብቻ ሳይሆን በአስታወስነው ቁጥር ብዙዎቻችን ሲያስቀን ይኖራል። በገቡበት አብዮታዊ ቃል ኪዳን ፀንተው እስከ መጨረሻ ከታገሉት የደርግ አባላት አንዱ በመሆን በአብዮት ሂደት የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ የማዕከላዊ ኮሚቴ ተለዋጭ አባል ለመሆን በቅቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን የኢትዮጵያን የጦር ኃይሎች እርስ በእርሳቸው በማዋጋት ደም ለማፋሰስ፣ ደርጉን በመከፋፈልና ብሎም በማፍረስ ሕዝባዊውን አብዮት ለመቀልበስ ከማሻጠር አልፈው ሊያጠፉን ስለሞከሩ ሐምሌ 15 ቀን 1966 ዓ.ም ከሥልጣናቸው ወርደው ከመሰሎቻቸው፣ ግን እያስለቀሙ ካሰሯቸው ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር ተቀላቀሉ።

## ምዕራፍ ስድስት

# ደርግ ከልጅ ሚካኤል እምሩ መንግሥት ጋር

ደርግ ከልጅ እንዳልካቸው መንግሥት ጋር የቆየባቸው ቀናቶች በሳምንታት የሚቆጠሩ በጣም አጭር ጊዜ ሆነው ሳለ ግን በብዙ ችግሮችና ፈተናዎች የተሞሉ ነበሩ። ደርጉን ሲፈታተኑ የነበሩት አፄ ኃይለሥላሴና ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ብዙ ነበሩ።

በኮንጎ የሰላም ማስከበር ዘመቻ በተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት በኩል የተከፈላቸውን አበል የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ መንግሥት ወስዶ አልከፈላችሁም ተብለው በሀሰት የተንቀሳቀሱት የጦር ኃይልና የፖሊስ ሠራዊት አባሎች ደርግን ለመጣል በመሣሪያነት ያገለግላሉ ተብሎ ስለታመነበት፣ ንጉሡ አበላችሁ እንዲከፈላችሁ አዘው የከለከላችሁ ደርግ ነው በመባላቸው ሥራ አናሰራ ብለው የራስምታት ከመሆናቸው ባሻገር ሠራዊቱን ከፋፍለው በተለይም የክብር ዘበኛውን ክፍለ ጦር ለዚህ ዓላማ አሰልፈው ሊያዋጉን ሞክረዋል።

የራስ ብሩ ልጅ መርዕድ ብሩና የእንቁሥላሴ ልጆች በሰሜን ሸዋ፣ የላስታ ላሊበላ አውራጃ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ብርሃነመስቀል ከአያሌ ግብራበሮቻቸው ጋር በወሎ፣ የአውሳው ባላባት ሱልጣን አሊ ሚራህ በአፋር፣ ፊታውራሪ ትርፌና አያሌ ግብራበሮቻቸው በጎጃም፣ ራሱን የይሁዳ አንበሳ ሠራዊት ብሎ ይጠራ የነበረው ፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች ስብስብ የገጠሩን መሬት ለአራሹ አዋጅ ለማክሸፍ በደቡብ ኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል የጀመሩት በአብዮቱ ማግስት ነው።

ይሄ በኤርትራ፣ በሐረርጌና በባሌ ከቅድመ አብዮት ጀምሮ በውጊያ ከሚያዋክቡን ተገንጣዮችና ምንደኞች በተጨማሪ ነው። የትግራዩ ገዥ ልዑል ራስ መንገሻና የጎንደሩ ገዥ ሜ/ጀኔራል ነጋ ተገኝ ከመንግሥት ደሞዝ እየተከፈሉ ዘመድ ከዘመዱ እንዲሉ ነውና ልባቸው በመሸፈቱ ከደርግ ጋር አይጥና ድመት ነበሩ።

ከመሃሉ መርጦ የላከን ሠራዊት ራሱ ውስጡ ባሉ የአብዮቱ ፀሮች እየተገፋ ያስቸግረን ነበር። በሰሜን በሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር፣ በአየር ኃይሉ፣ በምድር ጦር አየር ክፍል፣ በምድር ጦር መሃንዲስ ክፍል፣ በምድር ጦር ወታደር ፖሊስና የክብር ዘበኛው ክፍለ ጦር ውስጥ የነበሩ የኮንጎ አበል ጠያቂዎች ብቻ ሳይሆኑ ጥቂትም ቢሆኑ ፀረ-አብዮተኞችና ሥርዓት አልበኞች ነበሩ።

ደርጉ ከወህኒ ቤት አውጥቶ ነፃ ከለቀቃቸው የፖለቲካ እስረኞችና በባዕድ ሃገር ከመኖር ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ከጠራቸው የፖለቲካ ስደተኞች መካከል ፀረ-ደርግ፣ ፀረ-አንድነትና በአምስተኛ ረድፈኝነት ተሰልፈው አገራቸውንና አብዮተኞችን ብቻ ሳይሆን ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወግተዋል።

በቅድመ አብዮት የሶማሊያ መንግሥት ምንደኛ ሆኖ ራሱን የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ድርጅት መሪ በማለትም ሰላም ሲያደፈርስ ተይዞ ለብዙ አመታት የታሰረው የደገሐቡር አውራጃ ባላባት የነበረው ደጃዝማች መቅተል ጣሂር በአብዮቱ ማግስት በነፃ ከተለቀቀ በኋላ ወደ ሶማሊያ ኮብልሎ በመሄድ የሶማሊያ መንግሥት የመስፋፋት ወረራ እንዲሳካ ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር።

በቅድመ አብዮት ሜጫና ቱለማ በመባል በሚታወቀው ጥቂት የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት የሚያንቀሳቅሱት ድርጅት የአመራር አካል ናችሁ ተብለው ከታሰሩትና በአብዮቱ ማግስት በነፃ ከተለቀቁት መካከል የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ክፍል አዛዥ የነበሩት ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ከሻለቃ ኃይሉ ረጋሳ ጋር ሸፍተው ደርጉን ሊወጉ ሲዘጋጁ ተይዘው ታሰሩ።

ላለማንዛዛት ተቀጥቤ እንጅ እነኝህን ስለሚመስሉ ከሀዲዎች ብዙ ለማለት ይቻላል። የኮንጎ ዘማቾች አበል ጥያቄ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ደርጉ እስከ ተቋቋመበት ጊዜ ድረስ ንቅናቄውን የሚመራው ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበረው በኋላ የደርጉ ምክትል ሊቀመንበር የሆነው ሻለቃ አጥናፉ ነበር።

የአራተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊትን በአጠቃላይ ለአብዮቱ ለማንቀሳቀስ የቻለው በኮንጎ ዘማች ኮሚቴ ሊቀመንበርነቱ ተንጠላጥሎ ሲሆን ከሱ ሌላ በደርጉ ውስጥ ብዙ የኮንጎ ዘማቾች ስለነበሩ የኮንጎን አበል ጉዳይ በተመለከተ የደርጉ አባላት አቋም አንድ ያለመሆን ብዙ ችግር አድርሶብናል።


ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ከሥልጣን በወረዱበት ሐምሌ 15 ቀን 1966 ዓ.ም በደርግ ምርጫ ልጅ ሚካኤል እምሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። በታሪክ አጋጣሚ በኢትዮጵያ አብዮት የመጀመሪያው ምዕራፍ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ከመሣፍንት የተወለዱ ምሁራን ይሁኑ እንጂ እንደሚታወቀው ልጅ እንዳልካቸው የተመረጡት በንጉሡ ሲሆን ልጅ ሚካኤል የተመረጡት በደርግ ነው። ሁለቱ ግለሰቦች በአቋምና በሚያራምዱት ርዕዮተ ዓለም በጣም የተለያዩ ሰዎች ናቸው።

ሆኖም ከዚህ በላይ ስለእሳቸው እንዳስረዳሁት ታላቅ ጥረት በጎ ፈቃድና ጊዜ የሚጠይቁ ስራዎችን አብረን ለመስራት ቀርቶ ለወራቶችም አብረን ለመቆየት ባለመቻሉ ከእሳቸው መገላገል ግድ ሆነ።

ከልጅ ሚካኤል እምሩ ጋር እኔ በግል ደርጉ ባቀዳቸው በሽግግሩ ወቅት ስለሚከናወኑት አብዮታዊ ተግባሮች ብቻ ሳይሆን የአብዮቱን እስትራቴጂ ግቦች ጭምር በስፋትና በጥልቀት ተወያይተናል። በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሀከላችን መተማመንና መተሳሰብን ለመፍጠር በመቻላችን ወሳኝ የሽግግር ጊዜ ባልነው ጊዜ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ታላላቅ አብዮታዊ ተግባሮችን ለማከናወን ችለናል።

ከልጅ ሚካኤልና እሳቸው ከሚመሩት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጋር ብዙ ጠቃሚ ስራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰራን ሲሆን በተለይ ለአንባቢ መግለፅ የምፈልገው፣ የገጠሩን የእርሻ መሬት አዋጅ፣ የሠራተኞች መደራጃና መተዳደሪያ ወዘተ ሕጎች ጥናትና ዝግጅቶች የተጀመሩት በልጅ ሚካኤል ጠቅላይ ምኒስትርነት ጊዜ መሆኑን ነው።

የአብዮቱን ባህሪ፣ አቅጣጫና ዓላማውን ለሕዝቡ ያስተዋወቀውን፣ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመስረት ያለንን ዓላማና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመፍጠር የሚያስችለውን የፖለቲካ ፕሮግራም ያዘጋጀነው ከልጅ ሚካኤል ጋር ሲሆን እሳቸው የማያውቁት አንድ ነገር ቢኖር የንጉሡን ከሥልጣን የማውረድ እቅዳችንን ብቻ ነው።



ልጅ ሚካኤል እምሩ

በኢትዮጵያ ለሕዝብ የወገኑ ጠንካራ ዲሞክራቶች ናቸው ከሚባሉት በጣም ጥቂት ቀደምት ምሁራን መካከል ልጅ ሚካኤል እስከ አባታቸው ግምባር ቀደም ስለሆኑ የደርግ ምርጫ በተራማጅ ምሁራንም የተደገፈ ነበር። ስለሆነም የደርግና የልጅ ሚካኤል እምሩ ግንኙነትና የትግል ትብብር ከልጅ እንዳልካቸው ጋር እንደነበረው ጊዜያዊና ስልታዊ ሳይሆን በመተማመን ላይ የተመሠረተ የርዕዮት ዓለም ትስስር ነበር።

የደርግ አብዮታዊ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ሥር ነቀሉ የመሬት አዋጅ፣ የርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽንን ማጠናከርና ሥራውን ማስጀመር መርማሪ ኮሚሽኑን ሥራ ማስጀመር፣ የኤርትራን ችግር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በፓርላማ ደረጃ ለውይይት ማቅረብና ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ ማቋቋም ወዘተ ከብዙዎቹ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

የመርማሪ ኮሚሽኑ አባላት ዝርዝር:

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ኮማንደር ለማ ጉተማ | ሊቀመንበር |
| 2ኛ/ ሻለቃ መርሻ አድማሱ | አባል |
| 3ኛ/ አቶ ሁሴን እስማኤል | አባል |
| 4ኛ/ አቶ ባሮ ቱምሳ | አባል |
| 5ኛ/ ዶክተር መሥፍን ወ/ማርያም | አባል |
| 6ኛ/ ዶክተር በረከት ኃብተሥላሴ | አባል |
| 7ኛ/ ሻምበል ምትኬ ደበሌ | አባል |
| 8ኛ/ አቶ ሀሩይ ዋበቡ | አባል |
| 9ኛ/ ዶክተር መኮንን ወ/ማርያም | አባል |
| 10ኛ/ ኮሎኔል ኃይለማርያም አረዶ | አባል |
| 11ኛ/ አቶ መዋዕለ መብራቱ | አባል |

የየካቲትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታላቅነት ይበልጥ ለማጉላት ብቻ ሳይሆን፣ ዝሬውን ገባራቸው፣ ወዘደሩን የምንዳ ባሪያቸው የመከላከያ ሠራዊቱን የግል ሎሌአቸው፣ የሕዝቡን የጋራ የሆነ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ራሱን እንደ ቁሳቁስ የኪስ ገንዘባቸው በማድረግ ሲመዘብሩ በሚኖሩ ፊውዳል ገዥ መደቦች ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ለዓለም አድህሮት ትምህርትና መቀጣጫ ይሆን ዘንድ የምርመራ ኮሚሽኑን መቼምና የትም ተደርጎ የማይታወቅ እጅግ ታሪካዊ የሆነ ተግባር እንዲያከናውን አቅደን ነበር። ይሄውም፣

1ኛ/ በሥልጣናቸው ባልገዋል፣ የአለአግባብ በልጽገዋል፣ በሕዝብ ላይ የተለያዩና ኢሰባዊ የሆኑ ግፍና በደሎችን ሲሰሩ ኖረዋል በመባል የተከሰሱት ባለሥልጣኖች ላይ የሚደረገው የምርመራ አፈፃፀም ወንጀልን ከማጣራት ፋይዳ ባሻገር ለሰው ልጅ ሁሉ ትምህርትና መቀጣጫ ሊሆን በሚያስችል ዝግጅትና ሂደት፣ በብዙሃን ማሰራጫ ጥበብና ቴክኒክ ተደራጅቶና፣ የምርመራውና ብሎም የፍርዱ መድረክ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ በተለያዩ አያሌ ቋንቋዎችና ተንቀሳቃሽ ፊልሞች አማካኝነት ለዓለም ሊሰራጭ በሚችልበት ሁኔታ መሥራት ስለሚቻልበት፤

2ኛ/ የምርመራው ይዘትና ሂደት፣ የጥራት ደረጃና ትምህርት ሰጭነቱ በዓለም ደረጃ ተቀባይነት ለኖረው የሚገባ ከመሆኑም ሌላ የተመርማሪዎቹን ባለሥልጣኖች ቅደም ተከተል በተመለከተም የመጀመሪያው ሰው ወይም ተመርማሪ፣ የጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር አራማጅ ገዥ መደቦች ቁንጮ የሆኑት አፄ ኃይለሥላሴ እንዲሆኑ፤

3ኛ/ ከንጉሡ ጀምሮ በጠቅላላ ተከሳሾችና እንዲሁም ከዚህ በኋላ የሚወሰደው ወይም የኢትዮጵያን ሕዝብ እድል የሚወስነው የፖለቲካ እርምጃ በምርመራው ውጤትና በፍርዱ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን፣ በኔ የተመራ፣ የደርጉ ም/ሊቀመንበር ሻለቃ አጥናፉ አባተ ያለበት አምስት የደርግ አመራር አካላትን የያዘ ቡድን ወይም የደርግ ልዑካን ዛሬ ቀኑን በውል በማላስታውሰው በነሐሴ ወር እኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ድረስ ሄደን በኮሚሽኑ መሰብሰቢያ ክፍል ውስጥ የኮሚሽኑ አመራር አካላት ሁሉ ባሉበት የደርጉን እቅድና ፍላጎት በዝርዝር አስረድተን በዚያ ሁኔታ ይሰራ ዘንድ ከወዲሁ አስፈላጊው መሰናዶ ሁሉ ይደረግ ዘንድ ትብብራቸውን ጠየቅን።

በዚያን ጊዜ ለእኛ ባልተከሰተ ሁኔታ የኮሚሽኑ አባላት ከሆኑት ከፊሉ ማለት ይቻላል የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትም የሚፃረሩ ገንጣዮችና አስገንጣዮች፣ አመራሩን ጨምሮ ወግ አጥባቂ ቀኝ ክንፍ ምሁራን በመሆናቸው ሃሳባችንን ካለመቀበላቸውና ካለመተባበራቸውም በላይ ገንጣይ አስገንጣዮቹ ጄነራል አማን ሲወገዱ አገራቸውን እየከዱ ወደ እኩይ ተግባራቸው ሲሰማሩ ውስጣቸው በነበሩት ጥቂት አብዮታዊ ግለሰቦች ተረድተን የኮንጎን ዘማች ሠራዊት የአበል ጥያቄ ችግር ከፈታን በኋላ ኮሚሽኑ ሕዝብ የጣለበትን አደራና ኃላፊነት ሳይወጣ ተበትኗል።

ደርጉ የኮሚሽኑን ትብብር በጠየቀ ጊዜ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር የነበሩት ዶክተር መሥፍን ወ/ማርያም ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ፕሮፌሰር መሥፍን ጥያቄያችንን ተቀብለው እስኪ እናጥናውና ወይም ጥቂት እናላምጠውና መልስ እንሰጣችሁ ሳይሉና ከተቀሩት የኮሚሽኑ አባላት ጋር ሳይመክሩ እዚያው በቅጽበት ወይም በችኮላ ከጥርሳቸው የሰጡን መልስ ከዚህ የሚከተለው ነበር፤-

1ኛ/ ከተመርማሪዎቹ አንደኛውና ቀዳሚው ንጉሡ ይሁኑ ብለን ላቀረብነው ሀሳብ ከደረደሯቸው አንዱ ነጥብ በሕግ ላይ የተመሠረተ ነበር። ይህውም "የሚያስፈልገው ኃይልም ሆነ ጠብመንጃው ያለው እናንተ እጅ ሆኖ ሳለና፣ በዙፋናቸው ላይ ንጉሡን አስቀምጣችሁና ህገ መንግሥቱ እንዳለ ሆኖ፣ እኛ ይህንን ተግባር በብእራችን እንድናከናውንላችሁ መጠየቃችን አግባብ ስላይደለ የቀረበውን ሀሳብ ለመቀበል አይቻለንም" የሚል ነበር።

2ኛ/ ሁለተኛው ምክንያታቸው እናንተ ባቀረባችሁት ሀሳብ መሠረት ምርመራውም ሆነ ብሎም ፍርዱ በትምህርትነትና በመቀጣጫነት እንዲያገለግል ለዓለም ሕዝብ ይቅረብ ቢባል ዓመታቶችን የሚያስቆጥር ጊዜ ማስፈለጉ አያጠያይቅም።



ከግራ ወደ ቀኝ - ልጅ ሚካኤል፣ እኔ፣ ሜ/ጄነራል ተፈሪ እና ሻለቃ አጥናፉ

እንዲህ ከሆነ ደግሞ “በስፔን ሕዝባዊ አብዮት እንደሆነው፣ ንጉሡ በዙፋናቸው ላይ እስከ ህገ መንግሥታቸው ተቀምጠው፣ ደርግንና ኮሚሽኑን አንድ ሌላ የፖለቲካ ጎርፍ መጥቶ ጠራርጎን ሊሄድ ይችላል” የሚል ነበር።

ጊዜያዊ የሕዝብ መማክርት ሸንጎ የተቋቋመው በአብዮቱ የሕዝቡን ተሳትፎ ሚና ለማስፋት ከነበረን ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ባሻገር ለሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ የሚያስፈልጉ አብዛኛው ቅድመ ሁኔታዎች በመማክርቱ ሸንጎ ይጠናሉ፣ ይዘጋጃሉ፣ ብሎም ወተግባር ይተረጎማሉ በሚል ግርድፍ ሀሳብ ላይ ተመስርተን ነው ያቋቋምነው ማለት ይቻላል።

የአብዮቱ ሂደት በፈጠራቸው አዳዲስ ሁኔታዎችና በተለይም የሕዝቡ በሙያና በብዙሃን ሕዝባዊ ድርጅቶች የመደራጀት ሂደት፣ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአብዮቱ ማግስት የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መከሰት ወይም መፈጠር፣ ለአብዮቱ መሪ የፖለቲካ ድርጅት መመስረት አጣዳፊነት፣ እየጎላና እየገፋ በመምጣቱና በሌሎችም ምክንያቶችና ተቋማቶች የሸንጎ ተግባርና ኃላፊነት እጅግ መጣበብ ብቻ ሳይሆን የሥራ መደራረቦችም ተከሰቱ።

ለማስረጃ ያህል፣ የሕግና የሕግ ሀሳቦችን ማመንጨትን በመሳሰሉ የሥራ ዘርፎች ከደርጉ ጉባዔ፣ ከሚኒስትሮች ምክር ቤትና እንዲሁም ከሕግና ፍትህ ሚኒስቴር ጋር፣ ከዚህ በለጠ ደግሞም ሕዝብን በማንቃትና በማደራጀት የሥራ ዘርፍ ረገድ ከሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ጋር ወዘተ መደራረብና መወራረስ መፈጠሩን በሚገባ ያስተዋሉ የመማክርቱ ሸንጎ አባላት፣ ሸንጎ የተቋቋመው መቋቋም ከሚገባው ጊዜ ብዙ ጊዜ ቀድሞ መሆኑን መግለጽ ለጊዜው እንዲበተንና በሚያስፈልግበት ጊዜ እንዲቋቋም ሃሳብ ማቅረባቸው ይኸኛም በኩል ሲታይ ትክክል በመሆናቸው የመማክርት ጉባዔው እንዲፈርስ ሆነ።

የጊዜያዊ ሕዝባዊ መማክርት ሸንጎ አባላት ዝርዝር፣-

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ አቶ ገመዳ ጎንፋ | የጉባዔው ሊቀመንበር |
| 2ኛ/ ዶክተር አሻግሬ ይግለጡ | የጉባዔው አባል |
| 3ኛ/ አቶ አሻግሬ በየነ | የጉባዔው አባል |
| 4ኛ/ የመቶ አለቃ ጳውሎስ ቦጋለ | የጉባዔው አባል |
| 5ኛ/ አቶ ለገሰ አየለ | የጉባዔው አባል |

| | |
|---|---|
| 6ኛ/ አቶ አበበ ጥላሁን | የጉባዔው አባል |
| 7ኛ/ አቶ በለጠ አወቀ | የጉባዔው አባል |
| 8ኛ/ አቶ ሳሙኤል ገዛኸኝ | የጉባዔው አባል |
| 9ኛ/ አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ | የጉባዔው አባል |
| 10ኛ/ ቀኛዝማች ይጥና አበበ | የጉባዔው አባል |
| 11ኛ/ አቶ በየነ አብዱ | የጉባዔው አባል |
| 12ኛ/ ዶክተር እዮብ ገ/ክርስቶስ | የጉባዔው አባል |
| 13ኛ/ አቶ አሰፋ ሊበን | የጉባዔው አባል |
| 14ኛ/ አቶ አወል አደም አባዋሬ | የጉባዔው አባል |
| 15ኛ/ ዶክተር ጥቀሂር ኃይሉ | የጉባዔው አባል |
| 16ኛ/ አቶ መንግሥቱ ኃይለማርያም | የጉባዔው አባል |
| 17ኛ/ አቶ ጥላሁን አበበ | የጉባዔው አባል |
| 18ኛ/ አቶ አህመድ ሰኢድ አሊ | የጉባዔው አባል |
| 19ኛ/ አቶ አፈወርቅ ወንድሙ | የጉባዔው አባል |
| 20ኛ/ አቶ ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ | የጉባዔው አባል |
| 21ኛ/ አቶ ሰይፉ ይገዙ | የጉባዔው አባል |
| 22ኛ/ ኮሎኔል ለገሰ ወ/ማርያም | የጉባዔው አባል |
| 23ኛ/ ዶክተር ኃይሌ ወ/ሚካኤል | የጉባዔው አባል |
| 24ኛ/ አቶ ካሳ አሥራት | የጉባዔው አባል |
| 25ኛ/ አቶ ከበደ ደስታ | የጉባዔው አባል |
| 26ኛ/ አቶ አውጋቸው ከፍያለው | የጉባዔው አባል |
| 27ኛ/ አቶ ወሌ ቸኮል | የጉባዔው አባል |
| 28ኛ/ ዶክተር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ | የጉባዔው አባል |
| 29ኛ/ አቶ ፅጌ ፍሰሀ | የጉባዔው አባል |
| 30ኛ/ አቶ በዛብህ ደምሴ | የጉባዔው አባል |
| 31ኛ/ አቶ ወ/ማርያም ወ/ሚካኤል | የጉባዔው አባል |
| 32ኛ/ አቶ በዛብህ ገብሬ | የጉባዔው አባል |
| 33ኛ/ አቶ ፀጋዬ አበራ | የጉባዔው አባል |
| 34ኛ/ አቶ ብርሃኔ ገብሬዩ | የጉባዔው አባል |
| 35ኛ/ አቶ ንዋይ ወ/ፃዲቅ | የጉባዔው አባል |
| 36ኛ/ የመቶ አለቃ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ | የጉባዔው አባል |
| 37ኛ/ አቶ ወርቁ ሀ/ወልድ | የጉባዔው አባል |
| 38ኛ/ አቶ መንግሥቱ ለማ | የጉባዔው አባል |
| 39ኛ/ አቶ ደስታ ታንቁ | የጉባዔው አባል |
| 40ኛ/ አቶ ጌታቸው በላቸው | የጉባዔው አባል |
| 41ኛ/ አቶ ደርቤ ታፈሰወርቅ | የጉባዔው አባል |
| 42ኛ/ አቶ ግርማ | የጉባዔው አባል |
| 43ኛ/ አቶ ዳኛቸው | የጉባዔው አባል |
| 44ኛ/ አቶ ረዳኢ | የጉባዔው አባል |
| 45ኛ/ አቡነ ሳሙኤል | የጉባዔው አባል |
| 46ኛ/ አቶ ሻረው | የጉባዔው አባል |
| 47ኛ/ ሀጂ ሱሌማን | የጉባዔው አባል |

**ጊዜያዊ የሕዝብ መማክርት ሸንጎ አባላት ዝርዝር ከዚህ ዝርዝር ሊልቅ ይችላል። ሆኖም ይህንን ዝርዝር ለማግኘት ታላቅ ችግር የገጠመኝ ከመሆኑም ሌላ አንባቢ እንደሚያስተውለው የጥቂቶቹን የአባት ስም ለመፃፍ ያልቻልኩ ብቻ ሳይሆን በዚህ ታሪክ ስማቸው ያልተገለፁ አባላትም ሊኖሩ ይችላሉ። ላደርግ ከምችለው ውጭ ስለሆነ አዝናለሁ።**

**የልጅ ሚካኤል እምሩ ካቢኔ አባላት ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።**

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ልጅ ሚካኤል እምሩ | ጠቅላይ ሚኒስትር |
| 2ኛ/ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴ | የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ም/ጠቅላይ ሚኒስትር |
| 3ኛ/ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ | የግቢ ሚኒስትር |
| 4ኛ/ አቶ በለጠ ገብረፃዲቅ | የመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስትር |
| 5ኛ/ ሌ/ጀነራል አማን ሚካኤል አንዶም | የጦር ኃይሎች ኢታማጆርና የሃገር መከላከያ ሚኒስትር |
| 6ኛ/ ጓድ ዶክተር ኃ/ገብርኤል ዳኘው | የትምህርት ሚኒስትር |
| 7ኛ/ አቶ በላቸው አሥራት | የፍርድና ፍትህ ሚኒስትር |
| 8ኛ/ አቶ ተክለኝ ገዳሙ | የፖስታና የመገናኛ ሚኒስትር |
| 9ኛ/ አቶ መሐመድ አብዱራህማን | የንግድ ሚኒስትር |
| 10ኛ/ ዶክተር ጀማል አብድርቃድር | የጤና ጥበቃ ሚኒስትር |
| 11ኛ/ አቶ ነጋሽ ደስታ | የገንዘብ ሚኒስትር |
| 12ኛ/ ዶክተር ዳኛቸው ይርጉ | የግብርና ሚኒስትር |
| 13ኛ/ ጓድ ኃይሉ ይመኑ | የማዕድን ሚኒስትር |
| 14ኛ/ አቶ ተፈራ ኃይለሥላሴ | የሠራተኛና የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር |
| 15ኛ/ ኮሎኔል በላቸው ጀማነህ | የሃገር አስተዳደር ሚኒስትር |
| 16ኛ/ ጓድ ብርሃኑ ዋቀዮ | የፕላንና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር |
| 17ኛ/ ጓድ ሽመልስ አዱኛ | የስርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽነር |
| 18ኛ/ አቶ ይድነቃቸው ተሰማ | የወጣቶችና የስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር |
| 19ኛ/ ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ | በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚ/ዴኤታ |
| 20ኛ/ አቶ ተፈራ ደግፌ | የብሔራዊ ባንክ ገዥ |


ለንጉሣችሁ ፡ ተገዙ፡
ከእግዚአብሔር፡ የተሰጠ
ነውና፡፡
የተማሪ ድምፅ
ሕዝባዊ
መንግሥት
ይቋቋም
መሬት
ለአራሹ
የኢትዮጵያ
ወዝአደር
ደም

ፀደይ መኳሬት

## ምዕራፍ ሰባት

# ዘውዱን ለመገርሰስ የተደረጉ የመጨረሻ ዝግጅቶች

ወደ ነሐሴ ወር መገባደጃ ስንጠጋ ለአብዮቱ መንደርደሪያ የሚሆኑት በርካታ መሰረታዊ ሕዝቡን ያስደሰቱ ተግባሮች ከማከናወናችን ጋር የጉልታዊውን ማህበራዊ ሥርዓት አስከፊ ገጽታ ለማጋለጥና ሕዝቡን ለማንቃት የተደረጉት ጥረቶች በአብዛኛው ስኬታማ ስለነበሩ ሕዝቡ በበዝባዥና በጨቋኝ ገዥዎቹ ላይ ያደረበት ጥላቻ ለስር ነቀል ለውጥ አዘጋጅቶት ስለነበር፣ ዘውዱን ወደ መገርሰስ መሰናዶ አመራን።

ዘውዱን ለመገርሰስ ከተወሰዱት የመሰናዶ ርምጃዎች ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፣

1ኛ/ ንጉሡና በተለይም ንጉሣዊያን ቤተሰቦች በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች፣ በወለጋ፣ በከፋ፣ በሲዳሞ፣ በባሌና በአርሲ ወዘተ ክፍለ ሃገሮች የተከፋፈሉትን የአንበሳ ድርሻ የሆነ ሰፊና ለም የገጠር መሬት መጠን፣

2ኛ/ ከንጉሡ ጀምሮ ቤተሰባቸው፣ መሣፍንቱና መኳንንቱ በሽርክና ወይም (በሼር) አቋቁመው ይጠቀሙባቸው የነበሩትን የተለያዩ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋሞች፣ የሚያገላብጡትን ካፒታልና የአባላቱን የነፍስ ወከፍ ድርሻ መጠን በገንዘብ፣

3ኛ/ የአገሪቱ ርዕሰ ከተማ የአዲስ አበባ ብቸኛ ባለቤት በመሆን የተከፋፈሉትን የከተማ ቦታ መጠንና አይነት፣ መሬቶቹ የሚገኙበትን የከተማ ክልሎች ወዘተ በማመልከት፣

4ኛ/ የንጉሡንና የንጉሣዊያን ቤተሰቦችን፣ የመሣፍንቱን ቅምጣላ ኑሮ፣ ሠርግና ምላሽ፣ የሚመገቡባቸውን ከወርቅና ከብር የተሰሩ የቤትና የወግ እቃዎች፣ የውሾች መመገቢያዎችና መቃብር ሳይቀር በተንቀሳቃሽ ፊልም ተቀርጾ ሕዝቡ እንዲያስተውለውና እንዲሰማው፣

5ኛ/ የክብር ዘበኛው ክፍለ ጦር አባልና የንጉሡ አንጋች የነበሩ መኮንኖች፣ የቤተመንግሥቱ ሠራተኞችና አሽከሮቻቸው፣ የሚዛመዷቸውና የቤተመንግሥቱን ውስጣዊ ገበና እናውቃለን የሚሉ ግለሰቦች እኛ ሳንጠይቃቸው በራሳቸው ፈቃደኝነትና አነሳሽነት ወደ ደርጉ ጽሕፈት ቤት እየመጡ ንጉሡ ከመንገሳቸው በፊት ራስና እንደራሴ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ በስዊዝ ባንክ ገንዘብ ሲከቱ እንደኖሩ፣ በእንግሊዝና በሜክሲኮ ህንፃዎች እንዳሰሩ ወዘተ በመናገር የሰጡንን መረጃዎች በመመርኮዝ በጎድ ፍቅረሥላሴ ወግደረስ የሚመራ የደርግ ልዑካን ልከን የሚወደንና የምንወደው የሚሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሀብ እየሞተ ስለሆነ በባዕድ ሃገር ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ አውጥተው እንዲለግሱት በጽሑፍ

ጥያቄ አቀረብንላቸው "ለመሆኑ በሚልዮንና በቢልዩን የሚቆጠር ገንዘብ አይታችሁ ታውቃላችሁ?" ብለው በማፌዝ እንቢታቸውን ገለጹ፤

6ኛ/ እንቢታቸውን ለሕዝብ ይፋ ከማድረጋችን በፊት የአክስታቸው ልጅና አብሮ አደጋቸው የሆኑትን ልዑል ራስ እምሩን በአማላጅነት በመላክ በባዕድ ሃገር ያስቀመጡትን ገንዘብ በረሀብ እየሞተ ላለው ሕዝብ ቢቸሩት የፈፀሙትን በደል እንደሚያካክስላቸው፤ ስማቸውን ከማደስ ባሻገር ታሪካቸውንም እንደሚያሳምርላቸው በማሳሰብ ለሁለተኛ ጊዜ ጠይቀናቸው ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ያስቀመጥነው ገንዘብ የለም ማለታቸውን ለሕዝቡ በይፋ ገለጽን።

7ኛ/ ዘውዱን ለመገርሰስ ከተደረጉት መሰናዶዎች የመጨረሻውና ከባድ የነበረው የ1967 ዓ.ም የዘመን መለወጫ አጥቢያ የዓለም ሕዝብ እንዲያነባ ያደረገውንና በጆናተን ዲንበልቢ የተቀረፀ የወሎን ሕዝብ የረሀብ እልቂት የሚያሳየውን ተንቀሳቃሽ ፊልም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲታይ ማዘጋጀት ነበር።

ምስጢር ለመጠበቅ ሲባል የዘውዱን መገርሰሥ የመጨረሻ እቅድ የነደፍነውና ዝግጅቱን የሰራነው ጥቂት ጓዶች በመሆናችን የመሰናዶ ጊዜ ባልነው የነሀሴ ወር መገባደጃ ሳምንት ከተፈጠረው ፋታ የነሳን የሥራ ጫና ጋር በደርግ አካባቢ የነበረው ውጥረት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር የምንሰራው ሌሊትም ቀንም ያለ በቂ ምግብና እንቅልፍ ስለነበር ያሳምንት ለዘላለም በሕይወቴ እስካለሁ ድረስ የሚረሳኝ አይደለም። መውደቅ ቀርቶ የራስ ምታት እንኳን ስላልጎበኘኝ በጤንነት በመሥራቴም እስከ ዛሬ እደነቃለሁ።

ለዘመን መለወጫ አጥቢያ ምሽት የምናደርጋቸው ዝግጅቶች በሙሉ ተጠናቀው የቀሩን የመጨረሻዎቹ ሥራዎቻችን ሦስትና በሦስት ኮሚቴዎች የሚከናወኑ ነበሩ።

አንድኛውና የመጀመሪያው ሥራ፣ በመላ ኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞችና በአዲስ አበባ ሰላምና ፀጥታን ለማስከበር ጀነራል አማን ያሉበት በደርጉ የመከላከያና የደህንነት ኮሚቴዎች ቅንጅት ሌሊቱን ሲከናወን የነበረው፣ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ሳያቋርጥ በጦር ኃይሉ፣ በፖሊስ ሠራዊትና በየክልሉ አስተዳደርና ደህንነት ተቋሞች የመገናኛ ድር ለደርግ ማዕከል ይፈስ የነበረው ሪፖርት፣ ሠራዊት፣ ፀጥታ አስከባሪዎችና የደህንነት ኃይሎችን የማንቀሳቀስ ሥራ ነበር።

ሁለተኛውና ሦስተኛው በኔ የሚመሩት የሕግ ኮሚቴና የማስታወቂያ፣ የፕሮፖጋንዳና የቅስቀሳ ኮሚቴ የሚያከናወኗቸው ሥራዎች ነበሩ። እነሱም፣ ንጉሡ ከሥልጣን የሚወርዱበትንና ከእሳቸው በኋላ የሚቀጥለውን ሁኔታ በሕግ ወይም በአዋጅ መቅረጽ፣ አዋጁን የሚያጅብና የሚያብራራ ሰፊ መግለጫ ማዘጋጀት ናቸው።

ደርግ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመን መለወጫ አጥቢያ ድረስ የተከናወኑትና የሚከናወኑት ማናቸውም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ርዕዮተ ዓለማዊም ሆኑ ድርጅታዊ ሀሳቦች የሚመነጩት፣ የሚታሰቡት፣ የሚታቀዱትና ወደ ተግባርም እንዲተረጎሙ የተመሩት በደርጉ አባላት በራሳቸው ብቻ እንጂ ከደርግ ውጪ በመጣ ምክር ወይም ዲቃላ ሀሳብ አልነበርም።

አዋጁን ለማርቀቅ ይረዱን ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለሙያ የሆኑትን የሃገር አስተዳደር ሚኒስትር የነበሩትን ኮሎኔል በላቸውንና የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን አባል የነበረውን ሻለቃ ወንዳየሁ ምህረቱን ከውጭ አስጠርተን ከእኛ ጋር ቀላቅለናል።

በመከላከያና በፀጥታ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩትን ኮሚቴዎች ይመሩ የነበሩት ጄነራል አማን ሊቃ መንበራችን እንደመሆናቸው መጠን የአዋጁን ረቂቅ የመጨረሻ ይዘት እንዲያውቁት ከመስክ አስጠርቼ ሳነብላቸው ካዳመጡ በኋላ አንድ ሀሳብ አቀረቡልኝ።

ይኸውም "ንጉሡን ለአንዴና ለመጨረሻ አስወግደናል ከማለት ለምን አልጋ ወራሹን እንተካለን ብለን አንልም? አልጋ ወራሹ በሽተኛና አካለ ስንኩል መሆናቸውን ማንም ስለሚያውቅ እንደምንቀልድ የሚገነዘብ ሲሆን ሌላው ካለሕዝብ ፈቃድ ዘውዱን ገረሰሳችሁ ብሎ ሊከሰን አይችልም። ይህንን ብናደርግ ይጠቅመናል እንጂ የሚጎዳን አይመስለኝም" አሉኝ።

ይህ አስተሳሰብ በኔ አእምሮ ጨርሶ አልታሰበም። እሳቸው እንዳሉትም ይጠቅም እንደሆን እንጂ ጉዳቱ ስላልታዬኝ በእቅድ ኮሚቴው ላይ ተነጋግረንበት በቀላሉ ስለተስማማን አዋጁ በዚህ ሁኔታ እንዲሰራ አደረግን።

ጠዋት በጉባዔው አዳራሽ ሁላችንም ባለንበት በአገሪቱ የሁለት ሰዓት የራዲዮ ፕሮግራም አዋጁ ሲሰማ፣ እንዴት አልጋ ወራሹን ተክተናል የሚል አዋጅ እንሰማለን የሚለው ተቃዋሚ በአዳራሹ ሁካታ አነሳ።

የአልጋ ወራሹን መንገስ ወይም መተካት በመቃወም በመጀመሪያ የተናገረውና ቤቱን የቀሰቀሰው ጓድ ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ነበር። አዋጁን በመደገፍ ፍቅረሥላሴን በመቃወም የተነሳ አንድም የደርግ አባል አልነበረም። የተቃወሙት ሁሉ የተሰማቸውን ስሜት እየተነሱ በመግለጽ እስኪረኩ መድረኩን ለቀቁ ከቆየሁ በኋላ ሁሉም ዝም አለና ፀጥታ ሲሰፍን፣ አልጋ ወራሹን እናነግሳለን ያልንበትን ምክንያት በቀላሉ አስረድቼ ችግሩ ወዲያው ተወገደ።

ለ1967 ዓ.ም አዋቢያ ማታ የወሎ ሕዝብ የርሀብ እልቂት ተንቀሳቃሽ ፊልም ለሕዝብ ከመታዬቱ በፊት ለንጉሡና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ከዚህ የሚከተለው መልዕክት በራዲዮና በቴሌቪዥን ተላለፈ።

ለመስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም የዘመን መለወጫ አጥቢያ ምሽት ከደርጉ ለንጉሡና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተላለፈ መልዕክት፡

ለዛሬ የዘመን መለወጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያልሆነ ተስፋ ማቅረብ አንፈልግም። ምክንያቱም የአንገሽገሸው መሆኑን እናውቃለንና። በዛሬው ቀን እርጥብ አበባ ወይም የዘንባባ ዝንጣፊ ገፀ በረከት አናቀርብለትም። ምክንያቱም የአገራችን መልክምድር በተፈጥሮ አጋጣሚ ተመክኝቶ ተገጧልና።

እኛ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምናቀርበው በረከት የወንድሞቹን፣ የእህቶቹን፣ የአባቶቹንና የእናቶቹን ወዘተ ችግር ተረድቶ፣ የጨቋኝ አስተዳዳሪዎቹን ግፍ ተመልክቶ፣ ራሱን በራሱ አነቃቅቶ፣ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚዘጋጅበትንና በአንድነት ታጥቆ የሚነሳበትን መንገድ መክፈት ነው።

ከፋፍሎ መግዛትን የሕግ ጣኦት አድርገው የሚያመልኩት ገዥዎቻችን በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችም ከፋፍለውናል። በኪሎዋት በማሳበብ ቴሌቪዥን ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ውጭ እንዳይወጣ፣ ራዲዮ ጣቢያዎች ለይስሙላ በየጠቅላይ ግዛቱ ቢቋቋሙም በጥሩ ሁኔታ ዜናዎችንና ትምህርታዊ መግለጫዎችን እንዳያስተላልፉ በማድረግ የማዳመጥ ኃይላችንን ቀንሰውታል።

ስለዚህ የማየትና የማዳመጥ እድል ለማይደርሳችሁ ወገኖቻችን በእጅጉ እያዘንን፣ ዛሬ ማታ የዘመን መለወጫን ምክንያት በማድረግ የወሎን ሕዝብ ረሀብ እልቂት የሚያሳይ ፊልም በቴሌቪዥን የምናቀርብ መሆናችንን እየገለፅን በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የምትገኙትን ወገኖቻችን ይህንን አሳዛኝ የእልቂት ፊልም እንድትመለከቱልን ንጉሡንና ሕዝቡን የጋበዝን መሆናችንን እናስታውቃለን።

ኢትዮጵያ ትቅደም

1967 ዓ.ም እጥቢያ ምሽት የደርግ አመራር አካላት ብቻ ስንቀር አብዛኛው የደርግ አባላት በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ማዕዘናት ባሉ የሕዝብ መናኸሪያዎች፣ መሰብሰቢያዎች፣ ሆቴሎች፣ የምግብና የመጠጥ ቤቶች ወዘተ ተሰማርተው ሕዝቡ የወሎን ሕዝብ የርሀብ እልቂት ሲመለከት የሚታይበትን ስሜት እንዲያስተውሉ ተልከው ነበር።

በቤተመንግሥቱም ውስጥ ለንጉሡ በጣም ቅርብ የሆኑ የአብዮቱ ደጋፊና ተባባሪዎቻችን ንጉሡ የወሎን ሕዝብ እልቂት ስለመመልከታቸውና ከተመለከቱም የሚታይባቸውን ስሜት እንዲያስተውሉና እንዲያመለክቱን መመሪያ ሰጥተን ነበር።

ከደርጉ ለንጉሡና ለሕዝብ የተላለፈውን መልዕክትና እንዲሁም የፊልም ግብዣ መሠረት የወሎን ሕዝብ የረሃብ እልቂት የሚያሳየውን አሳዛኝ ትርኢት ለመመልከት ሕዝቡ በጉጉት ሲጠባበቅ አመሸ።

ዘግናኙን የወሎ ሕዝብ እልቂት የሚያሳየው ፊልም ከአገራችን ጉልታዊ መሣፍንትና መኳንንት፣ ከንጉሳዊያን ቤተሰብና ቤተዘመድ ምቾትና ቅንጦት ኑሮ ጋር እየተነጣጠረ ተቀንባብሮ፣ ጥላሁን ገሠሠ ዋይ ዋይ እያለ በሚያንጎረጉረው የኀዘን እንጉርጉሮ ታጅቦ እጅግ አሳዛኝ በሆነ ዝግጅት ቀረበ።

በከተማው ያሰማራናቸው የደርግ አባላት የሚያቀርቡልንን አስተያየት ሳንጠብቅ ለደርጉ ጽሕፈት ቤት እየደወሉ ከፊሉ ሀዘናቸውን፣ ከፊሉ ቁጣቸውን፣ የተቀሩት በፊልሙ አቀራረብ አድናቆታቸውን የገለጹ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብዙ ስለነበሩ የዝግጅቱ ተልዕኮ ከጠበቅነው በላይ ስኬታማ እንደነበረ ማወቅ ተቻለ።

ፊልሙን ያስተዋለው ሕዝብ ይሆናል ብሎ ያልጠበቀውና ያልገመተው እጅግ አስቃቂ የሆነውን የወገኑን እልቂት በማስተዋል የተሰማውን ቁጭትና ኃዘን ለመግለጽ ያስቸግራል። በሕዝቡ ላይ የታዬው እጅግ ከባድና መሪር ኃዘን ነበር።

ንጉሡ የፊልሙን አብዛኛውን ክፍል ለመመልከት ከሞከሩ በኋላ እሳቸውም ያንን የመሰለ እልቂት መድረሱን ስላላወቁና ስላልገመቱም ራሳቸውን ተቆጣጥረው እስከ መጨረሻው ድረስ ለመመልከት ስለተሳናቸው ያለወትሯቸው በጊዜ ወደ መኝታ ቤታቸው መሄዳቸውን ነው የተነገረን።

ያስተዋሉት እልቂት መንፈሳቸውን ክፉኛ እንደጎዳውና የመንግሥታቸውንም ውድቀት አምነው ለመቀበል እንደተገደዱ የሚያጠያይቅ አልነበረም። ከሥልጣን እንዲወርዱ በተጠየቁ ጊዜም ያንገራገሩትና የጠየቁት ነገር አልነበረም።

ከቤተመንግሥታቸው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ማረፊያቸው ከመጡ በኋላ እኔና ሻለቃ አጥናፉ በፊታቸው ገጽታ ላይ ያስተዋልነውና ያነበብነው ይሄንኑ ነው። የመቆጣት፣ የንዴት፣ እንዴት ተደፈርኩ? ይሄ ሊደርስብኝ አይገባም ብሎ የመገበዝ ስሜት ሳይሆን በሀፍረትና በኃዘን አቀርቅረው ሰው እንዳያያቸውና እሳቸውም ሰው ላለማየት መፈለጋቸውን ነው ያስተዋልነው።

ከሥልጣን መውረዳቸውን የሚያበስረውን ዜና ሕዝቡ ሲሰማ ደግሞ የምሽቱ ኃዘንና ቁጣ በከፍተኛ ደስታና ፌንጠዝያ ተተክቶ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የባህልና የፖለቲካ ድርብ ሕዝባዊ በዓል ሆኖ ዋለ።

መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም በምሽቱ የዜና ማሰራጫ ሰዓት ከሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ ለደርግና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት መጉረፍ ጀምሮ ከሳምንታት በላይ ለሆነ ጊዜ ሰነበተ።

መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ምሽት የመጀመሪያው የእንኳን ደስ አላችሁና ደስ ያለን መልዕክት ሰፋ ባለ ታሪካዊ ሀተታ በማጀብ የላከልንና ለሕዝብ በመጀመሪያ የቀረበው የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር የላከው መልዕክት ነበር።

መስከረም 1 ቀን ጠዋት በሁለት ሰዓቱ የዜና ማሰራጫ የራዲዮ ፕሮግራም የንጉሡ ከሥልጣን መውረድ ቢነገርም፣ ንጉሡ ከሥልጣናቸው የወረዱት ከጠዋቱ አራት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ለአንድ ሰዓት ያህል በተካሄደው ሥርዓት፣ ታዛቢ ልዑል ራስ እምሩ ባሉበትና ጋዜጠኞች በተገኙበት ቤተመንግሥት ነው።

ከሥልጣን መውረዳቸውን በአዋጁ መሠረት አሳውቆ ወደ ተዘጋጀላቸው ማረፊያ እንዲያመጣቸው ከደርግ የተላከው ቡድን የተመራው በሻለቃ ደበላ ዲንሳ ነበር። አምስት ሰዓት ተኩል ገደማ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ በተዘጋጀላቸው ቪላ ውስጥ ካረፉ በኋላ እኔና ሻለቃ አጥናፉ ወዳረፉበት ቪላ በመግባት የሚገባቸውን ያክብሮት ሰላምታ ሰጥተን በመቅረብ አነጋገርናቸው።

ስለጤንነታቸው ከጠየቅናቸው በኋላ ያረፉበት ቪላ ጊዜያዊ ማረፊያቸው መሆኑንና የጎደለው ነገር ካለም ለማሟላት ዝግጁ ነን ስላቸው፣ "ምንም አይደል እግዚአብሔር እንደፈቀደ እንኖራለን" አሉኝ።

ንግግሬን በመቀጠል እዚህ እንዲያርፉ የሆነው ለደህንነትዎ ሲባል ነው ስላቸው፣ "ለደህንነታችንም የሚያውቀው ሁሉን የሚችለው አንድ አምላክ ብቻ ነው" አሉኝ። በወቅቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ነበር።

እዚህ አብሮዎት ያሉት ሰዎች እርስዎ የሚያውቋቸው አገልጋይዎችዎ ናቸው። ማንኛውንም የሚያስፈልግዎትን ነገር ሁሉ ይዘዟቸው። በተረፈ መልካሙን ሁሉ እንመኝልዎታለን ብያቸው ልንወጣ ስንል፣ "ልጃችን ልዕልት ተናኘ ወርቅእንድትጎበኘን ይፈቀድላታል?" ብለው ስለጠየቁን መቻሉን ገልጸንና እዚያው ቆመን ልዕልቲቱ እንዲመጡ አዘን ስንሰናበታቸው "እናመሰግናለን" አሉ።

ከልዕልት ተናኜ በስተቀር ማንም እንዲጎበኛቸው ጠይቀውና ስለ ማንም ተናግረው አያውቁም። በጥያቄያቸው መሠረት ልዕልት ተናኜም በራሳቸውና በተቀሩት ንጉሣዊያን ቤተሰቦች ጥጋብና እብሪት ምክንያት ካረፉበት ቤተመንግሥት ወደ ወህኒ እስኪላኩ ድረስ ተለይተዋቸው አያውቁም። ሀኪማቸው ፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ በቋሚነት በሳምንት አንዴና ከዚያም በተጨማሪ በፈለጉ ጊዜ ይጎበኟቸው ነበር።

ንጉሡን ከሥልጣን ባወረደው አዋጅ ውስጥ ከተካተቱት አንቀፆች አንዱ፣ ደርግ ወደ ጊዜያዊ አስተዳዳሪ ደርግነት ተለውጦ ዘላቂ ሕዝባዊ መንግሥት እስኪቋቋም ድረስ የደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ በወል የርዕሰ ብሔርነቱን ሥልጣን ይዞ አብዮቱን እንደሚመራ ይገልጻል። ሌላው አንቀጽ ደግሞ የደርጉ ሊቀመንበር የደርጉን ጉባዔ በመወከል ስለ ርዕሰ ብሔር ሆኖ አገሪቱንና በተጨማሪ መስተዳድሩን ሲመራ፣ የደርጉ አንደኛና ተቀዳሚ ሊቃነ መናብርት ደርጉን ይመራሉ። ደርጉንና የደርጉን የዕለት ተዕለት ሥራም ይሰራሉ ይላል።

በእኔም ሆነ በተቀሩት የደርግ አባላት አስተያየት አስፈላጊና አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር በሽግግሩ ወቅት መስተዳድሩ በልጅ ሚካኤል ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዲመራ ፍላጎታችን ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ አብዮቱ ቢያንስ የአጭር ጊዜ ግቡን ሳይመታ ከደርግ አባላት መካከል ወደ ቢሮክራሲው ተግባር መዛወር አብዮቱን ለቅልበሳ ማዘጋጀት ነው ብለን

ስለምናምን እንዳችንም በነፍስ ወከፍ ርዕሰ ብሔር ወይም ርዕሰ መንግሥት የመሆን ዓላማም ፍላጎትም አልነበረንም።

ስለሆነም እዚህ ችግር ውስጥ ላለመግባት ስንል ጄነራል አማንን የደርጉ ሊቀመንበር አድርገን የርዕሰ ብሔርነቱን ሥራ እንዲሰሩ ሲፈለግ በሳቸው በኩል ደግሞ ከርዕሰ ብሔርነታቸው ሌላ የመከላከያ ሚኒስትርነታቸው እንደያዙ መስተዳድሩን ጨምረው መጠቅለል ቀደም ያለ ዓላማቸው አድርገው የተዘጋጁበት ኖሮ፣ የደርግ ሊቀመንበርና የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከሆኑ በኋላ የመከላከያ ሚኒስትርነቱ ከእኔ እጅ አይወጣም በማለት አምርረው በመከራከራቸው ስንፈቅድላቸው ደግሞ፣ "የደርግ ሊቀመንበርና የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር አድርጋችሁኝ ሳለ በመከላከያ ሚኒስትርነቱ ልጅ ሚካኤል ሊመራኝ ስለማይችል ወይም ስለማይገባ መስተዳድሩን መምራት እንዳለብኝ የሚያጠያይቅ አይደለም" የሚለው ምክንያታቸው የማያነቃንቅ ስለነበረ ልጅ ሚካኤልን ሳንወድ ከጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው ማውረድ ተገደድን።

ይህም በመሆኑ መስከረም 1 ቀን እኔና ሻለቃ አጥናፉ ንጉሡን በአዲሱ ማረፊያቸው ቤት ካነጋገርን በኋላ፣ ጄነራል አማን በአዲስ አበባ የነበሩ የዲፕሎማቲክ ኮር አባላትን እየተቀበሉ እንዲያነጋግሩ አሳስበን እኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤልንና መላውን ሚኒስትሮች ለማነጋገር ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሄድን።

ለምክር ቤቱ አባላት የንጉሡ ነገሥቱን ከሥልጣን መውረድና ምክንያቱን በመግለጥ ስለ ወደፊቱም ሁኔታ የደርጉን እቅድ ካስረዳን በኋላ እስከ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ድረስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ ጠቅላላው የምክር ቤቱ አባላት ስላሳዩን ትብብር አመስግነን ለወደፊቱም በምክር ቤቱ አባላት ላይ እምነት ያለን መሆኑን ገልጸን ሁሉም በአሉበት ሥራቸውን እንዲሰሩ ባቀረብንላቸው ጥያቄ ሲስማሙ፣ ስለ ዘውዱ ህልውና የወደፊቱ የደርግ አቋም ምን እንደሆነ የጠየቁን የባህል ሚኒስትራችን የነበሩት አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ብቻ ነበሩ።

አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የረጅም ጊዜ የተለያየ የሥራ ልምድና የዲፕሎማሲ ተመክሮ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ታዋቂ ደራሲም እንደመሆናቸው መጠን ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነገሥታቱን ዘመን ታሪክ በመጻፍ ላይ ያተኮሩ ብቻ ሳይሆኑ፣ ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣናቸው በሕግ ተገድቦ በኢትዮጵያ የንጉሣዊያን አመራር እንዲቀጥል ከሚደግፉ ኢትዮጵያውያን አንዱ ሆነው ሳለ፣ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔ ስብሰባ በነበሩበት ጊዜ ግን ይህንን ሀሳባቸውን ለጉባዔው ለማቅረብ ድፍረቱ አልነበራቸውም። አፄ ቴዎድሮስ

# ምዕራፍ ስምንት

# ደርግና ሌ/ጄነራል አማን ሚካኤል አንዶም

ከደርግ መቋቋም በፊት በሕዝባዊው አመጽ ሂደት ውስጥ የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አባል ወጣት መኮንኖች አማንን ከጡረታ ወደ ሠራዊቱ መልሶ ለማምጣት የነበረን ፍላጎት ይሳካ ዘንድ እሳቸውን ከሕዝብና ከማያውቃቸው ሠራዊት ጋር በማስተዋወቅ በአብዮቱ አገራቸውን ያገለግሉ ዘንድ ለሥራና ለሥልጣን ስናሰናዳቸው እንደነበረ በአንባቢያን ዘንድ ይታወሳል።

እኔ በሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ውስጥ በጣም ወጣት በነበርኩበትና በመቶ አለቃ ማዕረግ ደረጃ ከጄነራል አማን ጋር የተዋወቅኩትና በቅርባቸው የሰራሁት በ1950ዎቹ ውስጥ ማለትም፣ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ከ14 ዓመት በፊት ነው።

በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ከእሳቸው ጋር የነበረኝ ግንኙነት በዓመታት ውስጥ በተገኙ አጋጣሚዎችና በጉብኝት መልክ ነበር። በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክልል መለዮ ለባሾች የተወከሉትን ተወካዮች መርቼ ደርጉን ለማቋቋም አዲስ አበባ ከተማ በገባን ዕለት ምሽት እቤታቸው በመሄድ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም እንዲሆኑ የምናደርግ መሆናችንን ስገልፅላቸው በደስታ፣ ፈንድቀው ሲያሰናብቱኝ የተናገሩኝ ቃል "የእናንተን ውለታ መክፈል የሚቻል ነገር አይደለም። እንድታውቀው የምፈልገው ነገር እስከ መጨረሻ ታማኛችሁና ታዛዣችሁ መሆኔን ነው" በማለት ቢሆንም፣ ይህ ሰው ይህንን የሚለውን በርግጥ ሊያደርገው ይችል ይሆን? ብለው እንደ ተጠራጠሩ ከሁኔታቸው መረዳት ችያለሁ።

በኔ አስተያየት ጄነራል አማን የነቁ ሰው ቢሆኑም የተሳሉ ፖለቲከኛ አልነበሩም። ጥሩ ወታደራዊ ባለሙያ ስለነበሩ አገሪቱን ይጠቅማሉ ብዬ ያሰብኩት የጦር ኃይሎቻችንን በአዲስ መልክ እንዲያቋቁሙ፣ እንዲያዘምቱና ከሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር የማይቀረውን ውጊያ ስናደርግ፣ ጦሩን እንዲመሩ እንጂ የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው ከሚኒስትሮች ጋር በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲመክሩ አልነበረም።

የጦር ኃይላችንን እንዲያቋቁሙና እንዲያዘምቱ ስል፣ ከሰሜን አሜሪካ መንግሥት በርዳታም ሆነ በግዥ የጦር መሣሪያ እንደማናገኝ እውቅ በመሆኑ ከህብረተሰባዊ አገሮች የምንገዛቸውን መሣሪያዎች በተፋጠነ ሁኔታ ለሠራዊቱ በማስተዋወቅ ለውጊያ ብቁ ማድረግ እንዳለብን በማሰብ ነው።

አብዛኛውን የደርግ አባላት አግባብቼና አሳምኜ እሳቸውን ወደ ደርግ ሳመጣ ከ14 ዓመት በፊት የማውቀው አማን ናቸው በማለት ተስፋ ነበር። ከ14 ዓመት በኋላ በ1966 ዓ.ም ሰኔ ወር ያገኘኋቸው ሰው እኔ የማላውቃቸው ሌላ አማንን ነው።

ከባለቤታቸው ተለይተው፣ የሚያስቀና ትዳራቸውን አፍርሰውና ልጆቻቸውን የትም በታትነው መንግሥት በሰጣቸው አንድ አነስተኛ ቪላ ውስጥ አንድ ካለ ትግርኛ ቋንቋ በስተቀር ሌላ ቋንቋ ከማይናገሩና ከማያዳምጡ ምስኪን ሽማግሌ ዘበኛቸው ጋር የሚኖሩትን ኑሮ ተመልክቼ አይኔን ለማመን ነው የተሳነኝ።

በሠራዊቱ ውስጥ በነበሩ ጊዜ፣ ስለ እውነትነቱ እርግጠኛ ባልሆንም ሀኪም ከልክሏቸው ነው እየተባለ መጠጥ ፍፁም አይጠጡም፣ ትንባሆም አያጤሱም ነበር። በአብዮቱ ወቅት አልኮልና ትንባሆ ሲያዘወትሩ ከማየቴ ሌላ አንዳንድ ጊዜ የማይባቸው ጤናማ ሰው የማያደርገውን አባዜ ስለነበረ፣ እኚህ ሰው እፅዋት (ድራግ) ሳይወስዱ አይቀሩም ብዬ እስከ መጠርጠር ደርሻለሁ።

ሠራዊቱ ውስጥ በነበሩ ጊዜ ሰዓት አክብረው የሚያስከብሩ፣ የሥራ ፈረስ የተባለ ስም የተሰጣቸው አይነተኛ የጦር መኮንን ሞዴል የነበሩ ሰው አእምሯቸው ዝጎና በጣም ሰንፈው ነው ያገኘኋቸው።

ቀድሞ በነበረው በአንድ ወጣት የመቶ አለቃና በአንድ ጄነራል መካከል ባለው የጭፍራና የአለቃ ግንኙነት፣ ከዚያም ባሻገር በኔ ልጅነት ምክንያት ያላስተዋልኩት ወይም አዲስ በሽታ ይልከፋቸው አላውቅም፣ ሲበዛ ተጠራጣሪ፣ ሸረኛና ገደብ ያጣ የሥልጣን ጥማት ያላቸው ሰው ሆነዋል።

የጦር ኃይል ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ይሆናሉ ብዬ በገባሁላቸው ቃል መሠረት ሰኔ 26 ቀን 1966 ዓ.ም በደርጉ ጥያቄ፣ የደርጉ ተወካዮችና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባሉበት ከቤተመንግሥት ተጠርተው ከሜ/ጄነራልነት ወደ ሌ/ጄነራልነት አድገው የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ሆነው በተሾሙ ዕለት ምሽት፣ እኔ፣ የደርጉ የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳንና የደርጉ ዋና ፀሃፊ ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሃና ሆነን እንኳን ደስ አለዎት ለማለት እመኖሪያ ቤታቸው ሄደን ስንገናኛቸው ከእሳቸው የጠበቅነውን አቀባበል ቀርቶ ጥቂት ፈገግታ እንኳን ባለማሳየታቸው ተገረምን።

በእኛ ቀደምትነትና ኩርኩራ እንዲናገሩ በማድረግ ደስ ያለዎት አይመስሉም ብላቸው፣ ስለ እራሳቸው ረጅም የሥራ ልምድ፣ አገልግሎት፣ ትምህርትና እውቀት ወዘተ ብዙ ከተናገሩ በኋላ "የምታውቁኝ ይመስለኛል። እኔ በዚህ ጊዜና በዚህ እድሜዬ ሌላው ቢቀር በመከላከያ ውስጥ ከማንም ሲቪል ትዕዛዝ ለመቀበል ዝግጁ አይደለሁም። መከላከያ ሚኒስትር ልታደርጉ ያሰባችሁት ማንን ነው?" ብለው ጠየቁን።

እኔ በዛ አጭር ጊዜ ውስጥ ሰውየውን ለማወቅ በመቻሌ, ብዙ ባልደነቅም አብረውኝ የነበሩት ሁለቱ ጓዶች መገረም ብቻ ሳይሆን በጣም ተናደው ነበር። እስካሁን ድረስ በኛ በኩል ለመከላከያ ሚኒስትርነት የመረጥነው ሰው የለም። በእርስዎ በኩል የሚታሰብ ሰው እንዳለ ከሰሞኑ በዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ እመከላከያው ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንነጋገርበታለን። አሁን ስለመሸ እንድንሄድ ይፍቀዱልን ብያቸው ተለየናቸው።

ከሁለቱ ጓዶች ጋር በመንገዳችን ላይ ስንነጋገር፣ የጠየቁት መከላከያ ሚኒስትርነት እንደሆነ ሁላችንም ተገንዝበናል። በኔ አስተያየት የመከላከያ ሚኒስትር ለመሆን ወታደርነት ወይም ወታደራዊ ሙያ ግድ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት ስለሌለኝ ኢታማጆሩ በወታደራዊ ሙያ ብቃት ያለው መኮንን ከሆነ ሚኒስትሩ አብዮታዊ ፖለቲከኛ ምሁር ሊሆን ይቻላል ባይ ነበርኩ።



ሌ/ጄነራል አማን አንዶም ሚካኤል

በዚህ ረገድ የሁለቱ ጓዶች አስተያየት ግን ከኔ የተለየ ነበር። "የመከላከያ ሚኒስትሩ ወታደራዊ ሙያ ያለው ወይም ወታደር ቢሆን ከኢታማጆሩ ጋር የተሻለ መግባባትን ሊፈጥር ከመቻሉ ባሻገር እኛ ዛሬ ባለንበት አብዮታዊ የትግል ወቅት የማናውቀውን ሰው በመከላከያ ሚኒስትርነት ከምናስቀምጥ እሳቸው ቢሆኑ እንመርጣለን" ስላሉ በበነጋታው በመከላከያ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከመከርንበት በኋላ ለደርጉ ጉባዔ አቅርበን ስለተደገፉ የመከላከያ ሚኒስትር አደረግናቸው።

ንጉሡ "የመከላከያ ሚኒስትራችንን መሾም የነበረብን እኛ ነን ወይንስ ደርግ?" ብለው ጠቅላይ ሚኒስትራቸውን እንደጠየቁ በደርግና በሚኒስትሮች ምክር ቤት አገናኝ ኮሚቴ አማካኝነት ተነገረን። ጄነራል አማን የመከላከያ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም፣ ም/ኢታማጆር ሹም፣ የምድር ጦር አዛዥና ም/አዛዥ፣ የአየር ኃይል አዛዥና ምክትል አዛዥ፣ የባህር ኃይል አዛዥና ም/አዛዥ የሚሆኑትን መርጠን ለደርጉ ጉባዔ ከማቅረባችን በፊት ጄነራል አማን ባሉበት እመከላከያው ኮሚቴ ላይ እንነጋገርበት ዘንድ ጠርተናቸው ግዕከላችን በመገኘታቸው ውይይቱ ሲጀመር፣ የአየር ኃይሉና የባሕር ኃይሉን አዛዦችና ምክትል አዛዦች መሾም ሲስማሙ "የጦር ኃይሉንና የምድር ጦሩን ሥራ እኔ ደርቤ መሥራት ስለማይሳነኝ በአሁኑ ጊዜ አስፈላጊ አይደለም" በማለት ፍፁም ያለመቀበል ስለሞገቱን ውይይቱ መልኩን ከመለወጡ ወይም አቅጣጫውን ከመሳቱ በፊት ይህ አጀንዳ ይደር ይቆይና ጥቂት አጥንተን በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን በማለት ውይይቱን መግታት ነበረብኝ።

በኔም ሆነ በመከላከያው ኮሚቴ አባላት ግንዛቤ ግለሰቡ እስከ አሁንም የደርጉን ጉባዔ ወክለው እንደ ርዕሰ ብሔር ከመሥራት በላይ ጠቅላይ ሚኒስትርም ሆነው በተጨማሪ መከላከያ ሚኒስትርነታቸው የማያስፈልግ ብቻ ሳይሆን ያለ እሳቸው ሰው የሌለን ይመስል የሚያስገምተንም ስለነበረ ይህንን ለመቀነስ ወይም ለማሻሻል ጊዜና ሁኔታው ሲፈቅድ እንወስናለን የምንል ሆነን ሳለ የጦር ኃይሎች ኢታማጆር ሹምነትና የምድር ጦር አዛዥነቱም ሥልጣን ጨምሩልኝ ብለው መጠየቃቸው ያስገረመን ብቻ ሳይሆን ጤንነታቸውንም ተጠራጥረናል።

ከዚህ በኋላ ከዚህ በሚያስቸኩሉ ሥራዎች ተወጥረን በነበረበት ጊዜ ጄነራል አማን ለጦር ኃይሎችና ለምድር ጦር አመራር ይመጥናሉ ብለውን በውይይቱ ጊዜ ዝርዝራቸውን ያቀረብንላቸውን መኮንኖች ማለትም፣ ሜ/ጄነራል ግዛው በላይነህን፣ ብ/ጄነራል ባህሩ ቱፋንና ብ/ጄነራል ጌታቸው ናደውን፣ ለውጡን የማይደግፉና የኔንም አመራር የማይቀበሉ

ስለሆኑ ያለአግባብ ብልፅግናና በሥልጣን ብልግና ተወንጅለው ከታሰሩት መኮንኖች ጋር መቀላቀል ያለባቸው ናቸው በማለት ሊያሳስሯቸው በመከላከያ ሚኒስቴር ህንፃ ያለውን ጦር የሚያሳድሙ መሆናቸውን በዚያ ሠራዊት የተወከለው የደርግ አባል ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ ከእኛም ከሥራ አስፈፃሚው አካላት ሳይማከር ከበቂ ማስረጃ ጋር የደርጉ ጉባዔ ላይ አንስቶ በመናገሩ የደርጉ አባላት በጄነራል አማን ላይ የነበራቸው በጎ አስተያየት ሁሉ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተለወጠ ማለት ይቻላል።

በሀሰት የተወነጀሉት ከፍተኛ መኮንኖች ምንም ነገር ሳይደርስባቸውና ጄነራል አማንም ሳይጠየቁ በተፈለጉበት ስፍራ ተሾሙ።

ቀደም ብሎ ልጅ እንዳልካቸው ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜና እሳቸው የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ደርጉ በጥብቅ አደራና ምስጢር የሰጣቸውን የመከላከያ ጉዳይ አንዱንም ሳይሰሩ ወይም ሳይጀምሩ ቆይተው ልጅ ሚካኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ ሚኒስትሮችን መርጠው ለደርጉ ጉባዔ በማቅረብ በሚያሾሙበት ጊዜ እደርጉ ጽሕፈት ቤት በመምጣት እንደ ተለመደው እኔን በግል ተገናኝተውኝ፣ "በእንዳልካቸው መንግሥት የሃገር አስተዳደር ሚኒስትር የሆኑት ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴ ያለቦታቸው ነው። ሰውዬው ካላቸው የሥራ ልምድና ችሎታ አኳያ አገራቸውን የበለጠ የሚጠቅሙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቢሆኑ ነው። የልጅ ሚካኤል የእድሜ እንጋፋ፣ በማዕረግና በፕሮቶኮልም ቀደምት ስለሆኑ ቢያንስ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን ይገባቸዋል" አሉኝ።

ንግግራቸውን በመቀጠል "ይህንን ሀሳብ የማቀርበው የደጃዝማቹን ሞራል ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት መሣሪያ የመጠየቁን ጉዳይ ሊያከናውኑልን የሚችሉት እሳቸው በመሆናቸው ነው" አሉኝ።

ደጃዝማቹ ራሳቸው ቅሬታቸውንና እንዲሁም ፍላጎታቸውን በጄነራል አማን በኩል እንዲደርስን ጠይቀው እንደሆነ ወይም የጄነራል አማን የራሳቸው አስተያየት ይሁን ለእኔ ግልጽ አልነበረም። ጠቅላይ ሚኒስትር ስንመርጥ ከእሳቸው ምክር ስላልጠየቅን እንጂ እንደ ጄነራል አማን አስተሳሰብ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን የነበረባቸው ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴ ናቸው።

ልጅ ሚካኤል እምሩን እኔና እርስዎ ብቻ ሳንሆን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከእነ አባታቸው ወይም ከነቤተሰቦቻቸው ማለት ይቻላል መሣፍንታዊ መደባቸውን የናቁ ተራማጅና የሕዝብ ወገን መሆናቸውን ያውቃል።

ስለ ደጃዝማች ዘውዴ እርስዎ ምን ያህል ያውቃሉ? እኝህ ሰው ለእርስዎ የሰጠንዎትን የመከላከያ ምስጢርና ገበናችንን ማወቅና መካፈል ያለባቸው ናቸው ብለው ያመኑበት ምክንያት ምንድነው? የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

"ይህንን ሳላመዛዝን እንዲህ ያለ ሀሳብ ይዞ ይቀርባል ብለህ የምታስብ ከሆነ እኔ ደግሞ በበኩሌ ጥያቄ ላቅርብልህና ለመሆኑ እኔንስ ታምኑኛላችሁን?" በማለት የቅሬታና የቁጣ ገጽታ ስላሳዩኝ እንደተለመደው እንደ ልጅ አባብዬ ለደርጉም አቀርባለሁ ብዬ ተለየኋቸው።

እኔና የደርጉ የአመራር አካላት የሆኑ ጓዶች ጄነራል አማንን ይህንን ያህል የምንከባከባቸውና የምንታገሳቸው ከሁሉ በፊት እንባቢ እንደሚያስታውሰው ለኔ በገቡልኝ ቃል መሠረት ምናልባት የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሊረዱን ይችሉ ይሆናል በሚል ተስፋ ሲሆን ሌላው፣ በሕዝቡና በሠራዊቱ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ለማድረግ ስንል ከሚገባቸው በላይ ከፍ ያለ ስም ስለ ሰጠናቸውና ስለ ካብናቸው ብቻ ነው።

ስለሆነም በእሳቸው ጥያቄ መሠረት ደርጉ ጉባዔ ላይ አቅርቤ በማስወሰን የልጅ ሚካኤል እምሩ ካቢኔ ሲቋቋም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይጠይቁንና ሳያሳስቡን እኛም ሳንገልጽላቸው ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ም/ጠቅላይ ሚኒስትር አደረግናቸው።

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የተለያዩ የሥራ ልምድ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ሃገር ወዳድና የአብዮቱ ፅኑ ደጋፊ የሆኑ ብዙ ሰዎች ስለነበሩ፣ ደጃዝማቹ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው እንደተሾሙ፣ "አንደኛ በኒው ዮርክ የኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲ ጽሕፈት ቤት የተቀመጡ ከፍተኛ ምስጢርነት ያላቸው ሰነዶች በደጃዝማቹ እጅ ከመግባታቸው በፊት በአስቸኳይ ወደ ደርጉ ጽሕፈት ቤት እንዲወሰዱና በሁነኛ ስፍራ ላይ እንዲቀመጡ፣ ሁለተኛ ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት መሣሪያ ለመጠየቅ ስለሚታሰበው ጉዳይ በጥብቅ የምናስጠነቅቀው ደጃዝማቹ ብዙ ዝርዝር ነገር ከማወቃቸው በፊት ይሄን የሚመለከተው ሥራ ከውጭ ጉዳይ ተወስዶ በደርጉ ጽሕፈት ቤት በደርጉ አባላት ብቻ እንዲካሄድ ነው።" በማለት አመለከቱን።

ጄነራል አማንን፣ ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት እንድንጠይቅ ስለታሰበው መሣሪያ ጉዳይ ምን ተደረገ? የትስ ደርሰናል ብዬ ብጠይቃቸው በደጃዝማች ዘውዴ በኩል እየተሰራ ነው ከማለት በስተቀር ምንም ሊያስረዱኝ አልቻሉም።

የተቀነባበረ ጉዳይ ይሁን ወይም የአጋጣሚ ነገር አገራቸውን ከድተው በጀርመን ሃገር ለረጅም ጊዜ ይኖሩ የነበሩትን የቀድሞ ጓደኛቸውን ኮሎኔል ተስፋ ደስታ የሚባሉትን መኮንን ጄነራል አማን በምስጢር ወደ ኢትዮጵያ ጠርተው ሁለቱ እየተወያዩ መሆናቸውን መረጃ ስለደረሰን የኮሎኔል ተስፋ ደስታን ማንነትና ተልዕኮ ለማወቅ ብርቱ ጥረት አደረግን።

ጄነራል አማንና ኮሎኔል ተስፋ ደስታ የተገናኙባቸው ምክንያትና የሚወያዩባቸው አጀንዳዎች ለማወቅ ከመቻላችን በፊት ሰውየው በመጡበት ሁኔታ ሹልክ ብለው ስለሄዱ ለማወቅ የቻልነው ኮሎኔሉ የአሜሪካ ሰውና ከአሜሪካኖች ተልዕኮ ያላቸው መሆኑን ብቻ ነው።

ኮሎኔሉ ተመልሰው በሄዱ ሰሞን ለጄነራል አማን ስልክ ደውዬ ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት መሣሪያ የመጠየቁን ጉዳይ ይርሱት አያስፈልገንም በማለት ጉዳዩን እኛው ራሳችን በከፍተኛ ምስጢር እንዲከናወን አደረግን።

የምስጢርነቱ ጉዳይ ይህንን ያህል የሚያሳስበን በኢራን መንግሥት በኩል ከአሜሪካ እንዲገዙ ገንዘብ የተከፈለባቸው ተዋጊ አውሮፕላኖችን እንዳንነጠቅ ነበር። በተደረገው ከፍተኛ ጥረት አውሮፕላኖቹና ራዳሮቹ ሲደርሱን ለብዙ መሣሪያዎች የሰጠነውን ቅድሚያ ክፍያ አጠናቀናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ይህንን ታላቅ ተግባር ያከናውኑልናል የተባሉት ደጃዝማች ከወራቶች በኋላ ለተባበሩት መንግሥታት አመታዊ ስብሰባ ወደ ኒው ዮርክ ስለሄዱ ለመሆኑ እኚህ ሰው ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ጋራ ንግግርስ ጀምረዋል ወይም የመሣሪያ ጥያቄ አቅርበዋል ለሚለው ጥያቄያችን መልስ ለማግኘት ስንል ሞስኮ ያለውን የኢትዮጵያ ኤምባሲና እንዲሁም አዲስ አበባ የሚገኘውን የሶቭየት አምባሳደር ብንጠይቃቸው ስለዚህ ጉዳይ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነገሩን። ደጃዝማቹም ከኒው ዮርክ ወደ አገራቸው አልተመለሱም።

በዚሁ ሰሞን በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ጄነራል አማን ደርግ ጽሕፈት ቤት በመምጣት በኤርትራ ክፍለ ሀገር ለመርማሪ ኮሚሽን አባልነት ስለተመረጠውና ወቅቱ በሰሜን አሜሪካ የግል ሥራ እየሰራ አካለ ስንኩል ሆኖ የተወለደ ህፃን ልጁን

እያሳከሙ ስለሆነው ዶክተር በረከት "ለልጁ መታከሚያና ለቤተሰቡ መተዳደሪያ ይሆነው ዘንድ መንግሥት በየወሩ ሁለት ሺ ዶላር በቋሚነት እንዲያዝላቸው" ሲሉ አሳሰቡኝ።

ዶክተር በረከት በኤርትራ ክፍለ ሀገር ሕዝብ የተመረጡትና የመርማሪ ኮሚሽን አባል የሆኑት ፈልገው በፈቃዳቸው እንጂ በመንግሥት ታዘው ወይም ተገደው እንዳልሆነ፣ ይህም ባይሆን እንዲህ ያለ ነገር እስከዛሬ ለማንም ያላደረግንና የማናደርግም ስለሆነ ዶክተር በረከት ለእርስዎ ባላቸው ቀረቤታ ይህንን ማድረግ ትክክል አይመስለኝም የሚል መልስ ስለሰጠኋቸው አኩርፈው ሥራቸውን ትተው ለብዙ ቀናት አሞኛል በማለት እቤታቸው ተኙ።

ቤታቸው በተኙበት ጊዜ ከእኔ ወይም ከእኛ የሚጠይቃቸው ሲያጡ ለሻለቃ አጥናፉ አባተ ስልክ ደውለው መኖሪያ ቤታቸው በመጥራት "እራሴን ትልቅ ሰውና የሃገር መሪ አድርጌ ለዶክተር በረከት ርዳታ ይደረግልሃል ብዬ ቃል ገብቼ ሻለቃ መንግሥቱ አዋረደኝ!" በማለት ይነግሩታል። ሻለቃ አጥናፉ ከሌሎች የደርግ አመራር ላይ ካሉ ጥቂት ጓዶች ጋር ይሆኑና ወደ እኔ መጥተው "ከጄነራል አማን ጋራ በገንዘብ ተጣሉ ከምንባል ሁለት ሺ ሳይሆን አንድ ሺ ዶላር ፈቅደን ይህንን ችግር እናስወግድ" በማለታቸው ገንዘቡ ተፈቀደና እሳቸውም ወደ ሥራቸው ተመለሱ።

ዶክተር በረከት አገሩንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድቶ ራሱን ሻዕቢያ በማለት ከሚጠራው ገንጣይ ድርጅት ጋር ከተቀላቀለም በኋላ ይከፈለው የነበረውን ገንዘብ ተከታትሎ ያስቆመ ሰው ስላልነበር ለብዙ ጊዜ ሲጠቀምበት መኖሩን መረዳት የቻልነው በአንድ ሌላ አጋጣሚ ብዙ ዘግይተን ነበር።

ጄነራል አማን መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም የደርግ ሊቀመንበር፣ የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር፣ ርዕሰ መንግሥትና የመከላከያ ሚኒስትር መሆናቸው የሰጣቸውን ደስታ የበረዘባቸው ብቻ ሳይሆን በጣም ያሳዘናቸው የደርጉ ጉባዔ በወል ርዕሰ ብሔር መሆኑና እሳቸው ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር ከመባል ፋንታ የደርጉ ጉባዔ ወኪልና የሚኒስትሮች ሰብሳቢ መባላቸው ነበር።

ይህንን ቅሬታቸውን ለጥቂት ቀን እንኳን ሸፍነው ማቆየት ስለተሳናቸው ዛሬ እለተ ቀኑን በማላስታውሰው በመስከረም ወር እህታቸው ቤት ምሳ ጋብዘውኝ "ለመስከረም 1 አጥቢያ ንጉሡን ከሥልጣን ለማውረድ ያረቀቃችሁትን አዋጅ ረቂቅ ስታነብልኝ አሁን የማነሳልህን ነገር ላነሳ ያልፈለኩት በከባድ ሥራ ከመወጠርህ በላይ በጣም ተዳክመህ ስላየሁህ እንጂ በሰራችሁት ሥራ በጣም ነው ያዘንኩት።

በዓለም ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ደርግ በምትሉት መላቅጡ በጠፋ መንግሥት መመራታችን የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ዓለምን ሲያስቅና ሲያስደንቅ የቆየ ቢሆንም መስከረም 1 ቀን ከዘውዱ ጋር መፍትሄ ሳታገኙለት አትቀሩም ተብሎ ሲጠበቅ አንድ ንጉሥ አውርዳችሁ 120 ሰው ማንገሳችሁ ማንንም አስገርሟል።

"መንግሥቱ! እንዲህ ልንቀጥል አንችልም አብዮቱ ግቡን መቷል። የደርግ ተልዕኮ አብቅቷል አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል" አሉኝ።

ሀሳባቸውን ለመረዳት፣ በተለይም አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ሲሉኝ መፈንቅለ ደርግ ያዘጋጁ ስለመሰለኝ ሀሳባቸውን ለመረዳት እንዲቻለኝ ሳስጨርሳቸው ፈልጌ "ምን አይነት መፍትሄ ነው የምንፈልግለት?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

"እኔ ፕሬዝዳንት፣ አንተ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የደርጉ ከፍተኛ የአመራር አካል የሆኑትን መኮንኖች ለምሳሌም እነ ሻለቃ አጥናፉንና መሰሎቹን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ሚኒስትሮች በማድረግና የቀሩትንም በሲቪሉ አስተዳደርና በመከላከያው ሠራዊት ውስጥ መበተን ነው።" አሉኝ።

የገረመኝ ነገር ገደብ ያጣው የሥልጣን ጥማቸው ሳይሆን የደርግና የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ተልዕኮ እሳቸውን መጨረሻው የሥልጣን ማማ ላይ እስከ ማውጣት ድረስ ብቻ አድርገው ለኔ ሲናገሩ ጥቂት እንኳን ሊያስቡ ያለመቻላቸው ነበር። ስለዚህም ከእሳቸው ጋር መሥራት ሳይሆን ለጥቂት ጊዜም መቆየቱ በጣም አደገኛ መሆኑም ግልጥ ብሎ ታየኝ።

"ጄነራል እርስዎን ከጡረታ ጠርቶ ከአንዱ ሥልጣን ወደ ሌላው እያሸጋገረ ዛሬ ካሉበት ደረጃ ያደረሰዎት ይሄ መላቅጡ የጠፋ እያሉ የሚጠሩት ደርግ ወይም የደርግ መንግሥት ነው። ይህንን ጥያቄ በዚህ ይዘት ካቀረቡት ዘንድ የእኔንም አስተያየት በጥንቃቄና በጥልቀት ለማዳመጥ እንዲሞክሩ በታላቅ ትህትና እጠይቅዎታሁ።

ደርግ በመላው በኢትዮጵያ ሕዝብ ባይመረጥም በዚያ ቀውጢና ፈተና ጊዜ ለአገሪቱ ታላቅ ሃላፊነት ባለውና በአስተዋፅዖ ድርሻውም ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል እጅግ በሚልቀው መለዮ ለባሽ የተመረጠ ነው። እስቲ ሰላማዊ ወይም ዲሞክራሲያዊ ሕይወት በሚመሩት በየትኛውም አገሮች ውስጥ አመራር የሚሰጡትን የሕዝብ መማክርት ጉባዔዎችና እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች መጠናቸውም ሆነ አሰራራቸውን እንዴ በአይነ ህሊናዎ ለመቃኘት ይሞክሩ።

ደርግ መለዮ ለባሽ ከመሆኑና በታሪክ አጋጣሚና በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ከተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ከመውጣቱ በስተቀር ቅድም ካነሳኋቸው የየአገሩ የፖለቲካ አመራር አካላት ልዩነቱ ምንድነው?

የምናካሄደው አብዮት ነው፤ ያም ሆኖ ደርግ አንድም የሕዝቦች ምክር ቤትን በሌላም መልኩ የፖለቲካ ፓርቲን ክፍተት ዘግቶና ተክቶ ሲመራ የተቀሩትን የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት እያቋቋመ ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋናው እርስዎ የሚመሩት ሕግ አስፈፃሚው ወይም መስተዳድሩ ነው። ጄነራል ብዙ ማለት ይቻላል ይሄ ሁሉ ደግሞ ሲሆን ደርግ ጊዜያዊ ነው።

ይህንን ተቋም እናፈርስና በእርስዎ ፕሬዝዳንትነትና በእኔ ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንተካው ማለት ለሃገርና ለወገን ምንም አይነት ፋይዳ ለማስገኘት ሳይሆን ሌላ ተልዕኮ ወይም አጀንዳ ያላቸው ግለሰቦች የሚያከናውኑት ተግባር ስለሆነ በዚህ አመለካከትዎና አስተሳሰብዎ ከእርስዎ ጋር ልቆም ቀርቶ እርስዎን አጥብቄ የማሳስብዎት ለእኔም ለእርስዎም ለኢትዮጵያ ሕዝብም ከማይበጀው አደገኛ የጥፋት መንገድ እንዲመለሱ ነው" አልኳቸው።

በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም ደርግን በተመለከተ ጄነራል አማን ብቻ ሳይሆኑ የብዙ ሲቪልና ወታደራዊ እቋም ከመስከረሙ የተለየ ነበር። ደርጉ እንደተቋቋመ የደርጉን ዓላማ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን የጦር ኃይሎች ዓላማ ጭምር በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ለሰበሰብነው የአዲስ አበባና ለአካባቢው መለዮ ለባሽ ንግግር ባደረኩበት ጊዜ፣ ደርጉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ እንጂ ራሱን በጉልታዊው ገዢ መደቦች የመተካት ዓላማ ስለሌለው አብዮታዊ ተልዕኮውን ካሟላ ወደ ጦር ሰፈሩ ይመለሳል ብዬ መናገሬን በመንቀፍ ጄነራል አማን በመከላከያ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤታቸው ከእኔ ጋር የደርጉን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጠርተው ከዶክተር መሥፍን ወ/ማርያም ጋር በመሆን "እንዴት ወደ ጦር ሰፈራችን እንመለሳለን ብለህ ትናገራለህ" በማለት ወቅሰውኝ ነበር።

በእህታቸው ቤት ምሳ ጋብዘውኝ ደርጉን ለመበተን ሃሳብ ባቀረቡ ማግስት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልክ ደውለው "በአዲሱ ዘመን መግቢያና በአሮጌው የፖለቲካ ሥርዓት ፍፃሜ የጦር ኃይላችንን መጎብኘት ተገቢ መስሎ ይታየኛል ምን ይመስልሀል?" ብለው ጠየቁኝ።

"የአሮጌው ሥርዓት ፍፃሜ ሳይሆን የአመታት መለዋወጥ ነው" ካልኩ በኋላ "እንዳሉትም ከዘውዱ መገርሰስ በኋላ ርዕሰ ብሔር ስለሆኑ ክርዕሰ ከተማችን እርቀው የሚያደርጉትን ጉብኝት የደርጉ ጉባዔ ማወቅና መፍቀድ ስላለበት ጥቂት ጊዜ ስጡኝ" በማለት ተለየኋቸው።

ለደርጉ ጉባዔ አቅርቤና በበጎ መንፈስ ተተርጉሞ ጦሩን እንዲጎበኙ ስለተፈቀደ ይሄው የተነገራቸውና ጉብኝቱን በምሥራቅ የአገሪቱ ክልል በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ያለውን ሠራዊት መጎብኘት ጀምረው በጦር ክፍሉ ሲዘዋወሩ ለጦሩ አዛዦች የሚነግሯቸው ደርግን ለማፍረስ ለእኔ ያቀረቡትን ሀሳብ ነበር።

"የደርጉ ተልዕኮ እዚህ ላይ አብቅቷል አብዮቱ ግቡን መቷል፤ አንድ ንጉሥ አውርደን 120 ንጉሥ በማንገሳችን የዓለም መሳለቂያ ብቻ ሳይሆን በዚህ አይነት መሥራትም አይቻልም።

ሻለቆቹ በጣም አብጠዋል (በደርጉ ውስጥ ያለነውን ሻለቆች ማለታቸው ነው)፤ ሰው የሚነግራቸውንና የሚመክራቸውን አይሰሙም። ጦሩ ይህንን አውቆ የላካቸውን ወኪሎቹን በአስቸኳይ መልሶ እንዲጠራ ማድረግ አለባችሁ" ነበር ሚሉት።

ሠራዊቱና የሠራዊቱ አዛዦች ከጄኔራል አማን የተሻለ ንቃት ስለነበራቸው፤ "እንዴት የደርጉ ተልዕኮ አብቅቷል፤ አብዮቱ ግቡን መቷል ብለው ይናገራሉ?" ብለው በመገረምና ጄነራሉ ፀረ-አብዮት ሴራ ያራምዳሉ ብለው በመገመት አብዛኛዎቹ አዛዦች ሪፖርት አቀረቡልን።

ከጄነራል አማን በሰላምና በጥበብ የምንለየው መቼና እንዴት ነው? እያልኩ እራሴን በምጠይቅበት ጊዜ ሰውየው ሳንዘጋጅ ወደ አንድ ትልቅ ችግርና ጥፋት እንዳይገፉን በማለት ከሐረርጌ እንደተመለሱ ጽሕፈት ቤታቸው ሄጄ፤ ደርግን እንበትን ብለው ያቀረቡልኝን ሀሳብ ለማንም እንዳልተናገርኩና እጅግ አደገኛ ነገርም በመሆኑ በሁለታችንም ዘንድ በጥብቅ ምስጢርነት እንዲጠበቅ አሳሰብኳቸው።

እንዲህ ያልኩበት ምክንያት እንዴ ዘባርቁያለሁ ሳልቀደም ልቅደም በሚል ተስፋ መቁረጥ ወደ ለየለት አደገኛ ጥፋት እንዳያመሩ ስል ነበር። እንደገመትኩትና እንዳሰብኩት ይህንን ስነግራቸው የመደሰትና የመዝናናት ስሜት ከገጻቸውና ከጠቅላላ ሁኔታቸው ለማንበብ ችያለሁ።

"እኔም በአንተ ላይ ባለኝ እምነት ለአንተ ብቻ እንጂ እንዲህ ያለውን ነገር ከማንም ጋር መነጋገር ስለማይቻለኝ ለማንም አልተናገርኩም" ሲሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ታላቅ ውሸት ዋሹኝ።

ከዚህ በላይ በዚያው ሳምንት ውስጥ በየአሥራ አምስቱ ቀን ሀሙስ በሚደረገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ እኔም እየተጠራሁ በቋሚነት እገኛለሁና ለስብሰባው አጥቢያ ረቡዕ ዕለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚኒስትር ዴኤታ ደረጃ የምክር ቤቱ ጸሐፊና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳት የሆኑት ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ ስልክ ደውለው "አጣዳፊና በጣም ከባድ ነገር ስለገጠመኝ እርስዎ ማወቅ አለብዎት ብዬ ስልክ በመደወሌ ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ" አሉ።

ግድ የለም በየቢሯችን ስልክ የተቀመጠው ለእንደዚህ አይነቱ ሥራ ነውና በእኔ በኩል እንዲህ ያለ ችግር የለም ካልኳቸው በኋላ "ስለ ኤርትራ ጉዳይ እርስዎና ጄነራል የተነጋገራችሁት ወይም በደርጉ ጉባዔ የተወሰነ ነገር አለ?" ሲሉ ጠየቁኝ።

እኔ እስከማውቀው በቅርቡ ስለ ኤርትራ የተነጋገርነው ነገር የለም ስላቸው፣ "ለኤርትራ የፌደሬሽን ሥልጣን የሚሰጥ ሕግ ረቂቅ በአቃቤ ሕጉ በአቶ አማኑኤል አምደሚካኤል አስረቅቀው በነገው የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ለውሳኔ እንዲቀርብ በአጀንዳ ይያዝ ዘንድ ታዝዣለሁ። የረቂቁም በርካታ ቅጅ በእጄ ላይ ይገኛል" አሉኝ።

ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ጄነራል አማን እጅግ በጣም አደገኛ ሰው ከመሆናቸው ባሻገር አእምሯቸው ጤናማ መሆኑን መጠራጠር የጀመርኩት በዚህ ጊዜ ነበር። ለፊታውራሪ ደምሴ፣ እንዲህ ያለ ነገር እኔም ሆንኩ ደርግ የማናውቅ ብቻ ሳይሆን ይህንን የማድረግም ሥልጣን የለንም፣ እርስዎ የታዘዙትን ያድርጉ፣ ነገ እኔና ሻለቃ አጥናፉ ስብሰባው ላይ እንገኛለን አልኳቸውና ይህንኑ ለሻለቃ አጥናፉ ስነግረው፣ እሱም በበኩሉ "እኚህ ሰው እውነት ይህንን ካደረጉ ጤነኛ አይመስሉኝም" አለ።

በበነጋታው ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ተገኝተን ምላተ ጉባዔ ስለነበር አጀንዳና የተለያዩ ሰነዶች ታድለውን ጉባዔውን ጄነራል አማን ከፈቱና ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ ስለተዘጋጁት አጀንዳዎች የተለያዩ መግለጫዎችን በመስጠት ከምንመለከታቸው ጉዳዮች ጋራ አስተዋወቁን።

የመጀመሪያውን አጀንዳ በተመለከተ ለግንዛቤ ይበጅ ዘንድ በአስረጅነት አቶ አማኑኤል አምደሚካኤል ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠየቁ። አቶ አማኑኤል በኋላ ጓድ በዚያ ጉዳይ ከዚያ በፊት ደርግም የሚኒስትሮች ምክር ቤትም የተወያየበትና መሰረታዊ ፖለቲካ ውሳኔ ላይ ተደርሶ ወደ ሕግ እንዲተረጎም የተመራ የመሰላቸው ይመስለኛል የተረቀቀውን ሕግ አንቀጽ በአንቀጽ እየተነተኑ ከማስረዳት በተጨማሪ ስለ ኤርትራ የሚያውቁትን ማጠናከሪያ መረጃ ጭምር ካቀረቡ በኋላ ጄነራል አማን በበኩላቸው የሚሉትን ብለው የምክር ቤቱን አባላት ለውይይት ጋበዙ።

ሚኒስትሮቹ በሙሉ ረቂቁን አንብበውታል። የጉዳዩንም ክብደት በሚገባ የሚገነዘቡ ናቸውና ከዚያ በኋላ ይጠባበቁ የነበሩት ጄነራል አማን እንደ ጋበዙት ለውይይት ሳይሆን 'በዚያ አጀንዳ ላይ ለመወያየት ምክር ቤቱ ሥልጣን አለው ወይ?' የሚል ጥያቄ ስለነበራቸው፣ ሁሉም እኔና ሻለቃ አጥናፉ ምን እንደምንል ለመስማት በጉጉት በመጠባበቅ ይመለከቱን ነበር።

እኔ ቅድሚያውን በመውሰድ "ይህ የሕግ ረቂቅ ከአንድ ታላቅ የፖለቲካ ውሳኔ መመንጨት ያለበት ይመስለኛል። በእኔ አስተያየት ይህንን የመሰለውን ታላቅ የፖለቲካ ውሳኔ ለመወሰን የሚያበቃ የፖለቲካ ተቋም በአሁን ጊዜ በኢትዮጵያ ያለ አይመስለኝም።

በጊዜው ያለው ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ወይም ተቋም ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብቻ ይመስለኛል። ስለዚህ ጉዳይ ደርግ የሚያውቀው ነገር የለም። ይህ ምክር ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም።

ስለዚህ እኔ የማቀርበው ጥያቄ፣ ይህ ጉዳይ እንዴት እዚህ ቀረበልን? ማንስ ነው ያቀረበው? ለዚህ መልስ እፈልጋለሁ" ካልኩ በኋላ የደርጉን አቋምም ሆነ የራሱን በተመለከተ ጓድ አጥናፉ የሚናገረው ይኖረዋል በማለት ንግግሬን አቆምኩ።

ጓድ ሻለቃ አጥናፉ "እኔም የነበረኝ ጥያቄ ጓድ ሻለቃ መንግሥቱ ያቀረበው ጥያቄ ስለነበር ለጥያቄው መልስ ከመሻት በስተቀር የምጨምረው አይኖርም" በማለት ተናገረ። ዘለግ ላሉ ደቂቃዎች በቤቱ ዝምታ ሰፈነ።

በሁሉም ሚኒስትሮች ገጽታ ላይ ጥያቄው የእኛም ጥያቄ ነው ብሎ የመርካት ይመስላል በፊታቸው ላይ የፈገግታ ፀዳል ይታይ ነበር። በደንባችን በስብሰባ አዳራሽ ውስጥና በስብሰባ ላይ ትንባሆ ማጤስ አይፈቀድም። ጄነራል አማን ለጥያቄው መልስ ይሰጣሉ ተብሎ ሲጠበቅ ፒፓቸውን አውጥተው በመለኮስ ቤቱን ካጡት በኋላ የቡና እረፍት እናድርግ ብለውን እሳቸው ቀድመው ከስብሰባው ክፍል በመውጣት ወደ ጽሕፈት ቤታቸው ገቡ።

እኔና ሻለቃ አጥናፉ ወትሮም እንደምናደርገው እሳቸውን ተከትለን ወደ ጽሕፈት ቤታቸው ስንገባ ሚኒስትሮቹ በሆንዓው ኮሪዶር ላይ ሻይና ቡና ይጠጡ ነበር። ከቡናው እረፍት በኋላ የምክር ቤቱ አባላት ሁሉ ወደ ስብሰባው አዳራሽ በመግባት ወንበራቸውን ይዘው ሳለ ጄነራል አማን ገብተው ሳይቀመጡ በቁማቸው "እራሴን ስላመመኝ ስብሰባውን የሚመራው ሻለቃ መንግሥቱ ነው" ብለው በመውጣት ወደ ቤታቸው ሄዱ።

እኔ ለምክር ቤቱ አባላት የመጀመሪያውን አጀንዳ በተመለከተ ጊዜና ሁኔታዎች ሲፈቅዱና አስፈላጊ ሲሆን አግባብ ባለው መድረክ ይቀርብ ይሆናል እስከዚያ ግን በተቀሩት ጉዳዮች ላይ እንወያይ በማለት የእለቱን ስብሰባችንን አጠናቀን ተለያየን።

እኔና ሻለቃ አጥናፉ ይህንን ታሪክ ለደርጉ ጉባዔ ቀርቶ ለደርጉ አባላትም አልተናገርንም፤ ብንናገር ኖሮ አማን ከሥልጣናቸው መባረር ብቻ ሳይሆን ከጓደኞቻቸው ጋር ይቀላቀሉ እንደነበር እርግጠኞች ነን።

ከዚህ በፊት እንዳደረጉት በእሳቸው ብሶና አኩርፈው፣ እቤታቸው ቢተኙና ከሥራ ገበታቸው ቢቀሩ ከሳቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መገላገላችን ይሆናል ብለን ወስነን ነበር።

በበነጋታው ማለዳ ጽሕፈት ቤታቸው ስደውል መግባታቸውን ስለ ገለጹልኝ ከሻለቃ አጥናፉ ጋር ጽሕፈት ቤታቸው በመሄድ፣ "በቅድሚያ በሰጡን ተስፋ መሠረት የኤርትራ ገንጣዮች በእውነት ምን እንደሚፈልጉ ማወቅ ያስፈልጋል። የምንፈልገው የሰላም መፍትሄ እነሱም በተለይም የኤርትራ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብም የሚስማሙበት እንጂ እኛና እርስዎ የምንገምተው ወይም መፍትሄ ነው ብለን የምንለውን መሆን የለበትም።

እኛ ሁላችንም ገንጣዮቹ የሚፈልጉት ፌዴሬሽኑ እንዲመለስ ከሆነና ፌዴሬሽኑን በመመለስ የኢትዮጵያዊያን ደም መፍሰሱ የሚቆም ከሆነ በበኩላችን ደስታውን አንችለውም። ለዚህ ግብ ግን የሚሰሩ ብዙ ሥራዎችና ቅድመ ሁኔታዎች አሉ።

ዛሬ የሠራዊቱንና የሕዝቡን ስነ-ልቦና ለእንደዚህ አይነቱ ውሳኔ ሳናዘጋጅ ድንገት ተነስተን የኤርትራ ሕዝብ ራሱ ያፈረሰውን ፌዴሬሽን መልሰናል ብንል ለኤርትራ ችግር መፍትሄ ከመሆን ፈንታ የእኛ መጥፊያ ነው የሚሆነው። በዚህ ይመኑ" አልናቸው።

እሳቸውም "ረቂቁን በትክክል አንብባችሁ እንደሆነ ፌዴሬሽን የሚል ነገር የለበትም። ኤርትራ ክፍለ ሀገር ራሱን የቻለ አስተዳደር ሆኖ ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከርዕሰ ብሄሩ ጋር ብቻ ነው የሚል ነው" አሉ።

"ከሁሉ በፊት እርስዎና አቶ አማኑኤል እንዳሰባችሁት በብዙ የግንኙነት ድር የተሳሰረውን አንድ ክፍለ ሀገር ከርዕሰ ብሄሩ ጋር ብቻ በሚደረግ ግንኙነት ይሰራል መባሉ ሳይንሳዊ አይደለም አይሰራም።

አሁን ወደዚያ ክርክር ሳንሄድ፣ ጄነራል እንዲህ የሚያስቡማ ከሆነ በጣም የዋህነት ነው። ግመል ሰርቆ እየጎተቱ እራስን እንደመደበቅ ያለ ነገር ነው። እርስዎ ስም የለሽ ፌዴሬሽን ቢሉትም አሁን የሚያስኬድ ነገር አይደለም። በመጀመሪያ ከወንበዴዎቹ የሰላም ንግግር ይጀመር። ይህ ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው" ብለን ባቀረብነው ሀሳብ ለጊዜው ተስማማን።

የደቡብን ጦር ከጎበኙ በኋላ ወደ ኤርትራም እሄዳለሁ ብለውን ተለየናቸው። እንዳሉትም አራተኛ እግረኛ ብርጌድን ለመጎብኘት ነገሌ ቦረና ሄዱ። የአራተኛ ብርጌድን ጠቅላይ ሰፈርና ከሶማሊያ መንግሥት ጋር በሚያዋስነን ጠረፍ ላይ በተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙትን የብርጌዱን ተዋጊ ሻለቆችና የብርጌዱን ጠቅላይ ሰፈር ለመጎብኘት በተዘዋወሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ከጦሩ አዛዦች ጋሬ ባደረጓቸው ውይይቶች አንድና ብቸኛ ጉዳይ በሐረርጌ እንዳደረጉት ሁሉ ደርግን ስለመበተን ነበር።

ጄነራል አማን ወደ ሰሜኑ ክፍለ ሀገራችን ኤርትራ ሄደው የክልሉን መለዮ ለባሾችና የክፍለ ሃገሩን የተለያዩ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ በከረን ከተማ የከረንን ሕዝብ ሰብስበው፣ "ኤላብሬድ ላይ ሰላማዊውን ሕዝብ የፈጁ የክፍለ ሃገሩ ፖሊስና የሁለተኛ ክፍለ ጦር አባሎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይደረጋል" ብለው ተናገሩ።

ኤላብሬድ የሚባለው ስፍራ በአሥመራና በከረን መካከል ያለ አትክልትና ፍራፍሬ የሚያለሙና የቀንድ ከብት የሚያረቡ ገበሬዎች የሚኖሩበት ትንሽ መንደር ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ጎንጣዮች በዚህ መንደር ውስጥ አድፍጠው በጦሩና በፖሊስ ክፍሎች ላይ ከፍ ያለ አደጋ አድርሰው በጦሩም በወንበዴውም ላይ የሞትና የመቁሰል ጉዳት ደርሶ ነበር።

ይህ ንግግራቸው በመላው ኤርትራ ሲሰማ፣ ለአንድነት ለተሰው ለእነዚያ ጀግኖች መታሰቢያ እናቆምላቸዋለን ከማለት ፋንታ እንዴት ዛሬ ኤርትራ መጥተው ከሞት የተረፉት ለፍርድ ይቀርባሉ ብለው ይናገራሉ በማለት የክልሉ መለዮ ለባሾች የመወያያ አጀንዳ ሆኖ ይሰነብታል።

በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላና በምዕዋ ያደረጉትን ጉብኝት አጠቃለው አሥመራ በመግባት፣ በአሥመራ ከተማና በአካባቢው ያሉትን መለዮ ለባሾች ሰብስበው ለማናገር ስፍራው ደርሰውና የክብር ሰላምታ ተቀብለው ለንግግር በተሰናዳላቸው መድረክ ላይ ሲቆሙ ከተሰበሰበው ሠራዊት መካከል አንድ የሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ባልደረባ የሆነ የሃምሳ አለቃ እጁን ከፍ አድርጎ በማንሳት "ክቡር ጄነራል ንግግርዎን ከመጀመርዎ በፊት እኔ የምናገረው አለኝ" ይላቸዋል።

ትንሽ እንደ መገረም ይላቸውና "ወደዚህ ውጣና የምትናገረውን ተናገር" ይሉትና፣ ከሠራዊቱ መካከል ወጥቶ ፊትለፊት በመቆም "ጄነራል አማን እኛ እርስዎን አናውቅዎትም። ደርግ ነው የሚያውቅዎት። ደርግ ለምን ዓላማ ወደ ኤርትራ እንደላከዎትም አይገባንም። እኔ በዚህ ሠራዊት ስም ልነግርዎት የፈለኩት፣ ኤርትራ ጭቃ ውስጥ ገብተው ከመጨማለቅዎ በፊት እንዲህ እንዳማረብዎት አሁኑኑ ወደ አዲስ አበባዎ እንዲመለሱ ነው የምመክርዎ" ይላቸውና ወደ ነበረበት ሰልፍ ተራ ይመለሳል። የተሰበሰበው ሠራዊት በሙሉ ከዳር እስከ ዳር የሃምሳ አለቃውን ንግግር በመደገፍ አካባቢውን በማያባራ ጭብጨባ ከማድመቅ ባሻገር 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚባለውን የጊዜውን ተወዳጅና ዝነኛ አብዮታዊ መዝሙር በሕብረት መዘመር ይጀምራል።

አዛዦቹ ማቆም አልቻሉም። ጄነራል አማን በመናደድ ንግግሩን ሳያደርጉ ወደ ቤተመንግሥት ይመለሱና ሠራዊቱም ይበተናል። ቤተመንግሥት እንደደረሱም ወደ አዲስ



ሌ/ጀነራል አማን ኤርትራን በጎበኙበት ወቅት

አበባ ስልክ ይደውሉና፣ እሳቸው ጡረታ ላይ በነበሩበት ጊዜ እንደሳቸው ጡረታ ወጥተው በዘውድ ምክር ቤት አማካሪነት አብረዋቸው ይሰሩ የነበሩትን የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጆች፣ ቢትወደድ አስፌሃ ወ/ሚካኤልንና ንቡረዕድ መላከሰላም ዲሜጥሮስ ገብረማርያምን በፖሊስ ታድነው ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር እንዲታሰሩ ያዛሉ።

ንቡረዕድ መላከሰላም ዲሜጥሮስ ገብረማርያም የኦርቶዶክስ ቤተክህነት ምሁርና የፖለቲካ እውቀት ያላቸው ግምባር ቀደም የኤርትራ ነፃነትና የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ትግል ታላቅ አርበኛ ናቸው። የኤርትራ ፌዴሬሽን በኤርትራ ሕዝብ ምክር ቤት ሙሉ ድምፅ ፈርሶ የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ፍፁም በሆነበት ጊዜ የምክር ቤቱ ም/ፕሬዝዳንት የነበሩና የአንድነት ግንባታው ሁለተኛ መሀንዲስ ናቸው ተብሎ ይነገርላቸዋል።

ቢትወደድ አስፍሃ ወ/ሚካኤል በፋሽስት ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን በቅኝ ገዥው መንግሥት ውስጥ በሲቪል ሠራተኝነት ተቀጥረው የአስተርጓሚነትና የፖለቲካ አማካሪነት ሥራ በመሥራት ከሃገር ተወላጆች ከፍተኛ ስፍራ የነበራቸው እንደ ውስጥ አርበኛ ለወገኖቻቸው ብዙ በጎ ነገሮችን ያበረከቱ እንደሆኑ ይነገራል። በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያም በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች የአስተዳደር ሥራና ወደኋላም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ በመሥራት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ሥራ ልምድ ያካበቱ ብቻ ሳይሆን ኤርትራን ነፃ በማውጣትና ብሎም ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ መቀላቀል ይደረግ በነበረው የፖለቲካ ትግል ከፍ ያለ አስተዋፆ ያደረጉ ሰው ናቸው።

ከኤርትራ ነፃነት ግኝትና ፌደሬሽኑ ከተመሠረተ በኋላ በኤርትራ የንጉሠ ነገሥት ምክትል እንደራሴ ሆነው የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ ለንጉሡና ለዋናው እንደራሴ ረዳትና ዋና አማካሪም ነበሩ። በመጨረሻ ፌዴሬሽኑ በፈረሰበት ጊዜም ከምክትል እንደራሴነታቸው ጋር የኤርትራ አስተዳደር መሪ ሆነው በመመረጣቸው ፌዴሬሽኑን በማፍረስ የኤርትራና

የኢትዮጵያ አንድነት ፍፁም እንዲሆን የኤርትራን ሕዝብ ወክለው የሰሩ ዋና መሀንዲስ ናቸው ተብሎ የሚነገርላቸው የአንድነት ኃይል በነበሩት የኤርትራ አርበኞች፣ የሃገር ፍቅር ማህበር አባላት፣ በኤርትራ ሕዝብና በተቀረውም የመሃል ሃገር ኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቁ፣ የተከበሩና የተወደዱ ስለነበሩ ጄነራል አማን ካሰሯቸው በኋላ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአሥመራና በአዲስ አበባ ነዋሪ በሆኑ አያሌ ወዳጆቻቸው የተደረገው እንቅስቃሴ ታላቅ የፖለቲካ አቧራ አስነሳ።

በአሥመራ የሃገር ፍቅር ማህበር አባላት ከጄነራል አማን ጋር የነበሩትን የደርግ አባላት እየቀረቡ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት በማለት በግምባር ቀደምትነት ታግለው ያታገሉንን መሪዎቻችን በአዲስ አበባ እንዲታሰሩ የተደረገው ማንን ለማስደሰት ነው? ጄነራል አማን ኤርትራ የመጣው ለዚህ ነው?" ሲሉ በአዲስ አበባም በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ደርግ ጽሕፈት ቤት የሚደወለው ስልክ ብዙ ነበር።

ጉዳዩ ለእኛም ዱብ ዕዳ ቢሆንም ጄነራል አማን በበኩላቸው ምክንያት ይኖራቸዋልና ወደ አዲስ አበባ እስከሚመለሱ ድረስ በትዕግስት መቆየቱ ይሻላል ብለን ጠብቅን።

በጄነራል አማን የተመራው የደርግ ልዑካን ወደ አዲስ አበባ በተመለሰ ማግስት እሁድ ቀን የኤርትራን ጉብኝት የሚመለከተውን ሪፖርት ለማቅረብ የተሰናዱ መሆናቸውን በመግለጽ በደርግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲደመጡ ስለጠየቁ ወደ አራት ሰዓት ገደማ በደርግ ጽሕፈት ቤት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መሰብሰቢያ ክፍል ተሰበሰብን።

ጄነራል አማን የክልሉን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታ፣ የሠራዊቱንና እንዲሁም ኀንጣዮቹ የሚያካሂዱትን የትጥቅ ትግል በተመለከተ ከፋፍለው በቅደም ተከተል ካቀረቡ በኋላ በኤርትራ ጭቃ ውስጥ ገብተው እንዳይጨማለቁ ያላቸውን የሃምሳ አለቃ ጉዳይ አንስተው ከፍ ባለ እልህና በቁጣ ከተናገሩ በኋላ የሃምሳ አለቃው በእስር ወደ አዲስ አበባ ተልኮ ፍርድ እንዲያገኝ በመጠየቅ ገለጣቸውን አበቁና "ምናልባት መናገር ካለብኝ ነገር የሳትኩት ቢኖር የደርጉ አባላት ሊያክሉበት ይችላሉ" በማለት አብረዋቸው ወደ ኤርትራ የሄዱትን የደርግ ቡድን አባላት ጋበዙ።

የደርጉ ቡድን መሪ የነበረው መኮንን እሳቸው ባሉት ወይም በረሱት ማሟያ ሳይሆን አብረን የቆየንበት የሥራ ባህሪ ስላስገደደን በበኩላችንም እንዲሁ ሰፋ ያለ ዝግጅት ስላለን ገለጣ እናደርግ ዘንድ ይፈቀድልን በማለት ጠይቆ በሰጠሁት የዓይን ጥቅሻ ሪፖርቱን ቀጠለ።

የመኮንኑ ሪፖርት በኤርትራ አከናወንን ከሚሏቸው ፋይዳዎች ይልቅ በደርጉ አባላትና በጄነራል አማን መካከል በነበረው ያለመግባባት ላይ ያተኮረ ሆኖ ከአቀረባቸው ፍሬ ሀሳቦች ጥቂቶቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፣

1ኛ/ ወደ ኤርትራ ስንላክ በደርጉ የተሰጠን ትዕዛዝና መመሪያ፣ በጄነራል አማን መሪነት እና በሕብረት እንደ አንድ ቡድን እንድንሰራ ቢሆንም ይሄ የእሳቸው ፈቃድና ፍላጎት ስላልነበረ አብረናቸው ሄደን አብረናቸው ተመለስን እንጂ ኤርትራ በቆየንበት ጊዜ እኛን አላቀረቡንም።

2ኛ/ በየአውራጃዎቹና በአሥመራም ቤተመንግሥት ብዙ የክፍለ ሃገሩን ነዋሪዎች እየጠሩ ሲያነጋግሩ እኛን ለማካፈል ካለመፈለጋቸው ሌላ ከሃገር ፍቅር አባሎች ወይም ከኤርትራ አርበኞች አንድም ሰው ባለማነጋገራቸው፣ እኛ በአረፍንበት ሆቴል ድረስ በመምጣት "ጄነራል አማን የአንድነት ጸሮችን ሲያነጋግር እኛን ያገለለበት ምክንያት ምንድነው?" በማለት በብስጭት ስሜት ጠይቀውናል።

3ኛ/ የከረንን አውራጃ በጎበኙበት ጊዜ የከረንን ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ሰብስበው ሲያናግሩ፣ “በኤላብሬድ የንፁሃን ሰላማዊ ዜጎችን ደም ያፈሰሱት ወታደሮች ለፍርድ ይቀርባሉ” ብለው በመናገራቸው የክልሉ ሠራዊት ለእነዚያ ጀግኖች መታሰቢያ እንዲቆምላቸው ከማድረግ ፋንታ እንዴት በሕይወት የተረፉትን ወንጀለኛ አድርገው ለፍርድ ይቅረቡ ይላሉ በማለት የጄነራል አማን ንግግር በሠራዊቱ ውስጥ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ መሰንበቱን ተገንዝበናል። በአሥመራ ከተማና በዙሪያዋ ያሉትን መለዮ ለባሾች ለማነጋገር በቀረበ ጊዜ በአንድ የሃምሳ አለቃ የተሰነዘረው የብልግና ንግግር የዚህ ውጤት ነው ብለን እንገምታን።

4ኛ/ ጄነራል እዚያ በነበሩበት ጊዜ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረትና አሁንም እዚህ እንዳሳሰቡት በሃምሳ አለቃው ላይ አንድ እርምጃ ቢወሰድ ከሠራዊቱ ጋር ትልቅ ቅራኔ ውስጥ እንደምንገባና ትልቅ ችግር እንደሚፈጠር ስለማያጠራጥር ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግ ዘንድ እናሳስባን።

5ኛ/ ጄነራል ሊያነጋግሩት የተሰበሰበው ሠራዊት በዚያ አሳዛኝ ሁኔታ ተበትኖ ሁላችንም ወደየማረፊያችን ሄደን ባረፍንበት ሆቴል የሃገር ፍቅር ማህበር አባላት ለሁለተኛ ጊዜ መጥተው “ለኤርትራ ነፃነትና ብሎም ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት ታግለው ያታገሉንን መሪዎቻችንን ጄነራል አማን ወደ አዲስ አበባ ስልክ ደውሎ ዛሬ አሳሰራቸው የሚል ዜና ደርሶናል። እንዴት እንዲህ ይደረጋል? ማንን ለማስደሰት ነው? አማን ወደ ኤርትራ የተላከው ይህንን እንዲያከናውን ነው?” በማለት ከፍ ባለ የብሶት ስሜት አነጋገረውናል።

በመጨረሻም ሪፖርታችንን ለማጠቃለል ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አጥብቀን የምናሳስበው በኤርትራ ክፍለ ሀገር የዚህ ቡድን ተልዕኮ ከገንቢነቱ ይልቅ አፍራሽነቱ ያደላ ወይም የጎላ ስለሆነ በተለይ የኤርትራ አንድነት አርበኞችንና የክልሉን ሠራዊት ስሜት ለመለወጥ ሌላ ቡድን እንዲላክ ነው” በማለት ንግግሩን አበቃ።

የመኮንኑ ንግግር ለጄነራል አማን የጥፊ ያህል ሲሆን በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በኩልም ፍፁም ያልታሰበና ያልተጠበቀ ድንገተኛ ዱብ እዳ ነበር።

“በአሥመራ የደረሰብኝ ውርደት አንሶ እዚህ ደግሞ በእነዚህ እንደዚህ እሰደባለሁ?” በማለት የምሬት ቃላቶችን ሲወረውሩ፣ የደርጉ አባሎች እፀፋውን በመመለስ በድጋሚ እንዳያዋርዷቸው ፈጥኜ የሻይ እረፍት በማለት ነገሩን መግታትና አዝማሚያውን መለወጥ ነበረብኝ።

በሻይ ቡናው እረፍት ጊዜ የደርጉ ቡድን ሪፖርት ከባድ ስለነበረ ጄነራሉ በንዴት ለሚወረውሩት ቃላት የደርጉ አባላት መልስ እንሰጣለን ብለው ሁኔታውን ወደባሰና ወደማያስፈልግ አቅጣጫ ላለመምራት እንድትታገሱ በማለት ማስጠንቀቅ ነበረብኝ።

ከእረፍት በኋላ ወደ መሰብሰቢያው ክፍል ተመልሰን እንደተቀመጥን ጄነራል አማን “እነዚህ ሰዎች ስለ እኔ ተልዕኮና ስለ ኤርትራ ሁኔታ የሚያውቁት ነገር ካለመኖሩ ሌላ በቆይታችንም ጊዜ ስለ ተከናወነው ነገር ግንዛቤ የሌላቸው ናቸውና የምናገረው አለኝ” ሲሉ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በእርስዎ ጥያቄ የተሰበሰበው እርስዎ የሚያቀርቡትን ሪፖርት ለማዳመጥ እንጂ የተልዕኳችሁን ውጤት ለመመርመር ስላልሆነ ይህንን ጉዳይ በሌላ መድረክ በሰፋት እንወያይበታለን።

ለክቡርነትዎ አንድና የመጨረሻ ጥያቄ አቅርቤ የዛሬውን ስብሰባ ብንዘጋው የሚሻል ይመስኛል ብዬ ያቀረብኩትን ሀሳብ እሳቸውም ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ስለተቀበሉት እኔ የመጨረሻ ያልኩትን ጥያቄ ከዚህ እንደሚከተለው አቀረብኩ።

ጥያቄውም፣ "ቢትወደድ አስፈሃ እና ንቡረዕድ ዲሜጥሮስ በመታሰራቸው በአዲስ አበባና በአሥመራ ከተሞች ብዙ የሕዝብ ጥያቄዎች ቀርበውልን ለመልሱ እርስዎን መጠባበቅ ነበረብን" የሚል ነበር።

ሁለቱን ግለቦች እንዲታሰሩ ያደረጉበትን ምክንያት ከማስረዳት ፋንታ "ፊውዳሎች ሲታሰሩ ይሄ የመጀመሪያ አይደለም። የእነዚህን መታሰር የሕዝብ ጥያቄ ያደረገው ነገር ምንድነው?" በማለት መልሰው ጥያቄ አቀረቡልኝ።

እነዚህን ሰዎች ለኤርትራ ነፃነትና ብሎም ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት ትግል ማምባር ቀደም አርበኞች ስለሆኑ በኤርትራም ሆነ በመሃል ሃገር በጣም የታወቁ የተከበሩና የተወደዱም ስለሆኑ በእኛ በኩል የታሰሩበትን ምክንያት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው አልኳቸው።

"እናንተ ከእነሱ አጫፋሪዎች እንደ ሰማችሁት የኤርትራ ነፃነትና አንድነት አርበኞች ሳይሆኑ ኤርትራን የሸጡ ከሀዲ የሃገር ነጋዴዎች ናቸው" አሉ። በሰጡን መልስ ከእኔ ጀምሮ እዚያ የተገኙት የደርግ አባላት በሙሉ በጣም ከመገረም የተነሳ ለጥቂት ደቂቃዎች እርስ በእርሳችን መተያየት ሆነ። ጄነራሉም ቢሆኑ ሳያስቡና ሳይጠነቀቁ በግንፍል ስሜት ከጥርሳቸው የወረወሩት መልስ በእኛ በኩል የሚሰጠውን ትርጉም ሳይረዱ እንዳልቀሩ ከገጻቸው ይነበብ ነበር።

"እነዚህ ከሀዲዎችና የሃገር ነጋዴዎች የሚሏቸው ሰዎች ኤርትራን ለማን ነው የሸጡት?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ እሳቸውም "አያችሁ! ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ዛሬ ሁለቱንም አገሮች እንዲህ ያለ ችግር ውስጥ መክተት ለእኔ ከሀዲነትና ነጋዴነት ነው" አሉን። እኛም የእለቱን ስብሰባ በዚሁ አቆምን።

እኛ ብንሳሳት ያርሙናል፣ ብንጣላ ያስታርቁናል፣ ብለን ያመጣናቸው ሰው ብዙ ስህተቶችን ሲሰሩ ከኢትዮጵያ አንድነት ጋር የተያያዙ ባለመሆናቸው የጄነራል አማን ኢትዮጵያዊነት ቀርቶ ሃገር ወዳድነታቸውን እንኳን ጥያቄ ውስጥ የከተተ አልነበረም።

ከዚህ በላይ በጠቀስነው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ስለ ሁለቱ የኤርትራ ታላላቅ አርበኞች የእሳቸውን አቋም ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ ከእሳቸው ጋራ አልነበርንም። በኋላም ሕይወት ለሚያስከፍል አደጋ የዳረጋቸውም ይሄው በኢትዮጵያና በኤርትራ አንድነት ጉዳይ ላይ ያላቸው የተደበቀ አቋምና የተደበቀ ምኞታቸውን ለማስፈፀም የሞከሩት እኩይ ተግባር ነበር።

ይህንን በተናገሩ ማግስት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ለእኔ ስልክ ደውለው "ትናንትና እነዚያ የደርግ አባሎች ባደረሱብኝ ከፍ ያለ ዘለፋና ስድብ እራሴ ስለዞረ በእውነት ነው የምልህ የተናገርኩትን አላውቅም። ኤርትራ ሄጄ ያከናወንኩትን ጉዳይ በሌላ መድረክ ላይ እንወያይበታለን ብለህ ስለነበር፣ አጥናፉ የሕግ፣ የፖለቲካና የእቅድ ኮሚቴዎች ሊቃነመናብርት ባሉበት ብቻ በደርጉ ጽሕፈት ቤት ተገናኝተን ባስረዳና ብንወያይበትስ?" ብለው ስለጠየቁ በበኩሌም ደስ ብሎኝ በበነጋታው እሳቸው በጠየቁት መሠረት ተሰበሰብን።

"ኤርትራ በቆየሁበት ጊዜ ብዙ ጠቃሚ ሀሳብ ያላቸውን የሃገር ሽማግሌዎችና የበረሽኞቹም ወላጆች ከሆኑ ሰዎች ጋር ተገናኝቼ ስለ አዲሲቱ ኢትዮጵያና ደርጉ የኤርትራን

ችግር ከፍ ያለ ቅድሚያ የሰጠውና ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለምፍታት ያለውን ብረቱ ፍላጎትና አቋም አስረድቻለሁ።

ከእነሱም ሁሉም ማለት ይቻላል በሰጡኋቸው መግለጫ ተደስተው “መንግሥት የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እርስዎ እንዳሉት ልባዊ ፍላጎት ያለው ከሆነ እኛ በችግሩ የምንሰቃየው ኤርትራዊያን መንግሥትን ከበረኸኞች ጋር ለማገናኘት ፍቃደኞች ነን በዚህ ረገድ የሚቻለንን ሁሉ እናደርጋለን” ብለውኛል አሉን።

ይህንን እንዴት፣ የትና መቼ ለማድረግ ወይም ሥራውን ለመጀመር እንዲቻላችሁ በመንግሥት በኩል ሊደረግላችሁ የሚገባውን ድጋፍና እቅዳችሁን አቅርቡልኝ በማለት የሦስት ቀን ጊዜ ሰጡኋቸው።

በሦስተኛው ቀን ሁሉም ሳይሆኑ ሽማግሌዎቹን የወከሉት ሦስት ሰዎች ቤተመንግሥት በቀጠሮው መጥተው ከዚህ የሚከተለውን ሀሳብ አቀረቡልኝ።

“ክቡርነትዎ እኛ ልናከናውነው ለሚፈለገው የሰላም ተልዕኮ ብዙ መሰናዶ ማድረግ እንዳለብን ግልጽ ነው። ሆኖም እኛ አሁን እዚህ ለእርስዎ ይሄ ይሄ ያስፈልጋል ብለን ብንናገር ወይም ብናቀርብ እኛ ተሳስተን እርስዎንም ማሳሳት ስለሚሆን፣ የምናሳስበው የሚፈለገውን መሰናዶ በማድረግ፣ እኛንም በሚያስፈልገን መንገድ ለመርዳት ብቻ ሳይሆን የሚያማክርና የሚመራንም አንድ የመንግሥት አገናኝ ሰው ተመርጦ እንዲሰጠንና አንድ ቢሮ በዚህ በአሥመራ ከተማ እዲከፈት ነው።

ከዚህ ሌላ የሰላም ፍለጋው መንገድ እንዲቃናልንና በበኸረኞቹም ዘንድ ሽምግልናችን ታምኖ ተቀባይነትን እንድናገኝ፣ የመንግሥት ወታደሮች በኸረኞቹን ማሳደዳቸውንና ማደናቸውን አቁመው የሰላም አየር ይገኝ ዘንድ መንግሥት የተኩስ አቁም አዋጅ እንዲያውጅ እናሳስባለን ብለውኛል።

በበኩሌ ሽማግሌዎቹ ባሳሰቧቸው በሁለቱም ነጥቦች አስፈላጊነት አምናለሁ። የዛሬውን ስብሰባ የጠየኩት በእናንተም ዘንድ ታምኖበት የሰላም ፍለጋው ሥራ እንዲጀመር ነው” የሚል ሀሳባቸውን አቀረቡልን።

ኤርትራ የሄዱበት ምክንያት ጦሩንና ሕዝቡን ለመጎብኘት ነው የሚል ሽፋን ብንሰጠውም አብዮ ጉዳይ ከገንጣዮቹ አመራር ጋር ለሰላም መፍትሄ መነጋገር የሚቻልበትን ሁኔታ ለማፈላለግ ስለሆነ በማንኛውም መንገድ የሰላም ንግግሩ የመጀመሩን አስፈላጊነት በስብሰባው ላይ የተገኙት የደርግ አባሎችም የሚያምኑበት ነበር።

ያም ቢሆን ጀነራል አማን ያቀረቧቸው ሀሳቦች ብዙ አነጋግረውናል። ከነዚህ ጉዳዮች በኔ አስተያየት ትልቅ ግምት የሰጠናቸውን ብቻ ከዚህ እንደሚከተው እገልጻለሁ፡

1ኛ/ የመጀመሪያው ከገንጣዩቹ ጋር ቢያንስ ግንኙነት ተፈጥሮ እነሱ ለሰላማዊ መፍትሄ ከመንግሥት ጋር ለመነጋገር ያላቸው ፈቃደኝነት ሳይታወቅ መንግሥት ቀድሞ ብቻውን ያለአንዳች መረጃ የተኩስ አቁምን ያህል አዋጅ አውጀን ትርጉሙ ቅሌትና ውርደት ብቻ እንዳይሆን ቢያንስ የገንጣዮቹን ለድርድር የመቅረብ ፍላጎት ለማወቅ የሚያስችለን ሥራ በቅድሚያ መሥራት አለበት የሚል ነበር።

2ኛ/ ገንጣዮቹ በመሠረቱ ከመንግሥት ጋር ለሰላም ውይይት የማድረግ ፍላጎት ሳይኖራቸው መንግሥት በሚያውጀው የተኩስ ማቆም አዋጅ ወታደሮቻችን ሲገዙና እንቅስቃሴያቸው ሲታቀብ ገንጣዮች በሁኔታው ተጠቅመው አንድ ያልተጠበቀ ወታደራዊ

አደጋ ቢያደርሱ አደጋው ከሚያደርሰው ጉዳት የባሰ አሁን በደርግና በሰሜን ሠራዊት መካከል ያለውን መልካም ሁኔታ ሲመርዝብን በገንጣዮች ወጥመድ ውስጥ ራሳችንን ከተትን ማለት አይደለም ወይ? የሚል ጥያቄ ነበር።

ጄነራል አማን የእኛን ስጋት አስመልክተው "ይህንን የመጀመሪያው ግንኙነት ለመፍጠር ቅድመ ሁኔታ አድርገው ሽማግሌዎቹ የጠየቁኝ ሽፍታና የመንግሥቱ ሠራዊት በሚፋለሙበት የጦር ሜዳ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ካለመቻሉ በላይ በበርሽኖቹ በኩል አምኖ የሚያናግረን ስለሌለ በመንግሥት በኩል ይህን ማድረግ ወሳኝ ነው ነው የሚሉኝ።

ይህ የመጀመሪያው የሰላም ጥረት ችግር አይገጥመውም፣ ወንበዴዎቹ ተቀብለውታል የሚያሰኝ ነገር ስለሌለበት በበኩሌ ሽማግሌዎቹን የምንጠይቃቸው ወይም እኔ ለእናንተ የምገባው ቃል አይኖርም። እኛ መንግሥት ነን። እነሱ ሽፍቶች ናቸው። ሁሉን ችለንና ታጋሾች ሆነን ለሰላም በሩን እንክፈት።

እንደምታውቁት በተኩስ አቁም ብቻ ሳይሆን እየተዋጉም ለሰላም መደራደር በዓለም የሚደረግና የተለመደ ነው። እነዚህ ሽፍቶች እስካሁን ባለ አቅማቸው ሲወጉን ነበር እየወጉንም ነው። እኛ የሰላሙን በር ለመክፈት ስንል ተኩስ በማቆም ቀዳሚ ስለሆንን ወትሮ ከሚያደርጉት ሌላ ምን ይጨምራሉ? እኛስ ምን እናጣለን?" ስላሉ የተናገሩት ለእኛ ጥያቄ መልስ ባይሆንም ለሰላም ስንል የሚመጣውን ለመቀበል እንዘጋጅ በማለት ተስማማን።

በኤርትራ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰላም መፍትሄ ለመፈለግ ለሚረዳው ቅድመ ሁኔታ መንግሥት ራሱ ቀደሞ አርአያ ለመሆን ተኩስ ማቆም ግዴታ ውስጥ መግባት አለበት በተባለው ሀሳብ ደርግ የሚስማማ ቢሆንም ጉባዔውን አወያይቶ የሚፈለገውን ውሳኔ ለማስወሰን የጦፈ ክርክር እንደሚከፈት በመታወቁ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በኩል የአቀራረብ ለውጥ አደረግን።

የኤርትራ ገንጣዮች በወደቀው ጉልታዊ ሥርዓት ማህበርና በአፄ ኃይለሥላሴ ምዕራብ መምንትና የሰሜን አሜሪካን መንግሥት አፍቃሪነት ምክንያት ተጠቅመው ራሳቸውን ነፃ አውጪ፣ ለሰላምና ለሶሻሊዝም ታጋይ በማድረግ ነበር ተራማጁን ዓለም የቀረቡት።

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ሳይሆን ሕዝባዊ አብዮት ነው። እስከ ዛሬ በገንጣዮች ላይ ፍፁም የሆነ ወታደራዊ የበላይነታችን እንደመጠበቁ ሁሉ አሁን ደግሞ አብዮቱ ፖለቲካዊ የማጥቃት እርምጃ መወሰድ አለበት በሚል ነው የተኩስ ማቆሙን ውሳኔ ያቀረብነው ወይም ያሳሰብነው።

ሰላምና ፀጥታ በደፈረሰበት የኤርትራ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አስተዳደር ክልል ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት፣ መንግሥት የተኩስ ማቆም ውሳኔ በመወሰን፣ ይህንንም በኤርትራ ለሚገኙት የጦር ኃይል አካሎችና ለፖሊስ ሠራዊት ክፍሎች ሁሉ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ሰጥቷል ተብሎ የተሰጠውን መግለጫ የክልሉ ሠራዊት ንዑስ ደርግ በኩሉ ለሠራዊቱ እንዲያስረዳ ተደረገ።

በጄነራል አማን እንደተነገረን፣ ለሰላሙ መፍትሄ ፍለጋ የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን ያሉን የሃገር ሽማግሌዎች መንግሥት በወሰደው እርምጃ ተደስተዋል። ከፖለቲካ ውሳኔ ጋር ለሠራዊቱ የተሰጠው ትዕዛዝና መመሪያ በመከላከያ ሚኒስቴር በኩል ስለነበር ዝርዝር ይዘቱን በውል ባላውቀውም መላው ሠራዊት ሰላምን ከማንም በላይ ስለሚፈልግ ለጊዜው የደረሰ ችግር አልነበረም።

የኤርትራ ፌደሬሽን መፍረስ ጄነራል አማንን በቅድመ አብዮት ማለትም ፌደሬሽኑ ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ ክፉኛ ሲያስቆጫቸው እንደኖረ የምንቀርባቸው መኮንኖች ሁሉ የምናውቀውና እሳቸውም ሳይሸሽጉ በርሽኞቹ የሚወጉት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳይሆን ፊውዳሉን ሥርዓት ስለሆነ በኤርትራ አብዮታዊ ትግል እየተካሄደ ነው ከማለት አልተቆጠቡም።

ለኤርትራ ሰላማዊ መፍትሄ ፍለጋ ይረዱን ይሆናል የሚል ተስፋ በሳቸው ላይ ያሳደርነው እውነት በረሽኞቹ የሚወጉት ሥርዓቱን ከሆነ ሥርዓቱን ካፈረስነው የአገሪቱ አብዮታዊያን ጋር እና እሳቸው ከሚመሩት መንግሥት ጋር የሚያዋጋቸው ምክንያት አይኖርም ብለን በማሰብ ነበር።

በድህረ አብዮት ጄነራል አማን የኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ እጅግ እንዳስቆጫቸው በተጨማሪ መረዳት የሚቻለው፤

1ኛ/ ግንኙነቱ ከእኔ ጋር ብቻ የሆነ ፍፁም ራስ ገዝ ሥልጣን ለኤርትራ ክፍለ አገር አስተዳደር እንስጥ ብለው ሊሆን የማይችል ወይም በምንም ሁኔታ የማይሰራ፣ በማን አለብኝነትና በሕገወጥነት ለምኒስትሮች ምክር ቤት ያቀረቡትና የከሸፈባቸው የኤርትራን መገንጠል የሚፈቅድ የሕግ ረቂቅ ነው።

2ኛ/ በዚህ ምክንያት ተናደው ጦር እንበኛለሁ በሚል ሰበብ በየጦር ክፍሉ እየተዘዋወሩ አብዮቱ ግቡን መቷል፤ የደርግ ተልዕኮ አብቅቷል ከማለታቸው ሌላ ደርጉን የሚመሩት ሻለቆች ጠግበዋል፣ አብጠዋል፣ ጦሩ መልሶ እንዲጠራቸው ማድረግ አለባችሁ እያሉ ደርጉን ለማፍረስ ያደረጉት ሙከራ ነው።

3ኛ/ በኤርትራ ጉብኝታቸው ጊዜ አንድም የአንድነት አርበኞችን ጠርተው ለማነጋገር ያለመፈለጋቸው፣ ከረን ከተማ ላይ ሕዝብ ሰብስበው ያደረጉት የክልሉን ሠራዊት በእጅጉ ያስቆጣ ንግግራቸው፤

4ኛ/ ኤርትራን ነፃ ለማውጣትና ብሎም ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ ለማዋሀድ በተደረገው ትግል ግንባር ቀደም አርበኞችና የውህደቱ መሀንዲሶች የተባሉትን ሰዎች እኛን ሳያማክሩ ማሰራቸው፣

5ኛ/ ደርጉ የሰጣቸውን ትዕዛዝና መመሪያ በመጣስ አብረዋቸው የሄዱትን የደርግ አባላት እሳቸው ከሚኖሩበት መኖሪያ ማለትም ከቤተመንግሥቱ የእንግዳ ማረፊያና ከሥራውም ከማግለል ባሻገር ከአስመራ ከተማ ወደየአውራጃዎቹ በጉብኝት ሲሄዱ እንኳን እንዳይከተሏቸው መከልከላቸው። ይህንን ስል በምንመራበት ጊዜያዊ ሕገመንግሥት የደርግ አባላት በሙሉ ወይም በወል የአገሪቱ ጊዜያዊ ርዕሰ ብሄሮች ናቸው። ጄነራል አማን የደርጉ ወኪል እንጂ በሕግ ርዕሰብሄር አይደሉም። በሌላ አነጋገር አብረዋቸው ለሥራ የሄዱት የደርግ አባሎች በሕጋችን ከጄነራል አማን እኩል ናቸው።

6ኛ/ የአስመራ ከተማ በጀብሃና በሻዕቢያ ጦር በተከበበበት ጊዜ የአየር ኃይላችን ለወገን ሠራዊት ድጋፍ እንዲሰጥ ከማንም ቀድመውና ፈጥነው ትዕዛዝ መስጠት ያለባቸው ሰው ይህንን ባለማድረጋቸው ደርጉ ለአየር ኃይላችን አዛዥ የሰጠውን ትዕዛዝ ሽረው አንድ ተዋጊ አውሮፕላን ካለእኔ ትዕዛዝ እንዳይነሳ ማለታቸው፤

7ኛ/ ገንጣዮች የአስመራን ከተማ በ10 ኪ/ሜትር ክብ ከበዋል፣ በሰላም ፍለጋ ውይይታችን ጊዜ ስጋታችንን እንደገለፅንልዎ የእኛን የተኩስ ማቆም ቀደምትነት እንደ ድክመት ገምተው በሁኔታው እየተጠቀሙ ነው ብዬ ስነግራቸው የበረሽኞቹ ወደ አስመራ

ከተማ መቃረብ ለሰላም ልውካኑ ሽማግሌዎች በቅርብና በቀላሉ እንዲያገኟቸው ይረዳል በማለት ማፌዛቸው፤

8ኛ/ የወንበዴዎቹ ማጥቃት የተጠናከረና ከበባቸውም እየጠበበ በመጣ ጊዜ የሰሜን ተከላካይ ጦር ለማጠናከር ከመሀል አገር ጦር በአጣዳፊ እንዲላክ ያደረግነው ጥረት እንዳይሳካ ልዩ ልዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ ያንን ያህል መከራከራቸው፤

9ኛ/ አንባቢ እንደሚያስታውሰው በአስመራ ዙሪያ በወገን ሠራዊትና በገንጣዮች መካከል እየተኪያሄደ ያለውን የውጊያ ሁኔታ ቃኝቶና ከክልሉ ሠራዊት መሪዎች ጋር ተወያይቶ ወታደራዊ መረጃ እንዲያቀርብልኝ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ሥላሴን በሚሥጢር ወደ አስመራ የላኩት እኔ ነኝ።

ተስፋዬ በወታደራዊ ካርታ የተደገፈ ወታደራዊ መረጃ አቀረበ እንጂ በጠቅላላ ስለኤርትራ ታሪክ፣ ስለ ወቅታዊው የፖለቲካ ችግርና ስለ ሕዝቡም ምንም የተናገረው ነገር ሳይኖር "ስለኤርትራ አንተ ምን ታውቃለህ? አንተን ብሎ ስለኤርትራ መረጃ አቅራቢ" በማለት ያንን ያህል ማበሻቀጥን ምን አመጣው?

በመጨረሻው በአስመራ ከተማ የሚዋጋውን ጦራችንን ለማጠናከር ተጨማሪ አግረኛ ጦር ይላክ ብለን ባልን ብቻ በጠቅላላው የደርጉ አባላት ላይ ከእሳቸው የማይጠበቅ ዘለፋ መሰንዘራቸውና ጉባዔውን ረግጠው ለአንዴና ለመጨረሻ ከእኛ መነጠላቸውን በማስታወስ ይህንን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ ስፅፍ "ጄነራል አማን ማን ነበሩ?" የኤርትራ ገንጣዩች ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ አድርገው የማያውቁትንና ያደርጋሉም ተብሎ የማይገመት እብሪትና ድፍረት እሳቸው ጉብኝታቸውን ጨርሰው አዲስ አበባ በተመለሱ ሳምንት ውስጥ የአስመራን ከተማ የወረሩት 'ጄነራል አማን ምን ብለው ቢያደፋፍሯቸው ነበር?' የሚል ጥያቄ ለእራሴ ማቅረብ ተገድጀለሁ።

ምናልባትም 'በመሃል አገር ያለው ሠራዊት በየመዕዘናቱ በውጊያ ተወጥሮ ስለሚገኝ ደርግ ወደ ኤርትራ የሚልከው ጦር የሌለው ከመሆኑም ሌላ እኔ ያለውጊያ በሰላም ፍለጋ ሰበብ በፈጠርኩላችሁ የተኩስ ማቆም ውሳኔ ተጠቅማችሁ በኃይል ነፃነታችሁን አውጁ' ብለው ነግረዋቸው ይሆን ብዬ ለራሴ ለአቀረብኩት ጥያቄ አወንታዊ መልስ ሰጥቻለሁ።

የተኩስ አቁም ውሳኔ በአዋጅ ተግባራዊ ከሆነና ሠራዊቱም ገንጣዮችን ማሳደድ እንዲያቆም በተደረገ በሳምንቱ ጥቅምት 17 ቀን 1967 ዓ.ም ራሳቸውን ጀብሃና ሻዕቢያ በማለት የሚጠሩት ሁለት የኤርትራ ገንጣይ ድርጅቶች የምፅዋን ወደብና ከተማዋን ከአሥመራ፣ ምዕራባዊውን ቆላማ ክልል ከረንን ጨምሮ ከአሥመራ ቆርጠው መንገድ በመዝጋት በሁለት አቅጣጫ በ10 ኪሎ ሜትር እርቀት የአሥመራን ከተማ ከበቡ።

በፍጹም መዝናናትና በማን አለብኝነት የኪነት ባለሙያዎቻቸው የአካባቢውን ባህላዊ ቀረርቶ፣ ፉከራና ዘፈን፣ በእስክስታና በዳንኪራ የነዋሪውን ሕዝብ ስሜት ሲሰቡ፤ ያላቸውንም የሰው ኃይልና ዘመናዊ ትጥቅ ለሕዝቡ ያሳዩ ነበር።

ይህንን ጉዳይ ለጄነራል አማን ደውዬ በማሳወቅ እርስዎ ባለዎት ግንኙነት የዚህን ድርጊት ምክንያት ሳያውቁ አይቀሩም ብዬ እገምታለሁና ሊያስረዱን ይችላሉ ወይ ብዬ ጥያቄ አቀረብኩ። "ከወታደራዊው የእዝ መስመራችን ሰምቼ መንስኤውንና ምክንያቱን ዓላማውንም ለመረዳት ጥረት በማድረግ ላይ እያለሁ ነው የደወልክልኝ" አሉኝ። ይህንን ጉዳይ በቸልታ ጊዜ መስጠት ምናልባት ያልጠበቅነውን አደጋ የሚያስከትል ሊሆን ይችላል።

ገንጣዮች የሚያከናውኑትን ተግባር ወታደሩ ሳይቀር በሰላማዊ ልብስ እየሄደ በሚገባ አስተውሎታል። ለእኔ የሚደረግልኝ ሪፖርት የሰላም ፍለጋ ሳይሆን የእኛን የተኩስ አቁም ውሳኔ በድክመት የመተርጎምና ከዚህ በፊት እንደተወያየንበትና እንደገመትነውም የፈጠርንላቸውን አመቺ ሁኔታ በአፍራሽ መልኩ ለመጠቀም ይመስላል።

በእኛ በኩል ብቻ የተፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ከሚያደርሱት ጉዳት ይልቅ ሠራዊቱና ሕዝቡ በመንግሥታችን ላይ የሚያሳድሩት ግምት የበለጠ ጎጂ ነው የሚሆነው ብለቸው "የያዝነው ጉዳይ ከፍ ያለ ትዕግስትን የሚጠይቅ ነው። ለሰላሙ ጥረት እናገለግላለን ያሉኝ ሰዎች በረሽኞቹ ቤታቸው ድረስ ስለቀረቡ የሁለቱንም ድርጅቶች አመራር አግኝተው ለማነጋገር ከዚህ የተሻለ እድል እንደማይገኝ መገንዘብ ተገቢ ነው።"

ይቅርታ ያርጉልኝና ጄነራል እቤታቸው ድረስ ሲቀርቡ ነው ያሉኝ? ብዬ ስጠይቃቸው፣ የኮረኮሯቸውን ያህል ስቀው እኔንም አሳቁኝና "ለማንኛውም ጊዜ ስጠኝና የምደርስበትን ሁኔታ እገልጽልሃለሁ" ብለውኝ ተለያየን።

ከጄነራል አማን ጋር ስንነጋገርበት የነበረውን ስልክ እንደዘጋሁ ከአሥመራ ጋር የምንገናኝበት ስልክ ጮኸ። የደወለው ሻለቃ ነሲቡ ታዬ የሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦርና የሰሜኑ ክልል መለዮ ለባሽ ንዑስ ደርግ ሊቀመንበር ነው። "ተከበናል፣ አንዱን አውራጃ ከሌላው፣ አንዱን የጦር ክፍል ከሌላው የሚያገናኙ ድልድዮች ፈርሰዋል መንገዶችም ተዘግተዋል።

ከምፅዋ ወደ አሥመራና ከአሥመራ ወደ አቆርዳት የተዘረጋውም የባቡር ሀዲድ ተነቃቅሏል። ይሄ ሁሉ ሲሆን ለሠራዊቱ የተሰጠው የተኩስ ማቆም ትዕዛዝ አልተነሳም። ጌታዬ! እዚህ ያለነው ሰዎች ስለሚሆነው ነገር ምንም ሊገባን አልቻለም። እናንት እዛ ያላችሁ ሰዎች የምታውቁት ነገር ካለ አስረዱኝ" አለኝ።

"እንዳልከው እኔ ያለሁት አዲስ አበባ ነው፣ አንተ አሥመራ ያለህ ሰው፣ እኔ ምን እንዳደርግ ትመክረኛለህ ወይም ምን እንዲደረግ ትፈልጋላችሁ?" የሚል ጥያቄ ሳቀርብለት "በአንደኛ ደረጃና በፍጥነት የተኩስ ማቆም አዋጁ ይነሳልን። በሁለተኛ ደረጃ በገላጣ ሜዳ ላይ ሰፍረው ፕሮፓጋንዳ የሚያካሂዱት የወንበዴ መንጋዎች ከነድርጅታቸው የአየር ኃይሉ እንዲያወድማቸው ትዕዛዝ በአስቸኳይ ይሰጥልን" ሲል አመለከተኝ።

ለሻለቃ ነሲቡ ጥያቄ ቅፅበታዊ መልስ መስጠት ተገቢ ቢሆንም የተጀመረውን የሰላማዊ መፍትሄ ጥረት አደናቃፊ ሆኜ ላለመገኘት የጄነራል አማንን መልስ ለሁለት ቀን በታላቅ ትዕግሥት ጠብቄ ያገኘሁት ነገር ካለመኖሩ በላይ በስልክ ስፈልጋቸው ይጠፉብኝ ጀመር።

ከሰሜን ንዑስ ደርግ ብቻ ሳይሆን ከእዙና ከአስተዳደሩ ጭምር ወንበዴዎቹ ወደ ከተማው ከመግባታቸው በፊት በአውሮፕላን እንዲደበደቡ የሚቀርብልኝ ጥያቄ በየእለቱ እየጨመረ ነበር።

የደርጉን የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን የሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር እዝ በጠየቀው መሠረት ሁለቱም የወንበዴ ጎራዎች ማለትም ሻዕቢያና ጀብሃ ዳግም በማያንሰራሩበት ሁኔታ ያሉን ተዋጊ አውሮፕላኖች በሙሉ ተነስተው እንዲደበድቡ ለአየር ኃይሉ አዛዥ ትዕዛዝ እንዲሰጥ አዘዝኩት። ሻለቃ ተስፋዬም ለአየር ኃይሉ አዛዥ ግልጽ ትዕዛዝ መስጠቱንና አዛዡም መቀበሉን አስታወቀኝ።

ትዕዛዙ የተሰጠው ጠዋት በሁለት ሰዓት ገደማ ሆኖ ሳለ ከሰዓት በኋላ ሻለቃ ነሲቡ ደውሎ በምሬት አነጋገር "ከንዑስ ደርግ ሊቀመንበርነቴ ብቻ ሳይሆን ከአባልነቴም እራሴን በፈቃዴ ለማግለል ወስኛለሁ። ጓድ ሊቀመንበር በተሰጠኝ ተስፋ መሠረት ወንበዴውን አየር ኃይሉ ባለመደብደቡ ዛሬ የኤርትራ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥ ብ/ጄነራል ጎይቶም በእሥራኤሎች የሰለጠኑትን የፖሊስ ኮማንዶዎች በሙሉ ይዞ ከሻዕቢያ ጋር ተቀላቅሏል" ሲለኝ፣ ትዕዛዙ የተሰጣቸው ጠዋት ነው ጉዳዩን እኔ እከታተላለሁ እናንተም በትዕግስት ተጠባበቁ በማለት ሻለቃ ተስፋዬን ለምን አየር ኃይሉ የተሰጠውን ትዕዛዝ እስካሁን እንዳልፈጸመ ስጠይቀው "አንተ ከሰው ጋር ስለነበርክ እንጂ ከአንዴም ሁለቴ ቢሮህ መጥቼ ነበር። የአየር ኃይሉ አዛዥ ቀድሞ ሳይነግረኝ አሁን ስጠይቀው ጄነራል አማን እኔ ካላዘዝኩ በስተቀር አንድም ተዋጊ አውሮፕላን እንዳይነሳ ብለው አዘውኛል ነው ያለኝ" አለ።

የአየር ኃይሉ አዛዥ አንድ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከአዛዥነቱ ተነስቶ ምክትል አዛዡ የተሰጠውን ትዕዛዝ እንዲያስፈጽም አስቸኳይ ትዕዛዝ ከሰጠን በኋላ የትዕዛዙን መንፈስና ምክንያት አየር ኃይል ተወካይ የሆኑት የደርግ አባላት በዚያው ሰዓት ደብረ ዘይት ሄደው ለሠራዊቱ እንዲያስረዱ ባደረግንበት ቀን፣ ሁለቱ ገንጣይ ወንበዴዎች በሁለት አቅጣጫ የአሥመራን ከተማ ክልል አጥቅተው በከተማው ጠርዝ ላይ ያሉ ጠቃሚ ገዢ መሬቶችን ተቆጣጠሩ።

አሥመራ የነበረው ጦር በመጠን ከእሱ የሚልቀውን የወንበዴ ሠራዊት ጥቃት ለመመከት ካደረገው ጥረት ጋር የአየር ኃይሉ ሚና ታላቅ አስተዋፅዖ የነበረው ቢሆንም ወንበዴው የጀመረውን የማጥቃት እርምጃ የሚገታ አልሆነም።

ወንበዴው በውጊያው የሞቱበትንና የቆሰሉበትን የሰው ኃይል በአዲስ ኃይል በመተካት ውጊያውን በብርታት ቀጠለ። የመንግሥቱ ሠራዊት እንዳይዋጋ ትዕዛዝ የተሰጠው ብቻ ሳይሆን በውጊያም እርስ በእርሱ እንዳይገናኝ መንገዶች የተዘጉ ከመሆናቸውም ሌላ ከአሥመራ ውጪ ያሉት ዋና ዋና አውራጃ ከተሞች ጦር ክፍሎችም ተከበዋል።

የሰሜኑ እዝ አዛዥና የንዑስ ደርጉ ሊቀመንበር በአንድነት በአስቸኳይ ረዳት ጦር ከመሃል ሃገር እንዲላክላቸው ስለጠየቁኝ የእዝ ጠገግ ሳልከተል ከአዲስ አበባ ጦር የሚዘጋጅበትን ሥራ እየሰራሁ፣ ምን አይነት ጦር፣ በምን ያህል መጠን፣ እንዴት መርዳት እንደሚቻልና ጠቅላላውን የኤርትራ ሁኔታ ለ24 ሰዓት ያህል ቃኝቶ ሪፖርት እንዲያቀርብልኝ የሃገር ደህንነት ብሔራዊ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆነውን ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ሥላሴን ወደ አሥመራ በአየር መጓጓዣ በምስጢር ላኩት።

ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬን መላክ ያስፈለገበት ምክንያት በመረጃ ባለሙያነቱ ብቻ ሳይሆን በኤርትራ በርከት ላሉ ዓመታቶች ያገለገለና፣ ሠራዊቱንና ሕዝቡን፣ መልክዓ ምድሩን እስከ ፖለቲካ ባህሪው ደህና አድርጎ የሚያውቅ ሰው ስለነበረ ነው።

አሥመራ ሄዶ ከሠራዊቱ አመራር አካላት፣ ከንዑስ ደርግ አባላት፣ ታማኝ ከሆኑ የክፍለ ሃገሩ ነዋሪዎችና የኤርትራ አርበኞች ጋር ተወያይቶ፣ የወንበዴውን የጦር አሰላለፍና የተቆጣጠራቸውን ስፍራዎች ቃኝቶና ሁሉንም ነገር ተመልክቶ በመመለስ የአስገነዘበኝ "በዚህ ሳምንት አጠናካሪ ጦር ካልላክን ገንጣዮቹ ከተማውን ተቆጣጥረው መንግሥት ለማወጅ እንደሚበቁ መጠራጠር አያሻም። አሁንም ቢሆን ገንጣዮቹን ከተማውን ከመቆጣጠር የገታቸው የእኛ ጦር ጥንካሬ ሳይሆን በሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች መካከል ባለው ልዩነትና የሥልጣን ክፍፍል አለመግባባት ነው የሚመስለኝ" በማለት አስረዳኝ።

ህዳር 5 ቀን 1967 ዓ.ም ጠዋት የጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬን ሪፖርት ተቀብዬ፣ ወዲያው የኤርትራን ሁኔታ በተመለከተ ለደርጉ ጉባዔ የአስቸኳይ ስብሰባ አጀንዳ አዘጋጅቼ ጄነራል አማን በተገኙበት የጓድ ተስፋዬ ሪፖርት በደርጉ የስብሰባ አዳራሽ ተደመጠ።

ጄነራል አማን የደርጉ ሊቀመንበር ቢባሉም የእሳቸው ሥራ ድርሻ፣ ከርዕሰ ብሔርነታቸው ሌላ ከመከላከያ ሚኒስትርነታቸው በተጨማሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን መምራት ሲሆን የደርጉን ውስጣዊ ሥራ በተመለከተ የአመራር ኃላፊነቱ የሁለታችን ምክትል ሊቃነ መናብርቶች ነበር።

ለጉባዔው የቀኑ አስቸኳይ አጀንዳ ይዘት ከተነበበ በኋላ ወደ ውይይቱ ከመግባታችን በፊት የጉባዔው አባላት ስለ ወቅታዊው የኤርትራ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ለእኔ እንዳስረዳኝ ለጉባዔው ከኤርትራ ያመጣውን መረጃ በካርታ እየተረዳ በጥሩ ትንታኔ አቀረበ።

በጓድ ተስፋዬ የመረጃ አቀራረብ ላይ ጥያቄ ያለው ሰው ቢኖር እንዲጠይቅ መድረኩን ለጥያቄ ስከፍት፣ ጄነራል አማን ይሉኝታና ትእግስት ባጣ ቁጣ ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬን "አንተ ለመሆኑ ስለ ኤርትራ ምን ታውቃለህ? አንተን ብሎ ስለ ኤርትራ መረጃ አቅራቢ" በማለት ከእሳቸው እንደበት በማይጠበቅ ቃላቶች አበሻቅጠው ነቀፉት።

ጄነራል አማን ጓድ ተስፋዬን በሚዘልፉ ጊዜ ከፊሉ የደርግ አባላት ጣልቃ ለመግባት እጃቸውን አንስተው መድረክ ሲጠይቁ ከፊሉ 'እኝህን ሰው ያስቆሟቸዋል ወይስ ዝም ብለው ይመለከቷቸዋል?' በማለት እኔንና ሻለቃ አጥናፉን ይመለከቱን ነበር።

ጄነራሉ በጓድ ተስፋዬ ላይ የጀመሩትን ዘለፋ ለማቆም ስላልቻሉ በእርግጥም ጣልቃ ገብቼ እንዳስቆማቸው ሁኔታው አስገደደኝ፡ "መኮንኑ በሙያውና በተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ታዞ ወደ ኤርትራ በመሄድ ባቀረበው ሪፖርት ሊመሰገን ሲገባ በተቃራኒው ይህንን ያህል መዘለፉ አግባብ ካለመሆኑ ባሻገር ሪፖርቱን ያቀረበው ለእርስዎ በግል ሳይሆን እርስዎንም ለሚያካትተው ለዚህ ታላቅ ጉባዔ መሆኑ እየታወቀ የተሰነዘረው ዘለፋ በጓድ ተስፋዬ ላይ ብቻ ሳይሆን ተስፋዬን በአዘዙት የአመራር አካላትና በጉባዔውም ላይ ነው።

ክቡር ሊቀመንበር ይህንን የመሰለ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርተን ብንነጋገር ወግና አግባብ ከመሆኑ ባሻገር ለሥራ ጥራትም የሚበጅ ነው ብዬ ነው እንጂ ዛሬ በኤርትራ የሚታየውን ገሀድ ነገር መረጃ አቅራቢ ሳያስፈልግ ራሱን ገላጭ ስለሆነ ወደ እለቱ አስቸኳይ አጀንዳ እናምራ" ብዬ ያቀረብኩት ሀሳብ በቤቱ ስለተደገፈ ሌ/ ኮሎኔል ተስፋዬን ከማመስገን በላይ ለደረሰበት ዘለፋ ይቅርታ ጠይቄ ወደ ሥራው እንዲሄድ አሰናበትኩና ውይይቱ ተጀመረ።

መድረኩ ለውይይት ሲከፈት ለመናገር ቅድሚያውን የወሰዱት አሁንም ሊቀ መንበሩ ጄነራል አማን ነበሩ። ለጉባዔው በጠቅላላ ያቀረቧቸው ጥያቄዎችና የወረወሯቸው ቃላቶች በጓድ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ላይ ከሰነዘሩት ዘለፋ ብዙም የተለየ አልነበረም።

"እናንተ!" አሉ። "እናንተስ እዚህ የተሰበሰባችሁ በሙሉ ስለ ኤርትራ ምን ታውቃላችሁ? ምን የምታውቁት ነገር አለ?" ማለት ሲጀምሩ፣ ጓድ ሻምበል አሊ ሙሳ ተነስቶ "ጓድ ሻለቃ መንግሥቱ እኛ እኝህን ሰው እናውቃቸውም እርስዎ ነዎት ከፍ ያለ የሃገር ፍቅር ያላቸውና ለውጥ ፈላጊ ናቸው በማለት በእጅ በእግራችን ገብተው ያሳመኑንና የደርግም የሃገርም መሪ ያደረግናቸው።

እነ ቢትወደድ አስፍሀ ኤርትራን ለኢትዮጵያ ሽጧት ካሉ በኋላ በእኛ በኩል አማን ብሎ የደርግ አባልና የሃገር መሪ ቀርቶ፣ አማን ብሎ ኢትዮጵያዊ አናውቅም። እኝህ ሰው በዚህ አብዮትና በኢትዮጵያ ላይ ለሚያደርሱት ማናቸውም ነገር ከእናንተ ከሁለታችሁ ሊቃነመናብርት እራስ እንወርድም" ብሎ ሲቀመጥ የጉባዔው አባላት በሙሉ በከፍተኛ ጭብጨባ ደገፉት።

ከጓድ ሻምበል አሊ ሙሳ በኋላ አብዛኛው የጉባዔ አባላት ለመናገር መድረክ ይሰጣቸው ዘንድ እጃቸውን አንስተው አየሁ። መድረክ ብሰጥ ጄነራል አማን በዚያ ሁሉ ሰው እንደሚሰደቡና እንደሚዋረዱ አውቃለሁ። ውጤቱም የተሰበሰብንበት ታላቅ የሃገር ጉዳይ ስቶ በእሳቸው መሪነት በጣም አሳዛኝና አፍራሽ ወደ ሆነ ተግባር እያመራን መሆናችን ግልጽ ስለነበር፣ ይህንን ሁኔታ ለማቀዝቀዝና ብሎም በመለወጥ ቢያንስ ጄነራሉን በሰላም ለመሸኘት የሻይ ቡና እረፍት ጠይቄ ከአዳራሹ ወጣን።

እኔና ሻለቃ አጥናፉ ወትሮም እንደምናደርገው ከእሳቸው ጋር ወደ ጽሕፈት ቤታቸው ስንሄድ፣ በተፈጠረው ሁኔታ በጣም ያዘኑና የተጨነቁ፣ በእድሜም በሰል ያሉ ጥቂት የደርግ አባላት ብቻ ሳይሆኑ የተሰደበው ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተሰፋዬ ወ/ሥላሴም ተጨምሮ ተከትለውን መምጣት ጄነራል አማንን በትህትናና በአክብሮት ግን በግልፅነት፣ ለእኛ መሪና መካሪ መሆን ያለብዎት ሰው እንዴት ይህንን የመሰለ ነገር ይናገራሉ? ብለው ወቀሷቸው። የሻይ ቡና እረፍቱ አበቃና ወደ አዳራሹ ገብተን ሁላችንም ስፍራችንን ያዝን።

ጓድ አሊ ሙሳ ያንን የመሰለ ነገር ከተናገረ በኋላ የጄነራል አማን የመጨረሻ ነው ብለን ገምተን የጄነራል አማንን ወደ አዳራሹ መመለስ ልናምን አልቻልንም።

የቀረበው አጀንዳ በጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ የመረጃ አቅርቦትና እንዲሁም ከክልሉ ወታደራዊ እዝ፣ ከንዑስ ደርግና ከክፍለ ሃገሩ አስተዳደር ጭምር የቀረበልን ጥያቄና ማሳሰቢያ፣ የገንጣዮቹ ማጥቃት ተሳክቶ አሥመራ ከተማን ለመቆጣጠር የተቃረቡ ስለሆነ የአውሮፕላን መረፊያው በገንጣዮቹ ቁጥጥር ስር ከመዋሉ በፊት በቂ አጠናካሪ ጦር በአጣዳፊ በአየር ይላክልን ብለው ስለጠየቁ፣ የጠየቁት ረዳት ጦር በአጣዳፊ ይላክላቸው ዘንድ እርምጃ እንድንወስድና ከዚሁ ጋር ተዛማች የሆኑ ጉዳዮችም ነበሩን።

ጄነራል አማን በዚህ ጊዜ ራሳቸውን ተቆጣጥረው ለመናገር እየሞከሩ ነበርና "የቀረበው መረጃ ከታመነበትና አሥመራ ላለው ጦር ረዳት ጦር እንዲላክ ከተፈቀደ ቀሪው ዝርዝር በመከላከያ በኩል ተጠንቶ የሚደረግ ነውና በዚህ ጉባዔ ስለዚህ ብዙ መነጋገር አያስፈልግም" የሚል አስተያየታቸውን ሰጡ።

እንደ ጦር ኃይላችን የአሰራር ልምድና ደንብ እሳቸው ያሉት ትክክል ቢሆንም መተማመን ስለጠፋና ጊዜም ስለሌለ በማለት የቀረበውን የማዘናጊያ ስልት ተቃውሜ ጦር በአጣዳፊ አሥመራ የሚደርስበት ጉዳይ እዚያው እንዲወሰን አሳሰብኩ።

እኔ ቀደም ብዬ ከምድር ጦር ዘመቻ መምሪያና ከአንደኛ ክፍለ ጦር ንዑስ ደርግ ጋር ተነጋግሬ ሁለት ብርጌድ እግረኛ ጦር አዘጋጅቼ ነበር። ሻለቃ አጥናፉም ስለ ጉዳዩ አጣዳፊነትና ስለ ሚጠይቀው አስቸኳይ ውሳኔ ከእኔም በጠንከረ አነጋገር ከተቀመጠበት ተነስቶ የጄነራል አማንን የማዘግያ ስልት ተቃወመ።

ጄነራል አማን "እዚህ ከሚወሰን የጦር ሥምሪት ዝርዝር ወታደራዊ ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ሳይሆን በቦታው ይወሰን ያልኩት በጦር አይነትና በጦር አላላክ ረገድ ያለውን የሎጂስቲክና የአስተዳደር ዝባዝንኬ በማሰብ ነው። ለምሳሌ በበኩሌ በአውሮፕላን እግረኛ ጦር መላኩ

አሁን ያለውን የኤርትራ ወታደራዊ ሁኔታ ይለውጠዋል የሚል እምነት የለኝም። አስፈሪነት፣ ተንቃናቂነትና የተኩስ ኃይል ያለው ታንከኛ ጦር ነው መላክ የሚያስፈልገው” አሉ።

ይህንን ሲሉ በተናገሩት ነገር እራሳቸው አምነውና ትክክል ነው ብለው ሳይሆን፣ ለኤርትራ ረዳት ጦር እንዳይላክ ተከላከለ እንዳይባሉ፣ ጦር የመላኩን አስፈላጊነት ተቀብለው ጦር እንዳይሄድ ብዙ ጊዜ ለማባከን ያቀረቡትን የማዘግያ ሀሳብ የሚያስገርም ከመሆኑ ሌላ እዚያ ያለነው መኮንንኖች የወታደራዊ ሳይንስ ድሃ በማድረግ የሚሰድብ ነበር።

በአስቸኳይ ወደ ኤርትራ ረዳት ጦር የመላኩ አስፈላጊነት ታምኖበት ውሳኔ ከተገኘ በኋላ በጦር አይነትና ስምሪት ጉባዔውን በማነጋገር በሚባክነው እያንዳንዱ ደቂቃ በአሥመራ ጀግኖች የሚወድቁ መሆናቸው ስለተሰማኝ ጊዜ ለመቆጠብ ስል የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም የሆኑትን ሜ/ጄኔራል ግዛው በላይነህን ጠርቼ በጉባዔው አዳራሽ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀረብኩላቸው፡

“በአሁኑ ጊዜ የሰሜኑ ክፍለ ጦራችን ኃይሉ በመመናመኑ ወንበዴዎች አንዱ ጦር ከሌላው ጋር እንዳይገናኝና እንዳይረዳዳ ከማድረጋቸው በላይ የአሥመራን ከተማ በ10 ኪ/ሜ እርቀት ከበው ጥቃት በመጀመራቸው የክልሉ እዝ በአስቸኳይ ረዳት ጦር እንዲላክለት መጠየቁን ብቻ ሳይሆን አሥመራ ያለውን ወታደራዊ ሁኔታ ከማንም በላይ ወይም በበለጠ ይከታተላሉ። በዚህ አጣዳፊና አደገኛ ሁኔታ የወንበዴውን ጥቃት ለመከላከልና ብሎም መልሶ ለማጥቃት ለኤርትራ ምድር የሚያስፈልገን ታንከኛ ጦር ነው ወይስ እግረኛ ጦር?” የሚል ነበር።

ጄኔራል ግዛው በቀረበላቸው ጥያቄ ተገርመው ለመሳቅ ቢዳዳቸውም ራሳቸውን በመቆጣጠርና ኮስተር በማለት መልስ ከመስጠት ፋንታ መልሰው ጥያቄ ነበር ያቀረቡት፡

“ለመሆኑ እኛ ታንኮች አሉን እንዴ? እኔ እስከ ማውቀው ታንኮች የሉንም። ምናልባት ታንኮች የምንለው በኦጋዴን ያሉትን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሰሩ ያረጁ ታንኮች እንደሆነ ለታንክ ውጊያ በተመቸው ገላጣ ሜዳ፣ በታንክና በብረት ለበስ ጦር ሊወጋን ከተዘጋጀው ከሶማሊያ መንግሥት ጦር ጋር ለስሙም ቢሆን ተፋጠው ያሉ ናቸው።

በእኔ አስተያየት በቂ ታንከኛ ጦር የሚያስፈልገን በምሥራቅ ግምባር ነበር። በሰሜኑ የአገራችን ክልል፣ ከሁሉ በፊት የምንዋጋው ቀላል መሣሪያ ከታጠቁ ሽፍቶች ጋር እንጂ ታንክ ከታጠቀ ሠራዊት ጋር አይደለም። ከዚህ ሁሉ በላይ የኤርትራ መልክዓ ምድር በተለይ ደጋው የአሥመራ አካባቢ ለታንክ ውጊያ የሚያመች አይደለም።

ይህ ሁሉ ይቅርና ኦጋዴን ያሉት አሮጌ ታንኮች ወደ ኤርትራ እንዲሄዱ የሚያስፈልግ ቢሆን እንዴት ነው የሚሄዱት? በምንስ ነው የሚጓጓዙት? የታንክ ማጓጓዣ የለንም። እየተነዱ ለምን አይሄዱም ብሎ ከዚህ ቤት የሚጠይቅ ሰው አለ ብዬ አላምንም። ይሂዱ ቢባል ግን አንዳቸውም ከሐረርጌ ክፍለሀገር ሳይወጡ በየመንገዱ ተሰባብረውና ወላልቀው ነው የሚቀሩት።

አሁን በአጣዳፊ ወደ ኤርትራ ሊላክ የሚገባው ብቻ ሳይሆን ለማድረግ የሚቻለንም እግረኛ ጦር መላክ ነው። ለደፈጣ ተዋጊ ወይም ለጎሪላ ጦር ተቃዋሚው ቢቻል በጥሩ ሁኔታ የሰለጠነ ኮማንዶ ካልተቻለም እግረኛ ጦር ነው ብዬ አስባለሁ” አሉ።

ጄኔራል ግዛውን አመስግኜ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ አደረግኩ። ለዚህ በጣም ተራ ነገር ጄኔራል ግዛውን መጥራት ባላስፈለገም ነበር፣ ይሁንና በዚህ እንዳንከራከር ሁኔታው ስላስገደደ ጊዜ ላለማባከን ገላጋይ መቸቱ በጅቷል ብዬ አስባለሁ።

"አሁን ወደ ውሳኔ እንድናመራ ጉባዔውን እጠይቃለሁ" ስል ጄኔራል አማን ድንፋታ በተሞላው ሁኔታ ተነስተው "የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የተቀላቀለው በራሱ ፍቃድ እንጂ በጦር ኃይል ተገዶ አይደለም። ሊሆንም አይችልም" ብለው ለመጨረሻ ጊዜ ጉባዔውን በመርገጥ ከአዳራሹ ወጥተው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

እሳቸው ጉባዔውን ረግጠው ከወጡ በኋላ በቀረበው አጀንዳ ላይ አስፈላጊውን ውይይት በማድረግ፣ ከአንደኛው የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር የተቀነሱ ሁለት ብርጌድ ጦሮች ህዳር 6 ቀን 1967 ዓ.ም ዓለም አቀፍ በረራዎችን በማቆም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ስናጓጉዝ፣ ገንጣዮቹ አሥመራን ለመቆጣጠር ከሠራዊታችን ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ ያካሂዱ ስለነበር ለርዳታ የደረሱት ብርጌዶች ከአውሮፕላን እየወረዱ በቀጥታ ወደ ውጊያው ነበር የገቡትና አሥመራን ያዳኑት።

የኤርትራ ጉዳይ አጀንዳ ካለቀ በኋላ ብዙ የደርግ አባላት "በጄኔራል አማን ጉዳይ ላይም ተነጋግረን ዛሬውኑ አንድ ዘላቂ ውሳኔ መስጠት አስፈላጊ ነው" የሚል ሀሳብ አቅርበው ነበር።

እኚህን ሰው ከጡረታ አምጥተን በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ታላላቅ ኃላፊነቶችን ከመስጠት ባሻገር የደርግ አባልና ሊቀመንበር ያደረግናቸው ስለሆነ ስለሚገለሉበት ሁኔታ ተገቢውን ጥናትና ዝግጅት አድርገን ለጉባዔው ውሳኔ ስለምናቀርብ የሚያስቸኩለን ምክንያት የለም በማለት በእዚያ ዕለት በነበረው የቁጣ ስሜት እንዳይወሰን አዘገየነው። አብዛኛው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት ጄኔራል አማንን በተመለከተ፣ ስህተት የተሰራው ከመጀመሪያው ለእሳቸው የሰጠነው ግምትና እምነት ነው ካሉ በኋላ የእሳቸውን ስህተት እኛ መድገም ሳይኖርብንና፣ ቅጣት፣ እስርና እንግልት ሳይደርስባቸው በጤና መታወክ ምክንያት አድርገን በሰላም ወደ ጡረታቸው እንመልሳቸው የሚል አቋም ነበረ።

በዚህ መንፈስ እናስናብታቸው ዘንድ ጊዜ ወስደን፣ በቅድሚያ አብዛኛው የደርግ አባላት ይህንን ሀሳብ ይደግፍ ዘንድ ለማግባባት እየሰራን የአስተዳደርና የሕግ ኮሚቴዎች በቅንጅት በሰላም ወደ ጡረታ የሚሄዱበትን ሁኔታ አጥንተው እንዲያቀርቡልንና ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ከተመለከተው በኋላ ለጉባዔው ይቀርባል የሚል ውሳኔ ላይ ተደርሶ ነበር።

የኤርትራን ሁኔታ በተመለከተ ሁለት ብርጌድ ረዳት ጦር ከላክንም በኋላ ወንበዴውም በበኩሉ ደጀን ጦሩን ከያለበት እየሰበሰበ አጥቂውን ጦር በየጊዜው እያጠናከረ የአሥመራ ሁኔታ አሳሳቢ ስላደረገው፣ በባሌ ክፍለ ሀገር ውስጥ ፀጥታ ሲያስከብር የነበረውን አንድ የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር፣ ከብሔራዊ ጦር ሁለት ብርጌድ ጦር፣ በዚሁ መጠን ከሠራዊቱ በጡረታ ተገልለው በእረፍት ላይ የነበሩትን እድሜያቸው እስከ ሰባ አመት የደረሰ አባት ጦሮችን ልከን የአሥመራ ከተማ በወንበዴዎች እጅ እንዳይወድቅ ማድረግ ቢቻልም ከበባው ለሁለት ዓመታት ያህል ቆይቶ የተጣሰው በ1970 ዓ.ም ሕዝባዊ ሠራዊት ካደራጀን በኋላ ነበር።

ይህንን በመሰሉ ውስብስብ ችግሮች ተወጥረን ሳለ ጄኔራል አማን አርፈው ቤታቸው በመቀመጥ የሚሰጣቸውን ውሳኔ ከመጠበቅ ፋንታ፣ መከላከያ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤታቸው በመሄድ የጦር ኃይሉን በደርጉ ላይ የሚያሳድም መልዕክት ጽፈው የጦር ኃይሎች መምሪያ ውስጥ ባለው የመገናኛ ማዕከል አማካኝነት ከላይ እስከ ታች በተለያየ የሥልጣን ደረጃ ላይ ላሉ ለመላው የጦር ክፍል አዛዦች ይላክ በማለት ሻምበል ፍቅሩ ከበደ ለሚባል የቅርብ እረዳታቸው ለሆነ መኮንን ይሰጡታል።

መኮንኑ የቅርብ ጓደኛችን ብቻ ሳይሆን ብልህና ንቁ የአብዮቱ ደጋፊ ስለነበረ የመልዕክቱን ይዘት ከተመለከተ በኋላ በመኪና እየበረረ መጥቶ ለደርጉ የደህንነት መምሪያ ያስረከብና ተመልሶ በመሄድ ለጄኔራል መልዕክቱ ተላልፏል ሲላቸው "ወደ ቤቴ ሄጃለሁ። አንተ ከዚህ ሳትንቀሳቀስ ከየጦሩ ክፍል የሚመጡ መልሶችን ቤቴ ድረስ አምጣልኝ" ብለው በማዘዝ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።

የጦር ኃይሎች የመገናኛ ማዕከል ይህንን የመሰለ ፀረ-አብዮት ተግባር መጠቀሚያ እንዳይሆን አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠትና አስፈላጊውን ሰው በቦታው ላይ ካስቀመጥን በኋላ ጄኔራል አማን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቤታቸው እንዲጠበቁ ተደረገ። የቤታቸው ስልክ መድረስ በሚችልበት ስፍራ ሁሉ እየደወሉ መሠረት በሌላቸው ግን መሰረ ክሶች ደርግን እየወነጀሉ የጦር ኃይሉንና ሕዝቡን ለአመጽ ከመቀስቀስ ሌላ ጉዳዮን ከሃገር ውጪም ለማሰራጨት ሞከሩ።

ስልካቸው እንዲቆረጥ ተደርጎ ለተለያዩ ተቋማት፣ ለጦር ክፍሎችና ለግለሰቦች የተናገሩትንና ያሰሙትን ፀረ-ደርግ፣ ፀረ-አብዮትና ፀረ-አንድነት ንግግሮች የቴፕ ቅጂ በደርጉ ስብሰባ አዳራሽ የደርጉ አባላት እንዲያዳምጡ ተደረገ።

የንግግሩ ይዘት በሀሰት ላይ የተመሠረተ ውንጀላ ከመሆኑም በላይ ጸያፍና ብልግና የተሞላው፣ ለብዙ ጊዜ ሲሰውሩ የሞከሩትን የአሮጌው ሥርዓት ናፋቂና የለየላቸው አድሃሪ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነበር።

ቴፑ ከተደመጠ በኋላ መላው የደርጉ አባላት በቁጣ እየተነሱ አሁኑኑ ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር ይቀላቀሉ ሲሉ ጠየቁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አመጽ ከተቀሰቀሰበት ከ1966 ዓ.ም ወርሃ የካቲት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሠራዊት ጄኔራል መኮንኖችን ከገዥው መደብ ጋር ፈርጆ ያስርና ከሥራቸው ያባርር ስለነበረ መከላከያ ሠራዊቱ መሪ አልባ እንዳይሆን ቢያንስ በጣም ጥቂቱን ጄኔራሎች ለማትረፍ ታላቅ ትግል አድርገናል።

በተለይና በቅድሚያ ለከፍተኛ ኃላፊነት ያጩናቸውን ጄኔራል አማንን በሠራዊቱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ቅስቀሳ የጀመርነው ከደርጉ መቋቋም በፊት ነበር።

ከሚገባቸው በላይ ስለ ካብናቸውና ስላሞካሸናቸው፣ መላው ሠራዊት ባይሆንም ቢያንስ ከፊሉና በተለይም እኔ የምወክለው ሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ጄኔራል አማንን ይመለከታቸው የነበረው በአክብሮትና በፍቅር ነበር።

ስለሆነም እሳቸውን ከሥልጣን ለማውረድ የምንወስደውን ርምጃ ሠራዊቱ በአሉታዊ ሁኔታ ተመልክቶ ለመቃወም እንዳይሞክርና አንድነቱ እንዳይናጋብን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን።

መደረግ ከነበረባቸው ጥንቃቄዎች ዋናውና የመጀመሪው ከሰኔ 26 ቀን 1966 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 4 ቀን 1967 ዓ.ም ድረስ ማለትም ጄኔራል አማን የደርጉን ጉባዔ ረግጠው እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ያከናወኗቸውን ፀረ-ደርግ፣ ፀረ-አብዮትና ፀረ-አንድነት ድርጊቶች፣ ሰነዶች፣ በቴፕ የተቀዱ ንግግሮች ተሰብስበው በማስረጃነት እንዲቀመጡ መዘጋጀት ነበረባቸው።

በቂና ምናልባትም ከሚፈለገው በላይ ማስረጃዎቹ ያሉን ቢሆንም የማስረጃዎቹ መኖርም ሆነ ትክክለኛነት የሚታወቀው በደርጉ አባላት እንጂ በሠራዊቱ ስላልሆነ፣ ለሠራዊቱ ከእኛ በተሻለ የሚቀርቡትን የንዑስ ደርግ አባላትን ከየጦር ክፍሉ መጥራትና ከዋናው ደርግ ጋር ማካተት የሠራዊቱን አንድነት ለመጠበቅ ታላቅ ፋይዳ ነበረው።

ከዚህም ሌላ በዓለም አቀፍ ብዙሃን ማሰራጫዎች በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ 32 ዓመት እድሜ ባለው በሻለቃ መንግሥቱና 66 ዓመት እድሜ ባላቸው ጄነራል አማን መካከል የሥልጣን ትግል እተካሄደ ነው እየተባለ የሚሰራጨውን የፈጠራ ወሬ ከንቱነትን የሚያጋልጥ መሆኑ በደርግ ስለታመነበት ህዳር 13 ቀን 1967 ዓ.ም በየጦር ክፍሉ ውስጥ ተቋቁመው የነበሩት ከ200 በላይ የሆኑ የንዑስ ደርግ አባላት ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው በደርጉ ስብሰባ አዳራሽ በመገኘት ከደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ ጋር የውሳኔ ተካፋይ እንዲሆኑ ተደረገ።

በስብሰባው አዳራሽ ወደ ዋናው አጀንዳ ከመግባታችን በፊት የወቅቱ የአገራችን ጠቅላላ ሁኔታ በአጠቃላይ በከፍተኛ ስጋት የምናስተውለው የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል ግንባታና ለወረራ የሚያደርገው ዝግጅት የሰሜኑ ሠራዊታችን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ለማስጠበቅ ከገንጣዩች ጋር የሚያደርገው የሞት ሽረት ትግል ተገለጠ።

በዚህ ባለ ብዙ ፈርጅ ውስብስብ ትግል ውስጥ በተለይ መከላከያውን በማደራጀት ሊረዱን ይችላሉ ብለን በማሰብ ከጡረታ ጠርተን፣ የደርግ ሊቀመንበርና የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ወዘተ ያደረግናቸው ሰው እኛን ከመርዳት ፋንታ የጉያ እሳት በመሆን የቱን ያህል እንደለበለቡን የሚያስረዳ ወንጀላቸው በማስረጃ ተደግፎ በዝርዝር ከተነገረ በኋላ ወደ አጀንዳው ዝርዝር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ስለ ወቅታዊ የአገራችን ሁኔታ በተሰጠው መግለጫ ላይ፣ ጥያቄ፣ ማብራሪያ የሚፈልግና ተጨማሪ ሀሳብ ያለው አስተያየቱን እንዲሰጥ መድረኩን ለጉባዔው አባላት ተከፈተ።

በአገሪቱ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅና ደቡብ ብቻ ሳይሆን በምዕራብና በመሃል አገርም ከአገር ገንጣዮች፣ ከውጭ ተስፋፊዎችና ከውስጥ ፀረ-ሕዝቦች ጋር ሠራዊታችን በመፋለም ላይ በነበረበት ወቅት ስለነበረ አብዛኛው የንዑስ ደርግ አባላት የተበሳቆሉና የተቆጡ ብሶተኞች ሲሆኑ የዋናው ደርግ አባላትም ቢሆኑ ጄነራል አማን ይሄንን ከመሰለ አስከፊ ሁኔታ ላይ ስለጣሉን 'ቁጭ ብለን የሰቀልነውን እንዴት ቆመን ማውረድ ይሳነን?' በማለት እንዲሁ የቁጣ ስሜት የነበራቸው ነበሩ።

ጥያቄ ያቀረበ ወይም የግል አስተያየት ለማቅረብ የፈለገ ሰው አልነበረም። ከሻይ ቡና እረፍት በኋላ የጉባዔው አባላት ስፍራቸውን እንደያዙ በጄነራል አማን ላይ በቀረበው ክስ ጉባዔው ይወያይ ዘንድ መድረኩ ተከፈተ።

የመቶ አለቃ ከዱ ዱሌ የሚባል ከምሥራቅ ግምባር የመጣ ነርስ መኮንን መድረክ ጠይቆ ተሰጠው። መኮንኑ የታወቀ ተናጋሪ ነው። አንድን ነገር ለማቀጣጠል ከፈለገ ይናገራል ከማለት እሳት ነው የሚተፋው ቢባል ማጋነን አይደለም።

የተነሳበት ዓላማ በጄነራል አማን ላይ ስለቀረበው ክስ አስተያየቱን ለመስጠት ሳይሆን የምንነጋገርበትን አጀንዳ በመቃወም ለማስለወጥ ነበር። ተነሳና "ጄነራል አማን ምንም ጥፋት የለባቸውም በወደቀው አሮጌው ሥርዓት ተወልደው ካደጉ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግዳጎዎች ከመሆናቸው ሌላ ፀረ-አብዮት ብቻ ሳይሆን ፀረ-አንድነትም የሆኑትን አድሃሪ ግለሰብ አብዮተኛና የሕዝብ ወገን ናቸው ብላችሁ የመከላከያ ሠራዊታችን መሪ ከማድረግ በላይ የአገሪቱም መሪ ያደረጋችኋቸው ሰዎች ናችሁ ጥፋተኞች።

ጄነራሉ ለራሳቸው መደብ እምነት ታማኝና የዓላማ ጽናት ያላቸው ሰው ናቸው ለማለት ይቻላል። እዚህ አሁን ባደመጥነው በቴፕ በተቀዳ ንግግራቸው፣ ከጄነራል ግዛው በላይነህ ጋር ሲነጋገሩ ያሉትን እጠቅሳለሁ 'እኔ እኮ የምታገለው ለጄነራል መኮንኖች ክብር ነው' ብለዋል።

ለቃመንበር መንግሥቱ ስለ ጄነራል አማን ወንጀል ሲነግሩን ‘በዚህ ሁሉ ውስብስብ ችግር ውስጥ እኛን ከመርዳት ፋንታ የጉያ እሳት ሆነው ሲለበልቡን ከረሙ’ ብለዋል።

እኔ እርስዎንና ይህንን ታሪካዊ ጉባዔ የምጠይቀው በዚህ ታሪካዊ ቀንና ታሪካዊ ጉባዔ ላይ መነጋገርና መወሰን ያለብን በአንድ ጄነራል ላይ ነው? በእኔ አስተያየት በጉያችሁ አቅፋችሁ የያዛችኋቸው እጅግ አደገኛ የጉያ እሳቶች እነዚህ አጠገባችሁ አስቀምጣችሁ የዶሮ ፍትፍት ምትመግቧቸው የጉልታዊት ኢትዮጵያ ታላላቅ መሣፍንት፣ መኳንንትና አያሌ አማን አንዶሞች እና ጄነራሎች ናቸው።

የጄነራል አማን የመፈንቅለ መንግሥት እቅድ ምናልባት ከሽፎ ይሆናል ግን ሌሎች አማኖች የሉም? ይሄ መንግሥት ቢገለበጥ እነዚህ የጉያ እሳቶች ለእኛ የአንድ ሰዓት እድሜ ይሰጡናል?

የሰሜኑን፣ የሰሜን ምዕራቡን፣ የሰሜን ምሥራቁን፣ የምሥራቁንና የደቡብን ቡርቦራና ብሎም የሶማሊያን ወረራ መክተን ኢትዮጵያንና አብዮቷን ለማዳን የምንችለው እነዚህን የጉያ እሳቶች እዚህ አስቀምጠን የዶሮ ፍትፍት እየመገብን ነው?

በውስጥ የታወጀብንን ጦርነት መክተን የምንረታው እነዚህን ሰዎች እዚህ ጉያችን አስቀምጠን ፍትፍት እየመገብን አይመስለኝም። ስለዚህ ለሊቀ መንበራችንና ለዚህ ታላቅና ታሪካዊ ጉባዔ በጥብቅ ላሳስብ የምፈልገው አሁን እዚህ መወያየት ያለብን ጄነራል አማን ፈፀሙ በተባለው ወንጀል ላይ ሳይሆን በቅድሚያ መወያየት ያለብን በቀረበልን አጀንዳ ላይ መሆን አለበት ባይ ነኝ” ሲል አብዛኛው የጉባዔ አባላት ተነስተው በመቆም በረጅም ጭብጨባ ደገፉት።

የውይይቱን መንፈስና አጀንዳ ብቻ ሳይሆን ቤቱንና አየሩን ፍፁም ለወጠው። በአመራር ልምዱ እንዲህ ያለና ያልተጠበቀ ዱብ እዳ ተፈጥሮ ጉባዔው ሲወጠር፣ የሻይ ቡና እረፍት ነው የምጠይቀው። በዚህ ዕለት የሻይ ቡና እረፍቱ የሰራው ለእኔ ሳይሆን ለመቶ አለቃ ከዱ ዱሌና ለመሰሎቹ ነበር። በዚህ እረፍቱ ጊዜ አጀንዳውን ለመለወጥ በአጀንዳው ላይ የመነጋገሩ ስልትና ጠቃሚነት ብዙሃኑ የንዑስ ደርግ አባላት እንዲገነዘቡት በመደረጉ አስቸጋሪውን ሁኔታ ለመፍጠር የረዳው በእረፍቱ ጊዜ በተደረገው የተቃዋሚዎቹ የሀሳብ ልውውጥ ነበር።

የመቶ አለቃ ከዱ ዱሌ በቅድሚያ በአጀንዳው ላይ እንነጋገር ብሎ ለመጠየቅ መብት ያለው ብቻ ሳይሆን የሕግም ድጋፍ የነበረው በመሆኑ ወደዚያ ላለመግባትና ወደ ተፈለገው ውሳኔ ለማምራት በእኔና በተቀሩትም የዋናው ደርግ አባላት የተደረገው የመከላከያ ሙግት ፋይዳቢስ ከመሆኑም ባሻገር የንዑስ ደርጉ አባላት በብዛታቸውም ደፈቁን።

በቅድሚያ በአጀንዳው ላይ እንነጋገር የተባለውን ጥያቄ ለመቃወም ከዚህ በላይ እንደገለጽኩት የሕግ ምርኩዝ ባይኖረንም፣ ሃገር አቀፍ በሆነ የሕዝብ ምርጫ እናንተ ዛሬ ፍርዳቸውን እኛ እዚህ እንመልከት የምትሏቸውን የቀድሞ ባለሥልጣኖች ወንጀል እየመረመረ ወደ ፍርድ የሚመራ መርማሪ ኮሚሽን በሕግ የተቋቋመ መሆኑን፣

መርማሪው ኮሚሽን በምርመራ እያጣራ ወደ ፍርድ የሚመራውን ጉዳይ የሚመለከቱ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው የፍርድ ቤቶች በሕግ መቋቋማቸውን፣ በአጠቃላይ ስለእነኝህ ተቋማት ተልዕኮና አሰራር በሕዝብ ከመታወቁ ባሻገር፣ አብዮቱ ‘ዓይን ያወጡ፣ አይናቸው ይውጣ’ የሚል አረታዊ ሕግ ሳይከተል ‘የተወነጀሉት የቀድሞ ባለሥልጣኖች ክስ ፍትሃዊ

በሆነ መንገድ እየተጣራ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ይታያል' ስንል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል ገብተናል ብንልም ያዳመጠን የለም።

ስለብዙዎቹ ይህንን ካላችሁ የጄኔራል አማንን ፍርድ እንድናይ ለምን ጠራችሁን? አሁንስ ስለ ሕግና ስለ ፍትህ የምንከራከረው በአሃዝ ላይ ነው ወይስ በሕግ ትርጉም ላይ ነው? የጄኔራል አማንን ወንጀል በዚህ ጉባዔ ላይ ማየት ከተቻለ ሌሎች በማናቸውም ጥፋትና የስጋት መመዘኛ ከጄኔራል አማን የሚልቁትንም ወንጀለኞች እንጨምር ማለታችን ስህተቱና ሕገ ወጥነቱ የቱና ምኑ ላይ ነው? እየተባለ የሚወረወረው ጥያቄም የሚያነቃንቅ ባለመሆኑና ጊዜውና ሁኔታው የተሰበሰበውን ሁሉ ስለአስተባበረው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊያቅደው ቀርቶ ባላሰበውና ባላዘጋጀው አጀንዳ ማለትም በጄኔራል አማን ጦስ ስልሳ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን ሰለባ ያደረገ ውሳኔ ለማስተናገድ ብንገደድም ለፍርድ የቀረቡት ባለሥልጣኖች ቁጥር አንድ መቶ ሀምሳ ሆኖ ሳለ በታላቅ ትግል ዘጠናውን ለማትረፍ ተችሏል።

ጄኔራል አማንን አገር ወዳድና የኢትዮጵያን አንድነት ደጋፊ አድርገን ከማየት በላይ የለውጥም ሃዋርያ በማድረግ ያንን ያህል ድርብርብና ወሳኝ ሥልጣን በመስጠት ቢያንስ አገርንና አብዮትን በማዳን ትግሉ አብረውን ይቆማሉ ያልናቸው ሰው የጥፋት መልዕክተኛ ሆነው ያንን በመሰለ ቀውስ ውስጥ ባይከቱን ኖሮ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም የተሰጠው አብዮታዊ ውሳኔ በዚያ መልኩ ይፈፀማል ተብሎ አይታሰብም።

ከህዳር 14 ቀን 1967 ዓም. በኋላ በተደረገው ውይይት ከጄኔራል አማን በኋላ ደርግንም ሆነ አገሪቱን ለመምራት ከደርግ አባላት በስተቀር ከውጪ ሰው መጠራት አይኖርበትም በሚል በብርቱ ያከራከረን ጉዳይ ነበር።

ሆኖም ደርጉን ስናቋቁም ከገባነው ቃል ኪዳን በተጨማሪ በህብረተሰባዊ የእድገት አቅጣጫ በመመራት ታላቅ ሕዝባዊ ዓላማ ያነገብን ስለሆነ በቢሮክራሲያዊ ሥራና ሃላፊነት ታስረን ከሕዝባዊ ዓላማችን እንዳንርቅ ወይም ዓላማችንን እንዳንስት ሌላ ግለሰብ ከውጭ ማምጣት እንዳለብን አምነንና ተማምነን ብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲን ተክተን ትግላችንን ቀጠልን።

የህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ ኢትዮጵያ የወያኔ ቅኝና የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት የእጅ አዙር ቅኝ ሳትሆን አብዮታዊ ሃገር ነበረች።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በኢትዮጵያ ይካሄድ የነበረው ሥር ነቀል ሕዝባዊ አብዮት ነበር። ሕዝባዊ አብዮት ማለት ደግሞ የሕዝብ የበላይነት ማለት ነው። ስለሆነም የህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ታሪካዊ ውሳኔ የሕዝብ ውሳኔ ነበር።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

# ደርግና ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ

ስለ ደርግና ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ከመተረኬ በፊት የኔንና የሻለቃ ተፈራ ተክለዓብን አብሮ አደግነትና የረጅም ጊዜ ወዳጅነት መግለፅ እወዳለሁ።

ሁለታችንም የወታደር ልጆች፣ በአዲስ አበባ በአንድ መንደር ያደግን፣ የልጅነትና የትምህርት ቤት ጓደኞችና አብሮ አደጎች ከመሆናችን ባሻገር በአዲስ አበባ በ1950 ዓ.ም በ19ኛው እጩ መኮንኖች ውድድር መመልመያ በተሰጠው ፈተና ላይ አብረን ጎን ለጎን ተቀምጠን ሁለታችንም በጥሩ ውጤት በማለፍ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ገባን።

በጦር ትምህርት ቤቱ የሚሰጠውን ኮርስ ስንከታተል ቆይተን ከሁለት ዓመት በኋላ በ1952 ዓ.ም መባቻ ላይ ስንመረቅ በአገራችን ሰሜን የኤርትራ ገንጣዮች አገርና ወገናቸውን ለመውጋት በካይሮ ተደራጅተው በተቀሩት የተለያዩ አረብ አገሮች ማለትም፣ በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በአልጄሪያና በሱዳን ወታደራዊ ሥልጠና የሚቀበሉበት ጊዜ ነበረ።

የኢትዮጵያን የአስተዳደር ክልል አንድ አምስተኛ አለኝታችን ነው የሚሉት ሶማሊያዎች ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ቅኝነት ነፃነታቸውን የሚያገኙበት ጊዜ ነበር።

በእነዚህ ሦስት የአገሪቱ ክልሎች ማለትም በሰሜን፣ በምሥራቅና በደቡብ ሠላምና ድንበር የማስከበር ተልዕኮ ያላቸውን የጦር ክፍሎች በሰው ኃይልና በአመራር ለማጠናከር ተፈልጎ ከ117 የ19ኛው ጊዜ ምሩቅ ወጣት መኮንኖች አሥራ አምስት ከመቶ በደቡብ ኢትዮጵያ ላሉ የጦር ክፍሎች፣ ሃያ አምስት ከመቶ በሰሜን ኢትዮጵያ ላሉ የጦር ክፍሎች አስር ከመቶ በመሐሉ ሃገር ሲደለደሉ የተቀረነው ስልሳ ከመቶ የሆነው የተደለደልነው ለምሥራቁ ክልል የጦር ክፍሎች በተለይም በኦጋዴን ነበር።

እንዳጋጣሚ ሆኖ በዚህም ጊዜ እኔና ም/የመቶ አለቃ ተፈራ ተክለዓብ ሳንለያይ በምሥራቁ ክልል በሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር እዝ ሥር ባለው በዘጠነኛ እግረኛ ብርጌድ ውስጥ ስንደለደል የተለያየነው በሻለቃ ደረጃ ብቻ ነበር።

የእሱ የመጀመሪያው እናት የጦር ክፍል ቀብሪደሐር አውራጃ የሚገኘው 13ኛው እግረኛ ሻለቃ ሲሆን የኔ፣ በዋርዴር አውራጃ የነበረውና ነብሮ በመባል የሚታወቀው ዘጠነኛው እግረኛ ሻለቃ ነበር።

እሱ በጥቂት ወራት ሲበልጠኝ የሁለታችንም እድሜ 19 ዓመት ነበር። በዚያን ጊዜ በነበረው የመኮንኖች እጥረት ምክንያት አንድ የሻምበል ማዕረግ ያለው መኮንን ሊሠራው የሚገባውን ሥራ ወይንም ኃላፊነት በአንዳንድ የጦር ክፍሎች ውስጥ ለምክትል የመቶ

አለቆች ይሰጥ ስለነበር ወደ እናት የጦር ክፍላችን እንደደረስን ሁለታችንም የየክፍላችን ጥብቅ የትምህርትና የዘመቻ መኮንን ሆንን።

ከአንድ ዓመት በኋላ በ1953 ዓ.ም በነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት ከከሸፈ በኋላ የሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ብ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ጄኔራል ፅጌ ዲቡን ተክተው የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሆነው ሲሾሙ፣ ብ/ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም የሦስተኛው እግረኛ ክፍለጦር አዛዥ ሆነው ሐረር መጡ።

ሐረር በደረሱ ማግሥት አጋዴን ከነበሩት አንዳንድ የጦር ክፍል አዛዦች በምስጢር የተላከላቸው ደብዳቤ በታህሳሱ መፈንቅለ መንግሥት የሙከራ ጊዜ የቀደማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት ከደው አማጺያኑን ደግፈዋል ተብለን በአዛዦቻችን የተወነጀልን የስምንት መኮንኖች የወንጀል ሐተታ ነበር።

የተወነጀልነው መኮንኖች የስም ዝርዝር ከዚህ ግርጌ የተመለከተው ነው።

1ኛ/ የመቶ አለቃ ባዩ ይርዳው
2ኛ/ የመቶ አለቃ ዘየደ ድንበሩ
3ኛ/ የመቶ አለቃ ሞልቶት
4ኛ/ ም/የመቶ አለቃ ተፈራ ተክለዓብ
5ኛ/ ም/የመቶ አለቃ ኤፍሬም ገብረሃና
6ኛ/ ም/የመቶ አለቃ ዘለቀ መንግሥቴ
7ኛ/ ም/የመቶ አለቃ ዳንኤል ደስታ
8ኛ/ ም/የመቶ አለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም

በኔ በኩል ጄኔራል አማንን ማክበር፣ ማፍቀርና ባለውለታችን ማለት በዚህ ጊዜ ይጀምራል።

የአባት ያህል በእድሜ የሚበልጡኝና በማዕረጋቸው ብዙ የሚልቁን አዛዦቻችን ሊመሩን፣ ልጅነታችንን አይተው ሊመክሩን ሲገባ በተገኘው አጋጣሚ እኛን በመወንጀል እነሱ የሥርዓተ ማህበሩና የንጉሡ ታማኝ ተብለው ለመሾምና ለመሸለም የጻፉትን ወንጀል ጄኔራል አማን ከተመለከቱ በኋላ የወነጀሉንን አዛዦች ከያሉበት ጠርተው በገፅ "አባቴን ተክቻለሁ ያሉት ወራሽ ዘውዱ አልጋወራሽ እያሉ እነዚህን ወጣት መኮንኖች ከሐዲ ብላችሁ በመወንጀላችሁ በኔ አስተያየት ወንጀለኞች እነሱ ሳይሆኑ እናንተ ናችሁ። እኔ በማዘው ክፍለጦር ውስጥ የማዛቸውን ወጣት መኮንኖች የሚመራ፣ የሚያስተምርና የሚመክር እንጂ የሚወነጅል አዛዥ አልፈልግም" በማለት ገስፀው ከመለሷቸው በኋላ የተወነጀልነውን መኮንኖች በሙሉ ከነበርንበት የጦር ክፍል እያንዳንዳችንን ወደ ሌላ የጦር ክፍል ሲያዛውሩ እኔንና ም/የመቶ አለቃ ተፈራ ተክለዓብን ሐረር ጠርተው፣ እሱን በሰሜን አሜሪካ በአትላንታ ጆርጂያ ስቴት ወሰጥ ባለውና በታወቀው የጦር ትምህርት ቤት ውስጥ ከፍተኛ የእግረኛ መኮንን ትምህርት እንዲከታተል፣ እኔን በዚሁ በሰሜን አሜሪካ በሳቫና ኢሊኖይስ ስቴት ውስጥ በሚገኘውና በታወቀው ታላቅ የወታደራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርመርና ጥናት እሚደረግበትና የተለያዩ ቴክኒካዊ ሙያዎች ሥልጠና እሚሰጥበት ተቋም ላኩን።

እኔ በኢሊኖይ የቆየሁበት የትምህርት ጊዜ ከመቶ አለቃ ተፈራ የትምህርት ጊዜ ያጠረ ስለነበረ ቀድሜ ወደ አገሬ በመመለሴ ጄኔራል አማን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ባነጋገሩኝ ጊዜ ነው ከኔ ጋር የስምንት መኮንኖችን የስም ዝርዝር በማሳየት ስለተወነጀልንበትም ጉዳይ ያስረዱኝና ምስጢር ስለሆነ ለማንም እንዳትናገር ያሉኝ።

ቃሉን በመጠበቅ ለማንም ሳልናገርኖሬ ታሪክ በመሆኑ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ በትግላችን ታሪክ ውስጥ አክዬ ለሕዝብ ያቀረብኩት።

በአዛገቻችን የተወነጀልነውን የስምንት መኮንኖች የስም ዝርዝር ካሳዩኝና ስለተወነጀልንበትም ምክንያት ካብራሩልኝ በኋላ እሳቸው በሠራዊቱ ውስጥ በአጠቃላይና በኮሪያ ጦርነት በተለይ የገጠሟቸውን አያሌ ገጠመኞች በማስረዳት፣ በዚህ የፊውዳል ሥርዓተ ማህበር ውስጥ በአጭር እንዳትቀጭ ተጠንቀቀህ እራስህን ጠብቅ በማለት ያስናበቱኝ።

የመቶ አለቃ ተፈራም የትምህርት ተልዕኮውን አከናውኖ ስለተመለሰና ሁለታችንም በክፍለ ጦሩ መምሪያ ውስጥ በጄኔራል አማን አጠገብ እንደሞያችን ሥራ ተሰጥቶን በሐረር ከተማ ለመኖር በመቻላችን አንዲት አነስተኛ የጭቃ ቤት ተከራይተንና አንዲት መጋቢ ቀጥረን በዩጋንዳ ርዕሰ ከተማ በካምፓላ ያለው በዚያን ጊዜ በአፍሪካ ትልቅ ስም ከነበረው ማካረሬ ዩኒቨርሲቲ በመላላክ ትምህርት የድግሪ ፕሮግራም እሱ የሕዝብ አስተዳዳር እኔ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ኮርስ መከታተል ጀመርን።

በመላላክ ትምህርት የምንከፍለው ገንዘብ ከወር ደመወዛችን ከግማሽ በላይ ይወስድብን ስለነበረ የገጠመንን የገንዘብ ችግር የተረዱልን አዛዣችን ጄኔራል አማን የየወሩን ክፍያ በሙሉ ከክፍለ ጦሩ ልዩ የገንዘብ ገቢ እንዲከፈልልን በማዘዝ ትልቅ ችግር አቃለሉልን።

በአንባቢ ዘንድ ይታወስ እንደሆን ስለጄኔራል አማን ስተርክ ባለውለታዬ ነበሩ ያልኩት ለኔ ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች በሚያደርጉት አባታዊ ተግባራቸው ምክንያት ነው።

በእኛም ቅርባቸው በነበርን ወጣት መኮንኖች በኩል እሳቸውን እጅግ በማፍቀርና እንደ አባታችን በመመልከት ያላባራ እድገትና መልካም ስም ማግኘት ስንመኝ፣ እሳቸው ወይንም ሥራቸው የተሳካ እንዲሆንና ከእኛም ባሻገር በሠራዊቱ እንዲወደዱ አቅማችን በፈቀደልን መጠን ከልባችን ስንጥር ነበር።

ወጣት መኮንኖች በአጠቃላይ፣ እኔና ተፈራ በተለይ ቋሚ ሥራችን አድርገን በየደረስንበት ሥፍራ፣ ላገኘነው ለሠራዊቱ አባሎችና ለሲቪሉ ሕብረተሰብ ጭምር አዛዣችንን የምንጠራቸው አማን ብለን ሳይሆን አንበሳው እያልን ነው። ጄኔራል አማን በሐረርጌ ክልል የሚጠሩት አንበሳው በመባል ነበር።

አንበሳው አዛዣችን የሦስተኛውን እግረኛ ክፍለ ጦር አርማ የተቆጣ አንበሳ በማድረግ አንበሳው ክፍለጦር ያሰኙት ከመሆናቸው ባሻገር ክፍለ ጦሩን ከአገሪቱ እግረኛ ክፍለጦሮች ሁሉ በማናቸውም ረገድ የላቀ በማድረግና በማዘመን፣ የተለያዩና ያላቋረጡ ወታደራዊ ትምህርቶች በመስጠት የሚያምኑ ሰው ስለነበሩ ለዚህ ተግባር ይረዱኛል በማለት ያስመጧቸው አሜሪካውያንና እሥራኤላዊያን መኮንኖች አብረውን ይሰሩ ስለነበር፣ በእነኝህም አዛዣችን የሚጠሩት አማን በመባል ሳይሆን ኤ-ማን (A-Man) በመባል ነው። ብለን ስለነገርናቸውና እነሱም ይህንኑ ስላዛመቱት፣ ጄኔራል አማን አገራችን በነበሩ ባዕዳን ወታደራዊ ልዑካን ዘንድ የሚጠሩት ጄኔራል ኤ-ማን በመባል ነበር።

በዚህ ሁኔታ የእሳቸውን ስምና ዝና እናሳድጋለን ብለን ያደረግነው ነገር ሁሉ እሳቸውን የጎዳ እንጂ የጠቀመ አልሆነም። እቻቸው የሆኑት የማዕረግ ጓደኞቻቸውና የበላዮቻቸው ሲቀኑባቸው ቤተመንግሥቱ ሳይጠረጥሩና ሳይፈሩ አልቀሩም ያሰኘን፣ በዕድሜ የሚልቋቸው ብዙ ጄኔራሎች እያሉ የእሳቸው በጡረታ ከሠራዊቱ መገለል ነው።

እሳቸው ከአንበሳው ክፍለ ጦር አዛዥነት ሲነሱ የተኳቸው ጄነራል አበበ ገመዳ ናቸው። ጄነራል አማንና ጄነራል አበበ በጣም የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑም ጄነራል አበበም በጣም ጥሩ አዛዥ ነበሩ።

ሻምበል ተፈራ ተክለዓብን የክፍለ ጦር የትምህርት መኮንን ሲያደርጉት እኔንም ካሰብኩት ማዕረግ በላይ ሲሆን አንድ ከፍተኛ ኃላፊነት ለመስጠት አሰበው፣ አሥመራ ቃኘው ከሚባለው የአሜሪካኖች ወታደራዊ መደብ አዛዥ ጋር ተነጋግረው በማስፈቀድ በቃኘው መደብ ወይንም የጦር ሠፈር ውስጥ የሥራ ልምድ እንድቀስም ታዝዤ ለመጀመሪያ ጊዜ አሥመራ ለሁለት ወራት ቆየሁ።

በአሥመራ ቆይታዬ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ቅርንጫፍ የትምህርት ተቋም ተከፍቶ፣ በአሥመራ ከተማ ነዋሪ የሆኑና የትምህርት ፍላጎት የነበራቸው ሰዎች ከሲቪሉም ከመለዮ ለባሹም በዲፕሎማና በድግሪ ደረጃ የሚሰጡ የተለያዩ ትምህርቶችን ሲሳተፉ ተመለከትኩ።

ከዚህ በፊት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ቅርንጫፍ ከፍቶ የትምህርት አገልግሎት ስለመስጠቱ መረጃ አልነበረኝም።

ወደ አሥመራ የተላኩበትን ተልዕኮ በሁለት ወር አከናውኜ ወደ ሐረር ስመለስ ለተፈራ ከእንግሊዝ ወዲያ ከባዕድ ሃገር የተልዕኮ ትምህርት መማራችን ቀርቶ በአገራችን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ቅርንጫፍ በሐረር እንዲከፈት ማድረግ አለብን ብዬ ካነጋገርኩት በኋላ እሱም በሃሳቤ በመስማማቱ የአንድ ሳምንት ፈቃድ ተቀብለን ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሄድን።

በዚህ ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝንዳንት ልጅ ካሳ ወ/ማርያም የሚባሉ ወጣት ግለሰብ ነበሩ። እሳቸውን ማሳመኛ ያልናቸውን አያሌ ምክንያቶች በመደርደር እንደ አሥመራው በሐረርም የዩኒቨርሲቲውን ቅርንጫፍ በመክፈት ይተባበሩን ዘንድ ጠየቅናቸው።

በትብብሩ ሳያመነቱ እንደውም ተደስተው ፈቃደኛነታቸውን ከገለፁልን በኋላ እናንተ እንደ አሥመራ ከተማ ነዋሪዎች ለቅርንጫፍ መሥሪያ ቤትና የመማሪያ ክፍሎች፣ ከዚያው ከአካባቢው በተለያዩ ሞያዎች በሁለተኛ ድግሪ የተመረቁና ለማስተማር ፈቃደኛ የሆኑ መምህራን ልታገኙ ከቻላችሁ የመምህራኑን ደሞዝ ለመክፈልና ቅርንጫፉን ለመክፈት ዝግጁ ነኝ ብለውን ወደ ሐረር ተመለስን።

ሐረር እንደደረስን የክፍለ አገሩን የትምህርት ሚኒስቴር ወኪል ጽሕፈት ቤት ሠራተኞችና ዋናውንም ሰው ደህና አድርገን የምናውቃቸው ስነበሩ በወሰድነው እርምጃ ተደስተው በልዑል መኮንን ስም የሚጠራው የከተማው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በምሽት ለቅርንጫፉ አገልግሎት እንዲውል ፈቀዱልን።

በመምህራን በኩል በኋላ ልጅ ካሳ ከአሥመራ መምህራን በዓይነትም ሆነ በመጠን እጅግ የተሻለ ነው ያገኛችሁት እንዳሉት፣ ከሐረር ወታደራዊ አካዳሚ የተለያየ ሞያ ያላቸው ሕንዳዊ ፕሮፌሰሮች በዚያን ጊዜ የሐረር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሳይንስና የማትስ መምህር የነበሩ ሌላ ሕንዳዊ ዶክተር፣ ሁለተኛ ድግሪ ያላቸው ሕንዶችና የሠላም ጓድ የሚባሉ አሜሪካዊያን ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋምና ከዓለማያ ግብርና ኮሌጅ እንዲሁ በርካታ ኢትዮጵያዊ ምሁራን በአጠቃላይ በቂ መምህራን ማግኘት ተቻለ።

የመምህራን ማፈላለጉን ሥራ እኛ ካከናወንን በኋላ ቀሪውን ቴክኒካዊ የሆነውን ቅርንጫፉን የማቋቋም፣ ሥርዓተ ትምህርቱንና ጠቅላላ ቅርንጫፉን የመምራትን ጉዳይ በተመለከተ እኛን ወክለውና በኋላም የቅርንጫፍ ርዕሰ መምህር ሆነው እንዲሠሩ የመረጥናቸውን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ በመምህርነት የኖሩና ዶክተር ጋዘላ የሚባሉትን ሕንዳዊ ምሁር ይዘን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በመሔድ ያደረግነውን መሰናዶ በመግለፅ ዶክተር ጋዘላን ከልጅ ካሳ ጋር አስተዋውቀን በመተው እኛ ተመለስን።

ከዚህ በኋላ የነበረብን ቀሪ ሥራ ተማሪ ማፈላለግና ማሰባሰብ ነበረ። በዚህ ረገድ እንዳሰብነው ብዙ ትምህርት ፈላጊዎቹ ባናገኝም ቅርንጫፉን ለመክፈት የሚያበቃ የተማሪ ቁጥር አስመዘገብን።

በጥቂት ወራት ውስጥ በዩንቨርስቲው ፕሬዝዳንትና በዶክተር ጋዘላ ጥረት ቅርንጫፉ ተከፍቶ ሥራውን በመጀመሩ እኔና ሻምበል ተፈራ ከማካሪሬ ዩኒቨርሲቲ ጋር ስናደርግ የነበረውን የመላላክ ትምህርት አቋርጠን በቅርንጫፉ ለአንድ ዓመት ትምህርታችንን ለመከታተል ብንችልም በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች የቅርንጫፉ ተጠቃሚ ግን አልሆንም።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር የኮሌጅ ወይንም የዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል የትምህርት መሰናዶ ያላቸውን መኮንኖች ወደተለያዩ አገሮች ከመላክ ባሻገር በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ማስተማር ጀምሮ ስለነበረ እኔና ሻምበል ተፈራ የክፍለ ጦር አዛዣችን ጄነራል አበበ ገመዳ ይፈቅዱልን ዘንድ ብንጠይቃቸው 'የጠየቃችሁት በእውነት ጊዜ ነው። ሁለታችሁንም ለተለያዩ ብርቱ ሥራዎች ስለምፈልጋችሁ የአንድ ዓመት ጊዜ ስጡኝ' በማለት አቆዩን።

በኔ አስተያየት ጓደኝነታችንን የሚያውቁ ከመሆናቸው በላይ አብረን ስለጠየቅን እኔን ከሻምበል ተፈራ ላለመለየት ብለው እንጂ ለአጣዳፊና እንዳሉትም እጅግ ከባድ ለሆነ ሥራ የፈለጉት እኔን ነበር።

የመጀመሪያው የሶማሊያ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው የሰሜን ሶማሊያ ተወላጅ ኢብራሂም ኢጋል የሚባለው ግለሰብ በምዕራቡ ዓለም የተማረና የፖለቲካ አስተሳሰቡም ምዕራብ ዘመም ከመሆኑ ጋር እንደሌሎቹ የሶማሊያ ፖለቲከኞች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በጠብና በፍጥጫ ሳይሆን በሰላምና በመተሳሰብ የምንፈልገውን ለማግኘትና በመልካም ጉርብትና ለመኖር ይቻላል የሚል አመለካከት የነበረው ግለሰብ ነው።

ይህ አቋሙ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ስለሚታወቅና ስለሚደገፍም በሁለተኛው የጠቅላይ ሚኒስትር ምርጫ እሱ ወድቆ ሌላ አክራሪ ግለሰብ እንዳይመረጥ ለመርዳት ተፈልጎ በተለያዩ የድንበር ላይ ወታደራዊ ግጭቶችና ውጊያዎች በህገወጥ ንግድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገብተው ሲሠሩ በየጊዜው በፊናስ ዘበኞች በጠረፍ ጠባቂ ፖሊሶችና እንዲሁም በጦሩ እየተማረኩና እየተያዙ በኢትዮጵያውያን የተወሰዱ የሶማሊያ ከበርቴዎችና ነጋዴዎች ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችን የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብስቦ ቢሰጠኝና እኔም ለባለንብረቶቹ በመልስላቸው በምርጫው ደምጽ አሰጣጥ የሚደግፉኝ ከመሆኑ ሌላ ከታላቋ ጎረቤታችን ከኢትዮጵያ ጋር በሠላምና በመልካም ጉርብትና መኖር ይበጃል የተሰኘውን የኔን አቋም አብዛኛው የሶማሊያ ሕዝብ ሊደግፍ ስለሚችል በዚህ ረገድ እርዱኝ በማለት ለንጉሡ ያመለክታል።

ንጉሡ በቀጥታ የሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦርና በሐረርጌ ክፍለሃገር የበላይ አስተዳዳሪ ለሆኑት ለጄነራል አበበ ገመዳ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢጋል በጠየቀውና በገለጠው ሁኔታ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሶማሊያ ከበርቴዎች ንብረት ናቸው የተባሉትን ተሽከርካሪዎች

ከያሉበት እፈላልገው በማሰባሰብና የተበላሹም ቢኖሩ በማደስ በአስቸኳይ አስረክብ ብለው ትዕዛዝ ይሰጣሉ።

ጄነራል አበበ ገመዳ ይህንን ንጉሡ የሰጧቸውን ትዕዛዝ እኔ እንድፈፅም ነው ዩኒቨርሲቲ ከመግባት ያስቀሩኝ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኢጋል ወደ ሶማሊያ እንዲመለሱ ዝርዝራቸውን ያቀረበው ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ቁጥር እኔና ጄነራል አበበ የሐረርጌን ምድር ከመርገጣችን በፊት ለብዙ ዓመታት የሶማሊያ ነጋዴዎች በህገወጥነት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሲያንቀሳቅሷቸው አብዛኛዎቹ በጥይት እየተደበደቡ የተያዙ፣ በድንበር ላይ ውጊያና ወታደራዊ ግጭቶች ለወታደሩ ቀለብና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲያቀርቡ የጋዩና የተማረኩ ከመሆናቸው በላይ አብዛኛዎቹ በእርጅናና በጊዜ ብዛት ከተሽከርካሪነት ወደ ተሽከርካሪ አፅምነትና አፈርነት የተለወጡትን ስለነበር ንጉሡ የፈለጉትን አድርገን ልናስደስታቸው የሚቻለን ስለአልነበረ ጄነራል አበበ እጅግ የተጨነቁበት ጉዳይ ከመሆኑ ሌላ ሥራውም በጣም ውስብስብ ያለ አስቸጋሪ ሥራ ነበር።

ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር ኢጋልና አፄ ኃይለሥላሴ እንደፈለጉት ማድረግ ባይቻልም ከፊሉን ያህል ሰብስብንና በከፍተኛ ወጪ አድሰን ለማሥረከብ በመቻላችን ንጉሡና ጄነራል አበበ ብቻ ሳይሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢጋልም ቢሆን ይቻላል ብሎ ያልገመተውን የተሽከርካሪ መጠን በማግኘቱ መደሰት ብቻ ሳይሆን ተደንቋል።

እንደተፈለገውም ኢብራሂም ኢጋል ባገሩ በሰሜኑ ክልል ብቻ ሳይሆን በደቡብም ክልል ከፍተኛ ድምፅ አግኝቶ ለሁለተኛ ጊዜ ተመረጠ።

ከዚህ በኋላ የተከተለው አሳዛኝ ነገር፣ አንድ ዓመት ያህል እንኳን ሳይቆይ የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይሎች ኢታማጆር ሹም የነበረው ኮሎኔል ዚያድ ባሬ የሶማሊያ ነፃ አውጪና የመጀመሪያ ፕሬዝዳንት የነበረውን ዶክተር አብዱ ረሺድ ሸርማርኬን አስገድሎ መንግሥት በመገልበጥ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢጋልን ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ጋር በመልካም ጉርብትና መኖርን የሚመርጡ አያሌ ደጋግና ሠላም ወዳድ የሶማሊያ ሕዝብ መሪዎች ለብዙ ዓመታት ዘብጥያ መጣላቸው ነው።

ጄነራል አበበ በጣም ተደስተው ስለነበረ እኔንም ያስደሰቱ መስሏቸው ከተሰጠኝ አስቸጋሪ ሥራ ፍጻሜ በኋላ ወዲያው በ1962 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ደግሞ ለከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርት ወደ ሰሜን አሜሪካ እንድሔድ ታዘዝኩ።

ለሁለተኛ ጊዜ የተላኩበት ትምህርት በመጀመሪያ ጊዜ ከተላኩበት የተለየ፣ ከጊዜም አንፃር ዘለግ ያለና ከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርት ሲሆን ክፍለ አገሩም ሜሪላንድ ስቴት ነበር።

ትምህርት ቤቱ የሚጠራው በከተማዋ ስም አበርዲን ፕሩቪንግ ግራውንድ በመባል ነው። ፕሩቪንግ ግራውንድ የተባለበት ምክንያት ከባሕር ኃይልና ከአየር ኃይል መሣሪያዎች በስተቀር የአሜሪካ የምድር ጦር ልዩ ልዩ የውጊያ መሣሪያዎች፣ ጥይትና ፈንጂዎች፣ ታንኮች፣ ብረት ለበስና ባለጎማ ተሽከርካሪዎች በጠቅላላው ለወታደራዊ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች ሁሉ ማለት ይቻላል የሚጠኑበት፣ የሚፈለሰፉበት፣ ንድፍ (ዲዛይን) የሚሠራበት፣ ከአምራች የሲቪል ኢንዱስትሪዎች ጋር በመዋዋል የሚያሥመርት የተመረቱትን በተግባር ፈትኖ መከላከያ ሚኒስቴር እንዲቀበል የሚያፀድቅ፣ በግምጃ ቤት

አቀማመጥና አያያዛቸውን፣ አጠቃቀምና ጥገናቸውን ለተገልጋዩ ሠራዊት የሚያስተምር ታላቅ የመፈተኛ፣ የምርምርና የሥርፀት ተቋም በመሆኑ ነው።

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያቶችና ደረጃዎች ከኔ በፊት ብዙ ኢትዮጵያዊያን መኮንኖች ተምረውበታል።

ተቋሙ አበርዲን በምትባለዋ አነስተኛ ከተማ አጠገብ 700,000 ሔክታር ስፋት ባለው መሬት ላይ የተንጣለለና በውስጡ ማናቸውም የአንድ ከተማ አገልግሎት ያለው ግን በጥብቅ የሚጠበቅ የጦር ሠፈር ነው።

ተቋሙ ከሚያከናውነው የሥራ ባሕርያት የተነሳ የጠላት ሠርጎ ገቦችን ለመከላከል ሲባል በጥብቅ የሚጠበቅና በጸረ-መረጃ ድርጅቶች የተጠናከረ ወይም የታጠረ ሲሆን ከመፈተን፣ ከምርመራና ከስርጸት በተጨማሪ የጦር መሣሪያዎች ሙዝየም ወይንም የታሪክ መዘክር ነው።

የታሪክ መዘክሩ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው የሚፈለግባቸውን አገልግሎት በጊዜያቸው ሰጥተውና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጣን ዕድገትና እንዲሁም ከአሜሪካ የጦር ኃይሎች ፍላጎት አንፃር አርጅተው በሌላ ተተክተው ከጥቅም ወይም ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የሃገር ሥሪቶች፣ በ1ኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች ወዘተ የተማረኩ አያሌ የተለያዩ መሣሪያዎች በግልፅ የሚታዩበት፣

ሁለተኛው በአገልግሎት ላይ ያሉና ከሚፈቀድላቸው የአገሩ ባለሥልጣኖች በስተቀር ለማንም ግልፅ ያልሆኑ መሣሪያዎች መዘክር ነው።

አሜሪካኖች የጦር መሣሪያ ማምረት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ያመረቷቸው የተለያዩ አያሌ መሣሪያዎች በቤተ መዘክሮቹ ይገኛሉ።

እንደ ቴክኖሎጂዎቹ ብዛትና መራቀቅ ትምህርት ቤቱ የሚሰጣቸው ትምህርቶችም እጅግ የበዙና የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በሁለት የሚከፈሉም ናቸው። በሁለት የተከፈሉት ትምህርቶች ግልፅና ምስጢር ሲባሉ፣ ምስጢር የሚባሉትን አሜሪካዊያን ብቻ የሚሳተፏቸው ሲሆኑ፣ ግልፅ የተባሉት ለአሜሪካውያንና የውጭ ሃገር ሰዎች ተቀላቅለው የሚማሯቸው ናቸው።

በዚሁ መጠን ከሲቢሉም፣ ከወታደሩም፣ ከአሜሪካዊያኑና ከወጭ ሃገር ሰዎች የተማሪውም ብዛት ከፍ ያለ ነው። እኔ በተላኩበት የትምህርት ደረጃና እማርበት በነበረው ክፍል ከአሜሪካውያን ሌላ፣ ከአረቡም፣ ከእሲያ፣ ከማዕከላዊውና ከደቡብ አሜሪካ ወዘተ አገሮች የመጡ ነበሩ።

በሁለተኛው ተልዕኮዬ የቀሰምኳቸው ትምህርቶች በከፊል ከአገራችን የዕድገት ደረጃ አንፃር አገሬን የምጠቅምባቸው ባይሆኑም ለራሴ ከፍ ያለ እውቀት የሰጡኝና የአመለካከቴን አድማስ በጣም ያሰፉ ነበሩ።

ሰሜን አሜሪካ በሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገት ከምታደርገው እጅግ የተፋጠነ እርምጃ ምክንያት ከሰባት ዓመት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ስመለስ እኔ በትምህርት ሂደቱ በቅርብ ሳስተውለው፣ ልነካውና ልማረው በቻልኩበት ረገድ ብቻ እንኳን ታላቅ ለውጥ ተመልክቻለሁ።

በመጀመሪያው በአሜሪካ ቆይታዬ እማርበት በነበረው ክፍል ማናቸውንም ነገር ለማሥላት የምንጠቀምበት መሣሪያ ተንሸራታች ማሥመሪያ ወይንም ስላይድ ሩለር እንጂ

የአሁኑ የኪስ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ እንኳን ያልነበረ ሲሆን ከሰባት ዓመት በኋላ በኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ መገልገል ተጀምሮ ነበር።

እርግጥ የኮምፒዩተር ቴክኖአሎጂ ገና መጀመሩ ስለነበር እንደዛሬው በዓለም የተራባ፣ ማንም የሚያውቀውና የተራቀቀ ሳይሆን በጣም ግዙፍና ግርድፍ ነበር። ቴሌቪዥን ሙሉ በሙሉ ጥቁርና ነጭ የነበረው ወደ ቀለም ተለውጧል።

ሶቭየት ኅብረት ቀድማ ሳተላይትና የጠፈር መንኮራኩር ወደ ህዋ በመላኳ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደኋላ ቀርተናል የተሰኘው አመለካከት የምሁራን ብቻ ሳይሆን የሕዝብም የመወያያ አጀንዳ እንደነበረ ሳስታውስ ከሰባት ዓመት በኋላ አሜሪካም የዚህ ቴክኖሎጂ ባለቤት ሆናለች። ለኔ ጎላ ጎላ ብለው የታዩኝን ብቻ ገለፅኩ እንጂ ብዙ ማለት ይቻላል።

አሜሪካን ከሰባት ዓመት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ለማየት ያጋጠመኝ ዕድል አሜሪካዊያን ምንም ዓይነት መሻሻል ሳያደርጉ እዚያው በነበሩበት ቦታ ያገኘኋቸው፣ ወይንም ከአውሮፓ አህጉር ብቻ ሳይሆን ከዓለም ወደ ኋላ የቀሩት ስለሰው ስብዕናና እኩልነት ባላቸው አመለካከትና በማህበራዊ ንቃተ ህሊናቸው ነው።

በፖለቲካ ረገድ የአሜሪካ ሕዝብ ካተኮረባቸው አቢይ ጉዳዮች ቅድሚያውን ይዞ የነበረውና በቬትናም ጦርነት በጣም የተራቀቁ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የታጠቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ሠራዊት ጦርነቱን በአጭሩ ቀጭቶ በድል አድራጊነት ይመለሳል ተብሎ ሲታሰብ በተቃራኒው ድል እየሆነና እያለቀ ስለነበረ ሕዝቡ የተከፋበትና መንግሥቱን ወደመቃወም ያመራበት ጊዜ ነበር።

በቬትናም ጦርነት ውስጥ ጣልቃ ገብተን ልጆቻችንን የምናስፈጀው ያለአግባብ ነው መውጣት አለብን በሚሉና፣ ጦርነቱን በመደበኛ ውጊያ የምናሸንፍ ስላልሆነ ኒውክሌር መጠቀም አለብን በሚሉ ወገኖች ሕዝቡ ተከፋፍሎ ነበር።

መንግሥት በበኩሉ ሁሉቱንም አዝማሚያዎች ለማለዘብና በቬትናም የሚዋጋበትን ምክንያት በማስረዳት ሕዝቡን በማግባባት የጦርነቱ ደጋፊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበረ።

በዚህ ጊዜ በጄነራል ደጎል የምትመራዋ ፈረንሳይ የአሜሪካን ሠራዊት ከአገሯ በማስወጣት ከሶቭየት ሕብረት ጋር በመግባባት ለዘብተኛ አቋም በመያዟ ፈረንሳይ ከሐዲ ነች የሚል ወቀሳና ጥላቻ በአሜሪካ ሕዝብ ውስጥ ሥር ሰዶ ነበር።

በአፍሪካ አሜሪካዊያንና በመጠኑም ቢሆን በአይሁዶች ላይ የሚደረገው የዘር መድሎ ተቃሎ ጥቁሮች ቢያንስ የመምረጥና የመመረጥ መብት በሕግ ቢያገኙም ተግባራዊነቱ አጠያያቂና አስቸጋሪም ስለነበረ ትግሉም አላባራም።

የአፍሪካ አሜሪካዊያንን የእርነትና ብሎም የመብት ትግል መጠነኛ ውጤት እንዲያገኝ ያደረገው የዓለም ሠራተኞና ኮሚዩኒስቶች ንቅናቄ መጎልበት በአፍሪካና በካረቢያ በቅኝ ተገዢነት ቀንበር ውስጥ ተጠምደው የነበሩ ብዙ አገሮች ነፃነታቸውን አግኝተው የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አባላትን ቁጥር እየመዘኑ መምጣት፤ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ መጠናከርና አሜሪካ የተዘፈቀችበት የቬትናም ጦርነት ባስከተለባት የውጭ ተፅዕኖ በዓለም እየተወገዘች እየቀለለችና እየተገለለች በመሔዷ ነበር።

የአሜሪካ ኢምፖሪያሊዝም የነፃው ዓለም መሪ የሠላምና የዲሞክራሲ ጠበቃ ነኝ እያለ ቢገበዝም፣ በዘር መድሎና በሰባዊ መብት ረገጣ ብቻ ሳይሆን ጥቁሮችን በእብሪትና

በግፍ በማሸበርና በመፍጀት የሚተካከለው የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ የነጮች መንግሥት ብቻ ነበር።

የዓለምን ሶሻሊስት ሥርዓት ማህበርና የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ያጥላላና ያራከሰ መስሎት ነፃው ዓለም እያለ የሚጠራቸው ምዕራባዊዎቹ የአውሮፓ መንግሥታት ቅኝ ግዛቶቻቸውን እየለቀቁ ከሞላ ጎደል ለዓለም አቀፋዊ ሕግ በመገዛት የሰውን ልጅ እኩልነት፣ የህሊና ነፃነትና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነትን ተቀብለው በውስጣቸው ያሉ ወግ አጥባቂ፣ ለዘብተኞች ዲሞክራቶች፣ ሶሻል ዲሞክራት፣ ሶሻሊስቶችና ኮሚኒስት ፓርቲዎች ህልውናቸው በሕግ ታውቆና ተጠብቀው፣ ተቻችለው በተከታዮቻቸው የሕብረተሰብ ክፍል ፈቃድና ድጋፍ፤ በነፃነትና በሠላም ለፓለቲካ ሥልጣን ሲወዳደሩና በአንድ ጣራ ሥር ተቀምጠው ለአገራቸው በኃራ ሲመክሩ፣ ሰሜን አሜሪካን ፖለቲካና ኢኮኖሚ በመቆጣጠር ሕዝቡን በዲሞክራሲ ጎዳና እንመራዋለን ማለት ብቻ ሳይሆን የምዕራቡ ዲሞክራሲ ጠባቂና ጠበቃ ነን የሚሉት ቡርዥዋ ገዢ መደቦች ይህንን ለማድረግ ቀርቶ በሰውልጅ እኩልነትም አያምኑም።

በሰው ልጆች መካከል ሊኖር የሚገባውን የሀሳብና የአመለካከት ልዩነትም አይቀበሉም። አገሪቱ ህልውናዋን ካገኘችበትና መንግሥት ከመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በመድበለ ፓርቲ ስም ለፖለቲካ ሥልጣን ይወዳደራሉ የሚባሉት፤ የማይጨመሩና የማይቀነሱ የማይለወጡና የማይሻሻሉ ሁለቱ ሪፓብሊክና ዲሞክራት የሚባሉ ፓርቲዎች ሁለቱም አንድ የቡርዥዋ ገዢ መደብ፤ አንድ ዓይነት ርዕዮትን የካፒታሊስት ሥርዓት የሚያራምዱ፤ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው ለማለት ይቻላል።

የሶሻሊዝምና የኮሚኒዝምን ንድፈ ሃሳብ ወይንም የሰውን ልጅ ማህበራዊ የዕድገት እቅጣጫ አራማጆችን ስብአዊ ፍጡር ያልሆኑ ፍጥረት፣ ጭራቅ የሚባል ነገር ካለ ጭራቅ አድርገው በማሳየት በፕሮፓጋንዳ መሣሪያቸው የሚመሩትን ሕዝብ ዓይንና ህሊና በድንቁርና ሰም መርገውታል።

ሕዝባቸውን ኮሚኒዝም ይበላሃል እያሉ ከማስፈራራትና ከማደንቆር ባሻገር፣ ሕብረተሰብአዊ ወይንም ማህበራዊ የሆነው ሥርዓት በዓለም ላይ እንዳይስፋፋ መከላከልም የአሜሪካ ሕዝብ የተፈጥሮ ግዴታ ነው በማለት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ኮሪያዊያን ከጃፓን ወታደራዊነት ጋር ለነፃነት በሚያደርጉት የትጥቅ ትግል ውስጥ ጣልቃ ገብተው ያፈሰሱት የአራት ሚሊዮን ኮሪያዊያን ደም ያነሰ ይመስል በድጋሚ እንደዋዛ ወደ ቬትናም ጥቂት ወታደራዊ አማካሪዎችን ልከው በጀመሩት ጣልቃ ገብነት ሂደት በሚሊዮን የሚቆጠር ሠራዊታቸውን ማግደው ባስከፈላቸው መስዋዕትነት ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች ባሎቻቸውን ያጡ ሴቶችና አባቶቻቸውን ያጡ ልጆች ጦርነቱን በፅኑ ያወግዙ ነበር።

በወታደራዊ ግልጋሎት ግዴታ ደንብ ለውጊያ የሚመለመሉ ወጣት አሜሪካዊያን የጦርነቱ ሠለባ ላለመሆን፣ ወደ ማዕከላዊና ደቡብ አሜሪካን ወደ አውሮፓ ወዘተ አገራቸውን እየጣሉ ይኮበልሉ ነበር።

በጦርነቱ ተማርከው የታሠሩ የጦር ኃይሎች አያሌ አባላት የተከማቹበትን አንድ የሰሜን ቬትናም የጦር እሥር ቤት የልዩ ተግባር ጦር ድንገተኛ ወረራ አድርጎ እስረኞቹን በማውጣት ለአውሮፓ የገና በዓል ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመቀላቀል አስደስቶ የሕዝቡን ድጋፍ በማግኘት በፕሬዝዳንት ሊንደን ጆንሰን አስተዳደር የተደረገው እጅግ ጀብደኛ የሆነ ሙከራ ከሽፎ አስፈቺዎቹ የአሜሪካ ስፔሻል ፎርሶች ተይዘው በመታሠራቸው የአሜሪካ

ምክር ቤት አባላት ሳይቀሩ ከሕዝቡ ጋር ወግነው ፕሬዝዳንት ጆንሰን ከሥልጣን ይውረዱ እስከማለት የደረሰ ሕዝባዊ ውዝግብ አስተውያለሁ።

እዚህ ላይ በጣም የሚያስገርመው ነገር አብዛኛው የአሜሪካ ሕዝብ የቬትናምን ጦርነት በፅኑ ሲቃወምና ሲያወግዝ አብዛኛው የቤተክርስትያን ካህናቶች ወይንም መንፈሳዊ አባቶች ነን ባዮች ጦርነቱ ለአገራችን ሥልጣኔና ደህንነት ሲባል በእግዚአብሔር ልጆችና በዲያቢሎስ ልጆች መካከል የሚደረግ ትግል ስለሆነ መደገፍ ያለበት ጦርነት ነው በማለት ነው ሕዝቡን የሚሰብኩት።

የአሜሪካ ሕዝብ በልማዳዊ አነጋገር ወታደሩን ጂ.አይ እያለ ነው የሚጠራው። በመንግሥት ድጋፍና ስጦታ የሚኖር ለማለት ሲሆን ስለጦርነቱ ቅዱስነትና ትክክለኛነት ሕዝቡን የሚያስተምሩት ቄሳውስት፣ ጂ.አይ ማለት የእግዚአብሔር አምሳል ማለት ነው እስከ ማለት መድረሳቸው ነው።

በኢኮኖሚው ረገድ አሜሪካኖች በታሪካቸው ከአሥራ ዘጠንኛው መቶ ሐያኛው እስከ አርባኛው ድረስ በሃያ ዓመታት ውስጥ ያደረጉትን የዕድገት እመርታ ከማናቸውም ጊዜ ወደር የለውም እያሉ በኩራት ያስታውሱታል። ይህም እውነት ነው።

የቬትናም ጦርነት በፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ የሸቀጣ ሸቀጥ ዋጋ መናር፣ በተለይም የምግብ ዋጋ ማሻቀብና የሥራ ገበታው መጥበብ ወይንም የሥራ አጡ ቁጥር በጣም መጨመሩን ሕዝቡ በስፋት ሲወያይበት፣ ሠራተኛው በየጊዜው በሚያደርገው የሥራ ማቆም አድማ ኢኮኖሚውንም እንደጦሩ ግምባር እያሽመደመደው ነበር።

የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ነጻው ዓለም የሚለውን ምዕራብ አውሮፓንና ምዕራብ ዘመም የሆነውን ታዳጊውን ዓለም በፀረ-ሶቬትና በፀረ-ኮምኒዝም ግምባር ለማሠለፍ ይቻለው ዘንድ ላያሌ አገሮች ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ወዘተ ድጋፍ በተጨማሪ አገሪቱ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝት፣ ለአገር ግምባታና በቁሳዊ ሃብት ልማት የደረሰችበት ማራኪ የዕድገት ደረጃ በማስጎብኘትና በማሳየት የግለሰቦችንም ስሜት ለመግዛት ጥረት ስለሚያደርጉ ከትምህርት ፕሮግራማችን ጋር ታክሎ ቢያንስ በየወሩና ከዚያም ባነሰ ጊዜ ውስጥ አሜሪካንንና አሜሪካዊያንን የማሳወቅ ፕሮግራም አላቸው።

በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት በአሜሪካ ቆይታዬ በትምህርቱ ጣልቃ የተለያዩ ክፍለ ሃገራትን፣ አስደናቂ ነገሮችንና የታሪክ መዘክሮችን ኢንዱስትሪዎችንና የተለያዩ የልማት ሥፍራዎችን፤ ዩንቨርስቲዎችን፤ የጥናትና የምርምር ተቋሞችን፤ የተለያዩ የጦር ሠፈሮችንና የጦር ኃይሉን ተቋሞች፣ በአጠቃላይ የአገሪቱን ገጠርና ከተሞች የመጎብኘት እድል አግኝቻለሁ። የአገሪቱን ተፈጥሮ፤ እድገት፤ የሕዝቡን አኗኗር፤ ባህል ልማድና ወግ ጠለቅ ብዬ ለማየት ችያለሁ።

የጉብኝቱ ፕሮግራም በአመዛኙ የሚካሄደው በበጋውና በፀደይ ወራቶች ስለሆነ በአየኋቸው ክልሎች የተፈጥሮ ውበት፣ ልምላሜ፤ ሰው ሠራሽ ወይንም የሰው ፈጠራ በሆኑት ልማትና ግንባታዎች ተደንቄያለሁ።

ጥንት የአገሪቱ ነዋሪ በነበሩት ቀይ ሕንዶች መቃብር ላይ ከሁለት መቶ ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከአውሮፓ በተጋዘ የሠለጠነ የሰው ኃይል፤ ካፒታልና ቴክኖሎጂ፤ ከአፍሪካ በተጋዘ ነፃ የባሪያ ጉልበት የተደረገው ግንባታ፤ ተዓምር የሚባል ነገር ካለ ተዓምር ነው ቢባል ማጋነን አይመስለኝም።

አዲሲቱ ሰሜን አሜሪካ ከተገኘችበት እስከ ተገነባችበት ድረስ ያለውን ጊዜ ከአንድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ወቅት ጋር ስናመዛዝነው፣ ዘመነ መሣፍንት እየተባለ በሚጠራው ሥርዓተ አልበኞቹ የኢትዮጵያ ጉልተኛ መሣፍንቶች የገነቡትን በማፍረስ ከፈጀባቸው ጊዜ ብዙ የሚበልጥ አይደለም።

የአሜሪካ ታላቅነትና የዓለም መሪ ነኝ ያሰኛትም ትምክህተኝነት የዚሁ የግንባታው ውጤት መሆኑ አያጠያይቅም። አገሪቱ በጠቅላላ በዚያን ጊዜ የነጮች ዓለም ናት ብትባልም፤ በሰው ዘር ጥንቅር ግን በዓለም አቻ ያላት አይመስለኝም። ነጩ፣ ጥቁሩ፣ ቢጫውና ጠይሙ፣ እንዲሁም ቋንቋና ባህሉ ሲታይ የሰው ዘር ሙዝየም ነች ለማለት ይቻላል። አገሪቱ በሰውና በቁሳዊ ኃይል ግንባታ በዓለም ከፍተኛውን ሥፍራ ይዛ ሳለ እንደሌሎቹ ጥንታዊ አገሮች የኔ ነው የምትለው ታሪክና ባህል ግን የላትም።

የሕዝቡ ውጥንቅጥነት፣ የካፒታሊስት ሥርዓትና ምጣኔ ሃብታዊ ሥልተ ምርት በሚፈጥሩት ገደብ አልባ እራስ ወዳድነት፣ የነዋይ ሴሰኝነት፣ የሞራል ዝቅጠት፣ እረጋ ሠራሽ በሆነው ባህል ብሽቅጥነትና በሕዝብ ጋጠወጥነትም ቅድሚያውን ይዛለች።

አሜሪካ፣ አሜሪካዊ ያልሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ባዕዳንን ያስተማረችና እያስተማረችም ያለች ስትሆን እራሷ ግን የሁለት ዓይነት መሐይማን ሃገር ነች ለማለት ይቻላል።

የመጀመሪያዎቹ ማይማን ወይንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ስማቸውን ለመጻፍ የሚቸገሩ የቀለም ማይማን ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ የተማሩ ማይማን ናቸው።

ገዢው የቡርዧው መደብ የሌላውን ዓለም ሕዝቦች ኋላቀር፣ በብረት መጋረጃ የተጋረዱና አገራቸውንም የሕዝቦች እሥር ቤት ብሎ በመፈረጅ እንደሌሉ አድርጎ፣ ሰሜን አሜሪካን ብቸኛ ዓለምና የዓለም መሪ፤ ማህበራዊ ፍትህ፤ ዲሞክራሲና ብልፅግና የሠፈነበት ዓለም ናት ብሎ ሕዝቡን ስለሚነግረው፤ አብዛኛው ሕዝብም የተነገረውን እውነት ነው ብሎ አምኖ በመቀበል ሌላ ዓለም ያለ አይመስለውም።

በየመንደሩ ያሉት ቴሌቪዥኖች፣ ራዲዮኖች፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሌት ከቀን የውስጡንና የአካባቢውን ዜናዎችና የሸቀጥ ማስታወቂያዎች፣ የአሜሪካንን ታላቅነትና ብቸኛ ዓለምነት የሚያጋንንና ሌላውን የሚያራክስ ፕሮፖጋንዳ ስለሚግቱት ስለሌላው ዓለም የሚሰማ ጆሮና የሚያስተውል ህሊና እንዳይኖረው አድርገው አደንቁረውታል።

ለፈጣሪ ታዛዥና አገልጋይ በመሆናችን ሀቀኛና እግዚአብሔርን የምንፈራ ክርስቲያኖች ነን የሚሉትም መንፈሳዊ ተቋሞችና ግለሰቦችም የሥርዓቱ መሣሪያ በመሆን ሕዝቡን ለማደንቆር የሚጫወቱት ሚና ከመንግሥትም ፕሮፖጋንዳ የላቀ ነው።

ለማጠቃለል፣ ሰሜን አሜሪካ ታላቅ ሕዝብ ያላት ታላቅ ሃገር፤ ውብ ተፈጥሮና እያሌ አስደናቂ የፈጠራ ውጤቶች የበዙባትና ተፈጥሮም ያደላት፤ በዕውቀታቸው እጅግ የላቁና የተራቀቁ ሳይንቲስቶች መሐንዲሶች ወዘተ በአጠቃላይ የዕልፍ አእላፍ ምሁራን ሃገር መሆኗ፤

ከሰፊው ሕዝብም መካከል መልካም የሚያስከብር ሥነልቦናና ሥነምግባር ያላቸው ቅን፣ ደጎችና በጎአድራጊዎች ያሉበት ሃገር መሆኗ ባይካድም ከዚህ አንፃር ደግሞ የመረጃ ድህነት የሚያጠቃቸው፣ አመራሩና ፕሮፖጋንዳው ያሳሳታቸው የሁለት መሐይማን ሕብረተሰብና የብዙ ግብዞች ሃገር መሆኗን ቆይታዬ አስገንዝቦኛል።

እኔ በትዕዛዝ ለወታደራዊ ትምህርት ወደ ሰሜን አሜሪካ ስላክ ከጓደኛዬ ከሻምበል ተፈራ ተክለዓብ ጋር አብረን ባቀረብነው ጥያቄ መሠረት የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር የዩንቨርስቲውን ትምህርት ስለፈቀደልን፤ እሱ በካምፓላና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የሐረር ቅርንጫፍ ሲከታተል የነበረውን የሕዝብ አስተዳደር ሞያ ትቶ የሲቪል ምሕንድስና የድግሪ ኮርስ መከታተል መጀመሩን ጻፈልኝ።

እኔም የአሜሪካ መንግሥት የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር አሜሪካ የጦር መኮንኖች የተሠማሩበትን ወታደራዊ ሙያ ማጠናከሪያ በግል ጊዜያቸው በመንግሥት ገንዘብ በምሽት ፕሮግራም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ይሰጣቸው የነበረውንና ተዛማጅ በመባል የሚታወቀው የትምህርት እድል ለእኛም እንዲሰጠን በዚያው ጊዜ አብሮን የነበረውን ኢትዮጵያዊ መኮንን ሻምበል ተሰፋዬ ሕሩይን ጠይቀን ስለተፈቀደልን፣ እሱ የመካኒካል ምህንድስና እኔ የጀመርኩትን የኢኮኖሚ ኮርስ ቀጥዬ በካምፓላና ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሐረር ቅርንጫፍ በአገኘሁት የአንድ ዓመት ክሬዲት ሌላ በተጨማሪ የአንድ ዓመት ለማግኘት ቻልኩ።

ከአንድ ዓመት በኋላ በ1963 ዓ.ም መባቻ ላይ ወደ አገሬ ስመለስ፣ ጄነራል አበበ ገመዳ ከሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥነት የክብር ዘበኛው ክፍለ ጦር አዛዥና የንጉሡ ልዩ ኤታማዦር ሹም ሆነው ሲሾሙ በምትካቸው የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው የተሾሙት ሜ/ጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ ነበሩ።

የተላኩበትን የትምህርት ተልዕኮ ስጨርስ ለማንም የውጭ ሃገር ተማሪ መኮንን እንደሚያደርጉት አሜሪካንን እንድጎበኝ ትምህርት ቤቱ የአንድ ወር ፈቃድና አበል ሰጥቶኝ በአስቸኳይ ወደ አገሬ ተመለስኩ።

በአስቸኳይ የተመለስኩበት ምክያንት፣ በኢትዮጵያ ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ዩንቨርስቲው ከመከፈቱ በፊት ደርሼና የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልቼ ትምህርቴን ለመቀጠል ነበር።

በተሰጠኝ የፈቃድ ጊዜ ውስጥ ያደረግሁት ጥረት ተሳክቶና በኢኮኖሚ የሁለት ዓመት ደህና ክሬዲት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ አቅርቤ ተቀባይነት አገኘሁ።

በዚያን ጊዜ በሃገር መከላከያ የውጭ ሃገርና የሃገር ውስጥ ከፍተኛ የሲቪል ትምህርት ጉዳይ ዋና ዲሬክተር የነበረው አቶ ክፍሌ ወርቁ ጥረቴንና ውጤቴን በማድነቅና ፍፁም ተባባሪ በመሆን ለ1963 ዓ.ም ትምህርት ከተመዘገቡት ተማሪ መኮንኖች ሁሉ ቅድሚያውን በመስጠት የመጀመሪያ ሰው አድርጎ ከመዘገበኝ በኋላ የክፍለ ጦሬን አዛዥ የትብብር ወይንም የፈቃድ ደብዳቤ ይዤ በቶሎ እንድመለስ በማሳሰብ አሰናበተኝ።

አቶ ክፍሌ ወርቁ ይህንን ውለታ ስለዋለልኝ ሳይሆን በሃገር መከላከያ ውስጥ ካለው የረጅም ጊዜ የሥራ ልምድና ስለ ሃገር መከላከያ ተልዕኮና ተግባር ባለው ሰፊ ግንዛቤ፣ በአብዮቱ ማግሥት የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ አድርገነው ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ የሚለው ግን ሕዝብ አሸባሪ ድርጅት ገድሎታል።

ከአሜሪካ ይዤው የመጣሁት ፈቃድ ወደ መገባደዱ ገደማ ስለነበረ ሌላ የአንድ ወር ፈቃድና ዩኒቨርሲቲ የመማር ፈቃድ ለማግኘት ሐረር በመሄድ ከዚህ በፊት እኔ በመኮንንነት ማዕረግ የምቀድማቸው አያሌ መኮንኖች የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ዕድል ሲሰጣቸው እኔ በነበረኝ የሥራ ባሕሪና ውጥረት ለመማር ያለመቻሌን፣ ጄነራል አበበ ገመዳ ሰጥተውኝ የነበረውን ተስፋና መከላከያ ሚኒስቴር የፈቀደልኝ ከሁለት ዓመት በፊት ሆኖ ሳለ ልሳተፍ

ያልቻልኩት በትዕዛዝ ወታደራዊ ትምህርት በሰሜን አሜሪካ እንድከታተል በመደረጉ መሆኑን በመዘርዘር፤ ጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ እንዲፈቅዱልኝ በጽሑፍ አመለከትኳቸው።

ማመልከቻዬን ከተመለከቱ በኋላ ጽሕፈት ቤታቸው አስጠርተውኝ ስቀርብ፣ "ከሁሉ በፊት የአንተ አቻ የሆኑ ብቻ ሳይሆኑ የአንተ አንጋፋ የሆኑና የብዙ ዘመን አገልግሎት ያላቸው እያሌ መኮንኖች አንዴ እንኳን ወደ ውጭ ሃገር የመሔድ ዕድል ሳያገኙ አንተ ሁለት ጊዜ ሔደህ ከተመለስክ በኋላ ሥራ ገበታህ ላይ ከመገኘት ፋንታ ዩኒቨርሲቲ ካልገባሁ በማለት የምታስቸግረው ኢትዮጵያ የአንተ ብቻ አገልጋይ መስላ ነው የምትታይህ?" በማለት "አዲስ አበባ ያለፈቃድ ቦዝነህ ያጠፋኸውን ጊዜ የአንድ ወር ደሞዝ ቀጥቼ እድሮ ሥራህ ላይ ሳትመለስ ጅጅጋ አዲስ በተቋቋመው ሜካናይዝድ ብርጌድ ተዛውረህ እንድታስተምር ወስኛለሁ።" በማለት እኔ እንድናገር ምንም ዓይነት ዕድል ሳይሰጡኝ ከጽሕፈት ቤታቸው አስወጡኝ።

ከዚህ በፊት በስምና በመልክ እንጂ ጄነራል ኃይሌን በቅርብ አላውቃቸውም። በእላቸው ቁጣና ቅጣት ሳልበገር ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የምድር ጦር አዛዥ ለነበሩት ለጄነራል ድረሴ ዱባለ ትምህርቱ እንዲፈቀድልኝ ብቻ ሳይሆን ጄነራል ኃይሌ ከሚያዙበት ክፍለጦርም እንድዛወር አመለከትኩ።

በአዲስ አበባ የነበሩና የጄነራል ኃይሌን ማንነት የሚያውቁ መኮንኖች ሲያገኙኝ ኃይሌ ባይከዳኝ ታሪኩን በሙሉ መኮንኖች ሲቀብር የኖረ በጣም አደገኛና የተረገመ ፍጡር ነው።

አይቻልም፣ አይሆንም ከማለት በስተቀር በጎ ነገር ለመሥራት የተፈጠረ ፍጡር አይደለም ሰው ከነከሰ አይለቅም። ያጠፋሀልና ከእሱ ጋር ለመታገል ባትሞክር ይበጅሃል ብለው የመከሩኝ ብዙ ነበሩ።

ተበደልኩ ብየ ያመለከትኳቸው የምድር ጦር አዛዥ የነበሩት ጄነራል ድረሴ በገፅ ጠርተው ሳያነጋግሩኝ በማመልከቻዬ ላይ በጽሑፍ የሰጡት መልስ ታሥሮና በወታደር ፖሊስ ታጅቦ ለጄነራል ኃይሌ ባይከዳኝ እንዲላክ የሚል ነበር። ለብዙዎቹ ወጣት መኮንኖች ከዚህ የሰፋና የላቀ የትምህርት እድል ሲሰጣቸው እኔ የአንድ ዓመት ትምህርት ብቻ ብጠይቅ መከልከሌ በእጅጉ አሳዝኖኛል።

ሳልገደድ በራሴ ፈቃድ ወደ ሐረር ተመለስኩ። ጄነራል ኃይሌ መመለሴን ሲሰሙ ለሁለተኛ ጊዜ ጽሕፈት ቤታቸው አስጠርተው "ለሁለተኛ ጊዜ አዲስ አበባ ያለሥራ የቦዘንክበትን የወር ደሞዝክን በድጋሚ ቀጥቼሀለሁ። ዛሬውኑ ጅጅጋ 10ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈር ሔደህ ሪፖርት ባታደርግ ታሥረህ እንድትሔድ አደርጋለሁ" ስላሉኝ በትዕዛዙ መሠረት ወደታዘዝኩበት ሄድኩ።

በጅጅጋ የተሰጠኝ አዲሱ ሥራ ሹመት ሳይሆን ወትሮ ከነበረኝ ኃላፊነትም ሆነ ከችሎታዬ ዝቅ ያለና በቅጣት መልክ የተሰጠኝ ውሳኔ ነው። ዩኒቨርሲቲ እንድትማር አልፈቅድም ማለት ብቻ ሲቻል ልማር ባልኩ ብቻ ይህንን ማድረጋቸው ፍፁም አግባብ መስሎ አልታዬኝም።

በዚያው በ1963 ዓ.ም ውስጥ ጄነራል ኃይሌ በዕድገት የጦር ኃይሎች ም/ኤታማጆር ሹም ሆነው ወደ ጦር ኃይሎች ጽሕፈት ቤት ሲዛወሩ የተኳቸው ሜ/ጄነራል ነጋ ተገኝ ነበሩ።

ጄኔራል ነጋ በጦር ኃይሎች የትምህርትና የዘመቻ መኮንን ስለነበሩና ጄኔራል ኃይሌ በኔ ላይ የፈፀሙትን በደል ያውቁ ስለነበር የሦስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው እንደመጡ የወሰዱት አንድና የመጀመሪያ እርምጃ እኔን ከጅጅጋ መጥራት ነበር።

ከዚህ በኋላ ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ዋዜማና አጥቢያ በተለያዩ አጋጣሚዎች አዲስ አበባ ስመላለስ ከሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ ጋር ሆነን ጄኔራል አማንን ከመንብኘትና ከማነጋገር ሌላ ከሻለቃ አጥናፉ አባተ ጋር ሊያስተዋውቀኝ ሞክሮ ባይሳካም ሐረር ተቋቁሞ በነበረው ህቡዕ የሠራዊቱን አብዮታዊ ኮሚቴ ወክሎ አዲስ አበባና በአካባቢው ካሉት የተለያዩ የጦር ክፍሎች ጋር አገናኝ እንደሆን በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

እንበሳውን ሦስተኛ እግረኛ ክፍለጦሩን ወክሎ አገናኝ ከመሆን አልፎ በነ ሻለቃ አጥናፉና በነ ኮሎኔል ይገዙ ወዘተ አስተባባሪነት በአዲስ አበባና በአካባቢው ያሉትን የጦር ክፍሎች ብቻ ሳይሆን የፖሊስ ሠራዊቱንም ጨምሮ መላውን መለዮ ለባሽ በማስተባበር ሠራዊቱ ለሦስተኛ ጊዜ ከጦር ሠፈሩ ወጥቶ የአገሪቱን ቴሌቪዢንና ራዲዮ ማሠራጫ ማዕከል እንዲቆጣጠር በተወሰደው እርምጃ ከሻለቃ አጥናፉ ጋር የሻለቃ ተፈራ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በከፍተኛ ድፍረት የአገሪቱ መለዮ ለባሾች ወኪሎች በአራተኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ ሠፈር ይሰበሰቡ ዘንድ ጥሪ ያደረገው።

ያንን ወሳኝ ጥሪ እስከ አደረገበት ደቂቃ ድረስ በየቀኑ ብቻ ሳይሆን በየሰዓቱ በሁለታችን መካከል ያላቋረጠና የተመሠጠረ የስልክና የወታደራዊ ራዲዮ ግንኙነት ነበር።

በመላው የአገሪቱ መለዮ ለባሽ ክፍሎች በኮታ ተመጥኖ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ በኋላ ደርግ አዲስ አበባ ላይ እናቋቁም ዘንድ አዲስ አበባ መለዮ ለባሾች በሻለቃ ተፈራ ተክለአብ አማካኝነት የቴሌ ግራም ጥሪ በቀረበልን ጊዜ በምስራቅ መለዮ ለባሾች በኩል ተወካዮችን ለመምረጥ ያደረግነውን ሁሉ አንባቢ እንደሚያስታውሰው አስረድቻለሁ።

በደነገግነው የምርጫ ደንብ ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ከኔ ሌላ የተቀሩት ተመራጮች ለማግኘት ባለመቻላቸው ሠራዊቱን ከመወከል ጋር እኔንም ይረዱኛል የምላቸውን መኮንኖችና የበታች ሹማምንት መርጬ በመምራት ወደ አዲስ አበባ እንድሄድ በተወሰነ ጊዜ በሻለቃ ተፈራ እምነትና ፍላጎት እኔ ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሀናን ሳይሆን እሱን እንድመርጥ ይጠብቅ ኖሯል።

በእኔ በኩል ደግሞ፣ ከሁሉ በፊት እሱ አዲስ አበባ በተቋቋመው የመለዮ ለባሾች ኮሚቴ ውስጥ የአመራር ስፍራ ይዟል ብዬ ከማመን ባሻገር እሱ በሌለበት እሱን ሐረር ለማስመረጥ ይቻላል ብዬ ካለማሰቤም በላይ ስለማይቻልም ባለመሞከሬ እንደከዳሁት አድርጎ ገምቷል።

ስለሆነም፣ እኔ የምሥራቁን ክልል መለዮ ለባሾች ልዑካን መርቼ አዲስ አበባ በደረስኩ ማግሥት ከሻለቃ አጥናፉ ጋር ተመካክሮ በአውሮፕላን ወደ ሐረር በመሄድ የሦስተኛን ክፍለ ጦር ሠራዊት እንዳስረዳ ከአዲስ አበባ የመለዮ ለባሽ ኮሚቴ ታዝዤ ስለመጣሁ ጦር ይሰብሰብልኝ በማለት ጠይቆ ጦር ሲሰበሰብለት እናንተን ይወክላሉ ተብለው አዲስ አበባ የተላኩት ተወካዮች ምርጫ ወይንም አወካከል አጋዴን ያሉትን የጦር ክፍሎች ያካተተ ስለአይደል ትክክለኛ ምርጫ አልነበረም።

የሐረርና የአካባቢው መኮንኖች ለመንግሥቱ በሰጡት ትክክል ያልሆነ መብት ይረዳኛል ብሎ በእናንተ ስም የመረጠው ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሃና ለዚህ አብዮት ምንም ዓይነት

አስተዋፅኦ ያላደረገ፤ በችሎታውና በፖለቲካ ንቃቱ ለዚህ ተልዕኮ ብቃት የሌለው ሰው ነው።

ይህንን ክፍለ ጦር ወክዬ ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ሠራዊት ጋር አገናኝ ሆኜ ብዙ ከመድከሜም ሌላ በወጣት መኮንኖች እንዲመራ የሚል ሃሳብ ያመነጨሁት እኔ ስለሆንኩ፤

የጦር ኃይሎች የጀመሩትን አብዮት ለመምራት ይቻላቸው ዘንድ በአዲስ አበባ አስተባባሪውን ኮሚቴ ለማቋቋም ጥሪ ያቀረብኩት እኔ ስለሆንኩ ሻለቃ ገ/የስ ተመልሶ ክፍለ ጦሩን ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር መወከል ያለብኝ እኔ ነኝ" በማለት ጦሩን ይከፋፍልና ከፍ ያለ ቀውስ ይፈጥራል።

የክፍለ ጦሩ ም/አዛዥ የነበሩት ብ/ጄነራል ግርማ ፈለቀ ይህንን ብሶትህን እዚህ ይዘህ ከመምጣት ይልቅ እዚያው አዲስ አበባ ለሻለቃ መንግሥቱና ላከኝ ለምትለው ኮሚቴ አስረድተህ መፍትሔ ልታገኝ ሲገባህ እዚህ መጥተህ በዚህ ሁኔታ ጦሩን መከፋፈል አግባብ አይደለም ይሉታል።

እኔ ብሶቴን የማስረዳው ለመንግሥቱ ኃይለማርያም ሳይሆን ለወከልኩት ኦጋዴን ላለው ጦር ሔጄ አስረዳለሁ ሲል፤ እዚህ የፈጠርከው ቀውስ አንሶ ኦጋዴን ሔደህ እንድትበጠብጥ አንፈቅድም ይሉታል።

ጄነራሉ ይህንን ስለአሉት ሲበቀላቸው ፈልጎ ለጦሩ "ጄነራል ግርማ የእንዳልካቸው ምልምልና ደጋፊ ናቸው። እዚህ ተዛውረው ከመምጣታቸው በፊት እንዳልካቸው ያቋቋመው የብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽን አባል ሆነው አብዮቱን ለመቀልበስ ከሚጥሩ ሰዎች አንዱ ነበሩ" በማለት ወንጅሎ ጦሩ አሥሮ ወደ አዲስ አበባ እንዲልካቸው ሲያደርግ የጦሩም አዝማሚያ ሲለወጥ የተመለከቱ መኮንኖች ስልክ ደውለው ለአንድ ቀን መጥተህ ተፈራ የፈጠረውን ችግር ካላስወገድህ በሠራዊታችን መካከል የከፋ ነገር ይፈጠራል ብለን በብርቱ ሰግተናል ይሉኝና ደርግ ለአንድ ቀን እንዲፈቅድልኝ እጠይቃለሁ።

የደርጉ አባላት በሙሉ፤ አይቻልም። እዚህ ከሰጠንህ ኃላፊነት የሚልቅና የሚያሳስብ አንዳችም ነገር ሊኖር ስለማይችል ለአንድ ቀን ቀርቶ ለአንድ ሰዓትም መሔድክን አንስማማም ሲሉኝ፤ ሻለቃ ገ/የስ ወ/ሃና ሻለቃ ተፈራ ተክለዓብ አስተባባሪው ኮሚቴ ነው የላከኝ በማለት ሐረር ሔዶ ሠራዊቱን በመከፋፈል ታላቅ ቀውስ ስለፈጠረ የሻለቃ መንግሥቱ መሔድ የግድ አስፈላጊ ነው ይላል።

እዚህ ላይ ሻለቃ ተፈራ ሐረር ለምን ሔደ? የላከውስ ማነው? ሲባል ሻለቃ አጥናፉ አባተ ጦሩን እንዲያስተባብር የላክነው እኛ ነን ሲል ጉዳዩ ሌላ መልክ ይይዛል።

ሦስተኛው ክፍለ ጦር ተባብሮ ወኪሎቹን ከላካ በኋላ አስተባባሪ ተብሎ የተላከው ግለሰብ ሻለቃ መንግሥቱን በመቃወም የተደረገ ሴራ ነው በማለት ሻለቃ ተፈራ ታሥሮ ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ ይወሰንና ሻለቃ ተፈራ ካሳሠራቸው ጄነራል ጋር ታሥሮ አዲስ አበባ ይመጣል።

እኔ በድጋሚ ደውዬ የነገሩን መነሻና መድረሻ በመጠየቅ ስለሁኔታው ከተረዳሁ በኋላ የሻለቃ ተፈራ ብሶትና ሊያስፈፅም የፈለገው ነገር ስለገባኝ አዲስ አበባ እንደ ደረሰ ወደ እስር ቤት ከመሔዱ በፊት ራሱን እንዲከላከል ብቻ ሳይሆን ለአብዮቱ ያደረገውን አስተዋፅኦ ሐረር ለጦሩ እንዳደረገው ሁሉ ለደርጉ ጉባዔም እንዲያስረዳና ከእኛ ጋር እንዲቀላቀል አደርጋለሁ በማለት አስጠርቼ ስለተፈጠረው ሁኔታ ለደርጉ እንዲያስረዳ አደርጋለሁ።

በተሰጠው ዕድልና መልካም አጋጣሚ የእሱን ማንነት ለጉባዔው ከማስረዳት ፋንታ ደርጉ የማይቀበለውንና ለእሱም የማይበጀውን አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ስለዘባረቀ፤ እኝህ መኮንን በጥብቅ ታሥረው መመርመር ያለባቸው ሰው ናቸው ይባልና እንዲታሠር ይወሰናል።

ታሥሮ ምርመራ ችሎት እንዲገባ ቢወሰንም ከፊውዳሎችና ከፀረ-አብዮተኞች ጋር መታሠር ያለበት ሰው አይደለም በማለት ስድስት ኪሎ አልጋ ወራሽ ግቢ ባለው የአንድ እግረኛ ሻለቃ የጦር ሠፈር ውስጥ በቁም እሥር እንዲጠበቅና የሁለታችንም ጓደኞች በሆኑ መኮንኖች ከችኩልነቱና ከጀብደኝነቱ ይታረም ዘንድ እንዲመከር አደርጋለሁ።

በጦር ሠፈሩ ውስጥ በነበረው አንፃራዊ ነፃነት እየተዘዋወረ ፀረ-ደርግ ቅስቀሳ ሲያካሂድ ተያዘ ተብሎ ይከሰስና ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር እንዲቀላቀል ተደርጎ ለዓመታት ከታሠረ በኋላ ደርጉም በምሥራቅና በሰሜን አንፃራዊ የጦር ሜዳ ድል ተቀዳጅተን በተረጋጋንበት ጊዜ እሱም ነፃነቱን አግኝቶ ወደ ሠራዊቱ በመመለስና የነበረውን የሻለቃ ማዕረግ በመልበስ በምሕንድስና ሞያው በሃገር መከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ እንዲሠራ ተደረገ።

ከዚህ በኋላ እኔ ላየውና ላነግግረው ስፈልግ በእሱ በኩል የጥላቻ ይሁን ወይንም የማፈር እንደሆነ ባልገባኝ ምክንያት የተለያዩ ምክንያቶችና ዘዴዎች በመፍጠር እንዳንገናኝ የሚያደርግ መሆኑን በመገንዘቤ ላለማስቸገር ፍላጎቴን ገታሁ ።

ሻለቃ ተፈራ ተክልዓብ በአባቱ ከትግራይ ብሄረሰብ በእናቱ ከኦሮሞ ብሄረሰብ የሚወለድ ብሩህ ጭንቅላት ፅኑ የአገር ፍቅር ያለውና አገሩን ለመለወጥ ሲታገል የነበረ አብዮተኛ ነው። በተሳሳተ ግምት ተከፍቶ ከእኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከደርግም ጋር ግጭት ፈጥሮ እስከንለያይ ድረስ የእድሜ ልክ ጓደኛዬና የፖለቲካ እምነቴ ተጋሪ በስደት ላይ ሆኜ ማረፉን በመስማቴ በእጅጉ አዝኛለሁ።

# ምዕራፍ አስር

# ደርግና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ

ከግንቦት ስምንቱ መፈንቅለ መንግሥትና ዝምቧቤ ሀራሬ ላይ ከተደረገው ጋር የኔን ሕይወት ለማጥፋት ለአሥራ አንድ ጊዜ ከተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ በተረፈ ሕይወት በመኖሬ እንደኔ ለመዳን ባለመታደላቸውና አፈር ስለተጫናቸው ራሳቸውን ለመከላከል በማይችሉ ወንድሞቼ ላይ አስተያየት መስጠትን ያህል ሕሊናዬን የሚከብደው ነገር ባይኖርም በዚህ ትግላችን ባልኩት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ ውስጥ የምጠቃቅሳቸው ሰዎች፣ በአብዮታችን ዋዜማ፣ አጥቢያ፣ ማግሥትና እንዲሁም በመጀመሪያው የሽግግር ወቅት አብረውን የነበሩ በመሆናቸው የአብዮቱ ታሪክ አካል ናቸው።

ይህንን ታላቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ በተቻለኝ የተሟላ ታሪክ ለማድረግ ከመጣር ባሻገር ባለታሪኩ ሕዝብ እውነቱን ማወቅ መብቱ ነው ብዬ ስለማምን አንዳንዶቹን ማስታወስ ተገድጃለሁ።

ሻለቃ አጥናፉ አባተ በኋላ ሌ/ኮሎኔል ከዚህ በላይ እንደጠቀስኩት አንዳንዶቹ ከምላቸው ሰዎች ተራ ሳይሆን የአብዮቱ ፋና ወጊና ግምባር ቀደም መሪ ከሚባሉትም ግምባር ቀደም የነበረ ነው።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የጦር ኃይሎች አብዮታዊ ንቅናቄ ከምንለው በፊት በአብዮቱ ዋዜማና አጥቢያ በተለያዩ መከንኖች በተመሩት ሁለት የጦር ኃይሎች ንቅናቄዎች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ፣ የኮንን ዘማቾች የአበል ጥያቄ መሪና አስተባባሪ ነበር።

የኮንን ዘማቾች ኮሚቴ መሪና አስተባባሪ እንዲሆን ከጦሩ የቀረበለትን ጥያቄ ለመቀበል የፈቀደው በዘማችነቱ በሚያገኘው አበል ተጠቃሚ ለመሆን ብቻ ሳይሆን በእጅጉ የሚጠላውን የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት በዚህ አጋጣሚ ለመታገልና ለመጣል ይቻል ይሆናል በሚል እምነቱ እንደነበረ የነገረኝ በኔ ሊቀመንበርነት ደርግን ከአቋቋምን በኋላ እኔና እሱ፣ አንድ ሕዝብና አንድ ሃገር በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር ለአንድ የፖለቲካ ዓላማ ተባብረንና ተሳስበን መሥራት እንደአለብን ለመጀመሪያ ጊዜ በግል በተወያየንበት ጊዜ ነው።

የጦር ኃይሎች ሦስተኛው አብዮታዊ ንቅናቄ ብለን የምንጠራውን አብዮት የሚመራ ወሳኝ፣ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ በኋላ ደርግን የፈጠረው የአዲስ አበባ መኮንኖችና በጠቅላላው መለዮ ለባሾች ጥረት ስኬታማነት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ካደረጉት ግለሰቦች ሻለቃ አጥናፉ አሁንም ግምባር ቀደም ነበር።

ለሦስተኛው የጦር ኃይሎች አብዮታዊ ንቅናቄ መፈጠርና ፍሬያማነት፣ በፊውዳላዊው ገዢ መደብ ላይ ወሳኝ ተፅዕኖ ከማድረግ ባሻገር የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ በዚያ ድፍረትና

ልበ ሙሉነት ያለፍርሀት በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለውጥ ብሎ እንዲንቀሳቀስ ያደረጉት፤ በአገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት ሠፍረው የአገራቸውን ድንበር፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብር፣ ደህንነትና አንድነት ሲያስከብሩ የነበሩትና ከአዲስ አበባ ከተማ ብዙ ርቀው የሚገኙት ማለትም፣ በመጀመሪያ የደቡብ፣ ቀጥሎም የሰሜንና በኋላም የምሥራቁን ክልሎች መለዮ ለባሾችን የመሩት አብዮታዊያን ቢሆኑም፤ እንደ ሻለቃ አጥናፉና እንደ ሻለቃ ተፈራ የመሰሉ መኮንኖች በአዲስ አበባ ባይገኙ ኖሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በዚያ ሁኔታ መከሰት ወይንም ለመፈንዳት ይችል ነበር ለማለት እቸገራለሁ።

ደርግን ስናቋቁም በኔና በሻለቃ አጥናፉ መካከል ስለተፈጠረው ሁኔታ እንደገለጥኩት የመላው ኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ወኪሎች በአራተኛ እግረኛ ክፍለጦር ጠቅላይ ሠፈር ከመሰብሰባችን በፊት ተሰብስበው ለነበሩ የአዲስ አበባ የጦር ክፍሎችና ለፖሊስ ሠራዊት ወኪሎች አመራር በመስጠት ላይ በነበረበት ጊዜ በሰጠሁት አስተያየት ነው በኔ ላይ ጥላቻ ያደረበትና ግጭት የተጀመረው።

ሆኖም ደርግ አመራሩን እንድረከብ ሲያደርገኝ ካለ አጥናፉና ካለ አራተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ትብብር መሥራትና አብዮቱን መምራት እንደሚያዳግት ተገንዝቤ ስለነበር፤ እሱ ምክትል ሊቀመንበር ካልሆነ የተሰጠኝን ኃላፊነት እንደማልቀበል በማያዳግም ሁኔታ ገልጫለሁ።

ይህንን ያደረግሁበት ምክንያት ለደርጉና ብሎም ለአብዮቱ ደሕንነት ብቻ ሳይሆን የሻለቃ አጥናፉን አስተዋፅኦ እግምት ውስጥ በማስገባት ነበር።

ደርግን አዋቅረን፤ የሥራ መመሪያ አውጥተንና የሥራ ክፍፍል አድርገን ስለደርግ መቋቋም በብዙሃን ማሠራጫዎች ከአበሰርን በኋላ እኔ የወሰድኩት የመጀመሪያ እርምጃ፤ ለምክትሌ ለሻለቃ አጥናፉ ራሴን ማስተዋወቅ፣ የእሱ ዓላማና ፍላጎት ምን እንደሆነ መረዳትና አገራችንን ወዴትና እንዴት መምራት እንደ አለብን በመወያየት የእሱን ማንነት ማወቅ ነበር።

የእሱን እምነትና ፍላጎት ከመግለፅ ፋንታ "አንተ ነህ መሪያችን በቅድሚያ አንተ እንዴትና ወዴት ልትመራን እንደአቀድክ ንገረኝና የኔን ሃሳብ እገልጥልሀለሁ" ስላለኝ በበኩሌ እራሴን ሳልከልል ለአገሬ ለኢትዮጵያ የምመኘውን ዘርዝሬ አስረዳሁት።

የኔ ፍላጎትና ምኞት፣ ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ወይንም በሕዝባዊ ሥርዓት እንድትመራ መሆኑን ስገልጥለት፣ "እኔም ከዚህ የተለየ ሃሳብ የለኝም" ስላለኝ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለአንዲት ኢትዮጵያና ለአንድ የፖለቲካ ዓላማ ነው የምንታገለው ብዬ አምኛለሁ።

በዚህ መተማመን ታላቁን ትግል ቀጥለን እያለ፤ በመጀመሪያ ያውም ከምንወክለው የጦር ኃይል ያጋጠመን የመጀመሪያው ችግር የኮንጎ ዘማቾች ተወካይ ኮሚቴ ያለአንዳች ማስረጃ ወደ ስላሣ ሚልዮን የኢትዮጵያ ብር ይከፈለን በማለት በኃይል ገንዘብ ለመንጠቅ ያደረገው ሙከራ ነበር።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው፤ ልጅ እንዳልካቸው ደርግን ለማፍረስ መሣሪያ ያደረጉት የኮንጎን ዘማቾች የአበል ጥያቄ ጉዳይ ስለነበር "ግርማዊ ንጉሡ ነገሥትን አስፈቅጄ አበላችሁን ልከፍላችሁ ስል የከለከለኝ ደርግ ነው" በማለታቸውና የኮንጎ ዘማች ሠራዊት በሙሉ በኔ ላይ ሲዘምት፤ ሻለቃ አጥናፉ የኮሚቴው መሪና አስተባባሪ ሆኖ ምንም ስለአላደረገና ምንም ዓይነት ርዳታ ስለአላደረገልኝ፤ አጥናፉ እንደነገረኝ እውን ነኝ ያለውን ይሆን? የሚል ጥርጣሬ አሳድሮብኝ ነበር።

አጥናፉ፤ ኢትዮጵያ በማህበራዊ ሥርዓት መመራት አለባት ብዬ አምናለሁ ቢልም ስለማህበራዊ ኢኮኖሚና ንድፈ ሃሳብ በጽሑፍም ሆነ በአንደበቱ እምነቱንና እውቀቱን የገለጠበት ጊዜ ስለአልነበረ ሻለቃ አጥናፉ ማን ነው ብለው የሚጠይቁ የደርግ አባላት ቁጥር ትንሽ አልነበረም።

ዛሬ እርስቱን በማላስታውሰው ጉዳይ ላይ ስንወያይ "ካፒታሊዝም ሰው-በላ ሥርዓት ነው በማለት ስለካፒታሊስት ሥርዓት ምንነት የማይናቅ አስተያየት በመስጠቱ ፀረ-ካፒታሊስትነቱን ገለጠ በማለት የተደሰቱ የደርግ አባላት ጥቂት አልነበሩም።"



ሻለቃ አጥናፉ አባተ

የሻለቃ አጥናፉን ባሕሪና ጠቅላላ ማንነቱ በቅርብ እንደተመለከትኩትና ደርግን በገጠሙት ብዙ አጋጣሚዎችም እንዳየሁት ጀግና መኮንን ነው። ወንድነትን በሚፈትኑ አጋጣሚዎች ሁሉ ሲደናገጥና ሲርበተበት አላየሁትም።

አገሩን ከልብ የሚያፈቅር ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛ ብቻ ሳይሆን አገሩን ለመለወጥ የሚፈልግ አብዮተኛ ስለመሆኑም ከኔ ይልቅ ተግባሩ ይመሰክርለታል።

ተንኮለኛ፤ ውስብስብና በአጠቃላይ ክፉ ሰው አይደለም። በኔ አስተያየት ቀናና ደግ ብቻ ሳይሆን በጣም የዋህም ነው። ከመናገር ዝምታን ይመርጣል፤ ሲናገርም ትልቅ የንግግር እውቀትና ስጦታ ያለው ነው የሚባል አይደለም።

እንደሁኔታው በተለይም አፍላ የአብዮት ጊዜ በምንለው የመጀመሪያው አምስት ዓመታት ውስጥ በነበረው ፋታ የማይሰጥ ውጥረት ምክንያት የደርጉ ጉባዔ ማራቶን እየተባለ ይጠራ ነበር።

አዘውትረን ጧት በማለዳ፤ ማለትም ከንጋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ የተቀመጥን ቀኑን ውለን የምናድርበትም ጊዜ ነበር። ብዙ ጊዜ ምሳ አንዳንዴም እራት ታስበው የሚውሉበት ጊዜ ነበር።

የሞቀ ወይንም የጦፈ ውይይት፤ አንዳንዴም ሙግት ማለት ይቻላል በያዝንበት ጊዜ ሻለቃ አጥናፉ ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው ድንገት ይነሳና ከአጀንዳችን ወይንም ከምንወያይበት አርዕስት የራቀ ነገር ይናገርና ከቤቱ ተቃውሞ ሲደርስበት ይበሳጭና አኩርፎ ይመስለኛል ለብዙ ጊዜ ዝም ማለቱ ስለሚያሳስበኝ አጥናፉ ከእኛ ጋር ነህ? ብዬ ስጠይቀው ምን ማለትህ ነው ብሎ ቢቆጣም መሳተፉን ይቀጥላል።

የሚያደርጋቸው ንግግሮች ብዙ ጊዜ አጭርና ግልፅ ናቸው። ዲፕሎማሲያዊ አነጋገርና የፖለቲካ አሽሙር አያውቅም ከማለት ሊጠቀም አይፈልግም ማለት ይሻላል።

በዚያ ቀውጢና እጅግ ፈታኝ ወቅት ደርጉ በኔና በእሱ ላይ የጣለው ኃላፊነት ኑሮአችንን የስቃይ ኑሮ አድርጎት ስለነበርና ለማንበብ ቀርቶ ለእንቅልፍም ጊዜ ስለአልነበረን፣ አጥናፉ ያንብብ አያንብብ አላውቅም።

የሻለቃ አጥናፉ ዋናው ወይንም ትልቁ ችግር የሰው ወሬ መስማትና በሰው መመራት ነው። አዘውትሮ የሚያገኛቸው ሰዎች፣ ወዳጆቹና አማካሪዎቹ የኦርቶዶክስ ቀሳውስት ወይንም ካህናቶች፣ የአሮጌው ሥርዓት አራማጆች፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነበሩ የታወቁ ቀኝ መንገደኛ ምሁራን ብቻ በመሆናቸው ይህንን የሚያውቁ የደርግ አባላት ሁሉ ሥጋት ነበራቸው። ከእነኝህ ምሁራን ጥቂቱና በጣም መሠሪዎቹ ወያኔን የጠሩና ያመጡ ሲሆኑ እስከዛሬ ለሃገር ተቆርቋሪና ለሕዝብ አሳቢ መስለው ያወናብዳሉ።

እነ ዶክተር በረከት ኃብተሥላሴና ሌሎቹም መሰሎቹ ወዳጅና ተቆርቋሪ መስለው በሃገር ልጅነት በመቅረብ ጄነራል አማንን ክፋት በመምከር ለስልሳ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነው ባልጠበቅነውና ባላቀድነው ሁኔታ ላይ እንደጣሉን ሁሉ አጥናፉንም ከጎኔ ገንጥለው በመውሰድ የጥፋት መሣሪያ ያደርጉታል የሚል ታላቅ ፍርሃት ስለነበረኝ እኔና የተወሰኑ ጓዶች ከነበረን ሥራ በተጨማሪ አጥናፉን ስንጠብቅ ነው የኖርነው ብል ለማጋነን አይደለም።

ብዙ ንትርኮቼና አግባብቼ በቅርባችን በሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት አመራር ላይ ከነበሩ በሳል አብዮታዊ ምሁራን ጋር ላጎዳኘው ጥረት አድርጌ የተሳካልኝ ስለመሰለኝ ተደስቼ ነበር።

ውጤቱ እኔ የጠበቅሁት ሳይሆን ተቃራኒው ሆነና ኢሕአፓ ሕዝብን ማንቃትና ማደራጀትን በመሰል አብዮታዊ ተግባር ላይ የተሠለፉትን ሁሉ ባንዳ ምሁራን እያለ ከማጥላላት በላይ እኛ ሳናውቅ በደርግ ውስጥ አድፍጠው የነበሩ ወኪሎቹ በደርግም ውስጥ ፀረ-የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ቅስቀሳ ማድረግ ከጀመሩ ሰንብተው ነበር።

ኢሕአፓ ያልሆኑ ሌላ አጀንዳ የነበራቸው የደርጉ ቀኝ ክንፎች፣ እነ ሻለቃ ሲሣይ፣ እነ ሻለቃ ሀሩይ፣ እነ ሻለቃ አሥራት ወዘተ ፀረ-ድርጅት ጸሕፈት ቤት ስለነበሩ በዚህ መስመር አኳያ ከኢሕአፓ ጋር ግምባር በመፍጠር ሻለቃ አጥናፉንም እንደምንም ብለው ይመርዙታል።

ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ደርግ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት እስከተቋቋመበት ጊዜ ድረስ የኔ ፅኑ ደጋፊና ረዳት ሆኖ ሻለቃ አጥናፉን ገፍትሮ የምክትል ሊቀመንበርነቱን ሥልጣን ለመውሰድ ያላደረገው ጥረት ባይኖርም ምኞቱ በኔም በጓዶቼም አልተደገፈም።

ሻለቃ አጥናፉ አንዳች ስህተት ሠራ ተብሎ በደርግ በሚወቀስበት ጊዜ፣ ጉዳዩን በማጋነንና በማቀጣጠል ተጨማሪም ጥፋትና ወንጀል ፈልጎ ከሥልጣን ለማውረድ ያደረጋቸውን ሙከራዎች እኔ ብቻ ሳልሆን አንዳንድ የደርግ አባላት ተገንዝበው ታዝበውታል።

ሻለቃ ሲሣይ አጋጣሚ ጠብቆ በደርጉ ጉባዔ ላይ አጥናፉን በማሳጣት ለማጥቃት ካደረጋቸው አያሌ ሙከራዎች ሁለቱን ብቻ ብገልፅ ይበቃል ብዬ አስባለሁ።

አንደኛውና የመጀመሪያው፣ የአዲስ አበባ ነጋዴዎች በሕዝቡ ላይ ሲያካሄዱት የነበረውን ገደብ አልባ ብዝበዛ በጥቂቱም ቢሆን ለመግታት ብለን ለሥራው አግባብ ያላቸውን



ከሻለቃ አጥናፉ እና ከሻለቃ ደበላ ጋር

የተለያዩ ባለሙያዎች ያሰባሰበ አንድ የገበያ ዋጋ ተማኝ ኮሚቴ አቋቁመን ጓድ ሻለቃ አጥናፉ በሃገር ውስጥ ንግድ መሥሪያ ቤት በአጠቃላይ፤ ላቋቋምነው ዋጋ ተማኝ ኮሚቴ በተለይ አመራር በመስጠት የሥራውንም መሳካት በቅርብ እንዲከታተል እናደርጋለን።

ኮሚቴው የዋጋ ትመናውን ሥራ በሚሠራበት ጊዜ አንድ የደርግ ተወካይ መካከላችን ቢገኝ የማያዳግም ሥራ ለመሥራት ስለሚያስችል አንድ የደርግ አባል ይመደብልን ብለው የኮሚቴው አባላት ሻለቃ አጥናፉን ስለጠየቁት አንድ የባሻነት ማዕረግ ያለው የበታች ሹም የደርግ አባል ይላክላቸዋል።

ባሻው ከኮሚቴው ጋር ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ አጥናፉ በዚህ ዝርዝር ሥሩ ወይም ተመሩ ብሎ ይስጠው ወይንም ራሱ ያዘጋጀው ለማወቅ አልተቻለም፣ አንድ የዋጋ ዝርዝር የተጻፈበት ሠንጠረዥ ይዞ ባለሙያዎቹ በጥናት የደረሱበትን ዋጋ በመቃወም ደርግ የወሰነው ይህንን ነው ሲላቸው በፍርሀት ደርግ ከወሰነ እያሉ ይመስለኛል ባሻው የሚለውን እየተቀበሉ የተመዘገበውና በኋላም ሕዝብ እንዲያውቀው ተብሎ በብዙሀን ማሠራጫ የወጣው ዝርዝር የሕዝብ መሣለቂያ ይሆናል።

ከእያሌ የእህልና የጥራጥሬ ወዘተ ዋጋዎች አንዳንድ ቧልተኞች የእንቁላል ዋጋ አምስት ሳንቲም ብቻ መሆን የሕዝብ መወያያ አድርገው የደርግ እንቁላል እየተባለ ይቀለድ ነበር።

ይህ እንዴትና በማንስ አማካኝነት ደርግ የወሰነው ዋጋ እንደተባለ ጉዳዩ በአጀንዳ ተይዞ ለደርግ ጉባዔ በውይይት በቀረበበት ጊዜ ሻለቃ ሲሣይ ከማንም ቀድሞ በመነሳት "የደርጉ ም/ሊቀመንበር ለሆነ ሰው ይህ ጉባዔ የሰጠው ሥራና ኃላፊነት በዚህ ሁኔታ ተሠርቶና ተመርቶ የሕዝብ መሳቂያና መሳለቂያ ሲያደርገን ይህ ጉባዔ ለሌተናል ኮሎኔል አጥናፉ የሚሰጠው ፍርድ ምንድን ነው? ይህንን ለማከናወን ያልቻለ ግለሰብ እንዴት እዚህ ሥልጣን ላይ ሊቆይ ይችላል?" ወዘተ በማለት ከፍ ዝቅ አድርጎ ማዋረድ ብቻ ሳይሆን ከሥልጣኑም እንዲወርድ ጠየቀ ማለት ይቻላል።

በጉዳዩ ላይ ተወያይተን የደረስንበት፤ የአጥናፉ ጥፋት ቢባል ባሻውን መላኩ ካልሆነ በቀር የተቀረውን ስህተት የፈፀመው ባሻው ራሱ ስለነበር አጥናፉ ከጥፋቱ ነፃ ሆነ። ባሻውም ካለ ዕውቀት ሕዝቡን የጠቀመ መስሎት ከመሰል ጓዶቹ ጋር መክሮ ያደረገው ስለሆነ እንዲህ ያለ ስህተት እንዳይሠራ ከተሰጠው ግሳጼና ማስጠንቀቂያ በስተቀር የደረሰበት ነገር አልነበረም።

ሁለተኛውና ከመጀመሪያው የከፋ አደገኛ ውንጀላ የሰነዘረው፣ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አዲስ አበባ ያለውን የጥይት ፋብሪካ መሥሪያ ቤት በጎበኘበት ጊዜ በተመለከተው ሁሉ በመደሰቱ ሠራተኛውን ሰብስቦ ካመሰገነ በኋላ የደሞዝ ጭማሪ ይደረግላችኋል ብሎ ይናገርና ሠራተኛውን ያስጨበጭባል።

ይህ ድርጊት በምሽቱ ዜና በራዲዮና በቴሌቪዥን "የደርጉ ም/ሊቀመንበር ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ለጥይት ፋብሪካ ሠራተኞች የደሞዝ እድገት ፈቀዱ" ተብሎ ሲነገር ዜናውን የሰማን ሁሉ ደንግጠናል።

እኔ ለማስታወቂያ፣ ለቅስቀሳና ለፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ ሊቀመንበር ለሌ/ኮሎኔል አሥራት እቤቱ ደውዬ ኮሎኔል አጥናፉ እንዲህ ብሎ አይናገርም በስህተት የተላለፈ ዜና ስለሚመስለኝ አሁኑኑ ማስተባበያ ስጥ ብዬ አዛለሁ።

ዜናውን ለቴሌቪዢንና ለራዲዮ ያስተላለፈው እሱው ራሱ ኖሮ፤ "ስህተት የለበትም አጥናፉ ያለውን ነው በዜና ማሠራጫ ፕሮግራም እንዲነገር ያደረግሁት" ሲለኝ ከመላክህ በፊት የጻፍከውን ነገር ለአጥናፉ አሳይተኸዋል ብዬ ስጠይቀው አለማድረጉን ስለነገረኝ አንተም የጥፋቱ ተሳታፊ ነህ ብዬ ስልኩን ዘጋሁ።

እንደሚጠበቀው ከማንም ቀድሞ ማለዳ ደርግ ግቢ በመገኘት "ትናንት የተባለውን ሰምታችኋል?" በማለት ላገኘው የደርግ አባል ወሬውን ሲያዛምት ቆይቶ ጉዳዩ ወዲያው በዚያው ጧት ለጉባዔው ቀርቦ ስንነጋገርበት፤ የአጥናፉን ስህተት በማጋነንና ጉባዔው አንድ ትልቅ እርምጃ በአጥናፉ ላይ እንዲወሰድ ለማድረግ ብዙ ሞከረ።

ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ ለተከሰሰበት ክስ መልስ ሲሰጥ "የጥይት ፋብሪካን ከጎበኘሁ በኋላ ሠራተኛውን በአንድ ቦታ አሰባስቤ በተመለከትኩት ሥራችሁ ሁሉ በጣም ተደስቻለሁ። ፋብሪካውን አሁን ካለበት ሁኔታ በጣም በላቀ የማስፋፋትና የማሳደግ እቅድ ስለአለን የእናንተም ደሞዝ ከድርጅቱ ጋር አብሮ እንዲያድግ የሚቻለንን እናደርጋለን አልኩ እንጂ በዜና ማሰራጫዎች እንደተነገረው የደሞዝ እድገት ፈቅጃለሁ አላልኩም" በማለቱ እሱ ታምኖ ስህተቱ ዜናውን በዚያ መልክ እንዲተላለፍ ያደረገው የሌ/ኮሎኔል አሥራት ሆነ።

ከዚህ አንፃር የሚገርመው ነገር፤ በፀረ-የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት አጥናፉን በመጠምዘዝና በማሳመን ከደርጉ ቀኝ ክንፍና ከኢሕአፓ ጋር ለማሠለፍ መቻሉ ነው።

በአንባቢ ዘንድ እንደሚታወሰው ልጅ እንዳልካቸው ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ከልጅ ሚካኤል እምሩ ጋር ለሽግግሩ ወሳኝ አስተዋፆ አላቸው ብለን ቅድሚያውን ከሰጠናቸው አብዮታዊ ተግባሮች አንዱ የአብዮቱ የመጀመሪያና የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ግብ ነው ለምንለው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምሥረታ ቅድመ ሁኔታዎች፣ የሕዝቡ መንቃት፣ ሕዝቡ በየፈርጁ ማለትም በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በመደብና በተለያዩ ብዙሃን ድርጅቶች መደራጀት ነበር።

ይህንን ለማድረግ ደግሞ የአብዮቱን ባህሪያት አቅጣጫውን የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ግቦቹን ለሕዝቡ የሚያሳይ መመሪያ ከመሆኑ ጋር የፖለቲካ ድርጅቶችን

የሚፈጥረውንና ብሎም ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን ለመመስረት የሚያስችለውን የፖለቲካ ፕሮግራም ማውጣት ነበር።

እነኝህን ቁልፍ ጉዳዮች ያቀፈውንና የኢትዮጵያ የእድገት አቅጣጫ ኅብረተሰባዊነት መሆኑን የሚያስረዳው የፖለቲካ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በቅድሚያ ቀደምት የሆኑትን ሁለት አብይ ጉዳዮችን ማለትም የፖለቲካ ፓርቲዎችን መፈጠር የገጠሩ የእርሻ መሬት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች በይዞታ የሚታደልበትንና ገበሬው በማህበር የሚደራጅበትን ነበር።

የመሬቱን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ገበሬው የሚላኩትን የአገሪቱን የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተማሪዎች፣ መምህራኑንና ወታደሩን በፈቃደኝነት ብቻ ሳይሆን በደስታ ለማንቀሳቀስ ሲባል ከመሬቱ አዋጅ በፊት የተናኘው የፖለቲካ ፕሮግራም በተጠበቀውና በተፈለገው አይነት ለማንቀሳቀስ አይነተኛ መሳሪያ ሲሆን የፖለቲካ ድርጅቶችን ግን በታሰበውና በተጠበቀው አይነት የመፍጠሩ ፍንጭም አልታየም።

ስለሆነም ከሕዝቡ የመደብና የብዙሃን ድርጅቶች ጋር የፖለቲካ ድርጅቶችንም ጊዜያዊ አስተዳደር ደርግ እራሱ ማደራጀት ይቻለው ዘንድ ለዚህ የሚያገለግሉ፣ ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን አብዮታዊ ምሁራን መልምለን የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤትንና የፖለቲካ ትምህርት ቤትን ማቋቋም እንደነበረብን ይታወሳል።

'አዋጅን በጆሮ' እንዲሉ ሻለቃ ሲሣይ "ለቃመንበር መንግሥቱ እኛን ንቆና ከድቶ ውይይቱና ሥራው፣ በጠቅላላው ውሎና አዳሩ ሁሉ ሕዝቡን ያነቃሉ፣ ያደራጃሉ ብሎ ካመጣቸው ምሁራን ጋር ብቻ ሆኗል። ከእኛ ጀርባ ከምሁራኑ ጋር በምስጢር አንድ ድርጅት እያደራጀ ነው" የተሰኘ ወሬ በደርጉ ውስጥ ያሰራጫል። ሌ/ኮሎኔል አጥናፉና ሌሎችም ጓዶች የሚባለው እውነት ነው ብለው በመቀበል ወይንም እኔን በመጠራጠር ከኢሕአፖ ወኪሎች ጋር ተባብረው በእኔ ላይ ሴራ ይጠነስሳሉ። ይህንን ክስና ብሎም ሴራ አስመልክቼ 'አዋጅን በጆሮ' ያልኩበትን ምክንያት ከዚህ እንደሚከተለው አስረዳለሁ።

መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ማለትም በኢትዮጵያ የፊውዳሉ ሥርዓት ቁንጮ የነበረውን ዘውድ ከገረሰስንበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1968 ዓ.ም መግባደጃ ድረስ በነበረው የጊዜ ክልል ውስጥ በተከታታይና ባላቋረጠ ሁኔታ ከአሮጌው የፊውዳል ሥርዓት ዋና ዋናዎቹንና አብዛኛዎቹን ላዕላይና ታዕታይ መዋቅሮች አፈራርሰን ስለነበረ በ1968 ዓ.ም የአብዮቱን በዓል ባከበርንበት ማግሥት የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተወያይቶ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጀንዳ ለውይይት አቀረብኩ።

እነሱም፣ አንደኛ በአዋጅ ወይም በሕግ ባፈረስናቸው የአሮጌው ሥርዓት መዋቅር መቃብር ላይ የአዲሱን የፖለትካ ሥርዓት አካላት ግንባታ በአስቸኳይ መጀመር የለብንም ወይ?

ፊውዳላዊውን የሀብት ምጣኔ ሥልተ ምርትና የግል ይዞታ ወደ ማህበራዊ ወይም ወደ ሕዝባዊ ይዞታ የመለወጡን ተግባር እንዲሁ በአስቸኳይ መጀመር የለብንም ወይ? የሚሉ ነበሩ።

ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጊዜ ወስዶ በሰፊውና በዝርዝር ከተወያየባቸው በኋላ የአቀረብኳቸው ጥያቄዎች ከምንመራበት ሥርዓተ ማህበርና ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ፕሮግራማችን አንፃር የቀረቡት ጥያቄዎች ትክክል ብቻ ሳይሆኑ የቀረቡት በወቅቱ ነው ሲሉ የኮሚቴው አባላት በሙሉ የድጋፍ ድምፃቸውን ሰጡ።

በሁለቱ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተወያይቶ ተገቢውን ውሳኔ በሙሉ ድምፅ ከሰጠ በኋላ በሦስተኛ ተራ አጀንዳ የአነሳሁት ጥያቄ፣ የአዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት አካላትና እንዲሁም የሥርዓቱን ላዕላይና ታህታይ መዋቅሮች የመገንባት ተግባር ለማፍረስ እንዳደረግነው በሕግ ወይም በአዋጅ ብቻ የምንወጣውና በቢሮክራሲው አማካኝነት በወኪል የምናስፈፅመው ሳይሆን አብዮቱ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር የደርጉን ድርጅታዊ መወቅር ከነአሰራር ዘይቤው በመለወጥ ወይም በማሻሻል የደርጉን አባላት ሕዝቡ መካከል ተገኝተው ከሕዝቡ ከመማር ባሻገር ሕዝቡን እያስተባበሩ ከዚህ በኋላ ያለውን ብርቱ ትግልና እንዲሁም መስዋዕትነት የሚጠይቅ ውስብስብ ወሳኝ አብዮታዊ ተግባር መምራት አለባቸው ብዬ ያቀረብኩትን ሀሳብ አሁንም ኮሚቴው በሙሉ ድምፅ አፀደቀው።

ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያፀደቃቸው ሦስቱ መሰረታዊ ጉዳዮች ለደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ ውይይትና ብሎም ለመጨረሻ ውሳኔ ቀርበው እንደተለመደው ሰፋ ያለ ጊዜ የወሰደ ሰፊና ዝርዝር ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በጉባዔው አባላት ሙሉ ድምፅ በመርህ ደረጃ ስለፀደቁ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑበትን የአፈፃፀም ስልት የማቀዱና ብሎም ተግባራዊ የማድረጉ ጉዳይ በእኔ አስተባባሪነት የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ድርሻ ስለሆነ በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢነቴ ሃላፊነቱን ወስጄ ከዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚያጠኑና ወደ ተግባርም የሚተረጉሙ አስፈፃሚ ተቋማት እንዲቋቋሙ አደርግሁ። እነሱም፡

1ኛ/ በቅድሚያ በየግንባሩ የሚካሄደውን ውጊያና በአጠቃላይም የትጥቅ ትግሉ አመራር ሙሉ በሙሉ በደርጉ ትከሻ ላይ ብቻ ወድቆ የነበረውን ሁኔታ በመለወጥ፣ የጦር ኃይሎች አዣዦች፣ የደርጉ የመከላከያ ኮሚቴ፣ የደርጉ የደህንነት ኮሚቴ አመራር አካላትና ለሥራው አግባብ ያላቸው ሚኒስትሮች የተካተቱበት ብሔራዊና አብዮታዊ የመከላከያ፣ የፀጥታና የደህንነት ምክር ቤት አቋቋምን።

2ኛ/ በብሔራዊ አብዮታዊ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፀጥታ ምክር ቤት መርሐዊ መመሪያና ስትራቴጂያዊ እቅድ የሚመሩና ሠራዊቱን በመስክ ለመምራት ድርጅታዊ ብቃትና ሥልጣን ያላቸው ክልላዊ የሠራዊት እዞች ለማቋቋም ከውጪ የምንጠብቀው የጦር መሣሪያ እንደቀረበልን ከመከላከያ ሠራዊቱ አደረጃጀት ጋር ተግባራዊ ሆኖ እንዲሰራበት በእቅድ ደረጃ ወሰንን።

3ኛ/ በአገራችን ላይ በደረሰው የአየር ንብረት ቀውስ ምክንያት ለተራበው፣ ጦርነቱ በአስከተለው ችግር ኑሯቸው ለተቃወሰና የመኖሪያ ክልላቸውን እየተው ለመሰደድ የተገደዱ የህብረተሰቡን ክፍሎች፣ በትግሉ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው የአብዮታዊ ሠራዊታችን አባሎች፣ ሰላማዊ ዜጎችና አሳዳጊ ላጡ ሕፃናት ቅድሚያ በመስጠት ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሄ ከመሻት ባሻገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ለአያሌ ምዕት-ዓመታት ከነበረበት ኋላቀርነት ከድህነት ከማውጣት ጀምሮ ምርትና የምርት ኃይሎችን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ማህበራዊ ይዘት ደረጃ በደረጃ የማስፋት ተልዕኮ ያለውና በልዩ ልዩ የልማትና የግንባታ ዘርፎች የተዋቀረ ብሔራዊና አብዮታዊ የእቅድና የምርት ዘመቻ መምሪያ አቋቋምን።

4ኛ/ አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት የመገንባት ግምባር ቀደም ተልዕኮ ያለው አብዮታዊ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲና ብሎም ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም ስለሚቻልበት ሁኔታ ስልትና ስትራቴጂ የሚነድፍ አንድ ከደርግና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተወጣጣ ኮሚቴ አቋቋምን።

ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸው ተቋማት አቋቋምን እያልኩ ለመግለፅ የፈለኩበት ምክንያት የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከአብዮቱ የእድገት ደረጃ አንፃር የደርጉም የተቋም መዋቅርና የአሰራር ባህሪ መሻሻል አለበት በማለት በሰጠው ውሳኔ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮች አንዱ ከሌላው ጋር በአለው ቁርኝት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በኋላ ቀጥሎ በሌላ አርእስት ስር ከምተርካቸው ጉዳዮች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ለአንባቢ ከወዲሁ ግንዛቤ እስጨብጬ ለማለፍ ያደረኩት መሆኑን በመግለፅ ወደ ተነሳሁበት የፓርቲና ብሎም የሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ ጉዳይ አመራለሁ።

አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓትና የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት የመገንባት ግምባር ቀደም ተልዕኮ ያለው አብዮታዊ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲና ብሎም ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም ስለሚቻልበት ሁኔታ ስልትና ስትራቴጂ የሚነድፍ አንድ ከደርግና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተውጣጣ ኮሚቴ አቋቋምን ያልኩት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

የኮሚቴው ሰብሳቢ እኔ፣ የኮሚቴ ጸሃፊ የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ የደርግ አባል፣ የማስታወቂያና የመርሐ ብሔር ሚኒስትር የሆኑት ልጅ ሚካኤል እምሩ አባል፣ የትምህርት ሚኒስትሩ ዶክተር ኃ/ገብርኤል ዳኘው አባል፣ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስትር ጓድ ዘገየ አስፋው አባል ነበርን።

ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ የሚጠራው ድርጅት አባል ሳይሆን "ኢሕአፓ" ባንዳ የሚላቸውን አብዮታዊ ምሁራንና የደርጉን ግራ ክንፍ በአንድ ላይ ለማስመታት መልካም አጋጣሚ የተገኘ መስሏቸው የጀመሩትን ፀረ-ሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ቅስቀሳ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ለሚመራው የደርጉ ቀኝ ክንፍም የሚያገለግል ሆኖ በመገኘቱ የጋራ ግምባር መፍጠር አስቻላቸው።

"እኛን ትቶና ከድቶ ውሎና አዳሩ፣ ሕዝብ እንዲያነቁና እንዲያደራጁ ብሎም ካመጣቸው ምሁራን ጋር ሆኗል" ተብየ የታማሁበት ጉዳይ፣ ለአብዮታችን ማዕከልና መሪ በመሆን መላውን የኢትዮጵያ አብዮታዊያን የሚያሳስብ የፖለቲካ ድርጅት ለመፍጠር በማደርገው ጥረት ምክንያት ነበር።

ለዚህ ተግባር የተቋቋመውና በኔ የሚመራው ኮሚቴ በሳምንት አንዴ እየተሰበሰብን እንወያይ ነበረ። ከተወሰኑ ስብሰባዎችና የሃሳብ ፍጭት በኋላ፣ አብዮታዊያንን በአካል በማሰባሰብ፣ በሃሳብ በማቀራረብ፣ ሕብረት ለመፍጠር የሚያስችልና ብሎም በደረጃ ወደ ውህደት በማምራት አንድ ወጥ አብዮታዊ ፓርቲ ለመፍጠር የሚያስችለን የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት የተባለ ተቋም ሕጋዊ ህልውና ሰጥተን ብናቋቁም ተገቢ ነው እሚል ውሳኔ ላይ ደረስን።

ተቋሙ በሕዝብ አደራጅነቱ ዋና ግቡ፣ ሕዝቡ የፓርቲ አመራር የሚቀዳጅበትን ሁኔታ መፍጠር ቢሆንም ተግባሮቹ በዝርዝር ሲዘረዘሩ ከዚህ እንደሚከተሉት ይሆኑ ዘንድ ተስማምተናል።

1ኛ/ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማንቃትና በማደራጀት ሕዝባዊ ሥልጣኑን ለመረከብ የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ከማመቻቸት ባሻገር በኢትዮጵያ አብዮታዊ የፖለቲካ ባህል ሥር እንዲሰድ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ።

2ኛ/ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማና እዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ክልሎች ለሕዝቡ የፖለቲካ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም ትምህርቱንና የትምህርት ቤቱን አስተዳደር መምራት።

3ኛ/ ሕዝቡ፣ አገሩን፣ አንድነቱን፣ አብዮቱንና የአብዮቱን ድሎች ነቅቶ እንዲጠብቅ ከማድረግ ባሻገር ለኢኮኖሚው ዘመቻ ማነሳሳት ወዘተ ነበሩ።

የኮሚቴው የመጨረሻ ተግባር፣ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ የሚቋቋመውን ዋናውን የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት የሚያቋቁሙና የሚመሩ ከክፍለ ሃገራት እስከ ወረዳዎች በሚቋቋም ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ የሚሠሩና በየፖለቲካ ትምህርት ቤቶች የሚሠሩ በሳል አብዮታዊ ምሁራንን ማፈላለግና ማሰባሰብ ነበር።

በዚህ ረገድ የኮሚቴው አባላት ብቻ ሳንሆን ሌሎችም ተባብረውን የበርካታ ግለሰቦችን ስም ስላገኘን፣ እኔና ልጅ ሚካኤል በመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ጸሐፊነት ለአንድ ወር ያህል ምሁራኑን በተራ እየጠራን ፈቃደኝነታቸውን ከማወቅ ሌላ ለችሎታቸው መመዘኛ የሚሆኑ መጠይቆችን በማቅረብና ሰፋ ባለ ሁኔታ በማነጋገር ስም ዝርዝራቸው ከዚህ ግርጌ የተመለከቱትንና ለዋናው ጽሕፈት ቤት አመራር የሚመጥኑትን ምሁራን መልምለን የተቀሩትን እነሱ እንዲመለምሉ ነው ያደረግነው።

ለዋናው የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት የተመለመሉ ምሁራን:

1ኛ/ ጓድ ዶክተር አለሙ አበበ
2ኛ/ ጓድ ዶክተር ሰናይ ልኬ
3ኛ/ ጓድ ኃይሌ ፊዳ
4ኛ/ ጓድ ዶክተር አሰፋ መድሐኔ
5ኛ/ ጓድ ዶክተር መለሰ ተክሌ
6ኛ/ ጓድ ዶክተር ነገደ ጎበዜ
7ኛ/ ጓድ ሸዋንዳኝ በለጠ
8ኛ/ ጓድ የወንደወሰን ኃይሉ
9ኛ/ ጓድ ዶክተር በዛብህ ማሩ
10ኛ/ ጓድ ፍቅሬ መርዕድ
11ኛ/ ጓድ ባሮ ቱምሳ ነበሩ

ስለ ፓርቲና ብሎም ሪፓብሊክ ምሥረታ ስልትና ስትራቴጂ የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ከመቋቋሙ በፊት ቀደም ብዬ ለደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ አስረድቼ የተስማማንበትና ሁሉም የተደሰተበት ብቻ ሳይሆን ሂደቱንም በየግዜው ለሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አስረዳ ነበር።

በሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት አማካኝነት እንዲፈጠር በሚፈለገው የአገሪቱ ተራማጆች ሕብረትና ብሎም ውህደት የደርግ አባላትንም ያካተተ ነበር።

ወደዚህ ስትራቴጂያዊ ግብ ለመቃረብ ሥልቱ ከሚፈጠሩት አብዮታዊ ድርጅቶች ጋር ግንባር ወይም ህብረት በመፍጠርና ብሎም በመዋሀድ ለደርግ አባሎች ዋስትና የሚሆን አብዮታዊ ሰደድ የተባለ ድርጅት በማቋቋም ሌ/ኮሎኔል አጥናፉንና ሌሎቹን ከሳሾቹን ጄኔራል ተፈሪ ባንቲን ጨምሮ የአብዮታዊ ሰደድ መሥራችና የአመራሩ አካል ስለአደረግኳቸው በደርግ ውስጥ ኢሕአፓ የፈጠረውን አንጃ አጥፍቼ ከዚያ በፊት የነበረውን የደርግን አንድነት ፈጠርኩ ብዬ አምኜ ነበር።

በእርግጥም በሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት የአገሪቱን አብዮታዊያን በማሰባሰብ አንድ አብዮታዊ ፓርቲ መፍጠርና በእሱም አመራር ወደተቀረው አብዮታዊ ግባችን ለማምራት የተደረገው ጥረት አብዛኛውን የደርግ አባላት እጅግ ያስደሰተና በኔላይ ያላቸውን እምነት ይበልጥ ያጠናከረ ሲሆን፣ በደርግ ውስጥ ለነበረው የኢሕአፓ ቡድንና ለነሻለቃ ሲሣይ ያላሰቡትና ያልጠበቁት መርዶ ሆነ።

በዚያን ጊዜ ባልተከሰተልኝና በኋላ በተገኘው አስተማማኝ መረጃ አማካኝነት እንደተረዳነው በሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት የአገሪቱን አብዮታዊያን በማሰባሰብ አብዮታዊ ፓርቲ ለመመሥረት የታቀደው ዕቅድ ተግባራዊ መሆን ከቻለ ሕብረተሰብአዊ ኢትዮጵያን እንገነባለን ማለታችን መፈክር ብቻ ሳይሆን በተግባርም እሙን ሊሆን የተቃረበ መሆኑን የተረዱ የአገሪቱ ቀኝ ክንፍ ምሁራን ተሰባስበው ይህንን ደርግ የሚያደርገውን የተፋጠነ እርምጃ በአስቸኳይ ማቆም ያስፈልጋል ይሉና ይህንንም ማድረግ የምትችሉት እናንተ ናችሁ በማለት ለኢሕአፓ ወኪሎችና ከእነሱ ጋር ፀረ-የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ግምባር ለፈጠረው አንጃ ምክራቸውን ይሰጣሉ።

በዚህ ምክር ውስጥ የኢትዮጵያን አብዮት በማዳፈን ረገድ የላቀ ፍላጎት የነበረው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የውጭ የስለላ ወኪል በአዲስ አበባ ያለበት ሲሆን፤ አንጃውንና አሜሪካኖችን የሚያገናኘው የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ያደረግነው ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ የሚባለው መኮንን ነው። ሻለቃ ኪሮስ የደርግ አባል አይደለም።

የደርግን እርምጃ በአስቸኳይ ማቆም የተባለውን ዕቅድ አሜሪካኖችና አንጃዎቹ ከተስማሙበት በኋላ እኔን የመግደሉን ተግባር የማከናወኑን ተልዕኮ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ ለሚጠራው ሽብርተኛና ነፍሰ ገዳይ ድርጅት ይሰጥና መስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ከታላቁ ቤተመንግሥት አራተኛ እግረኛ ክፍለጦር ግቢ ውስጥ ወደነበረው መኖሪያ ቤቴ ስሔድ ግድያው ተሞከረብኝ።

ግድያውን ለመፈፀም በታቀደበት ዕለት የጂቡቲ ሕዝብ ከፈረንሳይ ቅኝነት ነፃ የሚወጣበት ጊዜ ተቃርቦ ስለነበር 'ኢትዮጵያ ምን አቋም መያዝ አለባት' በተሰኘ ጉዳይ ላይ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጉዳዩ አግባብ ያላቸውን ባለሙያዎች ሰብስቤ ስወያይ ቆይቼ ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ከምሽቱ ስብሰባውን በመበተን ከስብሰባው አዳራሽ ስወጣ ግቢው በጣም ጭር ብሏል።

ለወትሮ ተጠባብቀን የምንሔደው ጄነራል ተፈሪና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ በጊዜ ጥለውኝ ወደየቤታቸው ሔደዋል። ጽሕፈት ቤት እንደገባሁ የደርጉ ጥበቃ ኃላፊና የዘመቻ መኮንኖችን ሌ/ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው መጥቶ አፋር ውስጥ ስለተፈጠረ የፀጥታ ችግር ሲያሥረዳኝ ለአኩል ሰዓት ያህል ቆይቼ ካሰናበትኩት በኋላ በምንዝበት ትልቅ ላንድሮቨር ውስጥ እንደተለመደው የታጠቁ ሁለት አጃቢዎቼ አብረውኝ ተቀምጠውና አንድ ሌላ ቶዮታ መኪና ላይ በተሳፈሩ አጃቢዎች እየታጀብኩ ወደ መኖሪያ ቤቴ አመራሁ።

የምንዝው በፊት በር ጎዳና አድርጌ ጋንዲ ሆስፒታል ስደርስ ወደ ግራ በመጠምዘዝ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ በማምራት ነበር። ሆስፒታሉን አልፌን ከስታዲየሙ ጎን ባለችው ትንሽ የእግር ኳስ ሜዳ ስንደርስ አንድ መትረየስ የተጠመደ ተሽከርካሪ እኔ በምንዝበት ላንድሮቨርና በሚያጅበኝ ቶዮታ መካከል ገብቶ ከኋላዬ ተኩስ ሲከፍት በዚያው ጊዜ ውስጥ ከመንገዱ ግራና ቀኝ አድፍጠው የሚጠብቁኝ ሰዎች ከመሬት ሌላ ተኩስ ከፈቱብን።

ከመሬት የሚተኮስብንን በፍጥነት አልፌን ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ስንደርስ ከመንገዱ ግራና ቀኝ አድፍጠው የሚጠብቁን ሌሎች ሰዎች የአውቶማቲክ ጠብመንጃ ተኩስ ከፈቱብን። ተኩሱ በጣም ቅርብ ነበር። እርቀቱም ከኛ ከሃያ ሜትር አይበልጥም። በጣም በመቅረቡ፤ ከጠብመንጃዎቹ አፈሙዝ የሚወጣው ብልጭታ አይኖቻችንን አወረው፤



በተኩስ የተበሳሳቸው ላንድሮቨር

ምንም ነገር አናይም። በዚህ ጊዜ ስጋቴ ተኩሱ ከሚያደርስብን ጉዳት ሌላ የኔ አሽከርካሪ ከሕንጻ ጋር ያላትመናል የሚል ነበር።

ይሔ ሁሉ ሲሆን መትረየስ እየተኮሰ የሚከተለን ተሽከርካሪ ተኩሱን ለአፍታም ያላቆመ ስለነበረ፤ እንዳልካቸው መኮንን ሕንጻ አጠገብ ስንደርስ እኔንና አጃቢዬን ወታደር ዮሐንስ አፈወርቅን በአንዳንድ ጥይት ከኋላ መቀመጫችን ላይ መታን።

አሁንም ከመሬት የሚተኮስብንን ተኩስ በፍጥነት አልፈን አራተኛ ክፍለ ጦር በራፍ ስንደርስ፤ ለሁለት ዓመታት ያህል በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ስኖር በየምሽቱ ከበሩ ውጭ በበራፉ ግራና ቀኝ መትረየስ የተጠመዱ ሁለት ጂፕ ተሽከርካሪዎችና በርከት ያሉና የታጠቁ ወታደሮችና ፓሊሶች እኔና አጥናፉ እስክንገባ ድረስ ይጠብቁን ነበር።

በዚህ ዕለትና ምሽት አጥናፉ ከኔ በፊት ብዙ ቀደም ብሎ ከገባ በኋላ ወታደር ፖሊሶች የሉም፤ መትረየስ የተጠመደባቸው ተሽከርካሪዎች የሉም፤ ወትሮ እበሩ ላይ የሚቆሙት ዘቦች በሩን ከውስጥ ዘግተው የት እንደሔዱ አይታወቅም።

በሩ ላይ ቆመን እንዲከፈትልን የተሽከርካሪ ጥሩንባ ስናጮኽ የሚከፍት አልነበረም። መትረየስ ጠምዶ እየተከታተለ የሚደበድበን ተሽከርካሪ በቆምንበት ቦታ ጥይቱን ሲያፈስብን የምንጓጓዝበትን ላንድሮቨር ኮፈን በተለይ ከኋላ ወንፊት አደረገው።

ያንን ሁሉ ጥይት ሲያፈስብን እኛን ሊፈጀን ያልቻለው፤ አንደኛ የላንድሮቨሩ ተጠባባቂ ጎማ ከኋላ ከበሩ ጋር ተያየዞ የተቀመጠ በመሆኑ ስለተከላከለልን፤ ሁለተኛ አሉሚኒየም የሆነ ወፍራም የመኪናው ገላና እንዲሁም የመኪናው የኋላ መቀመጫ ጥቅልል ሽቦዎችና ስፓንጆቹ ጥይቶቹን ውጠው እየቀነሱና እያበርዱልን ነው።



መትረፊን ለሕዝብ በቴሌቭዥን ባሳወቅንበት ጊዜ

ተስፋዬ እንዳለ የሚባለው ሌላው ያልተመታው አጃቢዬ እዚህ ቆመን ከምንደበደብ ወደ ንፋስ ስልክ እንቀጥል የሚል ሃሳብ አቀረበ። እሱ እንዳለው ወደ ንፋስ ስልክ መንዳት ብንቀጥል ከኋላ ለሚተኩስብን ተሽከርካሪ ጥሩ ኢላማ ከመሆን የሚያድነን ነገር ካለመኖሩ ሌላ ደሞስ የትና እስከየት ነው የምንነዳው ስለው በኔ አስተያየት የሚደበድብን የአራተኛ ክፍለጦር ወታደር ስለመሰለኝ በሩ ቢከፈትልንም ከውስጥ የሚጠብቀን ደህና ነገር አይመስለኝም አለኝ።

በእርግጥም የምናየው ሁኔታ ተስፋዬ ያለውን የሚያስኝ ሁኔታ ነበር። ሆኖም የሆነ ይሁን አልኩና ሾፌሩ በሩን በላንድሮቨሩ በርግዶ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጠሁትና በሩን በኃይል በርግዶ ሲገባ ከውስጥ በራፉ ላይ ቆሞ የነበረው ወይንም ሊከፍትልን የመጣ ይሁን አይታወቅም በሩ ሲበረገድ አንድ ወታደር ወደ ሰማይ ጉኖና ሦስት ሜትር ያህል ተወርውሮ ሲወድቅ አየነውና ዝም ብለነው አለፍን። ሌላ ሰው አላየንም።

ከዚህ ጊዜ በኋላ አራተኛ ክፍለ ጦርን ትቼ ታላቁ ቤተመንግሥት ግቢ የኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ገበዝ ይኖሩበት የነበረ የመንግሥት ቤት ውስጥ ገባሁ።

እኔ በጥይት የተደበደብኩበት የአራተኛ ክፍለ ጦር የበር ጥበቃ በዚያ ዕለት የተነሳበትንና በሩም የተዘጋበትን ጉዳይ የሚመረምር ኮሚቴ አቋቋምን ተብሎ በጀኔራል ተፈሪ ቢነገረኝም፤ የምርመራው ውጤት ለኔ ምስጢር ሆኖ ቀርቷል። እኔም ለመከታተልና ለማወቅ አልፈልግሁም እንጂ ለማወቅ በጭራሽ የሚያስቸግር ወይንም የሚገድ ጉዳይ አልነበረም። ይህንንም ያደረግሁት ለደርግ አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ስል ነው። የምርመራው ውጤት ይፋ ሆኖ የግድያው ዕቅድ አውጭዎችና ጠቅላላው እድምተኞች

ቢጋለጡና ደርጉን የሚያደፈርስና የሚያፋልስ ሁኔታ ቢፈጠር የአድሀሮትን ምኞትና ፍላጎት አስተናገድኩ ማለት ነበር።

የግድያ ሴራ ፈጣሪና መሪ አድርጌ ወይንም ዋና ተጠርጣሪ አድርጌ ያየሁት ጄነራል ተፈሪንና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉን ሆኖ ሳለ፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ በብሔራዊ ደሕንነት በኩል የተገኘው መረጃ እንዳስረዳኝ የግድያው ተዋናይ አክተሮች የሻዕቢያና የኢሕአፓ ሥልጡን ነፍሰ ገዳዮች መሆናቸው ተረጋግጧል። ሁሉም ባይሆኑ ከፊሉ የእጃቸውን አግኝተዋል።

የግድያው ሙከራ የአብዮታውያንን ትብብር የማጠናከርና ብሎም መሪ ድርጅት የመፍጠሩን አስቸኳይነት ያስገነዘበን በመሆኑ እርምጃችንን ከማፋጠን አልገታንም።

በዚህ ጊዜ ሶማሊያዎች አገራችንን ወርረው ለሰባት ወራት የያዙበትና በእኛም በኩል የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከታጠቀው የጦር መሣሪያ በዓይነትም በመጠንም የተሻለ ባይቻል የተመጣጠነ ለማግኘት የደርጉን የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር ጓድ ብርሃኑ ባይህንና የደርጉ የመከላከያ ኮሚቴ አባል ጓድ አዲስ ተድላን ይዤ ዓለምን እዞር ነበር።

በዚህ ጊዜ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉን መካሪዎቹ መንግሥቱን ለማስወገድ ያለህ መልካም አጋጣሚ አሁን ነው ያሉት ይመስላል ይከተሉኛል ብሎ የገመታቸውን ጥቂት የደርግ አባላትና ከደርግ ውጭም አንዳንድ የሠራዊቱን አባላት እየጠራ የአብዮታዊ ሰደድ አንጃ ለሆነ የክርስትያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሰው መመልመል ከመጀመሩ ሌላ “ሊቀመንበር መንግሥቱ የሚችለውን ያህል ገንዘብ በሰንዱቅ ጭኖ ስለሔደ ተመልሶ አይመጣም” በሚል ወሬ በማስወራት የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ምሁራንን በማስፈራራት ለማባረር ከሞከረና ሌላ በአንድ ምሽት መፈንቅለ መንግሥት ሞክሮ ለጥቂት ሰዓታት በታላቁ ቤተመንግሥት ተኩስ በማስከፈት ቀውስ ከፈጠረ በኋላ በደርጉ የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር በሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳንና በደርጉ የደሕንነት ኮሚቴ ሊቀመነበር በሻለቃ ተካ ቱሉ መሪነትና አስተባባሪነት፤ በተወሰኑ በሳልና ተራማጅ የደርግ አባላት ጥረት የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በእጭሩ ይከሽፋል።

ይህም ነገር በይፋ ቢታወቅና የመፈንቅለ መንግሥት እድምተኞቹ ቢጋለጡ ደርግን የሚያፈርስና ብሔራዊ ቀውስ የሚያደርስ መሆኑን በመገንዘብ ሌ/ሎሎኔል አጥናፉ አባተን ከዚያ በኋላ ያንን የመሰለ እጅግ አደገኛ ተግባር ላለማሰብ ቃል አስገብተው ጉዳዩ ለኔም ለሕዝብም ጥብቅ ምስጢር እንዲሆን ያደርጋሉ።

በእርግጥም ታላቅና ሃገር አቀፍ አደጋ ነበር። አጥናፉ መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የሞከረው እኔ ሃገርና አብዮትን አድን የሆነ መሣሪያ በምፈልግበት፤ አሥመራ በአስር ኪሎ ሚትር እርቀት በገንጣዮች በተከበበትና የአገራችን አንድ አምስተኛ መሬት በወራሪው በሶማሊያ ሠራዊት በተያዘበት ጊዜ ነበርና።

የእኔና የሁለቱ ጓዶቼ ማለትም፤ የብርሐኑና የአዲስ ተልዕኮ ከጠበቅነው በላይ ተሳክቶ ወደ አገራችን ተመልሰን፤ በአንድ ወገን ወራሪውን የሶማሊያ ሠራዊት በመልሶ ማጥቃት ከአገራችን በማስወጣት ዝግጅቱ በአጥጋቢ ሁኔታ እየተኪያሔደ እያለ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ የወዝአደር ሊግ (ወዝሊግ)፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢጭአት)፣ እና የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮታዊ ፓርቲ (ማሌሪድ) የሚባሉት ድርጅቶች በውስታችን መሠረት ከሕቡዕ እንቅስቃሴ ወጥተው በይፋ ህልውናቸውን የሚያበሥር የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ባሠራጩበት ጊዜ አብዮታዊ ሰደድም እንዲሁ ህልውናውን አበሠረ።

በዚህ ጊዜ ነበር ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ የሚጠራው ድርጅት፤ "የፋሽስታዊ ምርጥ መኮንኖችና የባንዳ ምሁራን የአብዮት ቅልበሳ ቅንጅት" በማለት ዲሞክራሲያ በሚለው በራሪ ወረቀቱ አብዮቱንና አብዮታውያንን ከሚያጥላላና ከሚያራክስ ፀረ-አብዮት ፕሮፓጋንዳ ጋር በነጭ ሽብር የአገሪቱን አብዮታዊ ምሁራን የሕዝቡን ብዙሀን ድርጅቶች መሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣኖችን መረሸን የጀመረው።

በደርግ ውስጥ የተፈጠሩትን አንጃዎች በአጠቃላይ፤ በሌ/ኮሎኔል አጥናፉና በሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ የሚመራው ቡድን በተለይ በየጊዜው የሚሸርቡትን ሴራና የሚሞክሩትን አደገኛ ሙከራ በህሊናቸው እየዘገቡ ሁኔታው ቢፈነዳ በቅድሚያ በደርግ ህልውና ላይ ከዚያም በአብዮቱ ደህንነት ላይ፤ ከሁሉም በላይ በአገሪቱ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን በመረዳት የሚሰጣቸውን የምስጢር አደራ በዚያ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ መጠበቃቸው እስከዛሬም ያስገርመኛል።

በእኔ ላይ ከተሞከረው ግድያ በኋላ ግድያውን በመቃወም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር በመላ አገሪቱ በያለበት፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ከየቤቱ በነቂስ ወጥቶ ከሰጠኝ ድጋፍ በተጨማሪ የአዲስ አበባ የከተማ ማህበራት በየከፍተኛው ክልል የሚኖረው ሕዝብ ለ4 ቀናት ተራ ገብቶ ታላቁ ቤተመንግሥት እየመጣ ሊያጽናናኝ ያደረገው ጥረት ለዘላለም በህሊናዬ ተቀርፆ ይኖራል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኔ ጋር መሆኑን ተቃዋሚዎቼ በመመልከታቸውና እኔም በየጊዜው የሚደገሰልኝን ሴራ እየቀደምኩ በማክሸፍ ሠላም የተገኘ ስለመሰለኝ የደርግን አሠራር ዘይቤ ከአብዮቱ እድገት አንፃር ለመለወጥ ለደርጉ ጉባዔ በዚያው በመስከረም ወር 1969 ዓ.ም አንድ ዕቅድ አቀረብኩ።

የዕቅዱ ይዘትና ዓላማም፤ የአሮጌውን ሥርዓት ላዕላይና ታህታይ መዋቅር በአብዛኛው ስለአፈራረስን ከእንግዲህ ወዲያ እኛው ራሳችን ከፈጠርነው ጊዜና አዲስ ሁኔታ ጋር የአሠራር ዘይቤያችንንም መለወጥ የሚገባ ከመሆኑ ሌላ ለአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓትና ለማህበራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ብቻ ሳይሆን የፓርቲያችንን የአብዮታዊ ሰደድን ሕዋሶች በሕዝቡ ውስጥ ለመፍጠር ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ መሠማራት ይኖርብናል።

አዲስ አበባ በቤተመንግሥት ውስጥ ተቀምጠን ጥቂት አብዮታዊ ምሁራን በመላክ አብዮት በወኪል መምራት አንችልምና ሥራ እንከፋፈል ብዬ ያዘጋጀሁትን አዲስ መዋቅር አዲስ የሥራ ክፍፍል ከነመምሪያው አዘጋጅቼ አቀረብኩ።

ይህ አዲሱ የደርግ መዋቅር ከቀድሞው መዋቅር ልዩነቱ በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴና በደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ መካከል የማዕከላዊ ኮሚቴ ተቋም መጨመሬ ብቻ ነው።

በአሠራር በኩል መሠረታዊ ለውጥ ያስከተለው የደርጉ ጉባዔ በቋሚነት ተቀምጦ ዕለት በዕለት ያከናውናቸው የነበሩ አያሌ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤትና የመከላከያ ሚኒስቴር ሥራ የነበሩ ከመሆናቸው ባሻገር ጉባዔው ያወጣቸው የነበሩ ፖሊሲዎች፤ አብዮቱን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችና አዋጆች ሁሉ በአብዛኛው ስለተጠናቀቁና ቀሪው ሥራ የወጡትን ፖሊሲዎች፤ ድንጋጌዎችና አዋጆች፤ ዕቅዶችና የፖለቲካ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ማድረግ ስለነበረ፤ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሥራው ወዳለበት መስክ መሠማራት ማስፈለጉ ነው።

በዚህም ምክንያት ወደተለያዩ የአገሪቱ ገጠሮችና የሥራ መስኮች የሚሠማሩት ብዙሁኑ የደርግ አባላት የሚሰበሰቡበት ጉባዔ፤ በየስድስት ወር እንዲጠራ፤ ማዕከላዊው ኮሚቴ በየሦት ወር እንዲጠራ ሆኖ ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ እንደ ፓርቲ የፖለቲካ ቢሮ



ከሻለቃ አጥናፉ እና ከሻለቃ ግብረየስ ወ/ሃና ጋር

ጉባዔውና ማዕከላዊ ኮሚቴው በማይሰበሰቡበት ጊዜ የሚሠራውን የየዕለቱን ሥራ እነሱን ወክሎ በቋሚነት የሚሠራበትን የአሠራር ዘይቤ ነው ያቀረብኩት።

አዲሱ የደርግ ተቋም መዋቅርና የሥራ ክፍፍል ዓላማ ከፍ ብዬ ከገለፅኳቸው ታላላቅ ተግባሮች ሌላ የአንድ አብዮታዊ ፓርቲን የአሠራር ልምድና ወግ እንዲያስተምረን ተብሎም የታሰበ ነበር።

የታቀዱት የመዋቅርና የሥራ ክፍፍል ለውጦች ጠቀሜታዎች ከዚህ በላይ የገለፅኳቸው ብቻ አልነበሩም።

እንደሚታወቀው በደርግ ውስጥ ከሻለቃ ማዕረግ ጀምሮ በተዋረድ ተራ ወታደሮችን ጭምር ያካተተ ሲሆን እስከዚህ ጊዜ ድረስ የደርጉ አባላት በህገ መንግሥቱ መሠረት በወል ርዕሰ ብሔሩን ተክተው በእኩልነት ተመሳሳይ ሥራ እየሠሩ፤ ወይንም ታሪካዊና አብዮታዊ ተግባር በወል የሚያከናውኑ ናቸው።

እያንዳንዳቸው አንድ ስህተት ላይ ቢወድቁ ወይንም አብዮታዊ ቃል ኪዳናቸውን ቢስቱ የሚደርስባቸው ቅጣት እጅግ ከባድ በሆነበት ሁኔታ ሃገርንና ሕዝብን እያገለገሉ፤ በሌላ አነጋገር በግዴታ ረገድ ሁሉም እኩል ሆነው በመብት ረገድ ብዙሃኑ እጅግ የተበደሉና በድህነት የሚሰቃዩ ስለነበሩ፤ አዲሱ የሥራ ስምሪት ሥራው ከሚጠይቀው ልዩ ልዩ መብትና በተለይም ከደሞዝ ክፍያ ጋር የተሳሠረ በመሆኑ የተዛባውን አስተዳደር ለመለወጥ እንዲያስችለን የታቀደ ነበር።

ይህንን ሃሳቤን ቀደም ብዬ ለጄነራል ተፈሪና ለሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አማክሬያቸው መደገፍ ብቻ ሳይሆን ግሩም ነው በማለት አድንቀውታል።

ጉዳዩ ሰፋ ያለ ስለነበረና በጥቂቱ ለሳምንት ያህል ያነጋገረን ስለነበረ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ 'ኢሕአፓና' ሌሎችም አድሀሮት በሰጡት አመራርና ምክር፤ መንግሥቱ ኃይለማርም ከሕዝብ ማደራጃ ምሁራን ጋር መክሮና ዶልቶ ከእነሱ ጋር የአገሪቱን አመራር አጠቃሎ በመያዝ ደርግን ወደ ገጠር ሊያሠማራና ብሎም ሊያፈርስ ነው በማለት ለደርጉ አባላት ስለነገሩዋቸው ሁሉም ባይሆኑ አብዛኛው እውነት ነው ብለው በማመን በኔ ላይ ሲዘምቱና ደም አልባ መፈንቅለ መንግሥት ሲያደርጉ ጄነራል ተፈሪና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ እኔን መርዳት ቀርቶ ሃሳቡን ለእኛም አካፍሎን ተስማምተናል ሳይሉ ከተቃዋቃሚው ቡድን ጋር አበሩ።

ደርግን ስመራ አያሌ ከባድ ፈተናዎችና ችግሮች ገጥመውኛል። ለማስረጃም ያህል፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ናቅፋ ላይ የ15ኛ ሻለቃ ለስድስት ወር መከበብና ጦር ልከን ልናድነው ባለመቻላችን መደምሰሱ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁ ተሰኔና አፋቤት የነበረው ጦራችን መደምሰስ፤ የከረን መያዝ፤ በምሥራቅ በተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የኦጋዴን ክልል ከመቆጣጠሩ ሌላ ዋርዴርን ለማመን በሚያስቸግር ጀግንነት ሲከላከሉ የነበሩት ነባሩ 22ኛ እግረኛ ሻለቃና አዲሱ ነበልባል ሻለቃ እስከመጨረሻው ጥይትና ሰው ታግለው መደምሰሳቸው፤ የጅጅጋ መያዝ፤ የአሥመራ መከበብ፤ ምፅዋን የሚመግበው የዶጋሊ የውሃ ማደያ መያዝ፤ የሌ/ኮሎኔል ዳንኤል በኢሕአፓ መገደል ወዘተ ብዙ ማለት ይቻላል።

ሕይወቴንም ለማጥፋት ከተደረገው ሙከራ በላይ እጅግ ያሳዘነኝ ነገር ቢኖር ይህ በሐሰት የተወነጀልኩበት አድማና መፈንቅለ መንግሥት ነው።

እዚህ ላይ አንባቢን ለማስገንዘብ የምፈልገው አርዕስቴ "ደርግና ሻለቃ አጥናፉ" የሚል ስለሆነ ኢሕአፓ የሞከረውን መፈንቅለ መንግሥት ለማስታወስ የፈለግሁበት ምክንያት በዚህ ጊዜ የሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አቋም ምን እንደነበረ ለመግለፅ ብቻ ስለሆነ ይህንን በዚሁ አቆማለሁ።

'ኢሕአፓ' ስለመራው መፈንቅለ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ስለ ጄነራል ተፈሪ ባንቲ ማንነት እንዴት ለዚህ ኃላፊነት እንደመረጥናቸው፤ ለምን እንደመረጥናቸውና በኋላ እንዴት እንደተለወጡ በቅፅ ሁለት አብዮታዊ የሚባሉት የአገሪቱ የፓለቲካ ድርጅቶች የመደብና የሃገር ጠላቶቻቸውን በጋራ ከመከላከልና ብሎም ሃገርና አብዮትን ከማዳን ይልቅ፤ ከፊሉ ከገንጣዮችና አስገንጣዮች፤ ከፊሉ ከሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ጋር፤ የተቀሩት በድርጅት እብጠትና በብቸኝነት የሥልጣን ጥማት እርስ በርስ ስለተዋጉበት ሁኔታ ለመተረክ ቃል ገብቼ ወደ ርዕሴ እመለሳለሁ።

በኢሕአፓ የተሸረበው ሴራና መፈንቅለ መንግሥት ዓላማው ፀረ-መንግሥቱ ብቻ ሳይሆን ፀረ-አብዮት መሆኑ ተጋልጦ ከከሸፈ ጥቂት ሳምንት በኋላ ሰበበኛው ዕቅዴ በደርጉ ጉባዔ ይሁንታን አግኝቶ አብዛኛው የደርግ አባላት በሹመትና በደሞዝ እድገት ለሥራ ወደ የክልሉ ተሰማርተው ስለሚያከናውኗቸው አያሌ አብዮታዊ ተግባሮች በምንወያይበት ጊዜ የአገራችን የእድገት አቅጣጫ ኅብረተሰባዊነት ወይም ሶሻሊዝም ነው፤ ካፒታሊዝም ሰው-በላ ሥርዓት ነው። መመሪያት ያለብን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው። ብሎ በለውጡ ባቡር አብሮን መጓዝ ብቻ ሳይሆን የአብዮቱ ሁለተኛ መሪ ጓድ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ በድንገት ከመቀመጫው ተነስቶ፤ ከደርጉ አብዮታዊ ዓላማ ጥቂት ብዛባ በኢትዮጵያ ትቅደም ስይፍ

እንገቴ ይቀላ ብሎ ለአብዮቱ ቃል ኪዳን የገባው መሪ ከዚህ የሚከተለውን የክህደት ፀረ-አብዮት ንግግር አደረገ።

"ከአገራችን ባህል፣ ኃይማኖትና ታሪክ ጋር ፈፅሞ የማይገጥምና የማይስማማ የሶሻሊስት ሥርዓት እንከተላለን ብለን አገሪቱን የጦርነት አውድማ አደረግናት።"

"አገራችንን ለውጭ ወራሪ ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ሕብረተሰብ እንድትገለል አደረግናት። ሰው በረሃብ የሚሞትባት የችጋር ሃገር አደረግናት" ሲል መላው የደርግ አባላት ለመናገር የፈለገውን ተናግሮ እስኪጨርስ ትዕግሥት ስላጡ ቆመው በጩኸት በውግዘት አቋሙትና ተቀምጠው ለመናገር መድረክ ይሰጣቸው ዘንድ ሁሉም ማለት ይቻላል እጃቸውን አወጡ።

እኔ እስከማውቀው ድረስ አጥናፉ በቀንና በስብሰባ አዳራሻችን ውስጥ ቀርቶ በምሽትም እቤት ውስጥ የሚጠጣ አይመስለኝም። የዚህን እለት ይህንን ሰው ምን ነካው? ምናልባት ጠጥቶ ይሆን ብለው የተጠራጠሩ ብዙዎች ነበሩ። እኔ ጠጥቶ ይሆን ብዬ በማሰብ ጠረን እስከመፈለግ ድረስ ነበር። ምክንያቱም የተናገረው ነገር በምንም ዓይነት የእሱ ንግግር ሊሆን አይችልምና ነው። ምናልባት የተናገረውን ነገር አምኖበት ከሆነ ያንን መድረክ፣ ያንን ቀንና ጊዜ ለምን መረጠ? እሱ ያንን ስለተናገረ የደርጉን ዓላማ ሊያስለውጥ ቀርቶ የሚያዳምጠውም እንደሌለ እያወቀ ያንን የመሰለ አደገኛ ንግግር ለማድረግ ለምን ፈለገ? ብዙ የሚያጠያይቅ ነው።

የኤርትራ ክፍለ አገር ርዕሰ ከተማና ወደቡ በገንጣዮች በተከበቡበት፣ ሌሎች ጠባብ ብሄረተኞችና ፀረ-ሕዝቦች ኢሕአፓን ጨምሮ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባና በየክልሉ ነጭ ሽብራቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜና የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ድንበር 700 ኪ/ሜትር ጥሶ በመግባቱ ኢትዮጵያ አለቀላት አበቃላት እያሉ ተቁርቋሪ በመምሰል እያሟረቱ ሕዝቡን ትጥቅ የሚያስፈቱና ግድ የለም ወራሪው የሱማሌ ሠራዊት ይምጣና መሿለኪያ ሲደርስ እንዋጋለን እያሉ የሚያፌዙትና የእሱ ጓደኞች የሆኑት አድሃሪ ምሁራን ይናገሩታል ተብሎ በመረጃ ምንጫችን የሚነገረንን በአጥናፉ አንደበት ለደርግ አባላት ቢነገር የትግል ዓላማቸውን ሊለውጡ ይችላሉ ብለው የነገሩትን ነው የተናገረው።

በተሰጣቸው መድረክ እያንዳንዱ የደርግ አባል እየተነሳ ያወረደበትን ከባድ ዘለፋና ውግዘት ዛሬ ለማስታወስ ይቸግረኛል። ብዙዎቹ ከአደረጓቸው ንግግሮች እጅግ ጥቂቶቹን ጨምቄ ከዚህ እንደሚከተለው ለማቅርብ እሞክራለሁ። የመጀመሪያው ተናጋሪ ከመቀመጫው በመነሳት ፊቱን ወደ ብዙሃኑ የጉባዔ አባላት በማዞር "የአብዮቱና የሕዝቡ ፀሮች ይህንን መንግሥት በመጣል አብዮቱን ለማዳፈን ብለው በየጎዳናው ሲናገሩት የምንሰማውን እንዴት በስብሰባ አዳራሻችን ከአብዮቱ ሁለተኛ መሪ ከጓድ ኮሎኔል አጥናፉ እንሰማው" በሚል ጥያቄ ንግግሩን ጀምሮ ከበድ ከበድ ያሉ ብዙ ኃይለ ቃሎችን ወረወረ።

ሁለተኛው ተናጋሪ እንደመጀመሪያው ተናጋሪ ፊቱን ወደ ብዙሃኑ የደርግ አባላት በማዞር "ጓዶች" አለ። "ጓዶች! ዛሬ በአገራችን የሚካሄደውን የሲቪል ጦርነት ልናቆም መጣን እንጂ እኛ አልፈጠርነውም። በማለት ጀምሮ ምክትል ሊቀመንበራችን በራሳቸው ፍላጎት ከአብዮቱ ባቡር ዘለው ወርደዋል" በማለት ንግግሩን ደመደመ።

ተከታዩ ተናጋሪ "እኛ የኢትዮጵያን ሠራተኛ መደብ ከምንዳ ባርነት፣ ገበሬውን ከገባርነትና ከዘላለም ድህነት ነፃ ለማውጣት መጣን እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለችጋር አልዳረግነውም። ለመሆኑ የትግራይና የወሎ ሕዝብ ረሀብ የተከሰተው መቼ ነው? ደርግ



ከጄነራል ተፈሪ እና ከሻለቃ አጥናፉ ጋር

የተቋቋመው መቼ ነው? ርሀቡን ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከዓለም የደበቀው ማን ነው? ግቤ አዋሽ ነው ብሎ ለወረራ 15 ዓመታት የተዘጋጀውን ተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ለመመከት ኢትዮጵያን ከውርደትና ከጥፋት ለማዳን መጣን እንጂ እኛ ነን አገራችንን ለወረራ ያጋለጥናት?" የሚል ጥያቄ አቅርቦ ተቀመጠ።

ሌላው ተናጋሪ "ምክትል ሊቀመንበር ተብዬው አገራችንን ከዓለም ኅብረተሰብ እንድትገለል አደረግናት ብለዋል። መቼና ከየትኛው ዓለም ኅብረተሰብ ነው ያገለልናት? እንደ እውነቱ ከሆነ የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ፣ ጥገኛና ቡችላ በመሆኗ ዓለም ያወገዛትንና ያገለላትን አገር ነው ዛሬ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ሰላም ወዳድና ዲሞክራቲክ አገሮች፣ የዓለም የሠራተኛ ንቅናቄ፣ የዓለም ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ፣ የዓለም አብዮታዊያንና ህብረተሰባዊ አገሮች ጎራና አባል ያደረግናት እኛ አይደለንም?"

ኮሎኔል የዓለም ሕብረተሰብ የሚሉት ኢምፔሪያሊዝምን ይመስለኛል። ይህንን አብዮት የሚመራው አንድ ጠንካራ የኮሚኒስት ፓርቲ ቢሆን ኖሮ ለአንድ ከሀዲ የሚገባ የመጨረሻው አብዮታዊ ቅጣት ይሰጣቸው ነበር። "ይህ ደርግ እኝህን ሰው ምንድን ነው የሚያደርገው? የኢትዮጵያ ትቅደም ሰይፍ መመዘዝ ያለበት ዛሬ ነው። የኮሎኔል አጥናፉ ከእኛ ጋር ጉዞ እዚህ ላይ ያበቃል" ብሎ መፈክር ሲያሰማ ሁሉም የደርግ አባላት ተነስተው መፈክሩን አስተጋቡ።

በደርግ ታሪክ አባላችን በሆነ ጓድ ላይ በዚያ ሁኔታ ከፍያለ ነቀፋና ዘለፋ የተሞላበት ንግግር ሲናገሩ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። አዝማሚያውም አደገኛ ስለነበር የተወሰንን የደርግ አባላት ተደናግጠናል።

ማታ ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ ለአጥናፉ ቤቱ ደውዬ በጤናህ ነው ዛሬ ያንን የመሰለ ነገር የተናገርከው? ምን ሆንክ? ምንድን ነው በአእምሮህ የተሠረፀው? የደርጉ አዝማሚያ

ገብቶሃል? እባክህ ነገ ጧት ውይይቱ ከመጀመሩ በፊት ይህንን ማለቴ አይደለም በአነጋገሬ አብዮቱን ጎድቼና እናንተን አሳዝኜ ከሆነ ይቅርታ አድርጉልኝ በልና ለእኛም ጣልቃ ገብነት መንገድ ክፈትልን በእሳቱ ላይ ውሃ እንድናፈስበት እርዳን ብዬ ስጠይቀው ባለቤቱም ይሰሙ ነበር።

የሰጠኝ መልስ "አንተን የሚያሳስብህ ነገር የለም። የምናገረውንና የማደርገውን የማውቅ ሰው ነኝ" የሚል ነው።

በበነጋታው ማለዳ በአንድ ሰዓት ገደማ የመከላከያና የደሕንነት ኮሚቴዎች መሪዎች ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳንና ሻለቃ ተካ ቱሉ እቤቴ መጥተው "ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ያንን የመሰለ ነገር ከተናገረና በአፀፋው ብዙ የደርግ አባላት አጥናፉን በመቃወምና በመወንጀል ከባድ ክስ ካቀረቡ በኋላ ኮሎኔል አጥናፉን ወደ ቤቱ መስደዳችን ስህተት ይመስለናል።

ከዚህ በኋላ አጥናፉም ምክትል ሊቀመንበር መሆኑ ቀርቶ በደርግ አባልነት ከኛ ጋር ይቆያል ተብሎ አይታሰብም። ከዚህ በኋላ እያያዛችን እንደዚህ ከሆነ፤ አንድም ራሱን ሊገድል ይችላል፤ ወይንም ሌላ ሰው ሊያበላሽ ይችላል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ሊሠወርና ሊሸፍት ስለሚችል ዛሬ ከመጣ ለምሳ ወደ ቤቱ ከመላክ ፋንታ በጥበቃ ስር ማድረግ ይኖርብናል የሚል ሃሳብ ከማቅረብ ባሻገር ከስብሰባ አዳራሽ ውጭ የሚቀመጡትን የደርግ አባላት እራስ መጠበቂያ የነፍስወከፍ መሣሪያዎች በሙሉ ዛሬ ማንም በማይደርስበት ሥፍራ ለማስቀመጥ ወስነናል በዕረፍት ጊዜ መሣሪያችን የት ሔደ የሚል ጥያቄ ቢቀርብ መልስ ልትሰጣቸው ይገባል ሲሉም አሳሰቡኝ።

ለጥንቃቄ ያቀረቡትን ሃሳብ ተቀብዬ፤ አጥናፉን በጥበቃ ሥር የማዋሉ ጉዳይ የሚወሰነው በዛሬው ስብሰባችን ላይ አጥናፉ በበኩሉ በሚወስደው እርምጃ ወይንም በሚሰጠው መልስ ላይ የተመሠረተ ነው የሚሆነው ብያቸው ተለያየን።

እንደተለመደው ከጧቱ በሁለት ሰዓት የደርግ አባላት በሙሉ በጉባዔው አዳራሽ ተገኝተን ከተቀመጥን በኋላ፤ ትናንት ባልተጠበቀና ባልታሰበ ሁኔታ ኮሎኔል አጥናፉ ያደረገውን ንግግር ምክንያት በማድረግ ብዙዎቻችሁ ብዙ ኃይለ ቃል ወንዝራችኋልና ዘለፋው በዚህ ቢያበቃ የሚሻል ይመስለኛል ብዬ መናገር ስጀምር፤ ብዙዎቹ እጃቸውን አንስተው ኮሎኔል አጥናፉ ስለተናገሩት አስተያየታችንን ያልሰጠን ብዙ ስለሆን መድረኩ ይሰጠን ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ።

ዛሬም ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ በተናገረው ነገር ላይ አስተያየት መስጠቱ እንዲቀጥል ከተፈለገ ኮሎኔል አጥናፉም በበኩሉ የሚናገረው ያለው ስለሚመስለኝ ቅድሚያውን ለእሱ እሰጣለሁ በማለት አጥናፉ እንዲናገር ጋበዝኩት።

ይህንን ማድረጌ ማታ በስልክ ያቀረብኩለትን ሃሳብ ተቀብሎኝ ራሱን ለመከላከልና ለማዳን ይናገራል ወይንም ይቅርታ በመጠየቅ ክሱንና ዘለፋውን ለማስቆም ይረዳኛል በማለት ነበር።

በእሱ በኩል ለዚህ ስለአልተዘጋጀ፤ እነሱ የሚሉትን ብለው ከጨረሱ በኋላ የምናገረው ይኖረኛል። አሁን ግን ለመናገር አልፈልግም ስለእለ የመናገሩን ዕድል በተራ ለሌሎች ሰጠሁ።

ብዙዎቹ አጥናፉ ለተናገረው የተቃውሞ ንግግር ማድረግ ብቻ ሳይሆን ስለአጥናፉ እናውቃለን የሚሉትንና በኔና በተወሰኑ የደርግ አባሎች የማይታወቁ እንግዳ ነገሮችን

በማጋለጥ ከተናገሩት ብዙ አባላት መካከል ትዝ የሚለኝ ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ የተናገረው ነገር ነው።

ሻለቃ ጌታቸው ይነሳና "ኮሎኔል አጥናፉ እዚህ ቦታና እዚህ ሥልጣን ላይ መቀመጥ የሌለበት አድሐሪ ነው" ካለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል፤ "ሊቀመንበር መንግሥቱ መሣሪያ ልመና ወደ ሶቭትና እንዲሁም ወደተቀሩት ሶሻሊስት አገሮች በሄዱበት ጊዜ ጽሕፈት ቤቱ ጠርቶኝ፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሊያቋቁም የሚሞክረው ማርክሳዊ ፓርቲ ለኢትዮጵያ እንደማይበጃት ከአያሌ ዕውቅ የአገሪቱ ምሁራን ጋራ መክረን ክርስቲያን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ለማቋቋም ወስነናልና አንተም የዚህ ፓርቲ አባል እንድትሆን እፈልጋለሁ ብሎኛል" ሲል፤ በብዙሃኑ የደርግ አባላት እኔን ጨምሮ አጥናፉ ይህንን ያደርጋል ብለን የምናስብ ካለመሆናችን ሌላ ለጉዳዩ ፍጹም ባዕድ ስለነበርን ከመገረም የተነሳ በቤቱ እርስ በርስ የመነጋገር ሁካታ ተፈጠረ። የደርጉን አባላትም ቁጣና ትኩሳት ጨመረ።

እዚህ ላይ በመጠኑ ከሥነሥርዓት ውጭ የሆነ አነጋገርም ስለተጀመረ፤ ሁኔታውን ለማቀዝቀዝ ስል የሻይ እረፍት እናድርግ ብዬ ከአዳራሽ ወጣን።

በሰማሁት ነገር ተገርሜ ብቻዬን አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጬ ከራሴ ጋር ስነጋገር ብቸኛ የሆነው አጥናፉ መጥቶ ከጎኔ ሲቀመጥ ደግሞ ከፍ ያለ ኃዘን ተሰማኝ። ወታደሮች ለሁለታችንም ሻይ አቅርበውልን ስንጠጣ የደርግ አባላት እንደልዩ ነገር ይመለከቱን ነበር።

ለብዙ ደቂቃ ዝም ካልኩ በኋላ፤ምንም ነገር እንዳልተደረገ ሁሉ ከአለንበት ሁኔታ ውጭ በሆነ ርዕስ ላነጋግረው ስጀምር፤ እሱም በዚያው መንፈስ ያነጋግረኝ ጀመር።

በኔና በእሱ መካከል ያ ዛሬ የማላስታውሰውና ለመነጋገር ያህል ብቻ ያደረግነው የማይረባ ንግግር መጨረሻችን ነበር።

ክፉኛ እየቀፈፈኝና እያስጠላኝ በአጥናፉ ላይ የሚወርደውን ወንጀል ለመስማት ወደ ስብሰባው አዳራሽ ተመልሰን ገባን።

በዚህ ጊዜ መድረክ እንዲሰጣቸው የጠየቁት በደርጉ ውስጥ ሽማግሌ ወይንም የእድሜ አንጋፋዎቻችን የምንላቸውና በዕድሜያቸው ብቻ ሳይሆን በገንቢ ምግባራቸውም የምናከብራቸው ጓዶች፤ እነ ሌ/ኮሎኔል መኩሪያ፤ እነ ሌ/ኮሎኔል ፋንታዬ፤ እነሻለቃ ተካና እነ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ነበሩ።

በተራ እየተነሱ፤ ትላንትናና ዛሬም ስለ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ የተነገረው ሁሉ እኛም የምናውቀው እውነት ነው። ይሄ ብቻ አይደለም ሊቀመንበር መንግሥቱ የጦር መሣሪያ እፈልጋለሁ በሚል ሰበብ ገንዘብ ጭኖ ላለመመለስ ሔዷል ብሎ ለግቢው ሠራዊት ከማውራቱ በላይ በዚያው ግዜ ውስጥ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ሞክሯል።

ለደርግና ለሠራዊቱ አንድነት ስንል የሠራቸውን ክፋቶች ሁሉ ከማንም ሰውረን በምስጢር ልንጠብቅለትና እሱም በበኩሉ ይህንን የመሰሉ ስህተቶች ዳግመኛ ላይሠራ፤ የአሮጌው ሥርዓት ናፋቂ ከሆኑ አድሐሪ ምሁራን ጋር ላይገናኝና ላይመክር ለምንነውና ከእናንተ ቃል አልወጣም ብሎ ቃል ከገባልን በኋላ ነው ዛሬ ደግሞ ከእሱ ቀርቶ ከማንም ጤናማ አእምሮ ካለው ግለሰብ አንደበት የማይወጣ ነገር የተናገረው።

በእኛ አስተያየት የተናገረው የራሱን እምነት ሳይሆን ጓደኞቹ አድሐሪ ምሁራን የመከሩትን ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ጓድ ኮሎኔል አጥናፉ ከኛ ጋር የሚያደርገው ጉዞ እዚህ ላይ ያበቃ ይመስለናል ሲሉ፤ የደርጉ አባላት በሙሉ ከመቀመጫቸው ተነስተው አብቅቷል አሉ።

ከዚህ በኋላ የምሳ ጊዜ ይሆንና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ ወደ ቤቱ ሳይሆን ወደ ማረፊያ ቤት ይሔዳል። ከዚህ በኋላ አላየሁትም።

እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብና ምናልባትም ዓለም ጭምር ስለደርግ ማወቅ ያለበት አንድ ነገር አለ። ለምንወዳት አገራችን ለኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ በመታገል ሕይወታችንን እንሰጣለን ብለን ለራሳችን ቃል ኪዳን ስንገባ፣ ከገባነው አብዮታዊ ቃል ኪዳን ዝንፍ ብንል፣ የኢትዮጵያ ትቅደም አብዮታዊ ሠይፍ ይረፍብን በማለት ምለን ነው።

ብዙ ሰዎች፣ ምናልባትም ጠቅላላው ሕዝብ እንደሚመስለው ወይንም እንደሚያምነው ከደርግ አባላት አንዱ ቃል ኪዳኑን ቢያጎድል፣ የክስ ዶሴ ተከፍቶ እማኝ ተቆጥሮና ጠበቃ ተቀጥሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚደረግ ሙግት አይኖርም።

የሚፈረድልን ወይንም የሚፈረድብን ተገድደን ሳይሆን ወደን በገባንበት የደርጉ ጓዳዊ የቃል ኪዳን ፍርድ ቤት መሆኑን ነው።

ሌ/ኮሎኔል አጥናፉን የትግል ጓዳችን ብቻ ሳይሆን ምክትል ሊቀመንበራችን አድርገን ከሦስት ዓመታት በላይ አስጨናቂውን ጉዞ አብረን ተጉዘናል። እውነተኛ የፖለቲካ እምነቱን የሚያውቀው ራሱ ብቻ ነው። እኛ እሱን ያመነው በገባው ቃል ኪዳን ነው።

ውስጣዊ እምነቱ ምንም ይሁን ምን በተግባሩ ግን ከኛ እስከተለየበት ቀን ድረስ አብዮታዊ ጓዳችን ነበር። በተግባር የሦስቱም የጦር ኃይሎች ንቅናቄ አባልና ንቁ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የአብዮታዊው ደርግ ፈጣሪም ነበር።

በየዋህነቱና በክፉ መካሪዎቹ ወደኋላ ቃል ኪዳኑን ሳተ። አብዮት ልጆቿን ትበላለች እንደሚባለው ጓድ አጥናፉንም የፈጠረው ደርግ በላው።

# ምዕራፍ አስራ አንድ

# ደርግና አፄ ኃይለሥላሴ

በዚህ ታሪክ መግቢያ ስለ አፄ ኃይለሥላሴ ከልደት እስከ ንጉሠ ነገሥትነት የተጓዙበትን የታሪክ ጎዳና በጣም አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለመቃኘት ተሞክሯል።

በዘመነ መንግሥታቸው ከአከናወኗቸው አያሌ በጎና ገንቢ ተግባሮች መካከል በጣም ጎልተው የታዩትን ከመዳሰስ ጋር የገጠሟቸውንም አንዳንድ አሳዛኝ ወይንም አስከፊ ገጠመኞችና ድክመቶቻቸውንም ለማስታወስ ተሞክሯል።

በዚህ ደርግና አፄ ኃይለሥላሴ በተሰኘ አርዕስት ሥር የማቀርበው ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ማግስት ጀምሮ ከሥልጣናቸው እስከ ወረዱበትና ብሎም እስከ አረፉበት ጊዜ ድርስ በደርግና በእሳቸው መካከል የነበረውን ሁኔታ ነው።

በደርግና በእሳቸው መካከል በነበረው ቆይታ የተከሰቱ አንዳንድ ጉዳዮችን ከመግለጼ በፊት ግን አፄ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በነበራቸው ገደብ አልባ ፈላጭ ቆራጭ መለኮታዊ የሥልጣን ዘመናቸው ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረባቸውን አገልግሎት አልሰጡም በማለት በቅሬታና በብሶት የሚታወሱበትን አያሌ ነገሮች ትቼ ለአገሪቱና ለሕዝቡ ብቻ ሳይሆን እንደውም በይበልጥ ለራሳቸው ደህንንት፣ ታሪክም መልካም ስም ያተርፍላቸው የነበሩ ውሳኔዎችን መወሰን ተስኗቸው ያልተጠቀሙባቸው ወርቃማ ጊዜዎች ወይንም ዕድሎች እያሉ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆኑ ባዕዳንም እስከ ዛሬ የሚያወሷቸውን ለመግለፅ እወዳለሁ።

አንደኛ ወይም የመጀመሪያ የተሳተ ወርቃማ እድል ይባል የነበረው በአገራችን ሰፍኖ በኖረው ጉልታዊ ሥርዓትና የሥርዓቱም ነፀብራቅ በሆነው የአመራር ጉድለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአያሌ ምዕት-ዓመታት የነበረበት አሳፋሪ ድህነትና የሰቆቃ ሕይወት ያነሰ ይመስል በ1928 ዓ.ም በፋሽስት ኢጣሊያ መወረሩን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ክብሩንና ነፃነቱን ተገፎ ቅኝ ከመሆኑ ጋር የሚስተካከል ውርደትና አሳዛኝ ነገር የለም።

የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ካደረሰው እልቂትና ውርደት ወዘተ ጋር ታክለው በታሪክ ከሚታሰቡ አሳዛኝ ጉዳዮች አንዱ ደግሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሰደድ ነው። በጊዜው የኢትዮጵያ የነቁ መንፈሳዊ አባቶች፣ አረጋዊ የየህብረተሰቡ መሪዎች፣ ለነፃነት የታገሉ አርበኞችና በአገሪቱ ምሁራን ዘንድ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለአምስት ዓመታት አውሮፓ በተለይም እንግሊዝ በስደት መቆየት ሁለት ገፅታ ነበረው።

አንደኛ ያለጥርጥር ከፍ ያለ የመንፈሥ ጉዳት የሚያደርስና ቅስም የሚሰብር የኃዘንና የፈተና ጊዜ ሲሆን፣ ሁለተኛውና በጎ ገፅታው በአምስት ዓመታት የስደት ጊዜ የአውሮፓን

አሀጉር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ወዘተ እድገት በአጠቃላይና የእንግሊዝ ሕዝብ በዘውድ አመራር ስር የተቀዳጀውን የቡርዧ ዲሞክራሲ ሕዝቡ መካከል እየኖሩ ማስተዋሉ ለአንድ በጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ተወልዶ ማደግ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ አውራ ወይም ቁንጮ ለሆነ አፄ ኃይለሥላሴን ለመሰለ ግለሰብ ታላቅ ትምህርት ነው ተብሎ ነበር የታመነው።

ከስደት መልስ አፄ ኃይለሥላሴ ፍፁም ስለሚሻሻሉና ምናልባትም ስለሚለወጡ ኢትዮጵያንም ይለውጧታል፣ በእንግሊዝ ዘውዳዊ መንግሥት የዲሞክራሲ ዘይቤ ይመሯታል የሚል ግምትና እምነት በብዙ ኢትዮጵያዊያን ህሊና ተሰርፆ ነበር።

የዚህ ግምትና እምነት ቀዳሚ አራማጅ ጥንድ ዓላማ በማንገብ ማለትም፣ የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ታግሎ ከኢትዮጵያ ምድር ከማስወጣት ባሻገር ለአገሪቱ ሪፐብሊካዊ የመንግሥት አመራር የማቀዳጀት ዓላማ ሲታገሉ የነበሩ አርበኞችና የአገሪቱ ምሁራን ነበሩ።

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ አፄ ኃይለሥላሴ መለወጥ አለባቸው፣ ይለወጣሉም ብለው አያሌ ኢትዮጵያዊያን ሊያስቡ ከተገደዱባቸው ምክንያት አንዱም፣ ኢጣሊያኖች በአምስት ዓመት ቆይታቸው ኢትዮጵያን ለውጠዋት ስለነበረ ንጉሡ አገራቸውን ወደ ነበረችበት አስከፊ ሁኔታ ለመመለስ አይቃጣቸውም በማለት ነበር።

እንደሚታወቀው አፄ ኃይለሥላሴ ከስደት ተመልሰው አገሪቱም ሰውም መለወጣቸውን ቢመለከቱም በእሳቸው በኩል መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማድረግ ቀርቶ መጠነኛ ጥገናዊ የፖለቲካ ለውጥ ለማድረግ እንኳን ፍላጎቱም፣ የህሊና ዝግጅትም አልነበራቸውም።

ሕዝቡ የተሻለ አስተዳደር ሲጠብቅ ከራስ አበበ አረጋይ የአርበኞች ጎራ በስተቀር ሌሎቹን በተለይም ለውጥ የሚጠይቁትን አርበኞች በማግለል የባንዳን የስደተኛ ግምባር ከመፍጠር ሌላ የፈረሰውን የመሣፍንት መደብ መልሰው በየጉልቱና በየአባቱ ጉልት በመትከል ኢጣሊያ ነፃ ያወጣውን አርሶ አደር መልሰው ገባርና ጢሰኛ አደረጉት።

"የሚወደንና የምንወደው" እያሉ የሚደልሉትን የኢትዮጵያ ሕዝብ መውደድ ቀርቶ በመሪነታቸው የሚያስቡለት ቢሆን ኖሮ ኢጣሊያኖች የኢትዮጵያን መሣፍንታዊ መደብ አፍርሰው የፈጠሩትን የካፒታሊስት ሥልተ-ምርት ወይም የምጣኔ ሀብት መርህ ተጠቅመው የአገሪቱን የመሬት ይዞታ ለመለወጥ የገጠማቸውን መልካም አጋጣሚ ሊጠቀሙ አልፈለጉም።

በዚህ ያዘኑት አርበኞችና ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ከራሳቸው ቤተ-ዘመዶችም ጭምር "ርዕሰ ብሔርነትዎን ይዘው መስተዳድሩን ለሕዝቡ በመስጠት እንደሌሎቹ የዓለም ነገሥታት ለሕግና ለሕዝብ ፈቃድ ተገዝተው በክብርና በሰላም ይኑሩ" ብለው የመከሯቸው ሰዎች ብዙ ቢሆኑም እሳቸው ፈቃደኛ አልሆኑም።

ገደብ አልባ እራስ ወዳድነታቸውን የሥልጣን ፍቅራቸውን የከለሉ መስሏቸው የተሰጣቸውን ምክር ላለመቀበል ይሰጡ የነበረው ምክንያት "እናንተ እንደምትሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን አልጠየቀም፣ ለዚህ አይነቱ የፖለቲካ ሥልጣን ወግ የበቃ ሕዝብ አይደለም። ወዘተ በማለት ለሕዝቡ ያላቸውን ንቀት ነበር የሚገልፁት።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የአገሪቱ አንጋፋ አርበኞችና በጊዜው የነበሩ ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች አፄ ኃይለሥላሴን ከዙፋናቸው በአመፅ ለማስወገድ የተለያዩ ግን ያልተሳኩ ሙከራዎችን ለማድረግ የተገደዱት።



አፄ ኃይለሥላሴ

ይህንን በተመለከተ "ኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ ከሆነ ዘውዳዊ አገዛዝ ወጥታ ለሕግና ለሕዝብ ፈቃድ ተገዝቶ በሚመራ ሪፐብሊካዊ መንግሥት መተዳደር አለባት" ከሚሉትና በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ አፄ ኃይለሥላሴን "እምባገነናዊ አገዛዝዎን ትተው መስተዳዳሩን ለሕዝብ በመስጠት እንደ ስለጠኑት ነገሥታት ለሕግና ለሕዝቡ ፈቃድ ተገዝተው በሰላም ይኑሩ" ብለው ከመከሩ ሰዎች አንዱ የነበሩት ቢትወደድ አዳነን እና እድምተኞቻቸውን ከሀያ አምስት ዓመታት የሰቆቃ ግዞት በኋላ አብዮታችን ነፃ ባወጣቸው ጊዜ በአገሪቱ ብዙሃን ማስራጫ የሰጡትን ታሪካዊ መግለጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይዘነጋው ተስፋ አደርጋለሁ።

ቢትወደድ አዳነ እና ግብራበሮቻቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከዙፋናቸው ለማስወገድ ያቀዱትን አመፅ ተካፋይ የነበሩት ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ አጋልጠው በወታደር በማሳፈስ ለሀያ አመስት ዓመታት ያህል በግዞት ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ ነፃነታቸውን በአገኙበት ጊዜ በመሪው በቢትወደድ አዳነ ከተሰጠው መግለጫ ሌላ አዛውንቱ በተራ እየቀረቡ ለደርግ ካስረዱት ሰፋ ያለ ሀተታ ነው ጨምቄ በማሳጠር ለማስታወስ የሞከርኩት።

ይህንን ታሪክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስታወስ የተፈለገው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ለማጣጣል ወይም ለማስጠላት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩና በባህሉ አገሩን አፍቃሪ መሪዎቹን አክባሪ፣ ትህትናና ትዕግሥት የተሞላው በመሆኑ መሪዎቹም ሊያደንቁትና ሊያከብሩት ሲገባ በድክመት የተረጎሙት መሆኑን ለማስታወስ ነው።

በተለይም ራሳቸውን "ሞአንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ፡ ስዩመ እግዚአብሔር" በማለት የሚጠሩት ግለሰብ በሂደት ሰው መሆናቸውን እስከ መዘንጋት ድረስ የመገበዛቸውን እውነታ ለማስታወስ ነው። በአፍሪካ፣ በእስያና በአውሮፓ ወዘተ አህጉራት ያሉ የሃገር መሪዎች ፀሎት ለማድረስ ቤተ ክርስቲያን በሚገኙበትና በሌሎችም አጋጣሚዎች የአገራቸውን መንፈሳዊ አባቶች በሚገናኙበት ጊዜ በመንፈሳዊ ትህትናና አክብሮት ከአንገታቸው ዝቅ ብለው መስቀል ሲሳለሙ ነው የሚታዩት።

በአገራችን በኢትዮጵያ ግን አቡኑ ወይም ፓትሪያርኩ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፊት በቀረቡ ጊዜ በተቃራኒው ከአንገታቸው ብቻ ሳይሆን ከወገባቸውም ዝቅ ብለው በማጎንበስ የንጉሡን ጣቶች መሳማቸውን ነው ስናስተውል የኖረነው። ንጉሣችን ባዕዳንን ካልሆነ በስተቀር ወገናቸው የሆነውን ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያዊት እጅ ሲጨብጡ ታይቶ አይታወቅም።

ኢትዮጵያዊያንን በመናቅ ወይም በመጠየፍ ይመስላል ከአልጋ ወራሹ ጀምሮ መላው የአገሪቱ ባለሥልጣናት ሲቪሎቹም ሆነ ወታደሮቹ ንጉሡ ፊት በቀረቡ ቁጥር መሬት ላይ ወድቀው ጫማቸውን ሲስሙ ነው የኖሩት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ መሣፍንት፣ መኳንንትና ወይዛዝርት እንዲሁም ካህናቱ በሙሉ ንጉሡን በርቀት በስልክ፣ በቅርብ በገፅ በሚያነጋግሩበት ጊዜና እንዲሁም ሲጠሩ እመሬት ላይ ተደፍተው ነው እኔ ታማኝ ባሪያዎ በማለት ነፃ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ ክብራቸውንም ጥለው ወይም አዋርደው ነው የኖሩት።

ይህንን የሚሉትና የሚያደርጉት በራሳቸው አነሳሽነት ወይም ፈቃደኝነት አድርባይ በመሆን ሳይሆን የአፄ ኃይለሥላሴ ታላቅነት ስዩመ እግዚአብሔርነት መግለጫ የቤተ መንግሥቱ ሕግ ስለሆነ ታዘውና ተገደው ነው። ይህንን ባያደርጉ የቤተ መንግሥቱ ቅልብ አልፍኝ አስከልካይ መኮንኖች ማጅራታቸውን ይዘው ነው ንጉሡ ጫማ ስር የሚደፏቸው።

ወደ ርዕሴ ልመለስና ሁለተኛ የተሳተ ወርቃማ ጊዜ ወይም እድል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስቱ አልቆ በቃኝ አሻፈረኝ ብሎ ያመፀበት ጊዜ ወይም አብዮታዊው ወቅት ነው። መላው ዓለም፣ ከኢትዮጵያም ህብረተሰቦች ምሁራን ነን የሚሉት ጭምር አንድን ማህበራዊ ሥርዓት መለወጥ ዓላማው ያደረገ ሕዝባዊ አብዮትንና በአንድ የፖለቲካ ቡድን ወይም አማፂ እድምተኞች የአንድን መንግሥት የአመራር ማዕከል ግለሰብ ወይም አካል በሌላ ግለሰብ ለመለወጥ ወይም ለመገልበጥ ከሚደረግ መፈንቅለ መንግሥት ጋር ያለውን ከፍ ያለ ልዩነት ከመረዳት ጉድለት የተነሳ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ አብዮት የሚድኸው መፈንቀለ መንግሥት ከማለታቸው ሌላ፣ ደርግ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ዘውዱ እስከ ተገረሰሰበት ጊዜ ድረስ የነበረውን የመጀመሪያ የሽግግር ጊዜ ወይም ሂደት የተለያየ ትርጉምና ስም ሰጥተውት እንደ ነበር የሚታወስ ነው።

አብዮቱን የሚመራውን ደርግ የሚይዘው የሚጥለውን ያጣ፣ በፍርሀት ውሳኔ መስጠት የተሳነውና የሚደናበር እያሉ በወቅቱ መተቸት ብቻ ሳይሆን ይሄንኑ የተሳሳተ አስተያየታቸውን አብዮቱ ከተቀለበሰም በኋላ እስከ ዛሬ የሚፅፉ አሉ።

በዚህ ታሪክ መቅድምና መግቢያ ስለ ደርግ አመሰራረት እንደገለፅኩት የደርግ አባላት በቅድመ አብዮት ተፈላልገን ተገናኝተን፣ በጎሳ በፖለቲካ ድርጅት ተሰባስበን ሳይሆን ከአገሪቱ የተለያዩ የጦር ክፍሎች ሠራዊቱ በነፍስ ወከፍ የመረጠንና የማንተዋወቅ ሰዎች ስለነበርን ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት እርስ በእርሳችን ከመተዋወቅ አስፈላጊነት ባሻገር ሁላችንም በየጦር ክፍሉ በትክክል መመረጣችንን ለማረጋገጥ፣ አንድ የጋራ የፖለቲካ ዓላማና እንዲሁም መመሪያ መፍጠር እንደነበረብንና ይህም ጊዜ እንደሚጠይቅ ለመረዳት ማንንም የሚያዳግት አይመስለኝም።

በኢትዮጵያ ሥርነቀል ማህበራዊ ለውጥን ለሚያስገኝ ዓላማ ተግባራዊነት ደግሞ በጥራትና በጥንቃቄ የተጠና የትግል ስልትና ስትራቴጂ የመንደፍ አስፈላጊነትንና ይህም ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ ለማንም ሰው ግልፅ ነው ብዬ አስባለሁ።

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያ በአብዮታዊ ነውጥ ላይ ያለች ሃገር እንደመሆኗ መጠን በቀናት ሳይሆን በየሰዓቱ የሚፈጠሩትንና የሚለዋወጡትን ልዩ ልዩ ክስተቶችና ቀውሶች ነቅቶ መከታተል፣ መቆጣጠርና እንደ የጠባያቸው የሚያስፈልጋቸውን መፍትሄዎች በመሻትና ቆራጥ ፈጣን አመራር መስጠትን የሚጠይቅ ቀውጢ ጊዜ ነበር።

በየሰዓቱ የሚከሰቱና የሚለዋወጡ አያሌና ውስብስብ ችግሮችን ለመቆጣጠር ከሚደረጉ ጥረቶች ጋር ሌላው ትኩረታችንን የሚጠይቅ አብይ ጉዳይ አፄ ኃይለሥላሴን ራሳቸውንና ሥልጣናቸውን የሚመለከተው አስቸኳይ ጉዳይ ነበር።

የአፄ ኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭና ፍፁም መለኮታዊ ሥልጣን ከየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ጀምሮ በደረሰበት ጥቂት የጦር ኃይሎች ጉሸማና ይህም በለኮሰው የሕዝብ አመፅ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየተፍረከረከ ነበር። ሲፈራ የነበረው መለኮታዊ ሥልጣን እንደዚያ ባጭር ጊዜ ውስጥና በጥቂት ጉሸማ የተፍረከረከበትና ብሎም የፈረሰበት ምክንያት የኢትዮጵያ ገዥ መሣፍንትና መኳንንት መደብ የነቃ የጋራ ፖለቲካዊ ዓለማ የነበረውና ህልውናውን ለመጠበቅ እንደ መደብ የተደራጀ ስላልነበረ ነው።

የተበታተነና ሕብረት'ያልነበረው፣ በንዋይ ሌሰኝነትና በሥልጣን ሽሚያ እርስበእርሱ የሚናከስ፣ አንዱ በሌላው ላይ ከሚሰራው ሻጥር አልፎ መደቡ የሚያራምደው ማህበራዊ ሥርዓትና በመደቡ ላይ የሚያንዣብበውን አብዮታዊ ዳመና ለማስተዋል የተሳነው መደብ ስለነበረ ነው።

የኢትዮጵያ የመሣፍንትና የመኳንንት መደብ ለረጅም ጊዜ ገደብ አልባ በሆነ ምዝበራ፣ ሙስናና በድሎት ሕዝብ እየረገጠ በሕዝብ ጀርባ ላይ ታዝሎ ሊቆይ የቻለው በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዙፋን መከታውና ጠለላው አድርጎ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዙፋንና መለኮታዊ ሥልጣን ጠንካራ ማህበራዊ መሠረትና አጥር መሳፍንቱና መኳንንቱ ሳይሆኑ የአገሪቱ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የስለላ መረቦቻቸው ናቸው። የሞአንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ ስዩመ እግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣን መፈሪያና መታፈሪያ የሆኑት የጦር ኃይሎች ከየካቲት ጀምሮ የሕዝባዊው አመፅ ቀስቃሽና ፋና ወጊ ስለሆኑ በጦር ኃይላችንና በተፈሪ መኮንን መካከል የነበረው የግንኙነት መስመርና የእዝ ሰንሰለት በጣም የሰለሰለ ነበር።

ከመላው የአገሪቱ መሣፍንትና መኳንንት ጋር የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማደጎና ታማኝ የነበሩት ከፍተኛ መኮንኖች በሙሉ ብዙሃኑ መለዮ ለባሽ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸው ጊዜ የሰለሰለው የግንኙነት መስመር ለአንዴና ለመጨረሻ ተቋረጠ ወይም ተበጠሰ።

በአብዮቱ ማግስት ከሰኔ 22 እስከ 30 ድረስ በነበሩት ቀናቶች ውስጥ የአፄ ኃይለሥላሴ መለኮታዊ ሥልጣን ቁልፍ የነበሩትን የአገሪቱን የደህንነት አመራር ማዕከል፣ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የነበሩትን ቅርንጫፎቹን፣ የንጉሡን ኢ.ታማጆር ጽሕፈት ቤትና በስሩ የነበረውን የኤሌክትሮኒክ የስለላ መሣሪያ በአገሪቱ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ የደህንነት ጽሕፈት ቤት ስር የነበረውን ሌላውን የኤሌክትሮኒክ የስለላ ተቋም ወይም የስልክ ጠለፋ፣ ቤተ መንግሥቱን፣ የንጉሡን ልዩ ጽሕፈት ቤት፣ የዙፋን ችሎቱን፣ የዙፋን ምክር ቤቱን ወዘተ በጠቅላላው የሥልጣናቸውን አውታሮችና የስለላ መረቦቻቸውን በቁጥጥራችን ስር አደረግን።

ማንም ሊያውቀውና ሊገነዘበው የሚገባ ነገር፣ ለወግ ካልሆነ በስተቀር ከተግባር አኳያ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣናቸው የወረዱት በመስከረም ሳይሆን በሰኔ ወር መገባደጃ ላይ መሆኑን ነው። ይህንን በማድረጋችን የንጉሡ ታሪክ እዚህ ላይ አበቃ፣ የዘውዱ ህልውና አከተመ ማለት ካለመሆኑም በላይ አሁንም ማንም ሊያውቅና ሊገነዘበው የሚገባ ሌላው ነገር፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ግብና ዓላማ አገሪቱ ስትመራበት የነበረው ሥርዓተ-ማህበር እንጂ በቤተ መንግሥታቸው የታሰሩትን የጃጁት ግለሰብ አልነበሩም።



አፄ ኃይለሥላሴ ከቤተ መንግሥት ወደ ማረፊያ ቤት ሲወሰዱ

ለሕዝባዊ አብዮቱ ደህንነት ጠንቅና ለሂደቱ እንቅፋት እስካልሆነ ድረስ ከእኛ ጋር ተባብረው የተጠየቁትን ሁሉ እስከፈፀሙ ድረስ ዘውዱን ተሸክመው ለሌላ ስማንያ ዓመታት በኢዩቤልዩ ቤተ-መንግስታቸው ቢቀመጡ ለእኛ ችግራችን አልነበረም።

በዚያ እድሜና ተክለሰውነት በየሰዓቱ በሚሰሙት ነገር፣ ይህም በሚፈጥርባቸው ውጥረትና ጭንቀት የደም ንዝረታቸው አድጎ ልባቸው እንዳይቆም በየቀኑ ሐኪም እንዲጎበኛቸው እናደርግ ነበር። ጤንነታቸው በመልካም ሁኔታ ላይ የነበረ ቢሆንም በመንፈስ እንዲጎዱ ስላልፈለግን ለማፅናናት ስንል፣ ኢትዮጵያን ለማስቀደም የምናደርገውን ሰላማዊ ጥረት እስከደገፉ ድረስ የጦር ኃይሉ ለዙፋኑ ታማኝ ነው ብለን በብዙሃን ማሰራጫ መግለፃችን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚታወስ ይመስለኛል።

የአብዮቱ እስረኛ ቢሆኑም በቤተ መንግሥታቸው ምንም ነገር ስለማይጎልባቸው በአገልጋዮቻቸው እየተገለገሉ፣ የሚጠብቋቸውም የሚያውቋቸው የክብር ዘበኞቻቸው ነበሩ። የማይፈቀድላቸው ከቤተ መንግሥታቸው ቅጥር ግቢ መውድጣትና ለጊዜው ከባዕዳን መገናኘት እንጂ ልጆቻቸውና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው በፈለጉ ግዜ ይጎበኛቸው ነበር።

ኢትዮጵያን የሚያስቀድም ዓላማ እስካልተቃወሙ ድረስ ታማኞችዎ ነን ስላልናቸው በበኩላቸው ለእኛ ያላቸውን ታማኝነት ለመግለፅ ሲሉ እኛ ከእሳቸው ባልጠበቅነው ሁኔታ ብዙ ተባብረውናል፣ ብዙ ሥራዎችንም አቃለውልናል። ከበኩር ልጃቸው ከልዕልት ተናኘ ጀምሮ መላውን የአገሪቱን መሣፍንት፣ መኳንንት፣ ካህናትና መኮንኖች በቁጥራችን ስር እንድናውል እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትራቸውም ተባብረውናል።

የአብዮቱ ማግስት ባልነው የመጀመሪያው ወሳኝ የሽግግር ወቅት ካልተገደድን በስተቀር የአንድ ኢትዮጵያዊ ደም እንዳይፈስ፣ አስፈላጊ ያልሆነ ቀውስና ትርመስ እንዳይፈጠርና አንዲት ጥይት እንኳን እንዳትተኮስ ያቀድነው ትዕግሥትና ጥበብ የተሞላው ሰላማዊ የትግል ስልት ለተወሰነ ጊዜ ሰርቶልን ነበር።

የአብዮቱ ማግስት ባልነው ወሳኝ የሽግግር ወቅት ያቀድነው ሰላማዊ የትግል ስልት የኢትዮጵያን ሕዝብ አኩሪና የረጅም ጊዜ ህልውና ታሪክና ጥንታዊ ሥልጣኔ፣ የሕዝቡን ትዕግሥት፣ አስተዋይነትና ኩራት ባካተተ ሁኔታ ለአፍሪካ ምሳሌ በመሆን ዓለምን ለማስደነቅ በነበረን ምኞት፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴንና የዘውዱን ህልውና ጉዳይ ልናስወስን አቅደን የነበረው በሕዝብ ብያኔ ድምፅ ነበር።

ስለ ደርጉ ማንነትና ምንነት ምንም ዓይነት መረጃና ግንዛቤ ባልነበራቸው ሰዎች አብዮታችን የሚድኸው መፈንቅለ መንግሥት የሚል ስም ያገኘበት አንዱም ምክንያት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአያሌ ምዕት ዓመታት የዲሞክራሲ ጥያቄ መልስ ይሰጣል ተብሎ በአርቃቂ ጉባዔ ሲዘጋጅ የነበረው ሕገ መንግሥት እስኪጠናቀቅ ለመጠበቅ የተገደድነው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሥልጣንና የዘውዱ ህልውና ከህገ መንግሥቱ ጋር ለሕዝቡ ብያኔ ድምፅ ለማቅረብ በነበረን አቅድ መሠረት ነው።

ይታወስ እንደሆን የፓርላማው መማክርት እንደተለመደው በክረምቱ ወቅት ለሦስት ወራት መበተናቸው ቀርቶ በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ የጠየቅናቸው፣ ለአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ መሣሪያ ሆኖ የኖረውን የሕግና የሕዝብ የበላይነት ሥልጣን፣ እንደ ፓርላማ ወይም ሕዝብ እንደሚወክል ምክር ቤት መረከብ የሱ ተግባርና ተልዕኮ ከመሆንም በላይ ታሪካዊውን የሥልጣን ርክክብ በተመለከተ የሚያስተናገዱቸው ታሪካዊ ተግባራትም ስለነበራቸው ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግሥት ማለቅና አመፃዊ ቁጣ ምክንያት ለሦስተኛ ጊዜ ይሻሻላል ተብሎ ለሕዝብ ቃል የተገባለት ሕገ መንግሥት ደርግና መላው የኢትዮጵያ አብዮታዊያን እንደሚፈልጉት የኢትዮጵያ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ የእድገት አቅጣጫ የሚለውጥ ይሆናል ተብሎ ባይታሰብም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭ መለኮታዊ ሥልጣን ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያስገኛል ብለን ገምተን ነበር።

መገመት ብቻ ሳይሆን የሚረቀቀው ሕገ መንግሥት በቅርፁም ሆነ በይዘቱ የምንጠብቀው ሕገ መንግሥት ሊሆን ስለመብቃቱ የአርቃቂው ጉባዔ አባላት በሆኑ ተባባሪዎቻችን አማካኝነት በአንክሮ የምንከታተለው ታላቅ ጉዳይ ነበር።

የአርቃቂው ጉባዔ አባላት አብዛኛዎቹ በአገሪቱ አሉ የሚባሉ ወግ አጥባቂዎችና የአሮጌው ሥርዓት ወኪሎች በመሆናቸው፣ ሁለንተናዊ የሥርዓት ለውጥ ቀርቶ ጥገናዊ የፖለቲካ ለውጥ እንኳን እንደማያስገኙ በመረዳታችን የንጉሡንና የወግ አጥባቂዎቹን የጉባዔ አባላት አፍራሽ ወይም አድሀሪ ተፅእኖ በመመዘን በማቃለልና የጉባዔውን ተራማጅ ክንፍና ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማበረታታት የረቂቁን ይዘት በሕዝብ ጥያቄ መሠረት ለማስለወጥ አንባቢ እንደሚያስታውሰው የጣልቃ ገብነት እርምጃ ወሰድን።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሕገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔውን ሰብሳቢና ጸሃፊውን ወይም ሁለቱንም ደርጉ ጽሕፈት ቤት ጠርተን በመረቀቅ ላይ ባለው ፋይዳ ቢስ የሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ያለንን ብርቱ ተቃውሞ መግለፅ ስንችል ከዚህ በተሻለ ይጠቅማል፣ የኮሚሽኑን አባላት ሁሉ ማግኘት ይቻላል፣ ለታሪክም ይበጃል ብለን በማሰብ ህገ መንግሥቱን አርቃቂው ጉባዔ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተገኝተን የጉባዔው አባላት በሙሉ ባሉበት መድረክ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአያሌ ምዕተ ዓመታት የዲሞክራሲ ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ መልስ የሚሰጥ ሕገ መንግሥት ታዘጋጃላችሁ ተብሎ ሲጠበቅ፣ እንደ ተለመደው የአንድን ግለሰብ መለኮታዊ ሥልጣን ዛሬም ለመደረት የተሰበሰባችሁ ከሆነ ጊዜያችሁን በከንቱ ነው የምታባክኑት በማለት አቋማችንን ገለፅንላቸው።

የሚያሳዝነው ነገር እኛ ሰላማዊና ገንቢ ብለን ያደረግነው ጣልቃ ገብነት በደርግና በቤተ መንግሥቱ፣ በደርግና በመስተዳድሩ መካከል የተፈጠረውን ሰላም፣ መረጋጋትና መልካም ግንኙነት አበላሽቶ ለሰላ ቅራኔና ብሎም ለአደገኛ ግጭት ምክንያት ሆነ።

ንጉሡንና ዘውዱን ለማዳን ሲሉ ከአገሪቱ መሣፍንትና መኳንንት ጋር ቅራኔ ውስጥ በመግባት ከደርግ ወግነው ንጉሡን መሰረታዊ የፖለቲካ ለውጥ እንዲቀበሉ ያደርጓቸዋል የተባሉት ጠቅላይ ሚኒስትር በተቃራኒው ታማኛችን ነው የሚሉት ደርግ የስልጣንዎና የዙፋንዎ ፀር ነው በማለት ንጉሡን ስለመረዟቸው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉሡና ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ደርግን ወደ ማፍረሱና ብሎም ወደ ማጥፋት ሴራ አመሩ።

ደርግን ለማፍረስ፣ ለማጥፋትና መለዮ ለባሹን እርስ በእርሱ ለማዋጋት ወዘተ ያደረጓቸው ጥረቶች ደርግና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው በተሰኘው ርዕስ ስር የተገለፁ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይሆንም።

በደርግና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መካከል የነበረውን የመቻቻል፣ የመረጋጋት የመግባባት ሰላማዊ ቆይታ በይበልጥ ያበላሸውና ቅራኔውን ያከረረው በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ መጠየቃችን ነው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በዘመነ መንግሥታቸው ብቻ ሳይሆን ደጃዝማች ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ለስልሳ ዓመታት ለሃገርና ለወገን ተቆርቋሪና የእሳቸውንሥልጣን ተቀናቃኝ የነበሩ እያሌ ኢትዮጵያዊያንን በግፍና በተንኮል ያጠፉ እጅግ ግብዝና ራሳቸውን ወዳድ ቢሆኑም ሌላውን በጎ ምግባራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እሳቸው በሌሎች ላይ እንደ አደረጉት ሳናጉላላቸውና ሳናዋርዳቸው የተንከባከብናቸው፣ ታሪካቸውንም ልናሳምርላቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ወርቃማ እድል እንዲያገኙ ለማድረግ ያቀድነው፣ እሳቸውም በበኩላቸው የደጉን የኢትዮጵያ ሕዝብ ውለታ ተገንዝበው በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ እንዲመልሱለት ነበር።

ለአርባ አራት ዓመታት ያህል በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ወርቅና ገንዘብ የግብጹ ፋሩቅ እንደ አደረጉት የባዕዳን ሲሳይ ሆኖ ሳይቀር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እንዲውል እናደርጋለን በሚል ተስፋ ነበር። መጠኑን በውል ለማወቅ ቢያዳግተንም በአውሮፓ በተለይም በስዊዝ ባንክ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ማስቀመጣቸው አጠራጣሪ አልነበረም።

በአብዮቱ ፍንዳት ማግሥት ከንጉሡ ጀምሮ የንጉሣዊያን ቤተሰቦችን፣ የመሣፍንቱን፣ የመኳንንቱንና የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖችን ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብቶችን አይነትና መጠን አጥንቶና አጣርቶ እንዲያቀርብ ያቋቋምነው አጣሪ ኮሚቴ ንጉሡ በስዊዝ ባንክ አስቀምጠዋል ስለሚባለው ገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን መረጃ አቅርቦልናል፣

1ኛ/ ራስ ተፈሪ የንግሥት ዘውዲቱ እንደራሴና አልጋ ወራሽ ሆነው በ1922 ዓ.ም አውሮፓን በጎበኙበት ጊዜ፣ አውሮፕላኖችና የተለያዩ የጦር መሣሪያዎች፣ የህትመትና የህክምና መሣሪያዎች ወዘተ መግዣ ተብሎ መጠኑ በውል ያልታወቀ ገንዘብ ይዘው በመሄድ በስዊዝ ባንክ ካስቀመጡ በኋላ ተገዝተው ወደ ሃገር የገቡት ሁለት ትንንሽ አውሮፕላኖችና የህክመና መሣሪያዎች ብቻ እንደሆኑ፣

2ኛ/ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ ባለቤታቸው እቴጌ መነን ንግሥት ዘውዲቱን ተክተው የእየሩሳሌም ገዳም የበላይ ጠባቂነት ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ በእሥራኤል ባንክ ሂሳብ ከፍተው በየዓመቱ መጠኑ የተሰወረ ገንዘብ ይልኩ እንደነበረ፣

3ኛ/ ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በክብረ መንግሥት አውራጃ አዶላ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሲመረት የነበረው ወርቅ በሙሉ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ሲገባ የነበረው ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት ሳይሆን ወደ ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት እንደሆነና በ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ አማፂያኑ በብዙሃን ማሰራጫ ይህንን ምስጢር ለሕዝብ በማጋለጣቸው የምርቱ ከፊል ወደ መንግሥቱ ግምጃ ቤት እንዲገባ ሲወሰን የተቀረው እስከ አብዮቱ አጥቢያ ድረስ ወደ ቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤት እንደሚገባ፣

4ኛ/ በ1928 ዓ.ም የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራን ለመመከት የተደረገው ጥረት ያለመሳካቱ እየታወቀ በመጣ ጊዜ በሃገር ውስጥ ባንኮችና በመንግሥት ግምጃ ቤት የነበረ ገንዘብና ወርቅ በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ተብሎ በንጉሡ ስም ወደ እየሩሳሌም፣ ወደ ካይሮና ካርቱም ባንኮች ሐለመላኩ፣

5ኛ/ በመጨረሻም ንጉሡ ወደ አውሮፓ ሄደው የፖለቲካ ትግል ያደርጉ ዘንድ ሲወሰን ለእሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለአገልጋዮቻቸው መተዳደሪያ፣ ለፖለቲካ ሥራ ማስኬጃ ከተመደበው ገንዘብ ሌላ ከአውሮፓ እና ከሰሜን አሜሪካ የጦር መሣሪያ እየተገዛ ለአርበኞች እንዲላክ ተብሎ በአገሪቱ ባንኮችና በመንግሥቱ ግምጃ ቤት ከነበረው ገንዘብ ከፊሉ ከእቴጌ መነን ጋር ወደ እሥራኤል ሲላክ የተቀረው ከንጉሡ ጋር ወደ አውሮፓ እንደሄደና ንጉሡ በእንግሊዝ መንግሥት ርዳታ በሱዳን በኩል ወደ ሃገር ሲገቡ በእንግሊዝ መንግሥት ችሮታ ለሰሜን ምዕራብ አርበኞች ከታደለው ጥቂት መሣሪያ በስተቀር ለኢትዮጵያ አርበኞች በኢትዮጵያ መንግሥት ወጪ ምንም ዓይነት መሣሪያ እንዳልተገዛ፣

6ኛ/ የፋሽስትን ወረራ በየጦር ግንባሩ ይከላከል የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት በመበተኑ ንጉሡ ከጦር ግምባር ሲመለሱ፣ ወራሪው ሠራዊት አዲስ አበባ ከገባና ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ መሆኗን ዓለም አውቆ ከተቀበለ ወራሪው መንግሥት በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር የትም ያለውን የኢትዮጵያ መንግሥት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረትና ገንዘብ አለኝታዬ ነው ሊል ስለሚችል፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በማዕከላዊ ምሥራቅና በአፍሪካ ባንኮች የተቀመጠ የኢትዮጵያ መንግሥት ገንዘብ በሙሉ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስም በግል የባንክ ሂሰባቸው እንዲዛወር መደረጉንና ከነፃነት ማግኘት በኋላ በግል የባንክ ሂሳባቸው የተቀመጠው ገንዘብ ወደ መንግሥት ሂሳብ ወይም ባንክ እንዳልተዛወረ የሚያስረዳው የጥናትና የምርመራ ውጤት መረጃ በማግኘታችን ነው ቢያንስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወቅታዊ ችግር በመጠኑም ቢሆን ሊያቃልል የሚችል ገንዘብ አለ ብለን ለማመን የቻልነው።

በስዊዝ ባንክ ገንዘብ መቀመጡን ለማወቅ የተደረጉ ጥረቶች ከዚህ በላይ የገለፅናቸው ብቻ አልነበሩም። የባንክ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶችን የመሰሉ ሰነዶችን በቤተ መንግሥት ውስጥ ስናፈላልግ ንጉሡ ይኖሩበት በነበረው በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ልዩ የጥናትና ጽሕፈት ቤታቸው ውስጥ የነበረ የብረት ካዝና ሲከፈት አንድ እጅግ የተዋበ የቆዳ ቦርሳ ተገኘ።

ቦርሳው የተቆለፈ ስለነበረ ቁልፉን ማግኘት አልተቻለም። የቦርሳውን ቁልፍ ሰብሮ በውስጡ ያለውን ነገር ለማየት ሲቻል ከቦርሳው ውበት የተነሳ አጣሪው ቡድን እንዲሰበር ባለመፈለጉ ከቤተ መንግሥቱ ለንጉሡ በጣም ቅርብና በተጠቀሰው ጽሕፈት ቤታቸው ውስጥ የሚሰራ አገልጋይ ተፈልጎ ሲጠየቅ ካዝናውንም ሆነ ቦርሳውን ከንጉሡ ሌላ የሚከፍት እንደሌለ ይገልፃል።

"ከዚህ ካዝናና ቦርሳ ውስጥ የሚያስቀምጡት ሰነድ ከፍተኛ ምስጢርነት ያላቸውና የግላቸውን ጉዳዮች የያዙ ናቸው። ቦርሳውን የሚከፍቱበትን ትንሽ ረቂቅ ከወርቅ የተሰራ ቁልፍ እንደቀለበት በጣታቸው ሰክተው ነው የሚይዙት" ብሎ ጠቆመ።

ያጣሪው ቡድን መሪ እኔ ዘንድ ቀርቦ ይህንን ካስረዳኝ በኋላ ቁልፉን ከንጉሡ ጣት አውልቆ ለመውሰድ ይፈቀድለት ዘንድ ጠየቀ። በደርግ ሥራ አስፍፃሚ ኮሚቴ ላይ ከተነጋገርንበት በኋላ የደርጉ ጥበቃ ሃላፊ የሆነው ሌ/ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ከንጉሡ ጣት አውልቆ እንዲሰጠው ታዘዘና ንጉሡ ቁልፉን ሰጡ።

ሁኔታው ስለአስደነቀን ቁልፏን አስመጥተን መላው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተመለከትናት። አጣሪው ቡድን ቦርሳውን ሲከፍት በውስጡ ያገኘው የስዊዝ ባንክ የሚጠቀምበትን የባንክ ሂሳብ መግለጫ የሆኑ በርካታ ሰነዶችን ነበር።

ወረቀቱ ወደ ውሃማ ቀለም የሚያደላ ሰማያዊ መልክ ያለው፣ የትም የማይገኝ ልዩና ምርጥ ወረቀት ሲሆን የእያንዳንዱ ሰነድ መጠን ከቀድሞ አንድ የኢትዮጵያ ብር ጋር ይቀራረባል። የሰነዱን ምንነት ወይም የድርጅት አድራሻ የሚገልፅ የራስጌ ጽሑፍ ወይም ማህተም የሌለው፣ በላዩ ላይ የተፃፉት ፊደላት ሳይሆኑ እንደ ጽሑፍ በስፋትና በረጅሙ የተደረደሩ የአውሮፓ አሀዞች ነበሩ።

እንደገመትነው ንጉሡ ብቻ እንዲያውቁት የተመሰጠረ ነው። አጣሪው ቡድን የብሔራዊ ባንክ ገዥ ለነበሩት ለአቶ ተፈራ ደገፌ አቅርቦ ስለ ሰነዱ ምንነት ቢጠይቃቸው ምንነቱን ለማወቅ እንዳልቻሉ ገልፀዋል። የሰነዱን ምንነት የሚያውቁ ሰዎች በሃገር ውስጥ ተፈልገው ስላልተገኙ የወዳጅ ሶሻሊስት ሃገር የደህንነት ሰዎች ባደረጉልን ትብብር የስዊዝ ባንክ የሚጠቀምበት ልዩና ምስጢራዊ የባንክ ሂሳብ መግለጫ ሰነድ መሆኑን ለማረዳት ችለናል።

ከዚህ በኋላ ነው እኔና ሻለቃ አጥናፉ ቀርበን "በስዊዝ ባንክ ገንዘብ እንዳስቀመጡ የሚገልፅ ማስረጃ አግኝተናል። ይህንን ስንል ግን እርስዎ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሰውረው ለግል ጥቅምዎ ነው ለማለት ሳይሆን ማንም እንደሚያደረገው ለክፉ ቀን ለሃገርዎ ብለው እንዳስቀመጡ ነው የምናምነው" በሚል ማግባቢያ ቀረብናቸው።

"ግርማዊነትዎ እንደሚያውቁት ከምንጊዜውም እጅግ የከፋ ችግር የኢትዮጵያን ሕዝብ የገጠመው አሁን ነው። በረሀብ እየሞተ ነው። ይህንን ገንዘብ ወደ ሃገር አስመጥተው ለሚወድዎትና ለሚወዱት ችግረኛ ሕዝብዎ ቢለግሱት ለሕዝብዎም ለሃገርዎም ታላቅ ውለታ ነው የሚሆነው።

... እርስዎም በሕዝብዎ ዘንድ የበለጠ እንደተከበሩና እንደተወደዱ ያኖርዎታል። ታሪክዎንም ያሳምርልዎታል" አልናቸው። በጥሞና ካዳመጡኝና ለተወሰኑ ሴኮንዶችም ዝም ብለው ካሰቡ በኋላ "እነጋገርሀ ማለፊያ፣ የእስተዋይና የጨዋ አነጋገር ነው። የተሳሳትከው እኛ ገንዘብ በባዕድ ባንክ አስቀምጠናል ብለህ ማሰብህ ነው። ያስቀመጥነው ገንዘብ የለም።" በማለት ቁርጥ ያለ መልስ ሰጡኝ።

ከዚህ በኋላ ነበር ልዑል ራስ እምሩን እቤታቸው ድረስ ሄደን በስዊስ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ስለመኖሩ ማስረጃ እንዳለን፣ ንጉሡን ይህን ብለን በማግባባትና በልመና መልክ ብንጠይቃቸው ያስቀመጥነው ገንዘብ የለም ብለው ስለካዱ እርስዎ ያማልዱን ብለን የጠየቅናቸው።

ልዑል ራስ እምሩ ለጥያቄያችን መልስ ከመስጠታቸው በፊት በርካታ ጥያቄዎችን ነበር ያቀረቡልን። ከጥያቄዎቹም ጥቂቶቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ። "በስዊዝ ባንክ ገንዘብ ስለመኖሩ ያለን ማስረጃ ምን ያህል አስተማማኝ እንደሆነ፣ ምናልባትም እኛ በስዊዝ ባንክ አለ የምንለው ገንዘብ ቢኖርና ንጉሡ አለ ብለው ቢያምኑ እሳቸውንም ያለአግባብ የበለፀጉና

በሥልጣን የባለጉ ብላችሁ ለፍርድ እንደማታቀርቧቸው ገልፃችሁላቸዋል ወይ” የሚሉና ሌሎችም ነበሩ።

ላቀረብልን ጥያቄዎች ሁሉ እሳቸው ይጠብቋቸው የነበሩ በጎ መልሶችን ከመስጠታችን በተጨማሪ አብዮቱን ሳይቃወሙ እስከ አሁን ሲያደርጉ እንደቆዩት ትብብራቸውን ከቀጠሉ፣ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ አምባገነናዊ ሥልጣናቸውን ትተው የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር በመሆን ለሕግና ለሕዝብ ፈቃድ ተገዝተው ከኖሩና በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ በሙሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰጡ ከሆነ ምንም ነገር እንደማይደርስባቸው በእኛ ስም እርስዎ ቃል ሊገቡላቸው ይችላሉ አልናቸው።


ልዑል ራስ እምሩም እንደ ንጉሡ የሰጡናቸውን መልስ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ ለማሰብ ጥቂት ጊዜ ወስደው ከዚህ የሚከተለውን አሉን። “እኔና ግርማዊነታቸው እንዛመድና አብረን አደግን እንጂ በሀሳብ የምንግባባ ሰዎች አይደለንም። ይህንን አሁን እናንተ ያቀረባችሁት ሀሳብ ከብዙ ጊዜ በፊት እኔ ብቻ ሳልሆን በሌሎችም በመደጋገም በማሳሰባችን አንወደድም።

አሁን እኔ ሄጄ ያስቀመጥከው ገንዘብ ካለ ስጥ ብለው ገንዘብ ስጥ የምትለኝ አንተም ገንዘብ አስቀምጧል ብለህ ብታምን ነው ብሎ የሚጣላኝ ብቻ ሳይሆን የእናንተ ተባባሪ አድርጎ ስለሚመለከተኝ ልረዳችሁ ስለመቻሌ እርግጠኛ አይደለሁም” አሉን።

በክፉ እንዳይጠረጥርዎ ያሰብንላቸውን በጎ ነገሮች ያስረዷቸው። ይህ ወርቃማ እድል እንዳያመልጥህ ብለው ይምከሩልን። ከእርስዎ ሌላ በዚህ ጉዳይ ሊረዳን የሚችል ሰው የለምና ይቸገሩልን አልናቸው። “ቀደም ብላችሁ ለእሱ የነገራችሁትንና አሁን ይህንን ለእኔ ያላችሁኝን ነገር በድጋሚ እፊቱ እኔ ብቻ ሳልሆን ልዕልት ተናኘ ልዕልት ሳራ ባሉበት ንገሩትና ከዚያም በኋላ እኔም የምለው ይኖረኛል።” በሚል ጥያቄያችንን ተቀበሉና እንዳሉትም እሳቸውና ልዕልቶቹ ባሉበት እኔና ሻለቃ አጥናፉ ሆነን በድጋሚ የገንዘቡን ጥያቄ አቀረብን። ንጉሡ ጥያቄያችንን በድጋሚ ሰምተው መልስ ከመስጠታቸው በፊት ለአባታቸው ዙፋንና ታሪክ ሲሉ አባታቸውን በማግባባት ይረዳሉ ተብሎ የተጠሩት ልዕልት ተናኘ ቅድሚያውን በመውሰድ በቁጣ “ገንዘብ በስዊዝ ባንክ ለማስቀመጣችን ማስረጃ አለህ?” ብለው ስለጠየቁኝ በአክብሮት ማስረጃ እንዳለንና ይህንንም ግርማዊነታቸው እንደሚያውቁ ገለፅኩ።

ልዕልት ተናኘ ቁጣቸውን በመጠቀል፣ “ሺህ ማስረጃ ቢኖራችሁም እናንተ የአባቴ ወራሽ ልትሆኑ አትችሉም። ልጆች አለናቸው፤ በኃይላችን እንጠቀማለን ብትሉ ከውጭ ጠበቃ ገዝተን እንሞግታችኋለን!” አሉን። ልዕልት ሳራም ተጨምረው “አባታችን ገንዘባቸውን ለልጆቻቸው ማውረስ መብታቸው ነው። ይህንን መብታቸውን ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም!” በሚል ጭቅጭቅና ጩኸት ንጉሡንም፣ ልዑል ራስ እምሩንም እናናግር ብለው በብርቱ አወኩን።

እንድንደማመጥ ለምኜ እኛ ከእናንተ የአባታችሁን ውርስ ለመጋራት አይደለም እዚህ የጠራናችሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየሞተ ስለሆነ የሚወደንና የምንወደው የሚሉትን ሕዝባቸውን ከሞት ለማዳን በባንክ የተቀመጠ ገንዘባቸውን በአባትነታቸውና በመሪነታቸው እንዲለግሱት ነው ስል፣ ንጉሡም በድንገትና በቁጣ “ሻለቃ ከዚህ በፊት ጠይቀህኝን እኛ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሰውረን የትም ያስቀመጥነው ገንዘብ የለም ብለን ነግረንሀል” በማለታቸው ልዑል ራስ እምሩ ምንም ሊናገሩ ስላልቻሉ የገንዘብ ጥያቄ ጉዳይ በዚህ አበቃና እንደሚታወሰው እንቢታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተገለፀ።



አፄ ኃይለሥላሴ

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ሥልጣን ለሕዝቡ እንዲሰጡና በሕግ ተገድበው ዙፋናቸው ላይ እንዲቀመጡ ቢጠየቁ "ሕዝቡ ለእንደዚህ ያለው ሥልጣንና የፖለቲካ ወግ የበቃ አይደለም" የሚል ነበር መልሳቸው። የዚያን ጊዜውን መልሳቸውን እንቀበልና እንዳሉትም ምናልባትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተጠየቀለት ሥልጣን አልበቃም እንበል።

በ1966 ዓ.ም የካቲት እሳቸው ለሕዝቡ ለዚያ ሥልጣን አልበቃም እንዳሉት ሕዝቡ በፈንታው ፊውዳላዊ የግፍ አገዛዝ በቃኝ ብሎ በአመፅና በሥልጣናቸው የባለጉበትን፣ ያለአግባብ የበለፀጉትን ባለሥልጣኖቻቸውን በቁጥጥር ስር አድርጎ ለፍርድ ለማቅረብ የተዘጋጀበትና የእሳቸውም መለኮታዊ ሥልጣን ሊያከትም በተቃረበበት ጊዜም ሥልጣኔ አይነካም፣ በባዕድ ሃገር ያስቀመጥኩት ገንዘብም የባዕድ ሲሳይ ይሁን እንጂ አልሰጥም አሉ።

ከዚህ በኋላ ነበር ሕዝቡን በመደለል ያለአግባብ በመበልፀግና በፖለቲካ ሥልጣናቸው በመባለግ ተወንጅለው ከታሰሩት ባለሥልጣኖቻቸው በፊት ለመርማሪው ኮሚሽን እንዲቀርቡ፣ ብሎም የእሳቸው ሥልጣንና እንዲሁም የዙፋናቸው ህልውና በፍርድ እንዲወሰን ለማድረግ ያቀድነው።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው መርማሪው ኮሚሽን ሥራውን ጀምሮ እንደ ባለሥልጣኖቹ የሥልጣን ደረጃና የወንጀል አይነት የተለያዩ ፍርድቤቶች ተቋቁመውና ዳኞችም ተሰይመው ነበር። መርማሪው ኮሚሽን ለምርመራውም ሆነ ለፍርዱ የሥርዓቱ ቁንጮ ለሆኑት አፄ ኃይለሥላሴ ቅድሚያውን እንዲሰጥ፣ ድርጊቱና ሂደቱም ለሰው ልጅ ሁሉ መቀጣጫና ትምህርት ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ ይካሄድ ዘንድ የምርመራ ኮሚሽኑን የጠየቅነው።

እኔና ሻለቃ አጥናፉ የጎበኘናቸውና ያነጋገርናቸው ሦስት ጊዜ ነው። አንደኛው፣ ከሥልጣናቸው ወርደው አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ወደ ተዘጋጀላቸው ማረፊያ በመጡ ዕለት፣ ሁለተኛውንና ሦስተኛው በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ ስንጠይቅ ።

ደርጉ መሥሪያ ቤቱን ከአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሲያዛውር ንጉሡን ጨምሮ እስረኛ ባለሥልጣኖችም ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተዛውረዋል። ከታሰሩት ባለሥልጣኖች ብዙዎቹ የጤና ችግር እንደነበረባቸው ሁሉ በሰኔ

ወር 1967 ዓ.ም ንጉሡም በፊኛና በሽንት መሽኛቸው የጤና መታወክ ደርሶባቸዋል የሚል ሪፖርት ስለቀረበልን ሐኪማቸውን ፕሮፌሰር አሥራትን ጠርተን በማነጋገር ስለ ሁኔታቸው ከተረዳን በኋላ ከማረፊያቸው ወደ ሆስፒታል ሄደው አስፈላጊው ህክምና ይደረግላቸው ዘንድ በሙያው የላቁ ሐኪሞች ከውጭ እንዲመጡ በተጠየቀው መሠረት ታዝዞ መታከማቸውን ጤንነታቸው በመልካም ሁኔታ ላይ እንደነበረ አስተውለናል።

በነሐሴ ወር ከዚህ በፊት የታወቀው የጤና ችግራቸው ያገርሸ ወይም ሌላ ዛሬ የማላስታውሰው እንደገና ስለመታመማቸው ተነግሮን እንደተለመደው ተገቢው የጤና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ከታዘዘ በኋላ ማረፋቸው ስለተነገረን በብዙሃን ማሰራጫ ሕዝቡ እንዲያውቀው ተደረገ።

ነሐሴ 21 ቀን ጠዋት አቡነ ቴዎፍሎስ ከሁለት ረዳቶቻቸው መንፈሳዊ አባቶች ጋር በመሆን መጥተው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ፀሎተ ፍትሐት ተደርጎ የቀብራቸው ሥርዓት እንዲከናወን ስለጠየቁ ከደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር መክሬ ከሰዓት በኋላ ውሳኔው ይገለፅልዎታል ብዬ አሰናበትኳቸው።

የደርግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ላይ የቀብራቸውን ሁኔታ በተመለከተ መደረግ ስላለበት ነገር ስንወያይ ፓትሪያርኩ ያቀረቡትን ሀሳብም ተወያይተንበት ከብዙዎቹ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የቀረበው ሀሳብ፤

1ኛ/ ንጉሡ ስደተኛ እንጂ አርበኛ ስላይደሉ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ፍትሀትም ሆነ ቀብር ሊደረግላቸው እንደማይገባ፤

2ኛ/ ከሥልጣናቸው ከወረዱ በኋላ እንደ አንድ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊ ግለሰብ እንጂ እንደ ንጉሥ መታዬት እንደሌለባቸው፤

3ኛ/ አፅማቸው ማረፍ ያለበት እዚሁ ባረፉበት አቅራቢያ በባእታ ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን፤

4ኛ/ ፍትሀትን በተመለከተ ምንም ዓይነት ወይም የተለየ የዜና መግለጫ ሳይሰጥ አቡኑ ከጥቂት ካህናት ጋር የፍትሀቱን ሥርዓት እንዲያከናውኑ ተወስኖ በዚሁ ሁኔታ ተፈፀመ።

አብዮታዊው መንግሥት ከፈረሰና ኢትዮጵያ የወያኔ ቅኝ ከሆነች በኋላ፤ ወያኔ በሃገር ላይ የፈፀመውን ክህደት፣ የባዕድ ምንደኝነት፣ ፀረ-አንድነት፣ የመገንጠልና የማስገንጠል ወንጀሉን የከለለና ከወንጀለኛነቱ የሚያፀዳው እየመሰለው አብዮታዊያንንና አብዮትን ለመኮነን ብሎ አውርቶ ያስወራቸውን ብዙ ወሬዎች ሰምተናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት እውነት፤ ደርግ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሕይወት ላይ ምንም አይነት ውሳኔ ያልሰጠ መሆኑን ነው።

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የጉልታዊውን ሥርዓተ ማህበር ላዕላይና ታህታይ መዋቅር ስለማፈራረስ

በዚህ ታሪክ መቅድም ስለ አብዮታችን ባህሪና ዓላማ ስገልፅ ከኢትዮጵያ ብዙ ቀድመው በአውሮፓ የተካሄዱት ህብረተሰባዊ ወይንም የሶሻሊስት አብዮቶችን ፈለግ ለመከተል ካለመቻሉም በላይ ለጊዜው አስፈላጊም ስለአልነበረ ኢትዮጵያን በመሰሉ ታዳጊ አገሮች ለማህበራዊ ለውጥ ይበጃል ተብሎ በታመነበት በአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርህ ለመመራት የሶሻሊስት አብዮት ለማካያሄድ በዕድገት ኋላቀርነት የተጓደሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት እንዲቻል የተመራ ትግል ነበር ብያለሁ።

በተጨማሪም ደርግ ከተቋቋመ በኋላ ከሰኔ 1966 ዓ.ም ጀምሮ አብዮቱ የሚጠይቀውን አጣዳፊ ተግባሮች ማከናወን በአብዮቱ ማግሥት የየዕለቱ ቋሚ ተግባራችን ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜያችንን የሰጠነውና አብይ ትኩረታችን የነበረው፤ የአብዮቱን ሂደት በሦስት ክፍለ ጊዜ በመከፋፈል፤ የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ በሚል ዕቅድና የትግል ስትራቴጂ በመንደፍ ነበር ማለቴም የሚታወስ ነው።

የአጭር ጊዜ ዕቅድና የትግል ስትራቴጂ የምንለው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ የምንለውን አብዮት በመጀመር በቅድሚያ የሚፈለጉትን ቅድመ ሁኔታዎች የምናከናውንበትን ወይንም የምናመቻችበትን የትግልና የሽግግር የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው።

በኢትዮጵያ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የመጀመሪያ ምዕራፍ ወይንም የሽግግር ጊዜ ክልል ውስጥ የሚከናወኑ መሠረታዊ የሆኑ ሁለት ተግባሮች ነበሩ።

ከእነዚህ አንደኛውና የመጀመሪያው የአሮጌውን ጉልታዊ ሥርዓተማህበር ላዕላይ መዋቅር ማፈራረስና በፍራሹ ላይ አብዮቱን ለዘለቄታው የሚመራ የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም በፓርቲው መሪነት የአዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት አካላትና የአብዮቱን ማህበራዊ መሠረቶች መገንባት ሲሆን፤

ሁለተኛውና ተከታዩ ተግባር የጉልታዊውን ሥርዓተማህበር ታህታይ መዋቅር ወይንም የኢኮኖሚውን ዋና ዋና መሠረቶች በማፈራረስ የግል ይዞታዎችን ወደ ወል ይዞታነት ደረጃ በደረጃ ማዞር ወይንም መለወጥ ነው።



ሀደይ መጽሔት

በዚህ በአብዮት ጅምርና በመጀመሪያው ምዕራፍ በማፍረስ ረገድ በተወሰዱት ርምጃዎች አብዮታችን የቱን ያህል ፈጣንና ቀልጣፋ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ ደረጃ የተወሰዱት ርምጃዎች ምን እንደሚመስሉ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ዕድገት የሚያስገኙትን ቁሳዊ ፋይዳ አንባቢ ይረዳ ዘንድ ከ1966 ዓ.ም እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ የትግላችንን የሦስት ዓመታት አብዮታዊ ፍሬዎች በመጽሐፉ የመጨረሻ ገፆች አንባቢ እንዲመለከታቸው ተዘርዝረዋል።

## ክፍል ፲

# መሬት ለአራሹ

# ምዕራፍ አስራ ሦስት


# የገጠሩን የእርሻ መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ የሚያደርገው አዋጅ ጥናትና መሰናዶ

የገጠሩን የእርሻ መሬት የይዞታ ለውጥ፣ አስተዳደር ወይም አዋጅ ወዘተ ማለት ሲቻል ለዚህ ርዕስ መሬት ለአራሹ የተሰኘውን ርዕስ የመረጥኩት የኢትዮጵያን አርሶ አደሮች የአያሌ ምእት ዓመታት የመሬት ጥያቄ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ታሪካዊ መልስ ባገኘበት በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት የገጠሩን መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ የሚያደርገውን የመሬት ለአራሹ አዋጅ በተግባር የመተርጎም ተልዕኮ በነበረው በእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ዘምተው አርሶ አደሩን ከማይምነት ለማላቀቅ ቀለም ሲያስተምሩ ፣ በፖለቲካ ሲያነቁና ብሎም መሬት ሲያከፋፍሉ በፀረ-ሕዝብ ፊውዳሎች የተገደሉትን፣ በሚኖሩበት ዳስ ሌሊት እንደተኙ በእሳት የጋዩትን፣ በደራሽ ውሃ የተበሉትን ወዘተ ወጣቶች ለማስታወስ ነው።

የእኔ ትውልድ የሆኑት አብዮታዊ ወጣቶች በሰሌዳ አደባባይ ይዘውት ይውጡ እንጂ በኢትዮጵያ የገጠር የእርሻ መሬት ጥያቄ የአሮጌውን ጉልታዊ ሥርዓት እድሜ ያህል የቆየ ጥያቄ ነው። በኢትዮጵያ የጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር የመሬት ይዞታ አስተዳደር ሕዝቡን ሲያስለቅስ፣ ሲያታግልና ሲያጋድል የኖረ ጥያቄ ነው። ሆኖም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት ደረጃ ለጥያቄው ከሞላ ጎደልም ቢሆን ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ መልስ ለመስጠት የተሞከረው በቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ነው።

አፄ ቴዎድሮስ ቀዳሚ ዓላማቸው አድርገው ከተነሱበት የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት መልሶ ከመገንባት ዓላማቸው ጋር ሌላው ያተኮሩበት ታላቅ ብሔራዊ ጉዳይ የመሬት አስተዳደር ለውጥ በማድረግ የኢትዮጵያን አርሶ አደሮች ሕይወት በማሻሻልና አስተዳደሩን በማቃናት አገሪቱን ወደ ዘመናዊ የኢኮኖሚ እድገት ለመምራት ሲሉ የእድገትና የመሻሻል ፀር ከሆኑት ከየክልሉ መሣፍንቶች ጋር በመቀጣቀጥና ከካህናቱ ጋር ክፉ ቅራኔ ውስጥ በመግባት ሕይወታቸውን ከሰጡበት ምክንያት አንዱ መሬት ወይም የደሀው የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ነበር።

ከቴዎድሮስ በኋላ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ከዚህ ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸውን አብዮታዊያን ወጣት ትውልድ ጨምሮ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት ይቻላል፤ ገጠሬው ወይም ገበሬው ብቻ ሳይሆን ሕይወቱ ከግብርናው ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረው ከተሜው ጭምር በኢትዮጵያ የገጠሩን የእርሻ መሬት ይዞታ መሻሻል ወይም ለውጥ ሲመኝና ሲለምን ኖሯል።



የኢትዮጵያ የገበሩ ህይወት ይህንን ይመስላል

በኢትዮጵያ የሕዝባዊው አብዮት ጠረን ሊሸተን ቀርቶ አብዮት የሚባል ነገር እስከ ስሙም በማይታወቅበት ጊዜ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገራችን የመሬት ስሪት ወይም ይዞታ ትክክል እንዳልሆነ ማንም ሳይነግረው ከኑሮውና ከሕይወቱ ምሬት ስለተረዳው ነበር የመሬት ይዞታ ለውጥ ፅኑ ፍላጎት ያደረበት።

ይህንን ለማለት የደፈርኩት ደርግ ተቋቁሞ ትግሉን ከጀመረበት ከመጀመሪያው ዕለት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ምን አይነት መንግሥት ያስፈልጋታል? በምን አይነት የፖለቲካ ሥርዓት ወይም የእድገት አቅጣጫ መመራት አለባት? የሚል ጥያቄ አንስተን መወያየት በጀመርንበት ጊዜ በቅድሚያ የመሬት አዋጅ አውጀን የኢትዮጵያን አርሶ አደር ከጉልተኞች ቀንበር ነፃ ካወጣነው በኋላ ነው ስለ መንግሥት ዓይነትና ስለ ፖለቲካ ሥርዓት መወያየት ያለብን በማለት አመራር ላይ ባለነው አካላት ላይ ታላቅ ግፊት ያደረጉብን ጠቅላላው የደርግ አባላት ነበሩ።

በኢትዮጵያ የመሬት ይዞታ ለውጥን በተመለከተ የደርግ አባላቱ በሙሉ የማያዳግም ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋል የሚል ጠንካራና የጠራ አቋም ያላቸው ከመሆኑም ሌላ ለውጡም አሁን ዛሬ ይሁን የሚሉ ነበሩ።

ደርግን እንደ አገራችን የጥድ ቤት ማገርና ግድግዳ ካስተባበሩት ብዙ ምክንያቶች አንዱና የመጀመሪያው የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ነበር ለማለት ይቻላል።

ጉልታዊውን የመሬት ይዞታ ለመለወጥ የሚያስፈልገን አዋጁን በጥቂት የወረቀት ገጾች ማርቀቅ ብቻ ሳይሆን፣ እንዴት እንደሚለወጥ፣ በምን አይነትና መጠን እንደሚለወጥ፣ አጠቃላይ የገጠሩን መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የገጠሩን መሬት ባለቤት ወይም ባለ ይዞታ የምናደርገውን ገበሬ አደረጃጀትና ብሎም አብዮታዊ ድሉን እንዳይነጠቅ ማስታጠቅን ወዘተ የመሳሰሉ ብዙ ጥናትና መሰናዶ እንዲሁም ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግ ስለነበር የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት በፈረሰ ማግስት በ1966 ዓ.ም ሐምሌ ወር መገባደጃ ላይ ነበር ከማናቸውም ጉዳይ በፊት ቀድሞ አብዮታዊ የመሬት ይዞታ ጥናት እንዲጀመር የተደረገው።

ጉልተኞችና የመሬት ከበርቴዎች ከወዲሁ ለአመጽ እንዳይጋበዙብን በማለት የመሬት ይዞታ ለውጥ ይካሄድ የነበረው በጥብቅ ምስጢር ነበር።

ጥናቱን የሚያጠኑ ባለሙያዎች መካከል ብዙ ያከራከሩ ጉዳዮች ስለነበሩ ከጠበቅነው በላይ ረዘም ያለ ጊዜ ወስዷል። በገጠር የእርሻ መሬት የዞታ ላይ በሚደረገው ለውጥ የአስተዳደርና የመሬት መጠን፣ ገበሬውን ከማደራጀት ጋር የጉልተኞችንና የገባር ገበሬዎችን ግንኙነት ለአንዴና ለመጨረሻ የሚቆርጠው ወይም የጉልታዊውን ሥርዓት ማህበር ኢኮኖሚያዊ መሠረት የሚንደው የመሬት አዋጅ ጥናት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከተመረመረና ከፀደቀ በኋላ ነው ለደርጉ ጉባዔ ቀርቦ የመጨረሻውን ይሁንታ የሚያገኘው።

ጥናቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ስንመለከተው ብዙ አከራክሮ እንዲሻሻል ከተመለሰ በኋላ፣ ተሻሽሎ ተብሎ ለሁለተኛ ጊዜም የቀረበው ጥናት እንዲሁ ብዙ አከራክሯል።

ከአከራከሩን መሰረታዊ ጉዳዮች ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፡-

1ኛ/ አዋጁን እንዲያስፈፅሙ በእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ የሚሰማሩት ወጣት ተማሪዎች ከእድሜ ለጋነታቸው ባሻገር ምንም አይነት የሥራ ልምድ የሌላቸው ከመሆናቸው አንፃር ለሚላኩበት ስራ ብቃታቸው፣ ከሥነ-ሥርዓት ጉድለትና ከአፍራሽ የፖለቲካ ዝንባሌ አኳያ በገበሬው ሕብረተሰብ ውስጥ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ የሚል የስጋት ጥያቄዎች፣


2ኛ/ ለእያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ እና በይዞታ እንዲሰጥ የተተመነው የመሬት መጠን ነበር። አብዛኛው የምክር ቤቱ አባላት ወይም ሚኒስትሮች መሬት ከሚወሰድባቸው ጉልተኞችና የመሬት ከበርቴዎች ብቻ ሳይሆን አንድ ጋሻና ከዚያም በላይ የቀድሞው መንግሥት ለብዙ የጦር ኃይሉና የፖሊስ ሠራዊት አባሎች ያደለ ስለሆነ ከእነዚህ ኃይሎች የሚመጣው ተቃውሞ የመሬት አዋጁን ብቻ ሳይሆን የአብዮቱንም ደህንነት ሊያሳስብ ስለሚችል ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚታደለው የመሬት መጠን ከሁለት ጋሻ እንዳያንስ የሚል አስተያየት ነበራቸው።

ዘማቹን ወጣት በተመለከተ የነበረው ግምትና በስጋት ላይ የተመሠረተ አስተያየት ታሳቢነቱ አግባብ ቢሆንም የመሬቱን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ፣ መሬት ለአራሹ ካለው ወጣት ሕብረተሰብ የተሻለ ይህንን ተልዕኮ የሚቀበል ኃይል አልነበረም።

ስለሆነም መፍትሄው የእድሜ ብስለትና የሥራ ልምድ ባላቸው የአገሪቱ መምህራንና በአብዮታዊ ሠራዊት መኮንኖች በማጠናከሩ እርምጃ ተስማማን። ሁለተኛውን አከራካሪ ነጥብ ወይም ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚሰጠውን የእርሻ መሬት መጠን በተመለከተ፣ በኢኮኖሚያዊ ስሌትም ሆነ ከመሬት ቁጠባ አመለካከትና ከገበሬው አቅም አንፃር ሲታይ ሁለት ጋሻ የእርሻ መሬት ለእያንዳንዱ ገበሬ መስጠት እንደማይቻል ከብዙ ክርክር በኋላ ለመስማማት ተቻለና እጥኚ ባለሙያቹ የመጨረሻ ትልቁን የመሬት መጠን ወይም ጣራውን ከአንድ ጋሻ ጀምረው ከዚያ በመለስ የተለያዩ አማራጮችን ከመጨረሻው መጠን ወይም ወለል ጋር አጥንተው እንዲያቀርቡልን ውሳኔ ተሰጥቶ ጥናቱ ለሦስተኛ ጊዜ እንዲመለስ ሲደረግ፣ በዚያም ጊዜ አንድ ጥማድ በሬ ያለውና ራሱ አርሶ የሚበላ ብርቱ ገበሬ በአንድ ዓመታዊ የእርሻ ወቅት ማረስ የሚችለው የመሬት መጠን ምን ያህል ሄክታር እንደሆነና አባወራው ገበሬ ራሱን ጨምሮ አምስት ቤተሰብ ያለው ቢሆን፣ የዓመት ዘሩን የዓመት ጉርሱን፣ የዓመት ልብሱንና ወዘተ የሚያስፈልጉትን ለማግኘት ለአጠቃላይ ፍጆቱ ማምረት ከሚችለው ምርት መጠን ጋር አገማምቶ መጠኑን በኪሎ ክብደትና እንዲሁም በገንዘብ አይነት እንዲያቀርቡልን መመሪያ ሰጠን።

በመጨረሻ በወጣው የጥናት ረቂቅ ባለሞያዎቹ ያቀረቡልን አማራጭና ለአማረጮቹም የሰጡት ዝርዝር ምክንያቶች ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ያስቻሉን መፍትሄዎች ሆነዋል።

አንዱ ብርቱ ወይም ትጉህ ሰራተኛ ነው የሚባል ገበሬ በአንድ ጥማድ በሬ በአንድ ዓመታዊ የእርሻ ወቅት ሊያርስ የሚችለው የመሬት መጠን ከፍተኛው ሁለት ሄክታር እንደሆነ፣ ራሱን ጨምሮ አምስት ቤተሰብ ያለው ገበሬ ከሚያርሰው ሁለት ሄክታር መሬት የሚያመርተው ምርት ለዘር፣ ለዓመት ጉርሱና ልብሱ በጠቅላላው ለምግብ ፍጆታቸውና ለሌሎች ፍላጎታቸው በቂ ስለመሆኑ አረጋገጡልን።




ለመሬት አዋጅ የተደረገው የድጋፍ ሰልፍ

የምክር ቤቱ አባሎች በበኩላችን መሬቱ ሁሉ አንድ አይነት ሳይሆን፣ ለምና ጠፍ ስላለ፣ የቤተሰቡም ቁጥር ባለሙያዎቹ ካቀረቡልን መጠን እጥፍ ሊሆን ስለሚችል ገበሬውና ቤተሰቡ ወደ ዘመናዊ እርሻ ከመሸጋገራቸው በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ያላንዳች እጥረት በተትረፈረፈ ምርት ደስተኛ ኑሮ ይኖሩ ዘንድ፣ የመሬቱ አይነትና የቤተሰቡ ብዛት ለመሬት ግምት ዋና መሠረት ሆነው ለእያንዳንዱ አርሶ አደር በነፍስ ወከፍ የሚሰጠው የእርሻ መሬት ዝቅተኛው መጠን ወይም ወለሉ 2 ሄክታር ሆኖ ከፍተኛው መጠን ወይም ጣራው 10 ሄክታር እንዲሆን ተወሰነ።

ይህ ውሳኔ በሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት ሙሉ ድምፅ ከፀደቀ በኋላ ለደርግ ጉባዔ ለመጨረሻው ይሁንታ በቀረበ ጊዜ፣ በደርጉ አባላት ዘንድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥናቱ ሲመላለስ እንደነበረና የደርጉ ተወካይ የሆንነው እኔና ሻለቃ አጥናፉ በተሳተፍንበት የጦፈ ክርክር የተደረገበት ስለመሆኑ ግንዛቤ ስለነበረ ስለ አዋጁ መታወጅ ወቅታዊነት ዘገየ ከማለት በስተቀር ከዚህ ያለፈ አንዳች ጥያቄም አልነበረም።

ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚታደለው መሬት መጠንም ሙሉ ስምምነት የነበረ በመሆኑ አዋጁን ተግባራዊ ከማድረግ የአፈፃፀም ጥያቄ ላይ በመወያየት ብቻ ታሪካዊው የመሬት አዋጅ ፀድቆ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም ታወጀ።

በኢትዮጵያም ሆነ በተቀረው ጠቅላላው ዓለም የአሮጌው ወይም ፊውዳል ሥርዓተ ማህበር ህልውና በገጠሩ የእርሻ መሬት ላይ የሚያካሂደው አሮጌው የግብርና ሥልተ ምርትና በገባሩ ደሃ ገበሬና በጉልተኛው መካከል ያለው የምርት ግንኙነት ነው።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር ሞቶ የተቀበረው የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም ነው። በዚህ የሕብረተሰብ የእድገት ደረጃ አብዮት ወይም የመደብ ሹም ሽር ማለትም ከአሮጌ የምርት ግንኙነት አኳያ ይኸው ነው።

## ምዕራፍ አስራ አራት

# እድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ

የገጠሩን የእርሻ መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ የሚያደርገውንና የጉልታዊውን ሥርዓተ ማህበር ታህታይ መዋቅር ወይም ዋና የኢኮኖሚ መሠረት የሚያፈራርሰውን አብዮታዊ እርምጃ ለመውሰድ ከተደረጉት ጥናትና መሰናዶዎች አንዱ የመሬት አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀና የተደራጀ መጠነ ሰፊ የሰው ኃይል በመላው የኢትዮጵያ ገጠር ማሰማራት ወይም ማዝመት ነበር።

የዘመቻው መጠሪያ፣ ዓላማና ተግባሩ በአንድ ቃል ሲጠቃለል፣ እድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ በመባል ይታወቃል። የዘመቻው ስም እንደሚያስረዳው የዘማቹ ተልዕኮ፣ የመሬት አዋጁ ከመታወጁ በፊት ከጭቁኑና ምዝብሩ ደሀ የገበሬ ሕብረተሰብ መካከል በመገኘት አርሶ አደሩን ስለሚጠብቀው የመደብ ትግል፣ በትግሉም ስለሚቀዳጀው ድል፣ በጠቅላላው ስለ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱና በተለይም አብዮታዊው የመሬት አዋጅ ለኢትዮጵያ ገበሬ በተለይና በአጠቃላይ ለአገሪቱ ማህበራዊ እድገት የሚያስገኘውን ፋይዳ በማስረዳት፣ ለገበሬው ሕብረተሰብ የፖለቲካ ንቃት በመስጠት፣ በዚሁ የጊዜ ክልል ውስጥ ተማሪው፣ ምሁሩና ወታደሩ በገበሬው መኖርያ ሰፈር እስከተገኙ ድረስ ገበሬውን ከነቤተሰቡ ከማይምነት ጨለማ በማውጣትና በመጨረሻም የመሬቱ አዋጅ ሲታወጅ፣ በአዋጁ ድንጋጌና መመሪያ መሠረት በጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር የጉልተኞችና የመሬት ከበርቴዎች ገባር፣ ጢሰኛና ሎሌ ወዘተ ለነበረው ድሀ በነፍስ ወከፍ እንደ አካባቢው የሰው ብዛትና ተፈጥሮአዊ ተጨባጭ ሁኔታ የእርሻ መሬት ማከፋፈል ነው።

ገበሬው የማንም ተገዥ ሳይሆን የራሱ ጌታ በመሆንና ምርቱን በማሳደግ ከድህነት እንዲላቀቅ፣ የራሱን ማህበራዊ ደህንነትና ሰላም እንዲያስከብርና አብዮታዊ ድሉን በፀረ-ሕዝቦች ሳያስነጥቅ ለመጠበቅ በሚያስችለው ሁኔታ በማህበር ማደራጀት ነበር።

በደርጉ የእቅድ ኮሚቴ ውስጥ አቅደን የነበረው፣ የመሬቱን አዋጅ በገጠሩቱ ኢትዮጵያ ■ምቶ ተግባራዊ እንዲያደርግ ያሰብነው ወታደሩን ነበር። በቅድመ አብዮት አገራቸውንና ወገናቸውን መውጋት የጀመሩት ገንጣይና አስገንጣዮች የሚያደርሱብንን ጥቃት እያጠናከሩ ከመሄዳቸው በላይ የሶማሊያና የሱዳን መንግሥታት የጦር ኃይሎች በጋራ ድንበራችን ላይ መጠነ ሰፊ ጦር ማከማቸትና በዚሁ የጊዜ ክልል ውስጥ የአሜሪካኖቹ ኒው ዮርክ ታይምስ ወርሃዊ መጽሔት ላይ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ካርታ በመጽሔቱ ሽፋን የፊት ገፅታ ላይ ኢትዮጵያ ከሰሜንና ከምሥራቅ ክልሎቿ ዳርቻ የተቀጣጠለ ታላቅ የሰደድ እሳት እያጋያት ወደ መሀሉ ክልል ሲያመራ ዓይንን በሚስብ ሁኔታ ስለው ከካርታው ግርጌ፣ "የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መሪዎች ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነቷን ወይም ሶሻሊዝምን መምረጥ



ይገደዳሉ” በማለት ጦርነት እንደታወጀብን ስለ አስገነዘቡን፣ በመከላከያ ሠራዊት ፋንታ ለመሬት አዋጁ ተግባራዊነት ከሠራዊቱ መካከል ልናገኝ የቻልነው በጣም አነስተኛ ቁጥር ነበር።

ስለሆነም ሌላው አማራጭ ከማንም በፊት የኢትዮጵያን ጭቁን ገበሬ ወክሎ ‘መሬት ለአራሹ’ የሚል ሰሌዳ ይዞ አደባባይ ከወጣው ወጣት የሕብረተሰብ ክፍል የተሻለ ኃይል አልነበረም።

በተወሰኑ የመከላከያ ሠራዊቱ አባላትና በአገሪቱ ጠቅላላ መምህራን እየተመራ ወጣቱ እንዲዘምት በመንግሥት በተጠየቀ ጊዜ አብዛኛው ወጣት ፈቃደኛና ደስተኛ ቢሆንም ወጣቱን የሕብረተሰብ ክፍል የማይወክሉ ጥቂቶች ዘመቻውን ተቃዋሚ ሆነው በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዘመቻው የተዘጋጀውን ብዙሃኑን ወጣት ማወክ ጀመሩ።

እነዚህ ወጣቶች በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ውስጥ የበቀሉ፣ ተማሪውን ሲያሳስቱና ሲከፋፍሉ ቆይተው ማህበሩን ካፈረሱ በኋላ በድህረ አብዮት ለይቶላቸው ከግራ ቀደምትነትና ከሥርዓተ አልበኝነት አቋማቸው ተስፈንጥረው አብዮቱን ለመቃወም በአምስተኛ ረድፍ የተሰለፉና በኋላም ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ በጠራው ቡድን የተመሩ ናቸው።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው የመሬት አዋጅ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ በሚመከርበት ጊዜ ከሚኒስትሮቹ አብዛኛዎቹ፣ መንግሥቱን የሚቃወም ተማሪ በገበሬው ላይ ችግር እንዲፈጥር እንዴት እንልካለን በሚል ስጋት የተሚገቱት በእነዚህ በፀረ-አብዮት ወጥመድ ውስጥ በገቡ ጥቂት ተማሪዎች ምክንያት ነበር።

ዘመቻውን ከሚቃወሙ የኢሕአፓ ጀሌ ወጣቶች በተለይም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበሩትን “በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያ አስፈሪ የጨለማ ዘመን መሬት ለአራሹ ብሎ አደባባይ የወጣ አብዮታዊ የወጣት ትውልድ አካል ሆናችሁ እንዴት ዘመቻውን ትቃወማላችሁ?” ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ‘የሰጡን መልስ፣ የኢሕአፓን አቋም የሚያንፀባረቀውን፣ “በመሬት ለአራሹ ሰበብ ደርግ ወጣቱን ወደ ገጠር የሚልከው የራሱን ሥልጣን ለማጠናከር አቅዶ ስለሆነ ሕዝባዊ መንግሥት ካልተቋቋመ በስተቀር የመሬቱ አዋጅ አስፈላጊ አይደለም፣ እኛም አንዘምትም” የሚል ነበር።

እዚህ ላይ የሚያስገርመው ገጠመኝ፣ ደርግ በተቋቋመ ማግስት አባላቱ “በመንግሥት አይነትና ምርጫ ላይ መወያየቱን ትተን አጣዳፊ የመሬት አዋጅ እናውጅ” ሲሉ፣ ኢሕአፓና ጀሌዎቹ ደግሞ “ከሕዝባዊው መንግሥት ምስረታ በፊት የመሬት አዋጅ አያስፈልግም” ማለታቸው ነው።

ይህንን ጉዳይ በተመለከት የደርጉ ጉባዔ በሚገባ ተወያይቶበት የወሰደው አቋም (ሕዝባዊ መንግሥት የአብዮቱ የቅርብ ጊዜ የትግል ስልት ግብ አንዱ ስለሆነ በመርህ ደረጃ ከዚህ ቡድን ልዩነት የለንም።



ዕድገት በሕብረት ክተት ላይ

ልዩነታችን ሕዝባዊ መንግሥት እንዴትና መቼ በሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ሕዝባዊውን መንግሥት የሚያቋቋሙት የሰፊው ሕዝብ ግምባር ቀደም ክፍል የሆኑት አምራቾቹ የሠራተኛውና የገበሬው መደብ በቅድሚያ መደራጀት አለባቸው።

እነዚህ ሁለቱ ወሳኝ መደቦች የሚደራጁት የጉልታዊ ሥርዓተ-ማህበር ላእላይና ታህታይ መዋቅር ከፈራረሰና፣ አሮጌው የምርት ግንኙነት ከተበጣጠሰ በኋላ ሥርዓቱ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ነው ሕዝባዊ መንግሥት ወይም አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ሊመሠረት የሚችለው።

የጉልታዊው ገዥ መደብ ቁንጮ የነበረው ዘውድ መገርሰስ ጥቂት ቀንደኛ አባላቱ በቁጥጥር ስር መዋል ብቻ የጉልታዊ ሥርዓት ማህበራዊ መሠረትና ጠቅላላ እክቱ ፈረሰ ማለት ካለመሆኑ ባሻገር፣ ሰፊው ሕዝብ አልነቃም፣ አልተደራጀም፣ አልታጠቀም፣ የአሮጌው ሥርዓት አራማጅ ኃይሎች በፖለቲካና በኢኮኖሚ ኃይላቸው በጥንካሬ እየታገሉን ባሉበት ጊዜ ከእውነተኛ የአብዮቱ ወገኖች መካከል ሕዝባዊ መንግሥት ዛሬ አሁን የሚል ካለ ሳይንሳዊ የሆነ ምክንያቱን ይዞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊትና በዲሞክራሲው መድረክ ላይ በግልፅና በገሀድ ሊከራከረን ሲገባ የኢትዮጵያን ገበሬዎች የአያሌ ምዕተ ዓመታት ዲሞክራሲያዊ የመሬት ጥያቄ መልስ እንዳያገኝ ገበሬው እንዳይታጠቅና እንዳይደራጅ የማድረግ መብት የለውም።

በዚህ አኳያ የሚመጣ ጥያቄ የአምስተኛ ረድፎች የአብዮት ቅልበሳ ጥያቄ ስለሆነ ዘመቻው መቀጠል ነው ያለበት ሲል ወሰነ። በዚህ ውሳኔ መሠረት ዋናው ኃይል ወጣቱ ና መምህራኑና ወታደሩ በመሪነትና በአስተባባሪነት የተካተቱበት 60,000 ዘማቾች የሚዘምቱበት፣ አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ በደርግ ተወካይ በሚመራው የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ጠቅላይ መምሪያ ለወራት ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ታህሳስ 12 ቀን 1967 ዓ.ም ዘመቻው ታውጆ በታላቅ በዓልና ስነ-ሥርዓት በመላው የአገሪቱ ክልሎች ዘማቹ ተሰማራ።

ከጠቅላላው ዘማች ከዘጠና ከመቶ በላይ ከአብዮታዊው ሠራዊትና የአገሪቱ መምህራን ጋር ሆነው ከዚህ በታች እንደሚከተለው መንግሥትም፣ ሕዝብም ከጠበቁት በላይ በታላቅ የገር፣ የወገን ፍቅርና እንዲሁም አብዮታዊ ስሜት ተልዕኳቸውን ፈፀሙ።

ዘመቻው የተሰጠው የጊዜ መጠን፣ አቅማቸውና እንዲሁም የአካባቢው ሁኔታ እንደፈቀደ ማይምነትን ተዋጉ፣ ገበሬውን በፖለቲካ አነቁ፣ ለእያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት አከፋፈሉ። ለእያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት ማከፋፈሉ ትልቁና አድካሚ ሥራ ከተከናወነ በኋላ በየ80 ሄክታር መሬት ላይ አንድ የገበሬ ቀበሌ ማህበር፣ በጠቅላላው ሀያ አምስት ሚሊዮን የገበሬ አባወራዎችን ወይም ቤተሰብ ያቀፈ 7,000 የቀበሌ ገበሬ ማህበሮች በመላው ኢትዮጵያ ገጠር አቋቋሙ።

ለሁለት ዓመታት ያህል ተማሪዎች ከትምህርታቸው፣ መምህራን ከማስተማር ተግባራቸው፣ የመከላከያ ሠራዊቶቻችን ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው አርሶ አደር ወገናቸውን ሲያገለግሉ በእነሱና በገበሬው ላይ ፀረ-ሕዝቦች የሰነዘሩባቸውን የተለያዩ ጥቃቶች በመከላከል መረር ተጋድሎ የፈፀሙ ብዙ ሲሆኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ተሰውተዋል።

ለማጠቃለል፣ ታሪካዊው የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ተልዕኮ ውጤት ሲገመገም ገንቢም አፍራሽም ገፅታዎች አሉት። በቅድሚያ ገንቢውን የተመለከትን እንደሆነ ከዚህ በላይ በጥቂቱ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ለዘመቻው በፍቃደኛነት ከተመዘገቡት ወጣቶች ከ98 በመቶ በላይ ዘመቻውን ተካፍለዋል።

ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑት ዘማቾች መንግሥትና ሕዝብ ከጠበቁት በላይ አኩሪና አብዮታዊ ተግባር አከናውነዋል። የዘመቻው ዝግጅት፣ አደረጃጀት፣ ስምሪት፣ ሂደትና ውጤቱ በአጠቃላይ በዓለም ደረጃ የተደነቀ ልዩ ዘመቻ ነበር።

ከኢትዮጵያ የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ጋር በዓለም ታሪክ የሚወዳደሩና የሚመሳሰሉ ሰላማዊ፣ ሕዝባዊና አብዮታዊ ዘመቻዎች ቢኖሩ፣ በሩሲያና በቻይና ሕዝባዊ አብዮት አፍላ ወቅት መሬት ለማከፋፈልና ገበሬውን ለማደራጀት የተደረጉት ዘመቻዎች ሲሆኑ ከነዚህ ሌላ፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በኩባ የተደረገው ዘመቻ በዓላማውና በተግባር አፈፃፀሙ ከእኛ ጋር ፍፁም የሚመሳሰለውና፣ በዚሁ የጊዜ ክልል ውስጥ፣ በኢራን ማይምነትን ለመዋጋት፣ በሕንድ ከማይምነት ጋር ርሀብንና ድህነትን ለመዋጋት የተካሄዱት አረንጓዴ ዘመቻዎች በመባል የሚታወቁት ብቻ ናቸው።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ማለትም አብዮትና አብዮታዊ አመራር ቀርቶ የፖለቲካ ፓርቲ በማይታወቅበትና እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ የፖለቲካ ባህል ድህነት በሰፈነበት የጭቆና ጨለማ ዘመን በአዲስ አበባ ጎዳናና አደባባዮች "መሬት ለአራሹ" የሚል የፖለቲካ ሰሌዳ ይዞ የወጣው ትውልድ አካል የሆነው ወጣት የሕብረተሰብ ክፍል ኢሕአፓ ሕዝባዊውን የመሬት አዋጅ በፅኑ ከሚቃወሙት ጉልተኛ መሣፍንቶችና የመሬት ከበርቴ ፊውዳል መኳንንቶች ጎራ አሰለፈው።

የመሬቱን አዋጅ ተግባራዊ የሚያደርገው የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ በአድህሮት ሴራና ግርግር ሊገታ ወይም ሊስናከል ያለመቻሉን ሲገነዘብ ጀሌዎቹን በብዙሃን ዘማች ወጣት ውስጥ አስርጎ በማሰማራት፣ የዘመቻውን መድረክ ለአምስተኛው ረድፍ ሠራዊት የሰው ኃይል መመልመያ መድረክ በማድረግ ከተጠቀመበት በኋላ የዘመቻውን የተልዕኮ ጊዜ እንኳን ሳይጠብቅ ጀሌዎቹን በመጀመሪያው ዓመት ከዘመቻው አስኮብልሎ በመመለስ ለሃገር አቀፍ የነጭ ሽብር ዘመቻ በፍልስጤሞች ቀኝ ክንፍ ፋታህ በሚባለውና በያሲን አራፋት በሚመራው ድርጅት፣ በጀብሃና በሻዕቢያ እየተረዳ ማሰልጠንና መደራጀት ጀመረ።

## ምዕራፍ አስራ አምስት

# የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ገበሬዎች የቀበሌ ማህበር ወደ ከፍተኛ ንቃት፣ ድርጅት፣ ምርትና ማህበራዊ ይዞታ የማሸጋገር እምርታ

በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የገጠሩን የእርሻ መሬት ከጉልተኛ መሣፍንቶችና ከመሬት ከበርቴ መኳንንቶች ወስዶ፣ ገባር፣ ጢሰኛና ሎሌ ለነበረው ደሀ ማከፋፈል በሰው ልጅ ታሪክ በ19ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ የተጀመረና አቻ የሌለው ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ እርምጃ ቢሆንም ከህብረተሰባዊ የእድገት አቅጣጫ አንፃር የአብዮቱ ስትራቴጂያዊ ግብ አልነበረም።

ከሶሻሊዝምና ብሎም ከኮምኒዝም ማህበራዊ ሥርአትና ሥልተ ምርት አኳያ የመሬት ለአራሹ አብዮታዊ እርምጃ አርሶ አደሩን ከባርነትና ከገባርነት ነፃ ካወጣ በኋላ፣ ደረጃ በደረጃ አያሌ ውስብስብ የትግልና የግንባታ እርከኖችን ተሸጋግሮ በከፍተኛ ደረጃ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆን፣ ምርትና የምርት ኃይሎችን፣ በማሳደግ፣ የተትረፈረፈ ምርት በማምረት፣ የምርትና የሥራ ክፍፍሉ፣ ከእያአንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ መከፋፈሉ ደረጃ ከመድረሱም ባሻገር ከመሬት ለአራሹ አዋጅ አንፃር የሶሻሊዝምና ብሎም የኮምኒዝም ግብ፣ ንዑስ ከበርቴ የሆነውን የገበሬውን መደብ ወይም የሕብረተሰብ ክፍል በሙሉ ወደ ወዛደራዊ መደብ በመለወጥ፣ መደብ አልባ ሕብረተሰብ መፍጠር ነው።

የአብዮቱ ስትራቴጂያዊ ግብ ይሄ መሆኑን ካስረዳሁ ዘንድ የእነዚህ ደረጃዎች ቅደም ተከተል፣ ረጅም ትግልና የግንባታ ስልት በተለይ የገበሬውን ኅብረተሰብና የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ፣ የመጀመሪያው የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የአስር ዓመት ጠቅላላ የልማትና የግንባታ እቅድ በትግላችን ቅፅ 2 እና 3 በተከታታይ በስፋትና በዝርዝር ለማቅረብ ቃል በመግባት በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የመጀመሪያ ምዕራፍ ለማከናወን የተሞከረውን ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የመሬት ለአራሹ አብዮታዊ አዋጅ በተግባር መተርጎሙን የመጀመሪያው ምዕራፍና ለእያንዳንዱ ደሀ ገበሬ በነፍስ ወከፍ እንደ ገበሬው ቤተሰብ ብዛትና ፍጆት፣ እንደ መሬቱ አይነትና የአካባቢው ተጨባጭ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ከሁለት እስከ አስር ሄክታር የእርሻ መሬት ማከፋፈልና በየስማንያ ሄክታር መሬት ላይ አንዳንድ የገበሬ ቀበሌ ማህበራቶችን ማቋቋም ነበር።



የገበሬው ማህበር አባላት በውይይት ላይ

በአገሪቱ የአስተዳደር ክልሎች ጠገግና ተዋረድ መሠረት የገበሬውን የቀበሌ ማህበር በወረዳ፣ በአውራጃ፣ በክፍለ ሀገርና ብሎም በሃገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን የገበሬዎች ማህበር ማቋቋምና በየደረጃቸውና ክልላቸው እንደ አንድ ነፃ የኢኮኖሚ ተቋም እንዲንቀሳቀሱ ሕጋዊ እውቅናና ህልውና መስጠት ነበር።

ከዚያም በኋላ በገበሬ ቀበሌ ማህበር ተደራጅተው በማህበራዊ የፖለቲካ ንቃታቸው በድርጅታዊ ጥንካሬና በምርታማነታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱት፣ በግብርና ሚኒስቴር የገበሬዎች ማደራጃ መምሪያ እየተጠኑና እየተገመገሙ ገበሬዎቹ እያንዳንዳቸው የነፍስ ወከፍ ወይም ማህበሩ በወል ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ ተደረገ።

በዚህ መሠረት በነፍስ ወከፍ ወይም በወል እውቅና ያገኙ ገበሬዎች እንደ ብዛታቸው ከሦስት ግለሰብ ገበሬዎች ጀምሮ እንደ ገበሬዎቹ ፈቃደኝነትና የመሬት ስፋት እየታዩ በአምራቾች የሕብረት ሥራ የገበሬ ማህበር ተደራጁ።

በዚህ የአሰራር አይነትና ሂደት በእድገት የሚቋቋሙና አንዱ ከሌላው በቅርፅም ሆነ በይዘት ከፍተኛነት የተለያዩ ሦስት ዓይነት የሕብረት ሥራ የገበሬዎች ማህበራት በኢትዮጵያችን በብዛት የተቋቋሙ ሲሆኑ እነሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

አንደኛውና የመጀመሪያው የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር (ማልባ) ይባላል። በማልባ ደረጃ ለመደራጀት በአንደኛው ደረጃ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ውስጥ አባል ሆኖ ለጥቂት ዓመታት መሥራትንና በዚህ ማለፍን ይጠይቃል። በማልባ ደረጃ ያለ የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር፣ የእርሻ መሬት የወል ወይም የማህበሩ ሆኖ፣ ለእያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ መኖሪያ ቤቱን የሚሰራበትንና የጓሮ አትክልት የሚያለማበት 2,000 ካሬ ሜትር መሬት ይፈቀድለታል።



ገበሬው በሕብረት ሥራ ላይ

በማልባ ደረጃ፣ የጓሮ አትክልት፣ የቤት እንስሳዎች፣ ማረሻ በሬዎችን ጨምሮ የማምረቻ መሣሪያዎች ወዘተ የግል ሲሆኑ የእርሻ መሬት የወል ወይም የማህበሩ ነው።

ሁለተኛውና ከፍተኛው የአምራች ገበሬዎች የሕብረትሥራ ማህበር (ወልባ) ይባላል። በወልባ ደረጃ ያለ የአምራች ገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ገበሬ፣ የመኖሪያ ቤቱን የሚሰራበትና የጓሮ አትክልት የሚያለማበት መሬት መጠን 1,000 ካሬ ሜትር መሬት ብቻ በግል ይዞታነት ሲፈቀድለት የተቀሩት፣ የእርሻ መሬት፣ ማረሻ በሬዎችና የቤት እንስሶች እና የማምረቻ መሣሪያዎች የወል ወይም የማህበሩ ናቸው።

በወልባ ደረጃ ባለ የገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን አንድ ገበሬ በቅድሚያ የማልባ የሕብረት ሥራ ማህበር አባል በመሆን ለተወሰኑ አመታት መሥራትና ጊዜያ ማለፍ አለበት።

በገበሬና በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነትና ማህበራዊ ይዘት ወልባ ከፍተኛውንና የመጨረሻ ደረጃ ነው ለማለት ይቻላል።

ሦስተኛውና ከሁሉም ከፍተኛው ከሁለቱም ማህበራት ከማልባና ከወልባ በይዘትም ጭምን በቅርፅ ለየት የሚለው "ወላንድ" ይባላል። ወላንድ የአምራች ገበሬዎች ማህበር ወይም ስብስብ ሳይሆን፣ የወረዳ የአስተዳደር ክልሎች ባሉት ገበሬዎች ማህበራት ውስጥ የሚገኙና ከሁለት እስከ አምስት የሚሆኑ የማልባ ወይም የወልባን ወይም የሁለቱም ጥምር ማህበራት በበላይነት የሚያስተዳድር ለማህበራቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ የአገልግሎት የሕብረት ሥራ ማህበር ሲሆን የወላንድ የአገልግሎት የሕብረት ሥራ ማህበር ዝርዝር ተግባር ጠቅለል ባለ ሁኔታና ባጭሩ የሚከተሉት ናቸው፣

1ኛ/ በማልባ ወይም በወልባ ደረጃ ያለ የሕብረት ሥራ ማህበር ከመንግሥትና ከባንክ ወይም ከሌላ ምንጭ የሚያስፈልጋቸውን ለማህበሩ ልማትና ለልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎት የገንዘብ ብድር ማፈላለግና ማቅረብ፣



በባሌ ክፍለ ሀገር አንድ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበርን በጎበኘ

2ኛ/ ለከፍተኛ ልማት በከፍተኛ መጠን የሚያስፈልጉ እንደ ትራክተር፣ ማጨጃና መሰብሰቢያ የመሳሰሉትን የማምረቻ መሣሪያዎች ግዢና እንዲሁም ለአምራቾች ማህበራት በሃገርም ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ምርታቸውን የሚሸጡባቸውን ገበያዎች ማፈላለግና ማዋዋል፤

3ኛ/ ለማህበራቱ አባላት በግልና በወል የሚያስፈልጓቸውን ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች የመሥሪያ ቤቶች፣ የእርሻ መሣሪያ መጠገኛ ሆርሻዎች፣ ለገበሬው ልጆች ትምህርት ቤት ለማህበራቱ በወል እንዳስፈላጊነቱ ከክሊኒክ ጀምሮ እስከ ሆስፒታል ደረጃ ያሉ የጤና አገልግሎት መስጫዎችን ግድቦችን ወዘተ የመሳሰሉትን የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ለማስገንባት፤

4ኛ/ በማህበራቱ ውስጥ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የማህበሩን አባላት ኑሮና ሕይወት ለማሻሻል፡ ለማዘመንና ብሎም ለመለወጥ እንደ እድገታቸው የሚያስፈልጋቸውን ዘመናዊ ተክኖሎጂዎች የማስተዋወቅና የማቅረብ፤

5ኛ/ በሃገር አቀፍ እቅድ መሠረት በየደረጃው ላሉ ማናቸውም አይነት ማህበራት ማምረት ያለባቸውን የምርት አይነትና መጠን ኮታ በማደላደልና ከብሔራዊ የምርት እቅድ ጋር በማስተባበር ወዘተ ማህበራቱን የሚመራ የአገልግሎት ሕብረት ሥራ ማህበር ነው።

## ክፍል ፬

# የሠራተኛው መደብና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት

# ምዕራፍ አስራ ስድስት

# የኢትዮጵያ ሠራተኞች መተዳደሪያ ሕግ

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ማግስት ደርጉ የመጀመሪያው አድርጎ ቅድሚያና ታላቁን ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች ሁሉ ዋንኞቹ አርሶ አደሩን ከገባርነት፣ ወዛደሩን ከምንዳ ባርነት ነፃ በማድረግ ዲሞክራሲያዊ መብታቸውንና ድርጅታቸውን በመሬት ለአራሹ አዋጅና በሠራተኛው መተዳደሪያ ሕግ አማካይነት እንዲቀዳጁ ማድረግ ነገር።

በአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይነትና አመራር፣ የሠራተኛውን መተዳደሪያ ሕግ የሚያጠናና የሚያዘጋጅ አንድ የተለያዩ ሙያዎች ባላቸው ምሁራን የተቃመረ ኮሚቴ ተቋቁሞ በማጥናትና በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀረበው የሕግ ረቂቅ፣ የገጠሩን የእርሻ መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ ከሚያደርገው የመሬት ለአራሹ የሕግ ረቂቅ በላቀ ሁኔታ ከአከራከረን በላይ ያሟገተ ብቻ ሳይሆን ረጅም ጊዜም ወስዶብናል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ብዙ ጊዜ ወስዶ ከመከረበትና ተስማምቶ ካጸደቀው በኋላ እንደተለመደው የመጨረሻውን ይሁንታ በደርጉ ጉባዔ ማግኘት ነበረበት።

የመሬት አዋጅን ለገበሬው ለማስረዳት፣ ገበሬውን ከማይምነት ነፃ ለማውጣት፣ መሬት ለማከፋፈልና ብሎም ገበሬውን በማህበር ለማደራጀት የወሰደውን ጊዜ ያህልና መጠነ ሰፊ የሰው ኃይል ባያስፈልግም የሠራተኛውን መተዳደሪያ ሕግ ለሠራተኛው ለማስረዳትና ለማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ሠራተኛውን በማህበር ለማደራጀት በመቶዎች የሚቆጠሩ ባለሙያ ምሁራን በመላው የአገሪቱ የአስተዳደር ክፍሎች መዝመት ወይም መሰማራት ነበረባቸው።

የተዘጋጁት የሠራተኛ መተዳደሪያ ሕጎች ሁለት አይነት ነበሩ፡-

1ኛ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከቁሳዊ ምርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ወይም በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በልዩ ልዩ የግምባታና የጥገና ገራዦች፣ በማዕድን ፍለጋና የማምረት ተግባሮች፣ በመሠረተ ልማት ግምባታዎች በመጓጓዣና በመገናኛ፣ በባንክ፣ በገንዘብ ድርጅቶችና በሆቴል አገልግሎቶች ወዘተ ለተሰማሩ አምራች ወዛደሮች መተዳደሪያ ሲሆን፣

2ኛ/ የሠራተኞች መተዳደሪያ ሕግ፣ በቁሳዊ ምርት ከማምረት ተግባር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሌላቸው የሥራ መስኮች የተሰማሩትን ማለትም፣ እንደ ህክምና ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ በልዩ ልዩ ጥናትና ምርምር፣ በሕዝብ አስተዳደርና አመራር ወዘተ የተሰማሩ ሠራተኞች መተዳደሪያ ነው።

በሁለቱ ሥርቶ አደር የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ባለው የሥራ ባህሪ ልዩነት ብቻ ሳይሆን ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የተፋጠነ እድገትና ብሎም ኢንዱስትሪው

በአገሪቱ ኢኮኖሚ መሪነቱን የሚይዝበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል ሁለት አይነት ሕጎች ቢያስፈልጉም፣ ሕጎቹን ማስከበር ባልናቸው መሰረታዊ የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብቶችና በመሰረታዊ የሠራተኛ መብቶች ፍፁም ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው።

የተባበሩት መንግሥታትን ዓለም አቀፍ የሠራተኛ መብትና የሠራተኛ አስተዳደር መርህ የሚያሟሉ ከመሆናቸው ባሻገር በህብረተሰባዊ ባህሪያቸው ምክንያት በጣም የላቁ ናቸው።

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ፣ የማዕድኑንና የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚዎች ከሠራተኛው እድገትና ሕይወት ጋር በጥብቅ አስተሳስሮ ወይም አቆራኝቶ ለማደራጀት ስለሆነ፣ እዚህ ላይ የማተኩረው ከቁሳዊ ምርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባላቸው ሠራተኞች የመተዳደሪያ ሕግ ላይ ነው።

የአምራቹ ወዝ አደር መተዳደሪያ የሆነውን ሕግ በሙሉ እዚህ ላይ አንቀጽ በአንቀጽ መዘርዘር ሳያስፈልግ፣ የሠራተኞች ሳትሆን ታሪኳን በሙሉ ማለት ይቻላል እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ድረስ የገባር አርሶ አደሮችና የጉልተኞች ብቻ ሆና በኖረችው ኢትዮጵያ በቅርቡ የበቀለ የሠራተኛ መደብ ታሪክ፣ ሕይወትና መብት ላይ መሰረታዊ የሆነ የመሻሻልና የእድገት ለውጥ ካመጡት የሕጉ አንኳሮች ጥቂቱን ክፍሎች ብቻ በአጭሩ መግለጽ በቂ ነው ብዬ አስባለሁ።

የለውጡንና ወይም የመሻሻሉን ስር ነቀልነት አንባቢ ይረዳ ዘንድ፣ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የሰውን ልጅ ወዝና ጉልበት ያለ ሰብዓዊ መብት አክብሮትና ያለ ተመጣጣኝ ክፍያ በከበርቴዎች ለማስበዝበዝ ካገለገለው፣ ከቀድሞው የሠራተኛ መተዳደሪያ ሕግ ውስጥ ሆን ተብሎ የተገደፉትን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችና የሠራተኛ መብቶች ጥቂቱን ብቻ ከዚህ እንደሚከተለው እጠቁማለሁ።

ከሁሉ በፊት በጉልታዊት ኢትዮጵያ ፊውዳላዊ አሳዛኝና አሳፋሪ ባህል፣ የተለያዩ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች፣ አምራች ወዛደሮች፣ አርሶ አደሮችና ነጋዴዎች ወዘተ በሥራቸውና በሙያቸው ብቻ የተናቁና ከፊውዳሉ ሕብረተሰብ ክፍል የራቁና የተገለሉ ብቻ ሳይሆኑ፣ በፈጠራ ችሎታቸውና በአምራችነታቸው፣ አርሰው ባበሉ፣ ሸምነው ባለበሱ፣ የሃገር መከላከያ መሣሪያዎችን በአመረቱና በአስታጠቁ ወዘተ ጠይብ፣ ቀጋ፣ ፋቂ፣ መጫኛ ነካሽ፣ አፈር ገፊ ወዘተ እየተባሉ ይሰደቡ ነበር።

ይህ የአሮጌውና የባለጌው ባህላችን ውጤት የሆነ ሃገርና ሕዝብን ወደ ኋላ ጎታች የባህል ችግር በጥቂቱም ቢሆን ሊቃለልና ሊሻሻል የቻለው ከድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በኋላ በተወለደው አዲስ ትውልድ ተቃውሞና ትግል ነው።

ይህንን በመሰለ አሮጌና ባለጌ የባህል ተጽዕኖ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረውን የሠራተኛ መተዳደሪያ ተብዬውን ሕግ መለስ ብለን በጥቂቱ የቃኘን እንደሆነ፡-

1ኛ/ በዘር በሃይማኖት፣ በፆታና በመደብ መድሎ ምክንያት በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ አይከፈልም።

2ኛ/ በተባበሩት መንግሥታት ማህበር የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌ መሠረት፣ እናትና እህቶቻችን በእናትነታቸው፣ በቤት ባለቤትነታቸውና በሠራተኝነታቸው ወይም በአምራችነታቸው በሕብረተሰብ ሕይወትና እድገት ሂደት ቁልፍ ማህበራዊ ቦታ ስላላቸው ልዩ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ሲገባ በእርግዝናቸው የጊዜ ክልል ውስጥ ድጋፍ አይሰጣቸውም። በሚወልዱ ጊዜ፣ ደማቸው እስኪጠግ የተወለደው ወይም የተወለደችው ሕፃን ዓይኗን እስክትገልጥ ድረስ እንኳን ደሞዝ ቀርቶ በቂ የእረፍት ጊዜ አይሰጣቸውም።

3ኛ/ ወዛደሮች በሚያከናውኑት የሥራ ባህሪ ምክንያት ወይም በሥራ ላይ የጤና መታወክ ሲደርስባቸው የህክምና አገልግሎት ሊሰጣቸው ቀርቶ የአካል ጉዳት ቢደርስባቸውና ሕይወታቸውንም ቢያጡ ለቤተሰቦቻቸው የሚሰጥ ካሳ አልነበረም።

4ኛ/ ወንድም ሆነ የሴት ወዛደሮች የሥራ ዋስትና አልነበራቸውም። አሰሪው ወይም የማምረቻ መሳርያ ባለቤት በፈለገ ጊዜ ከሥራቸው ሊነቅላቸው ወይም ሊያባርራቸው ይችላል።

5ኛ/ ወንድም ሆነ የሴት ወዝ አደር ጉልበትና ጤንነታቸው እስካለ ድረስ የሥራ ግዴታቸውን እየተወጡ ለረጅም ዓመታት ሰርተው ወይም አገልግለው፣ በጤና መታወክ ወይም በእርጅና ሥራቸውን ቢያቆሙ ወይም መሥራት ሲሳናቸው ሕይወታቸውን የሚያቆዩበትና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት የጡረታ መብት የላቸውም።

6ኛ/ ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ዜጋዋ ለሆነ አምራች ወዝ አደር ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የምትነፍግ ብቻ ሳትሆን በአጠቃላይ ወዛደሩ ለሚሰጠው አገልግሎት፣ ለሚያፈስሰው ወዝና ላብ የተመጣጠነ ክፍያ አይከፈለውም።

ይህንን አሳዛኝ የአገራችንን ወዛደሮች የምንዳ ባርነት ከዚህ እንደሚከተለው በጥቂቱም ቢሆን ለአንባብያን ዘርዘር አድርጌ ለመግለፅ እወዳለሁ።

በድህረ አብዮት በአዲሱ የሠራተኛ መተዳደሪያ ሕገ ረቂቅ ላይ ስንወያይ ለግንዛቤ ማዳበሪያ ብሎ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀረበልን አንድ ጥናት እንዳስገነዘበን፣ ሰበንክ የሠራተኛ ዘርፍ በምንለው የሥራ መስክ ማለትም በየሰው ቤት በህፃን ሞግዚትነት፣ በቤት ሠራተኝነት፣ በአትክልተኝነትና በዘበኝነት ወዘተ የሥራ መስክ የተሰለፉት፣ ቡና የሚያነፍሱት እህቶቻችንና እናቶቻችን፣ በምግብ፣ በመጠጥና በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ወዘተ የሚሰሩ ቁጥራቸው በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ወደ ሚልዮን የሚቃረቡ ወዛደሮች የወር ደሞዝ ከ5 እስከ 15 የኢትዮጵያ ብር ነበር።

ይህንን የወር ደሞዝ ክፍያ በወር ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ ቀናት ስናሰላው፣ እያንዳንዱ ወዝ አደር በየቀኑ የሚደክመውና የሚያገለግለው በነፃ ወይም በሳንቲም ስብርባሪ ነው ማለት ይቻላል።


ይሄ ሁሉ ሲሆን የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት የባዕዳን ከበርቴዎችንና የአገሪቱን ባለጊዜዎች ክብርና ጥቅማጥቅም ሲያስጠብቅና ሲንከባከብ፣ የአገሪቱ ዜጋ የሆኑ አምራች ወዛደሮች መብትና ማህበራዊ ደህንነት የሚያስጠብቅና የሚያስከብርላቸው ሕግ አልነበረም።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ በኋላ ወይም በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የታወጀው የሠራተኛ መተዳደሪያ ሕግ፣ በሠራተኛው ክብር፣ ሞራል፣ ጥቅምና እንዲሁም በዲሞክራሲያዊ መብቱ ረገድ ያስከተለውን መሰረታዊ ለውጥ በጥቂቱ ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡-

1ኛ/ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የጾታና የእድሜ ወዘተ ልዩነትና መድሎ ሳይደረግ ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ እንዲከፈል ተደርጓል።

2ኛ/ የሠራተኛው የሥራ ዋስትና ፍፁም የተከበረ ነው። ማንም ሰው በግልም ሆነ በወል ወይም ማናቸውም ድርጅት በግልም ሆነ በመንግሥት ተቋም የወዛደሩን ጉልበት መዝብሮ ከሥራው ለመንቀል ወይም ለማባረር አይችልም።

3ኛ/ ማናቸውም ሠራተኛ በጤና መታወክ ወይም በእርጅና ሥራ መሥራቱን ሲያቆም ወይም መሥራት ሲሳነው የጡረታ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።



የሴት ወዛደር በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሥራ ላይ

4ኛ/ ሴት ወዛደሮች በእናትነታቸው፣ በቤት አስተዳዳሪነታቸውና በአምራች ወዝ አደርነታቸው የተለየ እንክብካቤ በተለይ በእርግዝናና በሚወልዱበት ጊዜ የሚደረግላቸው በመተዳደሪያ ሕግ ውስጥ ተደንግጓል። በዚህ መሠረት አንዲት ወዝ አደር በወለዱ ወይም በወለደች ጊዜ፣ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ለ75 ቀን የወሊድ ፈቃድ ከደሞዝ ጋር ይሰጣታል።

5ኛ/ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የአንድ የሠራተኛ ደሞዝ በተለይም የመጀመሪያው መነሻ ደሞዝ የሚወሰነው በአሰሪዎችና በማምረቻ መሣሪያ ባለቤቶች ሳይሆን በሕግ ነው። ለአንድ አምራች ወዝ አደር ወይም ሠርቶ አደር አነስተኛው ወይም የመጀመሪያው የወር ክፍያ ወይም የደሞዝ ወለል ወይም ዝቅተኛው 50 የኢትዮጵያ ብር እንዲሆን በሠርቶ አደሮች የመተዳደሪያ ሕግ ተደንግጓል።

6ኛ/ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወዛደሩ ከአሰሪዎች ትዕዛዝ ተቀባይ ብቻ ሳይሆን በሥራ አመራር፣ በንብረት፣ በሂሳብ ቁጥጥርና በምርት እቅድ ወዘተ ተሳታፊ ነው። በወዛደሩና በአስተዳደሩ መካከል ያለው ግንኙነት የጌታና የሎሌ ግንኙነት ሳይሆን በሥራ ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ጓዳዊ፣ የዓላማና የተግባር አንድነት ነው።

7ኛ/ አብዮታዊ የሠርቶ አደሮች መተዳደሪያ ሕግ ለሠራተኛው ለቀርብለት ስለሚገባው የትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለልጆቹ ትምህርት ቤት፣ ቤተሰቡን ያካተተ መኖሪያ ቤትና ለሠራተኛውና ለቤተሰቡ ሊሰጡ የሚገቡ የጤና አገልግሎቶች ሁሉ በመተዳደሪያው ተደንግጓል።

ከዚህ ባለፈ ዝርዝር ውስጥ ለመግባት ያልፈለኩት ከመንግሥት በጎ ፈቃድ እጦት ሳይሆን፣ ኢምፔሪያሊዝምና አድሀሮት ኃይሎች፣ የውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች ባወጁብን ጦርነትና ተፈጥሮም በአስከተለው ችግር እንደተመኘነው ለማድረግ ባለመቻሉ ነው።

## ምዕራፍ አስራ ሰባት

# የሠራተኛው ማህበርና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት

በሰው ልጅ ታሪክ ለሰብዓዊ ፍጡራን ከፍተኛውን የኑሮ ደረጃ ያቀዳጀውና የሰውን ልጅ የማሰብ፣ የመመራመርና የፈጠራ ችሎታ በመመስከር የአቶምንና የጠፈርን ምስጢር ያስገኘው የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው።

በሰው ልጅ ታሪክ ሂደትና በሕብረተሰብ እድገት ዓለምን በየጊዜው እየለወጠ ያለው ዘመናዊ፣ ተራማጅ የሕብረተሰብ ክፍልና መደብ ከካፒታሊስት ሥራዓተ ማህበር ጋር አብሮ የተፈጠረው የወዛደሩ መደብ ነው።

ኢንዱስትሪ የሠራተኛው መደብ ፈጣሪ፣ ሠራተኛው የኢንዱስትሪ ሕይወትና መሪ፣ አንዱ ከሌላው ጋር አብሮ የተፈጠረ መንትያና አንዱ የሌላው ነጸብራቅ፣ አብረው የሚያድጉ፣ አብረውና ተነባብረው የሚኖሩ ናቸው።

ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤና አመለካከት በመነሳት፣ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የሠራተኛው መደብ የተደራጀው ከኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ተጣምሮ ነው። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ አፍን ሞልቶ ኢንዱስትሪ ነበር ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩ ሐቅ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ገጽታ ያላቸው ቀላልና አነስተኛ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የጀንያና የሲሚንቶ ጥቂት ኢንዱስትሪዎች በፋሽስት ኢጣሊያ አጭር የወረራ ዘመን መቋቋማቸው ይታወሳል።

ከአምስት ዓመት ቆይታ በኋላ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት በኢትዮጵያ አርበኞችና በእንግሊዝ ሠራዊት ትብብርና ቅንጅት ተረግጦ ከወጣ በኋላ ነፃው የኢትዮጵያ መንግሥት ተረጋግቶና ሰክኖ እንደ አንድ ሃገር ነፃ መንግሥት የአገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታዎች ተቆጣጥሮ መምራት ከመቻሉ በፊት በነበረው የሽግግር ጊዜ የኢጣሊያ ቅሪት የሆኑት ኢንዱስትሪዎች ብዙዎቹ ችግር ላይ በመውደቃቸውና የማምረት ተግባራቸውን በማቆማቸው ከእነሱ ጋር አብሮ የተፈጠረው የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ በመክሰም ወደ መጥፋቱ እንዳመራ መግለጼም ይታወሳል።

በቅድመ ፋሽስት ኢትዮጵያ ወይም ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በፊት በአገራችን ኢንዱስትሪ ቀርቶ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ ነዋሪ ለነበረው ሕዝብ ብርሃን የሚሰጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ እንዳልነበረ የሚታወቅ ነው።

ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ መንግሥት፣ በአንዳንድ የሃገር ተወላጆችና በባዕዳን ከበርቴ ግለሰቦች የተደረገው ጥረት የኢጣሊያ ቅሪት የነበሩት አነስተኛና ቀላል ኢንዱስትሪዎች አንሰራርተው በሙሉ ኃይላቸው እንዲያመርቱ ለማድረግ ነበር።

እኔ በዚህ ታሪክ የማወሳቸውና ከቀድሞው ሥርዓት አብዮታዊት ኢትዮጵያ የተረከበቻቸው ኢንዱስትሪዎች የኢጣሊያ ቅሪት በሆኑት ጥቂት ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ላይ ከ1950 ዓ.ም መባቻ እስከ 1960 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ በኢጣሊያ መንግሥት ድጋፍና ርዳታ፣ በቆቃ ግድብ መጠነኛ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ኃይል በመገንባቱ፣ የሆላንድ፣ የሕንድ፣ የጃፓንና የኢጣሊያ ዜጎች የሆኑ መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች የተከሏቸውና በአመዛኙ የግብርና ጥሬ ምርት ጥገኛ ወይም ተጠቃሚ የሆኑ፣ የስኳር፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የጥቂት ብረታ ብረት ወዘተ ማምረቻ ቀላልና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ነው። እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ከመለስተኛው ከስኳር ኢንዱስትሪው በስተቀር ከባድ ኢንዱስትሪ በአገራችን አልነበረም። ይህንን ስል አንባቢ፣ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ምን ተደርጓል ብሎ እንደሚጠይቅ እገምታለሁ። ጥያቄውም ተገቢ ነው። በዚህ ጥያቄ በአጭሩ የበኩሌ መልስ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የተገነቡት ብዙ ናቸው የሚል ነው።

ከአብዮቱ ማግሥት ጀምሮ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ አብዮቱን በእንጭጩ ለመቅጨት ከውጪም ከውስጥም ጦርነት በማወጅ የአገራችንን ብሔራዊ ድንበር ጥሶ 700 ኪ/ሜ የገባውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ረግጠን እስክናወጣ፣ የሰሜኑ የአገራችን ክልል አካል የሆነውን የኤርትራን ክፍለ ሃገር በሙሉ ወርረው በመቆጣጠር የአሥመራን፣ የምፅዋንና የባሬንቱን ከተሞች ከብበው የተቀመጡትን ገንጣዮች መንጥረን በማባረር፣ በእኛና በሱዳን የጋራ ወሰን ዳርቻ በናቅፋ ተራሮች ላይ እስክናንጠለጥላቸው ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝነኛ መፈክር "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግምባር" የሚል ስለነበር በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የሰውም ሆነ የገንዘብ ኃይላችንንና እንዲሁም ጊዜያችንን ለልማትና ለግምባታ የምናውልበት እድል አልነበረም።

በዚህ የጦርነትና የሽብር ጊዜ ውስጥ አልፎ አልፎ በሚገኝ አንፃራዊ ፋታ ያተኮርነው፣ የአሮጌውን ሥርዓተ ማህበር ላዕላይና ታህታይ መዋቅር እያፈረስን የአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ማህበራዊ መሰረቶች የሆኑትን፣ የሠራተኛውና የገበሬውን የተለያዩ የአገሪቱን ባለሙያዎችንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማህበር ማደራጀቱ ላይ ነበር።

ማንም እንደሚያውቀው አብዮታችንን ቦርቡረው፣ ገዝግዘውና ወግተው እስኪቀለብሱትና አገራችንንም እስካስገነጣጠሉበት ጊዜ ድረስ ለ17 ዓመታት ኢምፔሪያሊዝምና አድህሮት ኃይሎች ያወጁብን ጦርነትና ሽብር አልቆመም። ሆኖም ወራሪውን የሶማሊያ ሠራዊት ካስወጣንና የገንጣይና የአስገንጣዮችን አከርካሪ በመምታት አንፃራዊ ሰላም ካገኘንበት ከ1970 እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ በነበረው የ10ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፊል ኃይላችንን ወደ ሃገር ልማት ግምባር ለማዞር ሞከርን።

በዚህ የ10 ዓመት የጊዜ ክልል ውስጥ ኢንዱስትሪን በተመለከተ በሃገር አቀፍ ደረጃ ኢሕአፓ ያወጀብንን ሽብር ከሕዝቡ ጋር እየተከላከልን የገነባናቸውን፣ በመገንባት ላይ የነበሩትን ጥናትና ዝግጅታቸው ተጠናቆ ለግምባታ የተዘጋጁትን ከባድ፣ መለስተኛ፣ ቀላልና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችንና የእደ ጥበብ ዘርፎች በትግላችን ቅፅ 2 እና 3 በጊዜ፣ በቦታ፣ በአይነትና በመጠን ሰፋና ዘርዘር አድረጌ አቀርባለሁ።



በመተሐራ የስኳር ፋብሪካን ስንጎበኝ

የዚህ ምዕራፍ አርዕስት፣ የሠራተኛው ማህበርና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ጣምራ አደረጃጀት ቢልም፣ በቅድሚያ ያደራጀነው የሠራተኛውን ማህበር ሳይሆን የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ነበር።

የኢትዮጵያዊያን ድህነት፣ የአገራችን የተፈጥሮ ሀብት እጦት ወይም እጥረት ሳይሆን የሰው አለመሥራት፣ የአገሪቱ ያለመልማትና ኋላቀርነት ነው። አንድ ሃገር ሰማ፣ ዘመነ ወይም በለፀገ የሚያሰኘው፣ በዚያ ሃገር ኢኮኖሚ ውስጥ የኢንዱስትሪው ስፋት፣ እድገትና የመሪነት ደረጃ ነው። ኢንዱስትሪውን በምናደራጅበት ጊዜ ኢትዮጵያን ከድህነትና ከኋላቀርነት ለልፈኝነት ተራ አውጥተን በተፋጠነ ሁኔታ ለማዘመንና ለማበልጸግ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አመራርና አደረጃጀት ወሳኝነት አለው።

ይህም ከብዙ ከለሙ አገሮች ተሞክሮ ያስተዋልነው ብቻ ሳይሆን እንደ አቅማችን በበኩላችንም የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተፋጠነ ሁኔታ ለማልማትና ለማስፋፋት፣ በሰው ኃይል ስልጠና፣ በአመራርና በአደረጃጀት ምን መደረግ አለበት ለምንላቸው ጥያቄዎቻችን መልስ ለማግኘት ባደረግነው ጥናት የደረስንበት ግኝት፣ የኢንዱስትሪው መንትያና መሪ የሆነውን የሠራተኛውን መደብ አደረጃጀት ከኢንዱስትሪው ብናጣምረው፣ ያለው ጠቀሜታ ነው።

በሰው ኃይል ስልጠና ከአንዱ የማምረቻ ተቋም በተፈለገ ጊዜና በተፈለገው መጠን ሰውን አዘዋውሮ መጠቀም፣ በሰው ኃይል ቁጠባ፣ በገንዘብና በሎጂስቲክ አደላደል፣ የአንዱ ማምረቻ ድርጅት ወዛደሮች ከሌሎች ለመማር ወይም ልምድ ለመለዋወጥ፣ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለመንከባከብ፣ ለማደስና ለማዘመን ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ

ለመለወጥ፣ ለጥናትና ለምርምር፣ በአጠቃላይ ለምርትና ለምርት ኃይሎች እድገትና የአመራር ስኬታማነት በጣም ጠቃሚ ሆኖ ነው ያገኘነው።

ስለሆነም ከአሮጌው ሥርዓት የተረከብናቸውን ኢንዱስትሪዎች በቅድሚያና እንደ ባህሪያቸው፣ በወገን በወገናቸው በማሰባሰብ፣ የብረታ ብረት፣ የኬሚካልና የጨርቃ ጨርቅ ወዘተ በስምንት ተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ሕብረት አደራጀናቸው።

ከባዕዳን ከበርቴዎችና ከኢትዮጵያ ጉልተኞች ከተቀናጀ ብዝበዛ ነፃ በመውጣት ታላቅ የመንፈስ ተሃድሶ ያገኙትን ሠራተኞች፣ በቅድሚያ በማህበራቸው ወይም በሚያመርቱባቸው በእያንዳንዱ መሰረታዊ የማምረቻ ተቋማት ወይም ኢንዱስትሪ፣ ከዚያም በሁለተኛ ደረጃ እንደተገለጸው በስምንት ተመሳሳይ ኢንዱስትሪዎች ሕብረትና በሌሎች ስድስት የአገልግሎት ዘርፎች ማለትም፣ በኮንስትራክሽን፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በዘመናዊ ግብርና፣ በገንዘብ ድርጅቶችና ባንኮች፣ በሆቴል አገልግሎቶችና በሰበነክ ዘርፎች፣ በአጠቃላይ በስምንት ኮርፖሬሽኖችና በስድስት ዘርፎች በድምሩ በ12 ተቋሞች ከአደራጀናቸው በኋላ ኮርፖሬሽኖቹንና ዘርፎቹን ደግሞ በሃገር አቀፍ ደረጃ በኢትዮጵያ ሠራተኞች አጠቃላይ ምክር ቤት የአመራር ጠገግ አዋቀርናቸው።

ከሠራተኛው ማህበራት ውስጥ ሰበነክ ዘርፍ በማለት የምንጠራው በአሮጌው ሥርዓት ከየትኛውም መደብና የሕብረተሰብ ክፍል በከፋ ሁኔታ የተበደሉና የተጨቆኑ ብቻ ሳይሆኑ የተዋረዱና ሰብዓዊ ክብራቸውንና መብታቸውን ተገፍፈው የኖሩ ወዛደሮች ናቸው።

በቁጥራቸውም ከገበሬው ቀጥሎ በአገሪቱ ሁለተኛውን ደረጃ የያዙ፣ በየግለሰቡ ቤት በእሽክርናና በግርድና ወዘተ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ለፍቶ አዳሪ ምስኪን የሕብረተሰብ ክፍል ናቸው። እነኚህ የወዝ አደር ክፍሎች ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን የተጎናጸፉት፣ በሠራተኛ ወግ እና በሠራተኛ ማህበር የተደራጁት በታላቁ አብዮት ነው።

በመንግሥት ላዕላይ መዋቅር ውስጥ ኢንዱስትሪውን በተፋጠነ ሁኔታ ለማስፋፋትና ለማሳደግ ይበጃል ተብሎ በታመነው መሠረት፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን አቋም ከሌሎቹ ሚኒስቴሮች ጋር በማሻሻል የእደ ጥበቡን ኢንዱስትሪም በውስጡ በአንድ መምሪያ አማካኝነት እንዲያስተዳድር ሆኖ ከተቋቋመ በኋላ በተደረገው ሌላ አጠቃላይ ጥናትና በተለይም ከ10 ዓመቱ አጠቃላይ የልማትና የግምባታ ዕቅድ ግቦች አንፃር ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የተፋጠነ እድገት በተሰጠው ትኩረት በሦስት ሚኒስቴሮች ማለትም፣ በግብርናና በገበሬዎች ማደራጃ ሚኒስቴር፣ በመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር በቡና፣ በሻይና በቅመማ ቅመም ልማት ሚኒስቴር እንዲመራ በተደረገው መሠረት፣ ኢንዱስትሪውም በከባድ ኢንዱስትሪ፣ በቀላልና አነስተኛ ኢንዱስትሪና በእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማለትም በሦስት ሚኒስቴር ለማቋቋም ታቅዶ የሦስቱን ሚኒስቴሮች መቋቋም የጠየቁ ግምባታዎች እስኪጠናቀቁና አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ድረስ እንዲዘገዩ ተደረገ።

## ምዕራፍ አስራ ስምንት

# በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ

እደ ጥበብ በታሪክ የሰው ልጅ የመጀመሪያው ቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎች ቀዳሚ መሠረት ነው። በረጅም ጊዜ የታሪክ ሂደት የሰው ልጅ ወደ ህዋው ላደረገው ጉዞ ምክንያትና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ኢኮኖሚ አባት ነው ለማለት ይቻላል። የእደ ጥበብ ፈጠራ ውጤቶች ወይም ምርቶች ባይኖሩ ጥንታዊው የሰው ልጅ አድኖ፣ በእሳት አብስሎ ለመመገብና በእንስሳት ቆዳ ራሱን ለመከፈን ባልቻለ ነበር።

እደ ጥበብ ከሰው ታሪክ እኩል ረጅም እድሜ ያለውና የዛሬው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አባት ሆኖ ሳለና ተአምር የሚባል ነገር ካለ ተአምር የሚያሰኝ ታላቅ የለውጥና የመሻሻል ጉዞ አድርጎም፣ ውጤቱ የሆነው እጅግ ውስብስብና በገፍ አምራች የዘመናችን ቴክኖሎጂ ወይም ኢንዱስትሪ ዛሬም አልተካውም።

ውብና ረቂቅ የእደ ጥበብ ምርቶች የሚጠይቁት ማሽን ሳይሆን በሙያው የተራቀቀውን ሰው ብርቱ ጥንቃቄና ወርቃማ ጣቶችን ነው። አገራችን ኢትዮጵያ ለዛሬው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባዕድ ትሁን እንጂ በጥንታዊ የሥልጣኔዋ ጊዜ በእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ምርቷ በዓለም ከታወቁት አገሮች አንዷ ስለመሆኗ በዚህ በትግላችን መቅድምና መግቢያ ብዙ ተብሏል።

ባለሙያውን ወይም ፈጣሪውን የሚያሰባስበው፣ የሚያበረታታው፣ የሚያደራጀውና የሚመራው በማጣቱ እንጂ ዛሬም በኢትዮጵያችን የእደ ጥበቡ ሙያ ከዳር እስከዳር ነው። የእደ ጥበቡ ሙያና ውጤቱ ወይም ምርቱ ረቂቅነትና ተደናቂነቱ ብቻ ሳይሆን በቁሳዊ አገልግሎት ፋይዳውም በዓለም ላይ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ በመሆኑ ከግብርናውና ከኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ቀጥሎ ሰፊ የሥራ መስክ የሆነ የሰው ልጅ መተዳደሪያ ነው።

በመሬት ለአራሹ አዋጅ ነፃውን አርሶ አደር፣ በሠርቶ አደሩ መተዳደሪያ ሕግ አማካኝነት ነፃ የሆነውን ሠርቶ አደር ከአደራጀን በኋላ ያተኮርነው በእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ነበር።

ኢንዱስትሪ አለ በማይባልበት፣ ድህነትና ሥራ አጥነት በሰፈነባት ኢትዮጵያን በመሰለች ሃገር የዕደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚና የሥራ መስክ በአሮጌው ሥርዓት ለረጅም ዘመናት ተንቆና ተረስቶ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ አብዮታዊያን ግንዛቤና አመለካከት፣ ኢትዮጵያዊያንን ከድህነትና ከሥራ አጥነት ችግር ለማላቀቅ ብቻ ሳይሆን አገሪቱን በተፋጠነ ሁኔታ የኢንዱስትሪ ሃገር ለማድረግ ቁልፍ ከሆኑ የግንባታ ስልቶች አንዱ፣ ቀዳሚውና ዋናው የአገሪቱን የእደ

ጥበብ ባለሙያዎች በሙሉ አሰባስቦ በየሙያቸው በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ነው።

አነስተኛ፣ ቀላል መካከለኛና ብሎም ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ለማደራጀት የሚደረገው ጥረት የአገሪቱ አቅም እንደፈቀደ የሚቀጥል ሆኖ ኢትዮጵያን ወደ ስር ነቀል የኢንዱስትሪ አብዮት ለመምራት ስልቱ፣ ነባሩንና ሰፊውን የእደ ጥበብ ባለሙያ ሕብረተሰብ በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ነው የሚለው ሀሳብ ወይም እቅድ ተምኔታዊና ስሜታዊ ግምት ሳይሆን ውጤቱ በታሪክም የተረጋገጠ ነው።

ዛሬ በእድገት ጥለውን የሄዱት የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አህጉራት ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ ጃፓኖች፣ ቻይናዎች፣ ሕንዶችና እሥራኤልን ጨምሮ በሩቅ ምሥራቅ ክልል የሚኖሩት ሕዝቦች መካከል "ነብሮች" የተባለ ስም የተሰጣቸውና ኢንዱስትሪዎች እንደ እንጉዳይ የፈሉባቸው አገሮች የተጠቀሙበት የግንባታ ስልት ነው።

እነዚህ እንደ ኢትዮጵያ ጥንታዊና ኋላቀር ከነበሩ የእስያ አገሮች መካከል በተለይ "ነብሮች" የተባሉት፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ አዲስ ጥበብ እና ቴክኖሎጂ ሲፈጠር ወዲያው ዘለው ልክ እንደ "ነብር" አፈፍ አድርገው በመውሰድ ቴክኖሎጂውን ከፈጠሩት አገሮች ቀድመው በማምረት መልሰው ለሰሜን አሜሪካና ለአውሮፓ ገበያዎች በገፍና በርካሽ ዋጋ ያቀርቡታል።

እነዚህ ኋላቀር የነበሩ የእስያ አገሮች እጅግ በመበልፀጋቸው የሕዝቦቻቸው የኑሮ ደረጃ ከአውሮፓውያንም ኑሮ ልቆ ከመሄዱ ባሻገር በቴክኖሎጂውም ተራቀው አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የዘመናችን የከፍተኛ ምርምርና የፈጠራ ውጤት ነው በማለት የሚመጻደቁበትን የኤሌክትሮኒክ ቴክኖሎጂ የጎጆ ኢንዱስትሪ አድርገውታል።

የኢትዮጵያን አርሶ አደሮች የሕብረት ሥራ ማህበራት ያደራጁ ዘንድ በአንድ የገበሬዎች ማደራጃ መምሪያ አጠናክረን ለግብርና ሚኒስቴር ሃላፊነትን እንደሰጠነው ሁሉ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርንም እንዲሁ በአንድ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ መምሪያ አጠናክረን የአገሪቱን የተለያዩ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ያደራጅ ዘንድ ሃላፊነቱን ሰጠነው።

ይህንን ታላቅ ተግባር ወይም ተልዕኮ የሰጠነው ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን በሠርቶ አደር ፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ከተቋቋሙት የፓርቲው የአመራር ዘርፎችና መምሪያዎች መካከል አንዱን የተለያየ ሙያ ባላቸው ምሁራዊ የሰው ኃይል የተጠናከረውን ዘርፍ በሁለት መምሪያዎች በመከፈል አንዱን መምሪያ የገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማደራጃ፣ ሌላውን የእደ ጥበብ የሕብረት ሥራ ማደራጃ መምሪያ በማድረግ ተጨማሪ ሃላፊነት ሰጠን።

በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች፣ ከክፍለ ሀገር እስከ ወረዳና ብሎም እስከ ቀበሌ የገበሬ ማህበራት ድረስና እንዲሁም በየከተሞቹ ከከተማ አጠቃላይ ምክር ቤቶች ጀምሮ እስከ ቀበሌ ማህበራት ድረስ ላሉት ተቋማት ካድሬዎች በየበኩላቸው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን እንዲረዱ ከጥብቅ አደራ ጋር መመሪያ በመስጠት በ1971 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የማደራጀቱ ተግባር በሃገር አቀፍ ደረጃ ተጀመረ።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በነበሩት የእደ ጥበብ ማደራጃ መምሪያ የተሰባሰቡት ወጣት ምሁራን ሥራውን የጀመሩት በቅንነትና



የቆዳ ፋብሪካን ስንጎበኝ

ከፍተኛ የሥራ ፈቃደኝነት ሲሆን በቀረበልን የማደራጃ ጥናት መሠረት እንዲደራጁ የተፈለጉት የእደ ጥበብ ሙያዎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ:

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1ኛ/ የብረታ ብረት ሥራዎች | የሕብረት ሥራ ማህበር | | |
| 2ኛ/ የወርቅ፣ የብርና የከበሩ ድንጋይ ሥራዎች | " | " | " |
| 3ኛ/ የእንጨት ሥራዎች | " | " | " |
| 4ኛ/ የቀንድ ሥራዎች | " | " | " |
| 5ኛ/ የቆዳ ሥራዎች | " | " | " |
| 6ኛ/ የፀጉር ሥራዎች | " | " | " |
| 7ኛ/ የጭራ ሥራዎች | " | " | " |
| 8ኛ/ የጅማትና የሸቦ ሥራዎች | " | " | " |
| 9ኛ/ የቃጫ ሥራዎች | " | " | " |
| 10ኛ/ የዘንባባ ሥራዎች | " | " | " |
| 11ኛ/ የግቻና የአለላ ሥራዎች | " | " | " |
| 12ኛ/ የሸመና ሥራዎች | " | " | " |
| 13ኛ/ የአፈርና የሸክላ ሥራዎች | " | " | " |
| 14ኛ/ የቀርከሃና የሸንበቆ ሥራዎች | " | " | " |
| 15ኛ/ የድንጋይ እነፃና ወቀራ ሥራዎች | " | " | " ናቸው። |

የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን በአጠቃላይ በአምራቾች የሕብረተሰብ ሥራ ማህበራት ማደራጀት ተንቆና ተረስቶ የቆየውን ሙያቸውን ከማደስ ባሻገር በአምራችነት ራሳቸውንና አገራቸውን ይረዱ ዘንድና የተቀሩትም የአገሪቱ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በየበኩላቸው ድጋፍና ትብብራቸውን ያሳዩ ዘንድ በብዙሃን ማሰራጫዎች ሰፊ ቅስቀሳ ተደረገ።

ስለ እደ ጥበብ ሙያና ምንነት በአጠቃላይ፣ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ስለሚኖረው ታላቅ አስተዋፅዖና ለሥራ አጡ ስለሚከፍተው የሥራ እድል ሕዝቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ተሞክሯል።

የማደራጀቱ ሥራ ከተጀመረበት ጥቂት ወራት በኋላ ባንዳንድ ከተሞችና ገጠሮች፣ በተለይም በአዲስአበባ ከተማና በአካባቢዋ፣ በብረታብረት፣ በእንጨት፣ በፀጉር፣ በአለላና በዘንባባ ሥራ ወዘተ መስክ የተደራጁ ማህበራትን የኢንዱስትሪ ምኒስቴር በብዙሃን ማሰራጫዎች አማካኝነት አልፎ አልፎ ለሕዝብ ማቅረብና ማስተዋወቅ ጀመረ።

አቀራረቡ በመጠኑም ቢሆን የተጋነነ ከመሆኑ በላይ ያስተዋልናቸው ማህበራት በምርታቸው አይነትና ጥራት፣ በሥራ ቦታቸው አደረጃጀት ወዘተ የአገሪቱን የአመራር አካላት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም አልሳቡትም። ምክንያቱም ባለሙያዎቹ ወትሮ በየሙያቸውና በየግል ጥረታቸው ሲያከናውኑት ከነበረው የሥራ ዘይቤና ሲያመርቱት ከነበረው ምርት የተለየና በመንግሥት አመራር የተደራጀና የተመራ የሕብረት ሥራ አልመሰለም።

ሆኖም ገና ተማሪዎች ስለሆንን በሂደት ብዙ ነገሮች እንደሚሻሻሉ ተስፋ አድርገን ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየን በኋላ በ1972 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ስለ እደ ጥበባት ማህበራቱ እድገትና በአጠቃላይ ስላሉበት ሁኔታ ግምገማ አድርጎ የሚያሳውቀን አንድ የባለሙያዎች ቅምር ቡድን አሰማራን።

የእደ ጥበቡ ባለሙያዎች አምራቾችን ማህበራት ማደራጀት ማለት፣ ከሙያተኛው ሕብረተሰብ የቁጥር ብዛት፣ ከሙያው አይነት ብዛት፣ ከምርቱ ጥራት፣ ከአመራረቱ ማህበራዊ ይዘት፣ ለቦዘነውና ለሥራ አጡ ብሎም ለሴተኛ አዳሪው ከሚከፍተው የሥራ እድል ባሻገር ከኢንዱስትሪው ጋር የአገሪቱን የወዝ አደር መደብ በከፍተኛ ደረጃ ማስፋት ማለት ስለ ሆነ ፓርቲያችን የሰጠው ትኩረት በዚያው መጠን እጅግ ከፍተኛ ነበር።

በዚህ አይነት ስለሚታዩውና ስለሚጠበቀው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች የሕብረት ሥራ ማህበራት ገምጋሚው ቡድን ያቀረበልን ግምገማ ያስገነዘበን ቢኖር፣ ከምንጠብቀው ውጤት ብዙ በጣም ብዙ ሩቅ መሆናችንን ነው። በዚህ አይነት ቅሬታዬን የገለጽኩት ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር ላለማለት ነው።

ለእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚ የሰጠነው ትኩረት፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ በአምራቾች ሕብረት ሥራ ለማደራጀት የተወሰደው እርምጃ፣ ለዚህ የሥራ መስክና ክፍለ ኢንዱስትሪ የታቀደው ዓላማና እንዲሁም ግብ በጣም ትክክል ሆኖ፣ ከዚህ ባለፈ በተግባር ይቻላል ተብሎ የቀረበልን ጥናትና የአፈጻጸም ስልቶች በሙሉ በስህተት የተሞሉ መሆናቸውን ነው የተገነዘብነው።

የስህተቶቹ ዋና ምንጭ፣ ይህንን ሰፊ የፈጠራ ሙያ ቴክኒካዊ ባህሪ፣ በአምራቾች ማህበር ማደራጀቱን የምርቶችን አይነትና መጠን፣ ማህበራቱ የሚያስፈልጋቸው የማምረቻ መሣሪያዎች አይነት እና የጥሬ እቃ ምንጮች ወዘተ በዝርዝርና በውል የሚያውቅ ባለሙያ በአገሪቱ ያለመኖር ነው።

ይህንን በግልጽ የተረዳነው ሥራው ከተጀመረ በኋላ በተደረገው ግምገማ ነው። እንዲህ ያሉ ሰዎችን የሚያፈራ የማሰልጠኛ ተቋም እስከዚህ ጊዜ ድረስ አገሪቱ አልነበራትም። የእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚ ለሺ ዓመታት ተረስቶና ፍፁም ተዳክሞ እንደመቆየቱ መጠን በሙያው በቂ እውቀት ያላቸውና በተወሰነ ደረጃም አመርቂ ልምድ ያላቸው ሰዎችም አልነበሩም።

ከእደ ጥበቡ ሙያ ጥቂት ቀንጭቦ ከያዘውና የግርማዊት እቴጌ የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት በመባል ከሚታወቀው አንድ አነስተኛ የማሰልጠኛ ተቋም በስተቀር ሌላ አልነበረም። የማደራጀቱንና የማምረቱን ሥራ በእጅጉ ውስብስብ ያደረጉት ቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ ከባለሙያዎቹ ስርጭትና ከልዩ ልዩ የኑሮ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ሰበነክ ጉዳዩችም ነበሩ።

የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በመላ አገሪቱ ከተማና ገጠር፣ በማህበረሰቡና በየብሄረሰቡ ውስጥ በንፍስ ወከፍ ተበታትነው ራሳቸውን ለማኖር ሌትተቀን የሚዋትቱ፣ የተደራጀ ሀብትና የተሟላ ኑሮ የሌላቸው ባተሌ ወዛደሮች በመሆናቸው እነዚህን በአጭር ጊዜ ከያሉበት አሰባስቦ በማህበር ማደራጀት ቀላል ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ከተደራጁም በኋላ ራሳቸውን ችለው በብቃት እስኪያመርቱ ድረስ በብዙ ረገድ የመንግሥት ድጋፍ የሚፈልጉ ስለመሆናቸው በጥናቱ ውስጥ የታሰበ አልነበረም።

ይህንን የመሰለ ሰፊ እጅግ ውስብስብና ከልምድ አንፃር እንግዳ የሆነ ሥራ እንዲያሰተባብሩና እንዲመሩ ብቻ ሳይሆን እንዲያስተምሩ የተመለመሉት ወጣት ምሁራን ካድሬዎች ራሳቸው በቅድሚያ መማር የነበረባቸው ነበሩ።

የአደራጆቹ ዝርዝር ቀርቦልን እንደ ተመለከትነው አብዛኛዎቹ የኢኮኖሚ፣ ጥቂቶች የሲቪልና የመካኒካል ምህንድስና ከዚህ የቀሩት የሶሻል ሳይንስ ምሩቃን ናቸው። ይህ ሁሉ ስህተትና ጉድለት ኖሮም ባሕር የሆነውን ሥራ ለመምራት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውስጥ የተደራጀው የሰው ኃይል ከሚፈለግበት ተልዕኮና ተግባር፣ ከእደ-ጥበቡ ባለሙያዎች ቁጥርና ስርጭታቸው ጋር ሲነፃፀር ያለማጋነን ዓባይን በማንኪያ ለመጭለፍ እንደመሞከር ነው።

ጥናቱሲጀመርከመነሻውየተመለመሉትአደራጆችያላቸውእውቀትናልምድእደ-ጥበብን ሳይሆንአነስተኛኢንዱስትሪዎችንማደራጀትንከመሆኑሌላ፣ አደረጃጀቱንመምሰልቀርቶፍፁም ከማይቀራረበው ከገበሬ አምራቾች የሕብረተሰብ ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ጋር በማስተያየት የተወሰደው ግምት ለስህተቶች ሁሉ መነሻ ሆኗል።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ሥራው እንደሚፈለገው ሊካሄድ ባለመቻሉ፣ የተቋቋሙት ማህበራት እንዲጠናከሩና በየጊዜው እንዲሻሻሉ አስፈላጊው ሁሉ እየተደረገ፣ በፈለግነው ዓይነትና መጠን እንዲሁም ደረጃ መላውን የእደ-ጥበብ ባለሙያዎች ለማደራጀት ይቻል ዘንድ ሌላ ጥልቀትና ጥራት ያለው ጥናት ተደርጎ፣ አደራጆችን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ብቻ ሳይሆን ባለሙያዎቹንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በጥራት ለማምረት የሚያስችላቸው የእውቀት የልምድ ማጎልበቻ ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት፣ በአጠቃላይ ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገትና መሻሻል የሚሰሩ የጥናትና የምርምር ተቋማት የሚቋቋሙበት ርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲወሰዱ ዳግም ሌላ ውሳኔ መስጠት ነበረብን። ለማጠቃለል የኢንዱስትሪዎችን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ በተለያዩ ምዕራፎች በተደጋጋሚ በተገለፀው መሠረት በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በሚገባ ተደራጅቶ አድጎና ሰፍቶ በአገሪቱ ኢኮኖሚ የመሪነቱን ስፍራ እንዲያዝ በሦስት ሚኒስቴር አስተዳደር እንዲደራጅና እንዲመራ አድርገን የነበረው ሁኔታ ያረካን ባለመሆኑ፣ ሁኔታው ተሻሽሎ በአራት የሚኒስቴር ተቋማት ማለትም፣ በከባድ ኢንዱስትሪ፣ በቀላልና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ፣ በእደ ጥበብ ኢንዱስትሪና በሃገር መከላከያ ኢንዱስትሪ እዲደራጁና እንዲመሩ ተወስኖ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ለጊዜው በአንድ ራሱን በቻለ ኮሚሽን አመራር እንዲመራ ተደረገ። ሁለት ሚኒስቴሮች ከመቋቋም ለጥቂት ጊዜ እንዲዘገዩ የተደረገበት ምክንያት፣

1ኛ/ ግንባታ ላይ የነበሩ የየብስ ተሽከርካሪዎች ማምረቻ፣ የትራክተሮችና በአጠቃላይ የግብርና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣

2ኛ/ ለሰላማዊ ተግባርና የሃገር መከላከያ አገልግሎት የሚውሉ አውሮፕላኖችንን መርከቦችን መገጣጠሚያ የመለዋወጫ እቃዎቻቸውን ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣

3ኛ/ ማናቸውንም ኢንዱስትሪዎች እራሳቸው የሚያመርቱት ወይም የኢንዱስትሪዎች ኢንዱስትሪ የሆነው የማሽንቱል ኢንዱስትሪ ግንባታ፣

4ኛ/ ከሁሉም በላይ የኢንዱስትሪዎች ግንባታ በስፋትና በተፋጠነ ሁኔታ ለመገንባት ወሳኝነት የነበራቸው፣ የተፈጥሮ ጋዝ ቁፈራና ልማት፣ የብረት ማዕድን ቁፈራና ልማት፣ ከዋቢ ሸበሌው ሌላ በባሮና በጊቤ ወንዞች ላይ በግድብ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የተጀመሩ የግንባታዎችን ፍፃሜ በመጠባበቅ ነበር።

# ክፍል ፫

# በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ለሰላም የተደረጉ ጥረቶች

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

# አብዮታዊት ኢትዮጵያን ለማዳን አማራጭ የሌለው መድኃኒት

ከጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር ሌላ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለኋላ ቀርነትና ለአሳፋሪ ድህነት ከዳረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋናው በሰላም ለመኖር ያለ መታደላችን፣ በረጅሙ ታሪካችን አገራችንን ከማልማትና ከመገንባት ይልቅ በአብዛኛው የገነባነውን ስናፈርስ መኖራችን ነው።

ከመካከለኛው ዘመን መባቻ ጀምሮ ባለፉት አንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ ስድስት መቶ ዓመታት የጦርነት፣ የሽብርና የፍጅት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል። አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት የታዬው በዛጉዌ ነገሥታት ዘመን መንግሥት ለሦስት መቶ ዓመታት፣ በጎንደር ነገሥታት ጊዜ የመጀመሪያው አንድ መቶ ዓመታትና በመጨረሻም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ለግማሽ ምዕት ዓመታት ብቻ ነው።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ አብዮታዊያን ለአገራችን የእድገት አቅጣጫ የሶሻሊዝምን ሥርዓተ ማህበር ስንመኝ የነበረው፣ ለሰው ልጅ ከሚያስገኘው ነፃነት፣ ማህበራዊ ፍትህ፣ እኩልነትና የተፋጠነ ማህበራዊ እድገት ባሻገር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአያሌ ምዕት ዓመታት የሰላም ችግር ዘላቂ መፍትሄ ያስገኛል በማለት ነው።

በኢትዮጵያ ለአያሌ ምዕት ዓመታት ሕዝቡን እርስበሱ በማዋጋት፣ በመከፋፈል፣ ለሁከት፣ ለሽብርና ለጦርነት ከዳረጉት መሰረታዊ የመደብ፣ የማህበረሰቦችና የብሔረሰቦች፣ የሃይማኖትና የጾታ መድሎና ቅራኔዎች ብቻ ሳይሆን ከእነኚሁ ጋራ በተያያዙና በሌሎችም ምክንያቶች ወደ አገራችን የሚፈሱትንም ችግሮችና ቅራኔዎች በመፍታት ከአካባቢያችንና ቅርብ ጎረቤቶቻችን ጋር በሰላምና በመልካም ጉርብትና ለመኖር ያስችለን ይሆናል የሚል ግምትና ተስፋ ነበረን።

ኢትዮጵያን ወይም የአፍሪካን ቀንድ የሚዋሰነው መካከለኛው ምሥራቅ፣ በአባይ ሸለቆና በአካባቢው ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዓለም ላይም ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ጎረቤታችን የሆነው ይህ ታሪካዊ አህጉር የሰው ልጅ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ እምነቶች የፈለቁበት ወይም የተፈለሰፉበት የጥንቱ ዓለም፣ የአውሮፓ፣ የእስያና የአፍሪካ አህጉራት የንግድ መናኸሪያና የመገናኛ ድልድይ የሆኑትን፣ የቀይ ባሕር፣ የአትላንቲክ፣ የሜድትራንያንና የሕንድ ውቂያኖስን የውሃ መንገዶች በማካተት ያስተሳሰረና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው ክልል ነው። ስትራቴጂካዊ በሆነ ባህሪው፣ አቀማመጡና ዓለም አቀፍ

ሰበቱ፣ ጥንታዊ ግብጾች፣ ባቢሎናዊያን፣ ኢትዮጵያዊያን፣ ፐርዣዎች፣ ግሪካዊያንና ሮማውያን ወዘተ ክልሉን ለመቆጣጠር በጦርነት ሲራኮቱበት ኖረዋል።

ከሰባተኛው ምዕት ዓመት መባቻ ጀምሮ እስከ መካከለኛው ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከዚሁ ክልል ሃይማኖትን ሽፋን አድርጎ የተነሳው የእስልምና እምነት አራማጅ የሆነው አረባዊና እስላማዊ ኃይል ንቅናቄ ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ ዓለምን በመስቀል ጦርነት ሲያነኩር ቆይቷል። ከዚህ በኋላ እስከ ቅርብ ጊዜ ማለትም እስከ ሀያኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ በተከታታይና በፈረቃ አውሮፓዊያን የቅኝ ግዛት ኃይሎች በተለይም ፈረንሳይና እንግሊዝ ወዘተ ክልሉን ቅኝ ግዛታቸው አድርገው ሲኖሩ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ የጀርመን፣ የጃፓን ና የኢጣሊያ መንግሥታት ቅንጅት ጎራ በሰነዘረው ጥቃት እነሱን አድክሞ ራሱም ሲጠፋ በመካከለኛው ምሥራቅ ቀድሞ ያልነበሩ ቅኝ ግዛት ሰራሽ የሆኑ ነፃና ትንንሽ የአረባዊ መንግሥታት ተፈጠሩ።

እነዚህ ከርስ ምድር ውስጥ ባለ የነዳጅ ዘይት ሀይቅ ላይ የተቀመጡ ነፃና ትንንሽ አረባዊ መንግሥታት ነፃነታቸውን፣ ህልውናቸውንና የነዳጅ ሀብታቸውን ከወራሪ ለመከላከል የማይችሉ ፊውዳላዊ መንግሥታት የምዕራቡን ኃያላን መንግሥታት በአጠቃላይ፣ የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም በተለይ ጥገኛ ወይም ተለጣፊ በመሆናቸው በክልሉ ነባር ከሆኑትና አረባዊ ብሔርተኝነት ከሚሰማቸው መንግሥታት ጋር ቅራኔ ተፈጠረ።

ጊዜ የማይሽረው ወይም የማይለውጠው የአረቦችና የእሥራኤሎች ቅራኔና ፍልሚያ መንስኤ ሆኖ ኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር የቀሰቀሰው አዲስ የአረብ ብሔርተኝነትና አዲስ የተፈጠሩት የእስልምና እምነት አክራሪ ኃይሎች መከፋፈል ተጨምሮ ክልሉ ከማንኛውም የዓለም ክልሎች በተለየ ሁኔታ ቋሚ የቀውስና የጦርነት ክልል ሆነ።

ከስትራቴጂያዊ አቀማመጡ በተጨማሪ የዓለም ከሀምሳ በመቶ በላይ የነዳጅ ዘይት ቅምጥ ሀብት ጎተራ በመሆኑ የጊዜአችንን የዓለም ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ ሳበ።

የፍልስጤሞች ችግርና አረቦች ከእሥራኤል ጋር ያላቸውን ቅራኔ በጦርነት እንፈታለን ብለው ለአንድ ሰሞን ሕብረት በፈጠሩበት ጊዜ እሥራኤሎችን የሚደመስሱበትን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ከሶቭየት ሕብረት በገፍ በመሸመት የሶሻሊስት አገሮች ዓይነተኛ የመሣሪያ ገበያ ሆኑ።

እሥራኤልን የሚደግፈው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔርያሊዝም እድምተኞችን ለመበቀል ሲሉ የነዳጅ ዘይት ምርታቸውን መቀነስና የገበያ ማዕቀብ ማድረግ ሲጀምሩ፣ ወታደራዊ ፍጥጫው በአረቦችና በእሥራኤሎች መካከል ከመሆን አልፎ አድማሱን በማስፋት የናቶና የዋርሶ ዓለም አቀፍ ወታደራዊ ድርጅት መፋጠጫ በመሆኑ የሦስተኛው የዓለም ጦርነት የመፈንዳት ምክንያት የሚሆነው በርሊን ሳይሆን መካከለኛው ምሥራቅ ነው በማለት የተነበዩ ብዙዎች ናቸው።

በታላቁ የኢትዮጵያ አብዮት መቃረብያ የጊዜ ክልል ውስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ በአዲስ ሁኔታ ከተከሰተው የአረብ ብሔርተኝነትና የእስልምና እምነት አክራሪነት ሌላ በርከት ያሉ አገሮች በፀረ-ኢምፔሪያሊስት የውጭ ግንኙነት መርሆ ግራ ዘመም የሆነ የፖለቲካ አቋም በመያዝ ከሶቭየት ሕብረት፣ ከሕዝባዊት ቻይናና ከቀሩት የዓለም ማህበራዊ ኃይሎችና የዓለም አብዮታዊያንና ተራማጆች ጋር ሕብረት ፈጠሩ።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በአፍሪካ የተለያዩ ክልሎች ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር ለነፃነት የሚደረገው ትግል የተጧጧፈ በዓለም ማህበራዊ ኃይሎች የትጥቅ፣ የቁሳቁስ፣ የሞራልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ትብብር ስለነበረ ይህንን አርአያ ተከትለው የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ አምራች የሆኑትና ሌሎቹም የአረብ መንግሥታት ለአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች ግምባር ይሰጡ በነበረው ድጋፍ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ በገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ በተባበሩት መንግሥታት መድረክ በፀረ-ኢምፔሪያሊስትና በፀረ-ፅዮናዊነት አቋማቸው ከአፍሪካና ከመላው ታዳጊ ዓለም የሚሰጣቸው ድጋፍና ተደማጭነታቸው እየሰፋና እየተጠናከረ ሄደ።

የሶቭየት ሕብረት መንግሥትና ኮሚኒስት ፓርቲው የአረቦችን የዘይት ሀብት ብቻ ሳይሆን በዓለም ፖለቲካ የሚጫወቱትንም ሚና በመመልከት ይመስላል ከሰሜን አፍሪካ የጀመረ መካከለኛውን ምሥራቅ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ በስተቀር የአፍሪካ ቀንድን፣ የአባይ ሸለቆ አገሮችንና ብዙ የአፍሪካ መንግሥታት የጦር ኃይሎችን በዘመናዊ የዋርሶ ትጥቅ አስታጠቃቸው።

ግራ ዘመም ብዬ ከፈረጅኳቸው ወይም ከጠቀስኳቸው የሰሜን አፍሪካ፣ የመካከለኛ ምሥራቅ፣ የአፍሪካ ቀንድና የአባይ ሸለቆ አገሮች መካከል ግብጽ፣ ሊቢያ፣ ሶሪያና ኢራቅ ሲገኙ ከዚህም አልፈው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ርዕዮት እንመራለን ያሉ አልጄሪያ፣ ደቡብ የመን፣ ሱዳንና ሶማሊያ ጥቂቶቹ ሲሆኑ የፍልስጤም ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ገንጣይና አስገንጣዮችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሶሻሊስት ካምፕና የእነዚህ አገሮች አጋር ወይም ወገን ተብለው ሁለገብ ድጋፍ ያገኙ ነበር።

በኃይለሥላሴ የምትመራዋ ኢትዮጲያ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለአፍሪካ አብዮት ጠንቅ ስለሆነች መመታት አለባት ተብሎ በተፈረደባት መሠረት፣ የኤርትራንና የኦጋዴን ገንጣዮች በማደራጀትና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ድጋፍ በመስጠት ኢትዮጵያን መቦርቦርና ማድማት ከጀመሩ ዓመታት ማስቆጠራቸው ብቻ ሳይሆን የኤርትራና የኦጋዴን ጉዳይ በአረብ ሊግ አማካኝነት ወደ ተባበሩት መንግሥታት መድረክ ለመውሰድ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ለመስጠት እየዶለቱ ነበር።

ኢትዮጵያን የከሰሩና ሊያጠፏትም የተነሱ አያሌ የአረብ አገሮች ለገንጣዮች የሚልኩትን መሣሪያና ትጥቅ፣ መድሃኒትና ስንቃስንቅ፣ አልባሳት ልዩ ልዩ ቁሳቁስ ወዘተ በመቀበል፣ በማከማቸትና ገንጣዮቹ በአስፈለጋቸው መጠንና ጊዜ የሚያቀርቡላቸው ብቻ ሳይሆን የገንጣዩቹ ማስልጠኛ መታከሚያ መዝናኛ ከተሞችና ምሽጎች ካርቱምና ሞቃዲሾ ነበሩ።

ለአፍሪካ ቀንድና ለአባይ ሸለቆ እንዲሁም በቅርቡ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ለኢትዮጵያ ባደላ ሁኔታ የቆየው ወታደራዊ የኃይል ሚዛን ወደ ሶማሊያና ወደ ሱዳን ወዘተ ከደፋ ቆይቷል። አገራችን ይህንን ለመሰለ ወታደራዊ ስጋትና እንዲሁም በኢኮኖሚ ውድቀት ላይ በነበረችበት ጊዜ በጦር ኃይሉ ከፍተኛ መኮንኖች ጉትጎታና ግፊት አፄ ኃይለሥላሴ ለመጨረሻ ጊዜ ዋሽንግተንን በመጎብኘት ለአሜሪካ መንግሥት ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርበው ነበር።

“በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስና በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ በተካሄደው ጦርነት ምክንያት ጋር ተፈጥሮም ባስከተለው አደጋ በትልቅ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ከመገኘታችን ላይ በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት በሚፈልጉና ለኢትዮጵያ በጎ በማያስቡ ጠላቶቻችን ተከብበናል።

እስከ ዛሬ ለተደረገልን ሁለገብ ርዳታ ምስጋናችን ታላቅ መሆኑን እየገለጥን የሰጣችሁን ጥቂትና አሮጌ መሣሪያ ዛሬ ጠላቶቻችን ከታጠቋቸው ጋር በመጠንም ሆነ በአይነት ሊመጣጠኑ የሚችሉ ስላልሆኑ የተለመደውን የአሜሪካዊያን ርዳታና ለጋስነት ኢትዮጵያ ዳግም ለመጠየቅ ተገድዳለች” የሚል ነበር።

አፄ ኃይለሥላሴ በአሜሪካ መንግሥት ሲያመልኩና ሲመኩ ኖረው፣ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ለአቀረቡት ጥያቄ የተሰጣቸው መልስ፣ የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም እንዲሉ “አሜሪካ ለኢትዮጵያ ደህንነትና መከላከያ የምትጨነቅበትና የምትረዳበት ምክንያት የሚሆን እዳ ወይም ግዴታ የለባትም” የሚል ነው።

ሶቭየት ሕብረት በአፍሪካ ቀንድ ራሷን ለማጠናከር፣ በባቤል መንደብ ሥርጥ አቅራቢያ በበርበራ ወደብ የአየር ኃይልና የባሕር ኃይል ሠራዊት መገልገያ የሆነ ታላቅ ወታደራዊ የጦር ሰፈርና የሎጂስቲክ ዴፖ ስትገነባ፣ አሜሪካኖች አሥመራ ከተማ ላይ የነበራቸውን ወታደራዊ የመገናኛ መደብ በሳተላይት ቴክኖሎጂ ስለተኩ ክልሉን ጥለው ለመውጣት እየተዘጋጁ ነበር።

በመሰረቱ ቢቸግርና የመሪዎቻችንም መደባዊ ጀርባና አመለካከት ከዚህ ውጪ ሊያይና ሊያስብ ባለመቻሉ እንጅ  በዓለም ከነበረን መልካም ስም፣ ከትግል ታሪካችንና በጊዜው የአፍሪካ መሪነታችን አንፃር ስልፋችን ከዓለም የቅኝ ግዛት ኃይሎችና ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር መሆን አልነበረበትም። ስህተቱ ከታሪክና ከስም አንፃር ብቻ የሚታይ ሳይሆን ተፈጥሮ ወይም መልካምድርና እንዲሁም ታሪክ ካስተሳሰረን የአካባቢያችን ኃይሎችና ከጎረቤቶቻችን ጋር እንደሚያናክሰንና የማንመከታቸውን የዘይት ባለ ሃብት የሆኑ ጠላቶች እንደሚገዛልን የታወቀ ነበር።

የማንክደው ነገር ቢኖር በሰሜን አሜሪካ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ተምረዋል። ከዚህ በተረፈ ኢትዮጵያ በአሜሪካኖች ምክንያት ጠላት መግዛት ብቻ ሳይሆን አንድነቷንና ሰላሟን ከማጣትና ከድህነት በስተቀር የተረፋት ወይም የተጠቀመችው ነገር አልነበረም። ውስጡን በማያውቁ ኢትዮጵያዊያንና እንዲሁም አንዳንድ ባዕዳን ብዙ የሚነገርለትን ሰሜን አሜሪካ ለኢትዮጵያ ስትሰጥ የነበረውን የመከላከያ ድጋፍ ብንመለከት፣ ለአርባ ሺህ ሠራዊት በ25 ዓመታት ውስጥ የቀረበልን መሣሪያ ጠቅላላ ዋጋ 250 ሚልዮን የአሜሪካ ዶላር ነበር።

የዚህ ገንዘብ መጠን አረቦች ለአካባቢው በጥባጮች በየዓመቱ ከሚለግሷቸው የገንዘብ መጠን በእጅጉ ዝቅ ያለ ነበር። ስለሆነም የአብዮቱ አንደኛው ተልዕኮ ኢትዮጵያን ይህንን ከመሰለ የተዛባ አሰላለፍ፣ የፖለቲካ ኪሳራና ወታደራዊ ከበባ አውጥቶ ሰላሟንና አንድነቷን ለማስከበር ነበር።

# ምዕራፍ ሃያ

# ድህረ አብዮት ኢትዮጵያ
# የሰላም ጥረት በኢትዮጵያዊያን መካከል

ለአያሌ ምዕት ዓመታት የጉልተኞች ገባር ጢሰኛና ሎሌ የሆኑ አርሶ አደሮች አሳዛኝ የሰቆቃ ኑሮ ምክንያት የነበረው ጉልተኛው ብቻ አልነበረም። ጉልታዊው ሥርዓትና ጉልተኛው ያስመረረው ከፋኝ ባይ አርሶ አደር ከባድ ወንጀል የሰራ፣ ነፍስ ያጠፋ ወይም ሰው የገደለ ወዘተ እንደሆን ከሕግ በመሸሽ እንደ ምንም ብሎ አንድ ነፍጥ ገዝቶ ወይም ቀምቶ፣ ቤት ንብረቱን ትቶ፣ ዱር ቤቴ በማለት፣ በቅሚያ፣ በዘረፋና በነፍስ ግድያ ለመኖር ይወስናል። ፋኖ ወይም ሽፍታ በመሆን መከረኛውን አርሶ አደር ሕብረተሰብ እየዘረፈ፣ እየገፈፈና እያሰቃየ መኖር በኢትዮጵያ ገጠር የተለመደ ነው ከማለት ይልቅ ባህል ሆኖ ኖሯል ማለት ነው የሚሻለው።

ይህ የከፋው ሽፍታ ወይም ፋኖ፣ ለፍቶ በማምረት ከሚኖረው አርሶ አደር በተሻለ እንደ ልቡ ያሻውን በልቶና ጠጥቶ፣ ለብሶና ተደስቶ የሚኖረው መስሉና አካሉ የሆነውን መከረኛ ገበሬ እየነጠቀና እየዘረፈ ነው። ሥራው ወይም በአጠቃላይ ኑሮው ቅሚያ፣ ዘረፋ፣ የገበሬውን በረት መድፈርና ጎተራ መገልበጥ፣ ከዚያም በላይ ሲከፋና ሲያመር የገበሬውን ጎጆ እስከ ማቃጠልና ገበሬውን ራሱን እስከመግደል ይደርሳል። ሕግ አስከባሪዎች ፈልገው የማይደርሱበት፣ ሕግ የማይገዛውና የማይዳኘው አጼ በጉልበቱ ወይም አጼ በነፍጡ ነው።

ሽፍታው ከሚያከናውነው እጅግ የከፋ እኩይ ተግባር ባላነሰ የሚያሳዝነው ሕዝቡን በተጫነው ኋላ ቀር አጉል ልማድ፣ ባህልና የማህበራዊ ንቃት ጉድለት የተነሳ ይህንን የመሰለውን ነፍሰገዳይ ወንጀለኛ ከማውገዝና ከመኮነን ፈንታ በጎ ተግባር እንደፈፀመ ጀግና የገጠሩ ሴት በየመንደሩ፣ እረኛው በየአረሁና በየዱሩ በዘፈን እያሞካሹና እያወደሱ ይበልጥ እንዲተብትና እንዲኩራራ ማድረጋቸው ነው።

የየክልሉና የየብሄረሰቡ ልማድና ባህላዊ አመለካከት በመጠኑም ቢሆን አንዱ ከሌላው የተለየ ቢሆንም፣ ሽፍትነት ወይም ፋኖነት እንደ ብሔራዊ ባህል ተወስዶ አገር አቀፍ ሆኗል። ልዩነት ቢኖር፣ በስም ወይም በአጠራር ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ ክልል ነዋሪ የሆነው ሕዝብ ከፋኝ፣ የመሃሉ ክልል ሕዝብ ፋኖ ሲለው የደቡብ ክልል ሕዝብ ደግሞ ሽፍታ በማለት ይጠሩታል።

ፋኖዎች ወይም ሽፍቶች ምግባራቸው እንደአራዊት ነው ለማለት ይቻላል። ቀን በየምሽጋቸው አድፍጠው ወይም ተኝተው በመዋል የሚንቀሳቀሱት እንደ አራዊት ሌሊት ብቻ ነው። በአብዮቱ አጥቢያ በኢትዮጵያ የነበሩት ፋኖዎች ቁጥር ወይም መጠን በውል

የሚታወቅ ባይሆንም እጅግ ብዙ እንደነበሩ ግን አያጠራጥርም። ምክንያቱም የየክልሉ አርሶ አደሮች ብሶታቸውን ሲገልፁ የነበሩት ሳይጋነን እውነት ከሆነ፣ ጀምበር ጠልቃ ከገባችና ምሽቱ ለዓይን ከያዘ በኋላ በሽፍታ የማይጎበኝ የገበሬ በረትና በሩ የማይንኳኳ የገበሬ ቤት የለም ነው የሚሉት።

ለሽፍታ አንገዛም፣ በሽፍታ አንበዘብዝም በማለት አርሶ አደሩ በወልም ሆነ በነፍስ ወከፍ ራሱንና ንብረቱን ለመከላከል የሞከረ እንደሆነ፣ ፋኖዎቹ አርሶ አደሩን ፍፁም ተስፋ ለማስቆረጥና የማንበርከክ ርህራሄ አልባ የሆነ ስልት አላቸው። እንደ አስፈላጊነቱ በነፍስወከፍ ወይም በወል ተጠራርተው በጥቂት ቁጥር ይሰበሰቡና አይበገሬውን ገበሬ ለማስደንገጥና ኃይላቸውን ለማሳየት ከእለታት አንድ ቀን በአንድ ባልተጠበቀ ለሊት በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ በገበሬው ጎጆ ላይ የተኩስ ውርጅብኝ ያወርዱበትና ይሄዳሉ።

በዚህ ሙከራ ገበሬው ያልተደናገጠና ሀሳቡን ያልለወጠ እንደሆነ ከገበሬው የቤት እንስሳት አንዱን ወይም ጥቂቱን ወስደው ይበሉበታል። በዚህም ምንም አይነት ለውጥ ካላሳየ ከበድ ወዳለው እርምጃ በማምራት ሕይወቱ የሆኑትን ማረሻ በሬዎቹን ያርዱበታል። በእነኚህ ሁሉ ርምጃዎች ገበሬው ያልተበገረ ከሆነ መኖሪያ ጎጆውን በላዩ በማቃጠል የመጨረሻ ቅጣት ይቀጡታል።

ይህንን የመሰለ ተደጋጋሚ ብቻ ሳይሆን ፍፁም ሥርነቀል የሆነ ቅጣትና ጥቃት የደረሰበት አርሶ አደር ያለው ምርጫ፣ መሸነፉን አምኖና ተቀብሎ በቀረ ሕይወቱ ለፋኖው ገባርና ተገዥ ሆኖ መኖር ያለዚያም ከፋኝ መረረኝ ብሎ እሱም በተራው ቤት ንብረቱን ትቶ ዱር ቤቴ በመሆን ፀሩ የሆነውን የሽፍታ ጎራ ማጠናከር ነው። ማረሻ በሬዎቻቸውን ያጡና ቤታቸው የተቃጠለባቸው አርሶ አደሮች መልሰው በማንሰራራት ቤት ንብረት ለማፍራት የሚቻላቸው ስላልሆነ በአመዛኙ ምርጫቸው ከፋኝ ብለው የሽፍታውን ቁጥር ማበራከት ነው።

አርሶ አደሩ የሕብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን በተለያየ የሥራ መስክ በገጠር የሚኖረው ባተሌና በተለይም ነጋዴው ሕብረተሰብ ዘላለም ሽፍታ ሲያሰቃየው፣ የገዥው መደብ አባላትና በጠቅላላውም መንግሥት ተብዬው በሰላም የሚኖሩት ሕዝቡን ከመቀማትና ከመዝረፍ በስተቀር ሽፍታው የፖለቲካ ተልዕኮ ወይም ዓላማ ስለሌለው ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ማግስት አብዮቱ የመጣባቸው መላው አድሀሮት ከጀመሩት ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ተግባር ሌላ በኢትዮጵያ ገጠር የተከሰተው ሌላ ነገር፣ ሽፍቶች በጠቅላላው መንግሥት የለም፣ መንግሥት ፈርሷል፣ ሕግና ሥርዓት የለም በማለት ከሚያደፍጡበት ደን ወጥተው በቀን ብርሃን በሕዝቡ ውስጥ እየተዘዋወሩና ሕዝቡን እያስፈራሩ መንግሥትን በመተካት እነሱ ሕግም ዳኛም፣ አስተዳዳሪም ለመሆን በመሞከር በአንዳንድ ክልሎች ግብርና ቀረጥ እስከመቀበል መድረሳቸው ነበር።

የደርጉ ልዑካን ቡድኖች አዘውትረው አርሶ አደሩን በያለበት ለመጎብኘት ችግሩንና ብሶቱን ለመረዳት ከሚያደርጉት ጥረት ባሻገር ለመሬቱ አዋጅ ተግባራዊነትና ብሎም ለመጭው ረጅም የመደብ ትግል ለማዘጋጀት በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ከአርሶ አደሩ ሕብረተሰብ የሚቀርብላቸው አቤቱታ፣ "ይህ አብዮት ከሽፍታ ተገዥነትና ተበዝባዥነት የሚያድነን ወይም ነፃ የሚያወጣን መቼና እንዴት ነው" የሚል ነበር።

የደርጉ ጉባዔ ብዙ ያሰበበትና የተወያየበት ቢሆንም ለገጠሬው ሕዝብ ጥያቄ ፈጣን የተግባር መልስ ለመስጠት በምንችልበት ሁኔታ ላይ አልነበርንም።ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች መማሪያ እየተቀበሉ ከሚወጉን ገንጣዮችና አስገንጣዮች በተጨማሪ በየክልሉ እየተሰበሰቡ የሚወጉን የታጠቁ ፊውዳላዊ ቡድኖች በርካታ ስለነበሩ፣ ለእነኚህ ፀረ-ሕዝቦች

***መፍትሄ ሳናገኝላቸው ተቻኩለን ከአገሪቱ ሽፍቶች ወይም ፋኖዎች ጋር ብንጋጭ ወይም ብንዋጋ የተርብ ቤት እንደመቀስቀስ ስለሆነ አንፃራዊ ሰላም የነበረው የኢትዮጵያ ገጠር ሰላሙ ደፍርሶ እንዳይቸገር ሰላማዊ መፍትሄ መፈለግ ነበረብን።***

***ይህ የፋኖዎች ጉዳይ በድጋሚ በደርጉ ጉባዔ ላይ የተነሳው በመሬት ለአራሹ አዋጅ ላይ በምንወያይበት ጊዜ ስለነበረ አዋጁ በጉባዔው ፀድቆ ከታወጀ በኋላ ብዙ ጊዜ ሳናጠፋ በወቅቱ በመላው ኢትዮጵያ ዱር ቤቱ ብለው ለሚኖሩ፣ ከፋኞች፣ ሽፍቶችና ፋኖዎች ከመሬቱ አዋጅ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብሔራዊ የሰላምና የምህረት አዋጅ አወጅን። የአዋጁም ይዘት እንደማስታውሰው ከዚህ የሚከተለው ነበር።***

## አዋጅ

አሮጌው ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር አገራችንን ከሥልጣኔና ከእድገት እርምጃ ገትቶና ወደኋላ ጎትቶ፣ ሕዝቡን አደንቁሮ፣ መዝብሮና ረግጦ በመግዛት ከአደረሰው የበደል ፅዋ ሲጎነጭ የኖረው መላው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ቢሆንም፣ ታሪኩን በሙሉ የጉልተኛ መጫወቻና መኳንንት ገባርና ሎሌ በመሆን የኖረው የኢትዮጵያ አርሶ አደር ስቃይና ሰቆቃ በየትኛውም ሕብረተሰብ ላይ ከደረሰው በጣም የከፋ ነው።

የአያሌ ምዕት ዓመታት ስቃይና ሰቆቃ አይነቶችንና ምክንያቶችን በዚህ የሰላምና የምህረት አዋጅ ዘርዝረን የምንወጣው ባይሆንም፣ አንዱን፣ ለዚህ አዋጅ መታወጅ ምክንያት የሆነውን በአጭሩም ቢሆን ከዚህ በላይ የተረከነው የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች አሳዛኝና አስከፊ ኑሮ ወይም ሕይወት በታላቁ ሕዝባዊ አብዮታችን አፍላ ዘመን ለአንደና ለመጨረሻ ተወግዶና ከከፋኞች ህሊና ተፍቆ ታሪክ እንዲሆን ማድረግ የአብዮታዊው መንግሥት ብቻ የታሪክ ወይም የሥራ ግዴታና ድርሻ ሳይሆን የመላው የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይም የአርሶ አደሮች ሁሉ ታሪካዊና አብዮታዊ ግዴታም መብትም ነው።

እስከ ዛሬ በጉልታዊው ሥርዓትና ጉልተኞች በፈፀሙባችሁ ግፍና በደል ተማርራችሁ እና ተከፍታችሁ፣ ቤትና ትዳራችሁን ትታችሁ፣ ዱር ቤቴ ለማለት የተገደዳችሁ፣ የአካላችሁ ክፋይ በሆነው ሰላማዊና አምራች አርሶ አደር ወንድማችሁ ላይ ህገ ወጥ ሥራ ስትሰሩ ለቆያችሁ ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ አብዮታዊው መንግሥትና ወገናችሁ የሆነው ሰፊው አርሶ አደር ምህረት አድርገውላችኋል።

ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን በወረረችበት ጊዜ ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው አገራቸውንና ወገናቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ያወጡት የኢትዮጵያ አርበኞች ድርጅቶች የመሠረት ድንጋይ ሆነው በማገልገል ታሪክ የሰሩት በጊዜው የነበሩና በሥርዓቱ የተከፉት ስለነበሩ እናንተን ሲያሰቃይ ከነበረው ከአሮጌ ሥርዓትና የሥርዓቱ ተጠቃሚና አራማጅ ከሆኑት ከአድህሮት ጋር የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያደርገው ትግል ውስጥ ጉብታችሁ በመሳተፍ ታሪክ እንድትሰሩ ወገናችሁ ከሆነው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና ከአብዮታዊው መንግሥት አብዮታዊ ጥሪ ቀርቦላችኋል።

የገጠሩን የእርሻ መሬት የደሀው ገባር አርሶ አደር ይዞታ በሚያደርገው አብዮታዊ አዋጅ ተጠቅማችሁ፣ የገጠሩ መሬት ለአርሶ አደሩ ተከፋፍሎ ከማለቁ በፊት ፈጥናችሁ ወደ ተወለዳችሁበት ቦታ ወይም ወደ ፈለጋችሁበት ቀዬና ቀበሌ ከነትጥቃችሁ በመግባትና የመሬት ባለቤት በመሆን፣ አምርታችሁ በሰላም ከመኖር ባሻገር በትግል ልምዳችሁና በግል መሣሪያችሁ በገበሬ ቀበሌ ማህበራት የአብዮት ጥበቃ ተቋማት ውስጥ በአባልነት በአመራር አካልነት ወገናችሁን አርሶ አደሩን መደብ እንደምትከሱ፣ አገራችሁን እንደምታገለግሉና ለአብዮቱ ዘብ እንደምትቆሙ እምነታችን ፅኑ ነው።

ኢትዮጵያ ትቅደም

ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደ ተገለጸው በኢትዮጵያ ገጠርና በአርሶ አደሩ መካከል ለአያሌ ዓመታት ስር ሰዶ የኖረው ችግርና የአርሶ አደሩ ስቃይ ያበቃበት ሰላማዊ መፍትሄ ተገኝቶ፣ ዱር ቤቴ ብሎ በቅሚያና በዘረፋ የኖረው ፋኖ፣ ከፋኝና ሽፍታ አዋጁ በሰጣቸው ዋስትና ተማምነው፣ የተደረገላቸውን ጥሪ ተቀብለው፣ በመላው ኢትዮጵያ የነበሩ በሙሉ ከነትጥቃቸው በመግባት የእርሻ መሬት እየተቀበሉና ከሰላማዊ አርሶ አደር ጋር እየተቀላቀሉ በማምረት ሰላማዊ ኑሯቸውን ጀመሩ።

እንደ ተጠየቁትና እንደተጠበቀባቸውም የአብዮቱን ደህንነት በመጠበቅ የአድሃርያንን ጥቃት ከመከላከል አልፈው ሃገርን ከውስጥ ገንጣዮችና ከውጭ ወራሪዎች ለማዳን በተደረገው የእናት ሃገር ጥሪ ፈጥነው አዎንታዊ መልስ በመስጠት፣ በሕዝባዊው ሠራዊትና በመደበኛው የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ እየተመለመሉ በመሰለፍ ያከናወኑት ፍልሚያ ከፍተኛና ታሪካዊ ነበር።

ከፋኞች ወይም ሽፍቶች በአዋጅና የሰላም ጥሪው ከህብረተሰቡ ጋር በመቀላቀላቸውና ትጥቃቸው የግል ንብረታቸው እንዲሆን ስለተፈቀደላቸው የገበሬውን የአብዮት ጥበቃ ኃይል በማጠናከር የአብዮቱ ዘብ ከመሆን በስተቀር የፈጠሩት አንዳችም ችግር ስለመኖሩ ከየትኛውም ክልል የደረሰን ሪፖርት አልነበረም።

ለብዙ ዘመናት አርሶ አደሩን ሲዘርፉና ሲገፉ የኖሩ ፋኖዎች በተደረገላቸው ምህረትና የሰላም ጥሪ ወደ ሰላማዊ ኑሮ ተመልሰው አምራች ዜጋ መሆን ከቻሉ፣ በተመሳሳይ ወንጀልና ምናልበትም ከወንጀልም ባነሱና በቀላሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች በአገራችን እያሌ ወህኒ ቤቶች ውስጥ ታስረው ለሚሰቃዩት ዜጎች ለምን ነፃነታቸውን ሰጥተን በተመሳሳይ አምራች ዜጎች አናደርጋቸውም? የሚል ጥያቄ አንስተን በደርጉ የእቅድ ኮሚቴ ውስጥ ባሉ ጥቂት ጓዶች መካከል ከተወያየን በኋላ ነፃነታቸውን የማንሰጥበት ምክንያት አይታዩንም በማለት ሁላችንም በሃሳቡ ተስማማንበት።

ነፃነታቸውን በመስጠቱ መሰረታዊ ሃሳብ ላይ ብንስማማም፣ እንደ ከፋኞቹ በአገሪቱ ወህኒ ቤት ያሉትን እስረኞች በሙሉ በአዋጅ ፈተን ብንለቅ አድህሮት፣ ሕዝቡን ለማዘረፍና ለማስፈጀት ብለው የአገሪቱን ወንጀለኞች ፈትተው ለቀቋቸው የሚል ዘመቻ ከፍተው ወሬውን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያዛምቱት ስለሚችሉ፣ ምንም አይነት ፍንጭ ሳንሰጥና በዜና መልክም ሳይሰራጭ መልቀቅ ነው ብለን የተስማማንበትን ውሳኔ፣ በሕግ ለደርጉ ጉባዔ የተሰጠውን ለእስረኞች ምህረት የማድረግና የአመክሮ ሕግን በመጠቀም በጥቂት ወራት የአገሪቱን ወህኒ ቤቶች ባዶ አደረግናቸው።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በአብዮቱ ማግስት በ1966 ዓ.ም ሰኔ ወር መላውን የአገሪቱን የፖለቲካ እስረኞች ፈተን በመልቀቅ የእስረኛውን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አቃለነው ነበር። ነፃነታቸውን ያገኙት እስረኞች ወደየትውልድ ቀየና መንደራቸው እየሄዱ በገበሬው ማህበራት ውስጥ በመሰግሰግና በልዩ ልዩ የሥራ መስክ በመስማራት አምራች ዜጎች ከመሆንና በብዛትም ልጅነትና ጤንነት ያላቸው በሚሊሻውና በመደበኛው ሠራዊት ውስጥ ስለተመለመሉ፣ በመፈታታቸው ምክንያት የተከሰተ ችግር አልነበረም።

በአንባቢ ዘንድ ይታወስ እንደሆን በአብዮት አደባባይ የአገሪቱን ወህኒ ቤቶች ወደ ሆስፒታልና ወደ ትምህርት ቤት እንለውጣቸዋለን ያልነው በዚህ ጊዜ ነበር። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበሩትን እያሌ ወህኒ ቤቶች በሙሉ እናጠፋለን በሚል ሃሳብ ሳንገበዝ አብዛኛውን ወደ ሆስፒታልና ወደ ትምህርት ቤትነት ለመለወጥ ፍላጎታችን ተምኔታዊ ወይም እንደ ጆርጅ ኦርዌል "የእንስሳት የወል እርሻ" አይነት ልብወለድ ሳይሆን ተግባራዊ

ሊሆን የሚችል ነበር። ሆኖም በጥባጭና አፍራሽ በበዛበት ሃገር ንፁህ ማን ይጠጣል እንዲሉ በዚህ ረገድ ያሰብነው ሃሳብ ስኬታማ አልነበረም።

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

## ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ችግር ሰላማዊ መፍትሄ ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች

ኤርትራ የተባለውን ክፍለ አገራችንን በተመለከተ ስለ ክፍለ ሃገሩ ሕዝብ ማንነት፣ ክፍለ ሃገሩን ከኢትዮጵያ አስተዳደር ለመነጠል ወይም ለመገንጠል መንስኤ ስለሆኑት ምክንያቶች፣ ችግሩ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ክፍለ ሃገሩ ከኢትዮጵያ እስከ ተገነጠለበት ጊዜ ድረስ በገንጣዮችና በኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች መካከል የተደረገው ትግል የወሰደውን ጊዜና ያስከፈለውንም መስዋዕትነት በስፋትና በዝርዝር በትግላችን ቅፅ-2 ለመተረክ ይሞከራል።

የዚህ ምዕራፍ አርዕስት እንደሚገልፀው ላስረዳ የፈለኩት፣ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ለ13 ዓመታት በኢትዮጵያዊያን ወንድማማቾች መካከል ይካሄድ በነበረው የትጥቅ ትግል ምክንያት የሚፈስሰውን ደም በአስቸኳይ ለማቆምና ችግሩን በጦር ሜዳ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት በአብዮቱ የመጀመሪያ ዓመታት የተደረጉትን ጥረቶች ነው።

ዓላማዩ ስለ ኤርትራ ለመተረክ ባይሆንም ወደ ተደረጉት የሰላም ጥረቶች ዝርዝር ከማምራቴ በፊት፣ ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ለመወያየት ገንጣዮቹ እስኪሰለቹን ድረስ ደግመን ደጋግመን የጠየቅንበት ዋና ምክንያት ከሆነው የሰላም ፍላጎታችን በተጨማሪ የመገንጠሉ ትግል ስለተጀመረበት፣ ኢትዮጵያ የኤርትራ ቅኝ ገዥ ነች የተባለችበት ምክንያት ፈፅሞ ሊገባን ስላልቻለ ወንድሞቻችን እንደዚያ እምርረው ለረጅም ጊዜ ሃገርና ወገናቸውን ለመውጋት የተገደዱት ያለምክንያት እንዳለመሆኑ መጠን ምክንያታቸውን ለማወቅ ታላቅ ጉጉት ስለነበረን የእነሱን እውነት ያስረዱናል በሚል ተስፋ ነበር።

የኢጣሊያ መንግሥት በ18ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ ከሰሜኖቹ የአገራችን ክልሎች አንዱ የሆነውን ባህረ ነጋሽ ክፍለ ሀገር ከወረረ በኋላ ክፍለ ሃገሩን ኤርትራ የተባለ ስም ይስጠው እንጅ ከዚያ በፊት በባህረ ነጋሽ ምድር፣ መንደር ወይም ከተማ፣ ወንዝ ወይም ተራራ፣ ግለሰብ፣ ማህበረሰብ ወይም ብሔረሰብ ወዘተ ኤርትራ በሚባል ስም የሚጠራ አንዳችም ነገር በታሪክ ስለማይታወቅ፣ የጆብሃና የሻዕቢያ መሪዎች ፋሽስታዊ ቅኝ ገዥዎች በሰጧቸው ስም መኩራራታቸው ብቻ ሳይሆን መስከራቸው በጣም ያስገርመን ነበር።

የኤርትራን ክፍለ ሀገር የሚያካትተው የአገራችን ሰሜናዊ ክልል ዛሬ አሥመራ በመባል የሚጠራውን ከተማና አካባቢውን ጨምሮ ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባህል ወዘተ ማዕከል፣ ርዕሰ ከተማ ወይም መንበረ መንግሥት ሆኖ የኖረውን፣ በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የተፈራረቁ ከመቶ በላይ ነገሥታት መናኸሪያና አፅመ ርስት እንዴትና በምን ሁኔታ ቅኝ ግዛታቸው እንዳደረጉት ይደንቀን ነበር።

ኤርትራ የተባለውን ክፍለ ሀገራችንን የመገንጠል ዓላማ አንግቦ የተነሳውና "የኤርትራ ነፃ አውጭ ግምባር" በአረብኛ "ጀብሃ" በማለት ራሱን የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት የተመሠረተው በ1953 ዓ.ም በኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር መንግሥት ቀስቃሽነት፣ አነሳሽነት፣ ግፊትና አደራጅነት በግብጽ ርዕሰ ከተማ በካይሮ ነው።

ግብፆች አባይን ከምንጩ የመቆጣጠር ዓላማቸውን የሞት ሽረት ጉዳይ አድርገው በኢትዮጵያ ላይ ያልሞከሩት ጥቃት፣ ያላደረጉት ጥረት ያለመኖሩንና ለዘለዓለም የሚተኙልን ያለመሆናቸውን ስለምናውቅ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ የመገንጠሉ ዓላማ እውነት ከኢትዮጵያዊያን ፍላጎት የመነጨ ነው ወይንስ ግብፃውያን በኢትዮጵያዊያን ምንደኞቻቸው እጅ ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚያካሂዱት የእጅ አዙር ጦርነት ነው? የሚል ጥያቄ ነበረን።

እንደሚታወቀው አብዮቱ የኤርትራን ችግር የተረከበ እንጅ የፈጠረው አይደለም። ከእነ ጄነራል አማን ጀምሮ ከብዙ የክልሉ ተወላጆችና ከሌሎችም ኢትዮጵያዊያን ስለ ኤርትራ ችግር በምንወያይበት ጊዜ የሚነገረው፣ ወንበዴና ከሃዲ እያላችሁ የምትጠሯቸው ታጋይ በረሃኞች በተለይም ሻዕቢያዎች ትግላቸው ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ማህበር ጋር እንጂ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አይደለም እየተባለ ነው።

ለ13 ዓመታት የወንድማማቾችን ደም ሲያፋስስ የቆየውን ጦርነት በአስቸኳይ ለማቆም ብቻ ሳይሆን ገንጣዮቹ ትግላቸው ከማህበራዊ ሥርዓቱ እንጅ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አይደለም ስለተባለና አብዮቱም ለኤርትራ ችግር አማራጭ የሌለው ብቸኛ መፍትሄ ይሆናል የሚል እምነት ስለ ነበረን ዘውዱ በተገረሰሰ ማግስት ገንጣዮቹ ከኢትዮጵያ አብዮት ጋራ እንዲቀላቀሉ አብዮታዊ ጥሪ ከማድረግ በተጨማሪ በተከታታይ ከዚህ የሚከተሉትን የሰላም ጥሪዎች አደረግን፣

1ኛ/ በኢትዮጵያ አብዮታዊያን አስተያየት የውስጥ እግር እሳት ያህል አንገብጋቢ የነበረው የኤርትራ ችግር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰውሮ ወይም ምስጢር ሆኖ ሲኖር ፓርላማው ተወያይቶበት ሰላማዊ መፍትሔ ያገኝለት ዘንድ የቀረበለት በአብዮቱ ማግስት በ1966 ዓ.ም በነሐሴ ወር ውስጥ ነው።

2ኛ/ ጄነራል አማን በቅድመ አብዮት "የኤርትራን ጉዳይ ለኔ መተው ትችላላችሁ፣ በረሃኞቹ ትግላቸው ከፖለቲካ ሥርዓቱ እንጅ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አይደለም። እነሱ ቀድመው አብዮት ሲያካሂዱ የተኛችሁት እናንተ ናችሁ"ብለው ቃል በገቡልን መሠረት የሰላም መፍትሄ እንዲያፈላልጉ ደርጉ ወደ ኤርትራ የላካቸው 1966 ዓ.ም በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ነው።

3ኛ/ የኤርትራ ክልል ሽማግሌዎች መንግሥትንና ገንጣዮችን ለሰላማዊ መፍትሄ በጠረጴዛ ዙሪያ ለማገናኘት እንስራ ዘንድ መንግሥት ብቻውን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለኤርትራ ክፍለ ሀገር የተኩስ ማቆም አዋጅ ያውጅ ብለው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የተኩስ ማቆም አዋጅ በማወጅ ሠራዊታችን ሳይንቀሳቀስ በየጦር ሰፈሩ ታቅቦ እንዲቀመጥ አደረግን። መንግሥት የወሰደውን የሰላም እርምጃ እንደ ድክመት ገምተው በሁኔታው



በመጠቀም የክልሉን ርዕሰ ከተማ አሥመራን ለአመታት በአስር ኪ/ሜ ርቀት መክበብ የቻሉት በዚሁ ዓ.ም በነሐሴ ወር መገባደጃ ነበር።

4ኛ/ በአገሪቱ የሕዝብ ምክር ቤት ወይም ፓርላማ የኤርትራ ችግር መፍትሄ እንዲፈለግለት በጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ አማካኝነት ቀርቦ በሕግ መምሪያውና በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አባሎች በጋራ ውይይት እየተደረገበት ሳለ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ሕዝብ ተወካዮች፣ ገንጣዮቹ አሥመራን በመክበባቸው ክፍለ ሃገሩን ከኢትዮጵያ እንደገነጠሉ ቆጥረው የድል አጥቢያ አርበኛ ለመሆን በፓርላማው የሚደረገውን የውይይት መድረክ ረግጠው በመውጣት ወደ ክፍለ አገራቸው ተመለሱ።

የገንጣዮቹን ከበባ በሙሉ ባናስወግደውም አሥመራን የመቆጣጠሩ ተስፋቸው እንዲመክን ከተደረገ በኋላ፣ በጓድ ብርሃኑ ባይህና በልጅ ሚካኤል እምሩ የተመራ አንድ ቡድን ወደ ኤርትራ ተልኮ፣ የፓርላማውን ውይይት ረግጠው የሄዱትን የሕዝብ ተወካዮች ለኤርትራ ነፃነትና እንዲሁም ኤርትራን መልሶ ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሃድ የታገሉ የሃገር ፍቅር ማህበር አባላትና የአመራር አካላት የሆኑ አርበኞችን፣ ሌሎች በክልሉ የታወቁ የሕዝብ መሪዎችና መንፈሳዊ አባቶችን በክፍለ ሃገሩ ምክር ቤት አዳራሽ በመሰብሰብ በአዲስ አበባ የተጀመረው ውይይት እንዲቀጥል የተደረገው 1967 ዓ.ም በጥቅምት ወር ነበር።

ለኤርትራ ችግር የሰላም መፍትሄ ፍለጋ ከተሰበሰቡ የክልሉ ነዋሪ ሽማግሌዎች አብዛኛው "በወደቀው መንግሥት ጊዜ ማንም ሳይጠይቀን በራሳችን አነሳሽነት ለሰላም መፍትሄ ግኝት ብዙ ደክመን ከመንግሥት ወገን ደጋፊና አዳማጭ አላገኘንም። ዛሬ ጉዳዩ ከእኛ እጅ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ሃገር ወጥቶ የአረቦች ልዩ ጉዳይ ስለሆነ የሚቻላችሁና የምትደመጡ ቢሆን እኛ የምንመክረው የአረብ መንግሥታት ለሚፈለገው የሰላም መፍትሄ ግኝት ይተባበሩንና በገንጣዮቹ ላይ ተፅዕኖ ያደርጉልን ዘንድ እንዲጠየቁ ነው" አሉ።

ሃሳባቸው ከሞላ ጎደል ትክክል መሆኑ ታምኖበት በ1967 ዓ.ም ታህሳስ ወር አንድ በከፍተኛ ደረጃ የተዘጋጀና የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጅ የሆኑ ሰዎችን ያካተተ

የልዑካን ቡድን ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ በግብጽ፣ በሊቢያ፣ በደቡብና ሰሜን የመን፣ በአልጄሪያ፣ በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በሳዑዲ አረቢያ፣ በሱዳንና በሶማሊያ ግዛት እየተዘዋወረ የመንግሥታችንን መልዕክት ለመሪዎቹ በማቅረብና ስለ ሰላም ፍላጎታችን በማነጋገር ርዳታቸውን ይለግሱን ዘንድ ታላቅ ጥረት አደረገ።

ከእኛ አይቅር ብለን ነው እንጂ አንባቢ ሊገምት እንደሚችለው ከነዚህ ከጠቀስኳቸው አገሮች መካከል በቁጥር የበለጡት ኢትዮጵያን የነከሱና ሊያጠፏት የተነሱ ስለነበሩ ልዑካኑ ኢትዮጵያዊያን በተለይ በግብጽ በኢራቅና በሶሪያ መሪዎች ትዕቢትና አቀራረባቸው በጣም አዝነዋል።

ከተቀሩትም በከፊል በዲፕሎማሲያዊ አቀራረቡ ከአንገት በላይ ግን በጨዋነት ልዑካኑን ተቀብለው ቢያስተናግዱም ከልብ ይረዱናል የሚል እምነት አልነበረም። ሱዳንና የመኖችን የመሰሉ አገሮች እንዲህ እንደጀመራችሁት ተስፋ ሳትቆርጡ የሰላም መፍትሄ የምትሉትን የፖለቲካ ፕሮግራም ከነአፈፃፀሙ ብታዘጋጁ ያንን መሣሪያ አድርገን ለሰላም ግኙቱ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን ስላሉን በኤርትራ ሕዝብ በራሱ ፍላጎት ካፈረሰው ፌዴሬሽን ለክፍለ ሃገሩ ሕዝብ ከሰጠው መብትና ሥልጣን እጅግ የላቀና ግልጽ የሆነ፣ ለማስረጃም ያህል ከመከላከያ፣ ከውጭ ጉዳይና ከገንዘብ ማተም በስተቀር የቀረውን ማናቸውንም መብትና ሥልጣን ለክልሉ አመራር የሚሰጥ ‘አዲስ የውስጥ አስተዳደር’ መፍትሄ ከነአፈፃፀሙ ዝርዝር ፕሮግራም አውጥተን ባቀረብንላቸው ጊዜ በአቀራረባችን ወይም በመፍትሄው ይዘት ተደስተው “ከዚህ በላይ የእነሱን የመገንጠል ጥያቄ ብቻ ታፀድቁ እንደሆነ እንጂ በሰላማዊ መፍትሄ ረገድ ሌላ ሊደረግ የሚችል ነገር ይኖራል ብለን አናምንም” በማለት አበረታቱን።

በዚህ ተስፋ ተበረታትተን የፖለቲካ ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ በአዲስ አበባና በአሥመራ ከበቂ ገንዘብና የሰው ኃይል ጋር የሰላም ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ ቢሮ አቋቁመን በመቀጠልም በተከታታይ ካርቱም፣ ሰነዓና ካይሮ ላይ ሌሎች ቢሮዎች ለመክፈት እየተዘጋጀን ነበር።

5ኛ/ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ያወጅነው በዚሁ ጊዜ ስለነበረ የፕሮግራሙን አጠቃላይ አላማና ግብ መሠረት በማድረግ የመንግሥቱ ተቃዋሚ ኃይሎች፣ በግምባር ቀደምትነት የኤርትራ ገንጣዮችና ሌሎችም ኢሕአፓን ጨምሮ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ነፃ አውጭነን የሚሉ የብሔረሰብ ድርጅቶች በሙሉ ያለአንዳች ቅድመ ግዴታ ድርጅታዊ ህልውናቸውና የፖለቲካ ፕሮግራማቸው የተከበረ ሆኖ፣ አሮጌውን የኢትዮጵያ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበርና የጊዜአችንን ፀረ-ዲሞክራሲና ፀረ-ሰላም የቅኝ ግዛት ኃይሎችን፣ የዘር መድሎንና ኢምፔርያሊዝምን እንቃወማለን ካላችሁ፣ በዚህ መለስተኛ ፕሮግራም በመሰባሰብ እና በኢትዮጵያ አንድነት ማዕቀፍ ውስጥ የጋራ ሃገር ለመፍጠርና ለመገንባት የሚያስችለን ውይይት የምናደርግበት የጋራ መድረክ እንፍጠር የሚል ብሔራዊና አብዮታዊ ጥሪ አደረግን።

6ኛ/ ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራሙ ጋር አከታትለን ፕሮግራሙን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ሕዝቡን የሚያነቃና የሚያደራጅ ጊዜያዊ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት የተባለ ተቋም በሕግ ስናቋቁም የኤርትራ ገንጣዮች ግምባር ቀደም በማድረግ የተለያዩ የፖለቲካና የብሔረሰብ ድርጅት ተወካዮች የሕዝብ ማደራጃው ተቋም ውስጥ በአባልነትና በአመራር አካልነት እንዲሳተፉ ሌላ ብሔራዊና አብዮታዊ ጥሪ አደረግን።



ላደረግነው የሰላም ጥሪ ከሻዕቢያ፣ ከጀብሃ፣ ከወያኔና ከኢሕአፓ በስተቀር በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር የነበሩ የፖለቲካና የብሔረሰብ ድርጅቶች በሙሉ አዎንታዊ መልስ ፈጥነው በመስጠት የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤቱንና የፖለቲካ ትምህርት ቤቱን አቋቋሙ።

ለማጠቃለል የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሲባል ወደ መላው የአረብ አገሮች ልዑካን የላክነው፡ 1ኛ/ ደርግ በተቋቋመበት ማግስት 2ኛ/ ዘውዱ በተገረሰሰበት ማግስት 3ኛ/ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራም በታወጀ ማግስት 4ኛ/ አዲሱን የውስጥ አስተዳደር እያዞርን ባስተዋወቅንበት ወቅት ነበር።

ለኤርትራ ገንጣዮች በተለይ ብሔራዊ የሰላም ጥሪ ያደረግነው፣

1ኛ/ ደርግ በተቋቋመበት ማግስት

2ኛ/ በጄነራል አማን ሚካኤል አንዶም አማካኝነት ገንጣዮቹ ባሉበት በኤርትራ ምድር

3ኛ/ እኔ ስለደርግ መቋቋምና ዓላማው የአዲስ አበባና የአካባቢውን መለዮ ለባሾች በመሰብሰብ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መግለጫ በሰጠሁበት በሐምሌ 7 ቀን 1966 ዓ.ም

4ኛ/ ዘውዱ ሲገረሰስ

5ኛ/ በእድገት በሕብረት የሥራ ዘመቻ ስምሪት ጊዜ

6ኛ/ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በገሀድ የአገራችንን ድንበር ጥሶ ወረራ ሲጀምር

7ኛ/ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ስናውጅ

8ኛ/ የኤርትራን ችግር ይፈታል ብለን አዲስና ልዩ የሰላም ፕሮግራም ከውስጥ አስተዳደር መብት ጋር ባወጅን ጊዜ ነበር፤

9ኛ/ የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤትን ባቋቋምንበት ጊዜ ለእነዚህ ሁሉ የሰላም ጥረቶቻችንና ጥሪያችን የተሰጠን መልስ ከሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ጋር ተባብረውና ተደምረው እንካችሁ ጥይት ነው። ይህም ሆኖ ተስፋ ባለመቁረጥ የሰላም ጥረቱን አላቆምንም።

በሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ላይ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት የማያዳግም ድል ከተቀዳጀ በኋላ፣ በሶሻሊስት አገሮች ገላጋይነት ማለትም በሞስኮ፣ በበርሊን፣ በሃቫና፣ በኤደንና በካርቱም በመጨረሻም በሮም ከተማ የሰላም ጥረትና ድርድሩ እንደቀጠለ ነበር። የእነዚህ ዝርዝር በቅፅ 2 ወደፊት በሰፋት ይገለጣል።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

# ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለማምራት በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የተደረጉ የሰላም ጥረቶች

ጎረቤታችን ከሆነው ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለማምራት የተደረጉትን የሰላም ጥረቶች ከመግለጽ በፊት በቅደሚያ፣ አፍሪካን ያሰለቸው የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግሥታት ጭቅጭቅ፤ በሁለቱ አገሮች መካከል ለተደረጉ አያሌ የወሰን ላይ ግጭቶችና ብሎም ወደ ጦርነት የወሰደን ምክንያት ምን እንደሆነ፣ በአፍሪካ ቀንድ ከኢትዮጵያ የተለየ ወይም የተነጠለ፣ ራሱን የቻለና በነፃ መንግሥትነት ታሪክ የሚታወቅ ሕዝብ ወይም ሃገር ስላለመኖሩና እንዲሁም ዛሬ ሶማሊያ በመባል የሚታወቀውን ጎረቤት ሕዝብ ማንነትና ምንነት ሰፋና ዘርዝር አድርጌ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው ብዬ አስባለሁ።

ስለሶማሊያ ሕዝብ መንግሥታዊ ህልውና ብጀምር፣ ከኢትዮጵያ የተነጠለ ወይም የተለየና ራሱን የቻለ ብሔራዊ ህልውናና ነፃነት የነበረው ሕዝብ ወይም መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ መኖሩ በታሪክ አይታወቅም። በታሪክ የሚታወቁት፣ በአፍሪካ ቀንድ ጠርዝ በቀይ ባሕርና ሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ይኖሩ ከነበሩት ጥንታዊ የባንቱ፣ የኦሮሞ፣ የአፋር ወዘተ ማህበረሰቦች መካከል አንዱ የሆነው የሶማሊያ ማህበረሰብ ነው።

የሶማሊያ ማህበረሰብ ሶማሊኛ ቋንቋ ከማይናገሩት ከሌሎቹ ከክልሉ ነዋሪ ማህበረሰቦች ጋር በከብቶች የግጦሽ መሬት፣ በውሃ እና በሌሎችም ምክንያቶችና ቅራኔዎች ሲጋጭ የኖረ የሕብረተሰብ ክፍል ነው። በክልሉ ከነበሩ ነባር ወይም ጥንታዊ አፍሪካዊ ህብረሰተቦች ጋር የተለያዩ ነገዶች ከማዕከላዊ ምሥራቅና ከእስያ ወደ ቀንዱ እየመጡ የተቀላቀሉበትን ጊዜና የሶማሊያ ማህበረሰብ በአፍሪካ ቀንድ ጠርዝ በባህሩ ዳርቻ ከመስፈሩ በፊት የት እንደነበረ የሚያስረዳ የታሪክ ፍንጭ ወይም መረጃ እንዳለ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጌ አልተሳካልኝም።

የማህበረሰቡ መሰረታዊ የዘር ቅምር አፍሪካ-እስያዊ ቢሆንም በታሪክ ሂደትና በራሱ ማህበረሰቡ እድገት የማህበረሰቡ አባላት ተዋህደው በቆዳ፣ በተክለ ሰውነታቸው ፍፁም ተመሳሳይ ከመሆናቸው ሌላ የሚናገሩት ቋንቋ አንድና ሶማሊኛ ብቻ በመሆኑ ሶማሊያዎች ፍፁም አንድ ወጥ ናቸው።

ይህንን አንድነት ወይም አንድ ወጥነት ደግሞ እንዲሁ በእድገትና በታሪክ ሂደት፣ መንፈሳዊ እምነትም ማለትም በአንድ የእስልምና እምነት ይበልጥ አጠናክረውታል።

እንደሚታወቀው የአፍሪካ ቀንድ ክልል የአየር ንብረትና መልክዓምድራዊ ተፈጥሮ፣ ተራሮች የሌለበት፣ ዘብጥና ኮረብታ ያልበዛበት ከባሕር ወለል ጋር የተቀራረበ ዝቅተኛና ዝርግ መሬት ሆኖ የቆዳ ስፋቱ 637,540 ካሬ ኪ/ሜትር ነው።

አልፎ አልፎ ከሚወርደው ከባድ ዝናብ ወይም ዶፍ በስተቀር ክልሉ የሚያገኘው አማካኝ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ200 እስከ 400 ሚ/ሜትር በመሆኑ ለግብርና አመቺ ስላልሆነ የሶማሊያ ሕዝብ በክልሉ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ በጥንታዊ የከብት እርባታ በዘላንነት የሚኖር ነው። የክልሉ ተፈጥሮ ለግብርና ኢኮኖሚና ለምርት ኃይሎች እድገት ያለመመቻቸቱ ሕዝቡን በከብት እርባታ ብቻ እንዲኖር በማድረግ ከአካባቢው ነዋሪ ሕዝቦች ሁሉ ኋላቀር አደርጎታል።

የሶማሊያ ሕዝብ ኢኮኖሚ እድገት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ለልማት ይበጃል ተብሎ የሚነገርለት ወንዝ ወይም ጅረት የለም። ከኢትዮጵያ ደጋማ ክልሎች እየተነሱ ሶማሊያን ወደሚያዋስኑት ወደ ምሥራቃዊው ቆላማ ክልሎች የሚፈሱት እንደ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ፣ አዋሽ፣ ዳዋና ወይብን የመሳሰሉ ወንዞችና ጅረቶች ሶማሊያ ምድር ሲደርሱ ወደ ማዕከላዊ ሶማሊያ ጠልቀው በመፍሰስ የመሀሉን ሃገር የተለያዩ ክልሎች ሳያጠጡ ወይም ሳያርሱ በሙሉ ማለት ይቻላል ሁሉም በሁለቱ አገሮች ወሰን ላይ ተገናኝተው ጁባ የተባለውን ታላቅ ጅረት በመሥራት በሶማሊያ ጠረፍ አድርገው ወደ ኬንያ ይፈሳሉ። አዋሽ በጂቡቲ ክልል ውስጥ ወደ አሸዋ ነው የሚገባው።

ከዝናብ እጥረት ባሻገር ወንዞችና ጅረቶችም ባለመኖራቸው በሶማሊያ ምድር የግብርና ተግባር ይካሄዳል ቢባል በደቡባዊው የጠረፍ ክልሎች ኢጣሊያኖች አገሪቱን በቅኝ ግዛትነት በሚገዙበት ጊዜ በጠረፍ ከሚያልፉት ወንዞች ጥቂቱን በተለይም ከዋቢና ከጁባ በቦይ እየጠለፉ ያቋቋሟቸው ጥቂት የጥጥ የሸንኮራ አገዳ፣ የማሽላ፣ የሩዝ፣ የአትክልና ፍራፍሬ ምርቶችን ለኢጣሊያ ሰፋሪዎች ፍጆታ ሲያመርቱ የነበሩ እርሻዎች ናቸው።

አብዛኛው የሶማሊያ ሕዝብ ገጠሬ ነው። ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ በከተማ ነዋሪው ሀያ በመቶ አይሆንም። አብዛኛው ከተሜ የሚተዳደረው በንግድ፣ በአነስተኛ የእደ ጥበብ የሥራ መስክና በሌሎች ከምርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሌላቸው የሥራ ዘርፎች ሲሆን የተቀረው ማለትም ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ ሰማንያ ከመቶ የሚሆነው በአገሪቱ የገጠር ክልሎች በተለይም ከኢትዮጵያና ከኬንያ ጋር በሚያዋስኗቸው ዳር አገሮች በከብት እርባታ የሚኖር ነው። በአገሪቱ ሰሜናዊና ምሥራቃዊ በረሃማ ክልሎች ከብት ለማርባት አመቺ ባይሆንም በእነኚህ በረሃማ ክልል ከሚኖረው ሕዝብ ከፊሉ ግመሎችና ፍየሎችን ሲያረባ የተቀረው ዓሣ በማስገር የዓሣ ምርት እየተመገበ ለከተሜውና ለውጭ ገበያም ያቀርባል።

አይነተኛ የሶማሊያ ሕዝብ መተዳደሪያና የአገሪቱ ኢኮኖሚ አውታር የሆኑ የቀንድ ከብቶች፣ የዳልጋ ከብቶችና ግመሎች በብዛት አሉ። በኔ ግምት ሶማሊያዎችን በከብት ሀብታቸው መጠንና ዓይነት በአፍሪካ የሚወዳደሯቸው አገሮች ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ኬንያ ብቻ ይመስሉኛል። ይህ ግምት በዘመናዊ ጥበብና በአውሮፓ ደረጃ ከብት ከሚያረቡትና የተለያየ የከብቶች ተዋፅኦ ከሚያመርቱት ከደቡብ አፍሪካና ከዝምቧቤ ጋር ሳላነፃፅር ነው። እነዚህም አገሮች ቢሆኑ በከብት ጥራት እንደሆነ እንጅ በመጠን የምሥራቅ አፍሪካ አገሮችን አይወዳደሩም።

ከከብትና ከብት ተዋፅኦ የሚገኘው ምርት ለሕዝቡ የምግብ ፍጆታ፣ አጠቃላይ መተዳደሪያ፣ ለውጭ ገበያና ለውጭ ምንዛሬ ግኝት አቻና ምትክ የሌለው የአገሪቱ ህልውናና ዋስትና ነው።

አስተማማኝ ወይም የተጨበጠ መረጃ አይኑር እንጅ በሶማሊያ ከርሰ ምድር የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ዘይት አለ እየተባለ ብዙ ይወራል። በኔ መረጃና እንዲሁም አስተያየት የሚኖር ይመስለኛል። ይህ የሆነ እንደሆነ ቁጥሩ ከሶስት እስከ አራት ሚልዮን የሚገመተው የሶማሊያ ሕዝብ ድህነት ደህና ሰንብች ይላል ማለት ነው። እንዲበለፅጉ የኔም ምኞት ነው።

ከዚህ በተረፈ ሌላ በምድር ወለል ላይም ሆነ በከርስ ምድር አለ የሚባል ምንም አይነት የተፈጥሮ ሀብት ባለመኖሩ የአገሪቱ ድህነት አጠያያቂ አይደለም። አገሩን ድርቅ አዘውትሮ ስለሚያጠቃው የአገሪቱ ዋና የኢኮኖሚ ምንጭ የሆነው የከብቱ መንጋና እንዲሁም አራዊቱ ብቻ ሳይሆኑ ሰዎቹም በብርቱ የሚጎዱበት፣ ዛፎች የሚጠወልጉበትና ለከብት ግጦሽ የሚያገለግለው ለም ሳር የሚደርቅበት ጊዜ ብዙ ነው።

በከተማም ሆነ በገጠር የሶማሊያ ሕዝብ በአጠቃላይ፣ በከብት እርባታ የሚኖረው በተለይ ዋና ችግሮች ከሆኑት አንዱ የሆነውን የውሃ እጥረትና ድርቅን ለመቋቋም ሰፋፊ ሰው ሰራሽ ኩሬዎች፣ ቢርካዎችና ጥልቅ ጉድጓዶች በወል እየቆፈረ ከባድ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ በእነዚህ ውስጥ የሚጠራቀመውን ወይም የሚያቁረውን ውሃ ለከብቱና ለሰው ይጠቀምበታል። በሶማሊያ ምድር ወይም ሃገር ከብት የሰው ሕይወት ሲሆን፣ ውሃ ደግሞ የከብቱም የሰውም ሕይወት ስለሆነ ያጋድላል። በአብዛኛው የሶማሊያ ገጠር እንደ ኢትዮጵያ ጉልትና ርስት ብሎ የመሬት ሰሪት ወይም የግል የመሬት ይዞታ አይታወቅም።

የገጠር መሬት፣ የከብቶች ግጦሽና ውሃ በጥንታዊው የጋርዮሽ ሥርዓት መሠረት የጎሳ ማህበራት ወይም ለጎሳዎች የተከፋፈለ የወል ይዞታ ነው። በአንዱ የጎሳ ይዞታ ወይም ክልል የዝናብ እጥረት ወይም እጦት ይፈጠርና ወይም የለየለት ቦና ወይም ከባድ ድርቅ ይከሰትና የአንዱ ጎሳ ማህበር ከብት አርቢዎች የከብቶቻቸውንና የራሳቸውን ሕይወት ለማዳን ሲሉ ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ወደ ሌላው የጎሳ ማህበር ክልል በሚገቡበት ጊዜ በሚፈጠረው ቀውስ ወይም ግጭት የብዙ ሰውና እንስሳት ሕይወት የሚወድቅበት ውጊያ መዋጋት የተለመደ ነው።

በአገራችን በኢትዮጵያ ጥንታዊው የኦሮሞ ማህበረሰብ ይመራበት ወይም ይተዳደርበት የነበረውን አይነት የገዳ ሥርዓትን የመሰለ የጎሳ ማህበራት መተዳደሪያ ሥርዓት አላቸው። የከብት እርባታ ዘይቤአቸውም ጥንት ጥንታዊ በመሆኑ ኑሯቸውን በቋሚነት ሳያደራጁ ለከብቶቻቸው የሚሆነውን የአየር ንብረትና ለምለም የግጦሽ ክልል በመፈለግ የከብቶቻቸውን ዱካና ጭራ እየተከተሉ ለዘላለም በተንቃናቂነት ከመኖራቸው የተነሳ የሃገር ድንበር ወይም ወሰን የተባለ ነገር አያውቁም ወይም አይቀበሉም።

ይህንን በመሰለው ከዘላንነት ባህሪና ሥነልቦና ጋር በተሳሰረው ታሪካቸው ከከብቶቻቸው ደህንነት በፊት ለሰው ሕይወት የማይጨነቁ፣ ሞትን የናቁ ጦረኛ ወይም ተዋጊዎች ናቸው። እርስ በርሳቸው ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሶማሊያ ብሔረሰብነታቸው ሶማሊኛ ተናጋሪ ያልሆኑትንና በአካባቢው ነዋሪ የነበሩትን ማህበረሰቦችንና ብሔረሰቦችን አዘውትረው የሚጋፉ፣ የሚወጉና ሁልጊዜም አጥቂና ተስፋፊ ናቸው።

በዚህ ባህሪያቸው ጥንት በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ በአፍሪካ ቀንድ ይኖሩ የነበሩትን የባንቱ፣ የኦሮሞና የአፋር ወዘተ ማሕበረሰቦች እየወጉ ከክልሉ በማባረር ዛሬ ቀንዱን በሙሉ የብቻቸው አድርገው ለመኖር ችለዋል።

ስለዚህ ነው ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ የምሥራቅ አፍሪካ ቀበሌ ነዋሪዎች "ሶማሊያዎች ግመሎቻቸው የረገጡትን ምድር ሁሉ አለኝታችን ነው ስለሚሉ ሰዎቹን ሳይሆን እንዳይቀርቡ

መከላከል ግመሎቻቸውን ነው።›› የሚሉት። ስለዚህ ነው እኔም በዚህ ታሪክ ውስጥ በብዛት ተሰፋፊ የሚለውን ቃል ለመጠቀም የመረጥኩት።

የሶማሊያ ብሔረሰብ ከአካባቢው ሕዝቦች የማይመሳሰል ያኗኗር ዘይቤ ያለው ለየት ያለ ሕዝብ ነው። ከአካባቢው ሕዝቦች የሚለየው አጥቂና ተጋፊነቱ አይደለም። ከአካባቢው ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን ምናልባትም የሶማሊያን ሕዝብ ከዓለም ሕዝብም የሚለየው ለጎሳ ማህበር ያለው ትርጉምና በአጠቃላይ ኑሮውና ህልውናው ለጎሳ ማህበር የሰጠው ግምትና ፋይዳ ነው።

በኢትዮጵያችን ብቻ ሳይሆን ቢያንስ በመላው አፍሪካ ጎሳ ለሚባለው የሕብረተሰብ አደረጃጀትና መለያ የሚታወቁት የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚለዩበትና የሚጠሩበትም ምክንያት በቋንቋ፣ በባህልና በልዩ ልዩ ወግ፤ ልማድና ምናልባትም ከዚሁ ሁኔታ በሚመነጨው አመለካከታቸውና ስነ ልቦናቸው ነው። በሶማሊያ ብሔረሰብ ዘንድ የጎሳ መለያ ወይም ትርጉም እነዚህ አይደሉም፤ የሶማሊያ ብሔረሰብ ልዩነት የሌላው አንድ ወጥ ሕዝብ ነውና። በሶማሊያ ሕዝብ ባህልና ትርጉም ጎሳ ማለት፣ አብሮ በአንድ ጠባብ አካባቢ መወለድና ማደግ፣ የመንደር ወይም የወንዜ ልጅ እንደማለት ነው። ጎሳው በሚተዳደርበት ደንብ ወይም ሥርዓት መሠረት ከማህበሩ አባላት በእድሜ አንጋፋነቱ፣ በጎሳ ማህበሩ ውስጥ ባሳለፈው ጊዜ ርዝመትና በአደረገው አስተዋፅኦ፣ በአስተዋይነቱና በጀግንነቱ፣ በአመራር ብቃቱና በመንፈሳዊ አባትነቱ ወዘተ የተመረጠ የጎሳ አባት የሚባል የጎሳ መሪ አላቸው።

ከባህል ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ከእስልምና እምነትም ጋር የተያያዘ ይመስላል የጎሳው አባት አስተዳዳሪና ዳኛ መንፈሳዊ አባትና የጦር መሪም ነው። ሕዝቡ ለጎሳ ማህበር ይህንን የመሰለ ትርጉምና ግምት ወይም እምነት በመስጠቱ አንድ የሶማሊያ ተወላጅ የሆነ ግለሰብ ሴትም ሆነች ወንድ ከቤትና ከቤተሰብ ቀጥሎ ያለ የእሱነቱ ወይም የእሷነት ዋስትና ወይም አለኝታ የጎሳ ማህበር ነው። ተማረ አልተማረ፣ ገጠሬ ይሁን ከተሜ እረኛ ይሁን ምሁር ያለ ጎሳ ማህበር ወይም ያለጎሳ ማዕቀፍ መኖር አይችልም። ማንም ሰው ጎሳ አለው ወይም ሊኖረው ይገባል። በሌላው የጎሳ ማህበር አባል በግል ወይም በወል እንዳይጠቃ የሚከላከልለት፣ ቢታመም የሚያስታምመው ቢታሰር የሚያስፈታውና የሰው ነፍስ በእጁ ቢጠፋ የነፍስ ዋጋ ጉማ የሚከፍልለት የጎሳው ማህበር ነው። በሃገር ጉዳይ፣ በአስተዳደርና በፖለቲካ ሥልጣን ምርጫ ወይም ውድድር የጎሳ ማህበር ድጋፍ አስፈላጊ ነው። የጎሳ ማህበር ይህንን የመሰለ ተልዕኮ ስለአለው በጎሳዎች መካከል የሚፈጠረው ቅራኔ በሌሎች አገሮች ከሚታየው ፓርቲዎች ለፖለቲካ ሥልጣን ከሚያደርጉትም ትግል በላይ በጎሳ ማህበራት ጠባብነትና ትምክህተኝነት የተነሳ ግጭት የአገሪቱ ሕዝብ የሚታመስበት፣ መንግሥት የሚፈርስበትና አገሪቱ ያላቋረጠ የሲቪል ጦርነት ውስጥ የገባችበት ሁኔታ ታይቶአል ወይም ተከስቷል።

የስዊዝ ቦይ ተከፍቶ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የአፍሪካን ቀንድ ከመውረራቸው ከአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት በፊት ከኢትዮጵያ የተነጠለ፣ አገራዊ ህልውና ያለው ነፃ የሶማሊያ መንግሥት በታሪክ ፍፁም አይታወቅም ብያለሁ። በአፍሪካ ቀንድ ከኢትዮጵያ የተነጠለ አገራዊ ህልውና የነበረው ነፃ መንግሥት በታሪክ የማይታወቅ ከሆነ፣ የሶማሊያ ሕዝብ ምን ነበር? ከማንስ ጋር ነበር? በእኔ አስተያየት የሶማሊያ ሕዝብና የሚኖርበትም ክልል የኢትዮጵያ አስተዳደር አካል ሆኖ እንደኖረ የሚያስገነዝብ ማስረጃ ከዚህ ቀጥሎ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡

1ኛ/ የአፍሪካ ታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ላጲሶ ጌ. ዴሌቦ፣ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በማለት ከውነው ባቀረቡት መጸሐፋቸው "የአክሱማዊያን መንግሥት በዘመነ ክርስትና ከ1000 እስከ 1100 ዓመት ምህረት ድረስ የግዛት ግንባታና ስፋት" በማለት በምርምርና ጥናት ከተገኙ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የታሪክ ማስረጃዎች እየጠቀሱ የጻፉልንን በቅድሚያ አቀርባለሁ።

"በዞስካሌስ ዘመነ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ የአክሱማዊያን የጠረፍ ግዛት ክልል በቀይ ባሕር ዳርቻ በሰሜን ከዛሬው ፖርት ሱዳን አካባቢ ጀምሮ በደቡብ ምሥራቅ እስከ ኤደን ባህረ ሰላጤ ዳርቻ የአዱሊስ ዓለም አቀፍ የወደብ ከተማና ንግድ በአክሱማዊያን መንግሥት ቁጥጥር ስር እንደነበረ ተመልክቷል" ይሉና፣ ከዘመነ ዞስካሌስ በኋላ በተነሱ የኢትዮጵያ አፄዎች በተከታታይ ኢትዮጵያን ለማስፋትና ለመገንባት ያደረጓቸውን ወታደራዊ ዘመቻዎች ከዚህ እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ።

"በዘመቻ አንድ፣ በዛሬ ትግራይና ጎንደር አካባቢዎች፣ ጋዝ (አድዋ) ሊግይ፣ ተእሞ፣ ጋምቤላ፣ ዘነገበነ፣ አገበ፣ ትማ፣ አታገውስ፣ ካላና ሰሌን ተብለው የሚጠሩ አሥራ ሁለት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን በመንግሥቱ ግዛት ስር አደረጓቸው።

በዘመቻ ሁለት፣ ከትግራይ በስተደቡብ ምሥራቅ በግምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ኤደን ባህረ ሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በእጣን ምርትና ንግድ ተዋቂ በነበረው ምድረ አነን፣ ምጤን፣ ስለእ፣ እርሀሲና ሰላቴ ተብለው የሚጠሩ አምስት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን የመንግሥቱ ግዛቶች አደረጓቸው።

በሦስተኛው ዘመቻ፣ የንጉሡ ጦር በእግርና በመርከብ ከአፍሪካ አህጉር ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በምዕራብ አረቢያ ጠረፍ በሰሜን ምዕራብ በወቅቱ የሮማውያን ይዞታ ከነበረው ከለኡኮመ ወደብ ጀምሮ በምሥራቅ እስከ ሳባ ሃገር፣ በደቡብ ደግሞ እስከ የባብል መንደብ ሠርጥ አካባቢ ድረስ ዘመቻ በማካሄድ ክናይደኮልፕቴና አራብቴ ተብለው የሚጠሩ ሁለት ስትራቴጂያዊ የጠረፍ አገሮችን የመንግሥቱ የባሕር ማዶ ቀበሌዎች አድርጎ በቀጥታ ያዛቸው" ይላሉ።

2ኛ/ ሌላው ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ጠቃሚ መረጃ ያቆዩን፣ አለቃ ታዬ ገብረማርያም "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ" በማለት ከውነው ባቀረቡልን መጽሐፋቸው ነው።

"በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ ሃገር ነበረች። ድንበሮቿ በምሥራቅ የሕንድ ውቅያኖስ፣ በደቡብ ስናር፣ በምዕራብ ነጭ አባይ፣ በሰሜን በርበር ወይም ምስር" ነበር በማለት ጽሑፋቸውን ይቀጥሉና ኢትዮጵያ ከምንላት አገራችን ነዋሪ የሆኑትንና ባሕርታዊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አቃመሩ የሚሏቸውን 23 ነገዶች ወይም ማህበረሰቦች ሲዘረዝሩ፣ በተለይም ከምፅዋ እስከ ጂቡቲ ባሉት የአገሪቷ ምሥራቃዊ ቆላማ ክልሎች ላይ በባህሩ ዳርቻ የሚገኙ ብለው ሲተነትኑ 21ኛ ተራ የሶማሊያ ብሔረሰብ እንደሆነ ይገልፃሉ።

እዚህ ላይ ለአንባቢ ላስገነዝብ የምፈልገው ያስመርኩባቸው ዓረፍተ ነገሮች ሁሉ ሶማሊያ ስለ ሚባለው የሕብረተሰብ ክፍልና ስለሚኖርበት ክልል የሚናገሩትን መሆኑን ነው።

3ኛ/ ቱርኮችና ግብፆች ከ15ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ እየተመላለሱ ቀንዱን ለመቆጣጠር በሞከሩበት ጊዜ ከተፈጠረው ችግር በስተቀርና፣ በ18ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃና ከስዊዝ ቦይ መከፈት በኋላ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ማለትም ኢጣሊያ፣

ፈረንሳይና እንግሊዝ ክልሉን በቅኝ ግዛትነት እስከያዙበት ጊዜ ድረስ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከአዱሊስና ከምፅዋ ጋር የኢትዮጵያ ሌላው ጥንታዊው ዓለማቀፋዊ ወደብ ዘይላ ዛሬ በርበራ በመባል የሚጠራው ወደብ መሆኑም በታሪክ የተረጋገጠ ነው።

4ኛ/ በቤኒቶ ሙሶሎኒ የተመራው ፋሽስቱ የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር በኤርትራና በኢጣሊያ ሶማሊያ ላንድ ወታደሮች የሚያደራጅ መሆኑን በማጋለጥ በኢጣሊያ ምክር ቤት ውስጥ የነበሩ ተራማጅ ግራ ክንፎች ማለትም፤ ዲሞክራቶች፣ ሶሻል ዲሞክራቶች፣ ሶሻሊስቶችና ኮሚንስት ፓርቲዎች በጠቅላላ የፋሽስቶቹን ኢትዮጵያን የመውረር እቅድ በፅኑ ይቃወሙ ስለነበር፣ በ1920 ዓ.ም የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ወሰን ጥሶ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ጠልቆ በመግባት ወልወልን በያዘ ጊዜ፣ ኢጣሊያ ፀብ አጫሪና ወራሪ መሆኗን ለመሰወርና በተለይም ጦርነቱን የሚቃወሙትንና ኢጣሊያ ወራሪ ናት የሚሉትን የኢጣሊያ ግራ ክንፎች ክስ ለማስተባበል ሲል ሙሶሎኒ የሮምን ነዋሪ ሕዝብ በሮም አደባባይ ሰብስቦ "ኢትዮጵያ ጥንታዊ ግዛቶቿን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን በኃይል መልሼ በእጇ አገባለሁ ብላ በመዛት ጦሯን በቅኝ ግዛቶቻችን ድንበር ላይ በማከማቸት ልትወጋን ስለተዘጋጀች እኛም ብንሆን ጦርነት ሳንገጥም ቅኝ ግዛቶቻችንን እጃችንን አጣምረን በመቀመጥ እያየን የምንለቅ አይደለንም። ስለዚህ ሃገርህን የምትወድ ኢጣሊያዊ ሁሉ ተነሳ" በማለት የተናገረው ሌላ ማስረጃ ነው።

የሶማሊያ ብሔረሰብ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት አስተዳደር የተነጠለው አሻፈረኝ ብሎ በአመፅ በመገንጠል ሳይሆን በአክሱም መንግሥት መዳከምና ብሎም መውደቅ ምክንያት አገሪቱ በደረሰባት ጠቅላላ ድክመት፣ በመላው የአፍሪካ ቀንድ የነበሩ ግዛቶቿን በሙሉ ለመቆጣጠርና ለመምራት ስለተሳናት እየተረሱ ከቀሩት ክልሎች አንዱ ቢሆንም በመሃከለኛው ዘመን በተለይም ከ14ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ እንደገና በኢትዮጵያ አፄዎች ግዛት ውስጥ ስለመተዳደሩ የአፄ ዘርዓያቆብ ታሪካዊ የሶማሊያ ጉብኝትና መዋዕለ ዜናዎች ያስረዳሉ።

የሶማሊያ ብሔረሰብ የሚኖርበት የአፍሪካ ቀንድ ዳርቻ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከስዊዝ ቦይ መከፈት በኋላ በ19ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ በኢጣሊያ የተያዘው ከኤርትራ መያዝ በኋላ ነበር። የተያዘውም በኃይል ወይም በጦር ኃይል ሳይሆን በኢትዮጵያ ሰሜን ምሥራቅ ክልል በአፋር ማህበረሰብ ባላባቶች እንደተደረገው ሁሉ የክልሉ ባላባቶች ዛሬ በደቡብ ሶማሊያ መቋዲሾና ኪሱማዩ በተባሉት የባሕር ዳርቻ ያለውን መሬት እየቆረሱ ስለሸጡት ነው።

የሰው ልጅ ዘር የበቀለበትና የሰው ልጅ ጥንታዊ ሥልጣኔ የፈለቀው ከአፍሪካ አህጉር ነው ቢባልም እንደ ጅምሩ አልቀጠለም። በሂደት ከማንም ቀድሞ የሰለጠነውንና በዓለም ልእለ ኃያልነቱም እጅግ ገናና የነበረውን የግሪክ አፄዎች መንግሥት ሥልጣኔ በመውረስ በዓለም ተንሰራፍቶ በነበረው ሰፊ የቅኝ ግዛቱ፤ ግዙፍ የመከላከያ ሠራዊቱና በሀብቱ አቻ ያልነበረው የሮም ቄሳሮች መንግሥት እንደነበረ የታወቀ ነው።

በግሪኮችና በኢጣሊያኖች ፋና ወጊነት የተጀመረው የምዕራብ ዓለም ሥልጣኔ ይበልጥ እየዳበረና እየተስፋፋ ዛሬ እስከደረሰበት ደረጃ ድረስ ያለውን የሳይንስ ቴክኖሎጂ እርምጃ፤ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የስነጥበብና የስነ ጽሑፍ እድገት የምዕራቡ ዓለም የታሪክ ምሁራን የሔሌኒክ ሥልጣኔ እያሉ ይጠሩታል።

የግሪኮች ሥልጣኔና ኃይል ሲዳከምና ብሎም ሲከስም በምትኩ የተተካው የሮማውያን ሥልጣኔና ኃይል እየዳበረና እየጠነከረ ሄዶ እስከ ሰባተኛው ምዕት ዓመት ድረስ በዓለም

ታሪክ ሰፊውንና ታላቁን ማህበራዊ ስፍራ ይዞ ከቆየ በኋላ እሱም በተራው መውደቅና ብሎም መክሰም የጀመረው በዚሁ በሰባተኛው ምዕት ዓመት ከመካከለኛው ምሥራቅ በተነሳ እስላማዊ የአረቦች ኃይል የጂሃድ ጦርነት በማያዳግም ሁኔታ ክፉኛ ተመትቶ ነው።

በጦርነቱ ተንኮታኩቶ የለቀቃቸውን ሰፌ የቅኝ ግዛቶቹን መልሶ ለመያዝ ሊያንሰራራ ቀርቶ በረጅሙ የኢጣሊያ ሕዝብ ታሪክ ኢጣሊያዊ ናቸው፣ የኢጣሊያ ክልል ወይም አካል ናቸው የሚባሉትንም አንጡራ ግዛቶቹን ከውጪ ወራሪዎች፣ በርቢሪዎችና ሥርዓት አልበኞች መከላከልና ማስተዳደርም ተስኖት ነበር።

የኢጣሊያ አስተዳደር አካል ከነበሩት ክፍለ ሀገሮች ውስጥ ከፊሉ በማመፅ ከማዕከላዊ መንግሥት አመራር እያፈነገጡ የራሳቸውን ህልውና ሲያውጁ፣ ከፊሉ ኃይል በተሰማቸው የጎረቤት መንግሥታት እየተወረሩ በመወሰዳቸው ለአያሌ ዘመናት በጥቂት ክልላዊ አስተደደር፣ ፍፁም በዳሸቀ ኢኮኖሚ፣ ሰላምና መረጋጋት ባልነበረበት ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ እየተላጋ መኖር የኢጣሊያ ሕዝብ እጣና ግዴታ ሆኖ ነበር።

በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ በቪክቶር አማኑኤል ርዕሰ ብሔርነት የሚመራ ዘውዳዊ መንግሥት በማቋቋም፣ የተበተነውን ሕዝብ መልሶ ለማሰባሰብና ለማቋቋም ቢሞከርም፣ ድህነት ሥራ አጥነት፣ ከእነዚህም የሚመነጨው የሕዝብ ተስፋ መቁረጥን የመሳሰሉ ከባድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች በመላው ኢጣሊያ ሰፍነው ነበር።

ከዚህ በፊት በዚሁ በትግላችን መግቢያ እንደገለጽኩት፣ በ1857 ዓ.ም በተደረገው የጠቅላይ ሚኒስትር ምርጫ የርዕሰ መንግሥቱን አመራር ለመያዝ የቻለው ካሚዩ ካቮር የተባለው ግለሰብ የተረከበውን አስተዳደር ለመምራት ስለተቸገረ "በኢኮኖሚዋ እጅግ የተዳከመችውንና በቆዳ ስፋቷም የኮሰመነችውን ኢጣሊያ እንድታንሰራራና ብሎም መልሳ እንድትቋቋም ለማድረግ የሚቻለው፣ እንደ ዘመነኞቹ የአውሮፓ ኃይላን መንግሥታት ማለትም፣ እንደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ፖርቹጋል፣ ቤልጂምና ሆላንድ እኛም በአፍሪካ አህጉር በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ቢያንስ አንድ በቆዳ ስፋቱና በተፈጥሮ ሀብቱ የታወቀ ሃገር በቅኝነት መያዝ አለብን" ሲል በኢጣሊያ ሕዝብ ምክር ቤት ብርቱ ቅስቀሳ ማድረጉን መግለጼ የሚታወስ ነው።

ከእነዚህ ከሁለቱ የኢጣሊያ ድርጅቶች ማለትም ከሀይማኖቱ ዘርፍና ከመንግሥት ለሰላዮቹ በገፍና በቋሚነት ይሰጣቸው በነበረው ገንዘብ ለአገራችን መሣፍንትና መኳንንት፣ እንዲሁም ወይዛዝርት፣ ጌጡን፣ የሀር ጨርቅና ሽቶውን፣ ለወንዶች ሽጉጥ፣ ልዩ ልዩ ጠብመንጃዎችንና የአውሬ ማደኛ እረሽ የመሳሰሉትን ገፀ በረከቶች በማቅረብ ሲተዋወቁ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ምሥራቅ ማለትም በአፋር ብሔረሰብ ክልል፣ እንዲሁም በምሥራቅ በሶማሊያ ብሔረሰብ ክልል ያሉትን ባላባቶች በበርካታ ገንዘብና ልዩ ልዩ ስጦታ ገዝተዋቸው ነበር።

በዚህ ዓይነት ስልት ከንጉሡ ነገሥቱ ጀምሮ ከእያንዳንዱ መሥፍን ጋር በመወዳጀትና ቢቱም በመግባት የመሣፍንቱን አቋም፣ የሕዝቡን ጠባይ፣ የአገሪቱን መግቢያ መውጫ፣ የመልክዓ ምድሩን ገጽታና የተፈጥሮ ሀብት ዘገባ ወደ ኢጣሊያ ይልኩ ነበር። እነዚህ ሪፖርቶች የኢጣሊያ ፋሽስቶች የአፍሪካን ቀንድ ለመውረር ያላቸውን ምኞት ያጠናከሩት ብቻ ሳይሆን የኢጣሊያን አመራር አካላትንና ሕዝቡን ጭምር ኢትዮጵያ ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ሀብት ያለበት ሃገር ነች ብለው እንዲያምኑ አድርገዋቸዋል። ከዚህ በተቃራኒ የኢጣሊያ ግራ ክንፍ የፖለቲካ ድርጅትና ተከታዮቻቸው "አዲሲቱን አገራችንን በኢንዱስትሪና በግብርና፣ በጠቅላላው በኢኮኖሚው መልሰን እናቋቁማት፣ ያለንን መጠነኛ ሀብትና እንዲሁም የሰው

ኃይል ለቅኝ ግዛት ፍለጋና ለጦርነት ከማዋል ፋንታ ለአገራችን ሰላም ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት እናውለው።" በማለት እስከ መጨረሻው ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል።

ጊዜው የሲዊዝ ቦይ ሊከፈት የተቃረበበት ጊዜ ስለነበረ የአፍሪካ ቀንድ ኢጣሊያንን ብቻ ሳይሆን አብዛኛውን የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችም ትኩረት የሳበ ብቻ ሳይሆን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ የአፍሪካን እህጉር በመቀራመት ላይ ይገኙ ነበር።

የኢጣሊያ መንግሥት ድክመቱን በመረዳትና አቅሙን በማወቅ እንደ ሁለቱ የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በመርከብ ጦር ልኮ ወደብ በኃይል የመያዙን ነገር ለኋላ ጊዜ አቆይቶ በገንዘብ በደለላቸው ወይም በገዛቸው የአፍሪካ ቀንድ ዳርቻ ነዋሪ ከሆኑ ባላባቶች ጋር በመመሳጠር በቅድሚያ በኢትዮጵያ ሰሜን ምሥራቅ ክልል የባሕር ዳርቻ ለወደብነት የሚያመችና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው አነስተኛ ስፍራ ለመቆጣጠርና ብሎም ወደብ በመሥራት ሁኔታው እንደፈቀደ ተንቀሳቅሶ ወደ ኢትዮጵያ ልብ ጠልቆ ለመግባት ወሰነ። የዚህ ስትራቴጂ ውጥን ወይም ጅምር በመንግሥት ደረጃና ይዞታነት ቢከናወን ከአካባቢው የቅኝ ግዛት ኃይሎች ማለትም፣ በፈረንሳይ፣ በቱርክና በግብጽ ዘንድ ጥርጣሬ ፈጥሮ ምናልባትም ግጭት እንዳያስከትል በአንድ ነጋዴ ኢጣሊያዊ ግለሰብ ወይም ኩባንያ ስም እንዲከናወን ታቀደ።

እዚህ ላይ ከማንም በፊትና በላይ መፈራት የነበረባት ኢትዮጵያ ስትሆን በኢጣሊያኖች ዘንድ የተናቀችበትና ጨርሶ እንደሌለች የተቆጠረችበትን ምክንያት ወደኋላ እገልጸዋለሁ። የአፍሪካን ቀንድ ደህና አድርጎ በመሰለል ተግባር የኢጣሊያንን መንግሥት ለቅኝ ግዛት ሃገር ባለቤትነት ከማነሳሳት ጀምሮ በቀይ ባሕርና በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ቁራጭ መሬት የመግዛቱን ጉዳይ በማውጠንጠን ከፍተኛውን ሚና ከተጫወቱት የኢጣሊያ ሰላዮች ዋናውና ግምባር ቀደሙ የሆነ ጁሴፔ ሳፔቶ የሚባል ግለሰብ ነው።

ይህ ግለሰብ የኢጣሊያ አንድነት ከመመስረቱ በፊት በ1830 ዓ.ም በወንጌላዊነት ሽፋን በሰሜን ኢትዮጵያ ለነበረው የአልአዛሪስት ሚሲዎን ትምህርት ቤት መምህር ተብሎ ከሮም በቀጥታ ወደ ምፅዋ መጣ። የምፅዋን የወደብ ከተማ ቋሚ መኖሪያው አድርጎ የአፍሪካ ቀንድን ጠቅላላ ጠረፋዊ ክልሎችና የቀይ ባሕር ዳርቻ በአጠቃላይ፣ ደቡብ ሶማሊያን ማለትም ዛሬ ሞቃዲሾና ኪሱማዩ ተብለው የሚጠሩት ከተሞች የተከተሙበትን አካባቢ፣ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክልል፣ ትግራይን፣ ጎንደርን፣ ወሎንና እንዲሁም አፋርን እየተዘዋወረና ለተወሰኑ ዓመታትም እየተቀመጠ ወንጌል አስተምራለሁ ከማለቱ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ቋንቋ አጠናለሁ እያለና አልፎ አልፎም ወደ አገሩ ወደ ኢጣሊያ እየተመላለሰ እስከ 1870 ዓ.ም ለ40 ዓመታት በኢትዮጵያ የሰለላ ተግባሩን በሚገባ እያከናወነ ለመቆየት የቻለ ግለሰብ ነው።ይህ ጊዜ በኢትዮጵያ የመሣፍንቶች የሽብር ዘመን ወደ ማለቂያው የተቃረበበት፣ አብዛኛዎቹ መሣፍንቶች በጥቂቱ አውራና ብርቱ መሣፍንቶች ክንድ እየተመቱ የተዳከሙበትና ብሎም የተደመሰሱበት፣ ሽንፈታቸውን በመቀበል እጃቸውን ለአሸናፊናዎች ሰጥተው፣ በጎንደር፣ በጎጃምና በወሎ ራስ አሊ፣ በሰሜን ትግራይ ደጃዝማች ውቤ፣ በሸዋ ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ የነበሩበት ጊዜና ኢትዮጵያ ተከፋፍላና ራሷን ጥላ፣ እንደ ጁሴፔ ሳፔቶ ላሉት ባዕዳን ሃገር ሰላዮችና ብሎም ለወራሪዎች የተጋለጠችበት ጊዜ ነበር።

ጁሴፔ ሳፔቶና ግብረአበሮቹ ለረጅም ዓመታት በተከታታይ ስለ አፍሪካ ቀንድ ያቀረቧቸው መረጃዎች ውጤት ጠቃሚ ሆነው ስለተገኙ በቀይ ባሕር ጠርዝ ላይ ለወደብ መሥሪያ ምቹና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው ስፍራ አጥንተው እንዲያቀርቡ ከመንግሥታቸው ትዕዛዝ ተሰጣቸው።

የኢጣሊያን መንግሥት ከወደብ ይልቅ ወደብ መሥሪያ ቦታ ለመፈለግ የተገደደው ወይም የመረጠው የጥንቱ አዱሊስ ይባል የነበረው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ወደብ በእስላማዊያን ኃይሎች ማለትም በአረቦች ከመፍረሱም በላይ ፍራሹም ከአክሱም የመጨረሻው ስርወ መንግሥት ጋር አብሮ ስለተቀበረ፣ በአዶሊስ ምትክ የተገነባውም የምፅዋ ወደብና አካባቢው በተለይም የሰሜኑ ክልል የባሕር ዳርቻ በአጠቃላይ ከ15ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ በቱርኮች ተይዞ ስለነበረ ነው።

ጁሴፔ ሳፔቶ ኢትዮጵያ በኖረባቸው አርባ ዓመታት ውስጥ በአፋር ክልል እየተዘዋወረ በገንዘብና በልዩ ልዩ ስጦታ በተወዳጃቸው የክልሉ ባላባቶች አማካኝነት በአሰብ ክልል የቀይ ባሕር ዳርቻ ለወደብነት የሚያገለግል ቁራጭ መሬት ለመግዛት እንደሚቻል ተማመነ። በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁም በደቡብ ሶማሊያ ክልል በገንዘብ በደለላቸው ወይም በገዛቸው ባላባቶች አማካኝነት የአሰብ አማራጭ ወይም ተቀጣይ የሚሆኑ ሌሎች ለወደብ የሚጠቅሙ ስፍራዎች በዛሬው ሞቃዲሾና ኪሱማዩ ሁለት ቁራጭ መሬቶችን መግዛት የሚችል መሆኑን ተገነዘበ። ቅድሚያውን ለአሰብ በመስጠት የስፍራውን ለወደብ አመችነትና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ካጠና በኋላ፣ ወደ አገሩ ኢጣሊያ በመሄድ ለመንግሥቱ ጥናቱን አቅርቦ በ1861 ዓ.ም አድሚራል ጉሊዩልም ከሚባለው የኢጣሊያ ከፍተኛ የባሕር ኃይል መኮንን ጋር በወታደራዊ መርከብ ወደ አፍሪካ ቀንድ መጡ።

የዚህ ጉዞ ዓላማም በአድሚራሉ እና በእሱም በሚመሩት የኢጣሊያ ወታደራዊና ሲቪል ጠበብት የጁሴፔ ሳፔቶ ጥቆማን እቦታው ላይ ተገኝተው በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጡ ስለነበር የተጠቆሙትን የሞቃዲሾን፣ ኪሱማዩን፣ የቤሉልንና የአሰብን ክልል ከጎበኙና ካጠኑ በኋላ በጁሴፔ ሀሳብና ጥቆማ ተስማምተው ቅድሚያውን ለአሰብ በመስጠት ምርጫውን ስለአፀደቁ የኢጣሊያም መንግሥት እንዲሁ የሁሉንም ሀሳብ ተቀብሎ አፀደቀው።

በዚህም መሠረት የኢጣሊያ መንግሥት ሩባቲኖ ለሚባል አንድ የኢጣሊያ የመርከብ ኩባንያ አምስት መርከቦች የሚሰሩበት አራት ሚልዮን ሊሬ ሲፈቀድለት ጁሴፔ ሳፔቶ ደግሞ በበኩሉ ለወደቡ መሥሪያ የሚሆነውን መሬት የሚገዛበትና ለሌሎችም አስፈላጊ ወጭዎች ሰማንያ ሺህ ሊሬ ተፈቅዶለትና አፍሪካ የተሰኘ ስም በተሰጠው የኢጣሊያ መርከብ አንድሪያ ኮርዚኒ ከሚባለው የስለላ ባልደረባው ጋር ተሳፍረው የቀረ ተግባራቸውን ለማከናወን ወደ አሰብ መጡ።

በኢጣሊያ ወገን ሁለቱ ሰላዮችና ገዥዎች፣ በመሬት ሻጮቹ ኢትዮጵያዊያን በኩል የክልሉ ባላባቶች የሆኑ ሀሰንቤን አብደላ ሻሂምና ኢብራሂም ቢምአህመድ ሻሙች፣ በአማኝነት ወይም በምስክርነት ከኢጣሊያኖች ወገን አራሲኦም አንቶኖሪና ክፒሎን ግራንዶኒ የተባሉ ሁለት የኢጣሊያ መርከበኞች፣ ከሻጮቹ ወገን አብደላ ኢበንና አሊ ኩሊ የሚባሉ ግለሰቦች ሆነው በቤሎንና በታጁራ መካከል ያለውን የባሕር ዳርቻ መሬት በ3,100 ማርትሬዛ ብር ኢትዮጵያኖቹ መሸጣቸውና ኢጣሊያኖቹ መግዛታቸውን ከተስማሙ በኋላ የግዥና ሽያጭ ውል ሰነድ በኢጣሊያንኛና በአረብኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ተፈረረሙ። የመሬቱ ግዥ ውል የተከናወነው በንጁሴፔ ሳፔቶ አማካኝነት ቢሆንም በኢጣሊያኖቹ የተገዛው መሬት ባለቤት ቀደም ብሎ በታቀደው መሠረት ሲኞር ራፋኤል ሮዛቲኒ የተባለ የመርከብ ኩባንያ ባለቤት ግለሰብ ነው።

ኢጣሊያ ከ18ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ኢትዮጵያን ለቅኝ ግዛትነት የተመኘችው በጁሴፔ ሳፔቶ የረጅም ጊዜና የተሳካ የስለላ ሥራ ውጤት ብቻ ሳይሆን ለአያሌ ምዕተ ዓመታት በአረቦችና በቱርኮች ተከብባ ከተዳከመች በኋላ ከውስጥ የተነሱ ሥርዓት አልበኛ

መሣፍንቶች እርስ በርስ ውጊያና ክፍፍል አገሪቱን ማዕከላዊ መንግሥት አልባ ስላደረጓት ነው። ኢጣሊያኖች አሰብን የረገጡበት ዘመን ቴዎድሮስ ሥርዓተ አልበኛ መሣፍንቶችን ተራ በተራ እየመቱ በመደምሰስ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት መስርተው የኢትዮጵያ አንድነት ለማደስ ሲቀጣቀጡ በመቅደላ ላይ ከወደቁ በኋላ ነው።

አፄ ቴዎድሮስን የተኳቸው አፄ ተክለጊዮርጊስ ናቸው ቢባልም የተክለጊዮርጊስ ግዛትና ተሰሚነት ከጎንደርና ከጎጃም ሳያልፍ፤ ደጃዝማች ካሳ በኋላ አፄ ዮሐንስ፤ በሸዋ ንጉሥ ምኒልክ እንዲቱን ኢትዮጵያ ለሦስት ተከፋፍለው ይገዟት ነበር። ሦስቱም ገዥዎች በየፊናቸው የውስጥ አስተዳደር ችግር፤ የዙፋን ባላንጣነት ክርክርና ብሎም ፍልሚያ ያዋከባቸው ስለነበረ፤ ሦስቱም በየበኩላቸው ካሉባቸው ተቃዋሚዎቻቸው ጋር ከመፋጠጥና ከመፋለም ባሻገር ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ለመውጣትም አንዱ ሌላውን ለመጣል የሚዘጋጁበት ጊዜ ስለነበር እንዳቸውም፣ አሰብን ለማዳን ማሰብ ቀርቶ ምናልባትም ኢጣሊያኖች አሰብ መግባታቸውን እስከ ወሬውም የሰሙት ብዙ ዘግይተው ሳይሆን አይቀርም። ከዚህ በኋላ በ1861 ዓ.ም መገባደጃ ላይ ኢጣሊያኖች በአሰብ ሰንደቅ ዓላማቸውን ማውለብለብ ጀመሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በባህሩ ጠርዝ አግድም ሰባት ኪ/ሜ ወደ ውስጥ በጥልቀት ሰላሳ ኪ/ሜ፣ ስፋት ያለውን ይዞታችን ብለው በመቆናጠጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ ሄዱ።

ስለዚህም፣ በአፍሪካ ቀንድ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ታሪክ የተወጠነው ከአሰብ ተቆርጦ በተሸጠ መሬትና ጁሴፔ ሳፔቶ በተባለው የቀበሮ ባህታዊ አማካኝነት ነው። በአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባሕር ዳርቻ አሰብን ከተቆናጠጡ በኋላ ነው እነጁሴፔ ከአሰብ የተደላደለ ወደብና ቤታቸው እየተንደረደሩ ሞቃዲሾንና ኪሱማዩ የተባሉትን ሁለት የባሕር ዳርቻ መሬቶች ከተለያዩ የሶማሊያ ብሔረሰብ ባላባቶች በመግዛት ኢጣሊያ እግሯን ካስገባች በኋላ ነው ያለአንዳች ተቃውሞና ውጊያ ሶማሊያን ቅኝ ግዛቷ ያደረገችው።

ኢጣሊያ ኃያልና እጅግ ገናና በነበረችበት በጥንቱ የሮም ቄሳሮች የአገዛዝ ዘመን ከአብዛኛው የዓለም ክፍል ጋር ለኢትዮጵያ አቅራቢያና እንዲሁም ጎረቤት የሆኑትን፣ ሰሜን አፍሪካንና መካከለኛውን ምሥራቅ ቅኝ ግዛቶቿ ስታደርግ ጥንታዊት ኢትዮጵያን ከአንድም ሁለት ጊዜ በጊዜው ኃያልና መጠነ ሰፊ በነበረው ሠራዊቷ ለመውረር ያደረገችው ሙከራ ስላልተሳካላት ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከማድረግ ወዳጅነቷ ይበጃል ብላ በአክብሮት ወዳጅነቷንና የትግል አጋርነቷን የፈለገች ሃገር፣ ያላንዳች ተቃውሞ፣ ትግልና ደም በ3100 ማርትሬዛ ብር ብቻ የአፍሪካን ቀንድ የቅኝ ግዛቷ ማድረግ ቻለች።

ሩባቲኒ የተባለው የኢጣሊያ የመርከብ ኩባንያ በኢጣሊያ መንግሥት ቀጥተኛ ርዳታና ገንዘብ የተሰሩትን አምስት ታላላቅ መርከቦች በአገልግሎት ላይ በማዋል ለ13 ዓመታት በአሰብ፣ በቤሉል፣ በመቃዲሾና በኪሱማዩ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን የወደብ ግንባታዎችን ሥራ ሲያከናውን ከኢትዮጵያም ሆነ ከማንም ወገን የጠየቀውና የተቃወመው ስላልነበረ በመደፋፈር በ1874 ዓ.ም ወደቦቹን ከነመርከቦቹ ለኢጣሊያ መንግሥት ቅኝ ግዛት የማድረጉና የመስፋፋቱ ሂደት በይፋ ቀጠለ።

በሶማሊያ ምድር የባሕር ዳርቻ ላይ ለመቆናጠጥና ብሎም ወደብ ለመሥራት የተደረገውን የጁሴፔ ሳፔቶ ጥረት ስኬታማ ለማድረግ እንግሊዞች ግብጾችን፣ ግብጾችም በበኩላቸው የዛንዚባሩ ሡልጣን፣ የዛንዚባሩ ሱልጣን ደግሞ በበኩሉ የደቡብ ሶማሊያ የባሕርዳርቻ ክልል የጎሳ ባላባቶችን በመደለልና በማግባባት የኢጣሊያ መንግሥት የቅኝ ግዛት በአፍሪካ ቀንድ ይመሠረት ዘንድ በትብብር ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የኢጣሊያ መንግሥት ከሩባቴኒ ኩባኒያ ወደቡን በተረከበበት ጊዜ የኢትዮጵያ መሪ አፄ ዮሐንስ ነበሩ። አፄ ዮሐንስ ዛሬ ኤርትራ ተብሎ በሚጠራው በሰሜኑ የአገራችን ክልል ግብጾችን ተገን አድርገው ከሸፈቱባቸው መሣፍንቶችና ከሸዋው ንጉሥ አፄ ምኒልክ ጋር በነበራቸው ትግል በአሰብና በቤሎል የወደቦች መሠራትንና በኢጣሊያ መያዝ ሊቃወሙ አልቻሉም ወይም አልፈለጉም።

ኢጣሊያኖች ለማስመሰል እንደሞከሩት በአሰብ መያዝ የኢጣሊያ መንግሥት እጅ የሌለበትና በኢጣሊያዊያንና በኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች ፈቃድና ፍላጎት የተደረገ የንግድ ጉዳይ ሳይሆን ከመቋዲሾ ጋር በአሰብ አማካኝነት ምፅዋንም ከግብጾች ተረክቦ በእጁ ለማድረግ ከእንግሊለዝ መንግሥት ጋር ይመሳጠር ነበር። በዚህ ሁኔታ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ፍላጎቱ የሰመረለት' የኢጣሊያ መንግሥት በአሰብ ወደብ ይዞታው ሳይገደብ እንዳሻው በመስፋፋት ወደ ሰባ ሺህ ካሬ ኪ/ሜ የሚሆነውን የአውሳ አውራጃ በሙሉ የቅኝ ግዛቱ አድርጎ በኢጣሊያዊ ዜጐች ኢጣሊያዊ አስተዳደር መሠረተ።

የአሰብ ወደብ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቂያኖስ ላይ ለሚደረግ የባሕር ጉዞ አማካኝና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው ከመሆኑ በላይ በየብስም ወደቡን የሚያካትተው ሰፊው የአውሳ አውራጃ መልካ ምድር ወደ ኤርትራና ትግራይ፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ ሐረርጌ፣ ጂቡቲና ብሎም በኢሳና ጉርጉራ በኩል ወደ ሶማሊያ በቀላሉ የሚያዘልቅ ዝርግና ቀና መሬት በመሆኑ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን መላውን የአፍሪካ ቀንድ፣ ቀይ ባሕርን፣ የሕንድ ውቂያኖስንና መካከላዊውን ምሥራቅ ለመቆጣጠር ለፈለገ ኃይል አሰብን መቆጣጠር በጣም ትክክል ነው።

በተመሳሳይ የሞቃዲሾ ወደብ ቀይ ባሕርን የሕንድ ውቂያኖስን መካከላዊውን ምሥራቅ የባብል መንደብን ሠርጥ፣ በባብል መንደብ ሠርጥ አማካኝነትም የስዊዝ ቦይን ወይም የግብጽን ስትራቴጂያዊ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ለመቆጣጠር ቁልፍ ቦታ ሲሆን ከሁሉም በላይ በኢጣሊያ ስትራቴጂያዊ እቅድ መሠረት ከሞቃድሾ ያለአንዳች ችግር ማለትም የተፈጥሮ መሰናክል ባለመኖሩ በአጭር ጊዜና በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ ልብ ለመጥለቅ ከአሰብና ከምፅዋም የተሻለ መቃረቢያ ነው። የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ሲወር ያደረገውም ይህንኑ ነው።

በጥንቷ ኢትዮጵያ በአሰብ፣ በቤሎል፣ በሞቃዲሾና በኪሱማዩ በገዛቻቸው ቁራጭ መሬቶች ወደቦቿን በመገንባትና ግንባታውንም በማጠናቀቅ፣ ወደቦቹን ከግል ኩባንያ ገዛሁ በማለት የባሕር፣ የአየርና የምድር ጦሯን በአስፈረመችበት ጊዜ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት አፄ ዮሐንስ ቢሆኑም የኢትዮጵያን መሃልና ደቡባዊውን ክልል ለመቆጣጠር አልበቁም።

የኢትዮጵያን ሰፊውንና ለሙን ክልል የሚቆጣጠሩት ንጉሥ አፄ ምኒልክ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር በመገናኘትና በመወዳጀት ከዘውድ ባላንጣቸው ከአፄ ዮሐንስ ጋር ለሚደረገው ፍልሚያና ብሎም ለወደፊት ዓላማቸው የአስፈለጓቸውን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችና በተለይም የጦር መሣሪያዎች የሚያስገቡት የአሰብን ወደብ በሚያስተዳድሩት የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች በአፋር ማህበረሰብ ሡልጣኖች አማካኝነት በአሰብ ወደብ ነበረ።

ይህ የኢጣሊያና ምኒልክ ወዳጅነት ወይም ሽርክና እድሜ ገዝቶ፣ የኢጣሊያ መንግሥት ከእንግሊዝና ከግብጽ መንግሥታት ጋር በመመሳጠር ሠራዊቱን ከአሰብና ከቤሎል ወደብ እያነሳ ምፅዋን ሲቆጣጠር፣ ከምፅዋም እየተነሳ የኤርትራን ደጋማ ክልል ለመቆጣጠር ባደረጋቸው የመጀመሪያዎቹ ያልተሳኩ ወረራዎች ከአፄ ዮሐንስ ጋራ በሚዋጋበት ጊዜ ሁሉ ምኒልክ የአሰብ ወደብ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ሌላ የጎረቤት ሃገር መሪ

ራሳቸውን ከወረራው አግልለው የአፄ ዮሐንስና የኢጣሊያ መንግሥት አስታራቂ ወይም ገላጋይ ለመሆን ሞክረው ነበር። ይህ ሁኔታ የሚገልፀው፣ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ አስረጂ መረጃ ባይኖርም አሰብና ብሎም የአውሳ አውራጃ በአጠቃላይ በኢጣሊያ መንግሥት መያዙን ምኒልክ የሚያውቁ ብቻ ሳይሆን መስማማታቸውንም ነው። ይሄ ብቻ አይደለም። አንባቢ ከዚህ ቀጥሎ ሊረዳ እንደሚችለው ሶማሊያ በኢጣሊያ መያዝ፣ የኤርትራ በኢጣሊያ መያዝና የውጫሌ ውል በጣም ተመሳሳይነት ያላቸው፣ ከምኒልክ ሥልጣንና ታሪካዊ ውሳኔ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ይህንን ስል ግን ምኒልክ ኢጣሊያኖችን ጠርተው አመጡ የሚባለውን ክስ የምጋራ ወይም የምስማማ አይደለሁም። እነኚህን ሁኔታዎች የፈጠረውና የወሰነውም የኢጣሊያ መንግሥት የቅኝ ግዛት ጥማትና የኃይል የበላይነት ነው ብዬ ነው የማምነው።

የሶማሊያን ብሔረሰብ ክልል አስመልክቶ የምኒልክና የኢጣሊያ መንግሥት የወሰን ክልል ውል የሚያስረዳው፣ የዛሬው የሶማሊያ መንግሥት ክልል ከኢጣሊያ ወረራ በፊት የኢትዮጵያ አካል የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ ሌላ ማስረጃ ነው። ክልሉን ልክ እንደ ሰሜኑና ስሜን ምዕራቡ የአገራችን ክልል ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች በፊት ቱርኮችና ግብፆች ለተወሰነ ጊዜ ተቆጣጥረውት ስለነበረ የሶማሊያ ብሔረሰብ መሪዎች ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር የነበራቸው ግንኙነትና ገባርነት መቋረጥ የጀመረው ወይም እየላላ የሄደው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይገመታል።

ከቱርኮችና ከግብፆች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ ከዚህ በላይ በተገለፀው የመሬት ግዥ ውል መሠረት የሶማሊያን ምድር የረገጡት ኢጣሊያኖች የሞቃዲሾንና የኪሱማዩን አካባቢ ወይም የሶማሊያ የባሕር ዳርቻ ቢቆናጠጡም፣ ከዚህ ባለፈ ሳይስፋፉ ከምኒልክ ጋር በመዋዋል በሰላም የቅኝ ግዛት የፈለጉ ይመስላል።

እንደተለመደው በሁለቱ አገሮች መካከል የጠነከረ ወዳጅነት ለመመስረት ወይም የነበረውን ለማጠናከር በንግድና በሌሎችም የኢኮኖሚ መስኮች ለመተባበር ይቻለን ዘንድ ለኢጣሊያ ዜጎች ማስፈሪያና እንዲሁም መሥሪያ የሚሆን መሬት ይፍቀዱልን ብለው የጠየቁት ምኒልክ እንጂ የሌሎትን የሶማሊያን መንግሥት ወይም መሪዎች አይደለም።

እንደሚታወቀው በዚያ ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያዊያን በተለይም መሣፍንቱና መኳንንቱ የሚፈልጉት አገራቸውን የሚገነቡበት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ወይም የማምረቻ መሣሪያዎችን ሳይሆን በአውሮፓ የተመረቱ ብርቅርቅ የፍጆታ እቃዎችን ሲሆን ከዚህ በላይ ምኒልክም ሆኑ ሌሎቹ ከፍተኛ ፍላጎታቸው የጦር መሣሪያ መግዛትና ማካበት ነው።

ይህንን ማድረግ የሚቻለው ባለ ኢንዱስትሪ ከሆኑት ከአንዱ የአውሮፓ ሃገር ወይም መንግሥት ጋር በመወዳጀት ስለሆነ ምኒልክም ከፈለጉት አውሮፓዊ ወዳጅ መንግሥት የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለማግኘት በበኩላቸው መስጠት የሚችሉት መሬት ስለሆነ በሶማሊያ ኢጣሊያኖች የጠየቁትን መሬት ቆርሰው ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኑ። በዚህ መሠረት በ1908 ዓ.ም ኢጣሊያኖች ከባህሩ ዳርቻ ጀምረው ወደ ውስጥ ሦስት መቶ ኪ/ሜትር ጥልቀት ያለው መሬት ወስደው ሊጠቀሙ እንደሚችሉና ይህም መሬት ወደ ፊት ሁኔታው እንዳመቻ የኢትዮጵያና የኢጣሊያን መንግሥት ወሰን ሳይሆን፣ የኢጣሊያ ሰፋሪዎችና የአካባቢው ነዋሪ ጎሳዎች መካከል ያለውን የመሬት ይዞታ የሚለይ የወሰን ምልክት እንደሚደረግበት ተስማምተው ተዋዋሉ።

የዛሬው የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሕዝቦች ወይም መንግሥታት ቅራኔና ብሎም ግጭት ምክንያት ከዚህ የወሰን ውል ባህሪ ይመነጫል። የወሰኑ ውል የፈጠረው ችግር በኋላ ነፃነቱን

ባገኘው የሶማሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ለፈጠረው ጠብ ወይም ቅራኔ ዋና ምክንያት ሆኖ ቆይቷል።

ዳግማዊ ምኒልክ መልካም ፍቃዳቸው ሆኖ የሶማሊያ ብሔረሰብ ከሚኖርበት የምሥራቅ ኢትዮጵያ ግዛታቸው በኢጣሊያ መንግሥት ጥያቄ መሠረት ከደቡብ ሶማሊያ የተወሰነ መሬት ቆርሰው ሲሰጡ በሁለቱ መንግሥታት መካከል በተደረሰበት ስምምነት መሠረት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢጣሊያ መንግሥት ቆርሶ የሰጠው መሬት ከባሕር ወደ ውስጥ የሚኖረው እርቀት በየብስ መለኪያ ከባህሩ ጠርዝ ጀምሮ ወደ ውስጥ ሦስት መቶ ኪ/ሜትር ሲል የኢጣሊያ መንግሥት በበኩሉ የለም በእርቀት መለኪያነት እንድንጠቀምበት የተስማማነው በየብስ መለኪያ ሜትር ሳይሆን በባሕር መለኪያ ኖቲካል ማይል ነው በማለት ሁለቱ መንግሥታት ስለተለያዩና ይህንንም ልዩነት የሚያስወግድ የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ሳይችሉ፣ የሶማሊያ ሕዝብ ነፃነቱን ያገኘና ኢጣሊያኖችም ሶማሊያን ለቀው ይሄዳሉ።

ከሶማሊያ ጋራ በአፍሪካ አህጉር በአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች መዳፍ ውስጥ ከነበሩ አገሮች ከሀያ በላይ ነፃነታቸውን ስላገኙ በአዲስአበባ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በአቋቋሙበት ቻርተር፣ የአገሮችን ወሰን በተመለከተ እያንዳንዱ ሃገር የጥንቱን ታሪክ እየጠቀሰ እንደ ምኞቱና እንደ ፍላጎቱ የአገሩን የፖለቲካ ካርታ ሊስል ወይም ሊቀርፅ ቢሞክር ለአፍሪካ ጥፋት እንጂ ልማት፣ ሰላምና አንድነት ሊበጁ ስለማይችል አማራጭ የሌለው መፍትሄ፣ ሁሉም ከቅኝ ግዛት ኃይሎች የተረከበውን ወሰን ተቀብሎና አክብሮ መኖር ነው በማለት ካይሮ ላይ የተፈረመውን ውል ሶማሊያ ብቻ አልቀበልም ስትል ኢትዮጵያ ለቻርተሩ እገዛለሁ አለች።

የአዲሱ የሶማሊያ ነፃ መንግሥት የየአገሩን ወሰን አስመልክቶ አፍሪካ የተስማማበትን ውሳኔ አልቀበልም ያለበት ምክንያት፣ ዛሬ በኢትዮጵያና በሶማሊያ ሪፐብሊክ መካከል ያለው ወሰን በነፃው በሶማሊያ መንግሥትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የተደረገ የጋራ ስምምነት የተከለለ ሳይሆን በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል የተደረገ ስምምነት ስለሆነ አዲሲቱ ሶማሊያና ኢትዮጵያ አዲስ የወሰን ክልል መካለልና መዋዋል አለባቸው በማለት ነው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሶማሊያን ጥያቄ ደግፎ አልተቀበለም። የተባበሩት መንግሥታት ማህበርም ቢሆን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተስማማበትን ማናቸውንም የአህጉሩን ውሳኔዎችና ድንጋጌዎች ሊነጋገርባቸው ፣ ሊጥስና ሊሽራቸው አይችልም። የሶማሊያ መንግሥት ግን ይህንን ዓለም አቀፍ ውሳኔ ባለመቀበል ባገኘው አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ መድረኮች ሁሉ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የወሰን ጉዳይ ያላነሳበትና ኢትዮጵያን ያልከሰሰበት ጊዜ የለም። ስለዚህም ነው ይህንን ርዕስ ስጀምር አፍሪካን ያሰለቸ ጭቅጭቅ ለማለት የተገደድኩት።

የሶማሊያ መንግሥት ለመስፋፋትና ታላቋ ሶማሊያ የሚሏትን ሃገር ለመፍጠር የነበረው ምኞት እጅግ ከፍተኛ ነበር። “በረሀብ የተቆራመድከውና በድርቅ የጠወለግከው ሐበሻ ከለሙና ከደጋማው አጽመ ርስትህ ላይ ገፍትሮ በዚህ ደረቅ መሬት ላይ ስለጣለህ ነው” እያሉ ሕዝቡን የሶማሊያ መሪዎች መመረዝ ከጀመሩ ብዙ ቆይተዋል። የአፍሪካ መሪዎች የየአገሮችን ወሰን አስመልክተው በድርጅታቸው ቻርተር ላይ በከፍተኛ ማስተዋል ያሰፈሩትን ውሳኔ ፈፅሞ አልተቀበለም። የአፍሪካ መሪዎች ለነሱ መስፋፋት ሲሉ ከወሰኑት ውሳኔ ወጥተው ምንም አይነት ድጋፍ የማይሰጧቸው ብቻ ሳይሆኑ እንዲያውም የሶማሊያ መንግሥት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ጠንቅና አፍራሽ ምሳሌ ነው በማለት

አምርረው በመቃወማቸው፣ የሶማሊያ መሪዎች ሌላ ካምፕ፣ ሌላ ሰፈር ወይም ድርጅት መፈለግ ጀመሩ። ታላቋ ሶማሊያ የሚለውን ሃገር መፍጠር የሚያስችለን የገንዘብ፣ የዲፕሎማሲና የሞራል ብቻ ሳይሆን በእስላማዊ ማህበር ወግና ልማድ ምናልባት በተዋጊ የሰው ኃይልም እንረዳ ይሆናል በማለት የዓለም የእስልምና እምነት ተከታዮች ማህበር አባል ሆኑ።

አረብ ነኝ ብሎ በፍፁም የማያምነውንና በሶማሊያነቱ የሚኮራውን ሕዝብ ለተመሳሳይ ዓላማ ሲሉ አረብ ነህ በማለት አገሪቱን የአረብ ሊግ አባል አደረጓት። የሶማሊያን ሕዝብ ወደ ሶሻሊስት ሕብረተሰብነትም እንለውጠዋለን በማለት አገሪቱን የሶሻሊስት አገሮች ማህበር ጎራ ሊያደርጓትም ሞክረዋል።

እኔ እንደምለው ሳይሆን በጊዜ ሂደት ታሪክ እንዳሳየንና ወይም እንዳረጋገጠው የሶማሊያ መሪዎች ነን የሚሉትን ሁሉ አልነበሩም። የእስልምና እምነት አክራሪነትና ሶሻሊስታዊነት የሚጣጣሙና አብረው የሚጓዙ ነገሮች አይደሉም። ሆኖም ሶማሊያዎችን ይህንን ሁሉ ለመሆን ያነሳሳቸው ታላቋ ሶማሊያ ከሚለው ምኞታቸው የሚመነጨው የመስፋፋት ፍላጎት እንጂ ኢትዮጵያ ወይም የአካባቢው አገሮች ይወሩናል ከሚል ሥጋት አልነበረም። ኢትዮጵያን ወሮ ለመስፋፋት ከነበራቸው ፅኑ ፍላጎት የመነጨ አጭበርባሪነት ነው። በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በጅቡቲና በኬንያም ላይ ለመስፋፋት የነበራቸውን ጠንካራ ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ ኃይልን የመረጡት በማጭበርበር፣ በሙግትና በጩኸት የመስፋፋት ዓላማቸው እውን እንደማይሆን በመገንዘባቸው ነው። ኃይልን አማራጭ የሌለው መሣሪያ አድርገው ሲመርጡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የማይሸከመውን የጦር ኃይል መገንባት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ በመውጋትና ቢቻልም በመገነጣጠል የሚያዳክሙላቸውን ምንደኛ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በማደራጀትና በመርዳት ጭምር ነበር። ሻዕቢያ፣ ወያኔና አነግ ወዘተ ለብዙ ዓመታት የሶማሊያ መንግሥት ትሩፋት ወይም ፍርፋሪ ለቃሚ ነበሩ።

የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ በሚያካሄደው ሽብርና ሠላምን የማደፍረስ ተግባር ብቻውን አልነበረም። ወትሮም ለኢትዮጵያ በጎ የማያስቡት የአካባቢው አድህሮት የሶማሊያን በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ፍላጎትና የገንጣይ አስገንጣዮች ምኞት መሳካት ኢትዮጵያን ፍፁም ስለሚያዳክምላቸው የእነሱም የቆየ ስትራቴጂያዊ ዓላማ ግቡን መምታት ስለሆን ከአሥራ ሦስት አገሮች በላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊትን ከሃገር ውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች ጋር አስተባባሪ ሆነዋል።

ማንንም ሳያስበውና ሳይጠብቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በድንገት በመፈንዳቱ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ያለውን ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህ የተሻለ መልካም አጋጣሚ እንደማይገኝ በማመን ኢትዮጵያን ለመውረር የወሰነ መሆኑን በመገንዘብ፤ ከዚህ በላይ የጠቃቀስናቸው የአካባቢው አድህሮት ከሶማሊያ ጋር የተባበሩ ብቻ ሳይሆን ለጠብ አጫሪነትና በሚከፍቱት የሕብረት ጦርነት ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የኤርትራንና የኦጋዴን ጉዳይ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት እጅ አውጥተው ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ የሚዶልቱ ሰለመሆናቸውና ለጦርነትም ስለመዘጋጀታቸው በ1968 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ አስተማማኝ መረጃ ስለአገኘን ራሳችንን ብቻ ሳይሆን በአጉል የመስፋፋት ስሜት የሶማሊያን መንግሥት ከዚህ ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ ለማዳን የሚከተሉትን የሠላም ጥረቶች ማድረግ ጀመርን።

ከሶማሊያ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለማምራት ቀደምቱን ጥረት የጀመርነው ከጂቡቲ ሕዝብ ነፃነት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነበር። ጥንት የአካባቢው ነዋሪዎች አቦከ

በማለት የሚጠሩትና ፈረንሳዮች ጂቡቲ የሚል ስም የሰጡት የሕንድ ውቂያኖስ ዳርቻ ቆላማ መሬት ኢትዮጵያ ሸቀጦቿን የምታስወጣበትና ከውጭም የምታስገባበት፤ ከውጭው ዓለም ጋር የምትገናኝበት ወደብና ከወደቡ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና ብቸኛውን የምድር ባቡር መንገዋ ለመዘርጋት ከፈረንሳዮች ጋር ለዘጠና ዘጠኝ ዓመታት የሚቆይ ውል አፄ ምኒልክ እስከተዋዋሉበት እስከ 1908 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ አስተዳደር አካል እንደነበር የሚያስረዳ ሌላ መረጃ ነው።

የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥትና የአካባቢው አድህሮት የሶማሊያ መሪዎችን የመስፋፋት ፍላጎት ተጠቅመው ለኢትዮጵያና ለሶማሊያ ሕዝብ የደገሱትን የጦርነት ሴራ ለማክሸፍ ያደረግነውን ጥረት ከመግለጼ በፊት ጂቡቲንና የጂቡቲን ሕዝብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተዋወቅ ጠቃሚ ይመስለኛል።

ዛሬ ጂቡቲ የሚባለው ወደብ፣ የወደቡ ከተማና እንዲሁም የምድር ባባሩ መስመር ከመዘርጋቱ በፊት ስፍራው እጅግ የሚሞቅ በረሃ፣ እፅዋትና ለምለም ሳር የሌለበት ደረቅና አሸዋማ ምድር በመሆኑ ሰው አልባ የነበረ ነው። በአካባቢው ነዋሪ የሆኑት የአፋርና የኢሳ ማህበረሰቦችን በተመለከተ ሁለቱ የተለያዩ ማህበረሰቦች ከመሆናቸው በስተቀር በተቀረው በማናቸውም በባህልና የአኗኗር ዘይቤዎች ስለ ሶማሊያ ብሔረሰብ ከተነገረው ሌላ ማለት አይቻልም።

የኢሳው ማህበረሰብ አለ ተብሎ በሚጠራበት የጎሳው ስምና ይህ ጎሳም የሚኖረው ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ከመሆኑ በስተቀር ከሶማሊያው ብሔረሰብ በምንም ረገድ የማይለይና የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነው። ሁለቱም ማህበረሰቦች በጥንታዊው የከብት ርባታ ዘይቤ የሚተዳደሩ በጠቅላላው ማለት ይቻላል ዘላን ህብረተሰቦች ናቸው።

ይህ የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ የባሕር ዳርቻ ለጎረቤቶቻችን ለማዕከላዊ ምሥራቅ ክልል ነዋሪ ለሆኑት አረባዊያን በጣም ቅርብ ከመሆኑ ባሻገር፣ አረቦች ከ7ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ሲመላለሱበት፤ ቱርኮች ከ15ኛው ምዕት ዓመታት ጀምሮ ተቆጣጥረውት ስለነበረ በዚህ የታሪክ ሂደት ከሁለቱ ማህበረሰቦች አብዛኛዎቹ የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆኑ ከመሀላቸው ከዚህ የሚለዩ ቢኖሩ ሌላ መንፈሳዊ እምነት ያልሰረፀባቸውና በነሱ አነጋገር በደዌ ወይም ሀይማኖት አልባ ናቸው።

ከአረቡ ዓለም ጋር የንግድና የባህል ግንኙነት ያደርጉ የነበረው በጥንቶቹ በዘይላና በታጁራ ወደቦች አማካኝነት ነበር። የኢሳው ማህበረሰብ አስፋፈር ዋናው የሶማሊያ ብሔረሰብ ከሰፈረበት ክልል ጋር ኩታ ገጠም በመሆን ወደ ምዕራብ የተዘረጋና በአመዛኙ በሐረርጌ ጥቂት በሸዋ ደጋና ወይና ደጋማ ክልል የሚኖር ሲሆን የአፋሩ ማህበረሰብ ቁጥሩ እንደ መብዛቱ መጠን በምሥራቅ ከኢሳው ማህበረሰብ ጋር በመዋሰንና ወደ ሰሜን ምሥራቅ በመዘርጋት በሐረርጌ፣ በሸዋ፣ በወሎና በኤርትራ ክልሎች ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። ሁለቱም ማህበረሰቦች በታሪካቸውና በሙሉ የዘር ወይም የማህበረሰብ መሰረታቸው ወይም ሥራቸው ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በጥንቱ አቦክ በኋላ ጂቡቲ የባቡሩንና የሀዲዱን ግንባታ የሚያከናውኑት ፈረንሳዊያን መጥተው ራሳቸውን ለሥራው ማደራጀት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ግምባታውን እስከ አጠናቀቁበት ጊዜ ድረስ ከሰባት ዓመት በላይ የሆነ ጊዜ ወስዷል።

ሰው አልባ የነበረው ስፍራ ጥቂት በጥቂት ሰዎች የተሰበሰቡበት በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ነበር። በጂቡቲ የወደብ ግንባታ ከሚያከናውኑ ሠራተኞች ጊዜያዊ ሰፈርነት፣ ደረጃ በደረጃ የነጋች መንደርና ብሎም የአንድ ትንሽ ከተማ ይዘትና ቅርፅ በመያዝ ለጥቂት ሰዎች የተወሰኑ የሥራ መስኮችን እድል ከመክፈት ተነስታ ለወደቡና ለምድር ባቡሩ ሀዲድ

መዘርጋት ሥራ ከአካባቢው ነዋሪ ዘላኖች ይቀጠሩ ስለነበር፣ እነኚህን፣ የአባባቢውን ፀጥታ ለማስከበር የሰፈረውን የፈረንሳይ የጦር ኃይልና የአካባቢውን ገጠሬ ወይም ከብት አርቢ ጨምሮ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የጂቡቲ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ከ10,000 እስከ 15,000 ይገመት ነበር።

በዳግማዊ ምኒልክ መንግሥትና በፈረንሳይ ኩባንያ መካከል የተደረገው የዘጠና ዘጠኝ ዓመት የውል ጊዜ ሲያልቅ ወይም ሲያበቃ ወደቡንና የምድር ባቡሩን መስመር ለኢትዮጵያ መንግሥት አስረክቦ ለመሄድ ነበር። ማንም ሊያስተውልና ሊገምት እንደሚችለው በዚህ ዓይነት ውለታ በኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎትና ፈቃድ የተገነባ ወደብ በውሉ ጊዜ አጋማሽ የጂቡቲ ከተማ ወደ አንድ ሕዝብነት ወይም ሃገርነት ተለውጦ ከኢትዮጵያ የተነጠለና አንድ ራሱን የቻለ ነፃ ሪፐብሊካዊ መንግሥት ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ነገር አይደለም።

እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? ሁኔታው በጣም የሚያሳዝን ነው። ሁለቱ ሶማሊያዎች ማለትም፣ ሰሜኑ የእንግሊዝ ቅኝ የነበረውና ደቡብ የኢጣሊያ ቅኝ የነበረው ከ1950 እስከ 1951 ዓ.ም በቅደም ተከተል ነፃነታቸውን እንዳገኙ በመቀላቀል በእንግሊዞች አማካሪነት ታላቋ ሶማሊያ የሚባለውን ሃገር የመፍጠር ዓላማ ከማለማቸው በፊት በተለይ ሰሜኖቹ በእንግሊዞቹ እየተመከሩና እየተመኩ ኢትዮጵያን መተናኮልና ሰላሟን ማደፍረስ ጀመሩ። እንደማናቸውም የሕብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ በኢሳው ማህበረሰብ ውስጥ ለነበሩት ነፍሰ ገዳይ፣ ከብት ዘራፊ ሽፍቶች፣ ሌቦችና ቀማኛ ቡድኖች ግለሰብ ወንጀለኞች ምሽግና መጠጊያ ከመሆን ባሻገር እነኚህን ወንጀለኞች የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ በማደራጀትና በማስታጠቅ፣ በጂቡቲና በድሬዳዋ መካከል ባለው ክልል ለጥፋት አሰማሯቸው። የምድር ባቡር ሀዲድና በባቡሩ ላይ ያላቋረጠ አደጋ በመጣል ሀዲዱንና ድልድዮችን ማፍረስ በቆመው ባቡር ላይ ወረራ በማድረግ የተጫነውን ጭነት መዝረፍና ማውደም ብቻ ሳይሆን የባቡሩን ሠራተኞችና ተሳፋሪውን የሕብረተሰብ ክፍል በመግደል የወደብና የምድር ባቡሩን ሥራ በማወክ ብሎም ለማቆምና ፈፅሞ ጥቅም አልባ እስከ ማድረግ ደረሱ።

ወደቡና የምድር ባቡሩ መገንባት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በተለያየ ርቀት በባቡሩ ሀዲድ ዳርቻ ለባቡሩ ሥራ አገልግሎት ተብለው የተቋቋሙት ጣቢያዎች እንዲሁም በሂደትና በእድገት ከጣቢያነት ወደ መንደርነት ብሎም ወደ ከተማነት እያደጉ ትልልቅ ከተሞች ሆነዋል።

ለማስረጃ ያህል ከአቃቂ ጀምሮ የዛሬዎቹ ዱከም፣ ሞጆ፣ ደብረ ዘይት፣ ናዝሬት ወዘተ የድሬዳዋ ከተማ ጭምር የባቡሩ አገልግሎት መመስረት ውጤቶች ናቸው። ከድሬዳዋ ወዲያ ከሽንሌ ጀምሮ (ትልልቆቹን ብቻ ነው የምቆጥረው) ቢዮቅቢቤ፣ አሻ፣ አዲጋላ፣ ደወሌ ወዘተ እየተባሉ የንግድና የሕዝብ መናኸሪያ የሆኑ ከተሞች ተቋቁመዋል።

በእነኚህ ከተሞች አካባቢና አቅራቢያ ካለው ከብት አርቢ ሌላ በየከተሞቹ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በብዙ ሺ የሚቆጠር ነበር። ወንበዴዎቹ በባቡሩ ላይ ሆን ብለው አደጋ የሚጥሉትና ዘረፋ የሚያካሂዱት በእነዚህ ከተሞች አካባቢ ነበር። ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶችና የመንግሥቱ ወታደሮች በእነዚህ ከተሞችና አካባቢያቸው የሚኖረውን ሕዝብ ስለ ወንበዴው ያውቃል፣ ከወንበዴው ጋር ይተባበራል ከማለት አልፈው ከተሞቹ የወንበዴ ምሽግ ሆነዋል በማለት በየጊዜው ከመበዝበዝና ከማመስ አልታቀበም። በታንክና በተዋጊ አውሮፕላኖች ሳይቀር ሽፍቶቹ አደጋ በጣሉ ቁጥር እየደበደቡ ወደ ጂቡቲ ያባረሩት ሕዝብ ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ወይም ከአሩብ ሚሊዮን በላይ ሆኖ ከፈረንሳይ ቅኝነት ነፃ በመውጣት

ለሪፐብሊክ ምስረታ መስፈርት በቃ ካልኩ ስለሚበቃ ወደ ተነሳሁበት የሰላም ጥረት ዝርዝር አመራለሁ።

ጂቡቲ ከፈረንሳይ ቅኝነት ወጥታ ነፃነቷን የምታገኝበት ሁኔታ ከ1960 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ከቀረቡት ትልልቅ አጀንዳዎች አንዱ ሆኖ ሳለ ጉዳዩ የተጓተተው ወይም የዘገየው በጂቡቲ ሕዝብ መከፋፈል ነበር። የዘርና የጎሳ ሥራቸው ወይም ማህበራዊው መሰረታቸው በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነው የአፋርና የኢሳ ብሔረሰብ አባል የሆኑ በጂቡቲ ከተማና በአካባቢዋ ነዋሪ የሕብረተሰብ ክፍሎች የፈረንሳይ መንግሥት ነፃነታችንን ሰጥቶ ከአገራችን የሚወጣ ከሆነ የእኛ ምርጫ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር መልሰን መዋሀድ ነው የሚል አቋም ያዘ።

አፋሮችን ሳይጨምር ከፊል ኢሳዎችንና የሶማሊያ ብሔረሰብ አባሎችን ያቀፈ ሌላ የሕብረተሰብ ክፍል ከአዲስቱ የሶማሊያ ሪፐብሊክ ጋር እንቀላቀላለን የሚል አቋም ያዘ። ከዚሀ በላይ ከገለጽኳቸው ሁለት የፖለቲካ እድምተኞች የሚለዩ ከአፋር፣ ከኢሳና ከሶማሊያ ብሔረሰብ አባላት በተጨማሪ ልዩ ልዩ የውጭ ዝርያ ያላቸውና ግን የጂቡቲ ዜጎች የሆኑ የአፍሪካ፣ የአውሮፓ፣ የአረብና የኢስያ ወዘተ ትውልዶች ቅምር ከሆኑት ሁለት የፖለቲካ እድምተኞች መካከል አንዱ ነፃነት ሲል ሌላው ደግሞ "እኛ በምናስተውለው የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዳሻን ወይም እንደምንፈለገው የራሳችንን እድል ለመወሰን የሚያስችለን አይደለም። የጂቡቲ ሕዝብ ዛሬ እንዳለው ከቅኝ ገዥዋ ከፈረንሳይ ጋር ላልተወሰነ ጊዜ ካልቆየ በስተቀር ነፃነትም ሆነ ወይም ሌላ ምርጫ ቢያደርግ የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግሥታት መዋጊያ የጦር ሜዳ መሆኑ ነው" በሚለው በአጠቃላይ አራት ላይ የተከፈለና ከቅኝ ገዥዋ ከፈረንሳይ ራሱን ነፃ ለማድረግ ያለመዘጋጀቱ በመታወቁ ጉዳዩ ሲጓተት ቆይቶ እስከ ኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ ጊዜ ደረሰ።

አብዮታዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ከፈረሰው አሮጌ ሥርዓት የተረከባቸው አያሌና ውስብስብ ውስጣዊ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች፣ ተፈጥሮ ያስከተለው ቀውስ ሕዝቡን ለረሀብ አደጋ የዳረገበት ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆኑ ከገንጣይና አስገንጣዮች ጋር በትጥቅ ትግል ላይ እያለ በጂቡቲ ምክንያት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሶማሊያ ሕዝብ ጋር ላለማዋጋት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኃይለሥላሴ መንግሥት ሶማሊያ አለኝታዬ ናት፣ ወይም ከልሱን የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች እስከወረሩት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት የአስተዳደር ክልል ነበረች የሚል አቋም ነበረው።

ይህንን የኢትዮጵያ አለኝታ ጥያቄ በጦርነት ጊዜ እንግሊዞችም ቢሆኑ በኢትዮጵያዊያን ርዳታ የአፍሪካን ቀንድ እስኪቆጣጠሩ ድረስ አልተቃወሙም። የሶማሊያዎች ከኢጣሊያ ቅኝነት ነፃ ስለመሆን ጉዳዩ የተነሳው ወይም የተቀሰቀሰው የሶማሊያ ሕዝብና መሪዎች በአነሱት ጥያቄ ሳይሆን፣ ቅኝ ገዥዋ ኢጣሊያ ከጀርመን ጋር አብራ ባለ ቃል ኪዳን አገሮች ማለትም፣ እንግሊዝ ሶቭየት ሕብረትንና ሰሜን አሜሪካ ወዘተ ያሉበትን ጎራ ወግታ ከተሸናፊዎቹ መንግሥታት አንዷ ከሆነች በኋላ ቅጣት ሲገባት ተመልሳ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ የነበሩትን አገሮች መያዝ ስለሌለባት የኢጣሊያ ቅኝ የነበሩ አገሮች ነፃነታቸውን ማግኘት አለባቸው በመባሉ ምክንያት ነው።

የሶማሊያ ሕዝብ የነፃነቱን ንቅናቄ ሲጀምር የነበረው ችግር እንደ ጂቡቲ የሕዝብ መከፋፈል ሳይሆን አንዱና የመጀመሪያው ችግር የሶማሊያን ሕዝብ ከቅኝ ተገዥነት ነፃ ለማድረግ የተደራጀ ወይም የተቋቋመ ምንም አይነት የፖለቲካ ድርጅት ያለመኖሩ ሲሆን

ሁለተኛውና ምናልባትም ዋናው ችግር፣ የሶማሊያን ሕዝብ በነፃ መንግሥትነት የሚያቆመው ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ወይም አስተማማኝ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ያለመኖሩ ነበር።

በዚህ ምክንያት አዲሱ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር በመቸገሩ የቀድሞ ቅኝ ገዥዋ ኢጣሊያ ተመልሳ የሶማሊያ ሕዝብ ነፃነቱን ለማግኘት እስኪደራጅና እስኪሰናዳ ድረስ በሞግዚትነት ታስተዳድረው የሚል ውሳኔ ሰጠ። የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በቅድሚያ የሶማሊያን ሕዝብ ነፃ መሆን ሲቃወም ከመቆየቱ በተጨማሪ ኢጣሊያ በሞግዚትነት ወደ ሶማሊያ መመለሷን በፅኑ ተቃወመ። በተባበሩት መንግሥታት በኩል ሶማሊያ ወደ ኢትዮጵያ ትመለስ የሚል ድጋፍ ቀርቶ ለተወሰነ ጊዜ በሞግዚትነትም ለመርዳት ትበቃለች የሚል ግምት የሌለው ከመሆኑ ሌላ ከሶማሊያ ሕዝብ ወገን ኢትዮጵያ የምታቀርበውን ጥያቄ ተቃዋሚ እንጂ ድጋፍ የሰጠ አንድም የሕብረተሰብ ክፍል አልነበረም ወይም አልተገኘም። የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሶማሊያ አለኝታዬ ናት የሚለው አቋሙ እውነት ከልብ ከሆነ፣ ኢጣሊያ ሶማሊያን በቅኝነት ስትገዛ ከነበረችበት ከ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ኢትዮጵያ የኢጣሊያንን ቅኝ ገዥነት የተቃወመችበት ጊዜ የለም። በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ከቅኝ ገዥዋ ከኢጣሊያ ጋራ የነበረው ውዝግብ የወሰን ጥያቄ እንጂ ሶማሊያን በአለኝታነት የመጠየቅ ወይም የሶማሊያን ሕዝብ ነፃነት የሚመለከት ጥያቄ አልነበረም።

የኢትዮጵያ መንግሥት በታሪክ ለሶማሊያ ሕዝብ ነፃነት በገሀድ ጥብቅና የቆመበት ጊዜ ያለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የሶማሊያ ብሔረሰብ ለነፃነቱ ይንቀሳቀስና ይታገል ዘንድ ኢትዮጵያ የሰጠችው አመራር፣ የመንፈስና የቁሳቁስ ድጋፍ የለም።

በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያውቀው የሚገባ ነገር ቢኖር በታሪክ የሶማሊያ ብሔረሰብ ከኢጣሊያ ፋሽስቶች ቅኝነት ራሱን ነፃ ያደርግ ዘንድ አስፈላጊውን ቅስቀሳ ከማድረግ ጀምሮ የታጠቀ ነፃ አውጪ ግምባር አደራጅተው እስከማንቀሳቀስ ድረስ ታላቅ ጥረት ያደረጉት ወጣቱ ልጅ እያሱ ብቻ መሆናቸውን ነው። ልጅ እያሱ የተለያዩ ባላባቶችንና የጎሳ መሪዎችን ካነቁና ካነሳሱ በኋላ በእነሱም አማካኝነት ከመላው የሶማሊያ ጎሳዎች የተውጣጡና በትጥቅ ትግል መላውን ሶማሊያ ነፃ የሚያወጣ የአርበኞች ግምባር አደራጅተውና አስታጥቀው፣ የግንባሩን ተወካዮችና መሪዎች ጅጅጋ ከተማ ላይ ጠርተው የእስልምና እምነት ምልክት ያለበትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አሰርተው፣ ለግምባሩ አርማ እንዲሆን ስለሰጡ፣ ይህ እንዴትና ለምንስ እንደሆነ ከማንም በላይ በተሻለ የሚያውቁት ደጃዝማች ተፈሪ እንደማያቁና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን የተሰወረና ሃገር የሚበድል ሥራ እንደተሰራ አድርገው ልጅ እያሱ ሰልመዋል በማለት ወነጀሏቸው። ደጃዝማች ተፈሪ የሸዋን ካህናትና መሣፍንት እንዳሳመኑት ልጅ እያሱ አዘውትረው ወደ ሐረርጌ ሲመላለሱ የነበረውና እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ለወራቶች የሚቆዩት ሴት ስለወደዱ ሳይሆን የሶማሊያን ነፃ አውጪ ግምባር ለማደራጀት ነበር ።

ወደ አርዕስቱ ልመለስና የሶማሊያን ሕዝብ ነፃነት በተመለከተና እንዲሁም የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሶማሊያን አለኝታዬ ብሎ የመቆየት ጉዳይ ስህተት ብቻ ሳይሆን የተምታታም ጉዳይ ነው። በዚያ የጊዜ ክልል ውስጥ የእንግሊዝ ኢምፔርያሊዝም በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው አፍሪካ ፈላጭ ቆራጭ በነበረበት፣ ኦጋዴንና ኤርትራን ለኢትዮጵያ በአማራጭ ከማቅረብ ባሻገር ታላቋ ሶማሊያ የተሰኘውን የመስፋፋት ዓላማ ፈጥሮ ለሶማሊያ የፖለቲካ መሪዎች በሰጠበት ጊዜ ሶማሊያ አለኝታዬ ናት ብሎ መቅረትና የሶማሊያን ሕዝብ ነፃነት ያለመደገፍ ከእንግሊዝና ከመስሎቹ ጋር ቅራኔ ውስጥ ከመግባት ባሻገር ትርፉ የሶማሊያን ሕዝብ ለዘላለም ፀረ-ኢትዮጵያ ማድረግ ነበር።



አፄ ኃይለሥላሴና ዚያድ ባሬ በአዲስ አበባ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ ላይ ተገናኝተው ሲወያዩ

የኢትዮጵያ መንግሥት አቋም ስህተት ብቻ ሳይሆን አንዱ ከሌላው ጋር የሚቃረንና የተምታታ ነበር ያልኩበትን ምክንያት ላስረዳ። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድንበር የሕንድ ውቂያኖስና ቀይ ባሕር ናቸው የሚሉትና ከዚህ አባባል በተቃራኒው ከዛሬዋ ሶማሊያ ጋር ከመጨቃጨቅና ከመጋጨት አልፈን ለአውዳሚ ውጊያ የዳረገንን ችግር ከኢጣሊያ ጋር የፈጠሩት ዳግማዊ ምኒልክ ዛሬ ሶማሊያ የሚባለውን ምድር በኢጣሊያ መንግሥት በሰነድ ከአስረከቡ በኋላ ዳግም ኤርትራን ለማስረከብ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር በደረሱበት የውጫሌ ውል ውስጥ ኢጣሊያ በሸፍጥና በተንኰል ልትጠቀምበት የሞከረችውን አንቀፅ 17 የሚቃወምና የሚያወግዝ ደብዳቤ ለየመንግሥታቱ ሲጽፉ ወይም በጻፉበት ጊዜ ኤርትራንና አጋዴንን አለኝታዬ ናቸው፤ አገሬ ናቸው በማለት ሲያስታውቁ የቀረውን ማለትም ዛሬ የሶማሊያ ሪፑብሊክ ይዞታ የሆነውን ምድር አላከሉም ወይም አልጠየቁም።

መላውን ሶማሊያ አለኝታዬ ነው የሚለው የአፄ ኃይልሥላሴ መንግሥትም ከተግባር አኳያ አበክሮ ሲታገል የነበረው የአጋዴን አውራጃ ብቻ ለማስመለስ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ አፄ ኃይለሥላሴ በበኩላቸው ከአማካሪዎቻቸውና ከረዳቶቻቸው ተነጥለው ሲያራምዱት የነበረው ሃሳብ የአጋዴን ክልል በሙሉ ለእንግሊዝ መንግሥት ሰጥተው በሰሜን ሶማሊያ ወደ ዘይላ ወደብ የሚያደርስ ጠባብ መሬትና በወደቡ የመጠቀም መብት ብቻ ነበር። የጂቡቲና የሶማሊያ ሕዝቦች የነፃነት ጥያቄ መነሻና ግኝት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

የጂቡቲ ሁኔታ በየጊዜው እየተለዋወጠ ሄዶ በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክልልና በሕንድ ውቂያኖስ ዳርቻ ፈረንሳይ አንድ ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው ትንሽ መንደርና ሕዝብ ቅኝ ገዥ ቢያደርጋትም ለ99 ዓመታት የተደረገውን ውል መሠረት በማድረግ ብቻ ኢትዮጵያ ጂቡቲን አለኝታዬ ብትል አግባብ ሲሆን የሶማሊያ መንግሥት አቋም ግን የመስፋፋት ዓላማውን የማራመድ ተግባር ነው። ጊዜ፣ ታሪክ፣ ቦታና ሁኔታዎች ከሕብረተሰብ እድገት ጋር ሲለዋወጡ የተፈጠረውን ክስተት ከነባራዊው ሁኔታ ጋር በማገናዘብና በመገምገም አቋምን ማስተካከል ተገቢ ስለሆነ ጂቡቲን አስመልክቶ ጊዜና ታሪክ ላቀረበልን ጥያቄ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይቻለን ዘንድ በሳል፣ የፖለቲካ፣ የታሪክና የሕግ ባለሞያዎችን አሰባስበንና ጊዜም ወስደን ሰፊ ውይይት በማድረግ ከዚህ ግርጌ ወደምገልጣቸው እልባት ደረስን።

ኢትዮጵያ በአብዮቷ አማካኝነት የራሷን ውስጣዊ ችግሮች ሳትፈታ፣ በሰሜንና በደቡብ የአገሪቱ ክልሎች ከገንጣዮችና አስገንጣዮች እንዲሁም ከተለይዩ ፀረ-አብዮትና ፀረ-ሕዝብ ቡድኖች ጋር እየታገለች በጂቡቲ ምክንያት፣ ጂቡቲ አለኝታዬ ናት ከሚለው ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥትና ከጂቡቲ ሕዝብ ጋር መዋጋት ለአገራችን ጠቃሚ ካለመሆኑም በላይ ለመዋጋት ዝግጁ ያለመሆናችንም ግንዛቤ ተወሰደ።

በነፃነቱ መቃረብ መደሰት የነበረበት፣ ከኢትዮጵያና ከሶማሊያ ሊሰነዘር የሚችለውን ጥቃት በመፍራት ላይ ባለበት ጊዜ የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት የጂቡቲን ሕዝብ ነፃነት ክፉኛ ሲቃወም የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የሕዝቡን ነፃነት በመደገፍ ለነፃነቱ ግኝት የሚያስፈልገውን ሁሉ የበኩሉን ማናቸውንም ርዳታ ከመስጠት ፋንታ ነፃነቱን መቃወም የአብዮታዊያን ተግባር ሊሆን የማይገባ ከመሆኑ ባሻገር ከዚህ በፊት በሶማሊያ ሕዝብ ነፃነት ጊዜ የተሰራውን ስህተት መልሶ መድገም እንደሆነ ታመነበት።

የጂቡቲን ሕዝብ ነፃነት መደገፍ ማለት፣ የኢትዮጵያንና ጂቡቲን ሕዝብ የነበረ ታሪካዊ አንድነት መካድ ወይም መርሳት፣ የኢትዮጵያና የጂቡቲ ሕዝቦች መልሰው ለመዋሀድ ያላቸውን ፍላጎት ማገድ ወይም መንፈግ ማለት አይደለም። ወዳጅነትና ጉረቤትነት ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ታሪካዊ አንድነት ያለውን ሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ማሟላትና ነፃነት መደገፍ፣ ከሁሉ በፊት ሦስቱን ማለትም፣ የኢትዮጵያ፣ የጂቡቲንና የሶማሊያን ሕዝቦች አስፈላጊ ካልሆነ የጦርነት ውድመትና ጥፋት ማዳንና በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት ይፈጠር ዘንድ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተወሰደ አንድ በጎ እርምጃ ነው ተብሎ መተርጎም ያለበት ውሳኔ ነው የሚል ነበር። በጂቡቲ ነፃነት ምክንያት በጂቡቲ ውስጥ ወይም በሶማሊያና በኢትዮጵያ ምድር ይነሳ የነበረውን ውጊያ በማስቀረት ብቻ ሳንወሰን የጂቡቲን ነፃነት ምክንያት አድርገን ከሶማሊያ መንግሥት መሪዎች ጋር ለሰላም መነጋገሪያ መድረክ ለመፍጠር ሞከርን።

ታሪኩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ለአፍሪካ ቀንድ የሚበጀውን የጂቡቲን ነፃነት መደገፍ ብቻ ሳይሆን ለነፃነቱ ግኝትም የሚያስፈልገውን ርዳታ ሁሉ መስጠት ነው የሚለውን አቋም ከወሰድን በኋላ አንድ በኔ የተረቀቀ ደብዳቤ በማዘጋጀት፣ በአዲስ አበባ የደቡብ የመን አምባሳደር የነበረ ጓድ ጠርተን ለደቡብ የመን ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ ለጓድ አብዱል ፈታህ እስማኤል የሚሰጡ በስም የታሸጉ ፖስታዎችን ሰጠነው።

የአንዱ ፖስታ አድራሻ ለሶማሊያው ፕሬዝዳንት ጄነራል ዚያድ ባሬ ሲሆን ሁለተኛው ለደቡብ የመን ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ የሚሰጥ የዋናው ደብዳቤ ቅጅ ነበር። የደብዳቤው ይዘት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

"ኢትዮጵያ በወደቀው አሮጌው ሥርዓት ጊዜም ሆነ ዛሬ፣ የሶማሊያን ሕዝብ ደህንነት፣ ሰላም ማህበራዊ እድገትና መልካም ጉርብትና በስተቀር ከእናንተም ሆነ ከማንም አንዲት ቅንጣት መሬት አትፈልግም።

የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሕዝቦች ሳይሆኑ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች በፈጠሩት ችግር በሁለቱ አገሮቻችን መካከል እንዲኖር የምንመኘው ቀርቶ፣ የምናስተውለው ጠብና ጥላቻ ብቻ በመሆኑ ስናዝን እንኖር ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአያሌ ዘመናት አምጦ የወለደው አብዮት በፈነዳ ጊዜ ለምንወዳት አገራችንና ሕዝባችን ያስገኛል ብለን ከጠበቅነው ማህበራዊ ፍትህና እድገት እኩል ተስፋ ያደረግነው፣ ከወንድማችን ከሶማሊያ ሕዝብ ጋር በአንድ ርዕዮተ ዓለምና ማህበራዊ የእድገት አቅጣጫ ስለምንመራ በመካከላችን ያሉትን የቅኝ ግዛት ኃይሎች ስሪት የሆኑትን

ችግሮች በውይይት እየፈታን በመዋጋት ፈንታ በመቻቻል፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት በሰላም አብረን እንኖራለን በማለት ነው።

በአፍሪካ ቀንድ የሶማሊያ ሕዝብና ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ የተከተሉት የሰላምና የሶሻሊዝም ፈለግ ኢምፔሪያሊዝምንና የአካባቢውን አድህሮት ክፉኛ አስደንግጧቸዋል። ስለሆነም በሁላችንም ዘንድ ጊዜና ሥርዓት ባቆየን ችግሮቻችን ላይ ብቻ እያተኮርንና እየተናቆርን ብለንም አውዳሚ ጦርነት ውስጥ ራሳችንን ከትተን ሕዝባዊ አብዮታችንን በመቀልበስ ወደ እነሱ የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት የሚመልስ ሴራ እየተደገሰልን ነው።

ከታቀዱልን አያሌ ወጥመዶች አንዱና ቀዳሚው እየተቃረበ ባለው የጂቡቲ ሕዝብ ነፃነት ምክንያት እኛና እናንተ በጂቡቲ ውስጥ እንድንዋጋ ነው። በጂቡቲ ውስጥ ብንዋጋ የምንጠቀመው እኛ የጂቡቲ፣ የሶማሊያና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሳንሆን ፀረ-ሕዝቦች ብቻ መሆናቸውን አመዛዝነን የኢትዮጵያ አብዮታዊያን አገራችን ለረጅም ጊዜ በጂቡቲ ላይ የነበራትን ታሪካዊና ሕጋዊ አለኝታ አንስተናል።

በሁለቱ ሀገሮቻችን መካከል በተለይም በአፍሪካ ቀንድ በአጠቃላይ አስተማማኝ ሰላም ለማስፈን ካለን ምኞትና ከዚህም አኳያ ኢትዮጵያ ከምታደርጋቸው የሰላም ጥረቶች ይህ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

የሶማሊያ አብዮታዊያን አፀፋውን እርምጃ የሚወስዱ ብቻ ሳይሆን ለሁለቱ ሕዝቦቻችን ሰላም፣ ደህንነትና የጋራ ማህበራዊ እድገት የሚበጀውን ሁሉ በጋራ ለመምከር ለእናንተ ባመቸ ጊዜና ቦታ ለመገናኘት ዝግጁዎች ነን" የሚል ነበር።

ከአረቡ ዓለምና ከሶማሊያዎች ጋር በእጅጉ የሚቀራረቡት የመኖች ከመሆናቸው ባሻገር አብዱል ፈታህ እስማኤልና ዝያድ ባሬ ወዳጆች ስለነበሩ፣ ጓድ አብዱል ፈታህ እስማኤል የእኛ ደብዳቤ እንደደረሰው ለእሱ የተጻፈውን ከተመለከተ በኋላ ለፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ የተጻፈውን ወደ መቃዲሾ ወስዶ አደረሰ።

ደብዳቤው ላይ የሰፈሩት ፍሬ ነገሮች ሁለቱ በዝርዝር ከተወያዩባቸው በኋላ አብዱል ፈታህ የፕሬዝዳንት ዝያድን አጠቃላይ ሃሳብና እንዲሁም አስተያየት ጭምር የቃል መልስ ይዞ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ወደ እኛ ላከው። የተላከልን መልስ እኛ እንደላክነው ደብዳቤ ሳይሆን የቃል መልስ መሆኑ፣ ሶማሊያዎች በእኛ ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ ብቻ ሳይሆን የእነሱ ምርጫ ሰላም ያለመሆኑን የሚያስረዳን ነበር። የጄነራል ዝያድ የቃል መልስም ቢሆን በቀጥታ ወደ እኔ የሚያመራ ሳይሆን፣ ለእኔ እንዲነገረኝ ለአብዱል ፈታህ የተነገረውን ወይም የተሰጠውን መልስ ነው እንዲሁ በቃል የውጭ ጉዳዩ ሚኒስትር ያስረዳኝ ዘንድ የተላከው።

ለየመኑ መሪ እንደተነገረው የጄነራል ዝያድ ባሬ መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር። "እውነትና ልባዊ ከሆነ ደብዳቤው ላይ ሰፍረው ባነበብኳቸው የኢትዮጵያዊያን አስተያየቶችና የሰላም ሃሳቦች ተደንቄያለሁ። በደብዳቤው ላይ የሰፈሩት ሀሳቦች በእርግጥ እኛ ከምናውቃቸው ሐበሾች ወይም ኃይለሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ ገዥ መደብ አባላት ጭንቅላት የሚወጡ ሳይሆኑ ከአዲሱ ትውልድ የፈለቁ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ጂቡቲን በተመለከተ ኢትዮጵያ የወሰደችውን አቋም ለዓለም ይፋ ስታደርግ እኛም እንከተላታለን። ከአዲሶቹ የኢትዮጵያ የአመራር አካላት ጋር ተገናኝተን ለሁለቱ አገሮቻችን የጋራ ጥቅም፣ የጋራ ደህንነትና ሰላም ስለምንወያይበት ጊዜና ቦታ እናስብበታለን" የሚል ነበር።

በደቡብ የመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማካኝነት የተነገረንን የጄነራል ዝያድ ባሬን አስተያየት ካዳመጥን በኋላ ጉዳዩ ይፋ ሆኖ የሶማሊያና የእኛ ወዳጆች ለሆኑት የሶሻሊስት መንግሥታት ቢታወቅ እነሱን ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ለማድረግ የሚጋብዛቸው ወይም የሚያበረታታቸው ብቻ ሳይሆን ለጦርነት በተዘጋጀው የሶማሊያ መንግሥት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል ብለን ገመትን። ስለሆነም ኢትዮጵያ ለጂቡቲ ሕዝብ የነፃነት ግኝትና ለአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት ስትል የመሬት አለኝታዋን ያነሳችና የሶማሊያ መንግሥትም የሷን ፈለግ ተከትሎ ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም የበኩሉን ርምጃ እንዲወስድ ጥሪ ያደረገች መሆኗን በአዲስ አበባ ተቀማጭ የሆኑት የሶሻሊስት መንግሥታት አምባሳደሮች እንዲያውቁት በማድረጋችን ወሬውን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓለም አዘመቱት።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ ፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ ለደቡብ የመን ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ "ከአዲሱ የኢትዮጵያ የአመራር አካል ጋር ተገናኝተን ስለ ሁለቱ አገሮቻችንና ሕዝቦቻችን ሰላም፤ ማህበራዊ ደህንነትና እድገት በጋራ ስለመምከሩ እናስብበታለን" ያሉት መልስ ተከታይ ሂደት ይመስላል በ1969 ዓ.ም በመስከረም ወር፣ በሶቭየት ሕብረት በቀዶ ጥገና ህክምና ሙያ የሰለጠነ፣ የሶማሊያ ሶሻሊስት ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነ፣ የፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ የቅርብ የስጋ ዘመድና የፖለቲካ አማካሪ ዶክተር አደም ያሲን የሚባል ወጣት ወይም ልጅ እግር ሰው በቱሪስት መልክ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ጽሕፈት ቤት በመሄድ ከሶማሊያ ፕሬዝዳንት የተላክሁ ስለሆንኩ አቅርቡኝ ሲል ይጠይቃል።

በቅድመ አብዮት በሶማሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ከነበሩት አቶ አያሌው ማንደፍሮ ጋር ይተዋወቁ ስለነበረ ዶክተር አደምን ተቀብዬ በጠየቀው መሠረት ማንም በሌለበት ብቻውን ሳነጋግረው ለውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ሰዎቻችን እንደተናገረው በእጁ የሚሰጠኝ የጽሑፍ መልዕክት አልያዘም። የጽሑፍ መልዕክት ብቻ ሳይሆን ፕሬዝዳንቱ "ለእርሶ ሰላምታቸውንና በጎ ምኞታቸውን እንዳቀርብላቸው ጠይቀውኛል" ከማለት ሌላ ይህንን ብለውኛል የሚል የቃል መልዕክትም አልነበረም። ጠቅላላ አቀራረቡና አነጋገሩ ሁሉ እንዳስረዳኝ የመጣበት ዋና ምክንያት፣ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ያንን የመሰለ የሰላም ፍላጎት የሰፈረበት ደብዳቤ የጻፈውና ለውይይትም የጋበዘን ምን ነገር ቢያዘጋጅልን ወይም ሊሰጠን ቢያስብ እንደሆነ ሰልለህ ተመለስ ተብሎ የተላከ ይመስላል።

የፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬን መልዕክት ላደርስ መጣሁ ያለ ስለሆነ ከተቀበልኩት በኋላ የውይይታችን መክፈቻ እሱ ያመጣው መልዕክት እንዲሆን በማድረግ የመጣበትን ምክንያትና ያመጣውን መልዕክት እንዲያስረዳኝ ጠየቅሁት። "እርስዎ በየመኑ ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ በጓድ አብዱል ፈታህ እስማኤል አማካኝነት በላኩት ደብዳቤ ላይ የሰፈሩት የሰላም ፍላጎቶችና በጎ ቃላቶች፣ ለሁለቱ ሕዝቦቻችን ባለዎት በጎ ምኞት ፕሬዝዳንቱ በጣም ተመስጠዋል። እኔን ወደ እርስዎ ሲልኩኝ እንድነግርዎ የነገሩኝ፣ የእኛ ጥያቄ መሬት ነው፣ ወደ ጦርነት እየገፋን ያለው ችግርም የወሰኑ ችግር ነው። የጥያቄያችን መልስ በሻለቃ መንግሥቱ እጅ ነው። ሂድና የሚለንን ስማ፣ የሚሰጠንን ተቀበል ነው የተባልኩት" በሚል ጀመረ።

ውይይታችን በቀጠለና በሰፋ ቁጥር እልፎ አልፎ አውቆም ሆነ ሳያውቅ ከሰውዬው አንደበት የሚሰነዘረው "ይሄ የኔና የእርስዎ ግንኙነት ወሳኝና የመጨረሻ ነው፣ ለመሬት ጥያቄያችን ተገቢ መልስ ባይኖራችሁ በኃይል ወይም በውጊያ እናገኘዋለን" በማለት ለማስፈራራት የሚሞክር አቀራረብ ነበር። ከዚህም የተገነዘብኩት ሊወጉን መወሰናቸውን፣

በገንቡት የጦር ኃይልና በታጠቀው መሣሪያ እጅግ መመካታቸውን፤ ከመጠን በላይ መተበታቸውን ነበር። የእኛንም የሰላም አቀራረብ የተረጎሙት በድክመትና በፍርሀት እንጂ ከበጎ ፈቃድ ወይም ፍላጎት የመነጨ ነው ብለን ያለማመናቸውን በግልፅ የሚያስረዳ ነበር።

ሆኖም የሶማሌዎችን ፀባይና ባህል ከማወቄም በላይ እኔም ከእሱ ልረዳና ላውቀው የምፈልገው ነገር ስለነበረ በትዕግሥት እያዳመጥኩ እንዳውም ራሱን በበለጠ ከፍቶ በልቡ ያለውን ሁሉ እንዲናገር እሞክር ነበር። እኔ የምሰጠውን መልስ ከመጠበቅ በስተቀር በእርሱ በኩል ሌላ የሚነሳ ወይም የሚነገር ነገር ሳይኖር ለውይይታችን የተሰጠው የአንድ ቀን ግማሽ ጊዜ ተገባዶ በበነጋው ለሁለተኛ ጊዜ ለመገናኘት ቀጥሬ አሰናበትኩት። እሱን አሰናብቼ፤ ከደርግ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጉዳዩ አግባብ ያላቸውን ጥቂት ሰዎች ጠርቼ ዶክተሩ ከጄኔራል ዝያድ ባሬ ባመጣው መልዕክት ላይ ተወያይተን በበነጋታው በምሰጠው መልስ ብቻ ላይ ሳይሆን በአጠቃላይ ከሶማሊያዎች ጋር ስለ ሰላም ስለወሰን ብንነጋገር የምንጠቀምበትን የአቀአራረብ ስልት አቀድን።

በበነጋታው ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኝተን፤ ትናንትና የጄኔራል ዝያድ መልዕክት ነው ብለህ እንደነገርከኝ በሁለቱ አገሮቻችን መካከል መፍትሄ የሚያሻቸው ውስብስብ ችግሮች እንዳሉ አያጠያይቅም። ከችግሮቻችን ትልቁና ዋናው ከእኛ ሳይሆን እናንተ የምታነሱት የወሰን ጥያቄ ወይም የመሬት ጥያቄ ጉዳይ ነው። ስለወሰኑም ሆነ ስለሌሎቹ ችግሮቻችን መፍትሄ መገኘት አለበት። ሰው ለፈጠረው ችግር ሁሉ በጎ ፈቃድና ትዕግስት ካለ ሰው የማያገኘው መፍትሄ የለም። በዚህ እምነትና ግንዛቤ በእኛ በኩል ሁላችንም የችግሮቻችንን መንስኤ ወይም ታሪካዊ ምክንያት፣ የችግሮቻችንን እድሜ፤ ባህሪያቸውንና ውስብስብነታቸውን ተገንዝበንና አምነን ተቀብለን፤ እንደ ባህሪያቸውና ክብደታቸው ቅደም ተከተል በማውጣት፣ ከቀላሉ ወደ ከባዱ ወይም ከቀላሉ ወደ ውስብስቡ ደረጃ በደረጃ የአንድ ወገን ሳይሆን የጋራ መፍትሄ ልንፈልግላቸው ይገባል የሚል እምነት አለን። የሁለቱም አገሮች የአመራር አካላት በቅድሚያ ማመንና መቀበል ያለባቸው በሕዝባቸው መካከል ጥላቻን ሲዘሩ፣ የሕዝቦቻቸውን አእምሮ በጠላትነት ፕሮፓጋንዳ ሲመርዙ የኖሩ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ባልሆኑ ግጭቶች ደም ሲያፋሱ መኖራቸውንም ነው። ይህንን የምናምንና የምንቀበል ከሆነ፤ ብለንም እነዚህን ችግሮች ከሥራቸው ነቅለን ለመጣል በሕዝቦቻችን አእምሮ ሰላምን፣ ወንድምና እህትማማችነትን በመተካትና ፍቅርን በመዝራት መተሳሰብና መተማመንን መፍጠር አለብን።

እንዲህ አይነቱን በጎ ነገር ተግባራዊ ለማድረግ ለምሳሌ ያህል፤ በሕዝቦቻችን መካከል ስናካሄድ የነበረውን የጠላትነት ፕሮፓጋንዳ ማቆም፤ የፈረሰውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችንን መልሶ ማደስ፤ የባህልና የስፖርት ግንኙነት መመስረት፣ ብለንም ወደ የአየር መንገድ ግንኙነትና ወደ ጋራ ንግድ ወዘተ በመሄድ የመጨረሻውንና ትልቅ ነው የምንለውን የመሬት ወይም የወሰን ችግር ፈንቅለን ለመጣል የሕዝባችንን ትብብርና ሙሉ ፈቃድ እናገኛለን ብለን እናምናለን በተባሉት የማግባቢያ ሀሳቦች ዙሪያ ብዙ ካልኩ በኋላ ከእነኝህ አንፃር የሱን አስተያየት ጠየኩት።

"ጓድ መንግሥቱ እንደ ድፍረት እንዳይቆጥሩት ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ይህ አሁን የዘረዘሩልኝ የኢትዮጵያ የሰላም ስልት የምትሏቸው አቀራረቦች ለኔ አዲስ ነገር አይደሉም። በአለፉት ዘመናት የወደቀው ሥርዓት አራማጅ ከነበሩት ኢትዮጵያዊያን ጋር በተገናኘንባቸው መድረኮች ሁሉ ስንሰማቸው የነበሩ ሃሳቦች ናቸው። በእኛ አስተያየት ኢትዮጵያ ሁልጊዜ እነኝህን ስልቶች በየውይይቱ መድረክ ቀድማ የምትደረድራቸው፣ አሁን እርስዎ እንዳሉት በአገሮቻችንና ሕዝቦቻችን መካከል ስር ሰዶ የኖረውን ችግራችንን

ነቅሎ ለመጣል ሳይሆን ጊዜ የመግዣት ወይም የማዘግየት ስልቶች ናቸው ብለን ነው የምናምነው። የእኔ መሪ፣ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ይህንን ሃሳብ አቀረበልን ብዬ ብነግራቸው በእጅጉ ያዝናሉ። በኢትዮጵያ አብዮት የለም፣ ኢትዮጵያም አልተለወጠችም በማለት ተስፋ ይቆርጣሉ" አለኝና ለውይይቱ የተመጠነው ጊዜ ስለተገባደደ ለሦስተኛ ቀናት ወይም ለመጨረሻው ውይይት ቀጥሬው ተለያየን።

ለሦስተኛ ቀን የቀጠርኩበት ምክንያት ከእሱ ጋር በእዚያ አይነት የሚደረግ ውይይት ፋይዳ አለው ብዬ ሳይሆን ግለሰቡ የፕሬዝዳንቱ የቅርብ የስጋ ዘመድና የፖለቲካ አማካሪ ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ ሶማሊያ ከኢትዮጵያ የምትፈልገውን በርግጠኝነት ማወቅ ስለነበረብኝ ነው። በሦስተኛው ቀን ውይይታችንን ስንጀምር ያልኩት፣ ባለፉት የሁለት ቀናት ውይይታችን እንደተረዳሁት አንተ ከእኔ ለማግኘት የፈለከው ወይም የተላከው ከእኔ ጋር ስለ ሁለቱ አገሮቻችንና ሕዝቦቻችን ለመወያየት ሳይሆን ለእናንተ የመሬት ጥያቄ እኔ ምን መልስ እንዳለኝ ለማወቅ ብቻ ይመስለኛል። ይህ ግንዛቤዬ ትክክል ነው? ብዬ ስጠይቀው "የእኛ የመሬት ጥያቄ ወይም የወሰኑ ጉዳይ የመላው ሶማሊያ ችግር መሆኑን ይወቁልኝ እንጂ አሁን በገለጹልኝ መሠረት ግንዛቤዎ በጣም ትክክል ነው" አለኝ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን እስከ ዛሬ የምናውቀው በሁለቱ አገሮቻችን መካከል ያለው ወሰን የተከለለው የሶማሊያ ሕዝብ ነጻነቱን ከማግኘቱ በፊት በቅኝ ገዥዋ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል በተደረገ ስምምነት ስለሆነ በነፃዋ ሶማሊያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ሌላ አዲስ የወሰን ክልል ስምምነት መደረግ አለበት ማለታችሁን ብቻ እንጂ አንተ እዚህ እንዳቀረብከው ወይም ከመሪህ እንደተላከው አሁን ካላችሁ ይዞታ በተጨማሪ ከኢትዮጵያ የምትጠይቁትን መሬት ወይም እናንተ ወሰን ብላችሁ ስለምታስቡት የምናውቀው ነገር ስለሌለ ይህንን ልትገልፅልኝ ትችላለህ? አልኩት።

ከዚህ በኋላ የራስህን ግለሰባዊ አስተያየት ወይም የፕሬዝዳንትህን ሳይሆን ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ግንዛቤ ይበጀን ዘንድ ሃገርህ ሶማሊያ ወይም የሶማሊያ መንግሥት በርግጠኝነትና በማያዳግም ሁኔታ ወሰናችን ነው የምትሉትን ተነስና በዚህ የፖለቲካ ካርታ አማካኝነት አሳየኝ ብዬ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ካርታ ወደ ተሰቀለበት ለመሄድ ከመቀመጫዬ ስነሳ "ይቀመጡ ለዚህ ተዘጋጅቻለሁ" አለና በኢጣሊያኖች ጥንት የተሰራ የኢትዮጵያንና የሶማሊያን ምድር ያካተተ የፖለቲካ ካርታ ከሳምሶናይቱ ውስጥ አውጥቶ በመግለጥ እነሱ ወሰናችን የሚሉትን መስመር ያሳየኝ ጀመር።

ከኢትዮጵያ ሰሜን ምሥራቅ ዛሬ ጂቡቲና ኤርትራ ከሚዋሰኑበት ወሰን ጀምሮ፣ ሐረርጌን፣ ባሌንና ሲዳሞን በሙሉ ማለት ይቻላል የሶማሊያ ክልል የሚያደርግ ወይም ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የመሬት ቆዳ አንድ አምስተኛውን የሶማሊያ ይዞታ የሚያደርገውን የነሱን የወደፊት የምኞት ወሰን አሳየኝ።

በሁኔታው በጣም ተደንቄ ትቀልዳለህ መሰለኝ እውነቱን ንገረኝ ስለው "ጓድ መንግሥቱ ችግሩ እኮ ይሄ ነው። ኢትዮጵያዊያን ይህንን እውነት ለመቀበል ያለባችሁ ችግር ነው" የአፍሪካ ቀንድ የሰላም ችግር። እኔ ህፃን ሆኜ ገና አፌን ሳልፈታ አባቴ ያሳየኝ የነበረው የአገሬ ድንበር ይህንን ስለሆነ ይህንን አገሬ ስል ኖሪያለሁ" አለኝ።

አባቶቻችሁ ተሳስተው እናንተንም አሳስተዋቹኋል። የእናንተ ስህተት የሚጀምረው ይህንን የዛሬውን ወሰን ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ጋር የተስማማችበት ወሰን ነው ስትሉ ነው።ይህ አሁን ወሰን የሚባለውን ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ጋር አልተስማማችም፣ አልተቀበለችም፣ ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን በኃይላቸው ወርረው የያዙትን የመሬት መጠን የሚያስረዳ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ይህንን ወሰን ይሁን ብላ በሕጋዊ ወሰንነት የተቀበለችው፣ እናንተም እኛም አባል የሆንበት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ የአፍሪካ አገሮች በሙሉ ቅኝ ገዥዎች ጥለውላቸው የሄዱትን ወሰን ከመቀበል በስተቀር ከቅኝ ግዛት በፊት በነበረ ታሪካቸው እየተመለሱ እያንዳንዳቸው ሌላ የየአገራቸውን የፖለቲካ ካርታ ለመሳል ወይም ለመፍጠር ቢፈልጉ የአፍሪካዊያንን ጥፋትና እልቂት ነው የምንጋብዘው በማለትና በማስተዋል ስለወሰን በቻርተሩ የደነገጉትን ውሳኔ ስንቀበል ነው፤ ይህንን አሁን እናንተ ይለወጥ የምትሉትን ወሰን ወሰናችን ነው ብለን የተቀበልነው።

ይህ የአፍሪካ መሪዎች ውሳኔ በእኔ አስተያየት ከማናቸውም የአፍሪካ አገሮች ሁሉ የሚጠቅመው ሶማሊያን ነው። የዛሬው ነፃ የሶማሊያ መንግሥት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ተገዝቶ ይህንን ወሰን ካልተቀበለና ኢትዮጵያም የሶማሊያን ፈለግ ተከትላ ከቅኝ ግዛት በፊት ወደ ነበረ ይዞታዋ ለመመለስ ከፈለገች ድንበራችን የሕንድ ውቂያኖስ ነው። ይህ የሆነ እንደሆነ ታላቋ ሶማሊያ የምትሉት ቅዥት ቀርቶ ሶማሊያ ብሎ ሃገርና መንግሥት አይኖሩም አልኩት። ንግግሬንም በመቀጠል በአገራችን አበው የሚሉት አንድ የአነጋገር ልምድ አለ። "እዚያም ቤት እሳት አለ" ይላሉ። ትርጉሙ፣ ደሳ ውስጥ እየኖርክ የጎረቤትህን ቤት ለማቃጠል አትሞክር፣ ጎረቤትህ በፋንታው በእሳት ደሳህን የለኮሰው እንደሆን እንደ ጧፍ ይነድና ማደሪያ ብቻ ሳይሆን መኖሪያም አይኖርህም ለማለት ነው አልኩት። (ደሳ በአፍሪካ ቀንድ ጠርዝ በከብት ርባታ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ለዘላን ኑሯቸው በሚበጅ ሁኔታ ከሳር የሚሰሩት እንደ ድንኳን የሚያገለግል ተንቀሳቃሽ ጎጆ ነው)

"ክቡርነትዎ እንደ አባቶችዎ ደጅ ሳያስጠኑኝ በአስቸኳይ ተቀብለው ሰፊ የሥራ ጊዜዎን ሰውተው ለሦስት ቀን ስላነጋገሩኝ ክብር የሚሰማኝ ብቻ ሳይሆን ለዘላለም የማይረሳኝ ታሪክም ስለሆነ ከልብ አመሰግንዎታለሁ። እውነቱን ለመናገር እኔ ከማንም መልዕክት ይዤ የመጣሁ ሰው ሳልሆን ከእርስዎ ለመተዋወቅ ምኞት የነበረኝና በራሴ አነሳሽነት ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የመጣሁ ግለሰብ የሶማሊያ ዜጋ ነኝ" ብሎ ተሰናበተኝ።

ዶክተር አዳም ያሲን ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የሶማሊያ የጦር ኃይል ከኢትዮጵያ ጋር ለጠቅላላ ጦርነት እየተዘጋጀ፣ የተወሰኑ ኃይሎቹን በተለይም ስፔሻል ኮማንዶ የሚባሉትን የምድር ጦሩን አካሎች ወታደራዊ ይዘት የሌለው ጨርቅ እያለበሰ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በማስረግ በደፈጣ ውጊያ የምሥራቁን የኢትዮጵያ አንድ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት የማዳከም ተግባሩን ጀመረ።

ሶማሊያዎች የጋራ ድንበራችን ላይ መጠነ ሰፊ የጦር ኃይላቸውን አሰልፈው በሰርጎ ገብ ጎሬላዎች የጦርነቱን እሳት ማጫር በጀመሩበት ጊዜ ነበር እኔ ወደ ሞስኮ በመሄድ የሶቭየት ሕብረትን ኮሚንስት ፓርቲና የመንግሥቱን የአመራር አካላት በአጠቃላይ የፓርቲውን ዋና ጸሃፊ ጓድ ብሬዥኔቭንና ፕሬዝዳንቱን ጓድ ፖዶጎርኒን በተለይ ያነጋገርኩት።

በዚህ ጉብኝት እኔ የመራሁት ልዑካን አባላት ከነበሩት ጓዶች ዛሬ ትዝ የሚሉኝ፣ ጓድ ብርሃኑ ባይህ፣ ጓድ አዲስ ተድላ፣ ከጊዜያዊ ሕዝባዊ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ጓድ አለሙ አበበ ወዘተ ናቸው። ይህ የመጀመሪያው የሞስኮ ጉብኝታችን በአያሌ ኢትዮጵያዊያንና በባዕዳን ምክንያት ተብሎ የተተረጎመው የጦር መሣሪያ ለመጠየቅ እንደሄድን ተደርጎ ነው።

የመሣሪያ ፍላጎታችን የሚካድ ባይሆንም በመጀመሪያው ጉብኝታችንና፣ የሶቭየት አመራር የሶማሊያን በመስፋፋት ላይ የተመሠረተ የወረራ ፍላጎት እንዳይገፉበት እየተማጠኑና እያባበሉ ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር የሚቻልበትን መላ ይፈልጉ

ነበር እንጂ ኢትዮጵያን በሶማሊያ ላይ ሊያስታጥቁ ዝግጁ አለመሆናቸውን ስለምናውቅ መሣሪያ እናስጭናለን የሚል ዓላማ አልነበረንም።

በሶማሊያና በኢትዮጵያ መካከል ሰላማያዊ መፍትሄ ለማግኘት የማይቻል ሆኖ ነገሩ ከቁጥጥር ውጭ ቢሆን ደግሞ ኢትዮጵያን የመሰለ ሃገርና አብዮቷን ለሶማሊያ በመወገን የሚወጋ አንድም ሶሻሊስት መንግሥት እንደሌለ ስለምናውቅ የጉብኝቱ ዋናና ተቀዳሚ ዓላማ ለሶቭየት የአመራር አካላት የኢትዮጵያ አብዮት ስር ነቀል ባህሪና ዓላማ በዝርዝር ማስረዳትና ራሳችንንም ማስተዋወቅ ነበር።


ሁለተኛው የጉብኝቱ ዓላማ፣ የሶማሊያን ተስፋፊ መንግሥት በታሪክም ሆነ በሕግ ፊት እውነትነትና ተቀባይነት የሌለውን፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርን የጣሰና በመላው አፍሪካ የማይደገፍ፣ ምናልባትም ለአህጉሩ የሰላም ጠንቅ የሆነውን የተሳሳተ የመሬት ጥያቄ በማስረዳት ሶማሊያ ካቀደችው ወረራና እብሪት ተግታ በሰላም፣ በመቻቻልና በመረዳዳት ሁለቱ አብዮቶች በአፍሪካ ቀንድ ሥር የሚሰዱበት ሁኔታ በአስቸኳይ ካልተፈለገ የሶማሊያ መሪዎች እንደሚያምኑት በጦርነቱ ተጠቃሚ የሚሆኑት እነሱ ሳይሆኑ ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው አድህሮት በመሆናቸው ጉዳቱ ደግሞ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም ማህበራዊ ኃይሎች፣ ተራማጅና ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ሁሉ እንደሆነ ለማስረዳት ነበር።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የጉብኝቱ ዓላማ በሁለቱ አገሮቻችን ማለትም፣ በሶቭየት ሕብረትና በኢትዮጵያ መካከል የወዳጅነትና የአብዮታዊ ትብብር ውል ለመዋዋል ነበር። ትብብሩ ሁለገብ በመሆኑ የመከላከያ ጉዳይንም ይጨምራል።

በዚህ ግንኙነት ወይም ጉብኝት ከሶቭየት ሕብረት መሪዎች ጋር ባደረግናቸው ውይይቶችና የሀሳብ ልውውጦች ሁሉ ሶማሊያን ለማጣት ወይም ከሶማሊያ ለመውጣት አይወስኑ እንጂ የኢትዮጵያ አብዮትን አያስጠቁም የሚለውን የኔን እምነት አረጋግጠልኛል።

የሶቭየት መሪዎች በኢትዮጵያ አብዮት ሥርነቀል ባህሪና ሂደት የተደሰቱ ብቻ ሳይሆን የተደነቁም መሆናቸው ከመግለፅ አልተቆጠቡም። በአፍሪካ ቀንድ የሶማሊያ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮቶች መረዳዳት እንጅ  አንዱ የሌላው ፀር መሆን የለበትም የሚለውን የእኛ የሰላምና የመልካም ጉርብትና ፍላጎት ፍፁም ትክክል እንደሆነና ይህ የእነሱም እምነት ብቻ ሳይሆን ቋሚ አብዮታዊ መርሆ ወይም ፖሊሲ እንደሆነ ደጋግመው ከመግለፃቸውም በላይ ጉብኝቱን አስመልክትን ባወጣነው የጋራ አቋም መግለጫም ላይ በጠነከረ ሁኔታ ተንፀባርቋል። በመጨረሻም የሶማሊያዎችን ስሜት ላለመንካት መሆኑ ይገባናል ባዶ እጃችንን ላለመመለስ ለአምስት ክፍለ ጦር ትጥቅ ሲፈቅዱልን በዚያ ውስጥ የታንኮች ቁጥር 200 ብቻ ነበር። የመጀመሪያ ትውውቅና ግንኙነት ስለሆነ አመስግነን ብንቀበልም መሣሪያው በምንፈልገው ጊዜ አልደረሰንም። በዚህ አጋጣሚ አንባቢ ሊያውቀው የሚገባው በዚህ ወቅት ሶማሊያ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ታንኮች የነበሯት መሆኑን ነው።

ሌላው አፍሪካና ዓለም ያወገዘውን የሶማሊያን ህገወጥ የወረራ መሰናዶ አሜሪካ ከማውገዝ ፈንታ ደግፋ ሶማሊያ በኀደላት ወረራውን የሚያሳካላትን "ተጨማሪ መሣሪያ አቀርባለሁ" በማለት የጂሚ ካርተር መንግሥት የሶማሊያን መንግሥት ለወረራው ማበረታታቱን ነው። ይህ የአሜሪካ ለኢትዮጵያ ጠላትነት የመጀመሪያ ሳይሆን በ1928 ዓ.ም የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራን በመደገፍ በኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብ ስታደርግ፣ ሩሲያ በአድዋና በማይጨው ውጊያ የኢጣሊያንን ወረራ በማውገዝ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የተዋጋችባቸውን መሣሪያዎች ከፈረንሳይ ቀጥላ ያቀረበች ነበረች።




ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት
ከኢትዮጵያ የሚፈልገው
የመሬት መጠን

ሶቪየት ሕብረት "አብዮት አብዮትን አይወጋም" ከሚለው ፖሊሲዋ ባሻገር የመስፋፋት ፍላጎታችሁና ወረራችሁ በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በዓለምአቀፍ ሕግ ብቻ ሳይሆን በታሪክም አንፃር የምትደገፉ አይደላችሁም በማለቷ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር ተቃቃረች። የሰላም ጥረት የተደረገው ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለማምራት ብቻ ሳይሆን የታዳጊ አገሮችን ሕዝብ አመፅና ብሎም አብዮት በእነሱ ላይ የታወጀ ጦርነት አድርገው የሚፈሩትና የሚያከናውኑት ፀረ-ሕዝብ ተግባር አንድን አብዮታዊ ሃገር በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ማስጠላትና ከዓለም ሕብረተሰብ እንዲገለል ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ማዕቀቦች ጀምሮ በጦር ኃይል ጣልቃ እስከ መግባት በዓለም ላይ ያከናወኑትን ጥፋት ደህና አድርገን ከማወቃችን በላይ ከሶቪየት ሕብረት መንግሥት ራሳችንን የምንከላከልበት የጦር መሣሪያ ለመግዛት ስለመቻላችን እርግጠኞች አልነበርንም።

የኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት በሂደት እስኪገመገሙና ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ችኩለው ላለመጣላት ሲያቅማሙ ከመዘግየታቸው ባሻገር መሣሪያም ዘግይቶ ቢቀርብልንም በአሜሪካ የመከላከያ ቴክኖሎጂ ለሰለጠነውና አብሮ ለኖረው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የዋርሶን ቴክኖሎጂ አስታጥቆና አስተዋውቆ ወደ ውጊያ ማስገባት ስላሳሰበን ሶቭየቶቹን እየለመንን በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከአሜሪካ የመሣሪያ ገበያም ላለመውጣትና በግዥ የከፈልንበትን መሣሪያ ላለማጣት ስንል አሜሪካኖችን ላለማስቀየም የተደረገው የሰላም ጥረት ቀላል አልነበረም።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ በአፍሪካ ቀንድ፣ በመካከላዊው ምሥራቅ፣ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የአሜሪካ የጦር ኃይል በአየርና በባሕር ላይ ለሚያደርገው ወታደራዊ ቅኝት ለኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ስለላ ማዕከል የነበረውን በአሥመራ ወታደራዊ ማዕከል፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ወታደራዊ አማካሪዎች ጽሕፈት ቤትና በኢትዮጵያ የአሜሪካ የካርታ ሥራ ድርጅቶቻቸውን አላነሳንም ወይም አልዘጋንም።

የሰሜን አሜሪካና የምዕራቡ ዓለም መገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ ሕዝብና በአብዮቱ ላይ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ፕሮፓጋንዳ ሲያናፍሱ ከኢትዮጵያ የዜና ማሰራጫዎች ይሰጥ የነበረው መልስ የማናቸውንም ሃገር መንግሥትና ሕዝብ ላለመንካት ወይም ላለመተንኮስ ከፍተኛ ጥንቃቄ እየተደረገ ለድርጅቶች ብቻ ነበር።

ሕዝባዊት ቻይናን ወዳጅ በማድረግ፣ ከቻይና ሕዝብ አብዮት ተሞክሮ የመማር ፍላጎት የአብዛኛው አብዮታዊያን ምኞትና ፍላጎት ስለነበረ ብቻ ሳይሆን፣ በአፄ ኃይለሥላሴ የሚመራው ጉልታዊ ገዥ መደብ የሰሜን አሜሪካ ቡችላና የአይሁዶች አጋር ነው እያሉ የአገራችን ገንጣይና አስገንጣዮች ለእኩይ ዓላማቸው ተግባራዊነት የመሣሪያና የገንዘብ መለመኛ አድርገው በቻይናም ድጋፍ ተጠቃሚ ነበሩ።

ለአገራችን አንድነት፣ ሰላምና ደህንነት በግምባር ቀደምትነት ጠንቅ የሆኑት የሱዳንና የሶማሊያ መንግሥት ከሕዝባዊ ቻይና ተወዳጅተው ስለነበር የኢትዮጵያን ሕዝብና አብዮት በምን መልኩ ለቻይና አመራር አካላት እንደሚያቀርቡ ከእኛ የተሰወረ ስላልነበረ፣ ቻይና በተሳሳተ መረጃ የኢትዮጵያን ሕዝብና አብዮቱን ከመበደል ይልቅ እውነቱን ተረድታ ሲሆን አጋራችን ባይቻል ጠላት እንዳትሆነን ማድረግ ተገቢ ስለነበረ ሕዝባዊት ቻይናን የሰላም ጥረታችን ደጋፊ ለማድረግ ቤጂንግ በመሄድ ከአመራሩ አካላት ጋር የተገናኘነው በዚሁ ጊዜ በ1968 ዓ.ም አጋማሽ ነበር። ጉብኝቱ ይፋ ሳይሆን በምስጢር እንዲሆን የፈለግነው ከሶቭየት ሕብረትና ከአሜሪካ ጋር ያለን ጤናማ ግንኙነት እንዳይበላሽ ከነበረን ፍላጎት ሲሆን በእነሱም በኩል በአፍሪካ ወዳጆቻችን ከሚሏቸው ከሶማሊያና ከሱዳን ጋር በእኛ ምክንያት ያላቸው ግንኙነት እንዳይበላሽ በመፈለጋቸው በምስጢር መገናኘቱን ስለተስማሙበት ነው።

ቻይናን ስንጎበኝ የቻይና መንግሥትና ኮሚንስት ፓርቲው ሶቭየት ሕብረትንና እድምተኞቿን ቀልባሽ 'ሶሻል-ኢምፔርያሊዝም' እያለች በምታወግዝበት፣ ሊቀመንበር ማኦ ሴቱንግ እርጅናው ተጫጭኗቸው ብቻ ሳይሆን በፅኑ ታመው የአልጋ ቁራኛ በነበሩበት፣ የፓርቲው የተወሰኑ ከፍተኛ የአመራር አካል አባላት ታስረው ቀኝ መንገደኞች እየተባሉ በመላ አገሪቱ በሕዝብ በሚወገዙበት ጊዜ በኋላ ጋንጎች የተባሉት ነበሩ እኛን ያስተናገዱን። በኔ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን አባላት፣ ጓድ ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ ጓድ ብርሃኑ ባይህ፣ ጓድ ሞገስ ወ/ሚካኤል ከውጭ ጉዳይ ጓድ ብርሃኑ ዲንቃና ከጊዜያዊ የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ጓድ ነገደ ጎበዜ ነበርን። የእኛን አቀራርብ በተመለከተ በሞስኮ ከነበረን አቀራረብ ምንም አይለይም። እኔ በበኩሌ በዚያን ጊዜ የነበረኝ እምነትና ከእናንተ አብዮት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ብዙ ለመማር እንፈልጋለን የሚለው አቀራረቤ ስልት ወይም ዲፕሎማሲ ሳይሆን ልባዊ ነበር። በዚህ እነሱም ያመኑና የተደሰቱ ይመስላል።

በሚያስተናግዱን ጊዜ በየመድረኩ ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም እያሉ ታላቋን ሶቭየት ሕብረት ሲያወግዙ እኛ ተጋሪ ወይም ተባባሪ ያለመሆናችን ያላስደሰታቸው ብቻ ሳይሆን፣ እኔ በግልጽ "የሁለቱ የዓለማችን ግዙፍ ህብረተሰባዊ ኃይሎች ማለትም የሶቭየት ሕብረትና የሕዝባዊ ቻይና ቅራኔ ማርክሲያዊ የቅራኔን ሕግና ደረጃ የተከተለ ወይም የጠበቀ ነው ብለን የማናምን ከመሆናችንም በላይ በዓለም ኮሚኒስቶችና የሠራተኛው መደብ ንቅናቄ፣ ለዓለም አብዮታዊያን ሕብረት፣ የተግባርና የዓላማ አንድነት ታላቅ እንቅፋት በመሆኑ የምናዝን ነን" ማለቴ አስገርሟቸዋል።

የአስገረማቸው አስተያየቴ ሃቁን የሳተና በንድፈ ሃሳብም የተሳሳተ ነው ብለው ሳይሆን ለልመና የሄድኩ እንግዳ ሰምተውት የማያውቁትን ይህንን የመሰለ ሂስ በማቅረቤ

ነበር። ሂስ ባቀረብኩበት ጉዳይ ላይ የመካድ ወይም የማስተባበል አስተያየት ሳይሰነዝሩ ያሉኝ ነገር ቢኖር "ይህንን አስተያየትህን ለሩሲያዊያኖችም ዘክራቸው" ነበር።

ጉብኝቱ ውጤታማ ነበር። የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ስር ነቀል ባህሪ ከኔ መግለጫ ብቻ ሳይሆን ከተግባር ተረድተውታል። በአብዮቱ ሀቀኛነት አምነው ለሂደቱና ለጥንካሬው ድርጅትን አስመልክተው ለመስጠት በሞከሩት የድጋፍና የምክር አቀራረባቸው በአገራችን የምናውቀው የኢሕአፓ ጠረን ሸቶኛል። ይህ የሆነበትን ምክንያት በኋላ ጊዜና ታሪክ እንዳስገነዘበን፣ የደርግ ኢኮኖሚ ጉዳይ ኮሚቴ ለቃመንበር የነበረው ሞገስ ወ/ሚካኤል ደርግን እየወከለ ከአንዴም ሁለቴ ከእኔ በፊት ቻይና በተመላለሰ ጊዜ የሰራው ነገር ሁሉ የላከውን ደርግን ወክሎ ሳይሆን ኢሕአፓን ወክሎ ነበር። የሰላሙን ጥረታችንን በተመለከተ የሶማሊያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ጦርነት ማምራት እንደሚቃወሙ ከመግለፃቸው በላይ ገንጣይና አስገንጣዮችንም ጨምሮ ከዚህ ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያን አንድነትና አብዮት የሚያጠቁበት ሁኔታ በቻይና እንደማይደገፍ ቃል በመግባት አብዮቱንና አገራችንን ከጥቃት የምንከላከልበት፣ ታንኮችና ከባድ መድፎችን ያላካተተ ሁለት እግረኛ ክፍለ ጦሮችን በሚገባ የሚያስታጥቅ መሣሪያ ከበቂ ጥይቶች ጋር መለገስ ብቻ ሳይሆን ወዲያው ላኩልን።

አምስተኛ ቁልፉ ሞስኮ ነው በማለት ከሶቭየት አመራር ጋራ አጠቃልዬ ብመለከተውም አንባቢ መረዳት ያለበት፣ በሞስኮ ጉዞ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችንም በመጎብኘት አብዮቱንና ራሳችንን በማስተዋወቅ ለሰላሙ ጥረታችን የየበኩላቸውን ርዳታ እንዲያደርጉልን ከመጠየቅ ሌላ ከሁሉም ጋር ሁለገብ የሆነ የወዳጅነት፣ የትግል አጋርነትና የትብብር ውል ተዋውለናል።

የእነኚህ አገሮች ለኢትዮጵያ አጋርነት ቀስ እያለ ጊዜ ወስዶ ፍሬ ያፈራ ሲሆን የዩጎዝላቪያው መሪ የማርሻል ቲቶ አቀባበልና ድጋፍ ግን በመጠንና በአይነቱ ሳይሆን ሠርቦች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካላቸው ፍቅር አንፃር የተደረገ ነበር። እያሌ ቀላል መሣሪያዎችንና ሰባ የሰሩና የአሜሪካ ስሪት የሆኑ ታንኮችን ከበቂ ጥይት ጋራ ወዲያው ላኩልን፣ እነኚህ ታንኮች እኛ ከነበሩን ጥቂት የአሜሪካ ስሪት ታንኮች በኋላ የተሰሩና በጣም የሚሻሉ ከመሆናቸው ሌላ የእኛ ታንከኛ ሠራዊት ስልጠና ሳያስፈልገው ወዲያው ተቀብሎ በጥቅም ላይ አውሏቸዋል።

በመጋቢት ወር የሶቭየት አመራር ሞስኮ ካለው ከኢትዮጵያ አምባሳደር ጋርና አዲስ አበባ ባለው የሶቭየት ሕብረት ኤምባሲ በኩል በተደረገ የሁለት ቀጠና ግንኙነቶች አማካኝነት ወደ ፊት በኢትዮጵያና በሶማሊያ መሪዎች ደረጃ ለሚደረገው የሰላም ውይይት ዝርዝር ቅደመ ሁኔታዎችን የሚመክርና የሚያዘጋጅ ከፍተኛ ልዑካን ወደ ሞስኮ ላኩልን የሚል ማሳሰቢያ ደረሰን። እኛ እንደተጠየቅን ፈጥነን ከደርግና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተውጣጣ አንድ ቡድን በጓድ ብርሃኑ ባይህ መሪነት ላክን። ሶማሊያዎች ተገደው በተፅዕኖ እንጂ የሰላሙን ውይይት ስለማይፈለጉ እግራቸውን ሲጎትቱ ሰንብተው ከሚጠበቁበት ጊዜ ዘግይተው ነው ሞስኮ የገቡት። የሁለቱ አገሮች ልዑካን የሰላሙን ጉዳይ በጋራ ለማዘጋጀት ይቻላቸው ዘንድ በመጀመሪያ አስታራቂ በሆኑ ሃሳቦችና ስልቶች የሶቭየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የፓርቲው የፖለቲካ ቢሮ አባል የሆኑት ጓድ አንድሬ ግሮሚኮ የልዑካኑ ሰብሳቢና የሰላሙ ጉዳይ አቀነባባሪ በመሆን ከእያንዳንዱ ልዑካን ጋራ በፈረቃ ሲነጋገሩ ከሁለት ሳምንት ጊዜ በላይ ወስደባቸው።

የሁለቱ አገሮች የልዑካን ቡድኖች ሊቀራረቡና በጋራ አንድ የሰላም ፎርሙላ ሊያወጡ አልቻሉም። ችግሩ የሁለቱ ቡድኖች መሰረታዊ ልዩነት ብቻ ሳይሆን እነሱ እንዲያዘጋጁ የተፈለገው የጋራ የሰላም መፍትሄ ሃሳብ ወይም ፎርሙላ ራሱን የቻለ የመሪዎችን አገራዊ

ወይም ብሔራዊ ውሳኔ የሚጠይቅ ስለነበርና ቡድኖቹ ያንን የመሰለ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ ነበር። የሶማሊያ ቡድን የተሳከው በመድረኩ ላይ የታወቀውን አሰልቺ ኢትዮጵያ ከብሔራዊ ክልሏ አንድ አምስተኛ የሚሆነውን መሬት ቆርሳ ትስጠንና የሁለቱን አገሮችም የጋራ ወሰን በዚህ ላይ የተመሠረተ ይሁን የሚሉትን ጥያቄ ለማቅረብ ነው።

የኢትዮጵያ ቡድን በበኩሉ የሚለው፣ ይህንን ያህል መሬት ቀርቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ አጥቅ መሬት ቆርሶ ለማንም የመስጠት ሥልጣን ያለው ተቋም ወይም ግለሰብ ዛሬ በኢትዮጵያ የለም፤ ሊቀመንበር መንግሥቱ ራሱ እዚህ ቢገኝ ይህንን ማድረግ አይችልም። የሶማሊያ መንግሥት የሚጠይቀውን የመሬት መጠን ለጊዜው ወደ ጎን ትተን በመርህ ደረጃ አዲስ የወሰን ውል እንዋዋል ብንል እንኳን ከሕዝቡ ጋር በሕዝብ ፈቃድ ብቻ የሚሆን ስለሆነ፣ በቅድሚያ በጥላቻ የመረዝናቸውን ወይም ጠላቶች እንዲሆኑ ያደረግናቸውን የሶማሊያና የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል መቀራረብንና መተማመንን ሊፈጥሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ቀጥሎ ወደ ውስብስቡ ችግር እናምራ የሚል ነበር።

ግሮሚኮ ሊሰራ የማይችል አጉል ሃሳብ የሰላም መፍትሄ ብለው አስበው ያለመሥራቱን ለመቀበል ስለተሳናቸው በኢትዮጵያ ቡድን ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ሞክረዋል። “ኢትዮጵያ ሰፊና ትልቅ፣ እንዲሁም ከሶማሊያ ጋር ስትነፃፀር በጣም ሀብታም ሃገር ነች። የሶማሊያ መንግሥት በሚጠይቀው መጠን ባይሆንም ጥቂት መሬት በመስጠት ሶማሊያን ከጦርነቱ ወደ ሰላማዊ መፍትሄ ልትመልሷት የምትችሉ እናንተ ብቻ ናችሁ” የሚል አቋም ይዘው ነው የቀረቡት። ግሮሚኮ ከዚህም አልፈው “ይህንን ባታደርጉ ምናልባት ከዚህ የሰፋ መሬት ሶማሊያዎች በኃይላቸው ሊወስዱ ይችላሉ” ብለው እስከማስፈራራት መድረሳቸውን ጓድ ብርሃኑ ሲገልፅልኝ፣ ለግሮሚኮ ለመጨረሻ ጊዜ እንዲነግራቸው ያስገነዘብኩት “በታሪካችንና በባህላችን ያልተለመደውን፣ በሮማዊያኖችና በቱርኮች ወዘተ አንዲት አጥቅ መሬት ባለማስወሰድ ደሙን ሲያፈስና አጥንቱን ሲከሰክስ የኖረ ሕዝብ መሬት ቆርሰን ለሶማሊያ በመስጠት የኢትዮጵያ አብዮት ማስቀልበስ ብቻ ሳይሆን እኛም ከምንጠፋ፣ ሶማሊያዎች የሚሰንዝሩትን የመስፋፋት ጦርነት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆነን መጋፈጡን እንመርጣለን። እንደምናሸንፍም እርግጠኞች ነን” ብለህ ንገራቸው አልኩት። ብርሃኑም ያለው ይሄንኑ ነው። የሞስኮ የሰላም ጥረት ምንም አይነት ውጤት ሳያስገኝ በዚህ አበቃ።

በእኛና በሶማሊያ ወራሪ መንግሥት መካከል ጦርነቱ በስፋትና በይፋ ከመጀመሩ ከጥቂት ወራት በፊት በየካቲት ወር የመጨረሻው የሰላም ጥረት የተደረገው በደቡብ የመን ርዕስ ከተማ በኤደን ነበር። በዚህ ጊዜ ነው በሶቭየት ሕብረት የአመራር ጓዶችና ከመላው የምሥራቅ አውሮፓ የዋርሶ ባለ ቃል ኪዳን አገሮች መንግሥታትና ፓርቲ አመራሮች ጋር ኩባንና ደቡብ የመንን ጨምሮ እያሰጋ በመጣው ሶማሊያ ኢትዮጵያን የመውረር ጉዳይ ከመከሩበት በኋላ ወደፊት ሊከተል በሚችለው የአፍሪካ ቀንድ ተመሳሳይ አቋም ከመውሰድ በኋላ፣ ከአሜሪካ አህጉር ጓድ ፊደል ካስትሮ፣ ከአውሮፓ የምሥራቅ ጀርመን መሪ ጓድ ኤሪክ ሆኒከርና ከአረቡ ዓለም የደቡብ የመን ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊና ፕሬዝዳንት በጋራ በኤደን ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያና የሶማሊያ መሪዎችን በመሸንገል ጦርነቱን ለማቆም የሞከሩት።

እንዲህ ያለ የሸንጋዮች ምርጫ የታሰበውና የስብሰባው ስፍራ ኤደን ላይ እንዲሆን የተደረገው፣ ሶማሊያ የቀይ ባሕርና የህንድ ውቅያኖስ ተዋሳኝ ሃገር ብቻ ሳትሆን የአረብ ሊግና የእስልምና አማኞች ማህበር አባል በመሆኗም ውሎ አድሮም ሊፈጠር በሚችለው ቀውስ የሶማሊያ እብሪትና ህገ ወጥ ወራሪነት አንፃር በሶሻሊስቱ ዓለም በአጠቃላይ፣ በሶቭየት ሕብረት በተለይ ለሚወሰደው እርምጃ የተጠቀሱት አገሮች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተብሎ

እንጂ ሶማሊያዎቹ በኤደኑ የእርቅ ሽንገላ እንደማይሸነገሉ የታወቀ ነበር። በኋላ ለእኔ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ የጀርመኑ መሪ አንድ እክል ገጠማቸው ተብሎ እንደማይገኙ ተገለጸልኝ። የኩባው መሪ ጓድ ፊደል ካስትሮ ሶማሊያን በይፋ ለሦስት ቀናት ያህል ጎብኝተው መጋቢት 14 ቀን 1968 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ አዲስ አበባ መጥተው ተቀበልናቸው።

ወደ ሶማሊያ የሄዱበትንና ወደ እኛም የመጡበትን ምክንያት ቀደም ብለን አዲስ አበባ ባለው የሶቭየት ሕብረት ኤምባሲ አማካኝነት ተረድተናል። የመጡበት ጊዜ በአዲስ አበባ ከምሽ በኋላ ስለነበር እራት ጋብዘናቸው እንዲያርፉ ከተደረገ በኋላ በበነጋታው ከጠዋቱ ወደ አራት ሰዓት ገደማ በኢትዮጵያ ሕዝብ ቤተመንግሥት አንዲት አነስተኛ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ለውይይት ተቀመጥን።

ጓድ ፊደል ካስትሮ አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት ለሦስት ቀናት ሶማሊያን እንደጎበኙና ከፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ ጋር የኢትዮጵያና የሶማሊያን ጉዳይ አስመልክተው በሰፊው መወያየታቸውን፣ በውይይቱ ጊዜ በሶማሊያዎቹ ሁኔታ በእጅጉ መናደዳቸውን፣ ሶማሊያን ለብዙ ጊዜ የጎበኙ ሲሆን ይህ የመጨረሻው ጉብኝት በእጅጉ ያስጠላቸው መሆኑን ከነገሩን በኋላ "ሶማሊያዎቹ የሁለቱ አገሮቻችሁ ቅራኔ ከጦርነት በስተቀር በሰላማዊ መንገድ ይፈታል ብለው ስለማያምኑ ለጦርነት እንደተዘጋጁ" በግልጽ አስረዱን።

"ሶማሊያዎቹ በጣም ተብተዋል። የእነሱን ችግር ጦርነት ይፈታዋል ብዬ አላምንም። ጦርነቱን ግን እነሱ እንደሚጀምሩት አልጠራጠርም" ካሉ በኋላ "እንዳቀዱት የወዳጆቻቸውን ልመናና ምክሮች ሳይቀበሉ አሻፈረኝ ብለው ወደ ጦርነቱ ቢያመሩ ጠባቸው ከእናንተ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመላው የሶሻሊስት መንግሥታትና ከዓለም ተራማጆች ጋር እንደሆነ አያጠራጥርም። "ይህ የሆነ እንደሆነ ሁኔታው በጣም አሳዛኝ ነው የሚሆነው። ሶቭየቶችን ከማውቅበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ጉዳይ እንደተጨነቁት በሌላ በምንም ነገር እንዲህ ሲጨነቁ አስተውዬ አላውቅም። እኛን ኩባኖችን፣ ጀርመኖችንና የመኖችን የመጨረሻውን የሰላም ጥረት እድርገን ጦርነቱን እንድናስቆም የጠየቁን እራሳቸው ጓድ ብሬዥኔቭ ናቸው።

ሁላችንም በጓድ ብሬዥኔቭ የተጠየቅነውን ሽምግልና ከመቀበላችን በፊት እናንተን ሁለታችሁን ባለ ጉዳይ አገሮች በእኛ ሽምግልና ለመሸንገል ያላችሁን ፈቃድ ለመጠየቅ በሌሎቹም ተወክዬ ነው የመጣሁት። ሶማሊያዎቹ ይህንን የሰላም ውይይት ፍፁም ባይፈልጉትና ባይወዱትም ለጊዜው ኤደን ለመገናኘት ተስማምተዋል" አሉን። በእኛ በኩል ለእሳቸው የግል ግንዛቤና በእሳቸውም አማካኝነት ለሌሎቹ የሶሻሊስት መንግሥታት ያሳወቁ ዘንድ፣ ሶማሊያዎቹ ለጦርነት የተዘጋጁ ብቻ ሳይሆን ጦርነቱን በሁሉም የድንበሮቻችን ጠረፍ ውጊያ እንደ ጀመሩ ገልፀን ወረራውን በይፋ ከመግለፅ የተቆጠብነው ለእናንተ የሰላም ሽምግልና እድል ቅድሚያውን ለመስጠትና ብሎም ከእናንተ ጋር ለመምከር ብለን ነው ካልኩ በኋላ በቀጠሮው የኢትዮጵያ ልዑካን ኤደን እንደሚገኝ አስታውቄያቸው በዚያው ቀን ወደ ሞስኮ ሄዱ።

በገባነው ቃል መሠረት ከቀትር በኋላ በ12 ሰዓት ገደማ በኤደን መሸት ሲል ደረስን። የኩባ እና የሶማሊያ ልዑካን ከእኛ በፊት ብዙ ቀድመው በአስር ሰዓት ገደማ ነው የገቡት። ስብሰባው የሚጀምረው በምሽቱ ስለነበረ መዘግየታችን ያስከተለው ችግር አልነበረም። የየመን አመራር ጓዶች ከአውሮፕላን ማረፊያ ተቀብለው እንግዳ ማረፊያ ቤት ካደረሱን በኋላ የአስር ደቂቃ ያህል ጊዜ ሰጥተውን የመኖቹ ከኩባዊያን ጋር መተው እንደሚያነጋግሩን አሳወቁን። አገሩ ስለሚሞቅ ፊታችንን በቀዝቃዛ ውሃ ተለቃልቀን ስንጠብቃቸው፣ ጓድ

ፊደል ካስትሮ ከምክትል ፕሬዝዳንታቸው ጋር፣ ጓድ አብዱል ፈታህ ከፕሬዝዳንቱ ጋር አራት ሆነው መጡ።

ከስብሰባው በፊት ወደ እኛ የመጡበት ምክንያት "ሶማሊያዎቹ ይህ ውይይት እንዳይሳካ የማይፈጥሩት ችግር ስለሌለና ምናልባትም የእናንተን ትዕግሥት የሚፈታተን የብልግናና የዘለፋ ቃላቶችን ከመሰንዘርም ስለማይመለሱ በእናንተ በኩል እስከ መጨረሻው ትዕግስታችሁን እንጠይቃለን" አሉን። በእኛ በኩል ምንም ችግር እንደማንፈጥር በማረጋገጥና በማበረታታት መልሰን ሸኘናቸው። ስብሰባው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ተጀመረ። የስብሰባው ትንሽ አዳራሽና የእንግዳው ማረፊያው ህንፃ የተያያዙ ስለነበሩ የተገነዘብነው፣ ሁላችንም በቅርብ በአንድ አካባቢ ያለን መሆናችንን ነው።

የየመን ጓዶች በማናቸውም ረገድ ጥሩ መሰናዶ አድርገዋል። ወደ ስብሰባ አዳራሽ ከመግባታችን በፊት ለስብሰባው አዳራሽ ቅርብ የሆነ ሌላ የእንግዳ መቀበያ ወይም ማረፊያ አዳራሽ አስተናጋጆቹ እየተቀበሉ መቀመጫ ሲመሩና የሶማሊያው መሪ ማንንም ሳያነጋግር ወይም ሳይጨብጥ አዳራሹ ማዕከል ሜዳ ላይ ሁለት እጁን ሱሪ ኪሱ ከቶ ዘለግ ባለ ድምፅ "ሁለት ስቱፒድ የሆንን ሕዝቦች አስቸገርናችሁ አይደለም?" በማለት ተናግሮ ወደ መቀመጫው ሲያመራ ከአነጋገሩ በላይ ጠቅላላ ሁኔታው፣ ኩራቱና ትእቢቱ ደሜን ስላፈላው፣ ለትዕግስቴ ዳርቻ አይኖረውም ብዬ ለራሴ ቃል የገባሁት ሰውዬ፣ "የራስህን ስቱፒድነት ተናገር እኛ ግን አንተን ወይም እናንተን አይደለንም" ስለው አስተናጋጆቹ ተደናገጡ። ዝያድ ባሬ ያልኩትን ያልሰማኝ ይመስል "ምንድነው ያለው" እያለ ሰዎቹን ሲጠይቅ አስተውለው ነበር።

በየመኑ የፕሮቶኮል ሹም እየተመራንና ተራ በተራ እየተጠራን ወደ ስብሰባው አዳራሽ በመግባት በተሰናዳልን መቀመጫ መሠረት የአገራችንን ሰንደቅ አላማ በመመልከት ስፍራችንን ያዝን ስብሰባውን የመኖችና ኩባዊያን ናቸው በጋራና በፈረቃ የሚመሩት።

የአስተናጋጁ ሃገር ፓርቲ ጸሃፊ ጓድ አብዱል ፈታህ እስማኤል መድረኩን ወስዶ በእንኳን ደህና መጣችሁ የመቀበያ ንግግር ከፍቶ፣ ስለ ተሰበሰብንበት ምክንያት፣ ስለ ጉዳዩ አሳሳቢነት፣ ስለአካባቢው ወቅታዊ ሁኔታና ስለ አፍሪካ ቀንድ ታሪክ ወዘተ ሰፋ ያለ የመግቢያ ንግግር በማድረግ መድረኩን ለጓድ ፊደል ካስትሮ ሰጠ።

ጓድ ፊደል ካስትሮ ከአፍሪካ ቀንድ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር የራሳቸውን አህጉር የደቡብ አሜሪካንና የካሪቢያን ቀውሶች፣ በዚህ ምክንያት እጅግ ደሀና ኋላ ቀር የሆነው አህጉር ሕዝብ ያለበትን ድህነት፣ ርሃብና የጦርነት ሰቆቃ፣ ወደዚህ አስከፊ ሁኔታ እያመራ ስላለው የሶማሊያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የሶሻሊስቱን ዓለም ከፍተኛ ስጋት ከራሳቸው አስተያየት ጋር አክለው ሰፋ ያለ የመግቢያ ንግግር በማድረግ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ልዑካን ጥሪውን አክብረን ለሰላሙ ውይይት በመገኘታችንና የየመኖችን አቀባበል አመሰገኑ።

የሶማሊያው መሪ ፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ በየመኑ ዋና ጸሃፊ የመግቢያ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ለሶማሊያ ልዑካን ስለተደረገለት አቀባበል አስተናጋጁን ሃገር ካመሰገነ በኋላ በተለመደው ጎልዳፋ አነጋገር፣ በተረትና በተረብ እንዲሁም በበኩሉ ታሪክ የሚለውን ግን በታሪክ ፈፅሞ የማይታወቀውን ውሸት ዋሽቶ የአፍሪካን ቀንድ ሕዝቦች ሲጨቁንና ሲረግጥ ስለኖርው የሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም እያለ እኛን በነገር ከኮረኮመ በኋላ የንግግሩ መዝጊያ "ይህ የሰላም ውይይት የምትሉት የትም አያደርስም" አለ።

ንግግሩን በመቀጠልም "በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለሰላም የቆመ ሳይሆን የአባቶቹን ተግባር በተራው ሊያከነውን እንደተዘጋጀ እቅጩን ነግሮናል" አለ።

ይህ አባባሉ ለእኔ እንደገባኝ መንግሥቱ እቅጩን ነግሮናል የሚለው፣ የእኔና የዶክተር አደምን ውይይትና እንዲሁም ጓድ ብርሃኑ በሞስኮ የገለፀውን የኢትዮጵያን አቋም ማለቱ ነው።

አሁንም ንግግሩን በመቀጠል "ይህንን እየነገርናቸው የሶቭየት ጓዶች እኛን አልሰማ ብለው በሞስኮ ከሁለት ሳምንት በላይ በማይሰራ ፎርሙላ አጉል ደከሙ። ዛሬ ኢትዮጵያን የሚመሯትና አብዮታዊያን የሚባሉትን ሰዎች ካለፈው ጉልታዊ የኢትዮጵያ ገዥ መደብ በምንም ነገር የማይለያዩና የማይሻሉ ስለሆነ ዛሬም እናንተ እዚህ የምታደርጉት ጥረት ከንቱ ነው በማለት ገና ወደ አጀንዳው ሳንገባ በመግቢያ ንግግር ብቻ ቤቱን ውጥረት ውስጥ ከተተው። የንግግሩ ስልትና ዓላማ፣ ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት የየመንና የኩባ ጓዶች በስጋት እንዳሳሰቡን ለእሱ ስድብና ዘለፋ እኔ በፋንታዬ መልስ እንድሰጠውና በሚፈጠረው የሁለታችን መዋረፍ ብቻ ወደ መሰረታዊው ጉዳይ ሳንገባ በመግቢያው ንግግር ተጣልተን ስብሰባው እንዲበተን ነው።

የእኔ አብዮታዊ መንግሥት ከቀድሞው ጉልታዊው ሥርዓት አራማጅ ገዥ መደብ በምንም የማይለይ ነው እየተባለና የኢትዮጵያ ነገሥታት ኢምፔሪያሊስቶች እየተባሉ ሲጠሩ ለዚህ መልስ ብሰጥ የማሳዝነው የየመንና የኩባን ጓዶች ስለሆነ በአጭሩ አስተናጋጇን ሃገር በተለይ ባደረገችልን አቀባበል፣ በአጠቃላይ ኩባን የመናዊያን የውይይት መድረክ በመፍጠራቸውና በሰላም መፍትሄ ጥረታቸው ምስጋና በማቅረብ ብቻ ተናግሬ አበቃሁ።

በውይይቱ መግቢያ በተደረገው ንግግር ብቻ ከአንድ ሰዓት በላይ የሆነ ጊዜ ስለወሰደ ከዚህ በኋላ ውይይቱ ሳይቀጥል እራት ተጋበዝን። በአፍሪካ ቀንድ ጠርዝና በመካከለኛው ምሥራቅ በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚከናወኑ የልማትና የግንባታ ሥራዎች ወዘተ ካልሆኑ በስተቀር የወረቀት ሥራዎችና ስብሰባዎች የሚካሄዱት በምሽት ነው። ሌላውም ሥራ ቢሆን ከጠዋቱ 12 ሰዓት ገደማ ተጀምሮ እስከ አራት ሰዓት፣ ከቀትር ወይም ከምሳ በኋላ ከአሥር ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ገደማ ድረስ በአጠቃላይ በቀን ብርሃን የሚሰራው ከአራት እስከ አምስት ሰዓት ብቻ ሲሆን የተቀረው ሥራ የሚካሄደው በምሽት ነው።

በዚህ መሠረትና በየመኖቹ ልማድ፣ እኛ በኢትዮጵያ የምናርፍበትን የሌሊቱን ጊዜ ለውይይት ሊያደርጉት ባቀዱት መሠረት ነው፤ በስብሰባው መካከል ከ3 ሰዓት በኋላ የእራት ግብዣ የተደረገው። የእራት ግብዣው መደበኛ እራት ሳይሆን በቁም የሚወሰድ ኮክቴል መሰል ነገር ነበር።

በምግብ አዳራሹ ትይዩ ማዕዘናት ግራና ቀኝ ተራርቀው በተቀመጡ ሁለት ትልልቅ አግዳሚ ጠረጴዛዎች ላይ አንዱ የእስልምና እምነት ላላቸው ሌላው ለሌሎች የተለያዩ የምግብ አይነቶች ተደርድረውባቸዋል።

የመኖቹና ኩባዊያን ሱማሊዎቹን ለብዙ ዓመታት እንደሚያውቋቸውና በተለያዩ አጋጣሚዎች እየተገናኙ በአንድ ማዕድ ይመገቡ ነበር እንጂ ምግብን ከእምነት አኳያ ሲመርጡ አላየናቸውም ነው ያሉን። በዚያ ምሽት ግን ወደ መመገቢያው አዳራሽ እንደገባን ጄነራል ዝያድ ባሬ ከማንም በፊት የምግብ አዳራሽ ውስጡን በዓይኑ ከቃኘ በኋላ፣ የየመኑን ፕሬዝዳንት "የትኛው ነው ለእስልምና አማኞች የተዘጋጀው ምግብ" ብሎ ይጠይቀዋል። የየመኑ ፕሬዝዳንት "ለምንድነው ያልተለመደ ጥያቄ የምታቀርብልኝ? እኛ ከምንመገበው ምግብ ጠብ አለህ እንዴ?" ብሎ ሲጠይቀው "እስከ ዛሬ ተሳስተናል። ከእንግዲህ ወዲያ ወደ ነበርንበት ወደ ቀድሞ እምነታችን ተመልሰናል" በማለት መልስ ሰጥቶ ተከታዮቹን እየመራ ለእስልምና አማኞች ወደ ተዘጋጀው የምግብ ጠረጴዛ አመራ።

ለእስልምና እምነት ተከታዮች ተብሎ ወደ ተዘጋጀው የምግብ ጠረጴዛ የሄዱት የሶማሊያ ልዑካን ብቻ ናቸው። የየመኖቹ የእራት አዘገጃጀት ምሽቱን ብዙ ስለምንቀመጥ በቁም መመገቡ የሚሻል መሆኑን ከመገንዘብ ባሻገር ሰው እንደ ልቡ እየተንቀሳቀሰ እንዲዝናና እና አንዱ ከሌላው እንደ ፍላጎቱ እንዲወያይ ወይም እንዲነጋገር ብለው በማሰብ ሲሆን፣ ሶማሊያዎቹ ከሁላችንም ተነጥለው ብቻቸውን በአንድ የምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተኮልኩለው እርስ በርሳቸውም ሳይነጋገሩ ምግብ ሲለቃቅሙ ብቻ መቆየታቸው የራት ግብዣውን ሌላ የውጥረት መድረክ አድርጎት ቆየና ወደ አራት ሰዓት ገደማ ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ ተመለስን።

ኤደን ላይ የተደረገው የሰላም ውይይት ሞስኮ ላይ ከተደረገውና በጓድ አንድሬ ግሮሚኮ ከተመራው የሰላም ውይይት በአይነቱም ሆነ በይዘቱ የተለየ ነበር። ኩባኖችና የመናዊያን፣ ብቸኛው መፍትሄ ፈላጊ ሰፊዋና ትልቋ ኢትዮጵያ ብቻ ናት የሚል አስተያየት ሳይቃጡ ቀደም ብዬ ለማገለፅ እንደሞከርኩት የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት በኢኮኖሚውና በተለያዩ ማህበራዊ መስኮች በሶቭየት ሕብረት በተለይ፣ ኩባንና የመንን ጨምሮ መላው የሶሻሊስት መንግሥታት ከፍ ያለ ድጋፍ ከመስጠት በላይ የጀነራል ዝያድ ባሬን መንግሥት ኢትዮጵያ ብትወረው ራሱን ለመከላከል እንዲችል ባስታጠቁት የጦር መሣሪያ እጅግ ተኩራርቶና ተብቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ አጋጣሚ ጠብቆ ለወረራ መሰናዳቱን ማውገዣ መድረክ ነው ያደረጉት።

የየመኑ ፕሬዝዳንት ጓድ አቡዳል ፈታህ እስማኤል "ለሁለቱ አገሮች ሰላም፣ አብሮ የመኖርና ብሎም ለጋራ ብልፅግና የሚበጀው መቻቻልና መተሳሰብ እንጂ በጦርነቱ ተጠቃሚ የሚሆን አንድም ወገን ስለሌለ ከዚህ የተሳሳተ የጥፋት ጎዳና መመለስ አለባችሁ" በሚል ርዕስ ቀደም ሲል በስፋት ያደረገውን ንግግር በማጠናከር፣ ብልህነት በተሞላው አብዮታዊና ወዳጃዊ አቀራረብ ተናግሮ መድረኩን ለኩባዊያን ሰጠ።

በቅድሚያ ጓድ ራፋዔል ካርሎስ የሚባሉት የኩባ ሁለተኛ ምክትል ፕሬዝዳንት ከአያሌ ማስረጃዎች፣ ታሪኮችና ክስተቶች ጋር በማነፃፀርና በማገናዘብ በርሳቸው ረጅም እድሜና ተሞክሮ በዓለም ላይ የስተዋላቸውን አያሌ ግጭቶችና ጦርነቶች ዛሬ በአፍሪካ ቀንድ ካንዣበበው አደጋና የተሳሳተ አመለካከት ጋር እያነፃፀሩ አውግዘው ንግግራቸውን ሲደመድሙ፣ "ፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬን የመሰለ አዛውንትና የጊዜያችን የአፍሪካ አብዮታዊ በድንበራቸው ላይ የፈነዳውን ታላቅ አብዮት እንደ አንድ ታላቅ ፀጋና እድል በመመልከት ለደህንነቱና ለጥንካሬው ከጎኑ የሚቆሙ እንጂ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ አስተያየት ለውድቀቱና ብሎም ለጥፋቱ ብለው ለወረራ ጦራቸውን ያሰልፋሉ ብዬ ለማመን በጣም እቸገራለሁ። አያደርጉትም" በሚል ንግግራቸውን ደመደሙ።

ጓድ ፊደል ካስትሮ በእራት ግብዣው ጊዜ የሶማሊያው መሪ "እስከ ዛሬ ተሳስተናል ከእንግዲህ ወዲያ ወደ ነበርንበት ወደ ቀድሞው እምነታችን ተመልሰናል" በማለት የተናገረውን ሶሻሊስታዊ ወዳጆቹን ከድቶና ጀንዲውን ጠቅልሎ በሰሜን አሜሪካ ጉያ መግባቱን ነው የገለፀልን በማለት ክፉኛ ተናደዋል።

መድረኩን ከምክትል ፕሬዝዳንታቸው ወስደው ዝያድ ባሬ ባደረገው የመግቢያ ንግግር የሐበሻ ኢምፔርያሊዝም ማለቱንና በእራትም ጊዜ ወደ እምነታችን ተመልሰናል ወዘተ ያለውን ሁሉ በመጠቃቀስ "ለመሆኑ እናንተ ሶማሊያዎች በችግራችሁ ጊዜ ፈጥኖ የደረሰላችሁ ማን ነው? ምንም አይነት ጦርነት ሳይገጥማችሁ በርሃብ ብቻ በአገራችሁ ይሞት የነበረው የሰው ቁጥር ምን ያህል ነበር? እናንተ አብዮት ያላችሁትንና እኛም አብዮት

ነው ብለን የተቀበልናቸሁን ንቅናቄ ስትጀምሩ፣ ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው አድሀሮት ሊበሉን ነው ብላችሁ ወደ ሶሻሊስቱ ዓለም ለርዳታ ፍለጋ በመጣችሁ ጊዜ የተናገራችሁትን ታስታውሳላችሁ? ዛሬ በዚህ መድረክ እውነቱን አፍረጥርጠን መናገር አለብን። እናንተ ምን አላችሁ? ማንስ ናችሁ? ማንንስ ሆናችሁ ነው ይህንን ያህል የምትለመኑት?" ማለት ሲጀምሩ የሶማሊያው መሪ ትዕግሥት በማጣት ጣልቃ ገብቶ "እኛ አብዮታችንን ስንጀምር ማንም ከጎናችን የቆመ አልነበረም። ብቻችንን በትግላችን ነው ችግሮቻችንን ሁሉ የተወጣነው። ወዳጆች ብለን የተጠጋናቸው ሁሉ ጥለውን ቢሄዱም ጉዳያችን አይደለም" ካለ በኋላ "ለመሆኑ ፊደል ካስትሮ ይህንን የሰላም ውይይት ከሚሸመግሉት አንዱ ነህ ወይስ ለኢትዮጵያ ጥብቅና የቆምክ ወኪል ነህ?" በማለት ጠየቀ።

ፊደል ካስትሮ በቀረበላቸው ጥያቄ "እኔ የማንም ጠበቃ ወይም ወኪል አይደለሁም። ስለ እውነትና ስለ ሰላም ነው የምናገረው። ኢትዮጵያዊያን መድረኩ ሲሰጣቸው የማንንም ጥብቅና ሳይፈልጉ ራሳቸውን ለመግለፅ የበቁ ጓዶች መሆናቸውን እናውቃለን። እናንተ ይህንን ጦርነት ብትከፍቱ ለራሳችሁ ሰላምና ዘለቄታ ላለው ጥቅም ሳይሆን በእራት ግብዣው ላይ እንደተናገርከው ወደ ነበርክበት ተመልሰህ ለሜን አሜሪካን ለማስደሰት ብቻ ነው" ሲሉ፣ ዳግም ዝያድ ባሬ በበኩሉ መልስ ሲሰጥ መድረኩ ለብዙ ደቂቃዎች የሁለቱ ግለሰቦች መሟገቻ ብቻ ስለሆነ ጓድ አብዱልፈታ እስማኤል ጣልቃ በመግባት የሁለቱን ሙግት አቁሞ መድረኩን ለኢትዮጵያ ልዑካን ሰጠ።

መድረኩ ስለተሰጠኝ አመሰግኜ፣ እናንተ በኢትዮጵያ ተወክላችሁ ወይም ጥብቅና ቆማችሁ ሳይሆን በእውነትና በሃቅ መሠረት ላይ ቆማችሁ እኔ ልናገር የምፈልገውን ሁሉ ስለተናገራችሁ እናንተ ካላችሁት በላይ የምናገረው ብዙ ነገር አይኖረኝም። ጄነራል ዝያድ ባሬ ለተናገረው መልስ መስጠት እሱን መሆን መስሎ ስለሚታየኝ ወይም ስለሚሰማኝ አላደርገውም። ክህደቱን ለማስረዳት ብሎ "እስከ ዛሬ ተሳስተን ቆይተናል ከእንግዲህ ወዲያ ግን ወደ ነበርንበት ወደ ቀድሞ እምነታችን ተመልሰናል" ይበል እንጂ በበኩሌ ዛሬ እንደተረዳሁት ቀድሞም ቢሆን ነኝ የሚለውን ነበር ብዬ ለማመን በጣም እቸገራለሁ። ኢትዮጵያን የመሰለች አንዲት ከጉልታዊ ሥርዓተ ማህበርና ሥልተ ምርት ያልወጣች ታዳጊ ሃገር ኢምፔሪያሊስት ነች ማለት የንድፈ ሃሳብ ድህነት ብቻ ሳይሆን ጭልም ያለ ድንቁርናም ነው።

ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት በሶማሊያ ሕዝባዊ አብዮት የሚካሄድ መስሎን እኛም ልናጅበው የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት በታላቅ ጉጉት የተጠባበቅነው በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ሕዝባዊ ዲሞክራሲ የሰፈነበት አንድ የሕዝቦች ህብረተሰባዊ ግምባር እንፈጥራለን በሚል ምኞት ነበር። በጣም እናዝናለን፣ ዛሬ እንደተረዳነው በሶማሊያ አብዮት አልነበረም። በሶማሊያ የነበረውና ሁላችንንም ያታለለው አብዮት ሳይሆን ታላቋ ሶማሊያ የተሰኘ የሶማሊያ መሪዎች እብሪትና ቅዠት ነው። ጄነራል ዝያድ ባሬና ፓርቲው የሶሻሊስት ሥርዓት ተቀብለናል ያሉት ታላቋ ሶማሊያ የተሰኘ ቅዠታቸውን በኃይል ወይም በጦርነት እውን ለማድረግ ያስችለናል ብለው ያመኑበትን የጦር መሣሪያ ለማሰባሰብ የተደረገ አስደናቂ አጭበርባሪነት ነው።

በመጨረሻም ኩባዊያንና የመናዊያን ጓዶቻችን ላደረጋችሁት የሰላም ጥረት በራሴ፣ እዚህ ባለው የኢትዮጵያ ልዑካንና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ይህ የሰላም መድረክ በሶማሊያ ልዑካን እምቢተኝነትና ጦረኛነት ተዘግቶ ከመበተናችን በፊት ልታውቁት የሚገባ ነገር፣ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ



ፕሬዝዳንት ዝያድ ባሬ

ሕዝብና አብዮት ላይ ወረራውን በመጀመሩ ሕዝባችን በመከላከል ውጊያ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው ብዬ ንግግሬን አበቃሁ።

ዝያድ ባሬ በፀጥታ ሲያዳምጠኝ ከቆየ በኋላ ለእኔ ንግግር መልስ ለመስጠት ከመድረኩ ፈቃድ ሳያገኝ ከመቀመጫው ተንስቶ በመቆም፣ ጣቱን ወደ እኔ ቀስሮ "ውጊያ ተጀምሯል ያልከው ስለ ውጊያ ምንም እውቀት ስለሌለህ ነው። ውጊያ አልጀመርንም። ውጊያ ስንጀምር ውጊያ ምን እንደሆነ ታይና ከዚያ ትማራለህ" አለኝ።

እኔም አስተናጋጁን ይቅርታ ጠይቄ "ከጀመራችሁት ሌላ ያቆያችሁት ውጊያ ካለ በማናቸውም ጊዜና ስፍራ ጦርነቱን ልትከፍቱ ትችላላችሁ። በዚህ ጦርነት ማን ትምህርት እንደሚያገኝ እዚህ ያሉት ኩባዊያንና የመናዊያን ጓዶቻችን ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ሕዝብ በጠቅላላ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚረዳው ይሆናል" ስል፣ ዝያድ ባሬም "በል ጥሩ ነው ከእንግዲህ ወዲያ በጦር ሜዳ እንገናኝ" ብሎ ከሥርዓት ውጪ በብልግና መድረኩን በመርገጥ ስለወጣ የመጨረሻው የሰላም ጥረት በዚሁ ተዘጋ።

ያንን ምሽትና ሌሊት በሙሉ በውይይት ነው ያሳለፍነው። በሶማሊያው መሪ እብሪትና እንቢተኝነት የሰላሙ ውይይት መድረክ ሲዘጋ ነግቶ ነበር። በየመኖች እንደተነገረን የሶማሊያ ልዑካን ስብሰባውን ረግጠው ከስብሳባው አዳራሽ እንደወጡ ወደ አገራቸው ሲመለሱ፣ እኛ ለጥቂት ሰዓቶች ቆይተን የኩባን ልዑካን ለመሰናበት ወደ ማረፊያቸው ሄድን።

የመኖችና ኩባዊያን ከዚህ በኋላ ምንድነው የሚቀጥለው? ምን ይደረግ? ኢትዮጵያን እንዴትና በምን መንገድ እንርዳ በሚል የንግግር ዙሪያ በጓድ ፊደል ካስትሮ ማረፊያ ቤት ሲነጋገሩ ቆይተው የእኛን መድረስ ሲሰሙ የመኖቹ ወጡ።

ጓድ ፊደል ተቀብለውን የሰላሙ ጥረት ባለመሳካቱና ከእንግዲህ ወዲያ የሚጠብቀን ጦርነት በመሆኑ፣ ጦርነቱን ገጥመን የተሸነፍን ያህል በማዘንና በመጨነቅ ሊያፅናኑን ሞከሩ።



ስለ አፍሪካ ቀንድ ሁኔታ በቴሌቭዥንና በሬድዮ መግለጫ ሳቀርብ

የኢትዮጵያና የአብዮቱ ጠላቶች ሶማሊያዎች ብቻ ሳይሆኑ የውስጥም የውጭም ጠላቶቻችን ብዙ ከመሆናቸው በላይ እኛ ለውጊያ ባለመዘጋጀታችን ሶማሊያዎች ውጊያውን ሊያሸንፉ ይችሉ ይሆናል እንጂ በጦርነቱ የሚያሸንፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በውጊያው ሊያሸንፉን ይችላሉ ስልም እኛንና እነሱን በሚያዋስኑን የጠረፍ ክልሎች ጥቂት መሬት ላጭር ጊዜ ሊቆጣጠሩ ይችሉ ይሆናል ማለቴ እንጂ በኢትዮጵያ ላይ ሊስፋፉ ቀርቶ በሚይዙት መሬት ላይ ድንኳንም ሊተክሉ አይችሉም በማለት እኛ መልሰን እነሱን አፅናኝ ሆንን።

ጓድ ፊደል የእኛን በራስ የመተማመን አቋም ስላዳመጡ ተደስተው "ልክ ናችሁ። በጦርነት አሸናፊው አብዮት ነው። እኛ የጠላነው ላጭር ጊዜም ቢሆን በውጊያ መሸነፋችንን በመገመት ነው" በማለት ኩባንም የውጊያው ተካፋይና በሶማሊያ ተጠቂ አድርገው ተናገሩ።

በሶማሊያ መሪዎች እንቢተኝነትና ጦረኝነት የሰላሙ ጥረታችን መክሸፉን ለማስረዳትና ከዚህ በኋላ ስለሚሆነውም ነገር ለመወያየት ከኤደን ወደ ሞስኮ የሚሄዱ መሆናቸውን በመግለፅ በሳቸው አማካኝነት ለሶቭየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ ለጓድ ሊዮኔድ ብሬዥኔቭ እኔ የምልከው መልዕክት እንዳለ ጠየቁኝ።

ለጊዜው በእርስዎ የሰላሙ ጥረት መክሸፉ ከተነገራቸው በቂ ይመስለኛል። ከዚህ በተረፈ ጓዳዊ ሰላምታ ብቻ ቢያቀርቡልኝ በቂ ነው አልኳቸው። "እግረ መንገዴን ወደ ምሥራቅ ጀርመንም ደርሼ ሁኔታውን ለአገሪቱ ፓርቲ ዋና ፀሃፊ ለጓድ ኤሪክ ሆኒከር ካስረዳሁ በኋላ፣ የእኔ ሃሳብ ቢቻል ሆኒከርን ካልተቻለ ከከፍተኛው የአመራር አካል አባላት ምናልባትም ጓድ ላንበርዝን ይዤ ነው ሞስኮ የምሄደው። ሆኒከር ጥሩ የኢትዮጵያ ወዳጅ ከመሆናቸው በላይ ከዋርሶ ቃል ኪዳን አባል ሃገር መሪዎች ሁሉ በሞስኮ ተደማጭ ስለሆኑ "ሶቭየቶችን ለመቀስቀስ ብቻ ሳይሆን ለማሮጥ ነው የምንፈልገው" ሲሉኝ፣ የሽማግሌዎቹ



ከጓድ ፊደል ካስትሮ ጋር በአብዮት አደባባይ

ልብ እንዳይቆም መጠንቀቅ አለባችሁ በማለት ከተሳሳቅን በኋላ "አሁን ዋናው ጠላታችን ከሶማሊያ በላይ ጊዜ ነው። እንድሄድ ይፍቀዱልኝ" ብለው ተሰናበቱን።

ጓድ ፊደል ሲሰናበቱን ጊዜው ከጠዋቱ አራት ሰዓት ገደማ ነበር። የየመን አመራር ጓዶች ፊደል ካስትሮን የሚሸኙ ሰዎች ልከው በውይይቱ ጊዜ በተሰበሰብንበት ትንሽ አዳራሽ ውስጥ ቁርስ አዘጋጅተው ጋበዙን። የመኖቹ የሶማሊያዎችን የወረራ ዝግጅት በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በእነሱም ላይ የተቃጣ ያህል ተሰምቷቸዋል።

እነሱም እንደ ኩባዊያኑ "የእናንተ ጠላት ሶማሊያ ብቻ ሳትሆን ጊዜም ነው" አሉን። መላው የሶሻሊስት ጎራ ከእናንት ጋር ነው ካሉ በኋላ "ወደ አገራችሁ ከተመለሳችሁ በኋላ ሁኔታችሁን አረጋግጣችሁ በእኛ በኩል እንድናደርግ የምንትፈልጉትን ሁሉ ያለማመንታት ግለጡልን። ከጎናችሁ ቆመናል" በማለት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አብረውን በመሄድ ምንጊዜም በማይረሳ ስሜት አሰናበቱን።

# ክፍል ፯

# የውጭ ጥቃቶች

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት

# ከውጭ የተሠነዘሩብን ጥቃቶች አብዛኛዎቹ በጠላቶቻችን ብርታት ሳይሆን በኛ ድክመትና የዋህነት ነው!

በአገራችን በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የህልውናና የትግል ታሪክ የተከሰቱ አቢይ ክስተቶችንና የታሪክ አንኳሮችን በዚህ ታሪክ መግቢያና በሌሎችም የታሪኩ ክፍሎች ለመጠቃቀስ የሞከርኩ ቢሆንም በ19ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሕዝቦች ከፍ ያለ የደምና የሕይወት መስዋዕት የከፈሉበት ነው። በአፍሪካም ታሪክ፣ በአፍሪካዊያን መካከል ከተደረጉ ግጭቶችና ጦርነቶች ሁሉ በዓይነቱ ልዩና የመጀመሪያ ስለሆነው ሰለውጊያ ከመተረኬ በፊት አገራችንን ኢትዮጵያን፣ ሕዝቧንና መሪዎቿን በተደጋጋሚ ተጠቂዎች ካደረጓቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹን ማለትም ወዳጅ መስለው በመቅረብ ባዕዳን የፈፀሙብን ክህደትና ሸፍጥ በአጠቃላይ፤ አፄ ኃይለሥላሴ ብቸኛ አጋርና መከታ አድርገው በመመልከት ለአገራችን አያሌ ጠላቶችን የገዙባት ኢምፔሪያሊስት አሜሪካ ለኤርትራ የመገንጠል ሴራና ለሶማሊያ መንግሥት የመስፋፋት ወረራ የቱን ያህል አስተዋፅኦ እንዳደረገች በአንድ የዚህ ታሪክ ክፍል ውስጥ በማሰባሰብ ዘርዘር አድርጎ መግለጡ ሰለጦርነቱ ምክንያትና ባህሪ ግንዛቤ ከመሰጠቱ በላይ ለመጭዎቹ የኢትዮጵያ ትውልዶች ጠቃሚ ትምህርት ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ቢቻል ማንም ወዳጅ እንጅ  ጠላት እንዳይሆን ማድረግ ብልህነትና የዲፕሎማሲ ጥበብ ቁልፍ ምስጢር ሲሆን፤ ማንንም ዓይንን ጨፍኖ ማመን ግን እጅግ አደገኛ የሆነ የዋህነት ነው።

ከዚህ መሠረተ ሃሳብ በመነሳት ወደ አገራችን ጥንታዊ ታሪክ እርቄ ሳልሔድ የቅርቡን በተለይም የዘመነ ኢምፔሪያሊዝምን የአገራችንን ዙሪያና መግቢያ መውጫችንን የከበቡት የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና ሌሎቹም ግብረ አበሮቻቸው በአንድ ወቅት እኛን ለመጠጋት ሲሉ ወዳጅ መስለው በመቅረብ በሌላው ወቅት ሊያጠፉን እንዴት እንደተሠለፉብን ማስታወሱ ተገቢ ነው።

በሰፊውና በረጅሙ የታሪካችን ሂደት አልፎ አልፎ እስከ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ከአገሪቱ ድህነትና ኋላቀርነት የተነሳ በአቅም ማነስና በምርጫ እጦት ብቻ ሳይሆን በመሪዎቻችን ማለትም፣ በነገሥታቱ፣ በባላባቶች፣ የዛሬውን የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አሻንጉሊት ወያኔን ጨምሮ ሃገርን ያህል ነገር እየቀረሱ በመሸጥ የማይጠገኑ ጥፋቶችና እጅግ ታላላቅ ብሔራዊ ጉዳቶች ደርሰውብናል።

ከመንፈሳዊ ጉዳዮች ረገድ አንዱን ብቻ ብገልፅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናቱ ነገሥታቱና በእነዚህም አማካኝነት አብዛኛው ሕዝበ-ክርስቲያን ከአይሁዶች ጋር ባለን ጥንታዊ የታሪክ ግንኙነት ላይ ተመሥርተው የእሥራኤል አምላክ ያድነናል ይታደገናል በማለት ፈጣሪያችንና አዳኛችን የሚሉትን አምላክ ሲማልዱ ይሰማሉ።

አይሁዶች የኢትዮጵያን ሕዝበ-ክርስቲያን መንፈሳዊ እምነት የሚጋሩ አይደሉም፡፡ በክርስትና ያለማመን ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝበ-ክርስትያን ኢየሱስ እያለ የሚጠራውንና የሚያመልክበትን አይሁዶች “እኛ እስከምናውቀው ድረስ ኢየሱስ የሚባለው ከሌሎች ፍጡራን ያልተለየ አንድ ተራ አይሁዳዊ ግለሰብ ነው” የሚሉ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝበ-ክርስትያን ከአይሁዶች መንፈሳዊ እምነት ጋር የማይቀራረቡ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ግንኙነታችንንም በተመለከተ እስተሳሰቡም አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያስበውና ምናልባትም እንደሚያምነው አይሁዳዊያን ለኢትዮጵያዊያን ተመሳሳይ አመለካከት የላቸውም።

ነገሥታቶቻችን የዘር ሃረጋችን ከሰለሞን ዘር ይመዘዛል ሲሉ በመኖራቸው በዓለም የእስልምና አማኞች ዘንድ በአጠቃላይ በአረቦች ዘንድ በተለይ ጥቁር አይሁዶች ተብለን የጥቃት ኢላማቸው መሆናችንን በሚገባ የሚያውቁት የእሥራኤል መንግሥት የአመራር አካላት በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ በተለይም ወደ መጨረሻው ጊዜ በውስጥና በውጭ በጠላቶቻችን የእርዳ ተራዳ ርብርብ የወሳንሳ ተወጥረን ታላቅ ችግር ላይ በነበርንበትና የኢትዮጵያ አንድነት አደጋ ላይ በወደቀበት ጊዜ ከአረቦች ጋር ተሠልፈው ታላቅ በደል በመፈፀም አሳዝነውናል።

# ምዕራፍ ሃያ አራት

# በዳግማዊ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት

በዘመነ መሣፍንት የየክልሉ ጉልታዊ ገዥዎች ወገን በመለየት ተከፋፍለው ለሥልጣን ሲፋጁ አገሪቱን ከፋፍለውና አዳክመው ለቅኝ ግዛት ኃይሎች ወረራ ማጋለጣቸው ያነሰ ይመስል በየፊናቸው ከተለያዩ የቅኝ ግዛት ጥመኛ ከሆኑ የአውሮፓ መንግሥታት ጋር በመጻጻፍ ወዳጅ አበጅተው ለሥልጣን የሚያበቃቸው ኃይል ለማሰባሰብ ሲሉ የአገራቸውን ገበና ያጋልጡ እንደነበር ይታወቃል።

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በቀይ ባሕር ዳርቻ ክልሎች ነዋሪ የነበሩ ጥቂት ባላባቶች የሃገርን ገበና ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን የቅኝ ገዥ ኃይሎችን ወረራ ለማመቻቸት መሬት እየቆረሱ የሸጡ መሆናቸው ይታወሳል።

የትግሬው ደጃዝማች ካሳ በኋላ አፄ ዮሐንስ ቴዎድሮስን ለመውጋት ከሕንድ ለመጣው ወራሪ የብሪታኒያ ሠራዊት አዣዥ ለጄነራል ናፒየር ቀለብ በማቅረብ መንገድ በመሥራትና በመምራት ጠቃሚ የውጊያ መረጃ በመስጠት ወታደራዊ ተልዕኮው ስኬታማ ይሆን ዘንድ ከፍ ያለ ርዳታ አድርገዋል።

ኢምፔሪያሊስት እንግሊዝ ኢትዮጵያን ከተቀሩት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቹ ጋር ቀላቅላ የአፍሪካን ቀንድና ቀይ ባሕርን በቁጥጥሯ ስር ማድረግን አለመፈለግ ሳይሆን ለጠቅላላ ወረራ ባለመዘጋጀቷ ብቻ አፄ ቴዎድሮስን ለመበቀልና ዜጎቿን ለማስፈታት የተላከው ጦር ተልዕኮውን ፈፅሞ ወደ ሕንድ ሲመለስ ደጃዝማች ካሳን ለንጉሠ ነገሥትነት ያበቃቸውን ዘመናዊ መሣሪያ ጄነራል ናፒየር ሰጥቷቸው እንደሄደ ይታወቃል።

ይህ ሁኔታ በፈጠረው የታሪክ አጋጣሚ ደጃዝማች ካሳ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ ናፒየርን፣ የእንግሊዝን ንግሥትና መንግሥት የልብ ወዳጃቸውና አጋራቸው አድረገው በማየት በየጊዜው የተከሰቱ ችግሮቻቸውንና ደስታቸውን፣ የግላቸውንና የአገራቸውን ገበና እየገላለጡ ከማስረዳት ባሻገር በእንግሊዝ መንግሥት ጥያቄ በኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ የሱዳን መንግሥት ግዛት ውስጥ መሀዲስት በመባል የሚታወቁ የሱዳን የነፃነት አርበኞች ተከብበው የነበሩትን የግብጽና የእንግሊዝ ወታደሮች የብዙ ኢትዮጵያዊያንን ደምና ሕይወት በጠየቀ ውጊያ አስለቅቀውና እየመገቡ አጓጉዘው በምፅዋ ወደብ በማስወጣት አገራቸው በመላካቸው ከመሀዲስቶች ጋር በተፈጠረው የመረረ ቅራኔ እስከ መዋጋት ደርሰው ሕይወታቸውን ያጡበትን ሁኔታ በመጠቀም የእንግሊዝ መንግሥት ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር ተመሳጥሮ ኢትዮጵያን አስወረረ። በዚህ መዘዝ ኢትዮጵያዊያን እስከ ዛሬ እንደማለን። አፄ ዮሐንስ በወዳጅነት ታላቅ እምነት ጥለውበት ምሥጢራቸውን ሲያካፈሉት የነበረው ሰላይ ሙንሲንጀር የተባለው የስዊዝ ተወላጅ የግብጽ መንግሥት በ18ኛው ምዕት



አፄ ዮሐንስ

ዓመት በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት የሰነዘረውን ወረራ አቀነባባሪ ብቻ ሳይሆን የግብጽ ሠራዊት መሪ በመሆን ወግቷቸዋል።

በወንጌል መምህርነት መንፈሳዊ ሰውና የኢትዮጵያ ወዳጅ መስሎ ለ40 ዓመታት ለኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ሲሰልል የኖረው ጁሴፔ ሳፔቶ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ለመውረር የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታ በማመቻቸትና በማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ለወረራው መሳካትም ዋና መሣሪያ የሆነ ግለሰብ ነው።

አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ አንዱ ሌላውን ጥሎ ሥልጣን ለማጠቃለል ይቻላቸው ዘንድ በየበኩላቸው ኃይላቸውን ለማጎልበት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት በሁለቱም ዘንድ ወዳጅ መስለው በመቅረብ ወጣገባ እያሉና እንዲሁም በቋሚነት የሚያማክሩና በመላላክ የሚያገለግሉ ባዕዳን ግለሰቦች ነበሩ።

የውሃ፣ የአፈር፣ የእንስሳትና የእፅዋት ተመራማሪዎች ነን እያሉ አገራችንን ከሚቃኙት ሌላ የምህንድስናና የሕክምና ወዘተ ባለሞያዎች ነን በማለት ከቀረቡት በተጨማሪ ነገሥታቱን ሊያማክሩ ከተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታት ጋር በማገናኘትና በተለይም በመሣሪያ ግዢና አቅርቦት ረገድ ሲላላኩና ሲደልሉ የነበሩት የእስኮትላንድ፣ የኢጣሊያ፣ የጀርመን፣ የፈረንሳይ፣ የሩሲያና የስዊዝ ወዘተ ዜጎች የነበሩ ግለሰቦች በሙሉ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ይመኙ ለነበሩ የተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታት ወኪል ሆነው የሚሰልሉ ነበሩ።

ኢጣሊያኖች አፄ ዮሐንስንና ምኒልክን አዋግተው ሁለቱንም በማዳከም በኢትዮጵያ ላይ የጀመሩትን ወረራ ለማስፋፋት መላዋን ኢትዮጵያ ለመቆጣጠር በነበራቸው የሩቅ ዓላማ ስኬታማነት ከዮሐንስ ጀርባ የምኒልክ ወዳጅ በመምሰል ያቀርቡ በነበረው መሣሪያ ምኒልክ ተጠቅመው ለንጉሠ ነገሥታትነት ያበቃቸውን ኃይል ከመገንባት ባሻገር የኢጣሊያንን ወራሪ በአድዋ የጦር ሜዳ ድል ቢያደርጉም ጊዜ ወሰደ እንጂ የኋላ ኋላ የኢጣሊያ መንግሥት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ግቡን የመታ መሆኑን ኢትዮጵያዊያን መዘንጋት የለብንም።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት

# በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት

ዳግማዊ ምኒልክ ከጀርመን መንግሥት ጋር የወጠኑትን ወዳጅነት ለማጠናከር በነበራቸው ፍላጎት በየዓመቱ በአውሮፓ ክረምት ወይም የበረዶ ወቅት የጀርመን ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ እንዲያርፉበትና እንዲዝናኑበት በሸዋ ክፍለ ሃገር በመናገሻ አውራጃ በአዲስ ዓለም ወረዳ በርጋ በሚባለው ጅረት ዳርቻ ጉሬዛዎች በብዛት ስለሚኖሩበት የጉሬዛ አንባ እየተባለ በሚጠራውና ተፈጥሮ ባደለው ውብና ነፋሻ ሸለቆ ውስጥ አምስት ጋሻ መሬት ሰጥተዋቸው አንድ ትንሽ ዘመናዊ የአውሮፓ መንደር ገንብተው ይጠቀሙበት ስለነበረ ሸለቆው የጉሬዛ አንባ ከመባል ፈንታ የጀርመኖች ሰፈር እየተባለ ይጠራ ነበር።

ምኒልክ የጀርመኖችን ወዳጅነት ለማግኘት ያደረጉት ጥረት በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ ለጀርመን መንግሥት ኤምባሲ ጽሕፈት ቤት፣ ለኤምባሲው ሠራተኞች መኖሪያ፣ ለጀርመን ሕፃናት ት/ቤት እና ለጀርመን ባህልና የታሪክ መዘክር ወዘተ ህንፃ መሥሪያ የሚሆን ሰፌ የከተማ ቦታ ስለሰጧቸው በምኒልክ ዘመነ መንግሥት የጀርመን ዜጎች በኢትዮጵያ ተዝናንተውና ተመቻችተው በደስታ ይኖሩ ነበር።

በቀድሞው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ወግና ባህል የኢትዮጵያ ነገሥታት ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ የየመንግሥታቱን ወኪሎችና ዲፕሎማት እንደ ግል እንግዶቻቸው በመቁጠር በሚያደርጉላቸው መስተንግዶ መሠረት ዲፕሎማቶቹ በኢትዮጵያ እስከኖሩ ድረስ ላልተወሰነ ጊዜ ከሚደረግላቸው እጅግ ለጋስ የሆነ መስተንግዶ ሌላ ምንም ዓይነት መንግሥታዊ ተልዕኮ ሳይኖራቸው በእራሳቸው ፍላጎትና አነሳሽነት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በገነቡት ሰፈር ለሚኖሩት ጀርመናዊ ሃገር ጎብኚዎች በየዓመቱ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ወደ አገራቸው እስከሚመለሱበት ጊዜ ድረስ የሚመገቡት ዶሮ እና እንቁላል፣ የዳልጋና የቀንድ ከብቶች፣ የሚጠጡት ጠጅ ከቤተ መንግሥት ይላክላቸው ነበረ።

ይህንና ይህንንም በመሳሰሉ ሁኔታዎች ከጀርመን መንግሥትና ሕዝብ ጋር በተፈጠረው መልካም አዝማሚያና መቀራረብ ተማምነው ዳግማዊ ምኒልክ ለሃገር መከላከያ የሚሆኑ አንድ መቶ ሺህ ዘመናዊ ነፍጥና 50 የተራራ መድፎች ከበቂ ጥይቶች ጋር እንዲሸጡላቸው ጠይቀው የጀርመን መንግሥት ለመሸጥ ፈቃደኛ በመሆኑ፣ ለዚሁ መግባባት ማስረጃ ይሆን ዘንድ የውል ሰነድ ከተለዋወጡ በኋላ የአፈፃፀም ሂደት ቀጥሎ መሣሪያው ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣበት ሁኔታ ሲጠበቅ፣ በኢጣሊያንና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የተደረገው ጠንቀኛ የውጫሌ ውል በሁለቱ አገሮች መካከል ብቻ ሳይሆን በአውሮፓና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከልም የፖለቲካ ውዝግብ በፈጠረበት ጊዜ የጀርመን መንግሥት

ለተስፋፊው የኢጣሊያ መንግሥት ወግኖ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የነበረውን ወዳጅነትና መሣሪያ የመሸጥ ውል አፈረሰ።



አፄ ምኒልክ

በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያን ክዶ ለወረራ ከማጋለጥ ባሻገር በጊዜው በኤርትራ ቅኝ ገዥና የኢጣሊያ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ጄነራል ባራቴየሪ በኢትዮጵያ ላይ መጠነኛ የማጥቃት ውጊያ ሠንዝሮ፤ በኮአቲትና በሠንአፌ በራስ መንገሻ ጦር ላይ ጊዜያዊና መጠነኛ ወታደራዊ ድል በማግኘቱ የጀርመን ሠራዊት በኢትዮጵያ ላይ ድል የተቀዳጀ ይመስል ዳግማዊ ምኒልክን የካደው የጀርመን ንጉሥ ዳግማዊ ቪልሀልም የኢጣሊያ አቻውን ንጉሥ አምቤርቶን አስፈቅዶ ለጄነራል ባራቴዬሪ የጀርመን መንግሥት ታላቅ የጦር ሜዳ ጀብዱ ወታደራዊ ኒሻን እስከመሸለም ደርሷል።

ከአውሮፓ ባለኢንዱስትሪ ታላላቅ መንግሥታት መካከል ፈረንሳይና የሩሲያ መንግሥታት የውጫሌውን የፖለቲካ ሸፍጥና የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ተቃውመው ለኢትዮጵያ በመወገን ለዳግማዊ ምኒልክ የጦር መሣሪያ ባያቀርቡ ኖሮ፣ በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገችው ሳያስፈልግ የመጀመሪያው የ1888 ዓ.ም ወረራ ስኬታማ በሆነና ኢትዮጵያ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት በሆነች ነበር። እንግሊዝና ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በተለይ፤ በመላው የአፍሪካ ቀንድ ላይ በአጠቃላይ የነበራቸውን የመስፋፋት ፍላጎት በመቃወምና በመከላከል ፈረንሳይ ከአርባ ዓመታት በላይ ከኢትዮጵያ ጎን በጽናት ቆማ ነበር።

የኢጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ,ጋር የተዋዋለውን የውጫሌ ውል ምክንያት አድርጎ፤ ዳግማዊ ምኒልክ አገራቸው ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ሞግዚትነት ትተዳደር ዘንድ ተስማምተዋል በማለት በኢጣሊያንኛ ቋንቋ በተዘጋጀው የውል ቅጅ ላይ አክሎ በመጻፍ የፈጠረውን የፖለቲካ ሸፍጥ አልቀበልም ብላ በመቃወም ከሩስያ ጋር የመጀመሪያዋ ሃገር ብቻ ሳትሆን ተቃውሞዋን በአውሮፓ በማዛመትና ለተቃውሞው አፄ ምኒልክን በመቀስቀስ ያበረታታች ብቸኛ ሃገር ፈረንሳይ ነበረች። ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ፈረንሳይ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎና ተደማጭነት ነበራት። ብቸኛው ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የባቡር መጓጓዣና ወደብ ግንባታና አገልግሎት ለዘጠና ዘጠኝ ዓመታት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ውለታ ዳግማዊ ምኒልክ የተዋዋሉት በፈረንሳይ መንግሥት ትብብርና በሷ ፈቃድ ከፈረንሳይ የምድር ባቡር መጓጓዣ ገንቢ ኩባኒያ ጋር ነበር። እስከ ኢጣሊያ ወረራ ድረስ በኢትዮጵያ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተወሰደውና የተለመደው የባዕድ ቋንቋ ፈረንሳይኛ ነበር። በኢትዮጵያ የተቋቋመው

የመጀመሪያው ዘመናዊና አውሮፓዊ ትምህርት ቤት ይጠቀምበት የነበረው የማስተማሪያ ቋንቋ ፈረንሳይኛ ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት እስካሁን አለ። የአገሪቱ የንግድ ሕጎች ከፈረንሳይ የንግድ ሕጎች የተቀዱ ከመሆናቸውም በላይ የተዘጋጁትም በፈረንሳይኛ ቋንቋ ሲሆን የመጀመሪያው ብቸኛው በአውሮፓ ቋንቋ የሚዘጋጀው ኮሪየር ኢትዮጵያ በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን 1924 ዓ.ም አውሮፓን ለመጎብኘት የሄዱት በፈረንሳይ መንግሥት እንግዳነትና ግብዣ ነበር።

በአውሮፓና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የፖለቲካ፣ የንግድና የመከላከያ ወይም በጋራ ደህንነት መቀራረብና መረዳዳት የተጀመረው ዓመተ ዓለም እየተባለ በሚጠራው የጊዜ ክልል ከጥንት ግሪካዊያንና ሮማውያን ጋር ቢሆንም በርካታ የፈረንሳይ ዜጎች ኢትዮጵያን አዘውትረው ከመጎብኘታቸው በላይ በተለያዩ የሥራ ተልዕኮና ምክንያቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት በመኖራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተዋወቃቸው፣ ፈረንሳዮች ብሎ ለመጥራት ፈረንጆች የተሰኘ ስም ስለሰጣቸው በታሪክ ሂደትና በጊዜ ርዝመት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በጠቅላላ የነጭ ሕዝብ ዘር መጠሪያ ሆኖ ቀረ።

በዚህ ዓይነት ከአውሮፓ ብቸኛና የረጅም ጊዜ አስተማማኝ ወዳጅ ናት ተብላ በኢትዮጵያ ነገሥታት እምነት የተጣለባት ሃገር በቀድሞው የዓለም መንግስታት ማህበር ውስጥ ከእንግሊዝ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን አሳልፈው ለመስጠት የቤኒቶ ሙሶሎኒን የመስፋፋት ዓላማ የደገፉት አገሮች መሪና ቀንደኛ አስተባባሪ ሆነች።

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

# በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት

ኢትዮጵያ የፋሽስት ኢጣሊያን የእብሪት ወረራ ለመመከት የሚያስችላት የጦር መሣሪያ እንዲሸጡላት ሰሜን አሜሪካንንና የአውሮፓን ባለኢንዱስትሪ አገሮች ትብብር በጠየቀች ጊዜ ፈረንሳይ ራሷ በኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብ ማድረጓ ያነሰ ይመስል የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት ማዕቀብ እንዲያደርጉ አስተባባሪ ሆነች።

ፈረንሳይ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመችው ወራዳ ተግባርና ክህደት በዚህ ብቻ አላበቃም። በፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያና በዳግማዊ ምኒልክ መንግሥት መካከል ለ99 ዓመታት የሚቆይ የጂቡቲ ወደብና ከጂቡቲ አዲስ አበባ የተዘረጋው የምድር ባቡር መጓጓዣ የጋራ ጥቅም ውል የገባውን ሕግ በመጣስ የኢትዮጵያ መንግሥት ከፋሽስት ኢጣሊያ የእብሪት ወረራ ራሱን ለመከላከል በጂቡቲ ወደብ የጦር መሣሪያ እንዳያስገባ በመከልከል የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ቀዳሚና ከፊሉን የድል ግኝት ከማመቻቸት ሌላ ወራሪው ሠራዊት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላም በመላው ኢትዮጵያ የሚስፋፋበት የወረራ ተግባር ይሳካ ዘንድ በጂቡቲ ወደብና በምድር ባቡሩ መጓጓዣ፣ ሠራዊት፣ የጦር መሣሪያ፣ ስንቃስንቅ እና ነዳጅ ወዘተ በገፍ እንዳሻው እንዲያስገባና እንዲገለገል አድርጋለች።

የቀድሞው የዓለም መንግሥታት ሊግ ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ እንድትወረር ካደረገ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በጥገኝነት ለመቀበል የፈቀደው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካለው ወገናዊነት ለንጉሡ በነበረው ሰብአዊ ርህራሄ ሳይሆን ከዚህ በሚከተሉት ሁለት የፖለቲካ ጥቅሞች ሲል ነው።

የመጀመሪያው፣ ፋሽስት ኢጣሊያ የአፍሪካን ቀንድ ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ የነበራትን ፍላጎት በመደገፍ ከጀርመን ጋር ስትተባበር የፈረንሳይና የእንግሊዝ ወዳጅ በመሆን ቆይታ ኢትዮጵያን ከወረረች በኋላ አቋሟን በመለወጥ ከጀርመን እንዳትወግን ንጉሡን በመያዣነት ሊጠቀም በመፈለግ ነበር። ይህ የፖለቲካ ወጥመድ እንደተፈለገው ሳይሰራ ቀርቶ ኢጣሊያ ከጀርመን ጋር ብትሰለፍና የሁለቱ መንግሥታት የጦር ኃይሎች በጊዜው የጀርመን የአፍሪካ ኮር ይቆጣጠረው ከነበረው ከሰሜን አፍሪካ ምድር እየተንደረደሩ ግብጽን፣ መካከለኛውን ምሥራቅ፣ መላውን የአፍሪካ ቀንድና ቀይ ባሕርን በመቆጣጠር የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት በሕንድ ውቂያኖስና በኢስያ ክልል ካሉት ሰፊ ቅኝ ግዛቶቹ ለመቁረጥ ቢያስቡ አፄ ኃይለሥላሴን ወደ አገራቸው መልሰው ዙፋናቸው ላይ በማስቀመጥ፣ ቀይ ባሕርንና የሕንድ ውቂያኖስን ለመጠበቅ ወይም ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለውን የኢትዮጵያ መልክዓምድር፣ በተፈጥሮ ተዋጊ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የተደራጀውንና የታጠቀውን የኢትዮጵያ አርበኞች ግምባር፣ ከደቡብ፣ ከምሥራቅና ከምዕራብ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቹ ጋር አቀናጅቶ ከጀርመንና ከኢጣሊያ ጦር ኃይሎች ጋር መዋጋት ግዴታው

ስለነበረ ሊጠቀምባቸው ነበር። እንባቢ ለማስተዋልና ከዚህ ሁኔታ ለመረዳት እንደሚችለው የሆነውና በመጨረሻም የሰራው ይሄው ሁለተኛው የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት እቅድ ነው።

ከአውሮፓ ቀድማ በኢኮኖሚና በጦር ኃይል ግንባታ ያደረገችውን ከፍተኛ እድገት ከማድነቅ ባሻገር እንደ ምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት የቅኝ ግዛት ፍላጎት የላትም ብለው የሚያምኑ ከመሆናቸው ሌላ የቤኒቶ ሙሶሎኒ ቅጥ ያጣ የቅኝ ግዛት ፍላጎትና የወረራ ዝግጅት ስለ አስፈራቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሰሜን አሜሪካ ጋር ለመወዳጀት የቆየ ፍላጎት ነበራቸው።

ኢጣሊያ የአፍሪካን ቀንድ ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ በነበራት የቆየ ዓላማ በ18ኛ ምዕት ዓመታት ኢትዮጵያን ለመውረር ሞክራ በአድዋ የጦር ሜዳ የደረሰባትን ሽንፈት በ19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ለመበቀልና ዳግም ለመውረር ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅ ቆይታ፣ በኤርትራና በሶማሊያ የጦር ኃይል አካብታ ሁለተኛውን የጦርነት እሳት ለመጫር ስትል የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክልል አካል የሆነውን ወልወል በመባል የሚጠራውን የጠረፍ ወረዳ ወረረች።

የኢትዮጵያ መንግሥት በጊዜው የነበረው የዓለም መንግሥታት ማህበር የተቋቋመበትን መሰረታዊ ዓላማና በተለይም በማህበሩ አባል መንግሥታት ላይ ጥቃት ቢደርስ ወይም ጥቃት ሊደርስነው ተብሎ ቢገመት በአንድ ወይም በጥቂቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የማህበሩ አባል መንግሥታት ሁሉ የጋራ ሃላፊነት አለባቸው የሚለውን የማህበሩን ሕግ አንቀፅ 10 በመግለፅ ለማህበሩ ያቀረበው አቤቱታ በመንግሥታቱ ማህበር ጉባዔ ላይ ሳይሆን ከጉባዔው ውጭ በሚመረጡ ጥቂት አስታራቂዎች ይታይ ብሎ በመወሰኑ ምክንያት የታዬውን አዝማሚያ በመመልከትና ይህም ባሳደረበት ስጋት የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው ምርጫ ሰሜን አሜሪካ የመንግሥታቱ ማህበር አባል ባትሆንም የማህበሩ አባል አገሮች በጦርነት እንዳይፈላለጉ፣ ወይም አንዱ በሌላው ላይ ጦር እንዳይመዝ የሚከለክለውንና እሷም ወዳ የተቀበለችው "የኬሎ ግብሪያንድ" ስምምነት ግዴታዎች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በርዳታ መልክ ለሰሜን አሜሪካ መንግሥት አቅርቦ ነበር።

አንደኛው ጥያቄ አሜሪካ ባላት ክብደትና በኢጣሊያን ዘንድ በነበራት ተደማጭነት ኢጣሊያ ከወረራ ትገታ ዘንድ በጎ ተፅዕኖ እንድታደርግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ከአማላጅነትም አልፋ ሌሎች የማህበሩ አባል አገሮች ሳያስፈልጉ እሷ ብቻዋን ኢትዮጵያንና ኢጣሊያንን በመሸምገል እንደታስታርቅ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት በመልካም ግምትና በወዳጅነት ፍላጎት ያቀረባቸውን ሁለቱንም ጥያቄዎች አለቀበልም አለች። በፋሽስት ኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተጀመረውን ግጭት ከመሸምገል ይልቅ ኢጣሊያ ከሂትለር ጋር እንዳትወግን እንግሊዝና ፈረንሳይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ደምና ህልውና የሚጫወቱትን የፖለቲካ ቁማር በመደገፍ በኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብ ከማድረግ አልፋ የእሷ ተከታይ የሆኑትን አያሌ አገሮች በዚህ ሴራ አስተባበረች።

የቀድሞውን የመንግሥታት ማህበር እንዳሻቸው ሲያሽከረክሩ ከነበሩትና በኋላም ከገደሉት የምዕራብ አውሮፓ አውራ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር አሜሪካ ቀደም ብላ በኢትዮጵያ ላይ ስታሴር እንደነበረች መረዳት የሚቻለው፣ ከኢጣሊያ ወረራ ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ የነዳጅ ዘይት ፍለጋና የቁፋሮ ሥራ ለመሥራት በራሱ ፈቃድና አነሳሽነት ወደ

ኢትዮጵያ መጥቶ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የተዋዋለውን 'ስታንዳርድ ቫኩም' በመባል የሚታወቀውን ኩባኒያ እንዳይሠራ ማገዱ ነው። በጦርነቱ ሂደት ውስጥ አፄ ኃይለሥላሴ በእንግሊዝ ሃገር ስደት ላይ በነበሩበት ጊዜ ወደ አሜሪካ ለመግባት ቢጠይቁ የሰሜን አሜሪካ መንግሥት እስከመጨረሻው ከልክሏቸዋል።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደተመኙት አሜሪካ ወዳጅ ባትሆንም ከእንግሊዝ በርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ የተላከው ጦር አዛዦች የነበሩት መኮንኖች ወታደራዊ አምባገነን አስተዳደር በመመሥረት አገሪቱን ከፊል ቅኝግዛታቸው ከማድረግ ባሻገር ንጉሡ ነገሥቱን በማንኳሰስ በገዛ አገራቸው ስላዋረዷቸው ከእንግሊዞች ለመገላገል የነበራቸው መፍትሔ ከሰሜን አሜሪካ ጋር መለጠፍ ብቻ ነው የሚል እምነታቸውን ስለአጠናከረው ጥገኝነት ጠየቁ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በነበረው ጠቅላላ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ምክንያት ለማህበራዊ ፍትህና ለውጥ ይንቀሳቀስ የነበረው መላው የአውሮፓ ሠራተኛ መደብ በጦርነቱ ሂደትም ውስጥ ትግሉን ቀጥሎ ከጦርነቱ በኋላ በመላው አውሮፓ ይበልጥ በተስፋፋው የኢኮኖሚ ድቀት፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ፍትህ እጦት፣ ረሀብ፣ ሥራ አጥነትና አጠቃላይ ማህበራዊ ቀውስ እያሌ የአውሮፓ ገገር መደቦችና መንግስታት እየወደቁ ዲሞክራት፣ ሶሻሊስትና ኮሚኒስት ፓርቲዎች የፖለቲካ ሥልጣን ተቀዳጁ።

አሜሪካ ጦርነቱ በፈጠረላት መልካም አጋጣሚ ይበልጥ በጎለበተው የኢኮኖሚ፣ የገንዘብና እንዲሁም የጦር ኃይል ተመክታ የምዕራቡ ዓለም መሪ እኔ ነኝ ብላ ከማወጅ ባሻገር አውሮፓን በማጥለቅለቅ ላይ የነበረውን ሕዝባዊ አብዮት በማፈን የካፒታሊስት ሥርዓተማህበርን ከጥፋት ለማዳን ስትል በጦርነቱ የዳሸቁትን የአውሮፓ አገሮች መልሶ ለማቋቋምና ብሎም ለመገንባት ርዳታ በሚል ሽፋን የገንዘብና የጦርኃይሏን አቀናጅታ ዳግም ወደ ምዕራብ አውሮፓ መዝመቷ በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

በዚህ እቅዷ ከአውሮፓ በሁለተኛ ደረጃ ካተኮረችባቸው አንዳንድ ታዳጊ አገሮች ጋር ኢትዮጵያንም አክላ ከማየቷ ሌላ ኢትዮጵያም ጥገኝነት ስለጠየቀች፣ እንደአውሮፓ አቆጣጠር በ1942 ዓ.ም ከአሜሪካ የገንዘብ ብድርና ሌሎችንም ርዳታዎች ልታገኝ ይገባል በሚል ሃሳቧን መግለጧ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘንድ ተስፋ ፈንጥቋል። አሜሪካ ከኢጣሊያና ከሌሎቹ የአውሮፓ አውራ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር በማበር በኢትዮጵያ ላይ የያዘችውን አፍራሽ አቋም በማሻሻል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የርዳታና የማቋቋሚያ አስተዳደር ተጠቃሚ እንድትሆንም አደረገች።

አሜሪካ የምዕራቡ ዓለም ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም መሪ ነኝ ወደማለቱ ግብዝነት በተሸጋገረች ጊዜ እንግሊዝ በኢትዮጵያ ላይ ተክላ ለማቆየት የፈለገችውን የከፊል ቅኝ ግዛት አስተዳደር ደጋፊ ሆና ያለመገኘቷም ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የበለጠ ተስፋ ሰጥቷል።

በአንባቢ ዘንድ ይታወስ እንደሆን ከጦርነቱ በፊትና በጦርነቱ ሂደት ውስጥ በጀርመን፣ በኢጣሊያና በጃፓን መንግሥታት ቅኝነትና ወታደራዊ ይዞታ ሥር የነበሩ አገሮች የወደፊቱ ዕድል የጦርነቱ አሸናፊ በሆኑት አራቱ ታላላቅ መንግሥታት ማለትም፣ ሶቭየት ሕብረት፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ የተሰየሙበት የሠላም ጉባዔ እስኪወሰን ድረስ በእንግሊዞች አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ነፃ ሃገር አይደለችም።

ከዚህ በኋላ ከሃያ ዓመት በላይ እስከ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ድረስ የቆየው የኢትዮጵያና የአሜሪካ መንግሥት ግንኙነትና የተራድኦ ውል የተቋጨው አፄ ኃይለሥላሴ በስዊዝ ቦይ የአሜሪካንን መሪ ፕሬዝዳንት ሩዝቬልትን አግኝተው ባነጋገሩበት ጊዜ ነው።



በሁለቱ መሪዎች ግንኙነት አፄ ኃይለሥላሴ ያቀረቧቸውን፣ በእንግሊዝ መንግሥት ወታደራዊ ይዞታ ሥር ስለነበሩት የኤርትራና የኦጋዴን ክልሎች እንዲመለሱላት ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ላይ የምታቀርበውን ጥያቄ አሜሪካ ድጋፏን ከመስጠት ጭምር ሌላ በገንዘብ ብድር በኢኮኖሚና በመከላከያ ርዳታ ስለሚገኙበት ሁኔታም ነበር።

ከአፄ ኃይለሥላሴ ጥያቄ አንፃር አሜሪካንም በበኩሏ ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪካን መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ቀይ ባሕርንና የሕንድ ውቂያኖስን ስትራቴጂያዊ ክልሎች በባሕርና ባየር በቋሚነት በመቃኘትና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ለመሰለል ያስችላት ዘንድ በኤርትራ ክፍለሃገር ርዕሰ ከተማ በአሥመራና በምፅዋ ወደብ አካባቢ የተመረጡ ሥፍራዎች ለወታደራዊ አገልግሎት ይሰጧት ዘንድ የኢትዮጵያን መንግሥት ጠየቀች።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ዋና ጽሕፈት ቤቱ በአገሯ የተቋቋመውን አዲሱን የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ማሽከርከር ጀምራ አፄ ኃይለሥላሴ በመንግሥታቱ ቻርተር ላይ የሰፈረውን የዓለም ሠላም የሚጠብቀው፣ ወራሪን በጋራ ደህንነት መርህ በመቋቋም ነው የተሰኘውን ኃይለ ቃል ተግባራዊ ለማድረግ የአሜሪካን መሪነት ወሳኝ ነው ብለው ከማሰብ ባሻገር ይህን መርህ ለኢትዮጵያ ደህንነት ዋስትና ነው የሚል' እምነት ስለነበራቸው የኮሪያ ጦርነት በተቀሰቀሰ ጊዜ ከአሜሪካ ወራሪ ሠራዊት ጎን ተሠለፎ የሚዋጋ አንድ እግረኛ ሻለቃ ጦር አዘመቱ። በዚህ ሁኔታ በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ግንኙነትና በተለያዩ ጊዜያቶችና በተለያዩ ደረጃዎች የተደረጉ ውይይቶች እድገት አሳይተው ኢትዮጵያን በዓለም ፊት የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ ያደረጋት ጠንቀኛ ውል በሁለቱ መንግሥታት መካከል ተፈረመ። በውሉ ሰነድ ላይ የሠፈሩትን ሃተታዎች መዘርዘር ሳያስፈልግ ዋና ዋና ነጥቦቹ በአጠቃላይ ሲታዩ ከዚህ እንደሚከተሉት ናቸው:-

የኢትዮጵያ መንግሥት በሰሜን ኢትዮጵያ ክልል ለአሜሪካ መንግሥት ወታደራዊ አገልግሎት የሚውል የተወሰነ መሬት ሲሰጥ የአሜሪካ መንግሥትም በበኩሉ የኢትዮጵያን የምድር ጦርን፣ የአየር ኃይልንና የባሕር ኃይልን ያካተተ አርባ ሺህ የመከላከያ ሠራዊት የማስታጠቅ ግዴታ ገብቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት አሥመራ ላይ በሚቋቋመውና ቃኘው በመባል በሚጠራው ወታደራዊ ማዕከል ውስጥ የሚሠሩት፤ የኢትዮጵያን የጦር ኃይል የሚያማክሩት፤ በሌሎች የሲቪል አገልግሎት በኢትዮጵያ ለተሠማሩና የአሜሪካ ኤምባሲ ሠራተኞች ወዘተ ለሆኑ አሜሪካዊያን በኢትዮጵያ ባሕር፣ የአየር ክልል፣ የብስ ወይም ምድር ላይ በሙሉ እንደአሻቸው ያለገደብና አንዳች ቅድመ ሁኔታ የመንቀሳቀስ፤ የማረፍና በአስፈላጊ ጊዜ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማትን የመገምባት መብት እንዲሰጥ ያስገድዳል።

በዚህ ውል መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩት አሜሪካዊያን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊያን ላይ ምንም ዓይነት ወንጀል ቢፈፅሙ በኢትዮጵያ ፖሊስና በሌሎች ፀጥታ አስከባሪዎች እንዳይያዙ፤ በኢትዮጵያ ማረሚያ ቤቶች እንዳይጠበቁና በኢትዮጵያ የፍርድ ቤቶች እንዳይዳኙ በመፍቀድ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ህልውና፣ ክብር፣ ሕገ መንግሥትና ከህገ መንግሥቱም የሚመነጩትን የአገሪቱን ህጎች በመጣስ ሕዝቡንና አገሪቱን ያዋረደ ውል ነበር። ይሔው ውል ከዚህ በላይ ከተገለጡት ቅጥ ያጡ መብቶች በላይ ሌሎች የተለያዩ መንግሥታትን ወክለው በኢትዮጵያ የሚኖሩ ወኪሎች አምባሳደሮችና ዲፕሎማት ያልተሰጣቸውን ልዩ ልዩ መብቶች ለአሜሪካዊያን ይሰጥ ነበር።

የዚህን ውል መንፈስና ትርጉም በተመለከተ በአሜሪካዊያንና በኢትዮጵያዊያን መካከል ከፍ ያለ ውዥንብርና ልዩነት ሰፍኖ ቆይቷል። የውሉን ሠነድ ሳነበበ ሁሉ ውሉ በሠነዱ ላይ የሠፈሩት ጉዳዮች የማያሻሙ፤ አጭርና ግልፅ ሆነው ሳለ ከንጉሡ ጀምሮ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ግምትና ግንዛቤ፤ በአሜሪካና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል የጋራ ደህንነት የመከላከያ ውል እንደሆነ አድርገው ሲያስቡ አሜሪካዊያን ለውሉ ያላቸው ትርጉም ከኢትዮጵያዊያኑ በጣም የተለየና የራቀም ነበር።

ይህ ውል የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት የሚያዋርድ ብቻ ሳይሆን፤ መላው ሕብረተሰብዓዊ አገሮች፤ የዓለም ሠራተኞች ንቅናቄ፤ የዓለም ዲሞክራትና ሠላም ወዳድ ኃይሎች፤ ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር ለነፃነታቸው ሲታገሉ የነበሩ የአርነት ግምባሮችና መላው ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ኢትዮጵያን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቡችላ የሰሜን አትላንቲክ ወታደራዊ ሕብረት ተቀጥላና የዓለም አብዮት ጠንቅነች ብለው ከማውገዝ ባሻገር የጥቃት ዒላማቸው እንዲያደርጓት ምክንያት ስለሆነው ውል የአሜሪካ መንግሥት ግምት ውስጥ አስገብቶ ምንም ዓይነት ግንዛቤ ሳይወስድ በፍፁም ደንታ ቢስነት ስለኢትዮጵያ ደህንነትና መከላከያ እኔን የሚያገባኝ ነገር የለም በማለት ውሉን ይመለከት የነበረው በአሥመራ ከተማ ለተሰጠው መሬት የጥቂት ጊዜ የኪራይ ውል ወይም ኮንትራት አድርጎ ነበር።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና መንግሥታቸው የአሜሪካ መንግሥት የጦር ኃይል በቀይ ባሕር ዳርቻ በኢትዮጵያ ምድር መሥፈር የአካባቢው ፀረ-ኢትዮጵያ መንግሥታት ኢትዮጵያን መጋፋታቸውን መተናኮላቸውንና በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባታቸውን በመግታት አለኝታና መከታ ይሆናል ብለው ሲመኩ፤ የግብጽ መንግሥት ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ጋር የጀመረውን መቀራረብ ለመግታት ሲል የአሜሪካ መንግሥት የአስዋን ግድብ መገንቢያ ይሆን ዘንድ ከፍ ያለ መጠን ያለው ገንዘብ በ1959 ዓ.ም ለግብጽ መንግሥት ሲለግስ የአሜሪካ ቡችላ ለምትባለውና የአባይ ጅረት ምንጭ ለሆነችው ሃገር መንግሥት ማማከር ቀርቶ በመረጃ ደረጃ እንኳን ለመግለጥ ያላሰበበትን ጉዳይ በአሜሪካ እሥራኤላዊያን ትግልና ተቃውሞ ገንዘቡ ለግብጽ ሳይሰጥ ቀርቷል።

የአሜሪካ መንግሥት ይህንን የሚያደርገው የግብጽ መንግሥት የኤርትራን ገንጣዮች በካይሮ አደራጅቶ ኢትዮጵያን እንዲወጉ ባስማራበትና ገንጣዮቹ በአገራቸው ላይ የሚያካሂዱት ጥቃት ስኬታማ ይሆን ዘንድ የዘይት ከበርቴ የሆኑት የአረብ መንግሥታት የገንዘብና የቁሳቁስ ርዳታ እንዲሰጡ ከማስተባበር በላይ የካይሮ ራዲዮ ጣቢያ በይፋ ፀር-ኢትዮጵያ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የሚያካሂድ መሆኑን እያወቀ ነው።

ሶማሊያ ነፃነቷን እንዳገኘች በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የገባችውን ቃል አጥፋ በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ዓላማዋን በኃይል መተግበር የጀመረችው ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት በዓይነቱም በመጠኑም ከፍ ያለ የጦር መሣሪያ ካገኘች በኋላ ነው።

ኢትዮጵያ የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት በጦር ሜዳ ድል መትታ በማባረር ራሷን መልሳ ማቋቋም ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ለጋስ የሆነ የመከላከያ ድጋፍ ለመስጠት ያለውን ፈቃደኝነት በመደጋገም ገልጾ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ርዳታውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም።

የኢትዮጵያ መንግሥት በአሜሪካ መንግሥት ተማምኖ የሶቭየት ሕብረት መንግሥትን ችሮታ አልቀበልም ብሎ ከመለሰ በኋላ ነው የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ለሰሜን አፍሪካ፤ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለአፍሪካ ቀንድ አገሮች መሣሪያ ማቅረብ የጀመረው።

በተባበሩት መንግሥታት መድረክና በሌሎችም ዓለም አቀፍና አህጉራዊ መድረኮች ላይ በሚካሄዱ የፖለቲካ ትግሎች አሜሪካ የኢትዮጵያን ድጋፍ እየጠየቀችና አንዳንዴም እጅ እየጠመዘዘች በአያሌው ስትጠቀምብን ኖራለች። የእስልምና እምነት አራማጅ ሕዝቦች ማህበርና የአረብ ሊግ አባል አገሮች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባታቸውን ብቻ ሳይሆን ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በእነዚህ እየተረዳና እየተገፋ የአፍሪካን ቀንድ ሠላም ማደፍረስና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሠርጎ በመግባት ሽብር መንዛትን ዓይነተኛና ቋሚ ተግባሩ አድርጎ በቆየባቸው ዓመታት ውስጥ የአሜሪካ መንግሥት አንድም ጊዜ ይህንን እኩይ ተግባር በመቃወም ያወገዘበትና ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ድጋፍ የሰጠበት ጊዜ አይታወቅም።

የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት ሦስተኛውንና ከፍተኛውን ወታደራዊ ስምምነት ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ጋር ተፈራርሞ ባገኘው ከፍተኛ የጦር መሣሪያ የአፍሪካን ቀንድ ብቻ ሳይሆን ከደቡብ አፍሪካና ከግብጽ በስተቀር የመላውን አፍሪካ ወታደራዊ ሚዛን ደፍቶ ነበር። ከምሥራቅ አውሮፓ፣ ከቻይና፣ ከሰሜን ኮርያ፣ ከግብጽ፣ ከኢራቅ፣ ከሊቢያ፣ ከሶሪያ፣ ከአልጀሪያ፣ ከሱዳንና ከሶማሊያ ወደ ኤርትራ ገንጣዮች የጦር መሣሪያ መጉረፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ዳግም በጠላቶች ዙሪያዋን በተከበበችበትና በውስጥም የእነኝህ ቅጥረኞች የሆኑ ከሃዲ ገንጣዮችና አስገንጣዮች እየተበርበረች ባለችበት ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረበውን የመሣሪያ ጥያቄ የአሜሪካ መንግሥት ለመፍቀድ ቀርቶ ጥያቄውን ለመስማት እንደማይፈልግ ቢገልጥም በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል በምስጢር ተይዞ የኖረውን የሁለቱን አገሮች የተራድኦ ውል ገሓድ በማውጣት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ቡችላና የሰሜን አትላንቲክ ወታደራዊ ሕብረት ተቀጥላ ተብላ የተራከሰችውን ሃገር ለጠላቶቿ ማጋለጥ አልነበረበትም።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር አሜሪካ ስለገባችው የፀጥታና የውጭ ርዳታ ስምምነቶች መግለጫ በሰጠበት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሰኔ 1 ቀን 1970 ዓ.ም የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያን መንግሥት የግዛት አንድነት

የመጠበቅ ውለታ ወይም ግዴታ አልገባም በማለት ጠላቶቻችንን ሁሉ ከማስደሰት ባሻገር በተለይ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥትና የሃገር ውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች የጀመሩትን ወረራ አጠናክረው እንዲገፉበት አበረታቷቸዋል።

የሶማሊያ መንግሥት የመ ስፋፋት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል ኢትዮጵያን መውጋት የጀመረው ሰሜን ሶማሊያና ደቡብ ሶማሊያ በተናጠልና በተከታታይ ከእንግሊዝና ከኢጣሊያ ቅኝነት ነጻ ወጥተው እንደተዋሃዱ ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ ነው።

በወርሃ ታህሳስ 1953 ዓ.ም በዋርዴር አውራጃ በዳኖት ወረዳ በአንድ እግረኛ ብርጌድ ደረጃ የሚገመቱና ለወታደርነታቸው መለያ የሌላቸው ጨርቅ ለባሽ ጦሮችን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አስርጎ በማስገባት የኔ እናት የጦር ክፍል በነበረውና ነብሮ በመባል በሚታወቀው የዘጠነኛ እግረኛ ሻለቃ የጥበቃ ቀጠና ላይ የሰነዘረው ድንገተኛ ጥቃት የመስፋፋት ዓላማውን በኃይል ተግባራዊ የማድረግ ጅምር ነበር።

ሆኖም ከመስፋፋት ፍላጎታቸው አንፃር ወታደራዊ ፋይዳ ያስገኝልናል ብለው ሳይሆን እነሱ እንደሚሉት "የሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም ቅኝ የሆነው የኦጋዴን ክልል ሶማሊኛ ተናጋሪ ሕዝብ ነፃነቱን ለማግኘት የሚደርገው ትግል ነው" በማለት የመሬት ጥያቄያቸውን ዓለም አቀፍ ይዘት በመስጠት ከሶቭየት ሕብረት መንግሥትና ከአረብ ሊግ ድጋፍ ለመጠየቅ የሚረዳቸው የትጥቅና ፕሮፖጋንዳ ወይም ቅስቀሳ ነበር። ይህ ያልተጠናና በበቂ ወታደራዊ መረጃ ያልተደገፈ ፅብ የማጫር ውጊያ በተሠማራው አጥቂ የሶማሊያ መንግሥት ጦር ላይ ከፍ ያለ የሕይወትና የአካል ጉዳት ያስከተለ ስለነበር ከዚህ በኋላ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል እንዲህ ያለውን ጀብደኛ እርምጃ ከመውሰድ ለመቆጠብ ተገድዶ ነበር።

ከአንድ ዓመት በኋላ በ1954 እና በ1959 ዓ.ም አሁንም ለወታደራዊ ጠቀሜታ ሳይሆን የመሬት ጥያቄውን ዓለም ያውቅለት ዘንድ በተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ መድረኮች ላይ ከማቅረብ ባሻገር በትጥቅ ትግል ላይ ነን ለማለት ይመስላል ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ጋር የመጀመሪያውን የወታደራዊ ተራድኦ ውል ተዋውሎ ያገኘውን የጦር መሣሪያ በታጠቁ መደበኛ የጦር ክፍሎች ጠረፍ ጠባቂ ፖሊሶቻችንን በየጊዜው መተናኮል አዘወተረ።

በዚህ ሁኔታ የተጀመረው የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ በኃይል የመስፋፋት ጥረት ዕድገት አግኝቶ በሶማሊያና በሶቭየት ሕብረት መንግሥት መካከል ሁለተኛው የወታደራዊ ተራድኦ ውል ከተፈረመ በኋላ በተለይም በ1956ዓ.ም መጀመሪያ ልዩ ሥልጠና ያላቸውን ኮማንዶ ጦሮች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አስርጎ በማስገባት የኦጋዴንና የቦረናን ክልል የአውራጃና የወረዳ አስተዳዳሪዎች እያፈነ ከመውሰድና በጠረፍ ጠባቂ ፖሊሶቻችን ላይ አደጋ ከመጣል አልፎ ሁለቱን አገሮች በሚያዋስኑ የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገራት ማለትም በሐረርጌ፣ በባሌና በሲዳሞ ጠረፎች ላይ ለጥበቃ የሰፈረውን የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት በመዳፈር በመደበኛ ሠራዊቱ ቀደምትነት በርቀት በከባድ መሣሪያዎች መደብደብ ተጀመረ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሶማሊያ የዓለም እስላሞች ማህበርና የአረብ ሊግ አባል ሆነች።

የሶማሊያ መንግሥት በሞቃዲሾ የነበሩትን አሮጌ የኢጣሊያ ሥሪት የሬድዮ ጣቢያዎችን በማሻሻልና ተጨማሪ ሞገድ በመገንባት ለሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች በመንግሥታቸው ላይ እንዲያምፁና ብለውም እንዲገነጠሉ ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳ በተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች ቋንቋ ማሰራጨት ጀመረ።

የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያን የሚያክል ሃገር ሲከዳና እንደዚያ ሲያጣጥል የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ሶማሊያን በጦር ኃይል ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚም እየገነባት ነበር። በ1963 ዓ.ም በሶማሊያና በሶቭየት ሕብረት መንግሥት መካከል በተደረገው ሦስተኛው ወታደራዊ ውል መሠረት በዓይነትም በመጠንም እጅግ ከፍ ያሉ የጦር መሣሪያዎች ወደ ሶማሊያ በመግባታቸው የሶማሊያ ወታደራዊ መንግሥት እጅግ የተበተበትና ለወረራ ዝግጅት የጀመረበት ጊዜ ነበር። የኢትዮጵያን የጦር ኃይል አድክሞ ለሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት መንገድ የመጥረግና ሦስቱን ክፍለ አገራት ገንጥሎ ከሶማሊያ መንግሥት ግዛት ጋር የመቀላቀል ተልዕኮ ያለው የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ በሚባል ድርጅት የሚመራ የወንበዴ ሠራዊት አዘመተብን።

በዚህ ዓመት አከታትሎ ከመንግሥቱ መደበኛ ሠራዊትና ከምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ድርጀት ጋር እጅና ጓንት ሆነው ኢትዮጵያን የመገንጣጠል ተልዕኮ ያላቸው፣ ከኦሮሞ፣ ከአፋር፣ ከሲዳሞ ከአደሬ ወዘተ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች መካከል የተመለመሉ ጠባብ ብሔረተኛ ግለሰቦችን ያሰባሰቡ አምስት ድርጅቶች የሚመሩ ምንደኛ ገንጣዮችን ሊያሠማራብን ቻለ።

ከዚህ በኋላ በተከታታይ ዓመታት በሁለቱ አገሮች ድንበሮች ላይ በሶማሊያ ሠራዊት ፀብ አጫሪነት የተጀመሩ በተዋጊ አይሮፕላኖች በተለያዩ ከባድ መሣሪያዎችና በታንኮች የተደገፉ የእግረኛ ሠራዊት ውጊያዎች በተለያዩ ጊዜያቶችና ስፍራዎች በተለይም በየድ፣ በባሬ፣ በጎዶሬ፣ በዶሎ፣ በቶጎጫሌ፣ በኢነጉሀና በደበጉርያሌ ከሁለቱም ወገን በርካታ የሠራዊት አባሎች የተሰውባቸውና የተጎዳባቸው ውጊያዎች በሚካሄዱበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጀርባ በተደራጁና ከሶማሊያ ግዛት በመጡ ገንጣዮች በሕብረት የሚካሄዱት ጥቃቶች የኢትዮጵያን ምሥራቃዊና ደቡባዊ ክልል የጠረፍ አውራጃዎች ቀውጢ የውጊያ አውድማ አደረጓቸው።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ እኛንና ሶማሊያዎችን በሚያዋስኑ ክፍለ አገሮቻችን ፀጥታ በማስከበርና በድንበር ጥበቃ ተሰማርተው የነበሩ የኢትዮጵያ የጦር ክፍሎች በምሥራቅ ማለትም በዋናው የፍልሚያ ግምባር ሦስት እግረኛ ብርጌዶች ያሉት ሦስተኛው አንበሳ እግረኛ ክፍለ ጦርና በደቡብ የአንደኛው እግረኛ ክፍለጦር አካል የሆነው ባለጉች መለዮው አራተኛ እግረኛ ብርጌድ ብቻ ነበሩ።

ከዚህ በላይ በገለጥኩት አስጊ ወታደራዊ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግሥት ከጠቅላላ የምድር ጦር ተዋጊ ክፍሎች ወይም ከአራቱ እግረኛ ክፍለ ጦሮች 2ኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር በሰሜን ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር ብቻውን ሲታገል የቀሩትን አንደኛና አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ለሦስተኛው ክፍለጦርና ለአራተኛው ብርጌድ ማጠናከሪያ በሶማሊያ ግምባር ለማሰለፍ የተገደደበት ጊዜ ነበር።

ከዚህ በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል ፍልሚያ ጋብ ብሎ በአጋዴን፣ በባሌና በቦረና አንጻራዊ ሰላም የተገኘው የሰሜን ሶማሊያ ተወላጅ የሆነው ታዋቂው ፖለቲከኛ ኢብራሂም ኢጋል የሶማሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር በሆነበት ጊዜ ያቀረበው የሰላም ሀሳብ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ከፍጥጫም አልፈው በውጊያ ላይ የነበሩት የሁለቱ አገራት ሠራዊቶች ከነበሩበት ስፍራ በየበኩላቸው ወደ ኋላ 15ኪ/ሜትር ያህል ተራርቀው እንዲሰፍሩ በተደረገበት ውል መሠረትና ከዚያም ፕሬዝደንቱ ጄነራል ዚያድ ባሬ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ሊቀመንበር በሆነበት ጊዜ ነበር።

በሐረርጌ፣ በሲዳሞና በባሌ ክፍለ ሃገራት በተገኘው አንጻራዊ ሰላም ምክንያት 1ኛው የንጉሠ የክብር ዘብ ክፍለ ጦር አካል የሆኑት አምስት እግረኛ ሻለቆች ከጎዴ፣ ከአዋሬ፣ ከጅጅጋ፣ ከጉርሱምና ከቦረና ተነስተው ወደ መሃል ሃገር እንደተመለሱ የሰሜን ገንጣዮች፣ ጀብሃና ሻዕቢያ የኤርትራን ክፍለሃገር የአሥመራን ከተማ ጨምሮ ሌላው የውጊያ አውድማ ስለአደረጉት ከአንደኛውና ከሦስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦሮች ጦር እየተቀነሰ ወደ ሰሜን ለማሰማራት በተገደድንበት ጊዜ ነው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት የፈነዳው።

በአሜሪካ መንግሥት በእጅጉ ይተማመኑ የነበሩት ንጉሥ በዚያ ፈታኝና ወሳኝ በሆነ የሥልጣናቸው ማክተሚያ ጊዜ ዋሽንግተን በመሄድ የመከላከያ ርዳታ ለምነው ምንም ሳያገኙ አፍረው ከመመለሳቸው ሌላ ሶቭየቶች በሶማሊያ ሲጠናከሩ አሜሪካኖች ጥለዋቸው መሄዳቸውን ስላየን በድህረ አብዮት በእኛ በኩል ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የምንጠብቀው አንዳችም በጎ ነገር አልነበረም።

በአብዮታችን አፍላ ወቅት በአሜሪካ ሥልጣን ላይ የነበረው የጂሚ ካርተር መንግሥት የእኛን አቋም የተረዳ ብቻ ሳይሆን የአብዮታችንንም ሥርነቀል ባህሪ ተገንዝቧል። በመገንዘቡም፣ ፀረ-ሶቭየት፣ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሶማሊያ የሆኑ ሁለት አደገኛ የጥፋት እቅዶች አቀደ።

በአንደኛ ደረጃ የሶማሊያዎች ቅጥ ያጣ በኢትዮጵያ ላይ በኃይል የመስፋፋት ፍላጎትና እንዲሁም የውጊያ ዝግጅት በመጠቀም ኢትዮጵያዊያንና ሶማሊያዎችን አዋግቶ በቀላሉ የማይጠገን ቀውስ ውስጥ ከመክተት ባሻገር ለጋውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ አብዮት ቀልብሶ፣ አብዮታዊውን መንግሥት በመጣል የእነሱ ተገዥና አገልጋይ የሆነ አሻንጉሊት መንግሥት በኢትዮጵያ ማቋቋም ነበር።

እንባቢ ዛሬ የኢትዮጵያን ጠቅላላ ሁኔታ ለመመልከት እንደሚችለው በአብዮቱ አፍላ ዘመን ይህንን ማድረግ ቢሳነውም ከ17 ዓመታት በኋላ የሩሲያ ቀልባሾችም ስለተባበሩት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈፀመው በአብዮታችን ማግሥት አቅዶት የነበረውን የመጀመሪያ ፀረ-አብዮት፣ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሰላም እቅዱን ማለትም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ከታዳጊ አገሮች ሁሉ ለአሜሪካ መንግሥት በፍፁም ታዛዥነት የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥ የሆነውን አሻንጉሊት ወያኔን በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ማስቀመጥ ነው።

የሶማሊያ መንግሥት ለ15 ዓመታት በተዘጋጀበት ወረራ እንዲገፋበት አሜሪካ ታላቅ ግፊት ከማድረጉ ባሻገር ወረራው የተሳካ እንዲሆን የኢትዮጵያን የመከላከያ ገበና ዘክዝኮ የሚያሳይ ወታደራዊ የውጊያ መረጃ ለሶማሊያ መንግሥት አቅርቧል። በዚህ ሁኔታ ሶቭየቶች ሶማሊያን ለቀው ሲወጡ የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ያገኝ የነበረውን ማናቸውንም ወታደራዊ ቁሳቁሶች ከመተካት ባሻገር ለዘለቄታውም የሶማሊያ መንግሥት የሚያስፈልገውን የመከላከያ የኢኮኖሚ ድጋፍ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆኑን ገልጧል።

የሶማሊያን የመስፋፋት ፍላጎት ዝግጅት ለመጠቀም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ይህንን የመሰለ የጥፋት እቅድ ማቀዱ በእኛና በሶቭየቶች ላይ ታላቅ ችግርን ፈጥሯል። በቅድሚያ በአብዮቱ ማግስት በእኛ በኩል የነበሩትን ችግሮች ባስረዳ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ አብዮታዊው ደርግ በተለይ በቀውስ ባሕር ውስጥ እየተናወጠ በአሳርና መከራ ሃገርና አብዮት ለማዳን የምንቀዝፍ ነበርን ብል የችግራችንን ዓይነትና ባህሪ በትክክል ይገልጽ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

እዚህ ላይ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም እቅድ አስመልክቼ ከሶማሊያ የወረራ ዝግጅት አንፃር ብቻ የእኛ ችግር ከምንላቸው ወሳኙ፣ በዓለም እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የጦር መሣሪያዎች ታጥቆ፣ ለ15 ዓመታት ተደራጅቶና በጋራ ድንበራችን ላይ ተከማችቶ ወረራ ለመሰንዘር በተዘጋጀ ጠላታችን ፊት ቆመን ራሳችንን የምንከላከልበት ምንም ዓይነት መሣሪያ ያልነበረን መሆኑ ነው።

ሌላው ከፍተኛ ችግር የጊዜ እጥረት ነበር። መሣሪያ ብናገኝ እኳን አሜሪካኖች በሶማሊያ መንግሥት ላይ ከሚያደረጉት ግፊት አንፃር መሣሪያውን ታጥቀን ለውጊያ ለመዘጋጀት ያለን ጊዜ እጅግ በጣም የጠበበ መሆኑ ነው። የሶማሊያን ወረራ የመጀመሪያውን የሠራዊት ረድፍና ጎርፍ ለመከላከል ሳይሆን ከተከላከልን በኋላ ለመልሶ ማጥቃቱ ሶቭየቶች ያቀረቡልንን መሣሪያ በከፊል ኩባዊያን እንዲያንቀሳቅሱልን ለማድረግ የተገደድነው በጊዜ እጥረት ምክንያት ነበር።

የሶቭየት መንግሥትን በአፍሪካ ቀንድ የገጠመው እጅግ ውስብስብ ችግር የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ከልብ የመቀበሉና የመደገፉ ሁኔታ ስላለ በሶማሊያ ወረራ በጨቅላነቱ እንዳይቀለበስ ወረራውን ተቃውሞ እየተከላከለ ግን ከሶማሊያ መንግሥት ላለመቆራረጥና፣ ከሶማሊያ ለመውጣት ስለማይፈልግና ለዚህም ስላልተዘጋጀ ሶማሊያዎች እኛን ከድተህ ጠላቶቻችንን አስታጠቅህ በማለት ነገሩ እንዳይከር ሲያመነታ ለእኛ መሣሪያ የሚያቀርብልን መቼና እንዴት መሆኑን ለመረዳት ያለመቻላችን ሌላው ዋናውና ትልቁ ችግራችን ነበር።

ስለሆነም የሶቭየቶችን መሣሪያ ከመጠበቅ ፈንታ ሶማሊያ ብትወረን ራሳችንን የምንከላከልበት መሣሪያ ከዓለም የመሣሪያ ገበያዎች ፈልገን ለመግዛት ወሰንን። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከ20 ዓመት በላይ የሚያውቀውና ሲገለገልበት የኖረው የጦር መሣሪያ የሰሜን አሜሪካ የቴክኖሎጂ ውጤት ነው።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ሠራዊታችንን ለውጊያ ለማዘጋጀት ያለን ጊዜ እጅግ ጠባብ በመሆኑ የመሣሪያ ለውጥ በደራሽ ውሃ መካከል ቆሞ ፈረስ እንደመለወጥ ያህል ከብዶን ነበር። ስለሆነም የሚቻል ከሆነ ለመፈተን ብለን የመጀመሪያ የመሣሪያ ገበያ ምርጫችን ያደረግነው የሰሜን አሜሪካንን ገበያ ነበር።

እጅ በእጅ በሚደረግ ክፍያ አሜሪካኖች መሣሪያ እንዲሸጡልን በኢራንና በእሥራኤል መንግሥት አማላጅነት ጠይቀን የጂሚ ካርተር አስተዳደር ሊሸጥልን ፈቃደኛ መሆኑን ስለገለጠልን፣ በጥድፊያ የሚያስፈልጉንን የመሣሪያ ዓይነቶችና የመጠን ዝርዝር አቅርበን መሣሪያዎቹ ያወጣሉ ብለው አሜሪካውያኑ የጠየቁንን ገንዘብ በቅድሚያ ከፈልን።

በጣም ጥቂት የመጓጓዣ ሄሊኮፕተሮች፣ ራዳሮች፣ ፀረ-ታንክ መሣሪያዎችና 12 ርዕስ ውልብልብት መድፎች ከላኩልን በኋላ መላኩን አቆሙ። ከጦርነቱ በኋላ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮችና መንግሥታቸውን እየከዱ ወደኛ ከመጡ የሶማሊያ የጦር መኮንኖች እንደተረዳነው የአሜሪካን መንግሥት መሣሪያ ይሸጥልን ዘንድ ስንጠይቀው ለመሸጥ ፈቃደኛ መስሎ የታዬው የግብር ይውጣ ያህል እንጂ በዚያን ጊዜ እኛ ለመሣሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ አለን ብሎ አያምንም ነበር።

ገንዘብ የላቸውም ብሎ ከማሰብ ባሻገር በተግባር እንደታዬው ገንዘብ ቢኖረንም በእነሱ መሣሪያ የሶማሊያን ወረራ መክተን አገራችንንና አብዮታችንን በማዳን ሶማሊያን ማሳፈር፣ አሜሪካንንም ማሳፈር ከመሆኑ ሌላ እቅዳቸውንም ማክሸፍ ስለሆነ የገቡልንን ቃል ለውጠው መሣሪያቸውን መከልከል ብቻ ሳይሆን ከሌላ ገበያም እንዳንገዛ የቀረውን ገንዘብ ለአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት እዳ ማካካሻ አውለነዋል በማለት ነጠቁን።

## ክፍል ፯

# ሃገርንና አብዮትን የማዳን ጦርነት ዝግጅት

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

# የታጠቅ ጦር ሰፈር ምስረታ

በቅደምተከተል በተለያዩ ምዕራፎች የማቀርባቸው ወይም የምተርካቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን፣ ክብሩን አንድነቱንና ማህበራዊ አብዮቱን ከውጭ ወራሪዎች፤ ከውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች ለመከላከል ያደረገው የጦርነት መሰናዶዎች በሙሉ ማለት ይቻላል በንድፈሃሳብ ደረጃ የታቀዱት ከኤደን ወደ አዲስ አበባ በቀይ ባሕር ላይ እንበር በነበረበት ጊዜ ነው።

በመቶ ሺህ ካስፈለገም በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝባዊ ሠራዊት እናፈስበታለን፤ በሰሜን እየተከላከልን በምሥራቅ እናጠቃለን ወዘተ እያልኩ ከራሴ ጋር ስነጋገር ጎኔ ተቀምጦ የነበረው ጓድ ተስፋዬ ገብረኪዳን ጤንነቴን ስለተጠራጠር ሃዘንና ድንጋጤ በተመላ ቅይጥ ስሜትና ሥጋት ነበር የሚመለከተኝ። እኔ ግን ፍፁም ጤናማ ነበርኩ። በዚያ የአየር ላይ ጉዞ በሃሳብ ደረጃ ያውጠንጠንኳቸው ጉዳዮች ሁሉ አንድም ሳይቀሩ በምድር ላይ ተግባራዊ መሆናቸውን አንባቢ ወደፊት በሂደት አንብቦ ይረዳቸዋል።

ከኤደን ወደ አዲስ አበባ የተመለስነው መጋቢት 18 ቀን 1969 ዓ.ም ቅዳሜ ነበር። ከየመን ጓዶች ጋር በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስንወያይ ቆይተን አውሮፕላን ላይ የተሳፈርነው ከቀኑ ወደ ስምንት ሰዓት ገደማ ስለነበር አዲስ አበባ የገባነው ወደ አስር ሰዓት ገደማ ነው። መኖሪያ ቤቴ ከደረስኩ በኋላ እህል ውሃ ሳያስፈልገኝ ከአሥራ አንድ ሰዓት ገደማ የጀመርኩ ሌሊቱን በሙሉ ረጅምና ፍፁም ሠላም የሆነ እንቅልፍ ተኝቼ ነው እሁድ ማለዳ ተነስቼ ለሥራ የተዘጋጀሁት።

ከታሪኩና ከስሙ በስተቀር ሥፍራው የት እንደሆን የማላውቀውንና የሥጋ ሜዳ እየተባለ የሚጠራውን ቦታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳየኝ አባት እያለኝ እንደሌለኝ ደጃዝማች ከበደ ተሰማን የማላውቃቸው ሰዎች በወሬ አባት ስለአደረጉልኝ የኔ ወንድም እየተባለ የሚነግርለትና በዚያን ጊዜ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድኩማን መርጃ መምሪያ ኃላፊ ከመሆን ባሻገር በድህረ አብዮት በተለያዩ ታላላቅ ኃላፊነቶች ላይ የሠራና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው ጓድ ካሳ ከበደ ነው።

ወላጅና አሳዳጊ የሌላቸውን፤ በልመናና እጅግ በሚያሳዝን ጎስቋላ ሁኔታ ይኖሩ የነበሩ የጎዳና ሕፃናት ተሰባስበው የሚያድጉበትንና የሚማሩበትን ጊዜያዊ የሕፃናት መርጃ አምባ የሠራው፤ ከአዲስ አበባ ከተማ በግምት ከ25 እስከ 30 ኪ/ሜትር ርቀት በአምቦ መንገድ ላይ የሚገኝና ሥጋ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ላይ ነበር። ሥጋ ሜዳ የአካባቢው

ተፈጥሮና የመልክዓምድር አቀማመጥ አይቼን ሰቦት ነበር። በሥጋ ሜዳ በስተምዕራብ ወደ አዲስ አበባ ከተማ በሚያመራው አቅጣጫ ሁለት ትንንሽ ወንዞችና የገፈርሳ ግድብ ይገኛሉ።

በአፈ-ታሪክ ከብዙ ሰዎችና ከራሴም ቤተሰቦች ይህ ሜዳ የሥጋ ሜዳ የተባለበት ምክንያት ራስ ተፈሪ ከራስ ሚካኤል ጋር ለመዋጋት ሲሰናዱ የሸዋና የአካባቢውን ጦር ለዘመቻ የሰበሰቡትና ሠራዊቱ ወደ ወሎ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ባደረገው ቆይታ፣ እያሌ ፍሪዳ ወይም ሰንጋዎች በገፍ እየታረዱለት ለአሞራዎች እስኪተርፍ የተመገበበት ስፍራ በመሆኑ የሥጋ ሜዳ ተባለ ሲሉ ነገረውኛል።

ከተራ ወታደር አዳፍሬ አየለ፣ ከተራ ወታደር ተስፋዬ እንግዳ፣ ከተራ ወታደር ዮሐንስ አፈወርቅና ከሌሎች ስምንት ወጣት ወታደሮች ጋር በሁለት ላንድሮቨር ተሽከርካሪዎች ከጠዋቱ 3 ሰዓት ገደማ ወደ ስጋ ሜዳ ተጓዝን። ሥጋ ሜዳ እንደደረስን በሜዳው አራት ማዕዘን አቅጣጫዎች ጠለቅ ብዬ በመግባት የሜዳውን ዙሪያና ጠቅላላ አካባቢውን በዝርዝር ስቃኝ መልካ ምድሩ እኔ ለምፈልገው ጉዳይ በጣም ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ ደስ ብሎኝ ወደድኩት።

አካባቢውን በበለጠና በስፋት ዓይን እስከ ቻለ ድረስ ሊያመላክት የሚችልና ለአካባቢው ገዥ የሆነ አንድ ጉብታ ስላገኘሁ፣ በዚያ ጉብታ ጫፍ ላይ ወጥቼ በመቆም ግራ ቀኙን በአይኔ እየቃኘሁ፣ ይሄ የሠራዊት ማረፊያ ወይም የጦር ሰፈር፣ ይሄ የመሣሪያና የጥይት ማከማቻ ወይም ግምጃ ቤት፣ የምግብ ማደራጃ፣ የወዲያኛው የተኩስ መለማመጃ ወረዳ፣ ከዚያ ወዲያ የውጊያ ስልት መለማመጃ ወዘተ እያልኩ ከራሴ ጋር ስነጋገር በአጠገቤ የነበሩት አጃቢ ጓዶቼ በሚሰሙትና በሚያስተውሉት ነገር ግራ የተጋቡ ይመስላል እንደ እንግዳ በግ ትኩር ብለው ያስተውሉኝ ነበር። ከዚህ በፊት እዚህ ቦታ ከእኔ ጋር የመጣችሁ እነማን ናችሁ? ብዬ ስጠይቃቸው ጓድ ካሳ ከበደ ባስጎበኘኝ ጊዜ አብዛኛዎቹ አብረውኝ እንደነበሩ ገለፁልኝ። እንዲህማ ከሆነ የዚያን ሜዳ ስም ታውቃላችሁ ብዬ ስጠይቃቸው፣ ስጋ ሜዳ የሚባል መሆኑን ሲገልፁልኝ፣ ለምን ሥጋ ሜዳ እንደተባለ ግን አንዳቸውም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። እኔ ስለ ስጋ ሜዳ ታሪክ የሰማሁትን ያህል ካስረዳኋቸው በኋላ "ስጋ ሜዳ እንደገና ሌላ ታሪክ ይሰራባታል ወይም ታስተናግዳለች፣ ስሟም ከዛሬ ጀምሮ ታጠቅ ነው የሚባለው" ብያቸው በሄድንበት ሁኔታ ወደ ሰፈራችን ተመለስን።

ሰፈር እንደደረስን ጽሕፈት ቤት ገብቼ ለታጠቅ የጦር ሰፈር ግምባታና ከግምባታውም ጋር ለሚከናወኑ የተለያዩ ሥራዎች ከንዋኔ ሃላፊነት ወይም አግባብ ያላቸው ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች፣ የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የቴሌ ኮሚኒኬሽንና የኮንስትራክሽን ባለሙያ መሃንዲሶች በበነጋታው ማለትም ሰኞ ጠዋት በ4 ሰዓት ስጋ ሜዳ እንዲገኙ አሳሰብኩ። መጋቢት 20 ቀን 1969 ዓ.ም የተጠሩት ባለሥልጣኖችና የተለያዩ ባለሙያዎች በተገኙበት ሥጋ ሜዳን የታጠቅ ጦር ሰፈር ለማድረግ ያስፈልጋሉ ብዬ የምላቸውን ወይም መገንባት ያለባቸውን ልዩ ልዩ ተቋማት የሚቋቋሙበትን ክልሎች በምድሩ ላይ በእግር እየተዘዋወርን በዝርዝር ካሳየኋቸው በኋላ ሁላችንም ከስጋ ሜዳ ወደ እኔ ጽሕፈት ቤት ማለትም ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት በአንድ ላይ ተመለስን።

በታላቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ ባለው አነስተኛ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠን ጠላቶቿ ለኢትዮጵያ የደገሱላትን ጦርነት በማስረዳትና ራሳችንን ከዚህ ጥቃት ለመከላከል ያለን ጊዜ እጅግ በጣም አጭር በመሆኑ ሰው ሁሉ ሌሊትና ቀን እንዲሰራ ካሳሰብኩ በኋላ የሚሰራውን የሥራ ዝርዝር በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው አቀረብኩ።



“ከሁላችንም የሚጠበቀው የታጠቅ ጦር ሰፈር በአጣዳፊ ተገንብቶ ከ2 እስከ 3 ወር በሆነ ጊዜ ውስጥ ከሦስት መቶ ሺህ ያላነሰ ሕዝባዊ ሠራዊት ከመላው የኢትዮጵያ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል መልምለን ወደ ታጠቅ ማሰልጠኛ ማዕከል አንጉዘን ጠልለን፣ አልብሰን፣ መግበን፣ ጤንነታቸውን በሚገባ ተንከባክበን፣ አስታጥቀንና አደራጅተን የሚሰነዘርብንን ጥቃት ለመመከት መብቃት ነው።

ለዚህ አጣዳፊ ፍላጎታችን ተግባራዊነት የሚያስፈልገውን ሁሉ አቅዳችሁ፣ የሚያስፈልገንን የወጪና የፍጆት መጠን በሰው ኃይል፣ በገንዘብና በቁሳቁስ አይነትና መጠን አስልታችሁ እፊታችን ባለው አርብ ጠዋት ታቀርባላችሁ። ለጊዜው የሠራዊቱን መመገቢያ እቃዎች፣ መጠለያ ድንኳኖችና የጦር መሣሪያዎች በተመለከተ እናንተ ሳትቸገሩ ለኔ መተው ትችላላችሁ” የሚል መመሪያ ሰጡ። በዚህ ዕለት በኔ አስተያየት የሰጡት ትዕዛዝ እኔ በመጠንኩት የጊዜ ክልል ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል ብለው ሊያምኑ ቀርቶ መታሰቡም እንዳስደነቃቸው በብዙዎቹ ሰዎች የፊት ገፅታዎች ላይ በግልፅ ይነበብ ነበር።

ይህ የሆነበት ምክንያት ለመሥራት ያለመፈለግ ወይም ለሃገር ያለመቆርቆር ሳይሆን በእንዲህ ያለ ቀውጢ ወይም ቀውስ የተመላ ሁኔታ ውስጥ የመሥራት ልምድ ያለመኖር ነበር። ሆኖም ሁሉም የየሥራውን ድርሻ በየበኩሉ አይቶና ገምቶ፣ ከዚያም ከሌሎቹ ጋር ተቀናጅቶ ጉዳዩን በዝርዝር ከማየትና በእነሱ ግምትና ስሌት ይሆናል የሚሉትን



በታጠቅ የጦር ሠፈር ቦሩ በልምምድ ላይ

ሰርተው ከማቅረብ በፊት ከወዲሁ አሉታዊ አቋም መውሰድ አግባብ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ተቀባይነትም እንደሌለው ስለሚያውቁ ትዕዛዙን ተቀብለው ሄዱ።

ሁሉም የየበኩላቸውን ሰርተው በጋራም በመገናኘት በጥቂት ቀናት ውስጥ በጣም ግርድፍ የሆነ እቅድ ላይ የተመሠረተ ስሌት ሰረተው ከጊዜ አንፃር ግን የሚያስፈልገው ዓመት ባይሆን እንኳን በግድ በርካታ ወራቶችን የሚጠይቅ ነው ብለው መጡ።

ይህ ሊሆን እንደማይችል ከማስረዳት በላይ ወደ ጠብ ያመራ ክርክርና ሙግት በኋላ ማንም ወደደ ጠላ ሥራው መሰራት ስለነበረበት ተጀመረና በሚታዬው አስደሳች ውጤት ሁሉም ሰው፣ የማድረግ ፍላጎት ካለው የማይሰራው ነገር እንደሌለ በመረዳትና ከተግባር በመማር የታጠቅ ጦር ሰፈር ግንባታ ሥራ ተስፋ በሚሰጥ ሁኔታ ተያያዘ።

በሚያስተማምን ሁኔታና በተፈለገው ፍጥነት የታጠቅ ጦር ሰፈር ግንባታ መያያዙን ከተመለከትኩ በኋላ፤ የእናት አገራችን ድንበር በተስፋፊዎች መደፈሩን፣ የሃገር ውስጥ ገንጣይ፣ አስገንጣዮችና ሌሎችም ቦርቧሪዎች ከወራሪው የውጭ ጠላት ጋር ማበራቸውን፣ እነኚህና መላው የአካባቢው አድህሮት ኃይሎች በሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት አስተባባሪነት ለድንበር መጋፋት ብቻ ሳይሆን በህልውናችን ላይ ስለዘመቱ በአጣዳፊ ተንቀሳቅሰህ አገርህን፣ አብዮትህንና ህልውናህን አድን በማለት ሚያዚያ 4 ቀን 1969 ዓ.ም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእናት ሀገር ጥሪ አቀረብኩ።

ላደረግኩት የእናት ሀገር ጥሪ፣ ሚያዚያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር ከየቤቱ ንቅል ብሎ በመውጣት በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከየአቅራቢያው የገጠር መንደር ጀምሮ እስከ ክፍለ ሀገር ከተማዎች፣ አደባባዮችና ጎዳናዎች እየፎከረ፣ እያቅራራና እየሸለለ በመትመም አለን! አሰልፉን! በማለት መልስ ሰጠኝ።



ሠራዊቱ በታጠቅ የጦር ሠፈር በስልጠና ላይ

በዚህ ዕለት በአገሬ በኢትዮጵያ፣ በምወደውና በማከበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰማኝን ኩራትና መመካት ለመግለጥ ቃላቶች ያጥሩኛል። ሚያዝያ 7 ቀን 1969 ዓ.ም ጠዋት ወደ ታጠቅ የጦር ሰፈር በመሄድ የግንባታውን ሂደት ስመለከት አይኔን ለማመን ነው የተሳነኝ። አንድ ወረዳ ለመሆን ብዙ የማያንሳት ውቧና ሰፊዋ ሥጋ ሜዳ በጥሩ ቅየሳ የውስጥ መንገዶች ተጠርገው ኮረት ለብሰዋል፤ የኤሌትሪክና የውሃ ማደያ መስመሮች በሚገባና በብቃት ተዘረግተዋል፤ የአንድ መለስተኛ ሆስፒታል ህንፃ በመገባደድ ላይ ይገኛል።

ለጦር መሣሪያ ግምጃ ቤትነት፣ ለትጥቅና አልባሳት ግምጃ ቤትነት፣ ለእህል ግምጃ ቤትነት፣ ለማብሰያና ለመመገቢያ ወዘተ ቁሳቁስ ግምጃ ቤትነት፣ ለምግብ ማደራጃነት ወዘተ በቆርቆሮ የተሰሩ እጅግ ግዙፍ የሆኑ አዳራሾች የታጠቅን ሰፈር ያለማጋነን አንድ አነስተኛ ከተማ አስመስለዋታል። የቀረ ነገር ቢኖር የሠራዊቱ መጠለያ ብቻ ነው።

የምግብ ማዘጋጃውን ወይም ማደረጃውን በተመለከተ ለአንባቢ በጥቂቱ ተጨማሪ መግለጫ መስጠት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። የእንጀራ መጋገሪያውን ቤት ወይም ግዙፍ አዳራሽ ከማለት ይልቅ ያንድ ታላቅና ሰፊ ኢንዱስትሪ አንድ ወጥ ህንፃ ቢባል ነው የሚሻለው። በኢንዱስትሪው ህንፃ ውስጥ በአንድ ወገን በመቶ የሚቆጠሩ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ የሸክላ ምጣዶች በሰልፍ መደዳውን ተጥደዋል። በተቃራኒው የህንፃ ማዕዘን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ላይ ታላላቅ ወጥ የሚዘጋጅባቸው የብረት ድስቶች ተጥደዋል። በመግቢያ በር ትይዩ ባለው ሩቅ ሦስተኛው ረጅም የቤቱ ማዕዘን ግድግዳ ደግሞ የዳቦ መጋገሪያዎች በተርታ ተሰልፈዋል።

ይህን የገለፅኩት የምግብ ማደራጃ ኢንዱስትሪ የሚያገለግለው ለስልጠናው ጊዜ ስለሆን ለጦርነቱ ስንቅ ማደራጃ ኢንዱስትሪዎች ለጥቂት ጊዜ ግንባታቸው እንዲዘገይ



የታጠቅ የጦር ሠፈር አገልግሎቱን ሲጀምር ይህን ይመስል ነበር

ሆኗል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የቀረ ነገር ቢኖር ሠራዊቱ የሚጠለልባቸው ድንኳኖች፣ የመመገቢያ ቁሳቁሶችና አልባሳቶች ወዘተ ናቸው።

ለሠራዊቱ መጠለያ የሚሆኑትን ድንኳኖችና የመመገቢያ ቁሳቁሶች ለእኔ ተው ያልኩት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያመነታ እንደሚለግሰን በመተማመን ስለነበር ሕዝባዊ ሠራዊቱ የሚጠለልባቸውን ድንኳኖች፡ ምግቡን የሚመገብባቸውን ቁሳቁሶች ማለትም ሁለት ኩባያ፣ ሁለት ሳህን፣ ማንኪያና ሹካ፣ የጠረጴዛ ቢላ በየቤቱ ያለው ኢትዮጵያዊ አንዱን እንዲለግሰን ጠየቅሁ።

በመላ ኢትዮጵያ ያሉ ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ የተለያዩ መንግሥታዊና ግላዊ ተቋማት፣ እድሮችና ግለሰቦች ወዘተ ያሏቸውን ድንኳኖችና መመገቢያ ቁሳቁሶች በራሳቸው መጓጓዣ አጓጉዘው በማምጣት በታጠቅ ጦር ሰፈር ሜዳ ላይ ከሚያስፈልገው በላይ የተራራ ያህል ከመሩልን።

በመንግሥት በኩል ጥንድ የብርድ ልብስ፣ ጥንድ ካኪ ቱታ፣ አንድ የወታደር ቆዳ ቡት ጫማና የሸራ ጫማ ተዘጋጅቶ በታጠቅ ግምጃ ቤት ይገኛል። በዚህ የጦርነት መሰናዶ አልጋና ፍራሽ የማይታሰቡ ናቸው። ስለሆነም ከሁለቱ የብርድ ልብስ አንዱ የሚለበስ ሲሆን ሌላው ደግሞ የሚነጠፍ ነበር።

## ምዕራፍ ሃያ ስምንት

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሠራዊት አመሰራረት

ከመላው የአገራችን የአስተዳደር ጠገግ፣ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክፍለ አገሮች ከሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ብዛቱ አሥልተን ከ18 እስከ 40 ዓመት በሆነ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ጤናማና አካለ ሙሉ ወጣቶችና ጎልማሶች ሦስት መቶ ሺህ ወንዶ ዖታዎች ወደ ታጠቅ የጦር ሰፈር እንዲልኩልን ለየክፍለ ሃገሩ አስተዳዳር ኮታ ተምነን ሰጠን።

የምልመላ መስፈርቱ በየክልሉ ደርሶ ለሕዝቡ ሲነገር የተፈጠረው ችግር ፈቃደኛ ዘማች ማጣት ወይም የሰው ኃይል እጥረት ሳይሆን እንዝመት ባዩ ሕዝብ መብዛት ነበር። የዘማቹ እድሜ መጠን በ40 ዓመት ጣራ ብቻ የተወሰነው ለምንድ ነው? ከ40 ዓመት እድሜ በላይ የሆነ ሰው መዋጋት አይችልም ያለው ማነው? የሚሉና እኛስ እንዴት ተረሳን የሚሉት ሴት ፆታዎች ጥያቄ ነበር።

የፆታ እኩልነት በታወጀበት አብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ለአገራቸውና ለአብዮታቸው እንዳይዋጉ የተከለከሉት ለምንድ ነው? ይህንን የመሰለውን ውሳኔ እኛ ሴቶች የምንመለከተው ሴቶች እንዳይሞቱ ታዝኖላቸው ነው በማለት ሳይሆን ለወንዶች የተደረገ መድሎ አድርገን ነው በማለት አማረሩ። መንግሥት በበኩሉ አግባብ ነው ብሎ ያመነበትን መልስ ወይም ምክንያት ቢሰጥም ሴቱና ወንዶ አዛውንቱ ሊያዳምጡ አልፈለጉም።

በተሰጠው መስፈርት መሠረት የተመለመለው ምልምል ከየክልሉ ወደ አዲስ አበባ በየብስ ተሽከርካሪ መንቀሳቀስ ሲጀምር ከምልምሉ ጋር እየተቀላቀሉ ከሚያዝያ 21 እስከ 25 ድረስ ከየክልሉ የተላኩልን ምልምሎች ቁጥር ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ስለነበሩ ሳይመለመሉ በራሳቸው አነሳሽነት የመጡትን ወጣት ሴቶች በተጨማሪ ለመቀበል ስንገደድ የቀሩትን ወንዶ አዛውንት በመለመንና በማግባባት በመንግሥት ማጓጓዣ ከጥቂት የገንዘብ አበል ጋር ወደ የመጡበት መልሰን መላክ ነበረብን።

ከሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት የጦርነት ዝግጅት ጀምሮ ወረራውን እስከጀመረበት በወረራውም ሂደት የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት፣ ከሰሜን ገንጣይ አስገንጣዮችና ከአካባቢው ፀረ-ኢትዮጵያ አድሀሮት ኃይላት ጋር በአንድ የዘመቻ መምሪያ አዳራሽ ከዋሽንግተን የሚያስተባብረውና የሚመራው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ስለመሆኑ በተደጋጋሚ በብዙ አጋጣሚ ተገልጧል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነኚህ ፀረ-ሕዝቦች የተደገሰለትን ወረራ ለመከላከል እነሱ ባልጠበቁት ሁኔታ በዚያ አስገራሚ ፍጥነት ተንቀሳቅሶ ነፃ አውጭ ሕዝባዊ ሠራዊት ለማደራጀት ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ ነበር ኃይሉንና ትኩረቱን ለመበታተን ከሦስት ማለትም፣ ከሰሜን፣ ከምሥራቅና ከደቡብ ሌላ በተጨማሪ አራተኛ ግምባር በኤርትራ

ደቡብና በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ፣ ትግራይን፣ ጎንደርንና ወሎን ያካተተ አራተኛ ግምባር በመፍጠር ሰሜኑን የመገንጠል ሴራና የሶማሊያን ወረራ ስኬታማ ለማድረግ ሲሉ ወያኔን በተፋጠነ ሁኔታ አስታጥቀውና አደራጅተው ያሰማሩት።

ጀብሃ የአረቦች ፍጡር፣ ሻዕቢያ የአፄ ኃይለሥላሴ ናቸው። የወያኔ ፈጣሪ አባቱ ሻዕቢያ ቢሆንም አሳዳጊዎቹ የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ናቸው። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዋርሶን ስሪት መሣሪያ በሶማሊያ መንግሥት አቀባይነት ነበር ከተለየዩ የሶሻሊስት አገሮች እየገዛ ወያኔንን ያስታጠቀው።

በዚህ ጊዜ ነበር የሶማሊያ መሪዎችን መስታዎት ቤት ውስጥ እያኖሯቸው እሰው ቤት ላይ ድንጋይ መወርወር አያዋጣችሁም ብለን ያስጠነቀቅናቸው። ስለአልሰሙን ይሄው እስከ ዛሬ ድረስ የእጃቸውን እያገኙ ናቸው። ኤርትራን በማስገንጠል ዋና ምክንያት የሆኑት ሱዳኖችም እንደዚሁ። የአብዮታዊ መንግሥት ከፍተኛ የአመራር አካል አባል የሆኑ የደርግ አባሎች ብቻ ሳይሆኑ በ17ቱ ዓመታት ትግል እየጣሉ የወደቁት፣ ዛሬ ሃገር አልባ ሆነው የተሰደዱትና በወያኔ በረት ታጉረው የሚያሰቃዩት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን የኢትዮጵያን ሕዝባዊ ሠራዊት ሲያሰለጥኑ፣ ሲያደራጁና ሲያነቁ በነበሩበት ጊዜ፣ ሠራዊቱ የሚመገበውን እየተመገቡ፣ የሚጠጣውን እየጠጡ፣ የለበሰውን ቱታ ለብሰው፣ ከሠራዊቱ ጋር በአንድ ድንኳን ውስጥ አንድ የብርድ ልብስ እየተጋፈፉና መሬት ላይ እየተኙ ነበር ኢትዮጵያን ያዳኗት።

ለስልጠናው የተወሰነው ጊዜ ከ2 እስከ 3 ወር ብቻ በመሆኑ በዚህ በጣም አጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ ሠራዊቱን ለሚጠብቀው ውጊያ ያበቁታል ተብለው የታቀዱት የትምህርት አይነቶች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፣

1ኛ/ የኢትዮጵያን ሕዝብ የረጅም ዘመን የትግል ታሪክ በአጫጭሩና የፖለቲካ ትምህርት

2ኛ/ የስፖርት፣ የአካል ማጠንከሪያ፣ በተለያዩ ወቅቶችና የመሬት ገፅታዎች ላይ የእግር ጉዞ

3ኛ/ የእግር ሰልፍና አብዮታዊ መዝሙሮች

4ኛ/ የተለያዩ መሣሪያዎችን አጠቃቀም

5ኛ/ የተለያዩ የውጊያ ስልቶች ነበሩ።

ሕዝባዊ ሠራዊቱ የተውጣጣው ከመላው የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች ስለነበር፣ የሚሰጠው ትምህርት በእያንዳንዱ ምልምል ህሊና በሚገባ ይሠርፅ ዘንድ በአንድ ጊዜ በ15 የብሔረሰብ ቋንቋዎች ነበር በአስተርጓሚዎች አማካኝነት ይሰጥ የነበረው።

ሠራዊቱ በታጠቅ የጦር ሰፈር ከትቶ ስልጠናውን በጀመረባቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራቶች ለዒላማ ተኩስ የሚያገለግሉትን ያህል ከቻይና የመጣ መሣሪያ ብቻ ስለነበረ በየግምጃ ቤታችን ያለው በእነዚህ በተጠቀሱት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራቶች ሠራዊቱ በነፍስ ወከፍ የሚማርባቸውና የሚያነግባቸው መሣሪያ ለማደል ባለመቻላችን፣ የመሣሪያ ሰልፍና የውጊያ ስልት ይለማመድ የነበረው ሠራዊት ራሱ ከአካባቢው እየቆረጠ ባዘጋጀው መሣሪያ መሰል እንጨት ነበር።



ሠራዊቱ በታጠቅ የጦር ሠፈር በአንድነት ሲሰለጥን

የሕዝባዊ ሠራዊቱ በታጠቅ የጦር ሰፈር ስልጠና ልዩና ታሪካዊ የሚያደርገው የሠራዊቱ መጠን፣ የስልጠናው አይነት ወይም የትጥቁ ጥራት ብቻ ሳይሆን ለሠራዊቱ ይደረግ የነበረው የምግብ አደረጃጀትና አቅርቦት ጭምር ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ያለ ግዴታ በውዴታና በራሳቸው አነሳሽነት ሕይወታቸውን ለአገራቸውና ለአብዮታቸው የሚሰጡ እልፍ አዕላፍ ወንዴ ጀግኖች እንደነበሯት ሁሉ ሴቶችም ነበሯት። ሕዝባዊ ሠራዊቱን ለማደራጀት በተደረጉ ጥረቶች የእናቶቻችንና የእህቶቻችን አስተዋፆ እጥፍ ድርብ ነበር። ጀግና ወልዶ ለሃገር ከማበርከት ባሻገር፣ በፍልሚያው የመጀመሪያ ረድፍ መሰለፍ፣ በታጠቅ የጦር ሰፈር ለሠራዊቱ ባህላዊ የጦር ሜዳ ስንቅ መሰነቅ። በአዲስ አበባ ከተማ አጠቃላይ ሕዝባዊ ምክር ቤት አመራር አካላት በተለይም በጓድ አለሙ አበበ ማዕከልነት የከተማው ማህበራት አባላት የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ እናቶቻችንና እህቶቻችን ናቸው በፈረቃ በየእለቱ ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ ታጠቅ የጦር ሰፈር እየተመላለሱ ነው ሦስት መቶ ሺህ ሠራዊት እያበሰሉ የመገቡት።

ይህንን ለመሰለው የሃገር ኩራትና የታሪክ ቅርስ ለሆነው የሕዝብ አብዮታዊ ጥረት እንቅፋት የነበረው አንዱና ብቸኛው ችግር፣ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ እያለ የሚጠራው ድርጅት ነበር። ይህ ድርጅት ቀደም ብሎ የኢትዮጵያን ታሪካዊና አብዮታዊ የመሬት ለአራሹ አዋጅና እንዲሁም በእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ አማካኝነት ተግባራዊነቱን በመቃወም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመታገል የሞከረ መሆኑ ይታወቃል።

ኢትዮጵያን አዳኝ የሆነውን ነፃ አውጪ ሕዝባዊ ሠራዊት ማደራጀታችንን አምርሮ የተቃወመ ብቻ ሳይሆን፣ በእድገት በሕብረት ዘመቻ እንዳደረገው ሁሉ ለሕዝባዊ ሠራዊትነት በተመለመለው ምልምል ውስጥ ነፍሰ ገዳይ ጀሌዎችን አስርጎ ከሠራዊቱ ጋር ወደ ታጠቅ



በታጠቅ የጦር ሠፈር የሚሊሺያ ምረቃ ዝግጅት ላይ

የጦር ሰፈር በማስገባት በሠራዊቱ ውስጥ አፍራሽና በታች የሆነ መስሪ ወሬና ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨትና ሠራዊቱን በማሸበር ለማስኮብለል በከፍተኛ ደረጃ ተፈታትኖናል።

ሕዝብ ባወጣጣቸው መጠለያ ድንኳኖችና የመመገቢያ ቁሳቁሶች በመገልገልና እንዲሁም በመንግሥት ልዩ ልዩ አቅርቦት የሕዝባዊው ሠራዊት ሥልጠና ተሳክቶ ወደ መገባበዱ በተቃረበበት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወልና በግል በየቤቱ ለሠራዊቱ የጦር ሜዳ ባህላዊ ስንቅ በሚሰንቅበት፣ የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ እናትና እህቶቻችን በየቀኑ በሺህ ቁጥር የራሳቸውን ቤት ከውጭ ዘግተው የሠራዊቱን ምግብ በሚያደራጁበት ወቅት ነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ነኝ የሚለው ድርጅት፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሃገር አቀፍ የሆነ አጠቃላይ የሥራ መቆም አድማ ጥሪ ያደረገው።

"ኤርትራን ለመገንጠል የሚደረገው የትጥቅ ትግል፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከፊውዳሉ ገዥ መደብ ጋር የሚያካሂዱት ትግል አካል ስለሆነ መደገፍ አለበት" ከማለቱ ሌላ "የሶማሊያ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጭቁን ነው። ጭቁንን ጭቁን አይወጋውም" በማለት የእኔን የእናት ሃገር ጥሪና የሕዝባዊ ሠራዊቱን መደራጀት በመቃወም አምርሮ አወገዘ።

የሕዝባዊ ሠራዊት መደራጀት ደርግን በማጠናከር የአገዛዙን ዘመን ከማቆየት ወይም ከማርዘም ባለፈ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ፣ እንዲሁም ለአብዮቱ የሚያስገኘው ፋይዳ የለም የሚለው ኢሕአፓ ዲሞክራሲያ እያለ በሚያዘጋጀው ፀረ-አብዮት በራሪ ወረቀቱ ቅፅ 27፣ "ምርትና ትምህርት ከድል በኋላ" በማለት መላው የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ፣ በሱ አጠራር "ላብ አደር" እንዲሁም ከአፀደ ሕፃናት ጀምሮ እስከ አገሪቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ያሉ ተማሪና መምህራን የመማርና የማስተማር ሥራቸውን እንዲያቆሙ ጥሪ አደረገ።

የኢሕአፓ መሪዎች አልተገነዘቡትም እንጅ ድርጅታዊ ህልውናቸውና ፖለቲካዊ ሕይወታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲከስም ያደረጉት፣ እነሱ እንደሚሉት ደርግ፣

ወታደሩ፣ ወይም ባንዳ እያሉ የሚሰድቧቸው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ምሁራን ሳይሆኑ ራሳቸው ናቸው። በዚህ ጊዜ ነበር ሕዝቡ ከማን ድል በኋላ? ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ድል በኋላ? እያለ በመገረምና በመሳቅ አንቅሮ መትፋት ብቻ ሳይሆን "ሳያጠፉን እናጥፋቸው" በማለት ሕዝባዊ ክንዱን ከዳር እስከ ዳር ያነሳባቸው።

የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር የአመራር አካላትና ጠቅላላ አባላት፣ ኢሕአፓ ላቀረበው የሥራ ማቆም አድማ ለእንዴና ለመጨረሻ ዘላቂ መልስ ይሆነው ዘንድ፣ "እያመረትን እንዋጋለን! እየተዋጋን እናመርታለን!" የተሰኘውን ዝነኛ መፈክር ያነሱት። ተማሪው፣ መምህራንና ጠቅላላው የኢትዮጵያ ምሁራን ደግሞ "እየተማርን እንታገላለን፣ እየታገልን እንማራለን!" በማለት ነበር በመፈክር መልስ የሰጡት። በዚሁ ጊዜም ለኢሕአፓ መልስ ለመስጠት ሲል የኢትዮጵያ ሕዝብ "ነፃ አውጪው ሕዝባዊ ሠራዊታችን ይዘምታል፣ ያሸንፋልም። ኢትዮጵያ ቬትናምን እንጅ ቺሌን አትሆንም!" የሚልም መፈክር ማለት ጀመረ። በዚህ ጊዜ ነበር የኢሕአፓ መሪዎች ከሥርዓተ አልበኝነት ወደ ለየለት እብደትና ፀረ-ሕዝብነት ተግባር ያመሩትና የመላው ኢትዮጵያን የሠራተኛ፣ የገበሬዎች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ ባጠቃላይ የብዙሃኑንና የሙያ ማህበራትን፣ የገጠር ቀበሌ ገበሬና የከተማ ነዋሪ ማህበራትን መሪዎች፣ የትምህርት ቤቶችን ርዕሰ መምህራን፣ ሃገር ወዳድና አብዮታዊ ምሁራንን፣ የጦር መኮንኖችንና የደርግ አባሎችን በነቂስ እያደኑ መረሸን የጀመሩት።

በዚህም አልተገቱም። በዚሁ ጊዜ ውስጥ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሆኑ ሴቶች ላይ በማተኮር በየቀበሌው፣ በሚያሳዝንም በሚያስቅም ሁኔታ የሴቶች የኡኡታ ኮሚቴ በማስገደድ ለማቋቋም ሞክረው ስላልተሳካላቸው የነቁ ሴቶችን መረሸን የጀመሩት።

በዚህም አልረኩም፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ ታጠቅ የጦር ሰፈር እየተመላለሱ ሠራዊቱን የሚመግቡትን እናትና እህቶቻችንን "ለሕዝባዊ ሠራዊቱ ምግብ ማደራጀቱን ካላቆማችሁ ትረሸናላችሁ" በማለት ማሸበር ጀመሩ። የኢትዮጵያ የሴቶች ጀግኖች ሃገር ነች ለማለት የፈለኩት፣ በኢሕአፓ ነጭ ሽብርና ግድያ ሳይፈሩ ወይም ሳይበገሩ፣ በሚጓጓዙባቸው አውቶቡሶች ውስጥ ወደ ታጠቅ ጦር ሰፈር ለመሄድ ወይም ለመመለስ በከተማው ጎዳናዎች ሲያልፉና ሲያገድሙ፣

"ማን ይፈራል ሞት<br>ማን ይፈራል<br>ለእናት ሃገር ሲባል!"

የተሰኘውን ዝማሬ ፈጥረው በመዘመር፣ እንኳን ሥራቸውን ሊያቆሙ ቀርቶ መላውን የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ፀረ-ኢሕአፓ በማድረግ ኢሕአፓን ያጠፉ ዘንድ ለፀረ-ኢሕአፓ አመፅ አነሳሱት። ለሠራዊቱ ምግብ የሚያደራጁትን ሴቶች መግደል በጀመረበት ጊዜ ነው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ "አስታጥቁን አታስገድሉን" በማለት ሴት ወንዱ፣ ወጣትንና አዛውንቱ ከየቤታቸው ንቅል ብለው በመውጣትና ዱላ ይዘው በመምጣት በአብዮት አደባባይ የያዙትን ዱላ እየጣሉ የእንጨት ክምር የሰሩት።

ይህ ሁሉ ሲደረግ፣ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ የሚጠራው ድርጅት እንዲህ የሚያደርገው አባዜ ወይም ችግር የሚመነጨው፣ ከአጠቃላይ የፖለቲካ ባህል ድህነታችን ነው፣ ያለ መብሰልና ያለ መስከን ነው፣ አብዮትና ሥርዓት አልበኝነት ተምታቶበት ነው ወዘተ ከማለት አልፈን ፀረ-አንድነትና ፀረ-አብዮት ነው ወደሚለው ትርጉም በማምራት ኢሕአፓን በጠላትነት አልፈረጅነውም።



የአባት ጦር በታጠቅ የጦር ሠፈር ሰልፍ ላይ

ከሥርዓተ አልበኝነት ወደ አብዮተኝነት እንመልሰዋለን በሚል ተስፋ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የፖለቲካ ፕሮግራም በታወጀበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያ አብዮተኞች በፀረ-ፊውዳል፣ በፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና በፀረ-ኢምፔሪያሊዝም አቋምና መለስተኛ ፕሮግራም ግምባር ፈጥረን ለአገራችን ኢትዮጵያና ለሕዝቧ ማህበራዊ ፍትህና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንታገል ብለን አብዮታዊ ጥሪ ስናቀርብ ኢሕአፖ በግምባር ቀደምትነት የተጋበዘ ድርጅት ነው።

ጊዜያዊ ሕዝባዊ ማደራጃ ጽሕፈት ቤትንና የፖለቲካ ትምህርት ቤትን በአቋቋመው አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተጀመረው አብዮታዊ ጎዳና ላይ በመራመድ ወደ ሕዝባዊ ግቡ ይዘልቅ ዘንድ የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤቱን የሚመሩ አብዮታዊ ምሁራን ስንጠራ የኢሕአፖን የአመራር አካላትና አባላት በተለየ መልክ ጠቁመን በመጋበዝ ነው።

ጥሪውን ተቀብሎ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መልስ ሳይሰጥ በዘገየበትም ጊዜ በፀረ-አንድነትና በፀረ-አብዮት ጠላትነት ሳንፈርጀው በአብዮቱ ሰፈር ወይም በአብዮቱ ቅንፍ ውስጥ በማስቀመጥ በማርክሲስቶች ሕብረት ድርጅትና በእሱ መካከል ያለውን ትግል የመሣሪያ ትግል ማድረጉን ትቶ ወይም ከነጭ ሽብሩ ተገትቶ በሰላም፣ በፖለቲካና በርዕዮተ ዓለም ይታገለን ዘንድ ዳግም ጥሪ በማቅረብ የሁለት መስመር ትግል የሚል የውይይት ርዕስና መድረክ ፈጥረን ለውይይት ጋብዘነው ነበር። ኢሕአፖ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀ፣ የሚመጥንና የሚበቃ ድርጅት ሆኖ አልተገኘም።

ኢሕአፖ ያልነበረውንና የማይሆነውን ግምት ሰጥተን፣ ሲያደማንና ሲገለን እያቅማማን ራሳችንን ከማታለል ለመግታት የተገደድነውና አምስተኛ ረድፍ ነው ብለን ያመነው ወይም የፈረጅነው ሕዝባዊ ሠራዊቱ የሚመገበውን እህልና የሚጠጣውን ውሃ ለመመረዝ በተደጋጋሚ ሲሞክር እጅ ከፍንጅ ከተያዘበት ጊዜ በኋላ ነው።

## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

# ሕዝባዊ ሠራዊታችንን ለማስታጠቅ የተደረጉ ጥረቶች

ሕዝባዊ ሠራዊቱን በፖለቲካ የማንቃቱ፣ በስፖርትና በአካል ማጠንከሪያ አካሉንና መንፈሱን የመገምባቱ ፕሮግራም ተገባዶ ወደ መሣሪያ አጠቃቀምና የውጊያ ስልት ፕሮግራም ሲቃረብ ስልጠናውን በተመለከተ፣ የኢሕአፓን ነጭ ሽብር ከመከላከል በስተቀር ሥራው በተሳካና በሚያስተማምን ሁኔታ ይካሄድ ስለነበረ ከፊል ኃይላችንንና ትኩረታችንን ከሰው ኃይል መሰናዶ ወደ የጦር መሣሪያና ቁሳቁስ መሰናዶ በማዞር በታጠቅ የጦር ሰፈር ከተቋቋመው ግብረ ኃይል በተለየና በተጨማሪ ቀሪውን ሥራ የሚያካሂዱ አራት ኮሚቴዎችን ያቀፈና በቀደምት ሚኒስትራችን በጓድ ኃይሉ ይመኑ የሚመራ ግብረ ኃይል ስር የተቋቋሙትና በሚኒስትሮች የሚመሩት ኮሚቴዎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፣

1ኛ/ የመሣሪያ፣ ጥይቶችና የፈንጂዎች መሰናዶ ኮሚቴ

2ኛ/ የጠቅላላ የትጥቅና የአልባሳት መሰናዶ ኮሚቴ

3ኛ/ ነዳጅና ቅባቶች ጨምሮ የስንቃስንቅ መሰናዶ ኮሚቴ

4ኛ/ የህክምና መሣሪያዎችንና መድሀኒቶችን፣ የአየር የየብስና የባሕር መጓጓዣዎችንና ጥገናዎችን ጨምሮ ጠቅላላ የሎጀስቲክ መሰናዶ ኮሚቴዎች ነበሩ።

በኢትዮጵያ አንድነትና አብዮት ላይ የተደገሰውን የጦርነት ሴራ ለማስረዳት በአፍሪካ ቀንድ የሚኖሩ ሕዝቦች ባዕዳን ባዘጋጁላቸው ወጥመድ ውስጥ ሳይገቡ በመካከላቸው ያሉትን ቅራኔዎችና ችግሮች በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ ይሹ ዘንድ የሶሻሊስት መንግሥታትን የሽምግልና ርዳታ ስንጠይቅ እግረ መንገዳችንን ከሶቭየት ሕብረትና ከሌሎችም ከብዙዎቹ ጋር የትግል አንድነትና ሁለገብ የትብብር ውል መዋዋላችን ይታወሳል።

በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የሚያስገመግም የጦርነት ዳመና በመሆኑ የሰላሙ ጥረት ቢከሽፍ ያለው አንድና ብቸኛ ምርጫ ራሱን መከላከል መሆኑን እኛ ስለነገርናቸው ሳይሆን እያንዳንዱ ሶሻሊስት መንግሥት ስለ አፍሪካ ቀንድ ባላቸው መረጃ ችግራችንን ስለተረዱት በቃል ደረጃ የመከላከያ ድጋፍ እንሰጣችኋለን በማለት ተስፋ የሰጡን ብዙ ናቸው፤

እንባቢ ያስታውሳቸው ዘንድ እያንዳንዳቸውን በስም ብገልፃቸው፣ የሶቭየት ሕብረት፣ ሕዝባዊት ቻይና፣ ሕዝባዊት ኮሪያ፣ ምሥራቅ ጀርመን፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ቡልጋርያ፣ ሀንጋሪ፣ ሩማንያ፣ ዩጎዝላቭያ፣ ኩባና ደቡብ የመን ናቸው። አንዳንዱቹ በአይነትና በመጠን ለይተው

ይህንን ያህል እንሰጣችኋለን ሲሉን የቀሩት የሰላሙ ጥሪት ከሽፎ እናንተ ተጠቂ ብትሆኑ ከሰው ኃይል በስተቀር በማናቸውም ረገድ እንረዳችኋለን በማለት በደፈና አበረታተውናል።

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእናት ሃገር ጥሪ ሳቀርብ ብዙዎቹ በገቡልን ቃል መሠረት ይረዱናል የሚል ተስፋ ያደረግን ቢሆንም መቼ፣ ምን ዓይነትና በምን ያህል መጠን እንደሚረዱን በውል የተገነዘብነው ነገር ስላልነበረ የእነሱን ርዳታ ያለመጠበቅ በግዥ መሣሪያና ልዩ ልዩ ለውጊያ የሚያስፈልጉንን ቁሳቁሶች የመግዛት ዝግጅትና የሶማሊያን ከፍተኛ የመሣሪያ የበላይነት ለመመዘን የሚያስችለን ልዩ የውጊያ ስልትም አቅደን ነበር።

በዚህ ዕቅድ መሠረት ከማናቸውም ሃገር፣ ከምዕራብም ሆነ ከምሥራቅ ገበያ መሣሪያና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ወታደራዊ ቁሳቁሶች ሁሉ፣ ያቋቋምናቸው የተለያዩ የውጊያ መሰናዶ ኮሚቴዎቻችን እንደየተልዕኳቸው በየፊናቸው ከተለያዩ አገሮች ጋር፣ በዋጋ፣ በማቅረቢያ ጊዜ፣ በመሣሪያው ዓይነትና መጠን ወዘተ ድርድሮችን ያካሂዱ ነበር።

አፄ ኃይለሥላሴ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ብቸኛ ወዳጅ በማድረግና በመመካት ጦራቸውን በኮሪያ ጦርነት ጊዜ አዝምተው የችግሩ ተካፋይ ከመሆን ባሻገር በአገራችን በአሥመራ ከተማ ወታደራዊ መደብ በመስጠት፣ አረቦችን፣ ሶሻሊስት አገሮችንና ጠቅላላውን የዓለም ሰላም ወዳድና ዲሞክራቲክ ኃይሎችን ጠላትነት የገዙበት የሰሜን አሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተከበበበትና ከፍተኛ የጦርነት አደጋ ባንዣበበት ጊዜ ነው ኢትዮጵያን በመክዳት፣ ከወራሪው የሶማሊያ መንግሥትና ከውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች ጎን በመቆም የወታደራዊውን ተራድኦ ያቆመው እንጅ እኛ አንቀበልም ብለን አልነበረም። አሜሪካዊያን ያደረሱብን አደጋ የገንዘቡ መጠን ብቻ ሳይሆን ካለብን የጊዜ ችግር አንፃር ያልተጠበቀ ስለነበር በጣም ብናዝንም አልተደነቅንም። ምክንያቱም ከኢትዮጵያ አብራክ የወጡ ልጆቿ፣ ኋላ ቀርና ድሀ በመሆኗ እነሱ የፈለጉትን ሁሉ ስላልሰጠች ወይም ስላላሟላች ብቻ ከድተዋት ከፊሉ ከአሜሪካኖቹ ጋር ሲሰለፉባትና ሌሎች ከአረቦች ጋር ተሰልፈው ሲወጓት ከአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር ምን ይጠበቃል።

ቀደም ብለው በሰነድና በቃል ደረጃ ተስፋ ከሰጡን ሶሻሊስት አገሮች ፈጥነው ጥቂት መሣሪያዎችን የላኩልን፣ ሕዝባዊ ቻይናና ዩጎዝላቪያ ሲሆኑ ሌላው የሶማሊያ ወረራ ከመጀመሩ በፊት አርባ አምስት ሺህ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሶቪየት ሕብረት የተሰሩና በኋላ የተሰራውን አዲሱን የዋርሶ አውቶማቲክ ጠብመንጃ ጥይት የሚጎርሱ ባለ አገልግል መጋዘን አውቶማቲክ ጠብመንጃዎችን ከበቂ ጥይት ጋራ የላከችልን ሃገር ኩባ ናት። ይህንን አሮጌ መሣሪያ ስንፈትሸው ቃታውና መጋዘኑ ጥይቶችን የሚነክስ ሆኖ ስላገኘነው ለብዙ ጊዜ ሳንጠቀምበት በግምጃ ቤታችን ከቆየ በኋላ የተጠቀሙበት በእኛ የተረዱትና የጄነራል ዝያድ ባሬን መንግሥት የጣሉት የሶማሊያ ነፃ አውጪ ግምባሮች ናቸው።

1968 እና 1969 ዓ.ም ከፋሽስት ወረራ ወዲህ ከአብዮቱ ግኝቶች ወይም ድሎች በኋላ ባሉት ጊዜያቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ያዘነባቸውና የተሰቃየባቸው ዓመታት ሲሆኑ በተለይ 1969 እጅግ የከፋ ነበር።

በኤርትራ፣ ከምፅዋ የባሕር ኃይል ሰፈርና ከጥቂት የከተማው ክፍል፣ ከባሬንቱና ከአሥመራ ከተማ በስተቀር የተቀረው ምድር በሙሉ ደጋው በጀብሃ ቆላው በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር ስለነበሩና በክፍለ ሃገሩ ምንም አይነት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ስላልነበረ ከአርባ ሺህ በላይ ለነበሩ ወዝአደሮች ያለሥራ ደሞዝ እንከፍል ነበር።

ሕዝባዊ ሠራዊታችን በተዘጋጀለት የወታደራዊ ሥልጠና ፕሮግራም መሠረት የፖለቲካ ንቃትን፣ የስፖርትና የአካል ማጠንከሪያ የሠልፍና የእግርጉዞ ትምህርቱን ባገባደደበት ጊዜ



በታጠቅ ጦር ሠፈር ሰልጣኝ ሠራዊት የከፍት ቡድኖችን በቅርበት ሲመለከቱ

ከገዛናቸው የጦር መሣሪያዎች ውስጥ አብዛኛው ሃገር ውስጥ ገብተው ስለነበር በመጀመሪያው የውጊያው ምዕራፍና ለምሥራቁ ግምባር ውጊያ መቶ ሺህ እንዲሁም በመጀመሪያው ምዕራፍ በኤርትራ የሚታገለውን መደበኛ ሠራዊታችንን አጠንክሮ የመከላከል ውጊያ ለሚያደርገው ሃያ ሺህ ከዋናዎቹ የጦር ግንባሮች በኋላ ከአዲስ አበባ በጂቡቲ መንገድ እስከ ደወሌ፣ ከአዲስ አበባ እስከ አሰብ ወደብ ድረስ ያለውንና፣ ከአዲስ አበባ እስከ አሥመራ ያለውን ዋና የመገናኛ አውራ መንገዶች ጥበቃ ለሚሰማሩ ሰላሳ ሺህ በጠቅላላው ለሁለት መቶ ሺህ ሕዝባዊ ሠራዊት የመሣሪያ አጠቃቀምና የውጊያ ስልት ትምህርቱን ያጠናቀቀው የሚዋጋበትን አዲሱን ዘመናዊ መሣሪያ በነፍስ ወከፍና በቡድን ታጥቆ ነው።

የጦር ትምህርት በታጠቅ የጦር ሰፈር ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ሠራዊቱ ከወጣ በኋላ ትልቁን በጦር ሜዳ ጠላቱን ከመግጠሙ በፊት ለተወሰኑ ጊዜያቶች በተለያዩ የአየር ፀባዮችና የመሬት ገፅታዎች የተለያዩ የውጊያ ልምምዶችን እንዲያደርግና በተለይም ከሠራዊቱ ውስጥ ምናልባትም አብዛኛዎቹ አለማየት ብቻ ሳይሆን ከነወሬውም ሰምተውት የማያውቁትን የመድፎች ባራጅ ወይም ሰብስብ ተኩሶችና የአየር ድብደባዎችን የሚያስተዋውቃቸው ኘሮግራም ተዘጋጅቶላቸዋል። ከሥልጠና አኳያ በአስገዳጅ ምክንያት የሥልጠናው ጊዜ በጣም አጭር ቢሆንም አንድ ተዋጊ ሠራዊት ሊማራቸውና ሊያውቃቸው የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ የሆኑ ወታደራዊ ትምህርቶችን ሸፍኗል። ከዚህ የሚለየውንና የሚቀጥለውን ትልቁን ትምህርት የሚያገኘው በጦር ሜዳ ከተግባር ነው።

ከዚህ በተረፈ ያለምንም አስገዳጅ በራሱ ፈቃድና አነሳሽነት ከየቤቱ የመጣ ከመሆኑ ሌላ በሥልጣናው ወቅት ይደረግለት በነበረው የምግብ አቅርቦት፣ ይሰጠው በነበረው የጤና



ሠራዊታችን በአብዮት አደባባይ ሰልፍ ላይ

አገልግሎትና የፖለቲካ ንቃት ሌላ በየሳምንቱ በተለያዩ የአገሪቱ የኪነት ቡድኖች የተለያዩ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች ባህላዊ ጨዋታዎች፣ ሙዚቃዎችና ቲያትሮች የመሳሰሉት ትምህርት ሰጭና መዝናኛዎች ይቀርቡለት ነበር። አዝናኝና ትምህርት ሰጭ ከሆኑ ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ፊልሞች ጋር በዘመናዊ የውጊያ ፊልሞች አማካኝነትም ስለዘመናዊ ውጊያዎች ደህና ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል። በመጨረሻም ሠራዊቱን በለበሰው እጅግ ዘመናዊ የውጊያ ልብሶችና ትጥቆች፣ በታጠቀው ዘመናዊ መሣሪያና ጥራት ወታደራዊ ሞራሉና ለመዋጋት የነበረው ፈቃደኝነት ከፍተኛ ነበር።

## ምዕራፍ ሠላሳ

# የአብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አስተዳደር

በታጠቀው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጥራትና ብዛት ምክንያት ተብቶና ከኋላው ሆነው ለጥፋት በሚገፋፉት የስሜን አሜሪካን ኢምፔሪያሊስት መንግሥትና በአካባቢው አድሀሮት ኃይላት ተመክቶ የአገራችንን ምድር አንድ አምስተኛ አለኝታዬ ብሎ ለወረራ የመጣን ጠላት በሚገባ መክቶ ብሎም አሳፍሮና ረግጦ ለመመለስ መዘጋጀት የነበረብን፣ የረጅም ጊዜ ሥልጠና፣ ፅኑ የሃገር ፍቅርና ሕዝባዊ አቋም ያለው፣ ከጠላቱ በጣም የተሻለ ካልሆነም የተመጣጠነ ትጥቅ በታጠቀና በውጊያ ልምድ የበሰለ መደበኛ የጦር ኃይል በማዘጋጀት ነበር።

ጠላት ከ15 ዓመታት በላይ ለወረራ ተዘጋጅቶ፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አገሩን ከጥቃት ለመከላከል ያለመዘጋጀት ድክመት በመገንዘብ ብቻ ሳይሆን፣ አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በተቆጣና ትዕግሥቱ በተሟጠጠ ሕዝቧ አመፅ በመናወጥ ላይ መሆኗን በመመልከት፣ ኢትዮጵያን ለመውረር ከዚህ የተሻለ ጊዜና መልካም አጋጣሚ ዳግም አይገኝም ብሎ የመጣውን ጠላት ለመከላከል አብዮቱ ምንም ዓይነት ዝግጅት አልነበረውም።

ለዋናው ወራሪ ሠራዊት ሁኔታውን በማለሳለስና መንገድ ለመጥረግ ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ግዛት ሠርገው ወደ አገራችን የገቡት የደፈጣ ውጊያ ተዋጊዎች፣ ከውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች፣ የአሮጌው ሥርዓት ርዝራዥ ከሆኑት ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ፊውዳሎችና ከአምስተኛ ረድፎች ጋር በመቀጣቀጥ የተዳከመና የተመናመነ ብቻ ሳይሆን በብርቱ ፍልሚያ ላይ ያለ ጥቂት የቀድሞው መደበኛ ሠራዊት በስተቀር ሌላ ደጀን ተዋጊ አልነበረም።

የወደቀው መንግሥት የሶማሊያን ወረራ ለመከልከል ወይም ለሌላ ክፉ ጊዜ ብሎ በግምጃቤት ያስቀመጠው መሣሪያ አልነበረም። ይህንን በመሰለው ያልተመጣጠነ የኃይል አሠላለፍ የኛ ምርጫ ወይም የማድረግ ችሎታዎች ሁለት ብቻ ነበሩ።

1ኛ/ ባለን አጭር ጊዜ ውስጥ አጭር ሥልጠና የተሰጠው ግን በቁጥሩ ከጠላት የላቀ የሰው ኃይል ያለው መጠነ ሰፊ ሠራዊት በማሠለፍ የጠላትን የመሣሪያ የበላይነት ለመመዘን መቻል።

2ኛ/ የነፍስ ወከፍ ቀላል መሣሪያና መለስተኛ የቡድን መሣሪያዎችን ብቻ በታጠቀ መጠነ ሰፊ ሠራዊትና እንዲሁም በጠላት ዓይነትና ከአካባቢው የተፈጥሮ ባህሪያትና ለመሬቱ ገፅታ አግባብነት ባለው የውጊያ ሥልት ጠላትን እየተከላከልን ርምጃውን ገትተን በማቆም ጊዜ መግዛትና በፍልሚያው ሂደት የሠራዊታችንን የውጊያ ልምድ ከማጎልበት ጋር በዓይነትና በመጠን የጠላት ሠራዊት ከታጠቃቸው የተሻሉ መሣሪያዎችን በማካበት ተገትቶ የቆመውን ወራሪ ሠራዊት መደምሠስ ነበር።

በዚህ ዕቅድ መሠረት እንደሚታወቀው ሃገርንና አብዮትን ለማዳን እጅግ በተጣደፈ ሁኔታ ያዘጋጀነው የመከላከያ ሠራዊት፤ ከአሮጌው ሥርዓት የተረከብነው የቀድሞው ከጠላቶቹ ጋር ተናክሶ ያለ መደበኛ ሠራዊት፤ በአብዮቱ ማግሥት በአብዮታዊ ሥርዓትና መንፈስ ያሠለጠንናቸውና ያደራጀናቸው ነበልባል በሚባል ስም የሚጠሩ ጥሩ ሥልጠና የነበራቸው ሁለት እግረኛ ክፍለ ጦሮች በታጠቅ የጦር ሠፈር የሠለጠነው መጠነ ሰፊ ሕዝባዊ ሠራዊታችን ቅምር ወይም ቅይጥ ነበር። ይህን ማለት፣ በጣም ባጠረ ጊዜ ውስጥ በጠላት አስገዳጅነት የተዘጋጀው የመከላከያ ሠራዊታችን ሁለት ዓይነት ማለትም መደበኛ ሠራዊትና ሕዝባዊ ሠራዊት በመሆኑ አስተዳደሩም ሁለት ዓይነት ወይም ጉራማይሌ ሆነ።

በማንኛውም ሃገር እንደተለመደውና እንደሚደረገው የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት አባላት ከአገሪቱ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በፈቃዳቸው ወጣቶች እየተመለመሉ በተለያዩ ወታደራዊ ሞያዎች ከሠለጠኑ በኋላ በአገልግሎት ዘመናቸው በአገሪቱ አቅምና የመከላከያ ሠራዊት አስተዳደር ደንብ መሠረት በየዓመቱ በቋሚነት ወታደራዊ አልባሳት ሲታደላቸው፤ በየወሩ እንዲሁ በቋሚነት ደሞዝና ቀለብ ከመክፈል ሌላ ሌሎችም የተለያዩ መብቶችና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ስላሉ በአስተዳዳር ረገድ ከሕዝባዊ ሠራዊቱ የተለዩና በሰውኃይል መጠንም ከሕዝባዊ ሠራዊቱ በጣም አናሳ ናቸው።

መላው የሕዝባዊ ሠራዊቱ አባላት አብዮቱ ከጉልተኞችና ከፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች ገባርነት ጢሰኝነትና ሎሌነት በአጠቃላይ ከምዝበራና ከጭቆና ነፃ በማውጣትና በነፍስወከፍ የእርሻ መሬት በማደል በገበሬ ቀበሌ ማህበራት ካደራጃቸው የአገሪቱ አርሶ አደሮች መካከል የመጡ ሲሆኑ የቀሩት በመንግሥት አመራርና ቁጥጥር ሥር የሕዝብ ይዞታ ከሆኑት የተለያዩ የማምረቻ የማከፋፈያና የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ውስጥ ሲያገለግሉ ከነበሩ አምራች ወዛደሮች መካከል የተመለመሉ ናቸው።

እነዚህ የአገሪቱ አርሶ አደርና ወዝ አደር ቅምር የሆኑ የሕዝባዊ ሠራዊት አባላት በአስቸኳይ የእናት ሃገር ጥሪ በፈቃዳቸው አገራቸውንና አብዮታቸውን ለማዳን እንደመምጣታቸው በአስቸኳይ ሁኔታ አጭር ወታደራዊ ሥልጠና የተሰጣቸው፤ ከሚለብሱት ወታደራዊ የደንብ ልብስ፤ ከሚታጠቁት ትጥቅ፤ ከሚዋጉበት መሣሪያና ከሚመገቡት ቀለብ በስተቀር እንደ መደበኛው ሠራዊት ደሞዝ የሚከፈላቸው ስለአልሆኑ በመጠናቸውም በጊዜው ከነበረው መደበኛ ሠራዊት አምስት ጊዜ ያህል ይልቃሉ።

ጠላቶቻችን ከመበርከታቸው በላይ በአገሪቱ አራት ማዕዘናት፤ በመሃልና በዳር የሚወጉን በመሆናቸውና ጦርነቱ በመራዘሙ ውጊያው በኛ ፍላጎትና እቅድ መሠረት የሠመረ ሳይሆን በአገሪቱና በአብዮቱ ፀሮች ተፅእኖ የሚመራ በመሆኑ እቅዳችን ተቃወሰ እንጅ ለሕዝባዊ ሠራዊቱ የተደረገው አስቸኳይ የእናት ሃገር ጥሪ ለረጅም ጊዜ በፍልሚያው ላይ እንዲቆይ ሳይሆን የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከደመሰሰና የውስጥ ቦርቧሪዎችን አከርካሪ ከሰበረ ብኋላ ቀሪውን ሥራ ለመደበኛው ሠራዊት አስረክቦ ጠቅላላው ሕዝባዊ ሠራዊት ባይሆንም አብዛኛው ወደ ማምረት ተግባሩ እንዲመለስ ነበር።

ወደ ሠላማዊ ኑሯቸውና የማምረት ተግባራቸው የሚመለሱት ሁሉም አይደሉም ያልኩበት ምክንያት ሠራዊቱን የጠራነው ወሳኝ በሆነ አደጋ ላይ የወደቀችውን አገራችንንና አብዮቱን ከማዳን ባሻገር አብዮቱ ለሚገነባው አብዮታዊ መከላከያ ሠራዊት አስተማማኝነትና አብዮታዊ ጥራት ማህበራዊ መሠረት ይሆኑ ዘንድ በፊልሚያው ተፈትነው ነጥረው ከወጡት ውስጥ በአብዮታዊ መሥፈርት ዳግም እየመለመልን ፈቃደኞች የሆኑትን፤ በመደብና በርዕዮተ ዓለም ንቃታቸው የላቁትን መደበኛ ሠራዊት ለማድረግ እቅድ ስለነበረን ነው።

ለሕዝባዊ ሠራዊቱ ደሞዝ እንዳይከፈል የተደረገበት ምክንያት ተፈጥሮና ፀረ-ሕዝቦች ያደረሱት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ያነሰ ይመስል አገራችን ለጦርነት ሳትዘጋጅ ወይም ሳትሰናዳ ከውጭ የተሠነዘረብንን ጥቃት ለመከላከል በጠየቀን ከፍ ያለ የገንዘብ ወጭ ምክንያት የአቅም መወሰን ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የማምረቻ፤ የማከፋፈያና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች የዘመቱት ሠራተኞች ደሞዝ ሳይታገድ ወይም ሳይስተጓጎል በያንዳንዱ ዘማች ግለሰብ ፍላጎት መሠረት ለራሱ ወይም ለቤተሰብ እየተከፈለ ዘማቹ ያከናውን የነበረውን የማምረት የሥራ ድርሻ ባልዘመቱት ቀሪ ወዛደሮች በውል የፈረቃ ጥረት እንዲሸፈን በመንግሥት ስለተወሰነ ነበር።

ታላቁ አብዮታችን እያንዳንዱን የቀድሞ የጉልተኞች ገባሮች ጢሰኞችና ሎሌዎች ወዘተ የእርሻ መሬት ባለቤት ያደረጋቸው ብቻ ሳይሆን በገበሬ ቀበሌ ማህበር ያደራጃቸው ስለሆነ የዘማቾቹ አርሶ አደሮች መሬት ባልዘመቱት የገበሬ ቀበሌ ማህበር አባላት በወልና በፈረቃ እየታረስ እንደያንዳንዱ ዘማች ግለሰብ ፍላጎት የግብርናው አመታዊ ምርት በእህል ወይም በገንዘብ ለዘማቹ አርሶ አደር ቤተሰቦች እንዲከፍል በሃገር አቀፍ በመንግሥትና በአርሶ አደሩ አመራር መካከል ስምምነት ስለተደረገ ነበር።

የህበረተሰቦቻችን ዓይነትና የየአካባቢው አጠቃላይ ሁኔታና ማህበራዊ ንቃት፤ ከሁሉም በላይ ማይምነት፤ በአንዳንድ ክልሎች የአየር ንብረት ቀውስ በሚፈጥረው ችግርና ይህንን በመሰል ውስብስብ ሁኔታ ወስጥ አንድ ታላቅ ብሔራዊ ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የሥራ ልምድ፤ የመረጃ አሰባሰብና የዘገባ እውቀት ወይም ልምድ ያለመኖር፤ በየክልሉ ከላይ እስከታች በሥልጣን ላይ የነበሩት አስተዳዳሪዎችና በተለይም የገበሬው ሹማመንት የአመራር ድክመት፤ የጦርነቱ መራዘም፤ የዘማች አርሶ አደሮችን መሬት ማረሱና ቤተሰቦችንም የመንከባከቡ ጉዳይ እየተዳከመና እየተጓደለ መሄድ በተለይ በሰሜኑ ውጊያ በእያንዳንዱ አርሶ አደር ዘማች ግለሰብና በቤተሰቡ ላይ ብቻ ሳይሆን በአብዮቱ የአመራር አካላት ላይ ጭምር ከጦርነቱ ያላነሰ እጅግ ፈታኝ ችግር ፈጠረ።

ይህንን ችግር ለማቃለል ደረጃ በደረጃ እያሌ ርምጃዎች ከተወሰዱ በኋላ በመጨረሻ የመላውን ሕዝባዊ ሠራዊት ወርሃዊ የቀለብ አቅርቦት ከመደበኛው ሠራዊት ጋር ከማስተካከል ባሻገር ወርሀዊ ደመወዛቸውም ከመደበኛው ሠራዊት እኩል እንዲከፈላቸው ተደርጓል። በዚህ ምክንያት በአገሪቱ ላይ የሚደርሰውን የኢኮኖሚ ጣጣ ለጊዜው ወደጎን ልተውና ይህም ሆኖ የዘማቹን ቤተሰብ ችግር ሙሉበሙሉ ለማስወገድ አልተቻለም። ምክንያቱም፤ ከዚህ በላይ ለችግሩ አቢይ ምክንያት ናቸው ብዬ ከዘረዘርኳቸው ሌላ ከአርሶ አደሩ ሕብረተሰብ መካከል ነው ሕዝባዊ ሠራዊቱ የተመለመለው ብንልም በእድገት ደረጃቸው ኋላቀርነት በእርሻ ተግባር ለመኖር ያልበቁ የዘላኑ ሕብረተሰብ ክፍሎች፤ በአደን፤ ይህንንም በመሳሰሉና ምርታዊ ባልሆኑ ልዩ ልዩ እጅግ ኋላቀር የአኗኗር ዘይቤ የሚተዳደሩ ወገኖቻችን ቁጥር ቀላል አልነበረም።

አርሶ አደሩ ዘማች የተመለመለው ከመላው የአገሪቱ ገጠሬ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ከየጎጡና ከየመንደሩ በመሆኑ ይኖርባቸው የነበሩ ሥፍራዎች አብዛኛዎቹ የየብስ ወይም የአየር መጓጓዣዎች የማይደርሱባቸው፤ የፖስታና የስልክ አገልግሎት የሌላቸው በመሆናቸው ሕዝባዊ ሠራዊት ከደሞዝ ቆርጦ ወይም ከፍሎ ለቤተሰቡ እንዲሰጥለት ያዘዘውን ገንዘብ ለቤተሰቡ ማድረስ አልተቻለም።

ሃገርንና አብዮትን ለማዳን በምናደርገው የሞትሽረት ትግል የአገራችን ኋላቀርነት ያስከተለው እነዚህን ከዚህ በላይ የገለፅኳቸውን የአስተዳደር ችግሮች ወይም እክሎች

ብቻ ሳይሆን በሠራዊቱና በአገሪቱ የአመራር አካላት ሳይ ከፍ ያለ የመንፈስ ጭንቀትም አድርሷል።

በተለያዩ የጦር ግምባሮች ተሰልፈው ከተሰፋፊ የውጭ ወራሪዎች፣ ከውስጥ የአገሪቱና የአብዮቱ ፀሮች ጋር ሲፋለሙ ጥለው የወደቁትን ሕዝባዊ ጀግኖች እረፍት በአገራችን ባህልና ወግ መሠረት ለቤተሰቦቻቸው ማርዳትም አልተቻለም።

ሌላው ሁሉ ነገር ቢቀር ለአብዮታቸውና ለእናት አገራቸው ደህንነት ሲፋለሙ የወደቁ ሕዝባዊ ጀግኖችን እረፍት ለቤተሰቦቻቸው ማርዳት ያለመቻሉ ታሪካዊውን የእናት ሃገርጥሪ ላቀረብኩት ለኔ በግል ዘላለም የማይሽር የህሊና ቁስል ሰጥቶኛል።

በመንግሥት ይመሩ ከነበሩት የማምረቻ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች የዘመቱት የሠራተኛው መደብ አባላትን በተመለከት በደሞዝ አቅርቦት ረገድ የገጠመን ችግርና ከቤተሰብ የተሰማ ብሶት አልነበረም። ለማጠቃለል የሕዝባዊ ሠራዊቱን ብቻ ሳይሆን በመላው አብዮታዊ መከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ከፍልሚያው ሂደት የተከሰቱትን ባለብዙ ፈርጅ የአስተዳደር ውጥንቅጥ ችግሮች፣ ችግሮቹን ለማቃለል የተወሰዱትን ርምጃዎች ለጦርነቱ መራዘምና ብሎም ለሠራዊቱ ውድቀትና ለአብዮቱ መቀልበስ ያደረጉትን አስተዋጽኦ በሚከተሉት ቅፆች በዝርዝር ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

# የአብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የምንለው የአገሪቱን ሦስቱን የጦር ኃይሎች ማለትም የምድርጦሩን፣ የአየር ኃይሉንና የባሕር ኃይሉን በማጠቃለል ነው።

የኢትዮጵያ ከማለት ፋንታ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የምንልበት ምክንያት አገራችን በአብዮታዊ ንቅናቄ ላይ በመሆኗ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በቅድመ አብዮት በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥትና በሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት መካከል በነበረው የመከላከያ ተራድኦ ውል መሠረት ከ25 ዓመታት በላይ አገሪቱን ያገለግል የነበረው መከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት የሚመራው የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ወታደራዊ ሕብረት አገሮችና ምዕራብ ዘመም የሆኑ ታዳጊ አገሮች የሚጠቀሙበት የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት ዘይቤ ስለነበር ነው።

የምዕራብና የምዕራብ ዘመም ታዳጊ አገሮች ለማለት ያስፈለገበት ምክንያት በሶሻሊስቱ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት የሚመራው የዋርሶ ቃል ኪዳን አገሮች ሕብረት የመከላከያ ሠራዊትና በአዲሱ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ወደ ህብረተሰባዊ አብዮት በመሸጋገር ላይ ያሉ ታዳጊ አብዮታዊ አገሮች የሚጠቀሙበት የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት በአጠቃላይ ከወታደራዊ አደረጃጀት መርህ አኳያ ከፍያለ ወይም ሰፊ ልዩነት ባይኖርም ሁለቱ ወታደራዊ ሕብረት ጎራዎች ከቆሙለት ዓላማ፣ ከሚመሩበት ርዕዮተዓለም፣ ከሚተዳደሩበት ማህበራዊ ሥርዓትና ከሚያገለግሏቸው መደቦች አኳያ መሠረታዊ ልዩነቶች ስላሉ ነው።

የኢትዮጵያን ሕዝብ አቀርቅዞ ያኖረው ሥርዓተማህበር አራማጅ የሆኑትን የገዢው መደብ ቅሪቶችና ርዝራዦችን፣ የአብዮቱንና የአገሪቱን አንድነት የሚገዘግዙ ገንጣይና አስገንጣዮችንና አምስተኛ ረድፈኞችን በመመከት ብቻ ሳይሆን የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከአገራችን ረግጠን ለማስወጣት ያስችሉናል ያልናቸው ለኛ አጣዳፊ ችግሮች የሚበጁ ጊዜያዊና እንዲሁም በሂደት ዘላቂ፣ የሚሆኑትን ካለንበት የዕድገት ደረጃ አንፃር መጥነን መጠቀም ነበረብን።

የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት ስንልም የሠራዊቱን መንጋ በተለያዩ ደረጃዎችና በሥራ ክፍፍሎች ላይ የተመሠረተ የጦር አቋም መዋቅር ተዋረድ ወይንም የዕዝ ጠገግ በመፍጠርና ሠራዊቱን ወደሚጠብቀው የጦር ሜዳ ለማሠማራት ብቻ ሳይሆን በአደረጃጀቱ ዓይነትና እንዲሁም በትግሉ ሂደት አብዮቱ የራሱን አብዮታዊ ሠራዊት መፍጠር የሚችልበት የድርጊት ጅምርና የመከላከያ ሠራዊቱን ከአብዮታዊው ማህበራዊ ሥርዓት ጋር የማዋሃድ ዓላማ ያለው ጥረት ነበር።

በዚህ አደረጃጀትና ብሎም የትግል ሂደት አብዮቱ የራሱን ማለትም የወዝአደሩን ርዕዮተዓለም ማርክሲዝም ሌኒንዝምን የታጠቀ፤ በመካሄድ ላይ ባለው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መጠናቀቅ ለሶሻሊዝም ብሎም ለኮሚዩኒዝም ግምባታ የሚታገል፤ ለማህበራዊ ሥርዓቱ አስተማማኝ ማህበራዊ መሠረት በመሆን የፖለቲካ ሥርዓቱ አንዱና ቀንደኛው አካል የሆነ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት የመፍጠር ውጥን ነው። የመከላከያ ሠራዊቱ አደረጃጀት እናት አገራችንንና አብዮቱን ከጥቃት ለማዳን ብቻ ሳይሆን ከመከላከያ ግምባታ አንፃር የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችንን የፖለቲካ ፕሮግራም ተግባራዊ የማድረግ ተልዕኮ ያለው ክንውን ነው ለማለት ይቻላል።

በሌላ አነጋገር፤ አብዮታዊው መንግሥት የሚያራምደው ማህበራዊ ሥርዓት መመሪያ የሆኑትን የፖለቲካና ርዕዮተዓለም ትግል ከወታደራዊው አደረጃጀት ጋር በሚገባ ያካተተና የትጥቅ ትግሉን ከመደብ ትግሉ ጋር ያመላከተ አደረጃጀት ነው።

የአደረጃጀቱ አቢይ ትኩረት ሠራዊቱ የሥርዓተ ማህበሩ ጠንካራ ማህበራዊ መሠረትና የፖለቲካ ሥርዓቱ ቀንደኛ አካል እንዲሆን ከሆነ በመከላከያ ሠራዊቱና በፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት መካከል ለኖር ስለሚገባው ግንኙነት ለማወቅ በቅድሚያ የፖለቲካ ሥርዓቱን ምንነት መመልከት ያስፈልጋል።

የፖለቲካ ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው? ስለ ፖለቲካ ሥርዓት ምንነት ለመረዳት እንድንችል ይህ ፅንሰ ሃሳብ የሚገልጣቸውን ቃላት ማለትም ፖለቲካና እንዲሁም ሥርዓት የተባሉት ቃላቶች ምን ማለት እንደሆኑ በአጭሩ እንመልከት።

'ፖለቲካ' የተሰኘው ቃል ከግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን በአማርኛችን ትርጉሙ ሕዝብ ማለት ነው። ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ትርጉም አንፃር ሲታይ ግን ፖለቲካ የተሰኘው ቃል ከዚህ በላይ ከተሰጠው ትርጉም ወይንም ፅንሰ ሃሳብ ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው ቃል ነው። ፖለቲካ በመደቦች፤ በማህበራዊ ቡድኖችና እንዲሁም በሕዝቦች መካከል የሚኖር አንድ ዓይነት ግንኙነትን የሚያመለክት፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሥልጣን ጥያቄ ጋር በቅርቡ የተሳሰረ ትርጉም ያለው ቃል ነው።

በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ ፖለቲካ በአንድ መልኩ በሌኒን አገላለጽ የተጠቃለለ የኢኮኖሚ ነፀብራቅ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የተለያዩ የህብረተሰቡ መደቦች የየራሳቸውን መደባዊ ጥቅም ለማስከበር በሚቀርጿቸው የፖለቲካ ርዕዮተዓለም ይገለፃል። ከዚህም በላይ በመደቦች መካከል በሚካሄደው የመደብ ትግል ውስጥ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል። የዚህም መሠረታዊ መገለጫ የፖለቲካ ትግል ከፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ጋር በቅርቡ የተያያዘ ከፍተኛ የመደብ ትግል ቅርፅ መሆኑን ነው።

በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ይዘት የሚወሰነው መደቦች የየራሳቸውን የመደብ ጥቅም ለማስከበር በሚያዋቅሩትና ጥቅማቸው በሚንፀባርቅበት ርዕዮተዓለም ነው። ጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦች በሚገኙበት የህበረተሰብ እድገት ደረጃ ለምሳሌ በፊውዳሉ ሥርዓትና በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ገንኖ የሚታዬው ርዕዮተዓለም በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ ርዕዮተዓለም ነው።

በፖለቲካ ደግሞ የነዚሁ መደቦች ርዕዮተዓለም ተግባራዊ መገለጫ ሲሆን የገዢው መደብ ጥቅሞችን ለማስከበር የሚያዋቅራቸው የጥቅሙ ማስጠበቂያ ልዩ ልዩ ድርጅታዊ ተቋማት አማካይነት የራሱን መደባዊ ጥቅምና መላውን የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትቱ ሰፊ የሕዝብ ጥቅም አስመስሎ በሚያቀርባቸው የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ መሣሪያዎቹ አማካይነት የራሱን የመደብ ጥቅም ለማስፈፀም ይሞክራል።

ፖለቲካ የላዕላይ መዋቅር አካል እንደመሆኑ የሚወሰነው በተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት ላይ መሆኑ ቢታወቅም በሕብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የፖለቲካ ግንኙነቶች ይዘት ከኢኮኖሚው መሠረት በተጨማሪ በተለያዩ የህብረተሰቡ ቡድኖች፣ በግለሰቦች ጥቅምና እንዲሁም በየአገሩ ታሪክ፣ ባህልና ወግ ሊወሰን የሚችል መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ፖለቲካ በአንድ መልኩ በአንድ መንግሥት የፖለቲካ ዓላማ፣ ተግባርና፣ ከሌሎችም የማህበራዊ ሥርዓቱ አባላት ጋር በሚኖረው ግንኙነት ይወሰናል።

ከዚህ በላይ የፖለቲካን ምንነትና መሠረታዊ ትርጉም ባጭሩ ለመቃኘት ተሞክሯል። ዋናው ሃሳባችን የፖለቲካ ሥርዓትን ምንነት ለመገንዘብ ስለሆነ ይሄው ፅንሰ ሃሳብ የሚገለጥበትን ሁለተኛውን ቃል ማለት "ሥርዓት" የተሰኘውን ቃል ምንነት በአጭሩ እንመልከት።

'ሥርዓት' የተሰኘው ቃል በቀን ተቀን አጠቃቀሙ ለተመለከተው፣ ሕግ፣ ደንብና ከዚህም በማለፍ ሥነ የተባለውን ቃል ከኋላው በማከል ሥነ ሥርዓት የሚል ትርጉም መስጠት ይቻላል። አሁንም በአብዮታዊያን አመለካከት ሥርዓት የተሰኘው ቃል ከቃሉ ተራ አጠቃቀም የራቀና የላቀ ሰፊ ጽንሰሃሳብን ያዘል ቃል ነው። በዙሪያችን የሚገኙ በአጠቃላይም በዓለም ዙሪያ ያሉ ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ክስተቶች ሁሉ የተበታተኑና ጨርሶ የማይገናኙ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተወሰኑ የአደረጃጀት ቅርፅ ይዘው የሚገኙ ናቸው። የሰው ልጆች ሁሉ በተወሰነ ቤተሰብ፣ ማሕበረሰብ፣ ብሔረሰብና ብሔር ወይንም መደብ ወይንም የዜግነት ክፍል ተደራጅተው ይገኛሉ።

እንስሳትም የተወሰኑ የዘር ዓይነቶች ወይንም ደረጃ ይዘው የሚገኙ ናቸው። ከፊሎቹ ይበራሉ፣ ከፊሎቹ ይራመዳሉ፣ ሌሎቹ ይድሃሉ ወይንም ይሳባሉ፤ የተቀሩት በውሀ ውስጥ የሚኖሩት ይዋኛሉ። ሁሉም በተፈጥሮ ሕግ የተወሰነና የተቀናጀ የሥነ ሕይወታዊ አደረጃጀትና አከፋፈል አላቸው።

ሁሉም የተዋሃደው የሁለንተናዊው ዓለም ሥርዓት አካላት ናቸው። በዓለማችን ዙሪያ ማናቸውም ተፈጥሮአዊ ወይንም ማህበራዊ ክስተት በተፈጥሮ ሕግ አንዱ ከሌላው ፍፁም በሆነ መልክ ተነጣጥሎ አይኖርም ወይንም አይገኝም።

ተፈጥሯዊዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ሰው ሠራሽ ወይንም በሰዎች ፈጠራ ከተገኙ ቴክኖሎጂዎች መካከል፣ ለምሳሌ፣ የየብስ ተሽከርካሪዎችን በአየር ላይ የሚበሩ አውሮፕላኖችንና ባሕር የሚቀዝፉ ጀልባዎችን ወይም መርከቦችን ብቻ ብንወስድ እነዚህ የሚንቀሳቀሱበትን መንኮራኩር ወይንም ሞተር ብንመለከት እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉና የተዋሃዱ አካላት ያላቸው ሥርዓት ናቸው ለማለት ይቻላል። እያንዳንዱ መንኮራኩር የተሠራበት ዓላማና እንቅስቃሴው የሚወሰነው በመንኮራኩሩ አካላት መካከል ባለው ጤናማ ግንኙነትና ውህደት ነው። አንዱ መንኮራኩር ወይንም ሞተር ከውስጡ አንድ ተንቀሳቃሽ ወይንም አንቀሳቃሽ አካል ቢጎድለው ወይንም ብልሽት ቢገጥመው የየብሱ ተሽከርካሪ፣ የአውሮፕላኑ ወይንም የመርከቡ እንቅስቃሴ ሊታወክ፣ ሊገታና ብሎም ጨርሶ ሊቆም ይችላል። የአንድ ሥርዓት መሠረታዊ ትርጉም ከዚህ ምሳሌ ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ነው። ማናቸውም ሥርዓት የተፈጥሮ፣ የሕብረተሰብ የሰው ሰራሽ በአንድ ወጥ መንገድ የተደራጀና የተዋሃደ የነባራዊው ዓለም አካል ነው።

ለምሳሌ ስለምንኖርባት መሬት ተፈጥሮ፣ ባሕርይና እንቅስቃሴ ብናስብ በአንድ በኩል ሌሎች ፕላኔቶችና ከዋክብት ጨረቃን ጨምሮ የሚገኙበት ምሕዋር (ሶላር ሲስተም) አካል ስትሆን በኛ ምሕዋር ውስጥ ካሉት ሌሎች ፕላኔቶች አንዷ ናት። ሌሎችንም አያሌ ሳይንሳዊ

ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። በአማርኛችን 'ሥርዓት' የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ ቋንቋ 'ሲስተም' ለሚለው ቃል የተሰጠ ትርጉም ነው። ሥርዓት ማለት አንድ ውስጣዊ ድርጅት ያለውና አካላቱ በጥብቅ የተሳሠሩና በአንድነት ተጠቃልለው የሚንቀሳቀሱ፣ ከውጭ አካላት ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያ በጥብቅ ተሳሥረው የሚገኙ አካላትን ያዘለ ማለት ነው። ማናቸውም ዓይነት ሥርዓት የራሱ መዋቅር አለው ይህም በሥርዓቱ አካላት መካከል የሚኖረውን የግንኙነት ዓይነት ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ ጥንቅር ተግባሮችና ባህሪያትም ይወሰናል። በሥርዓቱ ላይ የሚካሄደው ማናቸውም ዓይነት መዋቅራዊ ለውጥ በሥርዓቱ መሠረታዊ ባህሪይ ላይ ለውጥ ማስከተሉ የማይቀር ነው።

ከዚህ ሌላ የማናቸውም ሥርዓት መለያ ባህሪይ የሥርዓቱ ጥንቅር ነው። ይህም ማለት ሥርዓቱን የሚያዋቅሩት አካላት ምንነት ነው። ለማጠቃለል በአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ወደ ሕብረተሰባዊ አብዮት ሽግግር ላይ ባሉ አገሮችና በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ በአጠቃላይ የሥርዓቱ ማህበራዊ ኃይሎች ወይንም ጥንቅሮችና የፖለቲካ ሥርዓቱ አካሎች የምንላቸው ፓርቲ፣ መንግሥትና ሰፊው ሕዝብ በመደብ፣ በሞያ፣ በፆታና በእድሜ ክልል በተደራጁባቸው ድርጅቶች ወይንም ማህበራት አማካይነት በሥርዓቱ ውስጥ ሠፊና ወሳኝ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን የሥልጣን ምንጭነት፣ የሕዝቡን ሥልጣንና የበላይነት የሚገለጥበት ሁኔታ ነው። ከዚህ መሠረተ ሃሳብ በመነሳት ላለንበት ርዕስ ማለትም ከመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት አኳያ ማተኮር ያለብን በፖለቲካ ፓርቲና በመንግሥት ምንነት ላይ ነው።

አብዮታዊ ፓርቲ በተለይም ማርክሲስት ሌኒንስት ፓርቲ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ አብዮታዊ ወይም የሠራተኛ ፓርቲ ከሌሎች የቡርዧዊ ፓርቲዎች የሚለየው የትግል መሣሪያውና መመሪያው የወዛደሩ ርዕዮተዓለም 'ማርክሲዝም ሌኒኒዝም' በመሆኑ ነው።

የሠራተኛው መደብና በአጠቃላይም የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ማህበራዊ እድገት የሠፈነበትን፣ የሰው በሰው መበዝበዝ ሥርዓት የሚያከትምበትን የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስት ሕብረተሰብ ለመገንባት በሚካሄደው የመደብ ትግል የሠራተኛውን፣ የገበሬውን መደቦችና የተቀሩትንም ጠቅላላ ሠርቶ አደር የኅብረተሰቡ ክፍሎችን የሚያነቃ የሚያደራጅ፣ የሚቀሰቅስና የሚያንቀሳቅስ አዝማች፣ የሠራተኛው መደብ ግምባር ቀደም ድርጅት ማለት ነው።

የቡርዧው የፖለቲካ ፓርቲዎችና መንግሥታቱ የመደብ ሕብረተሰብን ህልውናና በመደቦች መካከል ያለውን የቅራኔ ሀቅ ለመሸፈን የሚቻላቸው መስሏቸው መደቦች ስሌለሉ የመደብ ቅራኔም የለም በማለት ይሸፍጣሉ። የራሳቸውን መደብ ጥቅም ብቻ እያስከበሩና መላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ያለርህራሄ እየመዘበሩ ግን መደብ የማይመርጡ፣ ለአንድም መደብ እንደማይወግኑና የጠቅላላውን ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚያስጠብቁ፣ ፓርቲዎቻቸውና መንግሥታቶቻቸው ከሁሉም ሕብረተሰብ ጋር የተዋሃዱና ፍፁም ዲሞክራሲን እንደሚያራምዱ መስለው ኃይለኛ በሆኑ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎቻቸው ሕዝብን ያደናቁራሉ ያወናብዳሉ።

መሬት የግል ይዞታ በሆነበት፣ በምድር ላይና በከርሰ ምድር ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሃብቶችና ማዕድናት፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችና የንግድ ተቋሞች፣ ባንኮችና መላው የገንዘብ ድርጅቶች፣ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋሞች፣ ሆስፒታሎችና ሆቴሎችን ወዘተ የመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች በሙሉ በጥቂት ከበርቴ ግለሰቦች እጅ በሆኑበት ጭቆናና ብዝበዛ በሠፈነበት የመዳብ ሕብረተሰብ ውስጥ ፍፁም ዲሞክራሲ አለ ማለት ሃፍረተቢስነትና ገደብ አልባ

አጭበርባሪነት ነው። በካፒታሊስት ቀርቶ በሶሻሊስት ሥርዓትም ፍፁም ዲሞክራሲ የለም። ፍፁም ዲሞክራሲ የሚኖረው መደብ አልባ በሆነው በኮሚዩኒዝም ብቻ ነው። ህብረተሰባዊ ሥርዓት ፍትህና ሕዝባዊ ዲሞክራሲ የሰፈነበት ሥርዓት ነው የሚባልበት ምክንያት መሬትና ጠቅላላው ኢኮኖሚ ማህበራዊ ወይንም የሕዝብ ይዞታ በመሆኑ ነው።

ለእነሱ ጭቆናና ምዝበራ ባለመጋለጣቸውና ባለመመቻቸታቸው ምክንያት በህብረተሰባዊ ሥርዓተ ማህበር የሚመሩ ሕዝቦችና አገሮች በመራራ አብዮታዊ የመደብ ትግል የተቀዳጁትን ሕዝባዊ ዲሞክራሲና የሕዝብ ሕጋዊ የበላይነት አምባገነንነት ነው በማለት ማውገዝ ብቻ ሣይሆን ለማህበራዊው ሥርዓት ውድቀትና ብሎም ሞት የተቻላቸውን ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ተግባር ከማከናወን ባሻገር ጦርነት ያውጃሉ።

ከዚህ አንፃር አብዮታዊያን በተለይም ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲዎች የመደብ ሕብረተሰብን አመጣጥ ወይም አፈጣጠር፣ እድገት፣ የመደቦችና የኃይል አሠላለፍ፣ በተፃራሪ መደቦች መካከል ያለውን ቅራኔ፣ የቡርዧውን አድሐሪ ሥርዓትና የብዝበዛ ሥልት ፍርጥርጥ አድርገው ያጋልጣሉ። ለማጠቃለል፣ ማርክሲስት ሌኒኒስት የፖለቲካ ፓርቲ ማለት የማሕበራዊው ሥርዓት መሪ፣ የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት እምብርትና ዋና ማዕከል ማለት ነው።

በአንድ የፖለቲካ ሥርዓትነት ከተዋቀሩ የፖለቲካው ሥርዓት አካላት ሌላው በሥርዓተማህበሩ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ግዙፍ አካል "መንግሥት" ነው። የፖለቲካ ሥርዓት አመጣጥ ከሕብረተሰብ ፖለቲካ አደረጃጀት ጋራ የተያያዘ እንደመሆኑ መጠን መንግሥት በሕብረተሰብ እድገት ተከታታይ ታሪክ ውስጥ ከመደቦች መፈጠርና ከመደቦች ጥቅም ማስከበሪያ ማህበራዊ ተቋሞች መከሰት ጋር ተያይዞ መታዬት ያለበት ነው።

የመደቦች መከሰትና የመደብ ትግል በተወሰነ የሕብረተሰብ እድገት ደረጃ ላይ መታዬት በሕብረተሰብ ማህበራዊ አደረጃጀትና አወቃቀር ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። የህብረተሰብ ማህበራዊ ግንኙነት ዓይነቶች ለምሳሌ ፖለቲካዊ፣ ሕጋዊ ርዕዮተ ዓለማዊ ሆነው ሊከሰቱ ችለዋል። በሕብረተሰብ የማህበራዊ ኑሮ እድገትም ውስጥ ለፖለቲካና ለኢካኖሚ ጥቅም ማስከበሪያ አዳዲስ ማህበራዊ ተቋሞች ተከሰቱ። ከእነዚህ ማህበራዊ ተቋሞች መካከል የዋነኛነትን ስፍራ ይዞ የሚገኘው "መንግሥት" የምንለው ተቋም ነው። መንግሥትም በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የተከሰተ በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ማስከበሪያ መሣሪያ ነው።

በሕብረተሰብ አደረጃጀት እድገት ከተከሰቱ ማህበራዊ ተቋማት ወይም የፖለቲካ ሥርዓት አካላት ሁሉ መንግሥት ቀዳሚና እንደ ሰው ልጅ ታሪክ ጥንታዊ ነው። ጥንታዊ በመሆኑ የጥንታዊው መንግሥት ህልውና የጀመረው በጥንታዊው ሕብረተሰብ ውስጥ መደቦች ማቆጥቆጥ ሲጀምሩ በተመሰረቱ የተበታተኑ ትናንሽ ጨቅላ የፊውዳል ግዛቶች የአመራር አካል ወይም ላዕላይ መዋቅር በመሆን ነበር።

ከአያሌ ምዕት ዓመታት በኋላ በረጅም የጊዜ ሂደትና በሕብረተሰብ እድገት ጥንታዊዎቹን ዘውዳዊ የፊውዳል መንግሥታት በመተካት በሳይንስና በቴክኖሎጂ እድገት ላይ የተመሰረቱ በተለይም በኢንዱስትሪ በዳበሩ አገሮች ውስጥ ከ16ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ጀምሮ በተካሄደው የቡርዥዋ አብዮት ድል ማግስት በቡርዧዋው መደብ የበላይነት ላይ የተመሰረቱና ዛሬ በአብዛኛው የዓለም ክፍል የምናያቸው ብሔራዊ የቡርዧ መንግሥታት ተመሠረቱ።

መንግሥት የመደቦች መብትና ጥቅም ማስከበሪያ መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን የእኔ ሌላው ጥረትና ትኩረት የመንግሥቱ ብሔራዊ ወይም አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ደግሞ የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ቀንደኛ አባልና የመንግሥት መሣሪያ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ለማጠቃለል ቡርዧው የመደብ ሕብረተሰብን ህልውና ስለማይቀበልና በዚህም አመለካከቱ ምክንያት መደቦችና የመደብ ትግሎች አሉ ብሎ ስለማያምን የሰው ዘር በምድር ላይ እስከ አለ ድረስ መንግሥትም ከሰው ጋር ለዘላለም የሚኖርና ጊዜ የማይሽረው ተቋም ነው ይላል።

የቡርዧውን መደብ አስተሳሰቦችና ተግባሮች የሚፃረሩት ማርክሲስት አብዮታዊያን "መንግሥት በሕብረተሰብ ተከታታይ ታሪካዊ እድገት አማካኝነት ከመደቦች ጋር አብሮ የተከሰተ እንደመሆኑ በኮሚኒስት ሥርዓት መደቦች ሲጠፉ የመደብ ጥቅም ማስጠበቂያ መሣሪያ የነበረው መንግሥትም አብሮ የሚከስም መሆኑን" ያስገነዝባሉ።

ማርክሲዝም የምንኖርበት ዓለምና የዓለም አካል አንዱ ስለሆነው ሰው አጠቃላይ የሆነ ንድፈ ሀሳብ የሚሰጠን ሲሆን ስሙን የወሰደው ከ19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ እስከ መገባደጃው (ከ1818 እስከ 1833 ድረስ) ከ60 ዓመት በላይ የሆነ ጊዜውን በዚህ ንድፈ ሀሳብ ጥናትና ምርምር ከሰዋው የጀርመን ተወላጅ ታላቅ አብዮታዊ ፈላስፋ ካርል ማርክስ ነው።

ካርል ማርክስ የሠራተኛው መደብ ከካፒታሊስት ሥርዓት ጋር ለገጠመው ትግል የሚመራበትን የንድፈ ሀሳብ መሣሪያ ለማስጨበጥ ካደረጋቸው ጥረቶች ሁሉ ካፒታል የተባለው ሳይንሳዊ ምርምር ውጤት የሆነው የመጀመሪያውንና የላቀውን ታላቅ ስፍራ ይይዛል። ዓለምን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለመለወጥ የተነሳው ካርል ማርክስ "ካፒታል"ን ባያዘጋጅ ኖሮ ሰው-በላውን የካፒታሊስቶች ማህበራዊ ሥርዓትና በዝባዥ የሀብት ምጣኔ ሥልተ ምርት ባልታወቀና ባልተጋለጠ ነበረ። "ካፒታል" የማርክስ አስተምህሮ እጅግ የላቀ መሆኑን አረጋግጧል። ካፒታል የጥቂት ወራት ወይም ዓመታት ሥራ ሳይሆን የእድሜ ልክ ያልተቆጠበ ጥረት ውጤት ነው። ካርል ማርክስ ባላቋረጠና ባላሰለሰ ጥረት የጥናትና የምርምር ተግባሩን በጀመረበት 65ኛ ዓመት ላይ ስላረፈ የትግልና የርዕዮተ ዓለም ጓዱ የነበረው ፍሬድሪክ ኤንግልስ ቀሪውን ሥራ በማጠናቀቅ ካፒታልን ለንባብ በማብቃቱ የካርል ማርክስ እና የዓለም ሠራተኞች መደብ ታላቅ ባለውለታ ነው።

ሁለተኛውን ሌኒንዝም የተሰኘውን ስም የወሰደው እነዚህ ሁለት ታላቅ አብዮታዊ ምሁራን ያልደረሱበትን ዘመን ኢምፔሪያሊዝም፣ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምንና ሳይንሳዊ ኮሚንዝምን ከ1870 ዓ.ም እስከ 1924 ዓ.ም ከ50 ዓመት በላይ በማጥናትና በመመራመር የተሟላውንና ከተግባር ጋር የተዋሀደውን የወዛደሩን ርዕዮተ ዓለም ከማዳበር ባሻገር ወደ ተግባርም የለወጠው፣ በዓለም ታሪክ የመጀመሪያው የሶቪየት ሕብረት ሀብረተሰባዊ መንግሥትን ከመሠረተው የሩሲያ ተወላጅና ሌላው ታላቅ አብዮታዊ ምሁር ቭላድሚር ኤሊች ሌኒን ነው።

ስለሕብረተሰብ እድገት የሚመለከተው ሳይንሳዊ አቀራረብ የተመሠረተው እንደሌሎቹ ሳይንሶች ሁሉ በታሪክ እውነታ፣ በአካባቢያችንና ዓለም ነው። ማርክሲዝም የምንኖርበት ዓለምና ከዓለም አካል አንዱ ስለሆኑ ሰዎች አጠቃላይ የሆነ ንድፈ ሀሳብ የሚሰጠን ነው። ማርክስ፣ ኤንግልስና ሌኒን ሕብረተሰብ እንዴት እንደመጣ እንዴት እንደሚለወጥ፣ ወደ ፊትም የሚያደረጋቸው መንጠቅ ያሉ ለውጦች እንደሚኖሩ ጥልቅ ምርምሮችን አድርገዋል።

ጥናትና ምርምራቸው እነኝህ ለውጦች እንደ ውጫዊው ተፈጥሮ ሁሉ ድንገታዊ ሳይሆን በተወሰነ ሕግ ይጓዛሉ ወደሚል መደምደሚያ አድርሷቸዋል።

ይህ እውነት በሌሎች ስለ ህብረተሰቦች የተቀነባበሩና የተጻፉ ሃሳቦችን ካቀረቡትና አሁንም ከሚያቀርቡት ማለትም ከመንፈሳዊ እምነቶች፣ ከዘርና ከግለሰቦች ዝንባሌ ወይንም ከተምኔታዊ ሃሳቦችና አመለካከቶች ተጻራሪ በመሆን በሰዎች እለታዊ ገጠመኞች ላይ በመመሥረት በሕብረተሰብ ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳብ ለማቅረብ አስችሏል። ማርክሲዝም ሌኒንዝም የተሰኘው ሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ ከዘረኝነት፣ ከነዋይ ሴሰኝነት፣ ከተምኔታዊ አመለካከትና ከሞራል ዝቅጠት የፀዳ ነፃና ሰብአዊ ሕብረተሰብ ለመፍጠር፣ ለመገንባት ወይም የተጣመመውን ለማቃናትና በመለዋወጥ የተጀመረ ሳይንሳዊ ጥረት ነው። ማርክሲዝም ሌኒንዚም በማያቋርጥ ሁኔታ እየዳበረና በአዳዲስ ሳይንሳዊ እውነታዎች ላይ በተግባር እየዋለ ወደፊት የሚጓዙ ተራማጅ ንድፈሃሳብ ነው። ስለሆነም ማርክሲዝም ሌኒንዝም የተጠናቀቀና የበቃ ንድፈሃሳብ ሳይሆን ከሕብረተሰብ እድገትና ከታሪክ ሂደት ጋር እየተጓዘ የሚያድግ ነው።

የመከላከያ ሠራዊታችን አደረጃጀት አቢይ ትኩረት ሠራዊቱን የምንመራበት ሥርዓተ ማህበር ጠንካራ ማህበራዊ መሠረትና የፖለቲካ ሥርዓቱ ቀንደኛ አካል ለማድረግ መሆኑን ገልጫለሁ። በመከላከያ ሠራዊቱና በፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ለማወቅ በቅድሚያ የፖለቲካ ሥርዓቱን ምንነት መረዳት አስፈላጊ በመሆኑ የፖለቲካ ሥርዓት የተባለው ፅንሰ ሃሳብ የሚገልጣቸውን ቃላቶች ትርጉም ማለትም ‘ፖለቲካ’ እና ‘ሥርዓት’ የተሰኙት ከመዳሰሳቸውም በላይ ከፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ዋና ዋናዎቹን ማለትም የፓርቲን እና የመንግሥትን ምንነት በጥቂቱ አይተናል። በመጨረሻም ማርክሲዝም ሌኒንዝም የተባለውን አብዮታዊ ፍልስፍና ወይም የማህበረ-ሥርዓቱን የንድፈሃሳብ መመሪያ በመቃኘት በካፒታሊስትና በሕብረተሰብአዊ ሥርዓቶች መካከልና ብሎም ሁለቱን ተፃራሪ ሥርዓቶች በሚያገለግሉ የመከላከያ ሠራዊቶች መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነቶች ለመገንዘብ ችለናል።

በካፒታሊስትና በሶሻሊስቱ ሥርዓት ማህበሮች መካከል ያሉትን የኢኮኖሚ አደረጃጀትና አስተዳዳር የፖለቲካ አደረጃጀትና አስተዳደር እንዲሁም ማህበራዊ ሥርዓቶቹ የሚመሩበትን ፍልስፍና መሠረታዊ ልዩነቶች የተረዳን ከሆን ከእነኝህ በኋላ ማየት የሚኖርብን ሌላው ጉዳይ በወታደራዊ አደረጃጀት ረገድ ያሉትን ልዩነቶች ይሆናል። በሁለቱም ሥርዓቶች የመከላከያ ሠራዊቶች ወታደራዊ አደረጃጀቶች መካከል አያሌ ልዩነቶች ቢኖሩም ዋናዋናዎቹ መሠረታዊ ልዩነቶች የአንድ ግለሰብ ብቸኛ እዝና የወል እዝ በተሰኙ ሁለት የአመራር ዓይነቶችና በሠራዊቱ ወታደራዊ አደረጃጀት መዋቅራዊ ጠገግ ወይንም ተዋረድ ልዩ ልዩ አካላት ላዕላይ መዋቅር ልዩነቶች ናቸው።

ከዚህ በኋላ ወደፊት አግባብ ባለው ቦታ መጠናቸውን፣ ተልዕኳቸውን ወይንም ተግባራቸውን እንደ አደረጃጀታቸው ቅደም ተከተል በዝርዝር ከምገልጣቸው የተለያዩ የጦር ክፍሎች በዝቅተኛነቱ የመጨረሻ የሆነው “ጓድ” ተብሎ የሚጠራው የጦር ሕዋስ ነው።

ጓድ የምንለው የመጀመሪያው አነስተኛ የጦር ክፍልና ከእሱ ቀጥሎ ያለው ሁለተኛ “የመቶ” እና ብሎም ሦስተኛው “ሻምበል” ከምንላቸው የጦር ክፍሎች በላይ ካሉት ከሻለቃ ጀምሮ እስከ ሠራዊት ደረጃ ድረስ ላሉት የጦር ክፍሎች አመራር የሚሰጡ እዞች ወይንም ወታደራዊ ላዕላይ መዋቅሮች ውስጥ በሁለቱም ወታደራዊ ጎራዎች የተዋቀሩት ከዚህ በታች ከሻለቃ እስከ ብርጌድ ያሉት እዞች ያቀፏቸው የአመራር አካላት፣

1ኛ/ የክፍሉ አዛዥ
2ኛ/ ምክትል አዛዥ
3ኛ/ መሪ አንድ የሚባለው የአስተዳደር መምሪያ መኮንን
4ኛ/ መሪ ሁለት የሚባለው የውጊያ የመረጃ መምሪያ መኮንን
5ኛ/ መሪ ሦስት የሚባለው የትምህርትና የዘመቻ መምሪያ መኮንን
6ኛ/ መሪ አራት የሚባለው የንብረት ወይም የሎጅስቲክ መምሪያ መኮንንኖች ናቸው።

አዛዡ ክፍሉን በበላይነትና በፍፁም ወሳኝነት የመምራት ኃላፊነት ሲኖረው ምክትል አዛዡ ዋናውን አዛዥ የመርዳት፣ አዛዡ ክፍሉ መጥኖ የሚሰጠውን የሥራ ድርሻ የማከናወንና አዛዡ በማይኖርበት ጊዜ አዛዡን የመተካት ኃላፊነትና ተግባር ያለው መኮንን ነው። የተቀሩት የመምሪያ መኰንኖች በየሥራ ዘርፋቸው ያለውን ተግባር በብቃት የማከናወን አዛዡንና ምክትል አዛዡን የማማከር ኃላፊነት ነው ያላቸው። ከክፍለጦር ጀምሮ ሠራዊት ደረጃ ባሉ የጦር ክፍሎች ውስጥ ያሉ የእዝ አካላት ጋር ፍፁም ተማሣሳይነት ሲኖራቸው ከክፍለጦር ጀምሮ ወደላይ ያሉት የጦር ክፍሎች የሚለዩት የመምሪያ መኰንኖችን የሚያስተባብር፣ የክፍሉን አዛዥና ም/አዛዥ የማማከርና የመርዳት ኃላፊነት ያለው ኢታማጆር የሚባል የሥራ ድርሻ ያለው መኮንን መኖሩ ወይንም መታከሉ ነው። ከዚህ በላይ እስከ አሁን የተመለከትናቸው የመከላከያ ሠራዊት ወታደራዊ አደረጃጀቶች በሁለቱ ተፃራሪ የመከላከያ ሠራዊቶች መካከል መመሣሠል ወይም መቀራረብ ይታያል።

ከዚህ በኋላ በሁለቱ ሥርዓት ወይም ሠራዊት መካከል መሠረታዊ ልዩነቶች የሚፈጠሩት በመዋቅርና መዋቅሩ ባቀፋቸው አካላት ዓይነትና መጠን ብቻ ሳይሆን ከማህበራዊ ሥርዓቱ ከሚመነጩ አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶችና የአመራር ሥልቶች፣ ልዩነቶች ጭምር ነው።

እንደ ኢትዮጵያ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሂደት ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ አብዮታዊ አገሮችና በሶሻሊስት አብዮት ሂደት ውስጥ በሚገኙ አገሮች ውስጥ ባሉ አብዮታዊ የጦር ኃይሎች እዞች ወይንም ላዕላይ መዋቅሮች ውስጥ የተካቱት ከዚህ በላይ እንደታዬው አዛዥ፣ ም/አዛዥ ኢታማዥርና የመምሪያ መኮንኖች ብቻ ሳይሆኑ የአብዮታዊው ወይንም የህብረተሰባዊው ሥርዓት ነፀብራቅ የሆኑ የሠራዊቱ የፖለቲካ አስተዳደር መመሪያ ሃላፊና የሠራዊቱ ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ሃላፊ የሆኑ ተጨማሪ ሁለት ካድሬዎች በመዋቅሩ ውስጥ መካተት፣ የሠራዊቱን እዝ ወይም አመራር የአንድ ግለሰብ ሃላፊነት ብቻ ከማድረግ ፋንታ የወል እዝ መሆኑ ነው። እዚህ ላይ ሌላው ግንዛቤ ማግኘት ያለበት ጉዳይ፣ ካድሬ ስንል በፓርቲው ድርጅታው መዋቅር ውስጥ በቋሚነት የፓርቲውን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራ ወዘተ የሚያከናውኑ ሰዎች ብቻ ማለት ሳይሆን የፓርቲው አካል የሆኑ ጓዶች ሁሉ የተሰጠ ስም መሆኑን ነው።

የመከላከያ ድርጅቱ አካል በሆኑ የጦር ኃይሎችና በተለያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ የወል አመራር ስምንና እንዴት እንደሚሰራበት የሚያስረዳ ግልፅና ዝርዝር መመሪያ ቢኖርም መመሪያውን በትክክል ያለአንዳች ግድፈት የመከተልና በወል አመራሩ በሚገባ የመጠቀም ጉዳይ እንደየ ክፍሉ አዛዦች እውቀት፣ የሥራ ልምድ፣ የመደብ ጀርባና በአብዮት ላይ ባላቸው አቋምና ንቃተ ህሊና ደረጃ የሚወሰን ነው።

የወል እዝ ወይም የአመራር አካላት ማዕከል የየጦር ክፍሉ አዛዥ መኮንኖች ናቸው። ስለሆነም የአመራሩ ከፍተኛ ሃላፊነትና ተጠያቂነትም በቅድሚያ የሚያርፈው በአዛዥ መኮንኖችና በምክትል አዛዦች ላይ ነው። ይህም ሲባል የአዛዥ መኮንኑና የምክትል አዛዡ ከሁሉ በፊት የማዕረግ የበላይነት፣ የበላይ መሪነት፣ የሚሰጡት ትዕዛዝና መመሪያ



ተፈፃሚነት እንደተጠበቁ ሆነው የሠራዊቱ የፖለቲካ አስተዳደር መምሪያ ሃላፊ የሚወክለው ፓርቲ ነው። የወል አመራሩ አካል አባላት ሁሉም በአመራሩ ተሳትፎ ለውሳኔ በሚሰጡት ድምፅና ከዚህም አንፃር በሥልጣን እኩል መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ከወል አመራር በመለስ የእዝ አካል አባላት በየሥራ ዘርፋቸው የየግል ተልዕኳቸውን በተመለከተ የክፍሉ አዛዥና የምክትል አዛዥ ቀደም ብሎ የተነገረላቸው የእዙ ማዕከልነትና ሁለንተናዊ የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከሥራ ድርሻ አንፃር ማተኮር ያለባቸው በአጠቃላይ የጦሩ አስተዳደር፣ በአጠቃላይ የጦሩ ወታደራዊ ሙያና ስልጠና፣ የውጊያ ብቃትና ለጦሩ ከበላይ አካል በተሰጠው ወይም በሚሰጠው ወታደራዊ ግዳጅ መሠረት ውጊያን በመምራት ላይ ነው።

የሠራዊቱ ደህንነት ጥበቃ ሃላፊ ተልዕኮ በአጭሩ ወይም ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ በአጠቃላይ አገሪቱን፣ በተለይ የአብዮታዊ ሠራዊቱን ደህንነትና አንድነት ነቅቶ በመጠበቅ ከሙያ አንፃር አዛዦቹንና ሌሎቹን ከመርዳት ከማማከር ባሻገር ጦሩን ማስተማርና ማንቃት ናቸው።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በአንድ ሕዝብ አብዮታዊ ንቅናቄ ወይም ለፖለቲካ ሥልጣን በሚደረግ የመደብ ትግል አብዮታዊ በተለይም ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ የሕዝቡ አንቂ፣ አደራጅ፣ ቀስቃሽ፣ አዝማች፣ የማህበረ ሥርዓቱ መሪና የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት እምብርት ወይም ማዕከል ነው ብለናል።

በአንድ መከላከያ ሠራዊት ወይንም በአንድ የጦር ክፍል ውስጥ የወል እዝ አካል አባል የሆነ የሠራዊት የፖለቲካ አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ወይንም ወታደራዊ ካድሬ

ተልዕኮ በሠላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ ሠራዊቱ መካከል ተገኝቶ ፓርቲውን በመወከል ከዚህ በላይ ከሞላጎደል የተዘረዘሩትን የፓርቲ ተግባር ማከናወን ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ተልዕኮ አንፃር ከዝርዝር ተግባሮች በጣም ጥቂቱን፣ ማወቅ ቢያስፈልግ፣ ከተለመደውና ማንኛውም ሠራዊት ከሚከተለው መደበኛ ወታደራዊ ሥነሥርዓት ባሻገር ወይንም በተጨማሪ አብዮታዊው ሠራዊት በመደብ ንቃት ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አብዮታዊ ሥነሥርዓት እንዲላበስ ያደርጋል። በሠላም ጊዜ ብቻ ሳይሆን ቀውጢ በሆነ የውጊያ አውድማ እየተገኘ አርአያነት ያለው ኮሚኒስታዊ ተግባር ያከናውናል። የወገን አብዮታዊ ሠራዊት ምንጊዜም ሳይታክት እየተዋጋ በጠላቱ ላይ ድል ለመቀዳጀት ይተጋ ዘንድ ያላሰለሰ ቅስቀሳ ያደርጋል።

የጠላት ሠራዊት በራሱ የመተማመን ስሜት ከጊዜ ወደጊዜ እንዲቀዘቅዝ፣ የተዋጊነት ስሜቱ እንዲ ኮላሽና፣ ራሱንና መሪዎቹን እንዲጠራጠር፣ እንዲከፋፈልና ተፍረክርኮ እንዲንበረከክ ወይም እንዲፈርስ የሚያደርገው ወታደራዊ ፕሮፓጋንዳና ጠንካራ የሥነልቡና ውጊያ ያካሄዳል። በሚመራው የጦር ክፍል ውስጥ ያለውን የሰው ኃይል በጥቃቅን ቡድን በመከፋፈል የሠራዊቱን የውይይትና የጥናት ክበቦች ያደራጃል። ከሠራዊቱ መካከል በፖለቲካ ንቃታቸው በአብዮታዊ ንድፈሃሳብ ዕውቀታቸው የበቁትን ለአብዮቱ ዓላማና ብሎም ግብ መምታት አበክረው በፅናት የሚታገሉትን ቆራጥ ኰሚኒስቶች በነቂስ እየመለመለ የፓርቲው አባል ያደርጋል።

በዚህ ዓይነት ጥረትና የተግባር ሂደት በሠራዊቱ ውስጥ ከላይ እስከታች የፓርቲውን ድርጅት አዋቅሮ ይመራል። የዕዝ አካል በወል የሚያከናውናቸው ተግባሮች እጅግ ብዙዎች ስለሆኑ መዘርዘሩ አዳጋች ከመሆኑ ባሻገር አስፈላጊም ስለማይሆን ከበድ ከበድ የሚሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች በጥቂቱ ከዚህ እንደሚከተለው ለመጠቃቀስ ይሞክራል።

ማናቸውም የጦር ክፍሉን የሚመለከቱና ከፍ ያለ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ሁሉ የሚታሰቡት፣ የሚመከርባቸው፣ የሚታቀዱትና ወደ ተግባርም የሚተረጎሙት በወል አመራር ነው። አሁንም በጥቂቱ ለማወቅና ከሃገር አንድነትና ከሠራዊቱ ደህንነት ጋር የተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች የሚመከርባቸው፣ የሚታቀዱትና በተግባር ላይ ይውሉ ዘንድ ውሳኔ የሚሰጥባቸው በወል ነው።

የውጊያ ዕቅድ ዝግጅቶች የዘመቻ ትዕዛዞችና ማናቸውም የጦር እንቅስቃሴዎች የሠራዊቱ አባላት ሹመት ወይንም የማዕረግ እድገት፤ የሜዳይና የኒሻን ሽልማት፤ በአባላት ላይ ከፍተኛ የእሥርና ከማዕረግ ደረጃ ዝቅ የሚያደርግ ከሠራዊቱ የሚያሰናብትና በሕይወት የሚያስቀጣ ሕግና ፍትህ ነክ ጉዳዮች የሚታዩት በወል አመራር ነው።

ትምህርት፤ ከአንዱ ክፍል ወደሌላው ክፍል የአባላት ዝውውር፣ ከፍተኛ ወታደራዊ ወይም የሲቪል ትምህርት ዕድል የሠራዊቱ ጤናና ሞራል ጉዳዮች፣ ከፍተኛ የአስተዳደርና የሞራል ነክ ጉዳዮች ወዘተ የሚመከርባቸው፣ የሚታቀዱትና የሚወሰኑት በወል አመራር ነው።

የእዝ አካል አባላት በሙሉ የሚመክሩባቸው፣ የሚያቅዷቸውና ሲስማሙም ወደ ተግባር እንዲተረጎሙ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ሁሉ አጠቃላይ የአብዮቱን ዓላማ፣ የፓርቲውን የፖለቲካ ፕሮግራምና የመንግሥትን የሃገር ልማትና የመከላከያ ግምባታ ዕቅድ የሚፃረሩ እንዳይሆኑ መጠንቀቅና መጠበቅ የወልም የግልም አብዮታዊ ግዴታቸው ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ታሪኳን በሙሉ ስትማቅቅ የኖረችው በጉልታዊው ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ቢሆንም ከመጨረሻው ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮና ብሎም

በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ የካፒሊስት ሥርዓት ችግኝ ስለማቆጥቆጡ በዚህ ታሪክ የተለያዩ ክፍሎችና በተለያዩ አጋጣሚዎች ተገልጧል።

ከድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ አብዮታችን አጥቢያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህሪይ ከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት ነበር ማለት ይቻላል። ስለሆነም የአገሪቱ ዋነኛ ችግሮች የሚመነጩት ከፊውዳሊዝም፣ ከኢምፔሪያሊዝምና የእነዚህ የሁለቱ የቃል ኪዳን ወዳጅነት ከወለደው ከቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ነበር። የአብዮቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይሎች ሠራተኛው፣ አርሶ አደሩ፣ መለዮ ለባሹ፣ ከሰፊው ሕዝብ አብራክ የወጡ የአገሪቱ ለውጥ ፈላጊ ምሑራንና የተቀረው ባተሌ ዋቶአደር ደሀ ነው። ከእነዚህ አብዮታዊ ኃይሎች አንፃር ደግሞ ፊውዳሎች በፍፁም ተፃራሪነት ሲሰለፉ አብዮቱ በፀረ-ፊውዳሊዝም አቋም ብቻ ተወስኖ ግቡን የካፒታሊስት ሥርዓት ግምባታ በማድረግ አፍቃሪ ኢምፔሪያሊዝም እንዲሆን የሚመኙ የአገሪቱ ቡርዧዎችና ቢሮክራሲውን ከለላ አድርገው በማድፈጥ ለካፒታሊስት የዕድገት ፈለግ የቆሙ ንዑስ ከበርቴዎች የአብዮቱን ወደፊት መግፋት በመቃወም ተሠልፈዋል።

በሕዝባዊ አመፅ የፖለቲካ ሥልጣን ከአንዱ መደብ ወደ ሌላው መደብ በሚተላለፍበት ወይም በአብዮት ሂደት መነሻ ወቅት በአዲሱ ማህበራዊ ሥርዓት የሚስማሙ አካላትን፣ ለአብዮቱ ወደፊት መግፋት አለኝታና መከታ የሚሆኑ ማህበራዊ ኃይሎችን በሙሉ ለማደራጀትና ለማዋቀር የሚያስችል ረዘም ያለ ጊዜ ይጠይቃል። ይህንን በመሰለ የሽግግር ወቅት የአሮጌውና የአዲሱ ፖለቲካ ሥርዓቶች ባሕርያት ጎን ለጎን አብረው የሚገኙበትና ምናልባትም አሮጌው አይሎ አዲሱን መልሶ ለመድፈቅ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት አደገኛ ወቅት ነው። የአሮጌው ሥርዓት አካላት ሙሉ በሙሉ አልተወገዱም። የአዲሱም የፖለቲካ ሥርዓት አካላት ተደራጅተውና ተዋቅረው አሮጌውን ሥርዓትና አራማጁ የሆኑትን ገዥ መደቦች አልተኩም።

ከዓለም አብዮታዊ የትግል ታሪክ እንደተማርነው ከፓሪስ ኮሚዩን ጀምሮ ባለፉት አንድ መቶ ዓመታት በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ጊዜያት የፈነዱ እያሌ ሕዝባዊ አብዮቶች በጨቅላነታቸው የተቀለበሱት ይህንን በመሰለው አፍላ አብዮታዊ የሽግግር ወቅት ነው። በአንባብያን ዘንድ ይታወስ እንደሆነ ከ1967 ዓ.ም መጀመሪያ እስከ 1970 ዓ.ም መባቻ በነበሩበት ሁለት ዓመታት ውስጥ አገራችን ኢትዮጵያና አብዮቷ የነበሩበት ሁኔታ ፍፁም ይህንን የሚመስል ነበር።

የኢምፔሪያሊስት ካምፕና መላው አድህሮት ኢትዮጵያ አበቃላት አለቀላት ብለው አሟርተው ነበር። ይህንን ሁኔታ የተገነዘበው ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት "ከአሁን የተሻለ ጊዜ የለም" በማለት ነበር የጋራ ድንበራችንን 700 ኪ/ሜትር በመጣስ አገራችንን የወረረው። በዚህ ጊዜ ነበር ኢምፔሪያሊዝም በእሱም አስተባባሪነት ጎረቤቶቻችንና የአካባቢው አድህሮት ኃይላት፣ የውስጥ ገንጣይና አስገንጣዮች ተስፋ ለዘውድ ፊውዳሎችና ከእነሱ ያበሩት አምስኛ ረድፎች የተረባረቡብን። እነዚህ በፀረ-ኢትዮጵያ ግምባር አመራር የተሰባሰቡ ኃይሎች ጦርነት ባወጁብን በ1969 ዓ.ም አብዮታችን አሮጌዎቹን የፖለቲካ ሥርዓት አካላት በማፈራረስ ላይ ነበር እንጅ  አዲሶችን አልገነባንም። ሕዝቡ በየዘርፉ በመንቃትና በመደራጀት ላይ ነበር እንጅ  አልታጠቀም። አብዮቱን የሚመራ የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም። በእርዳ ተራዳ የታወጀብንን ጦርነት ለመከላከል የተዘጋጀ የጦር ኃይልና ሠራዊቱም የሚታጠቀው የጦር መሣሪያ አልነበረም።

የጊዜያዊውን አብዮታዊ መንግሥት መንኰራኩር ወይም ማሽን በማንቀሳቀስ አገሪቱን ከጥቃት ለማዳን፤ በተከታታይ ዓመታት የተከሰተው ድርቅ ብርቱ ጉዳት ያደረሰበትን ከመቶ ሺህ በላይ የሆነ ወገናችንን ለማዳን ቀን ከሌሊት ከልባቸው የሚጥሩ ሃገር ወዳድ ምሑራን ቢኖሩንም ሃገርና አብዮቱን ለማዳን ያዘጋጀነውን መከላከያ ሠራዊት የሚመሩ የጦር መኰንኖችና ልዩ ልዩ ወታደራዊ ጠበብት ታላቅ እጥረት ነበረብን። የአገሪቱ ከፍተኛ የመከላከያ ተቋማት ላዕላይ መዋቅሮች በከፍተኛ መሪ መኰንኖች እጥረት ምክንያት ባዶ ስለነበሩ የአገሪቱ መስተዳድር ማለትም፤ የሚኒስትሮች ምክርቤት የተቋቋመበትን ሃገርአቀፍ ተግባር ማከናወኑን ትቶ የመከላከያ ሚኒስቴሩ ጓዳ ወይንም ማዕድቤት ሆኖ ነበር ማለት ያስደፍራል።

ለጦርነቱ የመጓሪያና የጥይት፣ እንዲሁም የተለያዩ ፊንጂዎች፣ የስንቃስንቅ፣ የነዳጅና ቅባት የህክምና የትጥቅና የአልባሳት፣ የመድሃኒት አገልግሎት፣ ጠቅላላ የመጓጓዣዎች ወዘተ አቅርቦት ዝግጅት የሚከናወነው በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ውስጥ ነበር።

የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል እኛን ለመውረር የተደራጀውና የተዘጋጀው ለ15 ዓመታት የአገራችን የውስጥ በተለይም፤ የሰሜኖች ገንጣዮች ከአረብ መንግሥታት የሚጎርፍላቸውን መሣሪያና የውጊያ ልምድ ያካበቱት ለ17 ዓመታት ያህል ጊዜ ሲሆን የኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ጠቅላላ የዝግጅት ጊዜ ከሦስት ወር የማይበልጥ ነው። በእነዚህ ሁሉ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ብንዋጥና ብቻችንን ብንሆንም አስተማማኝ አለኝታ የሆነ አንድ ግዙፍ ኃይል ምንጊዜም ከጎናችን ነበረ። እሱም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአብዮቱ ጋር ነበር። ደርግ ሕዝብ ነበር። ሕዝብም ደርግ ነበር።

ሃገርንና አብዮቱን ለማዳን ያዘጋጀነው መከላከያ ሠራዊት በተዋጊ የጦር አቋም ለማደራጀት ከገጠሙን አያሌ ችግሮች ዋናና እጅግ አሳሳቢ የነበረው የሠራዊቱ ቁጥር እጅግ ብዙ በመሆኑ መጠን በዓይነትም በቁጥርም የሚመጥኑ የመሪ መኰንኖች ቁጥር ለማግኘት አለመቻሉ ነው።

የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በ1940ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ከሰሜን አሜሪካ መንግሥት ጋር የመከላከያ ተራድኦ ውል ሲዋዋል የኢትዮጵያ ጠቅላላ የጦርኃይል ቁጥር በአርባ ሺህ የሰው ኃይል የተተመነ በመሆኑ አገሪቱ የነበራትም የጦር መኰንኖች በዚሁ ምጣኔ መሠረት ቁጥራቸው በጣም ትንሽ ነበር።

ይህም ሆኖ መኰንኖቹም ሆኑ ሠራዊቱ በየምክንያቱ ከኃይል በሚጎድሉበት ጊዜ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዓይነትም ሆነ በመጠን ወዲያው አሠልጥኖ የመተካቱ ጉዳይ ብዙ የሚታሰብበት ስለአልነበር የጦር ኃይሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በአቋም የተተመነለትን የሰው ኃይል አሟልቶ የተገኘበት ጊዜ አልነበረም።

በሞት፣ በክዳት፣ በጡረታ፣ በበሽታ ወይንም በጤና መታወክ ብቻ ሳይሆን በምሥራቅና በደቡብ ግምባር ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ለደፈጣ ውጊያ መደበኛ ሠራዊቱን ጨርቅ እያለበሰ አሥርጎ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ከሚያስገባቸው ሽብር ፈጣሪዎች ጋርና በሰሜን ከገንጣዮች ጋር በሚደረገው ፍልሚያ በመሰዋትና በመቁሰል የመኰንኖች ቁጥር በጣም ተመናምኖ ነበር። ሕዝባዊ ሠራዊቱን በምናሠለጥንበትና ብሎም በምናደራጅበት ወቅት ይሔው የተዳከመና የተመናመነው መደበኛ ሠራዊት በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብና በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብና በመሃል ሃገር ከተስፋፊዎች፣ ከገንጣዮች፣ አብዮት ከመጣባቸው ፊውዳሎችና ከአምስተኛ ረድፎች ጋር በመተናነቅ ላይ ነበር።

ለሕዝባዊ ሠራዊቱ ከሕዝባዊ ሠራዊቱ ሌላ በተጨማሪ ላዘጋጀናቸው አንድ የታንክ ብርጌድ፣ አንድ አየር ወለድ ብርጌድ፣ ሦስት ኰማንዶ ብርጌዶችና ሁለት ነበልባል በመባል ለሚታወቁ እግረኛ ክፍለ ጦሮች አመራር እንዲሰጡ የሚፈለጉ የተለያየ ሙያና የተለያየ የማዕረግ ደረጃ ያላቸውን ጠቅላላ መኰንኖች ለጊዜው ትቼ የተስፋፋውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ የጦር ኃይል መክቶ በመከላከል ብሎም ረግጦ እንዲያስወጣ ለምናቋቁመው አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አመራር ብቻ ያስፈለጉን የጄነራል መኰንኖች ቁጥር ያውም በቁጠባ ዘዴ ተሠልቶ ከአርባ በላይ ነበር።

የእዙን ማዕከል ሐረር ከተማ ላይ አድርጎ ለተቋቋመው አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት ብቻ ያስፈለጉ ጄነራል መኰንኖችን ብቻ የገለጥኩበት ምክንያት በመላው የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት በየክፍሉ ደረጃና በየመኰንኖች የማዕረግ ደረጃና በየሙያቸው በማስላት የብዙ ሺህ መኰንኖች ዝርዝር ማቅረቡ አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ አንባቢ ችግራችንን ለመረዳት አይሳነውም ብዬ በመገመት ነው።

ማንም እንደሚያውቀው አብዮታችን ጨቅላ ወይም ለጋ ስለነበር የራሱን የጦር መኰንኖች አላፈራም። የሶሻሊስት ሥርዓት አርበኛ የሆኑ የጦር መኰንኖችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማፍራት የሚቻል ነገርም አልነበረም። ቀደም ብዬ አፍላና ቀውጢ የሽግግር ወቅት ባልኩት የጊዜ ክልል ውስጥ አብዮቱ ከአሮጌው ሥርዓት የወረሳቸው ጄነራል መኰንኖች በሠራዊት አመራር ላይ የነበሩት ቁጥር አምስት ያህል እንኳን አልነበረም።

እኔ እስከማስታውሰው ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ የምሥራቁን ግምባር ብቻ ሳይሆን በመላ የአገሪቷ የተለያዩ ማዕዘናት ይካሄድ የነበሩትን ውጊያዎች ለመቆጣጠርና ለመምራት በአገሪቱ ማዕከል በአዲስ አበባ ባቋቋምነው ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ውስጥ ይሠሩ የነበሩት ከፍተኛና ነባር ጄነራሎች የመከላከያ ሚኒስትሩና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ ሜ/ጄነራል ግዛው በላይነህ ብቻ ነበሩ።

ለአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አመራር ወደ 49 ጄነራል መኰንኖች ሲያስፈልጉ አንድም አልነበረንም። የሠራዊቱ እዝ ማዕከል የነበረው ኮሎኔል ሙላቱ ነጋሽ ነበር። ይህንን የመሰለ የጦር መሪዎች እጥረት የተፈጠረበት ምክንያት በሙስናና በሥልጣን ብልግና አብዮቱ ከሠራዊቱ ስለአገለላቸው ብቻ ሳይሆን በቀደመ አብዮት ኢትዮጵያ የጦር ኃይሉ ተቋም እጅግ ጠባብ በመሆኑ ወትሮም በሠራዊቱ አመራር ላይ የነበሩት የአገሪቱ ጄነራል መኮንኖች ቁጥር ከሰላሳ የሚበልጥ አልነበረም።

አዲሱን ነፃ አውጭ ሕዝባዊ የመከላከያ ሠራዊት በከፍተኛ ደረጃ ማለትም በሠራዊትና በክፍለ ጦር ደረጃ የተደራጁትን ክፍሎች ይመሩ ዘንድ በየግንባሩ የተሰለፈው መደበኛ ሠራዊት ውስጥ የጠራናቸውና ከፍተኛ ማዕረግ አላቸው የምንላቸውን የሻለቃ ማዕረግ ያላቸውን ነበር። እነዚህ ሠራዊቱን አሰልጥነው በጦር ሜዳ የመምራት ሃላፊነት የተሰጣቸው የመስክ መኮንኖች ብቻ ሳይሆን ከሠራዊቱ ኋላ የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት፣ የጦር ኃየሎችን መምሪያ፣ የምድር ጦርን መምሪያ፣ በእነዚህ ስር ያሉትን ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ወዘተ ውስጥ ያለውን እጅግ ሰፊና ውጥንቅጥ ሥራ ለመሥራት የነበሩት መኮንኖች እነዚህ የጠቀስኳቸውን በሻለቃ ማዕረግ ደረጃ የነበሩት ሲሆን የእነሱም ቁጥር ከሥራው ስፋትና ብዛት ጋር ጨርሶ የሚመጣጠን አልነበረም።

ከሶማሊያ ሠራዊት ጋር ለውጊያ ስንዘጋጅ የነበርንበት ሁኔታ ወይንም እውነታ ይሄ ስለነበር በዓይነትም በመጠንም አያሌ መኮንኖች የሚጠይቀውን አዲሱን የወል አመራር በመላው መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ቀርቶ በመጀመሪያው በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት

እዞችም ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ አልተቻለም ነበር። ችግሩ ውጊያ የሚመሩ መኮንኖች እጥረት ብቻ ሳይሆን ለውጊያው ስኬታማነት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ወታደራዊ ጠበብትና አብዮታዊ የፖለቲካ መኮንኖች ነው።

ወታደራዊ፣ የፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ባህሪ ባለው ውስብስብ የመደብ ትግልና ጦርነት የመከላከያ ሠራዊቱን ደህንነት፣ የሠራዊቱንና ሕዝቡን አንድነት ነቅተው የሚጠብቁ በሺህ የሚቆጠሩ የወታደራዊ ደህንነት ጥበቃ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ። ሠራዊቱ ለምንና ለማን እንደሚዋጋ ያወቀና በፖለቲካ እንደስሙ አብዮታዊና እርግጥም ሕዝባዊ ዓላማ ያለውና ሕዝብን ነፃ የሚያወጣ ሶሻሊስት አርበኛ ሠራዊት ለመፍጠር ፖለቲካውን የሚመሩ መኮንኖች መኖርና ያለመኖር ወሳኝ ሆኖ ሳለ በዚህ ረገድ የነበረብን ችግር ከሁሉም በላይ ነበር ከማለት ይልቅ ተስፋ አስቆራጭ ነበር ማለት የተሻለ ይሆናል። አብዮታችን ሊጋ በመሆኑ አብዮታዊ የፖለቲካ ሰዎች በመለዮ ለባሹ ውስጥ ይቅርና በመላው የአገሪቱ ምሁራን መካከልም ነበሩ ለማለት የሚያሰችል ሁኔታ እንዳልነበረ በዚህ ታሪክ መግቢያ ተመልክተናል።

በመከላከያ ሠራዊታችን ውስጥ አንድ መኮንን የፖለቲካ መሪ ወይንም ካድሬ ለመሆን ግለሰቡን የጦር መኮንን ካደረገው ወታደራዊ ሙያ ወይንም ወታደራዊ ሳይንስ ሌላ በተጨማሪ አብዮታዊ የፖለቲካ ሳይንስ እውቀት ብስለትና ከዚያ በላይ ጠንካራ እምነት ያለው ሊሆን ስለሚገባ እንዲህ ያሉትን ካድሬዎች በአጭር ጊዜ ለማፍራት የሚቻል አልነበረም። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል የተሞከረው ከዚህ ግርጌ በተመለከቱት ሁኔታዎች ነው።

የመከላከያ ሠራዊቱን አዋጊ መኰንኖች ኃይል ለማጠናከር በፖሊስ ሠራዊታችን ውስጥ ከሕግ ማስከበር ሙያ በተጨማሪ የውጊያ ሥልጠና ባላቸው ኰማንዶና ፈጥኖደራሽ ክፍሎች ውስጥ የነበሩትን አያሌ ወጣት መኰንኖችና የበታች ሹማምንት ወደ መከላከያ ሠራዊቱ ተቋም አዛወርናቸው። በመከላከያ ሠራዊቱ ተቋሞች ውስጥ ሻለቃ ከምንለው የጦር ክፍል ጀምሮ ወደላይ እስከ ሠራዊት ደረጃ ያሉትን ከመቶ አለቃ እስከ ሻለቃ ማዕረግ ያላቸው መኰንኖች እንዲመሩ ሲደረግ ከሻለቃ በታች ያሉትን መቶና ሻምበል የምንላቸውን ሁለት እጅግ ሰፊ ግን ዝቅተኛ የሆኑ የጦር ክፍሎች ከሃምሳአለቃ እስከ ሻለቃ ባሻ ድረስ ማዕረግ ያላቸው የበታች ሹማምንቶች እንዲመሯቸው ተደረገ።

በውጊያ አመራር በኩል የነበረው የመሪዎች እጥረት ችግር በዚህ ሁኔታ ሲቃለል በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት መሠረት የመከላከያ ሠራዊቱን የወል አመራር ተግባራዊ ማድረግ ባይችልም የሠራዊቱን ደህንነት ጥበቃና የፖለቲካ ሥራ በከፊልም ቢሆን መሥራት ግድ ነበር። በአብዮታችን አፍላ ዘመን በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ መለስተኛ የፖለቲካ ኘሮግራማችን ማዕቀፍ ውስጥ ተሰባስበው አብዮታዊ የፖለቲካ ፓርቲ ለመፍጠር የሚያስችል መሠረት እንዲጥሉ፣ ሕዝቡን በጋራ እንዲያንቃቁ እንዲያደራጁ ሲባል የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት መቋቋሙ ይታወሳል። በዚህ ሁኔታ የተሰባሰቡት አብዮታዊያን በፈጠሩት ማርክሲያዊ ሌኒናዊ የሕብረት ድርጅት ውስጥ የነበሩ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሲቪል አብዮታዊያን የነበሩንን አነስተኛ ቁጥር ወታደራዊ የፖለቲካ ካድሬዎች አጠናክረውና በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት እዝና በሥሩም ለተዋቀሩት የጦር ክፍሎች እዞች ውስጥ በሙሉ የሠራዊቱን ደህንነት ጥበቃና የፖለቲካውን ሥራ አጣምረው በመሥራት ሸፈኑልን።

ስለ አብዮታዊ መከላከያ ሠራዊታችን አደረጃጀት ያቀረብኩትን ማስገንዘቢያ ለማጠቃለልና የአደረጃጀቱን ዓይነት ወይንም የተቋማቱን ተዋረድ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ምዕራፍ በኋላ በዝርዝር የምተርከውን አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ያደረገውን ፍልሚያ በወታደራዊ ካርታ አማካኝነት በማስረዳበት ጊዜ የእያንዳንዱ የጦር ክፍል መለያ ሆነው በካርታው ላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ምንነት አንባቢ ይረዳ ዘንድ ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

በድህረ አብዮት በተለይም የሶማሊያን ወረራ ለመከላከል አዲስና አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ስናቋቋም የመጀመሪያ የሆነው አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት ለሰባት ወራት የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት ለመከላከል የተደራጀበትን ሁኔታ የሚያስረዳ መዋቅራዊ ሥዕል አቅርቤያለሁ።

እንደሚታወቀው አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት የተቋቋመው በጥድፊያ እጅግ አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ስለነበር ሠራዊቱ የተዋቀረው በሦስት መደበኛ እግረኛ ክፍለጦሮች፣ በአምስት ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦሮች፣ በአንድ ታንከኛ ብርጌድ በአንድ ያልተሟላ ሜካናይዝድ ብርጌድና በአንድ መድፈኛ ብርጌድ ነው። አራቱ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ከአርሶ አደሩ ሕብረተሰብ የተመለመሉ ሲሆኑ አንዱ ክፍለ ጦር ከአገሪቱ የተለያዩ የማምረቻና የማከፋፈያ ተቋማት ውስጥ የተመለመሉ ወዝአደሮች ክፍለጦር ነው።

ያልተሟላ በማለት የገለጥኩት ብርጌድ ከሜካናይዝድ ሻለቃ አካል አንድ ሻምበል የኩንጐ ዘማቾች በአመፁ ጊዜ ፀጥታ ለማስከበር ወደ አዲስ አበባ አምጥተነው ስለቀረ ነው። የታንክ ብርጌዱ፣ በቅድመ አብዮት በአገሪቱ ምሥራቃዊ ክልል ከነበሩን ሁለት አሮጌ የአሜሪካን ሥሪት ታንክ ሻለቆች አንዱን የዩጎዝላቪያ መንግሥት በችሮታ ከሰጠን 70 ታንኩች ጋር በማዳመር ያዋቀርነው ነው።

የመድፍ ብርጌዱንም በተመለከተ፣ እንዲሁ በድህረ አብዮት በአንበሳው ሦስተኛ ክፍለጦር እዝ ሥር የነበረውን አሮጌ የ105 ሚ/ሜ ሐዊትዘር መድፍ ሻለቃ፣ በድህረ አብዮት ከአሜሪካ የገዛነውን 155 ሚ/ሜ ርዕስ ውልብልቢት መድፍ ሻለቃ፣ የዲሞክራቲክ የመን መንግሥት በርዳታ ከላከልን አንድ 120 ሚ/ሜ መድፍ ሻለቃና ከ120 ሚ/ሜ ቢኤም ሮኬት ሻለቃ ጋር በመደመር ያዋቀርነው ነው።

በሠራዊቱ ማዕከላዊ መዋቅር ውስጥ የሚታዩት ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ማለትም የሕክምና፣ የመገናኛ ሻምበል ወዘተ አዲስ የተደራጁ ሳይሆኑ የአገሪቱን ምሥራቃዊ ጠረፍ ከ30 ዓመታት በላይ ሲጠብቅና ከሶማሊያዎች ጋር ሲፋለም ከኖረው ከአንበሳው ሦስተኛ እግረኛ ክፍለጦር አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት የወረሳቸው ናቸው። ከመከላከል ወደ ማጥቃት በተሸጋገርንበት ጊዜ የሠራዊቱ መዋቅር በሰው ኃይል፣ በመሣሪያ ብዛትና እንዲሁም ዓይነት በጣም ተሻሽሏል።

በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊትና በወራሪው የሶማሊያ የጦር ኃይል መካከል ለሰባት ወር የተደረገውን ፍልሚያ ታሪክ ለመረዳት እያንዳንዱን የጦር ክፍሎች የሚወክሉትን ወይም የሚያመለክቱትን ልዩ ወታደራዊ ምልክቶች ይመለከቷል።